ይህ የጥናት መምሪያ የሚያተኩረው በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ላይ በተሰማሩ ሰዎች ላይ ሲሆን የጥናት መምሪያውን በብዙ የተለያዩ መንገዶች መጠቀም ይቻላል። በግል የእግዚአብሔርን ቃል ለማጥናትም ሆነ በአዋቂዎች የሰንበት ትምህርት ቤት ወይም በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት መጠቀም ይቻላል።

ይሁንና መምሪያው የተዘጋጀው በትምህርተ–መለኮት ማስፋፊያ (ት.መ.ማ) መልክ ነው። በመሆኑም ይህ መጽሐፍ መምህርን ተክቶ ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርተ–መለኮት ወይም አገልግሎት ለተማሪው ጠቃሚ ትምህርቶችን ያስተላልፋል። ተማሪው በዚህ የጥናት መጽሐፍ እየተመራ ጥያቄዎችን በመመለስና የተማረውን ከሕይወቱ ጋር በማዛመድ በቀን አንድ ሰዓት ያህል ጊዜ ያሳልፋል።

ከሁሉም የላቀ ትርፍ የሚገኘው ደግሞ ተማሪዎቹ በሳምንት አንድ ቀን ተሰባስበው የተማሩትን ሲከልሱና የእግዚአብሔር ቃል እንዴት ካሉበት ሁኔታ ጋር እንደሚዛመድ ሲወያዩ ነው።

# የብሉይ ኪዳን

## የጥናት መምሪያና
## ማብራሪያ

## በትምህርተ መለኮት ማስፋፊያ (ት.መ.ማ)
## መልክ የተዘጋጀ

### 1ኛ መጽሐፍ

በመጀመሪያ በ1989 ዓ.ም ታተመ።
ከዚያም በ1992፥ በ1994 እና በ1996 ዓ.ም
በተደጋጋሚ ታተመ።

አሳታሚ፡-

BIBLE BASED BOOKS
SIM PUBLISHING

መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት ያደረጉ መጻሕፍት
የኤስ አይ ኤም ሥነ ጽሑፍ ክፍል
የፖ.ሣ.ቁጥር 127
አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

# ማውጫ

ገጽ


መግቢያ ....... 1

ትምህርት 1 – የብሉይ ኪዳን መሠረት ....... 4

ትምህርት 2 – የብሉይ ኪዳን ሥረ መሠረት ....... 33

ትምህርት 3 – የፔንታቱክ (አምስቱ የሕግ መጻሕፍት)
መግቢያ ....... 77

ትምህርት 4 – ዘፍጥረት ....... 115

ትምህርት 5 – ዘፍጥረት ....... 153

ትምህርት 6 – ዘጸአት ....... 174

ትምህርት 7 – ዘጸአት ....... 204

ትምህርት 8 – ዘሌዋውያን ....... 241

ትምህርት 9 – ዘኍልቁ ....... 269

ትምህርት 10 – ዘዳግም (ፔንታቱክ ክለሳ) ....... 302

ትምህርት 11 – የታሪክ መጻሕፍት መግቢያ/ ኢያሱ ....... 329

ትምህርት 12 – መጽሐፈ መሳፍንት/ ሩት ....... 369

ትምህርት 13 – 1ኛ ሳሙኤል ....... 410

ትምህርት 14 – 2ኛ ሳሙኤል ....... 450

ትምህርት 15 – 1ኛ ነገሥት ....... 484

ትምህርት 16 – 2ኛ ነገሥት ....... 520

ትምህርት 17 – 1ኛና 2ኛ ዜና መዋዕል ....... 558

ትምህርት 18 – ዕዝራ ....... 579

ትምህርት 19 – ነህምያ ....... 604

ትምህርት 20 – መጽሐፈ አስቴር/ የታሪክ መጻሕፍት ክለሳ ....... 621

ካርታዎች ....... 638

የጽሕፈት ሥራ ተግባር ....... 644

# መግቢያ

ለመሆኑ ከመንግሥት ወይም ከቤተ ክርስቲያንህ መሪ አንድ ደብዳቤ ቢደርስህ ደብዳቤውን ምን ታደርገዋለህ? ደብዳቤውን ሳታነበው ማስታወሻ ይሆንህ ዘንድ በግድግዳ ላይ ትለጥፈዋለህን? ደግሞም መሪው አንድ ነገር እንድታደርግ ቢጠይቅህ ታደርገዋለህን? ደብዳቤው የተጻፈው ግልጽ በሆነ ቋንቋ ቢሆንም እንኳ፥ ድብቅ የሆነ ትርጉም በመፈለግና የቃላትን ትርጉም በማዛባት የተሳሳተ መልእክት እንዲያስተላልፍ ታደርጋለህ? አታደርግም። ከአገራችን መንግሥት መሪ የተጻፈልን ደብዳቤ ቢደርሰን የምናደርገው የመጀመሪያ ነገር፡- ደብዳቤውን በመክፈት መሪያችን የሚለውን ነገር በጥንቃቄ ማንበብና በደብዳቤው ውስጥ የሚገኙትን ትእዛዛት በሙሉ ለመፈጸም መጣር ነው። መሪው ወዳጃችን ከሆነ ደግሞ ደብዳቤው የበለጠ ደስ የሚያሰኘን ይሆናል።

ክርስቲያኖች እንደመሆናችን መጠን ከመሪዎች ሁሉ የላቀ ኃይል ካለው መሪ ደብዳቤ የማግኘት ልዩ ዕድል አለን። እርሱ እያንዳንዳችንን እጅግ ይወደናል። ያም መሪ እግዚአብሔር አባታችን ነው። የተጻፈልን ደብዳቤ መጽሐፍ ቅዱስ ነው። የሚያሳዝነው ነገር ብዙዎቻችን ይህንን ደብዳቤ ወይም መጽሐፍ ለማንበብ የምንሰጠው ጊዜ በጣም ጥቂት መሆኑ ነው። ከዚህ የተነሣ ብዙውን ጊዜ መሪያችን እንድናደርግ የሚፈልገውን ነገር አናደርግም። ወይም ስናነብ ብዙ ጊዜ ከመጽሐፍ ቅዱሳችን የተደበቀ ትርጉም እንሻለን፤ እግዚአብሔር ሊነግረን የፈለገውን ነገር ትርጉም እንለውጣለን። ስለዚህ እግዚአብሔር ለእያንዳንዳችን ያለውን መልእክት እንስታለን።

በዚህ የጥናት መመሪያ አማካይነት እግዚአብሔር በተለይ ለእያንዳንዳችን ከሰጠን መጽሐፍ ውስጥ የተወሰነውን ክፍል እንመለከታለን። ብሉይ ኪዳንን ሰፋ ባለ ሁኔታ ለማወቅ በሚያስችለን መልክ እንመለከተዋለን። በእያንዳንዱ የብሉይ ኪዳን መጽሐፍ ውስጥ እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን ዋና ዋና መልእክቶች ለመማር እንፈልጋለን። ደግሞም የእግዚአብሔርን ቃል በተሳሳተ መንገድ እንዳንረዳውና ከሕይወታችንም ጋር ያለ አግባብ እንዳናዛምደው፥ በትክክል እንዴት እንደምንተረጉመው አንዳንድ መመሪያዎችን እንመለከታለን። በአገራችን የሐሰት ትምህርታቸውን የማረጋገጥ ሙከራ ለማድረግ ሲሉ የእግዚአብሔርን ቃል ትርጉም የሚያጣምሙ በርካታ የሐሰት

አስተማሪዎች አሉ፤ ስለዚህ ለእነርሱ መልስ ለመስጠት የእግዚአብሔርን ቃል እንዴት በትክክል መረዳት እንደምንችልና ሐሰተኛ አሳባቸውን ለመዋጋት እንዴት እንደምንጠቀምበት ማወቅ አለብን፤ (1ኛ ጢሞ. 4፡1-7 ተመልከት)። በተጨማሪም የተለያዩ የመጽሐፍ ቅዱስ አዋቂዎች ስለ አንዳንዶቹ መጻሕፍትና አተረጓጎም ያላቸውን የተለያየ አመለካከት እናያለን። በእንግሊዝኛ ቋንቋ በተጻፉ አንዳንድ ትርጓሜዎች ስለእነዚህ የምታነብብ በመሆኑ፥ ተግባራዊ መስሎ ባይታይም ስለ እነርሱ በቅድሚያ ማወቅህ መልካም ነው።

የብሉይ ኪዳን ጥናታችን 40 ሳምንታት ይፈጃል። ለዚህም ሁለት የጥናት መጻሕፍት ሲኖሩን፥ አንደኛው የመጀመሪያዎቹን 12 የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ያጠቃልላል። ሁለተኛው የጥናት መምሪያ በቀሩት የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ላይ ያተኩራል። የዚህ ጥናት ዓላማ አንተን ከብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ጋር ለማስተዋወቅ እንዲሁም እውነትን ከሕይወታችን ጋር ለማዛመድ እግዚአብሔር ለእያንዳንዳችን ያለውን መልእክት በጋራ ለመፈለግ ነው። የእግዚአብሔር ቃል እንድናውቀው ብቻ ሳይሆን፥ ከሕይወታችን ጋር እንድናዛምደው ጭምር የተጻፈ መሆኑን አስታውስ፥ የእግዚአብሔርን ቃል ከሕይወታችን ጋር ባናዛምደው፥ ከእግዚአብሔር ጋር ባለን መንፈሳዊ ጉዞ ላይ ተጽዕኖ ይኖረዋል፤ በመንፈሳዊ ሕይወታችንም እንዝላለን። ይህ ኮርስ ከእያንዳንዱ ተማሪ ብዙ መሥራትን ይጠይቃል፤ ነገር ግን ከራስህ ጋር ካዛመድከውና ጥያቄዎቹን በሙሉ በመመለስ የቤት ሥራዎቹን ከሠራህ፥ ብሉይ ኪዳንን በተሻለ አኳኋን ትረዳዋለህ፤ ከእግዚአብሔር ጋር ያለህ ጉዞም በጥልቀት ያድጋል። በምታውቃቸው ክፍሎች ላይ ብቻ ከማተኮር ይልቅ ለእግዚአብሔር ቃል በአጠቃላይ ፍቅር ይኖርሃል። እንዴት እንደምትጠቀምበትም ታውቃለህ። ሮሜ 15፡4 «በመጽናትና መጻሕፍት በሚሰጡት መጽናናት ተስፋ ይሆንልን ዘንድ አስቀድሞ የተጻፈው ሁሉ ለትምህርታችን ተጽፎአልና» ይላል።

> 1ኛ ጥያቄ፡- ኤፌ. 3፡14-9 አንብብ። ሀ) ጳውሎስ ለቤተ ክርስቲያን የጸለየው ጸሎት ምን ነበር? ለ) ይህ ጸሎት በዘመናችን ላሉትም አብያተ ክርስቲያናት የሚያስፈልገው ለምንድን ነው?

የጥያቄዎቹን መልስ በደብተር ላይ ጻፍ። የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት ከሌለህ፥ ለዚህ ጥናት እንዲረዳህ ለመግዛት ሞክር። አዲሱ የአማርኛ

መጽሐፍ ቅዱስ ትርጉምና የእንግሊዝኛ መጽሐፍ ቅዱስ ካሉህ ከእነርሱም ውስጥ አንብብ።

ተማሪውን በጥናቱ ይረዳው ዘንድ እያንዳንዱ ትምህርት በአምስት የየዕለቱ ትምህርቶች ተከፍሏል። የየዕለቱን ትምህርት (ክፍል) በአንድ አፍታ አጥንተህ ለመጨረስ ሞክር። አንዳንዶቹ ትምህርቶች ከሌሎቹ ረዘም ያሉ ስለሆኑ፥ ጠቅላላ ትምህርቱን ከሳምንታዊው ስብሰባ በፊት ለማጠቃለል የሚያስችል በቂ ጊዜ መስጠትህን አረጋግጥ። በትምህርቶቹ ውስጥ በርካታ አጣቃሽ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች አሉ። ስለዚህ «ተመልከት» የሚለውን ጥቅስ ሁሉ ለመመልከት እርግጠኛ ሁን። «ተመልከት» የሚል ቃል የሌለባቸውን ጥቅሶች ጊዜ ካለህ ትመለከታቸዋለህ፤ ወይም በሌላ ጊዜ ታጠናቸዋለህ።

የመጀመሪያዎቹ ሦስት ትምህርቶች ስለ ብሉይ ኪዳን አንዳንድ ጠቃሚ ትምህርቶችን ያስተዋውቃሉ። እነዚህ አሳቦች አዲስና አስቸጋሪ ቢሆኑም እንኳ እነርሱን ለመረዳት የተቻለህን ሁሉ አድርግ። አንዳንዶቹ ትምህርቶች አግባብነት ያላቸው ባይመስሉም እንኳ ዛሬ በኢትዮጵያ ውስጥ በእንግሊዝኛ የተጻፉ በርካታ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጓሜዎች ስለሚገኙ፥ እነዚህ ትምህርቶች በነርሱ ውስጥ ያሉትን አንዳንድ ጉዳዮች ለመረዳት ይጠቅሙሃል።

የዚሁ የጥናት መጽሐፍ አንደኛው ግብ መጽሐፉን የሚያጠኑ ሰዎች ሁሉ ብሉይ ኪዳንን ሙሉ በሙሉ እንዲያነቡ ለማበረታታት ነው። ስለዚህ የሚሰጡትን የንባብ ክፍሎች በሙሉ አጠናቅቆ ማንበብ በጣም አስፈላጊ ነው። መጨረሻ በሚሰጠው አጠቃላይ ፈተና ላይ እያንዳንዱ ተማሪ የተጠኑትን የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት በሙሉ ማንበብ ያለማንበቡን እንዲያሳውቅ ይጠየቃል።

* ማሳሰቢያ በዚህ መጽሐፍ ያሉት የዘመን አቆጣጠሮች እንደ ኤውሮጳ አቆጣጠር ናቸው። ዓ.ዓ. የሚለው ምሕጻረ ቃል ዓመተ ዓለም ማለቱ ሲሆን ከክርስቶስ ልደት በፊት የነበረውን ዘመን የሚያመለክት ነው።

# ትምህርት አንድ

## 1ኛ ቀን:- ብሉይ ኪዳን የእግዚአብሔር ቃል ነው።

2ኛ ጥያቄ:- 2ኛ ጢሞ. 3፡16-17 ና 2ኛ ጴጥ. 1፡20-21 አንብብ። ሀ) እነዚህ ቁጥሮች መጽሐፍ ቅዱስን በማስገኘት ረገድ ስለ እግዚአብሔር ድርሻ ምን ይናገራሉ? ለ) እነዚህ ቁጥሮች መጽሐፍ ቅዱስን በማስገኘት ረገድ የሰው ድርሻ ምንድን ነው ብለው ያስተምራሉ? ሐ) እነዚህ ቁጥሮች እግዚአብሔር መጽሐፍ ቅዱስን ለእኛ የሰጠበት ምክንያት ምንድነው ብለው ያስተምራሉ? መ) መጽሐፍ ቅዱስ በአንተ ሕይወት ውስጥ ለትምህርት፥ ለተግሣጽ፥ ልብን ለማቅናትና በጽድቅ ላለው ምክር እንዴት እንዳገለገለ ግለጥ።

መጽሐፍ ቅዱስ ምንድን ነው? እንደ ቁርአንና ሌሎች ሃይማኖታዊ ጽሑፎች ሁሉ የሰው ሥራ ነውን? ወይስ ሰውን መሣሪያ አድርጎ ሳይጠቀም እግዚአብሔር በቀጥታ ለሰዎች የሰጠው ነው? ዓላማውስ ምንድን ነው? መጽሐፍ ቅዱስ በራሱ ኃይል ያለው የምትሀት መጽሐፍ ነውን? እነዚህ ብሉይ ኪዳንን ማጥናት ከመጀመራችን በፊት ልንመልሳቸው የሚገቡ በጣም አስፈላጊ ጥያቄዎች ናቸው። ክርስቲያኖችም ሆኑ አይሁዶች ብሉይ ኪዳን የተለየ የእግዚአብሔር ቃልና በውስጡም እግዚአብሔር ራሱንና ዓላማውን ለሰው ልጅ የገለጠበት መጽሐፍ እንደሆነ ይናገራሉ። ክርስቲያኖች ከአይሁዶች የሚለዩት አዲስ ኪዳንም የእግዚአብሔር ቃል እንደሆነ ስለሚያምኑ ነው።

ብዙውን ጊዜ ክርስቲያኖች ስለ እግዚአብሔር ቃል ሁለት የተሳሳቱ ግንዛቤዎች አሉአቸው። የመጀመሪያው፥ ብዙ ክርስቲያኖች እግዚአብሔር እንዲጻፍ የፈለገውን ቃል ለተለያዩ ሰዎች ቃል በቃል አጽፎአቸዋል ብለው ያስባሉ፤ ስለዚህ አንዳንዶች ብሉይ ኪዳን በሚጻፍበት ጊዜ ጸሐፊዎቹ ምንም ድርሻ አልነበራቸውም ብለው ያስተምራሉ። በዚህ መልክ የተጻፉ አንዳንድ ክፍሎች ቢኖሩም (ለምሳሌ ዘጸ. 24፡4-7)፥ እነዚህን የብሉይ ኪዳን ክፍሎች የጻፉት ጸሐፊዎች ግን የሚጽፉት ጉዳይ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገባ የቅዱሳት መጻሕፍት አካል መሆኑን እንኳ አያውቁም ነበር። አልፎ አልፎም ጸሐፊዎቹ ከሌሎች መጻሕፍት የቀዱበት አጋጣሚ ነበር (ለምሳሌ:- ዘኁል. 22፡14-15፤ ኢያ. 10፡13)።

በሁለተኛ ደረጃ፥ እራሳቸውን ክርስቲያን አድርገው የሚቆጥሩ አንዳንድ ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል እንደሆነ ያለማሰባቸው ነው። ይልቁንም መጽሐፍ ቅዱስ የሰው ሥራ እንደሆነ ያስተምራሉ። መጽሐፍ ቅዱስ የአይሁድን ሃይማኖታዊ ልምምድ ለመረዳት የሚጠቅም እንጂ፥ እውነት አይደለም ብለው ያስባሉ። ሌሎች ደግሞ መጽሐፍ ቅዱስ እንደ ቁርአን ወይም እንደ ሂንዱ እምነት መጻሕፍት ነው፤ ምክንያቱም ሁሉም የሚናገሩት ሰው እግዚአብሔርን ለማወቅ ያደረገውን ጥረት ነው ይላሉ። አንዳንድ ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስ ገና ተጽፎ አላለቀም በማለት ዛሬም ቢሆን «የእግዚአብሔር ቃል» የሚሏቸውን ብዙ የሐሰት ትምህርቶች (ኑፋቄዎች) በመጨመር ላይ ይገኛሉ። የእነዚህ ትምህርቶች አመንጪ የሆኑት ሰዎች አሳባቸውን ከመጽሐፍ ቅዱስ እኩል በመቁጠር በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ያክላሉ፤ (ለምሳሌ፡- የይሖዋ ምስክሮች፥ የክርስቲያን ሳይንስ አማኞች፥ የሞርሞን ተከታዮች፥ ወዘተ)።

ስለ መጽሐፍ ቅዱስ በርካታ የተሳሳቱ አሳቦች በመኖራቸው፥ እምነታችን የተመሠረተውም በእርሱ ላይ በመሆኑ፥ ክርስቲያን የሆንነው ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ማመን ያለብን ነገር ምን እንደሆነ ግልጽ አሳብ ሊኖረን ያስፈልጋል። ይህንን አሳብ «መሠረታዊ የክርስትና እምነት ትምህርት ስለ መጽሐፍ ቅዱስና ስለ እግዚአብሔር» በሚለው ወደፊት በሚጻፈው መጽሐፍ ውስጥ ይበልጥ ጥልቅ በሆነ መንገድ መመልከት የሚቻል ቢሆንም አጠቃላይ የሆነ አጭር አሳብ ከዚህ እንደሚከተለው ቀርቧል፡-

1. መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል ነው። በ2ኛ ጢሞ. 3፡16ና 2ኛ ጴጥ. 1፡19 መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ እንደሆነና ጸሐፊዎቹ በመንፈስ ቅዱስ ተመርተው እንደጻፉት እናነባለን። መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል መሆኑን ራሱ በግልጥ ይናገራል፤ ስለዚህ እኛ ክርስቲያኖች ስለ መጽሐፍ ቅዱስ የሚከተሉትን ነገሮች እናምናለን፡-

    ሀ. መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ሙሉ ሥልጣን አለው። የእግዚአብሔርን ቃልና ፍላጎቶች ይዟል፥ ስለዚህ መጽሐፍ ቅዱስን በምናነብበት ጊዜ እግዚአብሔር በመካከላችን ያለና

የሚናገረን ያህል ነው። እግዚአብሔር የተናገረውም የተጻፈውም ቃሉ እኩል ሥልጣን አላቸው።

3ኛ ጥያቄ፡- ሀ) የእግዚአብሔርን ቃል ስለ መስበክም ሆነ ስለ ማስተማር ይህ ምንን ያስተምረናል? ለ) ሥልጣኑ ያለው የት ላይ ነው? (ኢሳ. 55፡11 ተመልከት)።

የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እንደ መሆናችን መጠን ሥልጣን ያለው የእግዚአብሔር ቃል ብቻ እንደሆነ ማስታወስ አለብን። የእኛ ቃላት ሥልጣን የሌላቸውና ስሕተት ሊገኝባቸው የሚችሉ ናቸው፤ ስለዚህ በምንሰብክበትና በምናስተምርበት ጊዜ የእኛ ኃላፊነት ሰዎች የእኛን አሳብ ሳይሆን የእግዚአብሔርን ቃል እንዲሰሙ፥ የእግዚአብሔርን ቃል ያለ አንዳች ስሕተት በግልጥ ማወጅ ነው (2ኛ ቆሮ. 4፡1-5፤ 2ኛ ጢሞ. 2፡15 ተመልከት)። ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል በሚሰሙበት ጊዜ ሥልጣኑና ኃይሉ ሕይወታቸውን ይለውጠዋል።

ለ. መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔርም የሰውም ሥራ ነው። መጽሐፍ ቅዱስን ለማስገኘት እግዚአብሔር ሰዎችን በመሣሪያነት በመጠቀም በራሳቸው ቃላትና የአስተሳሰብ መንገድ እንዲጽፉት አደረገ፤ ነገር ግን የጻፉት ቃል ውጤት ብሉይ ኪዳንን ጨምሮ በሙሉ የእግዚአብሔር ቃል ነው። ኢየሱስ እንዳለው በመጽሐፍ ቅዱስ ከሁሉ የምታንሰው ፊደል ወይም ነጥብ እንኳ በእግዚአብሔር ቁጥጥር ስለ ተጻፈ ሳይፈጸም አያልፍም (ማቴ. 5፡18 ተመልከት)።

ሐ. መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ሥራ ስለሆነ አንዳችም ስሕተት የለበትም። እግዚአብሔር ሊዋሽና ስሕተት ሊሠራ ጨርሶ እንደማይችል ሁሉ (ዕብ. 6፡18) ቃሉም አይዋሽም። ስለዚህ የእግዚአብሔር ቃል በግልጥ ከሚያስተምረው ነገር ጋር የማይስማማ ማንኛውም ዓይነት አመለካከት ስሕተት ነው። እውነት ምን እንደሆነ የሚተረጉመው የእግዚአብሔር ቃል-መጽሐፍ ቅዱስ ነው። በማንኛውም ጊዜ እኛም ሆንን ሌሎች የአንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችን እውነትነት በሚመለከት መጠየቅ ስንጀምር፥ በእግዚአብሔር ቃል ላይ እንፈርዳለን፥ በእግዚአብሔር ላይም ፈራጆች ሆንን ማለት ነው። መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ሥልጣን አለው እያልን ትክክል መሆን

አለመሆኑን መጠየቅ አንችልም። መጽሐፍ ቅዱስ ስሕተት ካለው በሕይወታችን ላይ ምንም ሥልጣን ሊኖረው አይችልም።

ይሁን እንጂ ይህንን ዐረፍተ ነገር በመጠኑ ግልጽ ማድረግ ይኖርብናል። መጽሐፍ ቅዱስ በቅጅዎቹ ሳይሆን በመጀመሪያው አንዳችም ስሕተት የለበትም። ይህም ማለት ሙሴ፥ ዳዊት፥ ጳውሎስ ወይም ሉቃስ ቅዱሳት መጻሕፍትን ሲጽፉ ሙሉ ለሙሉ የእግዚአብሔር ቃልና አንዳችም ስሕተት የሌለበት ነገር ጽፈዋል፤ ነገር ግን ሌሎች ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል በሚገለብጡበት (በሚቀዱበት) ጊዜ አንዳንድ ስሕተቶች ነበሩ ማለት ነው። በጥንት ዘመን በርካታ መጻሕፍትን ለማባዛት የሚያስችሉ ማተሚያ ቤቶች እንዳልነበሩ ማስታወስ ያስፈልጋል። ዛሬ እንኳ መጽሐፍ ቅዱስ በሚታተምበት ጊዜ የሆሄያት ስሕተት ሊኖር ይችላል፤ ስለዚህ ቅዱሳት መጻሕፍት በእጅ ሲጻፉ በዘመናት ሁሉ የነበሩ ጸሐፊዎች አንዳንድ ስሕተቶችን ሠርተዋል፥ ስለዚህ በአሁኑ ጊዜ ባሉት በርካታ ትርጉሞች ውስጥ ተርጓሚዎቹ አንዳንድ ጥቅሶችን በተለየ መንገድ ሊተረጉሙ እንደሚችሉ በመግለጥ የግርጌ ማስታወሻዎችን ጽፈዋል።

| |
|---|
| 4ኛ ጥያቄ፥ ማር.16ን በአዲሱ የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም ተመልከት። ከ9-20 ስላሉት ቁጥሮች በገጹ በስተግርጌ ላይ ምን ተጽፏል? |

ይህንን ሐቅ ለመረዳት ያስቸግራል። በአሁኑ ዘመን፥የመጀመሪያዎቹ ጹሑፎች የትኞቹ እንደነበሩ ለመወሰን ዐብይ ሥራቸው አድርገው የያዙት የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁራን አሉ። በሺህ የሚቆጠሩ የብሉይና የአዲስ ኪዳን ቅጂዎችን በመመልከት፥ የመጀመሪያው ቃል የቱ እንደነበር ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ ለመወሰን ይታገላሉ። የእነዚህ ምሁራን ሥራ ያላለቀ ስለሆነና እኛም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስላሉ ጥቅሶች መቶ በመቶ እርግጠኞች መሆን ባንችልም፥ ሆኖም ግን ምሁራኑ የሚከተሉትን ነገሮች ይነግሩናል።

1. መጽሐፍ ቅዱስ ከማንኛውም ሌላ ጥንታዊ መጽሐፍ በተሻለ ሁኔታ ተጠብቋል፤ ምክንያቱም አይሁዶችና ክርስቲያኖች የእግዚአብሔር ቃል እንደሆነ ያምኑ ስለነበር በትክክል ሊገለብጡት ይችሉ ዘንድ ከፍተኛ ጥንቃቄ አድርገዋል፤ ስለዚህ ከቁርአንም ሆነ ከማንኛውም ሌላ ጥንታዊ መጽሐፍ በተሻለ ሁኔታ ትክክለኛነቱ የተጠበቀ ነው። ደግሞም በሚጽፉበት ጊዜ ጸሐፊዎቹን የመራቸው መንፈስ ቅዱስ

በመሆኑ፥ ቅጂዎቹ ለዘመናት በሚጻፉበት ጊዜ ሁሉ ጉልህ ስሕተት እንዳይፈጽሙ ረድቶአቸዋል።

2. በተለያዩ ቅጂዎች መካከል ያሉት ልዩነቶች በአንድነት ሲታዩ፥ የአጠቃላዩ መጽሐፍ ቅዱስ ትንሽ ክፍል ናቸው። በሁሉም ቅዱሳት መጻሕፍት መካከል ስምምነት ስላለ፥ በእጃችን ያለው መጽሐፍ ቅዱስ ዘጠና ከመቶ በላይ (90%) ከመጀመሪያው መጽሐፍ ቅዱስ ጋር አንድ ዓይነት እንደሆነ እርግጠኞች ልንሆን እንችላለን።

3. በቅዱሳት መጻሕፍት ቅጂዎች መካከል ያለው ማንኛውም ልዩነት በየትኛውም የመጽሐፍ ቅዱስ ዋና ትምህርት ላይ ለውጥ የሚያመጣ አይደለም። ስለ እግዚአብሔር፥ ስለ ክርስቶስ ወይም ስለ መንፈስ ቅዱስ ማንነት፥ ስለ ደኅንነት መንገድ፥ ወዘተ ባለን ግንዛቤ ላይ የሚያመጡት አንዳችም ለውጥ የለም! ልዩነቶቹ እምነታችንን የሚለውጡ አይደሉም (ለምሳሌ በዕዝ. 2፡3-70ና በነህ. 7፡6-73 ያሉትን ዝርዝሮች አነጻጽር። በእነዚህ ሁለት ዝርዝሮች ውስጥ ያሉትን ልዩነቶች ጥቀስ)።

መ. መጽሐፍ ቅዱስ በነገሮች ሁሉ ላይ የመጨረሻው ባለሥልጣን ነው። እግዚአብሔር ማን እንደሆነ፥ ቀድሞ ምን እንዳደረገና ወደፊትም ምን እንደሚያደርግ፥ እንዲሁም ከፍጥረቱ የሚፈልገው ነገር ምን እንደሆነ በመናገር ረገድ የመጨረሻው ባለሥልጣን መጽሐፍ ቅዱስ ነው። ሌሎች እምነቶችና ልምምዶች በሙሉ መመዘን ያለባቸው በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ነው። የመጽሐፍ ቅዱስን ትምህርት የሚቃወም ማንኛውም ነገር ሊወገድ ይገባል።

| |
|---|
| 5ኛ ጥያቄ፡- ሀ) እንደ እግዚአብሔር ቃል ስሕተት ቢሆንም፥በሰዎች ዘንድ ግን እንደ መልካም የሚቆጠር አንድ ምሳሌ ከሕይወት ልምድህ ወይም ከምትኖርበት ባሕል ጥቀስ። ለ) ቤተ ክርስቲያንህ ሐሰተኛ ትምህርትን ለማሸነፍ ወይም እግዚአብሔር ከሰዎች ሕይወት የሚጠብቀው ነገር ምን እንደሆነ ለማስረዳት መጽሐፍ ቅዱስን በተሻለ ሁኔታ በንቃት ልትጠቀምበት የምትችልባቸውን መንገዶች ጥቀስ። |

ሠ. የመጽሐፍ ቅዱስ ዓላማ ስለ እግዚአብሔርና ስለ ፈቃዱ ልናውቀው የሚገባንን ሁሉ መንገር እንጂ እውነቶችን ሁሉ

ማሳወቅ አይደለም። መጽሐፍ ቅዱስ አሳብ የማይሰጥባቸውና ዳሩ ግን ልናውቃቸው የምንፈልጋቸው በርካታ ነገሮች ሊኖሩ ይችላሉ። ለምሳሌ:- እግዚአብሔር ዓለምን እንዴት እንደ ፈጠረ በግልጥ ለማወቅ እንጠይቅ ይሆናል፤ መጽሐፍ ቅዱስ ግን ስለዚህ በቂ ገለጣ አይሰጠንም፤ ነገር ግን ከእግዚአብሔር ጋር በእምነት እንድንራመድ የሚያስችሉን ነገሮች በሙሉ ተጠቅሰዋል። የመጽሐፍ ቅዱስ እምብርት እግዚአብሔር እንጂ ሰው አይደለም። የመጽሐፍ ቅዱስ ዓላማ እግዚአብሔር ማን እንደሆነ፥ ምን እንደሠራና ከሰው ምን እንደሚፈልግ መግለጥ ነው፤ ስለዚህ መጽሐፍ ቅዱስን በምናጠናበት ጊዜ ተቀዳሚው ትኩረታችን በእግዚአብሔር ላይ መሆን አለበት። እርሱንና ፈቃዱን በበለጠ ለመረዳት መጣር አለብን። እግዚአብሔርን እያወቅንና በትእዛዙ ብቻ ስንሄድ እንባረካለን።

6ኛ ጥያቄ:- ዳን. 11፡31-32 አንብብ። እግዚአብሔርን ለሚያውቁት የተሰጣቸው ተስፋ ምንድነው?

ረ. መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል ቢሆንም እንደ እግዚአብሔር ሊመለክ ግን አይገባውም። እኛ የምናመልከው እራሱን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የገለጠውን እግዚአብሔርን እንጂ መጽሐፍ ቅዱስን አይደለም። ይህ ማለት መጽሐፍ ቅዱስ በራሱ ምትሐት ወይም ኃይል የለውም ማለት ነው። እንደ መድኃኒት ልንጠቀምበት አይገባም። ለምሳሌ:- አንዳንድ ሰዎች አንድ ጥቅስ ከመጽሐፍ ቅዱስ ያጽፉና በአንገታቸው ላይ ያደርጋሉ፤ ከአደጋ ግን አይጠብቃቸውም፥ ወይም ቁስል ላይ ቢደረግ ፈውስ አይሰጥም። የመፈወስና የመጠበቅ ኃይል ያለው እግዚአብሔር ብቻ ነው።

7ኛ ጥያቄ:- ሀ) በእጃችን ያለው መጽሐፍ ቅዱስ በግዑዝ አካልነቱ የተለየ ኃይል እንዳለው የሚያምኑ ክርስቲያኖች አሉን? ለ) እንዴት አድርገው ይጠቀሙበታል? ሐ) ይህ ስሕተት የሆነው ለምንድን ነው? መ) የእግዚአብሔር ቃል ዓላማ ምንድን ነው።?

ሰ. መጽሐፍ ቅዱስ አንዳች ስሕተት የሌለበትና የተሟላ የእግዚአብሔር ቃል ነው። የአዲስ ኪዳን መደምደሚያ የሆነው የዮሐንስ ራእይ፥ ለመጽሐፍ ቅዱስም የመጨረሻው መጽሐፍ ነው

(ራእይ 22፡18-20 ተመልከት)። የምንጽፈው ወይም የምንናገረው ነገር እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ስሕተት የሌለበት ነው ልንል አንችልም። ይህ ማለት፡-

1. ማንም ሰው በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የሚጨመር ወይም መጽሐፍ ቅዱስን ሙሉ የሚያደርግ ሌላ መጽሐፍ ጽፌአለሁ ሊል አይችልም። ሌላ ወንጌል ወይም ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር እኩል ሥልጣን ያለው መጽሐፍ አለኝ የሚል ሰው ተሳስቶአል።

2. አንድ ሰባኪ በሚሰብክበት ጊዜ ወይም አንድ ጸሐፊ የመጽሐፍ ቅዱስ ማብራሪያ ወይም ለጥናት የሚያገለግል መጽሐፍ በሚጽፍበት ጊዜ፥ በተቻለው መጠን ትክክል የመሆን ሐላፊነት ያለበት ቢሆንም የሚናገረውና የሚጽፈው ነገር ስሕተት ሊኖርበት ይችላል። መጀመሪያ የመጽሐፍ ቅዱስ መጻሕፍትን የጻፉ ሰዎች የነበራቸው ሥልጣንና ብቃት ሊኖረው የሚችል ሌላ ተናጋሪ ወይም ጸሐፊ ጨርሶ ሊኖር አይችልም።

---

8ኛ ጥያቄ፡- ይህ እውነት ለሰባኪዎችና ለመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት መጻሕፍት ጸሐፊዎች ምን ማስተማር አለበት?

---

በምንሰብክበትና በምንጽፍበት ጊዜ ሁሉ በአእምሮአችን ልናስታውሳቸው የሚገባን ሁለት ነገሮች አሉ። የመጀመሪያው፥ እየሰበክን ወይም እየጻፍን ያለነው የእግዚአብሔር ቃል መሆኑን ሁልጊዜ የማስታወስ አስፈላጊነት ነው፤ ስለዚህ ዓቅማችን የፈቀደውን ያህል ትክክለኛ ሥራ ለመሥራት መጣር አለብን። ይህ ማለት ከመስበካችን ወይም ከመጻፋችን በፊት በሚገባ ልናጠናውና በምንሰጠው ትርጉም ከፍተኛ ጥንቃቄ ልናደርግ ይገባል ማለት ነው። ሁለተኛው ሰባክያን፥ አስተማሪዎች እንዲሁም ጸሐፊዎች እንደመሆናችን መጠን ትሑታን መሆን አለብን። በምድር ላይ ሳለን እውቀታችን ከፊል መሆኑንና ሁልጊዜ ትክክለኛ ሊሆን እንደማይችል እንደ ሐዋርያው ጳውሎስ ማስታወስ አለብን (1ኛ ቆሮ. 13፡12 ተመልከት)። ስለዚህ ሰዎች አንድን ክፍል የተረዱበት ሁኔታና ለእርሱም የሰጡት ትርጉም ከእኛ የተለየ ሲሆን እውነትን ሁሉ በሚገባ አለማወቃችንን በትሕትና ልንቀበል፥ የሌሎችን ሰዎች አተረጓጎም ለማዳመጥና በእግዚአብሔር ቃል ትምህርት ብርሃን ለመመርመር ፈቃደኞች መሆን አለብን። የመጽሐፍ ቅዱስን ግልጥ ትምህርት የሚቃወም ማንኛውም ነገር ስሕተት መሆኑ እርግጥ ነው፤ ነገር ግን

መጽሐፍ ቅዱስ ግልጥ የሆነ ትምህርት የማይሰጥባቸውን ርእሶች በሚመለከት ትሕትና ልናሳይና ለሌሎችም ሰዎች የተለየ አመለካከት እንዲኖራቸው ልንፈቅድ ይገባል።

ብሉይና አዲስ ኪዳንን ጨምሮ መጽሐፍ ቅዱስ ሙሉ የእግዚአብሔር ቃል ነው ብለን ካመንን፥ አንድ ሌላ ነገር ግልጥ ሆነ ማለት ነው። አዲስ ኪዳን በመጻፉ ስለ እግዚአብሔርና በሕይወታችን ውስጥ ስላለው ፈቃዱ ልናውቀው የሚገባን ነገር ሙሉ ሆኖአል ማለት ነው። ክርስቲያኖች ስለዚህ «አዲስ እውቀት» መፈለግ የለባቸውም። ይልቁንም እግዚአብሔር በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በገለጠው መሠረት ከእርሱ ጋር ያለንን ኅብረት ለማጽናት፥ በቃሉ ውስጥ ፈቃዱ እንደሆነ በግልጥ ያሳየንን ነገር ልንታዘዝ ይገባል። ከእግዚአብሔር ጋር ባለን ኅብረት እያደግን ስንሄድ አስደናቂ እውነቱን እንድንረዳ ማስተዋልንና ጥበብን አብዝቶ ይሰጠናል።

እነዚህ እውነቶች ስለ ብሉይ ኪዳን ምን ያስተምሩናል? ክርስቲያኖች እንደመሆናችን የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት በሙሉ የእግዚአብሔር ቃል መሆናቸውን መገንዘብ አለብን፤ ስለዚህ የእግዚአብሔርን ቃል በሙሉ ማጥናት የእኛ ኃላፊነት ነው። አምላካችን ማን እንደሆነና ከእኛ ምን እንደሚፈልግ ማወቅ አለብን። ስለዚህ የምንወደውንና የምናውቀውን ክፍል ብቻ ሳይሆን ብሉይ ኪዳንን በሙሉ ማጥናት አለብን። ኦሪት ዘሌዋውያን የመዝሙረ ዳዊትን ያህል ወይም ትንቢተ ሕዝቅኤል የ1ኛ ሳሙኤልን ያህል የእግዚአብሔር ቃል ነው። እያንዳንዱ መጽሐፍ ስለ እግዚአብሔርና ስለ ፈቃዱ የተወሰነ ነገር ያስተምረናል፤ ስለዚህ ከምንወደው ክፍል ብቻ ሳይሆን፥ ከሁሉም የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ልናጠናና ልናስተምር ያስፈልጋል።

> 9ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ብዙ ጊዜ የማናጠናቸውንና የማንሰብካቸውን የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ዘርዝር። ለ) የእግዚአብሔር ሰዎች ብዙውን ጊዜ እነዚህን መጻሕፍት የሚያልፉአቸው ለምንድነው? ሐ) ስለ እግዚአብሔር ፈቃድ የተሟላ አሳብና ትክክለኛ ግንዛቤ እንዲኖረን ቃሉን በሙሉ በቤተ ክርስቲያናችን ልናጠና የምንችልባቸው መንገዶች የትኞቹ ናቸው? መ) የእግዚአብሔርን ፈቃድ በከፊል ሳይሆን በሙሉ መረዳት የሚያስፈልገው ለምንድን ነው?

## 2ኛ ቀን፡- የብሉይ ኪዳን ቅጂዎቻችን እንዴት ሊደርሱን እንደቻሉ

እኛ ክርስቲያኖች የእግዚአብሔር ቃል ነው ብለን የምናምነው መጽሐፍ ቅዱስን ብቻ እንደሆነ ትናንትና ተመልክተናል። የእግዚአብሔርን ሙሉ ሥልጣን የያዘ ከመሆኑም ሌላ ክርስቲያን እውነትን የሚረዳበት መሠረት ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እግዚአብሔር ማንነቱን፥ ሰው ማን እንደሆነ፥ ከዘላለማዊ አምላክም ጋር ግንኙነት ለማድረግና እርሱን ደስ ለማሰኘት ምን ማድረግ እንዳለበት አስፈላጊውን እውነት ሁሉ እንደገለጠ እናምናለን። ዳሩ ግን ለመረዳት አስቸጋሪ የሆነ ሌላም እውነት ገልጾልናል። ይህም ክርስቲያኖች እንደመሆናችን መጠን የምናምነው እውነት አንዳችም ስሕተት የሌለበት የመጀመሪያው መጽሐፍ ቅዱስ ነው የሚል ነው። ዛሬ በእጃችን የሚገኘው መጽሐፍ ቅዱስ የያዛቸው ዋና ዋና ትምህርቶች ምንም ስሕተት የሌለባችው ቢሆኑም የመጽሐፍ ቅዱስ ቅጂዎችን በመገልበጥ ረገድ የታዩ አንዳንድ ስሕተቶች እንዳሉ እንገነዘባለን። ዛሬ በእጃችን ስላለው የመጽሐፍ ቅዱስ ቅጂ ጥቂት ነገሮችን እናጠናለን።

ብሉይ ኪዳን ረጅም ዕድሜ ያለው መጽሐፍ ነው። በ1400 ዓ.ዓ. አካባቢ ሙሴ የመጀመሪያዎቹን አምስት መጻሕፍት መጻፍ ጀመረ። ይህም ከ3500 ዓመታት ያህል በፊት ማለት ነው። የመጨረሻው የብሉይ ኪዳን መጽሐፍ የተጻፈው በ400 ዓ.ዓ. ገደማ ነበር፤ ስለዚህ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት በሙሉ ተጽፈው ለማለቅ 1000 ዓመታት ያህል ወስደዋል። በሌላ በኩል አዲስ ኪዳን ተጽፎ ያለቀው በ100 ዓ.ም. ነው። የአዲስ ኪዳን ዕድሜ በ2000 ዓመታት ያነሠ ነው፤ ስለዚህ አዲስ ኪዳንን በመገልበጥ ረገድ የተሠራው ስሕተት በብሉይ ኪዳን ከተሠራው ስሕተት ያነሰ ነው፤ ደግሞም ምሁራን የመጀመሪያዎቹ የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ከተጻፉ በኋላ በ150 ዓመታት ጊዜ ውስጥ ተሠርተው የነበሩ ቅጂዎችን በከርሰ ምድር ጥናት አማካኝነት አግኝተዋል፤ስለዚህ ምሁራን ከብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ይበልጥ የአዲስ ኪዳን መጻሕፍትን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ችለዋል። ምሁራን ያገኙአቸው አብዛኛዎቹ የብሉይ ኪዳን ቅጂዎች የመጀመሪያዎቹ መጻሕፍት ከተጻፉ ከብዙ መቶዎች ወይም ከአንድ ሺህ ዓመታት በኋላ የተገለበጡ ናቸው፤ ስለዚህ ከአዲስ ኪዳን

ይልቅ በርካታ ስሕተት የመፈጸም ዕድል ያለው በብሉይ ኪዳን ውስጥ ነው።

በጥንቱ ዓለም የጽሕፈት መኪናዎች፥ የጽሑፍ ማባዣዎችም ሆነ ወረቀት አልነበሩም። መጻሕፍት ሁሉ በእጅ መጻፍ ነበረባቸው። በጥንት ዘመን ሰዎች ለመጻፍ ይጠቀሙ የነበረው በተለያዩ ነገሮች ነበር። አንዳንዶች እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን ትእዛዝን በሚሰጥበት ጊዜ እንደተጠቀመው በድንጋይ ይጠቀማሉ (ዘጸ. 24፡12፤ 31፡18፤ ኢያ. 8፡32-35 ተመልከት)። ሌሎች በእርጥብ ሸክላ ላይ ይጽፉ ነበር። እርጥቡ ሸክላ ሲደርቅ በላዩ ላይ የተጻፈው ነገር ቋሚ ሆኖ ይቀራል። ሌሎች በእንስሳት ቆዳ ላይ ይጽፉ ነበር። በኋላ ደግሞ ሰዎች ፓፒረስ ተብሎ በሚጠራ ከሸምበቆ በተሠራ ነገር ላይ ይጽፉ ነበር። በድንጋይና በሸክላ የተጻፉት ነገሮች ለብዙ መቶ ዓመታት የቆዩ ቢሆኑም በእንስሳት ቆዳና በፓፒረስ የተጻፉት ግን ጊዜያዊና የሚበሰብሱ ነበሩ፤ ስለዚህ በሚያረጁበት ጊዜ ተገልብጠው ሌላ ቅጂ ሊዘጋጅላቸው ያስፈልግ ነበር። ሰዎች ለራሳቸው የግል ቅጂ እንዲኖራቸው ሲፈልጉም በእጃቸው በመጻፍ ሊገለብጡት ያስፈልግ ነበር። አይሁድ ብዙ ጊዜ የሚጽፉት በእንስሳት ቆዳ ላይ ሲሆን፥ እያንዳንዱ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል በብራና ጥቅል ላይ ይጻፍ ነበር። (ለምሳሌ ሉቃ. 4፡16-21)።

በጥንት ዘመን ብዙ ሰዎች ማንበብ አይችሉም ነበር። ጸሐፍት የተባሉ የተወሰኑ ሰዎች ብቻ ማንበብና መጻፍ ይችሉ ነበር። እነዚህ ሰዎች የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ደብተራዎችን የሚመስሉ ነበሩ። እነዚህ ጸሐፍት ለጥንታዊቷ እስራኤል በጣም አስፈላጊ ሰዎች ነበሩ። ለነገሥታቱ ልዩ አማካሪዎች በመሆናቸው፥ እንደ ዲፕሎማትና አምባሳደር ሆነው ወደ ሌሎች አገሮች ይላኩ ነበር። ለአይሁድ ግን ከሁሉ የሚበልጠው የእነዚህ ሰዎች ሥራ ቅዱሳት መጻሕፍትን መገልበጣቸው ነበር። ቅዱሳት መጻሕፍቱ ይቀመጡ የነበሩት ሰዎች በሚያመልኩበት በቤተ መቅደስ ስለነበር፥ በጥንቷ እስራኤል ጸሐፍቱ የአምልኮ መሪዎች የሆኑት ካህናትና ሌዋውያን ነበሩ። እነዚህ የጥንት ጸሐፍት የእግዚአብሔር ቃል ቅዱስ መሆኑን ያውቁ ስለነበር፥ ቅዱሳት መጻሕፍትን በጥንቃቄ ይገለብጡ ነበር። በ586 ዓ.ዓ. የኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ ከተደመሰሰና እስራኤላውያን በአሕዛብ መካከል ከተበተኑ በኋላ ቅዱሳት መጻሕፍትን ይገለብጡ የነበሩ ጸሐፍት ለአይሁድ ሕዝብ በጣም አስፈላጊ ሰዎች ሆኑ። እንደ ዕዝራ ያሉ ካህናት ጸሐፍት የሃይማኖት ሰዎች ሆኑ። እነዚህ ጸሐፍት (አንዳንድ ጊዜ

«የሕግ መምህራን» ይባሉ የነበሩ) ኢየሱስ በኖረበት ዘመን በሕዝቡ ላይ ታላቅ ሥልጣን ያላቸው ጠንካራ የፖለቲካ ፓርቲ ሆኑ። የኢየሱስ ጠላቶችም ነበሩ (ማቴ. 12፡38-39 ተመልከት)።

| |
|---|
| 10ኛ ጥያቄ፡- የብሉይ ኪዳን መጻሕፍትን ለመጠበቅ አይሁድ ያደረጉት ነገር ወይም ሁኔታ ከጥቂት ትውልድ በፊት የኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት በኢትዮጵያ ያደርጉት ከነበረው ሁኔታ ጋር እንዴት ይመሳሰላል? |

በ586 ዓ.ዓ. የኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ እስከተደመሰሰበት ጊዜ ድረስ መጽሐፍ ቅዱስን በመገልበጥ ረገድ ስሕተት ለመሥራት የሚያደርስ በቂ ምክንያት አልነበረም። ዋናው የመጽሐፍ ቅዱስ ቅጂ ያለው በኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ ውስጥ ነበር። እንደ እስራኤል ነገሥታት ያሉ አንዳንድ ሰዎች አንዳንድ ጊዜ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍትን ቢገለብጡም (ዘዳግ. 17፡18፤ 2ኛ ነገሥት 11፡12 ተመልከት)፤ ዛሬ በእጃችን እንዳለው የእግዚአብሔር ቃል በበርካታ ቁጥር አልነበረም። የእስራኤል ሕዝብ በዓለም ሁሉ በተበተኑበት ጊዜ ግን የተለያዩ ቅጅዎችና ትርጉሞች መኖር አስፈላጊ ሆነ። ለምሳሌ፡- እንደ ዳንኤልና ሕዝቅኤል ያሉ ሰዎች በባቢሎን ነበሩ። በባቢሎን ይኖሩ የነበሩ አይሁድ የራሳቸው የመጽሐፍ ቅዱስ ቅጂ ማግኘት አስፈለጋቸው። ብዙዎቹ አይሁድ በኋላ ወደ እስራኤል ቢመለሱም፥ ሌሎች በርካታ አይሁድ በባቢሎን ቀሩ። በባቢሎንም ሆነው ቅዱሳት መጻሕፍትን መገልበጥ ቀጠሉ። በባቢሎንና በኢየሩሳሌም ይኖሩ የነበሩ ጸሐፍት ቅጂዎቻቸውን ለማወዳደር ዕድሉ አልነበራቸውም፤ ስለዚህ በየስፍራው ባሉት ቅጂዎች መካከል ልዩነቶች መታየት ጀመሩ። ደግሞም በ200 ዓ.ዓ. አንዳንድ አይሁድ በግሪክ ቋንቋ የእግዚአብሔር ቃል አስፈለጋቸው። በግብፅና በሌሎች አካባቢዎች ስለኖሩና መጀመሪያ መጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈበትን የዕብራይስጥን ቋንቋ ስለረሱ በሚናገሩት በግሪክ ቋንቋ መጽሐፍ ቅዱስ አስፈለጋቸው፤ ስለዚህ ምሁራን ብሉይ ኪዳንን ወደ ግሪክ ቋንቋ ተረጎሙት። ይህም ትርጉም ሴፕቱዋጀንት በመባል ይታወቅ ጀመር። ክርስቶስ በኖረበት ዘመን ሴፕቱዋጀንት እጅግ ተወዳጅ ቅዱስ መጽሐፍ ሲሆን፥ ብዙ የአዲስ ኪዳን ጸሐፊዎችም ከዚህ ትርጉም ይጠቅሱ ነበር፤ ስለዚህ ሦስት ዋና ዋና የብሉይ ኪዳን ቅጂዎች አሉን። እነርሱም በኢየሩሳሌም የነበረው፥ በባቢሎን የነበረውና በግሪክ ቋንቋ የተጻፈው ናቸው (ከዚህ በታች ያለውን ሠንጠረዥ ተመልከት)። በሌሎች ስፍራዎች የነበሩ ሰዎችም የየራሳቸውን

ቅጅ መገልበጥ ጀመሩ። ለምሳሌ፡- ሳምራውያን አምስቱን የሙሴ መጻሕፍት (ፔንታቱክ) ለራሳቸው አምልኮ ገለበጡ፤ ስለዚህ በአዲስ ኪዳን ዘመን በርካታ የብሉይ ኪዳን ቅጂዎች ሲኖሩ፥ ማንም ሰው በቅጂው ውስጥ ስሕተት እንደነበረና እንዳልነበረ ለማወቅ አላወዳደረም፤ ስለዚህ በትርጉሞች ውስጥ ስሕተቶች እየጨመሩ መጡ። የትርጉሞች ወይም የቅጂዎች ስሕተቶችም እየጨመሩ የመጡት ጸሐፊዎቹ በሚገለብጡበት ጊዜ በሠሩት ስሕተት ምክንያት ነው።

**የመጀመሪያዎቹ መጻሕፍት**

| የግሪኩ መጽሐፍ ቅዱስ | የኢየሩሳሌም መጽሐፍ ቅዱስ | የባቢሎን መጽሐፍ ቅዱስ |
|---|---|---|

የመጻሕፍቱን ቅጂዎች በመገልበጥ እንዴት ስሕተቱ ሊፈጸም እንደሚችል የሚከተለውን መግለጫ እንመልከት፡- የማዕከላዊው ቤተ ክርስቲያን ጽሕፈት ቤት በየአውራጃው ለሚገኙ የአብያተ ክርስቲያናት ጽሕፈት ቤቶች አንድ ደብዳቤ እንደላከ አስብ። በደብዳቤውም ውስጥ የተወሰኑ መመሪያዎችና ደንቦች ነበሩ። እነዚህ የአውራጃ አብያተ ክርስቲያናት ይህንን ደብዳቤ በእጃቸው ገልብጠው ለወረዳ አብያተ ክርስቲያናት ቢሮዎች ይልካሉ፤ የወረዳ አብያተ ክርስቲያናት ቢሮዎች ደግሞ ይህን ደብዳቤ በእጃቸው ገልብጠው ለየአብያተ ክርስቲያናት ቢሮዎች ይልካሉ። እያንዳንዱ ቤተ ክርስቲያን ደግሞ ደብዳቤዎችን በእጁ ገልብጦ ለየአባላቱ ማደል ነበረበት እንበል። ይህን ነገር ማድረግ ቢኖርብን በዚህ ሂደት ውስጥ የሚሆኑ ሁለት ዋና ነገሮች ሲፈጸሙ እናይ ነበር። የመጀመሪያው፥ በእጅ በመገልበጥ ረገድ ስሕተት መታየት መጀመሩ ነው። ሰዎች በእጃቸው በመጻፍ በሚገለብጡበት ጊዜ አንዳንድ ፊደላትን ወይም ቃላትን ይተዋሉ። ደብዳቤው ከማዕከላዊው ቢሮ ማለትም መጀመሪያ ከተጻፈበት ቦታ እየራቀ በሄደ ቁጥር የስሕተቱ መጠን እየጨመረ ይሄዳል። ሁለተኛው፥ ስሕተቶቹ አንድ የተወሰነ መንገድ የሚከተሉ መሆናቸው ነው። አንድ የአውራጃ ቤተ ክርስቲያን ጽሕፈት ቤት ከማዕከላዊ ቤተ ክርስቲያን ጽሕፈት ቤት የመጣውን ደብዳቤ በሚገለብጥበት ጊዜ አንድ ቃል ቢተው ከዚያ አውራጃ ቤተ ክርስቲያን ጽሕፈት ቤት ደብዳቤ የሚደርሳቸው የወረዳ ቤተ ክርስቲያን ጽሕፈት

ቤቶች ሁሉ ተመሳሳይ ስሕተት የያዙ ይሆናሉ። ይህም ስሕተት ያንን ቃል ያለመያዝ ይሆናል።

የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት በተለያዩ ስፍራዎች በእጅ ጽሑፍ በሚገለበጡበት ጊዜም የተሠራው ስሕተት ይህንኑ የመሰለ ነበር፤ ስለዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁራን ያደረጉት አንድ ዋና ነገር ስሕተቱ ከየት እንደመጣ ለማወቅ የተገኙትን የተለያዩ ቅጂዎች ማወዳደር ነበር። በኢየሩሳሌም የተገለበጡትን መዛግብት ከባቢሎን፥ ከግሪክ እንዲሁም በኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ከሚገኘው የግዕዝ መጽሐፍ ቅዱስ ጋር ሁሉ ያመሳክራሉ። በዚህ ዓይነት የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁራን ከመጀመሪያው መጽሐፍ ቅዱስ ጋር የበለጠ የሚቀራረበው የትኛው እንደሆነ ለመወሰን የማያቋርጥ ጥረት እያደረጉ ነው። የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁራን ይህን በማድረግ ረገድ እርስ በእርስ ያልተስማሙበት ነገር ስለሚኖር ዛሬ በእጃችን ባሉ መጽሐፍ ቅዱሶች መካከል የትርጉም ልዩነት ሊኖር ቻለ።

በምዕራቡ ዓለም የሚገኙ አብዛኞቹ ቅዱሳት መጻሕፍት የተመሠረቱት ማሶሬቲክ በአይሁዶች በመባል በሚታወቁ አንዳንድ አይሁዳዊያን በተዘጋጀው የዕብራይስጥ መጽሐፍ ቅዱስ ላይ ነው። እነዚህ አይሁድ የኖሩትና የሠሩት ከ500-900 ዓ.ም. ባለው ጊዜ ነው። በዚያን ጊዜ ያገኙትን ሁሉንም መጽሐፍ ቅዱስ ወስደው የበለጠ ትክክል ነው ብለው ያሰቡትን ቅጂ ጻፉ። የላቲኑ (የሮማ ካቶሊክ መጽሐፍ ቅዱስና) በአሁኑ ጊዜ ብዙ የምንጠቀምባቸው ሌሎች መጽሐፍ ቅዱሶች የተተረጎሙት በእነዚህ አይሁድ ሥራ ላይ በመመሥረት ነው። እንደ ሶርያ፥ የሩሲያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያናት የሚጠቀሙበት መጽሐፍ ቅዱስና የግዕዝ መጽሐፍ ቅዱስ ዋና ምንጫቸው ሴፕቱዋጀንት የተባለው የግሪክ መጽሐፍ ቅዱስ ነው። (ሴፕቱዋጀንት ማለት ሰባ ማለት ነው። ይህ ስም የተሰጠው ብሉይ ኪዳንን ሰባ የሚሆኑ የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁራን በሰባ ቀናት ውስጥ ተርጉመውታል ተብሎ ስለሚታመን ነው)። ይህም ዛሬ በምንጠቀምበት በአማርኛው መጽሐፍ ቅዱስ ላይ እንዴት መጠነኛ ልዩነት እንዳመጣ በኋላ እንመለከታለን።

በ1948 ዓ.ም. የከርሰ ምድር አጥኚዎች በእስራኤል ውስጥ ሙት ባሕር በሚባለው አካባቢ ባለ ዋሻ ውስጥ በ200 ዓ.ዓ. የተጻፉ ቅዱሳት መጻሕፍትን አገኙ። የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁራን እነዚህን ቅዱሳት መጻሕፍት (የሙት ባሕር ብራናዎች በመባል የታወቁትን) አሁን በእጃችን

ከሚገኙ ቅጂዎች ጋር ሲያወዳድሩአቸው አንዳንድ ልዩነት ቢያገኙም በተመሳሳይነታቸውና የእግዚአብሔር ቃል በዘመናት ሁሉ በሚገለበጥበት ጊዜ በአንፃራዊነት ሲታይ በተገኘው ጥቂት ስሕተት ተደንቀዋል። ይህ እንዴት ሊሆን ቻለ? እኛ ክርስቲያኖች የመጽሐፍ ቅዱስ ደራሲ የሆነው እግዚአብሔር በዘመናት ሁሉ ለመለወጥ ይቃጣ የነበረውን የተለመደ አዝማሚያ እንደተቋቋመው እናምናለን። ትላንትና እንዳየነው እግዚአብሔር ቃሉን በሚያስደንቅ መንገድ ስለጠበቀው ዛሬ በእጃችን ያለው መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔርን ስለማወቅና ከእርሱ ጋር እንዴት ግንኙነት እንደምናደርግ የሚያስፈልገንን እንደሚነግረን እርግጠኞች ነን።

> 11ኛ ጥያቄ፥ አንድ ሙስሊም መጽሐፍ ቅዱስ ስሕተት የሞላበት ነው፤ ስለዚህ የእግዚአብሔር ቃል አይደለም ቢልህ እንዴት ትመልስለታለህ?

## 3ኛ ቀን:- መጽሐፍ ቅዱስን ለመተርጎም የሚጠቅሙ አጠቃላይ ሕጎች

> 12ኛ ጥያቄ፥ ሀ) እግዚአብሔር ለአንተ የተናገረባቸውን የተለያዩ መንገዶች ዘርዝር። ለ) በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እግዚአብሔር ለሰዎች የተናገረባቸውን የተለያዩ መንገዶች ዘርዝር (ዕብ. 1፡1-2 ተመልከት)።

በዘመናት ሁሉ እግዚአብሔር ራሱንና ፈቃዱን ለሰዎች በተለያዩ መንገዶች ገልጿል። ለአንዳንዶች እግዚአብሔር በቀጥታ በሚሰማ ድምፅ ተናግሯል። ለሌሎች በሕልምና በራእይ ተናግሯቸዋል። አንዳንዶች የእግዚአብሔር ግፊት በልባቸው ይሰማቸዋል። እግዚአብሔር እስካሁንም ድረስ ራሱንና ፈቃዱን በእነዚህ መንገዶች የሚገልጽ ቢሆንም፥ ዛሬ ራሱንና ፈቃዱን የሚገልጥበት ዋና መንገድ መጽሐፍ ቅዱስ ነው። ይህ እውነት በጣም አስፈላጊ የሆኑ ሁለት ጭብጦችን ያስተምረናል:-

1. እያንዳንዱ ክርስቲያን እግዚአብሔርን በጥልቀት ለማወቅ ብቻ ሳይሆን፥ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማወቅና ለመታዘዝ ቃሉን የማንበብና የማጥናት ኃላፊነት አለበት። ክርስቲያን የእግዚአብሔርን ቃል ማንበብ ስለሚችል እግዚአብሔርን ላለመታዘዝ ምንም ምክንያት ማቅረብ አይችልም። ማንበብና መጻፍ የማይችሉ ክርስቲያኖች እንዲማሩ የሚያነቃቃቸው አንዱ ነገር የእግዚአብሔርን ቃል

ለማንበብ እንዲችሉ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ በእያንዳንዱ ነገድ ቋንቋ እንዲተረጎም የሚያስፈልግበት አንዱ ዋና ምክንያት ይህ ነው። እግዚአብሔር ፈቃዱ ከእኛ እንዲሰወር አይሻም፤ ይልቁንም እርሱን እንድናውቀውና በፈቃዱ እንድንኖር ይፈልጋል። መጽሐፍ ቅዱስ በእያንዳንዱ ሰው ቋንቋ ሊጻፍ ይገባዋል፤ ምክንያቱም ይህ ሲሆን ሰዎች ያነበቡትን ነገር በግልጥ ይረዱታል። በዚህ መንገድ ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት ማድረግና እርሱን የበለጠ በማወቅ ለፈቃዱ ታዛዥ መሆን ይቻላል።

| |
|---|
| 13ኛ ጥያቄ፥ ሀ) ለመጽሐፍ ቅዱስ ትርጓሜ ሥራ ድጋፍ ለማድረግ ስለ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች ኃላፊነት ይህ ምን ሊያስተምረን ይገባል? ለ) የቤተ ክርስቲያን አባላት በግላቸው መጽሐፍ ቅዱስን ያጠኑ ዘንድ ለማበረታታት ስለ መሪዎች ኃላፊነት ይህ ምን ያስተምረናል? |

2. እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ግንኙነት ማድረግ የሚችልባቸው የተለያዩ መንገዶች በመጽሐፍ ቅዱስ ዳኝነት መመዘን አለባቸው። ብዙ ሐሰተኞች አስተማሪዎች ብድግ እያሉ እግዚአብሔር ተናግሮአል ይላሉ፤ ነገር ግን ተናግሮናል የሚሉት ነገር እግዚአብሔር በቃሉ በግልጥ ከተናገረው ነገር ጋር የሚቃረን ነው። ሰይጣንም ሕልምን መስጠት ይችላል። ሰይጣንም አንዳንድ ነገሮችን እንድናደርግ በልባችን ሊያነሣሣን ይችላል። እውነትን ከውሸት ለመለየት የምንችለው ሐሰተኛ አስተማሪዎች የሚናገሩትን ነገር ከእግዚአብሔር ቃል ጋር በማወዳደር ብቻ ነው። እግዚአብሔር የማይዋሽና የማይለወጥ ስለሆነ ዛሬ ለእኛ የሚገለጥልን ነገር ሁሉ በመጽሐፍ ቅዱስ ከገለጠው ነገር ጋር የግድ መስማማት አለበት።

| |
|---|
| 14ኛ ጥያቄ፥ ሀ) አንዳንድ ሰዎች እግዚአብሔር ተናገረን የሚሉበትን መንገድ ለመግለጥ የሚያስችሉ መግለጫዎችን ዘርዝር። ለ) ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር ስታወዳድረው እነዚህ ሰዎች የሚሉት ነገር ከእግዚአብሔር ጋር ይስማማል ወይስ ይቃረናል? ሐ) ሐሰተኛ አስተማሪዎች እግዚአብሔር ተናገረን ሲሉ ሰምተህ ታውቃለህን? መ) እግዚአብሔር በቃሉ እንዴት እንደተናገረህ የሚያስረዱ ምሳሌዎችን ጥቀስ። |

መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ራሱንና ፈቃዱን ለሰው ልጆች የገለጠበትና ዛሬም የሚገልጥበት መንገድ ነው ካልን፥ ልጆቹ እንደ መሆናችን ቃሉን ማጥናት ተቀዳሚ ተግባራችን መሆን አለበት።

እግዚአብሔር መጽሐፍ ቅዱስን የሰጠን ከእርሱ ጋር የግል ግንኙነት ለመመሥረት እንድንችል ነው፤ ስለዚህ ከእግዚአብሔር ጋር በጸሎት ብቻ ሳይሆን ያለማቋረጥ መጽሐፍ ቅዱስን በማንበብ ካልተገናኘን እግዚአብሔር እንድናውቀው የሚፈልገውን ያህል እርሱን አናውቀውም።

| |
|---|
| 15ኛ ጥያቄ፥ ሀ) ብዙ ክርስቲያኖች የእግዚአብሔርን ቃል ለማንበብ በጣም ጥቂት ጊዜ የሚሰጡት ለምንድነው? ለ) የእግዚአብሔርን ቃል ከማንበብና ከመጸለይ በጣም አስፈላጊ የሆነው የትኛው ይመስልሃል? ለምን? |

ከእግዚአብሔር ጋር ባለን ግንኙነት ያለማቋረጥ ልንከተላቸው የሚገባን ሁለት መንፈሳዊ ሥርዓቶች አሉ። ከእነዚህም አንዱ ጸሎት ነው። ብዙ ሰዎች በጸሎት ጊዜያቸውን ማሳለፍ ይወዳሉ። ለመጸለይ በማለዳ ይነቃሉ። ስለብዙ ነገር ይጸልያሉ። አንዳንድ ጊዜ ለእግዚአብሔር የልመና ጸሎት ብቻ ስለሚያቀርቡ ጸሎታቸው የስስታምነት ይሆናል። በጸሎታቸው እግዚአብሔርን ለማምለክና ለማመስገን ጥቂት ጊዜ ብቻ ይሰጣሉ። በጸሎት ከእግዚአብሔር ጋር እንነጋገራለን፥ እናመልከዋለንም። ደግሞም የከበደንን ነገር ወደ እርሱ ዘንድ በማምጣት እርሱ እንዲያቃልለው እንለምነዋለን፤ ነገር ግን እግዚአብሔር ለእኛ ሊናገረንና እርሱን ልናደምጠውም ይገባል። ሁለተኛው መንፈሳዊ ሥርዓት የእግዚአብሔርን ቃል ማንበብ ነው። የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ እኛን የሚናገረን፥ የሚያበረታታን፥ የሚመራን፥ ራሱንና ፈቃዱን ለእኛ የሚገልጠው . . . ወዘተ በቃሉ ነው። ክርስቲያን በመንፈሳዊ ሕይወቱ እንዲያድግ መጸለይና መጽሐፍ ቅዱስን ማንበብ ሚዛናዊ በሆነ መንገድ ሊከናወኑ ይገባል። ሁለቱም እኩል አስፈላጊዎች ናቸው።

| |
|---|
| 16ኛ ጥያቄ፥ የዚህ ሳምንት የጸሎት ጊዜህን መርምር። ሀ) የእግዚአብሔርን ቃል ለማንበብ ምን ያህል ጊዜ እንደወሰድክ ተከታተል። ለ) ለመጸለይ ምን ያህል ጊዜ እንደወሰድህ ጻፍ። ሐ) አንተ ልታደርገው ቀለል የሚልህ የትኛውን ነው? ለምን? መ) በሕይወትህ ውስጥ ጸሎትንና የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናትን እንዴት የማያቋርጥ ልምምድ ማድረግ ትችላለህ? |

ብዙ ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስን በተለይም ብሉይ ኪዳንን ለመረዳት በጣም አስቸጋሪ እንደሆነ አድርገው ይገምታሉ፤ ስለዚህ

የሚወዱአቸውንና የሚረዱአችውን ክፍሎች ያነብባሉ። ለመረዳት የሚከብዱትንና አስቸጋሪ የሆኑትን ክፍሎች አያነብቧቸውም።

**17ኛ ጥያቄ፥ ብዙ ጊዜ የማታነብባቸውንና ለመረዳት አስቸጋሪ የሚሆኑብህ ክፍሎች ያሉባቸውን የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ዘርዝር።**

ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ በሙሉ የእግዚአብሔር ቃል ከሆነ፥ እግዚአብሔር ለእያንዳንዱ መጽሐፍና ምንባብ ዓላማ አለው፤ ስለዚህ መጽሐፍ ቅዱስን በሙሉ ማንበብና መረዳት ለሁላችንም ጠቃሚ ነው። በጣም አስቸጋሪ የሆኑ የብሉይ ኪዳን ክፍሎች እንኳ ስለ እግዚአብሔርና ስለ ፈቃዱ የሚገልጡት ነገር አላቸው። እጅግ ከባድ የምንላቸው ክፍሎች ሁሉ «ለትምህርት፥ ለተግሣጽ፥ ልብን ለማቅናትና ጻድቅ ለሆነ ምክር» የሚጠቅሙ ናቸው (2ኛ ጢሞ. 3፡16)፤ ስለዚህ እግዚአብሔር በቃሉ በሚገኙ የተለያዩ ክፍሎች በኩል ለእኛ ሊገልጥ የፈለገውን ፈቃዱን መረዳት ጠቃሚ ነው። ብሉይ ኪዳንን በምናጠናበት ጊዜ በጣም አስቸጋሪ በሆኑ መጻሕፍት ውስጥ እንኳ የእግዚአብሔር ዓላማና መልእክት ምን እንደሆነ ለመረዳት እንጥራለን። መጽሐፍ ቅዱስን ለመረዳትና በትክክል ለመተርጎም ስንፈልግ ልናስታውሳቸው የሚገቡ ሦስት መሠረታዊ እውነቶች አሉ፡-

1. የመጽሐፍ ቅዱስ መሠረታዊ ትምህርት (መልእክት) ግልጥ ነው፤ ማንኛውም ክርስቲያን ሊያነበውና ሊረዳው ይችላል።

እግዚአብሔር የጻፈው የተደበቀ መልእክት አይደለም። ፈቃዱ እንዲታወቅና ልጆቹ ሁሉ እንዲከተሉት ይፈልጋል። እኛ ልጆቻችን በሚገባቸው መንገድ አንድን ነገር እንዲያደርጉ ትእዛዝ እንደምንሰጣቸው ሁሉ እግዚአብሔርም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ትእዛዛቱን የሰጠው ክርስቲያኖች ሁሉ እርሱ የገለጠውን ነገር መረዳት በሚችሉበት መንገድ ነው። የእግዚአብሔርን ቃል በማስተዋል የሚያነብ ማንኛውም ክርስቲያን እግዚአብሔር ማን እንደሆነ፥ ሰዎች ኃጢአተኞች እንደሆኑና ክርስቶስ ለሰዎች ኃጢአት ሁሉ በመስቀል ላይ እንዴት እንደሞተ በቂ ግንዛቤ ያገኛል። የእግዚአብሔር ቃል መረዳት የተሰጠው «ለተማሩ» ወይም «በመጽሐፍ ቅዱስ» ወይም በሥነ መለኮት ትምህርት ዲግሪ ላላቸው ብቻ አይደለም። የእግዚአብሔርን ቃል ለማጥናት ሰፊ ጊዜ የሰጡና የብሉይ ኪዳንን ዘመንና ባሕል በከፍተኛ ሁኔታ የተገነዘቡ ሰዎች የበለጠ ሊረዱአቸው የሚችሉአቸው አስቸጋሪ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶች

ቢኖሩም፥ መሪዎች እንደመሆናችን መጠን መጽሐፍ ቅዱስ እኛ ብቻ ልንረዳው የምንችልና ለእነርሱ ግን በጣም ከባድ ነው ብለን ለቤተ ክርስቲያናችን ምእመናን በፍጹም መናገር የለብንም። በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት መሠረት ክርስቲያኖች ሁሉ የእግዚአብሔር ካህናት ስለሆኑ፥ የእግዚአብሔርን ቃል በመንፈስ ቅዱስ እርዳታ ሊያጠኑና ሊተረጉሙት ይችላሉ (1ኛ ጴጥ. 2፡4-10፤ 1ኛ ዮሐ. 2፡27 ተመልከት)።

18ኛ ጥያቄ፥ ክርስቲያኖች መጽሐፍ ቅዱስን መረዳት የሚችሉት ልዩ መሪዎች ብቻ እንደሆኑ በማሰብ መጽሐፍ ቅዱሳቸውን ለራሳቸው ማጥናት በሚያቆሙበት ጊዜ አደገኛ የሚሆነው ለምንድነው?

2. እግዚአብሔር ራሱንና ፈቃዱን ለሰው ልጆች ሁሉ በግልጽ ገልጧል። የጻፈው የተደበቀ መልእክት አይደለም።

ብዙ ክርስቲያኖች እግዚአብሔር መጽሐፍ ቅዱስን የጻፈው «በሰምና ወርቅ» ነው ብለው ያስባሉ። እግዚአብሔር መጽሐፍ ቅዱስ እንዲጻፍ በሚያደርግበት ጊዜ የተጻፈውን ነገር እውነተኛ ትርጉም ከቃላቱ በስተጀርባ ሰውሮታል ብለው ይገምታሉ። ስለዚህ መጽሐፍ ቅዱስን ለመተርጎም በሚሞክሩበት ጊዜ ዘወትር የተሰወረ ትርጉምን ይፈልጋሉ። የምናመልከው አምላክ ግን ራሱንና ፈቃዱን በምሥጢራዊ ቃላት የሚሰውር አይደለም። እግዚአብሔር እኛን በቀጥታ ይናገረናል፤ እንድናውቀውና እንድንታዘዘውም ይፈልጋል።

ጓደኞችን ስለ ሕይወት በማንሣት አንድ ነገር እንድናደርግለት በመጠየቅ ደብዳቤ ቢጽፍልን የተሰወረ ትርጉም ከደብዳቤው መፈለግ የተለመደ አይደለም። የጻፈውን መልእክት እንዳለ እንቀበለዋለን። የእግዚአብሔርም ቃል ከዚህ ጋር ተመሳሳይ ነው። በአንድ በኩል ስናየው እግዚአብሔር ለእኛ የጻፈው ደብዳቤ ነው። እግዚአብሔር ስለ ራሱ ይነግረናል። ደግሞም እስካሁን ምን ሲያደርግ እንደነበረና እኛ ምን እንድናደርግ እንደሚፈልግ ይነግረናል። እግዚአብሔር ራሱንና ፈቃዱን ምሥጢራዊ ትርጉም ያላቸውን ቃላት በመጠቀም መደበቅ ልማዱ አይደለም።

3. ብዙ ጊዜ መጽሐፍ ቅዱስን ለመረዳት አስቸጋሪ የሆነው ከእኛ የተለየ ቋንቋ ለሚናገሩና በተለየ ባሕል ውስጥ ለሚኖሩ ሰዎች የተጻፈ በመሆኑ ነው።

ሁላችንም ብንሆን አንድን ነገር በምንሠራበት ወይም በምንናገርበት ጊዜ ሰዎች በተሳሳተ መንገድ ይረዱን ይሆንን? የሚል ፍርሃት ያደረብን ጊዜ ነበር። የራሳችንን ቋንቋ የሚናገሩና ከሁሉ በተሻለ ሁኔታ የሚያውቁን ቤተሰቦቻችን እንኳ አንዳንድ ጊዜ በተሳሳተ መንገድ ይረዱናል። በዕድሜ የገፉ አዛውንት ወጣቶችን፥ ወጣቶች ደግሞ አዛውንትን በተሳሳተ መንገድ ይረዷቸዋል። ይህ ደግሞ የተለያየ ቋንቋ በሚናገሩና የተለያየ ባሕል ባላቸው ሰዎች መካከል ያለ ነው። በርካታ ያለመግባባቶች ሊፈጠሩ ይችላሉ። በተለይም በተሳሳተ መንገድ መረዳት ሊኖር የሚችልባቸው ሁለት ሁኔታዎች አሉ፡-

ሀ. የሰዎችን ቋንቋ በተሳሳተ መንገድ መረዳት፥ የእንግሊዝኛ ቋንቋ የምታውቁ ሰዎች ከአፍ መፍቻ ቋንቋችሁ ጋር አንድ ዓይነት ወይም ፍጹም ተመሳሳይ የሆነ ትርጉም የሌላቸው በርካታ የእንግሊዝኛ ቃላት እንዳሉ ትገነዘባላችሁ። በቋንቋችሁ ሁለት ዓይነት ትርጉም የሚሰጡ ቃላት ከእንግሊዝኛው ትርጉም የተለዩ ናቸው። ብሉይ ኪዳን የአይሁድ ቋንቋ በሆነው ዕብራይስጥ ተጻፈ። ወደ አማርኛ፥ ወደ ኦሮምኛ፥ ወይም ወደ እንግሊዝኛ በሚተረጎምበት ጊዜ መጀመሪያ በተጻፈበት በዕብራይስጥ የነበረውን ዓይነት ትርጉም እንዲሰጥ ማድረግ ከባድ ነው፤ ስለዚህ ነው ለአንድ ቃል የተለያዩ ትርጉሞች የሚሰጡት። የግዕዝን ቋንቋ የማያውቁ ወይም አማርኛ የመጀመሪያ ቋንቋቸው ያልሆነ ብዙ ኢትዮጵያውያን በቀድሞው የአማርኛ ትርጉም ውስጥ ያሉ አንዳንድ ቃላት ምንም ስሜት አይሰጧቸውም፤ ስለዚህ እግዚአብሔር ሊለው የፈለገውን ነገር በተሳሳተ መንገድ ሊረዱ ወይም የእግዚአብሔርን ቃል መረዳት ከባድ ሊሆንባቸው ይችላል።

ለ. የሌሎችን ብሔረሰቦች ባሕል በተሳሳተ መንገድ መረዳት፥ ሁላችንም የምንኖረው በኢትዮጵያ ውስጥ ቢሆንም በአገሪቱ ውስጥ የተለያዩ ብሔረሰቦች መኖራቸው እርግጥ ነው። እያንዳንዱ ብሔረሰብ የራሱ የሆነ ባሕል ስላለው ከተለያዩ ብሔረሰቦች የሆኑ ሰዎች በአንድ ላይ ሲሆኑ፥ ብዙ ጊዜ አንዱ ሌላውን በተሳሳተ መንገድ ይረዳዋል፤ለምሳሌ በአንዳንድ ባሕሎች ለአንድ ሰው አንድን ነገር በግራ እጅ መስጠት ነውር ነው። በሌሎች ባሕሎች

ደግሞ በግራም ሆነ በቀኝ መስጠት ምንም ልዩነት አያመጣም። ለአንድ ባሕል ነውር የሆነው ነገር ለሌላው ባሕል ምንም አይደለም። ነገር ግን እንዲህ ዓይነት ቀላል ነገር ሳይቀር በሰዎች መካከል ያለመግባባትን ሊያመጣ ይችላል። በተመሳሳይ መንገድ ብሉይ ኪዳን የተጻፈው የራሳቸው ባሕል ላላቸው አይሁድ ነው። በኢትዮጵያ ውስጥ ለምንኖረው ለእኛ ወይም በተለይ ላለንበት ብሔረሰብ የተጻፈ አይደለም። ይህም ማለት አንዳንድ ጊዜ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉትን አንዳንድ ክስተቶች በተሳሳተ መንገድ ልንረዳ እንችላለን ማለት ነው። ወይም ደግሞ አንድን ተግባር ላንረዳው ስለምንችል የብሉይ ኪዳንን አንዳንድ ክፍሎች ከሕይወታችን ጋር ለማዛመድ በጣም ልንቸገር እንችላለን።

በእነዚህ ሁለት መንገዶች መጽሐፍ ቅዱስን በተሳሳተ መንገድ መረዳት በጣም ቀላል ስለሆነ ሁለት ነገሮችን በማድረግ በተሻለ መንገድ ለመረዳት መሞከር አለብን፡- የመጀመሪያው በዚያ ስፍራ በሥራ ላይ የዋሉትን ቃላት ትክክለኛ ትርጉም መረዳታችንን ማረጋገጥ አለብን። ለእግዚአብሔር ቃል ያለንን ትክክለኛ መረዳት ያዛቡብናል ብለን የምናስባቸውን ቃላት በትክክል ለመረዳት የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላትና ሌሎች የማብራሪያ መጻሕፍትን መጠቀም ይኖርብናል። ለምሳሌ፡- ደኅንነት፥ መዋጀት፥ቅድስናና ጽድቅ የሚሉት ቃላት ለአይሁዳውያን የሚሰጡትን ትርጉም መረዳት አለብን። ሁለተኛው ነገር፥ የእግዚአብሔርን ቃል በትክክል መተርጎም እንችል ዘንድና የአይሁዳውያንን ባሕል በትክክል ለመረዳት በመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላትና በሌሎች የማብራሪያ መጻሕፍት መጠቀሙ አስፈላጊ ነው።

19ኛ ጥያቄ፥ ሀ) መጽሐፍ ቅዱስን በምናጠናበትና በምንተረጉምበት ጊዜ ከላይ የተጠቀሱትን ሦስት እውነቶች ልናስተውላቸው የሚገባን ለምንድን ነው ብለህ ታስባለህ? ለ) እነዚህን መመሪያዎች የማይከተሉ ሰዎች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንዴት የእግዚአብሔርን ቃል በተሰሳተ መንገድ እንደተረጎሙት ግለጥ።

ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል በተሻለ ሁኔታ እንዲረዱና እንዲተረጉሙት ለመርዳት የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁራን ልንከተላቸው የሚገባን አንዳንድ መመሪያዎችን አዘጋጅተዋል። ዋናውና ጠቃሚው የእግዚአብሔር ቃል ምን እንደሚል እኛ የምናስበው ሳይሆን

የእግዚአብሔር ሥልጣን ያለው፤ እርሱ በቃሉ የሚለውና የተናገረው እንደሆነ ልብ ማለት ያሻል። የራሳችንን መረዳት ከመጽሐፍ ቅዱስ እንደተገኘ ከመቁጠር ይልቅ፥ እግዚአብሔር በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በእርግጥ የሚለውን ነገር ለመረዳት መሻት በጣም አስፈላጊ ነው። ስለዚህ ጉዳይ «የመጽሐፍ ቅዱስ አጠናን ዘዴዎች» በሚለው መጽሐፍ ውስጥ በይበልጥ የምንመለከተው ሲሆን የሚከተሉት ነገሮች ለእነዚህ ሕግጋት መግቢያ ብቻ ናቸው፡-

1. የመተርጎም ሂደት በትክክለኛ ቅደም ተከተላቸው ልናሟላቸው የሚገቡን የሁለት ጥያቄዎችን ቅርፅ የሚይዝ ነው። መጀመሪያ፥ የእግዚአብሔርን ቃል ለመተርጎም የሚፈልግ ሰው፡- «መጀመሪያ ለጻፈው ሰውና መጀመሪያ ደርሶት ለሚያነበው ማለትም ለተጻፈለት ሰው የሚሰጠው ትርጉም ምንድነው?» ብሎ መጠየቅ አለበት። ብዙ ጊዜ ክርስቲያኖች የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሉ ምን እንደሚል ከመወሰናቸው በፊት፥ ከግል ሕይወታቸው ጋር ሊያዛምዱት ይሞክራሉ፤ ዳሩ ግን እግዚአብሔር ከአንድ ክፍል ውስጥ ምን እንደሚያስተምረን ከመወሰናችን በፊት በውስጡ ባስቀመጠው መልእክት አማካይነት ለተጻፈላቸው ለመጀመሪያዎቹ ሰዎች ምን ለማለት እንደፈለገ መረዳታችንን ማረጋገጥ አለብን። ይህንን ካደረግን ብቻ ክፍሉን ከራሳችን ሕይወት ጋር እግዚአብሔር እንድናዛምደው በሚፈልገው መንገድ ልናዛምደው እንችላለን።

በሁለተኛ ደረጃ፥«ይህ ክፍል ዛሬ ለእኛ ምን ማለት ነው ?» የሚለውን ጥያቄ ለእራሳችን ማቅረብ አለብን ይህ ጥያቄ ሁልጊዜ ከመጀመሪያው ጥያቄ ቀጥሎ ሊመጣና ከእርሱም መልስ ጋር አብሮ ሊሄድ ይገባል። መጽሐፉ መጀመሪያ ሲጻፍ ምን ማለቱ እንደነበር በትክክል ለመወሰን ከቻልን ብቻ፥ ይህ ቃል ለዚህም ዘመን የሚሆን የእግዚአብሔር ቃል ነው ብለን በእርግጠኝነት ከሕይወታችን ጋር ልናዛምደው እንችላለን።

ብዙ ሰባኪዎችና አስተማሪዎች በዚህ ይሳሳታሉ። ብዙ ጊዜ ሊሰብኩት የሚፈልጉት ርእስ ይኖራቸዋል። ያንን ርእስ በአእምሮአቸው ይዘው ከርእሱ ጋር በአንድ ወይም በሌላ መንገድ የሚያያዙትን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ይፈልጋሉ። የጥቅሶቹን ዓውደ-ንባብ በማጥናት መልእክቱ የተጻፈላቸው የመጀመሪያዎቹ ሰዎች የተረዱት ነገር ምን እንደሆነ ለማረጋገጥ ብዙም አይጥሩም።

እንዲሁም ቀድሞ ለነበሩት ሰዎች የተጻፈውን ብቻ በማጥናት፥ ዛሬ ከሕይወታችን ጋር በማዛመድ ልናገኘው የምንችለውን ትምህርት መተውም ስሕተት ነው። በክርስትና ሕይወት ውስጥ ሊያጋጥሙ ከሚችሉ አደጋዎች አንዱ የእግዚአብሔርን ቃል እንደታሪክ፥ ሐሳብ፥ ወይም ሳይንስ ለእውቀት ብቻ ማጥናት ነው። የእግዚአብሔር ቃል ሕይወታችንን ለመለወጥ የተሰጠ ነው። ሊለውጠን እንዲችል ካልፈቀድንለት፥ መንፈሳዊ ሕይወታችን ወዲያውኑ ይደርቃል።

| |
|---|
| 2. ክፍሉን መጀመሪያ እንደተጻፈላቸው ሰዎች ለመረዳት እንድንችል የሚከተሉትን ነገሮች ማድረግ ያስፈልገናል፡- |

ሀ. የምናጠናው የሥነ-ጽሑፍ ዓይነት ምን እንደሆነ በመወሰን በተጻፈበት የሥነ ጽሑፍ ዓይነት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሉን ለመተርጎም መሞከር አለብን።

| |
|---|
| 20ኛ ጥያቄ፥ ሀ) በጽሑፎችን ወይም በስብከታችን የምንጠቀምባቸውን የተለያዩ የሥነ ጽሑፍ ዓይነቶች ዘርዝር። ለ) ከግል‌ጋሎት ላይ የዋለው የሥነ -ጽሑፍ ወይም የንግግር ዓይነት ምን እንደሆነ መወሰን ለምን ይጠቅማል? |

በየዕለቱ በምንገለገልበት ቋንቋ የተለያዩ ዓይነት የንግግር ዘዴዎችን እንጠቀማለን። በየዕለቱ ከምንጠቀምባቸው እነዚህን ከመሰሉ የንግግር ዓይነቶች በጣም ስለተላመድን የንግግሩን ዓይነት መሠረት በማድረግ በምናስብበት ጊዜ እንኳ መረዳትንና ትርጉሙን በሚመለከት እንለያያለን። ለምሳሌ፡- «እንቁላል ቀስ በቀስ በእግሩ ይሄዳል» የሚለውን ምሳሌ ስንሰማ ወዲያውኑ በዚህ ምሳሌ ውስጥ በጣም አስፈላጊው ነገር ቀጥተኞቹ ቃላት ሳይሆኑ ከምሳሌው በስተጀርባ ያሉ የሥነ - ምግባር ትምህርቶች እንደሆኑ እንረዳለን። በተጨማሪም «ሰምና ወርቅ»፥ ግጥሞች፥ታሪኮች ደብዳቤዎችና ልብ ወለድ ታሪኮች ወዘተ እንጠቀማለን።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አራት ዋና ዋና የሥነ - ጽሑፍ ዓይነቶች አሉ። መጀመሪያ፥ በዘጸአት፥ በዘሌዋውያንና በዘዳግም እንዳሉት ዓይነት ሕጎች አሉ። በሁለተኛ ደረጃ፥ የታሪክ መጻሕፍት አሉ። እነዚህ የታሪክ የአጻጻፍ ስልቶች እንደ መጽሐፈ ኢያሱና መሳፍንት ባሉ በአብዛኛዎቹ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ውስጥ ይገኛሉ። ሦስተኛ፥ የግጥም መጻሕፍት ናቸው። አብዛኛው የብሉይ ኪዳን ክፍሎችና በተለይም መዝሙረ ዳዊት

በግጥም የተጻፉ ሲሆን መልእክቱንም ለመግለጥ በተለያዩ ሥዕላዊ አገላለጾች ይጠቀማሉ። (ለምሳሌ፡- ዛፎች ሲዘምሩ እናያለን፤ (መዝ. [96]፡ 12)። አራተኛ፥ የነቢያት ቋንቋ ነው። እንደ ኢሳይያስና ኤርምያስ ባሉ አብዛኛዎቹ የትንቢት መጻሕፍት እንደሚታየው የነቢያት ቋንቋ የታሪክና የግጥም ድብልቆች ናቸው። ይህም የነቢያትን መልእክት ትክክለኛ አተረጓጎም የበለጠ ከባድ ያደርገዋል። ከእነዚህ አራት የሥነ ጽሑፍ ዓይነቶች የትኛውንም በምናጠናበት ጊዜ ልንጠቀምባቸው የሚገባን የትርጉም ሕግጋት አሉ። ጥቂት ቆይተን የተለያዩ የሥነ ጽሑፍ ዓይነቶችን እንዴት እንደምንተረጉም የበለጠ እናጠናለን።

ለ. በክፍሉ የሚገኙ ቃላት መጀመሪያ መልእክቱን ለጻፈው ሰውና ለመጀመሪያዎቹ የመልእክቱ አንባቢዎች ምን መልእክት እንደሚያስተላልፍ አስቀድመን መረዳት አለብን። ይህም በተለይ በጣም አስፈላጊ የሚሆነው እንደ ጽድቅ፥ ቅድስና፥ ወዘተ ያሉ የሥነ መለኮት ትምህርት ቃላትን ስናጠና ነው። ደግሞም «የተቀደሰ እጃችሁን አንሡ፤ በጠንካራው የቀኝ ክንዱ፥ በተቀደሰ መሳሳም ሰላምታ ተሰጣጡ፤» ወዘተ ያሉትን ሥዕላዊ አነጋገሮች መጠቀም በሚመለከትም ረገድ ትክክለኛ ግንዛቤ መጨበጡ አስፈላጊ ነው።

ሐ. መልእክቱ በተጻፈበት ጊዜ ስለነበረው ባሕልና የመጽሐፍ ቅዱስ ዘመን ሰዎች የቻልነውን ያህል ለመረዳት መጣር አለብን። መልእክቱ የተጻፈው አይሁድ በምርኮ በነበሩ ጊዜ ነው ወይስ በነፃነትና በብልጽግና ሳሉ ነው? በባርነት አገር ነበሩ ወይስ በራሳቸው ምድር? ገበሬዎች ነበሩ ወይስ የከተማ ነዋሪዎች? «እግዚአብሔር እረኛዬ ነው፤ እግዚአብሔር ዓለቴ ነው፤» ወዘተ የሚሉትን ቁልፍ አሳቦች ለመረዳት እነዚህ አስፈላጊዎች ናቸው። ለእግዚአብሔር የተሰጡት እነዚህ ስሞች የወጡት ከእስራኤላውያን የሕይወት ዘይቤ ሲሆን፥ በዚህ ዘመን ያላቸው መልእክት አንድ ላይሆን ይችላል።

21ኛ ጥያቄ፥ መዝ. (18)፡2 ተመልከት። የብሉይ ኪዳን ጸሐፊ «እግዚአብሔር ዓለቴ፥ አምባዬ፥ መሸሸጊያ፥ ጋሻዬ፥ የደኅንነቴ ቀንድና መጠጊያዬ ነው» ሲል ምን ማለቱ ይመስልሃል?

የአይሁድን ባሕል ማወቅም በጣም አስፈላጊ ነው። ለምሳሌ አህያ ስለማንነዳ፥ የአይሁድ አህያን የመንዳት ሥዕላዊ ገለጻ አይገባንም። የአይሁድ ነገሥታት የመጡት በሰላም እንጂ እንደ ወራሪ ንጉሥ አለመሆኑን በአህያ ላይ ተቀምጠው በመሄድ ያሳዩ ነበር። ኢየሱስ በአህያ ተቀምጦ ወደ ኢየሩሳሌም በገባ ጊዜ እንደ ድል ነሺ ሳይሆን እንደ ሰላም ንጉሥ መምጣቱን ያመለክት ነበር።

መ. የምናጠናውን ክፍል ዓውደ ንባብ መመልከት አለብን። የምንመለከተው አንድ ቁጥርን ብቻ ከሆነ፥ ቁጥሩ ባለበት ክፍል የሚገኘውን ምዕራፍ በሙሉ ማጥናት አለብን። ከምናጠናው ክፍል ፊትና ኋላ ስላሉት ምዕራፎችም ማወቅ አለብን። ደግሞም ጸሐፊቱ ያንን መጽሐፍ በሚጽፉበት ጊዜ የነበራቸውን ዓላማ ማወቅ ይገባናል። ይህን የብሉይ ኪዳን ጥናት የምናጠናበት አንዱ ምክንያት የጸሐፊውን አጠቃላይ ዓላማ በተሻለ ሁኔታ እንድንረዳና ከዚያም የየክፍሉቹን ትርጉሞች ማስተዋል እንድንችል ነው።

አንድ ቃልና አንድ ቁጥር ትርጉም የሚያገኙት ባሉበት አንቀጽ ውስጥ ነው። ለምሳሌ በ1ኛ ቆሮ. 7፡2 ጳውሎስ ሲጽፍ፥ «ከሴት ጋር አለመገናኘት (አለማግባት) ለሰው መልካም ነው» ብሏል። ይህንን ጥቅስ ብቻ ብንመለከት፥ ማንም ሰው ማግባት የለበትም የሚል ትምህርት ልናስተምር ነው። ክርስቲያኖች ሁሉ ያላገቡ መሆን አለባቸው ልንል ነው፤ ነገር ግን አንቀጹን በጥንቃቄ ብንመረምረው ጳውሎስ ሳያገቡ እንዲኖሩ ሰዎችን የሚመክረው እግዚአብሔርን በተሻለ መንገድ ለማገልገል ዓላማ እንደሆነ እንመለከታለን። ጳውሎስ ስለ ዝሙት ጠንቅ ለእያንዳንዱ ለራሱ ሚስት እንድትኖረውም ይመክራል።

እንደ ይሖዋ ምስክሮች፥ ኢየሱስ ብቻ፥ ወዘተ ያሉ በርካታ የሐሰት መምህራን ትምህርታቸው የተመሠረተው ዓውደ ንባቡን በጥንቃቄ ባልተመራመሩባቸው አንድ ወይም ሁለት ጥቅሶች ላይ ነው።

ሠ. አንድን ጥቅስ ወይም ንባብ መተርጎም ያለብን በቀረው የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት መሠረት ነው። እግዚአብሔር መጽሐፍ ቅዱስን ለማስጻፍ ብዙ የተለያዩ ሰዎችን ቢጠቀምም፥ ጸሐፊው ራሱ ስለሆነ፥ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉ አሳቦች በሙሉ እርስ በርስ መስማማት አለባቸው። እግዚአብሔር

አይዋሽም፤ ደግሞም አይለወጥም፤ስለዚህ በዘፍጥረት ያስተማራቸው ትምህርቶች ከሐዋርያት ሥራና ከራእይ ጋር የሚስማሙ መሆን አለባቸው። የአንድን ጥቅስ ትምህርት በማንረዳበት ጊዜ የቀረውን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል በመመልከት መሠረታዊ ትምህርቱን ልንረዳ እንችላለን።

ረ. መጽሐፍ ቅዱስ አንዳች ስሕተት የሌለበት ቢሆንም፥ የእኛ ማስተዋልና ለመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶች የምንሰጠው ትርጉም ከስሕተት የጠራ ሊሆን አይችልም። መረዳታችን ውሱን የሆነ የሰው ልጆች እስከሆንን ድረስ፥ የመጽሐፍ ቅዱስን አጠቃላይ ትምህርት በሙላት ልንረዳ አንችልም። የእግዚአብሔርን ቃል ምን እንደሚል ለመረዳት የምንችለውን ያህል መጣር አለብን፤ ነገር ግን በአተረጓጎማቸው ከሌሎች ሰዎች ጋር ሳንስማማ ስንቀር ትሑታን ልንሆንና ልዩነቶችን ልናስተናግድ ይገባል። ይህም ማለት የትኛውም የጥናት መጽሐፍ ወይም የመጽሐፍ ቅዱስ ማብራሪያ መቶ በመቶ ትክክል ሊሆን አይችልም ማለት ነው። ጸሐፊዎቹ ስሕተትን ላለማስገባት የሞከሩ ቢሆንም፥ ውሱን መረዳት ያላቸው ሰዎች ናቸውና መሳሳታቸው አይቀሬ ነው። ይኸውም ሰባኪዎችና የቤተ ክርስቲያን መሪዎችም ሳይቀሩ ስሕተት ሊሠሩ ይችላሉ ማለት ነው።

| |
|---|
| 22ኛ ጥያቄ፥ የሐዋ. 17፡11 ተመልከት። ሀ) የቤርያ ሰዎች የተመሰገኑባቸው ነገሮች ምን ነበሩ? ለ) ሰባኪዎችን በምናዳምጥበት ወይም የመጽሐፍ ቅዱስ ማብራሪያዎችን በምናነብበት ጊዜ የቤርያ ሰዎችን ምሳሌነት መከተል ያለብን ለምንድነው? |

ነገር ግን ልዩነቶች እንዲኖሩ በምንፈቅድበት ጊዜ ከመጠን በላይ ቻይና ታጋሽ (አቋም የሌለን) እንዳንሆን መጠንቀቅ አለብን። በመጽሐፍ ቅዱሳችን ውስጥ መሠረታዊ ትምህርቶች ላይ የአመለካከት ልዩነት ቢኖርም ትምህርቶችን በቀጥታ የሚቃወም ትርጉም ሊኖር አይችልም። ለምሳሌ «ኢየሱስ ብቻ» የሚባለው የሐሰት ትምህርት በተመረጡ ጥቂት ጥቅሶች ላይ ተመሥርቶ ሥላሴ እንደሌለ በመናገር መጽሐፍ ቅዱስ በግልጥ ያቀረበውን ትምህርት ይቃረናል፤ስለዚህ ለተከታዮቹ ትክክል አለመሆናቸው ሊነገራቸው ይገባል።

23ኛ ጥያቄ፥ ሀ) ሰዎች በቤተ ክርስቲያንህ ውስጥ በሚሰበኩበት ጊዜ ከእነዚህ ውስጥ በሚገባ ያልተጠቀሙባቸው ሕግጋት የትኞቹ ናቸው? ለ) የምንባብ አተረጓጎምን ለማረጋገጥ የሚረዱ፥ የምታውቃቸውን መጻሕፍት ዝርዝር ጻፍ። ሐ) የአንዳንድ ቃላትን ትርጉም ለመረዳት የሚጠቅሙ መጻሕፍትን ዝርዝር ጻፍ። መ) የብሉይ ኪዳንና የአዲስ ኪዳን ባሕል ለመረዳት የሚያስፈልጉ መጻሕፍትን ዘርዝር።

ለትክክለኛ ትርጉም ቁልፉ ምንድነው? በተቻለን መጠን የመጀመሪያው የመልእክቱ ተቀባይ አካል ለመሆን መጣር አለብን። አንድ ጊዜ የጸሐፊውን ዓላማ፥ የተጻፈላቸው ሰዎች የነበሩበትን ሁኔታ፥ ጸሐፊው የተጠቀመበትን የሥነ -ጽሑፍ ዓይነት ከተረዳን፥ እግዚአብሔር ለመጀመሪያ ተቀባዮች ያስተላለፈውን የመልእክት ትርጉም ለመረዳት እንችላለን። በዚህ ጊዜ ብቻ ከዘመናችን ጋር በትክክል እናዛምደዋለን። የእግዚአብሔር ቃል በታሪካዊ ዓውደ ንባቡ መሠረት ስንመለከተውና ስንረዳው በሥልጣን ልንሰብክና ልናስተምር፥ እንደ ብሉይ ኪዳን ነቢያትም «እግዚአብሔር እንዲህ ይላል» ልንል እንችላለን።

## 4ኛ ቀን፡- አንድን የንባብ ክፍል ለመተርጎም ተለማመድ

ትላንትና አንድን ክፍል ለመተርጎም የሚጠቅሙ የተለያዩ ሕግጋትን ተመልክተናል። ዛሬ ደግሞ አንዳንዶቹን ሕግጋት በሥራ ላይ ለማዋል የብሉይ ኪዳን መጽሐፍ ስታጠና ሕጉ እንዴት እንደሚጠቅምህ ትረዳለህ።

24ኛ ጥያቄ፥ የትላትናውን ትምህርት ከልስ። አንድን ክፍል በምንተረጉምበት ጊዜ ልንጠቀምባቸው የሚገባን የተለያዩ ሕግጋትን ዘርዝር።
25ኛ ጥያቄ፥ መጽሐፈ ሩትን እያነበብክ የሚከተሉትን ነገሮች ዝርዝር አዘጋጅ፡-

ሀ) ቃላት፥ በተለይ ደግሞ ፍቺ መስጠት የሚያሻቸውን የሥነ መለኮት ትምህርት ቃላት ትርጉም የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት በመጠቀም ጻፍ።

ለ) ከማናውቃቸው ባሕላዊ ልምምዶችና እንግዳ ሕዝቦች ጋር መተዋወቅ ይገባል። በመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት ውስጥ የተለያዩ ነገዶችን ማንነት ተመልከት። የተጠቀሱትን ስፍራዎች በካርታ ላይ ተመልከት።

ሐ) የመጽሐፉ ዋና ትምህርት ምንድን ነው? እግዚአብሔር መጽሐፉ በብሉይ ኪዳን ውስጥ እንዲገባ ያደረገው ለምን ይመስልሃል?

መ) እግዚአብሔር ዛሬም ቢሆን ከታሪኩ ውስጥ እንድናውቀውና እርሱን እንድንከተለው የሚፈልጋቸው አንዳንድ የሕይወት ክንዋኔዎች ምን ይመስሉሃል? እነዚህ ክንዋኔዎች የተያያዙት እንዴት ነው? እግዚአብሔር ዛሬ ሊያስተምረን የሚፈልገው ለምን ይመስልሃል?

ከጥናት ቡድንህ ጋር ስትገናኝ ያገኘኸውን ነገር ታካፍላለህ።

## አምስተኛ ቀን፡-

የዚህን ሳምንት ትምህርት በመከለስ ለሳምንታዊ ስብሰባ የውይይት ጥያቄዎችን ተመልከት።

## ሳምንታዊ ስብሰባ

1. ሳምንታዊው የአምልኮ ጊዜ፡- በየሳምንቱ በተገናኛችሁ ጊዜ መዝሙር በመዘመርና ከቃሉ በማንበብ እግዚአብሔርን እያመለካችሁ ልባችሁን አዘጋጁ። መሪው ከዚህ ሳምንት ትምህርት ርዕስ ወይም ጥቅስ ከ5-10 ደቂቃ ሊወስድ የሚችል ለጸሎት የሚያዘጋጅ ቃል ለማካፈል መዘጋጀት አለበት።

2. ጸሎት፡- የጸሎት ጥያቄዎችን ተለዋወጡና በአንድነት ጸልዩ። ለእርስ በርሳችሁና ለቤተ ክርስቲያን ስለሚያስፈልጋት ነገር ለ10 ደቂቃ አብራችሁ ጸልዩ።

3. ክለሳ፡- የዚህን ሳምንት ትምህርትን ለ 15 ደቂቃ ተመልከት። አስተማሪው እያንዳንዱ ተካፋይ የዚህ ሳምንት ትምህርቱን መጨረሱን ለማረጋገጥና ትምህርቱ የቱን ያህል እንደገባው ለማወቅ የተማሪዎቹን መልሶች መመልከት አለበት። እያንዳንዱ ተማሪ ከዚህ ትምህርት የተማረውን ነገር ይዘርዝር። በዚህ ጊዜ መሪው ስለዚህ ሳምንት ትምህርት አጭር ፈተና (መመዘኛ) ይስጥ።

4. ውይይት፡- በእያንዳንዱ ትምህርት ለውይይት የሚጠቅሙ ጥያቄዎች ይሰጣሉ። መምህር ሆይ፥ ልትወያዩባቸው የምትፈልጋቸው ሌሎች አሳቦች ካሉ መልካም ነው። በመጽሐፉ ውስጥ ከተዘረዘሩት ጥያቄዎች መካከል ቡድንህ ቢያጠናው የበለጠ ይጠቅማል

የምትለውን ምረጥ። በመጀመሪያ ሁሉም ሰው አሳቡን እንዲሰጥ እያደረግህ በጥያቄዎቹ ላይ ተወያዩ። በእነዚህ ጥያቄዎች መሠረት ከሕይወትህ ጋር ቃሉን በግልጥ ማዛመድህን አረጋግጥ። ይህ የእግዚአብሔርን ቃል ትምህርት ከዕለታዊ ሕይወትህ ጋር የምታዛምድበት ጊዜ ነው። ውኅንብር ሊፈጥሩ የሚችሉ የተሳሳቱ ነገሮችን የምታርምበትም ጊዜ ነው።

ሀ. 2ኛ ጢሞ. 3፡16-17፤ 2ኛ ጴጥ. 1፡20-21 አንብብ። 1) እግዚአብሔር መጽሐፍ ቅዱስን በማስገኘት ረገድ ስለ ነበረው ድርሻ እነዚህ ቁጥሮች ምን ያስተምሩናል? 2) ሰው መጽሐፍ ቅዱስን በማስገኘት ረገድ ስለነበረው ድርሻ እነዚህ ቁጥሮች ምን ያስተምሩናል? 3) እግዚአብሔር መጽሐፍ ቅዱስን ለእኛ የሰጠበትን ምክንያት በሚመለከት እነዚህ ቁጥሮች ምን ያስተምሩናል? 4) መጽሐፍ ቅዱስ «ለትምህርት፥ ለተግሣጽ፥ ልብን ለማቅናትና በጽድቅ ላለው ምክር» እንዴት እንደጠቀመህ ከሕይወት ልምምድህ መግለጫ ስጥ።

ለ. ክርስቲያን ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ሊሰጠው በሚገባው ትምህርት ላይ ተወያዩ። 1) በመጽሐፍ ቅዱስ መጻፍ ረገድ የሰው ድርሻ ምንድነው? 2) በመጽሐፍ ቅዱስ መጻፍ ረገድ እግዚአብሔር ያደረገው ነገር ምንድነው? 3) በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስላሉ ስሕተቶች የክርስቲያኖች እምነት ምንድን ነው? 4) በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በተለያየ ሁኔታ የተጻፈ ነገር አለና የእግዚአብሔር ቃል ባለመሆኑ ልንታመንበት አይገባም ስለሚሉ ሰዎች ምን መልስ ትሰጣለህ?

ሐ. 1) ብዙ ጊዜ የማናጠናቸውንና የማንሰብክባቸውን የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ዘርዝር። 2) እነዚህ መጻሕፍት ብዙ ጊዜ በእግዚአብሔር ሰዎች በቀላሉ የሚታለፉት ለምድነው? 3) ስለ እግዚአብሔር ፈቃድ ከሁሉ የተሻለና ትክክለኛ አመለካከት እንዲኖረን፥ የእግዚአብሔርን ቃል በሙሉ በቤተ ክርስቲያናችን የምናጠናባቸው መንገዶች የትኞቹ ናቸው? 4) የእግዚአብሔርን ፈቃድ በከፊል ብቻ ሳይሆን በሙላት ማወቅ ለምን ያስፈልጋል?

መ. 1) እያንዳንዱ ክርስቲያን በገዛ ቋንቋው መጽሐፍ ቅዱስ እንዲኖረው ለምን አስፈለገ? 2) እያንዳንዱ ክርስቲያን

የእግዚአብሔርን ቃል ያለማቋረጥ ማንበብ የሚያስፈልገው ለምንድነው?

ሠ. 1) እግዚአብሔር ለእኛ ፈቃዱን የሚገልጥባቸው አንዳንድ መንገዶች የትኞቹ ናቸው? 2) እግዚአብሔር አንተን በቃሉ እንዴት ተናገረህ? 3) እግዚአብሔር ተናግሮናል ስለሚሉት ሐሰተኛ አስተማሪዎች ሥዕላዊ መግለጫ ስጥ። 4) የተናገሩት ነገር እውነት ይሁን ውሸት በምን ልንለይ እንችላለን?

ረ. እያንዳንዱ ተማሪ ከመጽሐፈ ሩት ጥናት ምን እንደተማረ ያካፍል። እያንዳንዱ ተማሪ መጽሐፍ ቅዱስን የመተርጎምን መምሪያ እንዴት በሥራ ላይ አዋለ? እያንዳንዱ ተማሪ አንድን ክፍል የማጥናት ድክመቱን እንዴት እንደሚያሻሽል ተወያዩ።

5. ጸሎት፡- እግዚአብሔር የተማራችሁትን ነገር በተግባር እንድታውሉ እንዲረዳችሁ በመጸለይ ስብሰባውን አጠቃልሉ።

# ትምህርት 2

## 1ኛ ቀን፡ - ትምህርት ብሉይ ኪዳን

| |
|---|
| 1ኛ ጥያቄ፥ ሀ) የመጽሐፍ ቅዱስ ሁለት ዋና ዋና ክፍሎች የትኞቹ ናቸው? ለ) እንደዚያ ተብለው ለምን ተጠሩ? ሐ) ኪዳን የሚለውን ቃል ትርጉም ከመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት በመመልከት የተሟላ ትርጉም ጻፍ። መ) በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኙ የተለያዩ ኪዳኖችን ዘርዝር። ሠ) ኪዳን የሚለው ቃል ከእግዚአብሔር ጋር ያለንን ግንኙነት እንዴት ይገልጻል? |

ስለ መጽሐፍ ቅዱስ አንዳንድ መሠረታዊ መመሪያዎችን ስናጠና ቆይተናል። ክርስቲያኖች እንደመሆናችን መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል መሆኑን እናምናለን። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እግዚአብሔር ራሱን ለእኛ ይገልጥልናል። እርሱ ምን እንደሚመስልና ከእርሱ ጋርም ሕያው የሆነ ግንኙነት እንዲኖረን ከእኛ ምን እንደሚፈልግ እንማራለን። መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል በመሆኑ ስለ እግዚአብሔር ማንነት፥ ወደ መንግሥተ ሰማያት ስለሚወስደው መንገድ፥ ለእግዚአብሔር ስለመኖር ያለንን አሳብ ሁሉ የምንበይንበት መመዘኛ ነው። ማንኛውም አሳባችን፥ የባሕላችን አስተምህሮት፥ ወይም የሌሎች ሰዎች ትምህርት በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት መመዘን አለበት። ከመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ጋር የማይስማማ ማንኛውም ትምህርት መወገዝ አለበት። እንዲሁም እግዚአብሔር ስለ ራሱና ስለ ፈቃዱ የገለጠውን ነገር በሚገባ እንድንረዳ መጽሐፍ ቅዱስን በትክክል መተርጎም እንዳለብን ተምረናል። ይህንን ካላደረግን ግን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የራሳችንን አሳብ እንጨምራለን፥መጽሐፍ ቅዱስንም እንዳይናገረን እናደርገዋለን።

| |
|---|
| 2ኛ ጥያቄ፥ ሀ) «ብሉይ» የሚለው ቃል ትርጉም ምን እንደሆነ አንድን የኦርቶዶክስ ካህን ወይም ሌላ ሰው ጠይቅ። ለ) «ኪዳን» የሚለው ቃል ትርጉም በአማርኛ ምንድን ነው? |

እኛ ክርስቲያኖች መጽሐፍ ቅዱስ ሁለት ዋና ክፍሎች እንዳሉት እናውቃለን። የመጀመሪያው ክፍል «ብሉይ ኪዳን» ሲባል፥ ሁለተኛው ደግሞ «አዲስ ኪዳን» ይባላል። በኢየሱስ የማያምኑ አይሁድ የዕብራውያን መጽሐፍ ቅዱስ በሚባለው ብሉይ ኪዳን ብቻ ያምናሉ።

ለእነዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ሁለቱ ስሞች ለምን እንደተሰጡ ለመረዳት ሁለት ዋና ዋና ቃላትን መመልከት ያስፈልገናል።

1. ኪዳን:- ኪዳን የሚለው ቃል ትርጉሙን የወሰደው ሁለት ሰዎች ወይም ቡድኖች በመካከላቸው እርስ በርስ ከሚያደርጉት ስምምነት ነው። ከብዙ መቶ ዓመታት በፊት ኢየሱስ ከሞተና አሁን በአዲስ ኪዳን ውስጥ ያሉ በርካታ መጻሕፍት ከተጻፉ በኋላ ክርስቲያኖች ቅዱሳት መጻሕፍትን ለመግለጥ «ኪዳን» የሚለውን ቃል መጠቀም ጀመሩ። መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ራሱንና ፈቃዱን የገለጠበት መሆኑና እግዚአብሔር ራሱን ከሰው ልጆች ጋር በኪዳን ወይም በስምምነት ግንኙነት እንዲኖረው እንዳደረገ ተገነዘቡ። በማንኛውም «ኪዳን» ውስጥ ሦስት ዋና ዋና ክፍሎች አሉ:- በመጀመሪያ፥ በኪዳኑ ውስጥ የሚካተቱ አባላት አሉ። በመጽሐፍ ቅዱስ «ኪዳን» የሚለው ቃል የሚናገረው እግዚአብሔር ከተለያዩ ሰዎች ጋር ኅብረት እንዳደረገ ነው። አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔር እንደ አብርሃምና ዳዊት ካሉ ጋር ስምምነት አድርጓል። በሌላ ጊዜ ደግሞ እግዚአብሔር ከኖኅ ጋር እንዳደረገው ዓይነት ከሰው ልጆች ሁሉ ጋራ ስምምነት አድርጓል። የብሉይ ኪዳን ዋና ክፍል ግን እግዚአብሔር ከአብርሃም ልጆች ጋር (ማለትም ከአይሁድ ጋር) ስላደረገው ኪዳን የሚናገር ነው።

| 3ኛ ጥያቄ፥ የአዲሱ ኪዳን ስምምነት የተደረገው ከማን ጋር ነው? |
|---|

ሁለተኛ፥ ቃል ኪዳኑ እንዲጠበቅ እንዲሟላና እንዲፈጸም በአንዱ ወይም በሁለቱም የኪዳኑ አባላት መጠበቅ ያለባቸው ቅድመ ሁኔታዎች በኪዳኑ ውስጥ መኖር አለባቸው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሁለት ዓይነት ኪዳኖች ይገኛሉ። በሲና ተራራ ለአይሁድ ተሰጥቶ እንደነበረው (ዘጸ. 19-24) ዓይነት ያሉ አንዳንድ ኪዳኖች ቅድመ ሁኔታዎች ነበሩዋቸው። በሌላ አባባል እግዚአብሔር «እነዚህን ትእዛዛት ከጠበቃችሁ ለእናንተ እንደዚህ አደርግላችኋለሁ» ብሏል። ሌላው ዓይነት ኪዳን ግን ምንም ዓይነት ቅድመ ሁኔታ የሌለው የተስፋ ቃል ኪዳን ብቻ ነበር። የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ግን ምንም ዓይነት ቅድመ ሁኔታ የሌለው የተስፋ ቃል ብቻ ነበር። እግዚአብሔር ቃል ኪዳን ለገባላቸው ሰዎች ያለምንም ቅድመ ሁኔታ አንድ ነገር እንደሚያደርግላቸው ተናግሯል (ዘፍ. 12:1-3)። የዚህ ቃል ኪዳን ምሳሌ እግዚአብሔር ከአብርሃም፥ ከዳዊትና ዛሬም ከክርስቲያኖች ጋር ያለው አዲሱ ቃል ኪዳን ዓይነት

ነው። እግዚአብሔር በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሰጣቸውን ኪዳኖች በምናጠናበት ጊዜ ቅድመ ሁኔታ ያላቸውንና የሌላቸውን ለይቶ ማየት አስፈላጊ ነው።

ሦስተኛ፥ በኪዳኑ ውስጥ አንዱ ክፍል ለሌላው የሚሰጣቸው ተስፋዎች አሉ። በብሉይ ኪዳን ብዙ ጊዜ ኪዳኑን የሚጀምር እግዚአብሔር ስለሆነ፥ ተስፋንም ለተለያዩ ሰዎች የሚሰጥ እርሱ ነው። እነዚህ ተስፋዎች እንደሚፈጸሙ ጥርጥር የለም። ምክንያቱም ተስፋውን የሰጠው ሊዋሽ ወይም አሳቡን ሊቀይር የማይቻለው አምላክ ስለሆነ ነው።

4ኛ ጥያቄ፥ ኤር. 31፡31-34 አንብብ። በእነዚህ ቁጥሮች እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን የሰጣቸው ተስፋ ምንድነው?
5ኛ ጥያቄ፥ ማቴ. 26፡26-29 አንብብ። ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ የሰጠውን ጽዋ ምን ብሎ ጠራው? የመጀመሪያዎቹ 39 መጻሕፍት ብሉይ ኪዳን፥ 27ቱ ደግሞ አዲስ ኪዳን ተብለው እንዲጠሩ የወሰኑት የጥንት ክርስቲያኖች እግዚአብሔር ከሰዎች ጋር ያለው ኅብረት እምብርት የኪዳኑ አሳብ እንደሆነ ተገንዝበው ነበር።

በብሉይ ኪዳን ውስጥ እግዚአብሔር ለሰው ልጅ የሰጣቸው አያሌ የተለያዩ ኪዳኖች ይገኛሉ።

1. ከኖኅና ከሰው ልጆች ሁሉ ጋር የተደረገ ኪዳን (ዘፍጥ. 9፡1-17)፥ የሰውን ዘር ካጠፋው ውኃ በኋላ እግዚአብሔር ከኖኅና ከእርሱ በኋላ ከተነሡ የሰው ልጆች ሁሉ ጋር ቃል ኪዳን አደረገ። በዚህ ኪዳን ውስጥ ይታዘዙት ዘንድ እግዚአብሔር የሰጣቸው ግልጥ የሆኑ ትእዛዛት ነበሩ። ደግሞም በዚያ ቃል ኪዳን ውስጥ የሰውን ልጆች በውኃ ላያጠፋ እግዚአብሔር የገባውም ቃል ኪዳን ነበር። ብዙውን ጊዜ በሰማይ ላይ የምናየው ቀስተ ደመና ያንን ቃል ኪዳን የሚያስታውስ ነው።
2. ከአብርሃምና ከዘሩ ጋር የተገባ ቃል ኪዳን (ዘፍጥ. 12፡1-3)።

6ኛ ጥያቄ፥ ዘፍ. 12፡1-3 አንብብ። እግዚአብሔር ለአብርሃም የሰጠውን የተለያዩ ቃል ኪዳኖች ዘርዝር።

በብሉይ ኪዳን ከምናያቸው ቃል ኪዳኖች ሁሉ እጅግ በጣም አስፈላጊ የሆነው እግዚአብሔር ከአብርሃም ጋር ያደረገው ነው።

እግዚአብሔር ከዘፍጥ. 12-25 እንዲሁም በአጠቃላይ በብሉይ ኪዳን ላይ በዚህ ቃል ኪዳን ላይ መመሥረቱን ቀጠለ። ይህ ቃል ኪዳን በብሉይና በአዲስ ኪዳን ውስጥ ያሉትን ሌሎች ቃል ኪዳኖች ለመረዳት የሚያስችል መሠረት ነው። ከአብርሃም ጋር በተገባው ቃል ኪዳን ውስጥ በቀጥታ አብርሃምን ራሱን ብቻ የሚመለከቱ በርካታ የተስፋ ቃሎች አሉ፤ ነገር ግን ለብሉይ ኪዳን ትምህርቶችና ታሪክ መሠረት የሆኑ ሌሎች በርካታ የተስፋ ቃሎችም አሉ።

ሀ. እግዚአብሔር የአብርሃም ዘሮች የሆኑትን አይሁድ ወይም እስራኤላውያን ታላቅ ሕዝብ እንደሚሆኑ የተስፋ ቃል ሰጣቸው። የብሉይ ኪዳን የታሪክ መጻሕፍት ከዘጸአት ጀምሮ እስከ 2ኛ ዜና ድረስ ይህ ሕዝብ እዚህ ግባ ከማይባል ከአንድ ቤተሰብ ወደ ታላቅ ሕዝብነት እንዴት እንዳደገ የሚናገሩ ናቸው።

ለ. እግዚአብሔር የአብርሃም ዘሮች የተስፋ ምድር የሆነችውን ከነዓንን እንደሚወርሱ ተናገረ። ይህች ምድር የእነርሱ ርስት ትሆናለች አለ። የኢያሱ፥ የመሳፍንትና የ1ኛና 2ኛ ሳሙኤል መጻሕፍት እነዚህ የተስፋ ቃሎች በረጅም ጊዜ ውስጥ እንዴት እንደተፈጸሙ የሚናገሩ ናቸው።

ሐ. እግዚአብሔር ከአብርሃም በተለይም ከይሁዳ የዘር ግንድ አንድ ልዩ የሆነ ንጉሥ እንደሚወጣ የተስፋ ቃል ሰጣቸው (ዘፍጥ. 17:6፥16፤ 49:10)። ይህ የተስፋ ቃል በመጀመሪያ በዳዊት ተፈጸመ። በመጨረሻም በኢየሱስ ክርስቶስ ተፈጽሟል።

3. እግዚአብሔር በሲና ተራራ ከእስራኤል ሕዝብ ጋር ቃል ኪዳንን አደረገ (ዘጸ. 19-24)። እግዚአብሔር ምንም ዓይነት ቅድመ ሁኔታዎችን ከሰዎች ካልጠየቀባቸው ከሌሎቹ ቃል ኪዳኖች በተቃራኒ፥ በሲና ተራራ እግዚአብሔር ከአይሁድ ሕዝብ ጋር ያደረገው ስምምነት ቃል ኪዳኑ ይፈጽም ዘንድ እነርሱም ሊያሟሉት የሚገባ ቅድመ ሁኔታ ነበር። ብሉይ ኪዳን ብለን ከምንጠራቸው ከሠላሳ ዘጠኙ መጻሕፍት መካከል አብዛኞዎቹ እግዚአብሔር ከእስራኤል ጋር ስለገባው ቃል ኪዳን ከሚናገሩ ነገሮች ጋር የተያያዙ ነበሩ። በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር ከእስራኤል ጋር ቃል ኪዳን እንዴት እንደጀመረ (ዘፍጥረት እስከ ዘዳግም)፥ ለእስራኤላውያን የከነዓንን ምድር በመስጠት የገባላቸውን ተስፋ እንዴት እንዳከበረ

(ኢያሱ እስከ 2ኛ ሳሙኤል)፥ እንዲሁም እስራኤላውያን ከእግዚአብሔር ጋር የነበራቸውን ቃል ኪዳን እንዴት እንዳፈረሱና ለጊዜው እንደተፈረደባቸው (1ኛ ነገሥት እስከ ሚልክያስ) እናነባለን።

4. ከካህኑ ከፊንሐስ ጋር የተገባ ቃል ኪዳን (ዘኁል. 25፡10-13)፥ በዚህ ቃል ኪዳን እግዚአብሔር ለፊንሐስ ዘሮች ካህናት የመሆን መብት ሰጥቷል።

5. ከንጉሥ ዳዊት ጋር የተገባ ቃል ኪዳን (2ኛ ሳሙ. 7፡5-16)፥ እግዚአብሔር ለዳዊት የእርሱ ዘሮች በእስራኤል ሕዝብ ላይ ንጉሥ የመሆን መብት እንዳላቸው ቃል ኪዳን ገባለት። በመጨረሻ ይህ ቃል ኪዳን የይሁዳ አንበሳ በሆነው በኢየሱስ ክርስቶስ ተፈጸመ። እርሱ በእስራኤልና በሕዝቦች ሁሉ ላይ ንጉሥ ነው። አንድ ቀን ኢየሱስ ወደዚህች ምድር በመመለስ እንደገና ይነግሣል (ራዕ. 20፡4)።

6. አዲስ ቃል ኪዳን (ኤር. 31፡31-34)፥ የእስራኤል ሕዝብ እግዚአብሔር በሲና ተራራ ከቃል ኪዳኑ ጋር የሰጣቸውን ቅድመ ሁኔታ መጠበቅ ስላልቻሉ፥ እግዚአብሔር አዲስ ቃል ኪዳን እንደሚሰጥ አስታወቀ። በዚህ ቃል ኪዳን እግዚአብሔር ሕግን እንደሚያደርግና ለሰዎችም ይህንን ሕግ የመታዘዝ ችሎታ በልባቸው እንደሚሰጣቸው ተስፋ ሰጥቷል። ኢየሱስ በመስቀል ላይ በሞተ ጊዜ ይህንን አዲስ ቃል ኪዳን እንደጀመረው ሐዋርያት በኋላ ተገነዘቡ።

2. ብሉይ ኪዳን፡- የመጀመሪያዎቹን 39 ቅዱስ መጻሕፍት «ብሉይ» ብለው በመጥራታቸው የቀድሞዎቹ ክርስቲያኖች ከኢየሱስ መምጣት ጀምሮ አንድ አዲስ ነገር እንደተፈጸመ ያሳዩናል። በኤር. 31 የተሰጡት ተስፋዎች ተፈጽመዋል። እነዚህ የቀድሞ ክርስቲያኖች የመጀመሪያዎቹን 39 መጻሕፍት ብሉይ ብለው የጠሩባቸው ሦስት ምክንያቶች አሉ፡-

   ሀ. እግዚአብሔር አዲስ ቃል ኪዳንን በኤር. 31፡31-34 ላይ ስለሰጠ የቀድሞው ቃል ኪዳን አሮጌ ወይም ጊዜ ያለፈበት ሆኗል።

   ለ. ኢየሱስ ከመሞቱ በፊት በነበረው ሌሊት የሚያፈሰው ደም ይቅርታን የሚያስገኝ የቃል ኪዳን ደም እንደሆነ ተናግሮ ነበር።

ይህንን ቃል ኪዳን ኢየሱስ አዲስ ቃል ኪዳን ብሎ ባይጠራውም እንኳ እግዚአብሔር እውነተኛ የኃጢአት ይቅርታ የሰጠበት በትንቢተ ኤርምያስ የምናገኘው አሳብ መሆኑ ግልጽ ነው።

7ኛ ጥያቄ፥ ዕብ. 7፡18-22፤ 8፡6-13 አንብብ። ሀ) የዕብራውያን ጸሐፊ የቀድሞውን ቃል ኪዳን የጠራባቸውን ስሞች ዘርዝር። ለ) ይህ ጸሐፊ አዲሱን ቃል ኪዳን የጠራባቸውን ስሞች ዘርዝር። ሐ) ጸሐፊው ስለ ቀድሞው ቃል ኪዳን ምን ይላል?

ሐ. በሲና ተራራ የተሰጠው ቃል ኪዳን በዕብራውያን መልእክት «የቀድሞው፥ አሮጌው፥ የፊተኛውና ዘመኑ ያለፈበት» ተብሏል። በሌላ በኩል ኢየሱስ የጀመረው ቃል ኪዳን «አዲስ፥ የተሻለና የላቀ» ቃል ኪዳን ተብሎአል። እነዚህ ቃላት ሁሉ የሚያሳዩት ኢየሱስ ወደ ምድር ከመጣበት ጊዜ ጀምሮ ከእግዚአብሔር ጋር አዲስ ስምምነት የተደረገበት አዲስ ዘመን መጀመሩን የቀድሞ ክርስቲያኖች ምን ያህል ተገንዝበውት እንደነበር ነው። እንደ አንዳንድ የብሉይ ኪዳን ቃል ኪዳኖች፥ ይህ አዲስ ቃል ኪዳን በቅድመ ሁኔታ ላይ ያልተመሠረተ ነው፤ በሰው ፍጹም መታዘዝ ላይ ሳይሆን፥ በእግዚአብሔር የተስፋ ቃላት ላይ የተመሠረተ ነው።

8ኛ ጥያቄ፥ ሀ) የአዲስ ኪዳን የተስፋ ቃል በሲና ተራራ የተሰጠውን ሕግ በሙሉ ስለመጠበቅ አስፈላጊነት ለእኛ ምንን ያመለክታል? ለ) በአሁኑ ጊዜ ያሉ አንዳንድ ክርስቲያኖች በሲና ተራራ ለአይሁዳውያን ከተሰጡት ሕጎች አንዳንዶቹን የሚከተሉት ለምንድነው? ሐ) እነርሱ ከሚከተሏቸው ሕጎች አንዳንዶቹን ዘርዝር።

ስለ ብሉይ ኪዳን ቃል ኪዳኖችና ከአዲስ ኪዳን ጋር ስላላቸው ግንኙነት የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁራን አስተሳሰብ የተለያየ ነው። አንዳንድ ክርስቲያኖች ቃል ኪዳን አንድ ብቻ ነው፤ ይህም ብቸኛ ቃል ኪዳን እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር የገባው ቃል ኪዳን ነው ይላሉ። በብሉይ ኪዳን ቃል ኪዳን የተደረገው በሥጋም በመንፈስም የአብርሃም ልጆች ከነበሩት አይሁዳውያን ጋር ሲሆን፥ በአዲስ ኪዳን ደግሞ የአብርሃም መንፈሳዊ ልጆች ከሆኑት ከእግዚአብሔር ልጆች ጋር ነው (ገላ. 4፡21-31 ተመልከት)። ሌሎች ክርስቲያኖች ደግሞ ፍጹም የተለያዩ ሁለት ቃል ኪዳኖች ናቸው ይላሉ። የመጀመሪያው ከእስራኤል ሕዝብ ጋር ሲሆን

ሁለተኛው ደግሞ በኢየሱስ ክርስቶስ አምነው የተሠዋው ለኃጢአታቸው እንደሆነ ከተቀበሉት ሰዎች ሁሉ ጋር ነው። እነዚህኞቹ የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁራን እግዚአብሔር በሥጋ የአብርሃም ዘር ለሆኑ የገባቸው ቃል ኪዳኖችና ለቤተ ክርስቲያን የገባቸው ቃል ኪዳኖች በግልጽ መለየት አለባቸው ይላሉ። እነዚህ ልዩነቶች እንደዋና ነገር የማይታዩ ቢሆኑም እንኳ ብሉይ ኪዳንን የምንረዳበትና የምንተረጉምበት አብዛኛው መንገድ የተመሠረተው የብሉይና የአዲስ ኪዳን ልዩነቶች ምን እንደሆኑ ባለን መረዳት ላይ ነው።

9ኛ ጥያቄ፥ ሀ) በብሉይ ኪዳን የሚገኙ ቃል ኪዳኖችን በሙሉ ከልስ። ለ) የቅዱሳት መጻሕፍት ክፍሎችን በሙሉ አንብብ። ሐ) በእነዚህ ክፍሎች ውስጥ እግዚአብሔር የሰጠውን የተስፋ ቃላት ዘርዝር። መ) ለእነዚህ የተስፋ ቃላት የተሰጡ ሌሎች ቅድመ ሁኔታዎችን ዘርዝር። ሠ) ዛሬ ከእኛ ጋር በቀጥታ የሚያያዙ የተስፋ ቃላት የትኞቹ ናቸው? ረ) በብሉይ ኪዳን ዘመን ይኖሩ ለነበሩ ሰዎች ብቻ የሚሆኑትስ የተስፋ ቃላት የትኞቹ ናቸው?

## 2ኛ ቀን: - የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት እንዴት እንደተሰበሰቡ

10ኛ ጥያቄ፥ ሀ) በእንግሊዝኛው መጽሐፍ ቅዱስ የብሉይ ኪዳንን መጻሕፍት ቅደም ተከተል ከአማርኛው መጽሐፍ ቅዱስ ቅደም ተከተል ጋር አወዳድር። የተለያየ ቅደም ተከተል ያላቸው መጻሕፍት የትኞቹ ናቸው? ለ) የካቶሊክ እምነት ተከታይን መጽሐፍ ቅዱሱን እንዲያሳይህ ጠይቀው። ከአንተ መጽሐፍ ቅዱስ ይለያልን? በእነርሱ ብሉይ ኪዳን ውስጥ ስንት መጻሕፍት አሉ? ሐ) በመጽሐፍ ቅዱሳቸው ውስጥ ስንት የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት እንዳሉ አንዱን የኦርቶዶክስ ቄስ ጠይቅ።

ትላንትና ለመጀመሪያዎቹ 39 መጻሕፍት የቀድሞ ክርስቲያኖች እንዴት «ብሉይ ኪዳን» የሚል ስያሜ እንደሰጡ ተመልክተናል። ነገር ግን የብሉይ ኪዳን ክፍል መሆን ያለባቸው መጻሕፍት የትኞቹ እንደሆኑ ከእግዚአብሔር ቃል ውጭ እንደሆኑ ሊቆጠሩ የሚገባቸው መጻሕፍትስ የትኞቹ እንደሆኑ ክርስቲያኖች ከስምምነት ላይ የደረሱት እንዴት ነው?

የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁራን የተለያዩ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት በእግዚአብሔር መንፈስ የተጻፉ የእግዚአብሔር ቃል ስለመሆናቸው ይከራከራሉ። እንደምታስታውሰው የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ተጽፈው

የተጠናቀቁት በ1000 ዓመታት ውስጥ ነው። ከኦሪት ዘፍጥረት ጀምሮ እስከ ዘዳግም ያሉት የመጀመሪያዎቹ መጻሕፍት የተጻፉት በ1400 ዓ.ዓ. ነው። የመጨረሻ የሆነው መጽሐፍ ትንቢተ ሚልክያስ የተጻፈው በ400 ዓ.ዓ. ነው። በእነዚህ የ1000 ዓመታት ጊዜ ውስጥ መጽሐፍ ቅዱስን እንዲጽፉ እግዚአብሔር በተለያዩ ሰዎች ተጠቅሞአል። በመጀመሪያው ምዕተ ዓመት ከክርስቶስ ልደት ወዲህ በመጽሐፍ ቅዱሳችን ውስጥ ያሉት 39 መጻሕፍት በሙሉ በእግዚአብሔር መንፈስ ምሪት የተጻፉ እንደሆነ እናውቃለን።

የብሉይ ኪዳንን መጻሕፍት በአንድ ላይ ለማቀናጀት ብዙ ደረጃዎችን ማለፍ እንዳስፈለገ የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁራን ይገምታሉ።

የመጀመሪያ ደረጃ:- በንግግር የማስተላለፍ ባሕል ነው። የመጀመሪያው ደረጃ የእግዚአብሔርን ቃል ከትውልድ ወደ ትውልድ በንግግር የማስተላለፍ ዘዴ ነው። የእግዚአብሔር ነቢያት በእግዚአብሔር ሕዝቦች ፊት ቆመው «እግዚአብሔር እንዲህ ይላል» በማለት የእግዚአብሔርን መልእክት ያስተላልፉ ነበር (ሕዝ.5፡5 ተመልከት)። በዚህ የንግግር ዘዴ ይተላለፉ የነበሩ አንዳንድ መልእክቶች ሳይጻፉ ብዙ ዘመን ሳያልፉቸው አይቀርም። ለምሳሌ:- ከዘፍጥረት 1-50 ያሉት ሲሆኑ፥ ሌሎቹ ደግሞ ቶሎ የመጻፍ ዕድል አግኝተዋል።

ሁለተኛ ደረጃ:- የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ተጻፉ። የተለያዩ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ጸሐፊዎች በመንፈስ ቅዱስ ምሪት አማካይነት የእግዚአብሔርን ቃል በተለያዩ መጻሕፍት ጽፈዋል።

ሦስተኛ ደረጃ:- አይሁድ የእግዚአብሔር ቃል ናቸው ብለው የሚያስቧቸውን የተለያዩ መጻሕፍት መሰብሰብ ጀመሩ። ይህ ረጅም ጊዜ የወሰደ ሥራ ነው። ለምሳሌ:- መዝሙረ ዳዊት በአንድ ላይ ተጠርዞ ለመቀመጥ ብዙ መቶ ዓመታት ወስዶአል። አንዳንዶቹ መዝሙሮች የተጻፉት በ1400 ዓ.ዓ. በሙሴ፥ ሌሎቹ ደግሞ በ500 ዓ.ዓ. በዕዝራ የተጻፉ ናቸው። የብሉይ ኪዳን መጻሕፍትን በማሰባሰብና በማደራጀት ረገድ ዕዝራ ከፍተኛ ሚና እንደተጫወተ ብዙ ምሁራን ይገምታሉ።

አራተኛ ደረጃ:- አይሁድ የእግዚአብሔር ቃል ናቸው ብለው የተቀበሏቸውን የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ሁሉ ሰብስበው ቅደም ተከተል

በማስያዝ አስቀመጡአቸው። ይህ ማለት አንዳንዶቹን መጻሕፍት የእግዚአብሔር ቃል እንዳልሆኑ ቆጥረው አገለሉዋቸው ማለት ነው።

አይሁዳውያን እስከ መጀመሪያው መቶ ዓመት መጨረሻ ድረስ የእግዚአብሔር ቃል ናቸው ብለው የሚያምኑባቸውን የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት በአሁኑ መልካቸው ስለማስቀመጣቸው መረጃ የለንም። ዳሩ ግን ከክርስቶስ መምጣት በፊት 200 ዓ.ዓ. ማለትም የመጨረሻው መጻሕፍት ከተጻፈ ከ200 ዓመት በኋላ የእግዚአብሔር ቃል ናቸው ብለው አይሁድ የገመቱአቸውን መጻሕፍት በሙሉ አይሁዳውያን አውቀውና መርጠው እንደነበር የሚገልጥ ማስረጃ አለ።

ይህ ሂደት በጣም የተወሳሰበ ሊመስል ይችላል፤ ነገር ግን ክርስቲያኖች እንደመሆናችን መጠን ቃሉን በመጻፍ ሂደት ውስጥ ከሰዎች ጋር የሠራው እግዚአብሔር የተጻፉትን መጻሕፍት ያለአንዳች ስሕተት ሰዎች እንዲለዩ በማድረግ ረገድም እንደሠራ እናምናለን። እነዚህ መጻሕፍት የእግዚአብሔርን ቃልና ሥልጣን ይዘዋል።

የቀድሞ አይሁዳውያን የእግዚአብሔር ቃል የሆኑትን ክፍሎች ከብዙ መጻሕፍት መካከል ለመለየት የተጠቀሙበት መመዘኛ ምንድነው? በአዲስ ኪዳን ዋናው መመዘኛ:- «ይህ መጽሐፍ የተጻፈው በአንድ ሐዋርያ ነው ወይስ አብሮት በሚሠራ ሰው?» የሚል ነበር። የብሉይ ኪዳንን መጻሕፍት ለመለየት ግን አራት ዋና ዋና መመዘኛዎች የነበሩ ይመስላል። እነርሱም:-

1. መጽሐፉ በውስጣዊ ብቃቱና በመልእክቱ የእግዚአብሔር ሥልጣን እንዳለውና በእርሱ መንፈስ እንደተጻፈ የሚያሳይ ነገር አለን? የአይሁድ የሃይማኖት መሪዎች መጻሕፍቱን በሚመዝኑበት ጊዜ የእግዚአብሔር ጣት እንዳለበት እንዲያዩ መንፈስ ቅዱስ መርቶአቸዋል።

2. የመጽሐፉ ጸሐፊ እግዚአብሔር በመለኮታዊነቱ መሪ እንዲሆን የመረጠው ሰው ነበርን? ለምሳሌ ንጉሥ፥ ካህን፥ ነቢይ፥ ወይም እግዚአብሔር በኃይል የተጠቀመበት በእስራኤል ላይ የሚፈርድ ሰው ነበርን?

3. በመጽሐፉ ውስጥ የሚገኙ ትምህርቶች በሙሉ እርስ በእርስና እንዲሁም የእግዚአብሔር ቃል መሆኑ በታወቀ በሌላ መጻሕፍት ውስጥ ከሚገኙ ትምህርቶች ጋር የሚስማማ ነውን? ለምሳሌ:-

በትንቢት መጻሕፍት ውስጥ የሚገኙ ትምህርቶች በመጀመሪያዎቹ አምስት የሙሴ መጻሕፍት ውስጥ እግዚአብሔር ከተናገረው ነገር ጋር የሚስማሙ ናቸውን?

4. መጻሕፍቱ በአይሁድ የአምልኮ ጊዜ በተግባር ላይ ሊውሉ የቻሉ ናቸውን ወይስ ለሌላ ለተለየ ዓላማ ምንም አገልግሎት የማይሰጡ ናቸው? እያንዳንዱን መጽሐፍ በእጅ መገልበጥ ከባድ ድካም የሚጠይቅ ስለነበር፥ አይሁዳውያን ይገለብጡ የነበረው የእግዚአብሔር ቃል መሆናቸውን ያወቁዋቸውና ለእግዚአብሔር በሚሰጡት አምልኮ ውስጥ ሊጠቀሙባቸው የሚችሉትን ዓይነት ብቻ ነበር።

እነዚህ አይሁዳውያን፥ እግዚአብሔር በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ እንዲካተት የፈለገውን ነገር ብቻ መምረጣቸውን እንዴት እናውቃለን? በአንድ በኩል ስናየው፥ ልናውቅ አንችልም። ሰዎች ቃሉን እንዲጽፉ በማድረግ ከእነርሱ ጋር ግንኙነት ያደረገው እግዚአብሔር፥ በዓለም ላሉ ሰዎች ሁሉ እንዲደርስ የፈለገው ቃሉ ብቻ ተጠብቆ እንዲቆይ እንዳደረገ ማመን አለብን። በሌላ አንፃር ስናየው ግን የብሉይ ኪዳን መጻሕፍትን ሁሉ በምንመረምርበትና ዛሬ ካሉ ሌሎች መጻሕፍት ጋር በምናወዳድርበት ጊዜ ልዩነቱን ለማየት እንችላለን። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያልተካተቱት መጻሕፍት የመጽሐፍ ቅዱስን ያህል ጥራትና ብቃት ያለው መልእክት የላቸውም። በተጨማሪ የመጽሐፍ ቅዱስ መጻሕፍት እንደ ሌሎቹ መጻሕፍት ሳይሆኑ ምንም ዓይነት ያለመስማማት በማይታይበት ሁኔታ የመልእክት አንድነት ይታይባቸዋል። ሌሎች መጻሕፍት የእግዚአብሔር ቃል አለመሆናቸውን የምናየው እርስ በርስ የሚቃረኑ ትምህርቶች ስላሉባቸው ነው። እግዚአብሔር ብሉይ ኪዳንን እንዲጽፉ የተጠቀመባቸው የተለያዩ ሰዎች ቢሆኑም የብሉይ ኪዳን የመልእክት አንድነት ግን የሚያስደንቅ ነው። በተለያዩ መጻሕፍት መካከል ያሉ ትምህርቶች የተጻፉት በመቶ ዓመታት ልዩነት ቢሆንም፥ አንዳቸው ከሌላቸው ጋር በማይቃረን ሁኔታ ይስማማሉ። የእግዚአብሔር ልጆች እንደመሆናችን መጠን ዛሬ በእጃችን ያሉት ቅዱሳት መጻሕፍት የእግዚአብሔር ቃል መሆናቸውን በእርግጠኝነት መናገር እንችላለን። የእግዚአብሔር ሥልጣን ይገኝባቸዋል፤ ስሕተት አያስተምሩም፤ ስለ እውነተኛው እግዚአብሔርና ከእርሱ ጋር ሊኖረን ስለሚገባ ግንኙነትም በትክክል ያስተምሩናል። የእግዚአብሔር ቃል የሆነውንና ያልሆነውን

የወሰኑት አይሁድ እንዳልሆኑ ማስታወስ ጠቃሚ ነው። ይልቁንም እግዚአብሔር በእስትንፋሱ የተጻፈውንና በእርሱ መሪነት የተሰጠውን ቃል ለመለየት ሰዎችን ተጠቀመባቸው።

11ኛ ጥያቄ፥ ክርስቲያኖች ቅዱሳት መጻሕፍት የእግዚአብሔር ቃል እንደሆኑ እርግጠኞች መሆን ያለባቸው ለምንድን ነው?
12ኛ ጥያቄ፥ ሀ) መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ የተሟላና አንዳችም ስሕተት የሌለበት የእግዚአብሔር ቃል ከሆነ፥ ዛሬ እኛ በምንጽፋቸው መጻሕፍትና በምናዘጋጃቸው መልእክቶች ላይ እንዴት ተጽእኖ ያሳድርባቸዋል? ለ) እነዚህስ ጽሑፎቻችንና መልእክቶቻችን «የእግዚአብሔር ቃል» መሆን የሚችሉት እንዴት ነው? ሐ) «መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል ነው» ከምንለው አሳብ ጋር የእኛ መልእክት በምን ይለያል?

ዛሬ ሰዎች በሚሰጡት ስብከትና በሚጽፏቸው መልእክቶች አማካይነት እግዚአብሔር የሚናገር ቢሆንም፥ ለእነዚህ ጽሑፎችና ትምህርቶች ስለምንሰጠው የሥልጣን መጠን ጥንቃቄ ማድረግ አለብን። የእግዚአብሔርን ሙሉ ሥልጣን የያዘው፥ የተጻፈው የእግዚአብሔር ቃል ማለትም መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ ነው። ምንም ስሕተት የሌለበት እርሱ ብቻ ነው። የትኛውም መጽሐፍ ወይም ስብከት እንደ መጽሐፍ ቅዱስ አንዳችም ስሕተት የሌለበት ሊሆን አይችልም። እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ሥልጣን ያለው መልእክትም ሆነ መጽሐፍ የለም፤ የምንጽፈውም ሆነ የምንናገረው ነገር የሚመዘነው በመጽሐፍ ቅዱስ ነው። ሰባኪዎችና ጸሐፊዎች እንደመሆናችን መጠን መጽሐፍ ቅዱስን በጥንቃቄ ማጥናት የእኛ ሓላፊነት ነው። በመጨረሻ ግን ደካሞችና ኃጢአተኞች መሆናችንን በትሕትና መቀበል አለብን። ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ያለን መረዳት ውሱን ነው። ምንም ነቀፋና ስሕተት የለብንም ብለን ለመናገር አንችልም።

13ኛ ጥያቄ፥ ጸሐፊዎች፥ አስተማሪዎችና ሰባኪዎች ይህንን መገንዘብ የሚያስፈልጋቸው ለምንድነው? ክርስቲያኖች ሁሉ መጽሐፍ ቅዱስ የተሟላ መሆኑን ያምናሉ፤ (ራእ. 22፡18-19)። የዮሐንስ ራእይ ከተጻፈ ወዲህ በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ምንም ዓይነት መጽሐፍ መጨመር አይቻልም። ይህም ማለት ዛሬ በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ መጨመር ያለባቸው በመንፈስ መሪነት የተጻፉ መጻሕፍት አሉ የሚሉ ዛሬ የተነሡ የሐሰት ትምህርት አራማጅ ክፍሎች ተሳስተዋል ማለት

ነው። ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር እኩል አድርገው የሚያስተምሩትም ስሕተት ነው።

በ200 ዓ.ዓ. አይሁድ እንደ እግዚአብሔር ቃል መቆጠር አለባቸው ስለሚሉአቸው መጻሕፍት ግልጽ የሆነ አሳብ ነበራቸው፤ ነገር ግን በቅዱሳት መጻሕፍት የአቀማመጥ ቅደም ተከተል አልተስማሙም ነበር። ጸሐፊዎቹ ሲጽፉ ርእስ አልነበራቸውም። በኋላ ግን በመጽሐፉ የመጀመሪያ ዐረፍተ ነገር፥ ወይም መጽሐፉ የሚናገርለት ዋና ሰው ወይም መጽሐፉን ጽፎታል ብለው ይገምቱ በነበረው ሰው ስም በመሰየም ርእስ ይሰጡት ጀመር። በእንግሊዝኛውም ሆነ በአማርኛው (ግዕዝ) መጽሐፍ ቅዱስ ያሉት መጻሕፍት ርእሶች የተገኙት መጀመሪያ ሴፕቱዋጀንት ከሚባለው የግሪኩ መጽሐፍ ቅዱስ ወይም ከካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን የላቲን ቋንቋ መጽሐፍ ቅዱስ ነው። በመጀመሪያዎቹ መጻሕፍት ውስጥ ምዕራፍና ቁጥሮች አልነበሩም። ለመጽሐፍ ቅዱስ የምዕራፍ ክፍፍል የተሰጠው በ1228 ዓ.ም. ሲሆን፥ የቁጥር ክፍፍሎች የተደረጉት ደግሞ በ1547 ዓ.ም. ነበር።

አይሁድ የእግዚአብሔር ቃል ናቸው ብለው ያመኑባቸውን መጻሕፍት ሲያደራጁ በሦስት ዋና ዋና ክፍሎች ከፍለዋቸዋል።

14ኛ ጥያቄ፥ ሉቃ. 24፡44 አንብብ። ኢየሱስ በዚህ ስፍራ የሚጠቅሳቸው ሦስት የብሉይ ኪዳን ክፍሎች የትኞቹ ናቸው?

በዕብራይስጡ መጽሐፍ ቅዱስ አይሁድ በሦስት ዋና ዋና ክፍሎች የተከፋፈሉ ሃያ አራት መጻሕፍት ብቻ ነበራቸው። የመጀመሪያው የዕብራይስጥ መጽሐፍ ቅዱስ ዋና ክፍል ዛሬ አይሁድ ቶራኽ የሚሉት የሕግ ክፍል ነው። የሕግ መጻሕፍት የመጀመሪያዎቹን አምስት መጻሕፍት ማለትም ከኦሪት ዘፍጥረት እስከ ኦሪት ዘዳግም ያሉትን የያዙ ናቸው።

ሁለተኛው የዕብራይስጥ መጽሐፍ ቅዱስ ዋና ክፍል ነቢያት በመባል ሲታወቅ፥ በዚህ ክፍል ስምንት መጻሕፍት ይገኛሉ፡- ኢያሱ፥ መሳፍንት፥ ሳሙኤል፥ ነገሥት፥ ኢሳይያስ፥ ኤርምያስ፥ ሕዝቅኤል፥ እንዲሁም 12ቱ ነቢያት ናቸው። ከዚህ የምንመለከተው ሳሙኤል፥ ነገሥት እና 12ቱ ነቢያት (ከሆሴዕ እስከ ሚልክያስ) ራሳቸውን የቻሉ አንዳንድ መጻሕፍት ብቻ የሆኑ ናቸው። በአሁኑ መጽሐፍ ቅዱሳችን ውስጥ እንዳለው የተለያዩ መጻሕፍት አልነበሩም።

ሦስተኛው ዋና ክፍል «ጽሑፎች» በመባል ይታወቃል። በዚህ ክፍል ውስጥ በሦስት ንዑሳን ክፍሎች የተከፈሉ 11 መጻሕፍት አሉ። በመጀመሪያው ክፍል ሦስት የግጥምና የቅኔ መጻሕፍት (መዝሙረ ዳዊት፥ ምሳሌና ኢዮብ) ሲገኙ፥ በሁለተኛው ክፍል አምስት ጥቅል መጻሕፍት ነበሩ (መኃልየ መኃልይ ዘሰለሞን፥ ሩት፥ ሰቆቃወ ኤርምያስ፥ መክብብና አስቴር)። በሦስተኛው ክፍል ደግሞ «ታሪክ» ተብለው የሚጠሩ ዳንኤል፥ ከዕዝራ እስከ ነህምያ (አንድ መጽሐፍ)፥ ዜና መዋዕል (አንድ መጽሐፍ) ብቻ ነበሩ።

ዛሬ በምንገለገልበት መጽሐፍ ቅዱስ 39 የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት አሉ። ይህ የሆነው አንዳንድ መጻሕፍት ለሁለት ስለተከፈሉ ነው። ለምሳሌ ዕዝራና ነህምያ አሁን ሁለት መጻሕፍት ናቸው። 1ኛና 2ኛ ሳሙኤል፥ 1ኛና 2ኛ ነገሥት እንዲሁም 1ኛና 2ኛ ዜና መዋዕል ተከፍለዋል። የመጻሕፍቱ ቁጥር በዚህ ዓይነት የተለያዩ ቢሆኑም፥ አይሁዶችና ክርስቲያኖች እነዚህ መጻሕፍት የእግዚአብሔር ቃል መሆናቸውን ያምናሉ።

| |
|---|
| 15ኛ ጥያቄ፥ የመጽሐፍ ቅዱስህን ማውጫ ተመልከት። በአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ የሚገኙትን የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ቅደም ተከተል በመጠበቅ ሆሄያቸውን ጭምር በቃል አጥና። ይህንን ነገር ለፈተና በሚገባ ማወቅ አለብህ። |

ነገር ግን የካቶሊክና የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን መጽሐፍ ቅዱስ ከእኛ መጽሐፍ ቅዱስ ለምን ተለየ? ይህንን ጥያቄ ለመመለስ ትንቢተ ሚልክያስ ከተጻፈ በኋላ እስከ ኢየሱስ መምጣት ድረስ ወደነበረው ዘመን መመለስ አለብን። ይህ ዘመን 400 «የጸጥታ ዘመናት» በመባል ይታወቃል፤ ምክንያቱም በዚህ ጊዜ እስከ ሚልክያስ ዘመን እንደነበረው በእግዚአብሔር መንፈስ ተመርተው የእግዚአብሔርን ቃል የጻፉ ምንም ነቢያት እንዳልነበሩ አይሁድ ስለሚያምኑ ነው። እነዚህ ዘመናት በብሉይና በአዲስ ኪዳን ዘመናት መካከል ያሉ ስለሆኑ «በኪዳናት መካከል ያሉ ዘመናት» በመባል ይታወቃሉ። በተጨማሪ በጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ምን እንደተፈጸመ መመልከት አለብን።

በብሉይና በአዲስ ኪዳን ዘመናት መካከል የተጻፉ ሁለት ዓይነት ሥነ -ጽሑፎች ነበሩ። የመጀመሪያው ዓይነት ጽሑፍ «አፖክሪፋ» በመባል ይታወቃል። እነዚህ ጽሑፎች ከ300 ዓ.ዓ. እስከ 100 ዓ.ም. የተጻፉ

ናቸው። አፖክሪፋ ማለት ድብቅ ማለት ነው። በዚህ ስም የተሰየሙበት ሁለት ምክንያቶች አሉ፤ የመጀመሪያው፥ ብዙዎቹ መጻሕፍት የተደበቀ ወይም ምሥጢራዊ መልእክት ስለያዙ ሲሆን፥ ሁለተኛው ምክንያት፥ አይሁድ ከሌሎች ቅዱሳት መጻሕፍት ጋር እኩል ሥልጣን እንዳላቸው ስላላመኑበት ነበር። እነዚህ መጻሕፍት የተጻፉት በዕብራይስጥና በአራማይክ ቋንቋ ሲሆን አንዳንድ ጊዜ ከብሉይ ኪዳን ጋር ተያይዘው ይቀርባሉ።

አሥራ አራት ወይም አሥራ አምስት የሚሆኑት የአፖክሪፋ መጻሕፍት በመጀመሪያ የታዩት ሴፕቱዋጀንት ተብሎ በሚጠራው በግሪክ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ነው። አንዳንዶቹ በባሕሪያቸው ታሪካዊ ናቸው። በአዲስና በብሉይ ኪዳን መካከል የነበረውን ታሪክ ይናገራሉ። ሌሎቹ የፍቅር ታሪኮች እንዲሁም የነቢያት መጻሕፍት ናቸው። አይሁድ እነዚህ መጻሕፍት የብሉይ ኪዳን ክፍል መሆናቸውን የተቀበሉበት ጊዜ ጨርሶ የለም፤ ነገር ግን ደስ ስለ ተሰኙባቸው ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር እንዲቀመጡ ፈቅደው ነበር። በኋላ ግን አይሁድ እነዚህን መጻሕፍት እንደ እግዚአብሔር ቃል እንደማያይዋቸው ያልተገነዘቡና ሴፕቱዋጀንት በተባለው የግሪክ መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ ይጠቀሙ የነበሩ ግሪክኛ ተናጋሪ ክርስቲያኖች እንደ እግዚአብሔር ቃል ይመለከቱአቸው ጀመር። ክርስትና አይሁድ ባልሆኑ ሕዝቦች መካከል እየተስፋፋ በሄደ ቁጥር፥ እነዚህ መጻሕፍት እንደ እግዚአብሔር ቃል መታየታቸው እየጨመረ መጣ። ይህ ቢሆንም እንኳ የዕብራይስጥን ቋንቋ የሚያውቁ አብዛኞዎቹ ምሁራን የአፖክሪፋ መጻሕፍት በመጀመሪያው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንዳልነበሩ ተገንዝበው ነበር። ከ382 እስከ 405 ዓ.ም. ጀሮም የተባለው ሰው መጽሐፉን የሮማ ንጉሠ ነገሥት ቋንቋ በነበረው በላቲን እንዲተረጉም በሮማ ቤተ ክርስቲያን ተጠይቆ ነበር። ይህ መጽሐፍ ቅዱስ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን በይፋ የምትጠቀምበት መጽሐፍ ሲሆን ቨልጌት በመባል ይታወቃል። ጀሮም አፖክሪፋ የተባሉት መጻሕፍት የመጽሐፍ ቅዱስ አካል እንዳልሆኑ ቢያስብም እንኳ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንዲጨምራቸው ታዘዘ፤ ስለዚህ ከዚሁ ጊዜ ጀምሮ እነዚህ መጻሕፍት የካቶሊክ መጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ሆነው ቀሩ። ከ1500 ዓ.ም በኋላ ግን የፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናት (ሉተራን፥ ባፕቲስት ወዘተ) በመሠረታዊ የክርስትና ትምህርት ከካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ተነጥለው ሲወጡና በዕብራይስጥ ቋንቋ የተጻፈውን የመጀመሪያውን መጽሐፍ ቅዱስ

ሲመረምሩ የአፖክሪፋ መጻሕፍት በእግዚአብሔር መንፈስ ምሪት ከተጻፉትና የእግዚአብሔር ቃል ከሆኑት መጻሕፍት መካከል እንዳልሆኑ ተገነዘቡ፤ ስለዚህ መጽሐፍ ቅዱስን ሲተረጉሙ እነዚህን መጻሕፍት መተው ጀመሩ። አንዳንድ የትርጉም ዓይነቶች እነዚህን መጻሕፍት በብሉይ ኪዳን መጨረሻ በተለየ ክፍል ያደርጉአቸዋል።

የአፖክሪፋ መጻሕፍት ኢየሱስ በምድር ይኖር በነበረበት ዘመን የነበሩትን አይሁድ ታሪክና አስተሳሰብ ለመረዳት የሚያስችሉን የሚያኙ ነገሮች ያሉባቸው ቢሆንም እንኳ እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ሊቆጠሩ አይገባም። መጽሐፍ ቅዱስን የበለጠ ለመረዳት ስንፈልግ ልናነባቸው እንችላለን፤ የመጽሐፍ ቅዱስን ያህል ልናከብራቸው ግን አይገባም። ከሌሎች የቅዱሳት መጻሕፍት ክፍሎች ጋር የማይስማሙ ግልጽ የሆኑ ስሕተቶች ይታዩባቸዋል። ከካቶሊኮች ልዩ እምነቶች መካከል ፑርጋቶሪ ወይም ዓፀፋ - ንስሐ የሚባል፥ ሰዎች ከሞቱ በኋላ በሕይወት ሳሉ ስለሠሩት ክፉ ሥራ የሚዳኙበት ቦታ መኖሩ፥ መልካም ተግባር ከፈጸምን በእግዚአብሔር ዘንድ የተሻለ ምሕረትን እናገኛለን የሚለውና የሞተ ሰው ሬሳ ከመቀበሩ በፊት ጸሎተ ፍትሐት ማድረግና የመሳሰለው ሁሉ ከእነዚህ መጽሐፍ የተገኘ ነው።

| |
|---|
| 16ኛ ጥያቄ፥ በዛሬዪቱ የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ትምህርት እነዚህ አመለካከቶች እንዴት ይታያሉ? |

አንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት በመጽሐፍ ቅዱሳቸው የሚጨምሩት አንድ ሌላ ዓይነት ሥነ-ጽሑፍም አለ። በሁለተኛው ዓይነት የሥነ ጽሑፍ ሥራ «ሱደፒግራፋ» በመባል ይታወቃል። «በሌላ ሰው ስም የተጻፈ መጽሐፍ» ማለት ነው። እነዚህ መጻሕፍት የተጻፉት ከ200 ዓ.ዓ. እስከ 200 ዓ.ም. ነው። የተጻፉትም በሰዎች ዘንድ የበለጠ ተቀባይነት እንዲያገኙ በሚጥሩ ሰዎች አማካይነት ነው፤ ስለዚህ በሚጽፉበት ጊዜ በራሳቸው ስም ፈንታ የታወቀ የብሉይ ኪዳን ሰው ስም ይጠቀማሉ። ለምሳሌ «የአዳምና የሔዋን መጽሐፍ» እና «መጽሐፈ ሄኖክ» በመባል የሚታወቁ አሉ። የካቶሊክም ሆኑ የፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናት እነዚህ መጻሕፍት በእግዚአብሔር ምሪት የተጻፉ እንዳይደሉ ይስማማሉ። የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ግን እነዚህ መጻሕፍት የቅዱሳት መጻሕፍት ክፍል ናቸው ብላ ታምናለች፤ ስለዚህ ነው የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን በመጽሐፍ ቅዱስዋ ውስጥ ከሌሎች አብያተ ክርስቲያናት የሚበልጡ

መጻሕፍት ያሏት። የካቶሊክም ሆነ የኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ሠላሳ ዘጠኝ መጻሕፍት ያሉበትን የእኛን መጽሐፍ ቅዱስ ቢጠቀሙም እንኳ የታወቀው አቋማቸው እኛ የእግዚአብሔር ቃል ነው ብለን ከምናስበው የበለጡ መጻሕፍት እንደ አሏቸው ነው። ይሁዳ በመልእክቱ ከቁጥር 14-15 ከእነዚህ መጻሕፍት መካከል ከአንዱ ይጠቅሳል። ይህ ማለት ግን መጽሐፉ በሙሉ በእግዚአብሔር መንፈስ መሪነት የተጻፈ ነው ማለት አይደለም።

የተለያዩ መጽሐፍ ቅዱሶች እንዴት እንደተነጻጸሩ ለማየት የሚከተለውን ዝርዝር ተመልከት፡-

በአይሁድ በፕሮቴስታንት፥ በኦርቶዶክስና በካቶሊክ ብሉይ ኪዳን ውስጥ ያሉ መጻሕፍት

| የአይሁድ ብሉይ ኪዳን፥ | የፕሮቴስታንት ብሉ ይ ኪዳን፥ | የካቶሊክ ብሉይ ኪዳን | የኦርቶዶክስ ብሉይ ኪዳን |
|---|---|---|---|
| <u>ሕግ</u> | ፔንታቱክ (አምስቱ <u>የአራት መጻሕፍት)</u> | ፔንታቱክ (አምስቱ <u>የአራት</u> መጻሕፍት) | |
| 1. ዘፍጥረት | 1. ዘፍጥረት | 1. ዘፍጥረት | 1. ዘፍጥረት |
| 2. ዘጸአት | 2. ዘጸአት | 2. ዘጸአት | 2. ዘጸአት |
| 3. ዘሌዋውያን | 3. ዘሌዋውያን | 3. ዘሌዋውያን | 3. ዘሌዋውያን |
| 4. ዘኁልቁ | 4. ዘኁልቁ | 4. ዘኁልቁ | 4. ዘኁልቁ |
| 5. ዘዳግም | 5. ዘዳግም | 5. ዘዳግም | 5. ዘዳግም |
| <u>ነቢያት</u> | ታሪክ | <u>ታሪክ</u> | |
| 6. ኢያሱ | 6. ኢያሱ | 6. ኢያሱ | 6. ኢያሱ |
| 7. መሳፍንት | 7. መሳፍንት | 7. መሳፍንት | 8. መሳፍንት |
| 8. ሳሙኤል | 8. ሩት | 8. ሩት | 8. ሩት |
| 9. ነገሥት | 9. 1ኛ ሳሙኤል | 9. 1ኛ ሳሙኤል | 9. 1ኛ ሳሙኤል |
| 10. ኢሳይያስ | 10. 2ኛ ሳሙኤል | 10. 2ኛ ሳሙኤል | 10. 2ኛ ሳሙኤል |
| 11. ኤርምያስ | 11. 1ኛ ነገሥት | 11. 1ኛ ነገሥት | 11. 1ኛ ነገሥት |
| 12. ሕዝቅኤል | 12. 2ኛ ነገሥት | 12. 2ኛ ነገሥት | 12. 2ኛ ነገሥት |
| 13. 12 ነቢያት | 13. 1ኛ ዜና መዋዕል | 13. 1ኛ ዜና መዋዕል | 13. 1ኛ ዜና መዋዕል |

| | | | |
|---|---|---|---|
| ሆሴዕ | 14. 2ኛ ዜና መዋዕል | 14. 2ኛ ዜና መዋዕል | 14. 2ኛ ዜና መዋዕል |
| ኢዩኤል | 15. ዕዝራ | 15. ዕዝራ | 15. ዕዝራ |
| አሞጽ | 16. ነህምያ | 16. ነህምያ | 16. ነህምያ |
| አብድዩ | 17. አስቴር | 17. ጦቢት | 17. አስቴር |
| ዮናስ | | 18. ዮዲት | |
| ሚክያስ | <u>ግጥምና ቅኔ</u> | 19. አስቴር (ሌሎች | 18. ኢዮብ |
| ናሆም | | ተጨምረው) | 19. መዝሙረ ዳዊት |
| ዕንባቆም | 18 ኢዮብ | | 20. ምሳሌ |
| ሶፎንያስ | 19. መዝሙረ ዳዊት | 20. 1ኛ ማክቤዝ | 21. መጽሐፈ ተግሣጽ |
| ሐጌ | 20. መጽሐፈ ምሳሌ | 21. 2ኛ ማክቤዝ | 22. መጽሐፈ መክብብ |
| ዘካርያስ | 21. መክብብ | <u>ቅኔ</u> | 23. መኃልየ መኃልይ |
| ሚልክያስ | 22. መኃልየ መኃልይ | 22. ኢዮብ | |
| | | 23 መዝሙረ ዳዊት | 24. ኢሳይያስ |
| <u>ጽሑፎች</u> | <u>ትንቢት</u> | 24. ምሳሌ | 25. ኤርምያስ |
| 14. መዝሙረ ዳዊት | 23. ኢሳይያስ | 25. መክብብ | 26. ሰቆቃው ኤርምያስ |
| 15. ኢዮብ | 24. ኤርምያስ | 26. መኃልየ መኃልይ | 27. ሕዝቅኤል |
| 16. ምሳሌ | 25. ሰቆቃው ኤርምያስ | ዘሰሎሞን | 28. ዳንኤል |
| 17. ሩት | 26. ሕዝቅኤል | 27. የሰሎሞን ጥበብ | 29. ሆሴዕ |
| 18. መኃልየ መኃልይ | 27. ዳንኤል | 28. የጥበብ መጽሐፍ | 30. አሞጽ |
| ዘሰሎሞን | | | 31. ሚክያስ |
| 19. መክብብ | 28. ሆሴዕ | | 32 ኢዩኤል |
| 20. ሰቆቃው ኤርምያስ | 29. ኢዩኤል | <u>ትንቢት</u> | 33. አብድዩ |
| 21. አስቴር | 30. አሞጽ | 29. ኢሳይያስ | 34. ዮናስ |
| 22. ዳንኤል | 31. አብድዩ | 30. ኤርምያስ | 35. ናሆም |
| 23. ዕዝራ -ነህምያ | 32. ዮናስ | 31. ሰቆቃው ኤርምያስ | 36. ዕንባቆም |
| 24. ዜና መዋዕል | 33. ሚክያስ | 32. ባሮክ (የኤርምያስን መልእክት) | 37. ሶፎንያስ |
| | 34. ናሆም | 33. ሕዝቅኤል | 38. ሐጌ |
| | 35. ዕንባቆም | 34. ዳንኤል (ቀሪውን የትንቢተ | 39. ዘካርያስ |
| | 36. ሶፎንያስ | ዳንኤል ክፍል ሶስና፣የሠለስቱ | 40. ሚልክያስ |
| | 37. ሐጌ | ደቂ መዝሙር ቤልና ደራጎን) | |
| | 38. ዘካርያስ | 35. ሆሴዕ | 41. ዕዝራ ሱቱኤል |
| | 39. ሚልክያስ | 36. ኢዩኤል | 42. ዕዝራ ካልዕ |
| | * የታናናሽ ነቢያት | 37. አሞጽ | 43. ጦቢት |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | ቅደም ተከተል ይለያያል | 38. አብድዩ | 44. ዮዲት |
| | | 39. ዮናስ | 45. አስቴር |
| | | 40. ሚክያስ | 46. መቃብያን ቀዳማዊ |
| | | 41. ናሆም | 47. መቃብያን ካልዕ |
| | | 42. ዕንባቆም | 48. መቃብያን ሣልስ |
| | | 43. ሶፎንያስ | 49. ሲራክ |
| | | 44. ሐጌ | 50. ጸሎተ ምናሴ |
| | | 45. ዘካርያስ | 51. ተረፈ ኤርምያስ |
| | | 46. ሚልክያስ | 52. ሶስና |
| | | | 53. ባሮክ |
| | | | 54. ጥበብ |
| | | | 55. ሠለስቱ ደቂቅ |
| | | | 56. ተረፈ ዳንኤል |
| | | | 57. ኩፋሌ |
| | | | 58. ሔናክ |

** በአማርኛና በእንግሊዝኛ መጽሐፍ ቅዱሳችን ውስጥ ያሉት መጻሕፍት አንድ ዓይነት ቢሆኑም፥ በመጻሕፍቱ አቀማመጥ ቅደም ተከተል፥ ምዕራፎቹና ቁጥሮቹ በተጻፉበት ሁኔታ አልፎ አልፎ ልዩነት አለ። ይህንን በተለይ የምናየው በመዝሙረ ዳዊት ውስጥ ሲሆን በአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በቅንፍ ያለው ቁጥር ከእንግሊዝኛው ጋር አንድ ዓይነት ነው። ይህ የሆነው የአማርኛው መጽሐፍ ቅዱስ ለመጻሕፍቱ ቅደም ተከተል፥ ለምዕራፎቹና ለቁጥሮቹ የተጠቀመው የሴፕቱዋጀንቱን ትርጉም ስለሆነ ነው።

** የኦርቶዶክስ መጽሐፍ ቅዱስ የያዘው 58 የብሉይ ኪዳን መጻሕፍትና 27 የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ሲሆን በጠቅላላው 85 (ሰማንያ አምስት) ነው።

የአሁኑ የፕሮቴስታንት መጽሐፍ ቅዱስ የአዋልድ መጻሕፍትን አስቀርቶ በካቶሊክ መጽሐፍ ቅዱስ ያለውን የቩልጌትን ቅደም ተከተል ይከተላል። ይሁን እንጂ የፕሮቴስታንት አማኞች በዕብራይስጥ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንደ እግዚአብሔር ቃል የሚቆጠሩትን ብቻ ይቀበላሉ።

17ኛ ጥያቄ፥ በእግዚአብሔር መንፈስ ምሪት የተጻፉ የትኞቹ መጻሕፍት እንደሆኑና እንደ እግዚአብሔር ቃል መቆጠር የሌለባቸው መጻሕፍት የትኞቹ እንደሆኑ ማወቅ ጠቃሚ የሚመስልህ ለምንድን ነው?

## 3ኛ ቀን:- የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት የጊዜ ቅደም ተከተል

18ኛ ጥይቄ፥በመጽሐፍ ቅዱስ መጀመሪያ ያለውን ማውጫ ተመልከት። ቀደም ሲል ባነበብከውና ባጠናኸው የእግዚአብሔር ቃል መሠረት፥ የብሉይ ኪዳንን መጻሕፍት? ለመመደብ ከሚከተሉት የተሻለ ዘዴ ነው በምትለው ከፋፍላቸው። ሀ) በታሪክ መጻሕፍት፥ ለ) በግጥምና ቅኔ መጽሐፍ፥ ወይም ሐ) በነቢያት መጽሐፍ ውስጥ።

ከላይ ባየነው ሥንጠረዥ መሠረት ብሉይ ኪዳንን በተለያዩ ክፍሎች መከፈል እንችላለን። በመጀመሪያ ፔንታቱክ የተባለ ክፍል አለ። ፔንታቱክ ወይም የሙሴ ሕግ የመጀመሪያዎቹን አምስት ቅዱሳት መጻሕፍት ይዞአል። በእነዚህ አምስት መጻሕፍት ውስጥ ብዙ የተለያዩ የሥነ -ጽሑፍ ዓይነቶች አሉ:- ታሪክ፥ ግጥምና ቅኔ፥ ሕግና ትንቢት። ከአምስቱ ሦስቱ የሚናገሩት ከታሪክ ጋር የተያያዘ ነገር ነው። እነዚህም ዘፍጥረት፥ ዘጸአትና ዘኁልቁ ናቸው። የዘጸአትና የዘኁልቁ መጻሕፍት አንዳንድ ሕጎችን ይዘዋል። ደግሞም የተመረጠውን የአይሁድን ሕዝብ ታሪክ የሚናገር ክፍል ነው። ሁለት መጻሕፍት ማለት ዘሌዋውያንና ዘዳግም በአብዛኛው እግዚአብሔር ለእስራኤል ሕዝብ ስለ ሰጣቸው ሕግ ይናገራሉ። ዘሌዋውያን በተለይ እግዚአብሔር ለእስራኤል ሕዝብ በሲና ተራራ ላይ ሕግን ስለሰጠበት ሁኔታ ይናገራል። ዘዳግም ደግሞ ሙሴ ከ38 ዓመታት በኋላ እስራኤላውያን ወደ ተስፋዪቱ ምድር ከመግባታቸው ጥቂት ቀደም ብሎ እንዴት ሕጉን እንደደገመው የሚነግረን ነው።

በሁለተኛ ደረጃ ታሪክ የሚባል ክፍል አለ። በብሉይ ኪዳን ሁለተኛ ክፍል ውስጥ 12 መጻሕፍት አሉ። እነዚህ መጻሕፍት በኢያሱ መሪነት ወደ ተስፋይቱ ምድር ወደ ከነዓን ከገቡበት ጊዜ ጀምሮ (ኢያሱ)፥ ከ1000 ዓመታት በኋላ ከባቢሎን ምርኮ እስከተመለሱበት ጊዜ ድረስ (መጽሐፈ ነህምያ)፥ ያለውን የአይሁድ ሕዝብ ታሪክ ይናገራል። እነዚህ መጻሕፍት በአብዛኛው ጊዜ በቅደም ተከተል የተቀመጡ ናቸው። የቀሩት

የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት በተለያዩ ጊዜያት በዚህ የታሪክ ወቅት የተጻፉ ናቸው።

ሦስተኛው ክፍል፥ ግጥምና ቅኔ ይባላል። እነዚህ ከኢዮብ ጀምሮ እስከ መኃልየ መኃልይ ዘሰሎሞን ባሉት ጊዜያት ውስጥ የተጻፉ ናቸው። መጽሐፈ ኢዮብ በሙሴ ተጽፎ ይሆናል። አብዛኞዎቹ የግጥምና የቅኔ መጻሕፍት የተጻፉት በዳዊትና በሰሎሞን ዘመነ መንግሥት ነው። አንዳንዶቹ መዝሙሮች የተጻፉት ዘግየት ብለው በ400 ዓ.ዓ. በዕዝራ ነው፤ ስለዚህ እነዚህ አምስት የግጥምና የቅኔ መጻሕፍት የተጻፉት ረዘም ባለ ጊዜ ውስጥ ነው። ቅደም ተከተላቸው ግን ጊዜን የሚመለከት አይደለም።

አራተኛው ክፍላችን፥ ትንቢት ይባላል። በብሉይ ኪዳን ትንቢት ውስጥ የተመደቡ 17 መጻሕፍት አሉ። እነዚህ መጻሕፍት በተጨማሪ በ2 ምድብ ተከፍለዋል። የመጀመሪያው የታላቅ ነቢያት መጻሕፍት ሲሆን፥ በዚህ ክፍል ውስጥ አምስት መጻሕፍት ይገኛሉ፥ እነርሱም ከኢሳይያስ እስከ ዳንኤል ያሉት ናቸው። ታላቅ የተባሉትም በመልእክታቸው ርዝመትና ጥልቀት ነው።

ሁለተኛ የታናናሽ ነቢያት መጻሕፍት ናቸው። ከሆሴዕ እስከ ሚልክያስ ያሉት እነዚህ 12 መጻሕፍት በመጀመሪያው የዕብራይስጥ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አንድ መጽሐፍ ነበሩ።


| 1450 ዓ.ዓ. | 1410 ዓ.ዓ. | 1100 ዓ.ዓ. |
|---|---|---|
| ፔንታቱክ | | የተባበረው መንግሥት |

| 933 ዓ.ዓ. | 586 ዓ.ዓ. | 539 ዓ.ዓ. | 400 ዓ.ዓ. |
|---|---|---|---|
| የተከፋፈለው መንግሥት | ምርኮ<br>ዳንኤል (605 - 535)<br>ሕዝቅኤል (593 - 571) | ሐጌ (520) ከምርኮ መልስ<br>( ዘካርያስ) (520-480) | ሚልክያስ<br>(432-424) |

| | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ዘፍጥረት | ዘጸአት | ዘኍልቍ | ኢያሱ | መሳፍንት | 1ኛ ሳሙኤል | 2ኛ ሳሙኤል | 1ኛ ነገሥት | *2ኛ ነገሥት |
| ዕዝራ | ነህምያ | ኢዮብ | ዘሌዋውያን | ዘዳግም | ሩት | 1ኛ ዜና መዋዕል | 2ኛ ዜና መዋዕል | አስቴር |

* በ2ኛ ነገሥት ጊዜ የነበሩትን ነቢያት ሠንጠረዥ ከዚህ በታች ተመልከት።

853 ዓ.ዓ. ________ 800 ________ 700 ________ 600 ____ 586 ዓ.ዓ.


ኢዩኤል (835)
ዮናስ (782-753)
አሞጽ (760-753)
ሆሴዕ (755-715)
ኢሳይያስ (740-680)
ሚክያስ (735-700)
ናሆም (664-654)
ሶፎንያስ (632)
ኤርምያስ (627-580)
ዕንባቆም (609-605)
አብድዩ (605-586)
2ኛ ነገሥት

እላይ ያለውን ሠንጠረዡን አጥና። የሚከተሉትን ነገሮች ልብ በል። በመጀመሪያ፥ የእስራኤልን ታሪክ የጊዜ ቅደም ተከተል መግለጫ የሚሰጡ 11 መጻሕፍት ብቻ አሉ። እነዚህ መጻሕፍት ዓለም ከተፈጠረበት ጊዜ አንሥቶ እስራኤላውያን ከምርኮ እስከ ተመለሱ ድረስ ያለውን ታሪክ የሚያካትቱ ናቸው። በሌላ አነጋገር ከቀድሞው ዘመን ጀምሮ እስከ 400 ዓ.ዓ. ማለት ነው። የእነዚህ መጻሕፍት ታሪክ አብዛኛው ከ1450 እስከ 400 ዓ.ዓ. ያሉትን ዘመናት የሚያጠቃልል ነው።

በርካታ የሆኑት ሌሎች መጻሕፍት ታሪካዊ ናቸው፤ ነገር ግን ታሪካቸው የተፈጸመው በሌላ ታሪካዊ መጽሐፍ ዘመን ነው። ለምሳሌ የሩት ታሪክ የተፈጸመው በመሳፍንት ዘመን ነው። 1ኛና 2ኛ ዜና መጻሕፍት ከ2ኛ ሳሙኤል እስከ 2ኛ ነገሥት ያሉትን ታሪኮች ይደግማል። የመጽሐፈ አስቴር ታሪክ የተፈጸመው ደግሞ በዕዝራ መጽሐፍ ታሪክ ዘመን ነው።

ሁለተኛ፥ አብዛኞቹ መጻሕፍት የተጻፉት በእስራኤል ታሪክ ውስጥ በነበሩ ሦስት ጊዜያት ነው። በቅድሚያ፥ የመጀመሪያዎቹ አምስቱ የሙሴ መጻሕፍት (ፔንታቱክ) በሙሴ የተጻፉት እስራኤላውያን ለ40 ዓመታት በምድረ በዳ በተንከራተቱበት ጊዜ ነው። ሁለተኛ ጊዜ፥ አብዛኛዎቹ የግጥምና የቅኔ መጻሕፍት የተጻፉት በዳዊትና በሰሎሞን ዘመነ መንግሥት ነው። ሦስተኛ፥ ይሁዳ ከመማረኩ ጥቂት ቀደም ብሎ፥ ወዲያው ከምርኮ እንደተመለሱም በርካታ የነቢያት መጻሕፍት ተጽፈዋል። እነዚህ መጻሕፍት የተጻፉት እግዚአብሔር ኃጢአተኛ የሆኑት እስራኤላውያን ወደ ንሥሐ እንዲደርሱ ፈልጎ በላካቸው ነቢያት ነው።

19ኛ ጥያቄ፥ ሀ) የብሉይ ኪዳን መጻሕፍትን ክፍፍል በቃልህ አጥናና በእያንዳንዱ ክፍፍል ውስጥ ሊሆኑ የሚችሉትን መጻሕፍት ለይ። ለ) የብሉይ ኪዳን መጻሕፍትን ጊዜ ቅደም ተከተል በቃልህ አጥና።

## የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ታሪክ ጥናት

20ኛ ጥያቄ፥ የዓለምን፥ የኢትዮጵያንና የራስህንም ነገድ የሚመለከቱ ታሪኮችን ማወቅ ለምን ያስፈልጋል?

ሕይወታችን በሙሉ በታሪክ፥ ወይም ባለፈው ጊዜ በእኛ ሕይወት ውስጥ በተፈጸመውም ሆነ በዓለም ዙሪያ በመሆን ላይ ባሉት ክስተቶች

ተጽእኖ ሥር ነው። ለምሳሌ፡- ኢጣሊያን፥ ሩሲያን፥ አሜሪካን፥ እንግሊዝን፥ ወዘተ ሳናውቅና ከኢትዮጵያ ጋር ስላላቸው ግንኙነት ሳንረዳ፥ አዲሲቷን ኢትዮጵያ መረዳት ያስቸግረናል። እነዚህ ሕዝቦች ሁሉ በኢትዮጵያ ላይ አሉታዊም ሆነ አዎንታዊ ተጽእኖ ስለነበራቸው ያ ተጽዕኖ አሁንም ድረስ ውጤት አለው። እንዲሁም ደግሞ የምኒልክን ወይም የኃይለ ሥላሴን መንግሥት ሥረ-መሠረት ሳናውቅ አዲሲቷን ኢትዮጵያን ለመረዳት አንችልም። ለእነዚህ የተለያዩ ሕዝቦችና አገሮች ያለን አመለካከት የተለያየ ቢሆንም፥ ሁሉም ግን በእኛ ላይ ያሳደሩት ተጽዕኖ አለ። ያለፉትን ክስተቶች የበለጠ በተረዳን ቁጥር በአሁኑ ጊዜ በአገራችን የሚደረገውን ነገር በተሻለ ሁኔታ እየተረዳን እንሄዳለን።


መጽሐፍ ቅዱስን ስለመረዳትም ተመሳሳይ ነገር ማለት ይቻላል። መጽሐፍ ቅዱስ ታሪካዊ መጽሐፍ ነው። በብሉይ ኪዳን ውስጥ የተጻፉ ታሪኮች ከብዙ መቶ ዓመታት በፊት በመካከለኛው ምሥራቅ የተፈጸሙ የእውነተኛ ክስተቶች ታሪክ ነው። በዚያ ዘመን የነበሩ ታሪኮችንና የምድሪቱን ሁኔታ የበለጠ በተረዳን ቁጥር፥ መጽሐፍ ቅዱስን በተሻለ ሁኔታ እንረዳለን። ለምሳሌ በከነዓን ምድር ላይ የነበራቸውን ሚና ለመረዳት ስለ ግብፅ፥ ባቢሎን፥ ፋርስ፥ ሮም፥ ግሪክ ወዘተ ማወቅ በጣም አስፈላጊ ነው። የአይሁድና የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ከዓለም ታሪክ ጋር የተሳሰረ ነው። ይሁን እንጂ ከዓለም አመለካከት አንጻር አይሁድ በዓለም ታሪክ ውስጥ መጠነኛ ሚና ተጫውተዋል። ከእግዚአብሔር አመለካከት አንጻር ግን የታሪክ እምብርት ናቸው። እግዚአብሔር ስለመረጣቸው፥ መጽሐፍ ቅዱስን በእነርሱ በኩል ስለሰጠ፥ መሢሑ ኢየሱስ ክርስቶስን ወደዚህ ዓለም በእነርሱ በኩል ስለላከ ወዘተ. አይሁድ ከሌላው ሕዝብ ሁሉ ይልቅ እጅግ አስፈላጊ ሕዝብ ናቸው። ይህም ማለት አይሁድ በትውልዳቸው ከሌላ ዘር የተሻሉ ናቸው ማለት አይደለም። ነገር ግን ዓለምን በካህንነት እንዲያገለግሉ በእግዚአብሔር ተመርጠው ነበር፤ (ዘጸ. 19፡5-6)።

ብሉይ ኪዳን የዓለምን ሕዝቦች ታሪክ ለመናገር አይፈልግም። በግብፅና በመሰጴጦምያ ስለነበሩት አስደናቂ የሥልጣኔ ክስተቶች አያስተምርም። እነዚህን ሕዝቦች የሚጠቅሰው ከእስራኤል ሕዝብ ጋር በነበራቸው ግንኙነት አንጻር ብቻ ነው። ብሉይ ኪዳን ከምዕራቡ ዓለምና ከመካከለኛው ምሥራቅ አስቀድሞ ስለታየው የቻይና ታላቅ ሥልጣኔ የሚናገረው ነገር የለም።

ብሉይ ኪዳን እጅግ ጥንታዊ መጽሐፍ ነው። በውስጡ የያዛቸው ታሪኮች ወደማይታወቅ ኋለኛ ዘመን ይሄዳሉ፤ ስለዚህ አንዳንድ ድርጊቶች የተፈጸሙበትን ዘመን መናገር አስቸጋሪ ነው። ለምሳሌ፡- ዓለም የተፈጠረችበትን አዳምና ሔዋን በምድር ላይ መኖር የጀመሩበትን ዘመን በትክክል መናገር የሚቻልበት መንገድ የለም፤ ነገር ግን በከርሰ-ምድር ጥናት አማካይነት እርግጠኛ ልንሆንባቸው የምንችል ድርጊቶች የተፈጸሙባቸው ዘመናትም አሉ። ለምሳሌ፡- አብዛኛዎቹ የእስራኤል ነገሥታት የነገሡበትን ጊዜ በአንድና በሁለት ዓመት ልዩነት መወሰን ይቻላል።

21ኛ ጥያቄ፥ ሀ) የሚከተሉትን ሰዎች በታሪካዊ ቅደም ተከተል አስቀምጥ፡- ዳዊት፥ አዳምና ሔዋን፥ ሄኖክ፥ ኖኅ፥ ሳኦል፥ አብርሃም፥ ሰሎሞን። ለ) በብሉይ ኪዳን ታሪክ ውስጥ እጅግ ጠቃሚ ሚና የተጫወቱ ሌሎች የብሉይ ኪዳን ሰዎችን ጥቀስ።

የተለያዩ ሰዎች በተለያዩ መንገዶች የታሪክን ዘመናት ይቆጥራሉ። ቻይናዎች የራሳቸው መንገድ አላቸው። አይሁድ ከፍጥረት ጀመረ ብለው የሚናገሩት የራሳቸው መንገድ አላቸው። ክርስቲያኖችም የራሳቸው መንገድ አላቸው። ዛሬ አብዛኛው የዓለም ሕዝብ የክርስቲያንን የቀን መቁጠሪያ ይከተላል። ክርስቲያኖች ታሪክን በሁለት ታላላቅ ዘመናት ይከፍሉታል። የመጀመሪያው ዘመን ከክርስቶስ ልደት በፊት (ዓመተ ዓለም) ይባላል። ይህ ዘመን ከዓለም ፍጥረት ይጀምርና እስከ ክርስቶስ መወለድ ድረስ ይቀጥላል። ሁለተኛው ዘመን ከክርስቶስ ልደት በኋላ ያለው ሲሆን በአማርኛ ዓመተ ምሕረት (ዓ.ም.) ብለን እንጠራዋለን። (በእንግሊዝኛ ኤ.ዲ. ተብሎ ሲታወቅ የመጣውም ከላቲኑ «አኖ ዶሚኒ» ማለትም «የጌታችን ዓመት» ነው።) በክርስቲያኖች የቀን መቁጠሪያ ዓመቱ ወደ ኢየሱስ ልደት በቀረበ መጠን ቁጥሩ እየቀነሰ ይመጣል። ከክርስቶስ ልደት በኋላ ቁጥሩ እየጨመረ ይመጣል። የሚከተለውን መግለጫ ተመልከት፡-




በብሉይ ኪዳን ዘመን ቁጥሩ እንዴት እያነሰ ይሄድ እንደነበር ወደ ክርስቶስ ደግሞ እየቀረበ እንደመጣ ከሥዕሉ ልብ በል። ከክርስቶስ በፊት

በ2000 ዓመታት ገደማ የኖረው አብርሃም ከክርስቶስ ልደት በፊት 1000 ዓ.ዓ. ገደማ ከኖረው ከዳዊት ዘመን የበለጠ ቁጥር አለው። በሌላ አንጻር ስናየው ኢየሱስ ክርስቶስ ከተወለደ አንድ ሺህ ዘጠኝ መቶ ሰማንያ ስምንት ዓመታት አልፈዋል ማለት ነው።

በኢትዮጵያና በአውሮፓ የዘመን አቆጣጠር መካከል ልዩነት የሚታየው ለምንድነው? ምክንያቱ ኢየሱስ ክርስቶስ የተወለደበትን ጊዜ በሚመለከት መካከል አለመግባባት በመኖሩ ነው። ሰዎች የክርስቲያንን የቀን መቁጠሪያ ይጠቀማሉ። ኢየሱስ ክርስቶስ በተወለደበት ዘመን የቀን አቆጣጠርን ማንም አልጀመረም። ስለዚህ ኢየሱስ ክርስቶስ መቼ እንደተወለደ ትክክለኛውን ጊዜ ሊያውቁ አልቻሉም። ምዕራባውያን አገሮች የተከተሉት ግሪጎሪ የተባለው ሰው የጀመረበትን የቀን አቆጣጠር ነበር። ይህም የቀን መቁጠሪያ በ1582 ዓ.ም. የጀመረ ሲሆን የግሪጎሪያን የቀን መቁጠሪያ በመባል ይታወቃል። ኢትዮጵያ ደግሞ ሌላ የቀን መቁጠሪያን ትጠቀማለች። ሁለቱም የቀን መቁጠሪያዎች አዲሱን ዘመን የሚጀምሩት ከኢየሱስ ልደት ቢሆንም፥ እነዚህ የቀን መቁጠሪያዎች በስምንት ዓመታት ይለያያሉ።

የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁራን የመጽሐፍ ቅዱስን ታሪክ በተለያዩ ክፍለ ጊዜያት ይከፍላሉ። ቀጥሎ በብሉይ ኪዳን ያለውን የእስራኤል ታሪክ ባጭሩ እንመለከታለን።

1. ከአይሁድ የእምነት አባቶች (ፓትሪያርኮች) በፊት የነበረው ዘመን (2500-2000 ዓ.ዓ.)

ከዘፍ. 1-11 የጥንት ታሪኮችን አጭር መግለጫ እንመለከታለን። ታሪኩ የሚጀምረው የመጀመሪያዎቹ ወንድና ሴት ከተፈጠሩበት አጠቃላይ ታሪክ አጀማመር ነው። እግዚአብሔር ዓለምን እንዲሁም አዳምንና ሔዋንን የፈጠረበትን ጊዜ የሚያውቅ ማንም የለም። በእነዚህ የኦሪት ዘፍጥረት 11 ምዕራፎች የብዙ ሺህ ዓመታት ታሪክ አጠር ባለ መልኩ ቀርቧል። የእነዚህ ምዕራፎች ዋና ዓላማ ዓለም እንዴት እንደተጀመረች፥ ኃጢአት በዓለም እንዴት እንደተስፋፋ እንዲሁም ከአዳም እስከ አብርሃም ያለውን የአይሁድ የዘር ሐረግ ለመከተል ነው።

አይሁድ ሴማውያን ከተባሉ ዘሮች የተገኙ ነገዶች ወይም የሴም ዝርያ ናቸው። ሴማውያን በብዛት የሚኖሩት በመካከለኛው ምሥራቅ፥

በኤፍራጥስና በጤግሮስ ወንዞች መካከል በሚገኘውና መሰጴጦምይ በተባለው ሥፍራ ነው። የጥንት ሥልጣኔ የተጀመረው በዚያ ስፍራ ነው። ጽሑፍ፥ ሒሣብ፥ ሥነ ጥበብ፥ ሕግ፥ ሕክምና፥ ወዘተ በመጀመሪያ የተጀመረው በዚህ ስፍራ ነው። በ2100 ዓ.ዓ. ገደማ የመሰጴጦምያ ዋና ከተማ በደቡብ መሰጴጦምያ የምትገኘው የዑር ከተማ ነበረች። የደቡብ መሰጴጦምያን አብዛኛዎቹን ክፍሎች በሚቆጣጠር በአንድ ንጉሥ ሥር የምትገዛ ነበረች። ይህ ሁኔታ ባስገኘው ሰላም ምክንያት ለሥልጣኔ በፍጥነት ማደግ ምቹ ሁኔታ ተፈጥሯል። አብርሃምና አባቱ ካራን የመጡት ከዚህ ስፍራ እንደነበር እናያለን። አብርሃም የኖረበትን ትክክለኛ ዘመን ባናውቅም እንኳ፥ ዑርን ትቶ ወደ ከነዓን የሄደው በዚህ ዘመን መጨረሻ አካባቢ ነው።

ይህ ከተማ በሥልጣኔ ያደገና የላቀ እንደነበረ ማወቃችን፥ አብርሃም በሥልጣኔ እጅግ የበለፀገችውን አገር ትቶ ኋላ ቀር ወደ ሆነችው ወደ ከነዓን ለመሄድ ያደረገውን አስቸጋሪ ምርጫ ያሳየናል። እግዚአብሔር ሰውን ከአዲስ አበባ ወጥቶ በሐመር ባኮ፥ ወይም ራቅ ካሉ አካባቢዎች በአንዱ እንዲኖር የተናገረውን ያህል ነው። ምርጫው አስቸጋሪ ነበር። አብርሃም ያደረገውን በእምነት የመታዘዝ ከፍተኛ እርምጃ ያሳየናል።

| |
|---|
| 22ኛ ጥያቄ፥ ሀ) ዑርን ለቆ እንዲወጣ እግዚአብሔር ለአብርሃም የሰጠው ትእዛዝ አስቸጋሪ የነበረው ለምንድነው? ለ) ዛሬ እግዚአብሔር ለእኛ የሚሰጠን አስቸጋሪ የሆነ ተመሳሳይ ትእዛዝ ምንድነው? (ማቴ. 28፡19-20 ተመልከት)። ሐ) በአሁኑ ጊዜ የአብርሃም ምሳሌነት ለእኛ መልካም ትምህርት የሚሰጠን እንዴት ነው? |

2. የአይሁድ የእምነት አባቶች (የፓትሪያርኮች) ዘመን (2000-1600 ዓ.ዓ.)

በእነዚህ ዓመታት የዑር ከተማ ኃይል ማሽቆልቆል ጀመረ። መሰጴጦምያ በአንድ ንጉሥ መገዛቷ ቀረና «የከተማ ግዛቶች» ወደሚባሉ ትናንሽ ክልሎች ተከፋፈለች። ይህም ማለት ዋና ዋናዎቹ ከተሞች በአካባቢያቸው ያሉ ክልሎችን ሁሉ መቆጣጠር ጀመሩ። በእያንዳንዱ ከተማም ንጉሥ ነበር። ይሁን እንጂ ሕዝቡ እንደ ቀድሞው ታላቅና ኃያላን አልነበሩም። ይህም በተለይ የከነዓንን ምድር በሚመለከት እውነት ነበር። እያንዳንዱ ከተማ በንጉሥ ቁጥጥር ሥር ነበር።

አብርሃም፥ ይስሐቅና ያዕቆብ በከነዓን ምድር ይኖሩ በነበሩበት ጊዜ ምድሪቱ በሕዝብ ብዛት አልተጨናነቀችም ነበር። ይህ ማለት ከተለያዩ ነገዶች ጋር ሳይጋጩ በነፃነት ይንቀሳቀሱ ነበር ማለት ነው።

በእነዚህ ዓመታት የግብፅ አገር በአካባቢው ባሉ አገሮች ላይ የነበራት የበላይነት እያየለ መጣ። የከነዓንን ምድር ክልል ከዕለት ወደ ዕለት እየተቆጣጠረች መጣች። እንደሚታወሰው አብርሃም፥ ያዕቆብና ዮሴፍ ግብፅን ጎብኝተዋል። በእነዚህ ዓመታት ዮሴፍ በግብፅ ውስጥ በይበልጥ ሁለተኛው ኃያል መሪ ሆኖ ነበር።

ከዘፍጥረት 12-50 ያሉት ታሪኮችና መጽሐፈ ኢዮብ በዚህ የታሪክ ክፍለ ጊዜ ውስጥ የሚካተቱ ናቸው።

3. ግብፅ እስከ ዘመነ መሳፍንት (1600-1200 ዓ.ዓ.)

የግብፅ አገር ሥልጣኔ የጀመረው በ3100 ዓ.ዓ. ነው። ከ2700-2200 ዓ.ዓ. ባሉት ዘመናት ግብፅ እጅግ ኃያል ሆነች፤ በከነዓንም ላይ በከፍተኛ ደረጃ የበላይ ሆነች። እስካሁን ድረስ በግብፅ የሚታዩት አንዳንዶቹ ትላልቅ ፒራሚዶች የተሠሩት በዚህ ጊዜ ነው።

ነገር ግን ከ1800-1600 ዓ.ዓ. ከሶርያና ከከነዓን የመጡ «ሐይክሶስ» የተባሉ ነገዶች ግብፅን ተቆጣጠሩ። ይህም የግብፅ ኃይል እየተዳከመ የመጣበት ጊዜ ነበር። በእነዚህ ዓመታት ነበር በግብፅ የነበሩ ከ70 የማይበልጡ አይሁድ እስከ ከ1 ሚሊዮን በላይ የሆኑት።

በ1600 ዓ.ዓ. አካባቢ ግብፆች ዓመፁና እንደገና የራሳቸውን አገር ማስተዳደር ጀመሩ። ግብፆች የምድራቸው አብዛኛውን ክፍል የወሰዱባቸውን «የውጭ አገር ዜጎች» ጠሏቸው። ስለዚህ የቻሏቸውን ባሪያዎች ሲያደርጉ፥ ሌሎቹን ከአገር አስወጧቸው። አይሁድ በግብፃውያን ባርነት ቀንበር ሥር የወደቁት በዚህ ዘመን ነበር። በዚህ ጊዜ ግብፃውያን ደቡብ ሱዳንን፥ ከነዓንን በሙሉ እስከ ኤፍራጥስ ወንዝ ድረስ ያሉትን መንገዶች ያዙ። ግብፅ እንደገና ኃያል አገር ሆነች።

ነገር ግን በ1400 ዓ.ዓ. የግብፅ ኃይልና የበላይነት ማሽቆልቆል ጀመረ። በፍልስጥኤም ላይ የነበራቸውን አገዛዝ አጡ። ብዙዎቹ ምሁራን እንደሚያስቡት አይሁድ በግብፅ ከነበሩበት ግዞት ወጥተው ከነዓን በመድረስ የራሳቸውን አገር ያቋቋሙት በዚህ ጊዜ ነበር። ይህንን ከአራት

ዘጸአት ጀምሮ እስከ መሳፍንት ባሉት ክፍሎች ውስጥ እናገኘዋለን። መጽሐፈ ሩት የተፈጸመውም በዚህ የታሪክ ወቅት ነው።

| |
|---|
| 23ኛ ጥያቄ፥ እግዚአብሔር የግብፅን ታሪክ በመቆጣጠር ለሕዝቡ ጥቅም ያዋለው እንዴት ነው? ከ1400-1200 ዓ.ዓ. ከነዓን የታላላቅ ኃያላን መንግሥታት የጦርነት ሜዳ ሆነች። በሰሜን በኩል ወደ ከነዓን ዘልቀው በመግባት ጥቃት የሚያደርሱ ኬጢያውያን በመባል የሚታወቁ ነገዶች ነበሩ። በደቡብ በኩል ግብፆች የከነዓንን ድንበር ተቆጣጥረው ለመቆየት ይዋጉ ነበር። |

ከነዓን በጣም ጠቃሚ የነበረችው ለምንድነው? የተለያዩ ሁለት አህጉሮች መገናኛ ስለነበረች ነው፡- በደቡብ በኩል አፍሪካ፥ በሰሜን ደግሞ እስያ። ከግብፅ ወደ መስጴጦምያ የሚያልፉ ሁለት እጅግ ጠቃሚ የንግድ መሥመሮች ነበሩ። ከነዓን በስተምሥራቅ ያለው ምድረ በዳ ብቻ ስለሆነና በምዕራብ በኩል ደግሞ የሜዴትራኒያን ባሕር ስለነበር፥ ነጋዴዎች በደቡብ በኩል ካለው ከግብፅ ወደ ሰሜኑ መስጴጦምያ ለመሄድ በከነዓን ማለፍ ግድ ሆኖባቸው ነበር፤ እነዚህን የንግድ መሥመሮች የተቆጣጠረ ማንኛውም ክፍል ባለጸጋ ሆነ፤ ስለዚህ ውሾች በአጥንት ላይ እንደሚጣሉ እነዚህ አገሮች በከነዓን ላይ የበላይ ለመሆን ይዋጉ ነበር።

በዚህ ጊዜ ነበር መሳፍንት በእስራኤል የገዙት። በመሳፍንት ክፍለ ዘመን ያለማቋረጥ የምናነበው እግዚአብሔር ረድቶአቸው ነፃ እስኪያወጣቸው ድረስ የተለያዩ ነገዶች እስራኤልን ይገዙ እንደ ነበር ነው።

በ1200 ዓ.ዓ. ግብፅ ኃይሏን አስተባበረችና ከነዓንን መቆጣጠር ጀመረች። ይህ ማለት በግብፆችና በኬጢያውያን መካከል ከፍተኛ ጦርነት ነበር ማለት ነው። ኬጢያውያን ተሸነፉ። ዳሩ ግን በጦርነቱ ጦስ በከነዓን ዙሪያ የነበሩ በርካታ ከተሞች ተደመሰሱ።

## 4. የኋለኛው የመሳፍንት ዘመንና የሳኦል ዘመን (1200-1000 ዓ.ዓ.)

ግብፆች ኬጢያውያንን ቢያሸንፉም እንኳ ኃይላቸው ለረጅም ጊዜ አልቆየም። ኃይላችው ወዲያውኑ ያሽቆለቁል ጀመር። በውጤቱም በከነዓን ላይ የነበራቸውን አንዳንድ የበላይነት አጡ። በእነዚህ ዓመታት አንድ አዲስ ነገድ ወደ ከነዓን ምድር መግባት ጀመረ። ከሜዲትራኒያን ባሕር

ደሴቶች የመጡ በመሆናቸው «የባሕር ሰዎች» በመባል ይታወቁ ነበር። ከባሕር ሰዎች መካከል አንዱ ቡድን ፍልስጥኤማውያን በመባል ይታወቁ ነበር። ከዘመን መሳፍንት መጨረሻ ጀምሮ በዘመን ነገሥታት ሁሉ ፍልስጥኤማውያን ዋናዎቹ የአይሁድ ጠላቶች ነበሩ። ፍልስጥኤማውያን ከእስራኤላውያን የበለጠ በእውቀት የላቁ ነበሩ። በዚህ ዘመን ነበር የብረት መሣሪያዎችን የመሥራት ዘዴዎች ማወቅ የጀመሩት።

| |
|---|
| 24ኛ ጥያቄ፥ 1ኛ ሳሙ. 13፡19-23 አንብብ። ፍልስጥኤማውያን እስራኤልን እንዲቆጣጠሩ ይህ እውቀት እንዴት ረዳቸው? |

የመጨረሻዎቹ መሳፍንት ከነበሩት ከሳምሶንና ከሳሙኤል ጀምሮ እስከ ዳዊት መንገሥ ድረስ ፍልስጥኤማውያን አብዛኛውን እስራኤልን ይቆጣጠሩ ነበር። በእነዚህ ዓመታት ማንም እንደ ግብፅ ያለ ታላቅ መንግሥት ፍልስጥኤምን የገዛ አልነበረም። ይህ ዘመን የታየው በዘመን መሳፍንት መጨረሻና በ1ኛ ሳሙኤል ላይ ነው።

* (ማሳሰቢያ፡- ዛሬ በኢትዮጵያ ውስጥ በእነዚህ ጳለስጢና፥ ጳለስጢናውያንና ፍልስጥኤማውያን የተባሉት የተለያዩ ስሞች የግንዛቤ ችግር አለ። ጳለስጢና የሚለው ስም ከሜዲትራኒያን ደሴቶች ፈልሰው ወደ ከነዓን ለመጡ ሰዎች የተሰጠ ነው። ፍልስጥኤማውያን የእስራኤልን ጠረፍ መቆጣጠር ከጀመሩ ወዲህ በግብፅና በመስጴጦምያ መካከል የነበረውን ዋናውን መንገድ ያዙ። በውጤቱም የአሕዛብ መንግሥታት ሕዝቦች ያለማቋረጥ ከእነርሱ ጋር ግንኙነት ያደርጉ ነበር። ምድሪቱንም «የፍልስጥኤሞች» ምድር ወይም ጳለስጢና በመባል ተጠራች። ጳለስጢና በዮርዳኖስ ወንዝ በስተምዕራብ ከግብፅ እስከ ኤፍራጥስ ወንዝ ድረስ ያለው አገር በሙሉ የተለመደ መጠሪያ ሆኖአል። ስለዚህ ፍልስጥኤማውያን ከቀርጤስ ደሴት የመጡ አውሮጳውያንን ይመስላሉ። በአሁኑ ዘመን ያሉ ግን ፍልስጥኤማውያን ዐረቦች ናቸው፤ ስለዚህ ከቀድሞዎቹ ጋር አንድ ዓይነት አይደሉም። ከ700 ዓ.ም. በኋላ የዐረብ መንግሥታት እስራኤልን አሸንፈው በዚያ ይኖሩ ጀመር። እስራኤል በ1948 ዓ.ም. እንደገና የራሷን መንግሥት ስታቋቁም በዚያ የነበሩ አንዳንድ ዐረቦች ከዚያ ለቀቁ፤ ስለዚህ ፍልስጥኤማውያን በዘመናዊቷ እስራኤል ውስጥ የነበሩ አሁንም በእስራኤል ውስጥ በአንዳንድ ስፍራዎች ወይም ከእስራኤል ውጭ በስደት የሚኖሩ ዐረቦች ናቸው። የዘመናችን ፍልስጥኤማውያንና አይሁድ

የሚያደርጉት ትግል እስራኤል የእኔ ነው የምትለውን ምድር፥ ፍልስጥኤማውያንም የእኛ ነው በማለታቸው ነው።)

5. የዳዊትና የሰሎሞን መንግሥት (ከ1000 - 900 ዓ.ዓ.)

25ኛ ጥያቄ፥ 1ኛ ነገሥት 4:21-24 አንብብ። በሰሎሞን አመራር ጊዜ የእስራኤል መንግሥት ይዞታ ምን ያህል ነበር?

ግብፅ በፍልስጥኤም ላይ የነበራት ቁጥጥር እየቀነሰ ሲሄድና በመስጴጦምያ አንድ ኃያል መንግሥት ባለመተካቱ፥ የእስራኤል መንግሥት ኃይል እየጨመረ ሊሄድ ቻለ። በዳዊት የጦር አመራር የእስራኤል መንግሥት በደቡብ በኩል እስከ ግብፅ፥ በሰሜን በኩል ደግሞ እስከ ኤፍራጥስ ድረስ ተስፋፋ። በዚህ ጊዜ የእስራኤል ሕዝብ 12 የተለያየ ነገድ ከመሆን በአንድ ንጉሥ የሚተዳደር አንድ ሕዝብ ሆነ። ዋና ከተማዋ ኢየሩሳሌምም ተገነባች።

26ኛ ጥያቄ፥ የዳዊትን መንግሥት የክልል ዳርቻዎች ለመገንዘብ በጀርባ የሚገኘውን ካርታ ተመልከት። ይህ እግዚአብሔር በኦሪት ዘፍጥረት ውስጥ ከሰጠው የቃል ኪዳን ተስፋ ጋር እንዴት ይያያዛል? (ዘፍጥ. 15:17-21)።

ዳዊት ተዋግቶ የሕዝቡን የግዛት ዳርቻ ያሰፋ ሲሆን፥ ሰሎሞን ከአባቱ ወረሰ። በአብዛኛው የሰሎሞን ዘመነ መንግሥት ሰላም የነበረ ሲሆን የአባቱን የዳዊትን ምድር በሚገባ ተቆጣጥሮ ነበር፤ ነገር ግን በሕይወቱ መጨረሻ አካባቢ የተለያዩ መንግሥታት ዓመፅ እያየለበት ሄዶ ነበር። እርሱ ሲሞት አንድ የነበረው የእስራኤል መንግሥት ለሁለት ተከፈለ። የሰሜኑ መንግሥት «እስራኤል» ሲባል የደቡቡ «ይሁዳ» ተባለ።

ይህ ዘመን ለአይሁድ ሕዝብ «ወርቃማው ዘመን» በመባል ይታወቃል። ይህ ኃይላቸው ከፍተኛ ደረጃ ላይ የደረሰበት ዘመን ነበር። አስደናቂ የሆኑ አንዳንዶቹ ጽሑፎቻቸውም የተጻፉት በዚህ ጊዜ ነበር፤ በአይሁድ ታሪክ ከየትኛውም ጊዜ ይልቅ ሕዝቡ እግዚአብሔርን የተከተለበት ጊዜ ይህ ነበር። ምክንያቱም መሪዎቻቸው እግዚአብሔርን የሚፈሩ ሰዎች ነበሩ፤ ስለዚህ ዘመን በ2ኛ ሳሙኤል፥ 1ኛ ነገሥት 11ና 1ኛ ዜና፥ 2ኛ ዜና እስከ 9 ተጽፎ እናገኛለን። አብዛኛዎቹ የግጥምና የቅኔ መጻሕፍት (መዝሙረ ዳዊት፥ ምሳሌ፥ መክብብና መኃልየ መኃልይ ዘሰሎሞን) የተጻፉት በዚህ ዘመን ነበር።

27ኛ ጥያቄ፥ የአንድ የቤተ ክርስቲያን መሪ መንፈሳዊ ሕይወት በቤተ ክርቲያኒቱ አባሎች ሕይወት ላይ እንዴት ተጽዕኖ ሊያሳድር ይችላል?

6. የሶርያውያን በኃይል መነሣት (900-800 ዓ.ዓ.)

ከሰሎሞን ሞት በኋላ ኃያል የነበረው የእስራኤል መንግሥት ተከፋፍሎ መውደቅ ጀመረ። በዳዊትና በሰሎሞን ጊዜ በእስራኤል ቁጥጥር ሥር የነበሩ ሶርያውያን (አራማውያን ተብለውም ይጠሩ ነበር) ሰሎሞን ከሞተ በኋላ ማመፅ ጀመሩ። ወዲያውኑ ዋና ከተማቸውን ደማስቆ በማድረግ ኃያል መንግሥታት ሆኑ። በእነዚህ ዓመታት ጳለስጢና ውስጥ ሶርያውያን ኃያላን በመሆን አብዛኛውን የእስራኤልን ምድር ተቆጣጠሩ።

ሁለቱ ታላላቅ ነቢያት ኤልያስና ኤልሳዕ ያገለገሉትም በእነዚህ ዓመታት ነበር። የእስራኤልና የይሁዳ መንግሥታት ታሪክ ከ1ኛ ነገሥት 12 - 2ኛ ነገሥት 14 ድረስ ይገኛል። በተጨማሪ በ2ኛ ዜና ምዕራፍ 10-27 ተጽፎ እናገኛለን። ትናንሽ መጻሕፍት ከጻፉ ነቢያት አንዳንዶቹም መጻሕፍቶቻቸውን የጻፉት በዚህ ዘመን ነው።

7. የአሦር ጊዜ (850-650 ዓ.ዓ.)

ሶርያ ኃያል መንግሥት መሆን በጀመረችበት ጊዜ በሰሜን በኩል ደግሞ ሌላ በጤግሮስ ወንዝ የነበረው መንግሥትም ኃያል ሆነ። ይህ መንግሥት የአሦር መንግሥት ነበር። አሦራውያን መስጴጦምያን ተቆጣጠሩና በደቡብ በኩል ያሉትን ሶርያውያንን መዋጋት ጀመሩ። በመጨረሻም ሶርያውያንና የእስራኤል የሰሜኑ መንግሥት በአሦራውያን ተሸነፉ። በ722 ዓ.ዓ. የእስራኤል መንግሥት ተሸነፈና ሕዝቡ በአሦራውያን ተማርከው በመስጴጦምያ ሁሉ ተበተኑ። አሦራውያን አብዛኛውን የይሁዳን መንግሥት ቢቆጣጠሩም እንኳ በሕዝቅያስ መሪነት እግዚአብሔር ይሁዳን ታደገና ኢየሩሳሌም በአሦራውያን እጅ እንዳትወድቅ አደረገ።

የዚህ ዘመን ታሪክ በ2ኛ ነገሥት 15-23ና 2ኛ ዜና 28-36፡4 ይገኛል። አንዳንዶቹ ትናንሽ የነቢያት መጻሕፍትና ኢሳይያስም የተጻፉት በዚህ ጊዜ ነው።

8. የባቢሎን መንግሥት የአገዛዝ ዘመን 650-550 ዓ.ዓ.

በ650 ዓ.ዓ. ታላቁ የአሶር መንግሥት የተለያዩ ሕዝቦች ስለ ዓመፁበት መውደቅ ጀመረ። የአሦር መንግሥት በ612 ዓ.ዓ. በመስጴጦምያ ባቢሎን ተብሎ በሚጠራ መንግሥት ተሸነፈ። ባቢሎን ከአሦር ደቡብ በኤፍራጥስ ወንዝ አካባቢ የሚገኝ ነው። የባቢሎን መንግሥት በታላቁ መሪው በናቡከደነፆር በታላቅ ፍጥነት አድጎ ከባቢሎን ጀምሮ እስከ ግብፅ ያሉትን አካባቢዎች ተቆጣጠረ። ከ606-586 ዓ.ዓ. ሦስት ተከታታይ ዘመቻዎች ተደርገው የደቡብ ይሁዳ መንግሥት ተሸነፈና ሕዝቡም በምርኮኛነት ተወሰደ።

2ኛ ነገሥት 24-25ና 2ኛ ዜና 36 ስለዚህ ዘመን ይናገራሉ። ከታናናሽ ነቢያት መጻሕፍት አንዳንዶቹ፥ እንዲሁም ኤርምያስ፥ ሕዝቅኤልና ዳንኤል የተጻፉት በዚህ ጊዜ ነው።

9. የሜዶንና የፋርስ የአገዛዝ ዘመን 550-331 ዓ.ዓ.

በ550 ዓ.ዓ. የሜዶንና የፋርስ መንግሥታት በባቢሎን መንግሥት ላይ ዓመፁና በ539 ዓ.ዓ. አሸነፏት። ባቢሎን ይዛው የነበረውን ምድር በሙሉ ተቆጣጠሩና በዛሬ ጊዜ ቱርክ እስከሚባለው እስከትንሹ እስያ ድረስ ተስፋፉ። በቁጥጥራቸው ሥር ካሉ መንግሥታት ጋር በሰላም ለመኖር ስለፈለጉ የሜዶንና የፋርስ መንግሥታት ባቢሎናውያንና አሦራውያን የማረኳቸውን ሕዝቦች በሙሉ ወደየአገሮቻቸው እንዲሄዱና ቤተ መቅደሶቻቸውን እንዲሠሩ ፈቀዱላቸው። እንዲመለሱና ቤተ መቅደሳቸውን እንዲሠሩ ከተፈቀደላቸው መንግሥታት መካከል አንዱ የይሁዳ መንግሥት ነበር። በዘሩባቤል፥ በዕዝራና በነህምያ መሪነት ቤተ መቅደሱና የኢየሩሳሌም ቅጥሮች እንደገና ተሠሩ።

በብሉይ ኪዳን ውስጥ የምናነበው የመጨረሻው ኃያል መንግሥት ይህ ነው። እያንዳንዱን ታሪክ በመጽሐፈ ዕዝራና ነህምያ ውስጥ እናነባለን። የመጽሐፈ አስቴር ታሪክም የተፈጸመው በዚህ ጊዜ ነው። የሐጌ፥ የዘካርያስና የሚልክያስ መጻሕፍትም የተጻፉት የፋርስ መንግሥት በሥልጣን ላይ በነበረበት በ400 ዓ.ዓ. ነው።

ከዘመነ ብሉይ በኋላና በሁለቱ ኪዳኖች መካከል በነበረው ዘመን (400-0ዓ.ዓ.)፥ አይሁድ ከ166-63 ዓ.ዓ. ለአጭር ጊዜ ነፃነት ከማግኘታቸው በስተቀር ብዙውን ጊዜ በሌላ ሕዝብ ቁጥጥር ሥር ኖረዋል። በ331 ዓ.ዓ. ሜዶንና ፋርስ በግሪክ መንግሥት እጅ ወደቁ።

በኋላም የግሪክ መንግሥት በተራው ክርስቶስ በተወለደበትና የአዲስ ኪዳን ዘመን በተጀመረበት ጊዜ ጳለስጢናን ይቆጣጠር በነበረው በሮም መንግሥት እጅ ወደቀ።

የብሉይ ኪዳን የዓለምንና የእስራኤልን ታሪክ በምንመረምርበት ጊዜ በርካታ ነገሮችን ለማየት እንችላለን። እስራኤል በጣም ጠቃሚ የሆነችው በእግዚአብሔር እንጂ በሰው ዓይን እንዳልሆነ ማስታወስ አለብን። በአካባቢው ከነበሩ መንግሥታት ጋር ስትወዳደር ሁልጊዜ ከቁጥር የማትገባ ነበረች፤ ነገር ግን እስራኤል ለእግዚአብሔር በታዘዘች ጊዜ በአካባቢዋ ካሉ ሕዝቦች ሁሉ ይልቅ ብርቱ ነበረች። እግዚአብሔርን አልታዘዝም ስትልና በሕይወቷም ሆነ በአምልኮዋ አንዳንድ ነገሮችን ስትቀይጥ እግዚአብሔር ሊቀጣት ለአሕዛብ መንግሥታት አሳልፎ ይሰጣት ነበር።

| |
|---|
| 28ኛ ጥያቄ፥ ይህ ጉዳይ ቤተ ክርስቲያን ከዓለም ጋር በሚኖራት ግንኙነት አንፃርና እግዚአብሔር በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከሚሠራበት መንገድ ጋር ያለው ተመሳሳይነት ምንድን ነው? |

የእስራኤልን ሕዝብ ታሪክ በምናጠናበት ጊዜ አንድ ሌላ መሠረታዊ እውነት እናያለን። በዓለም ላይ ያሉ ክስተቶች የሚፈጸሙት ያለ እግዚአብሔር ቀጥተኛ ቁጥጥር ሳይሆን፥ ታሪክን በሙሉ የሚመራው እርሱ እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምረናል። አንዳንድ ነገሥታትና መንግሥታትን የሚያስነሣ ደግሞም የሚጥል እርሱ ነው። በዘመናችን ሳይቀር በዓለምም ሆነ በአገራችን የሚፈጸሙትን ታሪኮችንና ክስተቶችን ሁሉ የሚቆጣጠር አምላካችን እንደሆነ እርግጠኞች ልንሆን እንችላለን።

| |
|---|
| 29ኛ ጥያቄ፥ በአስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ ይህ እውነት ክርስቲያኖችን እንዴት ያበረታታቸዋል? |

## 4ኛ ቀን:- የመካከለኛው ምሥራቅ መልክዓ ምድር

| |
|---|
| 30ኛ ጥያቄ፥ በመጽሐፉ ጀርባ ያለውን ካርታ ተመልከት። በካርታውም ላይ የሚከተሉትን ስፍራዎች አመልክት። ሀ) ግብፅ፥ ለ) ባቢሎን፥ ሐ) አሦር፥ መ) መስጴጦምያ ሠ) የጤግሮስ ወንዝ፥ ረ) የኤፍራጥስ ወንዝ፥ ሰ) የዮርዳኖስ ወንዝ፥ ሸ) የሚዲትራኒያን ባሕር፥ ቀ) ከነዓን፥ በ) ሶርያ ተ) ትንሹ እስያ ቸ) ቀይ ባሕር። |

31ኛ ጥያቄ፥ ሀ) አሁን ባለንበት ዘመን በመካከለኛው ምሥራቅ የሚገኙ አገሮችን ስም ዘርዝር። ለ) በድንበሮቻቸው የሚገኙ የታወቁ የብሉይ ኪዳን አገሮች የትኞቹ ናቸው?
32ኛ ጥያቄ፥ ሀ) የአንድን ስፍራ መልክዓ ምድር መረዳት በዚያ ስፍራ የሚኖሩ ሰዎችን አኗኗር ለመረዳት እንዴት ይጠቅማል? ለ) መጽሐፍ ቅዱስን ለመረዳትና ለመተርጎምስ እንዴት ይጠቅማል?

የብሉይ ኪዳን ታሪክ እምብርት የከነዓን ምድር ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ይህ ስፍራ አራት ስሞች ተሰጥቶታል። በመጀመሪያ፥ ብዙ ጊዜ የሚጠራበት «ከነዓን» የሚለው ስም ነው።

33ኛ ጥያቄ፥ ዘፍ. 9፡18-27 ተመልከት። ከነዓን ማን ነው?

የኖኅ የልጅ ልጆች ከነበሩት መካከል ከነዓን የሚባለው አንዱ እንደ ነበረ በብሉይ ኪዳን እናነባለን። አባቱ በሠራው ኃጢአት ምክንያት እግዚአብሔር ከነዓንን ለሴምና ለያፌት ዘሮች ባሪያ እንዲሆን ረግሞት ነበር። በዘፍጥረት 10 እንደምናነበው የከነዓን ዝርያዎች በዮርዳኖስ ወንዝ በስተምዕራብ በዮርዳኖስ ወንዝና በሜዲትራኒያን ባሕር መካከል ሰፍረው ነበር። ይህ አካባቢ የኖኅ የልጅ ልጅ በሆነው በከነዓን ዝርያዎች ስም ከነዓን ተብሎ ተጠራ። ደግሞም ይህ አካባቢ ከነዓን ይባል የነበረው «የሐምራዊ ምድር» ለማለትም ነው። ምክንያቱም በከነዓን ይኖሩ የነበሩ ሰዎች በዘመኑ ሀብታሞች ሊለብሱ የሚችሉትን ሐምራዊ ቀለም ያላቸው ልብሶችን ይሠሩ ስለነበር ነው። ጳለስጢና የሚለው ቃል ከኤፍራጥስ ጀምሮ እስከ ግብፅ ያለውን ምድር በሙሉ የሚያጠቃልል ሲሆን፥ ከነዓን የሚለው ቃል ግን በጳለስጢና ውስጥ ያለ አነስተኛ ምድርን የሚጠቅስ ነው።

ሁለተኛ፥ ምድሪቱ አንዳንድ ጊዜ «የተስፋይቱ ምድር» በመባል ትጠራለች። ምክንያቱም እግዚአብሔር ከአብርሃም ጋር ቃል ኪዳን ባደረገ ጊዜ (በዘፍ. 15፡7) የከነዓንን ምድር ለአብርሃም ርስት አድርጎ እንደሚሰጠው ቃል ገብቶለታል። አብርሃምና ዝርያዎቹ ከ400 ዓመታት ለሚበልጥ ጊዜ ምድሪቱን ባይወርሱም እንኳ በእግዚአብሔር የተስፋ ቃል መሠረት የእነርሱ ነበረች። ለእስራኤል በርስትነት ተስፋ የተሰጠች ምድር ስለሆነች «የተስፋይቱ ምድር» ሆና ቀይታለች (ሕዝ. 48 ተመልከት)።

ሦስተኛ፥ ምድሪቱ አንዳንዴ «ጳለስጢና» ተብላ ተጠርታለች። ይህ ስም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ባይገኝም፥ አሕዛብ ለከነዓን ምድር

የሚሰጡት የተለመደ ስም ነው። (ስለ ፍልስጥኤማውያን፥ ስለ ጳለስጢናና ስለ ጳለስጢናውያን በትላንትና ትምህርታችን የተመለከትነውን ከልስ።)

አራተኛ፥ ምድሪቱ አንዳንዴ «እስራኤል» ተብላ ተጠርታለች። ይህ የሚያመለክትው ከ1400 ዓ.ዓ. - 70 ዓ.ም. እና ከ1948 ዓ.ም. ጀምሮ የአይሁድ ምድር መሆንዋን ነው። ከአይሁድ አባቶች አንዱ የሆነው ያዕቆብ በኋላ ስሙ እስራኤል ተብሎ እንደተለወጠ ይታወቃል (ዘፍ. 32፡28)። ስለዚህ እስራኤል የሚለው ስም የሚያመለክተው የያዕቆብን ዝርያዎችና በእግዚአብሔር የተስፋ ቃል ኪዳን መሠረት ስለወረሷት ምድር ነው።

እግዚአብሔር በጣም ትንሽ የሆነችውን የከነዓንን ምድር ይወርሱ ዘንድ ለአይሁድ የሰጠው ለምንድን ነው? እንደ አሜሪካ፥ ኢራቅ ወይም ኢትዮጵያን የመሳሰሉ ትልልቅ አገሮች ለምን አልሰጣቸውም? ስለከነዓን ምድር በጣም አስፈላጊ የሆነው ነገር ምንድን ነው?

የከነዓን ምድር ትልቅ አይደለችም። የእስራኤል መንግሥት በጣም ትልቅ የነበረችው በዳዊትና በሰሎሞን ዘመን ሲሆን በዚያን ጊዜም 800 ኪሎ ሜትር ርዝመትና 200 ኪሎ ሜትር ስፋት ነበራት፤ ይህም ከአሰብ እስከ አዲስ አበባ ያለው ርቀት ማለት ነው። ብዙ ጊዜ ግን የእስራኤል ምድር 225 ኪሎ ሜትር ርዝመትና 100 ኪሎ ሜትር ስፋት ብቻ ነበራት፤ ይህ ከአዲስ አበባ እስከ ሻሸመኔ ድረስ ካለው ርቀት ጋር የሚወዳደር ነው።

ከነዓን የዓለም እምብርት ለመባል ትችላለች፤ ምክንያቱም ሁለት ዋና ዋና አህጉራት ማለትም አፍሪካና እስያ የሚገናኙባት ቦታ ናት። በጥንት ዘመን ደግሞ በጣም ጠቃሚ የነበረችው፡- በአፍሪካ፥ በእስያና እንዲሁም በአውሮጳ ዋና የንግድ መሥመር ላይ ትገኝ ስለነበረ ነው። አሁንም ቢሆን በታሪክ ውስጥ እጅግ ጠቃሚ ሚና መጫወቷን ቀጥላለች፤ ምክንያቱም መካከለኛው ምሥራቅ በነዳጅ ዘይት ከፍተኛ ሀብት ያለው አካባቢ ስለሆነ ነው። የዚህ ዘመን ሥልጣኔ በነዳጅ ዘይት ላይ የተመሠረተ ነው። እንደ እውነቱ ከሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ራሱ እነዚህን ስፍራዎች ለመያዝ አሕዛብ በሚያደርጉት ትግል በምድር ላይ የመጨረሻው ጦርነት የሚካሄደው በእስራኤል ነው ይላል። በተጨማሪ፥ የዓለም የሥነ- መለኮት ትምህርት ማዕከልም ናት። የዓለም ሦስቱ ዋና ዋና ሃይማኖቶች ይሁዲነት፥ ክርስትናና እስልምና መሠረታቸውን ያገኙት ከእስራኤል ነው።

በጥንቱ መካከለኛ ምሥራቅ የነበሩ ታላላቅ አገሮች

የተለያዩ የጥንት ሕዝቦች የት እንደ ነበሩና ከአሁኑ ዓለም ጋር እንዴት እንደሚወዳደሩ ለማወቅ የጥንቶቹን ዋና ዋና የመጽሐፍ ቅዱስ ሕዝቦችና በጊዜያችን ከየትኛው አገር እንደሆኑ እንመለከታለን። ስለ እነዚህ ሕዝቦች በምታነብበት ጊዜ በመጽሐፉ መጨረሻ ላይ ባለው ካርታ የነበሩበት ስፍራ የት እንደሆነ ተመልከት።

1. ኢትዮጵያ ወይም ኩሽ:- በዕብራይስጥ መጽሐፍ ቅዱስ ከግብፅ በስተደቡብ ቀጥሎ የሚገኘው አገር ኩሽ ተብሎ ይጠራ ነበር። ኋላም በሴፕቱዋጀንት የግሪክ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ግሪኮች ይህንን ምድር ኢትዮጵያ ብለው ጠርተዋል፤ ስለዚህ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ኩሽና ኢትዮጵያ የአንድ ስፍራ ሁለት ስሞች ናቸው። የእንግሊዝኛና የአማርኛ ትርጉም መጽሐፍ ቅዱሶች ለዚህ ምድር «ኢትዮጵያ» የሚለውን የግሪክ ስም ይጠቀማሉ። የኩሽ ወይም የኢትዮጵያ ምድር ከአሁንዋ ኢትዮጵያ ጋር አንድ አይደለም፤ ነገር ግን በዓለም ታሪክ ውስጥ «ኑቢያ» ተብላ ትጠራ የነበረችው ዛሬ በሰሜን ሱዳን የምትገኝ አገር ነች። በመጽሐፍ ቅዱስ መልክዓ ምድር መሠረት ኑቢያ የመጨረሻዋ ደቡባዊ ክፍል ያለችው አገር ነች። የአሁንዋ ኢትዮጵያ መጀመሪያ ስምዋን ያገኘችው ከግሪኩ መጽሐፍ ቅዱስ ነው፤ ነገር ግን ኢትዮጵያ ወይም ኩሽ ብሎ መጽሐፍ ቅዱስ ከጠራው ስፍራ ጋር ሙሉ ለሙሉ ተመሳሳይ አይደለችም። የአሁንዋ ኢትዮጵያ ከአክሱም መንግሥት ውስጥ በተለያዩ ነገሥታት አመራር ሥር የነበረችና አሁን ወዳለው የክልል ዳርቻ እያደገች የመጣች ነች።

የሳባ ሕዝብ ዛሬ የመን ተብሎ በሚጠራው በደቡብ ምዕራብ ዐረቢያ የነበረ ሳይሆን አይቀርም። ነገር ግን አንዳንዱ የግዛቱ ክፍል በቀይ ባሕር ወደ ሰሜን ኢትዮጵያ ተስፋፍቶ ሊሆን ይችላል።

2. ግብፅ:- ልክ እንደ ጥንትነቷ ያለች ብቸኛ አገር ግብፅ ናት። በሰሜን ምሥራቅ አፍሪካ የምትገኝና ከጥንቱ ዓለም ታላላቅ ሥልጣኔዎች የአንደኛው ማዕከል የነበረች አገር ናት። በብሉይ ኪዳንም በተደጋጋሚ አገሪቱ በዚህ ሁኔታ ተጠቅሳለች። የሕይወቷ ሁሉ ምንጭ የሆነው ከኢትዮጵያና ከሱዳን የሚፈሰው የዓባይ ወንዝ ነው። የዓባይ ወንዝ በበጋም ሆነ በክረምት ጊዜ ለሰብልና ለከብቶች ውኃን

ስለሚሰጥ የግብፅ ምድር ሁልጊዜ ምግብ ያገኛል። አብርሃምና ያዕቆብ በድርቅ ጊዜ ወደ ግብፅ የሄዱት በዚህ ምክንያት ነው።

3. ከነዓን፡- የከነዓን ምድር የሚገኘው ከግብፅ በስተሰሜን ነው። በመጠን አነስተኛ ብትሆንም፥ የተለያዩ ሕዝቦችን ይዛለች። በዮርዳኖስ ወንዝ በስተምሥራቅ የጥንት እስራኤል ጠላቶች የነበሩ ሦስት የአሕዛብ መንግሥታት ነበሩ። በደቡብ ኤዶም፥ ከኤዶም በስተሰሜን ሞዓብና ከሞዓብ በስተሰሜን ደግሞ አሞን ነበሩ። እነዚህ አገሮች ይገኙ የነበሩት በአሁኑ ጊዜ ዮርዳኖስ ተብሎ በሚታወቀው አገር ምዕራባዊ ጫፍ ነው።

ከዮርዳኖስ ወንዝ በስተምዕራብ የእስራኤል ምድር ይገኛል። ታሪክ ሁሉ እስራኤላውያን የኖሩት በከነዓን ተራራማ አገር በአገሪቱ በስተ ደቡብ ከቤርሳቤህ በሰሜን እስከሚገኘው ዳን ድረስ ነው። በምዕራብ ሜዲትራኒያን ባሕር ዳርቻ በዘመነ መሳፍንት የእስራኤላውያን ዋና ጠላቶች የነበሩት ፍልስጤማውያን ይገኛሉ። ልክ እንደ ጥንቱ ዘመን ይህ ምድር ዛሬ እስራኤል ተብሎ ይጠራል። ነገር ግን ከዚህ አካባቢ የተወሰነው ክፍል በዘመናችን ባሉ ፍልስጥኤማውያን፥ በሶርያና በዮርዳኖስ የይገባኛል ጥያቄ ውስጥ ወድቋል።

4. ከእስራኤል በስተ ምሥራቅ የአራሚያን ወይም የሶርያ ሕዝቦች ይገኛሉ። ዋና ከተማቸው ደማስቆ የሆነው ሶርያውያን ብዙ ጊዜ የእስራኤል ጠላቶች ሆነው ሲቆዩ፥ በተለይ የእስራኤል መንግሥት ለሁለት ተከፍሎ በነበረ ጊዜ ዋና ጠላቶች ነበሩ። ዛሬ ይህ ሕዝብ ያለበት አገር ሶርያ ተብሎ ይጠራል።

5. ከእስራኤል በስተሰሜን ምዕራብ በሜዲትራኒያን ባሕር ዳርቻ ፊኒሺያ (ፊንቄ) የምትባል አገር ነበረች። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ይህ አካባቢ በተለይ የሚታወቀው በዋና ከተማዎቹ በጢሮስና በሲዶና ነው። ይህ ሕዝብ በጣም የሚታወቀው የሜዲትራኒያን ባሕር በሙሉ ይካሄድ በነበረው የባሕር ላይ ንግድ ነው። ዳዊትና ሰሎሞን ቤተ መቅደሱንና ቤተ መንግሥቱን ለመገንባት የሠለጠነ የሰው ኃይል ፍለጋ ወደ ጢሮስ ሄደው ነበር። በአሁኑ ጊዜ ይህ አካባቢ ሊባኖስ በመባል ይታወቃል።

6. ከእስራኤል በስተሰሜን ምሥራቅ ራቅ ብሎ አሦር፥ ባቢሎን፥ ሜዶንና ፋርስ የሚባሉ አራት አገሮች ነበሩ። የእነዚህ አራት አገሮች ሕዝቦች በተለይ መስጴጦምያ በሚባለው አካባቢ ይኖሩ ነበር። መስጴጦምያ የሚባለው አካባቢ የፋርስ ባሕረ ሰላጤን ይዞ በስተሰሜን ምዕራብ ከሁለት ታላላቅ ወንዞች ማለትም ከኤፍራጥስና ጤግሮስ አጠገብ የሚገኝ ነው።

ሀ. አሦር፡- አሦር የሚገኘው ከመስጴጦምያ በስተሰሜን በጤግሮስ ወንዝ አጠገብ ነበር። ዋና ከተማው ነነዌ ነበረ። በ700 ዓ.ዓ. አሦር በመስጴጦምያ፥ ጳለስጢናና በግብፅ ሁሉ ላይ የበላይነት አግኝታ የዓለም ኃያል መንግሥት ሆነች። እግዚአብሔር የሰሜኑን የእስራኤልን መንግሥት ለመቅጣትና ወደ ምርኮ ለመውሰድ አሦርን ተጠቀመ። አሦር ትገኝ የነበረው በአሁኒቱ ኢራቅ ድንበሮች ውስጥ ነው።

ለ. ባቢሎን፡- ባቢሎን የምትገኘው ከመስጴጦምያ በስተደቡብ ራቅ ብላ ነበር። ዋና ከተማዋም ባቢሎን ተብላ ትጠራ ነበር። በ600 ዓ.ዓ. የባቢሎን መንግሥት የዓለም ኃያል መንግሥት በመሆን መስጴጦምያን፥ ጳለስጢናንና የግብፅን መንግሥታት ተቆጣጠረች። እንደምታስታውሰው፥ የደቡብ ይሁዳን መንግሥት ያሸነፈውና ወደ ግዞት የወሰደው የባቢሎን መንግሥት ነበር። ባቢሎንም ትገኝ የነበረው በአሁኑ የኢራቅ መንግሥት ውስጥ ነበር።

ሐ. ሜዶን፡- ሜዶን ከመስጴጦምያ በስተሰሜን ምዕራብ የምትገኝ በመጽሐፍ ቅዱስ ከተጠቀሱና በሩቅ ሰሜን ከሚገኙ አገሮች አንዷ ናት። በመጽሐፍ ቅዱስ ከፋርስ መንግሥት ጋር እንደተዋሐደችና የሜዶንና የፋርስ መንግሥትንም እንደመሠረተች ተጽፏል። ይህ መንግሥት በ539 ዓ.ዓ. ተጀምሮ በ331 ዓ.ዓ. ወድቋል። የሜዶን መንግሥት የሚገኘው በሰሜን ኢራን ነበር።

መ. ፋርስ፡- የፋርስ መንግሥት የሚገኘው ከሜዶን በስተደቡብ ከፋርስ ባሕረ ሰላጤ አጠገብ ነበር። በብሉይ ኪዳን ውስጥ ፋርስ ከሜዶን መንግሥት ጋር በመተባበር፥ አይሁድን ወደ አገራቸው

እንዲመለሱና ቤተ መቅደሳቸውን እንዲሠሩ እንደፈቀደ ተጽፏል። ፋርስም የምትገኘው በአሁኗ ኢራን ውስጥ ነበር።

7. ትንሿ እስያ፡- ጥንታዊት የሆነችው ትንሿ እስያ ብዙ ጊዜ በብሉይ ኪዳን ያልተጠቀሰች ቢሆንም፥ በሐዋርያት ሥራ ውስጥ ግን ሐዋርያው ጳውሎስ በወንጌል አገልግሎት ጉዞው የሄደባት ስለነበረች በተደጋጋሚ ተጠቅሳለች። ነገር ግን በብሉይ ኪዳን ዘመን ትንሿ እስያ የኬጢያውያን ምድር ነበረች። ኬጢያውያን ጳለስጢናን ከ1400 - 1190 ዓ.ዓ. የገዙ ነበሩ። ብዙ ምሁራን እግዚአብሔር ከእስራኤላውያን ጋር በሲና ተራራ ያደረገው ቃል ኪዳን የኬጢያውያን ነገሥታት በቁጥጥራቸው ሥር ካዋሏቸው ሕዝቦች ጋር ካደረጉት ቃል ኪዳን ጋር ተመሳሳይ እንደነበር ይገምታሉ። ትንሿ እስያ በአሁኑ ጊዜ ቱርክ በመባል ትታወቃለች።

## የከነዓን መልክዓ ምድር

> 34ኛ ጥያቄ፥ ሀ) በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙ የተለያዩ ዓይነት የመሬት አቀማመጦችን ዘርዝር። ለ) ብዙ ሕዝቦች የሚኖሩት በየትኛው ዓይነት ምድር ላይ ነው?

የከነዓን ምድር በአካባቢው ከሚገኙት «ለም አገሮች» ውስጥ አንዱ ነው። ይህ የአዲስ ጨረቃ ቅርፅ ያለው ለም ምድር ከጤግሮስና ኤፍራጥስ ወንዞች አጠገብ ካለው ከመስጴጦምያ ጀምሮ ወደ ሜዲትራኒያን ባሕር በመዝለቅ፥ ከግብፅ ወንዝ ዳርቻ በስተደቡብና ከዓባይ ወንዝ በስተደቡብ ወዳለው አካባቢ ይደርሳል። በእነዚህ ለም አገሮች ብዙ ዝናብና ወንዞች ስላሉ ሰዎች በቂ እህል ያበቅሉ ነበር። አብዛኛው የጥንት ሥልጣኔ የተጀመረው በዚህ ክልል ነው። በዚህም ለም ክልል ነው የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ የተፈጸመው።

እንደ ኢትዮጵያ ሁሉ የከነዓንም ምድር ብዙ የተለያየ ዓይነት የመሬት አቀማመጥ ነበረው። በሰሜን የሔርሞን ተራራ ነበር። ይህ ተራራ 2800 ሜትር ከፍታ ያለው ረጅም ተራራ ነበር። ተራራው ብዙ ጊዜ በበረዶ የተሸፈነ ነበር። በደቡብ በኩል በዓለም ዝቅተኛ ስፍራ የሆነው ሙት ባሕር ይገኛል። እርሱም ከባሕር ጠለል በታች 400 ሜትር ነበር። ሙት ባሕር የተባለው፥ በውኃው ውስጥ ምንም ነገር በሕይወት እንዳይኖር የሚያደርጉ በርካታ ንጥረ ነገሮች ስላሉበት ነው።

በብሉይ ኪዳን ታላቁ ባሕር በመባል ይታወቅ በነበረው በሜዲትራኒያን ባሕር ዳርቻ አጠገብ ያለው የከነዓን ምድር ሜዳማና ለም ነበር። አንድ ሰው ከባሕሩ በስተምሥራቅ ሲጓዝ የምድሪቱ ከፍታ እየጨመረ ይመጣና የከነዓን መካከለኛ ምድር ተራራና ኮረብታ የሚበዛበት ክልል ሆኖ እናገኘዋለን። በጥንት ዘመን የባሕር ዳርቻዎች በአሕዛብ መንግሥታት ተይዘው ስለነበር ከእስራኤላውያን አብዛኛዎቹ የሚኖሩት በእነዚህ ተራሮች ላይ ነበር። ይህ መሬት በባሕር ዳር እንደሚገኘው ለም አልነበረም። ከከነዓን በስተምሥራቅ ሁለት ትላልቅ የውኃ ክፍሎች ነበሩ። በአዲስ ኪዳን ገሊላ በተባለው አካባቢ ማለት በስተሰሜን የገሊላ ባሕር ነበር። ይህ ንጹሕ የሆነ የሐይቅ ውኃ ብዙ የተለያዩ ስሞች ነበሩት። ብዙ ጊዜ በብሉይ ኪዳን የኪኔሬት ባሕር በመባል ይታወቅ ነበር (ዘኁ. 34፡11)። በተጨማሪ «የጌንሳሬጥ ባሕር» (ሉቃስ 5፡1) እና «የጥብርያዶስ ባሕርም» ይባል ነበር (ዮሐ. 6፡1)።

የገሊላ ባሕር ከእርሱ ተነሥቶ ወደ ታች ወደ ሙት ባሕር የሚፈሰው የዮርዳኖስ ወንዝ ምንጭ ነበር። ምድሪቱ በመካከለኛው ከነዓን ካሉት ተራራማ ስፍራዎች ወደ ታች በማሽቆልቆል ከባሕር ጠለል በታች ወደ ሆነው ወደ ዮርዳኖስ ወንዝ ትወርዳለች። ምድሪቱ ከዮርዳኖስ ወንዝ በስተምሥራቅ ወደ አንድ ሰፊ ሜዳ ፈጥና ትዘረጋለች። በዚህ ደልዳላ ሜዳ ነበር የጋድ፥ የሮቤልና የምናሴ ነገድ እኩሌታዎች የሰፈሩት። በዚህ ደልዳላ ሜዳ በምዕራባዊና ደቡባዊ ክፍል ዘላን ነገዶች ብቻ የሚኖሩበት ድንጋያማ በረሃ ነበር።

የአንድን ሕዝብ መልክዓ ምድራዊ አቀማመጥ መረዳት ያንን ሕዝብ ለማወቅ በጣም ይረዳል። ለምሳሌ፡- አንድ ሰው የኦጋዴንን ወይም የሰሜን ኢትዮጵያን መልክዓ ምድር ሳያውቅ ለዘመናት በኢትዮጵያ ላይ የተካሄዱትን የተለያዩ ጦርነቶች ወይም የአውሮጳውያንን ለቅኝ ግዛት መቋመጥ እንዴት እንደተጀመረ መረዳት ያስቸግረዋል። በተመሳሳይ መንገድ የከነዓንን ምድር አቀማመጥ ማወቅ መጽሐፍ ቅዱስን የበለጠ ለመረዳት ይጠቅማል። ለምሳሌ መጽሐፍ ቅዱስ ሁልጊዜ ለምን ወደ ኢየሩሳሌም ስለ «መውጣት» ይናገራል? ምክንያቱም ኢየሩሳሌም ያለችው በአቅራቢያዋ ከሚገኙ ሌሎች ስፍራዎች ሁሉ ከፍ ብላ ስለሆነና ሰዎች ወደ ኢየሩሳሌም ለመድረስ ሁልጊዜ ወደ ላይ መውጣት ስላለባቸው ነው።

የከነዓንን መልክዓ ምድር መረዳት ስለ እስራኤል የሚከተሉትን ነገሮች ለመረዳት ይጠቅመናል:-

1. እስራኤል በማያቋርጥ ጦርነት ውስጥ የነበረችበትን ምክንያት ለመረዳት ይጠቅመናል። ከነዓን የሦስቱ አህጉራት ማለት (የአውሮጳ፥ የእስያና የአፍሪካ) የንግድ ማዕከል ነበረች። ይህንን የንግድ ማዕከልነት የሚቆጣጠር ሁሉ ኃያልና ሀብታም ይሆን ነበር።

2. በነጋዴዎችና በገበሬዎች መካከል ትግል የተፈጠረው ለምን እንደነበር ያስረዳናል። ከነዓን የንግድ መናኸሪያ በመሆንዋ ምክንያት አንዳንድ እስራኤላውያን ከግብርና ይልቅ ንግድን ለመተዳደሪያነት መረጡ። በዚህም ምክንያት ሀብታም ለመሆን ችለው ነበር። ሀብታቸውን ግን ብዙ ጊዜ ድሀ የሆኑ ገበሬዎችን ለመጨቆን ይጠቀሙበት ነበር። በነቢያት መጻሕፍት ውስጥ ከተወገዙ ሥራዎች አንዱ ድሆችን መጨቆን ነው።

3. የከነዓን ምድር በጣም ትንሽ ነበር። ብዙ ጊዜ ርዝመቱ ከ240 ኪሎ ሜትር ስፋቱ ደግሞ ከ160 ኪሎ ሜትር የማይበልጥ ነበር። ይህች ትንሽ ምድር የአይሁድን ሃይማኖት ላለመቀበል ጸንተው በተቃወሙ የአሕዛብ መንግሥታት ተከብባ ነበር። አይሁድ ከአሕዛብ ጋር በቅርብ ተወዳጅተው መኖራቸው ከእነርሱ ጋር በጋብቻ የመጣመራቸው አንዱ ችግር ሆኖ ቆይቷል። እንዲሁም አሕዛብ የአይሁድን ሃይማኖት ብዙ ጊዜ ለምን እንዳበላሹት ያስረዳናል።

| |
|---|
| 35ኛ ጥያቄ፥ ዛሬ በቤተ ክርስቲያናችን እነዚህ ተመሳሳይ ችግሮች እንዴት ይታያሉ? |

በብሉይ ኪዳን የአይሁድ በእስራኤል ምድር የመኖር አሳብ ጥልቅ የሆነ የሥነ- መለኮት ትምህርት ነበረው። እግዚአብሔር ከአብርሃም ጋር ቃል ኪዳንን ባደረገ ጊዜ፥ የቃል ኪዳኑ አንድ ክፍል ምድራዊ የሆነው ከነዓን ነበር። እግዚአብሔር ለእስራኤል የሰጠው ተስፋ ነበር። ከዘፍጥረት ጀምሮ እስከ መሳፍንት ድረስ ያለው ታሪክ በአብዛኛው የሚናገረው እግዚአብሔር የተስፋ ቃሉን ለመጠበቅ የከነዓንን ምድር እንዴት ለአይሁድ እንደሰጠ ነው። እግዚአብሔር ከእስራኤል ጋር በገባው ቃል ኪዳን መሠረት የእርሱን ሕግ የመታዘዝ ሽልማት በምድሪቱ ያለማቋረጥ መኖር እንደሚሆን ተናግሮ ነበር። ሰላምና ብልጽግና ይኖራቸዋል፤ ነገር

ግን በቃል ኪዳኑ መሠረት የእርሱን ሕግ ያለመጠበቅ ከምድሪቱ የመውጣትን ችግር እንደሚያመጣም ሳያስጠነቅቃቸው አላለፈም። የቀረው አብዛኛው የብሉይ ኪዳን ታሪክ የሚያሳየው እስራኤላውያን ባለማቋረጥ ለእግዚአብሔር ባለመታዘዛቸው ከአሕዛብ ጋር ጦርነት ወደማድረግና ከዚያም ተሸንፈው በአሕዛብ መንግሥታት ወደ ምርኮ የመወሰዳቸው ታሪክ ነው። በነቢያት መጻሕፍት እግዚአብሔር ወደ ምድሪቱ እንደገና እንደሚመልሳቸውና በሰላም እንደሚኖሩ ለአይሁድ ቃል ገብቶላቸው ነበር። በእርግጥ አይሁድ ከተበተኑበት የዓለም ክፍል እንደሚመለሱና በከነዓን እንደሚኖሩ ቃል ተገብቶላቸዋል። በዚያን ጊዜ መሢሐቸው ኢየሱስ ክርስቶስ በኢየሩሳሌም በእነርሱ ላይ ይነግሣል። አይሁድ ለእስራኤል ምድር ያላቸውን ጥልቅ ፍቅር ለመረዳት በጣም አዳጋች ቢሆንም፥ የብሉይ ኪዳን ቃል ኪዳኖችን በሙሉ ከተመለከትንና ከምድራዊቷ የእስራኤል ምድር ጋር ያለውን ግንኙነት ከተገነዘብን፥ መጽሐፍ ቅዱስን ለመረዳት ብቻ ሳይሆን የእስራኤል ሕዝብ የጥንት ግዛታቸውን በሙሉ ለመቆጣጠር ያላቸውን ጥብቅ ፍላጎትም እንረዳለን። ዛሬ የእስራኤል ሕዝብ በምድር መኖሩ እግዚአብሔር የሰጠውን ተስፋ እያከበረ መሆኑን የሚያሳይ ምልክት ነው።

---

36ኛ ጥያቄ፥ ብሉይ ኪዳንን ማወቅ በዚህ ዘመን በአይሁድና በዐረብ መካከል ስላለው ትግል ለመገንዘብ የሚረዳን እንዴት ነው?

---

ይህ የእስራኤል ጥንታዊ ታሪክ ከለሳና የመልክዓ ምድር መለስተኛ ጥናት ብሉይ ኪዳን የተጻፈበትን ጊዜ ለመረዳት እጅግ የሚጠቅም ነው። የጥንት ሰዎች የኖሩበትን ዘመንና ቦታ ስናውቅ እግዚአብሔር ራሱንና ፈቃዱን ለእነርሱ ሲገልጥ ምን ማለቱ እንደ ነበር የበለጠ እንረዳለን። ይህ ለቃሉ የምንሰጠውን ትርጉም የበለጠ ትክክል ያደርገውና በምናስተምርበትና በምንሰብክበት ጊዜ «እግዚአብሔር እንዲህ ይላል» በማለት እንደ ጥንት ሰዎች መናገር እንድንችል ያደርገናል።

አምስተኛ ቀን፡-

የዚህን ሳምንት ትምህርት ከልስና ስለ ሳምንታዊው ስብሰባ ዝግጅት እንዲሆን የውይይት ጥያቄዎችን ተመልከት።

ሳምንታዊ የስብሰባ ጊዜ

1. ሳምንታዊው የአምልኮ ጊዜ

2. ሳምንታዊው የጸሎት ጊዜ

3. ትምህርቱን መከለስ

4. የውይይት ጊዜ

ሀ. 1) የጥንት ክርቲያኖች የመጽሐፍ ቅዱስን የመጀመሪያውን ክፍል ብሉይ ኪዳን፥ ሁለተኛውን ክፍል አዲስ ኪዳን ብለው የጠሩት ለምንድነው? 2) «ቃል ኪዳን» የሚለው ቃል ዛሬ እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ስላለው ግንኙነት የሚናገረው በምን መንገድ ነው? 3) መጽሐፍ ቅዱስ «ቃል ኪዳን» የሚለውን ቃል የተጠቀመበት መንገድና በአማርኛ አገልግሎት ላይ የዋለበት መንገድ ልዩነት አለውን? ካለውስ ልዩነቱ ምንድን ነው?

ለ. 1) በእኛ መጽሐፍ ቅዱስ ባሉት የብሉይ ኪዳን መጻሕፍትና በካቶሊክና በኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን መጽሐፍ ቅዱሶች መካከል ያለውን ልዩነት አነፃፅር። 2) በእኛ ብሉይ ኪዳን ያሉት መጻሕፍት በአይሁድ የተመረጡት እንዴት ነው? 3) በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉት መጻሕፍት ብቻ የእግዚአብሔር ቃል እንደሆኑ እርግጠኞች መሆናችን በጣም አስፈላጊ የሆነው ለምንድን ነው? 4) በተጻፈው ቃሉና ዛሬ እግዚአብሔር ለስብከት በሚጠቀምባቸው ሰዎች ሥልጣን መካከል ያለው ተመሳሳይነትና ልዩነት ምንድን ነው?

ሐ. 1) የጥናት መምሪያውን ወይም መጽሐፍ ቅዱስን ሳትመለከት 39ኙን የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት በቅደም ተከተል ዘርዝር። 2) የታሪክ መጻሕፍትን በሙሉ ዘርዝር። 3) የተቀሩት የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት በሙሉ ከታሪክ መጻሕፍት ጋር በጊዜ ቅደም ተከተል የሚያያዙበትን ሁኔታ ዘርዝር።

መ. 1) በጥንት ዘመን የከነዓን ምድር በጣም አስፈላጊ የሆነችው ለምንድነው? 2) በብሉይ ኪዳን አይሁድን የጨቆኑ የአሕዛብ አገሮች ስም ዘርዝር። 3) ዓለማዊ ታሪክን መረዳት መጽሐፍ ቅዱስን የበለጠ ለመረዳት እንዴት ይጠቅመናል? 4) ባለፈው ሳምንት መጽሐፈ ሩትን ስታጠና የመጽሐፍ ቅዱስን መልክዓ ምድርን ማጥናት ታሪኩን የበለጠ ለመረዳት እንዴት ጠቀመህ?

ሠ. 1) እግዚአብሔር አሕዛብን ስለ መቆጣጠሩና ስለ ኃያልነቱ በብሉይ ኪዳን ውስጥ በታሪክ ከሠራው ሥራ ምን እንማራለን? 2) ይህ ዛሬ እንዴት ያበረታታናል? 3) በተመሳሳይ መንገድ እግዚአብሔር በሕይወትህና በቤተ ክርስቲያንህ እንዴት ሲሠራ አየህ?

5. ጸሎት

# ትምህርት ሦስት

## 1ኛ ቀን:- የፔንታቱክ መግቢያ

በመጀመሪያዎቹ ሁለት ትምህርቶች፥ ስለብሉይ ኪዳን አንዳንድ የመግቢያ አሳቦች አጥንተናል፤ የእግዚአብሔር ቃል እንደሆነም ተመልክተናል። ከብዙ ዓመታት በፊት 39 የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት የእግዚአብሔር ቃል ይሆኑ ዘንድ በአይሁዶች እንዴት እንደተለዩ ተምረናል። በዚህ ሳምንት ፔንታቱክ ወይም የሙሴ ሕግ ተብለው የሚጠሩትን የመጀመሪያዎቹ አምስት የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት መመልከት እንጀምራለን።

ብሉይ ኪዳን የተጻፈው በሁለት ቋንቋዎች ነበር። አብዛኛዎቹ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት የተጻፉት በዘመኑ የአይሁድ ቋንቋ በነበረው በዕብራይስጥ ነበር፤ ነገር ግን የባቢሎንና በመካከለኛው ምሥራቅ ይኖሩ የነበሩ ሰዎች ዋና የንግድ ቋንቋ በነበረው በአራማይክ የተጻፉ አንዳንድ የብሉይ ኪዳን ክፍሎችም አሉ። ለምሳሌ:- ዳን. 2-7ና የዕዝራ አንዳንድ ክፍሎች የተጻፉት በአራማይክ ቋንቋ ነው። ይህ የሆነው በዚህ ጊዜ ብዙ አይሁድ በመካከለኛው ምሥራቅ ተበትነው በአሕዛብ መካከል በምርኮ ላይ ስለ ነበሩ ነው።

| |
|---|
| 1ኛ ጥያቄ፥ የሚከተሉትን ጥቅሶች ተመልከት፥ ዘዳ. 28፡61፤ ኢያ. 8፡31፤ (ሉቃ. 2፡22)፤ 2ኛ ዜና 31፡3፤ (ሉቃ. 2፡23)፤ ነህ. 8፡3። የመጀመሪያዎቹ አምስት የመጽሐፍ ቅዱስ መጻሕፍት ብዙ ጊዜ በአይሁድ ምን ተብለው ይጠሩ ነበር? |

የመጀመሪያዎቹ አምስት የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት አንዳንድ ጊዜ «ፔንታቱክ» እየተባሉ ይጠሩ ነበር። ፔንታቱክ የሚለው የግሪክ ቃል ትርጉም «አምስት ጥቅል መጻሕፍት» ማለት ነው። ይህም የሚያመለክተው በሙሴ የተጻፉትና በአይሁድ ዘንድ እንደ አንድ ክፍል የሚቆጠሩትን የመጀመሪያዎቹን አምስት የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ነው። ይህን ስም ብዙ ጊዜ የሚገለገሉበት በክርስቶስ ጊዜ የግሪክ ቋንቋ ይናገሩ የነበሩ አይሁድ ነበሩ። የዕብራይስጥ ቋንቋ ይናገሩ የነበሩ አይሁድ ግን ለእነዚሁ መጻሕፍት ሌሎች ስሞች ነበሯቸው። ብዙ ጊዜ «ሕግ» ወይም «ቶራህ» ብለው ይጠሯቸው ነበር። ቶራህ ለሕግ የተሰጠ የዕብራይስጥ ስም ነው።

በመጽሐፍ ቅዱስ በአጠቃላይ የመጀመሪያዎቹ አምስት የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት የተለያዩ ስሞች ተሰጥተዋቸዋል። አንዳንድ ጊዜ «የሕግ መጻሕፍት»፥ «ሕግ»፥ «የሙሴ የሕግ መጻሕፍት»፥ «የሙሴ ሕግ»፥ «በሙሴ መጽሐፍ ውስጥ ያለ ሕግ»፥ «የጌታ ሕግ»፥ «የጌታ ሕግ መጽሐፍ» እና «የሕግ መጽሐፍ» ተብለው ተጠርተዋል።

አይሁድ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍትን በሙሉ የሚያከብሩና በእግዚአብሔር መንፈስ ምሪት መጻፋቸውን የሚያምኑ ቢሆኑም ፔንታቱክ ወይም የሙሴ ሕግ መጻሕፍትን ከሁሉ አብልጠው ያከብሯቸዋል።

## የፔንታቱክ መጻሕፍት ጸሐፊ

የብሉይ ኪዳን የመጀመሪያ መጻሕፍትን ማን ጻፋቸው? እስካለፈው 100 ዓመታት ድረስ አይሁድም ሆኑ ክርስቲያኖች ሙሴ እንደጻፋቸው ያምኑ ነበር፤ ምክንያታቸውም የተመሠረተው በመጽሐፍ ቅዱስና በሽማግሌዎች ወግ ላይ ነው። ቀደም ሲል እንዳየነው፥ ከመጀመሪያዎቹ አምስት የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ስሞች አንዱ «የሙሴ ሕግ» የሚለው ነው።

---

2ኛ ጥያቄ፥ ዘጸ. 24፡3-4 እና ዮሐ. 5፡46-47 አንብብ። በእነዚህ ቁጥሮች መሠረት የመጀመሪያዎቹን አምስት የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት የጻፈው ማን ነው?

---

ከዘፍጥረት እስከ ዘዳግም ያሉትን መጻሕፍት የጻፈው ሙሴ ነው ብሎ መጽሐፍ ቅዱስ በቀጥታ ባይነግረንም እንኳ በፔንታቱክ ውስጥ የተካተቱ አንዳንድ ነገሮችን እርሱ እንደጻፋቸው ግልጽ ነው። በሲና ተራራ የተቀበላቸውን ሕግጋት እርሱ እንደጻፋቸው እናውቃለን። ከሙሴ ሞት በኋላ ኢያሱ ወዲያውኑ ተተክቶ ሕዝቡን መምራት ሲጀምር እንዲታዘዘው የተሰጠው፥ በሙሴ የተጻፈ መጽሐፍ ነበር፤ (ኢያሱ 1፡7-8 ተመልከት)። ከአዲስ ኪዳን ዘመን ቀደም ብሎ የመጀመሪያዎቹን አምስት የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት የጻፈው ሙሴ እንደሆነ አይሁድ አምነው ነበር። በአዲስ ኪዳን ውስጥም ቢሆን የፔንታቱክ መጻሕፍት አብዛኛዎቹን ሙሴ እንደጻፈ ተጠቅሶአል። ዘጸአት (ማር. 7፡10)፥ ዘሌዋውያን (ሮሜ 10፡5)፤ ዘዳግም (ማቴ. 19፡7-8) የተጻፉት በሙሴ እንደሆነ ኢየሱስና ሌሎች በግልጥ ተናግረዋል። የሕግ መጻሕፍት አመዳደብ እንደ ሙሴ መጻሕፍት

ሲሆን ይህም ሙሴ በጸሐፊነት የሚታይ መሆኑን ያመለክታል (ሉቃስ 24፡44 ተመልከት)።

በ1900 ዓ.ም. አካባቢ ግን ፔንታቱክን የጻፈው በእርግጥ ሙሴ ለመሆኑ ምሁራን ይጠራጠሩት ጀመር። የፔንታቱክን መጻሕፍት በሚመረምሩበት ጊዜ ከአንድ በላይ የሆኑ ጸሐፊዎች እንደጻፉት የሚያሳዩ በርካታ ነገሮችን አገኙ። ለምሳሌ፡- በአራት ዘፍጥረት ሁለት የተለያዩ የፍጥረት ትረካዎች አሉ (ዘፍ. 1 ና 2)፤ ሙሴ ከኖረበት ዘመን ከ500 ዓመታት በኋላ ይኖሩ የነበሩ የእስራኤል ነገሥታት ተጠቅሰዋል (ዘፍጥ. 36፡31)፤ እስከ ዘመነ መሳፍንት ድረስ ወደ ከነዓን ያልመጡ ፍልስጥኤማውያን ተጠቅሰው እናያለን (ዘፍጥ. 21፡34)፤ ደግሞም «እስከ ዛሬ ድረስ» የሚለው ቃል መጽሐፉ የተጻፈው ከሙሴ በኋላ መሆኑን የሚጠቁም ሐረግ ይመስላል (ዘፍጥ. 32፡32)። በተጨማሪም እነዚህ ምሁራን በአጻጻፍ ስልትና በቃላት አጠቃቀም ረገድ ያለው ልዩነት ራሱ የተለያዩ ጸሐፊዎች እንደጻፉት ያሳያል ይላሉ።

በዚህ ምክንያት የፔንታቱክ ጸሐፊ ማን ነው? የሚለውን ጥያቄ በሚመለከት አለመግባባት አለ። እነዚህ አምስት የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ስለተገኙበት መንገድ አምስት ዋና አመለካከቶች ወይም አሳቦች አሉ።

1. የፔንታቱክን መጻሕፍት ሁሉ የጻፈው ሙሴ ነው። ሙሴ ያልጻፈው የፔንታቱክ ክፍል ከእርሱ ሞት በኋላ የተጻፈው ዘዳግም 34 ብቻ ነው። ይህንን አቋም የያዙ ሰዎች እንደሚሉት ሙሴ ሌሎች መጻሕፍት ተጠቅሞ ሊሆን ይችላል፤ ነገር ግን እነዚህን አምስት መጻሕፍት ያዘጋጀና የጻፈ እርሱ ነው ይላሉ። አቋማቸውን ለመደገፍም የሚከተለውን መረጃ ይጠቁማሉ፡-

   ሀ. ዘኍል. 33፡2 እና በፔንታቱክ ውስጥ ያሉ ሌሎች ጥቅሶች መጻሕፍቱን የጻፈው ሙሴ ነው ይላሉ።

   ለ. በብሉይና በአዲስ ኪዳን የሚገኙ ሌሎች መጻሕፍት ሙሴ የፔንታቱክ ጸሐፊ እንደሆነ ይናገራሉ፤ (ዘኍል. 24፡3-4ና ዮሐ. 5፡46-47)።

   ሐ. በአይሁድም ሆነ በክርስትና አፈ ታሪክ መሠረት ጸሐፊው ሙሴ እንደሆነ ይነገራል።

መ. መጽሐፉን በጥልቀት በማጥናት የምንረዳው ነገር ጸሐፊው የድርጊቱ የዓይን ምስክር እንዲሁም የግብፅን ቋንቋና ባሕል የሚያውቅ ሰው መሆኑን ነው። እነዚህን መመዘኛዎች ሊያሟላ የሚችል ከሙሴ የተሻለ ሰው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ጨርሶ አልተጠቀሰም።

2. ሙሴ የፔንታቱክ ዋነኛው ጸሐፊ ነው። አሪት ዘፍጥረትን በሚመለከት የተጻፉት ጽሑፎች በሙሉ ለይቶ፥ አቀናብሮና አስተካክሎ ያዘጋጀ እርሱ ነው። ከቀሩት አራት መጻሕፍትም አብዛኛውን የጻፈው እርሱ ነው፤ ነገር ግን ሙሴ ከሞተ ከረጅም ጊዜ በኋላ አንድ ያልታወቀ ሰው አንዳንድ ጥቃቅን ነገሮችን አክሎባቸዋል። አምስቱ መጻሕፍት ሙሉ በሙሉ የተጠናቀቁት በመጽሐፈ ኢያሱ መጨረሻ አካባቢ ወይም ምናልባት በነቢዩ ሳሙኤል ጊዜ ነው።

3. የመጀመሪያዎቹ አምስቱ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት የተጻፉት በተለያዩ ሰዎች ሲሆን የተጻፉትም በብዙ መቶ ዓመታት ጊዜ ውስጥ ነው። ይህ አሳብ የተጀመረው በ1876 ሲሆን «በመረጃ የተደገፈ መላምት» ወይም «ጄ.ኢ.ዲ.ፒ. ቲዎሪ» በመባል ይታወቃል። ይህንን አመለካከት የሚደግፉ አብዛኛዎቹ ምሁራን ፔንታቱክም ሆነ የተቀረው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ስሕተት የሌለበት እውነተኛ የእግዚአብሔር ቃል መሆኑን አያምኑም። የአይሁድን ሃይማኖታዊ ልምምድ ለማሳየት የጥንት ሰዎች የጻፉት አድርገው ማመኑ ይቀላቸዋል። መጽሐፍ ቅዱስ በዓለም ዙሪያ እንደሚገኙ እንደ ሌሎች ሃይማኖታዊ መጻሕፍት ነው ይላሉ። እነዚህ ምሁራን በተአምራት፥ በነቢያትም ሆነ በመሳሰለው ለማመን ፈቃደኞች አይደሉም። ትንቢትና ተአምራትን ላለመቀበል አስቀድመው አእምሮአቸውን ያዘጋጁ ናቸው። ይህን መጽሐፍ ቅዱስን በመረዳትና በመተርጎም በኩል ተጽዕኖ ያደርግባቸዋል። ይህ አመለካከት በተለይ ላለፉት 50 ዓመታት ተከታዮች ያተረፈ ቢሆንም፤ በአሁኑ ጊዜ ግን እያሽቆለቆለ በመምጣት ላይ ይገኛል። ይህ አመለካከት ቀደም ብለን ባነሣነው ጉዳይ ላይ በማተኮር፥ ለፔንታቱክ መጻሕፍት አንድ ጸሐፊ ብቻ ሊኖር እንደማይችል ይናገራል። በመሠረቱ ይህ አመለካከት ፔንታቱክ ቢያንስ የአራት ዋና ዋና መጻሕፍት ጥርቅም ሆኖ በአራት መቶ ዓመታት የጊዜ ገደብ ውስጥ እንደተጻፈ የሚያስተምር ነው።

ሀ. የመጀመሪያው መጽሐፍ የሚጠራው በዕብራይስጥ ቋንቋ የእግዚአብሔር ስም በሚጀመርበት «ጀ» በሚለው ፊደል ነው። ስሙም «ጀሆቫ» (ያህዌ) ነው። ይህ ጽሑፍ በ9ኛው መቶ ክፍለ ዘመን (ዓ.ዓ.) የያህዌ እግዚአብሔርን ታላቅነት ለማግነን በፈለጉ አይሁድ እንደተጻፈ ይናገራል።

ለ. ሁለተኛው ጽሑፍ የሚጠራው አይሁድ ለእግዚአብሔር ከሰጡት «ኤሎሂም» ከሚለው ስም በተገኘው «ኢ» በሚለው ፊደል ነው። የዚህ ጽሑፍ ጸሐፊ ከእስራኤል የሰሜኑ ክፍል የመጣ ሲሆን የጻፈውም በ8ኛው መቶ ክፍለ ዘመን (ዓ.ዓ.) እንደሆነ የዚህ አመለካከት አራማጆች ይናገራሉ። ይህ ጸሐፊ «ኤሎሂም» በሚለው የእግዚአብሔር ስም ላይ አተኩሯል።

እነዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁራን ሁለቱ ጽሑፎች ከተጻፉና ሰማርያ በ722 ዓ.ዓ. በአሦራውያን እጅ ከወደቀች በኋላ ከይሁዳ ሳይሆን አይቀርም ተብሎ የሚታሰብ ሰው ወደ አንድ መጽሐፍ አጣምሮአቸዋል የሚል አሳብ ይሰነዝራሉ።

ሐ. ሦስተኛው ጽሑፍ ከመጨረሻው የፔንታቱክ መጽሐፍ በእንግሊዝኛ ዲዮተሮኖሚ ከሚለው ስም የመጀመሪያ ፊደል በመውሰድ «ዲ» ብለው ሰይመውታል። ይህ ሰው አሪት ዘዳግምን ከጻፈ በኋላ ከመጽሐፈ ኢያሱ እስከ 2ኛ ነገሥት ላሉት መጻሕፍት ደግሞ የመጨረሻ ማስተካከያ አድርጓል። ይህ የሆነው ከ630-600 ዓ.ዓ. በንጉሥ ኢዮስያስ ዘመን ሳይሆን አይቀርም ይላሉ።

መ. አራተኛው ጽሑፍ የተጻፈው በአንድ ካህን (ቄስ) ነው ብለው ስለሚያምኑ በእንግሊዝኛ ካህን (ፕሪስት) ከሚለው ስም የመጀመሪያውን ፊደል በመውሰድ «ፒ» ብለው ሰይመውታል። ይህ መጽሐፍ በአምልኮ ሕግጋትና በፔንታቱክ ውስጥ በሚገኘው የትውልድ የዘር ሐረግ ላይ የሚያተኩር ነው። የተጻፈውም ከ500-450 ዓ.ዓ. ነው።

በመጨረሻ፥ በ450 ዓ.ዓ. ገደማ ካህን የነበረ አንድ የመጻሕፍት አዘጋጅ አራቱንም መጻሕፍት በመውሰድ አሁን ዘፍጥረት፥ ዘጸአት፥ ዘሌዋውያን፥ ዘኁልቁና ዘዳግም ወደምንላቸው መጻሕፍት አቀናጃቸው።

የዚህ ፅንሰ አሳብ አራማጆች ይህን ያደረገው ካህን ዕዝራ ሳይሆን አይቀርም ይላሉ። ይህም ማለት የፔንታቱክ የመጨረሻ ሥራ አሁን በእጃችን ባለው መልኩ የተጻፈው በ450 ዓ.ዓ. ነው ማለት ነው።

ብዙዎቹ የጥንት የመጽሐፍ ቅዱስ ማብራሪያዎች ፔንታቱክን በሚተረጉሙበት ጊዜ ይህንን ንድፈ አሳብ ተከትለዋል። እግዚአብሔር ቃሉን እንዲጽፉ ሰዎችን በመንፈስ ቅዱስ ነድቶአቸዋል፤ ደግሞም መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል በመሆኑ ፍጹም የተለየ መጽሐፍ ነው ብለን ካመንን፥ ይህ አመለካከት ጨርሶ ተቀባይነት ሊኖረው እንደማይችል መገንዘብ አስፈላጊ ነው።

4. አራተኛው አመለካከት፥ በፔንታቱክ ውስጥ የሚገኙ በርካታ ታሪኮች ከትውልድ ወደ ትውልድ በአፈ ታሪክ (ሥነ- ቃል) ተላልፈዋል የሚል ነው። ከዚያም እነዚህ በአፈ ታሪክ (ሥነ-ቃል) የተላለፉ መልእክቶች በተለያዩ ጸሐፊዎች አማካይነት ተጻፉ። በመጨረሻ እነዚህ መጻሕፍት በአንድ አቀናባሪ ተሰብስበው ተቀናጁ። በ586 ዓ.ዓ. ይሁዳ ከተማረከች በኋላ መጽሐፉ አሁን ባለበት መልኩ ተስተካከለ።

5. አንድ የመጨረሻ አመለካከት የሚለው:- በባቢሎን ምርኮ ጊዜና አይሁድ ወደ ይሁዳ ከተመለሱ በኋላ (586-500 ዓ.ዓ.) የተለያዩ አዘጋጆች የዕብራውያንን ታሪኮች በሙሉ ሰብስበውና አስተካክለው አሁን በመጽሐፍ ቅዱሳችን በሚገኙ አምስት የተለያዩ መጻሕፍት መልክ አቀናበሩአቸው የሚል ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ የመጀመሪያዎቹን አምስት የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ጨምሮ የእግዚአብሔር ቃል እንደሆነና ሥልጣኑም እግዚአብሔር ራሱ የተናገረን ያህል መሆኑን የምናምን ክርስቲያኖች በመሆናችን ከላይ የተመለከትናቸውን አብዛኞዎቹን አመለካከቶች መቃወም አለብን። የጻፉት የተለያዩ ሰዎች ናቸው ለሚለው አባባላቸው መልስ አለን። አብዛኞቹን የፔንታቱክ መጻሕፍት ክፍሎች የጻፈው ሙሴ ነው የሚለውን አሳባችንን የምንለውጥበት አንዳችም ምክንያት የለንም፤ ነገር ግን ከሙሴ በኋላ የነበሩ ጸሐፊዎች ሙሴ ከሞተ ከብዙ ዓመታት በኋላ ለኖሩ ሰዎች ግልጥ ለማድረግ የተወሰኑ ቃላትን ጨምረው ሊሆን ይችላል የሚለውን አሳብ ልንቀበል እንችላለን። ለምሳሌ «በእነዚያ ቀናት» እና «ከነዓን የፍልስጥኤም ምድር ሆነች» የሚሉትን ቃላት ጨምረው ይሆናል (ዘፍጥ.

10፡14፤ 21፡32)፤ ነገር ግን የአዲስ ኪዳን ጸሐፊዎችና ጌታ ኢየሱስ ራሱም እንዳረጋገጡት የፔንታቱክ ጸሐፊ ሙሴ ነው በሚለው አቋማችን እንጸናለን።

3ኛ ጥያቄ፥ ሀ) አንድ ሰው ተአምራት የሚባሉ ነገሮች የሉም ብሎ ካመነ ይህ እምነቱ መጽሐፍ ቅዱስን በሚተረጉምበት መንገድ ላይ እንዴት ተጽዕኖ ሊያደርግ ይችላል? ለ) የእግዚአብሔርን ቃል በምንተረጉምበት ጊዜ በእኛ ላይ የሚያደርሰውን ተጽዕኖ በማሰብ አስቀድሞ በአእምሮአችን ስለምንይዘው አሳብ ልንጠነቀቅ እንደሚገባ ይህ ምን ያስተምረናል? ሐ) ራሳቸውን ክርስቲያን ብለው የሚጠሩ የተለያዩ ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል በሚተረጉሙበት ጊዜ እንደዚህ ዓይነት ተጽዕኖ ያደረጉባቸውን ትምህርቶች ዘርዝር፤ (ለምሳሌ፡- የይሖዋ ምስክሮች፥ ካቶሊኮች፥ የኦርቶዶክስ አማኞች፥ ቃለ ሕይወት፥ መካነ ኢየሱስ፥ ሰባተኛ ቀን አክባሪ አድቬንቲስቶች፥ ወዘተ)።

## 2ኛ ቀን፡- የፔንታቱክ መጻሕፍት ስሞች

4ኛ ጥያቄ፥ ሀ) በፔንታቱክ ውስጥ የሚገኙ የአምስቱን መጻሕፍት ስም ዘርዝር። ለ) በግዕዝ የእያንዳንዳቸው ርዕስ ትርጉም ምንድን ነው? የግዕዝ ትርጉሞቻቸውን ካላወቅህ ግዕዝ የሚያውቅ የኦርቶዶክስ ቄስ እንዲረዳህ ጠይቅ። ሐ) ከዚህ ቀደም በመጽሐፍ ቅዱስ ካለህ እውቀት በመነሣት አምስቱ መጻሕፍት እያንዳንዳቸው ስለምን እንደሚያስተምሩ በራስህ አባባል ጠቅለል ባለ መልኩ ጻፍ።

በፔንታቱክ ውስጥ አምስት መጻሕፍት ይገኛሉ። ሙሴ እነዚህን አምስት መጻሕፍት በሚጽፍበት ጊዜ ለእያንዳንዱ መጽሐፍ ስም ወይም ርዕስ አልሰጠም ነበር። በኋላ አንዱን መጽሐፍ ከሌላው ለመለየት አይሁድ ለእያንዳንዱ ጥቅልል የራሱ የሆነ ስም ሰጡት። የመጻሕፍቱን ርዕስ ብዙ ጊዜ የሚወስዱት በጥቅሉ ውስጥ ከሚገኘው ከመጀመሪያው ዓረፍተ ነገር መጀመሪያ ቃል ላይ ነበር። ለምሳሌ፡- ዘፍጥ. 1፡1፡- «በመጀመሪያ» . . . የሚል ቃል እናገኛለን፤ ስለዚህ አይሁድ የመጀመሪያውን የብሉይ ኪዳን መጽሐፍ «መጀመሪያ» አሉት። ኋላም የግሪክ ቋንቋ የሚያውቁ አይሁድ የዕብራይስጡን መጽሐፍ ቅዱስ ወደ ግሪክ ሲተረጉሙትና ሴፕቱዋጀንት የሚባለውን መጽሐፍ ቅዱስ ሲያዘጋጁ የመጽሐፉን ወይም የጥቅሉን ዋና አሳብ በአጭሩ ሊገልጥ የሚችል የራሳቸው የሆነ ርእስ ሰጡት። የእንግሊዝኛውና የአማርኛው የመጽሐፍ ቅዱስ ርእሶች የተገኙት

በሴፕቱዋጀንት መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከሚገኙት ርእሶች ነው። በአዲሱ የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ ስሞቹን ወደ አማርኛ ከመተርጎም ይልቅ ውስጥ ታዋቂነት ያለውን የግዕዙን ስም እንዲይዝ ተደርጓል።

1. ዘፍጥረት፡- በአማርኛ ዘፍጥረት የሚለው ቃል የመጣው እግዚአብሔር ሰማይን፥ ምድርንና በውስጧ ያሉትን ነገሮች እንዴት እንደፈጠረ ከሚናገረው ከመጽሐፉ የመጀመሪያ ሁለት ምዕራፎች ነው። የዘፍጥረት መጽሐፍ እግዚአብሔር ዓለምን እንዴት እንደፈጠረ ከመናገር እጅግ የሚበልጥ ነገር ስላቀፈ ይህ ስም ከሁሉ የተሻለና ትክክለኛ ስም አይደለም። በግሪክ «ጄነሲስ» የሚባለው የመጽሐፉ ስም «ጅማሬ» የሚል ትርጉም ያለው ነው። ይህ ስም በዘፍጥረት መጽሐፍ ውስጥ ስለሚገኙት ነገሮች የተሻለ መግለጫ ነው። የዘፍጥረት መጽሐፍ ስለ ፍጥረት ሁሉ ጅማሬ ይነግረናል። ስለ ሰው ልጅ ጅማሬ፥ ስለ ኃጢአትና ስለ ሞት ጅማሬ፥ ስለ ሥልጣኔ ጅማሬ፥ በዓለም ስለሚገኙ የተለያዩ ነገዶች ጅማሬና እግዚአብሔር ከእስራኤል ሕዝብ ጋር ስለገባው ቃል ኪዳን ጅማሬ ይገልጻል።

2. ዘጸአት፡- ዘጸአት የሚለው ቃል የአማርኛና የእግሊዝኛ ትርጉም፥ «መልቀቅ» ወይም «መውጣት» ማለት ሲሆን፥ የሚናገረውም እግዚአብሔር የእስራኤልን ሕዝብ ከግብፅ ባርነት እንዴት ነፃ እንዳወጣ ነው፤ ነገር ግን አብዛኛውን የኦሪት ዘጸአት ክፍል እግዚአብሔር በሲና ተራራ ከእስራኤል ሕዝብ ጋር ስለገባው ቃል ኪዳን ይናገራል።

3. ዘሌዋውያን፡- ዘሌዋውያን የሚለው የአማርኛና የእንግሊዝኛ ቃል፥ ሌዋውያን ተብለው ከሚጠሩት ከአንዱ የእስራኤል ነገዶች የተገኘ ነው። ሌዋውያን የካህናት ነገድ ሲሆኑ ስሙም የሚያመለክተው በኦሪት ዘሌዋውያን ከተጻፉ ሕጎች አብዛኛው እነርሱ እግዚአብሔርን እንዴት እንደሚያመልኩና በፊቱም በሥነ ምግባራቸው እንዴት ንጹሐን ሆነው መኖር እንዳለባቸው ለማመልከት፥ በተለይ የተሰጣቸው ስለነበር ነው። ነገር ግን እነርሱ ብቻ ሳይሆኑ የቀሩት እስራኤላውያን በሙሉ ሊከተሉአቸው የሚገባ በርካታ ሕጎችንም በመጽሐፉ ውስጥ እናገኛለን።

4. ዘኁልቁ፡- ዘኁልቁ የሚለው የአማርኛና የእንግሊዝኛ ቃል ትርጉም በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የእስራኤል ሕዝብ እንዴት ሁለት ጊዜ

እንደተቆጠሩ የሚያሳይ ነው። በመጀመሪያ ልክ ግብፅን ለቀው ሲወጡ ብዛታቸውን ለማወቅ ሲባል ተቆጠሩ። ከዚያም ከ40 ዓመታት በኋላ እንደገና ወደ ተስፋይቱ ምድር ለመግባት በተዘጋጁበት ጊዜ ተቆጠሩ። አሪት ዘኁልቁ የእስራኤል ሕዝብ ወደ ተስፋይቱ ምድር መግባትን በመቃወማቸው ለ40 ዓመታት በምድረ በዳ ስለመንከራተታቸው ይናገራል።

5. ዘዳግም፡- ዘዳግም የሚለው የአማርኛና የእንግሊዝኛ ቃል ሕግን ከመድገም ጋር የተያያዘ ነው። በአሪት ዘዳግም የእስራኤል ሕዝብ ወደ ተስፋይቱ ምድር ለመግባት በዝግጅት ላይ ነበሩ። ከ40 ዓመታት በፊት በሲና ተራራ እግዚአብሔር ሕግን ለሕዝቡ ሲሰጥ ያልነበረ አዲስ ትውልድ ነበር፤ ስለዚህ ሙሴ ከመሞቱ በፊት ሕጉን ለዚህ አዲስ ትውልድ በድጋሚ ሲሰጥ እናያለን። የአሪት ዘዳግም አብዛኛው ክፍል እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን በሲና ተራራ የገባውን ቃል ኪዳን እንዲፈጽምላቸው መጠበቅ ስለሚገባቸው ሕጋጋት የሚናገር ነው።

## በፔንታቱክ ውስጥ የሚታይ ታሪክ

| |
|---|
| 5ኛ ጥያቄ፦ ሀ) በፔንታቱክ ውስጥ የተጠቀሰው የመጀመሪያው ታሪካዊ ተግባር ምንድን ነው? (ዘፍጥ. 1፡1)። ለ) በፔንታቱክ ውስጥ የተጠቀሰው የመጨረሻ ታሪካዊ ተግባር ምንድን ነው? |

በፔንታቱክ ውስጥ ስለ ጥንቱ ታሪክ የሚገልጡ ሦስት መጻሕፍት አሉ፤ እነዚህ መጻሕፍት ዘፍጥረት፥ ዘጸአትና ዘኁልቁ ናቸው። በፔንታቱክ የተጠቀሰው የመጀመሪያው የዓለም አፈጣጠር ታሪክ ነው። እግዚአብሔር ዓለምን የፈጠረው መቼ እንደሆነ አናውቅም። ይህን በተመለከተ ምሁራን የተለያየ አስተሳሰብ አላቸው። አንዳንዶቹ ይህ የሆነው በ4000 ዓ.ዓ. ገደማ ነበር ይላሉ። ሌሎች ደግሞ ከ10000 ዓመታት ወይም ከዚያ በፊት ሊሆን ይችላል ይላሉ። ከዘፍጥ. 1-11 ድረስ ያለው ታሪክ መቼ እንደተፈጸመ በትክክል ለማወቅ አይቻልም። በፔንታቱክ ውስጥ ከሚገኙት ታሪኮች መካከል በትክክል ቀኑን ልንገምት የምንችልበት የመጀመሪያ ታሪክ የአብርሃም ሕይወት ታሪክ ነው። አብርሃም የኖረው በ2150 ዓ.ዓ. ገደማ ሲሆን የዘፍጥረት መጽሐፍ ታሪክ ያከተመው በ1800 ዓ.ዓ. አካባቢ ነበር። የቀሩት የፔንታቱክ መጻሕፍት ታሪክ ሙሴ ከተወለደበት ከ1525 ዓ.ዓ. ጀምሮ ሕዝቡ ነፃ

እስከወጡበት እስከ 1440፥ ከዚያም እስከ ሙሴ ሞት ድረስ 1400 ዓ.ዓ. ይቀጥላል።

## ፔንታቱክ የተጻፈበት ጊዜ

የፔንታቱክ አብዛኛው ክፍል የተጻፈው የእስራኤል ሕዝብ በምድረ በዳ በተንከራተቱባቸው ዓመታት ነው። ስለዚህ ሁሉም መጻሕፍት ማለትም ዘፍጥረት፥ ዘጸአት፥ ዘሌዋውያን፥ ዘኍልቁና ዘዳግም የተጻፉት ከ1446-1406 ዓ.ዓ. ነው።

ይሁን እንጂ በፔንታቱክ የተጻፉ ታሪካዊ ድርጊቶች የተፈጸሙባቸውን ጊዜያት ለመወሰን ስንሞክር አንድ ዐቢይ ችግር ይገጥመናል። ይህ ችግር የሚነሣው በዘጸአት ውስጥ በዕብራይስጡና በግሪኩ መጽሐፍ ቅዱስ መካከል ባለ የአንድ ጥቅስ ልዩነት ምክንያት ነው። የዕብራይስጡ መጽሐፍ ቅዱስ በዘጸ. 12፡40 አይሁድ በግብፅ ለ430 ዓመታት እንደነበሩ ይናገራል። የግሪኩ መጽሐፍ ቅዱስ ግን ለ215 ዓመታት ነበሩ ይላል። 430 ዓመታት የሚለው በይበልጥ ትክክል ሳይሆን አይቀርም (1ኛ ነገሥት 6፡1 ተመልከት)። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የቁጥሮችን ወይም የታሪኮችን ትክክለኛነት የማይቀበሉ አንዳንድ ምሁራን ወደኋላ ያደርጉታል። ስለ ፔንታቱክ ታሪክ ቅደም ተከተል ሁለት የተለያዩ አመለካከቶች የሚያሳየውን ከዚህ በታች ያለውን ሠንጠረዥ ተመልከት።

| የ430 ዓመታት ባርነት | የ215 ዓመታት ባርነት | ዘመናት |
|---|---|---|
| የእስራኤል ሕዝብ አባቶች<br>(2166-1805)<br>ወደ ግብፅ መሰደድ<br>(1876) | የእስራኤል ሕዝብ አባቶች<br>(1952-1589) | 2100 ዓ.ዓ.<br>2000 ዓ.ዓ.<br>1900 ዓ.ዓ. |
| በግብፅ የነበሩበት ጊዜ<br>(1876-1446)<br>ባርነት<br>(1730 ወይም 1580) | ወ ደ ግብፅ መሰደድ.<br>(1600) ዓ.ዓ. | 1800 ዓ.ዓ.<br>1700 ዓ.ዓ |
| | በግብፅ የነበሩበት ጊዜ<br>(1660-1446)<br>ባርነት (1580) | 1600 ዓ.ዓ.<br>1500 ዓ.ዓ. |
| በምድረ በዳ መንከራተት<br>(1446-1406) | በምድረ በዳ መንከራተት<br>(1446-1406) | 1400 ዓ.ዓ.<br>1300 ዓ.ዓ. |

| | | |
|---|---|---|
| ድል መንግትና መሳፍንት<br>(1406-1050) | ድል መንግትና መሳፍንት<br>(1406-1050) | 1200 ዓ.ዓ.<br>1100 ዓ.ዓ. |
| የተባበረው የእስራኤል መንግሥት<br>(1050-931) | የተባበረው የእስራኤል መንግሥት<br>(1050-931) | 1000 ዓ.ዓ.<br>900 ዓ.ዓ. |

የፔንታቱክ ታሪክ የተፈጸመው በሦስት የዓለም ክፍሎች ነው። የተጀመረው ከዘፍ. 1-11 ያለው ታሪክ በተፈጸመበትና የዔድን ገነት ባለበት መስጴጦምያ ነው። የእስራኤል ሕዝብ አባት የሆነው አብርሃም የመጣው ከመስጴጦምያ ሲሆን የይስሐቅና የያዕቆብ ሚስቶችም የመጡት ከዚሁ አገር ነበር። ከዚያም ታሪኩ ሦስቱ ዋና ዋና የእስራኤል ሕዝብ አባቶች አብርሃም፥ ይስሐቅና ያዕቆብ በእንግድነት ወደኖሩባት፥ እግዚአብሔር ለእነርሱና ለዘራቸው ሊሰጥ ቃል ወደገባላቸው ወደ ከነዓን ምድር ያመራል። በመጨረሻ ታሪኩ ስለ ጥቂቱ የያዕቆብ ቤተሰብ (70 ሰዎች) እንዴት ወደ ግብፅ እንደሄዱና ቁጥራቸው ወደ 2 ሚሊዮን አድጎ ታላቅ ሕዝብ እንደሆኑ ይነግረናል። ሕዝቡ ግን ባልተጠበቀ ሁኔታ የግብፅን የባዕድ አምልኮት ባሕል ለመዱ፤ የጣዖት አምልኮአቸውንም ተማሩ (ዘጸ. 32፡1-10)። እናም ግብፅን እንደራሳቸው አገር አድርገው መቁጠር ጀመሩ (ዘኁ. 11፡4-6)።

> 6ኛ ጥያቄ፥ በዚህ ዘመን ያለን ክርስቲያኖች በምድር ላይ በእንግድነት እንድንኖር የሚገባን ቢሆንም እንኳ ብዙ ጊዜ የባዕድ አምልኮዎችን ልማድ የምንለማመደው እንዴት ነው? (ዕብ. 11፡13 ና 1ኛ ጴጥ. 1፡1 ተመልከት)።

የፔንታቱክ አብዛኛው ታሪክ የሚያተኩረው የተመረጡት የእግዚአብሔር ሕዝብ ማለት እስራኤላውያን ከዓመታት የባርነት ቆይታ በኋላ ወደ ተስፋይቱ ምድር እንዴት እንደተመለሱ ነው። የፔንታቱክ ታሪክ የሚያበቃው በዘዳግ. 34 ስለ ሙሴ ሞት በተጻፈው ትረካ ነው።

## 3ኛ ቀን በፔንታቱክ ውስጥ የሚገኙ የሥነ ጽሑፍ ዓይነቶች

ፔንታቱክ በአንድ ጸሐፊ (ሙሴ) የተጻፈ የቅዱሳት መጻሕፍት አንድ ክፍል ቢሆንም፥ በውስጡ አራት የተለያዩ የሥነ-ጽሑፍ ዓይነቶች ይገኛሉ። ከፔንታቱክ አንድ የተወሰነ ክፍል ወስደን ለመተርጎም በምናጠናበት ጊዜ በሚገባ እንተረጉመው ዘንድ የሥነ-ጽሑፍ ዓይነት

ወስነን በዚያው መልክ መተርጎም ይገባናል። በፔንታቱክ ውስጥ አራት ዋና ዋና የሥነ-ጽሑፍ ዓይነቶች ይገኛሉ።

1. የታሪክ ጽሑፎች:- በብሉይ ኪዳን ውስጥ በብዛት የምናገኘው የሥነ -ጽሑፍ ዓይነት የታሪክ ጽሑፍ ወይም ትረካ ነው። መጽሐፍ ቅዱሳችንን በአጠቃላይ በሚመለከትም ይህ እውነት ነው። የብሉይ ኪዳንን ሥነ ጽሑፍ ስንመለከት ከመቶ አርባው እጅ (40%) ትረካ ነው። በታሪክ ጽሑፎች ውስጥ የቅዱሳት መጻሕፍት ጸሐፊው ማንኛውም ሰው በሚረዳው በቀላል ቋንቋ ታሪኩን ይተርካል። የሚናገረውም ምን እንደተፈጸመ ነው። ይህም ሆኖ መጽሐፍ ቅዱስን ልዩ የሚያደርገው የሚናገረው ታሪክ ተራ ያለመሆኑ ነው። ታሪኮቹ የተጻፉት በድሮ ጊዜ ምን እንደተፈጸመ ሊነግሩን ብቻ አይደለም።

---

7ኛ ጥያቄ፥ ሮሜ 15:4 እና 1ኛ ቆሮ. 10:11 አንብብ። የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኮች ዛሬ ለእኛ ያላቸው ዓላማ ምንድን ነው?

---

አንዳንድ ምሁራን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክን «የደኅንነት ታሪክ» ብለው ይጠሩታል። ሌሎች ደግሞ «የእግዚአብሔር ታሪክ» ይሉታል። የታሪክ ጽሑፎች ዋና ዓላማ እግዚአብሔር በፍጥረት ውስጥና በሕዝቡ መካከል ሲሠራ ማሳየት ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ዳር እስከ ዳር የምናየው አንድ ዋና ዓላማ እግዚአብሔር በታሪክ ውስጥ በተለያዩ ሰዎች ሕይወትና በልዩ ነገድ ውስጥ ሲሠራ ደኅንነትን እየገለጠ መሆኑን ነው፤ ስለዚህ መጽሐፍ ቅዱስ የሚናገረው ከዚህ በፊት ስለተፈጸሙት እውነተኛ ታሪካዊ ክስተቶች ቢሆንም ጸሐፊው ስለ እነርሱ በሚጽፍበት ጊዜ ሁለት ዓላማዎችን ይዞ ነበር። የመጀመሪያው፥ ባለፈው ጊዜ ምን እንደተፈጸመ በትክክል መናገር ሲሆን፥ ሁለተኛው ደግሞ፥ የእግዚአብሔር ሰዎች ባለፉት ጊዜያት ከኖሩት ሰዎች አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ምሳሌነት በመማር እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ሕይወት እንዴት መኖር እንደሚችሉ ለማሳየት ነው። ለምሳሌ:- ሳምሶን በአሉታዊ ምሳሌነቱ ትምህርት ልናገኝበት ለምንችለው ታሪክ አንድ ጥሩ ምሳሌ ነው (መሳ. 13-16)። ክርስቲያኖች እንደመሆናችን፥ ሳምሶን በፍትወተ ሥጋ ኃጢአት በመውደቁ ሕይወቱን እንዴት እንዳጠፋ በመመልከት፥ ሕይወታችንና አገልግሎታችን እንዳይበላሽ በፍትወተ ሥጋ ኃጢአት እንዳንወድቅ መጠንቀቅ እንዳለብን እንማራለን።

8ኛ ጥያቄ፦ ሀ) አንዳንድ ክርስቲያን መሪዎች ሳምሶን በወደቀበት አኳኋን የሚወድቁት እንዴት ነው? ለ) ከሳምሶን ሕይወት መጥፎ ምሳሌነት ምን ሊማሩ ይገባ ነበር?

ከታሪኮች በጎ ምሳሌነትም ልንማር ይገባናል። ለምሳሌ፦ አብርሃም ይስሐቅን ለመሠዋት ከፈቀደበት ታሪክ፦ እግዚአብሔር ከማንኛውም ነገር ይልቅ ከቤተሰባችንም በላይ እንዴት እርሱን መውደድ እንዳለብን እንደሚፈልግ እንማራለን (ዘፍ. 22)።

የብሉይ ኪዳንን ታሪካዊ ክፍሎች የምንተረጉምባቸው በርካታ መመሪያዎች አሉ። ከዚህ በታች የተሰጡት እግዚአብሔር ከታሪክ ውስጥ ምን ሊያስተምረን እንደሚፈልግ ለመረዳት እንድንችል ሁል ጊዜ በአእምሮአችን ውስጥ ልንጠብቃቸው ከሚገቡን ነገሮች ጥቂቶቹ ናቸው።

1. የብሉይና የአዲስ ኪዳን ታሪኮችን መረዳት የሚገባን በሦስት የተለያዩ ደረጃዎች ነው፤ (ቀጥሎ ያለውን ሥዕል ተመልከት)። በመጀመሪያ፦ እያንዳንዱ ታሪክ ከፍተኛ ደረጃ አለው። ታሪኩ በዚህ ደረጃው ስለ እግዚአብሔር ሰፊ ነገር ያስተምረናል። በዚህ ደረጃ ጸሐፊው ሊነግረን የሚፈልገው፦ እግዚአብሔር በአንድ ሕዝብ ወይም በግለሰቦች ሕይወት ውስጥ ሊሠራ ያለውን ዓለም አቀፋዊ ዕቅድ ነው። አብዛኛው የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ስለ እግዚአብሔር አካላዊ ሕልውና፦ ዓለምን ስለ መፍጠሩ፦ ስለ ሰው ልጅ ከፉትና በእግዚአብሔር ስለ መቤዠት አስፈላጊነት አንዳንድ ነገሮችን ያስተምረናል። ይህ ከፍተኛ ደረጃ እግዚአብሔር ሁሉን ነገር ለማስተካከል ስለ ሚሰጠው መሢሕም ይናገራል።

9ኛ ጥያቄ፦ አንድ የብሉይ ኪዳን ታሪክ ምረጥ። ይህ የመረጥከው ታሪክ ስለ እግዚአብሔር ባሕርይና ዓላማ፦ ከሰው ልጅ ጋር አብሮ ስለ መሥራቱ፦ ለሰው ልጅ ኃጢአተኛነት ወይም እግዚአብሔር የሰውን ልጅ ለመዋጀት ስላለው ዕቅድ ምን ያስተምረናል?

ሁለተኛው፦የታሪኩ መካከለኛ ክፍል ነው። ይህ ደረጃ ማዕከላዊ የሚያደርገው በብሉይ ኪዳን የእግዚአብሔር ሕዝብ የነበሩትን እስራኤልን ነው። በአዲስ ኪዳን ይህ ደረጃ የሚያተኩረው በኢየሱስና በቤተ ክርስቲያን ጅማሬ ላይ ነው። የብሉይ ኪዳን ታሪክ የሚያተኩረው በእስራኤል ሕዝብ አካባቢ ነው። የእስራኤል ሕዝብ በአብርሃምና በዘሮቹ

እንዴት እንደተጀመረ በዘፍጥረት እናነባለን። ከዘጸአት ጀምሮ እስከ 2ኛ ዜና ባለው ክፍል ደግሞ እግዚአብሔር ለእስራኤል ሕዝብ የተስፋይቱን ምድር እንዴት እንደሰጣቸው፥ በዳዊት በኩል የተሳካላቸው ሕዝብ አድርጎ እንዴት እንደለወጣችው፥ ሕዝቡ እንዴት በኃጢአት እንደወደቁና እግዚአብሔር እንደቀጣቸው እንመለከታለን። አብዛኛውን ጊዜ የብሉይ ኪዳን ታሪኮች እግዝአብሔር ከእስራኤል ሕዝብ ጋር እንዴት ይሠራ እንደነበረ ያመለክታሉ። ስለዚህ አንድን ታሪክ በምናጠናበት ጊዜ እግዚአብሔር ስለ እስራኤል ሕዝብ ምን እንደሚል መገመት አለብን።

**10ኛ ጥያቄ፥ ሌላ የብሉይ ኪዳን ታሪክ ምረጥ። ያ ታሪክ በእስራኤል ሕዝብ አጠቃላይ ታሪክ ላይ ምን የሚጨምረው ነገር አለ?**

ሦስተኛው፥ የእስራኤልን ሕዝብ ታሪክ የተሟላ የሚያደርጉት የግለሰቦች ታሪኮች አሉ። የአብርሃም፥ የሙሴ፥ የዳዊት፥ ወዘተ ታሪኮች ተጽፈው ይገኛሉ። ከእነዚህ ታሪኮች በርካታ መንፈሳዊ እውነቶችን እንማራለን።

እያንዳንዱ የግለሰብ ታሪክ የመጽሐፍ ቅዱስ ትረካ የተመሠረተበት ነው። ጸሐፊው የእያንዳንዱን ግለሰብ ታሪክ ሲጽፍ ትልቅ ዓላማ ነበረው። ሊነግረን የፈለገው የእስራኤልን ሕዝብ ታሪክ ቢሆንም፥ የእያንዳንዱ ግለሰብ ታሪክ የሚጫወተው ትልቅ ሚና አለው፤ ነገር ግን ከዚህም በላይ ጸሐፊው ሊነግረን የፈለገው ስለ እግዚአብሔርና ከሰዎች ጋር ስላለው ግንኙነት ነው።

ስለ እግዚአብሔር ማስተማር

ስለ እስራኤል ማስተማር

ስለ ግለሰቦች ማስተማር

2. የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኮች በትምህርት ቤት እንደምናጠናቸው ዓይነት የጥንት ሰዎች ታሪክ ብቻ አይደሉም። ይልቁንም እግዚአብሔርን ለመግለጥና ለሰዎች በሰዎች በኩል ምን እንዳደረገ የሚነግሩን ናቸው። የመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት በእግዚአብሔር ላይ እንጂ ሰዎች ባደረጉት ነገር ላይ አይደለም።

3. በብሉይ ኪዳን የታሪክ ጽሑፎች ውስጥ የቃላትን ተምሳሌታዊ ትርጉም መፈለግ የለብንም። ታሪኩን ልክ ተጽፎ እንዳለ በቀጥታ

ለመረዳት መሞከር ያሻል። ይህም ማለት ድርጊቱ በተፈጸመበት ታሪካዊ መሠረት ልንረዳው ያስፈልጋል ማለት ነው። ለመረዳት የማንችላቸው ባሕላዊ ነገሮች ካሉ ለመረዳት መሞከር አለብን። አንድን ታሪክ ከመተርጎማችን በፊት ባሕላዊ ነገሮችን ስለ መረዳት አስፈላጊነት ጥሩ ምሳሌ የሚሆነን ቦዔዝ በምሽት መጎናጸፊያውን በሩት ላይ ስለማኖሩ የሚናገረው ታሪክ ነው። በአይሁድ ባሕል ይህ አንድ ሰው የማግባት መግለጫ ነው (ሩት 3፡9)። እነዚህን የተለያዩ ባሕላዊ ተግባሮች ለመረዳት ካልቻልን፥ በታሪኩ ውስጥ ልንረዳቸው የማንችላቸው በርካታ ነገሮች ይኖሩና የእግዚአብሔርን ሥራና በታሪኩ ውስጥ በተመለከትነው መንገድ አንድን ነገር የፈጸመበትን ምክንያት ምን እንደሆነ ሳንረዳ እንቀራለን። ታሪኩን ለማሟላት አንዳንድ ነገሮችን በመገመት የራሳችንን አስተሳሰብ እንዳንጨምር መጠንቀቅ አለብን።

4. አንዳንድ ጊዜ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኮች ዋናውን ትምህርት በቀጥታ አያስተምሩም። እንደ አንዳዶቹ የመጽሐፍ ቅዱስ የማስተማሪያ ክፍሎች፥ (ለምሳሌ፡- ሮሜ) እግዚአብሔር እንድናውቀው የሚፈልገውን ነገር በቀጥታ አይናገሩም። ይልቁንም በታሪኩ ውስጥ ያለውን ትምህርት የምናገኘው በተዘዋዋሪ መንገድ ነው። ብዙውን ጊዜ ታሪኮቹ በሌላ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል የሚገኙ ቀጥተኛ ትምህርቶችን ይገልጻሉ። ለምሳሌ፡- በዳዊትና በቤርሳቤህ ታሪክ ውስጥ ዝሙት ስሕተት እንደሆነ በቀጥታ አልተናገረም። ይህ በዘጸ. 20፡14 ላይ በቀጥታ ተነግሯል። ይህ ታሪክ ግን በተዘዋዋሪ መንገድ እግዚአብሔር ዝሙትን እንደሚጠላ ያስተምራል።

5. እያንዳንዱን ታሪክ ለሥነ- ምግባር ወይም ለማስተማሪያነት ከመፈለግ ይልቅ አንድ ታሪክ የሌላ ትልቅ ታሪክ ክፍል አካል መሆኑንና ዋናው ትኩረቱም የትልቁን ታሪክ ዋና ትምህርት ማግኘት እንጂ ትንሹ ታሪክ ላይ እንዳልሆነ ልናስታውስ ያስፈልገናል።

6. በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኙ ታሪኮች እያንዳንዳቸው መንፈሳዊ መመሪያን ለማስተማር የተመረጡ ናቸው። የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፊዎች ሊጠቀሙባቸው የሚችሉ በርካታ ታሪኮች ነበሩ። አንድን ታሪክ በተለይ የመረጡበት ምክንያት ምንድን ነው? ምክንያቱም

እነዚያ ታሪኮች የሥነ ምግባር ወይም መንፈሳዊ ትምህርት ለማስተማር የተመረጡ ነበሩ፤ ስለዚህ አንድ ታሪክ በባሕላዊ መልኩ አንድ ጊዜ በግልጽ ከተረዳነው በኋላ ከታሪኩ የሚገኘውን ዋና መንፈሳዊ ትምህርት መፈለግ አለብን። ይህ ትምህርት ብዙ ጊዜ የሚገኘው በታሪኩ ውስጥ የሚገኙ ሰዎች ባደረጉት ምርጫ ወይም በፈጸሙት ተግባር ነው። ታሪኩን በመረዳት ሂደት ውስጥ ራሳችንን በውስጡ በማስገባት በዚያን ጊዜ የምንኖር ብንሆን ኖሮ ምን ይሰማን ወይም ምን እናደርግ ነበር? ብሎ መጠየቅ ብዙ ጊዜ በጣም ጠቃሚ ነው።

7. በትረካው ጽሑፍ ውስጥ ጸሐፊው የተፈጸመውን ነገር በትክክል የሚገልጽ መሆኑን መገንዘብ መልካም ነው። እርሱ ይህ ጥሩ ነው ላይል ይችላል። ለምሳሌ:- በዘፍ. 38 ይሁዳ ሴተኛ አዳሪ ናት ብሎ ከገመታት ሴት ጋር እንደ አመነዘረ እናነባለን። ይህ ስሕተት እንደሆነ ከሌሎች የቅዱሳት መጻሕፍት ትምህርቶች በግልጽ እንረዳለን። የጸሐፊው ትኩረት ግን ድርጊቱን መግለጥ ነው እንጂ የሰውዬውን ተግባር መደገፉ አልነበረም፤ ስለዚህ የመጽሐፍ ቅዱስን ታሪክ በምንመዝንበት ጊዜ ጸሐፊው ዝም ብሎ የተፈጸመውን ድርጊት መግለጥ (ለምሳሌ የአንድን ግለሰብ ኃጢአት) ወይም እነዚያ ታሪኮች የተከበሩና ልንከተላቸው የሚገባን መሆናቸውን እያስተማረን እንደሆነ መገንዘብ አለብን።

| |
|---|
| 11ኛ ጥያቄ፥ ዘፍ. 9:20-27 አንብብ። ሀ) በእነዚህ ቁጥሮች የተነገረው ታሪክ ምንድን ነው? ለ) በዚህ ታሪክ ውስጥ ልንረዳቸው የሚያስፈልጉ ባሕላዊ ነገሮች የትኞቹ ናቸው? ሐ) የዚህ ታሪክ የሥነ-ምግባር ትምህርት ምንድን ነው? መ) የሥነ- ምግባር ትምህርቱ የተገኘው ከአዎንታዊ ነው ወይስ ከአሉታዊ ተግባር? አብራራ። ሠ) ጸሐፊው በቀጥታ ስሕተት መሆኑን የማያሳየው፥ ነገር ግን ከሌላ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል የምንረዳው ምን ድርጊት ተገልጧል? |

2. ግጥምና ቅኔ:- በፔንታቱክ ውስጥ የጥንት የዕብራውያን ሥነ-ግጥምና ቅኔ ተሠራጭቶ እናገኛለን። ሥነ- ግጥምና ቅኔ በተለያዩ ባሕሎች ውስጥ የተለያየ ገጽታ ስላለው፥ አይሁድ እንዴት እንደሚጠቀሙበት ልንገነዘብ ያስፈልጋል። ቆየት ብለን እንደ መዝሙረ ዳዊትና መጽሐፈ ምሳሌ ያሉትን መጻሕፍት

በምናጠናበት ጊዜ ሥነ - ግጥምና ቅኔ እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚያስረዱ ሕግጋትን እንመረምራለን። ስለ ግጥምና ቅኔ ልንረዳው የሚገባ አንድ ዋና ነገር ብዙ ጊዜ የሚጻፈው በተምሳሌታዊ መግለጫ መልክ እንጂ በቀጥታ አለመሆኑን ነው። ለምሳሌ በመዝሙረ ዳዊት ዛፎች ለእግዚአብሔር ሲዘምሩ እንመለከታለን (መዝ. 96፡12 ተመልከት)። እኛ በምንዘምረው ዓይነት ዛፎች እንደማይዘምሩ እናውቃለን፤ ነገር ግን እኛ በቃላችን እግዚአብሔርን እንደምናመሰግን ዛፎችም እርሱ ፈጣሪያቸው በመሆኑ ያመሰግኑታል። ስለሆነም በሥነ - ግጥምና ቅኔ ቋንቋ፥ ቃላት ራሳቸው ተምሳሌታዊ ይሆኑና ከምልክቱ ወይም ከምሳሌው ጋር ተመሳሳይ የሆነ አንድ ተግባር ወይም እውነት ይጠቁማሉ። ሥነ - ግጥምና ቅኔን በምንተረጉምበት ጊዜ ምልክቶቹን ከእውነተኛ ትርጉም ወይም ከተሰወረ እውነት መለየት አለብን።

| |
|---|
| 12ኛ ጥያቄ፥ ዘጸ. 15፡1-18 አንብብ ሀ) ሙሴ ወደ እግዚአብሔር በዘመረው ዝማሬ ውስጥ የሚገኙትን ተምሳሌቶች ዘርዝር። ለ) እነዚህ ተምሳሌቶች ምን ያስተምሩናል? |

በእነዚህ ቁጥሮች ሙሴ መዝሙሩን የእግዚአብሔርን ታላቅነትና ክብር ለመግለጥ ይጠቀምበታል። በመዝሙሩ ውስጥ በርካታ ተምሳሌቶችን ይጠቀማል። ለምሳሌ፡- እግዚአብሔር የፈርዖንን ሠራዊት ሊያሸንፍ እንደቻለ አንድ ታላቅ ተዋጊ አድርጎ ያቀርበዋል። ከታሪኩ እንደምናስታውሰው ግን የፈርዖንን ሠራዊት ድል ለማድረግ እግዚአብሔር የተጠቀመው በታላቅ ውኃ ነው። እግዚአብሔር ቀኝ እጅና አፍንጫ እንዳለው ሆኖ ቀርቦ እናየዋለን። ከመጽሐፍ ቅዱስ እንደምንረዳው ግን እግዚአብሔር መንፈስ ስለሆነ እንደ እኛ ሥጋዊ አካል ሊኖረው አይችልም። ሙሴ እግዚአብሔር እንዴት ታላቅ እንደሆነና ለእስራኤል ለመሥራት ሲል ኃይሉን እንዴት እንደተጠቀመበት ለመግለጥ ስብአዊ አባባሉን በሥነ - ግጥምና በቅኔ መልክ አቅርቧል።

3. ትንቢት፡- በፔንታቱክ ውስጥ ተሰራጭተው የሚገኙ የተለያዩ ትንቢቶች አሉ። ከእነዚህ ትንቢቶች አንዳንዶቹ በቀጥተኛ ቋንቋ የቀረቡ ሲሆን (ምሳሌ፡- ዘፍጥ. 15፡13)፥ ሌሎቹ ደግሞ በተምሳሌነት ወይም በሥነ - ግጥምና በቅኔ መልክ

ቀርበዋል(ምሳሌ፡- ዘፍ. 49፡8-12)። በብሉይ ኪዳን የሚገኙ ትንቢቶች አብዛኛዎቹ በሥነ ግጥምና በቅኔ መልክ የቀረቡ ናቸው። ትንቢት በሥነ- ግጥምና በቅኔ መልክ ቀርቦ ተምሳሌታዊ የሆነ መግለጫ መያዙ ለመተርጎም በጣም ከባድ ያደርገዋል። በብሉይ ኪዳን ትንቢት ሁለት የተለያዩ ትርጉሞች አሉት። በመጀመሪያ፥ ትንቢት የሚለው ቃል በማንኛውም ጊዜ እግዚአብሔር ለሕዝቡ ቀጥተኛ ትምህርትን ለመስጠት ወይም ፈቃዱን ለመግለጥ አንድን ሰው ተጠቅሞ የሚያመጣው መልእክት ነው። በብሉይ ኪዳን የሚገኙ አብዛኛዎቹ ትንቢቶች ስለ ወደፊቱ ነገር የሚናገሩ አይደሉም፤ ነገር ግን እግዚአብሔር በዚያ ዘመን ለነበሩ ሰዎች እነርሱ ምን እንዲያደርጉ ይፈልግ እንደ ነበር የሚገልጥ መልእክት ነው። ሁለተኛ፥ በአንዳንድ ትንቢቶች እግዚአብሔር ወደ ፊት ምን እንደሚሆን አስቀድሞ ይገልጣል። በዘፍጥረት 49 እግዚአብሔር መሢሑ የሚመጣው ከይሁዳ ነገድ እንደሚሆን አስቀድሞ ለመናገር ያዕቆብን ተጠቅሞበታል፤ ስለዚህ የትንቢት መልክ ወዳለው የቅዱሳት መጻሕፍት ክፍል ስንደርስ የትኛው የወደፊትን ነገር እንደሚያመለክትና የትኛው ደግሞ በዚያን ጊዜ ለሚሆነው ጉዳይ የተለየ ትእዛዝ እንደሆነ መለየት ያስፈልገናል። እንዲሁም ያ ትንቢት የተሰጠው ለምን እንደሆነም በግልጥ መወሰን አለብን። ይህ ትንቢት የተነገረው በዚያን ጊዜ ለነበረ አንድ ሰው፥ ወይም ቡድን ነውን? ወይስ ዛሬ ካለን ሰዎች ሕይወት ጋርም የሚዛመድ ነው? ብለን መጠየቅና ለዚህ መልስ ለማግኘት መቻል አለብን። ከኢሳይያስ እስከ ሚልክያስ ያሉትን የነቢያት መጻሕፍት ስናጠና ይህንን በጥልቀት እንመለከተዋለን።

4. ሕግ፡- የፔንታቱክ አብዛኛው ክፍል «ሕግ» የተባለ የተለየ ዓይነት ሥነ-ጽሑፍ ነው። በአንዳንድ ረገድ የምድራችን ሕግጋት ድንጋጌዎች የሆኑት ደንቦች ዝርዝር ነው። አንዳንዶቹ ከዘጸአት እስከ ዘዳግም ባሉት መጻሕፍት ውስጥ ከእግዚአብሔር የተሰጡ ከ600 የሚበልጡ ሕግጋት እንዳሉ ገምተዋል።

እግዚአብሔር ለአይሁድ ይህን ሁሉ ሕግ የሰጠበት ምክንያት ምንድን ነው? የመጽሐፍ ቅዱስ ሕግ በእግዚአብሔርና በአይሁድ ሕዝብ መካከል ያለ ቃል ኪዳን አንዱ ክፍል ነበር። እግዚአብሔር እውነተኛ የአይሁድ

ንጉሥ እንደመሆኑ መጠን ሕይወታቸውን በሙሉ የሚገዙበትና የተለዩ «ቅዱስ» ሕዝብ ሆነው ለመኖር የሚችሉባቸውን የተለያዩ ግልጥ ሕግጋት ሰጣቸው። የእግዚአብሔር ልጆች እንደመሆናቸው መጠን ቅዱስ የሆነውን እግዚአብሔርን መምሰል ነበረባቸው።

| 13ኛ ጥያቄ፥ ቅድስና ዛሬ ለእኛ የሚያስፈልገው እንዴት ነው? |
|---|

እግዚአብሔር፥ አይሁድ የሕይወታቸውን የተለያዩ አቅጣጫዎች በሙሉ እንዲነካ ግንኙነታችውን በእርሱ ላይ እንዲመሠርቱ ይፈልግ ነበር። እስራኤላውያን በእግዚአብሔር ፊት የተቀደሰ ሕይወት እስከኖሩና እግዚአብሔር የሰጣቸውን የቃል ኪዳን ግዴታዎች እስካሟሉ ድረስ፥ ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት ይኖራቸው ነበር። ከዚያም እግዚአብሔር አምላካቸው ይሆንና ሥጋዊም ሆነ መንፈሳዊ ፍላጎታቸውን በማሟላት ከጠላቶቻቸው ሁሉ ይጠብቃቸው ነበር። ስለዚህ እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳን ለአይሁድ የሰጣቸው ሕግጋት የማይነካው የሕይወታቸው ክፍል አልነበረም። ከጎረቤቶቻቸው፥ ከመሪዎቻቸው ከመንግሥታቸውና ከራሱ ከእግዚአብሔር ጋር እንዴት መኖር እንዳለባቸው የሚናገር ነበር።

| 14ኛ ጥያቄ፥ ሀ) ከእግዚአብሔር ጋር ያለን ኅብረት ሕይወታችንን በሙሉ የሚነካው እንዴት ነው? ለ) በኢየሱስ ላይ ያለ እምነትህ ከቤተሰብህ፥ ከጎረቤትህ፥ ከመንግሥትህ፥ ከሥራህና ወዘተ ጋር ያለህን ግንኙነት እንዴት እንደለወጠ ከራስህ ሕይወት ምሳሌ ስጥ። |
|---|

እግዚአብሔር በፔንታቱክ ውስጥ ለአይሁድ የሰጣቸው ሕግጋት ሦስት ዋና ዋና የሕይወት ክፍሎችን የሚመለከቱ ነበሩ። በመጀመሪያ፥ የመንግሥት ወይም የሕዝብ ሕጎች ነበሩ። እነዚህ ሕጎች፡- የጋብቻ፥ የቤተሰብ፥ የውርስ፥ የንብረት ባለቤትነት መብት፥ የባሪያ፥ የቀረጥ፥ የደመወዝ ወዘተ ናቸው። ሁለተኛ፥ የሥነ- ምግባር ሕግጋት የነበሩ ሲሆን እነዚህም፡- የነፍስ ግድያ፥ ዝሙት፥ ያለፈቃዱ ሴትን የመድፈር፥ የሌብነት፥ የሐሰት ምስክር የመሳሰሉት ናቸው። ሦስተኛ፥ የሃይማኖት፥ የሥርዓት ሕግጋት ሲሆኑ እነዚህ ሕግጋት እስራኤላውያን እንዴት እግዚአብሔርን ማምለክ እንዳለባቸው፥ መሥዋዕት ማቅረብ እንዳለባቸው፥ በሥርዓት ቅዳሴ እንዴት ንጹሐን መሆን እንዳለባቸውና

ሃይማኖታዊ በዓላቸውን መቼ ማክበር እንደሚገባችው ወዘተ የሚናገሩ ናቸው።

15ኛ ጥያቄ፥ ሀ) በአሁኑ ጊዜ የኢትዮጵያ መንግሥት በተለይ የሚቆጣጠረው የትኞቹን ዓይነት ሕግጋት ነው? ለ) በኢትዮጵያ ያሉ ልዩ ልዩ ሃይማኖቶች የትኞቹ ዓይነት ሕግጋት ናቸው ያሉዋቸው? ሐ) በኢትዮጵያ ውስጥ በሚገኙ የተለያዩ ሃይማኖቶች ውስጥ አንዳንድ የሥነ ምግባርና ሃይማኖታዊ ሕግጋት የሚለያዩት እንዴት ነው?

በፔንታቱክ ውስጥ የሚገኙት ሕግጋት የሚከፈሉት በሦስት ዋና ዋና ክፍሎች ቢሆንም በዓይነታቸው ግን አምስት ናቸው። እነርሱም ፡-

1. በተለያዩ ሁኔታዎች ውስጥ ለሚነሡ ጉዳዮች የሚሆኑ ሕግጋት፥ እነዚህ ሕግጋት ብዙ ጊዜ «እንዲህ ቢሆን . . . እንዲህ ይደረግ» የሚሉ ቃላት ይገኙባቸዋል።

16ኛ ጥያቄ፥ ዘጸ. 22፡22-24 ተመልከት። ሀ) ይህ ሕግ የሚጠቅሳችው ልዩ ሁኔታዎች ምንድን ናቸው? ለ) የተጠቀሱት ቅጣቶችስ ምንድን ናቸው?

2. ቀጥተኛ ትእዛዛትን በመስጠት እግዚአብሔር ምን እንድናደርግ እንደሚፈልግ የሚናገሩ ሕግጋት፡- እነዚህ ሕግጋት አዎንታዊ (አድርግ . . .) እና አሉታዊ (አታድርግ . . .) የሚሉ ትእዛዛት ሊሆኑ ይችላሉ።

17ኛ ጥያቄ፥ ዘጸ. 20፡3-17 አንብብ። ሀ) በእነዚህ ቁጥሮች የሚገኙትን አዎንታዊ ትእዛዛት ዘርዝር። ለ) በእነዚህ ቁጥሮች የሚገኙትን አሉታዊ ትእዛዛት ዘርዝር።

3. ሊሆኑ ስለሚችሉ መላምታዊ ነገሮች የሚናገሩ ሕግጋት፥ እነዚህ ሕግጋት ሊሆኑ ስለሚችሉ ተግባራት ምሳሌዎችን ይሰጣሉ፤ ነገር ግን የምናከናውናቸውን ተግባራት በሚመለከት መከተል የሚገባን ብቸኛ ሁኔታዎች አይደሉም። ለምሳሌ በዘሌ. 19፡14 እግዚአብሔር እንዲህ የሚል ትእዛዝ ሰጥቷል፡- «ደንቆሮውን አትሳደብ፥ በዕውርም ፊት ዕንቅፋት አታድርግ፥ ነገር ግን አምላክህን ፍራ» የዚህ ሕግ ዓላማ እነዚህን የተለዩ ሁኔታዎች መቆጣጠር ብቻ አይደለም። ለምሳሌ፡- ይህ ማለት ዕውሩን

መስደብና ደንቆሮው ፊት ዕንቅፋት ማድረግ ተፈቅዷል ማለት ነውን? አይደለም። በዚህ ሕግ እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን ዕውሮችና ደንቆሮዎች የሚገባቸውን ስፍራ ባለመስጠት ከማጉላላት ይልቅ ሊያከብሩአቸው እንደሚገባ ማሳየቱ ነበር። ይህ ሕግ ከእኛ ይልቅ ጉድለት የገጠማቸውን ሰዎች በሚገባ ያለማክበርን የሚቃወም ነው።

4. እጅግ የከፋ በደል ከመፈጸም ጋር የተያያዙና ወንጀሉን በፈጸመው ሰው ላይ የሞት ፍርድ የሚያስከትሉ ሕግጋት ናቸው።

| |
|---|
| 18ኛ ጥያቄ፥ ዘጸ. 21፡14-17 አንብብ። የማይታዘዘው ሰው እንዲገደል እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን ያዘዛቸውን ልዩ ልዩ ሁኔታዎች ዘርዝር። |

5. በምሥጢር የተፈጸሙና ለማረጋገጥ አስቸጋሪ የሆኑ ጉዳዮችን የሚመለከት ሕግ፥ ብዙ ጊዜ ለእነዚህ ሕግጋት የሚሰጠው ቅጣት «እርግማን» ነበር። በምሥጢር የተፈጸመን ነገር መቆጣጠር ለሰው ልጅ አስቸጋሪ ስለሆነ እግዚአብሔር ራሱ ጥፋተኛውን መቅጣት አለበት። እነዚህን ሕግጋት የተላለፉትን ሰዎች እግዚአብሔር እንደሚቀጣቸው (እንደሚረግማቸው) ቃል ገብቶ ነበር። አንድ ሰው እነዚህን ሕግጋት ሲተላለፍ ቢያዝ፥ የሚደርሱበት የተለያዩ ቅጣቶች ቢኖሩም፥ የእነዚህ ዓይነት ሕግጋት ትኩረት ሕጉን የተላለፉ ሰዎች በሰው ባይያዙም እንኳ ሊቀጣቸው የሚችለው እግዚአብሔር እንደሚያያቸው ለመግለጥ ነበር።

| |
|---|
| 19ኛ ጥያቄ፥ ዘዳ. 27፡17-26 አንብብ። ሀ) ሕግጋቱን በተላለፈ ሰው ርግማን እንደሚደርስበት የሚናገሩትን የተለዩ ሕጎች ዘርዝር። ለ) ሰው ኃጢአታችንን ሊያይ ባይችልም እንኳ እግዚአብሔር አይቶ ይቀጣናል። ይህ እውነት ኃጢአትን ከማድረግ እና ቅጣትን እንደምናመልጥ ከማሰብ እንዴት ይጠብቀናል? የብሉይ ኪዳን ሕግጋት ለክርስቲያኖች ጥቅማቸው ምንድን ነው?<br>20ኛ ጥያቄ ፥ ሀ) ብዙውን ጊዜ እኛ ልንታዘዛቸው አይገባንም ብለን የምናስባቸው፥ የኦርቶዶክስ ክርስቲያኖች ግን የሚጠብቋቸውን ሕግጋት ዘርዝር። ለ) የሰባተኛ ቀን አክባሪዎች አድቬንቲስት ልንጠብቃቸው ይገባል የሚሉአቸውን የብሉይ ኪዳን ሕግጋት ዘርዝር። |

ስለ እነዚህ ሕግጋት ልንጠይቀው የሚገባ አንድ ዋና ጥያቄ «በአዲስ ኪዳን ዘመን የምንኖር ሰዎች ለእነዚህ የብሉይ ኪዳን ሕግጋት ልንሰጣቸው የሚገባ ስፍራ ምንድን ነው?» የሚል ነው። የብሉይ ኪዳን ሕግጋት ለእኛ ባላቸው ስፍራ የክርስቲያኖች አመለካከት የተለያየ ነው። በግልጽ ስሕተት የሆኑ ሁለት ዓይነት አመለካከቶች አሉ። የመጀመሪያው፥ የብሉይ ኪዳን ሕግጋት በሙሉ ዛሬ እኛንም ይገዙናል የሚለው አሳብ የተሳሳተ ነው። ከአዲስ ኪዳን ትምህርቶች በግልጽ እንደምንመለከተው ስለ ምግብ የተነገሩ ሕግጋት ዛሬ እኛን አይገዙንም። በብሉይ ኪዳን ሥጋቸው እንዲበላ የተፈቀዱ የተወሰኑ እንስሶች ነበሩ (ማር. 7፡14-23፤ የሐዋ. 10፡9-16)። እንዲሁም ቅዳሜን እንደ አምልኮ ቀን የመጠበቅ ሕግ እንደማይገዛን ተገልጾአል (ቆላ. 2፡16-17)። እነዚህን ሕግጋት መጠበቅ ባይከፋም፥ በክርስቲያን ላይ ሊሠለጥኑ የሚችሉ ግን አይደሉም።

ሁለተኛው አመለካከት ደግሞ፤ የትኞቹም የብሉይ ኪዳን ሕግጋት በአሁኑ ጊዜ እኛን የሚመለከቱ አይደሉም የሚለው የተሳሳተ አቋም ነው። አንዳንድ ክርስቲያኖች እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳንና በአዲስ ኪዳን ከሕዝቡ ጋር የተገናኘባቸው መንገዶች ፍጹም የተለያዩ ናቸው ብለው ያስተምራሉ። በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር የተገናኘው «በሕግ» አማካይነት ሲሆን በአዲስ ኪዳን ደግሞ ከክርስቲያኖች ወይም ከቤተ ክርስቲያን ጋር የሚገናኘው «በጸጋ» ነው። ይህ አመለካከት የትኞቹንም የብሉይ ኪዳን ሕግጋት መከተል የለብንም ለማለት ከሆነ የተሳሳተ ነው።

የብሉይ ኪዳን ሕግጋት ዛሬ በእኛ ሕይወት ውስጥ ሊኖራቸው ስለሚገባ ስፍራ አዲስ ኪዳን ምን እንደሚል በምንመረምርበት ጊዜ የሚከተሉትን እውነቶች እናገኛለን:-

1. የብሉይ ኪዳን ሕግጋት በሙሉ ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው የጻፉአቸው የእግዚአብሔር ቃል ክፍል ናቸው። እንደቀሩት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ለትምህርትና፥ በጽድቅ ላለው ልምምድ የሚጠቅሙ ናቸው (2ኛ ጢሞ. 3፡16)።

2. እግዚአብሔርን የሚገደው ሕግጋትን በውጫዊ ገጽታቸው መጠበቁ ብቻ አይደለም፤ ይልቁንም የልብን አሳብና መሻት ጭምር ይመረምራል። ለምሳሌ:- እግዚአብሔር «አታመንዝር» የሚለውን ሕግ ሲሰጥ የከለከለው በጋብቻ ያልተጣመሩ ሰዎች

የሚፈጽሙትን ፍትወት ብቻ ሳይሆን ሰውን ወደምንዝርና ሊመራ የሚችለውን ጽኑ የፍትወተ ሥጋ ፍላጎት አሳብ ጭምር ነበር (ማቴ. 5፡27-30)። እግዚአብሔርን ከልብ መታዘዝና ትእዛዛቱንም መጠበቅ ያለብን በውጫዊ አሳብ ብቻ ሳይሆን ከውስጥ በሆነ እውነተኛ ዝንባሌና ስሜትም ጭምር ነው።

ብዙውን ጊዜ ክርስቲያኖች አብልጠው የሚያስቡት ሰዎች እንደ ፍቅር፥ ደስታ፥ ሰላም፥ ራስን መግዛት፥ ወዘተ (ገላ. 5፡22-23) ካሉት ውስጣዊ ነገሮች ይልቅ ውጫዊ የሆኑት የመጽሐፍ ቅዱስና የቤተ ክርስቲያን ሕግጋትን እንዲጠብቁ ነው። ይህም «ሕግ አጥባቂነት» በመባል ይታወቃል። እግዚአብሔር የሰጠንን ሕግ እንድንጠብቅ የሚፈልግ መሆኑ ግልጽ ቢሆንም፥ የምንጠብቃቸው በተገቢ ምክንያቶች ወይም በእውነተኛ ውስጣዊ ዝንባሌዎች መሆኑን ማረጋገጥም ይፈልጋል።

| |
|---|
| 21ኛ ጥያቄ፥ ሀ) ሰዎች እግዚአብሔርን ደስ በሚያሰኝ ዝንባሌ ሊጠብቋቸው የሚችሏቸውን የመጽሐፍ ቅዱስ ወይም የቤተ ክርስቲያን ሕግጋት ዘርዝር። ለ) እግዚአብሔርን በትክክለኛ ዝንባሌ መታዘዝና በተሳሳተ አመለካከት መታዘዝ መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው? |

3. ሕጉ «ቅዱስ፥ ጻድቅና መልካም» ነው (ሮሜ 7፡12 ተመልከት)። ስለሆነም ይህ ዛሬም ለክርስቲያን ልምምድ ጠቃሚ ነው። ኢየሱስ ሕግን ሊፈጽም እንጂ ሊሽር እንዳልመጣ ተናግሮአል (ማቴ. 5፡17-20)። ስለዚህ ለክርስቲያን የብሉይ ኪዳንን ሕግ ማወቅና መረዳት በጣም አስፈላጊ ነው፤ ነገር ግን ሕግን ራሱን በመጠበቅና በመስጠት ረገድ እግዚአብሔር ባለው ዓላማና ዕቅድ መካከል ግልጥ የሆነ ልዩነት ማድረግ አለብን።

4. ከሕግ ሁሉ የሚበልጠውና ሕግን በሙሉ የሚፈጽመው የፍቅር ሕግ ነው (ማቴ. 22፡35-40 ተመልከት)። የፍቅር ሕግ ሁለት አቅጣጫዎች አሉት። በመጀመሪያ፥ ፍቅር ወደ እግዚአብሔር ማመልከት አለበት። እግዚአብሔርን በሙሉ ኃይላችን ልንወደው ይገባናል። እግዚአብሔርን እንደምንወደው የምንገልጽበት መንገድ ትእዛዛቱን መጠበቅ ነው (1ኛ ዮሐ. 5፡1-5)። ሁለተኛ፥ የፍቅር ሕግ ወደ ሰዎችም ማመልከት አለበት። በሙሉ ልባችን እግዚአብሔርን ከወደድንና ፍቅራችንን ለሰዎች ከገለጥን የእግዚአብሔርን ሕግጋት ሁሉ እየፈጸምን ነው ማለት ነው።

22ኛ ጥያቄ፥ ዘጸ. 20፡1-17 አንብብ። ሀ) ለእግዚአብሔርና ለሌሎች ያለን ፍቅር ዓሥርቱን ትእዛዛት የሚፈጽመው እንዴት ነው? ለ) ሌሎች አንዳንድ የቤተ ክርስቲያን ሕግጋትና ትእዛዛትን እንዲጠብቁ ትኩረት ከማድረግ ፈንታ እግዚአብሔርንና ሰዎችን የበለጠ እንዲወዱ እንዴት ማበረታታት እንችላለን?
23ኛ ጥያቄ፥ ገላ. 3፡21-25 አንብብ። ሀ) እነዚህ ጥቅሶች ስለ ብሉይ ኪዳን ሕግጋት ዓላማ ምን ያስተምሩናል? ለ) የብሉይ ኪዳን ሕግጋት ሰውን የሚገዙት እስከ ምን ድረስ ነበር?

5. ከብሉይ ኪዳን ሕግ ዋና ዋና ዓላማዎች አንዱ ለሰው ልጆች በሙሉ ኃጢአተኝነታቸውና በእግዚአብሔር ላይ ያለማቋረጥ ማመፃቸውን ማሳየት ነበር። በእያንዳንዱ ሰው ልብ ውስጥ በተፈጥሮ ያደረውን ክፉ ነገር ልክ እንደ መስተዋት ሆኖ ለማሳየት ነው። ሕግ ሰዎች ሁሉ ኃጢአተኞች መሆናቸውንና በመልካም ሥራቸው ራሳቸውን ማዳን እንደማይችሉ በግልጥ ያሳያል። እነዚህም ወደ ክርስቶስ ፊታቸውን እንዲመልሱና ከኃጢአታቸው ለመዳን በእርሱ ብቻ እንዲታመኑ ይገፋፋቸዋል።

24ኛ ጥያቄ፥ ሀ) በዚህ ዘመን ሰዎች መዳን ይችሉ ዘንድ ይህንን እውነት ማወቅ ያለባቸው ለምንድን ነው? ለ) ዛሬ ብዙ ሰዎች ወደ መንግሥተ ሰማያት መግባት ይችሉ ዘንድ ሕግን ለመጠበቅ እንዴት ይሞክራሉ? ሐ) ወደ መንግሥተ ሰማያት ለመግባት የሚያበቃ መልካም ተግባር ለመፈጸም ወይም ሕግን ለመጠበቅ የማንችለው ለምንድን ነው?

ለእስራኤላውያንም ሆነ ለመላው ዓለም ያለው የሕግ ዋና ዓላማ ወደ ኢየሱስ ወይም ወደ እግዚአብሔር ጸጋ እንዲመለከቱ መገፋፋት ነው (ገላ. 3፡24 ተመልከት)።

6. ብዙዎቹ የብሉይ ኪዳን ሕግጋት የክርስቶስ ኢየሱስን መምጣትና በኢየሱስ በማመን እንዴት መዳን እንደሚቻል ያመለክታሉ።

25ኛ ጥያቄ፥ ሉቃ. 24፡25-27 አንብብ። ኢየሱስ መሞትና ከሞት መነሣት እንዳለበት ለደቀመዛሙርቱ ለመግለጽ የተጠቀመው በምንድን ነው?

በብሉይ ኪዳን የተፈጸሙ ብዙ ታሪካዊ ድርጊቶች፥ ሰዎችና ነገሮች ሁሉ ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ ያመለክታሉ። እርሱ የአምሳላቸው ፍጻሜ ነው። ለምሳሌ አዳም የክርስቶስ አምሳል ነው (ሮሜ 5፡14-19 ተመልከት)። የፋሲካ በዓል የክርስቶስ የመስቀል ሞት አምሳል ነው (1ኛ ቆሮ. 5፡7)። ደግሞም የብሉይ ኪዳን የክህነት አገልግሎት የሊቀ ካህናችን የኢየሱስ ምሳሌ ነው (ዕብ. 7-9)።

የብሉይ ኪዳን ሕግጋትን በምናጠናበት ጊዜ እንዴት ልንተረጉማቸው ይገባል?

1. የእነዚህ ሕጎች ውጫዊ ሁኔታ ለአንድ የተለየ ሰው፥ ወይም ቡድን፥ ወይም ሰዎችን ሁሉ የሚመለከት ነውን? ብለን ልንጠይቅ ይገባል። ሕጉ የተሰጠው ለአንድ የተለየ ሰው ወይም ቡድን ከሆነ የሕጉን ውጫዊ አፈጻጸም መከተል አያስፈልገንም፤ ነገር ግን ከሕይወታችን ጋር ልናዛምደው የምንችል የሕጉ ውስጣዊ ዓላማ ብዙ ጊዜ ይኖራል።

2. እግዚአብሔር ያንን ሕግ በተለይ የሰጠበትን ምክንያት ለመወሰንም መሞከር አለብን። እግዚአብሔር ውስጣዊ የሆኑ የሕግ ዓላማዎችና ውጫዊ አፈጻጸማቸውንም በሚመለከት ጉዳይ አለው። ብዙ ጊዜ እግዚአብሔር ሕግን የሰጠበት ዓላማ ከሕይወታችን ጋር ሊዛመድ ይችላል።

3. በብሉይ ኪዳን ከተሰጡት ሕግጋት መካከል እንደገና እንታዘዛቸው ዘንድ በአዲስ ኪዳን የተሰጡ ልዩ ትእዛዛት መኖራቸውን መመልከትና ማረጋገጥ አለብን። በብሉይ ኪዳን የሚገኝ ሕግ በአዲስ ኪዳን ደግሞ ከተሰጠ ዛሬም ልንታዘዘው እንደሚገባ እርግጠኞች እንሆናለን (ለምሳሌ፡- ዝሙት፥ መግደል፥ መዋሸት፥ ወዘተ)።

4. ከብሉይ ኪዳን ሕግጋት መካከል በአዲስ ኪዳን ልንታዘዛቸው አስፈላጊ እንዳልሆነ የተጠቀሱ ሕጎች እንዳሉም ልንመለከት ያስፈልጋል። ለምሳሌ፡- ኢየሱስ ስለ ምግብ የተሰጡ ሕግጋት አስፈላጊ እንዳልሆኑ ተናግሯል። የዕብራውያን መልእክት ደግሞ ከኢየሱስ ሞት በኋላ እንስሳትን የመሠዋት ሥርዓት አስፈላጊ እንዳልሆነ ያስተምራል።

5. የተለያዩ የብሉይ ኪዳን ሕግጋት ስለ እግዚአብሔር ባሕርይ፥ ከእርሱ ጋር ስላለንና ከሰዎች ጋር ሊኖረን ስለሚገባ ግንኙነት የሚናገሩት ነገር አለን? ብለን ልንጠይቅ ያስፈልጋል።

6. ያ የተሰጠን ሕግ የኢየሱስ ክርስቶስ፥ የደኅንነት፥ ወይም የሌላ የአዲስ ኪዳን ጠቃሚ እውነት አምሳል እንደሆነ ለማወቅ መመርመር ያስፈልገናል፤ ነገር ግን ይህንን ስናደርግ በጣም መጠንቀቅ አለብን። የትኛው የብሉይ ኪዳን ክፍል የክርስቶስ አምሳል እንደሆነ፥ የትኛው እንዳልሆነ ለማወቅ የአዲስ ኪዳን ትምህርት ማረጋገጫ ብዙ ጊዜ ያስፈልገናል። በአንዳንድ ሰዎች ዘንድ የክርስቶስ አምሳል ባልሆኑት ነገሮች ውስጥ የክርስቶስን አምሳል የመፈለግ ዝንባሌ አለ።

26ኛ ጥያቄ፥ ዘጸ. 23ን አንብብ። ሀ) እነዚህን ስድስት ደረጃዎች በመጠቀም ልንጠብቃቸው የሚገባንን ሕግጋት ዘርዝር። ለ) ልንጠብቃቸው የማያስፈልጉ ሕግጋትን ዝርዝር ደግሞ ጻፍ። ሐ) አንዳንዶቹን መጠበቅ ሌሎቹን ደግሞ አለመጠበቅ የሚያስፈልግ ለምን እንደሆነ የሚመስልህን ምክንያት ጻፍ።

## 4ኛ ቀን፡- የኦሪት ዘፍጥረት መግቢያ

27ኛ ጥያቄ፥ «ዘፍጥረት» የሚለውን ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት ውስጥ ተመልከት። ስለ ጸሐፊው፥ ስለ ተጻፈበት ዓላማና ስለ መጽሐፉ አስተዋጽኦ ያገኘኸው ነገር ምንድን ነው?

ከብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ውስጥ ልናጠናቸውና ልንረዳቸው ከሚገቡን እጅግ ጠቃሚ መጻሕፍት አንዱ ዘፍጥረት ነው። ብዙ ክርስቲያኖች በዘፍጥረት ውስጥ የሚገኙትን ታሪኮች ቢያውቁም እንኳ፥ አብዛኛዎቹን ጥልቅ ትምህርቶች ግን አያጠኗቸውም። የዚህ መጽሐፍ ዓላማ ዘፍጥረትን በጥልቀት ማጥናት ባይሆንም፥ በመጽሐፉ ውስጥ የምናገኛቸውንና የተተከረባቸውን ዋና ዋና የሥነ-መለኮት ትምህርቶች ለመመልከት እንሞክራለን። ኦሪት ዘፍጥረትን ከሌላ የትመማ መጽሐፍ ማጥናት ትችላለህ።

## የኦሪት ዘፍጥረት ስያሜ

ለኦሪት ዘፍጥረት የተሰጠው ስም የመጣው ከግሪኩ መጽሐፍ ቅዱስ እንደሆነ ቀደም ሲል አጥንተናል። ዘፍጥረት የሚለው ቃል በመጽሐፉ የመጀመሪያ ሁለት ምዕራፎች ላይ እግዚአብሔር ነገሮችን ሁሉ ስለ

መፍጠሩ በሚናገረው መሠረተ አሳብ ላይ ያተኩራል። እንደግሪኩ ስያሜ መጽሐፉ የሚያተኩረው በተለያዩ ነገሮች «አጀማመር» ላይ ነው።

| |
|---|
| 28ኛ ጥያቄ፥ ከዚህ ቀደም ኦሪት ዘፍጥረትን በግል ካነበብከው በመነሣት አጀማመራቸው በመጽሐፉ የሆነ የተለያዩ ነገሮችን ዘርዝር። |

በዘፍጥረት ውስጥ የቀረውን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍላችንን ለመረዳት በጣም ጠቃሚ የሆኑ የብዙ ነገሮችን አጀማመር እንመለከታለን። ለምሳሌ፡- የፍጥረታትን አጀማመር እንመለከታለን። እግዚአብሔር ፈጣሪ ስለሆነ እርሱ የፍጥረታት ሁሉ ባለቤትና ተቆጣጣሪ ነው። በዘፍጥረት ውስጥ የወንድና የሴትን፥ የጋብቻን፥ የኃጢአትን፥ ስለ ኃጢአት የሚቀርብ መሥዋዕት፥ የተለያዩ ከተሞችን፥ የነፍስ ግድያን፥ የሥልጣኔ፥ የነገድና የጎሣዎችን፥ የተለያዩ ቋንቋዎችን አጀማመር፥ ወዘተ እናያለን። አብዛኛዎቹም በኦሪት ዘፍጥረት በመጀመሪያዎቹ 11 ምዕራፎች ውስጥ ይገኛሉ።

ከብሉይ ኪዳን ታሪክ አንጻር ስናየው ግን በጣም አስፈላጊ ክስተት የሆነው የእስራኤል ሕዝብ አጀማመር ነው። የኦሪት ዘፍጥረት አብዛኛው ክፍል (ምዕራፍ 12-50) ስለ እስራኤል ሕዝብ አጀማመር የሚናገር ነው። ይህም ሕዝብ እግዚአብሔር የመረጠው ነው።

## የኦሪት ዘፍጥረት ጸሐፊ

| |
|---|
| 29ኛ ጥያቄ፥ሀ) የኦሪት ዘፍጥረት ጸሐፊ እንደሆነ በይበልጥ የሚገመተው ማን ነው? ለ) እንደ አንዳንድ ምሁራን አስተሳሰብ ዘፍጥረት የተጻፈው እንዴት ነው? (ትም. 2 ክልስ)። ሐ) ሙሴ የሚለውን ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት ተመልክተህ ስለ ሕይወቱ በአጭሩ ጻፍ። መ) ኦሪት ዘፍጥረትን ለመጻፍ ሙሴ የተለየ ብቃት ያገኘው እንዴት ነው? |

በዘመናት ሁሉ ሙሴ ዘፍጥረትን ጨምሮ የፔንታቱክ ጸሐፊ መሆኑ ይገመት እንደነበር ቀደም ሲል ተመልክተናል። ጸሐፊው ሙሴ እንደሆነ በዘፍጥረት ባይጠቀስም እንኳ የቀሩቱ የፔንታቱክ መጻሕፍት ግን ሙሴ እንደጻፈው ያሳያሉ። አምስቱ የሙሴ መጻሕፍት በሙሉ እንደ አንድ ክፍል ስለሚቆጠሩ፥ ዘፍጥረትንም የጻፈው ሙሴ መሆን አለበት። ሙሴ ዘፍጥረትን አልጻፈውም ብለን የምናምንበት አንዳችም ምክንያት የለም።

ይልቁንም ሙሴ በዘፍጥረት ውስጥ የምናገኘውን ነገር ለመጻፍ በተለየ ሁኔታ ተዘጋጅቶ ነበር።

ለአይሁድ በብሉይ ኪዳን ዘመን ከነበሩ እጅግ ታላላቅ ሰዎች አንዱ ሙሴ ነበር። ከግብፅ ባርነት አውጥቶ ወደ ተስፋይቱ ምድር የመራቸው ሙሴ ነበር። ለእስራኤል ሕዝብ ሕግን ለመስጠት እግዚአብሔር የተጠቀመበት ሰው ሙሴ ነበር። አይሁድ የመጀመሪያዎቹን አምስት የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ዘወትር «የሙሴ ሕግ» ብለው የሚጠሩት ስለዚህ ነበር። ሙሴ ነቢይ፥ ካህን፥ ሕግ ሰጭ፥ ፈራጅ፥ አማላጅ፥ እረኛ፥ ተአምራት አድራጊና የአይሁድ ሕዝብ የፖለቲካ መሥራች ነበር።

ሙሴ የተወለደው ሌዊ ከተባለው የእስራኤል ነገድ እግዚአብሔርን ከሚፈሩ ወላጆች ነበር። ነገር ግን የተወለደው እጅግ አስቸጋሪ በሆነ ጊዜ ነበር። የእስራኤል ሕዝብ በግብፃውያን ባርነት ሥር ወድቆ፥ ግብፃውያንም እስራኤላውያን የሆኑ ወንዶች ልጆች ሁሉ በሚወለዱበት ጊዜ እንዲገደሉ ሕግ ያወጡበት ጊዜ ነበር። ግብፃውያን ይህንን ያደረጉበት ምክንያት እስራኤላውያን በቁጥር እጅግ ብዙ ይሆኑና ከዚህ ቀደም ሐይክሶሳውያን እንዳደረጉት ሊገለብጡን ይሆናል ብለው ፈርተው ስለ ነበር ነው። በእምነታቸው ጽናት የሙሴ ወላጆች ሊደብቁት እስከሚችሉበት ጊዜ ድረስ አሳደጉት። ሊደብቁት ከማይችሉበት ጊዜ ላይ ሲደርሱ ግን እግዚአብሔር እንደሚታደገው በመተማመን በዓባይ ወንዝ ዳር አስቀመጡት። የግብፅ መሪ የነበረው የፈርዖን ሴት ልጅ ባገኘችው ጊዜ ወደ ቤቷ ወስዳ እንደ ግብፃዊ አሳደገችው።

የሙሴ ሕይወት እያንዳንዳቸው 40 ዓመታት በሆኑ ሦስት ክፍሎች ሊከፈል ይችላል።

1. 40 ዓመታት በግብፅ - በፈርዖን ቤት ውስጥ፡- በእነዚህ 40 ዓመታት ውስጥ ሙሴ በሁለት የተለያዩ ባሕሎች ትምህርት አደገ። በመጀመሪያ፥ በአይሁድ ሃይማኖትና ከአባቶች በተወረሰ ትምህርት አደገ። ይህ የሆነው ለጊዜውም ቢሆን ያሳድጉት ዘንድ ኃላፊነቱ በተሰጣቸው በእኅቱ ማርያምና በእናቱ ነበር (ዘጸ. 2፡7-10)። ሁለተኛ፥ ሙሴ እንደፈርዖን ልጅ ሆኖ የማደግ ዕድል በማግኘቱ በዚያ ዘመን ሊኖር የሚችለውን ትምህርት ሁሉ ቀስሞ ነበር (የሐዋ. 7፡22 ተመልከት)። ግብፅ በዚያን ዘመን እጅግ የሠለጠነች አገር

ስለነበረች፥ ሙሴ እጅግ የተማረ ሰው ነበር ማለት ነው። እስጢፋኖስ ሙሴ «በቃልና በሥራው ሁሉ የበረታ ሆነ» ይላል።

ሙሴ ይህንን ሁሉ ትምህርት በመቅሰሙ፥እግዚአብሔር በኋላ ዘፍጥረትን ጨምሮ የመጀመሪያዎቹን አምስት የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት እንዲጽፍ ተጠቀመበት። አይሁዳውያን ከነበሩት ወላጆች ስለ ወገኖቹ እንደሰማ ጥርጥር የለውም። ወደ ኋላ ተመልሶ እስከ አዳምና ሔዋን፥ ኖኅ፥ በተለይም አብርሃም፥ ይስሐቅ፥ ያዕቆብና ዮሴፍ ያለውን የሕዝቡን አፈ ታሪኮችን ያውቅ ነበር። በግብፅ ታላላቅ ቤተ መጻሕፍት ስለአለፈው ጊዜ የሚናገሩ ታሪኮችን የማየት ዕድልም ገጥሞት ነበር። ይህ ታሪክ የዓለምን አፈጣጠር፥ በኖኅ ዘመን የነበረውን የጥፋት ውኃ፥ የዓለምን መከፋፈል ወዘተ የሚጨምር ነው። ሙሴ ዘፍጥረትን ለመጻፍ በጣም ብቁ ሰው ነበር።

በእነዚህ 40 ዓመታት ሙሴ እስራኤላዊ እንጂ ግብፃዊ እንዳልሆነ አልዘነጋም ነበር። ካደገ በኋላ አንድ ውሳኔ ለማድረግ ተገደደ። ውሳኔውስ ዓለማዊ የሆነ ዕድል ባለበት በፈርዖን ቤት ለመቆየት? ወይስ እግዚአብሔር የተለዩ የቃል ኪዳን ሕዝቡ አድርጎ ከመረጣቸውና አሁን ባሮች ከሆኑት ሕዝብ ጋር ማበር ይሆን?

30ኛ ጥያቄ፥ ዕብ. 11፡24-26 አንብብ። ሀ) ሙሴ ያደረገው ምርጫ ምን ነበር? ለ) ዛሬ ይህንን ምርጫ ማድረግ ያለብን እንዴት ነው? ምሳሌ ስጥ።

ሙሴ እስራኤልን ከግብፅ ባርነት ነፃ ለማውጣት የተመረጠ መሪ እንደነበር ተረድቶ ነበር (የሐዋ. 7፡25)። ነገር ግን የእግዚአብሔርን ጊዜ ከመጠበቅ ይልቅ በራሱ ኃይል ነፃ ሊያወጣቸው ሞከረ። ስለዚህ አንድን ሰው ከገደለ በኋላ የፈርዖንን ቤት ትቶ ከግብፅ መሸሽ ግድ ሆነበት።

2. 40 ዓመታት በምድያም ምድረ በዳ፡- በሰው አመለካከት የሚቀጥሉት 40 ዓመታት የባከኑ ይመስላሉ። ሙሴ በጣም የተማረ ሰው ቢሆንም በግ ማገድ ጀመረ። በእግዚአብሔር አመለካከት ግን በሙሴ ሕይወት ይህ በጣም አስፈላጊ ጊዜ ነበር። ምድረ በዳውና በግ ማገዱ እግዚአብሔር ሙሴን የእስራኤል ሕዝብ መሪ ወይም እረኛ ለማድረግ የሚያስተምርበት ቦታና ሥራ ነበር። በምድረ በዳው እግዚአብሔር በትምህርቱና በችሎታው የነበረውን ትምክሕት በማስወገድ ሙሴን

ትሑት አደረገው። ሙሴ ትሑት ከሆነና እግዚአብሔር በሕይወቱ እንዲሠራ በእርሱ ብቻ ከታመነ፥ ታላቅ ሥራን ይሠራ ዘንድ የእግዚአብሔር መገልገያ ለመሆን ተዘጋጅቷል ማለት ነው።

31ኛ ጥያቄ፥ ሀ) እግዚአብሔር ሙሴን በኃይል ይገለገልበት ዘንድ ትሑት ሊያደርገው ያስፈለገበት ምክንያት ምንድን ነው ብለህ ታስባለህ? ለ) የእግዚአብሔርን ሕዝብ በምንመራበት ጊዜ በችሎታችንና በእውቀታችን ስለ መመካት ይህ ምን ያስተምረናል? ሐ) ከሙሴ ለ40 ዓመታት በምድረ በዳ መኖር ስለ ቤተ ክርስቲያን አመራር ምን ለመማር ትችላለህ?

3. 40 ዓመታት የእግዚአብሔርን ሕዝብ ከግብፅ ወደ ከነዓን መምራት፡- አንድ ቀን እግዚአብሔር ሙሴን በሚቃጠል ቁጥቋጦ ውስጥ ተገናኘውና ወደ ግብፅ ተመልሶ እስራኤላውያንን ከግብፅ ነፃ በማውጣት እንዲመራቸው ጠራው። ሙሴ ወደ ግብፅ ለመመለስ ቢፈራም፥ በመጨረሻ ከእግዚአብሔር ጋር ተስማማ። እግዚአብሔር ሙሴን በፈርዖን ፊት ስለ እርሱ ሆኖ ይናገር ዘንድ ተገለገለበት። ሙሴ ያደረገው በፈርዖን ቤተ መንግሥት በመሆኑ በፈርዖን ዘንድ እውቅናን ማትረፉ አያጠራጥርም። አሥር ታላላቅ ተአምራዊ መቅሠፍቶችን በግብፅ ላይ በማምጣት እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ነፃ አውጥቶ በሙሴ አማካይነት 40 ዓመታት በምድረ በዳ መራቸው። በእነዚህ 40 ዓመታት ውስጥ እግዚአብሔር ሙሴን ፊት ለፊት ተገናኘው። እግዚአብሔር ለሙሴ ከዘጸአት እስከ ዘዳግም ድረስ የተጻፈውን ሕግ ሰጠው። ሙሴን ኦሪት ዘፍጥረትን፥ ዘጸአትን፥ ዘሌዋውያንን፥ ዘኁልቁንና ዘዳግምን እንዲጽፍ እግዚአብሔር ተጠቅሞበታል። ይህ ሁሉ ቢሆንም እንኳ ሙሴ ለእግዚአብሔር ስላልታዘዘ ወደ ተስፋይቱ ምድር እንዳይገባ ታገደ (ዘኁ. 20፡1-13)። ሕዝቡን እስከ ከነዓን ድንበር ድረስ አደረሳቸው። የተስፋይቱን ምድር በተራራ ጫፍ ላይ ሆኖ ከተመለከታት በኋላ ሞተ።

32ኛ ጥያቄ በቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሕይወት ውስጥ እግዚአብሔር እንዴት ኃጢአትን አክብዶ እንደሚያየው ይህ ምን ያስተምረናል?

## የኦሪት ዘፍጥረት ታሪክ ቅደም ተከተልና አስተዋጽኦ

33ኛ ጥያቄ፥ የሚከተሉትን ጥቅሶች ተመልከት ዘፍ. 2፡4፤ 5፡1፤ 6፡9፤ 10፡1፤ 11፡10፤ 11፡27፤ 25፡12፤ 25፡19፤ 36፡1፥ 9፤ 37፡2። ሙሴ:- «የ.....ታሪክ ይህ ነው» የሚላቸውን የተለያዩ ነገሮችን ዘርዝር።

ሙሴ ኦሪት ዘፍጥረትን በሚጽፍበት ጊዜ ግልጽ የሆነ አስተዋጽኦ ነበረው። መጽሐፉን ያቀናበረው «የ...-ይህ ነው» በሚሉት ቃላት ዙሪያ ነበር። ብዙ ምሁራን ይህንን አከፋፈል የኦሪት ዘፍጥረትን አስተዋጽኦ ለመንደፍ ይጠቀሙበታል።

1. መግቢያ:- የነገሮች ሁሉ አፈጣጠር (ዘፍጥ. 1፡1-2፡3)
2. ከአይሁድ አባቶች በፊት የነበረው ዘመን (ዘፍ. 2፡4-11፡26)
    - ሀ) የሰማይና የምድር መፈጠር ታሪክ (ዘፍ. 2፡4-4፡26)
    - ለ) የአዳም ትውልድ እና የልጆቹ ታሪክ (ዘፍ. 5፡1-6፡8)
    - ሐ) የኖኅ ታሪክ (ዘፍ. 6፡9-9፡29)
    - መ) የሴም፥ የካምና የያፌት ታሪክ (ዘፍ. 10፡1-11፡9)
    - ሠ) የሴም ትውልድ ታሪክ (ዘፍ. 11፡10-26)
3. የአይሁድ አባቶች ዘመን (ዘፍ. 11፡27-50)
    - ሀ) የታራ ትውልድ ታሪክ (ዘፍ. 11፡27-25፡11)
    - ለ) የእስማኤል ትውልድ (ዘፍ. 25፡12-18)
    - ሐ) የይስሐቅ ትውልድ ታሪክ (ዘፍ. 25፡19-35፡29)
    - መ) የዔሳው ትውልድ ታሪክ (ዘፍ. 36፡1-37፡1)
    - ሠ) የያዕቆብ ትውልድ ታሪክ (ዘፍ. 37፡2-50፡26)

ሙሴ ኦሪት ዘፍጥረትን በዚህ ዓይነት ቢያቀናብረውም ለማስታወስ ቀላል የሆነ ሌላ የቅንብር መንገድ አለ። የሚከተለውን አስተዋጽኦ እየደጋገምህ አጥና ወይም በቃልህ ያዝ:-

1. ከአይሁድ አባቶች በፊት የነበረው ዘመን (ዘፍ. 1-11)

ሀ. ፍጥረት (ዘፍ. 1-2)

ለ. የሰው ልጅ በኃጢአት መውደቅ (ዘፍ. 3-5)

ሐ. የጥፋት ውኃ በዓለም ላይ (ኖኅ) (ዘፍ. 6-9)

መ. የባቢሎን ግንብና የሰው ዘር መለያየት (ዘፍ. 10-11)

2. የአይሁድ የእምነት አባቶች ዘመን (ዘፍ. 12-50)

ሀ. አብርሃም (ዘፍ. 12-25)

ለ. ይስሐቅ (ዘፍ. 24-26)

ሐ. ያዕቆብ (ዘፍ. 27-36)

መ. ዮሴፍ (ዘፍ. 37-50)

ከዚህ በላይ ባለው አስተዋጽኦ ውስጥ ሁለት ነገሮችን ልብ በል:- በመጀመሪያ፥ ዘፍጥረት በሁለት ዓበይት ክፍሎች፥ ማለትም በዘፍጥረት 1-11 እንዲሁም በዘፍጥረት 12-50 እንደተከፈለ ልብ በል። የመጀመሪያው ክፍል የሚናገረው ስለ ጥንት ዘመን ሲሆን፥ ፍጥረታትን የመፍጠር ተግባር የተፈጸመው መቼ እንደሆነና ይህ ክፍለ ዘመን ምን ያህል ዓመታት እንደፈጀ ለማወቅ አንችልም። ዘፍ. 12-50 ደግሞ የሚናገረው ስለ አይሁድ ሕዝብ መመሥረትና ያንን ሕዝብ ስለ ጀመሩት አራቱ የእስራኤል አባቶች ታሪክ ነው።

ሁለተኛ፥ እያንዳንዱ ክፍል በአራት ንዑሳን ክፍሎች መከፈሉን ልብ በል። ከዘፍ. 1-11 ያለው የመጀመሪያው ክፍል ፍጥረትን፥ ውድቀትን፥ የጥፋት ውኃንና የባቢሎንን ግንብ የሚያጠቃልሉ አራት ክፍሎች አሉት። ከዘፍ. 12-50 ባለው ክፍል ደግሞ ትኩረት የተሰጣቸው አራት ዋና ዋና ሰዎች አሉ። ይህንን የዘፍጥረትን አስተዋጽኦ ብትከተል በመጽሐፉ ውስጥ የሚገኘውን ታሪክ ለማስታወስ ይረዳሃል።

## የኦሪት ዘፍጥረት ልዩ ባሕርያት

በኦሪት ዘፍጥረት ውስጥ መጽሐፉን የበለጠ ለመረዳት ማዕከላዊ የሆኑና ሙሴ ያካተታቸው አንዳንድ ልዩ ነገሮች አሉ።

1. ዘፍጥረት፥ እግዚአብሔር ከሰዎች ጋር ባለው ግንኙነት ዓላማውን ወደ ፍጻሜ ብዙ ጊዜ ለማድረስ ከተለመደው ባሕላዊ ሁኔታና ተግባር

ተቃራኒ በሆነ አቅጣጫ እንደሚጓዝ ያሳያል። ይህ በተለይ የታየው እግዚአብሔር ከበኩሩ (ከመጀመሪያው ልጅ) ይልቅ ሁለተኛውን በመምረጡ ነው። በኢትዮጵያ ውስጥ እንዳሉት በርካታ ባሕሎች አይሁድ የመጀመሪያ ልጅ ልዩ እንደሆነ በማመን፥ ከአባቱ ንብረት የሚበዛውን ክፍል መውረስ እንዳለበት ይስማሙ ነበር። እግዚአብሔር ግን በዚህ ሰው ሠራሽ ባሕል ራሱን አልወሰነም። ለምሳሌ፡- በዘፍጥረት ውስጥ እግዚአብሔር ከቃየን ይልቅ ሴትን፥ ከያፌት ይልቅ ሴምን፥ ከእስማኤል ይልቅ ይስሐቅን፥ ከዔሳው ይልቅ ያዕቆብን፥ ከቀሩት ወንድሞቻቸው ይልቅ ይሁዳንና ዮሴፍን፥ ከምናሴ ይልቅ ኤፍሬምን ሲመርጥ እንመለከታለን። ይህ ሁሉ የሚያስተምረን እግዚአብሔር በእኛ ባሕላዊ ግንዛቤ መሠረት ብቻ ለመሥራት የሚወሰን አለመሆኑን ነው። ይልቁንም ከእኛ ጋር ባለው ግንኙነት ሉዓላዊ ነው። የተለያዩ ግለሰቦችን የሚመርጠውና በአንዳንዶቹ በኃይል የሚሠራው በሌሎቹ ደግሞ ያንኑ ያህል በኃይል የማይሠራው እግዚአብሔር ራሱ ነው። ይህም እግዚአብሔር በሕይወታችን ላይ ባለው ኃይልና የበላይ ተቆጣጣሪነት ከፍተኛ አድናቆትን እንድንሰጠው የሚያደርግ እንጂ በአእምሮአችን ውስጥ ቅንዓትን የሚፈጥር መሆን የለበትም።

| |
|---|
| 34ኛ ጥያቄ፥ ሀ) ብዙ ክርስቲያኖች ሌሎች ክርስቲያኖች ባለጸጎች መሆናቸውን ወይም እግዚአብሔር ከእነርሱ ይልቅ በኃይል እየተጠቀመባቸው መሆኑን ሲገነዘቡ የሚቀኑት ለምንድን ነው? ለ) ሕይወታችንን ለእግዚአብሔር ዕቅድ አሳልፎ ስለመስጠት የሚያስተምረን ነገር ምንድን ነው? ሐ) በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በጣም አስፈላጊው ነገር፥እግዚአብሔር ለሰጠን ስጦታዎችና ችሎታዎች ወይም ሥራዎች ታማኝ መሆን ነው፥ ወይስ በሰዎች ላይ ታላቅ መሪ መሆን? መልስህን አብራራ። |

2. በኦሪት ዘፍጥረት ውስጥ ተምሳሌታዊ ትርጉም ያላቸው አንዳንድ ቁጥሮች ይገኛሉ። የሚከተሉትን ቁጥሮች ተመልከት፡-

ሀ) አሥር - በኦሪት ዘፍጥረት ውስጥ አሥር ዋና ዋና ክፍሎች አሉ፤ (አሥር ጊዜ «የ ... ይህ ነው» ታሪኮች) እንዲሁም በዘፍጥረት 5 ና 11 «አሥር» ትውልዶችን የሚጠቅሱ ትንተናዎች እናገኛለን»። ለአይሁድ አሥር የምሉዕነት ተምሳሌት ነው።

ለ) ሰባት - ሰባት የፍጥረታት ሥራ የተከናወኑባቸው ቀናት ከመኖራቸውም፥ በምዕራፍ 4 ውስጥ በሚገኘው የትውልዶች ታሪክ ውስጥ የሚገኙ ሰባት ስሞች፥ በጥፋት ውኃ ታሪክ ውስጥ የሚገኙ በርካታ ሰባት ቁጥሮች፥ለአብርሃም የተገቡ ሰባት ቃል ኪዳኖች፥ በግብፅ ውስጥ የደረሱ ሰባት የጥጋብና ሰባት የራብ ዓመታት እናገኛለን እንዲሁም 70 (7 ጊዜ 10) የኖኅና የያዕቆብ ዝርያዎች ናቸው። ሰባት ብዙ ጊዜ የፍጹምነት ምሳሌ ነው።

ሐ) አሥራ ሁለት - የያዕቆብና የእስማኤል ነገዶች እያንዳንዳቸው አሥራ ሁለት ነገዶች ነበሩ (ዘፍ. 25፡16፤ 49፡28)።

መ) አርባ፡- በጥፋት ውኃ ታሪክ ውስጥ የተለያዩ የ40 ቁጥር ክፍፍሎች እናያለን (ዘፍ. 6-9)። በኋላም እስራኤላውያን 40 ዓመታት በምድረ በዳ እንደተንከራተቱ እናነባለን።

አንድ ሰው ብሉይ ኪዳንን በሚያጠናበት ጊዜ እነዚህ ቁጥሮች ለአይሁድ የተለዩ እንደሆኑ ግልጽ እየሆነለት ይመጣል። ለምሳሌ 40 ቁጥር የፍርድና የፈተና ጊዜ ይመስላል (ለምሳሌ፡- ኢየሱስ በምድረ በዳ ለ40 ቀናት ተፈትኖአል)። ሰባት ማለት ደግሞ የተሟላ ወይም ፍጹም ማለት ነው፤ (ለምሳሌ፡- በዮሐንስ ራእይ መንፈስ ቅዱስ ሰባቱ የእግዚአብሔር መናፍስት ተብሎ ተጠርቷል)።

3. በዮሐንስ ራእይ የመጨረሻ ምዕራፎች የሚገኙት በተለይም መንግሥተ ሰማያትን የሚገልጡት ሥዕላዊ መግለጫዎች ከኦሪት ዘፍጥረት የመጀመሪያ ሦስት ምዕራፎች ስለ ዔደን ገነት ከተነገሩ መግለጫዎች የተወሰዱ መሆናቸው ትኩረትን የሚስብ ነው። እነዚህ መጻሕፍት የተጻፉት በ1500 ዓመታት ልዩነት መካከል ቢሆንም ይህን የመሰለ ግንኙነት በመካከላቸው መታየቱ፥ እግዚአብሔር የመጽሐፍ ቅዱስ ሁሉ ጸሐፊ መሆኑን የሚያሳይ ነው።

## የኦሪት ዘፍጥረት ዋና ዓላማ

የመጽሐፍ ቅዱስን አጠቃላይ ዓላማ ብንመለከት፥ ኢየሱስ ክርስቶስን መግለጥ ነው ለማለት እንችላለን። እርሱ «የእግዚአብሔር ቃል» ነው (ዮሐ. 1፡1-4፤ ዕብ. 1፡1-3)። «ኢየሱስ ክርስቶስ በብሉይ ኪዳን ተሰውሮአል፤ በአዲስ ኪዳን ግን ተገልጦአል» የሚል አንድ አባባል አለ።

በሌላ አባባል የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት በትንቢቶች አማካይነት የኢየሱስን መምጣት አሻግረው ተመለከቱ። እንዲሁም በሰዎች፥ በድርጊቶችና በነገሮች ሁሉ ውስጥ የመሢሑ መምጣት ሥዕላዊ መግለጫ ነበር። ስለሆነም ከኦሪት ዘፍጥረት ጀምሮ የኢየሱስ ክርስቶስን መገለጥ አጀማመር እናያለን። በዘፍጥረት ስለ ኢየሱስ የተነገሩ ትንቢቶችን አጀማመር እንመለከታለን። በአንዳንድ ታሪኮች ውስጥም የተደበቁ የኢየሱስ ተምሳሌቶች ወይም ሥዕላዊ መግለጫዎች አሉ። ብሉይ ኪዳንን ስናጠና እነዚህም ትንቢቶችና አምሳያዎች መፈለግ አለብን። ይህ ከኦሪት ዘፍጥረት ጀምሮ እስከ ዮሐንስ ራእይ የሚቀጥል «የደኅንነት መስመር» በመባል ይታወቃል።

ነገር ግን ሙሴ ፔንታቱክን የጻፈበት ዋና ዓላማ በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር ከእስራኤል ሕዝብ ጋር ያደረገውን «ቃል ኪዳን» ለመግለጥ ነበር። ፔንታቱክና መጽሐፍ ቅዱስን ለመረዳት መሠረታዊ የሆነው አሳብ ይህ ቃል ኪዳን ነው፤ ስለዚህ የኦሪት ዘፍጥረት ማዕከላዊ እውነቶች የሚያተኩሩት ቃል ኪዳንን በሚመለከት አሳብ ላይ ነው። ዘፍጥረት 1-11 ከተለዩ ሕዝቦች ጋር ቃል ኪዳን ያስፈለገበትን ምክንያት ይናገራል። የሰው ልጅ በአጠቃላይ ፈጣሪውን ክዶ ኃጢአትን እንዴት እንደመረጠ ይናገራል። ዘፍ. 12-50 ደግሞ እግዚአብሔር ከአንድ ሰውና ከቤተሰቡ ጀምሮ አይሁድ ተብሎ የተጠራ አንድን የተለየ ሕዝብ እንዴት እንደመረጠ ይገልጻል። እግዚአብሔር ዓለምን ወደ ራሱ ለመመለስ የፈለገው በእነርሱ በኩል ነበር።

| |
|---|
| 35ኛ ጥያቄ፥ ሀ) በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ያለው የቃል ኪዳን አሳብ ዛሬ በቤተ ክርስቲያን ወይም በአዲስ ኪዳን የሚታየው እንዴት ነው? ለ) የእስራኤል ሕዝብና የቤተ ክርስቲያን ዓላማ የሚመሳሰለው እንዴት ነው? ሐ) እግዚአብሔር አብርሃምን በመረጠው ጊዜ የነበረውን ዓላማ ዛሬ ቤተ ክርስቲያንህ እንዴት እየፈጸመችው ነው? |

5ኛ ቀን፡-

የዚህን ሳምንት ትምህርት ከልስና ለሳምንታዊው ስብሰባ ዝግጅት ይረዳህ ዘንድ የውይይት ጥያቄዎችን በመመልከት ተዘጋጅ።

ሳምንታዊ የስብሰባ ጊዜ

1. ሳምንታዊ የአምልኮ ጊዜ

2. ጸሎት

3. የትምህርቱ ክለሳ

4. ውይይት

ሀ. 1)ክርስቲያኖች ፔንታቱክን የጻፈው ሙሴ ነው የሚሉት ለምንድን ነው?

2) አንዳንድ ምሁራን ፔንታቱክን ሙሴ ስለ መጻፉ የሚጠራጠሩት ለምንድን ነው?

3) አስቀድመው በአእምሮአችው የተቀረፁ አስተሳሰቦች ስለ ፔንታቱክ በሚኖራቸው ግንዛቤ ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድረው እንዴት ነው?

4) የተለያዩ ክርስቲያኖች ስለ አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ መሠረታዊ ትምህርቶች አስቀድሞ በአእምሮአቸው ያወቁት አሳብ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኙትን ነገሮች ለመተርጎም እንዴት ተጽዕኖ ያደርግባቸዋል? (ለምሳሌ:- ሕግ፥ ትንቢት፥ ጥምቀት ወዘተ።)

5) ይህ ነገር ብዙም አስፈላጊ ባልሆኑት መሠረታዊ ትምህርቶች ላይ ባለን አመለካከት የበለጠ ትሑታን እንድንሆን እንዴት ይመራናል?

ለ. 1) በፔንታቱክ ውስጥ የሚገኙ አራት የተለያዩ ዓይነት ሥነ-ጽሑፎች ምንድን ናቸው?

2) ስለ እያንዳንዱ ዓይነት ከመጽሐፍ ቅዱስ ምሳሌ ስጥ።

3) ከኦሪት ዘፍጥረት ውስጥ ታሪካዊ የሆነ አንድ ክፍል ምረጥ። የአተረጓጎም ሕግጋት በዚህ ክፍል ላይ ተግባራዊ የሚሆኑት እንዴት ነው?

ሐ. 1) በብሉይ ኪዳን ውስጥ የሚገኙ የተለያዩ ሕግጋት የትኞቹ ናቸው? አንዳንድ ምሳሌዎችን ጥቀስ።

2) የብሉይ ኪዳንን ሕግጋት በኢትዮጵያ ውስጥ ከሚገኙ የመንግሥትና ልዩ ልዩ ሃይማኖታዊ ሕግጋት ጋር አወዳድር። ተመሳሳይነታቸውንና ልዩነታቸውን ግለጽ።

3) የብሉይ ኪዳን ሕግ ዓላማ ምንድን ነው?

4) በዚህ ዘመን ያሉ አንዳንድ ክርስቲያኖች አንዳንድ የብሉይ ኪዳን ሕግጋትን ዓላማ በተሳሳተ መንገድ የሚረዱት እንዴት ነው?

5) ሕግን የመተርጎሚያ መመሪያዎችን ተጠቅመህ ዘጸአ. 20፡3-17ን ተርጉም።

6) ዛሬ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሕግጋት ዓላማ ምንድን ነው?

7) እነዚህ ሕግጋት በተሳሳተ መንገድ ወደ «ሕግ አጥባቂነት» ሊያመሩ የሚችሉት እንዴት ነው?

መ. 1) አሪት ዘፍጥረትን በመጻፍ ሙሴ ብቃት ያለው ሰው የሆነው ለምንድን ነው?

2) እግዚአብሔር መሪዎችን ለማዘጋጀት ስለሚጠቀምበት መንገድ ከሙሴ ሕይወት ውስጥ ከእያንዳንዱ የ40 ዓመታት ክፍፍል ምን እንማራለን?

ሠ. 1) እግዚአብሔር ለአይሁዳውያን ባሕል ተቃራኒ በሆነ መንገድ በመሄድ በኩር ያልሆኑትን ወንዶች ልጆች የመረጠበት ምክንያት ምን ይመስልሃል?

2) እግዚአብሔር ዛሬም ቢሆን በሕይወታችንና በቤተ ክርስቲያናችን ውስጥ በሚሠራው ሥራ ለባሕላችን ተቃራኒ በሆነ መንገድ የሚሄድበትን አንዳንድ ሁኔታ ግለጽ።

ረ. 1) በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ያለው የቃል ኪዳን ጉዳይ ዛሬ በቤተ ክርስቲያን ወይም በአዲስ ኪዳን ውስጥ የሚታየው እንዴት ነው?

2) የእስራኤል ሕዝብና የቤተ ክርስቲያን ዓላማ የሚመሳሰለው እንዴት ነው?

3) እግዚአብሔር አብርሃምን በመረጠው ጊዜ የነበረውን ዓይነት ዓላማ ዛሬ ቤተ ክርስቲያንህ በምን አኳኋን እየፈጸመችው ነው?

5. ጸሎት

# ትምህርት 4

## 1ኛ ቀን:- ዘፍጥረት 1-11

በዚህ ሳምንት የአሪት ዘፍጥረትን ትምህርት በቀጥታ ወደ ማየት እናዘነብላለን። በየዕለቱ ተማሪው ከአሪት ዘፍጥረት የተወሰኑ ክፍሎችን እንዲያነብ መመሪያ ይሰጠዋል። ስለዚህ ጥናትህን ከመቀጠልህ በፊት ለየዕለቱ የተሰጠህን ክፍል አንብብ። በኮርሱ (በትምህርቱ) መጨረሻ የተሰጠህን የንባብ ክፍል በሙሉ አንብበህ ስለ መጨረስህ ትጠየቃለህ። የዚህ ኮርስ (ትምህርት) ጥናት አንዱ ግብ ተማሪዎች ብሉይ ኪዳንን በሙሉ በቅደም ተከተል እንዲያነቡ ለማድረግ ነው።

| 1ኛ ጥያቄ ዘፍጥረት 1-11 አንብበህ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልስ:- |
|---|

ሀ) በስድስት ቀናት ውስጥ በእያንዳንዱ ቀን ምን እንደተፈጠረ ከምዕራፍ 1 ዘርዝረህ ጻፍ። ለ) ከምዕራፍ 2 በባልና ሚስት መካከል ስለሚኖረው ግንኙነት ምን እንማራለን? ሐ) ከምዕራፍ 3-11 ኃጢአት በዓለም ላይ ያመጣው ነገር ምንድን ነው? መ) የእነዚህን ምዕራፎች ዋና ዋና ትምህርቶች ዘርዝር። ሠ) ከእነዚህ ምዕራፎች ስለ እግዚአብሔር የምንማራቸውን ነገሮች ጥቀስ። ረ) ከእነዚህ ምዕራፎች ስለ ሰው የምንማራችውን ዋና ዋና ትምህርቶች ጥቀስ። ሰ) ከእነዚህ ምዕራፎች ስለ ደኅንነትና በእምነት ስለመራመድ የምንማራቸውን ዋና ዋና ትምህርቶች ጥቀስ። ሸ) ከእነዚህ ምዕራፎች ለመረዳት የሚያስቸግሩ የተለያዩ ነገሮችን ጥቀስ።

## 2ኛ ቀን:-

መጽሐፍ ቅዱስ የሳይንስ ማስተማሪያ ወይም የታሪክ መጽሐፍ አይደለም። መጽሐፍ ቅዱስ ሳይንስንም ሆነ ታሪክን የሚመለከት መረጃ የያዘ ቢሆንም ዓላማው ግን ይህ አይደለም። የመጽሐፍ ቅዱስ ዓላማ እግዚአብሔር ራሱንና ፈቃዱን ለሰው ልጅ መግለጥ ነው። እግዚአብሔር ዛሬም ቢሆን ለሰው ልጆች የሚናገርበት ዋናው መንገድ መጽሐፍ ቅዱስ ነው። አንዳንዱ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት መረጃ ሳይንስንና ታሪክን የሚመለከት ጉዳይ ቢኖረውም፥ ሳይንስና ታሪክ መርምረው ያገኙት አብዛኛው ነገር በመጽሐፍ ቅዱስ አልተካተተም። ሆኖም መጽሐፍ ቅዱስ

የገለጠው ነገር ሁሉ በሳይንቲስቶችና በታሪክ አዋቂዎች ዛሬ ባይታመን እንኳ፥ ሊታመንና ተቀባይነት ሊያገኝ ይገባል። ክርስቲያኖች እንደመሆናችን ከሰዎች አስተሳሰብና አመለካከት ይልቅ የእግዚአብሔርን ቃል መምረጥ አለብን።

## ዘፍጥረት 1-2 የዓለም አፈጣጠር

እንደምናውቀው ዘፍጥረት 1፡1 እንደ ዮሐ. 1፡1 ወደ ጊዜና ወደ ታሪክ መጀመሪያ ይመልሰናል። ይህ የእግዚአብሔር መጀመሪያ ሳይሆን፥ የተፈጠሩ ነገሮች ሁሉ መጀመሪያ ነው። እግዚአብሔር ዘላለማዊ ስለሆነ መጀመሪያ የለውም።

ዘፍጥረት 1-2 የፍጥረታት ታሪክ አጠር ባለ መልክ አጠቃልሎ ያቀርበዋል። ዘፍጥረት 1 ፍጥረትን ሁሉ በመገምገምና በእያንዳንዱ ቀን የተፈጠረውን ነገር በመናገር የፍጥረታትን ታሪክ ያሳየናል። ከፍጥረታት ሁሉ በመጨረሻ የተፈጠረው የሰው ልጅ ምን ያህል ከሁሉ የላቀ ፍጡር መሆኑንም ያመለክታል። ዘፍጥረት 2 የሚያተኩረው ወንድና ሴት ሆኖ በተፈጠረው በሰው ልጅ ላይ ሲሆን፥ ይኖርበት ዘንድ ስለተዘጋጀለት ዔደን ተብሎ ስለሚጠራው ስፍራም ይናገራል።

በዘፍጥረት 1 እግዚአብሔር ነገሮች ሁሉ እንዴት እንደተፈጠሩ ለማሳየት አይፈልግም። ለምሳሌ መላእክት ወይም ሰይጣን የተፈጠሩት እንዴትና መቼ እንደሆነ የሚናገር ነገር የለም። ይልቁንም በቀላል ቋንቋ እግዚአብሔር የሁሉ ነገር ፈጣሪ እንደሆነ ተገልጧል። ስለዚህ የተፈጠሩ ነገሮች በሙሉ የፈጣሪያቸው የእግዚአብሔር ንብረት ናቸው።

> 2ኛ ጥያቄ፥ ሀ) እግዚአብሔር ፈጣሪያችን ስለሆነ ስለ እርሱ ሊኖረን የሚገባ አመለካከት ምን ዓይነት ነው? ለ) እግዚአብሔር ፈጣሪያችንን ልናከብር የምንችልባቸውን መንገዶች ግለጥ።

በዓለም ላይ የምናያቸው ነገሮች በሙሉ ስለተገኙባቸው መንገዶች የሚናገሩ አምስት የተለያዩ አመለካከቶች አሉ። ከእነዚህ መካከል ሁለቱ መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል መሆኑን የማይቀበሉ ክርስቲያን ያልሆኑ ሰዎች አመለካከቶች ናቸው።

ክርስቲያን ባልሆኑ ሰዎች የሚንፀባረቁ ሁለት አመለካከቶች

1. የተፈጠሩ ነገሮች በሙሉ ፈጣሪዎቻቸው የሆኑ የተለያዩ አማልክት የሥራ ውጤቶች ናቸው። ይህ አመለካከት እውነተኛውን አምላክ የማያውቁ የጥንት ሰዎች የሚያንፀባርቁት ነው። ለምሳሌ:- በብዙ አማልክት የሚያምኑ አንዳንድ ጣዖት አምላኪዎች:- ምድር የፀሐይ አምላክና የሴት ጨረቃ አምላክ ልጅ ነው ብለው ያምኑ ነበር። በተጨማሪም የሰው ልጅ ከአማልክት መካከል የአንዱ ዝርያ ነው ብለው ያምኑ ነበር። ይህም የቀድሞዎቹ ባቢሎናውያን፥ ግሪኮች፥ ሮማውያንና ከነዓናውያን አመለካከት ነበር። ዛሬም የብዙ አፍሪካውያን አመለካከት ሲሆን ሂንዱይዝም በተባለው በምሥራቃውያን እምነት ውስጥም የሚታይ ነው።

እግዚአብሔር የፍጥረታትን ታሪክ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንዲካተት ያደረገበት አንዱ ምክንያት እርሱ ብቻ የሁሉ ነገር ፈጣሪ እንደሆነ ለማሳየት ነው። ዛሬ እግዚአብሔር እስራኤላውያንንና እኛን አንድ እውነተኛ አምላክ ብቻ እንዳለ ሊያስተምረን ይፈልጋል። እግዚአብሔር «በምድርና በሰማይ ያሉ» ነገሮች ሁሉ ፈጣሪ ነው። ለሰው ልጅ ትክክለኛ ቦታው ራሱን ለእግዚአብሔር አሳልፎ በመስጠት ፈጣሪውና ጌታው መሆኑን ተረድቶ እርሱን በማክበር መኖር ነው።

2. የተፈጠሩ ነገሮች በሙሉ የተፈጥሮ «አዝጋሚ ለውጥ» (ኢቮሉሽን) ውጤቶች ናቸው። ይህ ፅንሰ አሳብ ብዙዎቻችን በመንግሥት ትምህርት ቤት የተማርነው ነው። አዝጋሚ ለውጥ እንዴት እንደተፈጸመ የሚያስረዱ በርካታ የተለያዩ ንድፈ አሳቦች ቢኖሩም፥ ይህ አመለካከት የሚያስተምረው ከብዙ ቢሊዮን ዓመታት በፊት አንድ ታላቅ ፍንዳታ ተፈጽሞ ፀሐይ፥ ከዋክብት፥ ሌሎች ፕላኔቶች፥ ወዘተ. ተፈጠሩ። በአንድ ባልታወቀ ምክንያት ሕይወት መጀመሪያ ከተፈጠረው ፕላኔት ይወጣ ጀመር። ከዚያም በመጀመሪያ ዕፀዋት፥ ቀጥሎም እንደ አሜባ ያሉ በጣም ጥቃቅን እንስሳት ተገኙ። እነርሱም ቀስ በቀስ እንቁራሪት ወደ መሳሰሉ እንስሳት ተለወጡ። እነዚያ ደግሞ ቀስ በቀስ ወደ ጡት አጥቢ እንስሳት ተለወጡ በማለት ነው፤ ስለዚህ በቀላል አማርኛ ሰው ከፍተኛው የአዝጋሚ ሂደት ለውጥ ውጤት ነው። ይህ አመለካከት ለእግዚአብሔርና እርሱ ለፈጠራቸው ፍጥረታት ሁሉ ምንም ቦታ አይሰጥም።

ሕዝ. 28፡11-17)። በእግዚአብሔርና በሰይጣን መካከል በተደረገው ጦርነት የመጀመሪያዋ ምድር ወደ ባዶነትና ጨለማ ተለወጠች በማለት ግምታዊ አስተሳሰባቸውን ይሰጣሉ።

ስለዚህ ይህ አመለካከት ያላቸው ሰዎች፥ ዘፍጥረት ምዕራፍ አንድን ምርኩዝ በማድረግ እግዚአብሔር ዓለምን እንደገና ጠግኖአል ወይም አድሶአል በማለት ያስተምራሉ።

ይህ አመለካከት ሙሉ በሙሉ እንደማይሆን አድርጎ ለመቃወም ባይቻልም ሁለት ዓለማት ስለ መፈጠራቸው መጽሐፍ ቅዱስ የሚሰጠው ማስረጃ የለም።

3. ዘፍጥረት 1 የሚናገረው እግዚአብሔር ዛሬ በዓለም ላይ የሚገኙትን ነገሮች ሁሉ እንዴት እንደፈጠረ ነው። ቁሳዊ የሆኑትን ነገሮች በሙሉ እግዚአብሔር በስድስት ቀናት ውስጥ የፈጠራቸው ናቸው። የተፈጠሩትም ከምንም ነው (ዕብ. 11፡3 ተመልከት)። ይህ አመለካከት በዘመናት ሁሉ አብዛኛዎቹ ክርስቲያኖች ያመኑበት ሲሆን ከሌሎች ሁሉ በተሻለ ሁኔታ ከመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ጋር የሚስማማ ነው።

ማንም ሰው እነዚህን አመለካከቶች «ማረጋገጥ» አይችልም። ይልቁንም ክርስቲያኖችም ሆኑ ክርስቲያን ያልሆኑ ሰዎች የሚከተሉአቸው እነዚህ አመለካከቶች እምነትን ወይም ሊያዩ የማይችሉትን ነገር መቀበልን ይጠይቃል። የማያምኑ ሰዎችን ሁሉ ማርካት በሚቻልበት መንገድ ክርስቲያኖች ሊገልጹዋቸው የማይችሉዋቸው አንዳንድ ነገሮች ቢኖሩም፥ በዕብ. 11፡3 እንደምናነበው እግዚአብሔር የሁሉ ነገር ፈጣሪ መሆኑን የምንቀበለው «በእምነት» ነው። ይህ ማለት እኛ የእርሱ ፍጥረት ነን። እርሱ ፈጣሪ በመሆኑ በእኛ ላይ ሙሉ ሥልጣን አለው። እኛም ለእርሱ በመገዛት መኖር አለብን።

6ኛ ጥያቄ፥ ሕይወታችንን በሙሉ ለእግዚአብሔር ለመስጠትና እርሱን ሙሉ በሙሉ ለመታዘዝ የምንቸገረው ለምንድን ነው?

እስካሁን ባለን እውቀት አንጻር እግዚአብሔር ዓለምን በስድስት ቀናት እንደፈጠረ ማመን ከሁሉም የሚሻል ነገር ይመስላል። እግዚአብሔር እንደሌለና ነገሮች ሁሉ የአዝጋሚ ለውጥ ውጤቶች እንደሆኑ የሚያምኑ ሰዎችን አጥብቀን መቃወም ያለብን ቢሆንም፥ እኛ

ስለ ፍጥረታት አፈጣጠር ካለን አመለካከት ለየት ያለ እምነት ያላቸውን ክርስቲያኖች መቀበል አለብን። ደኅንነታችን የተመሠረተው ስለ ፍጥረታት ባለን ትክክለኛ አመለካከት ሳይሆን፥ በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ባለን እምነት ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ፍጥረት የሚናገረው ታሪክ እኛ ለማወቅ የምንፈልገውን ነገር ሁሉ የሚያብራራ ሳይንሳዊ ዘገባ አይደለም። የፍጥረት ታሪክ የተገለጠበት ዓላማ እግዚአብሔር ፈጣሪ እንደሆነና እኛ የእርሱ ልዩ ፍጥረቶች እንደሆንን በግልፕ ለማስተማር ነው።

ይሁን እንጂ የእግዚአብሔርን ቃል ትክክለኛነት በምንም ዓይነት ሁኔታ ከመጠራጠር መጠንቀቅ አለብን። የእግዚአብሔርን ቃል ከለወጥንና እርሱ በግልጽ ከሚያስተምረን ነገር የተለየ አመለካከት ካለን፥ መሠረታችንን አጣን ማለት ነው። ስለ ፍጥረት አፈጣጠር መጽሐፍ ቅዱስ የሚሰጠው ትምህርት የተሳሳተ ከሆነ ስለ እግዚአብሔር ማንነት፥ ስለ ኢየሱስ ማንነትና እኛን እንዴት እንዳዳነን፥ ወዘተ. የሚሰጠው ትምህርትም የተሳሳተ ሊሆን ይችላል ማለት ነው። እኛም ሆንን ሌሎች ክርስቲያኖች የምንከተለው ማንኛውም አመለካከት በእግዚአብሔር ቃል ላይ በሚገባ የተመሠረተ መሆን አለበት።

ዘፍ. 1፡1-2 የፍጥረት ታሪክ መግቢያ ነው። በመግቢያው ውስጥ እግዚአብሔር የፍጥረት ሁሉ ምንጭ እንደሆነ ይገልጻል። የቀረው የፍጥረት ሥራም እንዴት እንደተከናወነ የሚገልጽ አስተዋጽኦ ይሰጣል። እግዚአብሔር ምንም ቅርፅ የሌላትን ዓለም ወስዶ ቅርፅ ሰጣት። እንዲሁም ባዶና አንዳች ያልነበረባትን ዓለም ወስዶ በተለያዩ ነገሮች ሞላት። የፍጥረታት ታሪክ እንዴት እንደተደራጀ የሚያሳየውን የሚቀጥለውን ሠንጠረዥ ተመልከት፡-

| ቀን | ቅርፅን ለመስጠት የተሠሩ ነገሮች | ቀን | ምድርን ለመሙላት የተፈጠሩ ነገሮች |
|---|---|---|---|
| 1ኛ ቀን | እግዚአብሔር ብርሃንን ፈጥሮ ከጨለማ ለየው | 4ኛ ቀን | እግዚአብሔር ፀሐይን ጨረቃንና ከዋክብትን ፈጠረ |
| 2ኛ ቀን | እግዚአብሔር በምድር የነበረውንና በጠፈር የነበረውን ውኃ ለየ | 5ኛ ቀን | 1. እግዚአብሔር ባሕርን በልዩ ልዩ እንስሳት ሞላ<br>2. እግዚአብሔር ሰማይን በአዕዋፍ ሞላ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 3ኛ ቀን | 1. እግዚአብሔር በምድር የነበረውን ውኃ ለየና የብስን ሠራ<br>2. በደረቅ ምድርም ላይ ተክል እንዲበቅል አደረገ | 6ኛ ቀን | 1. እግዚአብሔር በየብስ ላይ የሚኖሩ እንስሳትን ፈጠረ<br>2. እግዚአብሔር ሰውን በራሱ አምሳል ፈጠረ። |

ከዚህ ሠንጠረዥ የሚከተሉትን ነገሮች አስተውል:- አንደኛ፥ እግዚአብሔር ሁሉን ነገር የፈጠረባቸው ስድስት ቀናት ነበሩ። ሁለተኛ፥ የፍጥረትን ሥራ የሚመለከቱ ሁለት ዋና ዋና ክፍሎች አሉ። የመጀመሪያው ክፍል እግዚአብሔር ለምድር ቅርፅን እንደሰጠ የሚናገር ሲሆን፥ ሁለተኛው ክፍል ደግሞ እግዚአብሔር የፈጠረውን ነገር በተለያዩ ነገሮች እንደሞላ ይናገራል። ሦስተኛው፥ የሁለቱ ክፍሎች እያንዳንዱ ቀን የተያያዘ ነው። ለምሳሌ:- 1ኛና 4ኛ ቀናት በሰማይ ስላሉ ብርሃናት መፈጠር ይናገራሉ። 2ኛና 5ኛ ቀናት እግዚአብሔር ባሕርንና ጠፈርን ሲያዘጋጃቸውና ሲሞላቸው እናያለን። 3ኛና 6ኛ ቀናት ደረቅ ምድርን የማዘጋጀትና የመሙላት ሥራ የተከናወነባቸው ቀናት ናቸው። ይህም ዓለምን የመፍጠር ሥራ ግልጥ የሆነ ቅንብር ተደርጎለት እንደ ነበር ያሳየናል።

እግዚአብሔር ሰውን በፈጠረ ጊዜ ይህ ሥራ የሥላሴ ተግባር ነበር። በዘፍ. 1፡2 እግዚአብሔር በመንፈስ ቅዱስ ሥራ አማካይነት የመፍጠርን ተግባር እንዳከናወነ እናነባለን። እግዚአብሔር «እንፍጠር» እያለ ራሱን በብዙ ቁጥር ሲጠራ እንመለከታለን (ዘፍ. 1፡26)። ይህንን በተለያዩ መንገዶች መረዳት ቢቻልም፥ እግዚአብሔር ሦስት አካላት አሉት። እነርሱም እግዚአብሔር አብ፥ እግዚአብሔር ወልድ፥ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ሲሆኑ፥ አዲስ ኪዳን በሚሰጠው በዚህ ትምህርት መሠረት ሥላሴ ፍጥረትን በሚመለከት አብረው እንደወሰኑና ሦስቱም በመፍጠር ሥራ ውስጥ እንደተሳተፉ እናያለን።

## የሰው ልጅ መፈጠር

7ኛ ጥያቄ፥ ሀ) በዘፍጥረት 1 ስለ ሰው ልጅ መፈጠር የሚናገሩ ስንት ቁጥሮችን ታገኛለህ? ለ) ስለ ሰው ልጅ አፈጣጠር እግዚአብሔር ይህን የመሰለ ሰፋ ያለ ገለጻ የሰጠው ለምን ይመስልሃል? ሐ) የሰውን ልጅ አፈጣጠር የሚናገረው ታሪክ ስለ ሌሎች አፈጣጠር ከተነገረው ታሪክ

የሚለየው እንዴት ነው? መ) ሰው «በእግዚአብሔር አምሳል» ተፈጠረ ማለት ምን ማለት ይመስልሃል?

አብዛኛው የፍጥረት ታሪክ የሚያተኩረው አዳምና ሔዋን ተብለው በሚጠሩት በመጀመሪያዎቹ ሰዎች መፈጠር ላይ ነው። በዘፍ. 1 ሙሴ፥ እግዚአብሔር ወንድና ሴትን እንዴት እንደፈጠረ ባጭሩ ይገልጣል። ወንድና ሴት ሁለቱም የተፈጠሩት በእግዚአብሔር አምሳል ነው።

ሰው የተፈጠረው በእግዚአብሔር አምሳል ነው ማለት ምን ማለት ነው? ከዚህ ዐረፍተ ነገር በርካታ ጠቃሚ እውነቶችን እንመለከታለን፡-

1. ሰው ከእንስሳት የተለየ ነው። በአንዳንድ በኩል ሲታይ ሰው በሥጋዊ አካሉ ከእንስሳት ጋር የሚመሳሰል ቢሆንም፥ በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠረ ስለሆነ ከእንስሳት የተለየ ነው።

2. ሰው እግዚአብሔር ከፈጠራቸው ፍጥረታት ሁሉ የተሻለ ነው። ከማናቸውም ፍጥረታት ሁሉ በጣም ተፈላጊ ነው።

3. ሰው በእግዚአብሔር አምሳል ተፈጠረ። እግዚአብሔር እንደ እኛ ዓይነት ሥጋዊ አካል ስለሌለው አካላዊ አለመሆኑ ግልጥ ነው። ይልቁንም አምሳልነቱ በሚከተሉት ነገሮች ነው፡-

   ሀ. እግዚአብሔርም ሆነ ሰው ሁለቱም ስብዕና አላቸው። ይህም ማለት ያስባሉ፥ ያዝናሉ፥ ያቅዳሉ።

   ለ. እግዚአብሔርና ሰው ሁለቱም ክፉና ደጉን የመለየት የሥነ-ምግባር እውቀት አላቸው። በመሆኑም ክፉውን ወይም ደጉን የመምረጥ ችሎታ አላቸው። ሰው በመጀመሪያ በተፈጠረበት ጊዜ እንደ እግዚአብሔር ቅዱስ፥ ጻድቅ፥ ወዘተ ነበር።

   ሐ. እግዚአብሔርና ሰው ሁለቱም ገዥዎች ናቸው። እግዚአብሔር በፍጥረቱ ሁሉ ላይ ገዥ ነው። ሰውም የእግዚአብሔር ፍጥረታት ሁሉ ገዥ ነው።

   መ. እግዚአብሔርና ሰው ሁለቱም «መንፈስ» አላቸው። እግዚአብሔር መንፈስ ነው (ዮሐ. 4፡24 ተመልከት)። ሰውም ዘላለማዊ የሆነ መንፈስ አለው።

4. ወንድና ሴት ሁለቱም እኩል የእግዚአብሔር አምሳልነት አላቸው። ወንድ ከሴት የተለየ የእግዚአብሔር አምሳልነት የለውም፤ የእግዚአብሔርን አምሳልነት በተመለከተ ሴትም ከወንድ ያነሰ የአፈጣጠር ልዩነት የላትም።

እኛ ሁላችንም በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠርን ስለሆንን በእግዚአብሔር ፊት ምን ያህል ክብር አለን?

ዘፍ.2 የሚያተኩረው በሰው ልጅ አፈጣጠር ላይ ነው። የመጀመሪያዎቹ ወንድና ሴት አዳምና ሔዋን ይኖሩበት ስለ ነበረው እጅግ ውብ ስፍራ ስለ ዔደን ገነት እናነባለን። እንደተገለጸው ከሆነ ዔደን ገነት መስጴጦምያ አካባቢ የነበረች ስፍራ ትመስላለች። እንዲሁም ሴት እንዴት ከወንድ ጎን እንደተሠራችም በዚህ ምዕራፍ ይናገራል።

በወንድና በሴት የአፈጣጠር ታሪክ እግዚአብሔር ለወንዶችና ለሴቶች ሁሉ በጋብቻ ውስጥ ያለው አሳብ ምን እንደሆነ እንመለከታለን። ሁለቱም በእግዚአብሔር አምሳል ስለተፈጠሩ፥ እኩልነት መኖር አለበት። አንድ ሥጋ ስለሚሆኑ፥ አንድነት መኖር አለበት። ሳይለያዩ እስከሞት ድረስ በአንድነት መቆየት አለባቸው። የቅርብ ጓደኛሞች መሆን አለባቸው። ቅርበታቸው ከተለመደው ቤተሰባዊ አቀራረብ ማለት አባትና እናት ከልጆቻቸው ጋር ካላቸው ግንኙነት እጅግ የበለጠ መሆን አለበት። ወንድ በመጀመሪያ ስለተፈጠረ ሚስት ለባሏ ታዛዥ መሆን ይገባታል።

ባልና ሚስት በኅብረታቸው ውስጥ አንዳችም የተሰወረ ነገር ሳይኖር ሙሉ በሙሉ ግልጥ መሆን አለባቸው። ይህም «ራቁታቸውን ነበሩ፤ አይተፋፈሩም ነበር» ከሚለው ቃል የሚታወቅ ነው።

8ኛ ጥያቄ፥ ሀ) በዘፍጥረት 2 የተገለጸው የጋብቻ ሁኔታ ብዙ ሰዎች በጋብቻ ውስጥ የተለመደ ነው ብለው ከሚያስቡት ነገር በምን ይለያያል? ለ) የአንተ ወይም የወላጆችህ ጋብቻ በዘፍጥረት 2 ለትክክለኛ ጋብቻ ምሳሌነት ከቀረበው ከአዳምና ሔዋን ጋብቻ ጋር እንዴት የነጻጸራል?

## 3ኛ ቀን:- የአዳምና የሔዋን ኃጢአት

9ኛ ጥያቄ፥ ከዘፍ. 3 በሰው መጀመሪያ ኃጢአት በተሳተፉት ላይ የደረሰባቸውን እርግማን ዘርዝር።

ዘፍ. 3 ስለ ሰው የመጀመሪያ ኃጢአት ይናገራል። ይህም በእግዚአብሔር ላይ የፈጸመው የመጀመሪያው ዓመፅ ነበር። እግዚአብሔር በመጀመሪያ አዳምና ሔዋንን ሲፈጥር፥ በሥነ- ምግባር ፍጹም ነበሩ። የኃጢአት ተፈጥሮ ስለሌለባቸው ኃጢአት ሊያደርጉ የሚችሉበት ምክንያት አልነበረም። ምሁራን ይህንን «የንጽሕና ደረጃ» ብለው ይጠሩታል፤ ምክንያቱም በዚህ ጊዜ አዳምና ሔዋን ኃጢአት ምን እንደሆነ እንኳ አያውቁም ነበር። እግዚአብሔር አዳምና ሔዋንን በዔደን ገነት ባኖረ ጊዜ ከፍሬው እንዳይበሉ የከለከላቸው አንድ ዛፍ ነበር። ይህ ፍሬ «መልካሙንና ክፉውን ከሚያስታውቅ ዛፍ» የሚገኝ ነበር።

ሰይጣን በእግዚአብሔር ላይ ያመፀው አስቀድሞ ነበር። አዳምና ሔዋንም በእግዚአብሔር ላይ እንዲያምፁ በማድረግ ፍጥረታትን ሁሉ ሊያበላሽ ቆረጠ፤ ስለዚህ ሰይጣን ወደ ሔዋን ቀረበ። ስለ እግዚአብሔር ትእዛዝ የተምታታ አሳብ እንዲኖራት አደረገ። ከዚህም በኋላ ሔዋንን ትእዛዙን በሰጣት በእግዚአብሔር ዓላማና ባህርይ ላይ እንድትጠራጠር አደረጋት። አዳምና ሔዋን ሁለቱም የተከለከለውን ፍሬ በሉ። በመጀመሪያ የተታለለችውና በኃጢአት በመውደቅ ለእግዚአብሔር ያልታዘዘችው ሔዋን ብትሆንም አዳምም በኃጢአት የወደቀው እያወቀ ነው። እግዚአብሔርን በመታዘዝ ፈንታ ሔዋንን መከተል መረጠ። አንዳንድ ምሁራን፡- ሔዋን በተታለለች ጊዜ አዳም አብሮአት ነበር፤ሆኖም ከስሕተት እንድትርቅ ሊያደርጋት አልፈለገም ይላሉ።

| |
|---|
| 10ኛ ጥያቄ ፥ ኃጢአት በምናደርግበት ጊዜ አዳምና ሔዋን ከሠሩት ኃጢአት ጋር የሚመሳሰለው እንዴት ነው? |

የመጀመሪያው የሰው ልጅ ኃጢአት ፈጣሪ በሆነው እግዚአብሔር ላይ ማመፅ ነበር። ፈጣሪያቸው የሆነው ጌታ ፍሬውን እንዳይበሉ የመከልከል ሙሉ መብት ነበረው፤ ነገር ግን የራሳቸውን ፍላጎት ለማድረግ ስለፈለጉ ዓመፁ። በእያንዳንዱ ኃጢአት ውስጥ ያለው ተመሳሳይ ዝንባሌ ይህ ነው። እያንዳንዱ ኃጢአት በእግዚአብሔር ላይ የሚደረግ ዓመፅ ነው። ለእግዚአብሔር ራስን ባለመስጠት ለትእዛዙ አልገዛም ማለት ነው። ፈጣሪያችን ለሆነው ለእግዚአብሔር ትእዛዛት ራሳችንን ከማስገዛት ይልቅ በራሳችን ሕይወት ላይ ለመሠልጠን የምናደርገው ጥረት ነው።

የመጀመሪያው የአዳምና ሔዋን ኃጢአት ለብዙዎች የሚደርሱ አስጨናቂ ውጤቶችን አስከተለ።

1. አዳምና ሔዋን ከእግዚአብሔር ጋር የነበራቸውን ግንኙነት ወዲያውኑ አቋርጦ ከእግዚአብሔር እንዲደበቁ አደረገ።

2. በአራት ነገሮች ላይ ቅጽበታዊ ፍርድ አመጣ፡-

   ሀ. በእባቡ ላይ አካላዊና ተምሳሌታዊ ፍርድን አመጣ። እባብ ተፈጥሮው ተለውጦ በሆዱ የሚሳብ እንስሳ ሆነ። በእባብ ተመስሎ የቀረበው ሰይጣን ተፈርዶበት የመጨረሻ ሽንፈቱ ተነገረ።

   ለ. ሔዋንና ሴቶች ሁሉ ተፈረደባቸው። ከዚህ የተነሣ ልጅ መውለድ አስጨናቂ ሂደት ሆነ። ሴቶች ከባሎቻቸው ጋር የነበራቸው የእኩልነት ግንኙነት ተለውጦ ለባሎቻቸው የሚገዙ ሆኑ።

   ሐ. አዳምና ወንዶች ሁሉ ተፈረደባቸው። ሥራቸው ቀላልና የሚያስደስት መሆኑ ቀረና የቤተሰቦቻቸውን ሁሉ ፍላጎት ለማርካት በማያቋርጥ ፍልሚያ ውስጥ ገቡ።

   መ. ፍጥረት ተረገመ። የሰው ልጅ ወዳጅ መሆኑ ቀረና ጠላት ሆነ። ለእሾህ፥ አሜከላ፥ ራብ፥ የመሬት መንቀጥቀጥና ሌሎች አጥፊ ነገሮች መከሰቻ ሆነ።

3. የመጀመሪያውን እንስሳ መገደልና በመጨረሻም የሰዎች ሁሉ ሞትን አስከተለ። አንዳንድ ሰዎች እግዚአብሔር «ደም ሳይፈስ ስርየት የለም» (ዕብ. 9፡22) የሚለው መንፈሳዊ መመሪያ የጀመረው በዚህ ጊዜ ነው ይላሉ። እግዚአብሔር ለአዳምና ለሔዋን ራቁትነታቸውን ለመሸፈን ቁርበት ማልበስ ብቻ ሳይሆን፥ ለኃጢአታቸውም እንስሳን ሠዋ። በብሉይ ኪዳን ለጊዜውም ቢሆን ኃጢአቱን ይሸፍን የነበረው የእንስሳ ደም ነበር። በአዲስ ኪዳን ግን ኢየሱስ ለኃጢአት የሚሆን የመጨረሻ መሥዋዕት ሆነ (ዕብ. 9፡22፥ 26-27 ተመልከት)።

4. ከእነርሱ በኋላ በሰው ልጆች ሁሉ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ አስከተለ። አዳምና ሔዋን ከእነርሱ በኋላ ለሚወለዱ ሰዎች በሙሉ ራስ በመሆናቸው በሰው ልጆች ላይ ፍርድን አመጡ። ይህ ፍርድ የሰዎችን ሕይወት በምድር ላይ አስቸጋሪ ከማድረጉ ሌላ ሥጋዊ ሞት የሰው ልጆች ሁሉ የመጨረሻ ዕጣ መሆኑን እርግጠኛ አደረገው። ይህም ማለት ልጆቻቸው ሁሉ በእግዚአብሔር ላይ ያለማቋረጥ

ወደማመፅ የሚወስዳቸውን የኃጢአት ባሕርይ ጭምር ወረሱ ማለት ነው።

5. አዳምና ሔዋንን ከዔደን ገነት እንዲባረሩ አደረጋቸው። ይህ እርምጃ የጸጋም የፍርድም እርምጃ ነው። ከሕይወት ዛፍ ፍሬ ወስደው በመብላት በኃጢአት ለዘላለም እንዳይኖሩ እግዚአብሔር በጸጋና በፍርድ ከዔደን ገነት አባረራቸው።

| |
|---|
| 11ኛ ጥያቄ፥ የእነዚህ ኃጢአቶች ውጤት ዛሬ በሕይወትህ እንዴት ይታያል? |

በአዲስ ኪዳን፥ ክርስቶስ ኃጢአት ያመጣቸውን ነገሮች ማስወገድ ጀምሮ እናያለን። በባልና በሚስት መካከል የነበረው ግንኙነት መስተካከል ነበረበት። በመጨረሻም ዘላለማዊ መንግሥቱ ሲጀመር ይህንን እርግማን ሁሉ እግዚአብሔር እንደሚያስወግድ በዮሐንስ ራእይ ውስጥ እንመለከታለን (ራእ. 21-22)።

ዘፍጥረት 4-11 የኃጢአት በመላው ዓለም መሠራጨት

ከዘፍጥረት 4-11 ባለው ክፍል ውስጥ ሦስት ዋና ዋና ክንዋኔዎች አሉ። አንደኛ፥ አዳምና ሔዋን የመጀመሪያውን ክፉትና ኃጢአት ከሠሩበት ሰዓት ጀምሮ መስፋፋቱንና ከእነርሱ በኋላ የሚመጡትን ዝርያዎቻቸውን በሙሉ ማጥፋቱን ቀጠለ። ሁለተኛ፥ ከአዳም ጀምሮ እስከ አብርሃም ድረስ ያለውን የደኅንነት መስመር ማሳየት ነው። ሦስተኛው፥ እንደ ዓለም ፈቃድ መኖርን ትተው በእግዚአብሔር ፊት በጽድቅ የኖሩ የተለያዩ ሰዎችን ማሳየት ነው።

1. ኃጢአትና ፍርድ በሰው ዘር ላይ እንዴት እንደመጣ ተጠቅሶ እናገኛለን።

በእነዚህ ምዕራፎች ሁሉ የኃጢአትና የሞት ዋና አሳብ እንዴት እንደተጠቀሰ አስተውል።

ሀ. በዘፍ. 4 ቃየን በተገቢው መንገድ ለእግዚአብሔር መሥዋዕትን ማቅረብ እንዴት እምቢ እንዳለ እናነባለን። አንዳንዶች እግዚአብሔር ያልተቀበለው ደም የሌለበት ስለ ነበረ ነው ይላሉ፤ ነገር ግን እግዚአብሔር የቃየንን መሥዋዕት ያልተቀበለበት መሠረታዊ ምክንያት እርሱን የማምለኪያ ትክክለኛ መንገድ

ስላልነበረው ነው። እግዚአብሔር ባዘዘው መሠረት አምልኮውን አላቀርብም አለ። ይህም የመጀመሪያውን ነፍስ ግድያ አስከተለ። ቃየን ወንድሙ አቤልን ገደለ።

**12ኛ ጥያቄ፥ ዛሬ እግዚአብሔርን በተሳሳተ ዝንባሌ ወይም ውስጣዊ አሳብ ማምለክ እንዴት ይቻላል?**

ለ. የቃየንን ዝርያዎች የማያቋርጥ ዓመፅ እንመለከታለን። የቃየን ዝርያዎች ለሥልጣኔ ለእድገትና ለበርካታ ከተሞች መቆርቆር ምክንያት የሆኑ ቢሆንም፥ ብዙ ሚስቶችን ማግባት ጀመሩ። እንዲያውም ላሜሕ አንድ ወጣት ሰው በመግደሉ ጉራውን ነዛ (ዘፍ. 4:23-24)።

** ማስታወሻ:- (ብዙ ሰዎች ቃየን እና ሴት ከየት ሚስት እንዳገኙ በማሰብ ይደነቃሉ። የኦሪት ዘፍጥረት ታሪክ ብዙ ጊዜ ትኩረት የሚያደርገው በወንዶች ልጆች እንጂ በሴቶች ልጆች ላይ በደረሰው አይደለም፤ [ከዘፍ. 5:4]። እንደምንረዳው አዳምና ሔዋን ወንዶች ልጆች ብቻ ሳይሆኑ፥ ሴቶች ልጆችም ነበሯቸው፤ ስለዚህ ቃየንና ሴት የራሳችውን እኅቶች እንዳገቡ መገመቱ ትክክል ነው። ይህ ነገር ከብዙ ዓመታት በኋላ ከግብፅ እስከ ወጡበት ጊዜ ድረስ በእግዚአብሔር የተከለከለ አልነበረም [ዘሌ. 18])።

ሐ. ከአዳም እስከ ኖኅ ያለው የትውልዶች ታሪክ በተተነተነበት-በዘፍ. 5 በተደጋጋሚ የሚነገር አንድ ቃል አለ። ይህም ቃል «ሞት» የሚል ነው። ለበርካታ ዓመታት ቢኖርም እንኳ የሰው ልጅ መጨረሻው ያው ሞት ነው።

መ. በዘፍጥረት 6 የእግዚአብሔር ልጆች የሰውን ሴቶች ልጆች በማግባት ኃጢአት እንደሠሩ እንመለከታለን። ይህ ለመረዳት በጣም አስቸጋሪ የሆነ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ነው፤ ስለዚህ ጉዳይ ምንነት የሚቀርቡ በርካታ አሳቦች አሉ:-

1) «የእግዚአብሔር ልጆች» የሚለው ቃል ተፈጥሮአዊ ደረጃቸውን ትተው የሰውን ሴቶች ልጆች ስለ አገቡ መላእክት የሚናገር ሊሆን ይችላል። ይህንን አመለካከት ለመቀበል በጣም አስቸጋሪ የሚያደርገው መላእክት እንደማያገቡ ኢየሱስ ማስተማሩ ነው (ማር.

12፡25)። ሥጋዊ አካል የሌላቸው መንፈሳዊ ፍጥረታት ስለሆኑ ሴቶችን እንዴት ሊያገቡ ይችላሉ?

2) «የእግዚአብሔር ልጆች» የሚለው ቃል የፖለቲካ መሪዎችን ያመለክታል የሚሉም አሉ። (የጥንት ሰዎች መሪዎቻቸውን «አምላክ» ብለው ይጠሩ ነበር።) ኃጢአቱም፡- እነዚህ መሪዎች ከሴቶች ጋር የፍትወተ ሥጋ ፍላጎታቸውን ለመፈፀም የጋብቻን ቅድስና በመተላለፍ ብዙ ሴቶችን ማግባት መጀመራቸው ነው። በዚህም የሕዝቡን የሥነ-ምግባር መሠረት አበላሹት።

3) «የእግዚአብሔር ልጆች» ፈሪሃ-እግዚአብሔር ያላቸው፥ የተለዩና ሴት የተባለው ሰው ዘሮች ነበሩ። « የሰዎች ሴቶች ልጆች» የቃየን ዝርያዎች ነበሩ። ኃጢአቱ፡- ዛሬ ክርስቲያኖች የማያምኑትን እንዳያገቡ እንደተነገራቸው ሁሉ እግዚአብሔርን የሚፈሩ ሰዎች እግዚአብሔርን ከማይፈሩት ጋር ጋብቻ መመሥረታቸው ነበር (1ኛ ቆሮ. 7፡39፤ 2ኛ ቆሮ. 6፡14)። ይህ ነገር የእግዚአብሔር ቤተሰቦች የሆኑ ሰዎች ምግባረ ብልሹ እንዲሆኑና ብዙ ሰዎች በእግዚአብሔር ላይ ካላቸው እምነት እንዲርቁ መንገድ ከፍቷል።

ከእነዚህ አመለካከቶች የትኛው እንደሚሻል ማወቅ በጣም አስቸጋሪ ነው። ከሁሉ የሚሻለው ምርጫ 1ኛው ወይም 3ኛው አመለካከት ይመስላል። እያንዳንዱ አመለካከት የራሱ ችግር አለው። ዛሬም ቢሆን ከኃጢአታቸው በስተኋላ ያለው አሳብ ግልጥ ነው። እነዚህ የእግዚአብሔር ልጆች ከሚያገቡአቸው ሴቶች መንፈሳዊ መመዘኛን ከመፈለግ ይልቅ፥ ስለ አካላዊ ውበትና ስለ ፍትወተ ሥጋ ፍላጎት ብቻ ያስባሉ።

13ኛ ጥያቄ፥ ሀ) ዛሬ ሰዎች የትዳር ጓደኛ በሚመርጡበት ጊዜ ያላቸው ተመሳሳይ አመለካከት ምንድን ነው? ለ) አንድ ክርስቲያን የሚያገባው በመልክ ቁንጅናና ከጥሩ ቤተሰብ በመገኘት ብቻ ከሆነ ስሕተት የሚሆነው ለምንድን ነው? ሐ) የትዳር ጓደኛን የመምረጫ እጅግ ጠቃሚ መመዘኛዎች የትኞቹ ናቸው?

በኦሪት ዘፍጥረት 6 የሚገኘው ታሪክ በተፈጸመ ጊዜ ክፋትና ኃጢአት እጅግ ተስፋፍቶ ስለ ነበር እግዚአብሔር ሰውን በመፍጠሩ ተጸጸተ። ከእግዚአብሔር ጋር ትክክለኛ በሆነ ግንኙነት ይኖር የነበረ አንድ ሰው ኖኅ ብቻ ነበር፤ ስለዚህ ከዘፍ. 6-9 ባለው ክፍል እግዚአብሔር

የሰውን ዘር ለማጥፋት ስለተጠቀመበት የጥፋት ውኃ እናነባለን። የጥፋት ውኃ ዓላማ በክፋው የሰው ልጅ ላይ ለመፍረድና የእግዚአብሔር ሰው የሆነው ኖኅ በአዲስ መልክ እንዲጀምር ለማድረግ ነበር። ልክ እንደ አዳም ኖኅ የሰው ዘር ሁሉ ራስ ሆነ። ዛሬ በምድር ላይ ያሉ ሰዎች በሙሉ የተገኙት ከኖኅ ነው።

ሠ. ከዘፍ. 10-11 ክፍል ክፋት በጥፋት ውኃ ሊጠፋ እንዴት እንዳልቻለ እናያለን። ኖኅ የእግዚአብሔር ሰው ቢሆንም፥ እርሱና ቤተሰቡ የክፋት ባሕርይ ነበረባቸው። በመጀመሪያ፥ ኖኅ ጠጥቶ ሰክረና ጨዋነት በጎደለው መንገድ እራቁቱን ሆነ። ከዚያም የኖኅ ልጆች ከነበሩት አንዱ የሆነው ካም የአባቱን እርቃነ-ሥጋ አየ። ከዚህ የተነሣ የካም ልጅ የነበረውና የእስራኤል ሕዝብ ጠላት የሆኑት የከነዓናውያን አባት ከነዓን በኖኅ ተረገመ።

** (ማስታወሻ:- አንዳንድ ሰዎች የተረገመው ከነዓን እንጂ ካም ስላልሆነ ከነዓንም በኖኅ ላይ ኃጢአት ሠርቷል የሚል አስተሳሰብ አላቸው። በምንም ሁኔታ ይሁን ኖኅ በነቢይነት የከነዓን ዘር የሴምና የያፌት ዘሮች ባሪያ እንደሚሆን አስቀድሞ ተናገረ፤ ነገር ግን ይህን ታሪክ ነጮች ጥቁሮችን ለመግዛት ሊጠቀሙበት አይገባም)።

ሁለተኛ:- የኖኅ ዝርያዎች በሙሉ ብዙ ሳይቆዩ በኃጢአት ውስጥ ተዘፈቁ። በትዕቢታቸውና ሐሰተኞች አማልክትን ለማምለክ በመፈለጋቸው የባቢሎንን ግንብ ለመሥራት ተነሡ። ይህም ምድርን እንዲሞሉ ያዘዛቸውን እግዚአብሔር በተዘዋዋሪ መንገድ አንታዘዝም ማለት ነበር፤ ዳሩ ግን ለመበታተን አልፈለጉም ነበር (ዘፍ. 9:7፤ 11:4 ተመልከት)። አሁን ደግሞ እግዚአብሔር ቋንቋቸውን ደባልቆ እንዲበተኑ በማድረግ በሰው ልጆች ላይ ፈረደባቸው። በዘፍ. 10 በምድር የሚገኙ የሰው ዝርያዎች ሁሉ ከየት እንደመጡ ተጽፏል። ነጮችና የምሥራቅ ሰዎች የመጡት ከያፌት ዘር ነው። ዓረቦችና አይሁድ የመጡት ከሴም ዘር ነው። አፍሪካውያን ደግሞ የመጡት ከካም ዘር ነው።

| |
|---|
| 14ኛ ጥያቄ፥ ሀ) ኃጢአት በኖኅና በቤተሰቦቹ የመቀጠሉ እውነታ ኃጢአት ከትውልድ ወደ ትውልድ ስለ መተላለፉ ምን ይነግረናል? ለ) ዛሬ የኃጢአት ባሕርይ ከወላጆች ወደ ልጆች የመተላለፉን እውነታ እንዴት እናየዋለን? |

2. ከአዳም እስከ አብርሃም ያለው እግዚአብሔርን የሚፈራው ትውልድ።

የእነዚህ ምዕራፎች ሁለተኛ ዓላማ ደግሞ የአብርሃምን የዘር ሐረግ ወደ ኋላ በመመለስ እስከ መጀመሪያው ሰው እስከ አዳም ድረስ ማሳየት ነው። በዘፍጥረት 5 ሙሴ አሥር ትውልዶችን በመዘርዘር ከአዳም እስከ ኖኅ ድረስ ያለውን የትውልድ አመጣጥ አሳይቷል። በዘፍ. 11፡10-32 ደግሞ ሙሴ የአዳምን የዘር ሐረግ የኖኅ ልጅ እስከሆነው እስከ ሴም ከዚያም እስከ አብርሃም ድረስ ያሳያል። እርሱም የተመረጡና እሥራኤል ተብሎ የተጠራው የእግዚአብሔር ሕዝብ ራስ ነው። «አባት» የሚለው የዕብራይስጥ ቃል አያትን ወይም ቅድመ አያትን የሚያሳይ ስለሆነ እነዚህ ቁጥሮች አሥር ትውልዶችን ይሁን ወይም አንዱ የሌላው ዘር መሆኑን ብቻ የሚያሳዩ የሆኑ የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁራን ከስምምነት ላይ መድረስ አልቻሉም።

3. የዓለምን መንገድ ለመከተል እምቢ ያሉና ጻድቃን የሆኑ ሰዎች ምሳሌ፡-

አብዛኛው የዚህ ክፍል ታሪክ ትኩረት በዓለም ላይ ኃጢአት እየተስፋፋ ስለመምጣቱ ቢሆንም፥ ስለ ኃጢአትና ፍርድ በሚናገሩ ታሪኮች ውስጥ የተለዩ ሕዝቦች ታሪኮች ተሰውረው እናገኛለን። እነዚህም ሦስት የተለያዩ ሰዎች በብዙኃኑ ሕዝብ መካከል ያለውን ኃጢአት ተቋቁመው በእግዚአብሔርም ፊት የጽድቅን ሕይወት የኖሩ ናቸው።

የመጀመሪያው ሄኖክ ነበር። ስለ ሄኖክ ሕይወት የተጻፈልንና የምናውቀው ነገር «አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር ማድረጉ» ነው፤ ስለዚህም እግዚአብሔር ሞትን ሳያይ ወደ ሰማይ ወሰደው። እርሱም ሞትን ሳያይ ወደ መንግሥተ ሰማያት የተወሰደ የመጀመሪያ ሰው ነው።

ሁለተኛ፥ ኖኅን እናገኛለን። ስለ ኖኅ «በትውልዱ ጻድቅ ፍጹምም ሰው ነበር» ተብሎለታል (ዘፍ. 6፡9)። ስለሆነም ቀሪውን የሰውን ዘር በሙሉ ካጠፋው ውኃ እግዚአብሔር እርሱንና ቤተሰቡን አድኖአል። የጥፋት ውኃንና እግዚአብሔር ኖኅን እንዴት እንደጠበቀው የሚናገረውን ታሪክ ከዘፍጥረት 6-9 ባለው ክፍል እናገኛለን። በታሪኩ ውስጥ የሚከተሉትን ነገሮች ተመልከት፡-

1. የኖኅ መርከብ መጠን 140 ሜትር ርዝመት 23 ሜትር ስፋትና 13.5 ሜትር ከፍታ ያለው ነበር። ይህም ማለት ርዝመቱ ከእግር ኳስ ሜዳ ከፍታውም ሦስት ፎቅ ካለው ሕንጻ የሚበልጥ ነበር። ሦስት ወለሎች ወይም ፎቆች ነበሩት። መርከቡ አንድ በርና አንድ መስኮት ብቻ ነበረው። እስከ 1900 ዓ.ም. ድረስ ሰዎች እንዲህ ዓይነት ትልቅ መርከብ መሥራት አለመጀመራቸውን ማወቅ የሚያስገርም ነው። በአሁኑ ጊዜ በውቅያኖስ ላይ ዕቃ ጫኝ ተሽከርካሪዎችን የሚሸከሙ መርከቦች መጠናቸው ከዚያ የሚተካከል ነው። ኖኅ መርከቡን ለመሥራት 120 ዓመታት ፈጅቶበታል። ኖኅ ምንም ዝናብ ባያይና በሐይቅ (በባሕር) አካባቢ ካለመኖሩ የተነሣ ብዙ ውኃ ምን እንደሚመስል ባያውቅም እንኳ እግዚአብሔር እንዲሠራ ያዘዘውን ነገር በታማኝነት በመፈጸም መርከቡን ሠራ።

---

15ኛ ጥያቄ፥ እግዚአብሔር አንድን ነገር እንድናደርግ የጠየቀን ለምን እንደሆነ ባልተረዳንበት ሰዓት እንኳ እርሱን በመፍራት ልንታዘዘው እንደሚገባ የኖኅ ተግባር እንዴት ጥሩ ምሳሌ ይሆነናል?

---

2. የመርከቡ መሠራት ዓላማ በጥፋት ውኃ ጊዜ የኖኅን ቤተሰብና (8 ሰዎች) በምድር ላይ ከነበሩ እንስሳት በሙሉ አንድ አንድ ለማዳን ነበር። ሳይንቲስቶች ዛሬ በምድር ላይ ካሉ እንስሳት ሁሉ አንድ አንድ ቢገቡ መርከቡ ሊይዛቸው እንደሚችል አረጋግጠዋል። በአዲስ ኪዳን መርከቡ እግዚአብሔር ልጆቹን የመቤዠቱ ምሳሌ ነው (ዕብ. 11፡7፤ 2ኛ ጴጥ. 2፡5)። ደግሞም የጥምቀት ምሳሌ ነው (1ኛ ጴጥ. 3፡20-21)።

3. ኖኅና ቤተሰቡ በመርከቡ ውስጥ ለ377 ቀናት ቆዩ። (ከአንድ ዓመት በላይ ማለት ነው)። በእነዚህ ሁሉ ጊዜያት እግዚአብሔር ለእርሱና ለእንስሳቱ ሁሉ የሚያስፈልጋቸውን ነገር ይሰጣቸው ነበር።

4. ውኃው ምድርን ሁሉ ሸፍኖ ነበር። አንዳንድ ክርስቲያኖች የጥፋት ውኃው በመስጴጦምያ አካባቢ ብቻ በመሆን በዚያን ጊዜ በታወቀው ዓለም የነበሩትን ነገሮች ብቻ እንዳጠፋ አድርገው ቢያስቡም እንኳ ውኃው የሸፈነው ምድርን በሙሉ እንደሆነ ከታሪኩ በግልጥ እንመለከታለን። በጥንት ዘመን በሁሉም አህጉር ታላቅ ጥፋትን ያስከተለ ውኃ እንደነበር የሚያሳዩ ምልክቶች መገኘታቸው የሚያስገርምና የዚህን ታሪክ እውነተኛነት የሚያረጋግጥ ነው።

የመጽሐፍ ቅዱስን ታሪክ ባያውቁም እንኳ በዓለም ላይ የሚገኙ በርካታ ሕዝቦች በባሕላቸው፥ ዓለም እንዴት በውኃ እንደጠፋች የሚናገር ታሪክ አላቸው።

5. በጥፋት ውኃው መጨረሻ ላይ እግዚአብሔር ከኖኅ ጋር ቃል ኪዳን አደረገ። ቃል ኪዳኑን ከመስጠቱ በፊት አንዳንድ ትእዛዛትን ሰጠው (ዘፍ. 9፡17)።

ሀ. ምድርን ለመሙላት መባዛት ነበረባቸው፤

ለ. እንስሳት ሁሉ ለሰው ልጅ ለምግብነት ተሰጡት፤

ሐ. ኖኅ ደም እንዳይበላ ታዘዘ፤

መ. የሌላውን ሰው ነፍስ በግድየለሽነት የሚያጠፉ ሁሉ ይገደሉ ነበር።

ነገር ግን እግዚአብሔር ከሰው ልጆችም ጋር ተስፋንና ቃል ኪዳንን አድርጓል። ያም ቃል ኪዳን እግዚአብሔር እንደገና ምድርን በጥፋት ውኃ እንደማያጠፋ የሚናገር ነበር። ቀስተ ደመና እግዚአብሔር ከዚህ በኋላ ምድርን በውኃ ላለማጥፋት የገባውን ቃል ኪዳን እንደሚጠብቅ የሚያሳይ ምልክት ነበር።

| |
|---|
| 16ኛ ጥያቄ፥ 2ኛ ጴጥ. 3፡3-7 አንብብ። ምድር ወደፊት የምትጠፋው እንዴት ነው? |

ማስታወሻ:- አንዳንድ ሰዎች የኖኅን መርከብ በቱርክና በሩሲያ ድንበር ላይ በአራራት ተራራ ጫፍ አግኝተናል ቢሉም እስካሁን ድረስ ግን እውነትነቱ አልተረጋገጠም።

ሦስተኛ፥ የምናገኘው ሰው አብርሃም ነው። እርሱም በመስጴጦምያ ይኖር በነበረ ጊዜ እግዚአብሔር እርሱ ወደሚያሳየው ምድር ይወጣ ዘንድ ያዘዘው ሰው ነበር። ዘፍ. 12-25 በዚህ ልዩ የእግዚአብሔር ሰው ላይ ያተኩራል።

| |
|---|
| 17ኛ ጥያቄ፥ ሀ) እግዚአብሔርን ከሚፈሩ ሰዎች ሕይወት በክፉት ዓለም ውስጥ ስለመኖር ምን የምንማረው ነገር አለ? ለ) በእኛስ ፊት ይኸው ምርጫ እንዴት ነው? ሐ) ለእኛም የተዘጋጀው ተመሳሳይ ሽልማት ምንድን ነው? |

## 3ኛ ቀን:- ዘፍጥረት 12-24 የአብርሃም ታሪክ

ዛሬ የአሪት ዘፍጥረትን ሁለተኛ ዋና ክፍል ማጥናት እንጀምራለን። ዘፍጥረት በሁለት ዋና ዋና ክፍሎች እንደሚመደብ መመልከታችንን ታስታውሳለህ። ዘፍ. 1-11 የሚያተኩረው ከእስራኤል አባቶች በፊት በነበረው ዘመን ላይ ሲሆን፥ ዘፍ. 12-50 ደግሞ አራቱን የእስራኤል ዋና ዋና አባቶች ታሪክ ያሳየናል። እነርሱም:- አብርሃም፥ ይስሐቅ፥ ያዕቆብና ዮሴፍ ናቸው። በዛሬው ትምህርታችን የአይሁድ ሕዝብና በእግዚአብሔር ላይ እውነተኛ እምነት ያላቸው ሰዎች ሁሉ አባት የሆነውን የአብርሃምን ታሪክ እንመለከታለን። በዓለም ታሪክ ውስጥ እንደ አብርሃም እጅግ ጠቃሚ የሆኑ ሰዎች በጣም ጥቂቶች ናቸው። አይሁድም ሆኑ ዐረቦች ሁለቱም በሥጋ አባታችን አብርሃም ነው ይላሉ። እንዲሁም ክርስቲያኖችም አብርሃም መንፈሳዊ አባታችን ነው ይላሉ።

18ኛ ጥያቄ፥ ዘፍ. 12-24 አንብብ። ሀ) ከዘፍ. 12፡1-3 እግዚአብሔር ለአብርሃም ተስፋ የሰጠውን ሰባት በረከቶች ዘርዝር። ለ) በዘፍ. 15 እና 17 ወዘተ እግዚአብሔር ለአብርሃም የሰጠውን ተጨማሪ የተስፋ ቃላት ዘርዝር። ሐ) እነዚህ ቃል ኪዳኖች በብሉይ ወይም በአዲስ ኪዳን የተፈጸሙት እንዴት ነው? መ) አብርሃም በሕይወት ዘመኑ የሄደባቸውን ከተማዎች ወይም ቦታዎች ዘርዝር። እነዚህን ስፍራዎች በመጽሐፉ መጨረሻ ከሚገኘው ካርታ ላይ ተመልከት። ሠ) የአብርሃምን ሕይወት በአጭሩ አጠቃለህ አቅርብ። በእግዚአብሔር ላይ ያለውን እምነት እንዴት እንደገለጸ አስረዳ። በእምነት ስላልተራመደባቸው ጊዜያት ግለጥ ወዘተ። ረ) አብርሃም በእምነት የመኖር ጥሩ ምሳሌ የሆነው ለምንድን ነው? ሰ) የራስህን የእምነት ጉዞ ከአብርሃም ሕይወት የእምነት ጉዞ ጋር አወዳድረህ የሚመሳሰልባቸውንና የሚለያይባቸውን ነገሮች ጥቀስ።

## 4ኛ ቀን:-

ዘፍጥረት 11ን ባጠናንበት ጊዜ ከአብርሃም ቤተሰብ ጋር ተዋውቀናል። የአብርሃም ታሪክ የሚጀምረው በመስጴጦምያ በዑር ከተማ ነው። ዑር በመስጴጦምያ ከሚገኙ ታላላቅ ከተሞች አንዷ ስትሆን፥ የከፍተኛ ሥልጣኔ ማዕከልም ነበረች። ደግሞም ዑር የጣዖት አምልኮ

ማዕከል ነበረች፤ ምክንያቱም ሰዎቹ የጨረቃን አምላክ ያመልኩ ነበርና ነው።

19ኛ ጥያቄ፦ ኢያሱ 24፡2-3 አንብብ። በእነዚህ ቁጥሮች በዑር ስለ ነበረው የአብርሃም ቤተሰብ ሃይማኖታዊ ሕይወት የተጻፈው ምንድን ነው?

ስለ አብርሃም ቤተሰብ ምንም የተለየ ነገር አልነበረም። በዑር እንደነበሩ ሰዎች የአብርሃም አባት ታራና ቤተሰቡም የጨረቃና የከዋክብት አማልክትን የሚያመልኩ ይመስላል። ዳሩ ግን እግዚአብሔር ሉዓላዊ በሆነው ምርጫው የሥልጣኔና የሃይማኖት ብልሹነት ይታይባት የነበረችውን የዑር ከተማ ትቶ ሁሉንም ነገር እንደ አዲስ ወደሚጀምርበት ምድር እንዲሄድ አብርሃምን ጠራው።

የአብርሃምን ሕይወት ለመረዳት የኦሪት ዘፍጥረትን የመጀመሪያ ክፍል ማስታወስ አለብን። እግዚአብሔር የአሠራር መንገዱን የለወጠበት ምክንያት ምንድን ነው? ከሰዎች ሁሉ ጋር በእኩልነት ከመሥራት ይልቅ ከአንድ ሰውና ከአንድ ሕዝብ ጋር ለመሥራት ለምን መረጠ? መልሱ ያለው በዘፍጥረት የመጀመሪያ 11 ምዕራፎች ውስጥ ነው።

በአብርሃም ዘመን የዓለም ሁሉ መሠረታዊ ባሕርይ በእግዚአብሔር ላይ ማመፅ እንደነበር ታስታውሳለህ። እንዲከተሉት ለማድረግ እግዚአብሔር ለብዙ ዓመታት ከሰዎች ሁሉ ጋር ለመሥራት ሞክሯል። አሁንም በቀረው የብሉይ ኪዳን ክፍል እግዚአብሔር ዘዴውን ለወጠ። እግዚአብሔር አንድ ሰውና አንድ አነስተኛ ሕዝብ ለዓለም ብርሃን እንዲሆኑ ወሰነ። እግዚአብሔር ከሰዎች ሁሉ ጋር ሊኖረው የሚፈልገውን ግንኙነት በምሳሌነት እንዲያሳዩ የተመረጡ ነበሩ። ሌሎች ሕዝቦች እግዚአብሔር ከእስራኤላውያን ጋር ያለውን ልዩ ኅብረት እንዲመለከቱና ይህ ኅብረት በመንፈሳዊና በሥጋዊ መንገድ የሚያስገኘውን ሽልማት (በረከት) እንዲያዩ ዕቅዶ ነበር። እነዚህ ሕዝቦች ይህን ኅብረት አይተው ከእግዚአብሔር ጋር ወዳለው ልዩ ኅብረት እንዲመጡ የእግዚአብሔር አሳብ ነበር። እስራኤላውያን በዓለም ላይ የእግዚአብሔር ተወካዮች ነበሩ።

የሚያሳዝነው ግን የብሉይ ኪዳን ታሪክ እስራኤል ይህን ኃላፊነቷን መፈጸም አቅቷት መውደቋን የሚያሳይ መሆኑ ነው። በእግዚአብሔር ላይ ዓመፀች። ከዓለም ከመለየት ይልቅ እንደ ዓለም ተመላለሰች።

እግዚአብሔር ዓለምን ለእርሱ ትማርከለት ዘንድ ያሰበውን ዕቅድ ልታሟላ ስላልቻለች፥ ሥራውን ከቤተ ክርስቲያን ጋር በሚሠራበት በአዲስ ኪዳን ዘመን ለጊዜው ገለል ተደረገች።

> 20ኛ ጥያቄ:- ሀ) ለእስራኤል የነበረው ዓላማ ዛሬ እግዚአብሔር እኛ እንድንሆን ከሚፈልገው ነገር ጋር የሚመሳሰለው እንዴት ነው? ለ) እስራኤል በወደቀችበት መንገድ ቤተ ክርስቲያን ብዙ ጊዜ የምትወድቀው እንዴት ነው? ሐ) አንተና ቤተ ክርስቲያንህ በኅብረተሰቡ ውስጥ ይህንን ዓላማ የምታሟሉት እንዴት ነው?

በአዲስ ኪዳን የእግዚአብሔር የግንኙነት መስመር ተለውጦአል። ከዓለም ጋር በስፋት አልሠራም። ከአንድ ሕዝብም ጋር አልሠራም። ይልቁን ከተለያዩ ሕዝቦች መካከል ራሳቸውን ከዓለም ከለዩ ሰዎች ጋር መሥራት ጀመረ። ይህችም ቤተ ክርስቲያን ናት። ክርስቲያኖች የእርሱ ብርሃን እንዲሆኑና ለዓለም እንዲመሰክሩ ነበር። በሕይወታቸው በሚታየው ለውጥ ሰዎችን ወደ እግዚአብሔር መንግሥትና ቤተሰብ ሊስቡ ያስፈልግ ነበር። የእርሱ ልጆች ነን ብለን ከምናስበው፥ ከእኛ እግዚአብሔር የሚፈልገው ይህንን ነው። ይህንን ዓላማ ለሕይወታችን እያሳካን ነውን?

ሀ) ከላይ የተጠቀሰውን የቤተ ክርስቲያን ዓላማ አንተና ቤተ ክርስቲያንህ የምታሟሉባቸውን መንገዶች ጥቀስ። ለ) የተሻለ «የዓለም ብርሃንና ጨው» (ማቴ. 5:13-16) ለመሆን እንድትችሉ አሁን ከምትሠሩበት መንገድ በተለየ ሁኔታ ልታከናውኑ የምትችሏቸውን አንዳንድ ነገሮች ዘርዝሩ።

እግዚአብሔር በመጀመሪያ ዑርን እንዲለቅ የጠራው ታራን ይሁን ወይም አብርሃምን የምናውቀው ነገር የለም። ጥሪው የመጣው ግን ለአብርሃም ሳይሆን አይቀርም። አብርሃምም በዕድሜ የገፉ አባቱንና የወንድሙን ልጅ ሎጥን ከራሱ ጋር ይዞ ወጣ። የአብርሃም ወንድም የሆነው ናኮር ለጊዜው በዑር የቆየ ቢሆንም በኋላ ግን ወደኖረበት ወደ ካራን ሄደ። አበርሃምና ሣራ፥ ታራና ሎጥ ወደ ከነዓን ለመሄድ 1000 ኪሎ ሜትር ያህል ከተጓዙ በኋላ ወደ ካራን ከተማ ደረሱ። ወደ ከነዓን በሚወስደው መንገድ ላይ የነበረችው የመጨረሻዋ ዋና ከተማ ካራን ነበረች። ከግብፅ በመነሣት በከነዓን በኩል ወደ መስጴጦምያ በሚወስደው መንገድ ላይ ነበረች። ደግሞም የጨረቃ አምላክ የሚመለክባት ከተማ ነበረች። ታራ ምናልባት በእድሜ ስለገፉ፥ ወይም የለመደውን ባሕልና

ሃይማኖትን ትቶ ለመሄድ ባለመፈለጉ ከአብርሃም ጋር በካራን ሰፈረ። በዚህ ስፍራ የኖሩት ለምን ያህል ጊዜ እንደሆነ አይታወቅም፤ ነገር ግን ከታራ ሞት በኋላ አብርሃም የእግዚአብሔርን ጥሪ እንደገና ተቀበለና ወደ ከነዓን ሄደ።

## የአብርሃም መጠራት

ዘፍጥ. 12፥1-3 በመጽሐፍ ቅዱሳችን ከሚገኙ በጣም አስፈላጊና ጠቃሚ ክፍሎች አንዱ ነው። በብሉይና በአዲስ ኪዳን የነበረው የእግዚአብሔር ዕቅድ የተሠራበት መሠረት ነው። በእግዚአብሔርና በአብርሃም መካከል ለተደረገው ቃል ኪዳንም መሠረት ነው። አብርሃም በሕይወት እስከ ኖረበት ዘመን ድረስ እግዚአብሔር በመጀመሪያ በሰጠው የተስፋ ቃል ላይ በየጊዜው ይጨመርለት ነበር፤ ነገር ግን እግዚአብሔር አብርሃምን መጀመሪያ ሲጠራው የሰጠው ሰባት ተስፋዎች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ለሚገኙ ተስፋዎች ሁሉ መሠረት ናቸው።

የሚቀጥለው ሠንጠረዥ እግዚአብሔር ለአብርሃም የገባውን ሰባት የተስፋ ቃሎች እንዴት እንደፈጸመ ያሳያል። (እነዚህን ለፈተና አጥናቸው)

| ለአብርሃም የተሰጡ ተስፋዎች | የተስፋዎቹ መፈጸም |
|---|---|
| «ታላቅ ሕዝብ አደርግሃለሁ።» | የእስራኤል ሕዝብ |
| «እባርክሃለሁ።» | አብርሃም ባለጠጋ ሆነ። |
| «ስምህን አከብረዋለሁ» | አይሁድ፥ ዐረቦችና ክርስቲያኖች ሁሉም አብርሃምን እንደ አባታቸው ያከብሩታል። |
| «በረከትም ትሆናለህ።» | በአብርሃምና በዘሩ መጽሐፍ ቅዱስ ተጻፈ፤ ጌታ ኢየሱስ ተወለደ፥ ደኅንነት ወደ ዓለም መጣ። |
| «የሚባርኩህን እባርካለሁ።» | በዘመናት ሁሉ አይሁድን የሚባርኩ ሰዎችንና መንግሥታትን እግዚአብሔር ባርኮአቸዋል። |
| «የሚረግሙህን እረግማለሁ።» | በዘመናት ሁሉ አይሁድን የሚያሳድዱ ሰዎችንና መንግሥታትን እግዚአብሔር በተራው አጥፍቶአቸዋል። (ምሳሌ፡- ባቢሎን፥ አሦር) |
| «የምድር ነገዶች ሁሉ ባንተ ይባረካሉ።» | በአብርሃምና በዘሩ ዓለም ሁሉ ተባርኳል። ይህ በተለይ እውን የሆነው እግዚአብሔር እራሱን ለዓለም የገለጠው በአይሁድ በኩል ስለሆነና የዓለም ሁሉ አዳኙ ክርስቶስ አይሁዳዊ ስለሆነ ነው። |

እግዚአብሔር አብርሃምን ሲጠራው ይጠብቃቸው ዘንድ ሦስት ትእዛዛትን ሰጥቶታል:- 1) የሚኖርበትን ምድር ትቶ ይወጣ ዘንድ፥ 2) የአባቱን ቤተሰብ ትቶ ይወጣ ዘንድ፥ 3) እግዚአብሔር ወደሚያሳየው ምድር ይሄድ ዘንድ ነበሩ። አብርሃም የለመደውንና የሚያውቀውን ነገር ሁሉ ትቶ ወደማያውቀውና እንግዳ ወደሆነ ስፍራ ለመሄድ ትልቅ የእምነት እርምጃ ወሰደ። አብርሃም ግን ይህንን ትእዛዝ ሙሉ በሙሉ አልጠበቀም። የአባቱን ቤተሰብ ሁሉ ትቶ እንደመሄድ የወንድሙ ልጅ የሆነውን ሎጥን ይዞ ወጣ። አብርሃም የእግዚአብሔርን ትእዛዝ በከፊል መጠበቁ በኋላ በሕይወቱ ላይ ትልቅ ችግር አስከተለበት። ይህም የወንድሙ ልጅ የሆነው ሎጥ ከሌሎች ነገሥታት ጋር ወደ ጦርነት እንዲሄድ ያደረገው የቤተሰብ ክፍፍል ማስከተሉ ነበር።

21ኛ ጥያቄ፥ ዛሬም ቢሆን እግዚአብሔር በከፊል ብቻ እንዴት ልንታዘዘው እንደምንችል ምሳሌ ስጥ።

የአብርሃም ሕይወት በምድር ላይ ለሚኖረን የእምነት ጉዞ ጥሩ ምሳሌ ነው። ማንም ሰው እግዚአብሔርን ፍጹም በሆነ መንገድ መታዘዝ አይችልም። በሕይወታችን ዘመን እግዚአብሔርን የምንታዘዝባቸው ጊዜያት እንዳሉ ሁሉ በእግዚአብሔር ላይ የማንታመንባቸውና ለእርሱ የማንታዘዝባቸው ጊዜያትም አሉ። ስለ አብርሃም ሕይወት በዘፍጥረት የጥናት መጽሐፍ ውስጥ የበለጠ ማጥናት ትችላለህ። ቀጥሎ ግን ልናስታውሳቸው የሚገባን አጠቃላይ ነገሮች ብቻ ቀርበዋል።

1. እግዚአብሔር አስቀድሞ ለአብርሃም በሰጠው ተስፋ በምንም ቅድመ ሁኔታ ላይ ያልተመሠረተ ቃል ኪዳን ገባለት።

    ሀ. እግዚአብሔር ከግብፅ ጀምሮ እስከ ኤፍራጥስ ወንዝ ድረስ ያለውን ምድር በሙሉ ለአብርሃምና ለዘሩ እንደሚሰጥ ቃል ገባለት፤ (ዘፍጥ. 15፡ 18)።

    ለ. እግዚአብሔር አብርሃምን የብዙ ሕዝብ አባት፥ ሣራን ደግሞ የብዙ ሕዝብ እናት አደርጋችኋለሁ አላቸው፤ (ዘፍጥ. 17፡5፥ 15-16)። እግዚአብሔር፥ «ታላቅ አባት» የሚል ትርጉም የነበረውን አብራም የሚለውን የመጀመሪያ ስሙን «የብዙ ሕዝብ

አባት» የሚል ትርጉም ወዳለው ወደ አብርሃም ቀየረው። የሚስቱንም ስም ከሦራ ወደ ሣራ ቀየረው። ትርጉሙም «ልዕልት» ማለት ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር የሰውን ስም ሲቀይር፥ ሰው ከእርሱ ጋር አዲስ ግንኙነት ጀመረ ማለት ነው።

ሐ. እግዚአብሔር ቃል ኪዳን ለማድረግ የተለመደውን ባሕላዊ መንገድ በመጠቀም ማረጋገጫ ሰጠ (ዘፍጥ. 15)። በጥንት ዘመን ሰዎች ሃይማኖታዊ በሆነ ወይም በሌላ ሥነ - ሥርዓት ቃል ኪዳን ወይም ስምምነት ሲያደርጉ አንድ እንስሳን በማረድ ሥጋውን በትክክል ሁለት ቦታ ቅርጫ ይከፍሉት ነበር። ከዚያ በኋላ ቃል ኪዳኑን የፈጸሙት ሁለት ወገኖች በተከፋፈሉት ቅርጫ መሃል ይራመዱ ነበር። ይህን የሚያደርጉትም የቃል ኪዳን ስምምነታቸውን ቢያጥፉ፥ እነርሱም እንዲገደሉ መስማማታቸውን ለመግለጽ ነበር። አብርሃም ያንን በግልጽ በማየት በእምነቱ ይበረታ ዘንድ፥ እግዚአብሔር የተለመደ ቃል ኪዳን ምልክት ሰጠው፤ ነገር ግን አንድን ነገር ማስተዋል አስፈላጊ ነው። በቃል ኪዳን ምልክት ማድረጊያው መካከል የተረማመደው እግዚአብሔር ብቻ ነበር። ለምን? ምክንያቱም ይህ ቃል ኪዳን በምንም ቅድመ ሁኔታ ላይ የተመሠረተ አልነበረምና ነው። ይህንን ቃል ኪዳን ይፈጽም ዘንድ አብርሃም እንዲያደርገው የተጠየቀው አንዳችም ነገር አልነበረም። ይልቁንም የቃል ኪዳኑ መፈጸም የተመሠረተው እግዚአብሔር የሰጠውን ተስፋ በመጠበቁ ላይ ነበር።

መ. ነገሥታት ከአብርሃም ዝርያ እንደሚነሡ እግዚአብሔር ተስፋ ሰጥቶ ነበር፤ (ዘፍጥ. 17፡6)። ይህም የሚያመለክተው ዳዊትንና ልጆቹን በተለይ ደግሞ ለአብርሃም በጣም አስፈላጊ የሆነውን ኢየሱስ ክርስቶስን ነበር።

ሠ. እግዚአብሔር ለአብርሃምና ለአይሁድ በአጠቃላይ ከእርሱ ጋር ልዩ የሆነ ግንኙነት ያላቸው መሆኑን የሚያመለክት የሚታይ ምልክት ሰጣቸው (ዘፍጥ. 17)። ይህ ምልክት የእያንዳንዱ ወንድ ልጅ መገረዝ ነበር። በሥጋ አይሁድ የሆነ ማንኛውም ሰው አልገረዝም ቢል በእግዚአብሔርና በአብርሃም ልጆች መካከል

በተደረገው ቃል ኪዳን አይታቀፍም ማለት ነው፤ ስለዚህም የአብርሃም እምነት ስላልነበረው እውነተኛ አይሁዳዊ አልነበረም ማለት ነው።

2. አብርሃምን ያጋጠመው አደጋ፥የቃል ኪዳኑን መፈጸም ሊያሰናክለው የሚችል ነበር

ሀ. የአብርሃም የወንድም ልጅ የሆነው ሎጥ የፈጠረው አደጋ።

1. የአብርሃም ብቸኛ ዘመድ የሆነው ሎጥ ወራሹ ነበር (ዘፍጥ. 13-14)፤ ነገር ግን የእግዚአብሔር ዕቅድ የአብርሃምን ርስት የራሱ ልጅ እንዲወርሰው ነበር። ቃል ኪዳኑ በሎጥ ምክንያት በሁለት መንገዶች አደጋ ላይ ወድቋል። በመጀመሪያ፥ ሎጥ የአብርሃም ወራሽ ነበር። የአብርሃም ርስት ልጁ ወዳልሆነው ወደ ሌላ ሰው ያልፋልን? አብርሃም ልጅ ቢኖረውም እንኳ ወራሹ ማን ይሆናል በሚለው ጥያቄ ውስጥ አከራካሪ ነገር ሊኖር ይችላልን? ነገር ግን ሎጥ የተስፋይቱን ምድር በተወ ጊዜ የአብርሃም ወራሽ የመሆኑ ነገር ቀረ። ሁለተኛው፥ እግዚአብሔር እንደሚያወርሰው ለአብርሃም ተስፋ ሰጥቶት ነበር። ሎጥ የከነዓንን ምድር ለመውረስ ይመርጣልን? ሎጥ የፈለገው ምቹ የሆነ ምድርን ነበር። ከሁሉ የተሻለውን ምድር ለአጎቱ ለአብርሃም ሊለቅለት ሲገባ፥ እጅግ በጣም ጥሩ የመሰለውን ነገር ግን፥ እጅግ ክፉ የነበረውን የሰዶምን ምድር መረጠ። ስለዚህ ሎጥ የተስፋይቱን ምድር ከነዓንን ተወ። በራስ ወዳድነት ያደረገው ምርጫ ከእግዚአብሔር የበረከት ስፍራ ውጭ አደረገው። ለሁለተኛ ጊዜ እግዚአብሔር የከነዓንን ምድር ለአብርሃም ቃል ገባለት። ደግሞም ዝርያዎቹ ሊቆጠሩ እስከማይችሉ ድረስ እንደሚበዙ ተስፋ ሰጠው።

---

22ኛ ጥያቄ፥ ሥጋዊ ክርስቲያን መላ ሕይወቱን ለእግዚአብሔር አስገዝቶ አልኖርም በሚልበት ጊዜ የሚመርጠው ምርጫ ከሎጥ ምርጫ ጋር የሚመሳሰለው እንዴት ነው?

---

2. ሎጥ በሰዶም ሲኖር ሳለ በሰሜን ነገሥታት ተማረከና ቃል ኪዳኑን አደጋ ላይ ጣለው። በአብርሃም ዘመን፥ በከነዓን ምድር በርካታ የከተማ መንግሥታት ነበሩ። ገናና የሆነችው ከተማም በአካባቢዋ ያለውን ምድር ሁሉ ትማርክና በማስገበር ትገዛ ነበር። የዚያች ከተማ መሪም ንጉሥ ተብሎ ይጠራ ነበር። ይህ ታሪክ በተፈጸመ ጊዜ ሎጥ

ወደ ሰዶም ምድር ተንቀሳቀሰ። በመሐሉ በሙት ባሕር በስተደቡብ መጨረሻ አካባቢ እንደ ነበሩ በሚገመቱ በሰዶምና ገሞራ ከተሞችና በኤላም፥ በጎኢምና እላሳር (በመስጴጦምያ የሚገኙ) ከተሞች መካከል በተደረገው ትግል ሎጥም ተማርኮ ተወሰደ። በዚህ ጊዜ ሰዶምና ገሞራ በሰሜን ነገሥታት እጅ የወደቁ ቢሆንም ዓምፀው ግብር አንከፍልም አሉ፤ ስለዚህ የሰሜን ነገሥታት የደቡብ ነገሥታትን ለመቅጣት መጡ። ደቡቦቹ ተሸነፉና ሎጥን ጨምሮ፥ በርካታ ሰዎች በምርኮ ተወሰዱ። አብርሃምም የወንድሙ ልጅ መማረኩን በሰማ ጊዜ፥ ከእርሱ ጋር የነበሩ ሰዎችን በሙሉ (318 ወንዶች)፥ በከነዓን ምድር ከሚኖሩ አንዳንድ መሪዎች ጋር ይዞ ሄዶ የሰሜን ነገሥታትን በማጥቃት አሸነፋቸው። አብርሃም እነዚህን ነገሥታት ለመውጋት በብዙ መቶ የሚቆጠሩ ኪሎ ሜትሮችን ተጓዘ። ሎጥን ለማዳን ሲል ሕይወቱን አደጋ ላይ ጣለ። ይህም እግዚአብሔር በአብርሃም በኩል ሊጀምረው የነበረውን የተመረጠ ሕዝብን የማዘጋጀት ዕቅድ ሊያበላሽ ይችል ነበር፤ ነገር ግን እግዚአብሔር አብርሃምን ጠብቆ ድልን አጎናጸፈው።

| |
|---|
| 23ኛ ጥያቄ ፥ ሎጥ ከአብርሃም ምርጥ የሆነውን መሬት ቢወስድበትም አብርሃም ቸር ነበር። ከዚህ ምን እንማራለን? |

ሙሴ ይህንን ታሪክ ለምን ጻፈው? የሎጥን የሞኝነት ምርጫ በማሳየት፥ ራስ ወዳድነት ክርስቲያንን እንዴት ችግር ውስጥ ሊከተው እንደሚችል ለማሳየት ሊሆን ይችላል። በተጨማሪ ወደ ከነዓን ለመግባት በዝግጅት ላይ ያሉትን እስራኤላውያንን ለማበረታታትም ሊሆን ይችላል። አብርሃም ከእርሱ ጋር የነበሩት ጥቂት ቢሆኑም እንኳ እግዚአብሔር ግን ከእርሱ ጋር ስለነበር ታላቅ ኃይልን ለማሸነፍ ቻለ። እስራኤላውያን ወደ ከነዓን ምድር ሊገቡ በተዘጋጁ ጊዜ ቁጥራቸው ከጠላቶቻቸው ቁጥር ያነሰ ነበር፤ ነገር ግን እግዚአብሔር ከእነርሱ ጋር ስለሆነ በቁጥር እጅግ ጥቂት ቢሆኑም እንኳ በርካታ የሆኑትን የእግዚአብሔር ጠላቶቻችን አሸንፈዋል።

| |
|---|
| 24ኛ ጥያቄ፥ ዛሬ በጠላቶቻቸው ብዛት ለተዋጡት ክርስቲያኖች ይህ እንዴት ያበረታታቸዋል? |

3. የሎጥ በሰዶምና ገሞራ ላይ ከመጣው ፍርድ ማምለጥ በቃል ኪዳኑ ላይ ትልቅ አደጋ ሊፈጥር የሚችል ነበር፤ (ዘፍጥ. 18-19)። ሎጥ የሰዶምን ኑሮ ስለወደደ ወደ ከተማይቱ ገባ። እግዚአብሔር

በከተማይቱ ላይ በመፍረድ ሊያጠፋት ባሰበ ጊዜ ወደ ወዳጁ ወደ አብርሃም በመምጣት ዕቅዱን ገለጠለት (ዘፍጥ. 18)። አብርሃም ስለ ከተማይቱ እግዚአብሔርን አጥብቆ ለመነ፤ ነገር ግን አሥር ጻድቃን እንኳ ስላልተገኙባት እግዚአብሔር ከተማይቱን አጠፋት። ይሁን እንጂ እግዚአብሔር ለአብርሃም ብሎ ሎጥንና ሁለቱን ሴቶች ልጆቹን አዳናቸው። ሎጥ ወደ ከነዓን ተመልሶ የአብርሃም ወራሽ ሆነን? የለም፤ ሎጥ ወደ ከነዓን ከመመለስ ይልቅ በዋሻ ውስጥ መኖርን መርጦ እምቢ አለ።

የሎጥ ታሪክ ለሥጋዊ ክርስቲያን ጥሩ ምሳሌ ነው። ሎጥ ከአብርሃም ጋር በሰላም ቢኖር ኖሮ ከአብርሃም ጋር የእግዚአብሔርን የበረከት ፍሬ በሙሉ በተካፈለ ነበር። በረከቶቹ ግን በአብርሃምና በሎጥ መካከል አለመስማማትን አስከተሉ። በረከቶቹ ወደ ራስ ወዳድነት መሩት። ሎጥ ለሥጋዊና ለጊዜያዊ ጥቅም ሲል ከምድሪቱ ምርጥ ነው ብሎ ያሰበውን ነገር መረጠ። ይህ ምርጫው በነገሥታት እንዲማረክ፥ በመጨረሻም ሚስቱን፥ ንብረቱንና ሀብቱን ሁሉ እንዲያጣ ምክንያት እንደሚሆን አልተገነዘበም። ከሴት ልጆቹ ጋር ኃጢአት በማድረግ የእግዚአብሔርና የእስራኤላውያን ጠላቶች የሆኑ ሕዝቦች የተገኙባቸውን ልጆች ወለደ። የሎጥ ልጆች የሆኑት ሞዓብና ዓሞን፥ ሞዓባውያንና ዓሞናውያን የተባሉ ሁለት ሕዝቦች ሲሆኑ እነርሱም በብሉይ ኪዳን ዘመን ከእስራኤላውያን ጋር ያለማቋረጥ ይዋጉ ነበር።

---

25ኛ ጥያቄ፥ እግዚአብሔርን ደስ እያሰኙ ከመኖር ይልቅ እራሳችንን ደስ እያሰኘን የመኖርን ውጤት ምንነት ከሎጥ ታሪክ ምን እንማራለን?

---

ለ. የአብርሃም ሎሌ ኤሊዔዘር በቃል ኪዳኑ ፍጻሜ ላይ የፈጠረው አደጋ፡- (ዘፍጥረት 15)

በጥንት ዘመን አንድ ሰው ምንም ልጆች ከሌሉት ከሎሌዎቹ አንዱን ወራሽ አድርጎ ይሾመው ነበር። አብርሃም ለዚህ ጉዳይ የሾመው ተወዳጅ አገልጋዩ የነበረውን የደማስቆውን ሰው ኤሊዔዘርን ሳይሆን አይቀርም። የአብርሃም ፍላጎት ግን ከጉልበቱ የወጣው ልጁ እንዲወርሰው ነበር።

ከአብርሃም ታሪክ ውስጥ እጅግ በጣም አስፈላጊው ክፍል ዘፍጥረት 15 ነው። በዚህ ታሪክ ውስጥ እግዚአብሔር ቃል ኪዳኑን አደሰ።

እጅግ ጠቃሚ በሆነው በዚህ ታሪክ ውስጥ የሚከተሉትን ነገሮች ተመልከት፡-

1. እግዚአብሔር ለአብርሃም በርካታ ተስፋዎችን በመስጠት ቃል ኪዳኑን ጀመረ።

   ሀ. እግዚአብሔር ለአብርሃም ልጆቹ በሰማይ እንዳሉ ከዋክብት እንደሚበዙ የተስፋ ቃል ገባለት።

   ለ. ከግብፅ ጀምሮ እስከ ኤፍራጥስ ወንዝ ድረስ ያለው የከነዓን ምድር በሙሉ ለአብርሃም ዝርያዎች ተሰጠ።

2. አብርሃም ለእግዚአብሔር በእምነት መልስ ሰጠ። ዘፍጥ. 15፡6 እንዲህ ይላል፡- «አብራምም በእግዚአብሔር አመነ፥ ጽድቅም ሆኖ ተቆጠረለት።» አብርሃም የዳነው እንዴት ነበር? አንዳንድ ታላላቅ ነገሮችን ስላደረገ ነውን? ስለተገረዘ ነውን? አይደለም። እግዚአብሔር አብርሃምን የተቀበለውና ጻድቅ ብሎ የጠራው የገባውን የተስፋ ቃሉን ስላመነ ነው።

| |
|---|
| 26ኛ ጥያቄ፥ ዛሬ ለደኅንነት ከሚፈለግብን ነገር ጋር ይህ እንዴት ይመሳሰላል? (ሮሜ 4፡ 1-25 ተመልከት)። |

ሐዋርያው ጳውሎስ ይህንን የአብርሃምን እምነት በመውሰድ፥ እኛም የምንድነው ወይም ጻድቃን ተብለን የምንቆጠረው በምንሠራው መልካም ሥራ (ለድሆች በመስጠት፥ ባለመጠጣት፥ ዝሙትን ባለማድረግ ወዘተ) ሳይሆን በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ባለን እምነት ብቻ እንደሆነ ለመግለጽ ተጠቅሞበታል።

| |
|---|
| 27ኛ ጥያቄ፥ ይህ ትምህርት ወደ መንግሥተ ሰማያት የምንገባው በምንሠራቸው መልካም ተግባራት፥ማለትም በጥምቀት፥ ለድሆች በመስጠት፥ በመጾም ወዘተ ነው ብለው ከሚያስተምሩ ሰዎች የሚለየው እንዴት ነው? |

3. እግዚአብሔር ስለ አብርሃም ዝርያዎች የወደፊት ጉዳይ ተንብዮአል። እግዚአብሔር እስራኤላውያን ወደፊት መጻተኞች እንደሚሆኑ (በተስፋ የእነርሱ ብትሆንም እንኳ በከነዓን ውስጥ ምድር እንደማይኖራቸው) እና ለ400 ዓመታት በባርነት እንደሚቆዩ ለአብርሃም ተናገረ። በሙሴ ዘመን የነበሩ እስራኤላውያን ይህንን

ትንቢት በማወቃቸው ይበረታቱ ነበር፤ ምክንያቱም 400 ዓመታት እየተጠናቀቁ መሆናቸውን ቆጥረው ለመድረስ ይችሉ ነበር።

** (ማስታወሻ:- እግዚአብሔር አሞራውያን የኃጢአታቸው ጽዋ ስላልሞላ በጸጋው የንስሐ ጊዜ እንደሰጣቸው ይናገር ነበር። አሞራውያን ከኃጢአታቸው ይመለሱ ዘንድ እግዚአብሔር ለ400 ዓመታት በትዕግሥት ጠበቃቸው። አሞራውያን የከነዓናውያን ሌላ ስም ነው። እነርሱ ግን ከመመለስ ፈንታ በክፋታቸው እጅግ እየባሱ ሄዱ። ስለዚህ በመጽሐፈ ኢያሱ የእግዚአብሔር ፍርድ በአሞራውያን ላይ ይፈጸም ዘንድ እስራኤላውያን መሣሪያ ሆኑ። ሙሉ በሙሉ እንዲያጠፏቸውም ታዘዙ።)

ሐ. በቃል ኪዳኑ ፍጻሜ ላይ እስማኤል የፈጠረው አደጋ:- (ዘፍጥ. 16፤ 21:8-21)

ከአብርሃምና ከባሪያይቱ ከአጋር የተወለደው እስማኤል እግዚአብሔር ከአብርሃምና ከሣራ ሊያስገኘው ያቀደውን ተአምራዊ ልጅ የመወለድ ዕቅድ ሊያበላሸው ነበር። እግዚአብሔር በራሱ ጊዜ የሚሠራ መሆኑን በማመን ፈንታ አብርሃም በራሱ መንገድ የራሱን ልጅ በማዘጋጀት እግዚአብሔርን ሊረዳው ሞከረ። በዚያን ዘመን ሰው ከገዛ ሚስቱ ልጅ ማግኘት ካልቻለ ባሪያውን በመገናኘት ልጅ ይወልድ ነበር። በዚህ ዓይነት የተገኘውም ልጅ የልጅነት ሙሉ መብት በማግኘት ወራሽ ይሆን ነበር። አብርሃም ይህ ድርጊቱ የሚያስከትልበትን ኃዘን አልተገነዘበም ነበር። በቤቱ ውስጥ በሣራና በአጋር መካከል ጠብን ፈጠረ። ይህም ማለት የሚወደውን ልጁን እስማኤልን ከቤት ማባረር ነበረበት ማለት ነው። በኋላም በታሪክ እንደምናገኘው፥ የእስማኤል ዝርያዎች የሆኑት ዐረቦች፥ የአብርሃም ልጅ፥ የይስሐቅ ዝርያዎች የሆኑት የአይሁድ ክፉ ጠላቶች ሆኑ።

| |
|---|
| 28ኛ ጥያቄ፥ የራሳችንን አሳብ ወይም መንገድ በመጠቀምና አንድ ነገር በማድረግ እግዚአብሔርን ለመርዳት ስለመሞከር ይህ ምን ያስተምረናል? |

መ. አብርሃም እግዚአብሔር ሕይወቱን ለመጠበቅ እንደሚችል አላምንም በማለቱ በቃል ኪዳኑ ላይ የተፈጠረ አደጋ:-

አብርሃም ታላቅ የእምነት ሰው ቢሆንም፥ ሊወጣው ያልቻለው ደካማ ነጥብ በሕይወቱ ነበር። ይህም ደካማ ነጥብ እግዚአብሔር ሕይወቱን

እንደሚጠብቅ ሊታመንበት አለመቻሉ ነበር። በመጀመሪያ አብርሃምና ሣራ ወደ ግብፅ በወረዱ ጊዜ የተፈጸመ ታሪክ ነው (ዘፍጥ. 12፡10-20)። አብርሃም ወደ ግብፅ ይወርድ ዘንድ እግዚአብሔርን ስለመጠየቁ ምንም ማረጋገጫ የለንም። በእግዚአብሔር ላይ እምነት በማጣቱ ሕይወቱን ለመጠበቅ በከፊል ሲዋሽ እናየዋለን። ሣራን ለማግባት ሲሉ ይገድሉኛል ብሎ ስለፈራ ለግብፃውያን እኅቱ እንደሆነች ነገራቸው። ሣራ የአብርሃም አባት ከሌላ ሚስት የወለዳት ስለ ነበረች (ዘፍ. 20፡12) ይህ ማለቱ በከፊል እውነት ነው። ሣራ ሚስት እንድትሆነው ወደ ፈርዖን ቤት ተወሰደች። ይህ የሚያሳየው አብርሃም በእግዚአብሔር ላይ እምነት ማጣቱን ብቻ ሳይሆን፥ ቃል ኪዳኑን አደጋ ላይ እንደጣለው ነው። ፈርዖን ሣራን በሚስትነት ቢያስቀራት ኖሮ ለአብርሃም ከሣራ የሚገኝ ልጅና ሕዝብ ሊኖር አይችልም ነበር። እግዚአብሔር በዚህ መካከል ጣልቃ ሊገባና ሣራን ከፈርዖን እጅ ሊያድናት ይገባ ነበር። ይህም አብርሃም በእግዚአብሔር ላይ እምነት ያልጣለበት የመጀመሪያ ጊዜ ነበር።

ከብዙ ዓመታት በኋላ፥ አብርሃም በጌራራ ንጉሥ በአቤሜሌክ ፊት ይህንኑ ስሕተት ደገመው (ዘፍጥ. 20)። አብርሃም ስሕተቱን የሠራው በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ከሣራ ልጅ እንደሚያገኝ እግዚአብሔር ቃል ከገባለት ከጥቂት ጊዜ በኋላ ነበር። ይስሐቅ ከመወለዱ ጥቂት ቀደም ብሎ ሰይጣን ወደ አብርሃም ያመጣው ፈተና ነበር። ወደ ጌራራ ንጉሥ ዘንድ በሄደ ጊዜ ሣራ እኅቱ መሆንዋን ለሰዎቹ ነገራቸው። ይህም ንጉሡ ሣራን ሚስቱ አድርጎ ሊወስዳት ፈለገ። እግዚአብሔር ሣራ የአብርሃም ሚስት መሆንዋን ለንጉሡ በመንገርና በማስጠንቀቅ ቃል ኪዳኑን ከአደጋ ጠበቀው።

| |
|---|
| 29ኛ ጥያቄ፥ ዛሬስ እግዚአብሔር እንደሚጠብቀን በእርሱ በማመን ፈንታ፥ የራሳችንን ሕይወት ወይም ፍላጎታችንን ለመጠበቅ በመሞከር እነዚህን የመሰሉ ተመሳሳይ ፈተናዎች እንዴት እንጋፈጣቸዋለን? |

ሠ. ለወራሹ፥ ለይስሐቅ ተገቢ የሆነች ሚስት ያለማግኘት አደጋ፥ (ዘፍጥ. 24)

የአብርሃም የዘር ሐረግ እንዲቀጥል ይስሐቅ ሊያገባና ልጆችን ሊወልድ ይገባው ነበር፤ ነገር ግን ከአብርሃም አጠገብ ይኖሩ የነበሩት ሰዎች ሁሉ በአንዱ እውነተኛ አምላክ የማያምኑ ከነዓናውያን ነበሩ፤ ስለዚህ ይስሐቅ በካራን ካሉ ዘመዶቹ ዘንድ ማግኘት ነበረበት። ምናልባት

ይስሐቅ የካራንን ምድር ወዶ ሊቀር ይችላል የሚል ፍርሃት ስለ ነበረው አብርሃም ይስሐቅን ወደዚያ መላክ አልፈለገም። በሌላ በኩል ደግሞ በሰለጠነ ከተማ (በካራን) የኖረች ሴት፥ የነበረችበትን አገር ትታ የማታውቀውን ሰው ለማግባት በመቶ የሚቆጠሩ ኪሎ ሜትሮች ተጉዛ ትመጣለች ብሎ ማሰብም የሚያጠራጥር ነበር፤ ነገር ግን አብርሃም እግዚአብሔር ለልጁ ለይስሐቅ ትክክለኛዋን ሚስት ሊሰጠው እንደሚችል አመነ። አብርሃም አገልጋዩን ላከ፤ እግዚአብሔር ሥራውን ስለ ሠራ ርብቃ ወደ ከነዓን ለመምጣትና የይስሐቅ ሚስት ለመሆን ተስማማች።

30ኛ ጥያቄ፥ ሀ) ይስሐቅ የማታምን ሴት እንዳያገባ አብርሃም ያደረገው ጥንቃቄ በጣም አስፈላጊ የሆነው ለምንድን ነው? ለ) የገዛ ሚስቶቻችንንም ሆነ የልጆቻችንን ሚስቶች በጥንቃቄ ስለመምረጥ ይህ ታሪክ የሚያስተምረን ነገር ምንድን ነው? ሐ) የማይቻል በሚመስል ሁኔታ ውስጥ እንኳ እግዚአብሔር ትክክለኛ የትዳር ጓደኛ ሊሰጠን ስለመቻሉ ይህ ታሪክ ምን ያስተምረናል?

በአብርሃም ሕይወት ውስጥ ጠቃሚ የሆኑ ሌሎች በርካታ ታሪኮችም አሉ። በተለይ ደግሞ የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ተምሳሌት የሆኑ ሁለት ታሪኮች አሉ፡-

1. አብርሃም፥ የወንድሙን ልጅ ሎጥን ማርከው ወስደው የነበሩትን የሰሜን ነገሥታት አሸንፎ በሚመለስበት ጊዜ ከአንድ ልዩ ሰው ጋር ተገናኝቶ ነበር። ይህ ሰው በኋላ ኢየሩሳሌም የተባለችው የሳሌም ንጉሥ መልከ ጼዴቅ ነበር። አብርሃም ከጦርነቱ ምርኮ ከሆነው ሁሉ አንድ አሥረኛውን (አሥራት) ለዚህ ንጉሥ ሰጠው። ንጉሡም አብርሃምን ባረከው አከበረውም፤ (ዘፍጥ. 14፡17-24)።

31ኛ ጥያቄ፥ ዕብ. 6፡20-7፡24 አንብብ። ሀ) በእነዚህ ቁጥሮች መልከ ጼዴቅን ይመስላል የተባለለት ማን ነው? ለ) ከመልከ ጼዴቅ ጋር የሚመሳሰለው በምንድን ነው?

ስለ መልከ ጼዴቅ የምናውቀው ብዙ ነገር ባይኖርም፥ ወደ ዕብራውያን ሰዎች የተላከው መልእክት እርሱ የክርስቶስ ተምሳሌት ነው ይላል። «ተምሳሌት» በመጽሐፍ ቅዱሳችን የሚሰጠው ትርጉም አንድ የተለየ ድርጊት ወይም ሰው ወደፊት ስለሚመጣ ሰው ወይም ስለሚፈጸም ድርጊት ግልጽ የሆነ ምሳሌነት የሚያሳይ ነው። ለምሳሌ፡- የእስራኤል

ሕዝብ ከግብፅ ነፃ የመውጣት ታሪክ ከኃጢአት ነፃ የመውጣት ምሳሌ ነው። አዳም የሁለተኛው አዳም፥ የክርስቶስ ምሳሌ ነው (ሮሜ 5፡14)። በዚሁ ዓይነት፥ መልከ ጼዴቅም የሊቀ ካህናችን፥ የኢየሱስ ክርስቶስ ተምሳሌት ነበር። ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ መልከ ጼዴቅ ንጉሥም ሊቀ ካህንም ነው። መልከ ጼዴቅ ልክ እንደማንኛችንም ሰው በመሆኑ፥ የተወለደና የሞተ ቢሆንም፥ መቼ እንደተወለደና መቼ እንደሞተ አሪት ዘፍጥረት የሚያመለክተው አንዳችም ነገር የለም። ኢየሱስ ክርስቶስም፥ እንደ እግዚአብሔር ልጅ መጀመሪያና መጨረሻ የለውም። እርሱና የሊቀ ካህንነቱ ሥራ ዘላለማዊ ነው።

2. ይስሐቅ የ15 ዓመት ወጣት በሆነ ጊዜ እግዚአብሔር አብርሃምን ከእርሱና ከልጁ የላቀ ማንን እንደሚወድ ለማረጋገጥ ፈተነው። አንድ ልጁን ይዞ በሞርያም ተራራ እንዲሠዋለት እግዚአብሔር አብርሃምን አዘዘው (ዘፍ. 22)

| |
|---|
| 32ኛ ጥያቄ፥ ሀ) እግዚአብሔር ለአብርሃም ይህንን ፈተና የሰጠው ለምን ይመስልሃል? ለ) ዛሬም ለእኛ ሊሰጠን የሚችለውን ተመሳሳይ የፈተና ዓይነት ጥቀስ። |

አብርሃም ይህን ፈተና አልፎአል። ብዙ ኪሎ ሜትሮች ተጉዞ ወደ ሞርያም ተራራ በደረሰና ልጁን ለመሠዋት ቢላውን ባነሣ ጊዜ እግዚአብሔር በይስሐቅ ምትክ የሚሠዋ በግ ሰጠው።

ይህ በብዙ መንገድ የክርስቶስ ኢየሱስ ተምሳሌት ነው። ይስሐቅ የአብርሃም ብቸኛ ወይም ልዩ ልጅ እንደሆነ፥ ኢየሱስ ክርስቶስም የእግዚአብሔር አንድያ ልጁ ነው፤ (ዮሐ. 3፡16)። አብርሃም ልጁን-ይስሐቅን ይሠዋ ዘንድ እንደሰጠ፥ እግዚአብሔር አብም ልጁን ኢየሱስን ለዓለም ኃጢአት መሥዋዕት አድርጎ ሰጠ። ይህም ቢሆን እንኳ በሁለቱ ታሪኮች መካከል ከፍተኛ ልዩነት አለ። እግዚአብሔር አብርሃምን፥ ልጁን እንዲሠዋ የከለከለው ሲሆን፥ የገዛ ልጁ በመስቀል ላይ እንዲሞት ግን ፈቅዷል። አብርሃም ልጁን ለመሠዋት የወሰደው ወደ ሞርያም ማለትም ወደ ጽዮን ተራራ ሲሆን፥ ኢየሱስ ለኃጢአታችን የሞተውም በሞርያም ወይም በጽዮን ተራራ ነው። ይስሐቅ ወጣት ልጅ እንደመሆኑ መጠን አባቱ መሥዋዕት አድርጎ እንዳያቀርበው መከላከል እና እምቢ ማለት ሲችል፥ በጸጥታ በመታዘዝ ለመሠዋት እንደፈቀደ ሁሉ፥ ኢየሱስም

እግዚአብሔር አብ ይሠዋ ዘንድ ለወሰነው ውሳኔ በፈቃደኝነት ታዘዘ። በገዛ ፈቃዱ ሕይወቱን ሰጠ።

3. «የእግዚአብሔር መልአክ» መታየት። በአማርኛ መጽሐፍ ቅዱሳችን፥ በብሉይ ኪዳን:- «የጌታ መልአክ» ተብሎ የተጠራ ልዩ የሆነ መልአክ መኖሩን መለየት አስቸጋሪ ነው። ይህ መልአክ በዘፍጥረት፥ በዘጸአት፥ በዘኁልቁ፥ በ1ኛና በ2ኛ ሳሙኤል፥ በ1ኛና በ2ኛ ነገሥት እንዲሁም በ1ኛና በ2ኛ ዜና መዋዕል ውስጥ ተጠቅሷል። በኦሪት ዘፍጥረት ይህ መልአክ ከአጋር (ዘፍጥ. 16፡7-14፤ 21፡16-20)፥ ከአብርሃም (ዘፍጥ. 18፤ 22፡10-18)እና ከያዕቆብ (ዘፍጥ. 31፡11-13) እንደተገናኘ ተጠቅሷል። ይህ ልዩ የጌታ መልአክ ማን ነው? ስለዚህ መልአክ የተጠቀሱትን የተለያዩ ጥቅሶች ስንመረምር ወደሚከተሉት እውነቶች እንደርሳለን:-

ሀ. የጌታ መልአክ ከእግዚአብሔር የተለየ ነው። ይህን ስንል የጌታ መልአክ ስለ እግዚአብሔር ስለሚናገር እርሱ ከእግዚአብሔር የተለየ ሰብዕና አለው ማለታችን ነው።

ለ. የጌታ መልአክ ከእግዚአብሔር እንደሆነ ተጠቅሷል። ለምሳሌ:- አጋር ከጌታ መልአክ ጋር ከተነጋገረች በኋላ እግዚአብሔርን አየሁት አለች፤ (ዘፍጥ. 16፡10)።

ሐ. ይህ የጌታ መልአክ ይታያል ደግሞም ወዲያውኑ ይሰወራል። ግለሰቦች ወይም የእስራኤል ሕዝብ የእርሱ እርዳታ በሚያስፈልጋቸው በተወሰኑ ጊዜያት ይታይና ተግባሩን ከፈጸመ በኋላ ይሄዳል።

አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁራን፥ ይህ መልአክ በእግዚአብሔር ተልኮ የአንዳንድ ሰዎችን ወይም የእስራኤልን ሕዝብ እርዳታ በሚያስፈልጋቸው ነገር ሁሉ የሚረዳ አንድ ልዩ መልአክ ነው ብለው ያስባሉ። እግዚአብሔር ተብሎ የተጠራውም እንደ እግዚአብሔር መልእክተኛ ሆኖ የሚመጣና የእግዚአብሔር ተወካይ መሆኑ የታወቀ ስለሆነ ነው ይላሉ። ሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁራን ደግሞ ይህ መልአክ እግዚአብሔር ነው፤ እንዲያውም በአዲስ ኪዳን ሥጋ ከመልበሱ በፊት በብሉይ ኪዳን የተጠቀሰውን - ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ያመለክታል ይላሉ። ዘላለማዊ የሆነው የእግዚአብሔር ልጅ በብሉይም ሆነ በአዲስ

ኪዳን በሥራ ላይ እንደነበረና በምድር ላይ ለተወሰነ ጊዜ ብቻ ለሰዎች እየተገለጠ ይሰወር እንደነበር የሚያመለክት ይመስላል።

የአብርሃም ሕይወት የጊዜ ቅደም ተከተል


| በአብርሃም ሕይወት በጣም ዋና ዋና የሆኑ ታሪካዊ ድርጊቶች | የአብርሃም ዕድሜ |
|---|---|
| 1. አብርሃም በ2166 ዓ.ዓ. አካባቢ ተወለደ | |
| 2. አብርሃም ካራንን ትቶ ወደ ከነዓን ተጓዘ | 75 ዓመት |
| 3. የእስማኤል መወለድ | 86 ዓመት |
| 4. እግዚአብሔር የገዘረትን ቃል ኪዳንና የይስሐቅን መወለድ ተስፋ ሰጠው | 99 ዓመት |
| 5. የይስሐቅ መወለድ | 100 ዓመት |
| 6. የአብርሃም ይስሐቅን ለመሠዋት ማቅረብ | በግምት ወደ 115 ዓመት ይሆናል |
| 7. አብርሃም በ1991 ዓ.ዓ. አካባቢ ሞተ | 175 ዓመት |

ከአብርሃም ጋር የተገባው ቃል ኪዳን ለብሉይ ኪዳን ታሪክ ያለው አስፈላጊነት፡-

የአብርሃምን ሕይወት ጠቃሚነትና በመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ውስጥ ያለውን ሁኔታ ደጋግመን ብንገልጠውም አጥጋቢ አይሆንም። እግዚአብሔር ከአብርሃም ጋር የገባው ቃል ኪዳን ብሉይ ኪዳንን የምንረዳበትና የእስራኤልን ሕዝብ አስፈላጊነት የምንመዝንበት መሠረት ነው። ትንቢትን የምንረዳበት መሠረትም ነው። ለምሳሌ፡- እግዚአብሔር ከአብርሃም በኋላም ከእስራኤል ጋር ያደረገው ቃል ኪዳን በምንም ቅድመ ሁኔታ ላይ ያልተመሠረተ ነው ብለን ካመንን፥ ወደ ፊት ለእስራኤል ሕዝብ እግዚአብሔር ቃል ኪዳኖቹን ያከብራል። ቃል ኪዳኖቹ በቅድመ ሁኔታዎች ላይ እንደተመሠረቱ አድርገን ወይም የሚፈጸሙት በመንፈሳዊ ትርጓሜ በክርስቲያኖችና በቤተ ክርስቲያን ብቻ ነው ብለን ካመንን እስራኤል ከእንግዲህ ወዲህ በእግዚአብሔር ዕቅድ ውስጥ ስፍራ የላትም ማለታችን ነው።

እግዚአብሔር ከአብርሃም ጋር ያደረጋቸው እነዚህ የተስፋ ቃላት የብሉይ ኪዳኖች ታሪኮች የተመሠረቱባቸው መሠረቶች ናቸው።

የአብርሃምን ሕይወት ለማጥናት በርከት ያለ ጊዜ የወሰድነው ለዚህ ነው። የሚከተለውን ሥዕላዊ መግለጫ ተመልከት፡-




ከፍ ብሎ ከምንመለከተው ሥዕል እንደምንረዳው የብሉይ ኪዳን ታሪክ የተመሠረተው ከአብርሃም ጋር በተደረገ ቃል ኪዳን ላይ ነው። በቃል ኪዳኑ ውስጥ የብሉይ ኪዳንን ታሪክ እንደምሰሶ ሆነው የሚደግፉ ሦስት ዋና ዋና ነገሮች ነበሩ። የመጀመሪያው፥ አይሁድ የእግዚአብሔር ምርጥ ሕዝብ መሆናቸው ነው። ከሌላው ሕዝብ ጋር ካለው ከየትኛውም ዓይነት ቃል ኪዳን በተለየ ሁኔታ እግዚአብሔር ከእስራኤል ሕዝብ ጋር ቃል ኪዳን አለው። ሁለተኛው፥ የከነዓን ምድር ከእግዚአብሔር ዘንድ ለአይሁድ እንደተሰጣቸው የተገባ ተስፋ መኖሩ ነው። ሦስተኛው፥ ደግሞ ከአብርሃም ዘር ነገሥታት እንደሚነሡ የተሰጠው ተስፋ ነው። በኋላ እንደምናየው፥ እነዚህ ነገሥታት የሚመጡት ከይሁዳ ዘር በተለይ ደግሞ ከዳዊት ዘርያ ነው።

እግዚአብሔር ከአብርሃም ጋር ስለገባው ቃል ኪዳን ልንመለከታቸው የሚገቡ ሌሎች ሁለት እውነቶች አሉ። 1) እግዚአብሔር አሕዛብ በሙሉ በዘሩ እንደሚባረኩ ለአብርሃም ተስፋ ሰጥቶት ነበር። ይህ በረከት በተለያየ መልክ መጣ። እግዚአብሔር ራሱን ለሰው ልጅ ለመግለጥ አይሁድን ተጠቀመ። ምክንያቱም መጽሐፍ ቅዱስ በሙሉ የተጻፈው በአይሁድ

ስለሆነ ነው። የሚያምኑትን ሁሉ የሚያድነው - ጌታ ኢየሱስ በትውልዱ አይሁዳዊ ነው። 2) አብርሃም የእውነተኛ አማኞች ሁሉ አባት ነው። እንደ አብርሃም በእግዚአብሔር የሚያምኑ ሁሉ እግዚአብሔር ጻድቃን አድርጎ ይቀበላቸዋል። ከዚያም የአብርሃም መንፈሳዊ ልጆች ይሆናሉ።

| 33ኛ ጥያቄ፥ የአብርሃም መንፈሳዊ ልጅ የሆንከው መቼ ነው? |
|---|

5ኛ ቀን፡- የዚህን ሳምንት ትምህርት ከልስ። ለሳምንታዊው ስብሰባ ዝግጅት ይረዳህ ዘንድ የውይይት ጥያቄዎችን ተመልከት።

## ሳምንታዊ ስብሰባ

1. የሳምንቱ የአምልኮ ጊዜ
2. ጸሎት
3. የትምህርቱ ክለሳ
4. ውይይት

ሀ. 1) ስለ ዓለም አጀማመር ሰዎች በሚከተሉአቸው አምስት የተለያዩ አመለካከቶች ላይ ተወያዩ።

2) እነዚህን የተለያዩ አመለካከቶች በተናጠል የምታውቃቸውን ሰዎች በምሳሌነት አቅርብ።

3) በኦሪት ዘፍጥረት 1-2 ስለ እግዚአብሔር የምናገኘው ዋና ትምህርት ምንድን ነው?

ለ. 1) ሰው «በእግዚአብሔር አምሳል» ነው የተፈጠረው ስንል ምን ማለት እንደሆነ የሚመስልህን ሁሉ ጥቀስ።

2) ይህ የእግዚአብሔር አምሳል ዛሬ በሰዎች ሕይወት ውስጥ የሚታየው እንዴት ነው?

3) አዳምና ሔዋን በኃጢአት በወደቁ ጊዜ በእግዚአብሔር አምሳል ከተፈጠረው የሰው አካል የተበላሸው የትኛው ነበረ?

4) በኢየሱስ ስናምን ከዚህ አምሳል የሚታደሰው የትኛው ክፍል ነው?

5) ከዚህ አምሳል በመንግሥተ ሰማያት ብቻ ሙሉ ለሙሉ መታደስ የሚችለው የትኛው ነው?

ሐ. 1) የአዳምና የሔዋን ኃጢአት ዛሬ የሚጠናወተን እንዴት ነው?

2) እግዚአብሔር በመጀመሪያው ኃጢአት ላይ የሰጣቸው አራት ፍርዶች ዛሬ በዚህ ዓለም የሚታዩት እንዴት ነው?

3) እነዚህ አራት ፍርዶች ከሰው ልጅና ከዓለም ላይ የሚነሡት መቼ ነው?

መ) 1) የአብርሃም ሕይወት ለመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ በጣም አስፈላጊ የሆነው ለምንድን ነው?

2) ስለ እምነት ጉዞ ከአብርሃም ሕይወት የምንማረው ነገር ምንድን ነው? (አዎንታዊውንም ሆነ አሉታዊውን ምሳሌ ጥቀስ)።

3) እግዚአብሔር ለአብርሃም በገባው ቃል ኪዳን ውስጥ የሰጣቸውን ተስፋዎች ጥቀስ።

4) ከእነዚህ ተስፋዎች መካከል ዛሬም በሕይወታችን ውስጥ ድርሻ ያላቸው የትኞቹ ናቸው? እንዴት?

ሠ. 1) ዛሬ እኛ የምንድንበት መንገድ አብርሃም ከዳነበት ዓይነት መንገድ ጋር (ዘፍጥ. 15፥6) የሚመሳሰለው እንዴት ነው?

2) የኦርቶዶክስ ክርስቲያኖች፥ ሙስሊሞችና ሌሎች አንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት ደኅንነት በመልካም ሥራ እንደሚገኝ የሚናገሩት በምን ዓይነት መንገድ ነው ?

5. ጸሎት

# ትምህርት 5

## ዘፍጥረት 25-50

### 1ኛ ቀን፡- ዘፍጥረት 25-36 የይስሐቅና የያዕቆብ ታሪክ

እስካሁን ድረስ በኦሪት ዘፍጥረት ጥናታችን ውስጥ ሁለት ዋና ዋና ክፍሎች እንዳሉ ተመልክተናል። በመጀመሪያ፥ ከአይሁድ ሕዝብ አጀማመር በፊት ያሉትን ጊዜያት በአጭሩ የሚያካትተውን - ከዘፍጥ. 1-11 ያለውን ክፍል፥ በሁለተኛ፥ ደረጃ ደግሞ የአይሁድ ሕዝብ ራስ የሆነውን የአብርሃምን ታሪክ የሚያሳየውን - ከዘፍጥ. 12-24 ተመልክተናል። በተጨማሪ ለአብርሃም በተአምራት የተወለደለትን ይስሐቅ የተባለውን ልጁን ታሪክ መመልከት ጀምረናል።

ዛሬ ደግሞ የአብርሃም ልጅና የልጅ ልጅ ስለሆኑት ስለ ይስሐቅና ስለ ያዕቆብ መመልከት እንጀምራለን።

| |
|---|
| 1ኛ ጥያቄ፥ ከዘፍጥረት 25-36 ያለውን ክፍል አንብብ። ሀ) ከእነዚህ ምዕራፎች ስለ ይስሐቅ የምንማረው ነገር ምንድን ነው? ለ) ከእነዚህ ምዕራፎች ስለ ያዕቆብ የምንማረው ነገር ምንድን ነው? ሐ) በእነዚህ ምዕራፎች ውስጥ ቃል ኪዳኑን አደጋ ላይ ጥለውት የነበሩት ነገሮች ምንድን ናቸው? መ) በእነዚህ ምዕራፎች እግዚአብሔር ቃል ኪዳኑን ያስተላለፈውና የጠበቃቸው እንዴት ነው? ሠ) የዚህ ክፍል ዋና ዋና ትምህርቶችን ዘርዝር። ረ) ከእነዚህ ምዕራፎች ስለ እግዚአብሔር የምንማራቸውን አንዳንድ ነገሮች ጥቀስ። ሰ) ከእነዚህ ምዕራፎች በእምነት ስለ መራመድ የምንማራቸው ነገሮች ምንድን ናቸው? |

### 2ኛ ቀን፡-

ኦሪት ዘፍጥረት የአብርሃም ልጅ ስለሆነው ስለ ይስሐቅ ብዙ ነገሮችን አይነግረንም። እጅግ በጣም ታዛዥ ልጅ እንደነበረ የምናውቀው አብርሃም ሊሠዋው በነበረ ጊዜ በፈቃደኝነት በአባቱ ላይ በመታመን ሲታዘዝ በማየታችን ነው። የይስሐቅ ታሪክ ለያዕቆብ ታሪክ እንደመግቢያ ሆኖ የሚያገለግለን ነው። ያዕቆብ የ12ቱ የእስራኤል ነገዶች አባት በመሆኑ፥ ለአይሁድ ሕዝብ በጣም አስፈላጊ ሰው ነበር። ሙሴ፥ የአብርሃምን ታሪክ በመንገር የእስራኤልን ሕዝብ እንዴት እንደነበር ካሳየን በኋላ አሁን ደግሞ 12ቱ የእስራኤል ነገዶች እንዴት እንደተመሠረቱ ሊጠቁመን

ይጀምራል። የፔንታቱክ ታሪክ እምብርት እግዚአብሔር ከእስራኤል ሕዝብ ጋር በራሱ አነሣሽነት የመሠረተው ቃል ኪዳን መሆኑን አስታውስ።

## ይስሐቅ

ከዘፍጥረት 25-36 ድረስ ቃል ኪዳኑ አደጋ ላይ ወድቆ የነበረባቸውን የሚከተሉትን ሁኔታዎች ተመልከት፡-

1. ሌሎቹ የአብርሃም ልጆች ለይስሐቅ መተላለፍ የነበረበትን ቃል ኪዳን አደጋ ላይ ጥለውት ነበር። ቃል ኪዳኑ መተላለፍ ያለበት በተአምራት ለተወለደው ለተስፋው ልጅ፥ ለይስሐቅ እንጂ ለሌሎቹ አልነበረም (ዘፍጥ. 25፡1-18)። አብርሃም ሌሎች ልጆችም ነበሩት። የአብርሃምና የአጋር የመጀመሪያ ልጅ እስማኤል ነበር። ለይስሐቅ የተሰጡት የቃል ኪዳን ተስፋዎች ችግር እንዳይገጥማቸው አብርሃም እስማኤልን አስቀድሞ ከቤቱ አስወጥቶት ነበር (ዘፍጥ. 21፡8-21)። ሁለተኛ፥ ከሣራ ሞት በኋላ አብርሃም ካገባት ኬጡራ ከምትባል ሴት የወለዳቸው 6 ወንዶች ልጆች ነበሩት። አብርሃም፥ ከመሞቱ በፊት ስጦታ በመስጠት እነዚህን ስድስት ልጆቹን አሰናበታቸው። ይህም በርስት ጉዳይ ከይስሐቅ ጋር እንዳይጣሉ ታስቦ የተደረገ ነው።
2. የይስሐቅ ልጅን ያለ መውለድ አደጋ፡- ይስሐቅ ቃል ኪዳኑን የሚያስተላልፍለትና ርስቱን የሚወርሰው ልጅ እንደማይኖረው ያስመሰሉ ሁለት ምክንያቶች ነበሩ። በመጀመሪያ፥ እንደ ሣራ ሁሉ ርብቃም መካን ነበረች፤ ነገር ግን በኋላ እግዚአብሔር ዔሳውና ያዕቆብ የተባሉ ሁለት ልጆችን ሰጣት። ሆኖም እነዚህ ልጆች በሚወለዱበት ጊዜ እንኳ ሲጣሉ የነበሩና በሕይወታቸው ዘመንም ሁሉ እየተጣሉ የሚኖሩ ሆኑ። ከመወለዳቸው አስቀድሞ እግዚአብሔር የቃል ኪዳኑን መስመር የሚቀጥለው ሰው ታናሹ (ያዕቆብ) እንጂ ታላቁ (ዔሳው) አይሆንም በማለት ተንብዮ ነበር። እግዚአብሔር አሁንም ዓላማውን ከግቡ ለማድረስ ከሕዝቡ ባሕልና ከወላጆቻቸው ፍላጎት ተቃራኒ በሆነ መንገድ ተጓዘ (ዘፍጥ. 25፡19-23)።

ሁለተኛው አደጋ ደግሞ ርብቃ የሌላ ሰው ሚስት ልትሆን ነበር(ዘፍጥ. 26)። የዘፍጥረት 26 ታሪክ ከዘፍጥ. 25፡19-21 በፊት የተፈጸመ ሳይሆን አይቀርም። አብርሃምና ይስሐቅ ተመሳሳይ ድክመት

ነበራቸው። ይስሐቅም በባዕድ አገር በተገኘ ጊዜ እግዚአብሔር ሕይወቱን ሊጠብቅለት እንደሚችል ማመንና በእግዚአብሔር መደገፍ አቃተው። ይስሐቅ በፍልስጥኤማውያን ምድር ለመኖር ሄደ። ልክ እንደ አብርሃም የሚስቱን ማንነት ላለመናገር ዋሸ። ሣራ፥ ታራ ከሌላ ሴት የወለዳት የአብርሃም ግማሽ እኅቱ ስለነበረች፥ እኅቴ ናት ብሎ በከፊል ዋሽቶ ነበር። ይስሐቅ ግን ርብቃ የአጎቱ የልጅ ልጅ ስለነበረች እኅቴ ናት ብሎ ሲናገር ሙሉ በሙሉ ዋሸ። ርብቃ የሌላ ሰው ሚስት ትሆን ዘንድ ተወስዳ ቢሆን ኖሮ ይስሐቅ ቃል ኪዳኑን ሊያስተላልፍለት የሚችል አንዳችም ልጅ አይኖረውም ነበር። እግዚአብሔር ግን በዚህ ድርጊት መካከል ጣልቃ ገባና ርብቃን የሌላ ሰው ሚስት ከመሆን አዳናት።

> 2ኛ ጥያቄ፥ ስሕተት ብንሠራም እንኳ እግዚአብሔር እንደሚረዳንና የተስፋ ቃሉንም እንደሚጠብቅልን መገንዘባችን በዚህ ዘመን ላለን ለእኛ ምን ያህል ማበረታቻ ይሆንናል?

ዘፍጥ. 26 እጅግ ጠቃሚ ክፍል የሆነበት ሌላ ምክንያት አለ። በዘፍጥ. 26 ሁለት ስፍራዎች ላይ እግዚአብሔር ለአብርሃም የሰጠውን የተስፋ ቃል በማረጋገጥ፥ እነዚያው ተመሳሳይ ተስፋዎች ለይስሐቅ እንደተላለፉለት ያሳየዋል (ዘፍጥ. 26፡3-5፥ 23-24)።

3. የተስፋው ወራሽ የሆነው ያዕቆብ በዔሳው የመገደል አደጋ (ዘፍጥ. 25፡19-34፥27፡1-41)

ያዕቆብና ዔሳው በሚወለዱበት ጊዜ ባሕርያቸው ተወስኖ ነበር። ያዕቆብና ዔሳው ሲወለዱ እንኳ እየተጋፉ ነበር የተወለዱት። ያዕቆብ የኖረው ልክ እንደስሙ ትርጉም ነው። ያዕቆብ ማለት «አታላይ» ወይም «አደናቃፊ» ማለት ነው። ያዕቆብ በሚወለድበት ጊዜ እንኳ የወንድሙን ተረከዝ ይዞ በመውጣት ሊያደናቅፈው ሞክሮ ነበር። በሕይወቱ ዘመን ሁሉ ለወጣለት ስም በመኖር ዔሳውን ኋላም ላባን ሲያታልልና ሲያደናቅፍ ኖሯል።

በጊዜው በነበረው ባሕል መሠረት ታላቁ ልጅ ዔሳው የይስሐቅ ወራሽ መሆን ነበረበት። በእግዚአብሔር ዓላማ መሠረት ግን ያዕቆብ ወራሽ ሆኗል። ያዕቆብ ወራሽ መሆኑን ያውቅ እንደ ነበር አንዳችም ጥርጥር የለም፤ ነገር ግን ያዕቆብ እግዚአብሔር ይህንን በረከት እስኪሰጠው ድረስ እንደመታገሥ የዔሳውን ብኩርና ለመስረቅ ዓቀደ። በመጀመሪያ፥ ያዕቆብ

የዔሳውን ራብ ተጠቅሞ በጥቂት ምግብ ብኩርናውን ማለትም የይስሐቅ ወራሽ የመሆን መብት ገዛ። ሁለተኛ፥ ዔሳውን መስሎ አባቱን በመቅረብ ለወንድሙ የሚገባውን በረከት በመረከብ የማታለል ተግባር ፈጸመ፤ (ዘፍጥ. 27)። በረከቱ እግዚአብሔር ለአብርሃም የገባለትን ቃል ኪዳን ሁሉ የመውረስ መብትን ይጨምራል። በረከቱን ለያዕቆብ መስጠት የእግዚአብሔር ዕቅድ መሆኑን ይስሐቅና ርብቃ ቢያውቁም፥ እርሱን ከመታዘዝና ከመደገፍ ይልቅ ይስሐቅ የብኩርና መብትን ለሚወደው ልጁ-ለዔሳው ለመስጠት ሞከረ። ርብቃ ደግሞ ባሏ የሚታለልበትን መንገድ በማዘጋጀት የብኩርናውን መብት እርሷ ለምትወደው ልጇ- ለያዕቆብ ለማድረግ ፈለገች። እግዚአብሔር ግን ሁኔታዎቹን ሁሉ በመቆጣጠር የራሱ ዕቅድ እንደተፈጸመ አየ። በረከቱና የቃል ኪዳኑ በረከቶች በሙሉ ለያዕቆብ ተላለፉ።

3ኛ ጥያቄ፥ የወላጆች አንድ ልጃቸውን ከሌላው አስበልጠው መውደድ በቤተሰብ ውስጥ ሊፈጥር ስለሚችለው አደጋ ይህ ታሪክ ምን ያስተምረናል?

ዔሳው መታለሉን በተገነዘበ ጊዜ፥ ያዕቆብን ለመግደል ወሰነ። ይህም ነገር ያዕቆብ ከከነዓን ወደ ካራን እንዲሸሽ አደረገው። ከ20 ዓመት በኋላ ያዕቆብ ወደ ከነዓን ሲመለስ፥ ዔሳው እርሱን የመግደል አሳቡን ለመፈጸም ጥሩ አጋጣሚ ሆነለት። እግዚአብሔር ግን የዔሳውን ልብ ለወጠና ያዕቆብን እንደ ወንድም ተቀበለው፤ (ዘፍጥ. 33)።

4. ያዕቆብ በካራን ምድር በነበረበት ጊዜ የገጠመው አደጋ:-

የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን እንዳይፈጸም ዕንቅፋት ሊሆኑ የሚችሉ ሁለት ዋና ዋና አደጋዎች ያዕቆብን በካራን ምድር ገጥመውት ነበር። የመጀመሪያው፥ ያዕቆብ ወደ ተስፋይቱ ምድር ወደ- ከነዓን እንዳይመለስ የከለከለው አደጋ ነበር፤ (ዘፍጥ. 28-30)። በካራን ምድር ባለጸጋ ሆነ። ያዕቆብ ከከነዓን ወደ ካራን በሚጓዝበት ጊዜ እግዚአብሔር በቤቴል ተገናኘው። በሕልሙም እግዚአብሔር ሁለት ነገሮችን አሳውቆት ነበር:- 1) እግዚአብሔር በረከቱን የሚፈጽምለት በተስፋይቱ ምድር እንደሚሆን አስታወሰው። 2) የቃል ኪዳኑን በረከት አስቀድሞ ለአብርሃምና ለይስሐቅ እንደሰጠ አሁን ለያዕቆብ አስተላለፈለት፤ (ዘፍጥ. 28:12-15)። በባዕድ አገር በሚኖርበት ጊዜም ከእርሱ ጋር እንደሚሆን በመንገር አበረታታው።

ያዕቆብ ወደ ተስፋይቱ ምድር እንዳይመለስ ሊያደርገው የሚችለው አደጋ ካራን በደረሰ ጊዜ እየጨመረ መጣ። በመጀመሪያ ለሁለቱ ሚስቶቹ - ለልያና ለራሔል ሲል 14 ዓመታት ተገዛ። ሁለተኛ ደረጃ ደግሞ ለአማቹ ለላባ ቁሳቁሳዊ የሆነ ሀብትና ንብረት ለማስገኘት ብሎ ተጨማሪ 6 ዓመታት ተገዛ።

እግዚአብሔር ግን አታላዩን ያዕቆብን መለወጥ የጀመረው በካራን ምድር ነበር። ያዕቆብ ከእርሱ የባሰ አታላይ የሆነ አጎት አጋጠመው፥ እርሱም ላባ ነበር። እግዚአብሔር ሌላውን ሰው ለማጭበርበርና ቁሳቁሳዊ በረከት ለማግኘት የራስን ጥበብና የማታለል ዘዴ መጠቀም ከንቱ ጥረት መሆኑን ለያዕቆብ ለማሳየት ሲል ላባን ተጠቀመበት።

ከ12ቱ የያዕቆብ ልጆች 11ዱ የተወለዱት በካራን ነበር። ብንያም ግን የተወለደው ቆይቶ በከነዓን ምድር ነበር።

ሀ. የልያ ልጆች፡- ሮቤል፥ ስምዖን፥ ሌዊ፥ ይሁዳ፥ ይሳኮር፥ ዛብሎን

ለ. የራሔል አገልጋይ የሆነችው የባላ ልጆች፡- ዳን፥ ንፍታሌም

ሐ. የልያ አገልጋይ የሆነችው የዘለፋ ልጆች፡- ጋድ፥ አሴር

መ. የራሔል ልጆች፡- ዮሴፍ፥ ብንያም ናቸው።

** ማስታወሻ 1) ራሔልና ልያ ከአገልጋዮቻቸው ልጅ ለማግኘት በጊዜያቸው የነበረውን ባሕል ተጠቅመዋል። የአገልጋዮቻቸው ልጆች በሕግም አንፃር እንደ ራሳቸው ልጆች ይቆጠሩ ነበር።

2) የራሔል የመጨረሻ ልጅ ብንያም ወደ ከነዓን በገቡ ጊዜ ተወለደ። ዳሩ ግን ለራሔል ሞት ምክንያት ሆነ። ራሔል ብንያምን በምትወልድበት ጊዜ ሞተች።

3) ብሉይ ኪዳን አንድ ሰው ሊኖረው የሚገባው አንድ ሚስት ብቻ እንደሆነ በቀጥታ አያስተምርም ነበር። ነገር ግን አንድ ወንድ ከአንዲት ሴት ጋር ብቻ የሚፈጽመው ጋብቻ በሁለት ምክንያት ከሁሉ የተሻለ እንደሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ያስተምረናል። በመጀመሪያ፥ እግዚአብሔር አዳምን ሲፈጥር የሰጠው አንዲት ሴትን እንጂ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ አይደለም። ሁለተኛ፥ ከአንድ በላይ

ሚስቶች በሚኖሩበት ቤተሰብ ውስጥ ብዙ ጊዜ በሚስቶቹና በልጆቻቸው መካከል በሚፈጠር ቅንአት ምክንያት የማያቋርጥ ችግር ይከሰታል። በአዲስ ኪዳን ግን እግዚአብሔር በግልጥ ሕዝቡ አንድ ሚስት ብቻ እንዲኖራቸው አስተምሯል (1ኛ ጢሞ. 3፡2፥12)።

እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳን ከአንድ ሚስት በላይ ማግባትን በቀጥታ በመቃወም ለምን አልተናገረም? ለዚህ ምክንያቱ «በየጊዜው የሚሆን መገለጥ» ወይም «የገለጣ እድገት» ተብሎ የሚጠራው ነገር ነው። እግዚአብሔር ስለ ማንነቱ ከሰዎችም ምን እንደሚፈልግ ሁሉንም ነገር በአንድ ጊዜ አልሰጠም። ነገር ግን በዘመናት ሁሉ እግዚአብሔር ራሱንና ፈቃዱን ቀስ በቀስ እየጨመረና እያደገ በሚሄድ እውቀት በትዕግሥት ገልጧል። በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር ትኩረት ሰጥቶ ይገልጠው የነበረው፡- ሊመለክ የሚገባው ብቸኛውና እውነተኛው አምላክ እርሱ ብቻ እንደሆነና ሕዝቡ ሌሎች አማልክትን እንዳያመልኩ ነበር። ቆይቶ በአዲስ ኪዳን እግዚአብሔር አስቀድሞ አንድ ወንድ ከአንዲት ሚስት ጋር ብቻ እንዲኖር ያወጣውን ዕቅድ ይበልጥ ግልጥ አደረገው (1ኛ ጢሞ. 3፡2፥12)።

<u>4ኛ ጥያቄ፥ የአሥራ ሁለቱን የያዕቆብ ልጆች ስም በቃልህ አጥና። ከያዕቆብ ታሪክ ልጆችን ስለማሳደግ የምንማረው ነገር ምንድን ነው?</u>

ያዕቆብ በካራን እያለ የገጠመው ሁለተኛ አደጋ ከላባና ከቤተሰቡ ጋር የገጠመው ጠላትነት ነበር። እግዚአብሔር ያዕቆብን በቁሳቁሳዊ ነገር ስለባረከው ሀብታም ሆነ። ያዕቆብ እጅግ የተሳካለት ሰው ስለሆነ የሚስቶቹ ቤተሰቦች ቀኑበት። ላባም በያዕቆብ ድካም በመጠቀም ሊያጭበረብረው ሞከረ። በውጤቱም ያዕቆብ ላባን አጭበረበረው፤ የበለጡ ከብቶችንም አገኘ። በመጨረሻም ያዕቆብ ሕይወቱን ለማዳን መሸሽ ነበረበት። ላባም ያዕቆብን ሊይዘውና ሊገድለው ፈለገ። ዳሩ ግን ሁለቱ ሰዎች ከመገናኘታቸው በፊት ያዕቆብን እንዳይነካው እግዚአብሔር ላባን አስጠነቀቀው፤ (ዘፍጥ. 30፡25-31፡55)።

5. ያዕቆብና ቤተሰቡን ከሴኬማውያን በኩል አጋጥሞአቸው የነበረው አደጋ (ዘፍጥ. 34)፡- ያዕቆብ ወደ ከነዓን በተመለሰ ጊዜ ከከነዓን ወጣ ብላ በምትገኝ ሴኬም በምትባል ከተማ ይኖር ጀመር። የዚያች ከተማ መሪ የነበረው ሰው ልጅ የያዕቆብን ሴት ልጅ ደፈራት። በምላሹ የያዕቆብ ልጆች ሴኬማውያንን አታለሉአቸውና በከተማው

ውስጥ ያሉትን ወንዶች በሙሉ ገደሏቸው። ይህም የቀሩትን ከነዓናውያንን ቁጣ ሊያስከትል የሚችል በመሆኑ ያዕቆብን አደጋ ላይ ጣለው። በዚህ ጊዜ የእስራኤላውያን ቤተሰብ ቁጥር በጣም ጥቂት ነበር።

በዚህ ክፍል ውስጥ የሚገኙ ሌሎች አስፈላጊ እውነቶች፡-

1. ያዕቆብ ከእግዚአብሔር መልአክ ጋር ታገለ፤ (ዘፍጥ. 32፡22-31)። ያዕቆብ ከካራን ተመልሶ ከዔሳው ጋር ሊገናኝ ሲል በድንገት ከእግዚአብሔር መልአክ ጋር ተገናኘና ታገለ። ይህ መልአክ ባለፈው ሳምንት ያጠናነው ልዩ የእግዚአብሔር መልአክ ይመስላል። ለመጀመሪያ ጊዜ ያዕቆብ ከሥጋዊ በረከት ይልቅ መንፈሳዊ በረከትን ፈለገ። ለመጀመሪያ ጊዜ የበረከቱ ምንጭ የእርሱ ጥበብና ችሎታ ሳይሆን እግዚአብሔር መሆኑን አመነ። ከእግዚአብሔር ጋር የጀመረውን ይህን ግንኙነቱን ለማመልከት ስሙ «እስራኤል» ተብሎ ተለወጠ። እስራኤል ማለት «ከእግዚአብሔር ጋር የሚታገል» ማለት ነው። ይህ አዲስ ስም ቆይቶ የአይሁዳውያን ሁሉ መጠሪያ ሆነና ሕዝቡ እስራኤላውያን ተባሉ። ይህ ስም ለአይሁድ ሕዝብም የሚስማማ ነው። ምክንያቱም በአሉታዊ መልኩ በታሪካቸው ሁሉ አይሁድ ከእግዚአብሔር ጋር የሚታገሉ፥ እግዚአብሔርን ለመከተልና ለመታዘዝ የማይፈልጉ በመሆናቸው ነው።።

| |
|---|
| 5ኛ ጥያቄ፥ ሀ) የያዕቆብ ሕይወት ከአንተ የእምነት እርምጃ ጋር የሚመሳሰለው እንዴት ነው? ለ) ከያዕቆብ ታሪክ ስለመንፈሳዊ ነገሮች የምንማረው ምንድን ነው? |

2. በአሪት ዘፍጥረት የአጻጻፍ ባሕርይ መሠረት፥ ሙሴ የተመረጠውን የአይሁድን ሕዝብ ታሪክ ከመቀጠሉ በፊት ያልተመረጡትን የሌሎቹን ሕዝቦች የትውልድ ታሪክ ይተነትናል። ሙሴ የይስሐቅን ታሪክ ከመናገሩ በፊት የእስማኤልን የትውልድ ታሪክ እንደሰጠ ቀደም ሲል ተመልክተናል፤(ዘፍጥ. 25፡12-18)። በዘፍጥ. 36 ደግሞ የይስሐቅ ሌላው ልጅ የሆነውን - የዔሳውን የትውልድ ታሪክ ይተነትናል። ከዚያም ቀጥሎ የዮሴፍን ታሪክ ይነግረናል።

## 3ኛ ቀን:- ዘፍጥረት 37-50 የዮሴፍ ታሪክ

የዚህ የአሪት ዘፍጥረት የመጨረሻ ክፍል ዓላማ የእስራኤል ሕዝብ የከነዓንን ምድር ይወርሱ ዘንድ ቃል የተገባላቸው ሆነው ሳሉ፥ እንዴት ወደ ግብፅ እንደወረዱ ማሳየት ነው። ለአሪት ዘጸአትም በመግቢያነት የሚያገለግል ነው። ምክንያቱም አሪት ዘጸአት እስራኤላውያን በግብፅ 400 ዓመታት ከቆዩ በኋላ ወደ ተስፋይቱ ምድር ለመመለስ እንዴት እንደወጡ የሚያሳይ መጽሐፍ ነው። ታሪኩ የተፈጸመው በሙሴ ዘመን ገደማ ስለሆነ፥ ከሌሎቹ የእስራኤል አባቶች ታሪክ ይልቅ የዮሴፍን ታሪክ በዝርዝር ይነግረናል። በተጨማሪ ኃጢአታቸው የሚያስከትለውን ችግር ጨምሮ እግዚአብሔር በሕዝቡ ሕይወት የሚመጣውን ነገር ሁሉ እየተቆጣጠረ እንዴት ያለማቋረጥ እንደመራቸው እንመለከታለን።

> 6ኛ ጥያቄ፥ ዘፍጥ. 37-50 አንብብ። ሀ) ዮሴፍ ያያቸውንና የተረጎማቸውን ልዩ ልዩ ሕልሞች ዘርዝር። እያንዳንዳቸው እንዴት ተፈጸሙ? ለ) ዮሴፍ በምሳሌነት ሊቀርብ የሚችል ታላቅ የእግዚአብሔር ሰው የሆነው እንዴት ነው? ሐ) በዮሴፍ ሕይወት ውስጥ የእግዚአብሔር ቁጥጥር የታየባቸውን መንገዶች ዘርዝር። መ) በስደት ውስጥ ይቅርታንና ትዕግሥትን ስለማሳየት ከዮሴፍ ሕይወት የምንማረው ነገር ምንድን ነው?

## 4ኛ ቀን:-

ከብዙ ዓመታት በፊት፥ እግዚአብሔር በሌላ ምድር መጻተኞች ሆነው እንደሚኖሩና ለ400 ዓመታት በባርነት እንደሚገዙ ለአብርሃም ተናግሮት ነበር (ዘፍጥ. 15፡13)። በዮሴፍ ታሪክ ይህ ትንቢት መፈጸም ጀመረ። እግዚአብሔር የገባውን ቃል ኪዳንና የሰጠውን ተስፋ እኛ በምንፈልገው ፍጥነት ባይፈጽምም፥ ለሰጠው ተስፋና ቃል ኪዳን ግን ሁልጊዜ ታማኝ ነው።

1. ዮሴፍ ወደ ግብፅ የሄደበት ምክንያት (ዘፍጥ. 37):- ከዘፍጥረት ምዕራፍ 37 ጀምሮ የእግዚአብሔርን እጅ በሥራ ላይ እናያለን። እግዚአብሔር አንድ ዓይነት ትርጉም ያላቸውን ሁለት ሕልሞች ለዮሴፍ ሰጠው። በመጀመሪያ፥ የወንድሞቹ ነዶዎች ለእርሱ ሲሰግዱ ያያል። በሁለተኛው ሕልም ደግሞ ፀሐይ፥ ጨረቃና አሥራ አንዱ ከዋክብት ለእርሱ ሲሰግዱለት አየ። ይህ ሕልም በወንድሞቹ ላይ ገዥ

እንደሚሆንና እነርሱም እንደሚሰግዱለት ማለትም እንደ መሪያቸው ተቆጥሮ እንደሚያከብሩት የተሰጠ ትንቢት ነበር። ይህም ትንቢት ከብዙ ዓመታት በኋላ ዮሴፍ የግብፅ ጠቅላይ ሚኒስትር ሆኖ ወንድሞቹ ምግብ ፍለጋ ወደ እርሱ በመጡ ጊዜ ተፈጸመ።

2. ትዕማር የይሁዳን ዘር አዳነች (ዘፍጥ. 38):- በዮሴፍ ታሪክ አጋማሽ ላይ በሌሎች ወንድሞቹ በተለይም በይሁዳ ሕይወት ኃጢአትና ክፋት መኖሩን የሚያሳይ አሳዛኝ ታሪክ እንመለከታለን። የይሁዳ ትልቁ ልጅ ዔር ትዕማር የምትባል ከነዓናዊት አገባ፤ ነገር ግን አንድም ልጅ ሳይወልድ ሞተ። በዚያ ዘመን በነበረው ወግ መሠረት ይሁዳ የሚቀጥለውን ልጁን አውናንን ከትዕማር ጋር ማጋባት ነበረበት። በባሕሉ መሠረት የሚወለደው የመጀመሪያ ልጅ የሟቹ ወንድም የዔር እንደሆነ ይቆጠር ነበር። የቀሩት ልጆች ደግሞ የአውናን ይሆኑ ነበር። የመጀመሪያው ልጅም የብኩርናን መብት ያገኝ ነበር። በሞተውም ልጅ ምትክ ከአያቱ ርስት ይወርስ ነበር። ይህ ማለት ይሁዳ ለበኩር ልጁ ያወርሰው የነበረው ነገር የመጀመሪያ ልጁ ከሞተ በኋላ የሚተላለፈው ለሁለተኛ ልጁ ሳይሆን ከትዕማር ለተወለደው ለልጅ ልጁ ይሆናል ማለት ነው። አውናን በእግዚአብሔር ላይ ኃጢአት ስላደረገ እግዚአብሔር ቀሠፈው። ባሕሉን ለማክበርና ለወንድሙ ልጅ ለማሳደግ ያልፈለገ ይመስላል። ምናልባት ምንም ልጅ ባይወልዱ በሞተው ወንድሙ ምትክ የብኩርናን መብት እንደሚወርስ ሳይገምት አልቀረም። አውናን ከሞተ በኋላ ይሁዳ በባሕሉ መሠረት ሦስተኛ ልጁን ለትዕማር ለመዳር ፈቃደኛ ሳይሆን ቀረ። ግዴታውን ለእርሷና ለመጀመሪያ ልጁ ሳይፈጽም ቀረ፤ ስለዚህ እርሷና ልጆችዋ የብኩርና መብት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ይሁዳን አታለለችው። ራሷን ሴተኛ አዳሪ አስመስላ በማቅረብ አማችዋ የሆነው ይሁዳ ከእርሷ ጋር እንዲተኛ አደረገችው። ከእርሱም ፋሬስና ዛራ ብላ የጠራቻቸውን መንታ ልጆች ወለደች። ይህን በማድረግዋ የይሁዳን ዘር ከመጥፋት አዳነች። የብኩርናን መብትም በቤተሰቧ በማስቀረት ልጇ ለይሁዳ የተሰጠውን የተስፋ ቃል ወራሽ እንዲሆን አደረገች። የሚያስደንቀው ነገር ንጉሥ ዳዊትና የዳዊት ልጅ ተብሎ የሚጠራው የኢየሱስ ክርስቶስ ዘር የመጣው ከትዕማር ልጅ ከፋሬስ መሆኑ ነው (ማቴ. 1፡3)።

3. እግዚአብሔር ዮሴፍን በግብፅ ጠብቆ አከበረው (ዘፍጥ. 38-40)።

ሀ. እግዚአብሔር ዮሴፍን በጲጥፋራ ቤት አከበረው:- ዮሴፍ በዚህ ሰው ቤት ባሪያ ቢሆንም፥ ከእግዚአብሔር ምርጥ ሕዝቦች አንዱ ነበር። እስራኤላውያንን ከራብ በማዳን የተሰጣቸው ቃል ኪዳን ከፍጻሜ እንዲደርስ ለማድረግ በእግዚአብሔር የተመረጠው ሰው ዮሴፍ ነበር። ስለዚህ እግዚአብሔር ዮሴፍን አከበረውና በግብፅ ውስጥ ባለውና መሪ በነበረው በጲጥፋራ ቤት አገልጋዮች ሁሉ አለቃ እንዲሆን አደረገ። ከጲጥፋራ ሚስት ጋር ዝሙት ፈጽሞ ሕይወቱ ሁሉ እንዲበላሽና እንዲጠፋ ለማድረግ ሰይጣን ሞከረ። ዮሴፍ ግን በዚህ መንገድ እግዚአብሔርንና ጲጥፋራን ላለማስደብ ወስኖ የሰይጣንን ሙከራ ተቃወመ።

7ኛ ጥያቄ፥ ሀ) ለዮሴፍ ከጲጥፋራ ሚስት ጋር ዝሙት መፈጸም በጣም ቀላል የነበረው ለምንድን ነው? ለ) በዚህ ዘመን ብዙ ክርስቲያኖች በዚህ ኃጢአት የሚወድቁት ለምንድን ነው? ሐ) ይህንን ፈተና ስለማሸነፍ ከዮሴፍ ሕይወት የምንማረው ነገር ምንድን ነው?

ለ) እግዚአብሔር ዮሴፍን በወኅኒ ቤት አከበረው:- ምንም ጥፋት ያልነበረበት ንጹሕ የነበረው ዮሴፍ ወደ ወኅኒ ቤት ከገባ በኋላ በዚያ ለብዙ ዓመታት ቆየ። እግዚአብሔር በዚያም ቢሆን ሞገስን ሰጠውና በወኅኒ ቤቱ የእስረኞች አለቃ አደረገው።

የወኅኒ ቤቱ የእስረኞች አለቃ ስለነበር እዚያ ታስረው ከነበሩት ከፈርዖን ጠጅ አሳላፊና የእንጀራ አበዛ ጋር ለመገናኘት ቻለ። እነዚህ ሁለት ሰዎች በግብፅ ቤተ መንግሥት ውስጥ ከፍተኛ ባለሥልጣኖች ነበሩ። ጠጅ አሳላፊው ንጉሡ ወይን ጠጅ ከመጠጣቱ በፊት የሚቀምስለት ሰው ነበር። ይህም ንጉሡን ማንም ሰው በመርዝ ሊገድለው እንዳይችል የተደረገ ዘዴ ነበር። ብዙውን ጊዜ የጠጅ አሳላፊው የንጉሡ ምሥጢረኛና የቅርብ ጓደኛ ነበር። የእንጀራ አበዛውም ንጉሡ ለሚበላቸው ነገሮች ሁሉ ኃላፊነት ስለ ነበረበት በጣም ከፍተኛ ስፍራ የነበረው ሰው ነው። እነዚህ ሁለት ሰዎች በእስር ቤት በነበሩ ጊዜ ዮሴፍ ሊተረጉምላቸው የቻለውን ሁለት ሕልሞች አዩ። የጠጅ አሳላፊው ሕልም ትርጓሜ ንጉሡን ያገለግልበት ወደነበረው ወደ ቀድሞ ሥፍራው መመለሱ ነበር። የእንጀራ አበዛው ሕልም ትርጓሜ ደግሞ የንጉሡን ምሥጢር ስላባከነ በስቅላት እንደሚገደል ነበር። እነዚህ ሕልሞች በኋላ የፈርዖንን ሕልም ለመተርጎም

ወደ ቤተ መንግሥት እንዲጠራ ያደረጉት ስለነበሩ በጣም ጠቃሚ ሕልሞች ነበሩ።

4. እግዚአብሔር ዮሴፍን በፈርዖን ፊት አከበረውና ጠቅላይ ሚኒስትር አደረገው (ዘፍጥ. 40-45)።

ዮሴፍ የፈርዖንን ሕልም ከተረጐመ በኋላ እስከ ጠቅላይ ሚኒስትርነት ማዕረግ እንደደረሰ ይታወቃል። እግዚአብሔር በዮሴፍ በኩል ለፈርዖን ሰባት የጥጋብና ሰባት የረሃብ ዓመታት እንደሚመጡ በሕልሙ አሳወቀው። ዮሴፍ ጠቅላይ ሚኒስትር እንደመሆኑ መጠን ለረሀቡ ጊዜ የሚሆነውን እህል በጥጋቡ ጊዜ አዘጋጀ።

እግዚአብሔር ዮሴፍን ያን ወደ መሰለ ከፍተኛ የሥልጣን ቦታ ያመጣው ለምንድን ነው? ሀ. የግብፅን ሕዝብ ከራብ ለማዳን፥

ለ. የተመረጠውን የእስራኤልን ሕዝብ ከራብ ለማዳንና፥

ሐ. ለአብርሃም የገባውን የተስፋ ቃል ለመፈጸም ይችል ዘንድ የእስራኤልን ሕዝብ ወደ ግብፅ ለማምጣት ነው።

8ኛ ጥያቄ፥ ሀ) እግዚአብሔር ዕቅዱን ለመፈጸም ሲል ዮሴፍን በዚህ ዓይነት ካከበረው፥ ዛሬም ለእኛ እንዴት እንደሚሠራ ይህ ምን ያስተምረናል? ለ) እግዚአብሔር በዮሴፍ ሕይወት እንዳደረገው በአንተ ወይም በሌላው ክርስቲያን ሕይወት ያደረገውን ተመሳሳይ ነገር የሚገልጹ ምሳሌዎችን ዘርዝር።

ዮሴፍ ለባርነት የሸጡትን ወንድሞቹን ለመፈተን በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ እንዲያልፉ አደረጋቸው። እርሱን ለባርነት ስለሸጡበት ኃጢአት በእርግጥ መፀፀታቸውን ማየት ፈለገ። ይሁዳ ራሱን በብንያም ምትክ ለመስጠት የተዘጋጀ መሆኑንና ወንድሞቹም እንደዚያ የተቀጡበት ምክንያት እግዚአብሔር ራሱ ስለቀጣቸው እንደሆነ መቀበላቸውን ሲያይ ከኃጢአታቸው በእርግጥ መመለሳቸውን አወቀ። ከዚያ በኋላ ራሱን ገለጠላቸው።

9ኛ ጥያቄ፥ ሀ) ዮሴፍ ወንድሞቹ እንደተለወጡና በእርግጥ ከኃጢአታቸው እንደተመለሱ ማወቅ ለምን አስፈለገው? ለ) ክርስቲያኖች በእውነት ከኃጢአታቸው መመለሳቸውን በምን እናውቃለን?

5. የያዕቆብ ትውልድና ትንሹ የእስራኤል ጎሳ ወደ ግብፅ መውረድ (ዘፍጥ. 46-50)።

ዮሴፍ ጠቅላይ ሚኒስትር ከሆነ በኋላ ቤተሰቡ ወደ ግብፅ መጥተው እንዲኖሩ አደረገ። የእስራኤል ሕዝብ አባት የሆነው ያዕቆብም ወደ ግብፅ ወረደ። የዮሴፍን ልጆች ጨምሮ ወደ ግብፅ የመጡት እስራኤላውያን ጠቅላላ ቁጥር 70 ነበር። ከ400 ዓመታት በኋላ 70 የነበረው የእስራኤላውያን ቁጥር 2 ሚሊዮን ደርሶ ነበር።

ያዕቆብ ከመሞቱ በፊት ለልጆቹ ለእያንዳንዳቸው በረከቱን አስተላለፈ። እነዚህ በረከቶች የትንቢት መልክ ሲኖራቸው የተሰጡትም በቀጥታ ከእግዚአብሔር እንደመጡ ተደርገው ነበር። የያዕቆብ በረከቶችና ትንቢቶች የእግዚአብሔር ቃል ነበሩ፤ እግዚአብሔርም ፈጸማቸው።

ሀ) ያዕቆብ የዮሴፍን ሁለት ልጆች ኤፍሬምና ምናሴን ባረካቸው (ዘፍጥ. 48)። ይህንን በማድረግ ያዕቆብ የበኩር ልጅን መብት ለዮሴፍና ለልጆቹ ሰጠ። ደግሞም የብኩርናን መብት ከዮሴፍ ልጆች ለታናሹ ለኤፍሬም ሰጠ። እግዚአብሔር የርስቱን ዕጥፍ ለዮሴፍ ሁለት ልጆች ለኤፍሬምና ለምናሴ ስለሰጠ፥ በእስራኤል ሕዝብ ዘንድ ዮሴፍ የሚባል ነገድ አልነበረም። ይልቁንም በእርሱ ቦታ ኤፍሬምና ምናሴ የሚባሉ ሁለት ነገዶች ነበሩ።

ለ. ለአሥራ ሁለቱ ልጆች የተሰጠ በረከት (ዘፍጥ. 49)

| የተባረከው ነገድ | በረከትና ትንቢት | እርግማን |
|---|---|---|
| ሮቤል - | በኩር ልጅ የለም | ከያዕቆብ ቁባት ጋር ስላመነዘረና ኃጢአት ስላደረገ በረከቱን አጣ |
| ስምዖን - | የለም | ሴኬማውያንን በማታለላቸው በረከትን አጡ። የራሳቸው ርስት ሳይኖራቸው በእስራኤል ነገዶች መካከል ተበተኑ። |
| ሌዊ - | የለም | ሴኬማውያንን በማታለላቸው በረከትን አጡ። የራሳቸው ርስት ሳይኖራቸው በእስራኤል ነገዶች መካከል ተበተኑ። |
| ይሁዳ - | በወንድሞቹ ላይ የመንገሥ መብት ተሰጠው፥ ከእርሱም የመጨረሻ ንጉሥ ይወጣል | የለም |

| | | |
|---|---|---|
| ዛብሉን | በባሕር ዳርቻ ይኖራል | የለም |
| ይሳኮር | በብልጥግና ምድር<br>ይኖራል ነገር ግን<br>የሌሎች ባሪያ ይሆናል | የለም |
| ዳን | ለሕዝቡ ቅን ፍርድን<br>ያደርጋል<br>ብርቱ ጠላቶቹን ይቋቋማል | የለም |
| ጋድ | ከጠላቶቹ ጋር ጦርነት<br>ይኖርበታል<br>ነገር ግን ድል ይነሣል | የለም |
| አሴር | ለም ምድር ይኖረዋል | የለም |
| ንፍታሌም | እንደ አጋዘን ነፃ ሆኖ ይኖራል | የለም |
| ዮሴፍ | ፍሬያማና በጠላቶቹ ላይ<br>ባለ ድል ይሆናል | የለም |
| ብንያም | በጦርነት ኃይለኛ ይሆናል<br>ጠላቶቹንም ድል ይነሣል | የለም |

ከዚህ ሠንጠረዥ እንደምንመለከተው ያዕቆብ ልጆቹን እያንዳንዳቸውን ባረካቸው፤ ትንቢትም ተናገረላቸው። ነገር ግን ሦስቱ ልጆቹ ለልዩ ቅጣት ተለዩ። እነዚህም በኩሩ ሮቤል፥ ስምዖንና ሌዊ ናቸው። ሦስቱም የብኩርና መብት አጡ። ሮቤል የአባቱን መኝታ ደፈረ። ይህም በጥንት ባሕል ታላቁ ልጅ የአባቱን ርስት ለመውሰድ መፈለጉን የሚያሳይ ነበር። (ሮቤል አባቱ እስኪሞት ድረስ መጠበቅ አቅቶት ቁባቶቹን ወስዶ ከእነርሱ ጋር በመተኛት የቤቱ ራስ መሆኑን አወጀ)። ከዚህ የተነሣ ያዕቆብ ከሮቤል ላይ የበኩር መብት ወሰደበት። ስምዖንና ሌዊ ከነዓናውያን እኅታቸውን በመድፈራቸው የበቀል ሤራ ይወጥኑ ነበሩ። ይህ ዓመፅ የእስራኤል ሕዝብ መሪዎች ለመሆን የነበራቸውን ዕድል አከሸፈባቸው። አብዛኛው በረከት የተላለፈው ለዮሴፍ ቢሆንም የብኩርና መብትና መሪነት ግን ለይሁዳ ተሰጠ። ይሁዳ አራተኛው ልጅ ሲሆን የነገሥታት አባት ሆነ። የያዕቆብ ሦስት ትላልቅ ልጆች እርግማንን እንጂ በረከትን አልተቀበሉም፤ ነገር ግን ዮሴፍና ይሁዳ በረከትን ከተቀበሉ ከያዕቆብ ልጆች ከፍተኛ ድርሻ ተቀብሉአል። በእስራኤል ታሪክ ውስጥ ይህ አስፈላጊ ነበር፤ ምክንያቱም ቢባል በዮሴፍ ልጅ - በኤፍሬም ነገድና

በይሁዳ ነገድ መካከል የእስራኤል ነገዶች መሪ ለመሆን ሲባል ብዙ ጊዜ ትግል ይካሄድ ነበር።

10ኛ ጥያቄ፥ በመጨረሻ የኃጢአት ቅጣት የማይቀር ስለመሆኑ እነዚህ ታሪኮች ምን ያስተምሩናል?

6. ያዕቆብ በከነዓን ተቀበረ።

ይህ ዋጋ የሌለው ታሪክ ይምሰል እንጂ ሆኖም ግን የሚመስለው ግብፅ የአይሁድ ምድር እንዳልሆነች የሚያሳይ ስለሆነ በጣም አስፈላጊ ነው። በግብፅ መኖር የሚያስፈልጋቸው ለጥቂት ጊዜ ብቻ ነበር። በመጨረሻ የሚመለሱባት ከነዓን ምንጊዜም አገራቸው ነበረች። የያዕቆብ ሬሣ ለቀብር ወደ ከነዓን ተወሰደ። ቆየት ብሎ የዮሴፍ ሬሣም ለቀብር ወደ ከነዓን ተወሰደ፤ (ኢያ. 24፡32)።

አዲስ ኪዳን ይህንን ባይናገርም እንኳ ብዙ ምሁራን ዮሴፍን የክርስቶስ አምሳል አድርገው ያቀርቡታል። ሁለቱም ተሸጠዋል። ዮሴፍ ለባርነት ሲሸጥ፥ ኢየሱስ ደግሞ ከደቀ መዛሙርቱ በአንዱ ተሸጠ (አልፎ ተሰጠ)። ስለ ዮሴፍ በግልጥ የተጠቀሰ ኃጢአት የለም። ኢየሱስም ያለ ኃጢአት ነበር። እግዚአብሔር ኢየሱስንም ዮሴፍንም ሌሎችን ለማዳን ተጠቀመባቸው። እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ለማዳን ዮሴፍን ተጠቀመበት። ኢየሱስን ደግሞ በእርሱ የሚያምኑትን ሁሉ ለማዳን ተጠቀመበት።

11ኛ ጥያቄ፥ ከኦሪት ዘፍጥረት ጥናት ስለ እግዚአብሔርና ስለ ሰው ምን መማር ይቻላል?

በኦሪት ዘፍጥረት በግልጥ የተጠቀሱ የእምነት ትምህርቶች

1. እግዚአብሔር፡-

በኦሪት ዘፍጥረት ውስጥ የእግዚአብሔርን ማንነት ለመረዳት የሚያስችሉን አምስት ዋና ዋና ሥዕላዊ መግለጫዎችን እናገኛለን። እግዚአብሔር መጽሐፍ ቅዱስን ለእኛ የሰጠበት አንዱ ዋና ምክንያት እርሱ ማን እንደሆነ ሊገልጥልንና ከእኛ ምን እንደሚፈልግ ለማስረዳት መሆኑን ልብ በል። የእግዚአብሔርን ማንነት ለማወቅ የምንችለው፥ እርሱ ምን እንደሚመስል እኛ በምናስበው መንገድ ሳይሆን፥ እርሱ ከሚነግረን ነገር ነው።

ሀ. እግዚአብሔር የዓለም ሁሉ ታላቅ ፈጣሪ ነው። አንድ ቃል በመናገር ብቻ ፍጥረታትን ሁሉ እንዲሁም ሰውን ጨምሮ ፈጠረ።

ለ. እግዚአብሔር ቃል ኪዳን አድራጊ አምላክ ነው። እግዚአብሔር ከእንግዲህ ምድርን በውኃ እንዳያጠፋት ከኖኅ ጋር የገባውን ቃል ኪዳን ተመልክተናል። በኋላም ከአብርሃምና ከዘርያዎቹ ጋር ቃል ኪዳን ገብቶአል። ይህ ቃል ኪዳን እግዚአብሔር ከአይሁድ ጋር ላለው ልዩ ኅብረት መሠረት ነው። አሕዛብ የተባረኩት በዚህ ቃል ኪዳን መሠረት ነው። እግዚአብሔር ምንም ቅድመ ሁኔታ የሌለበትን ቃል ኪዳን አንድ ጊዜ ከገባ፥ ሕዝቡ ባይታዘዙትና ቢያምፁበትም እንኳ ያንን ቃል ኪዳን ለመፈጸም ይተጋል።

ሐ. እግዚአብሔር በኃጢአት ላይ ይፈርዳል። እግዚአብሔር ቅዱስና ጻድቅ ነው፤ ስለዚህ ኃጢአትን ሳይቀጣ አይተውም። በአዳምና በሔዋን፥ በቃየን፥ በኖኅ ዘመን በነበሩ ሰዎች፥ የባቢሎንን ግንብ ለመሥራት በሞከሩ ሰዎች ላይ እንደፈረደ ሁሉ ዛሬም በኃጢአት ውስጥ በሚኖሩ ሰዎች ላይ ለመፍረድ ቃል ገብቷል።

መ. እግዚአብሔር ኃጢአተኞችንም ይምራል፡- እግዚአብሔር ለኃጢአተኞች የሚገባቸውን ቅጣት በሙሉ ሰጥቶ አያውቅም። እርሱ መሐሪ ነው። አዳምና ሔዋን ኃጢአት ካደረጉ በኋላ እግዚአብሔር ፈለጋቸው። ብዙ ምሁራን እግዚአብሔር የእንስሳ ቆዳ ባለበሳቸው ጊዜ ስለ ኃጢአታቸው የመጀመሪያውን መሥዋዕት እንዳቀረበ ያምናሉ። ከኤድን ገነትም ያስወጣቸው የሕይወትን ዛፍ እንዳይበሉና ለዘለዓለም በኃጢአተኝነት እንዳይኖሩ ብሎ ነው። ይህን የመሰለ ምሕረት የሚገባቸው ባይሆኑም እንኳ ሎጥን ከሰዶም፥ ያዕቆብን ከላባና ከዔሳው እጅ አዳነ። እግዚአብሔር ከአሕዛብ ሁሉ መካከል በመረጠው ጊዜ አብርሃም እንኳ ራሱ ጣዖት አምላኪ ነበር።

ሠ. እግዚአብሔር በምድር ላይ የሚፈጸሙ ድርጊቶችን ሁሉ ይቆጣጠራል። ዓለምን የፈጠረው እርሱ ነው። እግዚአብሔር የጥፋትን ውኃ ላከ። ቋንቋቸውንም በመደበላለቅ ሰዎችን በምድር ላይ በተናቸው። የተመረጡት ሕዝቡን እንዳይጎዱ ወይም ዕቅዱን እንዳያበላሹ የነገሥታትን ሥራ ይቆጣጠራል። እግዚአብሔር ብልጥግናንና ድርቅን የመሳሰለውንም ነገር ወደ ምድር ይልካል።

**12ኛ ጥያቄ፡ ዛሬ እነዚህን የእግዚአብሔር ባሕርያት በሕይወታችን የምናየው እንዴት ነው?**

ሙሴ የእግዚአብሔርን ባሕርያት ከሚገልጽባቸው መንገዶች አንዱ በኦሪት ዘፍጥረት ውስጥ በጠቀሳቸው በርካታ የእግዚአብሔር ስሞች ነው። አይሁድ ስለ እግዚአብሔር «ስም» በሚነጋገሩበት ጊዜ የሚያተኩሩት በእግዚአብሔር ውጫዊ ስም ላይ ሳይሆን በእግዚአብሔር ባሕርይ ላይ ነበር። ስሙ እግዚአብሔር በእርግጥ ማን እንደሆነ ይገልጥ ነበር። ስለዚህ ሰዎች «የእግዚአብሔርን ስም እናመስግን» ሲሉ «እግዚአብሔርን እናመስግን» ማለታቸው ነበር።

እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳን ይጠራባቸው ከነበሩት ስሞች አንዳንዶቹና ትርጉማቸው ቀጥሎ ቀርቦአል።

| የእግዚአብሔር ስም | የስሙ ትርጉም |
|---|---|
| ኤል (ዘፍጥ. 35፡7) | የእግዚአብሔር መሠረታዊ ስሙ ሲሆን በእግዚአብሔር ኃይል ላይ ያተኩራል |
| ኤሎሂም (ዘፍጥ. 1፡1) በብሉይ ኪዳን በጣም ከታወቁት የእግዚአብሔር ስሞች አንዱ ነው። | እግዚአብሔር ፈጣሪና ገዥ፥ ኃይልን የተሞላ ግርማዊ ነው። |
| ኤል ኤልዮን (ዘፍጥ. 14፡18) | እግዚአብሔር ከሁሉ በላይ ወይም ከማንም ጋር መወዳደር የማይችል በአማልክት ሁሉ ላይ አምላክ ነው። |
| ኤል ሻዳይ (ዘፍጥ. 17፡1) | እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ፥ ሉዓላዊ ገዥ |
| ኤልሮኢ (ዘፍ. 16፡13) | እግዚአብሔር ሁሉን ያያል ከእርሱ የተሰወረ ነገር የለም |
| ያህዌ (ጀሆቫ) (ዘፍጥ. 2፡4) በብሉይ ኪዳን ከሚታወቁት የእግዚአብሔር ስሞች አንዱ ነው። | ልዩና ከሁሉም የበለጠ የተከበረ አይሁዳዊ ስም፥ ለእግዚአብሔር የተሰጠ ስም ሲሆን ፍፁም ታማኝነቱንና የቃል ኪዳን አምላክነቱን ያሳያል። የእግዚአብሔርን የምሕረት፥ የጸጋ የፍቅር ባሕርይ ያካትታል። |
| ያህዌ ይርኤ (ዘፍጥ. 22፡14) | በእግዚአብሔር ተራራ ይታያል ማለት እግዚአብሔር ያዘጋጃል። |
| አዶናይ (ዘፍጥ. 15፡2፥8) | እግዚአብሔርን በግል ለማምለክ የሚውል ስም፥ የእግዚአብሔር ጌትነት፥ ታላቅ ባለ ግርማ አምላክ። |
| አቢር ይስራኤል (ዘፍጥ. 49፡24) | እግዚአብሔር፥ የእስራኤል ኃያል። |

| |
|---|
| 13ኛ ጥያቄ፥ አምልኮ፥ እግዚአብሔር ስላደረገው ነገር ብቻ ሳይሆን፥ ስለ ማንነቱም ማመስገን ማለት ነው። ከላይ የተዘረዘሩትን ስሞች በመጠቀም ስለማንነቱ እግዚአብሔርን በጸሎት አመስግነው። |

2. የሰው ልጅ፡-

የሰው ልጅ የእግዚአብሔር ፍጥረት ቁንጮ መሆኑን ኦሪት ዘፍጥረት ያሳየናል። የሰው ልጅ በመጨረሻ የተፈጠረ ብቻ ሳይሆን፥ በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠረም ነው። ይህ አምሳል የሰው ልጅ በኃጢአት በመውደቁ ምክንያት እጅግ የተበላሸ ቢሆንም፥ ሙሉ ለሙሉ አልጠፋም። አሁንም የተፈጠርነው በእግዚአብሔር አምሳል ነው፤ ስለዚህ ይህ የሚያሳየው የሰው ልጅ የማያምን እንኳ ቢሆን፥ በእግዚአብሔር ዘንድ ታላቅ ዋጋ እንዳለውና በእኛም ዘንድ ይህ መታወቅ ያለበት እንደሆነ ነው።

እግዚአብሔር ለሰው ትክክለኛ የሆነውንና ያልሆነውን (ማለት ኃጢአትን የማድረግ፥ያለማድረግ መብት) የመምረጥ ፈቃድ ሰጥቶታል። ሰው የመሆን አንዱ ክፍል የመምረጥ መብት ነው። ስለዚህ ሰው እግዚአብሔርን ለመታዘዝ ወይም ላለመታዘዝ የመምረጥ ፈቃድ አለው። ሰው ምርጫውን መቆጣጠር ቢችልም ውሳኔው የሚያስከትላቸውን ነገሮች ግን መቆጣጠር አይችልም። ለእግዚአብሔር መታዘዝ በረከትን ያስገኛል፤ ለእግዚአብሔር አለመታዘዝ ደግሞ ፍርድን ያስከትላል። የሰው ልጅ ብዙ ጊዜ የሚያሳየው ባሕርይ አለመታዘዝ እንደሆነ ኦሪት ዘፍጥረት ያሳያል። የሰው ልጅ የእግዚአብሔር ፍጡር ቢሆንም፥ እግዚአብሔር በእርሱ ላይ ያለውን የአገዛዝ መብት ግን አልተቀበለም። ለእግዚአብሔር ላለመታዘዝ የመረጡ ሰዎች፥ የውሳኔያቸው ውጤት የሆነውን የእግዚአብሔርን ቅጣት እንደሚቀበሉ የተረጋገጠ ነው። አንድ ሰው እግዚአብሔርን መታዘዝ ከመረጠ፥ እርሱ ያከብረዋል።

| |
|---|
| 14ኛ ጥያቄ፥ ሀ) በኦሪት ዘፍጥረት ውስጥ ይህ ጉዳይ የታየው እንዴት ነው? ለ) ዛሬስ በሕይወታችን የምናየው እንዴት ነው? |

ሰዎች ሁሉ ከትንሹ ጀምሮ እስከ ትልቁ፥ በአፍሪካ ከሚኖሩት ጀምሮ በአውሮፓ እስካሉት፥ በጣም ከተማሩት ጀምሮ እጅግ ኋላቀር እስከሆኑት ድረስ ያሉት ሁሉ በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠሩ ናቸው። በዚህ መሠረት ነው ክርስቲያኖች በግልጽ ዘረኝነትን፥ ባርያ ፍንገላንና ፆንስ ማስወረድን ስሕተት ነው የሚሉት። የሰው ልጅ ሁሉ አንድ ነው። የሰው

ልጆች መጀመሪያ ከአንድ ሰው - ከአዳም፥ በኋላም ከኖኅ ተገኙ። የሰው ልጅ ከየትኛውም ዘር ይሁን፥ የትም ይኑር፥ ምንም ያህል ይማር፥ ጾታው ምንም ይሁን የእግዚአብሔር አምሳል ነው። ማንኛውም የጎሰኝነትና የዘረኝነት አመለካከታችን የትዕቢታችንና የኃጢአታችን ውጤት ሲሆን፥ ሁላችንም አንድ እንደሆንን የሚናገረውን የአሪት ዘፍጥረትን ትምህርት የሚቃረን ነው።

የቤተ ክርስቲያናችን አባሎች ጎሰኝነትን የመቃወም አቋም እንዲኖራቸው ይህንን ትምህርት እንዴት እንጠቀምበታለን? በኢትዮጵያ ውስጥ በዘረኝነት ወይም በጎሰኝነት ላይ የተመሰረተ ጥላቻ እንዴት ይታያል? ክርስቲያኖች እንደመሆናችን መጠን ይህንን ለመቃወም ምን ማድረግ አለብን?

3. ኃጢአት፡-

ሰዎች ፈጣሪያቸው በሆነው በእግዚአብሔር ሕግ ላይ የማመፃቸው ውጤት ኃጢአት ነው። ይህም በመጨረሻ ሥጋዊ ሞትን ያመጣል። ደግሞም የነፍስ ግድያን፥ የቤተሰብ አባላት መለያየትን፥ ዘረፋን፥ ስርቆትን፥ ሴትን አስገድዶ መድፈርን ወዘተ. ያስከትላል። አዳምና ሔዋን የሠሩት የመጀመሪያው ኃጢአት እጅግ አጥፊ የሆኑ ውጤቶች ነበሩት። በእግዚአብሔርና በሰው፥በባልና በሚስት መካከል ጠላትነትን አመጣ። ሴትና የመውለድ ችሎታዋ፥ ወንድና ለቤተሰቡ ምግብ የማቅረብ አስፈላጊነት ሁሉ በአሉታዊ ተጽዕኖ ሥር ወደቁ። የሰው ልጅ ሁልጊዜ ከኃጢአት ጋር ይታገል ዘንድ የአዳምና የሔዋን የኃጢአት ባሕርይ ለልጆቻቸው ሁሉ ተላለፈ።

4. ቃል ኪዳን፡-

በእግዚአብሔርና በሰው መካከል የሚደረግ ስምምነት ቃል ኪዳን ይባላል። ከሰው ጋር ቃል ኪዳን ለማድረግ ጀማሪ ሊሆን የሚችለው እግዚአብሔር እንጂ ሰው ስላይደለ ቃል ኪዳን የእግዚአብሔር ጸጋ ምልክት ነው። አንዳንድ ጊዜ ከእርሱ ጋር የቃል ኪዳን ተካፋይ ለሆኑ ሰዎች መመዘኛ ቢያበጅም፥ ብዙ ጊዜ እግዚአብሔር ቃል ኪዳን የሚያደርገው በምንም ቅድመ ሁኔታ ላይ ሳይመሠረት ነው። በታማኝነቱ ላይ የተመሠረተው ተስፋው እርሱ የመረጣቸውን ሰዎች

ይመለከታል፤ስለዚህ የቃል ኪዳኑ አካል የሆኑትን ሁሉ ይቅር በማለት በሕይወታቸው ፈቃዱን ለመፈጸም ያተጋል።

| |
|---|
| 15ኛ ጥያቄ፦ እነዚህ አራቱም የሃይማኖት ትምህርቶች እያንዳንዳቸው ከእግዚአብሔር ጋር ስላለን ግንኙነት ምን ያስተምሩናል? |

በኦሪት ዘፍጥረት ውስጥ ስለ ክርስቶስ የተነገሩ ትንቢቶችና ተምሳሌቶች፡- በኦሪት ዘፍጥረት ውስጥ ስለ ጌታ ኢየሱስ የተነገሩ በርካታ ትንቢቶችና ተምሳሌቶች አሉ።

1. አዳም፡- አዳም የመጀመሪያው ሰው እንደመሆኑ መጠን ከእርሱ ለመጡት የሰው ልጆች ሁሉ ራስና ተወካይ ነው። ኢየሱስም በእምነት የእግዚአብሔር ልጆች ለሆኑትና ለሚሆኑት ሁሉ ራስና ተወካይ ነው (ሮሜ 5፡ 12-19 ተመልከት)።

2. ዘፍጥ. 3፡15፡- ይህ የመጀመሪያው የመጽሐፍ ቅዱስ ትንቢት ነው። በሰይጣንና «በሴቲቱ ዘር» መካከል ስለሚኖረው ጦርነት ይተነብያል። ያ ዘር ማን ነው? በብሉይ ኪዳን የእግዚአብሔር ሕዝብ የሆኑትን እስራኤላውያንን ዛሬ ደግሞ ቤተ ክርስቲያንን ያመለክታል (ሮሜ 16፡20)። ከሁሉም ይልቅ ከሴት (ከማርያም) የተወለደውን ኢየሱስ ክርስቶስን ያመለክታል። ሰይጣን «ሰኮናውን ይቀጠቅጣል»። ይህም ሰይጣን ያነሣሣውን የኢየሱስ ክርቶስን የመስቀል ሞት የሚያመለክት ነው፤ ነገር ግን ኢየሱስ ራሱን ይቀጠቅጠዋል። ይህም የሰይጣንን መሸነፍና ሙሉ በሙሉ መጥፋት የሚያመለክት ነው (ራእ. 20፡1-10 ተመልከት)።

3. እግዚአብሔር እንስሳት ለኃጢአት መሥዋዕት የሚሆኑበትን ተግባር ጀመረ (ዘፍጥ. 3፡21)። ይህም ኢየሱስ ክርስቶስ በመጨረሻ ስለ ዓለም ኃጢአት ሊከፍለው ያለውን መሥዋዕትነት የሚያሳይ ነው፤ (ዕብ. 9፡27-28)።

4. የኖኅ መርከብ፡- በመርከቡ ውስጥ የነበሩት ሁሉ እግዚአብሔር በጥፋት ውኃ አማካይነት ካመጣው ፍርድ እንደዳኑ ሁሉ በክርስቶስ ኢየሱስ ያሉት ደግሞ በመጨረሻው ቀን ለማያምኑ ሰዎች ከተጠበቀው ፍርድ ይድናሉ፤ (1ኛ ጴጥ. 3፡20-21)።

5. መልከ ጼዴቅ:- መልከ ጼዴቅ፥ ሊቀ ካህንና ንጉሥ እንደ ነበር ሁሉ፥ ኢየሱስ ክርስቶስም ሊቀ ካህንና ንጉሥ ነው፤(ዘፍጥ. 14፡18-20፤ ዕብ. 6፡20፤ 7)።

6. ይስሐቅ:- ይስሐቅ ብቸኛው (ልዩ) የአብርሃም ልጅ እንደሆነ ሁሉ፥ ኢየሱስም የእግዚአብሔር ልዩ ልጁ ነው። አብርሃም ይስሐቅን እንደሠዋ ሁሉ እግዚአብሔርም ኢየሱስን የኃጢአት መሥዋዕት አድርጎ ሰጥቷል። ይስሐቅ በፍጹም ፈቃደኝነት ራሱን ለመሥዋዕት እንዳዘጋጀ ሁሉ ኢየሱስም ራሱን የኃጢአት መሥዋዕት አድርጎ አቀረበ።

7. ዮሴፍ:- ልክ ዮሴፍ ወደ ባርነት እንደተሸጠና ወገኖቹን ከራብ ሁሉ እንዳዳነ ኢየሱስም ለመሠዋትና ሕዝቡን ለማዳን ተሸጠ።

5ኛ ቀን:- የዚህን ሳምንት ትምህርት ከልስና ለሳምንታዊው የውይይት ጊዜ ራስህን አዘጋጅ።

## ሳምንታዊ ስብሰባ

1. የሳምንቱ የአምልኮ ጊዜ
2. ጸሎት
3. የትምህርት ክለሳ
4. ውይይት

ሀ) 1) ስለ ይስሐቅ ሕይወት ተወያዩ። ምን ዓይነት ሰው የነበረ ይመስልሃል? 2) እምነቱ ከአብርሃም ጋር የሚወዳደረው እንዴት ነው? 3) መልካም ወላጆች በመሆን ልጅን ስለማሳደግ ከይስሐቅና ከያዕቆብ ቤተሰብ የምንማረው ነገር ምንድን ነው?

ለ) 1) የያዕቆብን ሕይወት ግለጥ። ምን ዓይነት ሰው የነበረ ይመስልሃል? 2) እምነቱ ከአብርሃም እምነት ጋር የሚወዳደረው እንዴት ነው? 3) የይስሐቅና የያዕቆብ ሕይወት የእግዚአብሔርን ቃል ኪዳን አደጋ ላይ እንደጣለው ሁሉ እኛስ በተመሳሳይ ሁኔታ በማነጻጸር የእግዚአብሔር በረከት በሕይወታችን አደጋ ላይ እንዳይወድቅ ሊደረግ የሚችለው በምን ዓይነት መንገድ ነው? 4) በይስሐቅና በያዕቆብ ሕይወት ለቃል ኪዳኑ መፈጸም አደገኛ

ሊሆኑ ይችሉ የነበሩ ሁኔታዎች፥ ዛሬ በሕይወታችን ውስጥ የእግዚአብሔርን በረከቶች ከምናበላሽባቸው መንገዶች የሚመሳሰለው በምንድን ነው?

ሐ) 1) የዮሴፍን ሕይወት ግለጥ። ምን ዓይነት ሰው የነበረ ይመስልሃል? 2) እምነቱ ከአብርሃም እምነት ጋር የሚወዳደረው እንዴት ነው? 3) በቀልን ስላለመፈለግና በስደት ስለመጽናት ከዮሴፍ ሕይወት ምን እንማራለን?

መ) 1) በዘፍጥረት ውስጥ ያለውን ስለ እግዚአብሔር የሚናገረውን መሠረታዊ ትምህርት ከልስ። በዘፍጥረት ውስጥ በሚገኙ ታሪኮች፥ እነዚህ ትምህርቶች የሚታዩት እንዴት ነበር? 2) ስለ እግዚአብሔር ባሕርይ ወይም «ስም» የተሻለ ግንዛቤ ማግኘት እንዴት ያበረታታናል? 3) እግዚአብሔርን በተገቢው መንገድ ለማምለክ የመቻል ጉዳይ አንድ ሰው ስለ እርሱ ካለው ጥልቅ መረዳት ጋር ለምን ይያያዛል? 4) እግዚአብሔር ማን እንደሆነና በተሻለ ሁኔታ እንዴት ሊያመልኩት እንደሚችሉ የቤተ ክርስቲያን አባላትን ለማስረዳት ምን ማድረግ ይቻላል?

ሠ) 1) በዘፍጥረት ውስጥ ስለ ሰውና ስለ ኃጢአት የተሰጠውን ትምህርት ከልስ። እነዚህ መሠረታዊ ትምህርቶች ስለ ሰዎች ሊኖረን ስለሚገባው አመለካከትና አቀራረብ ምን ያሳዩናል? 2) እነዚህ መሠረታዊ ትምህርቶች ሰዎች በእግዚአብሔር ዓይን ምን ያህል ዋጋ እንዳላቸው፥ ከተለያየ ዝርያ ቢሆኑም እንኳ እኩል እንደሆኑ፥ ለኃጢአትና ለዓመፅ ስላላቸው ዝንባሌ ምን ያስተምሩናል? 3) ዘረኝነትን እየተቃወምን ለማስተማር ኦሪት ዘፍጥረትን እንዴት ልንጠቀምበት እንችላለን?

ረ) 1) በኦሪት ዘፍጥረት የሚገኙትን የክርስቶስን ተምሳሌቶች ግለጽ። 2) በኦሪት ዘፍጥረት ውስጥ ሌሎች ተምሳሌቶች አሉን? ካሉስ የትኞቹ ናቸው? ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ የሚያመለክቱትስ እንዴት ነው?

5. ጸሎት

# ትምህርት 6

## የኦሪት ዘጸአት መግቢያ

1ኛ ቀን:-

1ኛ ጥያቄ፥ ሀ) ከሁሉም በላይ አስፈላጊ የሆነና በሕይወትህ የተፈጸመ መንፈሳዊ ክስተት ምንድን ነው? ለ) ይህ ለአንተ በጣም አስፈላጊ የሆነው ለምንድን ነው? ሐ) ስለዚህ ጉዳይ እግዚአብሔርን በጸሎትና በመዝሙር ምን ያህል ጊዜ ታመሰግነዋለህ?

ብዙዎቻችን በሕይወታችን የተፈጸመውና ከሁሉ በላይ አስፈላጊ የሆነው መንፈሳዊ ክስተት ደኅንነታችን ነው በማለት ነው ለላይኛው ጥያቄ መልስ የምንሰጠው። ወደ ኋላ መለስ ብለን ስናስብ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ለመከተል የወሰንበትን ጊዜ እናስታውሳለን። ብዙዎቻችን ስለ ደኅንነታችን በጸሎታችን ወይም በመዝሙር እግዚአብሔርን እናመሰግነዋለን።

አይሁድ፥ በታሪካቸው ከሁሉም አብልጠው የሚያስታውሱት አንድ ድርጊት ነበር። ያም ድርጊት እግዚአብሔር ከባርነት ነፃ አውጥቶአቸው በምድረ በዳ ወደ ሲና ተራራ፥ ከዚያም ወደ ከነዓን የመራበት ነበር። ይህ ታሪክ በኦሪት ዘጸአት ውስጥ ይገኛል። በመዝሙረ ዳዊትና በነቢያት መጻሕፍት ጸሐፊዎቹ እግዚአብሔር የእስራኤልን ሕዝብ ከባርነት ነፃ አውጥቶ ወደ ከነዓን ስለ መራበት ጊዜ ወደ ኋላ መለስ ብለው ይጠቅሳሉ።

2ኛ ጥያቄ:- መዝ. 78ን ተመልከት። ይህ ምዕራፍ የሚናገረው ስለየትኛው ታሪካዊ ድርጊት ነው? 3ኛ ጥያቄ፥ ሀ) «መቤዠት» የሚለው ቃል ትርጉም ምንድን ነው? ለ) «መቤዠት» የሚለውን ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት ተመልከት። ሐ) እግዚአብሔር እስራኤልን ከግብፅ ባርነት ነፃ ስላወጣበት ድርጊት ይህ ቃል ለምን ተጠቀሰ? መ) ይህ ቃል ስለ ክርስቲያኖች ደኅንነት ለመናገርስ ለምን አገለገለ?

ኦሪት ዘፍጥረትና ሌሎች የታሪክ መጻሕፍት ያካተቱት የብዙ ዓመታትን ታሪክ ሲሆን፥ ከኦሪት ዘጸአት እስከ ኦሪት ዘዳግም ያለው ታሪክ ግን በ50 ዓመታት ጊዜ ውስጥ የተፈጸመ ነው። እንዲያውም ከዘጸአት እስከ ዘዳግም ባሉት ክፍሎች ውስጥ ከተፈጸመው ታሪክ አብዛኛው የአንድ

ዓመት ታሪክ ነው። እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ከባርነት እንዴት ነፃ እንዳወጣቸው በመናገር ይጀምርና በሲና ተራራ ከእስራኤላውያን ጋር እንዴት ቃል ኪዳን እንደገባ ይተነትናል። ከጠቅላላው የብሉይ ኪዳን ታሪክ አንድ ስድስተኛው (1/6ኛው) በእስራኤል ሕዝብ ታሪክ ውስጥ ስላለፈው ስለዚህ ጊዜ የሚናገር ነው። እስራኤል በእግዚአብሔር ዕቅድ ውስጥ ስላላት ልዩ ስፍራ ለመረዳት ከፈለግን፥ ሕዝቡ ስለሆነው ስለ እስራኤል የሚናገረውን ነገርና አጀማመራቸውም እንዴት እንደነበረ መረዳት የግድ ያስፈልገናል።

እግዚአብሔር እስራኤልን ከባርነት እንዴት ነፃ እንዳወጣና፥ ከዚያም በምድረ በዳ ለ40 ዓመታት እንዴት እንደተንከራተቱ የሚናገረው ታሪክ በአራት የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ተጽፎ እናገኘዋለን፤ ኦሪት ዘጸአት፥ ዘሌዋውያን፥ ዘኁልቊና ዘዳግም። ይህ ታሪክ በአራት ዋና ዋና ክፍሎች ሊከፈል ይችላል:-

1. የእስራኤል ሕዝብ ነፃ መውጣትና ወደ ሲና ተራራ መጓዝ፥ (ዘጸ. 1-18)
2. በሲና ተራራ የሕግ መሰጠት፥ (ዘጸ. 19-ዘኁ. 10:10)
3. 40 ዓመታት በምድረ በዳ መንከራተታቸው (ዘኁ. 10:11 - ምዕራፍ 21)
4. የእስራኤል ሕዝብ ወደ ከነዓን ከመግባታቸው በፊት በዮርዳኖስ ወንዝ ዙሪያ ያደረጉት ቆይታ፥ (ዘኁል. 22 - ዘዳ. 34)

| |
|---|
| 4ኛ ጥያቄ፥ ስለ ኦሪት ዘጸአት ከመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት ተመልከት። ስለ ኦሪት ዘጸአት ካነበብካቸው ነገሮች መካከል ዋና ዋና እውነቶች የትኞቹ ናቸው? |

## የመጽሐፉ ስም

| |
|---|
| 5ኛ ጥያቄ፥ በአማርኛ «ዘጸአት» ማለት ምን ማለት ነው? |

ዕብራውያን (አይሁድ) የፔንታቱክን ሁለተኛ መጽሐፍ በመጀመሪያው ዐረፍተ ነገር «የ . . . ስሞች እነዚህ ናቸው» ብለው ሰይመውታል። ይህም ስያሜ የተገኘው ከመጽሐፉ የመጀመሪያ ዐረፍተ ነገር ነው። የግሪኩ ሴፕትዋጀንት መጽሐፍ ቅዱስ ግን የመጽሐፉን ርእስ «ዘጸአት» ብሎታል። ለእንግሊዝኛውም ሆነ ለአማርኛው መጽሐፍ ቅዱስ

ርእስ መሠረት የሆነው ይህ የግሪኩ መጽሐፍ ቅዱስ ርእስ ነው። ዘጸአት ማለት «መውጣት» ወይም «መለየት» ማለት ነው። ለሁለተኛው የፔንታቱክ መጽሐፍ ይህ ርእስ የተሰጠበት ምክንያት፥ በውስጡ የሚገኘው ዋናው ታሪክ የሚናገረው እግዚአብሔር የእስራኤልን ሕዝብ በግብፃውያን ባርነት ሥር ከነበሩበት ሁኔታ እንዴት ነፃ እንዳወጣቸውና ከግብፅ ተለይተው ወደ ተስፋይቱ ምድር መጓዝ ስለ መጀመራቸው የሚናገር በመሆኑ ነው።

## ጸሐፊው

| |
|---|
| 6ኛ ጥያቄ፥ ሀ) ኦሪት ዘጸአትን እንደጻፈ የሚታመነው ሰው ማን ነው? ለ) ዘጸ. 17፡14፤ 24፡4 አንብብ። እግዚአብሔር ሙሴን ምን እንዲያደርግ አዘዘው? ሙሴስ ምን አደረገ? |

ከጥንት ዘመን ጀምሮ አይሁድም ሆኑ ክርስቲያኖች የኦሪት ዘጸአት ጸሐፊ ሙሴ እንደሆነ ይስማሙ ነበር። የእግዚአብሔር ቃል ሙሉ በሙሉ የእግዚአብሔር ቃል እንደሆነ የማያምኑ ምሁራን መጠራጠር የጀመሩት ባለፉት 200 ዓመታት ብቻ ነው።

ስለ ኦሪት ዘጸአት ጸሐፊ ሰዎች ሦስት ዋና ዋና አሳቦች ይሰነዝራሉ።

1. አንዳንድ ሰዎች የዚህ መጽሐፍ ጸሐፊ ኢያሱ ወይም በኢያሱ ጊዜ ሊቀ ካህን የነበረው ኤሊዔዘር ነው ብለው ያስባሉ። ኦሪት ዘጸአትን የጻፈውም ከሙሴና ከአሮን በሰማው አፈ - ታሪክ መሠረት ነው ይላሉ። ይሁን እንጂ ይህን አስተሳሰብ ለመደገፍ ያለው ማረጋገጫ በጣም ጥቂት ነው።
2. ጄ.ኢ.ፒ.ዲ. የሚለውን ንድፈ ሐሳብ የሚከተሉ ሰዎች (ስለ ፔንታቱክ ጸሐፊ በትምህርት 3 ያለውን ከልስ።) ኦሪት ዘጸአት የተጻፈው በሦስት ዋና ዋና ጸሐፊዎች ነው ይላሉ። እነዚህም «ጄ» ጄሆቫ፥ «ኢ» ኤሎሂም፥ «ፒ» ፐሪስት (ካህን) ተብለው የተሰየሙ ናቸው። የኦሪት ዘጸአት የመጨረሻ ቅጅ የተዘጋጀው ከ600-400 ዓ.ዓ. ከነበረው ጊዜ በፊት አልነበሩም ብለው ያስተምራሉ። ይህ አመለካከት በጣም ጥቂት መረጃ ያለው ሲሆን በርካታ የዘመኑ ምሁራንም አይቀበሉትም።
3. ሙሴ የኦሪት ዘጸአት የመጀመሪያ ጸሐፊ ነው። ስለዚህ መጽሐፉ የተጻፈው በ1400 ዓ.ዓ. አካባቢ ነው። ሆኖም ሙሴ ከሞተ ከጥቂት

ጊዜ በኋላ ሌሎች አዘጋጆች የኦሪት ዘጸአት ታሪክ ከተፈጸመ በመቶዎች ከሚቆጠሩ ዓመታት በኋላ ማንበብ ለሚችሉ አይሁድ የበለጠ ግልጽና በቀላሉ የሚረዱት ለማድረግ አንዳንድ ነገሮችን አክለውበታል። ይህም በሚከተሉት ምክንያቶች ከሁሉ የተሻለው አመለካከት ነው፡-

ሀ. ሙሴ እንዲጽፍ በእግዚአብሔር ታዘዘ። ደግሞም እርሱ እንደጻፈ በግልጥ ተጠቅሷል፤ (ዘጸ. 17፡14፤ 34፡1-5 ተመልከት)።

ለ. የኦሪት ዘጸአት ጸሐፊ ሙሴ መሆኑን ኢየሱስ በግልጥ ተናግሯል፤ (ማር. 7፡10 ተመልከት)።

ሐ. ሙሴ በቂ እውቀት ስለነበረውና ስለተፈጸሙት ድርጊቶች ሁሉ ደግሞ የዓይን ምስክር ስለነበር ሊጽፉት ከሚችሉት ሰዎች ዋነኛው እርሱ ነው።

መ. ከአንዳንድ ክፍሎች በግልጥ እንደምንመለከተው ኦሪት ዘጸአት በኋላ የተነሣ አዘጋጅ እንደገና አቀናብሮታል። የሚከተሉትን ተመልከት፡-

1. አብዛኛው ታሪክ የሚያወራው ስለ ሙሴ ሲሆን በሙሴ በራሱ የተጻፈ ግን አይመስልም፤ (ምሳሌ፡- ዘጸ. 6፡13፤ 11፡3)።
2. ከሙሴ ሞት በኋላ የተጨመሩ የሚመስሉ መግለጫዎች በበርካታ ስፍራዎች አሉ ፤(ለምሳሌ፡- ዘጸ. 16፡31-36)።

## የጸሐፊው የሙሴ ሕይወት

| |
|---|
| 7ኛ ጥያቄ፥ ሀ) ዘጸ. 2-3 አንብብ። እነዚህ ምዕራፎች ስለ ሙሴ የመጀመሪያዎቹ 80 ዓመታት የሚናገሩትን ዘርዝር። ለ) በትምህርት 3 ስለ ሙሴ ሕይወት የተመለከትነውን ከልስ። ሐ) ስለ ሙሴ በመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት የተጻፈውን አንብብ። በጻፍከው ዝርዝር ላይ ስለ ሙሴ ያገኘኸውን ተጨማሪ ነገር ጻፍ። |

### የኦሪት ዘጸአት ታሪክ የጊዜ ርዝመት

| |
|---|
| 8ኛ ጥያቄ፥ ዘጸ. 1-2፡10 አንብብ። የዘጸአት ታሪክ የሚጀምረው ከምንድን ነው? |

9ኛ ጥያቄ፥ ዘጸ. 19 አንብብ። በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የእስራኤል ሕዝብ ያለው የት ነው?

የኦሪት ዘጸአት ታሪክ የእግዚአብሔር ሕዝብ የሆኑት እስራኤላውያን በግብፅ ለመኖር እንዴት እንደመጡ አጭር መግለጫ ከሰጠን በኋላ፥ የሙሴን ልደት ታሪክ ይጀምራል። ከዘጸአት - ዘዳግም ባሉት መጻሕፍት ውስጥ ከሁሉም የላቀው ሰብዓዊ ገጸ ባሕርይ ሙሴ ነው። ኦሪት ዘጸአት የሚመደበው እስራኤላውያን ወደ ሲና ተራራ ደርሰው ሲሰፍሩ ነው። እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር ቃል ኪዳን የገባው በዚህ ስፍራ ነው።

የእስራኤል ሕዝብ በሲና ተራራ የሰፈሩት ለአንድ ዓመት ያህል ነው። በዚያም እግዚአብሔር እነርሱን በአስደናቂ ኃይል ተገናኛቸው። የእርሱ ቅዱስ ሕዝብ ሆነው እንዴት እንደሚኖሩ የሚያስረዱ ሕግጋትን ሰጣቸው። ከእርሱ ጋር የሚገናኙበትን የማደሪያውን ድንኳን እንዴት እንደሚሠሩም ነገራቸው። አብዛኛው የዘጸአትና የሌዋውያን ታሪክ የተፈጸመው በሲና ተራራ ነው።

## በዘጸአት ጊዜ የነበረው የግብፅ ታሪክ

የኢትዮጵያ ሕዝብ ታሪክ በዓለም ከሚፈጸመው ታሪክ ጋር በቅርብ የተቆራኘ እንደሆነ ሁሉ፥ የእስራኤል ሕዝብ ታሪክም ከጥንቱ ዓለም ጋር የተቆራኘ ነበር። ይህ ደግሞ በተለይ በዚያን ጊዜ ከሁሉም በላይ ገናና የነበረችውን ግብፅን በሚመለከት የበለጠ እውነትነት አለው።

10ኛ ጥያቄ፥ መዝ. 2፤ ኢሳ. 40፡15-25 አንብብ። ሀ) እነዚህ ቁጥሮች እግዚአብሔር በአሕዛብ ሁሉ ላይ ስላለው አገዛዝ ምን ያስተምሩናል? ለ) እነዚህ ቁጥሮች በአሁኑ ጊዜ እንዴት ያበረታቱናል?

እግዚአብሔር መንግሥታትን ሁሉ ይቆጣጠራል፤ ታሪካቸውንም ይወስናል። ደካሞች ይሁኑ ብርቱዎች ድንበራቸው የት ድረስ እንደሚሆን ሁሉ የሚወስን እግዚአብሔር ነው። እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ወደ ግብፅ በማምጣት በእነርሱ ውስጥ የሠራው ከራብ ሊያድናቸው ብሎ ነው። እንደምታስታውሰው፥ እግዚአብሔር ይህንን ያደረገው የግብፅ ጠቅላይ ሚኒስትር ባደረገው በዮሴፍ መሪነት ነው። ነገር ግን በግብፅ በተፈጸሙት ክስተቶች ስሙ ይከበር ዘንድ በግብፅ ሕዝብ መካከልም ሠርቷል።

11ኛ ጥያቄ፥ ኢ.ያ. 2፡8-11 አንብብ። በግብፅ የተፈጸሙት ታሪካዊ ድርጊቶች በዚያን ጊዜ ለነበሩት የአሕዛብ መንግሥታት ሁሉ ምን አስተማራቸው?

መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ግብፅ ታሪክ ብዙ አይነግረንም። ምክንያቱም የእግዚአብሔር ቃል ትኩረት ስለ ሕዝቡ ስለ እስራኤል፥ እንዲሁም በእነርሱ በኩልና በእነርሱም አማካይነት እንዴት እንደሠራ መናገር ነው፤ ዳሩ ግን በዚያ ጊዜ ስለነበረው ስለ ግብፅ መንግሥት ከዓለም ታሪክ ብዙ ለመማር እንችላለን። የአሪት ዘጸአት ታሪክ የተፈጸመው አዲሱ የመንግሥት ዘመን በመባል ይታወቅ በነበረው የግብፅ ታሪክ ጊዜ ነበር በማለት ብዙ ምሁራን ያምናሉ።

የኢትዮጵያ ታሪክ በተለያዩ ጊዜያት ሊከፋፈል እንደሚችል ሁሉ፥ የግብፅ ታሪክም በተለያዩ ጊዜያት ሊከፋፈል ይችላል። በ1800 ዓ.ዓ. ግብፃውያን መካከለኛው መንግሥት እየተባለ በሚጠራው መንግሥታቸው ይኖሩ ነበር። በዚህ ዘመን መጨረሻ አካባቢ የግብፅ መንግሥት በጣም ተዳከመ። በ1700 ዓ.ዓ. አካባቢ ከእስያ የመጣ ሐይክሶስ የተባለ የሴም ዘር ሕዝብ ግብፅን በመውረር ሥልጣን ጨበጠ። እነዚህ ሕዝቦች ከአይሁድ ጋር የሚዛመዱና እንደ እነርሱም መጻተኞች ስለነበሩ አይሁድ ከሐይክሶሳውያን ጋር ጥሩ ግንኙነት ነበራቸው፤ ዳሩ ግን በ1550 አካባቢ ግብፆች ሐይኪሶሳውያንን አባረሩና መንግሥታቸውን እንደገና ተቆጣጠሩ። ይህ ዘመን ከ1546-1085 ዓ.ዓ. ድረስ የቆየ ሲሆን የአዲሱ መንግሥት ዘመን በመባል ይታወቅ ነበር። ይህም በግብፅ ታሪክ ውስጥ ታላቅ ጥንካሬና እድገት የታየበት ጊዜ ነበር።

ግብፃውያን በባዕዳን ተገዝተው ስለነበር በምድራቸው በሚኖሩ የውጭ ዜጎች ሕዝቦች ሁሉ ላይ ተቃውሞ አካሄዱና እንደ ሐይኪሶስ ያሉትን አንዳንዶቹን አባረሩ። እንደ አይሁድ ያሉትን ደግሞ ባሪያዎች አደረጉ። አሪት ዘጸአት 1-12 ግብፆች አይሁድን ባሪያ ያደረጉበትን ይህን ጊዜ ያንፀባርቃል። ግብፃውያን አይሁድ በኃይል እያደጉ እንዳይሄዱ የፈሩበትን ምክንያት ያስረዳል። ሐይኪሶሶች እንዳደረጉት አይሁድም ምድራቸውን እንዳይወስዱባቸውና እንዳይገዙአቸው ይሠጉ ነበር።

12ኛ ጥያቄ፥ ቤተ ክርስቲያን ጠንክራ እንዳታድግ በሚፈልጉ በአንዳንድ በማያምኑ ሰዎች ላይ ይህ ተመሳሳይ ፍርሃት እንዴት ይታያል?

## የግብፃውያን ሃይማኖት

13ኛ ጥያቄ፥ ዘጸአት 32፡1-8 አንብብ። እስራኤላውያን እግዚአብሔርን የሚያሳዝን ምን ነገር አደረጉ?

እስራኤላውያን ከግብፃውያን ጋር ለ400 ዓመታት ኖረዋል። በዚህ ቆይታቸው ለእግዚአብሔር ባላቸው አምልኮ በንጽሕና መቆየት አልቻሉም። ይልቁንም የግብፃውያንን አማልክት ማምለክ ጀመሩ። በዘጸአት 32 እስራኤላውያን በእግዚአብሔር ላይ ሲያምፁና በጥጃ የሚመሰለውን የግብፃውያን አምላክ ሲያመልኩ እንመለከታለን።

14ኛ ጥያቄ፥ ሀ) ዛሬም ክርስቲያኖች ራሳቸውን ለእግዚአብሔር ንጹሐን አድርገው ከመጠበቅ ይልቅ በዙሪያቸው ያሉትን ሕዝቦች አስተሳሰብና ልማድን መከተል የሚቀላቸው እንዴት ነው? አንዳንድ ምሳሌዎችን ጥቀስ። ለ) ቤተ ክርስቲያንህ አባሎችዋ ዓለምን እንደማይመስሉና በእግዚአብሔር ፊት በንጽሕና እንዳሉ ለማረጋገጥ በየጊዜው ምን ታደርጋለች? ሐ) ቤተ ክርስቲያን አባሎችዋን ከዓለም አሉታዊ ተጽዕኖ ለመጠበቅ ምን የተሻለ ነገር ማድረግ ትችላለች?

ግብፃውያን በርካታ የተለያዩ አማልክትን ያመልኩ ነበር። ከእነዚህ አማልክት መካከል አብዛኞዎቹ በተፈጠረው ዓለም ውስጥ ያሉ ነገሮች ይመስሉ ነበር። ለምሳሌ፡- የፀሐይ አምላክን፥ የጨረቃ ሴት አምላክን፥ ወፎችን፥ እንደ ወይፈን ያሉ እንስሳትን ወዘተ. ያመልኩ ነበር። በአገራቸው በአጠቃላይ እነዚህን አማልክት የሚያመልኩባችውን በርካታ ቤተ መቅደሶች ሠርተው ነበር። ግብፃውያን በበርካታ አማልክት ያምኑ ስለነበር፥ የሌሎች ሕዝቦችን አማልክት በቀላሉ ማምለክ ይችሉ ነበር። እስራኤላውያንም እነዚህን አማልክት ለምደው ነበርና እነርሱን ለማምለክ ተመሳሳይ የሆኑ ምስሎችን መሥራት ጀመሩ። እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን የመጀመሪያዎቹን ሁለት ትእዛዛት የሰጠው የእነዚህን በርካታ አማልክት አምልኮን በመቃወም ነበር።

15ኛ ጥያቄ፥ ዘጸ. 20፡1-6 አንብብ። ሀ) በዚህ ስፍራ የምናገኛቸው ሁለት ትእዛዛት ምንድን ናቸው? ለ) ስለ እስራኤል ሕዝብ ታሪክ ባለህ ግንዛቤ መሠረት ብዙ ጊዜ እነዚህን ትእዛዛት የሚጥሱት እንዴት ነበር?

በሲና ተራራ እግዚአብሔር ለእስራኤል ሕዝብ የሰጣቸው የመጀመሪያዎቹ ሁለቱ ትእዛዛት በግብፃውያን ዘንድ በጣም ተለምዶ የነበረውንና እስራኤላውያን በግብፅ በቆዩበት ጊዜ የተለማመዱትን የጣዖት አምልኮ የሚያመለክቱ ነበሩ። እንደ አጋጣሚ እስራኤላውያን በታሪካቸው ሁሉ ከጣዖት አምልኮ ጋር ይታገሉ ነበር።

በመጀመሪያው ትእዛዝ እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን የነገራቸው እውነተኛ አምላክ የሆነውን እርሱን ብቻ እንጂ ሌሎች አማልክትን እንዳያመልኩ ነበር። ሁለተኛው ትእዛዝ የሚናገረው ደግሞ በጊዜው በጣም የተለመደውን የተቀረፀ ምስልን ወይም እግዚአብሔርን የሚወክል ነገር ማድረግን የሚመለከት ነበር። አማልክቶቻቸው በጥጃ ወይም በእባብ ወዘተ. የተመሰሉ ነበሩ። እነዚህንም ምስሎች ያመልኩ ነበር። እግዚአብሔር እርሱን የሚመስሉበትን አንዳችም ነገር እንዳያደርጉ አይሁድን በጥብቅ አዝዞአቸዋል።

16ኛ ጥያቄ፥ ሀ) እግዚአብሔር ሰዎች እርሱን የሚመስሉበትን አንዳችም ምስል ወይም ቅርፅ እንዳያደርጉ የፈለገበት ምክንያት ምን ይመስልሃል? ለ) ሰዎች በቤታቸው ወይም በቤተ ክርስቲያናቸው የሚያንጠለጥሉት የኢየሱስ ሥዕልስ ጉዳይ እንዴት ነው? እነዚህ የእግዚአብሔር ምስሎች ናቸውን? መልስህን አብራራ። ሐ) ክርስቲያኖች የኢየሱስን ሥዕል በቤታቸው መስቀል አለባቸውን? መልስህን አብራራ።

እግዚአብሔር መንፈስ ነው፥ በመሆኑም ማንኛውንም የተፈጠረ ነገር አይመስልም። ሰው እግዚአብሔርን በአንድ ዓይነት ቅርፅ ወይም ምስል ለመመሰል የሚያደርገው ሙከራ እርሱን ማክበር ሳይሆን ማዋረድ ነው። ሰው የእግዚአብሔርን ኃይልና ክብር ሙላት ለማወቅም ሆነ ለመገመት አይችልም፤ ስለዚህ እንዲህ ላለው ታላቅ አምላክ ክብርን የሚሰጥ ነገር ማዘጋጀት አንችልም።

ክርስቲያኖች በቤትም ሆነ በቤተ ክርስቲያን የኢየሱስን ሥዕል ስለ መስቀል የተለያየ አመለካከት አላቸው። ሙስሊሞች በቤታቸውም ሆነ መስጊዳቸው ማንኛውንም ዓይነት የእግዚአብሔር ምስል ላለማድረግ ይጠነቀቃሉ። ስለ ክርስቲያኖች የሚነቅፉት ነገር ቢኖር ራሳቸውን ክርስቲያን ብለው የሚጠሩ እነዚህ ሰዎች የእግዚአብሔርን፥ የኢየሱስን ወይም የመላእክትን ሥዕል በቤተ ክርስቲያናቸው ወይም በቤታቸው ያደርጋሉ ብለው ነው። ይህ ነገር እግዚአብሔርን የማያስከብርና ትእዛዙንም የሚቃረን ነው ብለው ያምናሉ።

ክርስቲያኖች ማንኛውንም የኢየሱስን ሥዕል በቤተ ክርስቲያናቸውም ሆነ በቤታቸው ስለ መስቀል እጅግ መጠንቀቅ አለባቸው። ለዚህም አራት ዋና ዋና ምክንያቶች አሉ:-

1. በዘጸ. 20፡4-6 የሚገኘው ሁለተኛው ትእዛዝ፥ ይህ በእግዚአብሔር ፊት ትክክል እንዳልሆነ በግልጥ የሚያሳይ ይመስላል።

2. ሥዕሎቹ ኢየሱስን አያስከብሩም። እንዴት ኢየሱስን በትክክል ወይም ብቃት ባለው መንገድ መግለጥ ወይም መሣል ይቻላል? መጀመሪያ፥ በአሁኑ ጊዜ ከሚኖሩ ሰዎች ኢየሱስን ያየ ስለሌለ ምን እንደሚመስል አናውቅም። ሥዕሉን መሥራት የምንችለው ባሕላዊ አስተሳሰባችንን መሠረት በማድረግ ብቻ ነው። ሁለተኛ፥ ኢየሱስ ከሰው ብልጫ ያለው ነው። እርሱ አምላክ ነው። እንደ አምላክነቱ ክብሩን፥ ኃይሉን፥ ችሎታውን፥ ግርማ ሞገሱን፥ ቅድስናውንና ፍቅሩን ወዘተ. በሚገባ ልንገልጥ አንችልም።

3. ሥዕሎች ለክርስቲያኖች በቀላሉ የማሰናከያ ዓለት ሊሆኑ ይችላሉ፤ በመጀመሪያ፥ የኢየሱስን ሥዕል ስንሰቅል መጥፎ ነገር ሆኖ ላይሰማን ይችላል። ስለ ኢየሱስ «እንድናስብና» ሕልውናው «እንዲሰማን» ብቻ ያደርጋል እንላለን። ወዲያውኑ ግን ወደ ኢየሱስ ምስል መጸለይ እንጀምራለን፤ በአእምሮአችንም ውስጥ ያ ሥዕል ይቀረፃል። እንግዲህ የምንጸልየው ለምስሉ እንጂ ለኢየሱስ አይደለም ማለት ነው። በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ሁሉ የሚታየው የክርስቲያኖች ዝንባሌ ሥዕሎችን ወደሚመለክ ነገር መለወጥ ነው። ይህ ደግሞ በተለይ በካቶሊክና በኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ይታያል።

17ኛ ጥያቄ፥ አንዳንድ የኦርቶዶክስ አማኞች ሥዕሎችን ወይም ሐውልቶችን ሲያመልኩ እንዴት እንዳየህ ግለጥ። ይህ እግዚአብሔርን የሚያስከብር ነው ወይስ የሚያዋርድ?

4. ሥዕሎች መጥፎ ምስክርነትን የሚያሳዩ ናቸው። በተለይ ሥዕል የምናመልክ ለሚመስላቸው ሙስሊሞችና አንዳንድ የኦርቶዶክስ ክርስቲያኖች መጥፎ ምስክርነት ይሆናሉ።

ሥዕሎች በእምነታችንና በምስክርነታችን ላይ የሚያመጡት አደጋ ሊሰጡን ከሚችሉት ከማንኛውም ዓይነት ጥቅም ይልቅ የሚያመዝን ነው። ስለዚህ እነዚህን ሥዕሎች በቤተ ክርቲያንም ሆነ በቤታችን አለመስቀል የሚመረጥ ይመስላል።

## እስራኤላውያን ከግብፅ ነፃ የወጡበት ጊዜ

እስራኤላውያን ግብፅን ለቀው ወደ ከነዓን መጓዝ ስለ ጀመሩበት ጊዜ ምሁራን ያለማቋረጥ ይከራከራሉ። ሁሉም ምሁራን የሚስማሙት ይህ ነፃ የመውጣት ተግባር የተፈጸመው ከ1450-1200 ዓ.ዓ. ባለ ጊዜ እንደ ሆነ ነው። ምሁራን የሚቀበሉዋቸው ሁለት ዋና ዋና ጊዜያት አሉ። በመጀመሪያ፥ የኋለኛ ጊዜያትን የሚቀበሉትን እናገኛለን። እነዚህ ምሁራን የዘጸአት ታሪክ የተፈጸመው ልክ በመጽሐፍ ቅዱስ እንደተጻፈው አይደለም ይላሉ። ጊዜን በሚመለከትም አሪት ዘጸአት ሕዝቡ ከግብፅ የወጡበትን ትክክለኛ ቀን አልዘገበም በማለት የሚተማመኑትና ምክንያት የሚያቀርቡትም ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጭ በከርሰ-ምድር ጥናትና በታሪካዊ መረጃዎች ላይ በመመሥረት ነው። ስለዚህ ከግብፅ የመውጣት ታሪክ የተፈጸመው በ1321-1205 ዓ.ዓ. አካባቢ እንደሆነ ይናገራሉ።

በመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ የሚያምኑ ምሁራን ከግብፅ የመውጣት ታሪክ የተፈጸመው ቀደም ብሎ ነው በማለት ቀኑን ወደ 1450 ዓ.ዓ. ይወስዱታል። ይህንን ቀን የመረጡበት ምክንያት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በሚገኙ ሁለት ጥቅሶች ሳቢያ ነው፤ እነርሱም፡- መሳ. 11፡26 እና 1ኛ ነገሥ. 6፡1 ናቸው።

18ኛ ጥያቄ፥ መሳ. 11፡26ና 1ኛ ነገ. 6፡1 አንብብ። እነዚህ ቁጥሮች እስራኤላውያን ከግብፅ ከወጡ በኋላ ምን ያህል ጊዜ አልፎአል ይላሉ?

በመሳ. 11፡26 እስራኤላውያን አንዳንድ ከተሞችን ለ300 ዓመታት ይዘው እንደነበር ይናገራል። ስለዚህ ከዘመነ መሳፍንት ጀምሮ ስናየው እስራኤል ከነዓንን በኢያሱ አማካይነት ከወረሱ 300 ዓመታት አልፈዋል ማለት ነው። ይሁን እንጂ በመሳፍንት ያለውን ጊዜ ጥርት አድርጎ ለመግለጽ አስቸጋሪ ስለሆነ፥ እስራኤላውያን ከግብፅ የወጡበትን ቀን ለመወሰን አይረዳንም።

በ1ኛ ነገሥ. 6፡1 ደግሞ ከግብፅ የመውጣት ታሪክ ከተፈጸመ 480 ዓመታት ማለፋቸውን ይናገራል። ይህም ቀን እስራኤላውያን ከግብፅ የወጡበትን ጊዜ በበለጠ ቅርበት ለመወሰን ይረዳናል። ምሁራን ከተለያዩ መረጃዎች በመነሣት የሰሎሞን መንግሥት አራተኛው ዓመት 966 ዓ.ዓ. እንደሆነ አረጋግጠዋል። ስለዚህ ከግብፅ የመውጣት ታሪክ የተከናወነው ከ480 ዓመታት በፊት ከሆነ የተፈጸመው በ1446 ዓ.ዓ. አካባቢ ነው ማለት ነው። ይህም እስራኤላውያን ከግብፅ የወጡበት ጊዜ እንደሆነ ልንጠራጠር የምንችልበት ምክንያት የለም።

## የኦሪት ዘጸአት አስተዋጽኦ

19ኛ ጥያቄ፥ ስለ ኦሪት ዘጸአት ከመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት አንብብ። እዚያ የሚገኘውን አስተዋጽኦ ገልብጥ። በሚቀጥሉት ገጾች የሚገኘውን አስተዋጽኦም አጥና።

በአጠቃላይ የኦሪት ዘጸአት ታሪክ በሦስት ዋና ዋና ክፍሎች ይከፈላል፡-

1. እስራኤላውያን በግብፅ ምድር (ዘጸ. 1-12፡36)

በዚህ የመጀመሪያ ክፍል ውስጥ ሦስት ዋና ዋና ነገሮች ተጠቅሰዋል። በመጀመሪያ የምናየው፥ የሙሴን ታሪክ ሲሆን ስለ ልደቱ፥ በምድረ በዳ ስላሳለፈው ጊዜና እግዚአብሔር እንዴት ለመሪነት እንደመረጠው እንመለከታለን።

በሁለተኛ ደረጃ፥ ስለ አሥሩ መቅሠፍቶች፥ እግዚአብሔር በግብፃውያን ላይ ለመፍረድና ሕዝቡን ከባርነት ቀንበር ነፃ ለማውጣት እነዚህን መቅሠፍቶች እንዴት እንደተጠቀመባቸው እንመለከታለን።

በሦስተኛ ደረጃ፥ በፋሲካ በዓል ታሪክ አማካይነት እግዚአብሔር የእስራኤልን ሕዝብ ከባርነት ቀንበር ነፃ በማውጣት እንዴት እንደመራቸው የሚያሳየውን ታሪክ እንመለከታለን።

2. ከግብፅ ወደ ሲና ተራራ የተደረገ ጉዞ (ዘጸ. 12፡37- ምዕ. 18)

እስራኤላውያን ወደ ሲና ተራራ ለመድረስ ያደረጉት ጉዞ ሦስት ወራት ፈጀባቸው። እግረ መንገዱንም የሚከተሉት ዋና ዋና ድርጊቶች ተፈጸሙ፡-

አንደኛ፥ እግዚአብሔር እስራኤላውያን ቀይ ባሕርን እንዲሻገሩ አስቻላቸው፥ ፈርዖንና ሠራዊቱን ግን አሰጠማቸው።

ሁለተኛ፥ እስራኤላውያን በሦስት ዋና ዋና ጉዳዮች በእግዚአብሔር ላይ አጕረመረሙ። ስለ መራራው ውኃ አጕረመረሙና ሙሴ፥ በእግዚአብሔር ኃይል ወደ ጣፋጭነት ለወጠው። እግዚአብሔር ለሕዝቡ መናንና ድርጭቶችን ለምግብነት ሰጣቸው። ሕዝቡ እግዚአብሔር ከዓለት ውኃ እስኪሰጣቸው ድረስ አጕረመረሙ።

ሦስተኛ፥ ከአማሌቃውያን ጋር ጦርነት ተካሄደ። እግዚአብሔርም ለእስራኤል ሕዝብ ድልን ሰጠ።

አራተኛ፥ የእስራኤልን ሕዝብ በመምራት ሥራ ሙሴን ይረዱት ዘንድ የሰባ ሽማግሌዎች ምርጫ ተካሄደ።

3. በሲና ተራራ የቃል ኪዳኑ መሰጠት (ዘጸ. 19-40)

የእስራኤል ሕዝብ በሲና ተራራ ላይ ለአንድ ዓመት ያህል ቆዩ። አሪት ዘጸአትና ዘሌዋውያንም ሕዝቡ በሲና ተራራ ላይ ስለነበሩበት ጊዜ ይናገራሉ። በሲና ተራራ የተደረጉ አራት ዋና ዋና ድርጊቶች በኦሪት ዘጸአት ውስጥ ተገልጸዋል።

አንደኛ፥- እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን በጽላት ላይ የጻፋቸውን ዓሠርቱን ትእዛዛት ሰጣቸው።

ሁለተኛ፥ የተቀደሱ ሕዝቦች ይሆኑ ዘንድ መጠበቅ ያለባቸውን የቃል ኪዳን መመዘኛዎች እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን ሰጣቸው።

ሦስተኛ፥ እስራኤላውያን እግዚአብሔርን የሚያመልኩበትን የመገናኛ ድንኳን አሠራር የሚያመለክት ትእዛዝ ተቀበሉ። በተጨማሪ በመገናኛው

ድንኳን ውስጥ ካህናትን ለአገልግሎት የመመደብንም ትእዛዝ ሰጣቸው። በሲና ተራራ ላይ እያሉ እነዚህን ትእዛዛት ፈጸሙ።

አራተኛ፥ እስራኤላውያን የጥጃ ምስል ሠርተው በማምለክ በእግዚአብሔር ላይ ኃጢአት አደረጉ፤ የማመንዘር ኃጢአትንም ፈጸሙ፤ እግዚአብሔርም በብርቱ ቀጣቸው።

| |
|---|
| 20ኛ ጥያቄ፥ ለመጨረሻ ፈተና ዝግጅት ይረዳህ ዘንድ እነዚህን ሦስት ዋና ዋና የኦሪት ዘጸአት ክፍሎችንና በውስጣቸው የተፈጸሙ ድርጊቶችን በሚገባ ከልስ። |

ከዚህ በታች የኦሪት ዘጸአትን ታሪክ በሚገባ ለማስታወስ የሚረዳ ዝርዝር አስተዋጽኦ ቀርቦአል፡-

1. እግዚአብሔር ሕዝቡን - እስራኤልን ከግብፅ አዳነ (ዘጸ. 1-18)
   - ሀ. እግዚአብሔር እስራኤልን እንደሚያበዛ የገባውን ቃል ኪዳን ፈጸመ (ዘጸ. 1)
   - ለ. እግዚአብሔር ሙሴን ለመሪነት መርጦ አዘጋጀው (ዘጸ. 2-6)፤
   - ሐ. እግዚአብሔር ግብፅን በአሥር መቅሠፍቶች መታ (ዘጸ. 7-11)፤
   - መ. እግዚአብሔር የፋሲካን በዓል ለእስራኤል ሕዝብ ሰጠ (ዘጸ. 12፡1-28)፤
   - ሠ. እስራኤላውያን ከግብፅ ወጡ (ዘጸ. 12፡29-51)፤
   - ረ. በግብፅ የተወለዱት የእስራኤላውያን በኩራት በሙሉ ተቀደሱ (ዘጸ. 13፡1-16)፤
   - ሰ. እስራኤላውያን ቀይ ባሕርን ተሻገሩ (ዘጸ. 13፡17-15፡21)፤
   - ሸ. እስራኤላውያን ወደ ሲና ተራራ ተጓዙ (ዘጸ.15፡22-18፡27)።
2. እግዚአብሔር በሲና ተራራ ከእስራኤል ሕዝብ ጋር ቃል ኪዳን አደረገ (ዘጸ. 19-24)

ሀ. አይሁድ ከእግዚአብሔር ጋር ለመገናኘትና ቃል ኪዳን ለመቀበል ተዘጋጁ (ዘጸ. 19)፤

ለ. እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን ዓሠርቱን ትእዛዛት ሰጣቸው (ዘጸ. 20፡1-17)፤

ሐ. እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን ስለተቀደሰ አንዋንዋር መመሪያ ሰጣቸው (ዘጸ. 20፡18-23፤ 33)፤

መ. እስራኤላውያን በቃል ኪዳኑ ተስማሙ፤ ቃል ኪዳኑም ተረጋገጠ (ዘጸ. 24፡1-8)።

3. እግዚአብሔር የሚመለክበትን የመገናኛ ድንኳን አሠራር የሚመለከት ትእዛዝ ሰጠ (ዘጸ. 25-40)

ሀ. የመገናኛውን ድንኳን ለመሥራት ዝግጅት ተደረገ (ዘጸ. 24፡9-31፡18)፤

ለ. እስራኤላውያን ጣዖትን በማምለክ ኃጢአት ላይ ወደቁ፤ ተፈረደባቸውም (ዘጸ. 32-34)፤

ሐ. የማደሪያው ድንኳን ተሠራና እግዚአብሔር አደረበት (ሕልውናውን ገለጠበት) (ዘጸ. 35-40)።

## 2ኛ ቀን፡-

### የኦሪት ዘጸአት ዓላማ

የፔንታቱክ መጻሕፍትን ለመጽሐፍ ቅዱስ መሠረትን ይጥላሉ። የኦሪት ዘፍጥረት ተቀዳሚ ተግባር በብሉይ ኪዳን የእግዚአብሔር ሕዝብ የነበሩትን የአይሁድን አጀማመር መግለጥ እንደነበር አይተናል። የኦሪት ዘፍጥረት መጨረሻ የሚያሳየው የእስራኤል ሕዝብ ከተስፋይቱ ምድር ውጭ በግብፅ እንዴት እንደተገኙ ነው። ኦሪት ዘጸአት እስራኤላውያን ወደ ታላቅ ሕዝብነት እንዴት እንዳደጉና ግብፅን ትተው ወደ ተስፋይቱ ምድር ወደ ከነዓን ለመመለስ እንዴት ጉዞ እንደጀመሩ ያሳየናል። ይህ መጽሐፍ እግዚአብሔር እስራኤላውያንን እንዴት ትልቅ ሕዝብ እንዳደረጋቸው፥ የተመረጡ ሕዝብ እንደ መሆናቸው መጠንም ከእርሱ ጋር ያላቸውን ግንኙነት የሚያስረዳውን ቃል ኪዳን እንዴት እንደገባ ይነግረናል።

ኦሪት ዘጸአት አራት ዋና ዋና ዓላማዎች አሉት። እነርሱም ፡-

1. እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ከባርነት እንዴት ነፃ እንዳደረጋቸው መናገር ነው። ይህ ታሪክ የመዋጀት ታሪክ ነው። «መዋጀት» የሚለው ቃል መጽሐፍ ቅዱስን ለመረዳት የሚያስችል ቁልፍ ቃል ነው። «መዋጀት» የሚለው ቃል የሚናገረው ተገቢውን ዋጋ በመክፈል ሰውን ከባርነት ነፃ ስለ ማውጣት ነው። በአዲስ ኪዳን ውስጥ በኢየሱስ ደም ከኃጢአት ባርነት ተዋጅተናል (ማር. 10፡45)። በብሉይ ኪዳን ግን የመዋጀትን ግልጥ ሥዕል የምንመለከተው እግዚአብሔር የአይሁድን ሕዝብ ከግብፅ ባርነት ለመዋጀት በሠራው ሥራ ውስጥ ነው (ዘጸ. 6፡6፤ ዘዳ. 15፡15 ተመልከት)።

እስራኤላውያን በትውልዶች ሁሉ እግዚአብሔር በግብፅ ከነበሩበት ባርነት እንዴት ነፃ እንዳወጣቸው ማስታወስ ነበረባቸው። ይህም እግዚአብሔር ከምንም ዓይነት ባርነት ነፃ እንዳወጣቸው ለማመን መሠረት ሆናቸው። በተጨማሪም የሌሎች አሕዛብን አማልክት ሳይከተሉ፥ በእግዚአብሔር ላይ ያላቸውን እምነት እንዲጠብቁ ረድቶአቸዋል።

2. የእስራኤል ሕዝብ ልዩ ወይም የተለዩ እንደሆኑ ለማስታወስ ነበር።

| |
|---|
| 21ኛ ጥያቄ፥ ዘጸ. 19፡3-6 አንብብ። ሀ) እስራኤላውያን በእነዚህ ቁጥሮች የተገለጡት እንዴት ነው? ለ) እነዚህን ቁጥሮች ከ1ኛ ጴጥ. 2፡5-9 ጋር አወዳድር። ቤተ ክርስቲያን ከእስራኤል ጋር የምትመሳሰለው እንዴት ነው? ሐ) የአንተ ቤተ ክርስቲያን ይህን ጥሪ እንዴት እየፈጸመች ነው? |

እግዚአብሔር እስራኤላውያንን በዚህ ምድር ከሚኖሩ ሌሎች ሕዝቦች ሁሉ ለይቶ የተለዩ ቅዱስ ሕዝብ እንዲሆኑ መረጣቸው። ከሌሎች ሕዝቦች ሁሉ የተለዩ ነበሩ። የእግዚአብሔር የግል ገንዘቡ ነበሩ። የእግዚአብሔር ካህናት የሆኑ ሕዝብ ነበሩ። እግዚአብሔር ከእስራኤል ሕዝብ ጋር ያደረገው ቃል ኪዳን የሕዝቡን ልዩ መሆን አጠናከረው። ከሌላው ሕዝብ ጋር ጨርሶ ባልተገናኘበት መንገድ ከዚህ ሕዝብ ጋር ተገናኘ፥እግዚአብሔር ለነዚህ ሕዝብ፥ በቃል ኪዳኑና በሲና ተራራ በሰጣቸው ትእዛዛት መሠረት በታዛዥነት ከተራመዱና ከኖሩ ብቻ፥ ከዓለም የተለዩ እንደሚሆኑ ሊያሳያቸው ፈልጎ ነበር። ይህ ሲሆን ብቻ ነው የካህናት መንግሥትና ቅዱስ ሕዝብ ሊሆኑ የሚችሉት (ዘጸ. 19፡5-6)።

በሲና ተራራ ላይ የተፈጸመው ቃል ኪዳን፥ በእግዚአብሔርና በእስራኤል ሕዝብ መካከል ሊኖር የሚገባውን ይህን ልዩ ግንኙነት አሳይቷል። እርሱን ብቻ ሊያመልኩ ይገባ ነበር። በእግዚአብሔር ፊት በመታዘዝና በቅድስና ሊኖሩ፥ በቅድስናቸውም እርሱን ሊመስሉ ይገባ ነበር፤ (ዘጸ. 22፡31)። በእርሱ በኩል እግዚአብሔር ለእነርሱ በተለየ መንገድ ኅብረት ያደርግ ነበር። በአእምሮአቸው ውስጥ የሚኖረው ክብሩን ሊያንፀባርቅ በሚችል የደመና ክብር እንጂ፥ በተቀረፀ ምስል ክብር አልነበረም። እግዚአብሔር «እርሱ የሚያድርበትን የመገናኛ ድንኳን» እንዲሠሩ አዘዛቸው (ዘጸ. 40፡33-38 ተመልከት)።

22ኛ ጥያቄ፥ 1ኛ ቆሮ. 3፡16-17፤ 6፡19 አንብብ። ሀ) በአዲስ ኪዳን ዘመን የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ምንድነው? ለ) በብሉይ ኪዳን ከነበረው ከመገናኛው ድንኳን ዓላማ ጋር እንዴት ይመሳሰላል?

3. እስራኤላውያን ልዩ የሆኑት በሕዝብነታቸው ታላቅነት ሳይሆን፥ በእግዚአብሔር ምሕረትና ሉዓላዊ ምርጫ መሆኑን እንዲያስቡት ለማድረግ ነው። እነርሱ እግዚአብሔርን አልመረጡትም፤ እርሱ መረጣቸው እንጂ። ሆኖም ይህ ልዩ መብት እግዚአብሔር በሲና ተራራ ከእነርሱ ጋር ባደረገው ቃል ኪዳን ውስጥ ለሚገኙት ቅድመ-ሁኔታዎች እስራኤላውያን ባላቸው መታዘዝ ላይ መመሥረት ነበረበት። እስራኤላውያን ካልታዘዙ፥ ከእግዚአብሔር ዘንድ የሚያገኙት አንዳችም በረከት አይኖርም።

4. ለእስራኤላውያን የእግዚአብሔርን ታላቅነት ለማሳየት ነው። ብዙ ጊዜ እግዚአብሔርን ሊረዳቸው እንደማይችል እንደ አንድ ደካማ ምስል አድርገው ያስቡት ነበር። የአብርሃምን፥ የይስሐቅንና የያዕቆብን ታሪክ የሰሙ ቢሆንም እንኳ በግል እግዚአብሔርን አልተዋወቁትም ነበር። ስለዚህ ከእግዚአብሔር ጋር ባላቸው ግንኙነት መጀመሪያ ታላቅነቱን ለእነርሱ ገለጠላቸው። እግዚአብሔር ታላቅነቱን የገለጠላቸው በተለያዩ መንገዶች ነው። በመጀመሪያ፥ ታላቅነቱንና ኃይሉን የበለጠ ሊገልጥ የሚችለውን የራሱን አዲስ ስም ሰጣቸው። ያ ስም «ጂሆቫ» ወይም «ያህዌ» የሚል ነበር፤ (ዘጸ. 3፡13-15 ተመልከት)። ሁለተኛ፥ በፍጥረታት ሁሉና በምድር ከሁሉም ይበልጥ ገናና በነበረው መሪ ላይ እንኳ 10 መቅሰፍቶችን በመላክ ኃይሉን ገለጠ። ሦስተኛ፥ ቅድስናውንና ኃይሉን በሲና ተራራ በነጎድጓድ

በታጀበ ታላቅ ድምፅ ገለጠላቸው (ዘጸ. 19፡15-19 ተመልከት)። አራተኛ፥ እግዚአብሔር ታማኝ መሆኑን ለአብርሃምና ለቀሩት የእስራኤል ሕዝብ አባቶች የገባላቸውን ተስፋ በመፈጸም አሳየ። እግዚአብሔር ለመረጣቸው ሰዎች ሁልጊዜ ታማኝ ነው። የገባውንም የተስፋ ቃል ዘወትር ይጠብቃል።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የእግዚአብሔር ፍላጎት ራሱን ለእኛ መግለጥ ስለሆነ በአራት ዘጸአት ያለው ከሁሉም የሚበልጥ ዓላማ ይህ ሳይሆን አይቀርም። እግዚአብሔር አምላካችንን የምናውቅ ሕዝብ መሆን አለብን። በተለይ ጥርጥር በተስፋፋበት በዚህ ዘመን የእግዚአብሔርን ባሕርይ ባወቅንና በተረዳን መጠን በእርግጠኛነትና በእምነት ዋስትና መኖራችን ይቀጥላል።

23ኛ ጥያቄ፥ እነዚህ አራት ዓላማዎች ዛሬ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚንፀባረቁት እንዴት ነው?

## 3ኛ ቀን፡- ዘጸአት 1-12

24ኛ ጥያቄ፥ ሀ) በአሁኑ ጊዜ አንተም ሆንክ በኢትዮጵያ ያሉ ሌሎች ክርስቲያኖች የምትጋፈጧቸው የመንፈሳዊ ውጊያ ክፍል የሆኑ ነገሮችን ዘርዝር። ለ) ብዙ ክርስቲያኖች እየተሸነፉ ያሉት እንዴት ነው? ሐ) እግዚአብሔር ለአንተና ለቤተ ክርስቲያንህ በእነዚህ ነገሮች ላይ ድልን ሲሰጥ ያየኸው እንዴት ነው?

ክርስቲያን በመንፈሳዊ ውጊያ ውስጥ መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምራል። ይህ ውጊያ በመጨረሻ በእግዚአብሔርና በሰይጣን መካከል በከፍተኛ ደረጃ የሚጧጧፍ ነው። ውጊያው ሰይጣንና የእግዚአብሔር ሕዝቦችንም ያሳትፋል። ሰይጣን የእግዚአብሔርን ሕዝቦች ለመጨቆን ብዙ የተለያዩ ነገሮችን ይጠቀማል። ሰዎች የሌሎች ባሪያዎች እንዲሆኑ በማድረግ ሥጋዊ እስራትን ሊያመጣ ይችላል። ሰዎችን የሚጨቁንና ወንጌልን የሚቃወም መንግሥትንም መሣሪያ ሊያደርግ ይችላል። የእግዚአብሔር ሕዝብ ከእውነት ዞር እንዲሉ ለማድረግ የሚፈልጉ ሐሰተኛ ሃይማኖቶችንም መጠቀም ይችላል። ብዙ ጊዜ ክርስቲያኖች ይህን በመሰለ መንፈሳዊ ውጊያ ውስጥ ሲገቡ እግዚአብሔር የተዋቸውና የሚሸነፉም ይመስላቸዋል፤ ይህ ግን እውነት አይደለም። መጽሐፍ ቅዱስ አሸናፊው ሁልጊዜ እግዚአብሔር እንደሆነ ይናገራል። እርሱ

መንግሥታትን፥ መሪዎችን፥ ሐሰተኛ ሃይማኖቶችን፥ ሰይጣንና አጋንንትን ሁሉ የሚቆጣጠር ነው። አምላካችን ገዥ ነው። እግዚአብሔር በራሱ ጊዜ ኃይሉን በጠላቶቹ ሁሉ ላይ ይገልጻል። አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔር አንዳዶችን ሲያነሣና ሌሎችን ሲጥል በሕይወት ዘመናችን ኃይሉን እናያለን። በሌላ ጊዜ ደግሞ የእግዚአብሔር ኃይል ጠላቶቹን ሁሉ እስከሚጥልበት፥ እስከመጨረሻው ጊዜ ድረስ ተሰውሮ ይቆያል።

ይህ የኦሪት ዘጸአት የመጀመሪያ ክፍል ታሪክ እግዚአብሔር ሰይጣንን ለማሸነፍ እንዴት እንደሠራ ይነግረናል። እግዚአብሔር የተመረጡትን ሕዝቦቹን ከባርነት ነፃ ለማድረግ የሠራውን ሥራ ይተርክልናል። እግዚአብሔር ዓላማውን ለመፈጸም ተፈጥሮንና መሪዎችን በመቆጣጠር ረገድ በሕዝቡ ሠርቷል።

25ኛ ጥያቄ፥ ዘጸ. 1-12 አንብብ። ሀ) የእግዚአብሔር ሕዝብ የነበሩበት ሁኔታ ምን ይመስል ነበር? ለ) እግዚአብሔር ሙሴን ለመሪነት ለማዘጋጀት እንዴት ሠራ? ሐ) የተመረጠ መሪ መሆኑን ለማረጋገጥ እግዚአብሔር ለሙሴ ያሳያቸው ሦስት ተአምራት ምንድን ናቸው? መ) ሙሴ የእስራኤልን ሕዝብ ከባርነት ነፃ ለማውጣት በሚሞክርበት ጊዜ ያገኘው የመጀመሪያ ውጤት ምን ነበር? ሠ) እግዚአብሔር ግብፃውያን፥ ሕዝቡን (እስራኤላውያንን) ይለቁ ዘንድ ያመጣባቸው አሥር መቅሠፍቶችን ዘርዝር። ረ) እነዚህ መቅሠፍቶች በግብፅ ላይ በወረዱ ጊዜ እግዚአብሔር ለሕዝቡ ለእስራኤል ያለውን እንክብካቤ እንዴት ገለጠ? ሰ) የፋሲካ በዓል ዓላማ ምን ነበር? ቀ) ከእነዚህ ቁጥሮች ስለ እግዚአብሔር የምንማራቸው ነገሮች ምንድን ናቸው? ሸ)እስራኤላውያን ግብፃውያንን «የበዘበዙት» በምን መንገድ ነበር?

4ኛ ቀን፡-

1. ዘጸአት 1. የእግዚአብሔር ሕዝብ በባርነት ቀንበር ሥር መሆን

ሀ. እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ስለባረካቸው ተባዙ (ዘጸ. 1፡1-7)

ኦሪት ዘጸአት የሚጀምረው የዘፍጥረትን የመጨረሻ ታሪክ በክለሳ መልክ አጠቃልሎ በማቅረብ ነው። ዘጸአት ፔንታቱክ ተብሎ የሚታወቀው መጽሐፍ ትልቅ ክፍል መሆኑን አስታውስ።

የእስራኤል ሕዝብ ወደ ግብፅ የወረዱት ለምንድ ነው? በባርነትስ የወደቁት እንዴት ነበር? እነዚህ የዘጸአት ምዕራፍ 1 ሁለት ዋና ዋና ጥያቄዎች ናቸው። እስራኤላውያን ወደ ግብፅ የወረዱበት ምክንያት የያዕቆብ ዝርያዎች፥ የአሥራ ሁለቱ ነገድ መሪዎች በሆኑት አሥራ ሁለቱ የያዕቆብ ልጆች መሪነት በዚያ ለመኖር መሆኑን ሙሴ ያስታውሰናል። መጀመሪያ ወደ ግብፅ በደረሱ ጊዜ 70 ሰዎች ብቻ ነበሩ። እግዚአብሔር ግን ለአብርሃም የገባውን የተስፋ ቃል አስቦና አክብሮ ታላቅና የተፈራ ሕዝብ አድርጎ አበዛቸው።

| |
|---|
| 26ኛ ጥያቄ፥ ዘፍ. 12፡2 አንብብ። ሀ) እግዚአብሔር ለአብርሃም የሰጠው ተስፋ ምን ነበር? ለ) ይህ ተስፋ በዘጸ. 1 የተፈጸመው እንዴት ነው? ሐ) ስለ እግዚአብሔርና ስለ ተስፋ ቃሎቹ ይህ ምን ያስተምረናል? |

በዘጸ. 1፡6 ና 1፡7 መካከል በመቶ የሚቆጠሩ ዓመታት ልዩነት አለ። እስራኤላውያን በሙሴ መሪነት ከግብፅ ለመውጣት በተንቀሳቀሱበት ጊዜ ቁጥራቸው ከሚሊዮን በላይ ይሆን እንደነበር ምሁራን ይገምታሉ። (በዘጸ. 12፡37 ሴቶችና ልጆች ሳይቆጠሩ ቁጥራቸው ስድስት መቶ ሺህ እንደነበር ተጽፏል።

ለ. እስራኤላውያን በባርነት ቀንበር ሥር የወደቁና የተጨቆኑ ነበሩ (ዘጸ. 1፡8-22)

በዘጸ. 1፡8 እንደምናነበው፥ ዮሴፍን የማያውቅ አዲስ ንጉሥ ተነሥቶ የእግዚአብሔርን ሕዝብ መጨቆን ጀመረ። ይህ ነገር የሆነው በግምት ዮሴፍ ከሞተ ከ200 ዓመታት በኋላ ነበር። በዚህ ጊዜ ግብፃውያን ሐይክሶሳውያንን አሸንፈው አገራቸውን እንደገና ማስተዳደር ጀምረው ነበር። የውጭ ዜጎች በአገልግሎት ሥልጣን እንዳይኖራቸው በመደረጉ፥ አይሁዶች በባርነት ቀንበር ተያዙ። ምሁራን ይህ ጭቆና የተጀመረው በ1550 ዓ.ዓ. ነው ይላሉ። ይህም ማለት አይሁድ ከባርነት ነፃ እስከ ወጡበት 1450 ዓ.ዓ. ድረስ፥ ለ100 ዓመታት በባርነት ቀንበር ሥር ቆይተዋል ማለት ነው።

ግብፆች አይሁዳውያንን ከማባረር ይልቅ ከተሞችን ለመገንባት ሊጠቀሙባቸው መረጡ። ስለዚህ ግብፃውያን አይሁዳውያንን ባሪያዎች አደረጉአቸው። አይሁዳውያን በግብፅ ውስጥ የሚገኙትን ከባድ ሥራዎች

ሁሉ ለመሥራት ተገደዱ። ነገር ግን ቁጥራቸው እጅግ እንዳይበዛና ግብፃውያንን ሥጋት ላይ እንዳይጥሉአቸው የግብፅ ንጉሥ እስራኤላዊ የሆነ ወንድ በሚወለድበት ጊዜ እንዲገደል አዋላጆችን አዘዘ። አዋላጆች ግን ይህንን ከማድረግ ተቆጠቡ።

በባርነት ቀንበር ሥር በነበሩበት ጊዜ እንኳ የእግዚአብሔር እጅ አልተለያቸውም ነበር። እግዚአብሔር የእስራኤልን ሕዝብ ስለባረከ የግብፃውያን ጥረት ሁሉ ከንቱ ሆኖ ቀረ። (ቁጥራቸው እጅግ እየጨመረ ሄደ፤)

| |
|---|
| 27ኛ ጥያቄ፥ በዚህ ውስጥ ስለታየው የእግዚአብሔር ኃይል ምን እንማራለን? |

2. እግዚአብሔር ሕዝቡን ከግብፅ ለማውጣት አንድ መሪን ጠራ (ዘጸ. 2-4)።

የሙሴ ሕይወት በሦስት ዘመናት ሊከፈል ይችላል፡- ሀ) ሙሴ እንደ አንድ ግብፃዊ ለ40 ዓመታት ሠልጥኗል። ለ) እግዚአብሔር ሙሴን በምድረ በዳ ለ40 ዓመታት አሠለጠነው። ሐ) ሙሴ የእግዚአብሔርን ሕዝብ ለ40 ዓመታት መርቷል።

ሀ. ሙሴ እንደ አንድ ግብፃዊ ሠልጥኗል (ዘጸ. 2፡1-10)።

ስለ ሙሴ የመጀመሪያ 40 ዓመታት የተጻፈው ነገር በጣም ጥቂት ነው። በሕፃንነቱ በግብፃውያን እጅ ከመገደል እግዚአብሔር በተአምር የጠበቀው ሰው ነው። ወላጆቹ ገና ከመወለዱ ጀምሮ ልዩ ልጅ እንደነበር የተረዱ ይመስላል። ምክንያቱም ያማረ ሕፃን፥ ወይም ተራ ያልሆነ ልጅ ተብሎ ተጠርቷል፤ (ዕብ. 11፡23 ተመልከት)። የሙሴ ወላጆች አቅማቸው የፈቀደውን ያህል ከሸሸጉት በኋላ፥ ሊደብቁት ከማይችሉበት ደረጃ ላይ ሲደርሱ፥ ይጠብቀው ዘንድ ለእግዚአብሔር አሳልፈው ሰጡት፤ በእግዚአብሔርም ታመኑ። በቅርጫት አድርገው በዓባይ ወንዝ ላይ አኖሩት። የእግዚአብሔር ጥበቃ በዚህ ሰው ላይ ምን ያህልና እንዴት እንደነበረ አስተውል፡-

1. እግዚአብሔር ሁኔታዎችን ስለተቆጣጠረ፥ የፈርዖን ሴት ልጅ በቅርጫት ተደርጎ በተቀመጠበት ወንዝ ዳር ሙሴን አገኘችውና እንደ ልጇ ልታሳድገው ወደ ቤቷ ወሰደችው?

2. የሙሴ እናትና እኅት በአስተዳደጉ ላይ ተጽዕኖ እንዲያሳድሩ እግዚአብሔር ሁኔታዎችን አመቻቸ። ሙሴ ዕብራዊ መሆኑን የተማረው ከየት ነበር? ስለ እግዚአብሔር የተማረውስ የት ነው? ከእናቱና ከእኅቱ እንደሆነ አይጠረጠርም።

28ኛ ጥያቄ፥ ወንጌልን ለልጆቻችን ስለማስተማር አስፈላጊነት ይህ ምን ያስተምረናል?

ሙሴ በግብፅ ያሳለፈው አብዛኛው ነገር አልተገለጸም። የምናውቀው ነገር ቢኖር በግብፅ ትምህርትና ጥበብ ሁሉ ማደጉን ነው (የሐዋ. 7፡22፤ ዕብ. 11፡24-27 ተመልከት)። ከግብፃውያን ትምህርት ቤቶች ከሁሉ በተሻለው ውስጥ ከንጉሣውያን ቤተሰብ ልጆች ጋር ሳይማር አልቀረም። አንዳንድ ምሁራን የግብፅ ንጉሥ ለመሆን በሚችልበት መስመር ላይ ነበር ይላሉ።

ሙሴ በግብፅ የተማረው ትምህርት በኋላ ፔንታቱክን ለመጻፍ ተግባሩ ጠቅሞታል።

ለ. ሙሴን በምድረ በዳ ውስጥ እግዚአብሔር አሠለጠነው።

ሙሴ የእስራኤልን ሕዝብ እንዲመራ እግዚአብሔር እንደፈለገው ሳያውቅ አልቀረም። ነገር ግን እግዚአብሔር እስኪሠራ መጠበቅ ሲገባው የራሱን እርምጃ በመውሰድ፥ አንዱን እስራኤላዊ ለመርዳት ሲሞክር አንድ ግብፃዊን ገደለ። ከዚያም በምድያን ወዳለው ምድረ በዳ ሄዶ በኋላ ልጁን የዳረለትን ዮቶርን በእረኝነት በማገልገል 40 ዓመታት አሳለፈ። ሙሴ በነፃነት ወደ ግብፅ ለመመለስ የቻለው በእርሱ ጊዜ የነበረው ንጉሥ ከሞተ በኋላ ብቻ ነው።

29ኛ ጥያቄ፥ ሀ) እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ነፃ ለማውጣት ያን ያህል ረጅም ጊዜ የቆየው ለምን ይመስልሃል? ለ) ሙሴ ከመምረጡ በፊት ለ40 ዓመታት የቆየውስ ለምንድን ነው? ሐ) የሙሴ ታሪክ ስለ መንፈሳዊ መሪነት ምን ያስተምረናል?

ሙሴ በምድረ በዳ የተማረውን ነገር በኋላ እግዚአብሔር ተጠቅሞበታል። ሙሴ የተዘጋጀው በመንፈሳዊ ሕይወቱ ብቻ ሳይሆን፥ በሥጋዊ ረገድም በምድረ በዳ መኖር እንዴት እንደሚቻል ተምሯል።

ስለዚህ በምድረ በዳ ስለመኖር አንዳችም እውቀት የሌላቸው አይሁዳውያን ወገኖቹን ለ40 ዓመታት በምድረ በዳ ለመምራት በቅቷል።

ሐ. የእስራኤል ሕዝብ መሪ እንዲሆን እግዚአብሔር ሙሴን ጠራው (ዘጸአት 3-4)።

እግዚአብሔር በመጀመሪያ ሙሴን የተገናኘበት መንገድ አስገራሚ ትዕይንት የታየበት ነበር። እሳት እየነደደበት ነገር ግን ተቃጥሎ የማያልቅ ቁጥቋጦ ባለበት ስፍራ ተገናኘው። እግዚአብሔር ለሙሴ ኃይሉን ሊያሳየው ፈልጎ ነበር። ደግሞም እሳት ብዙ ጊዜ የእግዚአብሔር ሕልውና ምልክት ነው፤ (ሕዝ. 1፡4-5፥ 27 ተመልከት)። የእግዚአብሔር ቅድስናም ምልክት ነበር። በፊቱ በቆመ ጊዜ በአይሁድ ልማድ መሠረት ጫማውን በማውለቅ አክብሮቱን እንዲገልጥ እግዚአብሔር ለሙሴ ነገረው።

በሙሴ ጥሪ ውስጥ የሚከተሉትን ነገሮች አስተውል፡-

1) እግዚአብሔር ሙሴን መረጠውና እስራኤልን ከባርነት ነፃ ለማውጣት መሪ እንደሚሆን ነገረው።

2) እግዚአብሔር ለሙሴ «እኔ እኔ ነኝ» ወይም ያህዌ በማለት ልዩ ስሙን ነገረው። ይህ ስም የእግዚአብሔርን ኃይልና በሕዝቡ በእስራኤል ላይ ያለውን የበላይ ተቆጣጣሪነት የሚገልጽ ነው።

3) ሙሴ በእግዚአብሔር የተመረጠ መሪ መሆኑን ያውቁ ዘንድ ለእስራኤላውያን እንዲያሳያቸው ሦስት ምልክቶችን ሰጠው፡-

ሀ) እግዚአብሔር የሙሴን በትር ወደ እባብ፥ እባቡን ደግሞ መልሶ ወደ በትር ለወጠው።

ለ) እግዚአብሔር የሙሴን እጅ በለምጽ መታውና ወዲያው ደግሞ ወደ ተለመደው መልኩ መለሰው።

ሐ) እግዚአብሔር ለሙሴ፥ «አንተ በእኔ የተመረጥክ መሪ መሆንህን እስራኤላውያን ካላመኑ ከዓባይ ወንዝ ውኃን ውሰድና ወደ ደምነት ለውጠው» አለው።

4) ሙሴ በ40 ዓመታት የምድረ በዳ ቆይታው ጊዜ በጣም ተለውጦ ነበር

በራሱ ብርታት መቆሙና መተማመኑ አብቅቶ ነበር። ስለዚህ አሁን ፈራና እኔ መናገር አልችልም ብሎ ለእግዚአብሔር መልስ ሰጠ። ይህም ሙሴ በእግዚአብሔር ለመታመን ፈቃደኛ አለመሆኑን የሚያሳይ ምልክት ነበር። እግዚአብሔር ለሙሴ ጥያቄዎች በሙሉ በትዕግሥት መልስ ሰጠና ለመታዘዝ ፈቃደኛ አለመሆኑን ሲያይ ተቆጣ። እኛም ብንሆን ያልገባንን ነገር ከእግዚአብሔር የመጠየቅ መብት አለን። ነገር ግን እግዚአብሔርን ለመታዘዝ እንድንችል ሁልጊዜ ጥንቃቄ ማድረግ አለብን። ከዚያም ወንድሙ አሮን ከእርሱ ጋር እንደሚሠራና አፈቀላጤው እንደሚሆን እግዚአብሔር ለሙሴ ነገረው።

5) ሙሴ ሊነጻና እግዚአብሔርን የመታዘዝ አስፈላጊነትን ሊማር ይገባው ነበር።

ወንዶች ልጆች ሁሉ እንዲገረዙ እግዚአብሔር ያዘዘ ቢሆንም (ዘፍጥ. 17 ተመልከት) ሙሴ ግን አልታዘዘም ነበር። ወንዶች ልጆቹ አልተገረዙም ነበር። ስለዚህ እግዚአብሔር ሊፈርድበት ተዘጋጀ። እግዚአብሔር ሙሴን በአንድ ዓይነት በሽታ የመታው ይመስላል። የሙሴ ሚስት የወሰደችው ፈጣን እርምጃ ሙሴን ከሞት አዳነው። ልጇን ገረዘች። «አንተ ለእኔ የደም ሙሽራ ነህ» ብላ የተናገረችውን ቃል ምንነት መረዳት በጣም አስቸጋሪ ነው። አንዳንድ ምሁራን እንዲህ ይላሉ፡- ሲፓራ አይሁዳዊት ስላልነበረች ይህ የግዝረት ባሕል ለእርሷ እንግዳ ነበር፤ ስለዚህ ሙሴ ልጆቹን እንዲገርዝ ሳትፈቅድ ቀረች። ነገር ግን ሙሴን ለማዳን ስትል ግትርነትዋን ተወችና ልጇን ገረዘች። ይህንን በማድረጓ በመጀመሪያ ለሙሴ የገባችውን ቃል ኪዳን በማደስ እንደ አዲስ ሙሽራ ቆጠረችው። ይህንን ያረጋገጠው በመገረዙ ምክንያት ከልጇ የፈሰሰው ደም ነው። ሆኖም የዚህ ሐረግ ትርጉም ግልጽ አይደለም። የታሪኩ ትርጉም ግን ግልጽ ነው። በታሪኩ ውስጥ ሁለት ዋና ዋና ነገሮች ትኩረት ተሰጥቷቸዋል፡- ሀ) ሙሴ የእግዚአብሔር ሕዝብ መሪ ይሆን ዘንድ ቤተሰቡም መንጻትና እግዚአብሔርን ለማገልገል የተዘጋጀ መሆን ነበረበት። ግዝረት እግዚአብሔር ደስ የማያሰኙ ነገሮችን ሁሉ ከሕይወት የማስወገድና ለእግዚአብሔር ቃል ኪዳን አልፎ የመሰጠት ምልክት ነው። ለ) ምንም ያህል ትንሽና ኢምንት ቢመስሉም እንኳ ለእግዚአብሔር ትእዛዛት ሙሉ ለሙሉ መታዘዝ አስፈላጊ እንደሆነ ሙሴን ማስተማር አስፈላጊ ነበር።

30ኛ ጥያቄ፥ ሀ) እነዚህን ሁለት እውነቶች ማወቅ ለሙሴ ለምን ያስፈለገው ነበር? ለ) ዛሬም ቢሆን የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እነዚህን እውነቶች ማስታወስ ለምን ይጠቅማቸዋል? ሐ) በዚህ ዘመን ያሉ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እግዚአብሔርን በከፊል ብቻ የሚታዘዙባቸውን ሁኔታዎች ግለጽ። መ) ይህ ነገር በአመራራቸው ላይ እንዴት ተጽዕኖ ያደርጋል?

3. በአፈ-ቀላጤው ሙሴ በኩል እግዚአብሔር ከግብፅ ንጉሥ ጋር ያደረገው ውዝግብ (ዘጸ. 5-11)

በዚያን ጊዜ ግብፅ በምድር ላይ ካሉ መንግሥታት ሁሉ በላይ የሆነ ኃያል መንግሥት ነበር። ነገር ግን የሰዎች ሁሉ ፈጣሪ ከሆነው ከእግዚአብሔር የሚበልጥ ታላቅነት ነበረውን? እነዚህ ምዕራፎች እግዚአብሔርን ወክሎ በሚናገረው በሙሴና በግብፅ መሪ በነበረው በፈርዖን መካከል የተፈጠረውን ውዝግብ ያመለክታሉ። ምናልባት ሙሴ ከዚህ የግብፅ ንጉሥ ጋር በቂ ትውውቅ ያለውና አብረው ያደጉም ሳይሆኑ አይቀሩም። (ማስታወሻ:- ፈርዖን የሚለው ቃል የአንድ የግብፅ ንጉሥ ስም አይደለም። የግብፅ መሪ የሚጠራበት የሥልጣን ስም ነው። «ንጉሥ» ከሚለው ቃል ጋር ተመሳሳይ ነው) በመጀመሪያ ፈርዖን ታላቅ ኃይል ነበረው። ሙሴ የእስራኤልን ሕዝብ እንዲለቅ ሲጠይቀው ፈርዖን እንዲህ ሲል መለሰ:- «ቃሉን እሰማ ዘንድ፥ እስራኤልን እለቅቅ ዘንድ እግዚአብሔር ማን ነው? እግዚአብሔርን አላውቅም፥ እስራኤልንም ደግሞ አልለቅም» (ዘጸ. 5:2)። ይህ ጥያቄ ከቀረበለት በኋላ ፈርዖን በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ ቀንበርን ጨመረ።

ከዚያም እግዚአብሔር በግብፅ ላይ አሥር መቅሠፍቶችን ላከ። በአሥሩ መቅሠፍቶች ታሪክ ውስጥ የሚከተሉትን ነገሮች አስተውል:-

ሀ. የግብፅ አስማተኞች ሊሠሩ የቻሉት ሙሴ ከሠራቸው ተአምራት ከፊሎቹን ብቻ ነበር። ሰይጣን ብዙ ኃይል ስላለው፥ ተአምራትን ማድረግ ይችላል። የሙሴ ተአምር፥ የግብፅ አስማተኞች በመጨረሻ ይህንን ማድረግ የሚችል እግዚአብሔር ብቻ ነው እስኪሉ ድረስ፥ ከእነርሱ ተአምር የሚበልጥ ነበር (ዘጸ. 8:19 ተመልከት)። በመጀመሪያዎቹ ሁለት መቅሠፍቶች የግብፅ አስማተኞች የሙሴን ተአምራት አስመስለው አሳዩ። በሦስተኛው

መቅሠፍት ላይ ግን ማስመሰል አልቻሉም። ከአራተኛው መቅሠፍት ጀምሮ ችግሩ የደረሰው በግብፃውያን ላይ ብቻ ነበር። እግዚአብሔር ስለጠበቃቸው በእስራኤላውያን ላይ የመቅሠፍቱ ችግር አይደርስም ነበር።

ለ. ፈርዖን ከእግዚአብሔር ዘንድ ተጨማሪ ፍርድን ያስከተለበትና በመጨረሻም በበኩር ልጁ ላይ ሞትን ያመጣው የልብ ድንዳኔ ቀስ በቀስ በሕይወቱ እየጨመረ ሄደ። መጽሐፍ ቅዱሳችን የሚናገረውን ነገር በትክክል ከተመለከትን፥ የሚከተሉትን ነገሮች እናገኛለን:- 1) ፈርዖን በሕዝቡ ላይ የደረሱትን አምስት መቅሠፍቶች አስቀድሞ ቢመለከትም፥ ልቡን አደነደነ፤ (ዘጸ. 8:15፥32)። ፈርዖን እያወቀ እውነትን አልተቀበለም። 2) ከዚያም እግዚአብሔር የፈርዖንን ልብ የበለጠ አደነደነው (ዘጸ. 9:12፤ 10:1፥ 27)።

ከዚህ ታሪክ ውስጥ በጣም አስፈላጊ የሆነ መንፈሳዊ እውነት ለማየት እንችላለን። እግዚአብሔር በመጀመሪያ የሰውን ልብ በማደንደን ፍርድን በሰው ሕይወት ላይ አያመጣም፤ ነገር ግን በንስሐ ለመመለስ ወይም እግዚአብሔርን ለመታዘዝ እምቢ በማለት ልቡን ማደንደን የሚጀምረው ግለሰቡ ራሱ ነው። ያ ግለሰብ ባለመታዘዝና በፍርድ ለመኖር ሲወስን፥ እግዚአብሔር ሰውዬውን በጀመረው የልብ ድንዳኔ እንዲገፋበት ያደርገዋል። እግዚአብሔር ልቡን ይበልጥ እያደነደነው ሲሄድ፥ሰውዬው ማመን ወደማይችልበት ደረጃ ላይ ያደርሳል። (በሮሜ 1:24-28 ልባቸውን ያደነደኑና በእግዚአብሔር የተፈረደባቸው ሰዎች ለምሳሌ ታገኛለህና ተመልከት)።

---

31ኛ ጥያቄ፥ በዚህ ሁኔታ ልባቸው የደነደነባቸውን ሰዎች አስተውለህ ታውቃለህን? ምሳሌ ስጥ።

---

ሐ. መቅሠፍቶቹ ለፈርዖን፥ ለግብፃውያንና ለእስራኤላውያን የእግዚአብሔር ኃይል ምልክቶች ነበሩ።

መ. እግዚአብሔር በግብፃውያን ላይ ፍርድን ለማምጣት ተፈጥሮአዊ መቅሰፍቶችን ተጠቀመ። እግዚአብሔር ተፈጥሮአዊ የሆኑ የአካባቢያችን ነገሮች ሁሉ ተቆጣጣሪ ነው:- እንደ እንቁራሪት፥ ውኃ፥ ድርቅ፥ በሽታ ወዘተ.።

ሠ. መቅሠፍቶቹ በሙሉ ፈታቸውን ያዞሩት በፈርዖን ላይ ብቻ ሳይሆን፥ በግብፅ አማልክትም ላይ ነበር። ግብፃውያን የዓባይን ወንዝ፥ ከብቶችን፥ ወዘተ ያመልኩ ነበር። ግብፃውያን የተደገፉባቸውና ያለማቋረጥ ያመለኩአቸው የነበሩ አማልክት የማይጠቅሙና ዋጋ የሌላቸው ነበሩ። ፈርዖንም እንደ አምላክ የሚታይበት ሁኔታ ነበር። ሆኖም ልጁ በተገደለበት ጊዜ ኃይል የሌለው መሪ መሆኑ ታወቀ። እግዚአብሔር ከግብፅ አማልክት ሁሉ በላይ ኃያል ስለሆነ፥ እስራኤላውያን የግብፅን አማልክት ለማምለክ መፈተን እንደሌለባቸው ሊያስተምራቸው ፈለገ።

## የሚከተለውን ሠንጠረዥ ተመልከት።

| የመቅሠፍቱ ዓይነት | በመቅሠፍቱ የተመታው የግብፃውያን አምላክ | ታሪኩ የሚገኝበት ክፍል |
|---|---|---|
| 1. የውኃ ወደ ደም መለወጥ | የዓባይ ወንዝ አምላክ አሲረስ ተሸነፈ | ዘጸ. 7:14-25 |
| 2. ምድሪቱ በጓጉንቸር ተመታች | የጓጉንቸሮች አምላክ ሄኪ ተሸነፈ | ዘጸ. 8:1-15 |
| 3. የምድሩ ትቢያ ወደ ቅማል ተለወጠ | ይህም ግብፃውያን ማምለክ እንዳይችሉ በሃይማኖታዊ ሥርዓት ያልነጹ አደረጋቸው | ዘጸ. 16-19 |
| 4. ምድሪቱ በዝንብ ተወረረች | ዝንቦች ወይም ጢንዚዛዎች ራአ ተብሎ፥ የሚጠራ የፀሐይ አምላክ ምልክቶች ነበሩ | ዘጸ. 8:20-32 |
| 5. ከብቶች በሙሉ በሕመም ተመተው ሞቱ | አፕሲስ የተባለው የኮርማ አምላክ ተመታ | ዘጸ. 9:1-7። |
| 6. ሰውና እንስሳ በቁስል ተመታ | የግብፅ አማልክት የሚያመልኩአቸውን ሰዎች መጠበቅ አልቻሉም፥ | ዘጸ. 9:8-12። |
| 7. ከሰማይ በረዶና እሳት ወረደ | የግብፃውያን የአየር አምላክ ተመታ | ዘጸ. 9:13-35። |
| 8. አንበጦች ሰብሉን በሙሉ አጠፉ | በዚህ እስክሮፕሲስ የሚባለውን ሰብል የሚጠብቀው አምላክ ተመታ | ዘጸ. 10:1-20። |
| 9. ምድሪቱ በጭለማ ተዋጠች | በዚህም ራአ የተባለው የፀሐይ አምላክ ኢሲስ የተባለችው የጨረቃ አምላክ ተመቱ | ዘጸ. 10:21-27 |
| 10. የወንድ በኩር መሞት | በዚህም የፈርዖን የበኩር ልጅ አምላክ ነው የሚለው አሳብ ተሸነፈ | ዘጸ. 12:29-32። |

32ኛ ጥያቄ፥ እግዚአብሔር በመቅሠፍቶች አማካይነት ካሳየው ኃይል የምናገኛቸውን መንፈሳዊ ትምህርቶች ዘርዝር።

** በራእይ 6-17፥ በመጨረሻው ዘመን በሰው ልጆች ላይ የሚመጡ ፍርዶች በግብፅ ላይ ከወረዱት መቅሠፍቶች ጋር ተመሳሳይ መሆናቸው የሚያስገርም ነው።

4. የፋሲካ በዓል አከባበር (ዘጸ. 12)።

ለሚቀጥሉት ሁለት ሳምንታት በሚኖረን ትምህርት ውስጥ፥ እግዚአብሔር ለአይሁድ በዓመቱ ውስጥ እንዲጠብቋቸው የሚገባቸውን ለአይሁድ የሰጣቸውን ሰባት ልዩ የሃይማኖት በዓላት አከባበር እንመለከታለን። ዛሬ ግን የመጀመሪያ በዓል ስለሆነው ስለ ፋሲካ በዓል አከባበር የመግቢያ አሳብ እንመለከታለን። የፋሲካ በዓል በእርግጥ ሁለት በዓላትን ያካተተ ነበር። ከፋሲካ በዓል ቀጥሎ የቂጣ በዓል ይከበራል።

የመጀመሪያው በዓል፥ ፋሲካ ስያሜውን ያገኘው የእግዚአብሔር መልአክ የግብፃውያንን ቤት በኩራት በሙሉ ሲገድል፥ በመዝጊያ መቃኖቻቸው ላይ ደም ያደረጉትን የእስራኤልን ቤት «ከማለፍ» አንፃር ነው። ይህ የአንድ ቀን በዓል ነበር። በመጀመሪያው የማለፉ (የፋሲካ) በዓል፥ እያንዳንዱ ቤተሰብ ምንም ጉድለት የሌለበትን አንዳንድ ጠቦት ያርድ ነበር። ከዚያም የጠቦቱ ደም መቃንና ጎበን ላይ ይቀባ ነበር። የቀረው የጠቦቱ ሥጋ ደግሞ ተጠብሶ ማታ ይበላ ነበር።

ከእስራኤላውያን እጅግ የታወቁ በዓላት አንዱ ይህ የፋሲካ በዓል ነበር። ይህም ኢየሱስ በመስቀል ላይ የሠራው ሥራ ምልክት ነበር። ኢየሱስ በመስቀል ላይ ስለሞተ፥ የእግዚአብሔር ፍርድ እኛን አለፈ። ክርስቶስ የፋሲካ በግ የተባለበት ምክንያት ይህ ነው (1ኛ ቆሮ. 5፡7፤ ዮሐ. 1፡29 ተመልከት)። ብዙ ክርስቲያኖች አይሁድ ደሙን በበሩ መቃንና ጎበን ላይ ማድረጋቸው የመስቀሉ ምልክት ነው ብለው ያምናሉ። እኛ በመታሰቢያነት የምናከብረው የጌታ እራት የተመሠረተው በፋሲካ በዓል ላይ ነው።

ከፋሲካ በዓል ቀጥሎ የቂጣ በዓል ይከበራል። አንድ ሳምንት የሚፈጅ በዓል ነው። አይሁድ እግዚአብሔርን ለማምለክ ራሳቸውን ያዘጋጁ ነበር። በመጀመሪያ በቤታቸው ያለውን ማንኛውንም እርሾ ያስወግዳሉ። እርሾ

ያለበት ማንኛውም ነገር ወደ ውጭ ይጣላል። እርሾ የክፋት ምልክት ስለሆነ፥ ይህንን ሲያደርጉ በመንፈሳዊ ነገር ራሳቸውን ከክፋት ሁሉ ማንጻታቸው ነው። ቀጥሎ እርሾ የሌለበትን ቂጣ ይጋግራሉ። ይህም እግዚአብሔር ከግብፃውያን እንዴት ነፃ እንዳወጣቸውና እንዴት ግብፅን በጥድፊያ ትተው መውጣት እንደነበረባቸው ለትውልዶች ሁሉ ማስታወሻ ነበር፤ (ዘጸ. 12፡11 ተመልከት)።

እርሾ የሌለበት የቂጣ በዓል እኛም ደግሞ ያለማቋረጥ ከኃጢአት ራሳችንን በማንጻት ለእግዚአብሔር የተቀደስን ሆነን እግዚአብሔር በእኛ ውስጥና በእኛ በኩል እንዲሠራ መዘጋጀት እንዳለብን የሚያሳይ ምልክት ነው።

| |
|---|
| 33ኛ ጥያቄ፡- አሁን ልብህን ለመመርመር ጊዜ ይኑርህ። የኃጢአትን እርሾ ከሕይወትህ አስወግደሃልን? ካላስወገድክ ኃጢአትህን ለእግዚአብሔር ተናዘዝ። የፋሲካው በግ ደምም ከኃጢአት ያነጻሃል፥ (1ኛ ዮሐ. 1፡9 ተመልከት)። |

ፈርዖን የበኩር ልጁ ከሞተ በኋላ እስራኤላዊያን እንዲሄዱ ፈቀደ። ግብፃውያን በጣም ተጨንቀው ስለነበር አይሁዳውያን ይሄዱላቸው ዘንድ ወርቃቸውን፥ ብራቸውንና ሌሎች ውድ ነገሮቻቸውን ሁሉ ሰጡአቸው። በዚህም አይሁድ ምንም ኃይል ሳይጠቀሙ ግብፃውያንን በዘበዙአቸው። (ይህም በዘፍ. 15፡14 ለተጻፈው ትንቢት መፈጸም ምክንያት ሆነ።) ይህንን ጥቅስ አንብብ።

5ኛ ቀን፡- የዚህን ሳምንት ትምህርት ከልስና ለሳምንታዊ ስብሰባ ዝግጅት ይረዳህ ዘንድ የውይይት ጥያቄዎችን ተመልከት።

## ሳምንታዊ ስብሰባ

1. ሳምንታዊ የአምልኮ ጊዜ

2. ጸሎት

3. የትምህርቱ ክለሳ

4. ውይይት

ሀ. 1) ነፃ የመውጣት ታሪክ ለአይሁድ በጣም ጠቃሚ የሆነው ለምንድን ነው? 2) ይህ ታሪክ ለደኅንነታችን ጥሩ መግለጫ

የሆነው እንዴት ነው? 3) እግዚአብሔር እንዴት እንዳዳናችሁ እርስ በርሳችሁ ተነጋገሩ። 4) «መዋጀት» የሚለው ቃል ለእስራኤላውያን የሠራው እንዴት ነው? 5) ይህ ቃል ለአንተስ የሚሠራው እንዴት ነው?

ለ. የሙሴን ሕይወት ከልስ። 1) እግዚአብሔር ሙሴን የመረጠው ለምንድን ነው? 2) ሙሴ ለአርባ ዓመታት በጎችን በሚጠብቅበት ጊዜ እግዚአብሔር ኃይል ሊያስታጥቀው ያስፈለገው ለምን ነበር? 3) በሙሴ ሥልጠና ውስጥ ለቤተ ክርስቲያን መሪዎች ጥሩ ምሳሌ የሚሆኑ ሌሎች ነገሮች ምንድን ናቸው? 4) ቤተ ክርስቲያን መሪዎችዋ የበለጠ ሙሴን እንዲመስሉ ምን ማድረግ ትችላለች?

ሐ. 1) እግዚአብሔር ከአሥርቱ ትእዛዛት መካከል የመጀመሪያውንና ሁለተኛውን ትእዛዛት የሰጠው ለምንድነው? 2) እነዚህ ለእስራኤላውያን ለመታዘዝ አስቸጋሪ የሆኑት ለምንድን ነው? 3) ዛሬ ክርስቲያኖች እነዚህን ትእዛዛት የማይጠብቁባቸውን መንገዶች ግለጽ። 4) ዛሬ የኢየሱስ፥ የቅዱሳንና የመላእክት ሥዕሎች በክርስቲያኖች ዘንድ ያላቸው ስፍራ ምን እንደሆነ ተወያዩበት።

መ. 1) የኦሪት ዘጸአት ዓላማ ምንድን ነው? 2) በኦሪት ዘጸአት ውስጥ ስለ እግዚአብሔር፥ ስለ እግዚአብሔር ሕዝብ፥ ስለ አመራር፥ ወዘተ. የምናገኘው ትምህርት ምንድን ነው? 3) ዛሬስ ኦሪት ዘጸአትን ማጥናት ለእኛ አስፈላጊነቱ ምንድን ነው?

ሠ. 1) የእግዚአብሔር ሕዝብ መሪ ይሆን ዘንድ ሙሴን ለማዘጋጀት እግዚአብሔር ያደረገው ምንድን ነው? 2) በዚህ ዘመን የቤተ ክርስቲያን መሪዎችን የምናዘጋጅበት መንገድ እግዚአብሔር ሙሴን ካዘጋጀበት መንገድ ጋር የሚነፃፀረው እንዴት ነው? ተመሳሳይነታቸው እንዴት ነው? ልዩነታቸውስ? 3) ከሙሴ የመጀመሪያ ሕይወት እርሱን ከሚፈራ መሪ እግዚአብሔር ስለሚፈልገው ነገር ምን ልንማር እንችላለን?

ረ. 1) እግዚአብሔር በፈርዖንና በግብፅ አማልክት ላይ ኃይሉን የገለጠው እንዴት ነው? 2) በቅርብ ዓመታት ውስጥ በተፈጸመው ታሪክ እግዚአብሔር በኢትዮጵያ ኃይሉን የገለጠው እንዴት ነው?

3) ስለማናውቀው የወደፊት ሁኔታ ሊኖረን ስለሚገባው ምላሽ ምን ማድረግ እንዳለብን ይህ ምን ያስተምረናል? 4) በጠላቶቹ ሁሉ ላይ ስላለው ታላቅነት እግዚአብሔርን በመዝሙር የምታመሰግኑበትን የአንድነት ጊዜ አሁኑኑ ወስኑ።

5. ጸሎት።

# ትምህርት ሰባት

## 1ኛ ቀን፡- ዘጸአት 13-18

አንድ ሰው የመንፈሳዊ ሕይወት ጉዞውን በመልካም ሁኔታ ጀመረ ማለት ያለማቋረጥ በእምነት ይጓዛል ማለት አይደለም። እግዚአብሔር አይሁዳውያንን ከግብፅ ባርነት በታላቅ ኃይል አወጣቸው። አይሁድ በታላቅ ደስታ ከምርኮኛነት ተላቀቁ። ነገር ግን ብዙም ሳይቆዩ መጠራጠር፥ ማጉረምረም ማማረር ጀመሩ። ከዚህም አልፈው ወደ ግብፅ ለመመለስ ከጀሉ። መንፈሳዊ አረማመዳቸው ልክ እንደ እኛው የድልና የሽንፈት ጊዜያትን ያካተተ ነበር። የእስራኤል ሕዝብ በምድረ በዳ ያሳለፉት ሕይወት በመንፈሳዊ ሕይወታችን ተጠንቅቀን እንድንኖር ለሁላችንም ማስጠንቀቂያ ሊሆን ይገባል። ተግባራችን እንደ እነርሱ እንዳይሆንና በአለማመን እንዳንወድቅ፥ ከስሕተታቸው መማር አለብን።

| |
|---|
| 1ኛ ጥያቄ፥ 1ኛ ቆሮ. 10፡1-13 አንብብ። ከእስራኤላውያን የምድረ በዳ ኑሮ መማር እንዳለብን ጳውሎስ የሚናገረው ምንድን ነው?<br>2ኛ ጥያቄ፥ ዘጸ. 13-18 አንብብ። ሀ) እስራኤላውያን ወደ ሲና ተራራ በሚጓዙበት ጊዜ የሠፈሩባቸውን ቦታዎች ሁሉ ዘርዝር። ለ) በእያንዳንዱ ስፍራ ስለተፈጸመው ነገር አጫጭር ገለጻ አድርግ። ሐ) ከዚህኛው የእስራኤላውያን ጉዞ የምትማራቸው መንፈሳዊ ትምህርቶች ዘርዝር። መ) የአንተና የቤተ ክርስቲያንህ ሕይወት ከእስራኤላውያን ጉዞ ጋር የሚመሳሰልበትን ነገር ዘርዝር። |

እስራኤላውያን ከግብፅ ወደ ሲና ተራራ ያደረጉት ጉዞ ሦስት ወር ገደማ ፈጀባቸው። እግዚአብሔር እስራኤላውያንን እንዲህ በሚያስደንቅ ድማሬ ከግብፅ ባርነት ካወጣቸው በኋላ፥ ፍጹም በሆነ እምነትና መታዘዝ ይጓዛሉ ብለን መጠበቃችን አይቀርም። በእስራኤላውያን ሕይወት የተፈጸመው ግን ይህ አልነበረም። ከግብፅ ወደ ሲና ያደረጉት ጉዞ በጣም አስቸጋሪ ነበር። በአስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ በእግዚአብሔር ከመታመን ይልቅ እርሱን ወደማማረርና በእርሱም ላይ ወደ ማጉረምረም አዘነበሉ።

3ኛ ጥያቄ፥ እኛ ክርስቲያኖችም ችግር በሚያጋጥመን ጊዜ የምናጉረመርመውና የምናማርረው እንዴት ነው? ለምን?

እስራኤላውያን ወደ ሲና ተራራ በሚጓዙበት ጊዜ ያለፉባቸው ቦታዎች ከዚህ እንደሚከተለው ተተንትነዋል። እስራኤላውያን የሄዱበትን መንገድ ለማወቅ ከመጽሐፉ በስተጀርባ ያለውን ካርታ ተመልከት።

1. አብዛኛዎቹ እስራኤላውያን በግብፅ በነበሩበት ጊዜ ከኖሩበት ከራምሴ ተነሥተው ግብፅን ለመልቀቅ ወደ ተዘጋጁበት ወደ ሱኮት ሄዱ (ዘጸ. 12፡37-13፡19)። በዚህ ስፍራ ሁለት ዋና ዋና ድርጊቶችን ፈጸሙ። በመጀመሪያ፥ በቂጣ በዓል ምን መደረግ እንዳለበት የወሰኑት በሱኮት ነበር። በሁለተኛ ደረጃ፥ የእስራኤልን በኩር ሁሉ ለእግዚአብሔር የመቀደስ ተግባር የተከናወነው በሱኮት ነበር (ዘጸ. 13፡1-16)።

በኩራትን የመቀደስ ተግባር እስራኤላውያን ለእግዚአብሔር አሥራትን ከሰጡባቸው መንገዶች አንዱ ነበር። እግዚአብሔር በዚህ ስፍራ ያስጀመረው መመሪያ በአይሁድ ዘንድ ከሰውም ሆነ ከእንስሳ ለእግዚአብሔር አሳልፎ የመስጠት ተግባር ነው። የእግዚአብሔር ሕዝብ ከምርታቸው ወይም ከእንስሶቻቸው መካከል ለእግዚአብሔር መስጠት ያለባቸው የመጀመሪያውን እንጂ የመጨረሻውን አልነበረም።

ስለ በኩር በተሰጠው ትምህርት ውስጥ የተካተቱት ሁለት ዋና ዋና ጉዳዮች አሉ። በቅድሚያ በኩር ስለሆኑት ሰዎች የተሰጠ ትምህርት እናገኛለን። 1) የእስራኤል ሕዝብ በሙሉ አንድ ሕዝብ እንደ መሆኑ መጠን በኩር ነበር። ይህም የሚያንፀባርቀው እግዚአብሔር ያዕቆብን ወይም እስራኤልን የተስፋው ልጅ የኪዳን ወራሽ አድርጎ በመምረጥ የበኩሩን ልጅ መብት እንደሰጠው ነው፤ ስለዚህ የያዕቆብ ልጆች የሆኑ እስራኤላውያን ሙሉ እንደ እግዚአብሔር ልዩ ልጅ ተቆጥረው የእርሱ በኩር ሆኑ (ዘጸ. 4፡22)።

2) ነገር ግን የበኩር ትምህርት የእስራኤላውያን የመጀመሪያ ልጆች የሆኑትንም ሁሉ የሚመለከት ነው። እያንዳንዱ በኩር ልጅ የእግዚአብሔር ነበረ። ምክንያቱም እግዚአብሔር የግብፃውያንን በኩር በመቅሠፍት ባጠፋ ጊዜ የእስራኤላውያንን በኩር ትቶ ነበር (ዘጸ. 12፡12-13)፤ ስለዚህ የበኩሩ ልጅ ወላጆች ገንዘብ ከፍለው ልጁን እንዲያስመልሱ ወይም «እንዲዋጁ» እግዚአብሔር ይፈልግ ነበር። ገንዘብ መክፈል ነበረባቸው (ዘኁል. 18፡15-16)።

3) በእስራኤላውያን በኩሮች ምትክ መላው የሌዊ ነገድ ለእግዚአብሔር ተሰጥቶ ነበር፤ (ዘኁል. 3፡41-51)።

ሁለተኛ፥ የእንስሳትን በኩር እናገኛለን። እንስሳትን በሚመለከት ሁለት ዓይነት ሕግጋት ነበሩ።

1) «ንጹሕ» እንስሳት የሚባሉና ለመሥዋዕትነት የተፈቀዱ እንስሳት ነበሩ። የተባዕት እንስሳ በኩር የእግዚአብሔር ስለሆነ መሥዋዕት ሆኖ በመሠዊያ ላይ ይቀርብና ይሠዋ ነበር። ሥጋውም ለካህናት ይሰጥ ነበር (ዘኁል. 18፡14-19)። 2) ለመሥዋዕት ይቀርቡ ዘንድ ያልተፈቀዱ «ንጹሐን ያልሆኑ» እንስሳትም ነበሩ። ንጹሕ ባልሆነው እንስሳ ምትክ እስራኤላውያን ጠቦት መስጠት ነበረባቸው። ጠቦቱንም በመሠዊያ ላይ አቅርቦ በመሠዋት ለእግዚአብሔር መስጠት ተገቢ ነበር።

| |
|---|
| 4ኛ ጥያቄ፥ ሀ) ለእግዚአብሔር አሥራት በምንሰጥበት ጊዜ የሁሉን ነገር በኩር ለእግዚአብሔር መስጠት መልካም መመሪያ የሆነው ለምንድን ነው? ለ) በአሁኑ ጊዜ ብዙ ክርስቲያኖች ለእግዚአብሔር ከመቶ ከአሥር እጅ (10%) በታች የሚሰጡት ለምንድን ነው? ሐ) ብዙ ክርስቲያኖች ከገንዘባቸውም ሆነ ከምርታቸው የተረፈውን ለእግዚአብሔር የሚሰጡት ለምንድ ነው? መ) ይህ መመሪያ ዛሬ አሥራትን ስለመክፈል የሚያስተምረን ነገር ምን ይመስልሃል? 5ኛ ጥያቄ፥ ሉቃ. 2፡7፤ ሮሜ 8፡29፤ ቆላ. 1፡15፥ 18 አንብብ። ሀ) በዚህ ስፍራ ለክርስቶስ የተሰጠው ማዕረግ ምንድን ነው? ለ) ይህ ማለት ምን ማለት ነው? |

2. ሕዝቡ ከሱኮት ወደ ኤታም አመሩ (ዘጸ. 13፡20-22)። ከሱኮት ወደ ተስፋይቱ ምድር የሚወስዱ ሁለት የተለያዩ መንገዶች ነበሩ። አንደኛው በሜዲትራኒያን ባሕር አጠገብ በፍልስጥኤማውያን ምድር ወደ ሰሜን የሚወስደው ሲሆን፥ የተለመደ የንግድ መስመር ነበር። ይህ መንገድ አጭር ስለሆነ፥ እስራኤላውያን በጥቂት ሳምንታት ውስጥ ከነዓን ይደርሱ ነበር፤ ነገር ግን እግዚአብሔር እስራኤላውያንን በዚህ መንገድ አልመራቸውም። ረጅምና አስቸጋሪ በሆነው ወደ ሲና በረሀ በሚወስደው መንገድ መራቸው። እግዚአብሔር ይህን ያደረገው ለምን እንደሆነ አናውቅም። ምናልባት በምድረ በዳው ልምምድና በሲና ተራራ ላይ ባሳለፉት ጊዜ የተመረጡ የእግዚአብሔር ሕዝብ

እንደመሆናቸው መጠን እንዴት መኖር እንዳለባቸው ሊያስተምራቸው የፈለገ ይመስላል። የጉዞው አስቸጋሪነት በእግዚአብሔር ላይ እንዲታመኑ ለማስተማር የታቀደ ነበረ።

| |
|---|
| 6ኛ ጥያቄ፥ በእርሱ ላይ ያለህን እምነት ለማነፅ እግዚአብሔር በሕይወትህ የሚከሰቱ አስቸጋሪ ሁኔታዎችን እንዴት ይጠቀምባቸዋል? |

በኤታም በጣም አስፈላጊ የሆነ አንድ ነገር ተፈጸመ። እግዚአብሔር ቀን በደመና ዓምድ ሌሊት ደግሞ በእሳት ዓምድ በመምራት ከእነርሱ ጋር መኖሩን አሳያቸው። በሚቀጥሉት 40 ዓመታት እግዚአብሔር እስራኤላውያንን በምድረ በዳ የመራቸው የእርሱን መኖር በሚገልጹት በእነዚህ ሁለት ምልክቶች ነበር። በኋላም የእግዚአብሔር ክብር ደመና የማደሪያውን ድንኳንና ቤተ መቅደሱን ሞልቶት ነበር። አይሁድ ይህን የእግዚአብሔር መኖር ደመና «የሽካይናህ ክብር» ብለው ይጠሩታል።

3. ከኤታም ተነሥተው ወደ ፊሀሒሮት በመምጣት ቀይ ባሕርን ተሻገሩ (ዘጸ. 14፡1-15፡21)። ፊሀሒሮት የት እንደሆነ እርግጠኞች ባንሆንም፥ በትልቅ የውኃ አካል ጠርዝ ላይ ያለ ስፍራ ነበር። እግዚአብሔር ውኃውን በከፈለላቸው ጊዜ እስራኤላውያን በትክክል የተሻገሩት የትኛውን የውኃ አካል እንደሆነ በማሰብ ምሁራን ብዙ ጊዜ መደነቅ ይዞአቸዋል። ያቋረጡት ባሕር መጠሪያ ስሙ «የሸምበቆ ባሕር» የሚል እንጂ ቀይ ባሕር አልነበረም። ያቋረጡት ያሁኑን ቀይ ባሕር ነው ማለት ትክክል አይመስልም። ብዙ ምሁራን እንደሚሉት እግዚአብሔር በተአምር ለሁለት ክፍሎች ያቋረጡት ውኃ በቀይ ባሕርና በሜዲትራኒያን ባሕር መካከል የነበረ አንድ ትልቅ ውኃማ አካል ነው።

እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን የመጀመሪያውን ፈተና በዚህ ስፍራ ሰጣቸው። ከፊት ለፊታቸው ታላቅ ውኃ፥ ከኋላቸው ደግሞ የፈርዖን ሠራዊት ነበር። ከጥቂት ቀናት በፊት 10 መቅሠፍቶችን በግብፅ ላይ በማውረድ ከፈርዖን ብርቱ እጅ ባዳናቸው እግዚአብሔር ላይ ታምነው ይሆን? የለም፤ በእግዚአብሔር አላመኑም ነበር፤ ነገር ግን እግዚአብሔር በምሕረቱ ውኃውን ለሁለት ከፈለው። እስራኤላውያን በደረቅ ምድር ሲሻገሩ፥ የግብፅ ሠራዊት ግን በውኃው ውስጥ ሰጥሞ ቀረ።

7ኛ ጥያቄ፥ በእግዚአብሔር ጠላቶችም ሆነ በሌሎች ችግሮች ልንሸነፍ የተቃረብን በሚመስለን ጊዜ እግዚአብሔርን ባለማመን ሊኖረን ስለሚችል ዝንባሌ ይህ ምን ያስተምረናል?

4. ከሸምበቆ ባሕር ወደ ማራ (ዘጸ. 15፡22-26)፡- በማራ እግዚአብሔር እስራኤላውያንን በሌላ ነገር ፈተናቸው። ይህም ፈተና የሚጠጡትን ውኃ እንደሚሰጣቸው በእግዚአብሔር ይታመኑ እንደሆነ ለመለየት የተደረገ ነበር። የነበረው ውኃ መራራ ስለ ነበር ሰው ሊጠጣው አይችልም ነበር፤ ስለዚህ ከግብፅ ባወጣቸው አምላክ ላይ በመደገፍ ወደ እርሱ በመጸለይ ፈንታ፥ በሙሴ ላይ ያጉረመርሙ ጀመር። ሙሴ በእግዚአብሔር የተመረጠ መሪ ስለነበር፥ ያጉረመረሙት በእግዚአብሔርም በሙሴም ላይ ነበር።

8ኛ ጥያቄ፥ ሀ) ይህ በቤተ ክርስቲያን መሪዎች ወይም በክልል ቤተ ክርስቲያን መሪዎች ላይ በምናጉረመርምበት ጊዜ ምን እያደረግን እንደሆነ ምን ያስተምረናል? ለ) በዚህ ረገድ ከእስራኤላውያን ጋር የምንመሳሰለው እንዴት ነው?

እግዚአብሔር በእኛ ላይ በኃላፊነትና በሥልጣን ባስቀመጣቸው ሰዎች ላይ በምናጉረመርምበት ጊዜ የሚሆነው ነገር ተመሳሳይ ነው። ያጉረመረምነው በእነርሱ ላይ ብቻ እንደሆነ ሊመስለን ይችላል፤ ዳሩ ግን የሚመሩት በእግዚአብሔር ተመርጠው ስለሆነ፥ የምናጉረመርመው በእግዚአብሔርም ላይ ጭምር ነው። እግዚአብሔር በጸጋው እንደገና ሙሴን በመጠቀም በተአምር ንጹሕ ውኃን ሰጣቸው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሕዝቡ በማራ ያሳለፉት ይህ ጊዜ በእግዚአብሔር ላይ የማጉረምረማቸው ምሳሌ ተደርጎ ይታያል (መዝ. 95፡7-11፤ ዕብ. 3፡7-19)።

5. ከማራ ወደ ኤሊም፥ ከዚያም ወደ ሲን ምድረበዳ መጡ (ዘጸ. 15፡27-16፡36)። ኤሊም ብዙ ውኃ ያለበት ስፍራ ነበር። ከዚያም የሲን በረሀ ተብሎ ወደሚጠራው ምድረ በዳ ሄዱ። አሁን እስራኤላውያን ግብፅን ከለቀቁ ልክ አንድ ወር ስለሆናቸው፥ በጉዞው መሰላቸት ጀምረው ነበር። የሚበሉትን ምግብ አጡ። ስለዚህ እንደገና በሙሴና በአሮን ላይ አጉረመረሙ። ምቹ ነው ብለው ወደጠሩት ወደ ግብፅ ኑሮ መመለስም ተመኙ። ነፃ ሆኖ ከመራብ፥ ባሪያ ሆኖ መጥገብ

ይሻለናል የሚሉ ይመስላሉ። አሁንም እግዚአብሔር እንደገና በምሕረቱ የሚያስፈልጋቸውን ነገር ሰጣቸው። «የሰማይ እንጀራ»፥ «መናን» ሰጣቸው (ዘጸ. 16፡4)። የድርጭትንም ሥጋ ላከላቸው። «መና» ማለት በዕብራይስጥ «ይህ ምንድን ነው?» ማለት ነው። እንዲህ የተባለበት ምክንያት እግዚአብሔር በመጀመሪያ ለእስራኤላውያን እንደሰጣቸው ምንነቱን ስላላወቁ ነበር። እግዚአብሔር የፈቀደላቸው ለየዕለቱ የሚሆነውን መና እንዲሰበስቡ ብቻ ነበር። እስራኤላውያን ለዕለት እንጀራቸው በእርሱ እንዲታመኑ ማድረጉ ነበር (ማቴ. 6፡11)። እግዚአብሔር እስራኤላውያንን አንድ ማድጋ ጎሞር ሙሉ መና ወስደው በመገናኛው ድንኳን ውስጥ ባለው ታቦት ሥር እንዲያስቀምጡ አዘዛቸው።

| |
|---|
| 9ኛ ጥያቄ፥ ዮሐ. 6፡32-51 አንብብ። ሀ) እነዚህ ጥቅሶች እውነተኛ «የሕይወት እንጀራ» የሚሉት ማንን ነው? ለ) ይህስ ለአንተ እውነትነቱ እንዴት ነው? |

6. ከሲን ምድረ በዳ ወደ ራፍቃ፥ ከራፍቃ ወደ ኤሉስ፥ ከኤሉስም ተጉዘው በራፈዲም ሠፈሩ (ዘኁል. 33፡12-13፤ ዘጸ. 17-18) እስራኤላውያን ወደ ሲና ተራራ የሚወስደውን የደቡብ ጉዞአችውን ቀጠሉ። ወደ ራፊዲም በደረሱ ጊዜም ሦስት ዋና ዋና ነገሮች ተፈጸሙ።

1. ውኃ ስላልነበራቸው እንደገና በሙሴ ላይ አጉረመረሙ። ዓለቱን በበትሩ እንዲመታ እግዚአብሔር ሙሴን አዘዘው። በመታውም ጊዜ ከዓለቱ ውኃ ወጣ። በመጽሐፍ ቅዱስ ይህ ድርጊት የእግዚአብሔር ሕዝብ እግዚአብሔርን የተፈታተኑበት ምሳሌ ሆኖ ቀርቧል። እግዚአብሔር እንደሚሰጣቸው በማመን እርሱን ከመጠበቅ ይልቅ «እግዚአብሔር በመካከላችን ነውን ወይስ አይደለም?» በማለት ፈተኑት (ዘጸ. 17፡7)። እግዚአብሔር በራሱ ጊዜ ፍላጎታቸውን እንደሚያሟላላቸው ከመተማመን ይልቅ፥ በራሳቸው ጊዜ እግዚአብሔር እንዲያደርግላቸው ግፊት አደረጉ።

| |
|---|
| 10ኛ ጥያቄ፥ ሀ) ዛሬም እግዚአብሔርን በተመሳሳይ መንገድ እንዴት ልንፈታተነው እንችላለን? ለ) ይህም በእግዚአብሔር ላይ እምነት ማጣት መሆኑን የሚያሳየን ለምንድን ነው? |

2. እስራኤላውያን ከአማሌቃውያን ጋር ተዋግተው አሸነፏቸው። እግዚአብሔር በሙሴ የተዘረጉ እጆች ላይ ድል እንዲመሠርት ማድረጉ የሚያስደንቅ ነው። የሙሴ እጆች ወደ እግዚአብሔር ጸሎት በተዘረጉ ጊዜ እስራኤላውያን ያሸንፉ ነበር። እጆቹን ባወረደ ጊዜ ግን አማሌቃውያን ያሸንፉ ነበር።

11ኛ ጥያቄ፥ ይህ ለጸሎት አስፈላጊነት እንዴት ጥሩ መግለጫ ይሆናል?

3. ዮቶር፥ የሙሴ አማት የእግዚአብሔርን ሕዝብ በመምራት ሥራ ውስጥ ይረዱት ዘንድ ሽማግሌዎችን ወይም የተለያየ ደረጃ ያላቸውን ሰዎች እንዲሾም ሙሴን መከረው። ሙሴ ሁሉንም ሰው ለመምራት ከሞከረበት ጊዜ ይልቅ፥ ይህን እንዳደረገ የእስራኤል ሕዝብ የበለጠ ስኬታማ በሆነ መንገድ ለመተዳደር ችሏል።

12ኛ ጥያቄ፥ ሀ) ይህ አሠራር ዛሬ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሊኖር ስለሚገባው አመራር ጥሩ ምሳሌ የሚሆነው እንዴት ነው? ለ) ይህ አሠራር ቤተ ክርስቲያንህ እንዴት እንደሚደረግ ወይም እንደማይደረግ ምሳሌዎችን ስጥ።

7. ከራፊዲም ወደ ሲና ተራራ (ዘጸ. 19)፡- እስራኤላውያን ከግብፅ ከወጡ ከሦስት ወራት በኋላ ወደ ሲና ተራራ ደረሱ። በዚያ ስፍራም እግዚአብሔር ለእርሱ የተቀደሱ ሕዝብ ይሆኑ ዘንድ እያዘጋጃቸው ለአንድ ዓመት ቆዩ። የቀሩት የአሪት ዘጸአት፥ ዘሌዋውያንና ዘኁልቁ ምዕራፍ1-10 ታሪክ የተፈጸመው በብሉይ ኪዳን የኮሬብ ተራራ በተባለው በዚህ በሲና ተራራ ላይ ነው (ዘጸ. 33፡6)።

13ኛ ጥያቄ፥ የእስራኤል ሕዝብ ወደ ሲና ተራራ ካደረገው ጉዞ ስለ ራሳችን የእምነት ጉዞ የምንማራቸው ጠቃሚ ትምህርቶች ምንድን ናቸው?

## 2ኛ ቀን፡- ዘጸአት 19-24

ምናልባት ከእስራኤል ሕዝብ ታሪክ ከሁሉም ላቅ ያለ ስፍራ ሊሰጠው የሚገባው ሕዝቡ በሲና ተራራ የቆዩበት የአንድ ዓመት ጊዜ ነው። እግዚአብሔር ራሱን በታላቅ ክብር ለሕዝቡ የገለጠው በዚያ ነበር። እግዚአብሔር ከእነርሱ ጋር ግንኙነት የሚያደርግበትን የሥነ-ምግባርና የመንፈሳዊ ሕይወት መሠረት የሰጣቸው በዚያ ነበር። በእግዚአብሔር

ሕዝብና በዓለም ሕዝብ መካከል የሚገኙ ዋና ዋና ልዩነቶች የተገለጡት በዚያ ነበር። ክርስቲያኖች ለሆንን ሁሉ ከእነዚህ መመሪያዎች አብዛኛዎቹ ዛሬም የሚሠሩ ናቸው። እኛም ለእግዚአብሔር የተለየን ሕዝብ መሆን አለብን። በዙሪያችን ካሉ ሕዝቦች ሁሉ የተለየ ኑሮ መኖር አለብን።

14ኛ ጥያቄ፥ ዘጸአት 19፡3-6 አንብብ። ሀ) ስለ እስራኤል ሕዝብና ስለ ዓላማቸው በእነዚህ ጥቅሶች የተጠቀሱ የተለያዩ ነገሮችን ዘርዝር። ለ) እግዚአብሔር ከእነርሱ ጋር ስለነበረው ግንኙነት ምን ልንማር እንችላለን? ሐ) ለእግዚአብሔር ሊኖራቸው የሚገባው ምላሽ ምን መሆን ነበረበት? መ) እግዚአብሔር እስራኤላውያንን በሚመለከት የተናገረውን ነገር በአዲስ ኪዳን ስለ ቤተ ክርስቲያን ከተነገረው ጋር አወዳድር። እኛ በዚህ አንፃር ከእስራኤላውያን ጋር የምንመሳሰልባቸው ወይም የምንለያይባቸው ነገሮች ምንድን ናቸው? (1ኛ ጴጥ. 2፡9 ተመልከት)።
15ኛ ጥያቄ፥ ዘጸ. 19-24 ተመልከት። ሀ) እግዚአብሔር ተፈጥሮውንና ኃይሉን ለእስራኤል ሕዝብ የገለጠባቸውን የተለያዩ መንገዶች ዘርዝር። ለ) የእግዚአብሔር ቅዱስነትና እርሱ ከሕዝቡ የሚፈልገው ቅድስና በእነዚህ ቁጥሮች የታየው እንዴት ነው? ሐ) ዓሥርቱን ትእዛዛት ዘርዝር። መ) እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን የሰጣቸው ትእዛዛት ለመሰሎቻቸው ያለባቸውን ኃላፊነት የሚያሳዩት እንዴት ነው?

እግዚአብሔር ከሕዝቡ (ከእስራኤል) ጋር በሲና ተራራ ያደረገው ግንኙነት፥ በሁሉም ዕድሜ ያሉ የእግዚአብሔር ሰዎች ከእርሱ ጋር ሊኖራቸው ስለሚገባ ግንኙነት መሠረት የተጣለበት ነው። በርካታ ሕግጋትና ሃይማኖታዊ ልምምዶች ሊለወጡ ይችላሉ። ዋናው መመሪያ ግን አሁንም ይሠራል። ዘጸአት 19-24 የሲና ተራራ ቃል ኪዳን የተመሠረተበት ነው። በእነዚህ ምዕራፎች በእርሱና በሕዝቡ (በእስራኤል) መካከል ልዩ የሆነው ግንኙነት እንዲቀጥል ከእስራኤል ሕዝብ የሚጠበቁትን የቃል ኪዳኑን ግዴታዎች እግዚአብሔር ገልጧል። በሲና ተራራ ስለተገባው ቃል ኪዳን የሚከተሉትን ነገሮች ማስታወስ አስፈላጊ ነው:-

1. በምንም ቅድመ ሁኔታ ላይ ሳይመሠረት እግዚአብሔር ከአብርሃምና ከዳዊት ጋር ከገባላቸው ሌሎች በርካታ ቃል ኪዳኖች በተቃራኒ

በሲና ተራራ የተደረገው ቃል ኪዳን በቅድመ ሁኔታዎች ላይ የተመሠረተ ነው። ማለትም ከእግዚአብሔር ዘንድ የሆነው በረከትና የእግዚአብሔር የተስፋ ቃል እንዲፈጸም እስራኤላውያን በቃል ኪዳኑ ውስጥ ለተጠቀሱት ትእዛዛት ታዛገች መሆን ነበረባቸው። እግዚአብሔር ለአብርሃምና ለዳዊት በሰጣቸው ሌሎች ቃል ኪዳኖች፥ እንዲሁም በአዲሱ ቃል ኪዳን (ኤር. 31፡31) በመታዘዝ ቅድመ ሁኔታ ላይ ያልተመሠረተ ተስፋ ሰጥቷቸው ነበር። የተስፋው ፍጻሜ የተመሠረተው ሰው በሚሰጠው ምላሽ ሳይሆን፥ በእግዚአብሔር ተስፋ ላይ ብቻ ነበር።

2. በሲና ተራራ የተሰጠው ቃል ኪዳን በዚያን ጊዜ በነበረው ባሕል ላይ የተመሠረተ ነበር። «የሱዜሪያን-ቫዛል» ቃል ኪዳን ተብሎ ተሰይሟል። እንዲህ ዓይነቱ ቃል ኪዳን በቅድመ ሁኔታዎች ላይ የተመሠረተ ነበር። ይኸውም በገዢ ንጉሥና በእርሱ አገዛዝ ሥር ከወደቁት ሌሎች ነገሥታት መካከል ከአንዱ ጋር የሚደረግ ቃል ኪዳን ዓይነት ነበር። በእንደዚህ ዓይነቱ ቃል ኪዳን ገዥው ንጉሥ በሥሩ ባለው ንጉሥ ላይ ፍጹም የሆነ መብትና ሥልጣን እንዳለው ይናገራል። በሥሩ ካለው ንጉሥ ፍጹም ታማኝነትና አገልግሎት ይጠብቃል። ይህ ንጉሥ ታማኝና ታዛዥ ከሆነ ከጠላቶቹ ሁሉ ሊታደገው ገዥው ንጉሥ ቃል ይገባለታል። ልክ እንደዚሁ፥ እግዚአብሔር በእስራኤል ሕዝብ ላይ ፍጹም ንጉሥ ነበር፤ ስለዚህ እስራኤላውያን የሚጠብቁትን ሕግ ሰጣቸው። እነርሱ ለእርሱ ታማኞችና ታዛገች መሆን ነበረባቸው። ለታማኝነታቸውና ለታዛዥነታቸው እግዚአብሔር ሊባርካቸውና ሊጠብቃቸው ቃል ገባ።

---

16ኛ ጥያቄ፥ ሀ) ይህ ነገር ዛሬ እኛ ከእግዚአብሔር ጋር ካለን ግንኙነት ጋር የሚመሳሰለው እንዴት ነው? ለ) እንዴትስ ይለያያል?

---

3. በሲና ተራራ የተገባው ቃል ኪዳን በደም መፍሰስ ጸንቶአል (ዘጸ. 24፡3-8 ተመልከት)።

---

17ኛ ጥያቄ፥ ማር. 14፡24 ተመልከት። የአዲስ ኪዳን አጀማመር ከብሉይ ኪዳን አጀማመር ጋር የሚመሳሰለው እንዴት ነው?

---

ከዘጸ. 19-24 ባለው ጥናትህ ውስጥ የሚከተሉትን 6 ነገሮች ልብ ማለት ጠቃሚ ነው:-

1. እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን ቃል ኪዳንን ከመስጠቱ በፊት ኃይሉንና ታላቅነቱን ገለጠ። ይህ የእግዚአብሔር ኃይልና ቅድስና (መለየት) በተለያዩ ብዙ መንገዶች ይታያል። ማንም ሰው ወደተቀደሰው ተራራ እንዳይቀርብ ወይም እንዳይነካው በሚለው ትእዛዝ ውስጥ ይታያል (ዘጸ. 19:12-13)። እስራኤላውያን ከእግዚአብሔር ጋር ለመገናኘት ራሳቸውን ማዘጋጀት እንዳለባቸው በተሰጠው ጥብቅ ትእዛዝ ውስጥ ትኩረት ተሰጥቶታል፤ (ዘጸ. 19:10-11)። እግዚአብሔር እጅግ ታላቅ የሆነው ኃይሉን በሚገልጥ ከተራራው ላይ በተገለጠ ነጎድጓድ፥ መብረቅ፥ ከባድ ደመና፥ እጅግ በሚያስተጋባ የቀንደ መለከት ድምፅ፥ የእሳትና የመሬት መንቀጥቀጥ ወዘተ. አሳይቷል (ዘጸ. 19:16-19)።

| |
|---|
| 18ኛ ጥያቄ፥ ሀ) እግዚአብሔር ከእስራኤል ሕዝብ ጋር ቃል ኪዳን ከመግባቱ በፊት ክብሩንና ኃይሉን የገለጠላቸው ለምን ይመስልሃል? ለ) እግዚአብሔር ዛሬስ ኃይሉን የሚያሳየው እንዴት ነው? ሐ) ዛሬ የእግዚአብሔርን ኃይልና ታላቅነት መረዳታችን አምልኮአችንን እንዴት ይለውጠዋል? |

በጊዜያችን ካሉት ችግሮች አንዱ፥ ክርስቲያኖች ስለ እግዚአብሔር ኃይልና ቅድስና ያላቸው አመለካከት ዝቅተኛ መሆን ነው። ብዙ ክርስቲያኖች እግዚአብሔርን አይፈሩም። የእግዚአብሔርን ኃይልና ክብር ይበልጥ በተረዳን ቁጥር፥ የሚገባውን ያህል ልናመልከውና ልናከብረው እንችላለን። በመከራና በስደት ውስጥ ሳለን እግዚአብሔር በአሕዛብ ሁሉ ላይ ያለውን ኃይልና ሥልጣን ደግሞም የበላይ ተቆጣጣሪነት ስናስታውስ በእግዚአብሔር ላይ ለመታመን ብርታት እናገኛለን። ለእግዚአብሔር ያለን ፍርሃት ሁልጊዜ እርሱ ለእያንዳንዳችን ካለው ጥልቅ ፍቅር ጋር መስተካከል አለበት። ይህ ፍቅር እግዚአብሔር «አባ አባት» (ሮሜ 8:15) ብለን የምንጠራበትን ድፍረት ይሰጠናል። አምልኮአችን ፍቅርና ፍርሃት ደግሞም አክብሮትና ቅርበት የሚታይበት መሆን አለበት።

2. እግዚአብሔር ከእስራኤል ጋር ቃል ኪዳን የማድረጉ ዓላማ እነርሱን ለራሱ የተለየ ርስት፥ የተለየ ሕዝብ፥ የንጉሥ ካህናት መንግሥትና የተቀደሰ ሕዝብ ለማድረግ ነበር (ዘጸ. 19:5-6)። በብሉይ ኪዳን

የእግዚአብሔር ዓላማ አንድ የተለየን ሕዝብ መምረጥ ነበር። በእስራኤላውያን ማንነት በኩል ምንም የተለየ ነገር አልነበረም። በቁጥር ብዙዎች ወይም ኃያላን የተማሩ ወይም የሠለጠኑ አልነበሩም። የተለዩ ወይም ልዩ ያደረጋቸው እግዚአብሔር በምሕረቱ ስለመረጣቸው ብቻ ነው። ስለዚህ የተለዩ ነበሩ።

ዛሬ እግዚአብሔር ሰዎችን የሚመርጠው ከተለየ የዘር ሐረግ ስለተገኙ አይደለም። ይልቁንም እርሱ ወንዶችንና ሴቶችን በዓለም ላይ ከሚገኙ ሕዝቦች ሁሉ የተለየ ዓይነት ሕዝብ ወይም ዘር እንዲሆኑለት ይመርጣል። ያ ሕዝብ ቤተ ክርስቲያን ናት። የዚህ ሕዝብ አካል የመሆን መመዘኛ እንደ ብሉይ ኪዳን ዘመን በሥጋ መወለድ አይደለም። ነገር ግን በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን የሚገኝ መንፈሳዊ ልደት ነው።

---

19ኛ ጥያቄ፥ ይህ እውነታ በተለያዩ ነገዶችና ጎሣዎች መካከል ያለውን እኔ ከሌላው እሻላለሁ የሚለውን አዝማሚያ እንዴት ያስወግደዋል?

---

እግዚአብሔር የእስራኤልን ሕዝብ የመረጠበት ምክንያት በሁለት ሐረጎች ተገልጸአል። በመጀመሪያ፥ «የንጉሥ ካህናት» እንዲሆኑ ነበር። ካህን መካከለኛ ነው። እግዚአብሔርንና ሰውን ወደ አንድነት በማምጣት ተግባር ውስጥ ለእግዚአብሔር ይሠራል፤ ስለዚህ እስራኤል፥ የካህናት ሕዝብ እንደመሆንዋ መጠን ልትፈጽማቸው የሚገባት ሁለት ተግባራት ነበሩዋት። 1) እግዚአብሔርን ማገልገል ነበረባቸው። 2) አሕዛብን በሙሉ ወደ እግዚአብሔር ለማቅረብና ከእግዚአብሔር ጋር እንዲታረቁ ለማድረግ መሣሪያ መሆን ነበረባቸው (ኢሳ. 49፡6)።

ሁለተኛው ሐረግ እስራኤል «ቅዱስ ሕዝብ» መሆን እንዳለባት ይናገራል። ይህም ማለት ሕዝብዋ ከአሕዛብ የተለየ ኑሮ መኖር ነበረባቸው ማለት ነው። ከዘጸአት - ዘዳግም ያሉት አብዛኛዎቹ ትእዛዛት እስራኤል ቅድስት መሆን እንዳለባትና የተቀደሰ ሕይወት መኖር እንደሚጠበቅባት በመግለጥ ይህን እውነት አንፀባርቀዋል።

3. ከእስራኤል ጋር የተደረገው ቃል ኪዳን የተመሠረተው በዓሥርቱ ትእዛዛት ላይ ነበር። እነርሱም እግዚአብሔር ራሱ የጻፋቸው ስለሆነ (ዘጸ. 20፡22) ዋና ወይም መሠረታዊ የቃል ኪዳን ሕግጋት ነበሩ። እነዚህ ትእዛዛት የመጡት ከሰማይ እንጂ ከሲና ተራራ አልነበረም።

የእግዚአብሔርን ዓለም አቀፋዊ ሕግጋት ስለሚያሳዩ፥ በየዘመኑ በሚኖሩ ሰዎች ሁሉ መጠበቅ አለባቸው።

ዓሥርቱ ትእዛዛት በሁለት ክፍሎች ተከፍለዋል። እነርሱም፦

1. አራቱ ትእዛዛት ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ሊኖረው በሚገባ ግንኙነት ላይ ያተኩራሉ።

ሀ. «ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይሁኑልህ።» እስራኤላውያን በዚያን ጊዜ በነበራቸው እውቀት እውነተኛው አምላክ አንድ ብቻ እንደሆነና ሌሎቹ ጣዖታት እንጂ አምላክ እንዳልሆኑ አያውቁም ነበር። እግዚአብሔር ግን የመጀመሪያና ፍጹም የሆነ ታማኝነት ፈለገ። እርሱን ብቻ ማክበርና መፍራት ነበረባቸው። አይሁድ እርሱን ብቻ ማምለክ ተገቢያቸው ነበር።

| |
|---|
| 20ኛ ጥያቄ፥ ዛሬ ለእኛ እንደ «አማልክት» ሊሆኑብን የሚችሉ አንዳንድ ነገሮች ምንድን ናቸው? |

ለ. «የተቀረጸ ምስል ለአንተ አታድርግ።» ይህ ትእዛዝ ለእግዚአብሔርም ሆነ ለሌሎች አማልክት ማንኛውንም ዓይነት ቅርፅ ወይም ምስል ማድረግን ይከለክላል። ዛፎችን ማምለክ፥ ወይም እግዚአብሔር ምን እንደሚመስል እነርሱ በሚያስቡት መንገድ ቅርፁን ወይም ምስሉን ማበጀት አይገባቸውም ነበር። (ስለ ምስሎች ባለፈው ሳምንት ያጠናነውን ተመልከት)።

ሐ. «የእግዚአብሔርን የአምላክህን ስም በከንቱ አትጥራ።» ለእግዚአብሔር ክብርን የመስጠት አንዱ ክፍል ስሙን ማክበር እንደሆነ ተመልክተናል፤ ስለዚህ የእግዚአብሔር ስም በየጊዜው እንደፈለግን የምንናገረው ወይም የምንጠራው መሆን የለበትም። ይህ ትእዛዝ ብዙ ጊዜ በሁለት መንገድ ይጣሳል፦ በመጀመሪያ፥ ክርስቲያን ያልሆኑ ሰዎች የእግዚአብሔርን ወይም የኢየሱስን ስም ለእርግማን ዓላማ መጠቀማቸው ነው። በሁለተኛ ደረጃ፥ ክርስቲያኖች የሆኑ ሳይቀሩ፥ ምንም ሳያስቡት ወይም ትርጉም በማይሰጥ መልኩ የእግዚአብሔርን ስም መጠቀማቸው ነው። ለምሳሌ፦ አንዳንድ ሰዎች ሲደነግጡ «በኢየሱስ ስም» ይላሉ። ወይም አንዳንድ ሰዎች በአንዳንድ ነገር ላይ ትኩረት ለማድረግ

ሲፈልጉ «በሕግ አምላክ» ይላሉ። ይህ የእግዚአብሔርን ስም በከንቱ መጥራት ነው።

| |
|---|
| 21ኛ ጥያቄ፥ ሀ) አንዳንድ ክርስቲያኖች የእግዚአብሔርን ስም ያለአግባብ መጠቀማቸውን እንዴት አየኸው? ለ) ሰዎች የእግዚአብሔርን ወይም የኢየሱስ ክርስቶስን ስም እንዲያከብሩ ለማስተማር ቤተ ክርስቲያንህ ምን እያደረገች ነው? |

መ. «የሰንበትን ቀን ትቀድሰው ዘንድ አስብ።» በብሉይ ኪዳን፥ እግዚአብሔር የሳምንቱን የመጨረሻ ቀን፥ ማለት ቅዳሜን ለእረፍትና ለአምልኮ ለየው። በአዲስ ኪዳን ክርስቶስ ከሞት የተነሣበትን ቀን ለማክበር፥ ክርስቲያኖች የአምልኮን ቀን ወደ እሑድ ለወጡት። ክርስቲያኖች ከዓሥርቱ ትእዛዛት መካከል እንዳለ ቃል በቃል ተቀብለው የማይታዘዙት ብቸኛ ትእዛዝ ይኸኛው ነው (ቆላ. 2፡16-17)፤ ነገር ግን የዚህ ትእዛዝ መንፈስ መጠበቅ አለበት። ለማረፍና እግዚአብሔርን ለማክበር በሳምንት አንድ ቀን ለጌታ መለየት አለብን። በመላው ዓለም የሚገኙ ክርስቲያኖች ይህ ቀን እሑድ እንዲሆን መርጠዋል።

በአራት ዘጸአትና ዘሌዋውያን የሚገኙ በርካታ ትእዛዛት አይሁድ ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸውን ግንኙነት እንዴት መጠበቅ እንዳለባቸውና እግዚአብሔርን እንዴት ማምለክ እንዳለባቸው የሚናገሩ ናቸው። እነርሱም ይህንኑ መሠረት አጠናከሩት።

2. ስድስቱ ትእዛዛት ሰዎች ከሌሎች ጋር በሚኖራቸው ግንኙነት ላይ የሚያተኩሩ ናቸው። የሚቀጥሉት ስድስት ትእዛዛት እርስ በርሳችን፥ በተለይም ደግሞ የእግዚአብሔር ቤተሰብ አካል ከሆኑት ሰዎች ጋር ሊኖረን ስለሚገባ ግንኙነት ይናገራሉ።

ሠ. «አባትህንና እናትህን አክብር።» እግዚአብሔር ወላጆቻቸውን እንዲያከብሩ፥ ለወላጆቻቸው እንዲጠነቀቁና፥ እንዲታዘዙ ሕዝቡን አዘዘ። ይህን ካላደረጉ በረከትን እንደማያገኙ ነገራቸው። እግዚአብሔር ለዚህ ትእዛዝ ምንም ቅድመ ሁኔታ አላኖረም። ወላጆችችንን ማክበር ያለብን ቸርና መልካም ሰዎች ሲሆኑ ብቻ አይደለም። የተማሩ ስለሆኑ ወይም ገንዘብ ስለሚሰጡንም ወዘተ. አይደለም። ሰዎች ወላጆቻቸውን ላለመታዘዝ የሚችሉበት አንድ

ወቅት ብቻ አለ። ይኸውም ወላጆቻቸው እግዚአብሔር በግልፕ አታድርግ ያለውን እንዲያደርጉ፥ ወይም አድርግ ያለውን እንዳያደርጉ ሲጠይቁአቸው ብቻ ነው። በዚህ ጊዜ ከወላጆቻቸው ይልቅ ለእግዚአብሔር መታዘዝ አለባቸው።

22ኛ ጥያቄ፥ በዚህ ዘመን ብዙ ወጣቶች፥ ክርስቲያኖችም ሳይቀሩ ይህንን ትእዛዝ የማይከተሉት እንዴት ነው?

ረ. «አትግደል።» ይህ ማለት ጨርሶ መግደል የለብንም ማለት አይደለም። እግዚአብሔር ይህንን የእርሱን ትእዛዝ በግድ የለሽነት የሚጥሱትን፥ በተለይ ደግሞ ሆን ብለው የሰዎችን ሕይወት የሚያጠፉትን ሰዎች በሞት እንዲቀጡ ለመንግሥታት መብት ሰጥቶአቸዋል (ሮሜ 13፡4 ተመልከት)። አንዳንዶች እንደሚያስተምሩት ይህ ሕግ ወደ ጦርነት መሄድን ጨርሶ የሚከለክል አይደለም፤ ይልቁንም ሕይወትን በግዴለሽነት ስለማጥፋት የሚናገር እንጂ።

ሰ. «አታመንዝር።» ይህ ትእዛዝ ሁለት ዓይነት ኃጢአቶችን ያጠቃልላል። የመጀመሪያው፥ በባልና ሚስት መካከል በግብረ ሥጋ ግንኙነት ረገድ ታማኝ ያለመሆን ኃጢአት ነው። ባልየውም ሆነ ሚስትየዋ ከሌላ ከማንኛውም ሰዎች ጋር የግብረ ሥጋ ኅብረት እንዲኖራቸው አልተፈቀደላቸውም። ሁለተኛው ደግሞ፥ ያላገቡ ሰዎች የሚፈጽሙት ማንኛውም የግብረ ሥጋ ግንኙነት ተግባር ነው። እግዚአብሔር እንዳዘዘው ግብረ ሥጋ መፈጸም ያለበት በጋብቻ በተጣመሩ ባልና ሚስት መካከል ብቻ ነው።

23ኛ ጥያቄ፥ ሀ) በቤተ ክርስቲያን አባላት መካከል በርካታ የሆነ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ኃጢአት የሚከሰተው ለምንድ ነው? ለ) አንዳንድ ሰዎች ማመንዝር ከወንድ ይልቅ ለሴት የከፋ እንደሆነ የሚያስተምሩት ለምንድን ነው? ትክክል ናቸውን? መልስህን አብራራ። ሐ) ቤተ ክርስቲያንህ «አታመንዝር» የሚለውን ሕግ እንዲያከብሩ ያገቡ የትዳር ጓደኞችንም ሆነ ያላገቡትን አባላትዋን እንዴት ማበረታታት ትችላለች?

ሸ. «አትስረቅ።» ይህ ማለት ስሕተት መሆኑን እያወቅህ፥ የራስህ ያልሆነውን ነገር ከሰው ላይ መውሰድ ለራስህ ማድረግ ስህተት

ነው። ይህም ገንዘብ ወይም ቁሳቁሳዊ ነገር መሆን ይችላል። ወይም በትምህርት ቤት ከሌላ ሰው ወረቀት ላይ የፈተና መልስ መቅዳት ወይም መኮረጅ ሊሆን ይችላል።

24ኛ ጥያቄ፥ ዛሬ ሰዎች (ክርስቲያኖች ሳይቀሩ) የሚሰርቁባቸውን የተለያዩ መንገዶች ግለጽ።

ቀ. «በባልንጀራህ ላይ በሐሰት አትመስክር።» ይህ ትእዛዝ ሁለት ዋና ዋና ነገሮችን ያንፀባርቃል። የመጀመሪያው በዳኛ ፊት ወይም ለአንድ ነገር ምስክርነት መስጠት በሚያስፈልግበት ሰዓት አንዳችም ነገር ሳንቀንስና ሳንጨምር እውነቱን በሙሉ እንዳለ የመናገር ኃላፊነት ነው። እውነትን መሸሽግ ወይም እውነትን በከፊል ብቻ መናገር ውሸትና ስሕተት ነው። ሁለተኛ ስላደረግነውና ስላየነው ነገር እውነትን ብቻ የመናገር ኃላፊነት አለብን። ይህ ትእዛዝ ሐሜትንና የመሳሰሉትን ይቃወማል።

በ. «የባልንጀራህን ቤት አትመኝ . . .።» መመኘት የብዙ ኃጢአት ምንጭ እንደሆነ ክርስቶስም፥ ጳውሎስም ተናግረዋል (ማቴ. 5፡20፤ ሮሜ 7፡7)።

25ኛ ጥያቄ፥ ማቴ. 22፡34-40 ሀ) ኢየሱስ ታላላቅ ያላቸው ሁለቱ ትእዛዛት ምንድን ናቸው? ለ) እነዚህ ሁለት ትእዛዛት ዓሥርቱን ትእዛዛት የሚጠቀልሉበት እንዴት ነው?

በብሉይ ኪዳን ከሚገኙ ሌሎች ሕጎች አብዛኛዎቹ እግዚአብሔርን እናከብር ዘንድ ከሚፈልጋቸው ከሁለቱ ኅብረቶች በአንዱ ላይ ማተኮር አለባቸው። በመጀመሪያ፥ እግዚአብሔርን የሚያከብሩና እርሱንም ስለማምለክ የሚናገሩ ሕጎች አሉ። ለምሳሌ፡- እስራኤላውያን እንዴት ማምለክ እንዳለባቸው (ዘጸ. 20፡22-26) እና ሊጠብቁዋቸው ስለሚገባቸው ሃይማኖታዊ በዓላት (ዘጸ. 23፡14-19) የተነገሩ ሕግጋት አሉ።

ሁለተኛ፥ እስራኤላውያን ከጎረቤቶቻቸው ጋር እንዴት መኖር እንዳለባቸው በግልጽ የሚናገሩ ሕግጋት አሉ። ምናልባት እነዚህን ሕግጋት ሁሉ ዛሬ መጠበቅ አስፈላጊ ባይሆንም እንኳ፥ እነርሱን በሚመለከት እርስ በርስ ሊኖረን ስለሚገባ ግንኙነት የምናወጣቸው በርካታ መመሪያዎች አሉ። አይሁድ አገልጋዮቻቸው የሆኑትን ሌሎች አይሁድ እንዴት መያዝ

እንዳለባቸው የሚናገሩ ሕግጋት ነበሩ (ዘጸ. 21፡2-11)። አንድ ሰው ወይም እንስሳ በሌላ ሰው ወይም እንስሳ በማወቅም ሆነ ባለማወቅ ጉዳት ሲደርስበት ሁኔታውን እንዴት መያዝ እንደሚገባ የሚናገሩ ሕግጋት ነበሩ (ዘጸ. 21፡12-36)። አንድ ሰው ንብረት ሲሰርቅ፥ ወይም ሲያበላሽ ሁኔታውን እንዴት መያዝ እንደሚያስፈልግ የሚናገሩ ሕግጋትም ነበሩ (ዘጸ. 22፡1-15)። በጋብቻ ውስጥ አለመተማመን በሚፈጠርበት ጊዜ ሁኔታውን እንዴት መያዝ እንደሚገባ የሚናገሩ ሕግጋት አሉ። ከሁሉም በላይ የእግዚአብሔር አሳብ ሰዎች ሁሉ በሰላምና በፍትሕ ተባብረው እንዲኖሩ ነበር (ዘጸ. 23፡1-9)።

5. እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን የሰጣቸው ሕግጋት ሰዎች ለሚሳተፉባቸው የተለያዩ ግንኙነቶች የሚጠቅሙ ትእዛዛት የሚገኙባቸው ናቸው። ከእነዚህ ሕጎች አብዛኞዎቹ በቀጥታ ተግባራዊ መሆን አለባቸው ማለት አይደለም። ነገር ግን እስራኤላውያን እርስ በርስ እንዴት መኖር እንዳለባቸው የሚያሳዩ ምሳሌዎች ነበሩ። የተቀደሱ የእግዚአብሔር ሕዝብ እንደመሆናቸው መጠን በዚህ በክፋት በተሞላ ዓለም ውስጥ እንዴት መኖር እንዳለባቸው የሚያሳዩ መመሪያዎች ሆነው የሚያገለግሉ ናቸው።

እነዚህን ሕጎች በምናጠናበት ጊዜ፥ ዛሬ ከሕይወታችን ጋር እንዴት እንደምናዛምዳቸው በጣም መጠንቀቅ አለብን። በመጀመሪያ ቋሚና ጊዜያዊ የሆኑ ሕግጋትን ለይተን ማወቅ አለብን፤ (ዘሌዋ. 17፤ ዘዳ. 12፡20-24 የጊዜያዊ ሕጎች ምሳሌዎች ናቸው)። አንድ ሕግ ጊዜያዊ ወይም ቋሚ መሆኑን ለመለየት በጣም ጥሩው መንገድ፥ በአዲስ ኪዳን እንደ ሕጉ እንደገና ተደግሞ እንደ ሆነና እንዳልሆነ ማየት ነው። በሁለተኛ ደረጃ፥ ደግሞ እግዚአብሔር ሕጉን በሚሰጥበት ጊዜ የነበረውን ዓላማ ወይም ምክንያት ማየት ነው። እነዚህ የተለያዩ ሕጎች በተናጠል በዚህ ዘመን የማይሠሩ ቢሆኑም እንኳ በውስጣቸው ያለው መመሪያ ግን አሁንም ዋጋ ያለው ነው።

| |
|---|
| 26ኛ ጥያቄ፥ ዘጸ. 23፡1-9 አንብብ። እነዚህን ሕግጋት በሁለት ከፋፍለህ ተመልከታቸው። ሀ) በመጀመሪያ፥ ዛሬም ልንጠብቃቸው የሚገባን ቋሚ የሆኑ ሕግጋት የትኞቹ ናቸው? ለ) ሁለተኛ፥ ጊዜያዊ የሆኑ በተናጠል ለአንድ ሁኔታ ብቻ የሚጠቅሙ ሕግጋት የትኞቹ ናቸው? ሐ) ከእነዚህ ሕግጋት የምናገኛቸው ዛሬ ለሕይወታችን |

የሚጠቀሙን መመሪያዎች የትኞቹ ናቸው? መ) ከእነዚህ ሕግጋት መካከል ዛሬ በክርስቲያኖች ላይ ችግር የሚፈጥሩ የትኞቹ ናቸው?

በዘጸ. 24 የእስራኤል ሕዝብ በቃል ኪዳኑ ቅድመ ሁኔታዎች ሁሉ እንዴት እንደተስማሙ ያሳያል። በስምምነታቸውና በፈሰሰው ደም ቃል ኪዳኑን አጸኑት።

## 3ኛ ቀን፡- ዘጸአት 25-40

ከዘጸአት 25-40 ባሉት ክፍሎች ሦስት ዋና ዋና ነገሮች ቀርበዋል። 1) እግዚአብሔርን የማምለኪያ ስፍራ የሆነው የመገናኛው ድንኳን እንዴት መሠራት እንዳለበት የሚናገረው መመሪያ ሰፊውን ክፍል ይዟል። ቀጥሎም የእስራኤል ሕዝብ የተሰጣቸውን ትእዛዝ ተቀብለው እግዚአብሔር የሚኖርበትን የመገናኛ ድንኳን እንዴት እንደሠሩ ይናገራል። 2) በሁለተኛ ደረጃ የካህናትና የሊቀ ካህኑ አልባሳት እንዴት እንደተሠሩ የሚናገር ክፍል እናገኛለን። 3) ሕዝቡ በእግዚአብሔር ላይ በማመፅ የጥጃን ምስል ሠርተው እንዴት እንዳመለኩ የሚናገር ክፍል እናገኛለን።

27ኛ ጥያቄ፥ ዕብ. 8፡1-6፤9፡1-14 አንብብ። የዕብራውያን ጸሐፊ የቀድሞውን የመገናኛ ድንኳን ከክርስቶስ ሥራ ጋር በማወዳደር ያቀረበው እንዴት ነው?
28ኛ ጥያቄ፥ ዘጸ. 25-40 አንብብ። ሀ) በመገናኛው ድንኳን ውስጥ የሚገኙትን የተለያዩ ዕቃዎች ዘርዝር። ለ) ለመገናኛው ድንኳን የሚያስፈልጉ ነገሮችን ሁሉ የሰጠው ማን ነበር? ሐ) እግዚአብሔር የመገናኛው ድንኳን እንዲሠራ ያዘዘበትን የተለያዩ ምክንያቶች ዘርዝር። መ) ሙሴ በተራራው ላይ በቆየበት ጊዜ እስራኤላውያን ምን ኃጢአት ሠሩ? ሠ) በእነዚህ ምዕራፎች ውስጥ የሙሴ ታላቅ መንፈሳዊ መሪነት የተገለጠው እንዴት ነው?

## 4ኛ ቀን፡-

1. የመገናኛው ድንኳን

እስከዚህ ጊዜ ድረስ እስራኤላውያን በመሠዊያ ላይ ያመልኩ ነበር። የየቤተሰቡ ኃላፊም ለቤተሰቡ እንደ ካህን ያገለግል ነበር። መሠዊያ ሠርቶ፥ በመሠዊያው ላይ ለእግዚአብሔር የሚሆን እንስሳ ይሠዋ ነበር።

በምድሪቱ ውስጥ በሚንቀሳቀስበት ጊዜ፥ ሌሎች መሠዊያዎችን ይሠራ ነበር። አሁን ግን እግዚአብሔር የእስራኤልን ሕዝብ ስለ መረጠና ለሕዝቡ የሚሆን ሕግ ስለ ሰጠ፥ የአምልኮ መንገዳቸውን ለወጠው። በመጀመሪያ፥ እግዚአብሔር እርሱን የሚያመልኩበት የመገናኛ ድንኳን እንዲሠሩ አዘዛቸው። ሁለተኛ፥ አምልኮውን ይመሩ ዘንድ ካህናትን ለዚህ ሥራ ለየ። በዚህ በዘጸአት ባለው የተወሰነ ክፍልና በኦሪት ዘሌዋውያን ሕዝቡ እግዚአብሔርን ለማምለክ እንዴት መቅረብ እንዳለባቸው የተጻፉ ትእዛዛት አሉ።

የእስራኤል ንጉሥ በሆነው በእግዚአብሔርና በሕዝቡ መካከል ቃል ኪዳን ከተደረገና የእግዚአብሔር አገልጋዮችም ካጸኑት በኋላ፥ ሕዝቡ እግዚአብሔርን የሚያመልኩበት የመገናኛ ስፍራ ይሆን ዘንድ የመገናኛ ድንኳንን እንዲሠሩ አዘዘ። የመገናኛው ድንኳን እግዚአብሔር ራሱንና ፈቃዱን ለሕዝቡ የሚገልጥበትም ስፍራ ነበር። እግዚአብሔር እንዳለው «በመካከላቸውም አድር ዘንድ መቅደስ ይሥሩልኝ» (ዘጸ. 25፡8)። የመገናኛው ድንኳን ዛሬ እንዳሉት ቤተ ክርስቲያኖቻችን ቋሚ ሕንጻ አልነበረም። እስራኤላውያን በሚሄዱበት ስፍራ ሁሉ በውስጡ ካሉት ዕቃዎች ጋር ይዘው ለመሄድ እንዲችሉ ተደርጎ የተሠራ ነበር። ቤተ መቅደሱ ቋሚ የማምለኪያ ስፍራ ተደርጎ በሰሎሞን የተሠራው ከ400 ዓመታት በኋላ ነበር።

ስለ መገናኛው ድንኳን የሚከተሉትን ነገሮች አስተውል፡-


1. የመገናኛው ድንኳን አንድ ብቻ ነበር እንጂ እንደ አሕዛብ የማምለኪያ ስፍራ ብዙ አልነበረም። እግዚአብሔር እስራኤላውያንን በመገናኛው ድንኳን ብቻ እንዲያመልኩ አዘዛቸው። ይህም እስራኤላውያንን ከመኮብለልና ሐሰተኞች አማልክትን ከማምለክ ለመጠበቅ ነበር።

2. የእስራኤል ሕዝብ የመገናኛውን ድንኳን ለመሥራት አስፈላጊ የሆኑ ነገሮችን የመስጠት ኃላፊነት ተጥሎባቸው ነበር። የእስራኤል ሕዝብ የመገናኛውን ድንኳን ለመሥራት ምን ያህል ከፍተኛ ጉጉት እንደነበራቸው የምናየው ለመሥሪያ ከሚያስፈልጉ ነገሮች በላይ በመስጠታቸው ነው። እንደ እውነቱ ከሆነ ሙሴ ሕዝቡን ከመስጠት እንዲቆጠቡ ይነግራቸው ነበር (ዘጸ. 36፡2-7)።

3. የመገናኛው ድንኳን የሚገኘው በእስራኤላውያን ሠፈር መሐል ነበር። ይህም እግዚአብሔርን ማምለክ በሕይወታቸው ከሁሉ በላይ አስፈላጊ ነገር መሆኑን የሚያሳይ ነበር (ዘኁል. 2፡17)።

4. የእግዚአብሔር መገኘት የተቀደሰ መሆኑንና ከኃጢአትም መለየቱን ለማመልከት፥ ከሕዝቡ በሐር መጋረጃ ተለይቶ ነበር።

5. የመገናኛው ድንኳን አወቃቀር እንደሚከተለው ነበር፡-




ለመገናኛው ድንኳን አራት የተለያዩ ክፍሎች ነበሩት። የመጀመሪያው፥ ከመገናኛው ድንኳን ውጭ ያለው ስፍራ ነው። ሰዎች እግዚአብሔርን ስለማምለክ አንዳችም ትኩረት ሳያደርጉ ሊመላለሱና ሊሠሩ የሚችሉበት ስፍራ ነው። ይህም ሕዝቡ የሚኖሩበት ስፍራ ነው። ሕዝቡን ከመገናኛው ድንኳን የሚለየው መጋረጃ ነበር። የመገናኛው ድንኳን እግዚአብሔር የሚያድርበትና እርሱ ሊመለክበት የሚገባ ስፍራ መሆኑ በግልጽ ታውቆ መከበር የሚገባው ነበር።

በሁለተኛ ደረጃ፥ ውጫዊው ክፍል ወይም «አምልኮ የሚፈጽሙ ሰዎች ያሉበት ክፍል» የሚባል ስፍራ ነበር። በዚህ ክልል ለአምልኮ የሚያገለግሉ ሁለት ዋና ዋና ዕቃዎች ነበሩ። እነርሱም የሚከተሉት ናቸው፡-

1) የነሐስ መሠዊያ:- መሠዊያው 2.5 ካሬ ሜትር ስፋትና 1 ሜትር ከፍታ ነበረው። እርሱም መሥዋዕቶች ሁሉ የሚቀርቡበት ትልቅ መሠዊያ ነበር። ማንኛውም ተራ ሰው ወደ እግዚአብሔር በመምጣት አምልኮ ለመፈጸም የሚችልበት ስፍራ ነበር። ከዚህ የበለጠ ወደ እግዚአብሔር ሊቀርብ ግን አይችልም ነበር። ከዚህ የበለጠ በመቅረብና ወደ መገናኛው ድንኳን ውስጥ በመግባት ለማምለክ የሚችሉት ካህናት ብቻ ነበሩ።

2) የነሐስ መታጠቢያ:- ይህም የተሠራው ከነሐስ ሲሆን፥ በውስጡ ውኃ ይደረግበት ነበር። ካህናት ወደ ቅድስት በመግባት እግዚአብሔርን ከማምለካቸውና ከማገልገላቸው በፊት፥ ንጽሕና ከጎደላቸው ከማናቸውም ነገሮች መንጻታቸውን ለማሳየት፥ እግሮቻቸውን የሚታጠቡት በዚህ ውኃ ነበር።

| |
|---|
| 29ኛ ጥያቄ፥ ይኸው መንፈሳዊ መንጻት በዚህ ዘመን ላሉ መሪዎች የሚያስፈልገው እንዴት ነው? |

በሦስተኛ ደረጃ፥ የሚገኘው ስፍራ ቅድስት ተብሎ የሚጠራው ነው። በዚያ በሰፊው የመገናኛ ድንኳን ክልል ውስጥ አነስተኛ ድንኳን ነበር። ይህ ድንኳን ሁለት ክፍሎች ያሉት ሲሆን፥ ሰፊው ክፍል ቅድስት ይባል ነበር። ቅድስት የተባለው ስፍራ እግዚአብሔር ለማገልገል ኃላፊነት ያለባቸው ካህናት በየዕለቱ አገልግሎታቸውን የሚፈጽሙበት ስፍራ ነበር። ቅድስት በተባለው ስፍራ ሦስት የአምልኮ ዕቃዎች ነበሩ።

1) በስተሰሜን በኩል የኅብስቱ መቀመጫ ወርቃማ ጠረጴዛ ነበር። የተሠራው ከግራር እንጨት ሲሆን በወርቅ ተለብጦ ነበር። በጠረጴዛው ላይ እያንዳንዳቸው አንዳንድ የእስራኤል ነገድ የሚወክሉ እርሾ የሌለባቸው አሥራ ሁለት ቂጣዎች ነበሩ። እነዚህ በየሳምንቱ እየተቀየሩ ካህናቱ ይበሏቸው ነበር።

2) በደቡብ የቅድስት ክፍል ደግሞ የወርቅ መቅረዝ ነበር። መቅረዙ ሰባት ቅርንጫፎች ነበሩት። በየጠዋቱና በየምሽቱ የሚሆነውን ነገር ለማድረግ ካህናቱ ይከታተሉ ነበር። መቅረዞቹም ሌሊቱን በሙሉ ሲበሩ ያድሩ ነበር።

3) በምዕራብ በኩል ቅድስትን ከተከታዩ ክፍል ከሚለየው መጋረጃ አጠገብ፥ ከወርቅ የተሠራ የዕጣን መሠዊያ ነበር። ይህ መሠዊያ

ከነሐስ መሠዊያው የሚያንስ ሲሆን፥ 1.2 ካሬ ሜትር ቁመት ነበረው። በዕጣን መሠዊያው ላይ ካህናቱ በየቀኑ ጥዋትና ማታ ዕጣን ያጥኑበት ነበር።

በአራተኛ ደረጃ፥ ቅድስተ ቅዱሳን የሚባል ስፍራ ነበር። ይህ አነስተኛ ክፍል ሲሆን፥ የያዘውም ታቦት ብለን የምንጠራውን አንድ የአምልኮ ዕቃ ብቻ ነበር። ይህ የእግዚአብሔር ዙፋን ስለነበር፥ ከመገናኛው ድንኳን ዕቃዎች ሁሉ የሚበልጥና የተቀደሰ ነበር። ታቦቱም ከግራር እንጨት የተሠራ ሆኖ በወርቅ የተለበጠ ነበር። ከ1 ሜትር ትንሽ የሚበልጥ ርዝመት ሲኖረው፥ 0.75 ሜትር ቁመትና ጎን ነበረው። ታቦቱ ክዳን ያለው ሳጥን ይመስል ነበር። በክዳኑ ጫፍና ጫፍ ላይ ክንፎቻቸው የሚያንዣብቡ የሚመስሉ ከወርቅ የተሠሩ የሁለት ኪሩቦች ምስል ነበረበት። ከሁለቱ ኪሩቦች ክንፎች በታች ያለው የክዳኑ ክፍል «የሥርየት መከደኛ» በመባል ይታወቅ ነበር። ምክንያቱም በዓመት አንድ ጊዜ እግዚአብሔር የሕዝቡን ኃጢአት ይቅር ይል ዘንድ ደም የሚረጨው በዚህ ስፍራ ላይ ስለነበር ነው። የእግዚአብሔር ክብር የሚያድረውም በሥርየት መከደኛው ላይ ነበር። ይህም ዙፋኑ ነበር። ከቅድስተ ቅዱሳን ንጉሥ ሆኖ እስራኤልን ያስተዳድር ነበር። ይህ የመገናኛው ድንኳን ክፍል እጅግ የተቀደሰ ስፍራ ስለነበር በዓመት አንድ ጊዜ ብቻ ወደ እርሱ የመግባት ሥልጣን ያለው ሊቀ ካህኑ ነበር።

በቃል ኪዳኑ ታቦት ውስጥ ዓሥርቱ ትእዛዛት የተጻፈበት ጽላት (ዘጸ. 25፡21)፥መና ያለበት ማድጋ (ዘጸ. 16፡32-34) እና ያቆጠቆጠች የአሮን በትር (ዘኁል. 17፡10) ነበሩበት። ኋላም የእግዚአብሔር ሕግ የተጻፈበት መጽሐፍ በታቦቱ አጠገብ እንዲቀመጥ ተደረገ (ዘዳ. 31፡26)።

> 30ኛ ጥያቄ፥ ሀ) የመገናኛውን ድንኳን በመሥራት ረገድ ከምናየው ከፍተኛ ጥንቃቄና ስፌ ተግባር ውስጥ የምንማራቸው አንዳንድ መንፈሳዊ መመሪያዎች ምንድን ናቸው? ለ) ከአራቱ ክፍሎች ውስጥ እግዚአብሔርን ስለ ማምለክ የምንማረው ነገር ምንድን ነው?

አንዳንድ ክርስቲያኖች እነዚህ የአምልኮ ዕቃዎች ወደ ክርስቶስ ያመለክታሉ ይላሉ። ለምሳሌ፡-

1) የነሐስ መሠዊያው፥ ክርስቶስ በእኛ ምትክ መሥዋዕት የመሆኑ ምልክት ነው (ሮሜ 5፡8)።

2) የነሐስ መታጠቢያው፥ ክርስቶስ ከኃጢአታችን እንደሚያነጻን ያመለክታል (1ኛ ዮሐ. 1፡9)።

3) የኅብስቱ ጠረጴዛ፥ ክርስቶስ የሕይወት እንጀራ መሆኑን ያመለክታል (ዮሐ. 6፡51)።

4) የወርቅ መቅረዙ፥ ክርስቶስ የዓለም ብርሃን የመሆኑ ምልክት ነው (ዮሐ. 8፡12)።

5) የዕጣን መሠዊያው፥ ክርስቶስ አማላጃችን መሆኑን ያመለክታል (ዕብ. 7፡25)።

6) የቃል ኪዳኑ ታቦት ክርስቶስ ንጉሣችን መሆኑን ያመለክታል (ራእ. 19፤ 16)።

ስለዚህ ጉዳይ የበለጠ ለመረዳት «ክርስቶስ በማደሪያው ድንኳን» የሚለውን መጽሐፍ ማጥናት ትችላለህ።

6. የመገናኛውን ድንኳን ለመሥራት እግዚአብሔር ሁለት ሰዎችን መርጦ ኃይል አስታጠቃቸው። እነዚህ ሰዎች ባስልኤልና ኤልያብ ይባሉ ነበር፤ (ዘጸ. 31፡1-11)። እግዚአብሔር የስብከትና ወንጌልን የማስተማር ሥራ እንደሚያከብር ሁሉ፥ የእጅ ሙያንም ያከብራል። ችሎታዎች ሁሉ ከእግዚአብሔር የተሰጡ ስጦታዎች ናቸው።

7. የመገናኛው ድንኳን ሥራ በተጠናቀቀ ጊዜ፥ እግዚአብሔር የክብር ደመናውን በማውረድ ሥራቸውን ሁሉ እንደተቀበለ አረጋገጠ። ሕዝቡን ሲመራቸው የነበረው ደመና በመገናኛው ድንኳን ላይ ወረደና ሞላው። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የእግዚአብሔር ክብር ከመገናኛው ድንኳ በሚነሣበት ጊዜ የእስራኤል ሕዝብ እግዚአብሔርን ለመከተል ይንቀሳቀሱ ነበር (ዘጸ. 40፡34-38)።

31ኛ ጥያቄ፥ ዮሐ. 1፡14ን አንብብ። «በእኛ አደረ» ማለት «በእኛ መካከል የመገናኛው ድንኳን ሆነ» ማለት መሆኑን አስተውል። ሀ) ይህ ጥቅስ፥ በዘጸ. 40 ከተጠቀሰው ታሪክ ጋር የሚነጻጸረው እንዴት ነው? ለ) ይህ ስለ ክርስቶስ ምን ያስተምረናል?

## 2. የካህናት አልባሳት

ከዚህ ቀደም፥ ከሙሴ ዘመን በፊት የቤተሰቡ ካህን የቤተሰብ ኃላፊ የሆነው ሰው እንደነበረ ተመልክተናል። ለእግዚአብሔር መሥዋዕትና ለመሠዋት ኃላፊነት የተሸከመው ሰው እርሱ ነበር። አሁን ግን እግዚአብሔር ያንን አሠራር ለወጠው። እርሱን ያገለግለው ዘንድ አንድ የእስራኤል ነገድ ለየ። ያም የተለየ ነገድ የሌዋውያን ነገድ ነበር። በብሉይ ኪዳን ዘመን ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት በመገናኛው ድንኳን እንዲሠሩ የተፈቀደላቸው ሌዋውያን ብቻ ነበሩ። በተጨማሪ የተመረጡ መንፈሳዊ መሪዎች እንዲሆኑ ከሌዋውያን መካከል እግዚአብሔር አንድ ቤተሰብን ለየ። እነርሱም አሮንና ልጆቹ ናቸው። የአሮን ዝርያዎች ካህናት ሆኑ። ለመገናኛው ድንኳን አጠቃላይ አገልግሎት ኃላፊነት የነበራቸው ሌዋውያን ሲሆኑ፥ ካህናቱ ደግሞ እግዚአብሔርን የማምለክ ፕሮግራም ይመሩ ነበር። በብሉይ ኪዳን ዘመን ካህናት ለሚከተሉት ነገሮች ኃላፊነት ነበረባቸው:-

1. ለእግዚአብሔር መሥዋዕትን በመሠዋትና ለሕዝቡ የኃጢአት ይቅርታን በማስገኘት፥ በእግዚአብሔርና በሰው መካከል መካከለኛ ሆኖ የማስታረቅን ተግባር መፈጸም ዋና ሥራቸው ነበር (ዘጸ. 28፡29-30፥43)።
2. ብዙ ጊዜ ኡሪምና ቱሚም በመጠቀም ለሕዝቡ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ይለዩ ነበር (ዘኁል. 27፡21)።
3. ቅዱሳት መጻሕፍትን የመገልበጥና ጠብቆ የማቆየት ኃላፊነት በተጨማሪም መጽሐፍ ቅዱስ ምን እንደሚል የማስተማር ኃላፊነት ነበረባቸው።
4. በመገናኛው ድንኳን ውስጥ የሚፈጸሙ ዕለታዊ ተግባራትን ማከናወንና በኃላፊነት መቆጣጠር ነበረባቸው።

> 32ኛ ጥያቄ፥ እነዚህ ኃላፊነቶች ዛሬ የቤተ ክርስቲያን መሪዎቻችን ካለባቸው ኃላፊነቶች ጋር የሚመሳሰሉት ወይም የሚለያዩት እንዴት ነው?

ካህናት ምን ዓይነት ሰዎች መሆንና በማደሪያው ድንኳን እንዴት ማገልገል እንዳለባቸው እግዚአብሔር ዝርዝር መመሪያዎችን ስለሰጠ፥

ቆይተን እርሱን እንመለከታለን። እንዲሁም ካህናት እንዴት መሥራት እንዳለባቸው መመሪያዎችን ሰጥቷል።

ካህናት መንፈሳውያን መሪዎች ስለሆኑ፥ ለእግዚአብሔር ራሳቸውን በቅድስና መጠበቅ ነበረባቸው። በእግዚአብሔር ፊት ላላቸው ልዩ ስፍራ መለያና ከመቀደሳቸው አስፈላጊነት አንጻር፥ እግዚአብሔር ልዩ የሆኑ ልብሶችን ሰጣቸው።

1. በመገናኛው ድንኳን ውስጥ የሚያገለግሉ ካህናት ልብሶች:- አገልጋዮች እንደ መሆናቸው ካህን መልበስ ያለበት አራት ዓይነት ልብሶች:-

   ሀ. ረጅምና ያልተሰፋ፥ እስከ እግር ድረስ የሚወርድ እጅጌ ያለው ኮት፥

   ለ. በሰማያዊ፥ በሐምራዊና በቀይ ጨርቆች የተሠራ የወገብ መታጠቂያ፥

   ሐ. በራስ ላይ የሚደፋ ቆብ፥

   መ. ከኮት ሥር የሚለበስ በፍታ የሆነ ዝንጉርጉር የውስጥ ልብስ ነበሩ።

2. የሊቀ ካህኑ ልብሶች በጣም የተለዩና ከሌሎች ካህናት ጎልቶ እንዲታይ የሚያደርጉት ነበሩ። እነዚህን ልብሶች የሚለብሰውም በመገናኛው ድንኳን በሚያገለግልበት ጊዜ ብቻ ነበር።

   ሀ. ረጅም መጎናጸፊያ:- ይህ ከአንገት ጀምሮ እስከ ጉልበት በታች ድረስ የሚደርስ ልብስ ነው። መልኩ ሰማያዊ ሲሆን፥ ሮማኖችና የወርቅ ሻኩራዎች (ቃጭሎች) ነበሩበት። ሻኩራ ለሁለት ምክንያት ጠቃሚዎች ነበሩ:- አንደኛ፥ ሊቀ ካህኑ በመገናኛው ድንኳን በሚያገለግልበት ጊዜ፥ ወደ ቅድስተ ቅዱሳን በመግባት ላይ መሆኑን ማስጠንቀቂያ ነበሩ (ዘጸ. 28፡35)። ሁለተኛ፥ ሊቀ ካህኑ በዓመት አንድ ጊዜ ወደ ቅድስተ ቅዱሳኑ ሲገባ፥ እንቅስቃሴ በማሰማት በሕይወት እንዳለና ቅዱስ የሆነው እግዚአብሔር እንዳልቀሠፈው ሕዝቡ እንዲያውቁ ነበር።

ለ. ኤፉድ፡- ከተልባ እግር የተሠራ (በፍታ)፥ ሁለት ጨርቆች የያዘና በሊቀ ካህኑ ትከሻ የሚያልፍ ነበር። መልኩም በወርቅ፥ በሰማያዊ፥ በሐምራዊና በቀይ ግምጃ የተፈተለ ነበር። ለሁለቱ ጫፎች እያንዳንዳቸው ስድስት ስድስት የእስራኤል ነገዶች ስሞች የተጻፉባቸው መረግድ (የከበረ ድንጋይ) ነበረባቸው። ይህም የሚያመለክተው፥ ሊቀ ካህኑ የእስራኤልን ነገዶች እንደሚወክልና በጌታ ፊት ሸክማቸውን እንደሚያቀርብ ነበር።

ሐ. የደረት ኪሱ 25 ካሬ ሳንቲሜትር የሆነ ጠፍጣፋ ነገር፥ በብዙ ኅብረ ቀለም ያሸበረቀ ነበሩት፡- ሁለት ዓላማዎችም ነበሩት። የመጀመሪያ፥ በእያንዳንዳቸው ላይ የእስራኤል ነገዶች ስም የተጻፉባቸው አሥራ ሁለት ዕንቁዎች ተሰፍተውበት ነበር። እነዚህም ድንጋዮች ሊቀ ካህኑ እግዚአብሔር ፊት እንዴት ሕዝቡን እንደሚወክል የሚያሳዩ ነበሩ። በደረቱ (በልቡ) ላይ መሆናቸው፥ በፍቅርና በርኅራኄ አሥራ ሁለቱን የእስራኤል ነገዶች ማገልገል እንዳለበት የሚያሳዩ ሊሆኑ ይችላሉ። በሁለተኛ ደረጃ፥ በደረቱ ላይ ባለው ጠፍጣፋ ነገር ሁለት ኪሶች ነበሩ። በሁለቱ ኪሶች ውስጥ ኡሪምና ቱሚም የሚባሉ ሁለት ልዩ ድንጋዮች ነበሩ። እነዚህ ሁለት ድንጋዮች ምን እንደሆኑ በእርግጥ የምናውቀው ነገር የለም። የስማቸው ትርጉም «ብርሃንና» «ፍጹምነት» የሚል ነው። የምናውቀው ነገር የጌታን ፈቃድ ለመወሰን አገልግሎት ላይ መዋላቸውን ነው (ዘኍል. 27፡21)።

መ. ሊቀ ካህኑ በቅጠል ቅርፅ በወርቅ የተሠራና በግንባር ላይ የሚንጠለጠል ነገርም ያደርግ ነበር። በላዩ ላይ «ቅድስና ለእግዚአብሔር» የሚል ጽሑፍም ነበረበት። ይህም የሚያመልኩት አምላክ ቅዱስ እግዚአብሔር እንደሆነ የሚያስታውስ ነበር፤ ስለዚህ ወደ እርሱ ሊቀርቡ የሚገባቸው በተቀደሰ ሕይወት ነበር። በተጨማሪም ሊቀ ካህኑ ለኃጢአት መሥዋዕትን በማቅረብ፥ ኃጢአተኛ የሆኑ ሰዎችን በእግዚአብሔር ፊት እንዴት የተቀደሱ እንደሚያደርጋቸው የሚያመለክት ነበር።

ካህናቱን ለአምልኮ ሥራ ለመለየት ከፍተኛ ጥንቃቄ ይደረግ ነበር። ለኃጢአታቸው የሚሆኑ መሥዋዕቶችም ነበሩ። ለተለየ አገልግሎት በእግዚአብሔር መለየታቸውን የሚያሳይ ዘይት የመቀባት ሥርዓትም ነበራቸው። በቀኝ አውራ ጣታቸው ላይ፥ በጆሮአቸውና በትልቁ የእግር

ጣታቸው ላይ የደም መረጨት ሥርዓትም ይካሄድ ነበር። ይህም የእግዚአብሔርን ቃል መስማት፥ የጌታን ሥራ መሥራትና፥ በእግዚአብሔር መንገድ መሄድ እንዳለባቸው የሚያሳይ ለመሆኑ አንዳችም ጥርጥር የለውም።

> 33ኛ ጥያቄ፡- ሀ) እግዚአብሔር ካህናትን በማንጻትና ለአገልግሎት በማዘጋጀት ይህን ያህል ጥንቃቄ ያደረገው ለምን ይመስልሃል? ለ) ስለ ቤተ ክርስቲያን አመራር ከዚህ የምንማረው ምን ይመስልሃል?

3. የጥጃ ምስል በማምለክ ሕዝቡ የሠሩት ኃጢአት

ስለ እስራኤል ሕዝብ ታሪክ የሚያስደንቅ ነገር፥ እግዚአብሔር ከሙሴ ጋር በተገናኘበት ተራራ ጫፍ ላይ እንኳ ቆመው፥ ከእግዚአብሔር ፊታቸውን መልሰው ኃጢአት መሥራታቸው ነበር። ወደ ተራራው በመመልከት የእግዚአብሔርን ሕልውና በደመናው ውስጥ ማየት ይችሉ ነበር። ኃያል የሆነውን እግዚአብሔር በመብረቅ፥ በነጎድጓድና በመሬት መንቀጥቀጥ ውስጥ ካዩና ሲናገራቸው ኃያል ድምፁን ከሰሙ ገና ጥቂት ጊዜ አልፎ ነበር። ይህም ቢሆን እንኳ ሙሴ እስኪመለስ ለ40 ቀናት መቆየት አልቻሉም። ሙሴ ሞቷል ብለው በመገመት እግዚአብሔርን ትተው፥ ጣዖትን ወደ ማምለክ ዞር አሉ። እግዚአብሔር ከግብፅ ምድር አውጥቶአቸው ነበር፤ ነገር ግን በግብፅ ምድር የነበረው የጣዖት አምልኮ ከልባቸው አልወጣም ነበር፤ ስለዚህ እግዚአብሔርን ትተው ከግብፅ ያወጣን አምላካችን ነው በማለት ከግብፅ አማልክት መካከል አንዱ የሆነውን ጥጃን ያመልኩ ጀመር (ዘጸ. 32፡4)።

እግዚአብሔር ይህንን ባየ ጊዜ የሰጠው ምላሽ ከባድ ነበር። እግዚአብሔር እስራኤላውያንን በሙሉ በማጥፋት በሙሴ በኩል አዲስ ሕዝብን ለማስነሣት ወሰነ። ሙሴ ግን እግዚአብሔር ሕዝቡን እንዳያጠፋ ለመነ። በዚህ ስፍራ ሙሴ ያለውን ነገር አስተውሎ መመልከት ጠቃሚ ነው (ዘጸ. 32፡11-14)። በመጀመሪያ፥ ለእግዚአብሔር ስምና ክብር የሰጠውን ትኩረት እንመለከታለን። እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ካጠፋ፥ የእግዚአብሔርን ኃይል የመሰከሩት ሕዝቦች ይህንን ተግባር በተሳሳተ መንገድ ይተረጉሙታል። የሙሴ ትኩረት እግዚአብሔር የሚገባውን ክብር በመቀበሉ ላይ ነበር። በሁለተኛ ደረጃ፥እግዚአብሔር በአብርሃም በይስሐቅና በእስራኤል በኩል ለራሱ ልዩ ሕዝብ እንደሚያስቀር ቃል የገባውን እንዲያስታውስ ይጠይቀዋል። እግዚአብሔር

ከእስራኤል ፍርዱን ይመልስ ዘንድ የሙሴን የአስታራቂነት አገልግሎት ተቀበለ።

34ኛ ጥያቄ፡ ሀ) ከዚህ ታሪክ ስለ እግዚአብሔር ባሕርይ የምንማረው ነገር ምንድን ነው? ለ) ከዚህ ክፍል ስለ ሙሴ ባሕርይ የምንማረውስ ነገር ምንድን ነው?

ነገር ግን ሙሴ የሕዝቡን ኃጢአት በተመለከተ ጊዜ፥ የወሰደውን እርምጃ መመልከት አስፈላጊ ነው። በመጀመሪያ፥ እግዚአብሔር በገዛ እጁ ቀርፆ ዓሥርቱን ትእዛዛት የጻፈበትን የድንጋይ ጽላት በቁጣ ሰባበረው። በሁለተኛ ደረጃ፥ ከወርቅ የተሠራውን የጥጃ ምስል ሰባብሮ ፈጨና በውኃ ተበጥብጦ ሕዝቡ እንዲጠጡት አደረገ። በሦስተኛ ደረጃ፥ ሕዝቡ ውሳኔ እንዲያደርጉ ጥሪ አደረገላቸው። ከጌታ ወገን የሆኑ በእርሱ በኩል እንዲሆኑ አደረገ። ሌዋውያን ወደ እርሱ ሲመጡ፥ የእግዚአብሔር የፍርዱ መሣሪያ እንደሆኑ ገልጾላቸው፥ ወንድሞቻቸው የሆኑትን እስራኤላውያን እንዲገድሉ አዘዘ። ሌዋውያኑም የሙሴን ትእዛዝ በመከተል በዚያን ቀን ብቻ ሦስት ሺህ እስራኤላውያንን ገደሉ።

35ኛ ጥያቄ፥ ሀ) ይህን ትእዛዝ ለመፈጸም አስቸጋሪ የሆነው ለምን ነበር? ለ) ይህ ነገር ስለ ኃጢአት አስቸጋሪነት (አስጨናቂነት) እና በጽኑ ሊፈረድበት እንደሚገባም ምን ያስተምረናል?

ሙሴ ወደ እግዚአብሔር ተመልሶ በመሄድ ለሕዝቡ መለመን ጀመረ። እንደገና የሙሴን የአመራር ብቃትና ታላቅነት እንመለከታለን። የተጨነቀው ለእግዚአብሔር፥ ለክብሩና ለቃል ኪዳኑ ላለው ታማኝነት ብቻ ሳይሆን፥ ለእግዚአብሔር ሕዝብም ነበር። ሙሴ ሕዝቡ በእግዚአብሔር ፊት የሠሩትን ታላቅ ክፋት አምኖ ተቀበለ። ከዚያም ከእግዚአብሔር ዘንድ ምሕረትን ለመነ። እግዚአብሔር ይቅር ሊላቸው ፈቃደኛ ካልሆነ፥ በሕዝቡ ፈንታ የራሱን የዘላለም ሕይወትን ሊሰጥ ዝግጁ መሆኑን ተናገረ። ከሕይወት መጽሐፍ ስሙን እንዲደመስስ እግዚአብሔርን ለመነ፤ (ዘጸ. 32፡32)።

ሙሴ በመሪነቱ ልዩና ታላቅ እንደነበር የሚያሳዩ ሌሎች ሁለት ታሪኮች አሉ። የመጀመሪያው፥ የመገናኛው ድንኳን ተሠርቶ ከመጠናቀቁ በፊት እንኳ ሙሴ ከሰፈር ውጪ ድንኳን ተክሎ እንደነበር የሚናገረው ታሪክ ነው። ይህ ድንኳን እስራኤላውያን የሚገናኙበት ነበር። ደግሞም

ሙሴ ከእግዚአብሔር ጋር የሚገናኝበት ስፍራ ነበር። ለእግዚአብሔር ቅርብ ከመሆኑ የተነሣ፥ የእግዚአብሔር ክብር ከፊቱ ያንጸባርቅ ነበርና ሕዝቡ ሊያዩት ባለመቻላቸው ሙሴ ፊቱን ይሸፍን ነበር። ሙሴ ከእግዚአብሔር ጋር ተገናኝቶ ሲያበቃ ድንኳኑን በሚለቅበት ጊዜ፥ ኢያሱ ግን እዚያው ይቆይ እንደነበር መመልከቱ ደስ የሚያሰኝ ነው፤ (ዘጸ. 33፡11)።

ሁለተኛው ነገር፥ ሙሴ የእግዚአብሔርን ሕዝብ ያለማቋረጥ መምራት ይችል ዘንድ የእግዚአብሔር መገኘት ሁልጊዜ ያስፈልገው እንደ ነበር መገንዘቡ ነው፤ ስለዚህ እንዳይተወው እግዚአብሔርን ለመነ። ክብሩንም እንዲያሳየው ለምኖታል። እግዚአብሔር በቸርነቱ ለዚህ ልመናው መልስ ሰጠውና በሙሴ ፊት ክብሩን አሳለፈ።

36ኛ ጥያቄ፥ ዘጸ. 32-33 እንደገና አንብብ። ሀ) በእነዚህ ምዕራፎች ውስጥ ሙሴ እግዚአብሔርን የሚፈራ ታላቅ መሪ መሆኑን የሚያሳዩትን ነገሮች ዘርዝር። ለ) እነዚህን እውነቶች ዛሬ በቤተ ክርስቲያን አመራር ውስጥ እንዴት ተግባራዊ ልናደርጋቸው እንችላለን?

በኦሪት ዘጸአት ውስጥ የሚገኙ ዋና ዋና ትምህርቶች፡-

1. እግዚአብሔር፡- የመጽሐፍ ቅዱስ ዋና ዓላማ ለሕዝቡ ያለውን የእግዚአብሔር ባሕርይና ሥራ መግለጥ ነው፤ ስለዚህ በዘጸአት ውስጥ ስለ እግዚአብሔር የምናያቸው በርካታ እውነቶች አሉ።

37ኛ ጥያቄ፥ ዘጸ. 3፡13-15 አንብብ። እግዚአብሔር በሚቃጠለው ቁጥቋጦ ውስጥ ራሱን በገለጸ ጊዜ ለሙሴ የተሰጠው ስም ማን ነበር?

ሀ. ያህዌ የእግዚአብሔር ልዩ ስሙ ነው፡- በኦሪት ዘፍጥረት ውስጥ በእግዚአብሔር የተሰጡ የተለያዩ ስሞችን ተመልክተናል። በጣም በብዛት ያየናቸው ግን ኤሎሄምና አዶናይ የሚሉትን ስሞች ነበር። እንደምታስታውሰው፥ የእግዚአብሔር «ስም» በዕብራውያን ባሕል የእግዚአብሔር ባሕርይ የሚገልጥ ነው። በኦሪት ዘጸአት እግዚአብሔር ሙሴን በተገናኘው ጊዜ ልዩ የሆነ ባሕርይውን ለሙሴ የሚገልጥበትን ያህዌ ያለውን የራሱን አዲስ ስም ሰጠው። ይህ ስም «እኔ፥ እኔ ነኝ» የሚል ነበር። በዕብራይስጥ ይህ ሐረግ «ጂሆቫ» ወይም «ያህዌ» የሚል ነው። በኋላ አይሁድ ይህ ስም ከሁሉም በላይ የተቀደሰው የእግዚአብሔር ስም ነበር ብለዋል።

የእግዚአብሔር ስም ጀሆቫ ወይም ያህዌ የተባለው ለምንድን ነው? የዕብራይስጥ ቋንቋ የሚጻፈው ምንም አናባቢ በሌለው ፊደላት ብቻ ነበር። ስለዚህ ይህ ስም በዕብራይስጡ ያለ አናባቢ ሲጻፍ ይሆናል። አይሁድ በምርኮ ወደ ባቢሎን ከተወሰዱና ከምርኮም ከተመለሱ በኋላ ይህን ይህውህ በሚለው የእግዚአብሔር ስም መጠቀም አቆሙ። ምክንያቱም ይህ ስም ለማንበብ በጣም የተቀደሰ ነው ብለው ስላመኑ ነበር። ስለዚህ እንደ ኤሎሂምና አዶናይ ያሉትን ሌሎች ስሞች ወይም ደግሞ «ቅዱሱ» ወይም የመሳሰሉትን ስሞች ብቻ መጠቀም ቀጠሉ። ከክርስቶስ ልደት በኋላ በ6ኛው መቶ ክፍለ ዘመን አይሁድ የአጻጻፍ ስልታቸውን ለወጡና ሰዎች ዕብራይስጥን ለማንበብ ማስታወስ ይችሉ ዘንድ አናባቢዎችን ማከል ጀመሩ፤ ስለዚህ ወደ ይህውህ ሲደርሱ፥ አዶናይ የሚለውን ስም ያስገኙትን አናባቢዎች እዚህም ላይ አከሉበት። (እነርሱም በላቲን ፊደል አ፡አ፡አ የሚሉት ሲሆኑ በሚጻፍበት ጊዜ ያህዌ የሚል ሆነ።) ይህንን ያደረጉበት ዋና ምክንያት ሰዎች ይህውህ ብለው ከማንበብ ይልቅ፥ አዶናይ እንዲሉ ነበር። በ1520 ዓ.ም. አካባቢ ግን ይህ የእግዚአብሔር ስም በትክክል ሥርዓት እንዲይዝ ተደረገና ጀሆቫ (ያህዌ) ተባለ። ይህንን ስም በቀላሉ የምታስታውሰው፥ የይሖዋ ምስክሮች ተብሎ የሚጠራ የሐሰት ትምህርትን የሚከተሉ ክፍል በመኖሩ ነው። የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁራን ግን እግዚአብሔር ለሙሴ የሰጠው የመጀመሪያው ስም መነበብ ያለበት ያህዌ ወይም ጃሄዌ ተብሎ እንጂ ጀሆቫ (ይሖዋ) ተብሎ አይደለም ብለው ያምናሉ።

ይህውህ የሚለው ቃል በዕብራይስጥ «እኔ ነኝ»፥ ወይም «እርሱ ነው»፥ ወይም «እርሱ ይሆናል» የሚል ትርጉም ከሚሰጠው ግሥ ጋር አንድ ዓይነት ነው። ይህም እስራኤላውያን ስለ እርሱ ባሕርይ እንዲያስታውሱ እግዚአብሔር የፈለገው ልዩ ስም ነው። እግዚአብሔር ከእስራኤላውያን ጋር የገባውን ቃል ኪዳን ለእነርሱ ለመግለጥ የተጠቀመበት የቃል ኪዳን ስም ነው። ይህ ስም ኢየሱስ በምድር ላይ በነበረበት ጊዜ «እኔ ነኝ» እያለ የተናገራቸው ዐረፍተ ነገሮች ሁሉ የተመሠረቱበት ስም ነው። ለምሳሌ፡- «እኔ የሕይወት እንጀራ ነኝ»፤ «እኔ የሕይወት ውኃ ነኝ»፤ «እኔ ትንሣኤና ሕይወት ነኝ» ወዘተ. እያለ በዮሐንስ ወንጌል የሰጣቸው መግለጫዎች ማለት ነው።

እግዚአብሔር ይህንን ስም በርካታ መንፈሳዊ እውነቶችን ለመግለጥ የተጠቀመበት ይመስላል። በመጀመሪያ፥ ዘላለማዊ የሆነውን የእግዚአብሔርን ባሕርይ በመግለጥ፥ እርሱ መጀመሪያና መጨረሻ እንደሌለው ያሳየናል። እርሱ ምንጊዜም ነበር። እግዚአብሔር ለሙሴ ሊያሳየው የፈለገው ነገር እርሱ ከዓለም መፈጠር መጀመሪያ የነበረው፥ ደግሞም ከእስራኤል ሕዝብ አባቶች ጋር ዘላለማዊ ቃል ኪዳን ያደረገው አምላክ መሆኑን ነው። በሁለተኛ ደረጃ፥ ደግሞ ይህ ስም እግዚአብሔር ራሱ የሕይወት ኃይል እንዳለውና ስለ ሕያውነቱ በማንም ወይም በምንም ነገር ላይ ያለመደገፉን ያሳያል። በሦስተኛ ደረጃ፥ ደግሞ እግዚአብሔር የማይታወቅ አምላክ እንዳልሆነ፥ የሩቅ አምላክም እንዳልሆነ ይልቁንም ለሚወዱትና በእርሱ ለሚያምኑ ቅርብ መሆኑን ያስተምረናል። አራተኛ፥ ይህ ስም እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ የሆነ፥ ብቃት ያለው በመሆኑ ሕዝቡ በምንም ሁኔታ ውስጥ ይሁኑ የሚያስፈልጋቸውን ነገር ሁሉ የሚያደርግ መሆኑን ያሳያል።

| |
|---|
| 38ኛ ጥያቄ፥ ሀ) እግዚአብሔር ለሙሴ ይህንን ስም መግለጥ ያስፈለገው ለምን ይመስልሃል? ለ) የዚህን ስም ትርጉም ማወቅ ለእኛ ጠቃሚ የሆነው ለምንድን ነው? ሐ) የእግዚአብሔርን ስምና ባሕርይ ማወቅ ዛሬ እኛን እንዴት ያበረታታናል? |

ለ. እግዚአብሔር ራሱን ለሰዎች የገለጠባቸው የተለያዩ መንገዶች:-
በኦሪት ዘጸአት ውስጥ የምናገኘው አንድ አስደናቂ እውቀት እግዚአብሔር ራሱን ለእስራኤል ሕዝብ የገለጠባቸው በርካታ መንገዶች ናቸው። እግዚአብሔር በአንድ መንገድ ብቻ ለመሥራት ራሱን አልወሰነም። ራሱን ለመግለጥ የተጠቀመው በተጻፈ ቃል፥ በፍጥረት፥ በሕልም ወዘተ. ብቻ አይደለም። በታሪክ ውስጥ ራሱን ለሕዝቡ የገለጠባቸው በርካታ የተለያዩ መንገዶች አሉ። ኦሪት ዘጸአትን በምታነብበት ጊዜ እግዚአብሔር ራሱን የገለጠባቸውን የሚከተሉትን መንገዶች አስተውል:-

1. «በጌታ መልአክ» በኩል (ዘጸ. 3:2፤ 14:19) ከኦሪት ዘፍጥረት ጥናታችን ውስጥ እንደምታስታውሰው፥ ይህ መልአክ እግዚአብሔር ተብሎ የተጠራ ልዩ መልአክ ነው። ይህ መልአክ በቤተልሔም ከመወለዱ በፊት የነበረው ኢየሱስ ክርስቶስ ሳይሆን አይቀርም።

2. በሌሎች መላእክት (ዘጸ. 23:20፤ 33:2)

3. በተአምራት (ዘጸ. 8፡16-19)

4. በሚቃጠል ቁጥቋጦ (ዘጸ. 3፡2)

5. በእሳት፥ በጢስና፥ በመብረቅ (ዘጸ. 19፡18-20)

6. በሚሰማ ድምፅ (ዘጸ. 24፡1)

7. በደመና ክብር (ዘጸ. 16፡10)

8. በደመናና በእሳት ዓምድ (ዘጸ. 40፡34-38)

9. ከሙሴ ጋር ፊት ለፊት በመገናኘት (ዘጸ. 33፡11)

| |
|---|
| 39ኛ ጥያቄ፦ሀ) ዛሬ እግዚአብሔር ራሱን ለእኛ የሚገልጥባቸው የተለመዱ መንገዶች የትኞቹ ናቸው? ለ)እግዚአብሔር ራሱንና ፈቃዱን አልፎ አልፎ ባልተለመዱ መንገዶችስ የሚገልጥባቸው የትኞቹ ናቸው? |

ሐ. በኦሪት ዘጸአት ውስጥ ስለ እግዚአብሔር የተገለጡ ሰባት እውነቶች፡-

1. እግዚአብሔር የሰጠውን ተስፋ ሁልጊዜ ይጠብቃል፤ ተስፋ የሰጠውን የቃል ኪዳን ግዴታም ይፈጽማል (ዘጸ. 2፡24)።

2. እግዚአብሔር በክፉዎች ላይ ይፈርዳል፤ ሕዝቡንም ከመከራቸውና ከችግራቸው ያድናቸዋል (ዘጸ. 12፡27)።

3. እግዚአብሔር ከሁሉም ነገር የሚበልጥና የበላይ ነው፤ ነገር ግን ለሚወዳቸው ደግሞ ቅርብ ነው (ዘጸ. 19፡10-15፥ 13-18)።

4. እግዚአብሔር ለመረጠው ለራሱ ሕዝብ ጥቅም ሲል አሕዛብን ሁሉ የሚገዛና የሚቆጣጠር ነው (ዘጸ. 15፡4-6፤ 13-18)።

5. እግዚአብሔር ቅዱስ ነው። ቅዱስ የሚለው ስም መሠረታዊ ትርጉም «መለየት» ማለት ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ቅዱስ የሚለው ቃል ሁለት የተሰወሩ ትርጉሞች አሉት። በመጀመሪያ፥ መለየት ወይም ልዩ ማለት ነው። እንደ እግዚአብሔር ያለ ማንም የለም። ከእግዚአብሔር ጋር የሚወዳደር ወይም እርሱን የሚመስለው ማንም የለም። አቻ፥ አምሳያ የለውም። እጅግ ከፍ ያለና ሕልውና ካላቸው ነገሮች ሁሉ በላይ ነው (ዘጸ. 15፡11፤ 18፡10-12)። በሁለተኛ

ደረጃ ደግሞ፥ ከኃጢአት የተለየ ማለት ነው። እግዚአብሔር በኃጢአት የተበላሸ አይደለም። በአጠገቡ ኃጢአት እንዲኖር አይፈልግም። ጻድቅ ከሆነው ባሕርይ ጋር የሚቃረን፥ ኃጢአት የሆነ ማንኛውንም ነገር ሊያደርግ ወይም ሊያስብ ጨርሶ አይችልም።

6. እግዚአብሔር ለሕዝቡ ጸጋንና ምሕረትን የተሞላ ነው። ቅጣት በሚገባቸው ሰዓት እንኳ በንስሐ ሲመለሱ ይቅር ይላቸዋል። ቅጣት በሚገባቸው ጊዜ እንኳ ለጸሎታቸው መልስን ይሰጣል (ዘጸ. 32፡11-14)።

7. እግዚአብሔር ሕዝቡን የሚያድን አምላክ ነው። እርሱ ከእስራት ይቤዣቸዋል፤ ከባርነት ይታደጋቸዋል፤ እንዲያገለግሉት፥ እንዲያመልኩትና እንዲታዘዙት ነፃ ያወጣቸዋል።

| |
|---|
| 40ኛ ጥያቄ፥ ሀ) ስለ እግዚአብሔር እነዚህን እውነቶች ማስታወስ ያለብን ለምንድን ነው? ለ) እነዚህ እውነቶች ዛሬ ለክርስቲያኖች መጽናኛ የሚሆኑት እንዴት ነው? |

2. እግዚአብሔር ሕዝቡን የሚመሩ ልዩ መሪዎችን ይመርጣል። እነዚህ መሪዎች ልዩ የሆኑት በችሎታቸው ሳይሆን እግዚአብሔር ስለመረጣቸው ነው። ሙሴን የእስራኤል ሕዝብ መሪ አድርጎ እግዚአብሔር የመረጠው ገና ከመወለዱ አስቀድሞ ነው። ሆኖም ግን እግዚአብሔር ሙሴን የተጠቀመበት በመንፈሳዊ አንፃር ሕዝቡን ለመምራት ዝግጁ በሆነበት ጊዜ ነው። በኦሪት ዘጸአት ስለ መሪነት የምናያቸውን የሚከተሉትን ነገሮች ልብ በል:-

ሀ. መሪዎችን የሚመርጥ እግዚአብሔር እንጂ ሰዎች አይደሉም። ምርጫውም የሚሆነው በሰውዬው ግላዊ ፍላጎት አይደለም።

ለ. እግዚአብሔር ምድራዊ የሆነ የኃይልና የአመራር እውቀት አይማርከውም። ይልቁንም መሪነትን የሚመለከት የዚህ ዓለም አስተሳሰብ (ለምሳሌ:- ትምህርት፥ ሥልጣን፥ ከአባቶች የተወረሰ ማዕረግ) እግዚአብሔር ከሚፈልገው ዓይነት አመራር ጋር በተቃራኒ የሚሄዱ ናቸው። ሙሴ በግብፅ ጥበብ ሁሉ ተኮትኩቶ አድጎ ነበር፤ ስለዚህ እስራኤልን የመምራት መብት እንዳለውና በራሱ ብርታት እስራኤልን ለመምራት እንደሚችል አሰበ። ይህ ግን አልሠራም። እግዚአብሔር ብዙ ጊዜ በአንድ መሪ

ከመገልገሉ በፊት፥ አስቀድሞ ያንን ሰው ዝቅ ያደርገዋል። እግዚአብሔር ይህንን የሚያደርገው፥ መሪው በእግዚአብሔር ብርታት እንጂ በራሱ መደገፍ እንደሌለበት እንዲማር ነው። በዚህ መንገድ ሰውዬው ክብር ከመውሰድ ፈንታ፥ እግዚአብሔር ክብሩን ለራሱ ይወስዳል። ሙሴ የእግዚአብሔር መገልገያ ለመሆን ከመዘጋጀቱ አስቀድሞ በምድረ በዳ በበግ እረኝነት ዓመታትን አሳልፏል።

ሐ. እግዚአብሔር ከየትኛውም የመሪ ባሕርይ ይልቅ ትሕትናንና በእርሱ ላይ ያለውን መደገፍ ያከብራል። እግዚአብሔር ሙሴን በራሱ ለመናገርም ሆነ ሕዝቡን ለመምራት እንደማይችል ዋስትና እስኪያጣ ድረስ ትሑት አደረገው።

መ. የእግዚአብሔር ሕዝብ መሪዎች ራሳቸውን ሳይሆን ሕዝቡን ማገልገል ይኖርባቸዋል። ሙሴ መሪነትን የተማረው «በጎችን» በማገልገል ነበር። ከዚያ በኋላ ብቻ ነበር ከእግዚአብሔር የሆኑ መሪዎች የሚመሩት በኃይልና በሥልጣን ሳይሆን በማገልገል ላይ የሚሆነው (ማር. 10፡45 ተመልከት)።

ሠ. ከእግዚአብሔር የሆኑ መሪዎች የሕዝቡን ጥቅም ከራሳቸው ጥቅም ያስቀድማሉ። እስራኤላውያን ኃጢአት በሠሩ ጊዜ እግዚአብሔር ሊያጠፋቸው ፈለገ፤ ሙሴ ግን እነርሱ ከሚጠፉ ይልቅ ራሱ እንዲጠፋና እነዚያ በሕይወት እንዲኖሩ ማለደ (ዘጸ. 32፡12)።

ረ. የእግዚአብሔር መሪዎች ሸክም የሆነባቸው ስለ ራሳቸው ክብርና ደህንነት እምብዛም ሳይጨነቁ ስለ እግዚአብሔር ክብርና ስለ ስሙ ክብር ነበር። እስራኤላውያን ኃጢአት ባደረጉና እግዚአብሔር ሊያጠፋቸው በተነሣ ጊዜ፥ ሙሴ ስለ እግዚአብሔር ስም ገዶትና ይህ ስም በአሕዛብ መካከል ሊኖረው ስለሚችለው ምስክርነት ተጨንቆ ጸለየ (ዘጸ. 32፡12)።

ሰ. ከእግዚአብሔር የሆኑ መሪዎች የመሪነትን ሸክም ከሌሎች ጋር ይካፈላሉ። ሙሴ የእግዚአብሔርን ሕዝብ የሚመራው እርሱ ብቻ እንዳልሆነ መማር ነበረበት። ኃላፊነቱን በሥራው ሊረዱት ከሚችሉ ሰባ ሽማግሌዎች ጋር መካፈል ነበረበት (ዘጸ. 18)።

ሸ. ከእግዚአብሔር የሆኑ መሪዎች በጸሎትና በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ከእግዚአብሔር ጋር የጠበቀ ግንኙነት ይኖራቸዋል። የእግዚአብሔርን ቃል በቅጽበት ይሰማሉ፤ ሙሉ በሙሉም ይታዘዛሉ። በኦሪት ዘጸአት ውስጥ፥ ሙሴ ከእግዚአብሔር ጋር ፊት ለፊት ሳይቀር በተደጋጋሚ ይገናኝ እንደነበር እናነባለን። በሙሴና በአመራሩ ውስጥ የምናየው የኃይል ምንጭ ይህ ነበር (ዘጸ. 33፡7)።

እነዚህ ከኦሪት ዘጸአት ውስጥ ስለመሪነት ከምናገኛቸው በርካታ መመሪያዎች ጥቂቶቹ ናቸው። የቤተ ክርስቲያን መሪ ከሆንክ ኦሪት ዘጸአትን በሙሉ በጥንቃቄ በማንበብ እግዚአብሔር ሙሴን ለመሪነት እንዴት እንዳዘጋጀውና እርሱም የተዋጣለት የእግዚአብሔር ሕዝብ መሪ እንዴት እንደሆነ መመልከት ጠቃሚ ነው።

41ኛ ጥያቄ፥ ሀ) ከላይ የጠቀስናቸው የመሪነት መመሪያዎች ዛሬም ላሉ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በጣም ጠቃሚ የሆኑት ለምንድን ነው? ለ) ከእነዚህ መመሪያዎች መካከል ብዙ ጊዜ ለቤተ ክርስቲያን ያልተጠቀሱትና ያልተገለጹት የትኞቹ ናቸው? ለምን? ሐ) ከእነዚህ መመሪያዎች መካከል ብዙ ጊዜ በቤተ ክርስቲያን ሥራ ላይ ያልዋሉትስ የትኞቹ ናቸው? ለምን? መ) ከምታውቃቸው የቤተ ክርስቲያን መሪዎች መካከል ከሁሉ ይሻላል የምትለውን ሰው አስብ። በአመራሩ ከእነዚህ መመሪያዎች ውስጥ በምን ያህሉ ይጠቀማል?

3. የእግዚአብሔር ሕዝብ ባሕርይ፡- በተለይ በኦሪት ዘጸአት ውስጥ ከምናገኘው የእስራኤል ሕዝብ ታሪክ፥ ዛሬም ያለው የእግዚአብሔር ሕዝብ ባሕሪያዊ ዝንባሌ ምን እንደሆነ ለማየት እንችላለን። የእስራኤልን ሕዝብ እግዚአብሔር ያዳናቸው እጅግ በሚያስደንቅ መንገድ ነበር። የእግዚአብሔርን ኃይል ሲያድናቸው አይተዋል። ከግብፃውያን እጅ በታደጋቸው ጊዜ እግዚአብሔርን በማምለክ ሐሴት አድርገዋል። ለእግዚአብሔር መገናኛ ድንኳን መሥሪያ የሚያስፈልገውን ነገር እንዲሰጡ በጠየቃቸው ጊዜ፥ ሙሴ በቃ አቁሙ እስኪል ድረስ በከፍተኛ ልግሥና ሰጥተዋል (ዘጸ. 35፡20-29፤ 36፡3-7)፤ ዳሩ ግን ልክ እንደ እኛ እስራኤላውያን ብዙ ጊዜ በኃጢአት ይወድቁ ነበር። በእግዚአብሔርና በመሪዎቹ ላይ ያጉረመርሙና ያማርሩ ነበር (ዘጸ. 16፡2-3)። እምነታቸው በጣም

ደካማ ስለነበር፥ ነገሮች በማይስተካከሉበት ጊዜ ከእግዚአብሔር ፊታቸውን ይመልሱ ወይም እግዚአብሔርን ይጠራጠሩ ነበር። የእግዚአብሔርን ክብር ያዩ ቢሆንም፥ ወደ ኃጢአት ያዘነበሉ ነበሩ። ከእግዚአብሔር ዞር ብለው ጣዖትን ያመልኩና ያመነዝሩ ነበር (ዘጸ. 32)። የተሻለ ሕይወት ይሰጠናል ብለው የሚያስቡት ዓለም ባርነት ቢሆንም እንኳ ያለማቋረጥ ወደዚያ ለመመለስ ይፈልጉ ነበር። ልክ በአብርሃም ውስጥ የኃጢአት ባሕርይ እንደታየ ሁሉ ያው ባሕርይ ወደ ልጆቹ ሁሉ ተላለፈ።

| |
|---|
| 42ኛ ጥያቄ፥ ሀ) ይህ የኃጢአት ዝንባሌ ዛሬ በቤተ ክርስቲያን የሚታየው እንዴት ነው? ለ) የእግዚአብሔር ሰዎች እንደዚህ የሆኑት ለምን ይመስልሃል? ሐ) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እንደመሆናችሁ መጠን አባሎቻችሁ ኃጢአትን ድል አድርገው ይኖሩ ዘንድ ልታደርጉ የምትችሉት ነገር ምንድን ነው? |

4. በአራት ዘጸአት ውስጥ ወደ ክርስቶስ የሚያመለክቱ በርካታ ነገሮች አሉ።

ሀ. ሙሴ የእስራኤልን ሕዝብ ከባርነት ነፃ ያወጣ በመሆኑ፥ ከኃጢአት ባርነት ነፃ አውጥቶ የሚመራን የክርስቶስ ምሳሌ ነው (ሮሜ 6፡6፥17-18)።

ለ. የፋሲካ በዓል የእግዚአብሔር ሕዝብ ከግብፅ ባርነት ነፃ የወጡበት በዓል እንደሆነ ሁሉ፥ ክርስቶስም ከኃጢአት ባርነት ነፃ ስላደረገን ፋሲካችን እርሱ ነው። ሞትን እንዳንሞት ደሙን ያፈሰሰልን የፋሲካ በግ ነው (1ኛ ቆሮ. 5፡7)።

ሐ. የሕዝቡን የሥጋዊ ምግብ ፍላጎት ለማርካት እግዚአብሔር በምድረ በዳ መናን እንደሰጣቸው፥ ክርስቶስም የሰዎችን መንፈሳዊ መሻት ሁሉ የሚያሟላ የሕይወት እንጀራ ነው (ዮሐ. 6፡35፥ 48)።

መ. እግዚአብሔር ከዓለት ውስጥ ለሕዝቡ ውኃን እንደሰጠ፥ ኢየሱስ የሕይወት ውኃ ነው። ውኃ የሚሰጥ ዓለት ነው (1ኛ ቆሮ. 10፡2-4)።

ሠ. የመገናኛው ድንኳንና የአምልኮ ሥርዓቱ በርካታ የክርስቶስ ተምሳሌቶችን ያመለክታሉ። በመገናኛው ድንኳን ውስጥ ስለሚገኙ የተለያዩ የክርስቶስ ተምሳሌቶች ዝርዝር ከዛሬው ትምህርት ተመልከት።

5ኛ ቀን፡- የዚህን ሳምንት ትምህርት ከልስና ለሳምንታዊው ስብሰባ ዝግጅት ይረዳህ ዘንድ የውይይት ጥያቄዎችን ተመልከት።

ሳምንታዊ ስብሰባ

1. የሳምንቱ የአምልኮ ጊዜ
2. የጸሎት ጊዜ
3. የትምህርቱ ክለሳ
4. ውይይት

1. ሀ) የእስራኤላውያንን መንፈሳዊ ጉዞ ግለጽ። የመንፈሳዊ ብርታታቸው ጊዜያት መቼ ነበሩ? የመንፈሳዊ ድካማቸው ጊዜያትስ መቼ ነበሩ? ለ) የእስራኤላውያን ጉዞ ከክርስቲያን መንፈሳዊ ጉዞ ጋር የሚመሳሰለው እንዴት ነው? ሐ) እስራኤላውያን በምድረ በዳ ከመንከራተታቸው አንፃር እግዚአብሔርን ደስ በሚያሰኝ መንገድ ስለመመላለስ የምንማረው ነገር ምንድን ነው?

2. ዘጸ. 19፡3-6 አንብብ። ሀ) በእነዚህ ጥቅሶች የሚገኙትንና ስለ እስራኤል ሕዝብና እንዲሁም ዓላማቸው የተጠቀሱትን የተለያዩ ነገሮች ዘርዝር። ለ) 1ኛ ጴጥ. 2፡4-5 አንብብ። የቤተ ክርስቲያን ዓላማ ምንድን ነው? ሐ) የእስራኤልና የቤተ ክርስቲያን ዓላማ ተመሳሳይነት እንዴት ነው? መ) እንደ ቤተ ክርስቲያን እግዚአብሔር ከእኛ ስለሚፈልገው ነገር ከእነዚህ ቁጥሮች የምንማረው ምንድን ነው?

3. ሀ) እግዚአብሔር ራሱን በሲና ተራራ ከገለጠበት መንገድ፥ ስለ ባሕርይው የምንማረው ነገር ምንድን ነው? ለ) እግዚአብሔር በሲና ተራራ በሰጠው ቃል ኪዳን ሕዝቡን ከራሱ ጋር ስለሚያዛምድበት ሁኔታ የምንማረው ምንድን ነው?

4. ማቴ. 22፡35-40፤ዘጸ. 20፡1-17 አንብብ። ሀ) ኢየሱስ ስለ ሁለቱ ታላላቅ ትእዛዛት የሰጠው ትምህርት አሥርቱን ትእዛዛት የሚያጠቃልለው እንዴት ነው? ለ) አሥርቱን ትእዛዛት ዘርዝር። እነዚህን ትእዛዛት ክርስቲያኖች ሊያፈርሱ ስለሚችሉበት መንገድ ለእያንዳንዳቸው ምሳሌ ስጥ። ሐ) እነዚህ ትእዛዛት ይጠበቁ ዘንድ ቤተ ክርስቲያንህ ምእመናንን ለማበረታታት ምን ማድረግ ትችላለች? መ) ኢየሱስ ከሰጣቸው ከሁለቱ ታላላቅ ትእዛዛት ይልቅ ብዙ ጊዜ በሌሎቹ ሕጎች ላይ የምናተኩረው እንዴት ነው? ለምንስ ይህን እናደርጋለን?

5. ሀ) ከመገናኛው ድንኳን ስለ እግዚአብሔር፥ ስለ ሰውና እግዚአብሔርን ስለ ማምለክ ምን እንማራለን? ለ) ስለ ካህናት ከተሰጠው ትምህርት ስለ ቤተ ክርስቲያን አመራር ምን እንማራለን? ሐ) ሙሴ የእስራኤልን ሕዝብ ከመራበት መንገድ በተለይ ከዘጸ. 32-33 ስለ አመራር ምን እንማራለን? መ) ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ ከሚያመለክቱ ምሳሌዎች ስለ እርሱ ምን እንማራለን?

5. ጸሎት

# ትምህርት 8

## 1ኛ ቀን የኦሪት ዘሌዋውያን መግቢያ

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ልንረዳቸው በጣም አስፈላጊ ከሆኑት አሳቦች አንዱ «የቅድስና» አሳብ ነው። ይህም የእግዚአብሔር ባሕርይ መሠረት ነው። እግዚአብሔር በኦሪት ዘሌዋውያን ውስጥ ቅዱስ እንደሆነ በመደጋገም ይናገራል። የእግዚአብሔር ሕዝቦች ማንነትና እግዚአብሔር ሕዝቦቹን ሊሆኑ የሚገባቸውን የሚያስረዳ መሠረታዊ አሳብ የቅድስና አሳብ ነው። የእግዚአብሔር ሕዝብ እንደ መሆናችን መጠን እግዚአብሔርን መምሰል አለብን። ዘሌዋ. 11፡44፡- «እኔ እግዚአብሔር አምላካችሁ ነኝና፤ ሰውነታችሁን ቀድሱ፥ ቅዱሳንም ሁኑ» ይላል።

| |
|---|
| 1ኛ ጥያቄ፥ «ቅዱስ» እና «መቀደስ» የሚሉትን ቃላት ከመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት እይ። የእነዚህን ቃላት ትርጉም ጻፍ። ሀ) እግዚአብሔር ቅዱስ የሆነው በምን መንገድ ነው? ለ) የእግዚአብሔር ሕዝብ ቅዱስ መሆን ያለብን በምን መንገድ ነው? ሐ) ቤተ ክርስቲያንህ ቅድስት ነችን? ግለጽ። መ) ብዙ አብያተ ክርስቲያናት እንዲሁም ክርስቲያኖች ለመቀደስ ያለባቸው ችግር ምንድን ነው? ሠ) ዘሌዋ. 11፡44ን በቃልህ አጥና። |

ኦሪት ዘሌዋውያን ስለ ቅድስና የሚናገር መጽሐፍ ነው። ይህ መጽሐፍ ለመረዳትና ለመተርጎም በጣም አስቸጋሪ ቢሆንም፥ በእግዚአብሔር ቅድስና ላይ የሚያተኩር በመሆኑና መመለክም ያለበት በቅዱሳን ሰዎች መሆኑን ከተገነዘብን፥ የኦሪት ዘሌዋውያንን መልእክት የበለጠ እንረዳለን።

## የኦሪት ዘሌዋውያን ርእስ

እንደሌሎቹ የፔንታቱክ መጻሕፍት ርእሶች ሁሉ የኦሪት ዘሌዋውያን - የአማርኛው ርእስም የተገኘው በግሪክ ከተጻፈው የብሉይ ኪዳን ትርጉም ከሴፕቱዋጀንት ነው። «ዘሌዋውያን» ማለት «የሌዋውያን ጉዳይ» ወይም «ስለ ሌዋውያን የተነገረ» ማለት ነው። ከጥናታችን እንደምናስታውሰው ሌዋውያን ከእስራኤል ነገዶች አንዱ ነበሩ። ዋናው ኃላፊነታቸው በብሉይ ኪዳን ዘመን ሁሉ በቤተ መቅደስ ውስጥ

እግዚአብሔርን ማገልገል ነበር። ከእነዚህ ተግባራት አብዛኞዎቹ የሌዋውያን አካል የሆኑት የአሮን ቤተሰቦች ቢሆኑም ሁሉም ሌዋውያን በቤተ መቅደስ ሥራ ውስጥ የማገልገልና የመርዳት ኃላፊነት ነበረባቸው፤ ስለዚህ ይህ ስም የሚያመለክተው፥ የዚህ መጽሐፍ አብዛኛው ክፍል የእግዚአብሔር ሕዝብ አምልኮ እንዴት እንደሚመሩ ለካህናት ትእዛዝንና መመሪያን ለመስጠት ትኩረት የሚያደርግ እንደሆነ ነው። ኦሪት ዘሌዋውያን የሚያተኩረው በአምልኮ ሕግጋትና ደንቦች ላይ ነው።

አይሁድ ለፔንታቱክ ሦስተኛ መጽሐፍ የሰጡት ስም የተለየ ነው። እንደልማዳቸው የመጽሐፉን ርእስ «እርሱም ጠራ» በማለት ሰይመውታል (ዘሌ. 1፡1)።

## የኦሪት ዘሌዋውያን ጸሐፊ

በኦሪት ዘፍጥረትና በዘጸአት ጥናታችን እንደተመለከትነው፥ ምሁራን የፔንታቱክ ጸሐፊ ማን እንደሆነና የተጻፈበት ጊዜ መቼ እንደሆነ የተለያዩ አሳብ በመስጠት ይከራከራሉ። ስለዚህ በትምህርት ሦስት ስለ ፔንታቱክ ጸሐፊ የተሰጠውን ገለጻ ተመልከት። የኦሪት ዘሌዋውያን ጸሐፊ ሙሴ እንደሆነ መጽሐፉ ባይናገርም፥ ከ25 ጊዜ በላይ «እግዚአብሔር ሙሴን እንዲህ ሲል ተናገረው» የሚል ቃል አለ። ስለዚህ ጸሐፊው ሥጋ ለባሹ ሙሴ እንደሆነ መገመቱ ትክክል ነው።

## ኦሪት ዘሌዋውያን የተጻፈበት ጊዜ

ኦሪት ዘሌዋውያን የተጻፈበት ጊዜ፥ ሕዝቡ ከግብፅ የወጡበትን ጊዜ አርቀው በሚገምቱ (1440 ዓ.ዓ.) እና አቅርበው በሚገምቱ- (1220 ዓ.ዓ.) መካከል ይለያያል። ሆኖም ከሁለቱ ጊዜያት 1440 ዓ.ዓ. ትክክል ይመስላል።

በኦሪት ዘሌዋውያን መጽሐፍ ውስጥ የተጠቀሱት ነገሮች ሁሉ የተፈጸሙት በሲና ተራራ ነው። ስለዚህ ሙሴ እስራኤላውያን በሲና ተራራ በነበሩበት ጊዜ ሕግጋትን በሙሉ ተቀብሎአል ብሎ መገመቱ ትክክል ነው። የጻፋቸውም በዚያው ጊዜ ሳይሆን አይቀርም።

## የኦሪት ዘሌዋውያን አስተዋጽኦ

ኦሪት ዘሌዋውያን በሁለት ዋና ዋና ክፍሎች ይከፈላል።

1. የተቀደሰውን አምላክ እንዴት ማምለክ እንደሚቻል (ዘሌ. 1-10)፡- በዚህ ክፍል እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን፥ ምን ዓይነት መሥዋዕት፥ በምን ምክንያት ማቅረብ እንዳለባቸው ይነግራቸዋል። በተጨማሪ እግዚአብሔርን ለማምለክ ብቁ ይሆኑ ዘንድ ቄሶች እንዴት እንደሚለዩም ተጽፏል።

2. በእግዚአብሔር ፊት እንዴት ቅዱስ ሕዝብ ሆኖ መኖር እንደሚቻልና የእግዚአብሔርን በረከት እንዴት መቀብል እንደሚቻል (ዘሌ. 11-27)፡- በዚህ ክፍል እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን የተለያዩ ትእዛዛትን ይሰጣል። እነዚህም ትእዛዛት የእግዚአብሔር እንደመሆናቸው መጠን በእግዚአብሔር ፊት በቅድስና እንዴት መኖር እንደሚችሉ ይገልጹላቸዋል።

| |
|---|
| 2ኛ ጥያቄ፥ እነዚህ ሁለት ዓበይት ነጥቦች በዚህ ዘመን ላሉ ክርስቲያኖች የሚያስፈልጉት እንዴት ነው? ከዚህ በታች የኦሪት ዘሌዋውያን ዝርዝር አስተዋጽኦ ተሰጥቶአል?- |

1. በመሥዋዕቶች አማካይነት የተቀደሰውን አምላክ ማምለክ (ዘሌ. 1-7)፡-

ሀ. የሚቃጠል መሥዋዕት (ዘሌ. 1)፥

ለ. የእህል ቁርባን (ዘሌ. 2)፥

ሐ. የደኅንነት መሥዋዕት (ዘሌ. 3)፥

መ. የኃጢአት መሥዋዕት (ዘሌ. 4)፥

ሠ. የበደል መሥዋዕት (ዘሌ. 5)፥

ረ. ስለ መሥዋዕቶች የቀረቡ ልዩ ልዩ ሕግጋት (ዘሌ. 6-7) ናቸው።

2. የተቀደሰውን የእግዚአብሔርን አምልኮ ለመምራት የካህናት መለየት (ዘሌ. 8-10)፡-

ሀ. ካህናት ለአገልግሎት ተለዩ (ዘሌ. 8)፤

ለ. ካህናት አገልግሎታቸውን ጀመሩ (ዘሌ. 9)፤

ሐ. የአሮን ልጆች ናዳብና አቢዩድ ለፈጸሙት በደል ፍርድ ተሰጣቸው (ዘሌ. 10)።

3. በተቀደሰው እግዚአብሔር ፊት የቅድስና አንዋኗር (ዘሌ. 11-27)፡-

ሀ. በሃይማኖታዊ ሥርዓት ሰውን «ስለሚያነጹት» እና «ስለሚያረክሱት» ነገሮች የተደረጉ ሕግጋት (ዘሌ. 11-15)፥

ለ. በእግዚአብሔር ፊት በቅድስና ስለመኖር የተደነገጉ ሕግጋት (ዘሌ. 16-25)፥

ሐ. የእግዚአብሔርን ሕግ በመታዘዝ የሚገኝ በረከትና ባለመታዘዝ የሚመጣ መርገም (ዘሌ. 26)፥

መ. በእግዚአብሔር ፊት ስለትን ስለ መፈጸም የተደነገጉ ሕግጋት (ዘሌ. 27) ናቸው።

## የኦሪት ዘሌዋውያን ዓላማ

የኦሪት ዘሌዋውያን ዋና ዓላማ «ቅዱስ» በሚለው ቃል ተጠቃልሎአል። በመጽሐፉ ውስጥ ቅዱስ የሚለው ቃል ከ90 ጊዜ በላይ ተጠቅሶአል። ጌታ ራሱ ቅዱስ እንደሆነ ይገልጻል። ሕዝቡም በእርሱ ፊት ቅዱስ ይሆኑ ዘንድ ይነግራቸዋል። ቅድስና በአንድ ሰው ሕይወት ውስጥ የማይነካው ነገር የለም። እግዚአብሔርን ለእስራኤል ሕዝብ እንዴት የተቀደሱ ሕዝብ እንደሚሆኑና የማያቋርጥ በረከት እንደሚያገኙ ነግሮአቸዋል። ያ ቅድስናቸው የሚያተኩረው በሁለት ዋና ዋና ነገሮች ላይ ነበር። በመጀመሪያ፥ በእርሱ ዘንድ ተቀባይነት ባለው መንገድ እግዚአብሔርን እንዴት ማምለክ እንደሚቻል ይናገራል።

ዛሬ በዓለም ላይ በርካታ የሃይማኖት ሰዎች አሉ። እግዚአብሔር ግን አምልኮአቸውን አይቀበልም። ለምን? ምክንያቱም እግዚአብሔርን የሚያመልኩት፥ እርሱ በሚመራቸው መንገድ ስላልሆነ ነው። እርሱ በሚቀበለው መንገድ እንዴት ልናመልከው እንደምንችል ሊነግረን የሚችል እግዚአብሔር ብቻ ነው። በብሉይ ኪዳን፥ ሰዎች መሥዋዕት በመሠዋት እንዴት እደሚያመልኩት ገልጾላቸዋል። በአዲስ ኪዳን ደግሞ ሰዎች እግዚአብሔርን ሊያመልኩ የሚችሉበት ብቸኛ መንገድ፥ በመጨረሻው መሥዋዕት በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ነው።

3ኛ ጥያቄ፥ ዮሐ. 14፡6 አንብብ። ሀ) ይህ ጥቅስ እግዚአብሔርን ስለምናመልክበት ብቸኛ መንገድ ምን ይነግረናል? ለ) ይህ ጥቅስ በዓለም ዙሪያ ስላሉና፥ በኢየሱስ ክርስቶስ ስለማያምኑት ሰዎች ምን ያስተምረናል?

በሁለተኛ፥ ደረጃ የተቀደስን የእግዚአብሔር ሕዝብ እንደመሆናችን መጠን በቅድስና እንዴት መኖር እንዳለብን ያሳያል። በኢየሱስ ላይ ያለን እምነት እውነተኛ ከሆነ፥ ወንጌል ሕይወታችንን መለወጥ አለበት። የሚለውጠው አምልኮአችንን ብቻ ሳይሆን፥ ከጎረቤቶቻችን ጋር ያለንን አኗኗር፥ አሠራራችን ወዘተ. ሁሉንም ነው። ኦሪት ዘሌዋውያን የተሰጠው፥ ሕዝቡ የእግዚአብሔር ቅዱስ ሕዝብ ሆነው እንዴት መኖር እንዳለባቸው ዝርዝር የሕይወት ሁኔታዎችን ለማሳየት ነው።

4ኛ ጥያቄ፥ ሀ) ክርስቲያን ከሆንክ ጀምሮ ሕይወትህ እንዴት እየተለወጠ ነው? ለ) አንተና ሌሎች የቤተ ክርስቲያንህ አባሎች የተቀደሰ ሕይወት የምትኖሩት እንዴት ነው? ምሳሌዎችን ጥቀስ።

## በኦሪት ዘሌዋውያን ውስጥ የሚገኙ ቁልፍ አሳቦች

ኦሪት ዘሌዋውያን ከኦሪት ዘጸአት ቀጥሎ መምጣቱ በጣም ትክክለኛ ነው። በኦሪት ዘጸአት የእስራኤል ሕዝብ እግዚአብሔርን የሚያመልኩበትን የመገናኛውን ድንኳን እንዴት እንደሠሩ ተመልክተን ነበር። በተጨማሪም የአምልኮ መሪዎች የሆኑት ካህናትና ሊቀ ካህናት በመገናኛው ድንኳን ውስጥ በሚደረገው አምልኮ ስለሚኖራቸው ዝግጅትም ተነግሮናል። አሁን ደግሞ በኦሪት ዘሌዋውያን በመገናኛው ድንኳን ውስጥ፥ አምልኮው ስለሚፈጸምበት መንገድ የተሰጠ መግለጫ እናገኛለን። ደግሞም ቅዱሱን እግዚአብሔር በመገናኛው ድንኳን ውስጥ ለማምለክ የተፈቀደላቸው ሰዎች መንፈሳዊ ሁኔታም ተገልጦ እናያለን። የሚከተሉት በኦሪት ዘሌዋውያን ውስጥ ከሚገኙ ዋና ዋና ትምህርቶች ጥቂቶቹ ናቸው:-

1. ቅድስና:-

ብዙ ክርስቲያኖች ምን ማለት እንደሆነ ባያውቁም እንኳ፥ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ካሉ እጅግ በጣም አስፈላጊ ቃላት አንዱ «ቅድስና» ነው። ኦሪት ዘሌዋውያን እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘትና

እርሱ በሕይወታችን ውስጥ ሳያቋርጥ በመገኘቱ ሐሴት እንድናደርግ ሁለት ነገሮችን ማድረግ አለብን ይላል። በመጀመሪያ፥ ተገቢ የሆነ ወይም የተቀደሰ አምልኮ መፈጸም ነው። ሁለተኛው ደግሞ፥ የተቀደሰ አኗኗር ነው። ስለዚህ ቅድስና ምን ማለት እንደሆነ መረዳት አስፈላጊ ነው።

«ቅድስና» የሚለው ቃል በመሠረቱ «መለየት» ማለት ነው። በብሉይ ኪዳን ቅድስና ስለ ሁለት ዓይነት መለየት ይናገራል። በመጀመሪያ፥ የእግዚአብሔር ካልሆነ ከማንኛውም ነገር መለየት ነው። እስራኤል «የተቀደሰ» ሕዝብ የተባለው ከአሕዛብ ተለይቶ፥ የእግዚአብሔር ስለሆነ ነው። እስራኤላውያን ከአሕዛብና ከተግባራቸው በመለየት በአኗኗራችው የተቀደሱ መሆን ነበረባቸው፤ ምክንያቱም አሕዛብ ለእግዚአብሔር የተለዩ አልነበሩምና። ለአምልኮ የተለዩ እንስሳት እንኳ የተቀደሱ ይባሉ ነበር። በኦሪት ዘሌዋውያን ውስጥ ትኩረት የተሰጠው አብዛኛው ነገር ከተለመዱ ነገሮች በመለየት ቅዱስ መሆንን የሚመለከት ነው። እግዚአብሔር ልዩ በመሆኑ ቅዱስ ነው። ከተፈጠሩ ነገሮች ሁሉ የተለየና የላቀ ነው። እንደ እርሱ ያለም ማንም የለም፤ እርሱን የሚመስል ማንም የለም።

ሁለተኛው፥ ከክፉ ሥነ - ምግባር መለየት ነው። የሥነ - ምግባር ቅድስና ከኃጢአት መራቅን የሚያመለክት ነው። እግዚአብሔር ኃጢአት ስለማያደርግና ሊያደርግም ስለማይችል በሥነ ምግባር የተቀደሰ ነው። ኃጢአታችንን ስንናዘዝና የክርስቶስ ደም ከኃጢአታችን ሁሉ ሲያነጻን በሥነ - ምግባር የተቀደስን እንሆናለን። ለእግዚአብሔር ሕግ በታዛዥነት ስንኖርና ኃጢአት ሕይወታችንን እንዳይቆጣጠር ጸንተን ስንቃወም በሥነ - ምግባር የተቀደሰ ሕይወት እንኖራለን።

በአዲስ ኪዳን፥ እኛ ክርስቲያኖች በሁለቱም መንገዶች የተቀደስን ነን። እግዚአብሔር ስለመረጠንና ከዓለም ስለለየን የተቀደስን ነን። ነገር ግን ኃጢአትን ድል የመንሣት ሕይወት በመኖር ደግሞ በቅድስና መመላለስ አለብን። በሕይወታችን የሚኖር ማንኛውም ኃጢአት በኢየሱስ ክርስቶስ ደም ሲታጠብ በእግዚአብሔር ፊት ብቁ ሆኖ ወደሚገኘው ወደ ቅድስና ደረጃችን እንደገና ሊመልሰን ይችላል።

5ኛ ጥያቄ፥ ሕይወትህን መርምር። ሀ) በመጀመሪያው መንገድ የተቀደስከው እንዴት ነው? ለ) በሁለተኛው መንገድስ የተቀደስከው እንዴት ነው? ሐ) በሕይወትህ ያልተቀደስህባቸው ክፍሎች ካሉ አሁን ተናዘዝና ከእነዚህ ኃጢአቶች ተመለስ።

## 2. ንጹሕና እርኩስ

አብዛኛው የኦሪት ዘሌዋውያን ክፍል ንጹሕ ስለሆኑና ስላልሆኑ ነገሮች፥ እንዲሁም ሰውን ንጹሕ ስለሚያደርጉና ስለማያደርጉ ነገሮች ይናገራል። ይህ ለእኛ እንግዳ ስለሆነ ለብዙዎቻችን ይህንን ሐሳብ መረዳት በጣም አስቸጋሪ ነው። በኦሪት ዘሌዋውያን ውስጥ የሚገኙትን፥ አብዛኛዎቹን ሕግጋት ለመረዳት የእግዚአብሔርን ዓላማዎችና የአይሁዳውያንን አስተሳሰብ መረዳት ያስፈልጋል።

በብሉይ ኪዳን፥ እግዚአብሔር ውጫዊ የሆኑ የአካል ጉድለቶችን የኃጢአት ተጽዕኖዎች ገላጭ ማስተማሪያዎች አድርጎ ሲጠቀምባቸው እናያለን። የአካል ጉድለት በራሱ ኃጢአት አይደለም። ነገር ግን አካለ-ጎዶሎ መሆን ኃጢአተኝነትን ያመለክት ነበር። ለምሳሌ፡- በሥጋው ምንም ዓይነት ጉድለት ያለበትን፥ ወይም ጤናማ ያልሆነ ሰው በክህነት እንዳያገለግል እግዚአብሔር አግዶታል (ዘሌ. 21፡17-21)። ለምን? ያ ካህን ኃጢአተኛ ነውን? አይደለም። ነገር ግን ጤናማ አለመሆኑ፥ በዓለም ላይ ኃጢአት መኖሩን የሚያሳይ ማስረጃ ነው። ስለዚህ እግዚአብሔር በኃጢአት ላይ ያለውን ጥላቻ ለእስራኤል ሕዝብ በግልጽ ለማሳየትና ከታወቀ ኃጢአት የመራቃቸውን አስፈላጊነት ለመግለጥ፥ አካለ-ጎዶሎ የሆነ ካህን በተቀደሰው በእግዚአብሔር ፊት እንዲያገለግል አልፈቀደም። በዘሌዋውያን ውስጥ ላሉ አብዛኛዎቹ ሕግጋት ይህ መመሪያ የሚሠራ ነው። ጤነኛ ያልሆኑ፡- እንደ የቤት የወር አበባ ወይም በሽታ ያሉቱ የኃጢአት ውጫዊ ምልክቶች ነበሩ! ስለዚህ ለመንጻት መሥዋዕት ይፈልጉ ነበር።

አይሁድ ነገሮችን ሁሉ በሁለት ክፍሎች ይከፍሉ ነበር። የመጀመሪያው «ቅዱስ» ወይም የተለየ የሚባለው ክፍል ሲሆን፥ ሁለተኛው ደግሞ፥ «የተለመደ» የሚባለው ክፍል ነው። እንስሳትም ሆኑ ሰዎች ከሌሎች ተለይተው ለእግዚአብሔር ሲሰጡ ቅዱስ (የተለዩ) ይሆናሉ (ለምሳሌ፡- ዘሌ. 21፡7-8)። ቅዱስ የነበሩ ነገሮች በሰዎች ዘንድ በማይገባ መንገድ ለተለመዱ ነገሮች አገልግሎት ሲውሉ፥ ቅዱስ

መሆናችው ይቀርና የተለመዱ ይሆናሉ። ለምሳሌ፡- አንድ ሰው ከመንጋዎቹ መካከል አንድን ጠቦት ለመሠዋት ቃል ቢገባ፥ ያ ጠቦት ቅዱስ ይሆናል። ለእግዚአብሔር የተለየ ይሆናል። ቅዱስ የሚሆነው በሥነ - ምግባር አልነበረም። ለእግዚአብሔር ተመርጦ በመለየቱ ብቻ ነው። ልክ እንደዚሁ፥ ሳምሶን በሥነ - ምግባር የወደቀ ወይም የተበላሸ ሕይወት ቢኖረውም፥ ለአንድ ለተለየ አገልግሎት በእግዚአብሔር በመመረጡ ብቻ የተቀደሰ ነበር። የተለመዱ (ተራ) የሆኑ ነገሮች፥ በሥነ ምግባር የሚፈተኑ አልነበሩም፤ ነገር ግን ለእግዚአብሔር ዓላማ ተመርጠው የተለዩ ሊሆኑ ይችላሉ።

«ንጹሕ የመሆንና ያለመሆን» አሳብ የሚጎለብተው ከዚህ ነው። በእግዚአብሔር ፊት ጤናማ የሆኑ ነገሮች ንጹሐን ናቸው። ማር የሚበሉና ሽሆናቸው የተሰነጠቀ እንስሳት ጤናማ ስለሆኑ፥ ንጹሐን እንስሳት ናቸው። ምንም ዓይነት አካላዊ ጉድለትና በሽታ የሌለባቸው ሰዎች ጤናማና የተለመዱ ስለሆኑ፥ ንጹሐን ናቸው፤ ነገር ግን ከተለመደው ነገር ውጭ የሆነ ማንኛውም ነገር «ንጹሕ አይደለም»። ንጹሕ ያልሆነ ነገር ሁሉ የኃጢአት ምልክት ስለሆነ፥ ወደ እግዚአብሔር ፊት ሊቀርብ ወይም ለእግዚአብሔር ሊሰጥ አይገባም ነበር። ለምሳሌ፡- አንድን ጠቦት በመሥዋዕትነት ለእግዚአብሔር በመስጠት ቅዱስ ማድረግ ይቻላል፤ ነገር ግን አንድ አካሉ ጉድለት ካለው (አንድ ዓይኑ ዕውር ቢሆን፥ ወይም ሽባ ቢሆን፥ ወዘተ.) ንጹሕ ስላይደለ፥ ለእግዚአብሔር ሊሠዋ አይገባም ወይም አንድ ሰው ያልተለመደ በሽታ ካለው ርኩስ ነበር። ከበሽታው ለመፈወሱና ንጹሕም ለመሆኑ ሁለንተናውን በማጠብ ካሳየና መሥዋዕት ካቀረበ እንደገና እንደቀሩት እስራኤላውያን እግዚአብሔርን ማምለክ ይችላል።

በኦሪት ዘሌዋውያን ውስጥ ያሉትን ሕግጋት በምታጠናበት ጊዜ የሚከተሉትን ነገሮች አስተውል፡-

1. ቅዱስ ለመሆን፥ ሰው ወይም ሌላ ነገር ተቀባይነት ባለው መንገድ ለእግዚአብሔር ይለያል። ይህ ካልሆነ የተለመደ ወይም ተራ ነገር ነውና ለማንኛውም ተራ አገልግሎት ብቻ ይውል ነበር።

2. አንድ ነገር ንጹሕ ለመሆን አካል ሙሉ መሆን ነበረበት። አካለ-ጎዶሎ የሆነ ነገር ንጹሕ ሊሆን አይችልም፤ ምክንያቱም ጤናማ ያልሆነ ነገር የሚያመለክተው ኃጢአትን ነውና።

3. አካለ ጎዶሎ የሆነ ነገር ሁሉ እርኩስ ነበር። ኃጢአት ባይሆንም እንኳ ኃጢአትን ስለሚወክል እንደገና ንጹሕ ይሆን ዘንድ መሥዋዕት ሊቀርብለት ያስፈልግ ነበር።

| |
|---|
| 6ኛ ጥያቄ፥ ሀ) ንጹሕ ስለ መሆንና አለመሆን የተሰጠው ትምህርት እግዚአብሔር በኃጢአት ላይ ስላለው ጥላቻ ምን ያስተምረናል? ለ) ይህ ስለተገለጠው የኃጢአት ተጽዕኖ ምን ያስተምረናል? ሐ) በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነትን ለማግኘት ስለ ግላዊ ቅድስና አስፈላጊነት ይህ ምን ያስተምረናል? |

በአዲስ ኪዳን እግዚአብሔር ንጹሕ መሆንና አለመሆንን በሚመለከት በውጫዊ ነገሮች ላይ አላተኮረም። ይልቁንም ሰውን የሚያረክሱት ውስጣዊ የሆኑ ወይም በሰው ልብ ውስጥ የሚፈጸሙ ነገሮች ናቸው። ምክንያቱም ግልጽ የሆነ ክፋትና ኃጢአት የሚገለጠው በሚታዩ መንገዶች (በጥላቻ፥ በቁጣ፥ በመግደል፥ በምንዝር፥ ወዘተ.) ሲሆን የሚመነጨውም ከልብ ነው (ማቴ. 15:8-20 ተመልከት)። አዲስ ኪዳን እኛ የተወለድነው «በኃጢአት» ነው ይላል። ምክንያቱም ሁላችንም የአዳምን የኃጢአት ባሕርይ ወርሰናል (ሮሜ 5:12-14)። የምንቀደሰው በመስቀል ላይ በተሰቀለው በኢየሱስ ሞትና ለደኅንነት በእርሱ ላይ በምንታመንበት ጊዜ ለልባችን እርሱ በሚሰጠን መንጻት ብቻ ነው (1ኛ ቆሮ. 6:9-11)።

3. ንጉሡ እግዚአብሔር ስለ ሕይወታችን አቅጣጫ ሁሉ ይገደዋል

ብዙ ጊዜ ክርስቲያኖች እግዚአብሔር የሚገደው በቤተ ክርስቲያን ስለምናደርገው ወይም በመንፈሳዊ ሕይወታችን ስለሚሆነው ነገር ብቻ እንደሆነ በማሰብ ይሳሳታሉ። ሥጋዊ ናቸው የምንላቸው ነገሮች እጅ ሥራን እንደ መሥራት፥ ከሰዎች ጋር መነጋገር፥ ትምህርት ቤት መሄድ፥ ወዘተ፥ እግዚአብሔርን ብዙ የሚያሳስበው አይደሉም ይላሉ፤ ዳሩ ግን እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ያስተማረው ስለ ማንኛውም የሕይወታቸው ክፍል ዝርዝር ጉዳይ ሁሉ እንደሚገደው ነው። ንጉሣቸው እንደመሆኑ መጠን እግዚአብሔር እስራኤላውያን እንዲታዘዙትና እንዲያከብሩት የሚፈልገው በሁሉም የሕይወታቸው አቅጣጫ ነው።

ስለዚህ በኦሪት ዘሌዋውያን ውስጥ ሁሉንም የሕይወት አቅጣጫ የሚነኩ ሕግጋትን እናገኛለን። እግዚአብሔርን እንደ ማምለክ ያሉ

ሃይማኖታዊ ጉዳዮች የሚመለከቱ ሕግጋት አሉ። ደግሞም እስራኤላውያን የእግዚአብሔር ሕዝብ እንደመሆናቸው መጠን እርስ በርሳቸው እንዴት መኖር እንዳለባቸው የሚናገሩ ሕግጋትም አሉ። ግላዊ ስለሆኑ ነገሮች (ለምሳሌ፡- በሽታ ወዘተ) የሚናገሩ ሕግጋት ደግሞ አሉ። እግዚአብሔር በእነዚህ ነገሮች ሁሉ ላይ ያለውን ፍላጎትና ቁጥጥር ለማሳየት ትእዛዛትን ሰጠ።

7ኛ ጥያቄ ፥ 1ኛ ቆሮ. 10፡31 አንብብ። ሀ) ይህ ጥቅስ ይህንን እውነት የሚገልጸው እንዴት ነው? ለ) እግዚአብሔር ደስ የሚሰኝባቸውንና እኛ የምናደርጋቸውን አንዳንድ የተለመዱ ነገሮች ጥቀስ። ሐ) እነዚህን ነገሮች ለእግዚአብሔር ክብር በማያመጣ መንገድ ልንጠቀምባቸው የምንችለው እንዴት ነው? መ) እነዚህን ነገሮች ለእግዚአብሔር ክብር በሚያመጣ መንገድ ልንጠቀምባቸው የምንችለውስ እንዴት ነው?

4. መሥዋዕቶች

በብሉይ ኪዳን፥ ሰው እግዚአብሔርን የሚቀርበውና የሚያመልከው መሥዋዕትን በማቅረብ ነበር። በአጠቃላይ አምስት ዓይነት የተለያዩ መሥዋዕቶች ነበሩ። የሚቃጠል መሥዋዕት፥ የእህል ቁርባን፥ የደኅንነት መሥዋዕት፥ የበደል መሥዋዕትና የኃጢአት መሥዋዕት ናቸው። እነዚህ መሥዋዕቶች ሁሉ የየራሳቸው ዓላማ ያላቸው ቢሆንም፥ የሚቀርቡበት ግን ሁለት ዋና ዋና ምክንያቶች አሉ፡-

1) አንዳንድ መሥዋዕቶች ለእግዚአብሔር ምስጋናንና ክብርን ለመግለጥ የሚቀርቡ ናቸው።

2) ሌሎች መሥዋዕቶች ደግሞ ከእግዚአብሔር ዘንድ የኃጢአት ይቅርታን ለመቀበል የሚቀርቡ ናቸው።

8ኛ ጥያቄ፥ ዘሌ. 17፡ 11ና ዕብ. 9፡22 አንብብ። የመሥዋዕት ዓላማ መሠረታዊ ግንዛቤ ምን ነበር? አብዛኛዎቹ የብሉይ ኪዳን መሥዋዕቶች የእንስሳት ደም የሚፈስባቸው ነበሩ። ስለመሥዋዕቶች ልናውቃቸው የሚገቡ በርካታ መሠረታዊና ጠቃሚ የሆኑ ነገሮች አሉ።

1. የእንስሳው ደም የእንስሳውን ሕይወት የሚወክል ነው። ስለዚህ ብሉይ ኪዳንና አዲስ ኪዳን የእንስሳት ደም የኃጢአት ስርየትን

ያስገኛል ሲሉ፥ እርቅን የሚያስገኘው በደሙ የተወከለው የእንስሳው ሞት ነው ማለት ነው። እንደዚሁም እኛ ስለ ክርስቶስ ደምና ስላለውም ኃይል ስንናገር፥ ስለ ሞተና በእርሱም ስለተገኘው ውጤት መናገራችን ነው።

2. የመሥዋዕት መሠረት ምትክ የመሆን ሐሳብ ነው። በብሉይ ኪዳን አንድ ሰው አንድን እንስሳ ለመሥዋዕት እንዲሆን ሲያቀርብ፥ በእንስሳው ራስ ላይ እጁን ይጭናል። ይህን ሲያደርግ ጥፋተኛ ስለሆነ ሞት ይገባዋል ብሎ ማወጁ ነበር። ነገር ግን የእንስሳው ሕይወት ለኃጢአተኛው ሕይወት ምትክ ሆኖ የቀረበ ነው። በአዲስ ኪዳንም እንደዚሁ፥ የኢየሱስ ክርስቶስ ሕይወት ለኃጢአተኛው ሕይወት ምትክ ሆኗል። የኃጢአትን ዕዳ ለመክፈል እያንዳንዳችን መሞት ሲገባን፥ በእኛ ፈንታ ኢየሱስ ሞተ።

3. የመሥዋዕቱ ውጤት ኃጢአትን ማስተሰረይ ነው።

| |
|---|
| 9ኛ ጥያቄ፥ ሀ) «ማስተስረይ» የሚለው ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት ውስጥ ተመልከት። ቃሉ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያለውን ሙሉ ትርጉም ጻፍ። ለ) ይህ ቃል እግዚአብሔር በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ስላደረገልን ነገር የሚገልጸው እንዴት ነው? |

«ማስተሰርይ» የሚለው ቃል በብሉይ ኪዳን በተደጋጋሚ ያገለገለ ሲሆን፥ በግሪኩ አዲስ ኪዳን ግን አንድ ጊዜ ብቻ እናገኘዋለን (ሮሜ 5፡11)። ማስተሰረይ እግዚአብሔር ለኃጢአተኛ ሰው ይቅርታን እንዲያገኝና ከራሱ ጋር እንዲታረቅ የሠራው ሥራ ነው። በብሉይ ኪዳን የቃሉ ትርጉም «ማጥፋት»፥ «መሸፈን»፥ «ማስወገድ»፥ ወይም «መጥረግ» ማለት ነው። ኃጢአተኛው በሚያቀርበው መሥዋዕት ከእግዚአብሔር ይቅርታን ለመግዛት አይሞክርም። ይልቁንም እግዚአብሔር ለኃጢአተኛው፥ በጸጋው ከእርሱ ጋር ሊታረቅ የሚችልበትን መንገድ ሰጠው። የእርቅ መሠረታዊ አሳብ፥ በሌላ እንስሳ መሠዋት እግዚአብሔር የኃጢአተኛው ኃጢአት እንዲሸፈን ያደርግ ነበር። ልክ እንደዚሁ፥ እግዚአብሔር ጻድቃን አድርጎ ይቀበለን ዘንድ፥ የኢየሱስ ክርስቶስ ሞት ኃጢአታችንን ይሸፍናል።

4. መሥዋዕቱ ራሱ ኃጢአተኛውን የሚያድን ወይም ይቅርታ የሚያስገኝለት አይደለም። መሥዋዕቱ ውጫዊ ማስረጃ ሲሆን

የኃጢአተኛው ውስጣዊ ዝንባሌ ማለትም ንስሐ መግባቱንም የሚያሳይ ነበር። ንስሐ ለመግባት የተዘጋጀ ልብ ከሌለና ለእግዚአብሔር ታዛዥ ለመሆን ይችል ዘንድ የሰውየው ሕይወት ካልተለወጠ፥ መሥዋዕቱ አንዳችም ዋጋ የለውም ፤(1ኛ ሳሙ. 15፡22-23፤ መዝ. (51)፡16-17፤ ሚክ. 6፡6-8 ተመልከት)።

---

10ኛ ጥያቄ፥ በዚህ ዘመን ለሚኖረን አምልኮ የዚህ እውነትነት እንዴት ነው?

---

5. የመሥዋዕት ዓላማዎች የሚከተሉት ነበሩ፡-

ሀ. የእግዚአብሔርን ቅድስናና እርሱ ኃጢአትን እንዴት እንደሚጠላ፥ ደግሞም ሁልጊዜ ኃጢአትን በሞት እንደሚቀጣ ለማስተማር ነው። በብሉይ ኪዳን በኃጢአተኛው ምትክ እንስሳ ይገደል ነበር። በአዲስ ኪዳን ደግሞ የኃጢአት ቅጣት የተከፈለው በኢየሱስ ሞት ነው።

ለ. የሰውን ኃጢአተኛነት ለማስተማር ነው። ሰው መሥዋዕት ባቀረበ ቁጥር ኃጢአተኛ መሆኑን ይመሰክራል። ደግሞም የኃጢአት ደመወዝ የኃጢአተኛው ወይም የእንስሳው ሞት መሆኑንም ያሳያል፤ (ሮሜ 6፡23)።

ሐ. ይቅርታ የሚገኘው የኃጢአተኛውን ኃጢአት ለመሸፈን በሚፈጸም የምትክ ሞት መሆኑን ለማሳየት ነው።

መ. አንድ ኃጢአተኛ፥ በእግዚአብሔር ፊት ሕይወቱን በንጽሕና የመጠበቅ ኃላፊነት እንዳለበትና ኃጢአት ከሠራም ለመንጻትና እንደገና ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት ለማድረግ ንስሐ መግባት እንዳለበት ለማስተማር ነው።

ሠ. የእግዚአብሔርን ምሕረትና ጸጋ ለማሳየት ነው። እግዚአብሔር እያንዳንዱ ኃጢአተኛ በግል ስለ ኃጢአቱ እንዲሞት መጠየቅ ይችል ነበር። ነገር ግን እርሱ እንደዚያ ቢያደርግ ኖሮ ሁላችንም ኃጢአተኞች ስለሆንን ማንም ሰው በሕይወት አይቀርም ነበር፤ ነገር ግን እግዚአብሔር፥ ኃጢአተኛን ሰው ከራሱ ጋር የሚያስታርቅበትንና ይቅርታ የሚሰጥበትን መንገድ ሁልጊዜ ማዘጋጀቱ ምሕረቱንና ጸጋውን ያሳያል። ቅዱስ ስለሆነ፥ ኃጢአትን ሳይቀጣ አይተውም፤ ስለዚህ እግዚአብሔር በኃጢአተኛ ምትክ የሌላን ሰው ወይም የሌላን ነገር ሞት

ጠየቀ። ነገር ግን መሐሪ ስለሆነ፥ ሰው ይቅርታ በመቀበል ከእግዚአብሔር ጋር የሚታረቅበትን መንገድ አዘጋጀ።

6. የብሉይ ኪዳን መሥዋዕቶች እግዚአብሔር ለኃጢአተኞች የሠዋውን የእግዚአብሔር በግ የሆነውን ኢየሱስ ክርስቶስን የሚያመለክቱ ተምሳሌቶች ናቸው (ዮሐ. 1፡29-31፤ ሮሜ 5፡6-11፤ ዕብ. 10፡10-12 ተመልከት)።

7. የብሉይ ኪዳን መሥዋዕቶች ክርስቲያኖች ዛሬ ለእግዚአብሔር የሚያቀርቡትን መሥዋዕት የሚያመለክቱ ናቸው።

| |
|---|
| 11ኛ ጥያቄ፥ ሀ) 1ኛ ጴጥ. 2፡5፤ ፊልጵ. 4፡18፤ ዕብ. 13፡15-18፤ ራእ. 5፡8፤ ሮሜ 15፡16-17፤ ሮሜ 12፡1፤ ፊልጵ. 2፡17፤ 2 ጢሞ. 4፡6 አንብብ። ክርስቲያኖች ለእግዚአብሔር ማቅረብ የሚገባቸውን መሥዋዕቶች ዘርዝር። ለ) እነዚህን መሥዋዕቶች በሕይወትህ እንዴት እየሠራህ ነው? ምሳሌዎችን ስጥ። |

8. በብሉይ ኪዳን ሳይታሰብ ለተሠሩ ኃጢአቶች የሚቀርቡ መሥዋዕቶች ብቻ ነበሩ። አንድ ሰው ግን አውቆ በእግዚአብሔር ላይ በሚያምፅበት ጊዜ ምንም መሥዋዕት ማቅረብና ይቅርታን መቀበል አይችልም ነበር።

## 2ኛ ቀን፡- ኦሪት ዘሌዋውያን 1-10

መሥዋዕቶችንና ዓላማቸውን በትክክል መረዳት እግዚአብሔር የኃጢአት ይቅርታ ያዘጋጀበትን መንገድ ለመረዳት ይጠቅማል። ኦሪት ዘሌዋውያን ኃጢአተኛ የሆነው የእስራኤል ሕዝብ የተቀደሰውን እግዚአብሔርን እንዴት ማምለክ እንዳለበት ዝርዝር መመሪያ ይሰጣል። እግዚአብሔር ቅዱስ ባይሆን ኖሮ፥ መሥዋዕት የሚባል ነገር ባላስፈለገም ነበር፤ ነገር ግን እግዚአብሔር ቅዱስ ስለሆነና ኃጢአትን ሳይቀጣ ስለማያልፍ፥ እንዲሁም መሐሪ ስለሆነ፥ ለእስራኤላውያን ወደ እርሱ እንዴት እንደሚመጡና የኃጢአታቸውን ይቅርታ እንደሚያገኙ ዝርዝር መመሪያ ሰጣቸው።

12ኛ ጥያቄ፥ ዘሌ. 1-10 አንብብ። ሀ) አምስቱን ዋና ዋና የመሥዋዕት ዓይነቶች ዘርዝር። ለ) የእያንዳንዱ መሥዋዕት ዓላማ ምን ነበር? ሐ) ስለ እግዚአብሔር ባሕርይ ከመሥዋዕቶች የምንማረው ነገር ምንድን ነው? መ) መሥዋዕት ስለ ኃጢአት ከፉነት የሚያስተምሩት ምንድን ነው? ሠ) ከካህናት ለአገልግሎት መለየትና ከአሮን ልጆች ሞት የምንማረው ምንድን ነው?

ዘሌ. 1-10 በሁለት የተለያዩ ርእሶች ያተኩራል። አጠቃላይ ክፍሉ የእግዚአብሔር ሕዝብ የሆኑት እስራኤላውያን እንዴት እግዚአብሔርን ማምለክ እንደ ነበረባቸው የሚናገር ቢሆንም፥ ዘሌ. 1-7 እስራኤላውያን እግዚአብሔርን ሊያመልኩ ስለሚችሉበት አምስት መሥዋዕቶች ይናገራል። ዘሌ. 8-10 ደግሞ የአምልኮ መሪዎች የሆኑት ካህናት ቅዱስ እግዚአብሔር የሚመለከበትን የአምልኮ ፕሮግራም ለመምራት እንዴት በጥንቃቄ እንደሚዘጋጁ ይናገራል።

1. ይቅርታን ለማግኘትና እግዚአብሔርን ለማምለክ የሚያስፈልጉ መሥዋዕቶች (ዘሌ. 1-7)።

በእነዚህ ዘሌዋውያን ምዕራፎች ለእግዚአብሔር ትክክለኛ የሆነ መሥዋዕትን በትክክለኛ መንገድ ስለ መሠዋት በርካታ ሕጎች ተሰጥተዋል። የሚከተሉት ሕግጋት መሥዋዕቶቹን ሁሉ ከሚመለከቱ መካከል ጥቂቶቹ ናቸው:-

ሀ. መሥዋዕቶቹ ሁሉ በመገናኛው ድንኳን ውስጥ፥ በነሐስ መሠዊያው ላይ መቅረብ ነበረባቸው።

ለ. እንስሶቹ ከመሠዋታቸው በፊት፥ መሥዋዕቱን የሚያቀርበው ሰው በእንስሳው ራስ ላይ እጆቹን ይጭናል። ይህም የሚደረገው ለሁለት ዓላማ ነው:- የመጀመሪያው፥ እንስሳው ራስ ላይ እጆቹን መጫኑ ምትክ መሆኑን ሰውዬው ተገንዝቧል ማለት ሲሆን፥ በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ ሰውዬው በዚህ ጊዜ ኃጢአቱን በመናዘዝ ምሳሌያዊ በሆነ መንገድ ኃጢአቱን ሁሉ በእንስሳው ላይ ያኖራል።

ሐ. ካህኑ እንስሳውን ያርዳል።

መ. የእንስሳው ደም በመሠዊያው ላይ ይረጫል።

ሠ. እንስሳው ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ይቃጠላል።

እስራኤላውያን በአምልኮአቸው ለእግዚአብሔር የሚሠዉአቸውን የአምስት መሥዋዕቶች ዝርዝር በሚከተለው ሠንጠረዥ ተመልከት።

| ስም | የሚቃጠለው ክፍል | ሌሎች ክፍሎች | የሚሠዋው እንስሳ | የሚሠዋበት ምክንያት | የሚገኝበት ክፍል |
|---|---|---|---|---|---|
| የሚቃጠል መሥዋዕት | ሁሉም | የለም | ተባዕት ሆኖ ነውር የሌለበት መሥዋዕቱን በሚያቀርበው ሰው ዓቅም | ለአጠቃላይ ኃጢአት ለእግዚአብሔር መስጠትን ያሳያል | ዘሌዋውያን 1 |
| የእህል ቁርባን | ከፊሉ | ካህናት ይበሉታል | እርሾ የሌለበት ቂጣ ጨው ያለበት የዳቦ ሙልሙል | የበኩራት ፍሬን ለእግዚአብሔር በመስጠት ስለ ሰብሉ እግዚአብሔርን ማመስገን | ዘሌዋውያን 2 |
| ስለ ደኅንነት<br>ሀ. የምስጋና መሥዋዕት<br>ለ. የስዕለት መሥዋዕት<br>ሐ. የበጎ ፈቃድ መሥዋዕት | ስቡ | በኅብረት ይበላል በካህናትና መሥዋዕቱን ባቀረበው ሰው ይበላል | ተባዕት ወይም እንስት እንደ አቅራቢው ዓቅም | ሀ. ላልተጠበቀ በረከት ምስጋና ለማቅረብ<br>ለ. ከችግር ስለ መዳን ስዕለትን ለመክፈል<br>ሐ. በአጠቃላይ ምሥጋናን ለመግለጥ | ዘሌዋውያን 3ና 22፡18–30 |
| የኃጢአት መሥዋዕት | ስቡ | ካህናት ይበሉታል | ካህናት ወይም ሕዝቡ፡– በሬ<br>ንጉሡ፡– ወንድ ፍየል<br>ግለሰቦች፡– ሴት ፍየል | አጠቃላይ መንጻት ሲያስፈልግና ለተለያዩ የግል ኃጢአቶች ያቀርባል | ዘሌዋውያን 4 |
| የበደል መሥዋዕት | ስቡ | ካህናት ይበሉታል | ነውር የሌለበት አውራ በግ | እግዚአብሔርን ወይም ሰውን ሲበድል | ዘሌዋውያን 5፡1–6፡7 |

ስለተለያዩ መሥዋዕቶች የሚከተሉትን እውነቶች አስተውል:-

1. የሚቃጠል መሥዋዕት በመሠዊያው ላይ ሙሉ ለሙሉ ይቃጠላል። ብዙዎች ይህ ስለ ኃጢአታችን መስዋዕት ይሆን ዘንድ ራሱን ሙሉ በሙሉ ለእግዚአብሔር የሰጠው የክርስቶስ ምሳሌ እንደሆነ ያስባሉ። በሮሜ 12፡1 ላይ ክርስቲያኖች ራሳቸውን ሕያው መሥዋዕት አድርገው እንዲያቀርቡ ሲጠይቅ በጳውሎስ አእምሮ የነበረው መሥዋዕት ይህ ሳይሆን አይቀርም።

2. እንደ አቅራቢው ሰው ዓይነቱ ይለያያል። በሥልጣን ላይ ያሉ ከፍተኛ መሥዋዕት ያቀርባሉ። ሀብታም የሆኑ ሰዎችም ትልቅ መሥዋዕት ያቀርቡ ነበር። ድሀ ሰው ርግብ ወይም እህል ብቻ ቢሆን እንኳ እንዲያቀርብ እግዚአብሔር ፈቅዶ ነበር። ምሕረቱን ሰዎች ሁሉ ሊቀበሉት የሚችሉ እንዲሆን የይቅርታ ማግኛ መንገድ አደረገው።

3. የበደል መሥዋዕት የሚቀርበው ካሣ ስለሚጠየቅባቸው ኃጢአቶች ነበር። ለምሳሌ:- አንድ ሰው አሥራቱን ለእግዚአብሔር ካልከፈለ፥ የበደል መሥዋዕት እንዲያቀርብ ይጠበቅበት ነበር። ወይም አንድ ሰው የራሱ ያልሆነውን ነገር ከጎረቤቱ ቢወስድ፥ የበደል መሥዋዕት እንዲያቀርብ ይፈለግበት ነበር። ነገር ግን የበደሉን ይቅርታ ያገኝ ዘንድ፥ መሥዋዕቱን ከማቅረቡ በፊት፥ ዕዳውን ለእግዚአብሔርም ሆነ ለሰው እንዲከፍል ይጠበቅበት ነበር። ዕዳውን ሲከፍል በዕዳው ላይ አንድ አምስተኛ እጅ መጨመር ነበረበት። ይህ በሌላ ሰው ላይ በደል በምንፈጽምበት ጊዜ ካሣ እንዴት መክፈል እንዳለብን የሚያሳይ ጥሩ ምሳሌ ነው። ገንዘብ ሰርቀን እንደሆነ ይቅርታ መጠየቅ ብቻ ሳይሆን፥ ገንዘቡን መመለስም አለብን።

> 13ኛ ጥያቄ፥ ሀ) ብዙ ጊዜ ክርስቲያን ገንዘብ ወይም ሌላ ነገር በሚሰርቅበትና ይቅርታ ለማግኘት በሚፈልግበት ጊዜ፥ የሰረቀውን ነገር ይመልሳል ወይስ ይቅርታ ብቻ ይጠይቃል? መልስህን አብራራ። ለ) የበደል መሥዋዕት ይቅርታ ከመጠየቅ በፊት ገንዘቡን ስለ መክፈል ምን ያስተምረናል? ሐ) የእግዚአብሔርን ይቅርታ ከማግኘት በፊት ከሌሎች ጋር ስለ መታረቅ ማቴ. 5፡23-24 ምን ይላል?

** መሥዋዕቶችንና ከክርስቶስ ሥራ፥ እንዲሁም ከክርስትና ሕይወት ጋር ያላቸውን ዝምድና የበለጠ ለመረዳት ዘሌዋውያንና ዕብራውያን የሚለውን የትመማ መጽሐፍ ማጥናት ትችላለህ።

2. የካህናት ለእግዚአብሔር አገልግሎት መለየት (ዘሌ. 8-10)

በእግዚአብሔር ፊት ማገልገል በቀላሉ የምናየው ነገር አይደለም። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በመሪነት ማገልገል በርካታ ኃላፊነትንና ከእግዚአብሔር ዘንድ ከባድ ፍርድን የሚያመጣ ነው (ያዕ. 3:1፤ ዕብ. 13:17)፤ ስለዚህ አሮንና ልጆቹ የእግዚአብሔርን ሕዝብ በተቀደሰ አምልኮ ለመምራት ሲዘጋጁ፥ እነርሱ ራሳቸውም ሆኑ የአምልኮ ዕቃዎቹ በሙሉ በጥንቃቄ እንዲነጹ ያስፈልግ ነበር። እነዚህ ምዕራፎች በአምልኮ ሰዓት እንዴት መጠንቀቅ እንዳለብንና የቤተ ክርስቲያን አመራር ምን ያህል ከፍተኛ ነገር እንደሆነ የሚያስገነዝበን ነው።

ቀጥሎ በእነዚህ ምዕራፎች ውስጥ የሚገኙ ዋና ዋና ነገሮች ተጠቅሰዋል:-

1. ሙሴ የአምልኮ ሥርዓት ከመጀመሩ በፊት ካህናትንና የአምልኮ ዕቃዎችን በሙሉ ያነጻቸው ነበር። ከኃጢአት ያነጻቸው ዘንድ የሚቃጠልና ባለማወቅ ስለተፈጸመ በደል የሚቀርብ መሥዋዕት ያቀርብ ነበር። ልዩ የሆነ አውራ በግ ያርድና በደሙ ቀኝ ጆሮን፥ የቀኝ እጅ አውራ ጣትና የቀኝ እግር አውራ ጣትን ለማስነካት ይጠቀም ነበር። ይህም እግዚአብሔርን ለመስማት፥ ሥራውን ለመሥራትና በመንገዱ ለመሄድ ዝግጁ መሆናቸውን ያመለክት ነበር። ከዚያም ሥራውን ከመጀመራቸውም በፊት ለአንድ ሳምንት ይቆዩ ነበር። አሮንና ልጆቹ በዝግጅት ለአንድ ሳምንት ከቆዩ በኋላ፥ ሁሉንም የመሥዋዕት ዓይነቶች በማቅረብ አገልግሎታቸውን ይጀምሩ ነበር። እግዚአብሔር በነሐስ መሠዊያ ላይ ያለውን መሥዋዕት የሚያቃጥል እሳት በመላክ አገልግሎታቸውንና አምልኮአቸውን መቀበሉን ያሳይ ነበር።

2. ሁለቱ የአሮን ልጆች በመገናኛው ድንኳን ውስጥ አገልግሎት ጀምረው ብዙም ሳይቆዩ እግዚአብሔር በሞት ቀጣቸው። የተሰጠው ምክንያት በጌታ ፊት የማይገባ እሳት ይዘው መቅረባቸው ነው። የናዳብና የአብድ ኃጢአት ምን እንደሆነ ግልጽ አይደለም። በተገደሉ ጊዜ ለዕጣን መሠዊያ የሚሆን ዕጣን ይዘው

ወደ ቅድስት የገቡ ይመስላል። ፍርዱ በርካታ ምክንያቶች ሊኖሩት ይችላሉ፡- ሀ) እግዚአብሔር ያልፈቀደውን ከሰል ወይም ዕጣን ተጠቅመው ይሆናል። ለ) ለሊቀ ካህኑ ብቻ የተፈቀደውን ሥራ ሠርተው ሊሆን ይችላል። ሐ) ያለ አሮንና ሙሴ ፈቃድ ዕጣን አጥነው ይሆናል። መ) ሰክረው ሊሆን ይችላል። ምናልባት ከእነዚህ ልጆች ሞት በኋላ፥ እግዚአብሔር ወዲያውኑ ለአሮንና ለካህናቱ በመገናኛው ድንኳን ከማገልገላቸው በፊት እንዳይጠጡ ያዘዛቸው ስለዚህ ይሆናል።

> 14ኛ ጥያቄ፥ ሀ) እግዚአብሔር በእነዚህ ሰዎች ላይ ወዲያውኑ ከባድ ፍርድ የሰጠው ለምን ይመስልሃል? ለ) የእግዚአብሔርን ሕዝብ ስንመራ ልንወስደው ስለሚገባን ጥንቃቄ ይህ ምን ያስተምረናል?

በእስራኤላውያንም ሆነ በቤተ ክርስቲያን የአምልኮ መጀመሪያ፥ እግዚአብሔር ፍጹም የሆነ ቅድስናን እንደሚፈልግ በኃጢአት ላይ ከባድ ፍርድ በመፍረድ ገልጧል (የሐዋ. 5፡1-11)። እግዚአብሔር ለእስራኤላውያንና ለአሮን በተለይም ለሕዝቡ ምሳሌ ይሆኑ ዘንድ ለመሪዎች የቅድስናን አስፈላጊነት ለማስተማር ፈለገ።

## 3ኛ ቀን፡- ዘሌዋውያን 11-22

እግዚአብሔር ሕዝቡን የጠራው በፊቱ ቅዱሳን እንዲሆኑ ነው። ከዓለም የተለዩ መሆን አለባቸው። ይህ ልዩ መሆን በውስጣዊ ሕይወታችን ከሚኖር ለውጥ ይጀምራል። እኛ አዲስ ፍጥረት ነን (2ኛ ቆሮ. 5፡17)። ለውጥ ሁልጊዜ መጀመር ያለበት ከውስጥ (ከልብ) እንጂ ከድርጊት አይደለም። ይህም ማለት ልባችን በፍቅር፥ በደስታ፥ በሰላም፥ በትዕግሥት፥ ወዘተ. (ገላ. 5፡22-23) መሞላት አለበት ማለት ነው። የተለዩ ዝንባሌዎችና ዓላማዎች ሊኖሩን ይገባል። ደግሞም ይህ ልዩነት ውጫዊ በሆኑ ተግባራት ራሱን ይገልጣል።

> 15ኛ ጥያቄ፥ ሀ) በጌታችን ባመንክ ጊዜ፥ እግዚአብሔር ልብህን የለወጠባቸው መንገዶች ምንድን ናቸው? ለ) በጌታ ባመንክ ጊዜ፥ እግዚአብሔር ተግባርህን የለወጠባቸው መንገዶች ምንድን ናቸው? ሐ) አንዳንድ ክርስቲያኖች በውስጣዊ ሳይሆን በውጫዊ ለውጥ ላይ ብቻ የሚያተኩሩት ለምንድን ነው? ይህ ትክክል ነውን?

የእስራኤል ሕዝብ የተለዩ መሆን ነበረባቸው፤ ቅዱሳን መሆን ነበረባቸው። ስለዚህ ልዩ መሆናቸውን ለማጠናከር፥ እግዚአብሔር በርካታ ሕግጋት ሰጣቸው። ሆኖም እነዚህ ሕግጋት የተሰጧቸው እንዲያው በዘፈቀደ አልነበረም። አብዛኛዎቹ ለእስራኤል ሕዝብ ጥቅም የዋሉ ግልጽ የሆኑ ዓላማዎች ነበራቸው።

| |
|---|
| 16ኛ ጥያቄ፥ ዘሌ. 11-22 አንብብ። ሀ) በእነዚህ ቁጥሮች የተጠቀሱ የተለያዩ የሕግ ዓይነቶችን ወይም ክፍሎችን ጥቀስ። ለ) የማስተሰርያ ቀን በዓል ዓላማ ምን ነበር? ሐ) ዘሌ. 18፡1-5 አንብብ። እነዚህ ቁጥሮች የአሪት ዘሌዋውያንን ትምህርት የሚያጠቃልሉት እንዴት ነው? መ) ከእነዚህ ምዕራፎች ስለተቀደሰ ኑሮ የምንማራቸው አንዳንድ መመሪያዎች ምንድን ናቸው? |

ዘሌ. 11-22 የእስራኤላውያንን የሕይወት ክፍል ሁሉ የሚነኩ በርካታ የሆኑ የተለያዩ ዓይነት ሕግጋትን ይዟል። እነዚህ ሕግጋት ጊዜያዊ ነበሩ። በአዲስ ኪዳን ዘመን ለምንኖር ለእኛ ግዴታዎች አይደሉም (ማር. 7፡14-22 አንብብ)።

1. ስለምግብ የተሰጡ ሕግጋት (ዘሌ. 11)፡- እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን እንዲበሉ የተፈቀዱላቸው ምግቦች ምን ዓይነት እንደሆኑ ነገራቸው። በመሬት ላይ የሚኖሩ፥ ማር በልተው የሚያመሰኩትና ሸኮናቸው የተሰነጠቀ እንስሳት ብቻ ለምግብነት ተፈቅደው ነበር። እነዚህ እንስሳት ብቻ «ንጹሐን» ሲባሉ የቀሩት ግን «ርኩሳን» ተብለው ነበር። ከዓሣ ዓይነቶች ክንፍና ቅርፊት ያላቸው ብቻ ለምግብነት ተፈቅደው ነበር። ከበራሪ እንስሳትና ከወፎች እንዲበሉ የተፈቀዱት የተወሰኑት ብቻ ነበሩ።

2. ሴቶች ከወለዱ በኋላ የሚጠብቁት የመንጻት ሥርዓት (ዘሌ. 12)፡- ሴት ከሰውነትዋ ደም በሚፈሳት በማንኛውም ጊዜ በሃይማኖታዊ ሥርዓት ያልነጻች (ርኩስ) ትሆናለች። ስለዚህ ደም ከሰውነትዋ የሚፈስባት ልጅ የመውለጃዋ ጊዜ ስለሆነ፥ ከተጠቀሰው ጊዜ በኋላ መሥዋዕት በማቅረብ እስክትነጻ ድረስ የረከሰች ትሆን ነበር።

3. ስለ ቆዳ በሽታ፥ በልብስ፥ ወይም በቤት ግድግዳ ላይ ስለሚታዩ ያልተለመዱ ምልክቶች የተሰጠ ሕግ (ዘሌ. 13-14)፡-

እንደምታስታውሰው፥ በአይሁዳውያን አስተሳሰብ ያልተለመደ ማንኛውም ዓይነት ነገር የኃጢአት ምልክት ወይም ምሳሌ ነው። ይህ በራሱ ኃጢአት ወይም የኃጢአት ውጤት አልነበረም። ያልተለመዱ የቆዳ በሽታዎችና በልብስ ወይም በቤት ግድግዳ ላይ የሚታዩ ምልክቶች ኃጢአትን የሚያመለክቱ ስለነበሩ፥ በተሰጠው ሕግ መሠረት የመንጻት ሥርዓቶች መፈጸም ነበረባቸው።

4. ከሰውነት የሚወጣ ያልተለመደ ፈሳሽ (ዘሌ. 15)፡- ከወንድም ሆነ ከሴት የሚወጡ የፍትወት ፈሳሾች ያልተለመዱ ሆነው ስለሚቆጠሩ፥ ሰውየውን (ሴትዮዋን) ያረክሳሉ። ስለዚህ እነዚህን ነገሮች የነካ ሰው ወይም በእነዚህ ሰዎች የተነካ ዕቃ መልሶ እስኪነጻ ድረስ የሚቆይበት የተወሰነ ጊዜ ነበር።

5. የማስተስርያ ቀን በአይሁዳውያን የቀን መቁጠሪያ ከሁሉም የሚበልጥ ሃይማኖታዊ በዓል ነው (ዘሌ. 16)። ስለዚህ እንዴት ሊጠብቁት እንደሚገባ የተሰጡ በጥንቃቄ የተሞሉ ትእዛዛት ነበሩ። የማስተስርያ ቀን ዓላማ ሕዝቡንም ሆነ የመገናኛውን ድንኳን በየዓመቱ ውስጥ ከገጠማቸው ከማናቸውም ዓይነት ዕርኩሰት ማንጻት ነው። ያለፈውን ዓመት ኃጢአት በማንጻት ሕዝቡ በእግዚአብሔር ፊት ንጹሕ የሆነ አዲስ የሃይማኖት ዓመት ይጀምሩ ዘንድ ነው። የማስተስርያ ቀን ሃይማኖታዊ ሥርዓት ኃጢአት በእነርሱ ላይ ያመጣውን አጠቃላይ ተጽዕኖ በማሳሰብ በእግዚአብሔር ፊት ያለማቋረጥ መንጻታቸው ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ ለአይሁድ የሚያሳይ ሃይማኖታዊ ሥርዓት ነበር። እግዚአብሔር በጸጋው ኃጢአታቸውን ይቅር እንዳለና ከእነርሱም እንዳራቀው ሕያው በሆነ መግለጫ ለእስራኤላውያን በማሳየት፥ ፍየልን ወደ በረሃ የመስደድ ሥርዓት ነበር። በቃል ኪዳኑ ታቦት የስርየት መክደኛ ላይ ደምን ይረጭ ዘንድ ሊቀ ካህኑ ወደ ቅድስተ ቅዱሳን የሚገባበት ብቸኛ ዓመታዊ ቀን ይህ የሥርዓት ቀን ነበር።

6. እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን ስለ እንስሳት ደም ግልጽ የሆነ መመሪያ ሰጣቸው። እንደምታስታውሰው ደም የእንስሳት ሕይወት ምልክት ነበር (ዘሌ. 17፡11)። ስለዚህ እንስሳትን በሚያርዱበት ጊዜ ደማቸውን ምን ማድረግ እንዳለባቸው እንዲጠነቀቁ ግልጥ የሆነ ትእዛዝ ተሰጥቶአቸው ነበር።

7. እግዚአብሔር፥ አንድ ሰው ማንን ማግባት እንዳለበትና ማንንስ ማግባት እንደሌለበት ግልጥ የሆነ ትእዛዝ ሰጥቷል (ዘሌ. 18)። በተጨማሪ ወንድና ሴት የግብረ ሥጋ ግንኙነት መፈጸም የሌለባቸውን ጊዜያት በሚመለከት ትእዛዛት ተሰጥተዋል።

8. እግዚአብሔር፥ ሕዝቡ ከእርሱ ጋርና እርስ በርስ ስለሚኖራቸው ግንኙነት ግልጥ የሆኑ ትእዛዛትን ሰጥቷል። የእግዚአብሔርን ሕግ በግልጥ የማይታዘዙ ሰዎች ሊደርስባቸው ስላለው ቅጣትም ተናግሯል (ዘሌ. 19-20)።

9. በመጨረሻም እግዚአብሔር ለካህናት የሚሆኑ ግልጥ ትእዛዛትን ሰጠ። እነዚህ ትእዛዛት ማን ካህን ሊሆን እንደሚችል፥ ካህን ማንን ማግባት እንደሚችልና እግዚአብሔርን እንዴት ማገልገል እንዳለበት የሚገልጡ ነበሩ (ዘሌ. 21-22)። የተቀደሰውን አምልኮ በመምራት ረገድ ዋናው ኃላፊነታቸው መሥዋዕትን ማቅረብ ስለነበር፥ በተለይ ይህን በሚመለከት እግዚአብሔር ለካህናት ግልጥ የሆነ ትእዛዝን ሰጣቸው።

| |
|---|
| 17ኛ ጥያቄ፥ ስለ እግዚአብሔር፥ ስለ ኃጢአት፥ ከእግዚአብሔር ጋርና እርስ በርስ ሊኖረን ስለሚገባ ግንኙነት ከእነዚህ ምዕራፎች የምንማራቸው ነገሮች ምንድን ናቸው? |

## 4ኛ ቀን:- ዘሌዋውያን 23-27

ሰዎች እግዚአብሔርን የሚያመልኩባቸው የተለዩ ቀናት ከሌሎቻቸው በቀር፥ የሳምንቱን ቀናት በሙሉ በሥራ ወደ ማሳለፍ በማዘንበል፥ ስለ መንፈሳዊ ነገር ለማሰብና እግዚአብሔርን ለማምለክ ጊዜ ሊያጡ ይችላሉ። ለአይሁድ ከተለመደው ዕለታዊ ተግባራቸው ዞር የሚሉባቸውንና ስለ እግዚአብሔር በማሰብ እርሱን የሚያመልኩባቸው የተለያዩ ሃይማኖታዊ በዓላትን ሰጣቸው። አይሁድ ሳምንታዊ የአምልኮ ቀን፥ ወርኃዊ የአምልኮ ቀን፥ በየዓመቱ የሚደረጉ ሰባት የአምልኮ ቀናት፥ በየሰባት ዓመቱ የሚሆን የአምልኮ ዓመትና በየ50 ዓመቱ የሚፈጸም ልዩ የአምልኮ ጊዜ ነበራቸው።

| |
|---|
| 18ኛ ጥያቄ፥ ሀ) እኛ የምንጠቀምባቸው ዋና ዋና ሃይማኖታዊ በዓላት የትኞቹ ናቸው? ለ) ትኩረታችንን የበለጠ በእግዚአብሔር ላይ እንድናደርግ የሚረዱን እንዴት ነው? |

19ኛ ጥያቄ፣ ዘሌ. 23-27 አንብብ። ሀ) የተለያዩ የአምልኮ ቀናትንና ዓላማቸውን ዘርዝር። ለ) እግዚአብሔርን በመታዘዝ የሚገኙ በረከቶችና ባለመታዘዝ የሚመጡ ቅጣቶች ምንድን ናቸው? ሐ) ለእግዚአብሔር የተገባ ስዕለትን ወይም ቃል ኪዳንን ስለመጠበቅ በዚህ ስፍራ የተሰጠው ትምህርት ምንድን ነው?

## 1. ሃይማኖታዊ በዓላት (ዘሌ. 23)

አይሁድ እርሱን ለማምለክ መለየት ስለሚገባቸው ቀናት እግዚአብሔር በግልጥ አዘአቸዋል። በመጀመሪያ፣ ሳምንታዊ የአምልኮ ቀን የሆነው ሰንበት ወይም ቅዳሜ ነው። እግዚአብሔር ከመፍጠር ሥራው ያረፈበትን የሰንበት ቀን ማንም ሰው በማክበር ማረፍና እግዚአብሔርን ማምለክ ስላለበት፣ በሰንበት እንዲሠራ አይፈቀድለትም ነበር።

ሁለተኛ፣ የወር መባቻ የተባለው ወርሐዊ የአምልኮ ቀን ነበር፤(ዘኁል. 10:10)። ይህ ቀን እግዚአብሔር ለአይሁዳውያን ሌላ ወር ስለሰጣቸው ለመታሰቢያ የሚያከብሩት ዕለት ነው።

ሦስተኛ፣ ዓመታዊ የአምልኮ ቀናት ነበሩ። እነዚህንም በዓላት በሰንጠረዥ መመልከት ይቻላል:-

| የበዓሉ ቀን ስም | ቀኑ | የበዓሉ አላማ | በዓሉ የሚያመለክተው ትንቢት | የሚገኝበት ክፍል |
|---|---|---|---|---|
| ፋሲካ | አንደኛ ወር (መጋቢትና ሚያዝያ) | እስራኤላውያን ከግብፅ ነፃ የወጡበት ቀን መታሰቢያ (ለአንድ ቀን) | ክርስቶስ የፋሲካው በግ መሆኑን ለማሳየት | ዘጸ. 12፡1–4 ዘሌ. 23፡5 (1ኛ ቆሮ. 5፡7) |
| የቂጣ በዓል | አንደኛ ወር ከፋሲካ በኋላ ወዲያውኑ | እግዚአብሔር ከግብፅ አቻኩሎ ነፃ እንዳወጣቸው (ለ1 ሳምንት) | ክርስቶስ ኃጢአት የሌለበት የእግዚአብሔር በግ መሆኑንና እኛም እንዴት ቅዱሳን መሆን እንዳለብን ለማሳየት (1ኛ ቆሮ. 5፡6–8) | ዘጸ. 12፡15–20 ዘሌ. 23፡6–8 |
| የበኩራት በዓል | በቂጣ በዓል ጊዜ ውስጥ (1ኛ ወር) | ምርቱንና የሚያስፈልጋቸውን የሚሰጣቸው እግዚአብሔር እንደሆነ ለማሳሰብ (ለ1 ቀን) | የክርስቶስ ትንሣኤ የበኩራት መሆኑን ለማሳየት (1ኛ ቆሮ. 15፡20–23) | ዘሌ. 23፡9–14 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| በዓለ ኀምሣ | ከፋሲካ በኋላ 50ኛ ቀናት (ግንቦት–ሰኔ) | የመከር መጨረሻንና የእግዚአብሔር የለጋስነት ስጦታን ለማክበር (ለ1 ቀን) | የቤተ ክርስቲያን ጅማሬ (የሐዋ. 2) | ዘሌ. 23፤9–14 |
| የመለኮት ድምፅ | የሰባተኛው ወር የመጀመሪያ ቀን(መስከረም–ጥቅምት) | ከሁሉም በላይ የተቀደሰውን ሰባተኛ ወር ለመጀመር፥ ሃይማኖታዊ አዲስ ዓመት ለመጀመር እስራኤልን ለእግዚአብሔር በጎነት ለማስረከብ (ለ1 ቀን) | የወደፊቱን የእስራኤልን መሰብሰብ ለማመልከት | ዘሌ. 23፤23–25 |
| የስርየት ቀን | በሰባተኛው ወር (መስከረም–ጥቅምት) | ለሕዝቡ ኃጢአት መሥዋዕት ለማቅረብ፤ ቤተ መቅደሱን ለአምልኮ ለማንጻት (1ኛ ቀን) | የክርስቶስን ሞት ለማመልከት (ሮሜ 3፤24–26) የወደፊቱን የእስራኤል ንስሐ ለማመልከት (ዘካ 12) | ዘሌ. 16፤ 23፥ 26–32 |
| የዳስ በዓል | በሰባተኛ ወር (መስከረም–ጥቅምት) | ለምርቱ ምስጋናን ለማቅረብ፤ የአርባ አመት የምድረበዳ ኑሮ ለማስታወስ፥ (1ኛ ሳምንት) | የወደፊቱን የእስራኤልን መንግሥት ለማመልከት | ዘሌ. 23–33–36 |

። አንዳንዶቹ የበዓል ቀናት ክርስቶስን የሚያመለክቱ መሆናቸው ግልፕ የሆነው ከአዲስ ኪዳን ትምህርት ነው። ነገር ግን አንዳንዶቹ በዓላት ስለ ክርስቶስ የሚያሳዩ ናቸው የሚለውን ግምታዊ አስተሳሰብ አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁራን ሲስማሙባቸው በሌሎቹ ግን ተቀባይነትን አላገኙም።

አራተኛ፥ ዓመታዊ ሰንበት የሚባል በየሰባት ዓመቱ የሚመጣ አንድ ልዩ በዓል ነበር (ዘሌ. 25፡1-7)። በዚህ ዓመት ሊያርሱም ሆነ መከር ሊሰበስቡ አይችሉም ነበር። ይህ ለእስራኤላውያን የሚያስተምረው መከሩ የሚመጣው ከእግዚአብሔር እንደሆነና ለምግባቸውም መታመን ያለባቸው በእግዚአብሔር እንጂ በራሳቸው ሥራ አለመሆኑን ነው።

አምስተኛ፥ የኢዮቤልዩ ዓመት የሚባልም ነበር (ዘሌ. 25፡8-55)። ይህ አምሳኛው ዓመት ወይም እንደ አይሁድ አቆጣጠር፥ የዓመታት ሰንበት ሰባተኛ ዙር ነው። በዚህ ዓመት ከማምረትና መከርን ከመሰብሰብ ማረፍ ብቻ ሳይሆን፥ ባሪያዎች ሁሉ ነፃ ይሆናሉ። መሬት በሙሉ ለባለቤቱ ይመለሳል። ይህም እነርሱም ባሪያዎች እንደነበሩ በማሰብ ለባሮች መራራት እንዳለባቸው እስራኤላውያንን ለማስተማር ነበር። መሬትን ለቀድሞ ባለንብረቶች የመመለሱ ሥርዓትም፥ ሀብታሞች የበለጠ እየበለጸጉ እንዳይሄዱና ድሆችም ምድራቸውን ሁሉ በማጣት የበለጠ ድሆች እንዳይሆኑ የሚከላከል ነው። እንዲሁም መሬት የእግዚአብሔር እንጂ የራሳቸው እንዳልሆነ ተገንዝበው፥ ለረጅም ጊዜ ማከራየት እንጂ መሸጥ እንደሌለባቸው ለማሳሰብ ነው።

ስለ ሃይማኖታዊ ቀናት የሚከተሉትን ነገሮች አስተውል፡- 1. በቁጥር 7 ላይ ትኩረት አለ። ሰባት በዓላት አሉ፤ አብዛኛዎቹ በዓላት ደግሞ በሰባተኛው ወር የሚከበሩ ናቸው። እያንዳንዱ ሰባተኛው ዓመትና የዓመታቱ ሰባት ሱባዔዎች በሙሉ የተቀደሱ ናቸው፤ ምክንያቱም በአይሁዳውያን አእምሮ ሰባት ፍጹምነትንና ብቃትን የሚያመለክት ልዩ ቁጥር ነው።

2. አይሁዳውያን ወንዶች ሁሉ ወደ ቤተ መቅደስ ሄደው እንዲያከብሩ የሚፈለግባቸው ሦስት በዓላት ነበሩ። እነርሱም ፋሲካ፥ በዓለ ኀምሳና የዳስ በዓል ነበሩ።

3. እነዚህ በዓላት ለአይሁዳውያን የማስተማሪያ መሣሪያዎች ነበሩ። እያንዳንዱ በዓል እግዚአብሔር ለልጆቻቸው ቀድሞ ምን እንዳደረገላቸው ለማስተማርና ራሳቸውንም ለማሳሰብ አመቺ ጊዜያት ነበሩ። (ለምሳሌ፡- በግብፅ በባርነት የነበሩበትን ጊዜና እንዴት ነፃ እንደወጡ) ደግሞም ለየዕለቱ በሚያስፈልጋቸው ነገር በእግዚአብሔር ላይ ያለማቋረጥ እንዴት ይደገፉ እንደነበር የሚያሳስቧቸው ነበሩ።

| |
|---|
| 20ኛ ጥያቄ፥ ሀ) የእኛ የገናና (የልደት) የፋሲካ (የትንሣኤ) በዓላት ከእነዚህ በዓላት ጋር የሚመሳሰሉት እንዴት ነው? ለ) ቀድሞ እስራኤላውያን ያደርጉት ከነበረው አከባበር ስለእነዚህ በዓላት ዓላማ ምን ልንማር እንችላለን? |

2. በመታዘዝ የሚገኝ በረከትና አለመታዘዝ የሚያስከትለው ቅጣት (ዘሌ. 26)

በሲና ተራራ የተሰጠው ቃል ኪዳን በቅድመ ሁኔታ ላይ የተመሠረተ ነበር። እግዚአብሔር፥ ሕዝቡን ሊባርካቸው ቃል የገባላቸው፥ የሚታዘዙትና የሚከተሉት ከሆነ ብቻ ነበር። ከታዘዙት እግዚአብሔር ምድሪቱን በልግሥናው በሰብል እንደሚባርካት፥ ሰላምን እንደሚሰጣት፥ ለሕዝቡ በጠላቶቻቸው ላይ ድልን እንደሚያቀዳጃቸው፥ እነርሱንና ከብቶቻቸውንም ፍሬያማ እንደሚያደርጋቸው፥ ከሁሉም በላይ በመካከላቸው እንደሚሆንና በልዩ መንገድ እንደሚገናኛቸው ገለጠላቸው።

የማይታዘዙት ከሆነ ግን እነዚህን ነገሮች ሁሉ አያገኙም ነበር። በዘሌ. 26፡14-45 የተጠቀሱት ቅጣቶች፥ በኤርምያስ ዘመን በአይሁድ ላይ ስለደረሱት ነገሮች አስቀድመው የተነገሩ ትንቢቶች መሆናቸውን መመልከት የሚያስገርም ነው።

| |
|---|
| 21ኛ ጥያቄ፥ 2ኛ ዜና 36፡20-21፤ ኤር. 26፡9-11 አንብብ። እነዚህ ጥቅሶች በዘሌ. 26 የተጠቀሱትን አንዳንድ ቅጣቶች የሚገልጹት እንዴት ነው? |

መታዘዝ ከእግዚአብሔር ጋር ላለን ኅብረትና በረከቱን ለመቀበላችን መሠረት ነው። እግዚአብሔርን ከታዘዝን ይባርከናል። በከፍተኛ ሥጋዊ በረከት ሊባርከን ይችላል፤ የየዕለት ምግባችንን ይሰጠናል፤ ሰላምን

በልባችን ያፈሳል፤ የእርሱ መሆናችንን ያረጋግጥልናል፤ ወዘተ። እርሱን ካልታዘዝነው ግን በአንድ ወቅት ሐሴት ስናደርግበት የነበረውን በረከት ከእኛ በመውሰድ ይቀጣናል። ውስጣዊ ሰላማችንና እርሱን የማወቃችንን ደስታ ይወስድብናል፤ ወዘተ። አንድ ጊዜ አንድ ሰው እንዲህ ብሏል:- «እግዚአብሔርን ባለመታዘዝ ከሚመላለስ ክርስቲያን የበለጠ ምስኪን በምድር ላይ የለም።»

22ኛ ጥያቄ፥ ሀ) የዚህን ነገር እውነተኛነት በሕይወትህ ምን ያህል አይተሃል? ለ) በሕይወትህ ምን ዓይነት የተደበቀ ኃጢአት እንዳለ ለመረዳት አሁን ራስህን መርምር። እግዚአብሔር ይቅር እንዲልህና በረከቱን እንዲመልስልህ ጸልይ።

5ኛ ቀን:- የዚህን ሳምንት ትምህርት ከልስና ለሳምንታዊው የስብሰባ ዝግጅት ይረዳህ ዘንድ የውይይት ጥያቄዎችን ተመልከት

## ሳምንታዊ የስብሰባ ጊዜ

1. ሳምንታዊው የአምልኮ ጊዜ
2. ጸሎት
3. የትምህርቱ ክለሳ
4. ውይይት
    1. ሀ) «ቅዱስ» ማለት ምን ማለት ነው? ለ) እግዚአብሔር ቅዱስ የሆነው እንዴት ነው? ሐ) ክርስቲያኖች በሁለቱም የቅድስና ትርጉሞች ቅዱስ የሆኑት እንዴት ነው? መ) የኦሪት ዘሌዋውያን ትምህርት ቅድስናን ለመረዳትና በእግዚአብሔር ፊት ቅዱስ የመሆናችንን አስፈላጊነት ለመገንዘብ እንዴት ይጠቅመናል?
    2. ሀ) አምስቱን የመሥዋዕት ዓይነቶች ዘርዝር። ለ) የእያንዳንዱ መሥዋዕት ዓላማ ምን ነበር? ሐ) በአዲስ ኪዳን እነዚህ ተመሳሳይ ዓላማዎች በክርስቶስ የተፈጸሙት እንዴት ነው? መ) በአዲስ ኪዳን የክርስቲያኖችን መሥዋዕቶች ዘርዝር። ሠ) እነዚህ በቤተ ክርስቲያንህ እየተፈጸሙ ያሉት እንዴት ነው?
    3. ሀ) ስርየት ማለት ምን ማለት ነው? ለ) በብሉይ ኪዳን ስርየት የሚገኘው እንዴት ነበር? ሐ) በአዲስ ኪዳን ስርየት የሚገኘው

እንዴት ነው? መ) ደምን የማፍሰስና ምትክ ሆኖ የማስተሰረይ ትርጉማቸው ምንድን ነው?

4. ሀ) እግዚአብሔር በናዳብና በአብዩድ ላይ ከባድ ፍርድ የሰጠው ለምንድን ነው? ለ) እግዚአብሔር በኃጢአት ላይ ስላለው አቋም ይህ ምን ያስተምረናል? ሐ) እግዚአብሔር ኃጢአትን በሚያደርጉ መሪዎች ላይ ስላለው አቋም ይህ ምን ያስተምረናል?

5. ሀ) በአሪት ዘሌዋውያን ውስጥ ከተሰጡት ሕግጋት እግዚአብሔር እያንዳንዱን የሕይወታችንን ክፍል በሙሉ ለመቆጣጠር ስለመፈለጉ ምን እንማራለን? ለ) የሕይወትን የተለያዩ ክፍሎችን ዘርዝር። (ለምሳሌ፡- ሥራ፥ ት/ቤት) በእነዚህ ስፍራዎች እግዚአብሔርን ልናከብር ወይም ላናከብር የምንችለው እንዴት ነው? መግለጫዎችን ስጥ።

6. ሀ) የአይሁድን ሃይማኖታዊ በዓላት ዘርዝር። ለ) የእነዚህ በዓላት እያንዳንዱ ዓላማ ምን ነበር? ሐ) በእሑድ፥ በጌታችን ልደትና በትንሣኤ በዓላቶቻችን እነዚህን ዓላማዎች እንዴት መፈጸም እንችላለን? መ) ለዛሬው ሕይወታችን ከኢዮቤልዩ በዓል ምን መማር እንችላለን?

7. ከአሪት ዘሌዋውያን ስለ እግዚአብሔር፥ ስለ ኃጢአት፥ ስለ አምልኮ ስለ ሰው ወዘተ. ምን ልንማር እንችላለን?

5. ጸሎት

# ትምህርት ዘጠኝ

## 1ኛ ቀን የኦሪት ዘኍልቊ መግቢያ

እስካሁን ድረስ ከፔንታቱክ መጻሕፍት መካከል የመጀመሪያዎቹ ሦስቱን ማለት ዘፍጥረት፥ ዘጸአትና ዘሌዋውያንን አጥንተናል። በዘፍጥረት እግዚአብሔር፥ አይሁድ የራሱ የተለዩ ሕዝብ እንዲሆኑና እንዲያገለግሉት እንዴት እንደመረጣቸው ተመልክተናል። በዘጸአት ደግሞ እግዚአብሔር ሕዝቡን ከባርነት እንዴት እንደተቤዣቸው አይተናል። ዘሌዋውያን የተዋጁ የእግዚአብሔር ቅዱስ ሕዝብ ሆነው መኖር ይችሉ ዘንድ፥ እግዚአብሔር ለአይሁድ ሕዝብ ስለሰጣቸው ሕግጋት ይናገራል። ዛሬ ደግሞ የእስራኤል ሕዝብ እምነትን በማጣቱ ምክንያት በእግዚአብሔር ተቀጥቶ በምድረ በዳ ለ40 ዓመታት እንደተንከራተተ የሚናገረውን ኦሪት ዘኍልቊን እናጠናለን።

| |
|---|
| 1ኛ ጥያቄ ሀ) የክርስቲያን ሕይወት እንደጉዞ የሚቆጠረው እንዴት ነው? ለ) የክርስቲያን የሕይወት ጉዞ ጅማሬ ምንድን ነው? ሐ) የጉዞው መጨረሻስ ምንድን ነው? መ) የራስህን ጉዞ የጀመርከው መቼ ነው? |

የክርስቲያን መንፈሳዊ አካሄድ በጉዞ መልክ በጥሩ ሁኔታ ተገልጿል። የክርስቲያን ሕይወት ዕድሜ ልክ የሚጠይቅ ረጅም ጉዞ ነው። አንዳንዶች ይህ ጉዞ «የመናኝ» ጉዞ ነው ይሉታል። ለክርስቲያኖች ይህ ጉዞ የተጀመረው በክርስቶስ ኢየሱስ በማመን በዳኑበት ጊዜ ነው። ጉዞውንም የምናጠቃልለው መንግሥተ ሰማያት ስንደርስ ነው። በጣም አስፈላጊ ነገር የጉዞው መጀመሪያ ሳይሆን፥ መንግሥተ ሰማያት እስክንደርስ ድረስ ጉዞውን እንዴት እንደምንጓዝ ነው። የድልና የመንፈሳዊ እድገት መንገድ ልንጓዝ፥ እንችላለን። ወይም ደግሞ የመንፈሳዊ ሕይወት ሽንፈትና የእምነት ጉድለት ጉዞ ልንጓዝ እንችላለን። የእምነት ጉድለትና አለመታዘዝ የሚታይበት ሕይወት ለመኖር ከመረጥን በግል የምንከፍላቸው በርካታ ዕዳዎች ይኖራሉ።

እግዚአብሔር የእስራኤልን ሕዝብ ከግብፅ ባርነት ነፃ ካወጣቸው በኋላ ወደ ተስፋይቱ ምድር የሚያደርጉትን ጉዞ ጀመሩ። ከሦስት

ወራት በኋላ በሲና ተራራ ራሱን ከገለጠላቸውና የእርሱ ሕዝብ በመሆናቸው የተለዩ የሚያደርጋቸውን ግልጽ ትእዛዛት ከሰጣቸው ከእግዚአብሔር ጋር ተገናኙ። በኦሪት ዘኍልቁ ወደ ከነዓን የሚደረገው ጉዞ ቀጥሎ እንመለከታለን። ከነዓን ለመድረስ ጥቂት ሳምንታት ብቻ ይፈጅ የነበረው ጉዞ 40 ዓመታት ወሰደ። ለምን? ምክንያቱም የእስራኤል ሕዝብ አለማመንና አለመታዘዝ ነበር። ኦሪት ዘኍልቁ በመንፈሳዊ ሕይወት ጉዞአችን እንዴት መራመድ እንደሌለብን የሚያሳዩ በርካታ ምሳሌዎችን፥ አለማመንና አለመታዘዝ የሚያስከትለውን ክፉ ፍሬ ያሳየናል። ስለዚህ ከእነዚህ ትምህርቶች በመጠቀም በመንፈሳዊ ሕይወታችን እግዚአብሔርን ሙሉ በሙሉ ለመታዘዝና ለታይታ ሳይሆን በእምነት ለመራመድ መወሰን አለብን።

> 2ኛ ጥያቄ፥ ሀ) ባለማመንና ባለመታዘዝ የተጎዝክባቸው ጊዜያት የትኞቹ ናቸው? በዚያን ጊዜ ምን ሆነ? ለ) ለእግዚአብሔር በመታዘዝና በእርሱ በማመን የኖርክባቸው ጊዜያት የትኞቹ ናቸው? ሐ) እምነትን በማጣት ከተራመድክባቸው ጊዜያት እነዚህ በምን ይለያሉ?

ኦሪት ዘኍልቁ ከኦሪት ዘጸአትና ዘሌዋውያን የሚቀጥል ታሪክ ነው። እስራኤላውያን ከሲና ተራራ ተነሥተው በከነዓን ምድር መግቢያ ድረስ ያደረጉትን ጉዞ ይገልጻል። በኦሪት ዘኍልቁ ታሪክ እግዚአብሔር እስራኤላውያንን በምድረ በዳ እንዴት እንደፈተናቸው በእግዚአብሔር ላይ ያለማቋረጥ እንዴት እንዳመፁ እንመለከታለን። ሕዝቡ ባለመታዘዛቸው ምክንያት ወደ ተስፋይቱ ምድር እንዲገቡ እግዚአብሔር ከመፍቀዱ በፊት፥ እንዴት አንድ ትውልድ በሙሉ እንዲጠፋ እንዳደረገ እንመለከታለን።

> 3ኛ ጥያቄ፥ ስለ ኦሪት ዘኍልቁ ከመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት አንብብ። ሀ) የኦሪት ዘኍልቁ ዋና ታሪክ ምንድን ነው? ለ) በመዝገበ ቃላት ውስጥ የሚገኘውን የመጽሐፉን አስተዋጽኦ ገልብጥ። ሐ) «ዘኍልቁ» የሚለው ቃል በአማርኛ ምን ማለት ነው? ትርጉሙን የማታውቅ ከሆነ ግዕዝ የሚያውቅ ሰው ፈልገህ ትርጉሙን ለመረዳት ሞክር (የኦርቶዶክስ ቄስ በዚህ ሊተባበርህ ይችላል)።

## የመጽሐፉ ርእስ

ከፔንታቱክ መጻሕፍት ውስጥ የአራተኛው መጽሐፍ ርእስ በአማርኛ «ዘኍልቊ» የሚል ሲሆን ትርጉሙም «መቁጠር» ማለት ነው። ይህ ርእስ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ አይሁዳውያን ሁለት ጊዜ የመቆጠራቸውን ታሪክ ያመለክታል (ዘኍል.1 እና 26)። የዚህ ርእስ ምንጭ ሴፕቱዋጀንት የተባለው የግሪክ መጽሐፍ ቅዱስ ነው።

በዕብራይስጡ መጽሐፍ ቅዱስ ግን የዚህ መጽሐፍ ርእስ «በምድረ በዳ ውስጥ» የሚል ነው። ይህ ቃል የተገኘው በመጽሐፉ ውስጥ ከሚገኘው የመጀመሪያ ዓረፍተ ነገር ከተወሰዱት ቃላት ነው። ይህ ርእስ በአማርኛም ሆነ በእንግሊዝኛ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከሚገኙት ርእሶች በብዙ ረገድ የተሻለ ነው። ምክንያቱም የአሪት ዘኍልቊ ዋና ታሪክ እስራኤላውያን በእግዚአብሔር ባለማመናቸው ምክንያት ለ40 ዓመታት በምድረ በዳ እንደተንከራተቱ ስለሚናገር ነው።

## ጸሐፊው

እንደቀሩት የፔንታቱክ መጻሕፍት ሁሉ የዘኍልቊ ጸሐፊ ማንነት የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁራን የሚያከራክር ሆኖ ቆይቶአል። የፔንታቱክ ጸሐፊ ማን እንደሆነ በጥልቀት ለመረዳት ወደ ኋላ ተመልሰህ ትምህርት ሦስትን መመልከት ትችላለህ። ክርስቲያኖችም ሆኑ አይሁድ የዚህ መጽሐፍ ጸሐፊ ሙሴ በመሆኑ አጥብቀው ይስማማሉ። ስለዚህ ዋናው የዘኍልቊ ጸሐፊ ሙሴ መሆኑን ማመን የተሻለ ነው (ዘኍል. 33፡2)። ሙሴ በዘኍልቊ ውስጥ የሚገኙትን አንዳንድ ነገሮች በቀጥታ ከእግዚአብሔር ተቀብሏል። በዘኍልቊ የተፈጸሙትን አብዛኛዎቹን ነገሮች በግል ተለማምዶአቸዋል። በጊዜው የነበሩትንም ሌሎች መጻሕፍት ተጠቅሞባቸዋል። ለምሳሌ ሙሴ፥ ምሁራን «የበለዓም መዝሙራት» (ዘኍል. 22-24)፥ «የሐሴቦን መዝሙር» (ዘኍል. 21፡27-30) እና «የጌታ ጦርነት መጽሐፍ» ብለው የሚጠሯቸውን መጻሕፍት አሪት ዘኍልቊን ለመጻፍ ተጠቅሞባቸዋል (ዘኍል. 21፡14-18 ተመልከት)። በመጽሐፉ ውስጥ ሙሴ ብዙ ጊዜ የሚጠቀሰው እንደ ሦስተኛ ሰው በመሆኑና (ዘኍል. 12፡3፤ 15፡22-23) እንዲሁም አንዳንድ የተጻፉ አስተያየቶችም መጽሐፉን በሌላ አቀናባሪ የተዘጋጀ ስለሚያስመስሉት (ምሳሌ፡- ዘኍል.

13፡11፤ 27፡14፤ 31፡53) ሙሴ ከጻፈው ከብዙ ዓመታት በኋላ፥ ሌላ ሰው አቀናብሮት ይሆናል።

## የኦሪት ዘኁልቊ ታሪካዊ ማጠቃለያ

የኦሪት ዘኁልቊ ታሪክ 38 ዓመታት ከ9 ወር የፈጀ ታሪክ ነው። ይህ መጽሐፍ የእስራኤል ሕዝብ በምድረ በዳ ስለመንከራተታቸው ይናገራል። ታሪኩ በሦስት ዋና ዋና ክፍለ-ጊዜያት ይከፈላል፦

1. በሲና ተራራ (ይህ የመገናኛው ድንኳን ተሠርቶ ካለቀበት ጊዜ ጀምሮ የእግዚአብሔር የክብር ደመና ሕዝቡን መምራት እስከ ጀመረበት ድረስ ያለው የ20 ቀናት ጊዜ ነው) (ዘኁል. 1-10፡11)።
2. በምድረ በዳ መንከራተት (ሕዝቡ በእግዚአብሔር ላይ በማመፃቸው የተንከራተቱበት የ38 ዓመታት ጊዜ) (ዘኁል. 10፡11-20፡13)።
3. ከቃዴስ እስከሞዓብ ምድር ድረስ የተደረገ ጉዞ (6 ወራት) (ዘኁል. 20፡14-36፡13)።

## የኦሪት ዘኁልቊ አስተዋጽኦ

1. እስራኤላውያን በሲና ተራራ (1፡1-10፡11)
2. ከሲና ተራራ እስከ ቃዴስ በርኔ የተደረገ ጉዞ (10፡11-13፡25)
3. የእስራኤላውያን በቃዴስ መሰፈርና ያ ትውልድ ሁሉ እስኪያልቅ ድረስ በምድረ በዳ መንከራተታቸው (13፡26-20፡21)።
4. ተተኪው የእስራኤል ትውልድ ከቃዴስ እስከሞዓብ ምድር ያደረገው ጉዞ (20፡22-21፡35)
5. የእስራኤላውያን በሞአብ ምድር መስፈር (22-36)

## የኦሪት ዘኁልቊ ዓላማና መልእክት

1. በመሠረቱ የኦሪት ዘኁልቊ ታሪክ፥ የእስራኤል ሕዝብ ከሲና ተራራ ጀምሮ እስከ ከነዓን ምድር ያደረገውን ጉዞ በአጭሩ የሚያቀርብ ነው። እስራኤላውያን በእግዚአብሔር ባለማመናቸው ምክንያት ወደ ከነዓን ምድር ለመግባት አለመቻላቸውንና በእነርሱ ላይ ስለ ተሠጠው የእግዚአብሔር ፍርድ የሚናገር ታሪክ ነው።

በአራት ዘፍጥረት ተጀምሮ በዘጸአትና በዘሌዋውያንም የቀጠለው የእስራኤል ሕዝብ ታሪክ አካል ነው።

2. እንደቀረው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል አራት ዘኍልቁም ስለ እግዚአብሔር ባሕርይ በግልጽ ያስተምረናል። መጽሐፉን በምታጠናበት ጊዜ፥ የሚከተሉትን የእግዚአብሔር ባሕርያት አስተውል:-

   ሀ. እግዚአብሔር ሕዝቡ በማይታዘዘው ጊዜም ቢሆን ታጋሽ ነበር። ኃጢአት በሚሠሩበት ጊዜ ጨርሶ አያጠፋቸውም። ነገር ግን ፈጥኖ ይቅር ይላቸዋል። ጸሎታቸውን ከመመለስና ፍላጎታቸውን ሁሉ ከማሟላት አይዘገይም።

   ለ. እግዚአብሔር «ቀናተኛና» ቅዱስ አምላክ ነው። ለእርሱ የሚገባውን ክብሩን ለመጠበቅ ቀናተኛ ነው። እርሱ ቅዱስ ነው፤ ማለትም ኃጢአት በሚፈጸምበት ጊዜ ተገቢውን ፍርድ ይሰጣል።

   ሐ. እግዚአብሔር ሕዝቡን «ለመፈተን» አስቸጋሪ ሁኔታዎችን ተጠቅሟል (ዘዳ. 8፡1-2 ተመልከት)። የአዳምን (ዘፍ. 2፡15-17)፥ የአብርሃምን (ዘፍ. 22፡1-14)፥ የዮሴፍን (ዘፍ. 22፡1-17) እምነት ለመፈተን አስቸጋሪ ሁኔታዎችን ተጠቀመ። እግዚአብሔር ፈተናን ወደ ሕዝቡ የሚልከው ሊያጠፋቸው ወይም ኃጢአት እንዲሠሩ ለማድረግ ሳይሆን፥ እምነታቸውን ለማጠንከር ነው።

> 4ኛ ጥያቄ፥ ያዕ. 1፡2-4 ና ሮሜ 5፡3-5 አንብብ። ሀ) ፈተና በሕይወታችን ውስጥ የሚቀርጻቸውንና የሚገነባቸውን ባሕርያት ዘርዝር። ለ) ይህ በሕይወትህ እንዴት ሲፈጸም አየህ? ሐ) ብዙ ክርስቲያኖች በሕይወታቸው ላይ ፈተና በሚደርስበት ጊዜ የሚያጉረመርሙት ለምንድን ነው? (1ኛ ዜና 29፡17፤ ኤር. 11፡20፤ መዝ. (139)፡23፤ ኢሳ. 48፡10-11 ተመልከት)።

እግዚአብሔር የእስራኤልን ሕዝብ የፈተነው ለምንድን ነው? ምናልባት ለዚህ ሦስት ምክንያቶችን መጥቀስ እንችላለን።

1) የእስራኤልን ሕዝብ ትሑት ለማድረግና የቃል ኪዳኑን ቅድመ ሁኔታዎች ለማሟላት፥ በእግዚአብሔር ብቻ መታመን እንዳለባቸው ለማስተማር ነበር። የብርታታቸው ምንጭ እርሱ እንደሆነ እግዚአብሔር ሊያስተምራቸው ይፈልግ ነበር።

2) እስራኤላውያን የእግዚአብሔርን በረከት ለመቀበል ለእርሱ በጥንቃቄ መታዘዝና በእርሱ ላይ መደገፍ እንዳለባቸው ለማስተማር ነበር። እግዚአብሔር የሚፈልገው ከፊል መታዘዝን ሳይሆን ፍጹም የሆነ መታዘዝን ነው። እግዚአብሔርን በከፊል ብቻ ስንታዘዘው ዓመፅ ስለሆነ፥ ሕዝቡን ከኃጢአት ለማንጻት ፍርድን ያመጣል።

3) የእስራኤላውያንን ውስጣዊ የልብ ሁኔታ በግልጽ ለማሳየት ነበር። ነገሮች ሁሉ በተመቻቹ ጊዜ በእግዚአብሔር መደገፍ እጅግ ቀላል ነው፤ ነገር ግን በእግዚአብሔር ላይ በእርግጥ እንደምንደገፍ የሚያሳዩን አስቸጋሪ ጊዜያት ናቸው (ዕብ. 3፡16-4፡2)። የሚያሳዝነው ግን እግዚአብሔር እስራኤላውያንን በፈተናቸው ጊዜ፥ በፈተናቸው ወደቁ። እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ከግብፅ አውጥቶአቸዋል። ዳሩ ግን አሁንም የግብፅ አለማመንና ውሸት በልባቸው ስለቀረ የተቀደሰ የእግዚአብሔር ሕዝብ ሆነው ወደ ተስፋይቱ ምድር ከመግባታቸው በፊት መንጻት ነበረባቸው። ስለዚህ እግዚአብሔር በእርሱ ላይ መታመንና ለእርሱ መታዘዝን ለማስተማር 38 ዓመታት በምድረ በዳ እንዲንከራተቱ ማድረግ ነበረበት።

5ኛ ጥያቄ፥ ሀ) እነዚህ ትምህርቶች ለዛሬስ የሚያስፈልጉን እንዴት ነው? ለ) በአሁኑ ጊዜ ያሉ ክርስቲያኖች ምላሽ በምድረ በዳ ከነበሩት አይሁድ ምላሽ ጋር የሚመሳሰለው እንዴት ነው? ሐ) ሕይወታችንን ከኃጢአት ፍላጎትና ዓለምን ከመምሰል ለማንጻት የምንቸገረው ለምንድን ነው?

መ. እግዚአብሔር ለእስራኤልና ለአብርሃም የገባውን ቃል ኪዳን ጠበቀ:- አብዛኞቹ እስራኤላውያን ባለማመናቸው እግዚአብሔር ቢፈርድባቸውም፥ በትዕግሥት እርሱን

ሊያከብሩ የሚችሉ ሕዝብ ያደርጋቸው ዘንድ የተለያዩ ተግባራትን ፈጸመ እንጂ፥ ሕዝቡን አላጠፋም። እግዚአብሔር ባሪያ የነበሩትን ሕዝቦችን ወስደና አንድ ነፃ ሕዝብ በማድረግ ከእነርሱ ጋር በሲና ተራራ የገባውን ቃል ኪዳን ለመፈጸም ይችሉ ዘንድ አዘጋጃቸው።

ሠ. እግዚአብሔር ተከታዩ የእስራኤል ትውልድ በእርሱ ማመንና ለእርሱ መታዘዝ እንደሚገባቸው ለማስጠንቀቅ ፈልጎ ነበር። አለበለዚያ፥ አባቶቻቸው በምድረ በዳ ያጋጠማቸው ዓይነት ፍርድ ያገኛቸዋል።

ረ. እግዚአብሔር ባለማመንና በዓመፅ ላይ ፈረደ። በብዙ ረገድ የኦሪት ዘኁልቁ ታሪክ ያለማመን፥ ያለመታዘዝና በዚህም ምክንያት በሕዝቡ ላይ የመጣው ፍርድ ታሪክ ነው። የእግዚአብሔር ሕዝብ በኃጢአታቸው ምክንያት ስላገኛቸው ፍርድና ሞት የተዘገበ ታሪክ ነው። ግልጽ የሆነው የኃጢአት ባሕርይ በእግዚአብሔር ላይ ማመፅ መሆኑን ያሳያል። ኃጢአት ድንገተኛ ስሕተት ወይም ያልታሰበ ክስተት አይደለም። ሆን ብሎ በእግዚአብሔር ላይ በግልጽ ማመፅ ነው።

በመንፈሳዊ ረገድ ኦሪት ዘኁልቁ የሚናገረው፥ ስለ እምነት እርምጃ፥ ይልቁንም ያለማመን ውጤቶችን በሚመለከት ነው። የእግዚአብሔር ሕዝብ፥ በእምነትና በመታዘዝ ከመኖር ይልቅ፥ ባለመታዘዝና ባለማመን የመመላለስ ዝንባሌ ነበራቸው። ስለዚህ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ያለማቋረጥ መንፈሳዊ ብስለት ያድጉ ዘንድ አባሎቻቸውን ሊያበረታቱ ይገባል። እኛ ወይ እያደግን ነው፥ አልያም አለማመንና አለመታዘዝ ወዳለበት ሥጋዊ ሕይወት እየተንሸራተትን ነው። የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ቤተ ክርስቲያን ጥልቅ የሆነ መንፈሳዊ ሞገስዋን ትታ፥ እግዚአብሔርን በግማሽ ልብ ማምለክ እንዳትጀምር መጠንቀቅ አለባቸው። አምልኮ ሥነ -ሥርዓት ብቻ ከሆነና በቤተ ክርስቲያን አባሎች ሕይወት ውስጥ ዕለታዊ መታዘዝ እንዲኖር የማያደርግ ከሆነ፥ በመጨረሻ ቤተ ክርስቲያን ትሞታለች።

6ኛ ጥያቄ፥ እነዚህን የአራት ዘኍልቁ መሠረታዊ ትምህርቶች ስትመለከት፥ ክርስቲያን ይህን መጽሐፍ ማጥናት የሚያስፈልገው ለምንድን ነው ብለህ ታስባለህ?

## 2ኛ ቀን ዘኍልቁ 1-12

የእግዚአብሔርን ሕዝብ በጥሩ ሁኔታ ለመምራት ጥሩ አደረጃጀት ያስፈልጋል። ጥሩ አደረጃጀት ከሌለ መምራት በጣም አስቸጋሪ ይሆናል፤ ሕዝቡም ስለሚምታታበት፥ የእግዚአብሔር ሥራ እንደሚጠበቀው ስኬታማ አይሆንም። ስለዚህ የእስራኤል ሕዝብ የሲና ተራራን ለቆ ወደ ቃዴስ በርኔ፥ ከዚያም ወደ ተስፋይቱ ምድር ከመሄዱ በፊት ሕዝቡን ለማደራጀት ይረዳው ዘንድ እግዚአብሔር ግልጥ ትእዛዛትን ሰጠ። ይህም ግራ መጋባትንና ውጤት አልባነትን ተከላከለ።

7ኛ ጥያቄ ሀ) ደካማ አደረጃጀት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንዴት ግራ መጋባትን እንደሚፈጥር አይተህ ታውቃለህ? ለ) የእግዚአብሔር ሥራ በሚገባ ከግብ እንዲደርስ መልካም አደረጃጀት የሚጫወተውን ሚና ጥቀስ። ሐ) ቤተ ክርስቲያንህ እንዴት እንደተደራጀች ግለጥ። መ) ከዚህ በተሻለ ሁኔታ እንዴት ልትደራጅ እንደምትችል አብራራ።

8ኛ ጥያቄ፥ ዘኍልቁ 1-12 አንብብ ሀ) እግዚአብሔር ሕዝቡ ይቆጠር ዘንድ ሙሴን ያዘዘው ለምን ነበር? ለ) የእያንዳንዱ ነገድ ሕዝብ ብዛት ምን ያህል እንደነበር ግለጥ።

3) ሕዝቡ በአጠቃላይ ምን ያህል ነበር? 4) ይህንን ዝርዝር በዘኍልቁ ምዕራፍ 26 ከሚገኘው ቁጥር ጋር አወዳድር። 5) በዘኍልቁ 26 ያለው ጠቅላላ ቁጥራቸውስ ምን ያህል ነበር?

ለ. 1) የእስራኤላውያን አሰፋፈር እንዴት ልሆን እንደሚገባ እግዚአብሔር ባዘዘው መሠረት አደረጃጀቱን የሚገልጥ ሥዕላዊ መግለጫ አቅርብ። 2) የመገናኛው ድንኳን አቀማመጥና የእያንዳንዱ ነገድ አሰፋፈር እንዴት ነበር?

ሐ. የተለያዩት የሌዋውያን ብድኖች ኃላፊነት ምን ነበር?

መ. እስራኤላውያን ወደ ቃዴስ በርኔ በሚጓዙበት ጊዜ ያለፉባቸውን የተለያዩ ቦታዎችና በእያንዳንዱም ቦታ ምን እንደተፈጸመ ተናገር። በመጽሐፉ ጀርባ ከሚገኘው ካርታ ጉዞአቸውን እይ።

ሠ አሮን ማርያም እግዚአብሔርን ያሳዘነ ምን ነገር ፈጸሙ?

1. እስራኤላውያን በሲና ተራራ ሰፈሩ (ዘኅ. 1-10)

ሀ. የእስርኤላውያን መቆጠር (ዘኍ. 1)

እንደምናስታውሰው፥ አራተኛው የፔንታቱክ መጽሐፍ ርዕስ በአማርኛ «ዘኍልቁ» የሚል ነው። ዘኍ. ምዕ. 1ና 26 የእስራኤል ሕዝብ ሁለት ጊዜ መቆጠራቸውን ያሳያሉ። ዘኍ. 1 የመጀመሪያው የእስራኤል ትውልድ ወደ ተስፋይቱ ምድር ጉዞ ከመጀመራቸው ጥቂት ቀደም ብሎ የተደረገውን ቆጠራ የሚያሳይ ሲሆን፥ ዘኍ. 26 ደግሞ ሁለተኛው የእስራኤል ትውልድ ወደ ከነዓን ከመግባታቸው በፊት የተደረገ ቆጠራ ነው።

የቆጠራው ዓላማ ምን ነበር? አራት ዋና ዋና ምክንያቶች ነበሩ? 1) ለመዋጋት የሚችሉ ስንት ወንዶች እንዳሉ ለምዋወቅ (ዘኍ. 1፡3 ተመልከት)፤ 2) የተለያዩ ተግባራት እንዲያከናውኑ ለማድረግ ስንት ሰዎች እንዳሉ ለማወቅ (ዘኍ. 3፡4)፤ 3) የእግዚአብሔር ሕዝብ ለሥራው አስራት እንዲሰጡ ለማድረግ (ዘጸ. 30፡11-16)፤ 4) የከነዓንን ምድር እንደየነገዱ ብዛት ለመከፋፈል (ዘኍ. 26፡53)።

| |
|---|
| 9ኛ ጥያቄ፥ ሀ) አንተ ባለህበት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ስንት ክርስቲያኖች እንዳሉ ማወቅ መልካም የሚሆነው ለምንድን ነው? ለ) የቤተ ክርስቲያንህን አባሎች ጠቅላላ ቁጥር አግኝ። ሐ) 2ኛ ሳሙ.24፡1-10 አንብብ። በዚህ ስፍራ የዳዊት ሕዝቡን መቁጠር ስሕተት የሆነው ለምንድነው? መ) የቤተ ክርስቲያናችንን አባሎች ስለ መቁጠር ይህ ምን ማስጠንቀቂያ ይሰጠናል? |

በቤተ ክርስቲያንህ ያሉትን ሰዎች ብዛት መቁጠር ስሕተት አይደለም። የዚህ ዓይነት እውነታዎችን ማወቅ እንዲያውም ብዙ ጊዜ ጠቃሚ ነው። በዚህ መንገድ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ደካማ

የሆኑትን የቤተ ክርስቲያኒቱን ልዩ ልዩ አካባቢዎች ለመርዳት ያስችላቸዋል። በአንድ አካባቢ ችግሮች እንዳሉ ለማወቅም ይረዳቸዋል። ለምሳሌ፥ የቤተ ክርስቲያን አባሎች ቁጥር እየቀነሰ ከሄደ፥ በዚያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ አንድ ችግር እንዳለ ግልጥ ይሆንልናል። በሌላ አንጻር አባሎችን የምንቆጥረው ብዛታችንን ለማወቅ ከሆነ፥ በቤተ ክርስቲያን አባሎቻችን ብዛት ወደ መታበይ፥ ከእግዚአብሔር ይልቅ በእነርሱ ቁጥር ወደ መመካት፥ ወዘተ ይመራናል። እግዚአብሔር ዳዊትን ባካሄደው ቆጠራ የቀጣው ባለው ተዋጊ ኃይል ለመመካት በመፈለጉ ብቻ ነበር። ድልን የሚሰጠው እግዚአብሔር መሆኑን ረስቶ በእርሱ ተዋጊ ኃይል ብዛት ተደገፈ።

በዘኍ.1 ና 26 ከተደረገው የእስራኤል ሕዝብ ቆጠራ፥ የሚከተሉትን ነገሮች መመልከት እንችላለን፡-

1. በሲና ተራራ በተካሄደው ቆጠራ ከ20 ዓመት በላይ የነበሩ ወንዶች ብዛት 603550 ሲሆን፥ ከ38 ዓመታት በኋላ ደግሞ ከዚሁ ከ20 ዓመት በላይ የነበሩ ወንዶች ቁጥር 601730 ብቻ ነበር። ቁጥሩ በከፍተኛ ሁኔታ ይጨምራል ብለን ስንጠብቅ፥ መቀነሱ አስገራሚ ነገር ነው። በ38 ዓመት ውስጥ ቁጥራቸው ዕጥፍ ይሆናል ተብሎ ነበር የተጠበቀው፤ ነገር ግን መጀመሪያ ከነበሩት እስራኤላውያን ከ38 ዓመታት በኋላ ሲቆጠሩ እጅግ አንሰው የተገኙ ሆኑ። ይህም እግዚአብሔር በአይሁዶች ላይ ያመጣው ፍርድ ውጤትና ምልክት ነው።

2. 20 ና ከዚያም በላይ ዕድሜ የነበራቸው ወንዶች ብቻ ተቆጠሩ። ይህም የሆነበት ምክንያት የቆጠራው ዋና ዓላማ ሊጋጠሟቸው ከሚችሉት ጠላቶቻቸው ጋር ሊዋጋ የሚችል ምን ያህል ኃይል እንደነበር ለማወቅ ነው። በምድረ በዳ የነበረው የእስራኤል ሕዝብ ብዛት ከ 2-3 ሚሊዮን እንደሚደርስ ምሁራን ይገምታሉ።

ይህ ከፍተኛ ቁጥር አንዳንዶች እውነተኛነቱን እንዲጠራጠሩ አድርጎአቸዋል። እነዚህ ሁሉ በምድረ በዳ እንዴት ለመኖር ቻሉ? ይህን ያህል ብዙዎች ከነበሩ፥ ከእነርሱ ጋር ሲነጻጸሩ በቁጥር እጅግ ጥቂቶች የነበሩትን ከነዓናውያን ፈጽመው ለማጥፋት ለምን አልቻሉም? (መሳ.1 ተመልከት)። ከዚህ የተነሣ አንዳንድ ሰዎች

የዚህን ቁጥር ትክክለኛነት ይጠራጠራሉ። የሕዝቡን ብዛት ለመቀየር የተሰጡ ሁለት አሳቦች ነበሩ፡- የመጀመሪያው፥ እግዚአብሔር ምን ያህል ሕዝብ ነፃ እንዳወጣ ለማሳየት የቀረበ ምሳሌ ብቻ ነው እንጂ ቁጥሩ ትክክለኛ ቁጥር አይደለም የሚል ሲሆን፥ ሁለተኛው ደግሞ፥ «አንድ ሺህ» የሚለው የዕብራይስጥ ቃል «ነገድ»፥ «ጎሣ»፥ «ክፍል» እንደሚል ተደርጎ መተርጎም አለበት የሚል ነው፤ ስለዚህ አንዳንድ ሰዎች ይህ ቁጥር በእስራኤል ውስጥ የነበረው ክፍል ቁጥር እንጂ የህዝቡ ብዛት አይደለም ይላሉ። ስለዚህ እንደ ቃሉ አተረጓጎም ከ18000-100000 ተዋጊ ኃይላት እንዲሁም በአጠቃላይ ከ72000-400000 የሚደርሱ እስራኤላውያን ነበሩ። ሆኖም ግን ይህን ለሚያህል ሕዝብ እግዚአብሔር ሊጠነቀቅና የሚያስፈልጋቸውን ሁሉ ሊሰጥ እንደሚችል ለመጠራጠር ምንም በቂ ምክንያት የለም፤ ስለዚህ ቀደም ብሎ ከላይ የተጠቀሰው ቁጥራቸው ትክክል እንደሆነ በመቀበል፥ በእስራኤል ምን ያህል ሕዝብ እንደ ነበር የሚያሳይ መሆኑን ማመን ተገቢ ነው።

3. በ38 ዓመታት ውስጥ በተካሄዱት ሁለት ቆጠራዎች የአብዛኛዎቹ ነገዶች ቁጥር በግምት እንደ መጀመሪያው ሆኖ የቆየ ሲሆን፥ ሁለት ነገዶች ብቻ ከፍተኛ ለውጥ አሳይተዋል። የምናሴ ነገድ በ20500 የጨመረ ሲሆን፥ የስምዖን ነገድ ግን በ37100 ቀንሷል። በእነዚህ ሁለት ነገዶ ውስጥ ይህ ከፍተኛ ለውጥ የታየው ለምን እንደሆነ አናውቅም።

4. ሌዋውያን በሕዝብ ቆጠራ ውስጥ አልገቡም ነበር፤ ምክንያቱም ወደ ጦርነት መሄድ አይጠበቀባቸውም ነበር፤ የእነርሱ ኃላፊነት በቤተ መቅደስ ውስጥ ማገልገል ነበር።

ለ. የእስራኤላውያንን ሰፈር ማደራጀት (ዘኁ. 2)

ምናልባት ቁጥራቸው ወደ 2 ሚሊዮን የሚጠጋው የእስራኤል ሕዝብ እያንዳንዱ ሰውና እያንዳንዱ ቤተሰብ የት መሆንና ድንኳኑን የት መትከል እንዳለበት በሚገልጥ መንገድ መደራጀት ነበረባቸው።

የሚከተለውን ሠንጠረዥ በመመልከት፥ የመገናኛው ድንኳን ያለው በእስራኤላውያን መሀል እንደ ነበረ አስተውል። ልክ እንደዚሁ፥

እግዚአብሔር የሕይወታችን፥ የአምልኮአችንና የፍላጎታችን ሁሉ፥ ወዘተ. እምብርት ነው (ማቴ.6፡33፤ ሉቃ.10፡27)።

ንፍታሌም　　አሴር　　ዳን

ኤፍሬም　　ሜራሪያውያን　　ይሁዳ

ምናሴ　ጌርሾናውያን　የመገናኛው ድንኳን　　አሮን ይሳኮር

ብንያም　　ቀዓታውያን　　ዛብሎን

ጋድ　　ስምዖን　　ሮቤል

ሐ. የሌዋውያን አሰፋፈርና ተግባር (ዘኍ.3-4)

እግዚአብሔር የሌዋውያንን ልዩ ልዩ ጎሣዎች በመገናኛው ድንኳን አካባቢ አሰፈራቸው። በምሥራቅ አሮን፥ ልጆቹና የእርሱ ዝርያዎች ነበሩ። እነርሱ ካህናት ስለ ነበሩ፥ በመገናኛው ድንኳን ውስጥ የሚካሄደውን አምልኮ በበላይነት የመምራት ኃላፊነት ነበረባቸው። ሌዋውያን ከዚህ በተጨማሪ በሦስት ይከፈሉ ነበር፤ በደቡብ በኩል ቀዓታውያን ነበሩ። የመገናኛው ድንኳን በሚንቀሳቀስበት ጊዜ በውስጡ ባሉት የተለያዩ ዕቃዎች ላይ ኃላፊነት ነበረባቸው። በምዕራብ ደግሞ ጌርሾናውያን ነበሩ። እነርሱም የመገናኛው ድንኳን፥ በሚንቀሳቀስበት ጊዜ የመገናኛው ድንኳን አልባሳትንና መጋረጃውን የማንቀሳቀስ ኃላፊነት ነበረባቸው። በሰሜን በኩል ደግሞ ሜራሪዓውያን ነበሩ። የመገናኛውን ድንኳን ምሰሶዎችና ግድግዳዎች የማንቀሳቀስ ኃላፊነት የእነርሱ ነበረ።

መ. የሰፈሩን ንጽሕና መጠበቅ (ዘኍ.5)

በዚህ ምዕራፍ እስራኤላውያን የሰፈሩበትን ቦታ ስለ መጠበቅ በርካታ ትእዛዛት ተሰጥተዋል። አንደኛ፥ እስራኤላውያን ቅርብ ለቅርብ ሆነው በአንድነት ይኖሩ ነበር። ስለዚህ በሽታ በቀላሉ ይዛመት ነበር፤ በመሆኑም ያልተለመዱ በሽታዎች ያሉባቸው ሰዎች እስኪፈወሱ ድረስ ከሰፈሩ ውጭ እንዲቆዩ እግዚአብሔር አዘዘ።

ሁለተኛ፥ ሕዝቡ የሚኖረው ተቀራርቦ ስለ ነበር፥ ክርክርና ጠብ ሊነሣ ይችል ነበር፤ ስለዚህ እግዚአብሔር በጎረቤቶቻቸው ላይ የማይገባ ነገር ቢያደርጉ፥ ይቅርታ መጠየቅና በወሰዱት ወይም

ባጠፉት ነገር ላይ ከአምስት አንድ እጅ ጨምረው ካሣ እንዲከፍሉ አዘዛቸው።

ሦስተኛ፥ እግዚአብሔር የኃጢአት መስፋፋት እንዴት መገታት እንዳለበት መመሪያዎችን ሰጠ። አንዲት ሴት በዝሙት ኃጢአት ተጠያቂ መሆን አለመሆኗን ለመወሰን የሚያስችል ያልተለመደ አደራረግ ተዘርዝሮአል። ይህ አደራረግ በብሉይ ኪዳን ውስጥ በየትኛውም ስፍራ በተግባር ሲውል አለመታየቱ፥ እስራኤላውያን በምድረ በዳ በነበሩበት ጊዜ ብቻ እንዲጠቀሙበት የተሰጠ ጊዜያዊ ትእዛዝ ይመስላል። እግዚአብሔር ሰው በአመንዝራነት ተጠያቂ መሆኑን ለመወሰን እርሱ ራሱ ዳኛ የሚሆንበትንና የሚወስንበት መንገድ ለእስራኤላውያን ሰጣቸው። ጥፋተኛ ያልሆነው ሰው «በመራራ ውኃ» እንዳይሞት የሚጠብቅና ጥፋተኛ የሆነውን ደግሞ እንዲሞት የሚያደርግ እርሱ ብቻ ነበር።

## ሠ. የናዝራዊነት ስእለት (ዘኍ. 6፡ 1-21)

ራሱን ለተወሰነ ጊዜ ለእግዚአብሔር ለመስጠት ለሚፈልግ ሰው፥ እግዚአብሔር ልዩ መመሪያዎችን ሰጠ። ራሱን ለእግዚአብሔር የለየ ሰው «የናዝራዊነትን ስእለት» ፈጽሟል ይባል ነበር። ሰው ለእግዚአብሔር የገባውን ስእለት ለመፈጸምና ከእግዚአብሔር ልዩ ጥበቃ እንዲሁም በረከት ለማግኘት ራሱን የመስጠት ጊዜ ይኖረዋል። የናዝራዊነትን ስእለት የሚያደርግ ሰው ሦስት ነገሮችን ማሟላት አለበት፡-

ሀ) የወይን ተክል ውጤት የሆነውን ማንኛውንም መብላት አይችልም ነበር። በእስራኤል ምድር የሚገኝ ዋነኛው ፍራፍሬና መጠጥም የወይን ፍሬ ውጤት ነው።

ለ. በናዝራዊነት ስእለት ሥር መሆኑን የሚያሳይበት ውጫዊ መንገድ ጸጉሩን ማሳደግ ነበር።

ሐ. ማንኛውንም አስከሬን መንካት አይፈቅድለትም ነበር።

ይህ አደራረግ በፍጹም ፈቃደኝነት የሚፈጸም መሆኑን ማስቷዋል ጠቃሚ ነው። በእግዚአብሔር ግፊት ሳይሆን፥ በሰውዬው ፈቃደኝነት

የሚፈጸም ነው። ደግሞም ጊዜያዊና ሰውዬው ለስእለቱ እስከተለየ ድረስ ብቻ የሚቆይ ነው።

ሳምሶን በናዝራዊነት ስእለት ሥር ለነበሩ ሰዎች ጥሩ ምሳሌ ነው። የእርሱ ስእለት ቋሚ በመሆኑ፥ ጉዳዩን የተለየ ያደርገዋል። አንዳንድ ሰዎች ኢየሱስ፥ የናዝሬቱ ኢየሱስ ተብሎ ስለሚጠራ፥ በዚህ ስእለት ሥር ነበረ ይላሉ። ይህ ግን ሊሆን እንደማይችል የምናየው ኢየሱስ ወይን እንደጠጣ የተገለጠ ነገር ስላለ ነው (ሉቃ.7፡33-34)። ይልቁንም ናዝራዊ የተባለው እርሱ ከናዝሬት ከተማ ስለነበረ ነው።

ረ. በመገናኛው ድንኳን ስለሚደረግ አምልኮ የተሰጡ ልዩ መመሪያዎች (ዘኁ.6፡22-8፡26)

ሰ) እስራኤላውያን ሊመሩበት የሚገባ መንገድ (ዘኁ. 9፡15-10፡10)

በምድረ በዳ በነበሩበት ጊዜ፥ እግዚአብሔር ሕዝቡን ለመምራት ሁለት ዋና ዋና መሣሪያዎችን ሰጥቶዋቸው ነበር። የመጀመሪያው፥ የእግዚአብሔር የደመና ክብር ነበር። ይህ ደመና የእግዚአብሔር ሕልውና ምልክት ነበር። በቀን ደመና፥ በማታ ደግሞ እሳት ይሆን ነበር። ደመናው የመገናኛውን ድንኳን ለቆ በሰማይ ላይ በሚሆንበት ጊዜ፥ ሕዝቡ የነበሩበትን ስፍራ ለቀው፥ ደመናውን እየተከተሉ በሚሄድ የሚቀጥለውን የሰፈራ ስፍራ እስኪያገኙ ድረስ መንቀሳቀስ፥ ደመናው ከመገናኛው ድንኳን ላይ እስካልተነሣ ድረስ ግን በዚያው መቆየት እንዳለባቸው ያውቁ ነበር።

> 10ኛ ጥያቄ፡- ሀ) እግዚአብሔር እንመራበት ዘንድ ለእኛ የሰጠን ምንድን ነው? ለ) እግዚአብሔር አንድን ጉዳይ በሚመለከት ግልጽ የሆነ መመሪያ ለአንተ የሰጠበትን ጊዜ ጥቀስ። ሐ) ምን ዓይነት የአመራር መንገድ በመስጠት ነበር የተጠቀመው?

ሁለት ልዩ መለከቶችን ሠርቶ ለካህናቱ እንዲሰጥ እግዚአብሔር ሙሴን አዘዞት ነበር። ሁለቱም መለከቶች በሚነፉበት ጊዜ ሕዝቡ ሙሴ ወደሚገኝበት ወደ መገናኛው ድንኳን ይመጣል። አንዱ መለከት ብቻ ሲነፋ፥ ወደ ሙሴ የሚመጡት መሪዎች ብቻ ነበሩ። እነዚህ

መለከቶች ጉዞ ለመጀመር ምልክት ለመስጠትና በተጨማሪ ጠላቶች ካሉ ለውጊያ ለማዘጋጀት ይጠቀሙ ነበር፤ እንዲሁም ለተለዩ ሃይማኖታዊ በዓላት ምልክት በመሆንም ያገለግሉ ነበር።

2. እስራኤል ከሲና ተራራ ተነሥተው ወደ ቃዴስ በርኔ እንደተጓዙ (10፡11-12፡16)

ሕዝቡ በሲና ተራራ 11 ወራት ከቆዩ በኋላ፥ ወደ ከነዓን ለመሄድ ጉዞ ጀመሩ። ይህ ጉዞ ጥቂት ወራት ብቻ የሚፈጅ ነበር። ነገር ግን 38 ዓመታት ፈጀ። እስራኤላውያን ከሲና ተራራ የከነዓን ምድር ደቡባዊ ጫፍ ወደ ሆነችው ወደ ቃዴስ በርኔ ለመድረስ የፈጀባቸው 11 ቀናት ብቻ ነበር። ነገር ግን እነዚህ 11 ቀናት በኃዘንና በእግዚአብሔር ላይ በማመፅ የተሞሉ ነበሩ። እስራኤላውያን ወደ ቃዴስ በሚጓዙበት ጊዜ ስለተፈጸሙት ነገሮች የሚከተሉትን አስተውል፡-

ሀ. የሲና ተራራ፡- ሰፈሩ ከተደራጀና የጉዞ ትእዛዝ ከተላለፈ በኋላ፥ የእግዚአብሔር ደመና ከመገናኛው ድንኳን ላይ ተነሥቶ ሕዝቡ ለጉዞ ተዘጋጀ። ሙሴም ሕዝቡን ወደ ከነዓን እንዲመራ የአማቱን የራጉኤልን ልጅ ኦቦብን ጠየቀው። (ማስታወሻ፡- ራጉኤል የዮቶር ሌላው ስም ነው) (ዘጸ.2፡18፤ 3፡1)።

ለ. ተቤራ ወይም የምኞት መቃብር (ዘኁ.10፡33-11፡35)፥ በዚህ ስፍራ ሦስት ዋና ዋና ነገሮች ተፈጸሙ፡-

1. ሕዝቡ በእግዚአብሔር ላይ ስላጉረመረሙ ከሰማይ የመጣ የእግዚአብሔር እሳት አንዳንዶቹን ገደለ።

2. ሕዝቡ ከመና ሌላ የሚበላ ነገር ስለፈለጉ በእግዚአብሔር ላይ አጉረመረሙ። የእግዚአብሔር የቸርነት ስጦታ የሆነውን መና እምቢ በማለታቸው እግዚአብሔር ይበሉ ዘንድ ድርጭትን ላከላቸው፤ ነገር ግን «ከግብፅ ለምን ወጣን» በማለት ጌታን ስላልፈለጉ ብዙዎቹ ሞቱ።

3. ሙሴ ሕዝቡን በመምራት ይረዱት ዘንድ ሰባ ሰዎችን መረጠ። የተመረጡት በሙሴ ብቻ ሳይሆን በእግዚአብሔር መሆኑን ለማረጋገጥ የእግዚአብሔር መንፈስ ወረደባቸው።

11ኛ ጥያቄ:- ሀ) ከእነዚህ ቁጥሮች ስለ እግዚአብሔር የምንማረው ነገር ምንድን ነው? ለ) እኛም ራሳችን አንዳንድ ጊዜ የእግዚአብሔርን የጸጋ ስጦታዎች በመቃወም ጥፋተኞች የምንሆነው እንዴት ነው?

3. ሐጼሮት (12፡1-16)

በሐጼሮት አንድ ያልታሰበ ነገር ተፈጸመ። የእስራኤልን ሕዝብ ለመምራት እግዚአብሔር በሙሴ ስለ ተጠቀመ፥ ወንድሙ አሮንና እኅቱ ማርያም ቀኑበት። በከፊል የቀኑበት ምክንያት ኢትዮጵያዊ በማግባቱ ነበር። አንዳንድ ምሁራን ሙሴ ኢትዮጵያዊቱን (ኩሻዊቱን) ያገባው የመጀመሪያ ሚስቱ ስለሞተችበት ነው ይላሉ። (ማስታወሻ:- በብሉይ ኪዳን ኢትዮጵያ (ኩሽ) የተባለው ስፍራ ዛሬ የምናውቀው የኢትዮጵያ ክፍል ሳይሆን በደቡብ ግብፅ የሚገኝ ክፍል ነው።) በተጨማሪም ክብሩን ሁሉ ሙሴ ማግኘቱ ትክክል አይደለም ብለው አሰቡ። እግዚአብሔር ከእነርሱም ጋር ተነጋግሯልና!

የእግዚአብሔር ምላሽ ጠንከር ያለ ነበር። ወደ መገናኛው ድንኳን ጠራቸውና በሙሴ ላይ ለመናገር መብት እንደሌላቸው ነገራቸው። ሙሴ ከእግዚአብሔር ጋር ፊት ለፊት በመነጋገር የተለየ ዕድል ነበረው። ስለዚህ በሙሴ ላይ ለተፈጸመው ዓመፅ አነሣሽ እንደሆነች የምንጠረጥራትን ማርያምን እግዚአብሔር ቀጣት። ማርያምም ለምፃም ሆነችና እስራኤላውያን ከሰፈሩበት ሰፈር ውጭ ለ7 ቀናት እንድትቆይ ሆነ። ሙሴም ስለ ጸለየላት እግዚአብሔር በምሕረቱ ፈወሳት።

12ኛ ጥያቄ:- ሀ) በመሪዎች መካከል ስለሚሆነው መቀናናት ከዚህ ታሪክ የምንማረው ነገር ምንድን ነው? ለ) አንዳንድ መሪዎች በሌሎች ላይ የሚቀኑት ለምንድን ነው? ሐ) በአመራር ስፍራ ላይ በምንሆንበት ጊዜ ክብርን ለራሳችን የምንፈልገው ለምንድን ነው? መ) ቅንዓት ክፉ ስለመሆኑ ከዚህ ታሪክ ምን መማር እንችላለን?

መ. በፋራን ምድረ በዳ የሚገኘው ቃዴስ በርኔ (ዘኁ. 12፡16)

3ኛ ቀን:- ዘኁ. 13-21

በሕይወታችን የምናደርገው ምርጫ ለሚያጋጥመን በጎም ይሁን ክፉ ነገር ሁሉ ወሳኝ ሚና አለው። በኢየሱስ ማመንን በመረጥን ጊዜ፥

የወደፊት ሁኔታችን ሁሉ ይለወጣል። ኢያሱና ካሌብ በእግዚአብሔር ለመታመንና ከነዓናውያንን ለመውጋት ሲወስኑ፥ ከዚያ ትውልድ መካከል ወደ ተስፋይቱ ምድር የሚገቡ ብቸኞቹ ሰዎች እነርሱ መሆናቸውን አላወቁም ነበር። የእግዚአብሔርን ትእዛዛት ላለመከተል በምንወስንበት ጊዜ፥ ለጊዜው የቱንም ያህል ትንሽ ቢመስለንም፥ በሕይወት ዘመናችን ሁሉ የሚታይ መጥፎ ውጤት ሊኖረው ይችላል።

| |
|---|
| 13ኛ ጥያቄ:- ሀ) መልካም ምርጫዎቻችን ለሕይወታችን በጎ ውጤት እንዴት እንደሚያመጡ አንዳንድ ምሳሌዎችን ጥቀስ ለ) ለእግዚአብሔር ባለመታዘዛችን እርሱ ይቅር ሊለን ቢችልም እንኳ ውጤታቸው በሕይወታችን ዘመን ሁሉ ሊከተሉን ለሚችሉ ነገሮች ምሳሌዎችን ጥቀስ። |

ሳኦል ለእግዚአብሔር ሙሉ ለሙሉ ለመታዘዝ ባለመወሰኑ መንግሥቱ ከእርሱ እንዲወሰድ አደረገ (1ኛ ሳሙ. 15፡2-3፥ 13-30)። ዳዊት ዝሙት በፈጸመና ከወዳጆቹ አንዱን ባስገደለ ጊዜ ቀሪው የሕይወት ዘመኑ በሙሉ በዚህ እንደሚነካ፥ በመንግሥቱና በቤተሰቡም ሰላም እንደሚጠፋ አላወቀም ነበር (2ኛ ሳሙ. 12፡1-14 ተመልከቱ)። እግዚአብሔር ይቅር ካለው በኋላ እንኳ የኃጢአቱ ውጤቶች ዳዊትን ይከተሉት ነበር። አንዲት ልጃገረድ ካላገባችው ወንድ ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት ኃጢአት ፈጽማ በምትናዘዝበት ጊዜ እግዚአብሔር ይቅር ይላታል፤ ነገር ግን ክብረ ንጽሕናዋን የማጣት ኃፍረቷን፥ ምናልባትም የማርገዝንና ሌላ ለማግባት ያለመቻልዋን፥ ወይም በኤድስ የመያዝን ኃፍረት ሊያስወግድላት አይችልም።

ወደ ከነዓን ጉዞ ከሚጀምሩበት ካለፈው አንድ ዓመት አንሥቶ እግዚአብሔር ኃይሉንና በጸጋ የተሞላ ቸርነቱን ለአይሁድ ሲገልጥ ቆይቶአል፤ ነገር ግን በቃዴስ በርኔ እንዲታመኑበትና ወደ ከነዓን ምድር በእምነት እንዲገቡ እግዚአብሔር ሲጠይቃቸው እስራኤላውያን እምቢ አሉ። በዚህ ውሳኔአቸው ምክንያት አይሁድ በሚከተሉት 38 ዓመታት በምድረ በዳ ተንከራተቱ። ከ20 ዓመት ዕድሜ በላይ የሆኑት በግምት ወደ አንድ ሚሊዮን የሚጠጉ ሰዎች በሙሉ አለቁ። ለእግዚአብሔር አለመታዘዝ በጭራሽ ያልገመቱትን ፍርድ

አስከተለባቸው። ስሕተታቸውን ለማረም እንኳ ቢሞክሩ ጨርሶ የማይቻል ሆነባቸው። የአራት ዘኁልቁ ክፍል የሆነው የዚህ ክፍል ታሪክ እግዚአብሔር ከግብፅ ባርነት በጸጋው ነፃ ያወጣቸው የእስራኤላውያን አለመታዘዝና ያስከትለው ውጤት ታሪክ ነው።

14ኛ ጥያቄ፥ ዘኁልቁ 13-21 አንብብ ሀ) ሰላዮችን ወደ ከነዓን የመላኩ ዓላማ ምን ነበር? ለ) 1) የአሥሩንና የሁለቱን ሰላዮች የተለያዩ ምላሾች አወዳድር። 2) ስለ ምድሪቱ የነበራቸው መረዳት አንድ የሆነው እንዴት ነው? 3) ስለ እግዚአብሔር የነበራቸው መረዳት የተለያየው እንዴት ነው? 4. ከዚህ የምንማረው ነገር ምንድን ነው? ሐ) ከአራት ዘኁልቁ ይህን ክፍል አለፍ አለፍ እያልክ ተመልከት። እስራኤላውያን የሄዱባቸውን ስፍራዎችና በየደረሱባቸው ስፍራዎች የተፈጸሙትን ነገሮች ዘርዝር። ከዚህ መጽሐፍ በስተጀርባ ከሚገኘው ካርታ ላይ ስፍራዎቹን ፈልገህ ተመልከት።መ) የሙሴን ኃጢአት ግለጥ። እግዚአብሔር ከፉኛ የፈረደበትና የቀጣው ለምን ይመስልሃል? ሠ) እስራኤላውያን የከነዓንን ምድር መውጋት በጀመሩ ጊዜ ያሸነፏቸውን ሕዝቦች ዘርዝር?

## 1. 12ቱ ሰላዮች (ዘኁ. 13-14)

እስራኤላውያን የከነዓንን ምድር ካዩ ከ400 ዓመታት በላይ ሆኖአል። አሁን የከነዓን ደቡባዊ ጫፍ በሆነው በቃዴስ በርኔ ሰፍረዋል። ይህም እግዚአብሔር ሊሰጣቸው ያለች ምድር ምን ያህል መልካምና ፍሬያማ እንደሆነች ለማየት እንጂ፥ የጠላቶቻቸውን ብርታት ለማየት አላስቻላቸውም። 12ቱ ሰዎች ወደ ከነዓን ምድር በመሄድ ለ40 ቀናት ምድሪቱን ሲሰልሉ ቆይተው የየራሳቸውን ዘገባ ይዘው ተመለሱ።

አሥሩ ሰላዮች በመጀመሪያ ዘገባቸውን አቀረቡ። ምድሪቱ ምን ያህል ፍሬያማ እንደሆነች ተናገሩ። እንዲያውም ምድሪቱ ከምታፈራቸው ነገሮች ለናሙና የሚሆን ነገርም አምጥተው ነበር። ዘገባቸው ግን በጠላቶቻቸው ብዛትና ታላቅነት ላይ የሚያተኩር ሆነ፤ ስለዚህ ወደ ከነዓን እንዳይሄዱ ሕዝቡን ተስፋ አስቆረጡአቸው።

ካሌብና ኢያሱ የተባሉት ሁለት ሰላዮችም ተመሳሳይ ዘገባ አቀረቡ። ሰላዮቻቸው ታላላቅ ነገሮች ተናገሩ፤ ነገር ግን ጠላቶቻቸው ምንም ያህል በቁጥር የበዙና ታላላቅ ቢሆኑም፥ በጠላቶቻቸው ላይ ከማተኮር ይልቅ፥ ሊያጠፉቸው በሚችለው በእግዚአብሔር ኃይል ላይ አተኮሩ።

15ኛ ጠያቄ፡- ሀ) በአሥሩና በሁለቱ ሰላዮች መካከል የነበረው የአመለካከት ልዩነት ለሕዝቡ በሰጡት ምክር ላይ ያሳደረው ተጽዕኖ ምንድን ነው? ለ) ዛሬ ጠላቶቻችንንም ሆነ ችግሮቻችንን ስለ መጋፈጥ ከዚህ ነገር ምን እንማራለን?

የሚያሳዝነው ሕዝቡ 2ቱን ሳይሆን 10ሩን ሰላዮች ተከተሉ። ዓይኖቻቸውን ከጠላቶቻቸው ሁሉ በላይ ከሆነው ከእግዚአብሔር ላይ አንሡና በችግራቸውና በራሳቸው ላይ አደረጉ። ሌሊቱን በሙሉ ሲያጉረመርሙ አድረው፥ ጠዋት የባርነት ምድር ወደሆነችው ወደ ግብፅ ለመመለስ ወሰኑ። እግዚአብሔር በቁጣው እስራኤላውያንን በሙሉ እንዳያጠፉቸው የሚከለክለው የሙሴ የማማለድ አገልግሎት ነበር። ሆኖም እግዚአብሔር በእስራኤላውያን ላይ ፍርድን አመጣባቸው። የሚከተሉትን ነገሮች ልብ በል፡-

1. እግዚአብሔር አሥሩን ሰላዮች ወዲያውኑ ገደላቸው።
2. ከ20 ዓመት በላይ የሆኑ ማለትም የእግዚአብሔርን ክብር ያዩና የተአምራቱ ምስክሮች የሆኑ ሰዎች በሙሉ የተስፋይቱን ምድር ሳይወርሱ በምድረ በዳ ማለቅ ነበረባቸው።
3. እስራኤላውያን በምድረ በዳ ለ40 ዓመታት ተንከራተቱ። ሰላዮቹ ለአንድ ዓመት ሙሉ በየቀኑ በከነዓን ነበሩ። በኋላ ግን ከከነዓን ውጭ ሞቱ።
4. ከዚያ ትውልድ መካከል ወደ ተስፋይቱ ምድር እንዲገቡ የተፈቀደላቸው ካሌብና ኢያሱ ብቻ ነበሩ።

እስራኤላውያን ካለማመን ኃጢአታቸው ንስሐ ለመግባት ቢሞክሩም እንኳ እግዚአብሔር ከተናገረው ፍርድ ወደ ኋላ አላለም። ያለ እግዚአብሔርና ያለ ታቦቱ ሕልውና እስራኤላውያን በራሳቸው

ኃይል ከጠላቶቻቸው ጋር ለመዋጋት ሞከሩ፤ ነገር ግን የተረፉቸው ሽንፈት ነበር።

16ኛ ጥያቄ:- ይህ ጠላቶቻችንን በራሳችን ኃይል ለመዋጋት ብንሞክር፥ ስለሚደርስብን ነገር ምን ያስተምረናል?

(ማስታወሻ:- ሕዝቡ 40 ዓመታት በምድረ በዳ ነበሩ ስንል፥ ከግብፅ ከወጡበት ጊዜ ጀምሮ ያሳለፉትን አንድ ዓመት ከሁለት ወር ጨምሮ ነው)

2. 38 ዓመታት በምድረ በዳ በተንከራተቱ ጊዜ የተፈጸሙ ነገሮች (ዘኁ.15-19)

ዘኁ. 15-19 በእነዚህ 38 ዓመታት የምድረ በዳ ኑሮ ስለነበሩት ሁኔታዎችና ስለተፈጸሙት ሁኔታዎች አንዳንድ ነገሮችን ይነግረናል። ቢሆንም በከነዓን በስተደቡብ ባለው ምድረ በዳ በመንከራተት ስላሳለፉት ጊዜ የምናውቀው ነገር በጣም ጥቂት ነው። ቆይታ ያደረጉባቸውን አብዛኛዎቹን ስፍራዎች አናውቃቸውም። የምናውቀው ነገር ቢኖር፥ ከፍተኛ ኃዘን የነበረባቸው ዓመታት መሆናቸውን ነው። ከአንድ ሚሊዮን የሚበልጡ ሰዎች ሞቱ። በእነዚህ ምዕራፎች የሚከተሉት ነገሮች ተተንትነዋል:-

1. ሕዝቡ ከነዓን በደረሱ ጊዜ ምን ዓይነት መሥዋዕት ማቅረብ እንዳለባቸው እግዚአብሔር ለሙሴ ነገረው፤ (15፡1-31)።

2. የሰንበት ዕረፍት ትእዛዝን እያወቀ የጣሰ ሰው በድንጋይ ተደብድቦ እንዲገደል ታዘዘ፤ (15፡32-36)። ይህ ቀላል ስሕተት አይደለም፤ ይልቁንም በእግዚአብሔር ላይ የተፈጸመ ግልጥ ዓመፅ ይመስላል። በእግዚአብሔርና በትእዛዛቱ ላይ ሆን ተብሎ ለሚሠራ ዓመፅ ይቅርታ የለም፤ ስለዚህ ሕጉን የተላለፈው ሰው በድንጋይ ተወግሮ እንዲገደል ይደረግ ነበር።

3. ሕዝቡ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ያስታውሱ ዘንድ በልብሶቻቸው ዘርፍ ላይ ቋጥረው እንዲያስሩት እግዚአብሔር ሙሴን አዘዘው (15፡37-41)። እግዚአብሔር ሕዝቡ ትእዛዛቱን በቀላሉ ለማስታወስ እንዲችሉ ለማድረግ ሞክሯል፤ ስለዚህ ቀኑን ሙሉ በማስታወስ ይታዘዙት ዘንድ ውጫዊ የሆኑ ምልክቶችን

እንዲያበጁ ነገራቸው። ሌሎች ማስታወሻዎችን (ዘዳ.6፡4-9 ተመልከት)

4. የተለያዩ የእስራኤል መሪዎች በሙሴና በአሮን ሥልጣን ላይ ዓምፀዋል (ዘኁ.6-17)። የዓመፁ መሪዎች ቆሬ፥ ዳታን፥ አቤሮንና አን ሳይሆኑ አይቀሩም፤ ሆኖም በሙሴና በአሮን ሥልጣን ላይ ያመፁ ሌሎች 250 ዋና ዋና የእስራኤል መሪዎች ነበሩ። የእግዚአብሔርን ሕዝብ ለመምራት ሙሴና አሮን የነበራቸውን ሥልጣን ተፈታተኑ። ሙሴ የፖለቲካ መሪ ሲሆን፥ አሮን ሊቀ ካህን ወይም ሃይማኖታዊ መሪ ነበር። ሙሴና አሮን እርሱ የመረጣቸው መሪዎች እንደሆኑ እግዚአብሔር ለሁሉም ሰው አሳየ።

   ሀ. የዓመፁ መሪ የነበሩት፥ ቆሬ፥ ዳታን፥ አቤሮንና አን ከነቤተሰቦቻቸው ከእስራኤል ሕዝብ ተለዩና መሬት ተከፍታ እነርሱና ቤተሰቦቻቸውን፥ እንዲሁም ንብረቶቻቸውን በሙሉ ዋጠች።

   ለ. ቆሬ ሌዋዊ ነበር፤ ስለዚህ የእርሱ ዓመፅ በተለይ አሮን በመገናኛው ድንኳን ውስጥ በነበረው ስፍራ ላይ ነበር፤ ስለዚህ እግዚአብሔር እርሱንና የተከተሉትን ሰዎች በሙሉ (በአጠቃላይ 250 ነበሩ) ጥናዎችን ወስደው እሳት እንዲያደርጉባቸውና ዕጣን እንዲጨምሩባቸው በመገናኛው ድንኳንም በእግዚአብሔር ፊት እንዲያቀርቡት አዘዘ። ይህንንም በሚያደርጉበት ጊዜ ከመገናኛው ድንኳን የወጣች እሳት ቆሬን፥ ዳታንን አቤሮንንና አንን የተከተሉትን 250 ሰዎች በላች። የዕጣን ማቅረቢያቸው በእሳት ተበልቶ ጠፍጣፋ ሆንና እግዚአብሔር ሙሴንና አሮንን እንደመረጠ እነርሱም ትክክለኞዎቹ የእስራኤል ሕዝብ መሪዎች እንደሆኑ ቋሚ መታሰቢያ ሆኖ ቀረ።

   ሐ. እነዚህ ዓመፀኛ መሪዎች ከሞቱ በኋላ፥ ሕዝቡ መሪዎቻችንን ገደልክብን ብለው በሙሴ ላይ አጉረመረሙ። እግዚአብሔርም ተቆጣና ከመካከላቸው 14700 ሰዎችን ገደለ። አሮን፥ የመሠዊያውን ጥና እሳትን በማድረግና እጣን በመጨመር

ለሕዝቡ ባይማልድ ኖሮ፥ የእስራኤል ሕዝብ በሙሉ ይጠፉ ነበር። ብዙ ክርስቲያኖች ዕጣንን በጥና ላይ ማጠን የጸሎት ምልክት ነው ይላሉ። አሮንና ሙሴ በእግዚአብሔርና በሕዝቡ መካከል አማላጅ ሆነው ሕዝቡን አዳኑ።

መ. ሊቀ ካህኑ አሮን ብቻ እንደሆነ እግዚአብሔር በሕዝቡ ሁሉ ፊት አረጋገጠ። እግዚአብሔር ባዘዘው መሠረት ሙሴ በእያንዳንዳቸው ላይ የአንድ ነገድ ስም የተጻፈባቸውን አሥራ ሁለት በትሮች ወሰደ። በአንድ ሌሊትም የአሮን በትር አቆጥቁጣ፥ቅጠሎች አውጥታና ፍሬ አፍርታ አደረች። ሊቀ ካህን የመሆኑ መብት ቋሚ ማስታወሻ ይሆን ዘንድ የአሮን በትር በቅድስተ ቅዱሳን በቃል ኪዳኑ ታቦት ውስጥ ተቀመጠች።

> 17ኛ ጥያቄ:- ሀ) በቤተ ክርስቲያን አመራር ላይ ያሉ ሰዎች፥ በስፍራው የተቀመጡት በእግዚአብሔር ምርጫ ስለሆነ ሊከበሩ እንደሚገባ ማወቅ አስፈላጊ የሆነው ለምንድን ነው? ለ) ይህ ታሪክ መሪዎች በእግዚአብሔር ፊት ስለ ሕዝቡ መማለድ ስላላቸው ሥልጣንና ሚና የሚያስተምረን ነገር ምንድን ነው?

5. ሕዝቡ ለካህናት ቅዱስ የሆነውን የእግዚአብሔርን አምልኮ መምራት ይችሉ ዘንድ መሥዋዕት እንዴት እንደሚሠዉና በእግዚአብሔር ፊት ንጽሕናቸውን እንዴት እንደሚጠብቁ የተሰጡ ትእዛዛት (ዘኁ. 18)።

6. የቀይ ጊደር መሥዋዕትና የሚያነጻ ውኃ ሥርዓት (ዘኁ. 19)፥ ኃጢአት ምን ያህል ኃይለኛ ተጽዕኖ እንደሚያሳድርና እግዚአብሔር ሌላ ግልጥ የሆነ ምልክትን ሰጠ:- በመጀመሪያ፥ ቀይ ጊደር ከእስራኤላውያን ሰፈር ውጭ ተወስዳ ትታረድና ሙሉ በሙሉ ትቃጠላለች። ከዚያም አመዱ ተወስዶ ከውኃ ጋር ይቀላቀላል። ይህ ውኃ የሞተን ሰው በድን በመንካት የረከሰውን ሰው የሚነጻበትን ሥርዓት የሚያመለክት ነበር። ውኃ ራሱ አያነጻም ነበር! ዳሩ ግን ውስጣዊ መንጻት አስፈላጊ መሆኑን ለማሳየት እግዚአብሔር የሰጠው ውጫዊ ምልክት ነበር።

7. ሙሴ ከዓለት ውስጥ ውኃ በማውጣት በእግዚአብሔር ላይ ኃጢአት በመሥራቱ ወደ ተስፋይቱ ምድር ወደ ከነዓን እንዳይገባ ተከለከለ (ዘኁ.20፡1-13)። ዘኁ. 20 እስራኤላውያን ከግብፅ ባርነት ነፃ በወጡ በ40ኛው ዓመት የተፈጸመ ይመስላል። ይህም ማለት የመጀመሪያዎቹ የእስራኤል ትውልድ በሙሉ ስለሞቱ፥ ሕዝቡ ወደ ተስፋይቱ ምድር ለመግባት ተዘጋጅተው ነበር ማለት ነው። እስራኤላውያን ወደ ቃዴስ በርኔ በመመለስ ወደ ተስፋይቱ ምድር ለመግባት ተዘጋጅተው ነበር። በዚህ ስፍራ ሁለት ዋና ዋና ነገሮች ተፈጸሙ:-

ሀ. የሙሴ እኅት ማርያም ሞተች።

ለ. ሙሴ ለእግዚአብሔር ሳይታዘዝ ቀረ። እስራኤላውያን (አዲሱ ትውልድ) ልክ እንደ አባቶቻቸው በእግዚአብሔር መታመንን ገና አልተማሩም ነበር። የሚጠጣ ውኃ ስላልነበራቸው፥ በሙሴና በአሮን ላይ አጉረመረሙ። ከ40 ዓመታት በፊት እግዚአብሔር ሙሴ ዓለቱን በመምታት ለሕዝቡ ውኃ እንዲያወጣ አድርጎ ነበር (ዘጸ.17፡5-6)፤ አሁን ግን እግዚአብሔር ሙሴን ለዓለቱ ተናገር ውኃም ይወጣል አለው። ሙሴ ባለመታዘዝና በቁጣ ዓለቱን ሁለት ጊዜ መታው፤ ከዓለቱ ውኃ ወጣና ሕዝቡን አረካ፤ ነገር ግን ሙሴ በዚህ መልክ ኃጢአት በመሥራቱ ወደ ተስፋይቱ ምድር እንዳይገባ ተከለከለ።

የሙሴ ኃጢአት ምን ነበር? እግዚአብሔር ሙሴን በዚህ ዓይነት ከባድ ቅጣት ለምን ቀጣው? የሙሴ ዋና ስሕተት አለመታዘዝ ብቻ አልነበረም፤ ነገር ግን በእግዚአብሔር ላይ ከመደገፍ ለእርሱ ያለውን ታዛዥነት ከመግለጥ ፈንታ በንግግሩ ኃይሉን እንደራሱ ኃይል አድርጎ አቀረበ። «በውኑ ከዚህህ ድንጋይ ውኃ እናወጣላችኋለን?» በማለት ትአምራቱን የሠራው እግዚአብሔር ሳይሆን እርሱና አሮን እንደሆኑ አድርጎ አቀረበ። ለእግዚአብሔር ብቻ ሊሰጥ የሚገባውን ክብር ለራሳቸው ወሰዱ። እንዲሁም ሙሴ በእግዚአብሔር ላይ እምነት እንደጎደለው የሚያሳይ ነገር አደረገ፤ ምክንያቱም ዓለቱን ሳይመታው፥ በመናገር ብቻ ውኃ ሊወጣ ይችላል ብሎ በእግዚአብሔር አልታመነም።

ይህ ታሪክ አስፈላጊ የሆነ መንፈሳዊ መመሪያን ያስተምረናል። ለእግዚአብሔር የሚሆነውን ክብር ለራስ ማድረግ እጅግ በጣም ክፉ ነገር ነው። በምንዘምርበት፥ በምንሰብክበት፥ በምንመሰክርበትና ሰዎች በሚድኑበት ጊዜ ማንኛውም ኃይል ከእኛ የሚወጣ አይደለም፤ ስለዚህ ከክብሩ የትኛውንም ክፍል መውሰድ አይገባንም፤ ነገር ግን በእኛ ውስጥ ለሚሠራው ለእግዚአብሔር ብቻ ክብር ልንሰጥ ይገባናል። በተጨማሪም፥ እግዚአብሔር አንድን ሰው ወደ ሥልጣን ወይም ወደ መሪነት ኃላፊነት ሲያመጣው፥ ከተራው ምእመን ይልቅ በሥራው ወደሚጠየቅበት ወደ ከፍተኛ ደረጃ የመጣ መሆኑን እንረዳለን፤ ምክንያቱም አንድ መሪ እግዚአብሔርን ባያከብርና ኃጢአትን ቢሠራ፥ ሌሎች በርካታ ሰዎች ኃጢአትን እንዲሠሩ ምክንያት ይሆናል።

| |
|---|
| 18ኛ ጥያቄ. ሀ) እግዚአብሔር በሙሴ ላይ ከባድ ፍርድ ያስተላለፈው ለምን ይመስልሃል? ለ) ከዚህ ነገር ስለ መንፈሳዊ መሪነት ምን እንማራለን? |

8. እስራኤላውያን ወደ ከነዓን ባደረጉት ጉዞ ኤዶማውያን አገራቸውን አቋርጠው እንዳያልፉ ከለከሉዋቸው (ዘኍ.20፡14-21)፤ ስለዚህ እስራኤላውያን በኤዶም ምድር ዙሪያ አድርገው ወደ ሞዓብ ምድር ረጅም መንገድ በመሄድ በቀጥታ ወደ ከነዓን መጓዝ ነበረባቸው።

9. ሊቀ ካህኑ አሮን በሖር ተራራ ሞተ (ዘኍ.22-29)። የሊቀ ካህንነት መብቱም ወደ ልጁ ወደ አልዓዛር ተላለፈ።

10. ዓራድ ከተባለው ንጉሥ ጋር የተደረገ ጦርነት (ዘኁ. 21፡1-3)፥ እስራኤላውያን በ40 ዓመታት ውስጥ የመጀመሪያ ጦርነት ያደረጉት ከከነዓን በስተደቡብ ከምትገኝ ዓራድ ከተባለች ከተማ ንጉሥ ጋር ነበር። የዓራድ ንጉሥ በድንገት አደጋ ጥሎ ያለ አንዳች ማስጠንቀቂያ የገጠማቸው ይመስላል። በውጤቱ እስራኤላውያን ተበቀሉዋቸውና እነርሱንና ከተሞቻቸውን በሙሉ አጠፉ። «ፈጽመው ደመሰሱ» የሚለው ቃል የዕብራይስጥ ትርጉም፥ አንድን ነገር ወይም ሰው ሙሉ በሙሉ ለእግዚአብሔር ከመስጠት ጋር የተያያዘ ነው። አንዳንድ ጊዜ ይህ ቃል ከ «ተለዩ» ወይም ከ

«ተቀደሱ» በኋላ ለእግዚአብሔር ስለሚሠዉት እንስሳ ለመግለጽ የሚያገለግል ቃል ነው። ይህ ቃል በጦርነት ዓውድ ስንጠቀምበት በዚያ ከተማ ውስጥ ያሉ እንስሳትንና ሰዎችን በሙሉ ስለማጥፋት ይናገራል። በዚያ ከተማ ያሉ እንስሳትና ሰዎች ሁሉ ለእግዚአብሔር እንደሆኑ ያህል ነው። እንስሳት ለእርሱ በብዛት የመሠዋታቸውን ያህል፥ ሰዎችም የእግዚአብሔር ፍርድና ጥፋት ዒላማ ሆኑ።

11. በእስራኤል ሕዝብ ላይ ለፍርድ የተላኩት መርዘኛ እባቦች (ዘኁ.21፡4-9)፥ ኤዶማውያን የእስራኤል ሕዝብ በምድራቸው እንዲያልፉ ስላልፈቀዱላቸው፥ ወደ ሰሜን ከመጓዛቸው በፊት ወደ ደቡብ ረጅም ጉዞን ማድረግ ነበረባቸው። ምናልባት ይህ ነገር ከጠየቀው ረጅም ጉዞ የተነሣ፥ ሕዝቡ በእግዚአብሔርና በሙሴ ላይ ማጉረምረም ጀመሩ። የእግዚአብሔርን መና አንበላም በማለታቸው፥ ለእነርሱ ባሳየው ቸርነት ጸጋውን እምቢ ማለታቸው ነበረ። ስለዚህ እግዚአብሔር በሕዝቡ ላይ ፈረደባቸው። መርዛማ እባቦችን ልኮ ብዙ እስራኤላውያን ተነድፈው እንዲሞቱ አደረገ።

ሕዝቡ ኃጢአታቸውን በተናዘዙ ጊዜ፥ የነሐስ እባብ እንዲሠራ እግዚአብሔር ሙሴን አዘዘው። ሕዝቡ ወደ ነሐሱ እባብ በእምነት በተመለከቱ ጊዜ ይፈወሱ ነበር።

> 19ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ዮሐ.3፡14-15 ተመልከት። ይህ ታሪክ የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ሞት ተምሳሌት የሆነው እንዴት ነው? ለ) እስራኤላውያን የዳኑበትና እኛም ደኅንነትን የምናገኝበት መንገድ ተመሳሳይ የሆሀው እንዴት ነው?

የነሐሱ እባብ ታሪክ የኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ ሆነ። ወደ ተሰቀለው የነሐስ እባብ በእምነት የተመለከቱ ሁሉ በሥጋቸው ፈውስ እንዳገኙ ሁሉ፥ ወደ ተሰቀለው ክርስቶስ በእምነት የሚመለከቱም መንፈሳዊ ፈውስን ያገኛሉ። እጅግ የሚያሳዝነው ነገር ግን ከጊዜ በኋላ እስራኤላውያን የነሐስ እባቡን ማምለክ መጀመራቸው ነው (2ኛ ነገ.18፡4 ተመልከት)። ሰይጣን ሁልጊዜ ለሕይወታችን መልካም የሆነን ነገር ይወስድና ወደ ማሰናከያ ዓለትነት ይቀይረዋል።

12. ወደ ሞዓብ ሜዳዎች የተደረገ ጉዞ (ዘኁ.21፡10-35)፥ ሕዝቡ ከምድረ በዳ ተነሥተው ወደ ሰሜን በመጓዝ፥ በሞአብ ምድር ላይ ሰፈሩ። ሊሰፍሩ ወደሚችሉበት ወደ እስራኤላውያን በአሞን ምድር ለማለፍ ፈቃድ በጠየቁ ጊዜ የአሞን ንጉሥ ሲሆን ሊወጋቸው ሞከረ። እስራኤላውያን ግን አሸነፉትና የአሞንን ምድር ወሰዱ። የባሳን ንጉሥ ዐግ ደግሞ እስራኤላውያንን ሊወጋ ሞከረ፤ ነገር ግን ሙሉ ለሙሉ ተሸነፈ። እነዚህ ስፍራዎች የምናሴና የጋድ ነገዶች የወረሷቸው ስፍራዎች ናቸው።

## 4ኛ ቀን:- ዘኁልቁ 22-36

እግዚአብሔር አንድን ሰው ለመባረክ ከወሰነ፥ ያንን ሰው መርገም አንዳች ፋይዳ ይኖረዋልን? የበለዓምና የሞዓብ ንጉሥ ታሪክ እግዚአብሔር የሚወዳቸውን ሰዎች፥ የእግዚአብሔር ሕዝብ ጠላቶች በምንም ዓይነት ብርታት ሊረግሟቸው ቢሞክሩም፥ እርግማናቸውን እግዚአብሔር እንደሚያከሽፍ ያሳያል፤ ሙከራቸውም ከንቱ ልፋት ብቻ ይሆናል። በተጨማሪ ይህ የበለዓምና የሞዓብ ንጉሥ ታሪክ የሚያስተምረን የእግዚአብሔርን ሕዝብ የሚያጠፋቸው ውጫዊ ስደት ሳይሆን፥ ከዓለም ጋር ጓደኝነት መግጠማቸውና ዓለምን መምሰላቸው እንደሆነ ነው።

20ኛ ጥያቄ:- ሀ) የማያምኑ ሰዎች አንተንም ሆነ ቤተ ክርስቲያንን ለመርገም ወይም የሚጎዳ ነገር በማድረግ በእናንተ ላይ ጉዳት ለማድረስ የሚያደርጓቸውን የከንቱ ሙከራ መንገዶች ዘርዝር። ለ) ክርስቲያን ዓለምን በመምሰል ሽንፈትን ሊከናነብ የሚችልባቸውን መንገዶች ዘርዝር።

21ኛ ጥያቄ:- ዘኁ.22-36 አንብብ። ሀ) በለዓም እስራኤልን ይረግም ዘንድ እግዚአብሔር ያልፈቀደው እንዴት ነው? ለ) እስራኤላውያንን ለማሸነፍ በለዓም የተጠቀመበት ምክር ምንድን ነው? (ዘኁ.31፡8፥16 ተመልከት)። ሐ) 2ኛ ጴጥ.2፡14-16 እና ይሁዳ 11 ተመልከት። ስለ በለዓም ምን ያስተምራሉ? መ) በሁለተኛው ቆጠራ ወቅት የተገኘውን የእስራኤልን ሕዝብና የተዋጊውን ኃይል ቁጥር በየነገዱ ጻፍ። ሠ) ወንጀልን ለሠሩ ሰዎች

መሸሸጊያና የስደት ከተሞች ይሆኑ ዘንድ የተለዩትን የስድስት ከተሞች ስም በዝርዝር ጻፍ።

1. ነቢዩ በለዓም (ዘኍ.22-25)፥ የሞዓብ ንጉሥ እስራኤላውያን የአሞንንና የባሳንን ነገሥታት እንዳሸነፉ በሰማ ጊዜ ፈራ፤ ስለዚህ ከምድያማውያን ጋር በመተባበር፥ እስራኤላውያንን በጦርነት ከማሸነፉ ይልቅ በመለኮት ኃይል በመርገም ሊያሸንፋቸው ሞከረ። በሰሜን መስጴጦምያ ብዙ ኪሎ ሜትር ርቆ የሚገኝ በጊዜው የታወቀ በለዓም የሚባል ምዋርተኛ ወይም ጠንቋይ ነበር፤ ስለዚህ የሞዓብ ንጉሥ በለዓምን ለመቅጠር ሞከረ። ቀጥሎ የምንመለከተው ነገር በበለዓምና የእስራኤል ጌታ በሆነው በእግዚአብሔር መካከል የተደረገውን ጦርነት ነው። በለዓም አማኝ ነበር ማለት በጣም አስቸጋሪና የማይመስል ነገር ነው። ሰዎችን በመርገም ባሳየው ስኬታማነት ታዋቂ የነበረ ጠንቋይ ለመሆኑ አንዳችም ጥርጥር የለውም፤ እግዚአብሔር ግን ከዚህ ክፉ ጠንቋይ ጋር ይነጋገር ዘንድ የማያስችለውን ሁኔታ አልፎ በቀጥታ ተናገረው፤ ስለዚህ በመጀመሪያ እግዚአብሔር የእስራኤል ሕዝብ በእርሱ የተባረከ ስለሆነ፥ ሊረግመው እንደማይችል የተናገረውን ቃል በመስማት የሞዓብን ንጉሥ በመርዳት እስራኤልን ከመርገም ተቆጠበ። በለዓም ግን ስስታምነቱ አሸነፈውና ወደ ሞዓብ ሄደ። እግዚአብሔር ኃይሉን ይገልጥ ዘንድ ወደ ሞዓብ እንዲሄድ በለዓምን የተወው ቢሆንም፥ በለዓም ያሰበው ግን በመስገብገብ ጥቅምን ማግኘት ነበር፤ ስለዚህ የእግዚአብሔር መልአክ በመንገድ ላይ ተገናኘው። የሚያስገርመው ነገር ከበለዓም በፊት መልአኩን ያየችው አህያይቱ መሆኗ ነበር። እንዲያውም እግዚአብሔር አህያይቱ ለበለዓም እንድትናገር አስችሎአት ነበር። ከዚህ ታሪክ በግልጽ የምንረዳው በለዓም ወደ ሞዓብ ምድር የሚሄደው በተሳሳተ ፍላጎት እንደነበር ነው። በለዓም ሦስት ጊዜ እስራኤላውያንን ለመርገም ሞከረ፤ ዳሩ ግን ሦስቱም ጊዜ እርግማኑ ወደ ምርቃት (በረከት) ተለወጠበት፤ ስለዚህ የሞዓብ ንጉሥ በለዓምን አባረረው። በለዓምም ከመሄዱ በፊት ስለ እስራኤል ሕዝብ ሁለት ተጨማሪ ዐረፍተ ነገሮችን ተናገረ።

በእነዚህ የመጨረሻ ንግግሮቹ ውስጥ ሁለት ዋና ዋና ትንቢቶች ነበሩ።

1) ሞዓብ «ከያዕቆብ በሚወጣ ኮከብ» ይሸነፋል፤ ይህም ሞዓባውያንን እንደሚያሸንፉ በዳዊት የተነገረ ትንቢት ለመሆኑ ጥርጥር የለውም (ዘኁ.24፡17)፤ ነገር ግን ብዙ ክርስቲያኖች ደግሞ ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር ላይ ስለመንገሡ የተነገረ ትንቢት ነው ይላሉ።

2) እንደ አማሌቃውያን ያሉ ሌሎች ሕዝቦችም በእስራኤላውያን መሸነፍ ነበረባቸው።

ይሁን እንጂ ዘኁ.25 የሚናገረው የሞዓብ ንጉሥ እስራኤልን ለማሸነፍ ተቃርቦ እንደነበር ነው።

በሞዓብ ምድር ቀንጆ የተባሉትን ሴቶች በሙሉ ወደ እስራኤላውያን ሰፈር በመላክ ከእስራኤል ወንዶች ጋር እንዲዳሩ አደረጉ። እነዚህ የቤተ መቅደስ ጋለሞታዎች ሳይሆኑ ስለማይቀሩ፥ እስራኤላውያን ማመንዘር ብቻ ሳይሆን ጣዖትም ያመልኩ ነበር። ከመጽሐፍ ቅዱሳችን በግልጥ እንደምንመለከተው በለዓም ከሞዓብ ምድር አልተመለሰም ነበር፥ (ለምሳሌ፡- ዘኁ.31፡8፥16)። ለገንዘቡ እጅግ ይሳሳ ነበር፤ ስለዚህ እስራኤላውያንን በምንዝርናና በጣዖት አምልኮ ይጥሉአቸው ዘንድ፥ በዚህም የእግዚአብሔር ቁጣ እንዲመጣባቸው ሞዓባውያንን የመከራቸው በለዓም ነበር። እግዚአብሔር ቅዱስ አምላክ መሆኑንና በኃጢአታቸው ሕዝቡን እንደሚያጠፋ ያውቅ ነበር። በኋላም እስራኤል ምድያማውያንን በጦርነት ባሸነፉ ጊዜ በለዓምን እንደ ገደሉ እናውቃለን፤ (ዘኁ.31፡8፤ ኢያ.13፡22 ተመልከት)።

እስራኤላውያን በዝሙትና ጣዖትን በማምለክ ኃጢአት ውስጥ ስለወደቁ፥ የእግዚአብሔር ቁጣ በላያቸው ላይ ነደደና 24000 ሰዎች ሞቱ። እግዚአብሔር በእስራኤል ላይ የጀመረው ይህ ፍርድ የቆመው፥ የአሮን ልጅ የአልዓዛር ልጅ የሆነው ፊንሐስ በጽድቅ ተቆጥቶ ምንዝርና ሲፈጽሙ የተገኙ ወንድና ሴት ከገደለ በኋላ ነበር።

እግዚአብሔር የፊንሐስን ቅንዓት አከበረ። ሁልጊዜ የክህነት መብቱን እንደሚጠብቅለት እግዚአብሔር ለፊንሐስ ቃል ኪዳን

ገባለት። ዔሊ በክህነት ካገለገለበት ከጥቂት ጊዜያት በስተቀር፥ ቤተ መቅደሱ እስከተደመሰሰበት እስከ 70 ዓ.ም. ድረስ የፊንሐስ ዘር የሊቀ ካህንነቱን አገልግሎት እንደያዘ ዘልቆአል።

> 22ኛ ጥያቄ፡- ሀ) በኃጢአት ላይ ቅንአትና ቁጣችንን ማሳየት ትክክል የሚሆነው መቼ ነው? ምሳሌዎችን ጥቀስ። ለ) በኃጢአት ላይ የምንቆጣው አንዳንድ ጊዜ ብቻ የሆነው ለምንድን ነው? ሐ) ይህስ ራሳችንን ከፊንሐስ ጋር ስናወዳድር ምን ያሳየናል?

2. ሁለተኛው የሕዝብ ቆጠራ (ዘኁ.26)፥ እስራኤላውያን ከ38 ዓመታት በፊት በሲና ተራራ በነበሩበት ወቅት ሙሴ ዕድሚያቸው ከ 20 ዓመት በላይ የሆኑ እስራኤላውያን ወንዶችን ሁሉ ቆጥሮ ነበር። ቁጥራቸውም 603 550 ነበር። ከ38 ዓመታት በኋላ የከነዓንን ምድር ለመውረስ ተዘጋጅተው ባሉበት ወቅት በተደረገው ቆጠራ የወንዶቹ ቁጥር 601 730 ሆነ።

3. የተለያዩ ትእዛዛት (ዘኁ.27-30) በዚህ ስፍራ ልንመለከተው የሚገባ የተለየ ነጥብ እግዚአብሔር ኢያሱን ተከታዩ መሪ አድርጎ እንዲሾም ሙሴን ማዘዙ ነው። በተጨማሪ በቤት ውስጥ ወንዶች ልጆች ከሌሉ ርስትን የማውረስ ጉዳይ ለሴት ልጆች እንደሚተላለፍ፥ በተቀደሱ ቀናት ለእግዚአብሔር ስለሚቀርቡ መሥዋዕቶች፥ ለእግዚአብሔር የተገቡ ስእለቶች ምን መደረግ እንዳለባቸው የተሰጡ ሕግጋት እናገኛለን።

4. ምድያማውያን ተቀጡ (ዘኁ.31)፥ ምድያማውያን ብዙ እስራኤላውያንን ስላጠፉ እግዚአብሔር ቀጣቸው። እስራኤላውያን ተዋግተው አሸነፏቸው። በለዓምም በዚህ ጦርነት ተገደለ። እግዚአብሔር ከምድያማውያን አብዛኞዎቹ እንዲገደሉ አዘዘ። ከምርኮውም እስራኤላውያን የተወሰነውን እንዲወስዱና የቀረውን ግን ወደ ጌታ እንዲያመጡ ታዘዙ።

5. ስለ ከነዓን ምድር የተሰጡ ትእዛዛት (ዘኁ. 32-36)፥ በእነዚህ ምዕራፎች ውስጥ የተካተቱ ሁለት ዋና ዋና ነገሮችን እናያለን። የመጀመሪያው፥ ሙሴ ከዮርዳኖስ ወንዝ በስተምሥራቅ ያለውን ስፍራ ለሦስት ነገዶች ርስት ይሆን ዘንድ ስለመስጠቱ ነው። ከፊሉ

የተሰጠው ለምናሴ ነገድ እኩሌታ ነው። (ለቀሪው የምናሴ ነገድ ከዮርዳኖስ ወንዝ በስተምዕራብ የሚገኝ ክፍል ተሰጥቶታል)። ይህንን ክፍል ያገኙት ሁለቱ የጋድና የሮቤል ነገዶች ሲሆኑ እነርሱም የቀሩት ወንድሞቻቸው በሙሉ የተሰጣቸውን የከነዓንን ምድር እስኪወርሱ ድረስ የዮርዳኖስን ወንዝ በመሻገር አብረዋቸው ሊዋጉ ቃል ገብተው ነበር። ሙሴ ከዮርዳኖስ ወንዝ በስተምዕራብ የሚገኘውንና ከከነዓናውያን በጦርነት የሚወሰደውን ምድር በሙሉ 9 1/2 ለሆኑት ለቀሩት የእስራኤል ነገዶች አከፋፈለ።

ሁለተኛው ነገር ደግሞ፥ ሙሴ የተወሰኑ ከተሞችን ለሌዋውያን መለየቱ ነበር። እንደምታስታውሰው፥ እግዚአብሔር የካህናት ዘር ለሆኑት ለሌዋውያን የሰጣቸው ምድር አልነበረም። ይልቁንም በከነዓን ምድር ሁሉ የተሰራጩ በአጠቃላይ 48 ከተሞች ለእነርሱ ተሰጥተው ነበር። የዚህን ተስፋ መፈጸም ለመረዳት (ኢያሱ 21ን ተመልከት)። ሙሴ በተጨማሪ ሦስት በስተምሥራቅ፥ ሦስት በዮርዳኖስ ወንዝ በስተምዕራብ፥ በአጠቃላይ ስድስት ከተሞችን «የስደተኞች ከተሞች» አድርጎ ለያቸው። እነዚህ ከተሞች በድንገት ሰውን ለገደለ ለማንኛውም ሰው መሸሸጊያ ወይም መጠጊያ በመሆን ያገለግሉ ነበር። ይህ በዘመኑ ከተለመደው በሟቹ ቤተሰብ ወይም ቤተ ዘመድ ከሚሰነዘር የደም በቀል የሚጠብቀው ነበር።

| |
|---|
| 23ኛ ጥያቄ:- ሀ) በኦሪት ዘኍልቁ ስለ እግዚአብሔር፥ በእምነት ስለ መራመድና ኃጢአት ስለሚያስከትለው ፍርድ ምን ተማርክ? ለ) የእስራኤላውያን ታሪክ ዛሬ በምድር ከሚኖሩ ከብዙ ክርስቲያኖች ታሪክ ጋር የሚመሳሰለው እንዴት ነው? |

ኦሪት ዘኍልቁ የሚያበቃው፥ እስራኤላውያን ከ400 ዓመታት በፊት እግዚአብሔር ለአብርሃም ተስፋ የሰጠውን ምድር ለመውረስ የዮርዳኖስን ወንዝ ሊሻገሩ ተዘጋጅተው በነበሩበት ሁኔታ ነው። ወደ ከነዓን ምድር ከመግባታቸው አስቀድሞ ግን እግዚአብሔር ከ39 ዓመታት በፊት በሲና ተራራ የሰጣቸውን ሕግ ሙሴ ሊያስታውሳቸው ፈለገ። ኦሪት ዘዳግም የሕጉን በዚህ መልክ መደገም የሚያሳይ ነው።

አሪት ዘኍልቁ የእግዚአብሔር ሕዝብ ብዙ ጊዜ ከመታዘዝ ይልቅ ባለመታዘዝ እንደሚኖር የሚናገር አሳዛኝ ታሪክ ነው፤ (ሮሜ 7፡7-25 ተመልከት)። በራሳችን ላይ ፍርድን የምናመጣው እኛው እራሳችን ነን። እግዚአብሔር ቅዱስና ኃጢአትን የሚቀጣ መሆኑን እናያለን፤ ደግሞም ሕዝቡ ምንም እንኳ ደጋግመው ቢያጠፉም እንዳላጠፉቸውና ይጠነቀቅላቸው እንደ ነበር እንመለከታለን። እግዚአብሔር ለእያንዳንዳችንም ጸጋ የተሞላ አምላክ ነው። እንደ ጳውሎስ ሁላችንም የባስን ኃጢአተኞች መሆናችንን መናገር እንችላለን (1ኛ ጢሞ.1፡15-16 ተመልከት)። እግዚአብሔር በጽድቅ ቢፈርድ ኖሮ ሊደርስብን ይችል የነበረው ቅጣት አልደረሰብንም፤ ግን ኢየሱስ ቅጣታችንን በመስቀል ላይ ተሸከመ። አሁን እግዚአብሔር፥ በኃጢአት ላይ በድል የምንራመድበትን፥ እርሱን በመታዘዝና በማክበር ለመኖር የምንችልበትን ኃይል ይሰጠናል። እንግዲህ ሌሎች ሰዎች ዓለማዊ በሆነ መንገድ ቢሄዱም እንኳ አንተ በቅድስናና በመታዘዝ ለመኖር ወስነሃልን› እንደ ፊንሐስ፥ ኢያሱና ካሌብ ለመሆን ፈቃደኛ ነህን?

| |
|---|
| 24ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ያለማቋረጥ ኃጢአት ብታደርግም እንኳ እግዚአብሔር እስከ ዛሬ ድረስ ስላሳየህ ትዕግሥት እርሱን ለማመስገን ጊዜ ይኑርህ። ለ) በእግዚአብሔር ፊት በንጽሕናና በድል ለእርሱ ክብርን በሚያመጣ መንገድ ለመኖር ትችል ዘንድ ዕለት ዕለት ብርታትና ኃይል እንዲሰጥህ ለምነው። |

5ኛ ቀን፡- የዚህን ሳምንት ትምህርት ከልስና ለሳምንታዊ ስብሰባ ዝግጅት ይረዳህ ዘንድ የውይይት ጥያቄዎችን ተመልከት።

ሳምንታዊ ስብሰባ

1. የሳምንቱ የአምልኮ ጊዜ

2. ጸሎት

3. የትምህርቱ ክለሳ

4. ውይይት

   1. ሀ) የክርስትና ሕይወት እንደ ጉዞ የሚሆነው እንዴት ነው? ለ) የክርስትና ሕይወታችን በምድረ በዳ ከተንከራተቱት

እስራኤላውያን ጉዞ ጋር የሚመሳሰለው እንዴት ነው? ሐ) በአሪት ዘኁልቁ ውስጥ ከሚገኘው የእስራኤላውያን ታሪክ እግዚአብሔርን ደስ በሚያሰኝ መንገድ ስለ መመላለስ የምንማረው ነገር ምንድን ነው?

2. ሀ) እግዚአብሔር እስራኤላውያንን በምድረ በዳ የፈተነው ለምን ነበር? ለ) እግዚአብሔር ዛሬስ የሚፈትነን ለምንድን ነው? ሐ) ያዕ.1፡2-4ና ሮሜ 5፡3-5 አንብብ። እነዚህ ጥቅሶች በሕይወትህ የተፈጸሙት እንዴት ነው?

3. ሀ) በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያለ ደካማ አስተዳደር ውዥንብር የሚፈጥረው እንዴት ነው? ለ) ጥሩ አስተዳደር የቤተ ክርስቲያንን ሥራ የሚረዳው እንዴት ነው? ሐ) እግዚአብሔር የእስራኤልን ነገዶች በሰፈሩበት ቦታና በጉዞአቸው ያደራጃቸው እንዴት ነበር? መ) ስለ መልካም አደረጃጀት ከአሪት ዘኁልቁ የምትማረው ነገር ምንድን ነው? ሠ) ቤተ ክርስቲያንህ የበለጠ ስኬታማ ለመሆን በተሻለ ሁኔታ የምትደራጅባቸው መንገዶች የትኞቹ ናቸው?

4. ሀ) በእስራኤል ሕዝብ መሪዎች መካከል የነበረው መቀናናት ሙሴንና እግዚአብሔርን ያስቸገራቸው እንዴት ነው? ለ) ስለ ቀናተኛ መሪዎች መንፈሳዊ ሕይወትና በእግዚአብሔርና በመሪነት ላይ ስላላቸው የተሳሳተ አመለካከት ይህ ምን ያሳየናል? ሐ) በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ቀናተኝነትን የምንዋጋው እንዴት ነው?

5. ሀ) ወደ ከነዓን ያስገባቸው ዘንድ በእግዚአብሔር ላይ በሚገባ ባለመታመናቸው፥ እግዚአብሔር በእስራኤላውያን ላይ ከባድ ፍርድን የበየነው ለምንድን ነው? ለ) የምናደርገው መልካም ምርጫ በወደፊት ሕይወታችን ላይ ለብዙ ዓመታት በጎ ውጤት ሊያመጣ ስለሚችልባቸው መንገዶች ተናገር። ሐ) የተሳሳተ ምርጫ ማድረግ በወደፊት ሕይወታችን ላይ ለብዙ ዓመታት በጎ ውጤት ሊያመጣ ስለሚችልባቸው መንገዶች ተናገር። ሐ) የተሳሳተ ምርጫ ማድረግ በወደፊት ሕይወታችን ላይ ለብዙ ዓመታት ከፋት ተጽዕኖ ሊያሳድር የሚችልበትን

ምሳሌ ጥቀስ። መ) እግዚአብሔር ይቅር ካለን በኋላ እንኳ ኃጢአት ለረጅም ጊዜ የሚዘልቅ ውጤት ያለው ስለመሆኑ ምን ለመማር እንችላለን?

6. ሀ) ዓለም የእግዚአብሔርን ሕዝብ ለመርገምና ለማጥፋት ስላላት ኃይል ከበለዓም ታሪክ የምንማረው ምንድን ነው? ለ) ለአንድ መሪ ስግብግብነት በሕይወቱ እንዴት አደገኛ ሊሆን እንደሚችል ከበለዓም ሕይወት የምንማረው ነገር ምንድን ነው? ሐ) የእግዚአብሔር ሕዝብ ዓለምን ሲመስሉ በዓለም እንዴት ሊሸነፉ እንደሚችሉ ከበለዓም ታሪክ ምን እንማራለን?

7. ሀ) ከአሪት ዘኁልቁ የተማርካቸውን መንፈሳዊ እውነቶች ዘርዝር። ለ) እነዚህን እውነቶች ለቤተ ክርስቲያንህ አባሎች የምታስተምራቸው እንዴት ነው?

5. ፀሎት

# ትምህርት 10

## 1ኛ ቀን፡- የኦሪት ዘዳግም መግቢያ

በፔንታቱክ መጻሕፍት ጥናታችን፥ በብሉይ ኪዳን የእግዚአብሔር ሕዝብ የነበሩት እስራኤላውያን መሠረታቸው ከሆነው ከአብርሃም ጀምሮ፥ ታላቅ ሕዝብ ወደ መሆን እስከ ደረሱበት ጊዜ ድረስ ያለውን ነገር ተመልክተናል። እግዚአብሔር በጸጋው ይህንን ታላቅ ሕዝብ በባርነትና በምድረ በዳም እያለ ተጠንቅቆ የመራበትን ኃይሉን መስከረናል። እግዚአብሔር ባመፁበት ሕዝብ ላይ የፈረደባቸው ቢሆንም፥ በምሕረቱ ለሕዝቡ እየተጠነቀቀ እስከ ተስፋይቱ ምድር ጫፍ ድረስ መርቶአቸዋል። ሙሴ የመጨረሻዎቹን ቃሎቹን ለአዲሱ የእስራኤላውያን ትውልድ የተናገረው በዚህ በተስፋይቱ ምድር ጫፍ ላይ ነበር። እነዚህ የመጨረሻዎቹ የሙሴ ቃሎች በኦሪት ዘዳግም ውስጥ ይገኛሉ። ከዚያም ሙሴ የተስፋይቱን ምድር ከሩቅ አሻግሮ አይቶ ሞተ።

### የኦሪት ዘዳግም ርዕስ

በአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ፥ ከፔንታቱክ መጻሕፍት መካከል የአምስተኛው መጽሐፍ ርዕስ ኦሪት ዘዳግም ይባላል። ይህ ስም ከሴፕቱዋጀንት የተገኘ ሲሆን፥ ትርጉሙም «ሁለተኛ ሕግ» ወይም «የሕግ ድግግሞሽ» ማለት ነው። ይህ ስም የሚያንፀባርቀው የኦሪት ዘዳግም አብዛኛው ክፍል እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን በሲና ተራራ የሰጣቸው ሕግ የተደገመበትና ተስፋፍቶ የቀረበበት መሆኑን ነው።

አይሁድ ይህንን መጽሐፍ በኦሪት ዘዳግም መጀመሪያ ቁጥር ላይ የሚገኙትን የሚከተሉትን ቃላት በመውሰድ «ቃሎቹ እነዚህ ናቸው» የሚል ርዕስ ሰጥተውታል።

### የኦሪት ዘዳግም ጸሐፊ

---

1ኛ ጥያቄ፥ የኦሪት ዘዳግም ጸሐፊ ማን እንደሆነ ከመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት ተመልከት።

---

በትምህርት 3 ስለ ፔንታቱክ መጽሐፍ ጸሐፊ የቀረበውን ትንተና ከልስ።

በዘመናት ሁሉ አይሁድም ሆኑ ክርስቲያኖች የኦሪት ዘዳግም ጸሐፊ ሙሴ እንደሆነ ይስማሙ ነበር። በቅርብ ጊዜ ውስጥ ግን ሰዎች ይህንን በሁለት ምክንያቶች በመጠራጠር ጥያቄ ማንሣት ጀምረዋል። አንደኛ፥ ሙሴ በአንድ በተቀደሰ ስፍራ የማምለክን አስፈላጊነት በሚመለከት ትኩረት ሰጥቶ ይናገራል፤ ይህ ግን በእስራኤል ታሪክ ውስጥ እስከ ንጉሥ ኢዮስያስና ሕዝቅያስ ድረስ በተግባር አልታየም። ሁለተኛ፥ ሙሴ በእስራኤል ንጉሥ ያለ ይመስል፥ ስለ ነገሥታት ይናገራል፤ ስለዚህ ኦሪት ዘዳግም የተጻፈው ነገሥታት እስራኤልን መግዛት ከጀመሩ በኋላ መሆን አለበት ይላሉ።

ሆኖም ግን ኦሪት ዘዳግም እነርሱ እንደሚሉት ቆይቶ የተጻፈ መሆኑን ይህ አያረጋግጥም። ሙሴ በተለያዩ ስፍራዎች የሚደረግ አምልኮ የሚያመጣውን ችግርና እስራኤልም በዙሪያዋ እንዳሉ እንደ ሌሎች ሕዝቦች ንጉሥ መፈለጓን አስቀድሞ በመገንዘብ፥ነገሥታቱን በሚመለከት መመሪያ መስጠቱንና በአንድ ስፍራ የማምለክን አስፈጋጊነት መናገሩን የሚጠቁም ሊሆን ይችላል። ዘዳግም ውስጥ ጸሐፊው ሙሴ እንደሆነ የተጠቀሱ ነገሮች አሉ (ዘዳግ. 1:5፤31:9፥22፥24)። በቀሩት ቅዱሳት መጻሕፍት የኦሪት ዘዳግም ጸሐፊ ሙሴ መሆኑ ተናግሯል (ለምሳሌ :- 1ኛ ነገ. 2:3፤8:53)። ሆኖም ግን፥ አብዛኛውን የመጽሐፉን ክፍል ሙሴ ነው የጻፈው የሚለው አሳብ እንደተጠበቀው ሆኖ፥መጽሐፉን ያቀነባበረው ሰው ከሙሴ ሞት በኋላ አንዳንዱን ነገር በመጨመር አጠናክሮት ሊሆን ይችላል (ዘዳ. 1-5፤ምዕራፍ 34)።

ኦሪት ዘዳግም የተጻፈው፥አይሁድ በምድር በዳ መንከራተታቸው አብቅቶ ወደ ከነዓን ምድር ከመግባታቸው በፊት ነው፤ይህም በ1400ዓ.ዓ. ገደማ መሆኑ ነው።

## የኦሪት ዘዳግም አስተዋጽኦ

ኦሪት ዘዳግም ሁሉንም ዓይነት ሁኔታ የሚጨምሩ የተለያዩ በርካታ ሕግጋት ያሉት በመሆኑ መጽሐፉን በአስተዋጽኦው ከፋፍሎ ማቅረቡ አስቸጋሪ ነው። ቀላሉ መንገድ ኦሪት ዘዳግምን በሙሴ ሦስት ዋና ዋና ስብከቶች ዙሪያ ማደራጀት ነው።

1. የሙሴ የመጀመሪያ ስብከት (ዘዳግም 1፡1-4፡43)

2. የሙሴ ሁለተኛው ስብከት (ዘዳግ. 4፡44-28፡68)

3. የሙሴ ሦስተኛው ስብከት (ዘዳግ. 29-33)

4. የሙሴ ሞት (ዘዳግ. 34)

ሆኖም ኦሪት ዘዳግም ሊደራጅ የሚችልበት፥የመጽሐፉን ባሕርይ የሚያመለክት ሌላ መንገድ አለ። ብዙ ምሁራን ኦሪት ዘዳግምን የሚያዩት በእግዚአብሔርና በሕዝቡ መካከል ያለ ሰነድ ወይም ቃል ኪዳን አድርገው ነው።

ቀደም ሲል እንዳየነው እግዚአብሔር ሕግን በሲና ተራራ በሰጠበት ጊዜ፥በመካከለኛው ምሥራቅ በሕዝቡ ባሕል መሠረት እንዴት እንዳደራጀው ተመልክተናል። «ሱዜረይም-ቫሳል» በመባል የሚታወቀውንና በ2ኛው ሺህ ዓ.ዓ. በኬጢያውያን መካከል በጣም ተለምዶ የነበረውን የስምምነት አሠራር ሲጠቀም እናያለን። ይህ ስምምነት አሸናፊ በሆነው ንጉሥ ወይም መሪዎችና ተገዢ በሆኑ ነገሥታት መካከል የሚፈጸም ነበር። በኦሪት ዘጸአት እግዚአብሔር ገዢ ንጉሥ ሆኖ፥ ቃል ኪዳኑን የዚህ ስምምነት እንደ ቫሳል (ሎሌ) ተቀባይ ከሆኑት ከእስራኤላውያን ጋር አድርጎ እናያለን። የሚከተለውን ባሕላዊ ያቃል ኪዳን ስምምነትን ኦሪት ዘዳግም እንዴት እንደሚመስሉ ተመልከት። እግዚአብሔር ንጉሥ (ሱዜረይም) መሆኑን እስራኤል ደግሞ ተገዢ (የስምምነቱ ውል ተቀባይ «ቫሳል» ወይም ሎሌ) መሆኗን አስታውስ።

1. የተናጋሪው ወይም የቃል ኪዳኑ ሰጭ መግቢያ፡- በዘዳግ. 1፡1-5 ተንፀባርቋል። ምንም እንኳ ተናጋሪው ሙሴ ቢሆንም የሚናገረው ንጉሡን- እግዚአብሔርን ወክሎ ነው።

2. የቃል ኪዳኑ ታሪካዊ አቀራረብ፡- ይህ በዘዳግ. 1፡6-3፡29 ሙሴ የእስራኤልን ሕዝብ ታሪክ ደግሞ በሚናገርበት (በሚከልስበት) ጊዜ እግዚአብሔር እነርሱን እንዴት እንደመረጣቸው፥ ከግብፅ ባርነት ነፃ በማውጣት ወደ ተስፋይቱ ምድር እንዴት እንደመራቸው በሚያሳየው ክፍል ተንፀባርቋል።

3. ስለ ቃል ኪዳኑ ከፍጻሜ መድረስ ይመሰክሩ ዘንድ ተገናኘው ሊታዘዛቸው የሚገባ የቃል ኪዳኑ ቅድመ ሁኔታዎች፡- በማክበር ይጠብቁት ዘንድ እግዚአብሔር ለእስራኤል ትእዛዛቱን ሁሉ በሰጠበት በዘዳግም 4-26 ይታያል።

4. የቃል ኪዳኑ ሕጋዊ ሰነድ ምን ማድረግ እንደሚገባ የተሰጡ መመሪያዎች፡- በኦሪት ዘዳግም 27፡2-3 ሙሴ ሕጉ በድንጋይ ላይ እንዴት እንደሚጻፍና እስራኤላውያን ወደ ተስፋይቱ ምድር በገቡ ጊዜ አስታዋሽ ሆኖ እንደሚቀመጥ መመሪያ ሰጠ።

5. ምስክሮች ተጠርተው ነበር (ዘዳግ. 31-32)፡- አሕዛብ ብዙውን ጊዜ ለምስክርነት የሚጠሩት ጣዖቶቻቸውን ነበር፤ ነገር ግን ሙሴ በመጀመሪያ ምስክር ይሆን ዘንድ መዝሙር ዘመረ (ዘዳግ. 31፡19-22)። ቀጥሎም በዘላለማዊ አምላክና በሕዝቡ መካከል ምስክር ይሆን ዘንድ ሰማይና ምድርን ጠራ።

6. ንጉሡ በረከትንና ርግማንን ወይም ለቃል ኪዳኑ በመታዘዝ የሚሰጥ ሽልማትንና ባለመታዘዝ የሚመጣ ቅጣትን ዘረዘረ፡- በዘዳግ. 28 እግዚአብሔር እስራኤላውያን ለቃል ኪዳኑ ቢታዘዙ የሚያገኙትን በረከት፥ ባይታዘዙ ደግሞ የሚጠብቃቸውን ቅጣት ወይም ርግማን የዘረዘሩበት ክፍል ነው።

ከዚህ የምንረዳው፥ኦሪት ዘዳግም በሲና ተራራ የተሰጠው የሕግ መደገም ብቻ ሳይሆን፥እስራኤላውያን አድቀድሞ በሲና ተራራ አባቶቻቸው ያደረጉትን ስምምነት ወይም ቃል ኪዳን ለሁለተኛ ጊዜ ማጽናታቸውን የሚያሳይ ሕጋዊ ሰነድ መሆኑን ነው። በሲና ተራራ እንደነበረው ቃል ኪዳን፥ በእግዚአብሔርና በእስራኤል ሕዝብ መካከል ሊኖር የሚገባውን ግንኙነት ዘርዝር አድርጎ የሚያቀርብ ነው።

| |
|---|
| 2ኛ ጥያቄ፥ ሀ) በዘመናችን የዚሁ ተመሳሳይ የሆነ ግንኙነት በእግዚአብሔርና በክርስቲያኖች መካከል የሚኖረው እንዴት ነው? ለ) ተመሳሳይ ነው ወይስ የተለያየ? አብራራ። |

## የኦሪት ዘዳግም መጽሐፍ ዓላማ

1. በኦሪት ዘዳግም፥በእግዚአብሔርና በእስራኤል ሕዝብ መካከል በሲና ተራራ ተደርጎ የነበረው የቃል ኪዳን ስምምነት እንደገና ተደገመና ሕጋዊ ሆነ። እንደምታስታውሰው፥በሲና ተራራ ላይ እግዚአብሔር ራሱን በገለጠበትና የሲና ተራራ ቃል ኪዳን በሰጠበት ጊዜ የነበሩ በዕድሜ ከ20 ዓመት በላይ የሆኑ ሰዎች ሁሉ በምድረ በዳ አልቀዋል። እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ከግብፅ ባርነት ያወጣበትና በዓይናቸው ያዩትን የግል ምስክርነት መስጠት የሚችሉ ዕድሜያቸው ከ60 ዓመት በላይ የሆኑ ሦስት ሰዎች ብቻ ነበሩ። እነርሱም ሙሴ፥ ኢያሱና ካሌብ ነበሩ። አሁን የእነርሱን ስፍራ ለመረከብ አዲስ ትውልድ ተነሥቷል። እነዚህ በሲና ተራራ ቃል ኪዳን ለመስማማት በቦታው አልነበሩም፤ ስለዚህ ወደ ከነዓን ከመግባታቸው በፊት ሙሴ የቃል ኪዳኑን ስምምነት ደገመላቸውና እግዚአብሔር በሲና ተራራ በሰጠው የቃል ኪዳን ስምምነት (ቅድመ ሁኔታዎች) ላይ ተመሥርቶ አስፋፋው።

---

3ኛ ጥያቄ፥ ሀ) እያንዳንዱ ትውልድ ከእግዚአብሔር ጋር ያለውን ግንኙነት በሙሉ ሊረዳና ከግል ሕይወቱም ጋር ሊያዛምድ የሚያስፈልገው ለምንድን ነው? ለ) ብዙ ወጣቶች ወላጆቻቸው ክርስቲያኖች ስለሆኑ ብቻ እነርሱም ክርስቲያኖች እንደሆኑ የሚያስቡት ለምንድን ነው? ሐ) ይህ አስተሳሰብ ስሕተተ የሆነው ለምንድን ነው? መ) እያንዳንዱ አዲስ ትውልድ ወንጌልን በሙላት እንዲረዳና እምነቱን በእግዚአብሔር ላይ በማድረግ ከእግዚአብሔር ጋር ግላዊ ግንኙነት እንዲኖረው ለመርዳት ቤተ ክርስቲያንህ ምን ማድረግ ትችላለች?

---

2. ሙሴ ኦሪት ዘዳግምን የጻፈው፥ የእስራኤል አዲስ ትውልድና የሚቀጥለው ትውልድ ቃል ኪዳን የሚጠይቀውን ቅድመ-ሁኔታ እንዲያሟላ ከልብ ለማደፋፈር ነው፤ ነገር ግን ሳይታሰብ በቃል ኪዳኑ ላይ ውስጣዊ ያልሆነ መታዘዝ እንዲደረግ አልወደደም ነበር። ሙሴ በቃል ኪዳኑ መሠረት ላይ ሁለት ዋና ዋና ትእዛዛት እንደነበሩ አስተውሎ ነበር። የመጀመሪያው፥ እግዚአብሔርን

በፍጹም ልብ የመውደድ፥የማክበርና የመታዘዝ ነገር መኖሩ ነው (ዘዳግ. 6፡4-9፤10፡12-13)። ሁለተኛ ደግሞ፥ ባልንጀራን የማክበር፥ተገቢውን ስፍራ የመስጠትና የመውደድ ትእዛዝ መሆኑ ነው፥(ዘሌ. 19፡18)። እስራኤላውያንና ክርስቲያኖች የእግዚአብሔር ቅዱስ ሕዝብ እንደ መሆናቸው መጠን ተገቢውን ዝምድናን ለመጠበቅ፥ከእግዚአብሔር ጋር ሕያው የሆነ የመታዘዝ፥እርስ በርስ የመፈቃቀድ ግንኙነት ሊያደርጉ ይገባል።

4ኛ ጥያቄ፥ ዘዳግ።10፡12-13 በቃልህ አጥና። እግዚአብሔርን መፍራት፥በመንገዱ መራመድና በፍጹም ልብና በፍጹም ነፍስ እርሱን መውደድ ማለት ምን ማለት ነው?
5ኛ ጥያቄ፥ ባልንጀሮቻችንን በምንወድበት ጊዜ ከትእዛዛቱ አብዛኛውን የምንጠብቀው እንዴት ነው?

3. ከዚህ ቀደም እግዚአብሔር ከእስራኤል ጋር ያደረገው የቃል ኪዳን መሠረት እግዚአብሔር በሁለት ጽላቶች ላይ ጽፎ ለሙሴ የሰጠው አሥርቱ ትእዛዛት እንደነበር ተመልክተናል። አሁንም ደግሞ በኦሪት ዘዳግም እነዚህን አሥር ትእዛዛት ከአይሁዶች አጠቃላይ ሕይወት ጋር ያላቸውን ዝምድና በግልጥ በሚያሳይ መንገድ አስፋፍቶ ያቀርባቸዋል። አንዳንዱ ምሁራን ሙሴ ይህንን መጽሐፍ ያዘጋጀው በአሥርቱ ትእዛዛት ዙሪያ ነው ይላሉ። በዚህ መሠረት ኦሪት ዘዳግምን የሚያብራሩት እንደሚከተለው ነው፡-

1. 1ኛ ትእዛዝ፡- ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይሁኑልህ። ሙሴ ይህንን ትእዛዝ ከኦሪት ዘዳግም 6-11 ባለው ክፍል ውስጥ አብራርቶታል። የእነዚህ ምዕራፎች ትኩረት እግዚአብሔር ፈጣሪ በመሆኑና እስራኤልን ከሌሎች አሕዛብ ለይቶ በመምረጡ ባለው መለኮታዊ ሥልጣን ላይ ነው፤ ስለዚህ እስራኤል ሌሎች አማልክትን ሳይሆን እግዚአብሔርን ልታከብርና እርሱን ብቻ ልታመልክ ይገባት ነበር። ትኩረቱ እግዚአብሔርን በመውደድና በመታዘዝ ላይ ነው። የእስራኤላውያን ተቀዳሚ ምርጫ እግዚአብሔርን ማምለክ ሲሆን እርሱ በሕይወታቸው ሁሉ ላይ የመጨረሻ ባለሥልጣን መሆን ነበረበት።

6ኛ ጥያቄ፣ ሀ) እግዚአብሔር ከእያንዳንዳችን ስለሚፈልገው ነገር ከላይ የምናየው የመጨረሻው ዐረፍተ ነገር ምንን ያመለክተናል? ለ) ይህ በሕይወትህ የታየው እንዴት ነው?

2. 2ኛ ትእዛዝ፡- የተቀረፀ ምስል ለአንተ አታድርግ (ዘዳግ. 12)። ይህንን ትእዛዝ በጥሩ ሁኔታ ለመረዳት አማልክቶቻቸውን የሚወክሉ በርካታ የተቀረፀ ምስል ካሉአቸው ከከነዓናውያን ጋር በማነጻጸር ማየት የተሻለ ነው። እስራኤላውያን የከነዓናውያንን ልምምድ ከመከተል ይልቅ ከፍተኛ ክብር እንዳለው በማወቅ ለእግዚአብሔር ክብር መስጠት ነበረባቸው። እውነተኛውን የእግዚአብሔር ባሕርይ በማወቅ እርሱን ሊያከብሩ ይገባ ነበር። እግዚአብሔር መንፈስ ስለሆነ በሥዕል ወይም በተቀረፀ ምስል ሊመሰል አይገባውም። የዘለዓለማዊውን አምላካዊ ታላቅነትን ስለማያንጸባርቅ፣ እግዚአብሔርን ግዙፍ በሆነ መንገድ ለመግለጥ መሞከር እርሱን መስደብ ነው። እንደ ከነዓናውያን አማልክት ከእርሱ የሚፈልገውን ነገር ለማግኘት በጥቃቅን መሥዋዕት የሚሸነገል አይደለም። የአምላኪውን ሰው የግል ፍላጎት ለማርካት የሚጠቅም ሊሆንም አይችልም። ይልቁንም እርሱ ሉዓላዊና ሁሉን የሚችል አምላክ ነው።

7ኛ ጥያቄ፣ ሀ) አንዳንድ ክርስቲያኖች ለእግዚአብሔር አንድን ነገር ለመስጠት ወይም አንድ ነገር እንደሚያደርጉለት ቃል በመግባት ወዘተ. ከእርሱ አንድ ነገር ለማግኘት የመሸንገል ሙከራ የሚያደርጉት እንዴት ነው? ለ) አንዳንድ ክርስቲያኖች እግዚአብሔርን በፍቅር ከማገልገል ይልቅ፣የግል ጥቅምን ከመፈለግ አንጻር ብቻ የሚያገለግሉት እንዴት ነው? ሐ) አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔር በፍቅር ከማገልገል ይልቅ የበለጠ እርሱ ስለሰጠህ ነገር ብቻ የምታገለግለው እንዴት እንደነበር ምሳሌ ስጥ። መ) ይህ ስሕተት የሆነው ለምንድን ነው?

3. 3ኛ ትእዛዝ፡- የእግዚአብሔር የአምላክህን ስም በከንቱ አትጥራ (ዘዳግ. 13፡1-14፡21)። ይህ ክፍል የሚገልጸው

እግዚአብሔርን በሕይወታቸው ሙሉ በተለይም ደግሞ በከንፈሮቻቸው የማክበርና ራሳቸውን አሳልፈው ስለ መስጠት አስፈላጊነት ነው። እስራኤላውያን ስለ እነዚህ ነገሮች እርግጠኞች ለመሆን፡- ሀ) ለእግዚአብሔር ያላቸውን አምልኮ ንጽሕናን መጠበቅ፥ ለ)ኃጢአትን እንደመጥላታቸው፥በመካከላቸው በሚከሰትበት ጊዜ መፍረድ፥ እንዲሁም ሐ) ንጽሕናቸውን ሊያጓድል የሚችሉትን ነገሮች ሁሉ በማስወገድ የተቀደሰ ሕይወት መምራት ነበረባቸው።

4. 4ኛ ትእዛዝ፡- የሰንበትን ቀን ትቀድሰው ዘንድ አስብ (ዘዳግ. 14፡22-16፡17)። ይህ ክፍል በእግዚአብሔር ማንነት ምክንያት ለእርሱ በሚገባው ክብር ላይ የሚያተኩር ነው። የእግዚአብሔርን የመፍጠር ሥራ የሚያስታውስ ስለሆነ እግዚአብሔር በሰንበት ቀን ሊመለክ ይገባዋል (ዘዳግ. 20፡11)። በተጨማሪ እርሱ እስራኤልን ከግብፅ ባርነት እንዴት ነፃ እንዳወጣ ያሳስበናል (ዘዳግ. 5፡15)። እግዚአብሔር የመልካም ነገሮች ሁሉና የእስራኤላውያን ነፃነት ምንጭ ስለሆነ፥ ለእርሱና የእርሱም ቤተሰብ ለሆኑት ሁሉ እግዚአብሔር ከሰጣቸው ነገር በመስጠት ሊያከብሩት ይገባ ነበር።

5. 5ኛ ትእዛዝ፡- አባትና እናትህን አክብር (ዘዳግ. 16፡18-18፡22)። እንደምታስታውሰው፥ከ1-4 ያሉት ትእዛዛት ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ስላለው ግንኙነት የሚናገሩ ሲሆን፥ከ5-10 ያሉት ደግሞ ሰው ከሌሎች ሰዎች ጋር ስላለው ኅብረት የሚናገሩ ናቸው። እግዚአብሔር ግድ የሚለው አንድ ዓይነት የሥልጣን ተዋረድ ስለሚከተለው ከወላጆቻችን ጋር ስላለን ግንኙነት ብቻ ሳይሆን፥ በተለያየ ሥልጣን ላይ ስላሉት ሁሉ ነው። በብሉይ ኪዳን ዋና ዋና የሆኑ አራት ዓይነት መሪዎች ነበሩ። ነቢያት የእግዚአብሔርን መልእክት ለሕዝቡ የማድረስ ኃላፊነት ነበረባቸው። ካህናት የተጻፈውን የእግዚአብሔር ቃል ለሰዎች የማስተማር ኃላፊነት ነበረባቸው። ነገሥታት በእግዚአብሔር ትእዛዛት ላይ የተመሠረተ የጽድቅ መንግሥት የማዋቀር ኃላፊነት የነበረባቸው ሲሆን፥ መሳፍንት ደግሞ እግዚአብሔርና ነገሥታት

ለመሠረቱት የአኗኗር ስልት ሕዝቡ መታዘዛቸውን የማረጋገጥ ኃላፊነት ነበረባቸው። እነዚህ ሁሉ መሪዎች መሠረታዊ ዓላማና ክብር ሊሰጣቸው የሚያስፈልጉበት ምክንያት፥ ከወላጆች ጭምር ሕዝቡ በሙሉ የእግዚአብሔርን ቃል እንዲማሩና ለእግዚአብሔር እየታዘዙ በመኖር እግዚአብሔርን እንዲያከብሩ ለማደፋፈር ነበር።

6. 6ኛ-8ኛ ትእዛዛት የሚያተኩሩት በሦስት የሕይወት ክፍሎች ላይ ነው፡- ሀ) ሰውን በመግደል ለ) በማመንዘርና ሐ) በመስረቅ። እነዚህ በዘዳግ. 19-24፡7 ድረስ ተብራርተው ቀርበዋል።

ሀ) የእያንዳንዱ ግለሰብ ሕይወት በእግዚአብሔር ፊት የተቀደሰ ስለሆነ መከበርና ከአደጋ መጠበቅ ይገባዋል፤ ስለዚህ የአንድን ሰው ሕይወት በግድየለሽነት ማጥፋት ስሕተት ነው። በወንጀሉ ምክንያት መንግሥት በአንድ ሰው ላይ ሞት ቢፈርድ ወይም ጦርነት በማስነሣቱ ምክንያት ቢገደል የተከለከለ አይደለም።

ለ. ጋብቻ ሕይወትን በአንድነት የመካፈል መሠረት ስለሆነ፥ እስራኤላውያን የጋብቻን ቅድስና በጋብቻ ውስጥ በታማኝነት በመኖር መጠበቅ ይኖርባቸው ነበር። ነገር ግን ይህ አሳብ እርስ በርስ መጎዳዳትን፥ ሰላምን አንድነትን የሚያበላሹ ነገሮች ሁሉ መፈጸም የለባቸውም በሚለው አሳብ ተጠቃሎ እናየዋለን።

ሐ. ሰዎች ሁሉ በእግዚአብሔር ዘንድ ታላቅ ክብር ያላቸው ፍጥረቶች እንደመሆናቸው መጠን፥የሰውን ክብር ወይም ዋጋ የሚነካ ማንኛውም ነገር መፈጸም የለበትም። ይህም መስረቅ ማለት ሊሆን ይችላል። በተጨማሪ በባርነት መልክ ሰውን የመሰል ፍጡር ነፃነቱን መገፈፍ ተገቢ አይደለም።

7. 9ኛ ትእዛዝ፡- በባልንጀራህ ላይ በሐሰት አትመስክር (ዘዳግ. 24፡8-16)። መዋሸት ወይም በሐሰት መመስከር በእግዚአብሔርና በሰዎች መካከል ላለው ግንኙነት ሁሉ መሠረት መሆን ያለበትን ነገር ማጥፋት ወይም ማበላሸት ነው። በእውነተኛነት ላይ የሚመሠረተውን መተማመን ያጠፋል። በሰዎች መካከል ያለውን እውነተኛነትና መተማመን የሚያጠፋ ነገር ሁሉ እንዳይደረግ ተከልክሏል።

8. 10ኛ ትእዛዝ፡- አትመኝ (ዘዳግ. 24፡17-26፡15)። መመኘት ማለት የሌላውን ሰው ንብረት የራስ ለማድረግ መፈለግ ማለት ነው። መመኘት የብዙ ኃጢአቶች መንስዔ ነው። የሌላውን ሰው መብት ተገቢ ባልሆነ መንገድ ወደ መጠቀም ይመራል። የእግዚአብሔር ሕዝብ የሆኑት እስራኤላውያን ግን እንደ እግዚአብሔር ሕዝብነታቸው፥ በኅብረታቸው ውስጥ ቅን ፍርድን በመፈለግ፥ እርስ በርሳቸውም ሆነ ከሠራተኞቻቸው፥ እንዲሁም ከሌሎች ጋር መልካም ግንኙነት መፍጠር ነበረባቸው።

> 8ኛ ጥያቄ፥ እግዚአብሔርን በሚያከብር መንገድ ከሌሎች ጋር ግንኙነት ስለ ማድረግ፥ ከእነዚህ አራት የመጨረሻ ነጥቦች ምን መማር እንችላለን?

## 2ኛ ቀን፡- ዘዳግም 1-11

> 9ኛ ጥያቄ፥ ሀ) በምድራችንም ሆነ በዓለም ላይ ያሉትን አብያተ ክርስቲያናት ታሪክ ማወቅ አስፈላጊ የሚሆነው ለምንድን ነው? ለ) ባለፉት 20 ዓመታት የተፈጸመውን የቤተ ክርስቲያንህን ታሪክ በአጭሩ ጻፍ። ሐ) የተፈጸሙት መልካምና ክፉ ነገሮች ምንድን ናቸው? መ) የቤተ ክርስቲያንህን ታሪክ ማወቅ ማድረግ ስለሚገባህ ነገርና መውሰድ ስላለብህ ጥንቃቄ ለማስገንዘብ እንዴት ይረዳሃል?

ታሪክን፥በተለይም ደግሞ የአብያተ ክርስቲያኖቻችንን ታሪክ ማወቅ ለሁላችንም ቢሆን በጣም ጠቃሚ ነው። ታሪክ ከታላላቅ መምህራኖቻችን አንዱ ነው። ታሪክ በተከታታይ ድርጊቶች ላይ የተመሠረተና የተቀናጀ ነው። እነዚህ ድርጊቶችና ለድርጊቶች መፈጸም ምክንያት የሆኑ ነገሮች መልካም አስተማሪዎች ናቸው። ለምሳሌ በእኛ ታሪክ ውስጥ የተፈጸሙ መልካም ነገሮች አሉ፤ ለሌሎች ወንጌልን የመንገር መልካም መንገዶች ታይተዋል፤ እነዚህ ነገሮች ዛሬም ለሌሎች ወንጌልን ለመናገር መመሪያ ሊሆን የሚችሉ መልካም ተግባራት ናቸው፤ ነገር ግን በሁሉም አብያተ ክርስቲያናት አሳዛኝ የሆኑ ድርጊቶች ተፈጽመዋል። የሐሰት ትምህርቶች ተስፋፍተዋል፤ በመሪዎች መካከል ቤተ ክርስቲያንን የሚከፋፍሉ ልዩነቶች ወዘተ. ታይተዋል። እነዚህን ነገሮች ልንመረምርና ምክንያታቸውን ልንረዳ፥

እንዳንደግማቸውም ልንጠነቀቅ ወይም ልናሻሽላቸው ይገባል። አንድ ሰው እንደተናገረው፡- ታሪካችንን፥ በተለይም ስሕተታችንን የማናውቅ ከሆነ ስሕተቶቻችንን መደጋገማችን አይቀርም። በየቤተ ክርስቲያኖቻችን የሚፈጸሙ ነገሮችን ሁልጊዜ መመርመር አለብን። መልካም ናቸውን ወይስ ለቤተ ክርስቲያንና ለወንጌል መስፋፋት ሥራ ወሳኝ ናቸው? እስካሁን እያደረግን ባለነው ነገር ልናሻሽላቸው የሚገቡ ነገሮች ወይም የምናደርጋቸው ነገሮች በተሻለ መንገድ ለማካሄድ እያደረግነው ያለነው ጥረት ምንድን ነው? እንዳይጠፉ ወይም እንዳይበላሹ ልንጠነቀቅላቸው የሚገቡ፥ ለቤተ ክርስቲያን በጣም አስፈላጊ ነገሮች ምንድን ናቸው? በማለት እየጠየቅን ተገቢውን ነገር ከታሪክ መማር አለብን። ያለፈውን ነገር ብቻ በማውሳት የታሪክ ባሪያዎች መሆን የለብንም፤ነገር ግን ታሪካችንን ለጊዜያችን በሚስማማ መንገድ ለእግዚአብሔር ከሁሉ የላቀ ክብርን እንዲያመጣ ልንጠቀምበት ይገባል።

| |
|---|
| 10ኛ ጥያቄ፥ ሀ) ከቤተ ክርስቲያንህ ነባር አባሎች መካከል ለአንዱ ቃለ መጠይቅ አድርግ። ቁልፍ የሆኑ የቤተ ክርስቲያንህን የቀድሞ ታሪኮች ጻፍ። ለ) የቤተ ክርስቲያናችን የቀድሞ ታሪክ ማወቅ ለአሁኑ ዘመን የሚጠቅመው እንዴት ነው? ሐ) ቤተ ክርስቲያን አባሎችዋ ታሪኳን እንዲያውቁና እንዲመዘግቡ ምን ማድረግ አለባት? |

አብዛኛው የብሉይ ኪዳን ክፍል ታሪክ ነው። ሊጠናና ለአእምሮ እውቀት የሚበቃ ታሪክ ብቻ ግን አይደለም። ዳሩ ግን እስራኤላውያን የእግዚአብሔር ሕዝብ እንደመሆናቸው መጠን ራሳቸውን እንዲያሻሽሉ የሚረዳ ታሪክ ነው። እግዚአብሔር በእነርሱ ወገን ሆኖ ሊሠራ ታላቅ ኃይል ያለው መሆኑን ለእስራኤላውያን የሚያስታውስ ታሪክ ነበር። አባቶቻቸው እንዳደረጉት በኃጢአት እንዳይወድቁ፥ ስለ መንፈሳዊ ውድቀት ግንዛቤ እንዲኖራቸው የሚያደርግ ማስጠንቀቂያም ነው። የአይሁድ ባሕልና ታሪክ ከእኛ የተለየ ቢሆንም፥ እግዚአእብሔርን በሚያስከብር መንገድ እንዴት መመላለስ እንደሚቻል ከመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ መማር እንችላለን።

አይሁድ ታሪክን መረዳት እንዳለባቸው ሙሴ ተገነዘበ፤ ስለዚህ ሕጉን ለሚቀጥለው ትውልድ መድገም ከመጀመሩ በፊት፥ የእስራኤል ሕዝብ ከግብፅ ከወጡ በኋላ ስላሳለፉት ነገር አጠር ያለ ታሪክ አቀረበ።

> 11ኛ ጥያቄ፡- ዘዳግ.1-11 አንብብ። ሀ) ሙሴ ለእስራኤላውያን ያስታወሳቸውን ዋና ዋና ታሪካዊ ድርጊቶች ዘርዝር። ለ) ሙሴ ስለ እግዚአብሔር በእነዚህ ምዕራፎች ውስጥ የሚያስተምረን ነገር ምንድነው? ሐ) በዚህ ክፍል የቀረቡትን ዋና ዋና ትእዛዛትና ከሕይወታችን ጋር እንዴት እንደሚዛመድም ጥቀስ። መ) በቤተ ክርስቲያንህ ውስጥ ስብከት መስጠት የሚያስችሉህ የተለያዩ ጥቅሶችና መንፈሳዊ መመሪያዎች ያሉባቸውን ዋና ዋና ክፍሎች ዘርዝር።

ሙሴና የእስራኤል ሕዝብ በተስፋይቱ ምድር ትይዩ በሞዓብ ሜዳማ ስፍራዎች ሰፈሩ። ሙሴ የእስራኤል ሕዝብ ወደ ተስፋይቱ ምድር የሚገቡበትና ወረራ በማካሄድ የሚይዙበት ጊዜ አሁን መሆኑን አውቆ ነበር። ወደ ከነዓን ከመግባታቸው በፊት ግን ሙሴ ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸውን ቃል ኪዳን ለአዲሱ የእስራኤል ትውልድ በማስታወስ ቃል ኪዳኑን እንደገና ሊያጸና ፈለገ። አሪት ዘዳግም በዚህ ቃል ኪዳን ሁለተኛው የእስራኤል ትውልድና ከእግዚአብሔር ጋር የተሳሰሩበት ታሪክ የተመዘገበበት መጽሐፍ ነው።

## 1. የእስራኤል ታሪክ (ዘዳ.1-3)

ለቃል ኪዳኑ መግቢያ ይሆን ዘንድ ሙሴ ያለፈው 40 ዓመት ታሪካቸውን ለእስራኤል ሕዝብ ያስታውሳቸዋል። እግዚአብሔር ከግብፅ እንዴት እንዳወጣቸው በዓይናቸው ያዩና መመስከር የሚችሉ ሦስት ሰዎች ብቻ አሁን በሕይወት ይገኙ ነበር። እነርሱም ሙሴ፥ ኢያሱና ካሌብ ነበሩ። አዲሱ ትውልድ ያለፈውን ታሪካቸውን የመርሳት አደጋ ያሠጋቸው ነበር፤ ስለዚህ ሕዝቡ በእምነትና በታዛዥነት በእግዚአብሔር ፊት ይመላለሱ ዘንድ፥ ለማበረታታት ሙሴ የ40 ዓመት ታሪካቸውን የሚመለከቱበትን ቁልፍ አሳቦች ይነግራቸዋል።

በኦሪት ዘዳግም ውስጥ የሲና ተራራ ብዙ ጊዜ የኮሬብ ተራራ በመባል ይታወቃል። በዚህ ክፍል የተጠቀሱ የሚከተሉትን ነገሮች ተመልከት፡-

ሀ. የእስራኤልን ሕዝብ በመምራት ሥራ ውስጥ ያግዙት ዘንድ ሙሴ መሪዎቹን ሾመ።

| |
|---|
| 12ኛ. ጥያቄ፡- ዘዳግ.1፡16-18 አንብብ። ሀ) በዚህ ስፍራ የተሰጡት መመሪያዎች ዛሬም የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ይከተሉአቸው ዘንድ ጠቃሚነታቸው እንዴት ነው? ለ) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እነዚህን መመሪያዎች የማይጠቀሙባቸው አንዳንድ ሁኔታዎች ምንድን ናቸው? |

ለ. 12ቱ ሰላዮች የተስፋይቱን ምድር አይተው እንዲመለሱ ተልከው ነበር። እስራኤል ግን በእግዚአብሔር መታመንና ወደ ተስፋይቱ ምድር መግባት እምቢ አለች።

ሐ. የእስራኤላውያን በምድረ በዳ መንከራተት፥

መ. ሴዎንና ዐግ ያግ የተባሉት ሁለት የከነዓናውያን ነገሥታት መሸነፍና የእስራኤላውያን ምድሪቱን መከፋፈል።

2. እስራኤላውያን እግዚአብሔርን ለማምለክ መሠረት የሚሆኑ የዋና ዋና ሕግጋት መግቢያ (ዘዳግ.4-11)።

በዚህ ክፍል ውስጥ የሚገኙ ስድስት ዋና ዋና ትምህርቶችን ተመልከት፡-

ሀ. ከእግዚአብሔር የሆነ በረከትና እውነተኛ ጥበብ ለእርሱ ፍጹም በመታዘዝ ይገኛሉ።

ለ. በከነዓን ምድር የተለመደውን የጣዖት አምልኮ እንዳይለማመዱ ከባድ ማስጠንቀቂያ ተሰጣቸው። «እግዚአብሔር የሚባላ እሳት» ስለሆነ ይህ በእስራኤላውያን ላይ ፍርድን ያመጣል።

እግዚአብሔር የፍቅርና የጸጋ አምላክ ስለሆነ፥ እንደ ቀላል ቆጥረን ኃጢአት ብናደርግም አይፈርድብንም ብለን ልናስብ አይገባንም።

እግዚአብሔር ሊፈራም ሊወደድም ይገባል። እግዚአብሔር ብቻውን እውነተኛ አምላክ ስለሆነ፥ እርሱን ብቻ ያመልኩ ዘንድ እስራኤላውያን ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ ነበረባቸው።

| |
|---|
| 13ኛ ጥያቄ፡- ብዙ ጊዜ እግዚአብሔር «የሚባላ እሳት» መሆኑን የምንረሳውና ስለ ቅጣት ሳናስብ ቀርተን እርሱን የማንታዘዘው እንዴት ነው? |

ሐ. የሕግጋት ሁሉ መሠረት የሆኑት አሥርቱ ትእዛዛት እንደገና መቅረብ።

መ. ለእግዚአብሔር የመታዘዝ ትክክለኛው ምክንያት ለእርሱ ያለን ፍቅር መሆን አለበት። በሁለንተናቸው እግዚአብሔርን መውደድ ነበረባቸው። የእግዚአብሔርን ትእዛዛት እርስ በርስ መማማርና ልጆቻቸውንም ማስተማር እንዳለባቸው እርግጠኞች መሆን ነበረባቸው። ሙሴ የእግዚአብሔርን በረከት ከተቀበሉና መማማርና በቤቶች መኖር ከጀመሩ በኋላ እግዚአብሔርን እንዳይዘነጉ ሙሴ አስጠንቅቋቸዋል (ዘዳግ. 6፡ 10-12 ተመልከት)።

| |
|---|
| 14ኛ ጥያቄ፡- ከስደትና ከችግር ጊዜ ይልቅ በሰላምና በብልጽግና ዘመን እግዚአብሔርን ማስታወስስ የሚከብደው ለምንድን ነው? |

ሠ. ከእግዚአብሔር መንገድ ዞር እንዳያደርጉአቸው በከነዓን ምድር የሚኖሩትን አሕዛብ ሁሉ ማጥፋት ነበረባቸው።

ረ. እውነተኛ ታዛዥነት ሕግን በውጫዊ መንገድ መከተል ብቻ ሳይሆን የልብ መለወጥንም ያካትታል። ሥጋዊ የአካል ክፍላቸውን (ሸለፈታቸውን) ብቻ ሳይሆን፥ ልባቸውንም መግረዝ ነበረባቸው። መታዘዝ የሚጀምረው እግዚአብሔርን ከመፍራት፥ በመንገዱ ለመሄድ ከመወሰን፥ ከሁሉ በላይ ደግሞ ወደ መታዘዝ ከሚመራቸው በልባቸው ከሚኖር ፍቅር ነበር።

15ኛ ጥያቄ፣ ሀ) ዛሬ ልባችን እንዴት እንደተገረዘና በፍጹም ልባችን እርሱን እንደወደድነው ማሳየት የምንችልበትን ምሳሌዎች ስጥ። ለ) በሁለንተናችን እግዚአብሔርን እንዴት መውደድ እንችላለን?

## 3ኛ ቀን:- ዘዳግም 12-26

ብዙ ሰዎች እግዚአብሔርን የሚገደው ለእርሱ ስላለን አምልኮ ብቻ ነው ይላሉ። በአእምሮአቸው «መንፈሳዊ» የሆነውን ነገር «ሥጋዊ» ከሆነ ነገር ይለያያሉ። እግዚአብሔር ግን ይህንን ልዩነት አላደረገም። እንዲያውም የምናደርጋቸው ነገሮች በሙሉ በእግዚአብሔር ዓይን መንፈሳዊ ናቸው። በ1ኛ ቆሮ.10፡31 ጳውሎስ «እንግዲህ የምትበሉ ወይም የምትጠጡ ብትሆኑ፥ ወይም ማናቸውንም ነገር ብታደርጉ ሁሉን ለእግዚአብሔር ክብር አድርጉት» ይላል። ስለዚህ እግዚአብሔር ግድ የሚለው አምልኮአችን ብቻ ሳይሆን ከሌሎች ክርስቲያኖች ጋር ስላለን ግንኙነትም ነው። ከማያምኑ ጋር ባለንም ግንኙነት ደስ ይለዋል። እግዚአብሔር እንዴት እንደምንሠራና እንደምናስተዳድር ያያል። እግዚአብሔርን የማይመለከተውና መመሪያ ያልሰጠበት አንዳችም የሕይወት ክፍል የለም። በኦሪት ዘዳግም፥ ስለ አምልኮና ስለ ሃይማኖታዊ በዓላት የተሰጡ ሕግጋትን እናገኛለን። ስለ ንግድ፥ ጋብቻ፥ ምግብ፥ ከምድር ስለሚገኝ ፍሬ፥ ስለ ቤተሰብ ሕይወት፥ ወደ ጦርነት ስለ መሄድ፥ የእግዚአብሔርን ሕዝብ ስለ መምራት ወዘተ የሚናገሩ ሕግጋትንም እናገኛለን። እኛ ግን ብዙ ጊዜ እግዚአብሔርን የሚያከብር ወይም የማያከብር ነገር እናደርጋለን! ልዩነቱ የሚመነጨው በውስጣችን ካለው ስሜታችን ነው። አንድ ነገር በእግዚአብሔር ተቀባይነት እንዲያገኝ ከተፈለገ ድርጊት ብቻ ሳይሆን የድርጊቱ ዓላማም ጭምር በእግዚአብሔር ፊት የተስተካከለ መሆን ይኖርበታል።

16ኛ ጥያቄ፥ ሀ) ብዙ ጊዜ የምናደርጋቸውና እግዚአብሔር አያገባውም የምንላቸው የተለመዱ ነገሮችን ዘርዝር። ለ) እነዚህ ነገሮች እግዚአብሔርን በሚያስከብር መንገድ እንዴት ሊደረጉ እንደሚችሉ መግለጫ ስጥ። ሐ) ለእግዚአብሔር ክብር በማያመጣ መንገድም እንዴት ሊፈጸሙ እንደሚችሉ ምሳሌዎችን ስጥ።
17ኛ ጥያቄ፥ ዘዳግ. 12-26 አንብብ። ሀ) እግዚአብሔር መመሪያ የሚሰጥባቸውን የተለያዩ የሕይወት እንቅስቃሴዎችን ለ)ከእነዚህ ትእዛዛት አንዳንዶቹን ዛሬም እንዴት ከሕይወታችን ጋር እንደምናዛምድ ምሳሌ ስጥ።

** እነዚህን ትእዛዛት ለማብራራት ጊዜ አንወስድም። ነገር ግን ያልተረዳሃቸው አንዳንድ ቢኖሩ፥ ዝርዝራቸውን ጻፍና በሳምንታዊው የስብሰባ ወቅት ከቡድንህ አባላት ጋር ተወያይባቸው።

## 4ኛ ቀን፡- ዘዳግም 27-34

18ኛ ጥያቄ፥ ዘዳግም 30፡ 15-18 አንብብ። ሀ) በሰው ፊት የቀረቡ ሁለቱ ምርጫዎች ምንድን ናቸው? ለ) የእነዚህ ምርጫዎች ውጤት በተናጠል ምንድን ነው? ሐ) እነዚህ የምንሰብከው ወንጌል ክፍል የሆኑት እንዴት ነው?

ብዙ ጊዜ ክርስቲያኖች ኃጢአት በመሥራታቸው ምክንያት ለሚያጋጥማቸው ችግር በአንድ ነገር ላይ ወይም በሌላ ሰው ላይ ይላከካሉ። አንዳንድ ጊዜ በሰይጣን ያመካኛሉ። ሌሎቹ ደግሞ እግዚአብሔርን ይወቅሳሉ። ሰይጣንም ሆነ እግዚአብሔር በምንወስነው ውሳኔ ላይ ተጽዕኖ ማሳደር ቢችሉም፥ የመጨረሻ ውሳኔ የማድረግ ኃላፊነት መውሰድ ያለብን እኛ ነን። ሰይጣን ከፈቃዳችን ውጭ ኃጢአት እንድንሠራ ሊያስገድደን አይችልም። በሌላም በኩል እግዚአብሔር፥ አንድን መልካም ነገር እንድናደርግ ፈቃዳችንን ጥሶ አያስገድደንም። በመጨረሻ እግዚአብሔር ምርጫውን ለእኛ ትቷል። ሕይወትን ወይም ሞትን፥ በረከትን ወይም መርገምን መምረጥ እንችላለን። ሙሴ ከመሞቱ በፊት እስራኤላውያን ማድረግ ስላለባቸው ትክክለኛ ምርጫ ሊያስታውሳቸው ፈለገ። በእግዚአብሔር

የሚሸለሙት ወይም የሚቀጡት ባደረጉት ምርጫ መሠረት እንደሆነ ሊያሳያቸው ወደደ።

እንደ ወንጌል ሁሉ ቃል ኪዳንም ተስፋ የተሰጠበትን በረከትና የቅጣት ማስጠንቀቂያዎችን ይዟል። ወንጌል «የምሥራች» ነው። ከኃጢአታቸው ያድናቸው ዘንድ በእግዚአብሔር ልጅ በኢየሱስ ክርስቶስ ለሚያምኑት ሁሉ የደኅንነት ተስፋ ይዞአል። እንዲሁም ወንጌል «ከፉ ወሬ» ነው፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር የሰጠውን ደኅንነት እንቢ ላሉ ዘላለማዊ ፍርድን ያውጃልና። የወንጌል መልእክተኞች እንደመሆናችን፥ መናገር ያለብን ሰው በማመኑ ምክንያት ስለሚያገኘው በረከት (ቃል ስለ ተገባለት በረከት) ብቻ ሳይሆን፥ ለማያምኑትም ሁሉ ስለተደረገውና ስለሚጠብቃቸው ዘላለማዊ ፍርድም ጭምር ነው። ወንጌል ለሰዎች ሞት ወይም ሕይወት፥ በረከት ወይም የሞት ፍርድ እርግማን ይዞ ይቀርባል። ሰዎች ወንጌልን የበለጠ እንዲወዱት ብለን ርግማኑን ወይም የሞት ፍርድ እንደተፈረደበት መደበቅ የለብንም። ሙሴ ከመሞቱ በፊት በፊታቸው ያለውን ምርጫ ለሕዝቡ በጥንቃቄ አሳያቸው።

---

19ኛ ጥያቄ፥ ሀ) በወንጌል መልእክት ውስጥ የተጠቃለሉትን የበረከት ዓይነቶች ዘርዝር። ለ) በወንጌል መልእክት ውስጥ የተጠቃለሉትን የርግማን ዓይነቶች ወይም ፍርዶች ዘርዝር። ሐ) ላልዳኑት ሰዎች ምርጫቸውን ያስተካክሉ ዘንድ ሁለቱንም ነገሮች ማሳየት የሚጠቅመው ለምንድን ነው? መ) ዛሬ ወንጌልን ለአንድ ሰው አካፍል። በመልእክትህ ውስጥ ሁለቱንም ማለትም የወንጌልን በረከትና ርግማንንም አቅርብ።

20ኛ ጥያቄ፥ ዘዳግ። 27-34 አንብብ። ሀ) ሕዝቡ ባለመታዘዛቸው ምክንያት የሚመጡባቸውን የርግማን ዓይነቶች ዘርዝር? ለ) ሕዝቡ በመታዘዛቸው ምክንያት የሚያገኙአቸውን የበረከት ዓይነቶች ዘርዝር። ሐ) ኢያሱ አዲሱ መሪ መሆኑን እግዚአብሔር ለሕዝቡ እንዴት አሳያቸው? መ) ከአሪት ዘዳግም ለራስህ ሕይወትም ሆነ ለቤተ ክርስቲያን የሚጠቅሙና ሊዛመዱ የሚችሉ መንፈሳዊ ትምህርቶችን ዘርዝር።

---

እያንዳንዱ ትውልድ ለእግዚአብሔር መስጠትና ቃል ኪዳኑን ማደስ አለበት። ከ40 ዓመታት በፊት፥ የመጀመሪያው የእስራኤል ትውልድ በሲና ወይም በኮሬብ ተራራ ከእግዚአብሔር ጋር በመገናኘት፥ ከእርሱ ጋር ቃል ኪዳን ገብቷል። አሁን ደግሞ ሕዝቡ ወደ ከነዓን ከመግባታቸው ጥቂት ቀደም ብሎ ሙሴ አዲሱ ትውልድ ቃል ኪዳኑን እንዲያረጋግጥ ሲያደርግ እንመለከታለን። እግዚአብሔር ደግሞ በሲና ተራራ የሰጠውን ሕግ ሲደግም እንመለከታለን። ከዚያም ወደ ከነዓን ምድር በሚገቡበት ጊዜ ቃል ኪዳኑን እንዴት እንደሚያጸኑ መመሪያ ሲተውላቸው እንመለከታለን። ሙሴ ሕጉን እንዴት በጽላት ላይ መጻፍ እንዳለባቸውና እንዴት በመታሰቢያነት እንደሚያቆሙት እስራኤላውያንን አዘዛቸው። ከዚያም በጌባል ተራራ ሕጉን እንዲያነብቡና በመታዘዝ የሚገኙትን በረከቶችና ባለመታዘዝ የሚመጡትን ርግማኖች እንዲደግሙአቸው አዘዘ።

| |
|---|
| 21ኛ ጥያቄ፥ ሀ) ሙሴ ይህንን ትእዛዝ ለአይሁድ የሰጠው ለምንድነው ብለህ ታስባለህ? ለ) ቀጣዩን ትውልድ በወንጌል ውስጥ ስለሚገኙት በረከቶችና ርግማኖች እንዴት ማስተማር እንዳለብን ይህ ምን ያስተምረናል? |

አብዛኛዎቹ በረከቶች፥ በተለይም ደግሞ ርግማኖች የተሰጡት በትንቢት መልክ ነው። የእስራኤልን ሕዝብ ታሪክ በማጥናት ወደ ፊት እየገፋን ስንሄድ፥ ሙሴ ለእስራኤል ሕዝብ የነገራቸው በረከቶችና መርገሞች በኋላ እንደ ተፈጸመ እንመለከታለን። መታዘዝ ሲኖር፥ በረከትም ነበር። ዳሩ ግን እስራኤላውያን ብዙውን ጊዜ ባለ መታዘዝ ተመላልሰዋል። ስለዚህ የእስራኤል ሕዝብ ታሪክ በአሪት ዘዳግም ውስጥ የተጠቀሱትን ርግማኖች ለቃል ኪዳኑ ባለመታዘዛቸው ምክንያት በእነርሱ ላይ መፈጸማቸውን የሚናገር ታሪክ ነው ለማለት እንችላለን። የእስራኤል ሕዝብ ታሪክ የተመዘገበባቸውን መጻሕፍት ስታጠና በእስራኤል ላይ የተፈጸመውን ቅጣት በአሪት ዘዳግም አስቀድሞ ከተነገረው ጋር ማወዳደር በጣም እንደሚጠቅም አስታውስ።

**22ኛ ጥያቄ፥ አንዳንዶቹ ርግማኖች በእስራኤል ሕዝብ ታሪክ እንዴት እንደተፈጸሙ መግለጫ ስጥ።**

ኦሪት ዘዳግም የሚያበቃው በሙሴ ሞት ታሪክ ነው። እግዚአብሔር አስቀድሞ፥ ኢያሱን እንደ ተከታይ መሪ አድርጎ እንዲቀበሉ ለሙሴ ነግሮት ነበር። ከዚያም ሙሴ ወደ ናባ ተራራ ሄደ። እግዚአብሔር በዮርዳኖስ ወንዝ ዙሪያ ያለውን የተስፋይቱን ምድር አሳየው። ከዚያም ሙሴ ሞተ። ትውልዶችን ሁሉ ያየን እንደሆነ በእስራኤላውያን ዓይን እንደ ሙሴ ያለ ታላቅ መሪ አልነበረም። ሙሴ በዚህ ስፍራ እንደ «እግዚአብሔር አገልጋይ» እንደ ነቢይና «እንደ» ተአምራት አድራጊ ሆኖ ቀርቧል። እግዚአብሔር ሕግን የሰጠው በእርሱ በኩል ስለሆነ፥ አይሁድ ሙሴን ሕግ ሰጭ አድርገው ይመለከቱታል።

**23ኛ ጥያቄ፥ ከሙሴ ሕይወት ስለ ቤተ ክርስቲያን የውስጥ አመራር ምን ለመማር እንችላለን?**

በኦሪት ዘዳግም ውስጥ የሚገኙ ዋና ዋና ትምህርቶችን ተመልክተናል፤ ለምሳሌ:-

1. ሰው ከእግዚአብሔርና ከሌሎች ጋር ላለው ኅብረት መሠረቱ «ፍቅር» በሚለው ቃል ውስጥ ይገኛል። ፍቅር የሚለው ቃል በኦሪት ዘዳግም ውስጥ 22 ጊዜ ተጠቅሷል። አንድ ሰው እግዚአብሔርን በፍጹም ኃይሉ ከወደደና ባልንጀራውን ከወደደ የቃል ኪዳን ሕግ የሚጠይቀውን ነገር ሁሉ ተሟላ ማለት ነው። በኦሪት ዘዳግም የእግዚአብሔር ሰዎች ከሁሉም ነገር በላይ በፍጹም ኃይላቸው እግዚአብሔርን እንዲወዱ ተጠርተዋል።

2. በኦሪት ዘዳግም ውስጥ የሚገኘው በጣም አስፈላጊ የሆነ ሁለተኛ ዋና ርዕስ «መታዘዝ» ነው። በመጽሐፉ ውስጥ 10 ጊዜ ተጠቅሷል። መታዘዝ የፍቅር ውጤት (ፍሬ) ነው። አንድን ሰው ካልታዘዝነው እንወደዋለን ማለት አንችልም። እንዲሁም ከልብ ሳንታዘዘው እግዚአብሔርን እንወደዋለን ማለት አንችልም።

ደግሞም እርስ በርስ የምንጎዳዳበትን ነገር እያደረግን እንዋደዳለን ማለት አንችልም።

3. አሪት ዘዳግም፥ የ«ሕግጋት» መጽሐፍ ነው። ብዙ ጊዜ ሕግን የጸጋ ተቃራኒ አድርገን እንመለከታለን። አይሁድ ግን የብሉይ ኪዳን ሕግጋትን የሚያዩት የእግዚአብሔር የጸጋ ምልክት እንደሆነ አድርገው ነው፤ ምክንያቱም እነርሱ የሚኖሩት እግዚአብሔርን እንዴት እንደሚያመልኩትና እርሱን ደስ የሚያሰኙበትንም መንገድ በማያውቁ አሕዛብ መካከል ነበር፤ ስለዚህ እግዚአብሔር በጸጋው እንዴት እንደሚያመልኩና እንዴት መኖር እንዳለባቸው ለመግለጽ ለአይሁድ ሕግጋትን ሰጣቸው። ለአይሁድ ሕግ እጅግ ደስ የሚያሰኝ ነገር ነው። ከብርና ከወርቅ የሚሻል ከማርም ይልቅ የሚጣፍጥ ነው፤ [መዝ. (119)፡ 10፤ (119)፡ 72]። እግዚአብሔር ለእስራኤል የነበረውን ፍቅር ራሱን በመግለጥና ሕግን በመስጠት አሳየ። ሕጉ በእነርሱ ዘንድ እንደ ሸክም የታየበት ጊዜ ጨርሶ አልነበረም።

እግዚአብሔር ሕግን በመስጠት ረገድ የነበረው ዓላማ ሰዎች እንዲሁም ዝም ብለው ሥርዓቶችን እንዲታዘዙ ብቻ አልነበረም። ይልቁንም፥ ሰዎች ለእርሱ ያላቸውን ፍቅር የሚያረጋገጥባቸው መንገዶች ነበሩ። ሰው በእግዚአብሔር ፊት በእውነተኛ የቅድስና ሕይወት እንዲኖር የሚመሩ ነበሩ። እግዚአብሔርን ደስ በማሰኘት እርስ በርስ በፍቅርና በሰላም እንዲኖሩ የሚያሳዩ ምሳሌዎች ነበሩ።

በአዲስ ኪዳን ጳውሎስ ሕግን አልተቃወመም፤ የተቃወመው አይሁድ ደኅንነታቸውን በሕግ ለማግኘት የነበራቸውን የተሳሳተ እምነት ነበር። ጳውሎስ እንዳለው «ሕጉ ቅዱስ ነው ትእዛዚቱም ቅድስትና ጻድቅት በጎም ናት» (ሮሜ 7፡ 12)። የብሉይ ኪዳን ሕግጋት ስሕተት አልነበሩም፤ በተሳሳተ መንገድ ደኅንነት ለማግኘት የሕግጋት አጠቃቀማቸው ግን ስሕተት ነበር።

ብዙ ክርስቲያኖች ዛሬ አይሁድ የሠሩትን ስሕተት ይደግማሉ። የዳኑት ሕግን በመጠበቅ ይመስላቸዋል፤ ደግሞም እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኙት በቂ ሕግጋትን በመጠበቅ እንደሆነ ይገምታሉ። ይህ

አስተሳሰብ ስሕተት ነው። ይህ በክርስቶስ ወዳለ ነፃነት ሳይሆን፥ ወደ ባርነት የሚመራ ሐሰተኛ ወንጌል ነው። ለሕግ በመታዘዛችን ለእግዚአብሔር ፍቅር እንዳለን እንገልጻለን።

> 24ኛ ጥያቄ፥ ሀ) አንዳንድ ክርስቲያኖች የዳኑት አንዳንድ ድርጊቶችን በመፈጸም እንደሆነ ይመስላቸዋል። እስቲ ምሳሌዎችን ስጥ። ለ) ሕግጋትን ወደሚጎዳ ነገር እንዴት ልንለውጣቸው እንችላለን?

4. ሙሴ በአሪት ዘዳግም ያተኮረበት ሌላ ነገር፡- አምልኮ በአንድ በተቀደሰ ቦታ በውስጠኛ ክፍል ብቻ መደረግ እንዳለበት ነው። እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ብዙ አማልክት እንደሌሉና በአንድ በተወሰነ ስፍራ ማለትም በመገናኛው ድንኳ የራሱን ሕልውና የገለጠ አንድ አምላክ ብቻ መኖሩን ገልጦላቸዋል፤ ስለዚህ ያንን እውነተኛ አምላክ በአንድ ስፍራ ብቻ ሊያመልኩ ይገባ ነበር። እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳን የነበሩ አይሁዶች የአሕዛብን ልምምድ በመከተል በርካታ የተለያዩ አማልክትን በተለያየ ቦታ ለማምለክ ሊፈተኑ እንደሚችሉ ያውቅ ነበር። የሚያሳዝነው ግን አይሁድ ይህንን የማስጠንቀቂያ ትእዛዝ ሳይከተሉ ስለቀሩ የጣዖት አምልኮ ለአይሁድ የሁልጊዜ ችግር ሆኖ ቀርቷል።

> 25ኛ ጥያቄ፥ ዮሐ. 4፡21-24 አንብብ። ጌታ ኢየሱስ ለእውነተኛ አምልኮ መሠረቱ ምንድን ነው አለ? በአንድ በተወሰነ ስፍራ ከማምለክ ጋር ያለውስ ግንኙነት ምንድን ነው?

5. ሰው ሊታዘዝ ወይም ላይታዘዝ እግዚአብሔር ነፃ ምርጫ ሰጥቶታል። እግዚአብሔር ማንንም አስገድዶ እንዲታዘዝ ወይም እንዳይታዘዝ አያደርግም። ሰው በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠረ ስለሆነ፥ የመምረጥ ነፃነት አለው፤ ነገር ግን ምርጫው የሚያስከትለውን ውጤት መከላከል አይችልም። የምርጫውን ውጤት የሚወስነው እግዚአብሔር ራሱ ነው፤ ስለዚህ እግዚአብሔርን ለመታዘዝ ብንመርጥ ሕይወት ሊሰጠን ቃል

ገብቶልናል፤ ተገቢውንም ሽልማት ይሰጠናል። አለመታዘዝን ከመረጥን ደግሞ እግዚአብሔር ይቀጣናል። ሰዎች ወይም መንግሥታት እግዚአብሔርን ላለመታዘዝ ሲመርጡ በራሳቸው ላይ የእግዚአብሔርን ፍርድ ያመጣሉ። ይህ ከመጽሐፍ ቅዱስ መሠረታዊ መመሪያዎች አንዱ ነው።

6. እግዚአብሔር የታሪክ አምላክ ነው። ይህ እውነተኛ ታሪክ በትምህርት ቤት እንደተማርነው ዓይነት አይደለም፤ የድርጊቶች ቅደም ተከተል ብቻ አይደለም። ኦሪት ዘዳግም የሚያስተምረን እግዚአብሔር ታሪክን የሚቆጣጠርና የሚወስን መሆኑን ነው። ታሪክ፥ እግዚአብሔር ዓላማውን በዓለም ላይ ለመፈጸም እንዴት እየሠራ እንዳለ የሚናገር ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ታሪክን እንዴት እንደተቆጣጠረና ተጽዕኖ እንዳደረገበት እንመለከታለን። እግዚአብሔር በዙሪያችን ያለውን ነገር እንዴት እንደሚቆጣጠር ባይገልጽልንም እንኳ ድርጊቶችን በሙሉ እስካሁን ድረስ እየተቆጣጠረ እንደሆነ እርግጠኞች ለመሆን እንችላለ፤ ዓላማውንም ተግባራዊ በማድረግ እየፈጸመ ነው።

| |
|---|
| 26ኛ ጥያቄ፥ እነዚህን እውነቶች ልናውቃቸውና ልናስታውሳቸው የሚያስፈልገን ለምንድን ነው? |

ኦሪት ዘዳግም ከአዲስ ኪዳንና ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ያለው ዝምድና

1. ፔንታቱክ ብለን ከምንጠራቸው ከመጀመሪያዎቹ አምስቱ የሙሴ መጻሕፍት አዲስ ኪዳን ብዙ ጊዜ የሚጠቅሰው ከኦሪት ዘዳግም ነው። ጌታ ኢየሱስ በምድረ በዳ በተፈተነ ጊዜ፥ የሰይጣንን ፈተና ለማሸነፍ ከኦሪት ዘዳግም ውስጥ ጠቅሷል፤ (ማቴ. 4፡4፥7፥10 ተመልከት)። ይህን መጽሐፍ ብዙ ባንጠቀምበትም፥ በአይሁድና በቀደምት ክርስቲያኖች አምልኮ ውስጥ ትልቅ ስፍራ የነበረውና ጠቃሚ ሚና የተጫወተ መጽሐፍ ነው።

2. በኦሪት ዘዳግም ውስጥ ስለ ክርስቶስ የተነገረ ድብቅ ትንቢት ነበር፤ (ዘዳግ. 18፡15-18 ተመልከት)። ይህ ጥቅስ የሚናገረው፥

እግዚአብሔር በእስራኤል ሕዝብ ታሪክ በተለያዩ ዘመናት ውስጥ የተለያዩ ነቢያትን እንደሚያስነሣ ቢሆንም፥ እግዚአብሔር የእርሱን መልእክት ለእስራኤል ሕዝብ የሚናገር አንድ ልዩ ነቢይ እንደሚያስነሣ የተነገረም ትንቢት ነው። በአዲስ ኪዳን የነበሩ አይሁድ ይህንን ነቢይ ሲጠብቁ ነበር (ዮሐ. 1፡21፥ 25፥ 45፤ የሐዋ. 7፡37 ተመልከት)። ነገር ግን መሢሑና ነቢዩ አንድ ሰው እንደሚሆን አልተገነዘቡም ነበር። ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ መሢሑም ስለ ነቢዩም የተነገረውን ትንቢት ፈጸመው።

## የፔንታቱክ ክለሣ

> 27ኛ ጥያቄ፥ ሀ) አምስቱን የፔንታቱክ መጻሕፍት ዘርዝር። ለ) በየመጻሕፍቱ ውስጥ የሚገኙትን ዋና ዋና ገጸ ባሕርያት ዘርዝር። ሐ) በእያንዳንዱ መጽሐፍ ውስጥ የሚገኘውን ዋና ዓላማ ወይም ትምህርት ዘርዝር። መ) በእያንዳንዱ መጽሐፍ ውስጥ የሚገኘውን የእስራኤልን ሕዝብ ታሪክ በአጭሩ ጻፉ።

የመጀመሪያዎቹ አምስቱ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ፔንታቱክ በመባል በአንድ መጽሐፍ ስም ይጠራሉ። ፔንታቱክ አምስት ንዑሳን-ክፍሎች ያሉት አንድ ትልቅ መጽሐፍ ነው። የመጀመሪያው መጽሐፍ ኦሪት ዘፍጥረት የሚባለው ሲሆን፥ የሚያተኩረው በነገሮች ጅማሬ ላይ ነው። በመጀመሪያ በዓለም አጀማመር ላይ ያተኩራል። ዋናው ትኩረቱ ግን በእስራኤል ሕዝብ አጀማመር ላይ ነው፤ ስለዚህ የእስራኤል ሕዝብ አባቶች የሆኑትን የአብርሃምና የይስሐቅንና የያዕቆብን ታሪክ ይነግረናል። ቀጥሎም የእስራኤል ሕዝብ እንዴት ወደ ግብፅ ምድር እንደመጡ ለመናገር የዮሴፍን ታሪክ ይጠቀማል።

ኦሪት ዘጸአት፡- እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ከነበሩበት የግብፅ ባርነት እንዴት በተአምር ነፃ እንዳወጣቸው የሚናገር ታሪክ ነው። የኦሪት ዘጸአት ዋና ትኩረት ግን እግዚአብሔር ከእስራኤል ሕዝብ ጋር ቃል ኪዳን ወደገባበት ወደ ሲና ተራራ እንዴት እንደመራቸው ነው። ኦሪት ዘጸአት በእግዚአብሔርና በእስራኤል ሕዝብ መካከል ስለተገባው ቃል ኪዳን ይነግረናል። በተጨማሪ እግዚአብሔር ያድርበት ዘንድና

እነርሱም በዚያ ያመልኩት ዘንድ እስራኤላውያን የመገናኛውን ድንኳን እንዲሠሩ በሰጠው ትእዛዝ ላይ የተደረገ ትኩረት እንመለከታለን።

ኦሪት ዘሌዋውያን፡- እግዚአብሔር በእርሱ ፊት የተቀደሱ ሕዝብ ሆነው ይኖሩ ዘንድ ለእስራኤል የሰጣቸው ሕግጋት የተመዘገበበት መጽሐፍ ነው። ይህ መጽሐፍ የተጻፈው እስራኤላውያን በሲና ተራራ ሰፍረው እያሉ ነው። ትኩረቱም እስራኤላውያን በዙሪያቸው ካሉ አሕዛብ ተለይተው እርሱን በሚያስከብር መንገድ እንዴት መኖር እንደሚገባቸው በማሳየት ላይ ነው።

ኦሪት ዘኍልቁ፡- እግዚአብሔር የእስራኤልን ሕዝብ እስከተስፋይቱ ምድር ጫፍ ድረስ እንዴት እንደመራቸውና እነርሱ ግን ባለማመናቸው ወደ ምድሪቱ ለመግባት እንዴት እንዳልቻሉ የሚናገር መጽሐፍ ነው። በዚህም ሳቢያ ያ ትውልድ በሙሉ እስኪያልቅ ድረስ ለ 40 ዓመታት በምድረ በዳ ተንከራትተዋል። የመጽሐፉ ታሪክ በእግዚአብሔር ላይ የተደረገ ዓመፅ ታሪክ ነው፤ ነገር ግን የእስራኤል ሕዝብ በዮርዳኖስ ምሥራቃዊ አካባቢ ያለውን ስፍራ በጦርነት አሸንፈው እንደያዙም ይናገራል። እስራኤላውያን ከከነዓን ምድር ፊት ለፊት ሰፍረው ወደ ምድሪቱ ለመግባት እስከተዘጋጁ ድረስ ያለውን ታሪክ ይነግረናል። ከዚያም እግዚአብሔር ከ400 ዓመታት በፊት ለአብርሃም የገባለት ቃል ኪዳን ይፈጸም ዘንድ ወረራውና ድሉ ይከተላል።

ኦሪት ዘዳግም፡- የእስራኤል ሕዝብ ወደ ተስፋይቱ ምድር ከመግባታቸው በፊት ሙሴ የተናገራቸው የመጨረሻ ቃላት ተመዝግበው የሚገኙበት መጽሐፍ ነው። ሙሴ ለአዲሱ የእስራኤል ትውልድ እግዚአብሔር በሲና ተራራ የሰጣቸውን ቃል ኪዳን ለማስታወስ ሦስት ዋና ዋና መልእክቶችን ይሰጣል። የእስራኤል ሕዝብም ለእግዚአብሔር የገቡትን ቃል ኪዳን አደሱ። ሙሴ በተጨማሪ ለቃል ኪዳኑ አለመታዘዝ የሚያስከትለውን ውጤት በመናገር አስጠነቀቃቸው።

የኦሪት ዘዳግም መጨረሻ በእስራኤል ሕዝብ ታሪክ ውስጥ የሚቀጥለው ደረጃ ወደሆነው ማለትም የከነዓንን ምድር ወደ መውረር

ታሪክ ያመጣናል። ይህ ታሪክ የሚገኘው በመጽሐፈ ኢያሱ ውስጥ ሲሆን የሚቀጥለው ሳምንት ጥናታችን ይሆናል።

| |
|---|
| 28ኛ ጥያቄ፡- ሀ) በፔንታቱክ ውስጥ በእምነት ምሳሌነታቸው የተጠቀሱትን ዋና ዋና ሰዎች ዘርዝር። ለ) በየትኛው መጽሐፍ እንደሚገኙና ቅደም ተከተላቸውንም ተናገር። ሐ) ከእያንዳንዳቸው ሕይወት የምናገኛቸውን መንፈሳዊ ትምህርቶች ጥቀስ። |

| |
|---|
| መ) ከእነዚህ ሰዎች መካከል አንዱን ምረጥና የዚያን ሰው ሕይወት የሚገልጥና ምሳሌነቱን እንዴት ልትከተለው እንደፈለግህ የሚያሳይ አንድ ገጽ ጻፍ። |

የዚህን ሳምንት ትምህርት ከልስና ለሳምንታዊው ስብሰባ ዝግጅት ይረዳህ ዘንድ የመወያያ ጥያቄዎችን ተመልከት።

ሳምንታዊው የስብሰባ ጊዜ

1. ሳምንታዊው የአምልኮ ጊዜ

2. ጸሎት

3. የትምህርቱ ክለሳ

4. ውይይት

   1. ሀ) የኦሪት ዘዳግም ዋና ዓላማ ምንድን ነው? ለ) ክርስቲያኖች እያንዳንዱ አዲስ ትውልድ ከእግዚአብሔር ጋር ያለውን ዝምድና ተረድቶ የግሉ ማድረጉን በዋናነት ማረጋገጥ ያለባቸው ለምንድን ነው? ሐ) የቤተ ክርስቲያንህ ወጣቶች ወንጌልን በትክክል መረዳታቸውንና ወንጌል በሚጠይቀው መመዘኛ መሠረት መኖራቸውን ለማረጋገጥ ቤተ ክርስቲያንህ እያደረገች ያለችው ነገር ምንድን ነው?

   2. ሀ) በዘዳግ. 10፡12-13 ያለውን የቃል ጥናት በቃልህ ያዘው። ለ) እነዚህ ቁጥሮች እግዚአብሔር ከእስራኤል የሚፈልገውን ዋና ጉዳይ እንዴት ይገልጻሉ? ሐ) እግዚአብሔር ከእኛ ስለሚፈልጋቸው ነገሮች እነዚህ ቁጥሮች የሚሳዩን ነገር ምንድን ነው? መ) እነዚህን ትእዛዛት

መከተላችንን በተግባር ልንገልጽባቸው የምንችልባቸውን መንገዶች ዘርዝር።

3. ሀ) አሥርቱ ትእዛዛት በጣም አስፈላጊ የሆኑት ለምንድን ነው? ለ) እነዚህ ትእዛዛት እግዚአብሔር ከእስራኤል የሚፈልገውን ነገር እንዴት በግልጽ ያሳያሉ? ሐ) ከእግዚአብሔር ከእራሱና ከሌሎች ጋር በሚኖረን ኅብረት ከእኛ ስለሚጠብቀው ነገር እነዚህ ትእዛዛት ምን ያስተምሩናል? መ) ክርስቲያን ሊያደርጋቸው ከሚችላቸው ነገሮች ሁሉ አምልኮ እጅግ አስፈላጊ የሆነው ለምንድን ነው? ሠ) አንተ በግልህና ቤተ ክርስቲያንህ ደግሞ በምእመናን ኅብረት አምልኮን ማሳደግ የምትችሉባቸውን መንገዶች ዘርዝር።

4. ሀ) በኦሪት ዘዳግም ውስጥ የሚገኙ ሦስት ዋና ዋና ቃላት ዘርዝር። ለ) እነዚህ ሦስት ቃላት እስራኤል ከእግዚአብሔር ጋር ሊኖራት ስለሚገባው ግንኙነት የሚገልጹት እንዴት ነው? ሐ) እነዚህ ሦስት ቃላት እኛ ክርስቲያኖች ከእግዚአብሔር ጋር ሊኖረን ስለሚገባን ኅብረት እንዴት ይገልጣሉ? መ) ከእነዚህ ሦስት ቃላት መካከል በቤተ ክርስቲያን ትኩረት የሚሰጥባቸውና የማይሰጥባቸው የትኞቹ ናቸው? ለምን?

5. ሀ) እግዚአብሔር በሰው ሕይወት ሁለንተናዊ ገጽታ ላይ ትኩረት እንዳለው ኦሪት ዘዳግም እንዴት ያስተምረናል? ለ) አንዳንድ ክርስቲያኖች እግዚአብሔር የሚገደው ስለሚያደርጉት መንፈሳዊ ነገር እንጂ በዕለት ተዕለት ሕይወታቸው ስለሚፈጸመው ማለት እንደ ሥራቸው፥ ቤተሰባዊ ግንኙነታቸው ወዘተ. ስላሉ ነገሮች እንዳልሆነ የሚያስቡት ለምንድ ነው? ሐ) እኛም ከምንፈጽማቸው የተለመዱ ተግባራት ዕለት ዕለት ክርስቶስን ሊያስከብሩ ወይም ሊያስነቅፉ የሚችሉትን በምሳሌነት ጥቀስ። መ) አንድን ነገር በምናደርግበት ጊዜ ከድርጊቱ ይልቅ ድርጊቱን ያደረግንበት ውስጣዊ ግፊት የበለጠ አስፈላጊ የሆነው ለምንድን ነው?

6. ሀ) የብሉይ ኪዳን ሕግጋት ስለ በረከት ተስፋ ይሰጡ የነበሩት እንዴት ነው? ለ) ስለ ፍርድ ተስፋ የሰጡትስ እንዴት ነበር? ሐ) አንድ ሰው የተባረከ ወይም የተረገመ መሆኑን የሚወስነው

ምን ነበር? መ) ይህ ከወንጌል ጋር የሚመሳሰለው እንዴት ነው? ሠ) በምንመሰክርበት ጊዜ ባመዛኙ ወንጌል የሚናገረውን ርግማን ወይም ፍርድ የምንደብቀው ለምንድን ነው? ረ) ላልዳኑ ሰዎች ስለሰጣችሁት ምስክርነት ውጤት እርስ በርስ ተነጋገሩ። የወንጌልን በረከትም ሆነ ርግማን በምስክርነትህ ውስጥ እንዴት እንዳካተትክ ግለጽ።

5. ጸሎት

# ትምህርት 11

## 1ኛ ቀን፡- የታሪካዊ መጻሕፍት መግቢያ

በዚህ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት መከፈቻ ጥናታችን እስካሁን ድረስ የመጀመሪያውን ክፍል ፔንታቱክን ተመልክተናል። ፔንታቱክ፡- ዘፍጥረት፥ ዘጸአት፥ ዘሌዋውያን ዘኁልቁና ዘዳግም የሚባሉ አምስት መጻሕፍትን ይዞአል። ከታሪካቸው አንፃር፥ እነዚህ መጻሕፍት የሚናገሩት ከፍጥረት መጀመሪያ ጀምሮ እስራኤላውያን ወደ ተስፋይቱ ምድር ለመግባት እስከተዘጋጁበት ጊዜ ድረስ ያለውን ሁኔታ ነው። የፍጥረት መጀመሪያ መቼ እንደነበር ምንም የምናውቀው ነገር ባይኖርም፥ የፔንታቱክ ታሪክ ግን በ1400 ዓ.ዓ. ገደማ ያበቃል።

አይሁድ እነዚህን የብሉይ ኪዳን የመጀመሪያ አምስት መጻሕፍት ልዩና በታሪካቸው ውስጥ ለተሰጡት የእግዚአብሔር መገለጦች ሁሉ መሠረታዊ እንደሆኑ ያምናሉ። ስለዚህ ከሌሎቹ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ሁሉ አብልጠው፥ እነዚህን አምስት መጻሕፍት ያከብራሉ።

የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ሁለተኛ ዋና ክፍል «ታሪካዊ መጻሕፍት» በመባል የሚታወቁ ሲሆን፥ እነዚህም ከመጽሐፈ ኢያሱ ጀምሮ እስከ መጽሐፈ አስቴር ያሉት 12 መጻሕፍት ናቸው።

| 1ኛ ጥያቄ፡- አሥራ ሁለቱን የታሪክ መጻሕፍት በዝርዝር አቅርብ። |
|---|

እነዚህ የታሪክ መጻሕፍት ከሙሴ ሞት ጀምሮ እስከ አስቴር ድረስ ያለውን የእስራኤል ታሪክ የሚናገሩ ናቸው። ስለዚህ ከ1400 ዓ.ዓ. - 430 ዓ.ዓ. ያለውን የ1000 ዓመታት ጊዜ ያካትታሉ። እነዚህ 12 መጻሕፍት የቀሩትን የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ታሪክ በሙሉ የሚያካትቱ ናቸው። የቀሩት የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ማለትም የግጥምና የቅኔ እንዲሁም የትንቢት መጻሕፍት በእነዚህ 12 መጻሕፍት የታሪክ ዘመን ውስጥ የሚጠቃለሉ ናቸው። የተጻፉትም በእነዚህ ታሪካዊ ወቅቶች ነው።

2ኛ ጥያቄ፡- በትምህርት 2፥ 3ኛ ቀን የሚገኘውን ሠንጠረዥ ተመልከት።

አይሁድ የታሪክ መጻሕፍትን በሁለት የተለያዩ ዓበይት ክፍሎች ይከፍሉአቸዋል። ከመጽሐፈ ኢያሱ እስከ 2ኛ ነገሥት ያሉ መጻሕፍትን «የቀድሞ ነቢያት» መጻሕፍት ብለው ይጠሯቸው ነበር። ይህም የሚያመለከተው አይሁድ እነዚህን መጻሕፍት የሚያዩአቸው እንደ ታሪክ መጻሕፍት ብቻ ሳይሆን፥ የቀድሞዎቹ ነቢያት የሠሩበት ጊዜም እንደሆነ ጭምር ነው። ከመጽሐፈ ሩት ጀምሮ እስከ መጽሐፈ አስቴር ድረስ ያሉትን መጻሕፍት ደግሞ «ጽሑፎች» ብለው የሚጠሩአቸው የአንድ ትልቅ ክፍል አካል አድርገው በመቁጠር ነው።

እነዚህ አሥራ ሁለት የታሪክ መጻሕፍት በሊቃውንት መካከል ከፍተኛ የሆኑ አወዛጋቢና አከራካሪ ነገሮችን ፈጥረዋል። አንዳንድ ምሁራን እነዚህ መጻሕፍት በእስራኤል ታሪክ ውስጥ እጅግ ዘግይተው የተጻፉ ናቸው ብለው ያስባሉ። ከመጽሐፈ ኢያሱ እስከ 2ኛ ነገሥት ያሉት መጻሕፍት የተጻፉት እንዲያውም ከኦሪት ዘዳግም ጋር በአንድነት ስለሆነ፥ «የዘዳግም ታሪክ» በመባል ይታወቃሉ ይላሉ። ከመጽሐፈ ኢያሱ እስከ 2ኛ ነገሥት ያሉት መጻሕፍት ዋና ዓላማ በኦሪት ዘዳግም እስራኤላውያን ባለማመናቸው ምክንያት ፍርድ እንደሚጠብቃቸው የተነገረው ትንቢት በአይሁድ ሕዝብ ታሪክ ውስጥ ፍጻሜ ማግኘቱን ለማሳየት ነው ብለው ያምናሉ።

የታሪክ መጻሕፍት በሙሉ የተጻፉት በአንድ ጸሐፊ መሆኑን መገመት በጣም አጠራጣሪ ቢሆንም፥ በጥልቀት ስንመለከታቸው ግን የታሪክ መጻሕፍቱ የእስራኤልን ታሪክ የተመለከቱት እግዚአብሔር ለዚህ ሕዝብ በሲና ተራራ ከሰጠው ቃል ኪዳን አንጻር ለመሆኑ ግልጥ ይሆናል። የታሪክ መጻሕፍትን የጻፉት የተለያዩ ጸሐፊዎች፥ የእስራኤል ሕዝብ ታሪክ እግዚአብሔር በኦሪት ዘዳግም የሰጠውን ተስፋና ቃል ኪዳን እንዴት እንደፈጸመ የሚናገር ታሪክ መሆኑን ተገንዝበው ነበር። የእግዚአብሔር ሕዝብ ለቃል ኪዳኑ በሚታዘዙበት ጊዜ እግዚአብሔር ያከብራቸውና ይባርካቸው እንደ ነበር ያሳያሉ፤ ነገር ግን እስራኤላውያን በታሪካቸው ሁሉ ያጋጠሟቸው ችግሮች ቃል

ኪዳኑን ለመታዘዝ ፈቃደኞች ያለመሆናቸው ውጤቶች እንደነበሩም ያመለክታሉ። የታሪክ መጻሕፍት ጸሐፊዎች ሊያሳዩን የፈለጉት ነገር እስራኤላውያን በርካታ ችግሮች እንደገጠሟቸውና በመጨረሻም የጠፉትና ወደ ምርኮ የተወሰዱት ለምን እንደሆነ ነው። ይህ የሆነው እግዚአብሔር ሕዝቡን መጠበቅ አቅቶት ሳይሆን፥ የኃጢአት ውጤት መሆኑን ለመግለጽ በመፈለጋቸው ነበር።

| |
|---|
| 3ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ብዙ ጊዜ፥ የበረከት እጦት በኃጢአት ላይ የተሰጠ ፍርድ ውጤት መሆኑን መረዳት አስፈላጊ የሚሆነው ለምንድን ነው? ለ) አማኞች በእግዚአብሔር ፊት የተቀደሰ ሕይወት ለመኖር እንዲጠነቀቁ ለማድረግ ይህ እንዴት ይረዳል? |

## የታሪካዊ መጻሕፍት ጸሐፊዎች

በታሪክ መጻሕፍት ሁሉ የሚታዩ የጋራ የሆኑ ዋና ሐሳቦች ቢኖሩም እንኳ መጻሕፍቱ በተለያዩ ሰዎች ተጽፈው በኋላ የተቀናበሩ ሳይሆኑ አይቀሩም። መጽሐፈ ኢያሱ፥ መሳፍንትና ሩት የተጻፉት የእስራኤል መንግሥት በተባበረ ጊዜ ሳይሆን አይቀርም። 1ኛ ና 2ኛ ሳሙኤል የተጻፉት ደግሞ በሰሎሞን ዘመነ መንግሥት፥ ወይም የእስራኤል መንግሥት ለሁለት ከተከፈለ በኋላ ሳይሆን አይቀርም። ከ1ኛ ነገሥት እስከ መጽሐፈ ዕዝራ ድረስ ያሉ መጻሕፍት ደግሞ አይሁድ ከምርኮ ከተመለሱ በኋላ የተጻፉ ናቸው። እነዚህ መጻሕፍት በተጻፉ ጊዜ ጸሐፊዎቹ ያኔ በነበሩት ሌሎች ታሪካዊ መጻሕፍት ተጠቅመው እንደጻፉ ይታመናል። እነዚያ መጻሕፍት ግን የእግዚአብሔር ቃል ስላልሆኑ፥ አንዳቸውም እስካሁን ድረስ አልቆዩም።

## የእስራኤል ሕዝብ ታሪክ ዐበይት ክፍሎች

የእስራኤል ሕዝብ ታሪክ በሚከተሉት ዋና ዋና ጊዜያት ሊከፈል ይችላል፡-

1. የእስራኤል ሕዝብ መመሥረት (ዘፍጥረት 12 - ዘዳግም መጨረሻ)፡- ይህ የእስራኤል ሕዝብ ታሪክ የሚናገረው፥ ጅማሬያቸው እንዴት እንደሆነና የተስፋይቱን ምድር ወርረው ለመውረስ እስከተዘጋጁበት ጊዜ ድረስ ታላቅ ሕዝብ ወደ መሆን እንዳደጉ ነው። ዘመኑም ከ2100 ዓ.ዓ. እስከ 1400 ዓ.ዓ.

ያለውን ጊዜ የሚያካትት ሲሆን፥ የእነዚህን ዓመታት ታሪክ በዚህ መጽሐፍ የመጀመሪያ ስድስት ምዕራፎች ውስጥ አጥንተነዋል።

2. የተስፋይቱን ምድር መውረርና መውረስ (ኢያሱ)፡- የዚህ ዘመን ታሪክ የሚያሳየን የእስራኤል ሕዝብ የተስፋይቱን ምድር እንዴት እንደወረሩና ድል በማድረግ እንደወረሱ ነው፤ ዘመኑም ከ1400-1375 ዓ.ዓ. ነው።

3. ዘመነ መሳፍንት (ከመጽሐፈ መሳፍንት - 1ኛ ሳሙኤል 8)፡- ይህ ዘመን ለእግዚአብሔር ባለመታዘዛቸው በተደጋጋሚ በተለያዩ ጠላቶች ስለ መሸነፋቸው በሚተርክ ዘገባ የተሞላ ከመሆኑ በስተቀር፥ስለ ዘመኑ እምብዛም የምናውቀው ነገር የለም። መሳፍንት፥ እግዚአብሔር ለእስራኤል ሕዝብ ከጠላቶቻቸው ያርፉ ዘንድ የሚያስነሣቸው ጊዜያዊ መሪዎች ነበሩ። ዘመነ መሳፍንት ከ1375 - 1050 ዓ.ዓ. ማለትም ሳኦል ንጉሥ እስከሆነበት ድረስ ያለው ጊዜ ነው።

4. የተባበረው የእስራኤል መንግሥት ዘመን (1ኛ ሳሙኤል 9 - 1ኛ ነገሥት 11፤ 1ኛ ዜና - 2ኛ ዜና 9)፡- ይህ ዘመን የእስራኤል ሕዝብ እንደ ታላቅ ሕዝብ የነበሩበት ዘመን ነው። ይህ ዘመን የመጀመሪያዎቹ ሦስት የእስራኤል ነገሥታት- ሳኦል፥ ዳዊትና፥ ሰሎሞን እያንዳንዳቸው 40 ዓመታት እስራኤልን የገዙበት ዘመን ነበር። በዚህ ክፍለ ዘመን ዋናው ትኩረት የነበረው በዳዊት ላይ ነው። በሙሉ ልቡ እግዚአብሔርን በመውደድና በእስራኤል ጠላቶች ላይ ድል በማድረግ ብዙ ነገሥታትን ለማንበርከክ እግዚአብሔር የተጠቀመበት ሰው፥ እንደ ዳዊት ያለ ታላቅ ንጉሥ እስራኤላውያን አይተው አያውቁም። ይህ የተባበረው የእስራኤል መንግሥት ዘመን ከ1050 - 930 ማለትም ዓ.ዓ. ሰሎሞን ሞት በኋላ ሕዝቡ እስከተከፈለበት ድረስ የሚዘልቅ ነበር።

5. የተከፋፈለው መንግሥት ዘመን (1ኛ ነገሥት 12-2ኛ ነገሥት 25፤ 2ኛ ዜና 10-36)፡- ከሰሎሞን ሞት በኋላ የእስራኤል ሕዝብ በሁለት መንግሥታት ተከፈለ። የሰሜኑ መንግሥት እስራኤል ተብሎ የተጠራ ሲሆን፥ የቆየውም ከ930 - 722 ዓ.ዓ ማለትም

መንግሥቱ በአሦራውያን እጅ ወድቆ ሕዝቡ ወደ ምርኮ እስከተወሰዱበት ድረስ ነበር። የደቡቡ መንግሥት ደግሞ ይሁዳ ተብሎ የተጠራ ሲሆን፥ ከ930 - 586 ዓ.ዓ. ማለትም መንግሥቱ ፈርሶ በባቢሎናውያን ወደ ምርኮ እስከተወሰደበት ድረስ ቆይቷል።

6. የምርኮ ዘመን (ሕዝቅኤልና ዳንኤል)፡- መጽሐፍ ቅዱስ ስለ 70ው ዓመት የምርኮ ዘመን የሚናገረው በጣም ጥቂት ነገር ነው፤ (586-536 ዓ.ዓ.)። እንደ እውነቱ ከሆነ፥ የይሁዳ ሕዝብ በምርኮ የቆየው ለ50 ዓመታት ብቻ ነው። ሰባው ዓመት የሚያመለክተው የመጀመሪያዎቹ የይሁዳ ሕዝብ ወደ ምርኮ ከሄዱበት ከ606 - 539 ዓ.ዓ. ማለት አይሁድ ወደ ከነዓን እስከተመለሱበት ድረስ ያለውን ጊዜ፤ ወይም ቤተ መቅደሱ ከፈረሰበት ከ 586 ዓ.ዓ ጀምሮ እንደገና እስከታደሰበት እስከ 516 ዓ.ዓ ድረስ ነው።

7. የይሁዳ መንግሥት ሕዝብ ከምርኮ መመለስ (ዕዝራና አስቴር)፡- በ536 ዓ.ዓ. የፋርስ መንግሥት የእስራኤልን ሕዝብ ወደ አገራቸው እንዲመለሱ ፈቀደ። የይሁዳ ሕዝብ በዘሩባቤል፥ በዕዝራና በነህምያ መሪነት እንደገና የራሳቸውን አስተዳደር መሠረቱ እንጂ የነበራቸውን ሉዓላዊነት ግን መልሰው አላገኙትም። በፋርስ ታላቅ መንግሥት ውስጥ እንደ አንድ ጠቅላይ ግዛት ነበሩ። ይህ ዘመን ከ536-400 ዓ.ዓ. ድረስ ቆይቷል። ከ400 ዓ.ዓ. በኋላ ያለውን ታሪክ ከብሉይ ኪዳን ውስጥ አናገኘውም። የብሉይ ኪዳን ታሪክ በሙሉ የሚናገረው እስከዚህ ዘመን ድረስ ስላለው ሁኔታ ብቻ ነው። በአዲስ ኪዳን መጀመሪያ ላይ የምናገኘው መጥምቁ ዮሐንስ እስኪመጣ ድረስ የእግዚአብሔርን ቃል የተናገረ የመጨረሻው ነቢይ ሚልክያስ ነበር።

8. 400 የጸጥታ ዓመታት፡- ከ400 ዓ.ዓ. ጀምሮ ክርስቶስ እስከመጣበት እስከ 4 ዓ.ዓ. ድረስ ስለነበረው ዘመን የሚናገር የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ የለም። አንዳንዶቹ የአዋልድ መጻሕፍት በዚህ ጊዜ ስለተፈጸሙት አንዳንድ ጉዳዮች ይናገራሉ። እነዚህ

ዓመታት በመለኮታዊ መንገድ፥ በእግዚአብሔር መንፈስ በመመራት ቃሉን ያስተላለፈ አንድም ነቢይ ስለ ሌለ፥ 400 የጸጥታ ዓመታት በመባል ይታወቃሉ።

---

4ኛ ጥያቄ፥ እነዚህን የእስራኤል ታሪክ ስምንት ክፍሎች አጥና። ለፈተናህ አስፈላጊ ናቸው።

---

## መጽሐፍ ቅዱሳዊ የታሪክ አመለካከት:-

ታሪክን ስለምንረዳበት መንገድ የተለያዩ ባሕሎችና የተለያዩ አመለካከቶች አሉ። ታሪክን የምንረዳበት መንገድ ዛሬ በዘመናችንና በዙሪያችን የሚፈጸሙ ድርጊቶችን ለመረዳትና ለመተርጎም ወሳኝ ነው። ቀጥሎ ሰዎች ታሪክን የሚረዱባቸውን ሦስት ዋና ዋና መንገዶች እንመለከታለን:-

1. ጣዖት አምላኪዎች ታሪክን የሚመለከቱበት መንገድ:- በጥንት ዘመንም ሆነ ዛሬ በአብዛኛው የዓለም ክፍል (አፍሪካ፥ እስያ፥ ደቡብ አሜሪካ) ሰዎች ታሪክን የሚረዱት ሰው ሊቆጣጠረው የማይችል፥ የማያቋርጥ ክስተት ሂደት እንደሆነ አድርገው ነው። ይህ አመለካከት በዓለም ላይ ለሚፈጸሙ ድርጊቶች ምክንያቶቹ ልንታመንባቸው የማንችል ጣዖታት ናቸው የሚል ዝንባሌ አለው። አንድ ጊዜ በረከትን በሌላ ጊዜ ደግሞ ጥፋትን ያመጣሉ። ይህንን የሚያደርጉበት ግልጽ የሆነ መንገድ የለም። ይልቁንም እኛ ሰዎች እንደመሆናችን በእነርሱ ምሕረት ሥር እንገኛለን። ስለዚህ ለጉዳዩ ከመገዛትና እንደ ሙስሊሞች «አላህ ከፈቀደ» ከማለት በስተቀር ምንም ምርጫ የለንም። ልናደርግ የምንችለው ብቸኛው ነገር፥ አማልክትን ደስ የሚያሰኛቸውን መልካም ተግባራት ለመፈጸም መሞከር ነው። እኛ ለእነርሱ መልካም ከሆንን እነርሱም መልካም ሊሆኑልን ይችላሉ ብለው ተስፋ ያደርጋሉ። በዚህ አመለካከት ታሪክን መጻፍ፥ ሰዎች ስለ ስኬታማነታቸው እንዲመኩ ከማድረግ ሌላ የሚፈይደው ነገር በጣም ትንሽ ነው። ታሪክ በሥልጣን ላይ ላሉ ሰዎች መግዛት መብታቸው መሆኑን የማረጋገጥ መሣሪያ ይሆናል ወዘተ።

2. ዓለማዊው የምዕራባውያን አመለካከት፡- ዛሬ በትምህርት ቤት የምንማረው ታሪክ የተመሠረተው በሌላ ዓይነት የታሪክ አመለካከት ላይ ነው። ይህ አመለካከት፥ በተለይ በአውሮጳና በሰሜን አሜሪካ ድጋፍ ያለው ሲሆን፥ ታሪክ በምድር ላይ የሚፈጸሙ ክስተቶች ዘገባ ነው ይላል። እንደዚህ አመለካከት፥ ታሪክ የሚወሰነው በእግዚአብሔር ሳይሆን በሰው ብቻ ነው። ታሪክን የምናጠናው፥ ሰው የሠራውን ስሕተት በማየትና ባለፈው ጊዜ ከተፈጸሙ ድርጊቶች ልምድ በመውሰድ በምድር ላይ ለራሳችን የተሻለ ሕይወት ለመኖር ነው። ይህ የታሪክ አመለካከት፥ ለተአምራትም ሆነ ለእግዚአብሔር ቦታ የለውም። በምድር ላይ የሚፈጸሙ ነገሮች፥ ጥፋቶችም ሆኑ ጠርነቶች ሁሉ በእግዚአብሔር ዕቅድ መሠረት ለመፈጸማቸው አንዳችም መረጃ የለም፤ በተፈጥሮ የሚሆኑ ናቸው ይላሉ። በዚህ የታሪክ አመለካከት፥ ምን እንደተፈጸመ መመዝገብና ማስቀመጥ ከሁሉ የበለጠ አስፈላጊ ነገር ነው። ከዚያም ታሪክ አዋቂዎች ክስተቱ የተፈጸመው በምን ምክንያት እንደሆነ ይመረምራሉ።

3. መጽሐፍ ቅዱስ ታሪክን የሚመለከትበት መንገድ፡- መጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ እግዚአብሔር በሰዎች ሕይወት ውስጥ የሚሠራው ሥራ ውጤት ነው በማለት ያስተምረናል። በምድር ላይ የሚፈጸሙ ነገሮች ሁሉ በእግዚአብሔር ቁጥጥር ሥር ያሉ ናቸው። ከመጀመሪያው አመለካከት በተቃራኒ፥ እግዚአብሔር ግልጽ የሆነ ዕቅድ እንዳለውና በምድር ላይ የሚፈጸሙ ነገሮች ሁሉ የዚያ ዕቅድ አካል ናቸው በማለት ያስተምረናል። የእግዚአብሔር ዕቅድ መጀመሪያ የነበረው (የፍጥረታት መፈጠር ታሪክ) እና ወደ መጨረሻውም (ዘላለማዊ መንግሥት) እያዘገመ ያለው ነው። የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፊዎች በምድር ላይ የሚፈጸሙ ነገሮች በሙሉ በእግዚአብሔር ቁጥጥር ሥር እንደሆነ ያምኑ ነበር። ስለዚህ ታሪክን በሚጽፉበት ጊዜ፥ ያተኮሩት በክስተቶች ላይ ሳይሆን በእግዚአብሔር ላይ ነበር። የታሪክ መጻሕፍት ዓላማ እግዚአብሔር የገባውን ቃል ኪዳን ለመፈጸም በታሪክ ውስጥ እንዴት እንደሚሠራ ማሳየት ነው። ጸሐፊዎቹ ጽሑፎቻቸውን የሚያነቡ ሰዎች እግዚአብሔር የፈጸመውን ድርጊት ለምን በዚያ

መልክ እንደፈጸመውና በሕዝብ ላይ ለምን እንደፈረደ እንዲረዱላቸው ይፈልጉ ነበር። እግዚአብሔር ታሪክን ወደ አንድ ትልቅ ዓላማ በመምራት ላይ እንደሆነ ግልጽ ቢሆንም፥ የእግዚአብሔር ሕዝብ ተግባር እርሱ የሚሰጣቸውን ምላሽ የሚወስን እንደነበር አስተምረዋል። ድርቅ፥ የመሬት መንቀጥቀጥ፥ ሕዝብና መሪዎች በእግዚአብሔር ቁጥጥር ሥር መሆናቸው በግልጽ ሰፍሮአል። እግዚአብሔር ታሪክን እየመራና እየሠራ የታሪክ የመጨረሻ ማጠቃለያ ወደሆነው ወደ እግዚአብሔር መንግሥት መመሥረት እያቃረበው ነው።

| |
|---|
| 5ኛ ጥያቄ፥ ሀ) እነዚህ ሦስት የታሪክ አመለካከቶች ተግባራዊ ሆነው ያየህባቸውን ምሳሌዎች ጥቀስ። ለ) እነዚህ የታሪክ አመለካከቶች እያንዳንዳቸው ዛሬ በዓለም ላይ ባለን አመለካከት ላይ እንዴት ተጽዕኖ እንደሚያሳድሩ ግለጽ። ሐ) ክርስቲያን መጽሐፍ ቅዱሳዊውን የታሪክ አመለካከት ማየት ያለበት ለምንድን ነው? መ) በአስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ በምናልፍበት ጊዜ፥ መጽሐፍ ቅዱሳዊው የታሪክ አመለካከት የሚያበረታታን እንዴት ነው? |

## ታሪካዊ መጻሕፍትን እንዴት እንደምንተረጉማቸው

| |
|---|
| 6ኛ ጥያቄ፥ በፔንታቱክ ውስጥ ያሉትን የታሪክ መጻሕፍት በሚመለከት በ3ኛ ቀን ትምህርት ውስጥ ያለውን ትምህርት 3 ከልስ። |

ብዙ ክርስቲያኖች የመጽሐፍ ቅዱስን ታሪካዊ መጻሕፍት እንዴት እንደሚተረጉሙና በተለይም ከሕይወታቸው ጋር እንዴት እንደሚያዛምዱ ባለማወቅ ይቸገራሉ። ከእኛ ባሕል ጨርሶ ልዩ በሆነ ባሕል ውስጥ ብዙ ያልተለመዱ ስሞች፥ ቦታዎችና ክስተቶች ይኖራሉ። ስለዚህ ብዙ ጊዜ በቀላሉ ከሕይወታችን ጋር ልናዛምዳቸው የምንችላቸውን ታሪኮች የመምረጥና የቀረውን የመጽሐፍ ቅዱስ የሥነ መለኮት ትምህርት ቸል የማለት ዝንባሌ ይታይብናል።

እግዚአብሔር መጽሐፍ ቅዱስን እንዲጽፉ ሰዎችን ሲመራ፥ ከሁሉም በላይ የተጠቀመበት የተለመደው መንገድ (የሥነ ጽሑፍ

ዓይነት) ታሪክ ነው፤ ስለዚህ እግዚአብሔር ራሱን የሚገልጥበት ከሁሉ የተሻለው መንገድ ይህ ከሆነ፥ እነዚህ ታሪኮች ዛሬም ለሕይወታችን ጠቃሚ የሚሆኑበትን መንገድ መረዳት በጣም አስፈላጊ ነው። የታሪክ መጻሕፍትን በምታጠናበትና ከሕይወትህ ጋር ለማዛመድ በምትሞክርበት ጊዜ ልትከተላቸው የሚገቡ መመሪያዎች ከዚህ በታች ቀርበዋል፡-

1. የቅዱሳት መጻሕፍት (የታሪክን መጻሕፍት ጨምሮ) ዓላማ የእግዚአብሔርን ዓላማዎችና ባሕርያት ለእኛ መግለጥ ነው። በእያንዳንዱ ታሪክ ውስጥ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ ስለ እግዚአብሔር ወይም ከሰዎች ጋር ስላለው ግንኙነት አንድ ነገር እንማራለን። የቀድሞ ሰዎች እግዚአብሔርን እንዴት ደስ እንዳሰኙት በማየት እግዚአብሔርን እንዴት ደስ እንደምናሰኝ እንማራለን። ኃጢአት የቀድሞ ሰዎችን እንዴት እንዳጠፋቸውና እግዚአብሔር ኃጢአተኛን እንዴት እንደቀጣ በመመልከት ኃጢአት ስለሚያመጣው ነገር እንማራለን።

2. በታሪክ መጻሕፍት ውስጥ በተናጠል ሊታዩ የሚችሉ የተለያዩ በርካታ ታሪኮች ቢኖሩም፥ እነዚህ ታሪኮች በመጽሐፍ ቅዱስ ወይም በእያንዳንዱ መጽሐፍ ውስጥ የአንድ ትልቅ ዓላማ አካል መሆናቸውን መረዳት በጣም አስፈላጊ ነው። ለምሳሌ፡- 2ኛ ሳሙኤል የተጻፈው የዳዊትን ታሪክ ለመናገር ብቻ አይደለም። ነገር ግን ስለ ዳዊት ታሪክ በምናነብበት ጊዜ፥ ስለ እግዚአብሔር፥ ስለ ኃጢአትና እግዚአብሔር፥ ስለ ሕዝቡ ዓላማ በርካታ ታላላቅ የመጽሐፍ ቅዱስ እውነቶችን እንድንማር ነው። የታሪክ መጻሕፍትን በምታነብበት ጊዜ፥ እያንዳንዱ ታሪክ በሦስት ደረጃ የሚታዩ እውነቶችን እንደሚያስተምር አስታውስ፤ እነዚህም፡-

   ሀ. በጣም አስፈላጊው (በከፍተኛው ደረጃ)፡- በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኙ ታሪኮች እያንዳንዳቸው መጽሐፉ እግዚአብሔርንና አጠቃላይ ዕቅዱን የሚገልጥባቸው አካል ናቸው። ስለዚህ መጽሐፍ ቅዱስን በምናጠናበት ጊዜ ልንወስደው የሚገባ የመጀመሪያ እርምጃ፡- ያ የምናጠናው ታሪክ እግዚአብሔር በደኅንነት ውስጥ ባለው ዓላማ፥

የእግዚአብሔርን ባሕርይ በመግለጥ ረገድ ባለን ግንዛቤ፥ እርሱ ከሰዎች ጋር ስላለው ግንኙነት ባለን መረዳት ወዘተ. ላይ የሚጨምረው ነገር ምን እንደሆነ መመልከት ነው።

| |
|---|
| 7ኛ ጥያቄ፥ መጽሐፈ ኢያሱ 6ን ተመልከት። ይህ ታሪክ በዘመናት ሁሉ ያለውን የእግዚአብሔርን ባሕርይና ዓላማ ለመረዳት እንዴት ይጠቅማል? |

ለ. የታሪኩ መካከለኛ ደረጃ የመጽሐፍ ቅዱስን ዋና ዋና አሳቦችን ያመለክታል። ለምሳሌ፡- ይህ መካከለኛ ደረጃ በብሉይ ኪዳን የእግዚአብሔር ሕዝብ እነማን እንደነበሩና (እስራኤላውያን) የእግዚአብሔር ዓላማ ለእነርሱ ምን እንደነበረ ይናገራል። አዲስ ኪዳን ደግሞ ስለ ቤተ ክርስቲያንና እግዚአብሔር ለእርስዋ ስላለው ዓላማ ይናገራል። የአብርሃም ጥሪ፥ ቀይ ባሕርን መሻገር፥ የጰንጠቆስጤ ቀን ወዘተ.፥ ስለ እግዚአብሔርና ስለ ቤተ ክርስቲያን ከፍተኛ ግንዛቤ እንዲኖረን ደግሞም እግዚአብሔር ለእነርሱ ያለውን ዓላማና እያደረገላቸው ያለውን ነገር ለመረዳት በጣም ይረዳናል። ስለዚህ በሁለተኛ ደረጃ አንድን ታሪክ በምንተረጉምበት ጊዜ፥ መወሰን ያለብን እነዚህ ታሪኮች ለእነዚህ ዋና ዋና አሳቦች የሚያበረክቱት አስተዋጽኦ ምን እንደሆነ ነው፤ (ለምሳሌ፡- ደኅንነት፥ የሰው ልጅ ኃጢአት፥ ኃጢአት በዓለም ላይ ስላመጣው ነገርና የመታዘዝ በረከት ወዘተ. ናቸው)።

| |
|---|
| 8ኛ ጥያቄ፥ መጽሐፈ መሳፍንትን አንብብ። ይህ ታሪክ እግዚአብሔር ለእስራኤል ሕዝብ ስላለው ዓላማ ባለን ግንዛቤ ላይ የሚጨምረው ነገር ምንድን ነው? |

ሐ. ዝቅተኛው የታሪክ ደረጃ የሚያመለክተው በተለይ በእያንዳንዱ ታሪክ ውስጥ ያለውን ትምህርት ነው፤ ለምሳሌ፡- በሳምሶን ታሪክ ውስጥ የእግዚአብሔርን ሥራ በምንሠራበት ጊዜ ስለ ቅድስና አስፈላጊነት ጸሐፊው ሊያስተምረን የፈለገው ነገር ምን እንደሆነ ወዘተ.።

9ኛ ጥያቄ፥ መጽሐፈ ሩት ምዕ. 2ን አንብብ። ይህ ታሪክ ሊያስተምረን የሚሞክረው ነገር ምንድን ነው?

በታሪኩ ውስጥ በተናጠል የምናገኘውን ትምህርት (መመሪያ) መፈለግ ያለብን ታሪኩ የሚያስተምራቸውን ታላላቅ እውነቶች አስቀድመን ከተረዳን በኋላ መሆን አለበት። ታሪካዊ መጻሕፍትን በተገቢ ሁኔታ ለመተርጎም ከፍተኛውን፥ መካከለኛውንና የመጨረሻውን የታሪክ ደረጃ ትርጉም መረዳታችንን ማረጋገጥ አለብን።

ታሪካዊ መጻሕፍትና ታሪኮች በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ የተጨመሩበት የራሳቸው የሆነ ልዩ ዓላማ አላቸው። ዓላማቸው በተናጠል ታሪኮቹን እንድናውቅ ብቻ አይደለም። ይልቁንም እነዚህ ታሪኮች እያንዳንዳቸው ትላልቅ እውነቶችን እንድንረዳ ሊያደርጉን የታሰቡ ናቸው። ስለዚህ ታሪካዊ መጻሕፍትን በምናጠናበት ጊዜ በታሪኮች ውስጥ በተደጋጋሚ የሚመጡትን ዋና ዋና ሐሳቦች ወይም እውነቶች መፈለግ አለብን። ይህ ሲሆን ብቻ ነው የታሪኩን ዓላማ ለመረዳት የምንችለው።

3. እያንዳንዱ የብሉይ ኪዳን ታሪክ ለአንድ ለተለየ ዓላማ የተመረጠና ስለ እግዚአብሔርና ስለ ብሉይ ኪዳን ታሪክ ባለን መረዳት ላይ ልዩ የሆነ ሚና የሚጫወት ወይም ተጨማሪ ነገርን የሚያክል ነው። የቅዱሳት መጻሕፍት ጸሐፊዎች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሊያካትቱት የሚችሉዋቸው በርካታ ታሪኮች ቢኖሯቸውም ሆኖም እነዚህን ተጨማሪ ታሪኮችን ዘለለዋቸዋል። ለምን? ምክንያቱ ሌሎቹ ታሪኮች፥ ለአጠቃላዩ የሥነ መለኮት ትምህርት ዓላማ፥ ለመጽሐፉ የሚያበርክቱት አስተዋጽኦ ስላልነበራቸው ነው። ጸሐፊዎቹ ሁሉ እያንዳንዱን ታሪክ በከፍተኛ ጥንቃቄ መረጡ፤ ስለዚህ በእያንዳንዱ ታሪክ ውስጥ ያለው ይህ ልዩ ዓላማ ምን እንደሆነ ለመረዳት መሞከር አለብን። አንዳንዶቹ ታሪኮች ለመረዳት አስቸጋሪ ቢሆኑም እንኳ፥ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተካተቱበትን ምክንያት ከተረዳን እግዚአብሔርን የበለጠ እንረዳዋለን።

4. የታሪክ መጻሕፍት ዓላማ እንደ ሰምና ወርቅ ያሉ የተደበቁ እውነቶችን ለማስተማር አይደለም። ነገር ግን መንፈሳዊ እውነቶችን በመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ውስጥ ለመግለጥ ነው። ስለዚህ መፈለግ ያለብን የተደበቁ ምሥጢሮችን ሳይሆን፥ በታሪኩ ውስጥ የሚገኙ ግልጥ የሆኑ ጠቅላላ መንፈሳዊ የሥነ - ምግባር ሕግጋትን ወይም እምነቶችን ነው። እግዚአብሔር እነዚህን ጠቅላላ የሥነ ምግባር ሕግጋት ወይም እምነቶች በቀጥታ ከመስጠት ይልቅ በግለሰቦች ተግባራዊ ሕይወት ውስጥ መግለጥ እንደሚሻል ያውቅ ነበር። ይህ መንገድ እነዚህ መንፈሳዊ የሥነ - ምግባር ሕግጋት ወይም እምነቶች አኗኗራችንን እንዴት እንደሚለውጡት ለማወቅ የሚረዳ ነው።

5. ታሪኮችን በምንተረጉምበት ጊዜ ታሪኩ የሚያስተምረን በአዎንታዊ ወይም በአሉታዊ ምሳሌነት እንደሆነ አስቀድመን መወሰን አለብን። አንዳንዶቹ ታሪኮች በእምነት እንዴት መኖር እንደሚቻል ምሳሌዎችን ይሰጣሉ፤ ስለዚህ በሕይወታችን ልናካትተው የሚገባ አዎንታዊ ምሳሌ ነው። ሌሎች ምሳሌዎች ለምሳሌ በመጽሐፈ መሳፍንት 19 ስለ አንድ ሌዋዊና ቁባቱ የተጻፈው ነገር የሚያስተምረን በአሉታዊ ምሳሌነቱ ነው። በታሪኩ ውስጥ እግዚአብሔር የሰዎቹን ተግባር በምንም ዓይነት እየደገፈ አይደለም። ይልቁንም እግዚአብሔር የተፈጸመውን ተግባር በግልጥ ይናገራል። የተፈጸመውን ታሪክ ምሳሌነት መከተል እንዳለብንና እንደሌለብን የምንወስነው ከተግባሩ ውጤት ነው።

6. በታሪክ መጻሕፍት ውስጥ የምናገኛቸው ታሪኮች የቀረቡት በአጭሩ ነው። ስለ ተፈጸሙት ድርጊቶች የሚኖረንን ጥያቄ ሁሉ ለመመለስ የቀረቡ አይደሉም፤ ጠቃሚ ትምህርቶችን ለማቅረብ ብቻ የተጻፉ ናቸው። በታሪኩ ውስጥ በግልጥ ስላልተነገሩ ነገሮች አትጨነቅ፤ (ለምሳሌ፡- ቃየል ሚስት ያገኘው ከየት ነው?) ይልቁንም፥ አስፈላጊ የሆነው ነገር በታሪኩ ውስጥ የሚገኙትን ዋና ዋና ትምህርቶች መረዳትና ከሕይወት ጋር ማዛመድ ነው።

7. አብዛኛዎቹ የብሉይ ኪዳን ታሪኮች ለእኛ ያልተለመዱ ባሕላዊ ነገሮችን ያካተቱ ስለሆኑ ታሪኩን ለመረዳት በምናደርገው ሙከራ፥

ለእኛ ያልተለመዱ ባሕላዊ ነገሮችን መረዳታችንን ማረጋገጡ አስፈላጊ ነው (ለምሳሌ:- ሩት ቦኤዝን «ልብስህን በባሪያህ ላይ ዘርጋ» [ሩት 3:9] ስትለው ምን ማለቷ እንደ ነበር ...)። በተጨማሪ ከራሳችን ባሕል ጋር ተመሳሳይ የሆነ፥ በዕብራውያን ባሕል ግን የተለየ ትርጉም ያለውን ነገር መረዳታችንን ማረጋገጥ አለብን፤ (ለምሳሌ:- ለአይሁድ የእረኝነት ሥራ የተከበረ ነው፤ በብዙ ኢትዮጵያውያን ዘንድ ግን ያልተማሩ ሰዎች ወይም የልጆች ኃላፊነት እንደሆነ ስለሚቆጠር ይህን ያህል የተከበረ አይደለም)።

ታሪካዊ መጻሕፍትን በምታነብበትም ሆነ በምትተረጉምበት፥ ደግሞም ከመጻሕፍቱ በምታስተምርበት ጊዜ እነዚህን መመሪያዎች ተጠቀም:- እግዚአብሔር እነዚህን የታሪክ መጻሕፍት ሲሰጥ ምን ሊያስተምረን እንደሆነ በመጀመሪያ ማወቅ አስፈላጊ መሆኑን አስታውስ። ይህ ሲሆን ብቻ ትርጉማችን የእግዚአብሔር ቃል መሆኑንና ስናስተምረውም የእግዚአብሔር ሥልጣን እንዳለው እርግጠኞች መሆን እንችላለን።

| |
|---|
| 10ኛ ጥያቄ፤ ሀ) የእግዚአብሔር ቃል በተገቢው መንገድ መተርጎም የሚያስፈልገው ለምንድን ነው? ለ) አንድን ታሪክ በተሳሳተ መንገድ በመተርጎም በርካታ ስሕተቶችና ሐሰተኛ ትምህርቶች ሊጀምሩ የሚችሉት እንዴት ነው? |

## 2ኛ ቀን:- የመጽሐፈ ኢያሱ መግቢያ

| |
|---|
| 11ኛ ጥያቄ፥ መዝ. (91):1-16 አንብብ። ሀ) በጠላቶቻችን ላይ ስለምንቀዳጀው ድል በዚህ ስፍራ የተሰጡ ተስፋዎች ምንድን ናቸው? ለ) እግዚአብሔር በእነርሱ ላይ ድል የሰጠህን አንዳንድ ጠላቶች ጥቀስ። ሐ) እግዚአብሔር፥ ቤተ ክርስቲያንህ በእነርሱ ላይ ድል እንድትጎናጸፍ ያደረጋትን አንዳንድ ችግሮችንና ጠላቶችን ጥቀስ። |

መጽሐፈ ኢያሱ በእግዚአብሔር ሕዝብ ጠላቶች ላይ ስለተገኘ ድል የሚናገር መጽሐፍ ነው። ዛሬም እኛ ድልን እንዴት እንደምናገኝ የሚያስተምረን መጽሐፍ ነው። ድልን የምናገኘው ለእግዚአብሔር

በመታዘዝ፥ በተቀደሰ ሕይወትና በእግዚአብሔር ላይ ባለን እምነት ስንመላለስ ብቻ ነው። ይህ መጽሐፍ ዛሬም ለእኛ የሚሆን በጣም አስፈላጊ መልእክት አለው። እግዚአብሔር እያንዳንዳችን ኃጢአትን፥ ሰይጣንን ወዘተ. ድል በማድረግ እንድንኖር ይፈልጋል። ቤተ ክርስቲያን እንደ መሆናችንም እግዚአብሔር በድል እንድንኖር ይፈልጋል። መጽሐፈ ኢያሱ በግልም ሆነ በቤተ ክርስቲያን ደረጃ በድል እንዴት እንደምንመላለስና የእግዚአብሔርን ጠላቶች ሁሉ እንደምናሸንፍ ሊያስተምረን ይችላል።

| |
|---|
| 12ኛ ጥያቄ፥ ስለ መጽሐፈ ኢያሱና ስለ ኢያሱ ሕይወት ከመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት አንብብ። ሀ) ስለ ኢያሱ ማንነት የተጠቀሱትን ነገሮች በሙሉ ዘርዝር። ለ) የመጽሐፈ ኢያሱ ጸሐፊ ማን ነው? |

### የመጽሐፈ ኢያሱ ጸሐፊና የተጻፈበት ጊዜ

መጽሐፈ ኢያሱን የጻፈው ማን ነው? የሚለው ጥያቄ የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁራንን አከራክሮአል። መጽሐፉን የጻፈው ማን ነው? የሚለውን ጥያቄ በሚመለከት ሦስት የተለያዩ አሳቦች አሉ:-

1. አንዳንዶች ፥መጽሐፈ ኢያሱ የተጻፈው በታሪኩ ውስጥ የሚገኙ ድርጊቶች ከተፈጸሙ ከ800 ዓመታት በኋላ ነው፤ የተጻፈውም ኦሪት ዘዳግምንና እስከ 2ኛ ነገሥት ያሉትን ሌሎች የታሪክ መጻሕፍትን በጻፈው ሰው ነው ይላሉ። ሆኖም በመጽሐፈ ኢያሱ ውስጥ የተሰጡትን ታሪካዊ ዘገባዎች ከተመለከትን መጽሐፈ ኢያሱ የተጻፈው ከዳዊት በፊት እንደሆነ ግልጥ ነው። ለምሳሌ:- ኢየሩሳሌም አልተወረረችም ነበር።

2. አንዳንዶች መጽሐፉን የጻፈው ኢያሱ ነው ይላሉ፤ ይህም ስለ ሞቱ ከሚናገረው ክፍል በቀር መጽሐፉን በሙሉ የጻፈው ኢያሱ ነው የሚለው የአይሁድ አመለካከት ነው። ከመጽሐፈ ኢያሱ 18፡8 ና 24፡25-26 እንደምንመለከተው፥ ኢያሱ አንዳንድ ነገሮችን ጽፎአል። ስለ ጦርነቶቹና ስለ ተካሄደባቸው ስፍራዎች ከሚሰጠው ገለጻ አንፃር፥ ጸሐፊው ድርጊቱ ሲፈጸም በዓይኑ ያየ ሰው ይመስላል። ይሁን እንጂ ጸሐፊው ኢያሱ እንደሆነ መጽሐፍ

ቅዱስ በግልጽ አይናገርም። መጽሐፉን የጻፈው ኢያሱ እንደሆነ የሚናገር ሌላ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል የለም።

3. ከኢያሱ ዘመን በኋላ፥ ምናልባትም በሳሙኤል ጊዜ መጽሐፈ ኢያሱ ተጽፎ፥ ወይም ተቀናብሮ ይሆናል። በመጽሐፈ ኢያሱ ውስጥ የመጽሐፉ የመጨረሻ ቅንብር የተከናወነው ኢያሱ ከሞተ ከብዙ ጊዜ በኋላ መሆኑን የሚጠቁም፥ «እስከዚህ ቀን ድረስም» የሚል ቃል ከ12 ጊዜ በላይ ተጠቅሶአል።

ስለዚህ የመጽሐፈ ኢያሱ ጸሐፊ አይታወቅም፥ ነገር ግን የመጻፉ ሥራ የተጠናቀቀው በዳዊት ጊዜ በ1000 ዓ.ዓ. ነው ማለቱ ይሻላል።

ከነዓንን የመውረር ታሪካዊ ሥረ - መሠረት

1. ከነዓንን ለመቆጣጠር የተደረገ ጦርነት

ከፔንታቱክ መጽሐፍ ጥናታችን እንዳየነው፥ የከነዓን ምድር ተፎካካሪ የሆኑ መንግሥታት ጦር ሜዳ ነበረች። ከ2000 - 1780 ዓ.ዓ. በአብርሃም ጊዜ ከነዓን በግብፅ ግዛት ሥር ነበረች። የግብፅ ኃይል በደከመና በቀነሰ ጊዜ በሐይክሶሳውያን ተወግታ ድል ሆነችና ከ1780-1550 ዓ.ዓ. በቁጥጥራቸው ሥር ሆነች። ግብፃውያን ሐይክሶሳውያንን አስወጥተው እንደገና ገናና መንግሥት ሆኑና አይሁድን በባርነት ገዟቸው። በ1440 ዓ.ዓ. አካባቢ የግብፃውያን ኃይል ቀነሰና እግዚአብሔር አይሁዳውያንን ከግብፅ ኃይል ነፃ አደረጋቸው። በዚህ ጊዜ ግብፃውያን በከነዓን ላይ የነበራቸውን የበላይነት አጡ።

በ1460 ዓ.ዓ. ከጳለስጢና በስተሰሜን እጅግ ራቅ ብሎ (በአሁኑ ዘመን ቱርክ በሚባለው ስፍራ) ሌላ ሕዝብ ተነሣ። ይህ ሕዝብ ኬጢያዊ ይባል ነበር። ይህ ሕዝብ ግብፅን አሸነፈና በሰሜን ከነዓን ላይ ጊዜያዊ የሆነ የበላይነት አገኘ። በዚሁ ጊዜ የአሦር መንግሥት ተነሣ ይህችን የተስፋ ምድር ለመውረስ የሚዋጉ ሦስት ትላልቅ መንግሥታት ስለነበሩ፥ በከነዓን ውስጥ የሚደረጉ በርካታ ጦርነቶች ቢኖሩም፥ ከነዓንን የተቆጣጠረ አንድም መንግሥት አልነበረም። ይህ ጦርነት

ኬጢያውያን ከተደመሰሱ በኋላ ግብፅ በከነዓን ላይ እንደገና የበላይነትን እስከተቀዳጀችበት እስከ 1280 ዓ.ዓ. ድረስ ቀጠለ።

ይህም ማለት እግዚአብሔር እስራኤልን ነፃ ለማውጣትና ለአብርሃም በገባው ቃል መሠረት፥ የከነዓንን ምድር ለመስጠት በተዘጋጀበት ጊዜ፥ ግብፅ በኃይሏ እንድትዳከም ሁኔታዎችን አመቻችቶ ነበር። በኋላም በ1300 ዓ.ዓ. በመሳፍንት ዘመን በመጽሐፉ ውስጥ ባይጠቀስም እንኳ ግብፅ እንደገና ኃያል አገር በመሆን ከነዓንን ተቆጣጥራ ነበር።

የዓለምን ታሪክ በምናጠናበትና ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር በምናወዳድርበት ጊዜ እግዚአብሔር በታሪክ ሁሉ አይሁዳውያን ከምርኮ ነፃ የሚወጡበትን መንገድ ለማዘጋጀትና ከነዓንን እንዲወርሱ ለማድረግ እንደሠራ በመገንዘብ እንደነቃለን። አይሁዳውያን ከባርነት ነፃ ለመውጣት የቻሉት ግብፃውያን በዚያን ጊዜ ደከመው ስለነበር ነው። ሦስት መንግሥታት ከነዓንን ለመውረስ በመታገል ላይ ስለነበሩ አንድ ታላቅና የታወቀ ኃይል የከነዓንን ምድር ለመቆጣጠር አልቻለም፤ ስለዚህ እስራኤላውያን እንደ ግብፅ፥ ኬጢያውያንና አሶራውያን ያሉ ታላላቅ መንግሥታት ጣልቃ ሳይገቡ ወረራ በማካሄድና ድል በማድረግ የከነዓንን ምድር ለመውረስ በቅተዋል።

| |
|---|
| 13ኛ ጥያቄ፥ ሀ) እግዚአብሔር በሕዝብ ሁሉ ላይ ተቆጣጣሪ እንደሆነና ይህንም በማድረጉ ለሕዝቡ ያለውን ዓላማ ለመፈጸም እንደሚሠራ ይህ ክፍል ምን ያስተምረናል? ለ) ይህንን መረዳት ዛሬ ለእኛ የሚሰጠው መጽናናት ምንድን ነው? |

2. የከነዓናውያን የፖለቲካ መዋቅር

ከነዓን በአንድ ንጉሥ ሥር ተጠቃልላ የምትተዳደር ምድር አልነበረችም። ይህም ራሱ ምድሪቱን ለመውረር ቀላል አድርጎታል። ከነዓን የምትተዳደረው «የከተማ ግዛቶች» በመባል ይታወቁ በነበሩ ትናንሽ መንግሥታት ነበር። ይህም ማለት በአካባቢው ያለው መሬት በአንዲት ሰፊና ትልቅ ከተማ ሥር ሆኖ በንጉሥ ይገዛ ነበር ማለት ነው። በመሆኑም የንጉሡ ሥልጣን በአካባቢያቸው ላለው ምድር ብቻ

ነበር። እነዚህ ከተሞች በጠላቶቻቸውና በወራሪ ዘላኖች እንዳይደፈሩ በትላልቅ ቅጥሮች የተከበቡ ነበሩ። እነዚህ የከተማ ግዛቶች ብዙ ጊዜ በውጭ ኃይል ቁጥጥር ሥር የሆኑና ለእነዚህ ኃይላት የሚገብሩ ነበሩ። እነዚህ ትናንሽ የከተማ ግዛቶች ጠላቶች ሊያጠቋቸው በሚመጡበት ጊዜ፥ በቃል ኪዳን ይተባበሩና የጠላቶቻቸውን ጥቃት ለመመከት ይታገሉ ነበር። ይህ ሁሉ በመጽሐፈ ኢያሱ ውስጥ ተንጸባርቆአል። የከነዓን ምድር አቀማመጥ አገሪቱ አንድ ሆና በአንድ ንጉሥ እንድትተዳደር የማያስችላት ስለነበረና ብዙ ጊዜ እንደ ግብፅ ባሉ ውጫዊ ኃይሎች ቁጥጥር ሥር ስለነበረች ለተፈጸመው ታሪካዊ ሁኔታ በዚህ መልክ ተደራጅታ ነበር።

በዚህ ሳይቀር የእግዚአብሔርን እጅ እናያለን። አንድ የሆነና የተባበረ መንግሥት ስላልነበረ ለኢያሱና ለእግዚአብሔር ሕዝብ ትናንሽ ከተሞችን ወይም የትናንሽ ከተሞችን ኅብረት ለማጥቃት ቀላል ነበር። በመጽሐፈ ኢያሱ ጥናታችን፥ ኢያሱ ምድሪቱን በአጠቃላይ ለመውረስ ሦስት ዋና ዋና የከተማ ግዛት ፌዴራላዊ ኅብረቶችን ብቻ ማሸነፍ እንደነበረበት እናያለን።

### 3. ከነዓን ለዓለም የነበራት አስፈላጊነት

የከነዓን ምድር ብዙ ሕዝብ ያልነበረባት ብትሆንም ለቀረው ዓለም በጣም ተፈላጊ ነበረች። አስፈላጊነቷ በነበራት ሀብት አልነበረም። አስፈላጊነቷ የሦስት ክፍለ ዓለማት፡- የአውሮፓ፥ የአፍሪካና የእስያ መገናኛ ስለነበረች ነው። ስለዚህ የበርካታ ንግዶች መተላለፊያ ነበረች። የዚህ ዓይነት የንግድ መተላለፊያ ስለነበረችና ጠቃሚ የወደብ አገልግሎት ስለ ነበራት ለመካከለኛው ምሥራቅ ኢኮኖሚ ካላት ጠቀሜታ አንፃር፥ ትላልቅ መንግሥታት እርሷን ለመቆጣጠር ይዋጉ ነበር።

### 4. የከነዓናውያን ሃይማኖት

| |
|---|
| 14ኛ ጥያቄ፥ ዘፍ. 15፡16 አንብብ። በዚህ ስፍራ እግዚአብሔር የአሞራውያን ኃጢአት ምንድን ነው ይላል? (አሞራውያን የሚለው ስም የከነዓናውያን ሌላ ስም ነው)። |

በቅርብ ዓመታት የከርሰ ምድር ተመራማሪዎች ስለ ከነዓናውያን ጥንታዊ ማምለኪያ ስፍራዎች በርካታ ነገሮችን አግኝተዋል። የከነዓናውያን ሃይማኖት እጅግ የተበላሸ በመሆኑ ተወዳዳሪ ያልተገኘለት እንደነበር አረጋግጠዋል። ሃይማኖታቸው በርካታ አማልክት ያሉት ብቻ ሳይሆን በብዙ የፍትወተ ሥጋ ኃጢአት ላይ የተመሠረተ፥ ወንዶችና ሴቶች በማምለኪያ ስፍራዎች በግልሙትና የተጠመዱበት፥ ፍትወተ ሥጋ ከእንስሳት ጋር ሁሉ የሚፈጸምበት ሃይማኖት ነበር። ልጆቻቸውንም ለጣዖቶቻቸው ይሠዉ ነበር።

ከነዓናውያን ከ70 የሚበልጡ የተለያዩ ተባዕትና እንስት አማልክት እንደነበሩ ያምኑ ነበር። እነዚህ ሁሉ የሁለት ዋና ዋና አማልክት - ኤልና አሼራህ የሚባሉ ልጆች እንደሆኑ ያምኑ ነበር። ኤል ዋና አለቃ የሆነው አምላክ ሲሆን፥ ስሙ አይሁድ የእግዚአብሔር ስም አድርገው ይጠቀሙበት ለነበረው ኤሎሂም መሠረት ነው። ይህን አምላክ ብዙ ጊዜ ከኮርማ ወይም በሬ ምስል ጋር ያያይዙት ነበር። የሚስቱ ስም አሼራ ነበር፤ (2ኛ ነገሥት 21፡7 አዲሱን የአማርኛ ትርጉም ተመልከት)። ከልጆቻቸው ዋና ከነበሩት መካከል አንዱ በአል ሲሆን የስሙ ትርጉምም ጌታ ማለት ነው። እርሱ የሌሎቹ አማልክት ሁሉ ጌታ ሲሆን ሰማይና ምድርን፥ ዝናብን፥ ወዘተ ይቆጣጠር ነበር። ሁለት ሚስቶች አግብቶ ነበር። አንደኛዋ የጦርነት አምላክ የነበረችው «እናቱ» አናት ነበረች። ሁለተኛዋ ሚስቱ ደግሞ «አሽቶሬዝ» ተብላ የምትጠራው የምሽት ኮከብ አምላክ የነበረችዋ ናት። «ሞት» የተባለው የሞት አምላክ ሲሆን፥ የበአል ጠላት ነበር። «ዮምም» የባሕር አምላክ የነበረና ከበአል ጋር ተጣልቶ የተሸነፈ ነው። «ሞሌክ» የአሞን አምላክ ሲሆን ብዙ ጊዜ ሰውን ከመሠዋት ጋር ይያያዝ ነበር። እነዚህ ከነዓናውያን ያመልኩአቸው ከነበሩ አማልክት ጥቂቶቹ ናቸው።

እግዚአብሔር አንድ ቀን የአሞራውያን ወይም የከነዓናውያን የኃጢአት ጽዋ ሲሞላ የሚፈርድበት ጊዜ እንደሚመጣ ለአብርሃም ተናግሮ ነበር። ያ የፍርድ ጊዜ እስራኤላውያን ወደ ከነዓን ለመግባት ወረራ ባካሄዱ ጊዜ ተፈጸመ።

አንዳንድ ሰዎች እግዚአብሔር ከነዓናውያንን ሙሉ በሙሉ እንዲያጠፉ እስራኤላውያንን አዝዞአቸው ነበር የሚለውን ትእዛዝ

ለመቀበል ይችገራሉ (ዘዳ. 7፡16፤ 20፡17-18 ተመልከት)። ይህ ቅን ፍርድ አይደለም ብለው ያስባሉ። ነገር ግን አራት ነገሮችን በቀጥታ ማስታወስ ይገባናል፡-

1) እግዚአብሔር በፈለገው መንገድ በኃጢአትና በኃጢአተኞች ላይ የመፍረድ መብት አለው። በበሽታ ወይም በሞት ሊቀጣ ይችላል። ደግሞም ሌሎች ሰዎችን በመቅጫ መሣሪያነት ሊጠቀም ይችላል። እግዚአብሔር በምሕረቱ ለከነዓናውያን ከኃጢአታቸው ንስሐ ገብተው እንዲመለሱ 400 ዓመታት ሰጥቶአቸው ነበር። ይህንን ዕድል ለመጠቀም ስላልፈቀዱ እግዚአብሔር እስራኤላውያንን የፍርድ መሣሪያው አድርጎ ተጠቀመባቸውና የከነዓናውያንን ወንዶች፥ ሴቶችና ልጆቻቸውን ሁሉ እንዲያጠፉ አዘዛቸው።

2) ከነዓናውያን ይህንን ፍርድ በራሳቸው ላይ ያመጡት፥ በእግዚአብሔርና እርሱ በልባቸው ባኖረላቸው ሕግጋት ላይ በግልጽ ስላመፁ ነው። ልባቸውን በእግዚአብሔር ላይ አደነደኑ (ኢያ. 11፡18-20)።

3) እግዚአብሔር፥ ከነዓናውያንን በሙሉ እንዲያጠፏቸው እስራኤላውያንን ያዘዘው አይሁድን ወደ ጣዖት አምልኮ እንዳይመልሱ ነበር፤ (ዘዳግ. 20፡16-17)። ይህንን ባለማድረጋቸው፥ ወዲያውኑ ከነዓናውያን እስራኤላውያንን ሲያስኮበልሉና የብልሹ ምግባሮቻቸው ሰለባዎች ሲያደርጉአቸው እንመለከታለን። እንዲያውም በመጨረሻ እስራኤላውያን ከእነርሱ ብሰው በመገኘታቸው እግዚአብሔር እንደፈረደባቸው እንመለከታለን፤ (2ኛ ነገሥት 21፡9)።

4) የከነዓን ምድር የእግዚአብሔር እንጂ የከነዓናውያን አይደለም። ስለዚህ እግዚአብሔር ለፈለገው ሰው ሊሰጠው መብቱ ነው።

> 15ኛ ጥያቄ፥ 2ኛ ነገሥት 17፡7-23፤ 21፡9ን አንብብ። ሀ) እስራኤላውያን የሠሩትን ኃጢአትና የተፈረደባቸውን ፍርድ ዘርዝር። ለ) እግዚአብሔር ኃጢአትን ስለ መጥላቱ ይህ ነገር ምን ያስተምረናል?

ሐ) ኃጢአትን እንዴት መጥላት እንዳለብንና በአብያተ ክርስቲያናት ውስጥ እንዳይስፋፉ እንዴት መጠበቅ እንዳለብን ከዚህ ምን እንማራለን? መ) ኃጢአት እንዳይስፋፋ ቤተ ክርስቲያንህ ልታደርግ ትችላለች ብለህ የምታስባቸውን ነገሮች ዘርዝር።

ምሁራን የመጽሐፈ ኢያሱ ታሪክ እጅግ አከራክሮአቸዋል። በተለይ ደግሞ የታሪኩን በትክክል መመዝገብ የሚጠራጠሩ አሉ። የሚከራከሩባቸውም ዋና ዋና ሐሳቦች ሦስት ናቸው:-

1. የእስራኤል ሕዝብ ከነዓንን መቼ እንደወረሩ:- መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ እንደሚያሳየው የእስራኤል ሕዝብ ወደ ከነዓን የገቡት በ1400 ዓ.ዓ. ነበር። ሐሳባቸውን በከርሰ ምድር (አርኪዮሎጂ) ጥናት ላይ የመሠረቱ አዋቂዎች እስራኤላውያን ወደ ከነዓን ምድር የገቡት ብዙ ቆይተው ወደ 1250 ዓ.ዓ. ገደማ ነው ይላሉ።

2. የእስራኤል ሕዝብ ከነዓንን ወርረው ምድሪቱን በአጠቃላይ የያዙት ምንኛ ፈጥነው ነው:- ሌሎች ምሁራን ከነዓንን የመውረርና የመያዝ ነገር ቀስ በቀስ በብዙ ክፍለ-ዘመናት የተፈጸመ ስለሆነ እስራኤላውያንም ምድሪቱን የወረሱት ቀስ በቀስ ነው ይላሉ። ጥቂት ምሁራን ደግሞ እስራኤላውያን 600000 ተዋጊ ሰዎች ቢኖሯቸው ኖሮ ማንም ሊቋቋማቸው እስከማይችል ድረስ በአጭር ጊዜ ምድሪቱን ሊወርሱ ይችሉ ነበር ይላሉ። ሌሎቹ ደግሞ እስራኤላውያን ምድሪቱን ለመውረስ ችግር ገጥሟቸው ነበርና፥ ይህን ያህል ተዋጊ ኃይል አልነበራቸውም፤ በማለት ከነዓንን ለመያዝ በቁጥርና በኃይል እስኪያድጉ ድረስ ብዙ ዓመታት ፈጅቶባቸዋል ይላሉ።

ከነዓንን በጦርነት የመውረርና የመያዝ ተግባር ልክ በመጽሐፈ ኢያሱ እንደተጻፈው በአጭር ጊዜ በ1400 ዓ.ዓ. የተፈጸመ ነው የሚለውን አቋም መያዝ ከሁሉም የተሻለ ነው።

3. በጣም የተለያዩና እርስ በርስ የሚጋጩ ሆነው የሚታዩ ቢመስሉም፥ መጽሐፈ ኢያሱና መሳፍንት እርስ በርስ የተያያዙት እንዴት ነው? አንዳንድ ምሁራን መጽሐፈ ኢያሱና መሳፍንት

እርስ በርስ የሚቃረኑ ናቸው ይላሉ። መጽሐፈ ኢያሱ የሚያስተምረው:- እስራኤላውያን ከነዓንን እንደወረሩና እንደተቆጣጠሩ ነው፤ መጽሐፈ መሳፍንት ግን ምድሪቱን ለመቆጣጠር እንዳልቻሉ ያሳያል ይላሉ።

ነገር ግን እነዚህን መጻሕፍት በጥልቀት ስናጠና በመካከላቸው ምንም ቅራኔ እንደሌለ እንገነዘባለን። መጽሐፈ ኢያሱ አብዛኛውን የከነዓን ምድር እንደተወረረና እንደተያዘ ቢናገርም (ኢያ. 11:23፤ 21:43-45)፥ አንዳንድ የምድሪቱ ክፍሎች አለመያዛቸውንም አይሸሽግም፤ (ኢያ. 13:1-6፤ 23:4-5፥ 13)። ሁለቱ መጻሕፍት ሁለት የተለያዩ ዓላማዎች አሏቸው። መጽሐፈ ኢያሱ የሚናገረው:- እግዚአብሔር የተስፋ ቃሉን እንዴት እንደፈጸመና ለእስራኤላውያን በጠላቶቻቸው ላይ እንዴት ድል እንደሰጣቸው ነው። በኢያሱ ዘመን መጨረሻ ምድሪቱ በሙሉ በእስራኤል ቁጥጥር ሥር ሆና ነበር፤ ዋና ዋና የተባሉ ጠላቶችም ተሸንፈው ነበር። ነገር ግን በምድሪቱ የነበሩት ጠላቶቻቸውን ሁሉ ለማስወጣት ሳያቋርጡ መታገልና መዋጋት የእስራኤላውያን ኃላፊነት ነበር። መጽሐፈ መሳፍንት የሚያሳየው ግን እግዚአብሔር እስራኤላውያን በጠላቶቻቸው ሁሉ ላይ ድል የሰጣቸው ቢሆንም፥ መዋጋታቸውን አቁመው ምድሪቱ ላይ ሰፍረው ቁጭ እንዳሉ ነው። ምድሪቱን ሁሉ ለመያዝ ሙከራ ባለማድረጋቸው፥ እግዚአብሔር የድል ክንዱን ከእነርሱ ላይ አነሣ። ስለዚህ በጠላቶቻቸው ላይ ድልን ለማግኘት አልቻሉም። አይሁድ በቀረው ታሪካቸው በሙሉ ባገኙት ድል ለመቀጠል ባለመዋጋታቸውና እግዚአብሔር በመራቸው መሠረት ጠላቶቻቸውን በሙሉ ባለማጥፋታቸው ችግር ውስጥ ገብተው እናያቸዋለን።

> 16ኛ ጥያቄ፥ የእግዚአብሔርን ትእዛዛት በከፊል ስለ መታዘዝ ከዚህ የምናገኘው ማስጠንቀቂያ ምንድን ነው?

## የመጽሐፈ ኢያሱ አስተዋጽኦ

የሚከተለውን የመጽሐፈ ኢያሱን አስተዋጽኦ አጥና:-

1. የእስራኤላውያን ወደ ከነዓን መግባት (ኢያሱ 1-4)

2. እስራኤላውያን ጠላቶቻቸውን እንደ አሸነፉ (ኢያሱ 5-12)
ሀ. ጠላቶቻቸውን ለማሸነፍ ያደረጉት ዝግጅት (ኢያሱ 5)

ለ. በከነዓን መካከለኛ ክፍል ባሉ ጠላቶች ላይ የተደረገ ዘመቻ (ኢያሱ 6-8)

ሐ. በደቡብ ከነዓን በሚገኙ ጠላቶች ላይ የተደረገ ዘመቻ (ኢያሱ 9-10)

መ. በሰሜን ከነዓን በሚገኙ ጠላቶች ላይ የተደረገ ዘመቻ (ኢያሱ 11)

ሠ. በእስራኤላውያን የተሸነፉ ጠላቶች ዝርዝር ማጠቃለያ (ኢያሱ 12)

3. የምድሪቱ ለልዩ ልዩ የእስራኤል ነገዶች መከፋፈል (ኢያሱ 13-21)

4. ኢያሱ ለተለያዩ ነገዶች ያደረገው የስንብት ንግግር (ኢያሱ 22-24)

## ኢያሱ የእስራኤል ሕዝብ መሪ

በብሉይ ኪዳን ውስጥ የሚገኙ ታላላቅ የእምነት ሰዎችን ያህል ስለ ኢያሱ የተነገረ ባይሆንም፥ ኢያሱ ታላቅ የእግዚአብሔር ሰው ነበር። ኢያሱ ከኤፍሬም ነገድ ሲሆን የመጀመሪያ ስሙ አውሴ ነበር፤ ትርጉሙም «ደኅንነት» ማለት ነው፤ (ዘኁ. 13፡8)። በኋላ ሙሴ ስሙን ኢያሱ አለው፤ ትርጉሙም «ጌታ ያድናል» ማለት ነው።

ማስታወሻ:- «ኢየሱስ» የሚለው ስም ኢያሱ (ጆሹዋ) ከሚለው የተወሰደ የግሪክ ስም ነው፤ ስለዚህ ኢየሱስ በአራማይክ ቋንቋ ኢያሱ ተባለ።

ኢያሱ በግብፅ፥ በባርነት ያደገ ሰው ነው። እስራኤላውያን ከግብፅ ባርነት ነፃ በወጡ በጥቂት ጊዜያት ውስጥ የእስራኤል ጦር አዛዥ ስለሆነ፥ አንዳንድ ሰዎች የአንድ የግብፅ የጦር መሪ ባሪያ የነበረ ሳይሆን አይቀርም ይላሉ፤ (ዘጸ. 17፡8-13)። እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ከግብፅ ባርነት ነፃ ሲያወጣ የተመለከተ ሲሆን፥ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በእግዚአብሔር ላይ ዓምፆ አያውቅም። በ40 ዓመታቱ የምድረ በዳ

ጉዞም የሙሴ ረዳት እንዲሆን ተመርጦ ነበር። ከሙሴ ጋር ወደ ሲና ተራራ ወጥቶ ነበር። ሙሴ እግዚአብሔርን ፊት ለፊት ካየ ወዲህ በመገናኛው ድንኳን ውስጥ አብሮት የነበረው ኢያሱ ለእግዚአብሔር ያለውን ታላቅ ፍቅር ለማሳየት በእግዚአብሔር ፊት ቆየ፤ (ዘጸ. 33፡11)። ከ12 ነገዶች የተመረጡ ምድሪቱን እንዲሰልሉ በተላኩ ጊዜ፥ ኢያሱ የኤፍሬምን ነገድ ወክሎ ሄደ፤ ከካሌብም ጋር በመሆን የእስራኤል ሕዝብ በእግዚአብሔር ማመንና ወደ ምድሪቱ መግባት እንዳለባቸው ተናገረ፤ በውጤቱም እግዚአብሔር እምነቱን አከበረና ወደ ተስፋይቱ ምድር እንደሚገባ ነገረው። እግዚአብሔር ሙሴን፥ ከእርሱ ቀጥሎ የሚመጣ መሪ አድርጎ ኢያሱን እንዲመርጠው ተናገረ። በኃይልም አስታጠቀው፤ (ዘዳ. 31፡14)። በኢያሱ መሪነት እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ወደ ከነዓን ምድር መራቸው። በከነዓናውያን ላይም ድልን ሰጣቸው። ኢያሱ የእስራኤልን ሕዝብ የመራው ከ25-30 ዓመታት ለሚደርስ ጊዜ ሲሆን፥ በመጨረሻም ሲሞት በኤፍሬም ምድር ተቀበረ። ኢያሱ ከመሞቱ በፊት በእግዚአብሔርና በእስራኤል መካከል የነበረውን ቃል ኪዳን አደሰ። ለእግዚአብሔር የነበረው ፍቅር ለእስራኤላውያን ባቀረበው ምርጫ ታውቋል፡- «የምታመልኩትን ዛሬ ምረጡ። እኔና ቤቴ ግን እግዚአብሔርን እናመልካለን» አላቸው (ኢያ. 24፡15)።

| |
|---|
| 17ኛ ጥያቄ፥ ሀ) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እንደመሆናችን፥ ዛሬ እግዚአብሔር ከእኛ ስለሚፈልገው ነገር የኢያሱ ሕይወት መልካም ምሳሌ የሆነው እንዴት ነው? ለ) ከኢያሱ ሕይወት ውስጥ ከምታየው ባሕርይ በሕይወትህ ልታያቸው የምትፈልጋቸውን ነገሮች ዘርዝር። |

## የመጽሐፈ ኢያሱ ርእስ

መጽሐፉ፥ መጽሐፈ ኢያሱ ወልደነዌ የሚለውን ስም ያገኘው በውስጡ ዋና ገጸ ባሕርይ ሆኖ ከቀረበውና የእስራኤል ሕዝብ መሪ ከሆነው ከኢያሱ ነው። ከሙሴ ሞት በኋላ፥ እግዚአብሔር ኢያሱን መረጠውና የከነዓንን ምድር ድል በመንሣት የእስራኤልን ሕዝብ እንዲመራ በኃይል አስታጠቀው።

## የመጽሐፈ ኢያሱ ዋና ዓላማ

መጽሐፉ የተሰየመው፥ በመጽሐፉ ውስጥ በሚገኘው ዋና ተዋናይ በኢያሱ ቢሆንም፥ ትኩረቱ ግን በእርሱ ላይ ሳይሆን በእግዚአብሔር ላይ ነው። የእግዚአብሔር ሕዝብ መሪ የሆነውና የእስራኤልን ጦር በመምራት ድልን ያስገኘው እግዚአብሔር ነው። ኢያሱ በእግዚአብሔር ትእዛዝ ሥር ያለ ሰብአዊ መሪ በመሆኑ ትእዛዙን በቀጥታ ይፈጽም ነበር።

ከሌሎች መጻሕፍት (መጽሐፈ መሳፍንት፥ ሳሙኤልና ነገሥት) ጋር በአንድነት ሆኖ የመጽሐፈ ኢያሱ ዋና ዓላማ እግዚአብሔር በታሪክ ውስጥ ከእስራኤል ጋር የገባውን ቃል ኪዳን እንዴት እንደፈጸመ ማሳየት ነው። መጽሐፈ ኢያሱ የሚያሳየው፥ እስራኤላውያንን ወደ ከነዓን ምድር በማምጣትና ለአብርሃም ከብዙ መቶ ዓመታት በፊት የገባውን ቃል ኪዳን በመፈጸም፥ የቃል ኪዳን ተስፋዎቹን በታማኝነት እንዴት እንደጠበቀ ነው (ዘፍ. 15፡18-21)። ለእግዚአብሔር ሕዝብ ምንም ያህል አስቸጋሪ ሆኖ ቢታይም፥ እግዚአብሔር ለሰጠው ተስፋ ታማኝ መሆኑን አሳየ።

መጽሐፈ ኢያሱ በጠላቶች ላይ ድል የሚገኘው በእግዚአብሔር ኃይልና አመራር ብቻ መሆኑን ያሳያል። ሕዝቡ በእርሱ ላይ በእምነት በሚደገፉበትና ሙሉ ለሙሉ እርሱን በሚታዘዙበት ጊዜ ብቻ ይፈጸማል። ኃጢአት የእግዚአብሔርን ሥራ የሚከለክል ሲሆን፥ እምነት ግን በእግዚአብሔር ሕዝብ መካከል የእግዚአብሔር ኃይል እንዲገለጥ ያደርጋል። ድል የሚገኘው በመታመንና በመታዘዝ ነው።

> 18ኛ ጥያቄ፥ ሀ) የመጽሐፈ ኢያሱ ዓላማ በመንፈሳዊ ሕይወት ጠላቶቻችን ላይ ድልን የማግኛ ምሥጢር ምን እንደሆነ የሚያስተምረን እንዴት ነው? ለ) ይህ በሕይወትህ ሲፈጸም ያየኸው እንዴት ነው? ሐ) እግዚአብሔር በሕይወትህ ስለሠራው ሥራ እርሱን ለማመስገን አሁኑኑ ጊዜ ይኑርህ።

19ኛ ጥያቄ፥ ሀ) ብዙ ክርስቲያኖች በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ሽንፈት የሚደርስባቸው ለምንድን ነው? ለ) ብዙ ክርስቲያኖች ያለማቋረጥ በኃጢአት የሚወድቁትና ጨርሶ ድል የማያገኙ የሚመስሉት ለምንድን ነው? ሐ) እግዚአብሔር ከእኛ የሚፈልገው ይህን ይመስልሃልን? ግለጥ።

እግዚአብሔር ለሕዝቡ ድልን ለመስጠት ቃል ገብቷል። ጳውሎስ ለሮሜ ክርስቲያኖች ሲጽፍ፥ «በዚህ ሁሉ ግን በወደደን በእርሱ ከአሸናፊዎች እንበልጣለን» ብሎአል (ሮሜ 8፡37)። በተጨማሪ 1ኛ ቆሮ. 15፡57፤ 1ኛ ዮሐ. 2፡13፤ 4፡4 ተመልከት። ይህ ድል ግን እንዲሁ በቀላሉ የሚገኝ ነገር አይደለም። ለዚህ ድል ዝግጅት ማድረግ ያሻናል። እምነት ሊኖረን ያስፈልጋል። ድል የሚገኘው ከእግዚአብሔር እንጂ በራሳችን ጥረት እንዳልሆነ ማወቅ ያስፈልጋል። በኃጢአት ላይ የድል ነሺነት ሕይወት በመኖር፥ የተቀደስን ልንሆን ያስፈልጋል። ለእግዚአብሔር ታዛዦች መሆን አለብን። የመጽሐፈ ኢያሱ የመጀመሪያ ክፍል እስራኤላውያን ከነዓንን ድል አድርገው በወረሱት ልምምድ በኩል እነዚህን አስፈላጊ መንፈሳዊ እውነቶችን ይገልጣል።

20ኛ ጥያቄ. ኢያሱ 1-12 አንብብ። ሀ) እግዚአብሔር ኢያሱን ለመሪነት ያዘጋጀው እንዴት ነው? ለ) እግዚአብሔር በጠላቶች ላይ ስላዘጋጀው የድል መንገድ ሁለቱ ሰላዮች የተማሩት ነገር ምን ነበር? ሐ) ቀይ ባሕርን መሻገር ለእስራኤላውያን የሚያሳየው ነገር ምንድን ነው? (ኢያ. 3፡10-13)። መ) ለመታሰቢያ ይሆን ዘንድ በዮርዳኖስ ምዕራባዊ ክፍል እስራኤላውያን የገነቡት ነገር ምን ነበር? ለምን? ሠ) በጌልጌላ ምን ተደረገ? ረ) ኢያሱ የተገናኘው የእግዚአብሔር ሠራዊት አዛዥ ማን ነበር? ሰ) በኢያሪኮ ላይ እግዚአብሔር ለአይሁዳውያን ድልን የሰጠው እንዴት ነበር? ሸ) እስራኤላውያን ጋይን ያላሸነፉት ለምንድን ነው? ቀ) እስራኤላውያን በኢባል ተራራ ምን አደረጉ? በ) አይሁድ እንዳያጠፏቸው የገባዖን ሰዎች ያደረጉት ምን ነበር? ተ) በእስራኤላውያን የተደመሰሱትን የተለያዩ ሕዝቦች ዘርዝር።

1. እስራኤላውያን ዮርዳኖስን በመሻገር ወደ ከነዓን ገቡ፤ (ኢያሱ 1-5)።

እስራኤላውያን በዮርዳኖስ ወንዝ ምሥራቃዊ ክፍል ሰፍረው ነበር። ከ40 ዓመታት በፊት የቀይ ባሕርን እንዲሻገሩ የረዳቸው እግዚአብሔር፥ ከሙሴ ሞት በኋላ ደግሞ የዮርዳኖስን ወንዝ እንዲሻገሩ አዘጋጃቸው።

ሀ. በመጀመሪያ ግን እግዚአብሔር የእስራኤል ሕዝብ መሪ እንደ መሆኑ ኢያሱን ወደ ፊት ለሚጠብቀው አዲስ ኃላፊነት ለማዘጋጀት ፈለገ (ኢያሱ 1)። ስለዚህም እግዚአብሔር ለኢያሱ አንዳንድ ትእዛዛትን ሲሰጠው እንመለከታለን፡- 1) ከሙሴ ጋር እንደነበረ ከኢያሱም ጋር እንደሚሆንና በጠላቶቹ ሁሉ ላይ ድልን እንደሚሰጠው ቃል ገባለት። 2) እግዚአብሔር ለኢያሱ እንዲበረታና እንዲጠነክር፥ እምነቱንም በእርሱ ላይ እንዲያደርግ ነገረው። 3) እግዚአብሔር ኢያሱን ከቃል ኪዳኑ ወይም በሙሴ በኩል ከሰጠው ሕግጋት እንዳይለይ አስጠነቀቀው። ይልቁንም እነዚህን ሕግጋት በሕይወቱ በመኖር ሊያሳይና በልቡ ሊሰውር ይገባው ነበር። እግዚአብሔር ለኢያሱ እንዲከናወንለት የሚያደርገው እርሱን ካወቀና ቃሉን ከታዘዘ ብቻ ነበር።

---

21ኛ ጥያቄ፥ እነዚህን ሦስት ነገሮች በዚህ ዘመን ያሉ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ማስታወስ የሚያስፈልጋቸው ለምንድን ነው?

---

ለ. እስራኤላውያን ዮርዳኖስን ከተሻገሩ በኋላ በመጀመሪያ ወደምትገኘዋ ከተማ ወደ ኢያሪኮ ኢያሱ ሁለት ሰላዮችን ላከ (ኢያሱ 2)። እነዚህ ሁለት ሰላዮች ረዓብን አገኙአት። ረዓብም በከነዓናውያን ልብ እግዚአብሔር ፍርሃትን እንዳደረገና እያንዳንዱ ሰው እግዚአብሔር ከአይሁድ ጋር ስለሆነ በእነርሱ መሸነፋችን የማይቀር ነው የሚል ግምት እንዳደረበት ነገረቻቸው።

ረዓብ ምን ዓይነት ሴት እንደነበረች ማወቅ አስቸጋሪ ነው። ሴተኛ አዳሪ የነበረች ሴት ትመስላለች፤ (ኢያ. 2፡1)። ነገር ግን ይህ ስለማንነቷ የሚገልጠው ቃል የሆቴል ቤት ዓይነት መኝታ ክፍሎችንም

የምታከራይ ቤት እንደሆነችም ሊያመለክት ይችላል። ሁለቱ ሰላዮችም ወደ እርሷ ቤት የገቡት ለዚህ ሊሆን ስለሚችል፥ በዚህ መልኩ ልንተረጉመው እንችላለን። ረዓብ ሰላዮቹን በመሸሸግ በእግዚአብሔር ላይ ያላትን እምነት ስለገለጠች፥ እርሱ አከበራት። በአዲስ ኪዳን የእምነት ምሳሌ ሆና ቀርባለች (ዕብ. 11፡31፤ ያዕ. 5፡25)። በኋላም ከይሁዳ ነገድ የሆነ ሰው ስላገባች፥ መሢሑ ክርስቶስ የመጣበት ዘር አካል ሆናለች፤ (ማቴ. 1፡5)። የዳነችው በእምነትና በመታዘዝ ቀይ ፈትልን በመስኮቷ በኩል ስላንጠለጠለች ነው። ብዙዎች ይህ እኛን ያዳነ የክርስቶስ ደም ምሳሌ ነው ይላሉ።

ሐ. እስራኤላውያን የዮርዳኖስን ወንዝ ተሻገሩ (ኢያሱ 3)። እስራኤላውያን የዮርዳኖስን ወንዝ በተሻገሩ ጊዜ እጅግ ሞልቶ እንደ ነበረ እናነባለን። ለመሻገርም የማያስችል ነበር። እግዚአብሔር ግን ተአምር ሠራ። ምናልባት በሚንሸራተት ጭቃ ወይም በመሬት መንቀጥቀጥ ምክንያት [መዝ. (114)3-4] በስተሰሜን 25 ኪሎ ሜትር ርቆ በሚገኝና እስራኤላውያን በተሻገሩት አዳም በሚባል ከተማ ውኃው ተገድቦ ይሆናል። በምንም መንገድ ይሁን፥ እግዚአብሔር ምንም ነገር ይጠቀም፥ ተአምር ነበር። 2 ሚሊዮን የሚሆኑ ሰዎች የዮርዳኖስን ወንዝ በየብስ ተሻገሩ።

ይህ ተአምር ሁለት ዋና ዋና ዓላማዎች ነበሩት። የመጀመሪያው፥ ሙሴ ሕዝቡን ቀይ ባሕርን እንዳሻገራቸው ሁሉ፥ ኢያሱም እውነተኛ መሪ መሆኑን ለማሳየት ነበር። ሁለተኛ፥ እስራኤላውያን እግዚአብሔር ከእነርሱ ጋር እንደሆነና በጠላቶቻቸው ላይ ድልን እንደሰጣቸው የሚያሳይ ነበር።

መ. እስራኤላውያን በዮርዳኖስ ምዕራባዊ ክፍል መታሰቢያን አቆሙ (ኢያሱ 4)። ኢያሱ በመጽሐፉ ውስጥ እስራኤላውያን ከእነርሱ በኋላ ለሚመጣ ትውልድ ቋሚ ማስታወሻ ይሆን ዘንድ እግዚአብሔር በዚህ ዘመን ለእነርሱ ያደረገላቸውን እንዲያውቁ፥ በርካታ ጊዜያት መታሰቢያ ያቆሙ ነበር። ለእያንዳንዱ የእስራኤል ነገድ አንድ አንድ ድንጋይ የቆመለትና በአጠቃላይ 12 ድንጋዮች በመታሰቢያነት የቆሙት እግዚአብሔር የዮርዳኖስን ወንዝ እንዲሻገሩ

እስራኤላውያንን እንዴት እንደረዳቸው በመታሰቢያነት ለማሳየት ነበር።

ሠ. በጌልጌላ የአይሁድ መገረዝ (ኢያሱ 5)። አይሁድ 40 ዓመታት እግዚአብሔርን ባለመታዘዝ ኖረዋል። ወንዶች ልጆቻቸውን አልገረዙም ነበር። ግዝረት አይሁድ በቃል ኪዳኑ ውስጥ ለመኖራቸው ውጫዊ ምልክት ነበር፤ በተጨማሪ ራሳቸውን ከኃጢአት የመለየታቸው ምልክት ነበር። በግብፅ ሲኖሩ የነበረባቸው የኃጢአት ነውር አልለቀቃቸውም ነበር፤ (ኢያሱ 5፡9)። ስለዚህ እግዚአብሔር አይሁድ ምድሪቱን እንዲወርሱ ከማድረጉ በፊት በመንፈሳዊ ሁኔታ ሊያዘጋጃቸው ያስፈልግ ነበር። በግዝረት የሕመም ስሜት ውስጥ ማለፋቸው እግዚአብሔር ከእነርሱ ጋር የገባውን ቃል ኪዳን የማክበራቸውን አስፈላጊነት የሚያሳስብ ነበር። በዚያ ቀን በምድረ በዳ ለ40 ዓመታት የተመገቡት መና አበቃና የከነዓንን ምድር ፍሬ መብላት ጀመሩ።

በዮርዳኖስ በስተ ምዕራብ ለመጀመሪያ ጊዜ አይሁድ በሰፈሩበት በጌልጌላ የተፈጸመ አንድ ሌላ በጣም አስፈላጊ ነገር ነበር። ጌልጌላ የእስራኤል ሕዝብ ጊዜያዊ ዋና ማዕከል ሆነች። በዚህ ስፍራ ኢያሱ «የእግዚአብሔር ሠራዊት አዛዥ» የሆነውን ተገናኘው። መዋጋት ከመጀመሩ በፊት፥ የእስራኤልን ጦር የሚመራው እርሱ እንጂ ኢያሱ እንዳልሆነ እግዚአብሔር ሊያስታውሰው ፈለገ። በመጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ብዙ ጊዜ «የሠራዊት ጌታ» በመባል ይታወቃል። ብዙ ጊዜ በመጽሐፍ ቅዱስ «የሠራዊት ጌታ» የተባለው እግዚአብሔር የእስራኤል ማለት የሕዝቡ ሠራዊት እውነተኛ መሪ ነበር። ኢያሱ በእርሱ ትእዛዝ ሥር ነበር። ብዙ ሰዎች የጌታ ጦር አዛዥ የነበረው ይህ አለቃ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው ብለው ያስባሉ።

22ኛ ጥያቄ ሀ) ለኢያሱ ይህንን እውነት የመረዳት አስፈላጊነቱ ምን ነበር? ለ) ዛሬ ይህንን እውነት ከሕይወታችን ጋር እንዴት ልናዛምደው እንችላለን?

ረ. እስራኤላውያን ኢያሪኮን ያለ ውጊያ ያዙ (ኢያሱ 6)። እስራኤላውያን የገጠመቻቸው የመጀመሪያዋ ከተማ

ጠንካራዋ ኢያሪኮ ነበረች። ዙሪያዋን በትልቅ ግንብ የታጠረች፥ በምሽት የሚዘጋ ትልቅ መዝጊያ የነበራት ስለሆነ፥ እርስዋን ማጥቃት ፈጽሞ አስቸጋሪ ነበር። ይህችን ከተማ ያለ አንዳች ጦርነት እንዲይዙዋት በማድረግ ድልን የሚሰጥ እግዚአብሔር እንጂ እነርሱ እንዳይደሉ አሳየ። እስራኤላውያን በኢያሪኮ ግንብ ዙሪያ በእምነት ስለዞሩ ቅጥሩ በሰባተኛው ቀን ወደቀ። በከነዓን ምድር በመጀመሪያ ልትጠፋ ያለችው ከተማ ኢያሪኮ ስትሆን በርሷም ውስጥ ያሉት ነገሮችን በሙሉ እንዲያጠፉ ወይም ለእርሱ ጥቅም ብቻ እንዲያውሉ እግዚአብሔር አዘዘ። ከጦርነቱ ምርኮ የሚገኝ ማንኛውም ነገር ቢሆን ለግል ጥቅም እንዳይውል ተከለከለ።

በተጨማሪ ኢያሱ ይህችን ከተማ እንደገና ለመገንባት የሚሞክር ሰው ሁሉ በልጆቹ ሞት መከራ ያገኘው ዘንድ ከተማይቱን ረገመ (በ1ኛ ነገሥት 16፡34 የዚህን ጥቅስ ፍጻሜ እናገኛለን)።

ሰ. እስራኤላውያን በኃጢአታቸው ምክንያት በጋይ ተሸነፉ (ኢያሱ 7-8)። እግዚአብሔር በጋይ በጣም አስፈላጊ የሆኑ ሁለት ትምህርቶችን ለእስራኤላውያን ማስተማር ነበረበት። በመጀመሪያ፥ ድል ለማግኘት መደገፍ ያለባቸው በእግዚአብሔር እንጂ በራሳቸው ኃይል እንዳልነበረ ነው። እስራኤላውያን ትንሿን የጋይ ከተማ ያለ እግዚአብሔር ርዳታ በራሳቸው ኃይል እንደሚያሸንፉ ገመቱ፤ ነገር ግን ተሸነፉ።

ሁለተኛው ነገር ደግሞ፥ እግዚአብሔር ለእነርሱ የሚሠራውን ሥራ በመካከላቸው እንዳይሠራ የሚከለክለው ኃጢአት እንደሆነ ማሳየት ነበረበት። አካን እግዚአብሔርን ስላልታዘዘና ከኢያሪኮ ከተማረከው ነገር ለራሱ የሚሆነውን ስላስቀረ እስራኤላውያን እንዲሸነፉ አደረገ። እስራኤላውያን በተሠራው ኃጢአት ከፈረዱና ከመካከላቸው ካስወገዱ በኋላ ብቻ እግዚአብሔር በጋይ ምድር ላይ ድልን ሰጣቸው። እግዚአብሔር በኃጢአት ላይ ያለውን ጥላቻ ለመግለጥና የእግዚአብሔርን ማኅበረሰብ ኃጢአት እንዴት ችግር ላይ ሊጥለው እንደሚችል ለማሳየት፥ ይህ ታሪክ፥ እግዚአብሔር አካንና ቤተሰቡ ሁሉ እንዲገደሉ መስማማቱን ያሳየናል። በእግዚአብሔር ሕዝብ መካከል የሚፈጸም ኃጢአት በዚያ ሰውና በእግዚአብሔር መካከል

የሚሆን ግላዊ ጉዳይ ብቻ ሳይሆን፥ የእግዚአብሔርን ሕዝብ በአጠቃላይ የሚመለከት ነው። በአከአብና በቤተሰቡ በተቃጠለ አካል ላይ የተከመረው ድንጋይ ኃጢአት እንዴት ሰዎችን እንደሚጎዳ የሚያሳይ የመታሰቢያ ሐውልት ሆኖ የሚያገለግል ነበር።

| |
|---|
| 23ኛ ጥያቄ፥ ሀ) ድል ለማድረግ ባለን ችሎታ ላይ ኃጢአት ስለሚያመጣው ችግር ምን መማር እንችላለን? ለ) ስለ እግዚአብሔር ባሕርይና ኃጢአትን በከባድ ሁኔታ እንዴት እንደሚመለከተው ከዚህ ታሪክ ምን መማር እንችላለን? ሐ) ብዙ ጊዜ ኃጢአትን እንደ ቀላል ነገር የምንመለከተው እንዴት ነው? መ) በኃጢአት ላይ ስላለን አመለካከት ይህ ምን ይላል? ሠ) ኃጢአትን በቀላል ሁኔታ መመልከት በአጭር ጊዜ ውስጥ በቤተ ክርስቲያን እንዲስፋፋ የሚያደርገው እንዴት ነው? |

የእግዚአብሔር ሕዝብ ጋይን ካሸነፉ በኋላ ወደ ሴኬም ተጓዙ። ሴኬም የሚገኘው በጌባል ተራራ ግርጌ ነበር። በጌባልና በገሪዛን ተራራ ላይ በእግዚአብሔርና በእስራኤላውያን መካከል የተደረገው ቃል ኪዳን ታደሰ። በጌባል ተራራ ላይ የእግዚአብሔርን ሕግ ቢጠብቁ ስለሚያገኙት በረከት ከፊሎቹ እስራኤላውያን አነበቡ። የቀሩት ደግሞ በገሪዛን ተራራ ላይ ሆነው የእግዚአብሔርን ሕግ ባይጠብቁ ስለሚገጥሟቸው ርግማኖች የተጻፉትን አነበቡ። ከዚያም በአንድነት ቃል ኪዳናቸውን አደሱ።

ሸ. የገባዖን ሰዎች እስራኤላውያንን አታለሉ (ኢያሱ 9)። ከትላልቅና ከተገነቡ ከተሞች ብዙ ኪሎ ሜትር ሳይርቁ የሚገኙት የገባዖን ሰዎች በኢያሪኮና በጋይ የነበረቱን ከነዓናውያንን በማሸነፍ ሙሉ በሙሉ እንዴት እንዳጠፏቸው ሰሙ። ስለዚህ ከሩቅ ቦታ የመጡና ከእስራኤላውያን ጋር ለመተባበር የፈለጉ በመምሰል ሊያታልሏቸው ወሰኑ። አይሁድም በጉዳዩ እግዚአብሔርን ሳይጠይቁ ከሰዎቹ ጋር ስምምነት አደረጉ። እግዚአብሔር ከከነዓናውያን ጋር ምንም ዓይነት ስምምነት እንዳያደርጉ አግዶአቸው ነበር፤ (ዘጸ. 34፡12፥ 15)። ስለዚህ ጉዳይ ንጉሣቸው የሆነውን እግዚአብሔርን ስላልጠየቁ ተታለሉ። ለገባዖን ሰዎች

ቃላቸውን ሰጥተው ስለ ነበር ምንም ነገር ያደርጉባቸው ዘንድ እግዚአብሔር አልፈቀድም። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንደምናየው እግዚአብሔር ሕዝቡ የገቡትን ቃል እንዲጠብቁ ከፍተኛ ትኩረት ያደርግ ነበር (ዘሌ. 19፡ 12-13)፤ ነገር ግን የገባዖንን ሰዎች ባሪያዎች አደረጉአቸው።

ቀ. ከደቡብ ከነዓን ነገሥታት ጋር የተደረገ ጦርነት (ኢያሱ 10)። የደቡብ ከነዓን ነገሥታት የገባዖን ሰዎች ከእስራኤላውያን ጋር መተባበራቸውን በሰሙ ጊዜ ገባዖንን ወጉ። እስራኤላውያንም ከገባዖን ሰዎች ጋር ባደረጉት ስምምነት የተነሣ የገባዖንን ሰዎች በዚህ ጦርነት መርዳት ግዴታቸው ነበር፤ ስለዚህ እስራኤላውያን አምስቱን የከነዓን ነገሥታት ወግተው አሸነፏቸው። እግዚአብሔር አሁንም ለእስራኤል ሲል ተአምር አደረገ። የእነዚህን አምስት ነገሥታት ሠራዊት ፈጽመው ይመቱ ዘንድ ፀሐይን እንድትቆም አደረገ። የእስራኤል ጦር ከገደላቸው ይልቅ እግዚአብሔር ከሰማይ በላከው፥ በበረዶ ድንጋይ የሞቱት ቁጥር ይበልጥ ነበር። ከዚህ በኋላ ኢያሱ ወደፊት በመገስገስ በደቡብ ከነዓን የሚገኙትን ሌሎች ዋና ዋና ከተሞች አሸነፈ።

** እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን መዋጋቱን የሚገልጸውን የዚህን ምዕራፍ ትኩረት አስተውል (ኢያ. 10፡14፥ 42)። ጠላቶቻቸውን እንዲያሸንፉ ያደረጋቸው የራሳቸው ብርታት ሳይሆን ስለ እነርሱ ሲል የተዋጋው የእግዚአብሔር ኃይል ነው።

| |
|---|
| 24ኛ ጥያቄ፥ በሕይወታችን ለሚያጋጥመን ለማንኛውም ድል ይህ ነገር እውን የሆነው እንዴት ነው? |

በ) የሰሜን መንግሥታት ተሸነፉ (ኢያሱ 11)። እስራኤላውያን በኢያሱ መሪነት በመካከለኛይቱ ከነዓን የሚገኙትን ዋና ዋና ነገሥታት (ኢያሪኮና ጋይን) እና እንደዚሁም የደቡብ ከነዓን ነገሥታትን ካሸነፉ በኋላ ወደ ሰሜን ከነዓን ከተሞች ዘመቱ (ኢያሱ. 11፡ 18)። ይህ ጦርነት ረጅም ጊዜ የወሰደ ቢሆንም (ኢያሱ 11፡ 18)፥ ሆኖም በሰሜኑም የሚገኙት ዋና ዋና ከተሞች በሙሉ ተሸነፉና እስራኤላውያን ተቆጣጠሩአቸው።

አሁን እያንዳንዱ ነገድ በምድሪቱ የቀሩትን ከነዓናውያን የማጥፋት ኃላፊነት ነበረበት። ነገር ግን ለእግዚአብሔር በመታዘዝ እንደማጥፋት ከቀሩት ከነዓናውያን ጋር በሰላም መኖርን መረጡ። በዚህም ምክንያት ወደ ፊት እንደምናየው፥ ከነዓናውያን ኃጢአትን ለእስራኤል ሕዝብ በማስለመድና እነርሱን ወደ ኃጢአት በመምራት የእግዚአብሔር ቁጣ በእስራኤላውያን ላይ እንዲመጣ አደረጉ።

ተ) በእስራኤል የተሸነፉ የ31 ነገሥታት ዝርዝር (ኢያሱ 12)።

25ኛ ጥያቄ፥ ከተሞቹ የት የት እንዳሉ ለማወቅ በዚህ መጽሐፍ በስተጀርባ ያለውን ካርታ ተመልከት።
26ኛ ጥያቄ፥ ሀ) በእግዚአብሔር ጠላቶች ላይ ድል ለመቀዳጀት የሚጠቅሙትን መመሪያዎች ከእነዚህ ምዕራፎች ውስጥ ዘርዝር። ለ) ድል አድራጊ ክርስቲያን እንድትሆን እነዚህን መሠረታዊ የሥነ ምግባር ሕግጋት ከሕይወትህ ጋር እንዴት እንደምታዛምድ ግለጽ።

## 4ኛ ቀን፡- ኢያሱ 13-24

ክርስቲያን በሕይወቱ ከሚያጋጥሙት አደገኛ ነገሮች አንዱ ሰላምና በረከትን በሚያገኝ ጊዜ እግዚአብሔርን መርሳት ነው። ሙሴ ስለዚህ ጉዳይ በዘዳ. 8፡7-20 ባለው ክፍል እስራኤላውያንን አስጠንቅቆአቸዋል። የከነዓን ምድር በሙሉ ለእስራኤላውያን (ለአሥራ ሁለቱም ነገዶች) ከተከፋፈለ በኋላ እያንዳንዱ ሰው በተሰጠው ምድር አርፎ ሲኖር ሕዝቡ በዕለታዊ ተግባራቸው እየተጠመዱ በመፈተናቸው እግዚአብሔርን የመርሳት ከፍተኛ ዝንባሌ ታይቶባቸው ነበር፤ ስለዚህ ኢያሱ ሕዝቡን ሁሉ ወደ ሴኬም ጠራና ቃል ኪዳኑን አደሰ። እግዚአብሔርን ወይም ሌላን ነገር እንዲመርጡ፥ በቃል ኪዳኑ ስምምነት እንዲኖሩ ወይም በእግዚአብሔር ላይ እንዲያምፁ ምርጫ ማድረግ እንዳለባቸው አስገነዘባቸው። እኛም ልክ እንደ እስራኤላውያን ሁሉ ራሳችንን ለእግዚአብሔር ለመስጠት የገባነው ቃል ኪዳን ያለማቋረጥ መታደስ አለበት። በመጀመሪያ እንዳመንን ወይም ራሳችንን ለእግዚአብሔር እንደሰጠን የገባነው ቃል ኪዳን ያለማቋረጥ መታደስ አለበት፤ አለበለዚያ መንፈሳዊ ሕይወታችን እየቀዘቀዘ ይሄድና እግዚአብሔርን እንረሳለን።

27ኛ ጥያቄ፥ ሀ) ሰላምና በረከት በሞላበት ጊዜ እግዚአብሔርን መርሳት በጣም ቀላል የሚሆነው ለምንድን ነው? ለ) ስለ ራስህ ሕይወት አስብ። በሙሉ ልብህ እግዚአብሔርን እንደምትወደውና እንደምትከተለው የገባኸውን ቃል ኪዳን ለመጨረሻ ጊዜ ያደስከው መቼ ነው? ሐ) እግዚአብሔር ስለ ሰጠህ በረከት ሁሉ እስቲ ለጥቂት ጊዜ አስብ። መ) ስለ እነዚህ ጉዳዮች ለአንድ አፍታ እርሱን አመስግን። ሠ) እግዚአብሔርን ለመከተል፥ እርሱን ሁልጊዜ ለማገልገል፥ በፊቱ በፍጹም ንጽሕና ለመመላለስ ወዘተ. የገባኸውን ቃል ኪዳን አድስ።

28ኛ ጥያቄ፥ ኢያሱ 13-24 አንብብ። ሀ) በመጽሐፉ በስተጀርባ የሚገኘውን ካርታ ተመልከት። ቦታ የተሰጣቸው ነገዶች ሁሉ ያሉት የት ነበር? ለ) ለካሌብ የተሰጠው ምን ነበር? ሐ) የስድስቱ መማፀኛ ከተሞች ዓላማ ምን ነበር? መ) ለሌዋውያን ስንት ከተሞች ተሰጡአቸው? ሠ) የጎሣ ጦርነት ሊያስከትል የነበረ በምሥራቅ በሚገኙ ጎሣዎች የተፈጸመ ተግባር ምን ነበር? ረ) ኢያሱ ከመሞቱ በፊት ለእስራኤላውያን የሰጠው ማስጠንቀቂያ ምን ነበር?

1. የከነዓን ምድር ለእስራኤላውያን መደልደል (ኢያሱ 13-21)።

አብዛኛው የከነዓን ምድር እንደተያዘ፥ እግዚአብሔር ለኢያሱ ምድሪቱን ለ12 ነገዶች እንዲያከፋፍል አዘዘው። እስካሁን ድረስ ያልተወረሩና ያልተያዙ ከተሞች በምድሪቱ ክፍል እንዲወርሱ የተደለደሉ ነገዶች የማስለቀቅ ኃላፊነት ነበረባቸው።

ሀ. ከዮርዳኖስ በስተ ምሥራቅ የሚገኙ ነገዶች፡- እንደምታስታውሰው፥ ሙሴ ከዮርዳኖስ በስተምሥራቅ የሚገኘውን ስፍራ ለሮቤል ለጋድ ነገዶችና ለምናሴ ነገድ እኩሌታ ሰጥቶ ነበር። አሁን ክልላቸው ተወስኗል።

ለ. ከዮርዳኖስ በስተምዕራብ የተደለደሉ ነገዶች፡- ለቀሩት ዘጠኝ ተኩል (9 1/2) ነገዶች ከዮርዳኖስ በስተምዕራብ የሚገኘው ክፍል ተሰጣቸው። በእግዚአብሔር ላይ ለነበረው እምነትና ጥንካሬ የይሁዳ መሪ ለነበረው ለካሌብ ልዩ ትኩረት ተሰጠውና የኬብሮንን ምድር አገኘ። ኢያሱ ለነገዶቹ ሁሉ የሚሆነውን

ምድር ደለደለ፤ ክልላቸውን ወሰነ፤ በክልላቸው ውስጥ ያሉትንም ከተሞች ነገራቸው። ከዚህ በኋላ በክልላቸው ውስጥ የሚገኙትን ከተሞች ሁሉ የመያዝ ኃላፊነት የእነርሱ ነበር። እያንዳንዱ ነገድ ገና ወርሮና አሸንፎ የሚይዘው ክልል ነበረው። ከአሥራ ሁለቱ ነገዶች ዋና ዋና ለሆኑት፥ ለይሁዳ፥ ለኤፍሬምና ለምናሴ ነገዶች ስለተሰጠው ምድር ሰፊና ጥልቀት ያለው ትንተና ቀርቦአል።

ሐ. የመማፀኛ ከተሞች፡- በዮርዳኖስ በስተምሥራቅ ሦስት፥ በስተምዕራብ ሦስት፥ በአጠቃላይ ስድስት ከተሞችን እግዚአብሔር የስደተኞች ከተሞች ይሆኑ ዘንድ ለየ። የእነዚህ ከተሞች ዋና ዓላማ አንድን ሰው በስሕተት ለገደለ ሰው የጥበቃ ስፍራ ለመስጠት ነበር። ከሟቹ ሰው ዘመዶች ሊደርስበት ከሚችል ብቀላ ለመዳን ከእነዚህ ከተሞች ወደ አንዱ መሸሽ ነበረበት። የዚህ ዓይነቱ የፍትሕ ሥርዓት በእስራኤል ነገዶች መካከል በቤተሰባቸው ውስጥ በሞተ ሰው ምክንያት ሊፈጠር የሚችለውን በቀልና የእርስ በርስ ግጭት ለመከላከል ነበር።

29ኛ ጥያቄ፥ ሀ) ይህ መንገድ በምድሪቱ ሰላምን ለማስፈን መልካም የሆነው ለምንድን ነው? ለ) በቀል ፍለጋ ወደበለጠ ጦርነትና ጥፋት የሚመራው እንዴት ነው? ሐ) ሮሜ 12፡17-21 አንብብ። ብዙ ክርስቲያኖች ይህንን ትእዛዝ የማይከተሉት ለምንድን ነው? መ) ክርስቲያኖች ብዙ ጊዜ እርስ በርስ በቀልን የሚፈላለጉት እንዴት እንደሆነ ምሳሌዎችን ስጥ። ሠ) ለእግዚአብሔር ቤተሰቦች ይህንን የማድረግ ውጤት ምንድን ነው?

መ. ምንም ምድር ያልተሰጣቸው ሌዋውያን በ12 ነገዶች የመሬት ድልድል ውስጥ ተሰራጭተው ያሉ 48 ከተሞች ተሰጧቸው። በተጨማሪ ከተሞቹን የሚከቡ ለሰብልና ለከብቶቻቸው ግጦሽ የሚሆን መሬት ተሰጣቸው።

2. ምሥራቃዊ ነገዶች ወደ አገራቸው ተመለሱ (ኢያሱ 22)። ከዮርዳኖስ በስተምሥራቅ የሚገኘውን ሥፍራ የወረሱት ነገዶች በስተምዕራብ የሚገኘውን ምድር ለመውረስ ያሉትን 9 1/2

ነገዶች ለመርዳት፥ እንደ እነርሱ ምድራቸውን እስኪወርሱ ድረስ ለመዋጋት ቃል ገብተው ነበር። ቃላቸውንም ጠብቀዋል። አብዛኛው የጦርነቱ ክፍል ተጠናቆ ስለነበር፥ ወደ ምድራቸው ለመመለስ ፈቃድ አገኙ። ወደ ስፍራቸውም ለመመለስ፥ ወደ ዮርዳኖስ ወንዝ በደረሱ ጊዜ የምሥራቁና የምዕራቡ ክልል ድንበር በሆነው ስፍራ ላይ ትልቅ መሠዊያን ሠሩ። የቀሩት እስራኤላውያን ግን፡- ይህን መሠዊያ የሠሩት 2 1/2 ነገዶች ጣዖታትን ለማምለክ ሲሉ ነው ብለው ገመቱ። ስለዚህ ቅዱስ በሆነ ቁጣ ወንድሞቻቸውን ለመውጋት ተነሡ። የትኛውም ነገድ ለዚህ ቃል ኪዳን የማይታዘዝ ቢሆን ፍርዱ የሚመጣው በሁላቸውም ላይ እንደሆነ ተገንዝበው ነበር። ነገር ግን የተሠራው መሠዊያ ዋናው ዓላማ፡- እነዚህ 2 1/2 የሚሆኑ ነገዶች የእግዚአብሔር ሕዝብ አካል ለመሆናቸው የቀሩቱ 9 1/2 ነገዶች፥ እንዲያውቁላቸው፥ለማስታወሻ የተሠራ እንጂ ለጣዖት አምልኮ እንዳልሆነ ገለጡላቸው። እነዚህ 2 1/2 ነገዶች በዮርዳኖስ ወንዝ አማካይነት ከሌሎቹ ነገዶች የተለያዩ ስለነበሩ እስራኤላውያን እንደ መሆናቸው መጠን ወደ እስራኤል ገብተው እግዚአብሔርን እንዲያመልኩ፥ እንደ ባዕዳን እንዳይቆጠሩ ቋሚ የሆነ ምልክት እንዲኖር ለማድረግ በመፈለጋቸው ነበር መሠዊያውን የሠሩት።

| 30ኛ ጥያቄ፥ እስራኤላውያን የተሳሳተ አምልኮ ወደ መካከላቸው እንዳይገባ ከነበራቸው ፍላጎት ምን እንማራለን? |
|---|

3. ኢያሱ ለእስራኤላውያን ያደረገው የስንብት ንግግር (ኢያሱ 23-24)

ኢያሱ የመሞቻው ጊዜ እንደተቃረበ በማወቁ፥ ቃል ኪዳናቸውን እንዲያድሱ የእስራኤልን ነገዶች በሙሉ በአንድነት ጠራቸው። ለእግዚአብሔር ሕግ መታዘዝ እንዳለባቸው ለሕዝቡ ለማስታወስ ፈልጎ ነበር። ሕዝቡም ቃል ኪዳናቸውን በሴሎ አደሱ። ይህ ስፍራ እስከ ዳዊት ዘመን ድረስ የእስራኤል ሕዝብ ሃይማኖታዊ ማዕከል ሆነ። የመገናኛው ድንኳን ያረፈውና እስራኤላውያን ለአምልኮ ይመጡ የነበረው ወደዚህ ስፍራ ነበር።

31ኛ ጥያቄ፡ ከመጽሐፈ ኢያሱ ጥናት ከሕይወትህ ጋር ሊታዛምድና በቤተ ክርስቲያንህ ላሉ ሰዎች ሊታስተምር የምትችላቸውን መንፈሳዊ ትምህርቶች ዘርዝር።

1. የከነዓንን ምድር ለአብርሃምና ለዘሩ ለመስጠት ቃል ኪዳን የገባው እግዚአብሔር የሰጠውን የተስፋ ቃል ኪዳን ፈጸመ፤ (ዘፍ. 12፡7፤ 15፡7፥ 18-21)። እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን በከነዓን ምድር በሚኖሩ ሰዎች ላይ ድልንና የከነዓንን ምድር ርስት አድርጎ ሰጣቸው።

እኛ አይሁድ ስላልሆንን እነርሱ ለከነዓን ምድር የነበራቸውን በስሜት የተሞላ ቅርበት ልንረዳ አንችልም። የተስፋይቱ ምድር እግዚአብሔር ከአብርሃም ጋር ደግሞም በሲና ተራራ ከገባው ቃል ኪዳን ጋር በቅርብ የተያያዘች ናት። እንዲያውም እስራኤል ከምድሪቱ ጋር ያላት ግንኙነት ለቃል ኪዳኑ ምን ያህል ታዛዥ ናት በሚለው ነገር ላይ የተመሠረተ ነበር። ለቃል ኪዳኑ አለመታዘዝ ማለት በነገሥታት ዘመን እንደሆነው ከምድሪቱ ተባርረው ይወጣሉ ማለት ነው። በንስሐ መመለስና ለቃል ኪዳኑ መታዘዝ ማለት እግዚአብሔር ወደ ሰጣቸው የተስፋ ምድር ይመለሳሉ ማለት ነው። አይሁድ በ1948 ዓ.ም. ወደ ከነዓን የመመለሳቸው ነገር እግዚአብሔር እስካሁንም ድረስ ለአይሁድ ቃል ኪዳኑን እየጠበቀ መሆኑን የሚያሳይ ምልክት ነው።

የክርስቲያን ርስት ከሚታይ መሬት ርስት ወይም ምድራዊ ተስፋ ጋር የተያያዘ አይደለም። የእኛ የተስፋ ምድር መንግሥተ ሰማያት ነው። እኛ የሰማያዊ አገር ዜጎች ነን። ቤታችን በዚያ ነው፤ የምንጓዘውም ወደዚያው ነው። አንድ ክርስቲያን ስለምድራዊ መሬት ወይም በምድር ስላለው ቤት ከሚገባ በላይ ትኩረት ሲሰጥ፥ በምድር ላይ የሚኖረው ለጊዜው እንደሆነና እውነተኛ ቤቱ በሰማይ እንዳለ ረስቷል ማለት ነው።

32ኛ ጥያቄ፥ የሚከተሉትን ጥቅሶች ተመልከት። ስለ ዘላለማዊ ቤታችን የሚናገሩት ነገር ምንድን ነው? ዮሐ. 14፡1-4፤ ዕብ. 11፡10፥ 16፤ ፊል. 3፡20።

2. የእምነት ሕይወት የጦርነት ሕይወት ነው። ድል መንሣት ያለባቸው በርካታ ጠላቶች አሉ። ለአይሁድ ጠላቶቻቸው በአካል የሚታዩ አገሮች ወይም ነገዶች ሲሆኑ፥ ሊሸነፉ ያስፈልግ ነበር። ለክርስቲያን ሦስት ጠላቶች አሉት፤ እነርሱም፡- ሰይጣን፥ የዓለም ክፉ ሥርዓትና በሁላችንም ዘንድ ያለው የቀድሞው (አሮጌው) የኃጢአት ባሕርይ ናቸው። እነዚህን ጠላቶች የምናሸንፍበት ብቸኛው መንገድ የእግዚአብሔር ኃይል ነው። ይህንን ኃይል የምናገኘው በውስጣችን እንደሚሠራ ስናምን፥ ለእግዚአብሔር ሕግጋት ስንታዘዝና በቅድስና በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ስንራመድ ነው።

እግዚአብሔር ለአይሁድ የሠራዊታቸውና የሰማይ ሠራዊትም አዛዥ እንደሆነ አስተምሮአቸዋል። ለሕዝቡ ለመዋጋት እንደተዘጋጀ መለኮታዊ ተዋጊ ሆኖ እንመለከተዋለን፤ (ኢያሱ 10፡14)። በነቢያትና በቅኔ መጻሕፍት ውስጥ ሁሉ እግዚአብሔር ታላቅ ተዋጊ ሆኖ እናየዋለን። እስራኤላውያን በእግዚአብሔር ትእዛዝ ያካሄዱት ማንኛውም ዓይነት ጦርነት ቅዱስ ጦርነት ነበር።

ክርስቲያኖች እንደመሆናችን መጠን በአካል የሚታይ ሥጋዊ ጦርነት የለብንም። ክርስቲያኖች መብታቸውን ለማግኘት ኃይልን መጠቀም ስሕተት ነው። ጦርነታችን መንፈሳዊ ነው፤ (ኤፌ. 6፡12)። ክርስቶስ እኛ ያለንበት መንፈሳዊ ጦር መሪ ነው፤ ስለዚህ ለእርሱ ትእዛዝ መገዛት አለብን። ለእርሱ በመታዘዝ በእርሱ ርዳታ ብቻ የሚያጋጥሙንን መንፈሳዊ ጠላቶች ለማሸነፍ እንደምንችል መገንዘብ አለብን።

33ኛ ጥያቄ፥ ኤፌ. 6፡12። ሀ) ጳውሎስ የሚናገረው ስለማን ነው? ለ) እነዚህን ጠላቶቻችንን የምንዋጋውና የምናሸንፈው እንዴት

ነው? ሐ) ለጦርነቱ ማረጋገጫ የሚሆኑ አንዳንድ ነገሮች ከሕይወትህ ጥቀስ።

---

3. ድል ለማግኘት በሚኖረን ብቃት ውስጥ የእግዚአብሔር ቃል ማዕከላዊ ነው። በመጽሐፈ ኢያሱ ውስጥ በእግዚአብሔር ቃል ላይ ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቷል። የእግዚአብሔርን ቃል፥ በቃል ልናጠና፥ ልንረዳውና ልንታዘዘው ያስፈልጋል፤ (ኢያሱ 1፡7-8፤ 23፡6 ተመልከት)።

4. በመንፈሳዊ ሕይወት ውስጥ ድል፥ በሦስት ነገሮች ላይ የተመረኮዘ ነው፡-

   ሀ. ነገሮችን በራሳችን ጥበብና ብርታት ከማድረግ ይልቅ ኃይል እንዲሰጠን በጌታ ላይ መታመን አለብን።

   ለ. የእግዚአብሔርን ቃል ልንረዳውና ልንታዘዘው ያስፈልጋል።

   ሐ. በእግዚአብሔር ፊት የተቀደሰ ሕይወት መኖር አለብን።

| |
|---|
| 34ኛ ጥያቄ፥ ከእነዚህ ሦስት ነገሮች ክርስቲያኖች ብዙ ጊዜ የማይጠብቋቸውና በዚህም ምክንያት በመንፈሳዊ ሕይወታቸው የሚሸነፉባቸው የትኞቹ ናቸው? |

5. እግዚአብሔር ከሁሉ የባሱ ኃጢአተኞችን ይቅር ይላል። ከዚያም በእርሱ ዕቅድ ውስጥ እጅግ ጠቃሚ ሚና እንዲጫወቱ ያደርጋል። ምንም ስፍራ የለውም የምንለው ሰው እንኳ በእግዚአብሔር ዕቅድ ውስጥ እጅግ ጠቃሚ ቦታ አለው። ረዓብ ጋለሞታና አሕዛብ ነበረች። ምንም ተስፋ የሌላት ሴት ነበረች። በእግዚአብሔር ከጥፋት ዳነች። ከይሁዳ ቤት የሆነውን ሰው አገባችና በሥጋ ኢየሱስ ከመጣበት ከዳዊት የዘር ሐረግ ውስጥ ተቆጠረች። ከአዳም ጀምሮ በአብርሃም፥ በዳዊት፥ ከዚያም በኢየሱስ ክርስቶስ የተዘረጋው የደኅንነት መስመር ውስጥ ገባች።

6. የጌታ ሠራዊት አዛዥ የነበረው ያለምንም ጥርጥር ኢየሱስ ክርስቶስ ነበር። እርሱ የነገሥታት ንጉሥ የጌቶችም ጌታ ነው። አንድ ቀን

ከሰማይ ሠራዊት ሁሉ ጋር ይገለጥና የእግዚአብሔርን ጠላቶች ሁሉ ያሸንፋል፤ (ራእይ 19፡11-21 ተመልከት)።

35ኛ ጥያቄ፥ ሀ) መጽሐፈ ኢያሱ በድል ስለመመላለስ ለማስተማር ክርስቲያኖችን እንዴት ይጠቅማቸዋል? ለ) ለቤተ ክርስቲያንህ አባሎች ይህን መጽሐፍ እንዴት እንደምታስተምር ዕቅድ አውጣ።

## 5ኛ ቀን

የዚህን ሳምንት ትምህርት ከልስና ለሳምንታዊው ስብሰባ ዝግጅት ይረዳህ ዘንድ የውይይት ጥያቄዎችን ተመልከት።

### ሳምንታዊ የስብሰባ ጊዜ

1. ሳምንታዊው የአምልኮ ጊዜ
2. ጸሎት
3. የትምህርቱ ክለሳ
4. ውይይት
    1. ሀ) የታሪክ መጻሕፍት ዋና ዓላማ ምንድን ነው? ለ) በረከቶችና ችግሮች አንዳንድ ጊዜ ለእግዚአብሔር ባለን መታዘዝና አለመታዘዝ ላይ የሚመሠረቱት እንዴት ነው? ሐ) በመታዘዛችን ምክንያት ችግሮች የሚያጋጥሙን ጊዜያት አሉን? አብራራ።
    2. ሀ) የእስራኤል ሕዝብ ታሪክ ስምንት የተለያዩ ክፍሎችን ዘርዝር። ለ) በእያንዳንዱ ክፍል ውስጥ የሚካተቱትን የብሉይ ኪዳን የታሪክ መጻሕፍት ዘርዝር።
    3. ሀ) ሦስቱን የታሪክ አመለካከቶች ግለጽ። እርስ በርሳቸው እንዴት እንደሚለያዩ ተናገር። ለ) እነዚህን አቋሞች የያዙ ሰዎችን በምሳሌነት ጥቀስ። ሐ) መጽሐፍ ቅዱሳዊ የታሪክ አመለካከት ለክርስቲያኖች ከፍተኛ ማበረታቻ የሚሰጠው እንዴት ነው?
    4. ሀ) በክርስትና እርምጃችን ውስጥ ድልን የምናገኘው እንዴት እንደሆነ የሚናገሩ አጠቃላይ የሥነ ምግባር መመሪያዎችን

ጥቀስ። ለ) የክርስቲያን ጠላቶች እነማን ናቸው? ሐ) ክርስቲያኖች ብዙ ጊዜ የሚሸነፉት እንዴት ነው? የሚሸነፉትስ ለምንድን ነው? መ) በቤተ ክርስቲያንህ የሚገኙ ክርስቲያኖችን በድል ስለ መመላለስ የምታስተምራቸው እንዴት ነው?

5. ሀ) እግዚአብሔር ከነዓናውያንን በሙሉ እንዲያጠፉ እስራኤላውያንን ያዘዘው ለምን ነበር? ለ) ይህ ስለ እግዚአብሔር ባሕርይና በኃጢአት ላይ ስላለው አመለካከት የሚያስተምረን ነገር ምንድን ነው?

6. ሀ) እስራኤል ከእግዚአብሔር ጋር የገባቸውን ቃል ኪዳን ማደስ አስፈላጊ የነበረው ለምንድን ነው? ለ) ከክርስቶስ ኢየሱስ ጋር ያለህን ግንኙነት በየጊዜው ማደስ አስፈላጊ የሆነው ለምንድን ነው? ሐ) ከዚህ ቀደም ከኢየሱስ ጋር የነበራችሁን ግንኙነት እንዴት እንዳደሳችሁ እርስ በርስ አሳብ ለአሳብ ተለዋወጡ። መ) ለእግዚአብሔር ክብርና አገልግሎት ሕይወታችሁን ሙሉ በሙሉ ለእግዚአብሔር ለመስጠት የጸሎት ጊዜ ይኑራችሁ።

5. ጸሎት

# ትምህርት 12

## 1ኛ ቀን:- የመጽሐፈ መሳፍንት መግቢያ

የመጽሐፈ ኢያሱ ታሪክ የደስታና የድል ታሪክ ነው። የእግዚአብሔር ሰዎች በእርሱ ርዳታ በቃል ኪዳኑ ተስፋ መሠረት ጠላቶቻቸውን አሸንፈው የከነዓንን ምድር ወርሰዋል። እስራኤላውያን በእነርሱና በእግዚአብሔር መካከል ለተገባው ቃል ኪዳን ለመታዘዝ የሰጡትን ቃል እንደገና አደሱ። የሚገርመው ግን የዚህ ሕዝብ ታሪክ በድል አልተደመደመም። ታሪኩ በመጽሐፈ መሳፍንት ይቀጥላል።

የመጽሐፈ መሳፍንት ታሪክ የኃዘንና የሽንፈት ታሪክ ነው። የእግዚአብሔር ሕዝብ ለእርሱ ለመታዘዝ እምቢ አሉ። ቃል ኪዳኑንም አላከበሩም፤ ስለዚህ ለቃል ኪዳኑ መታዘዝ እንዳለባቸው ለማስተማር እግዚአብሔር በጠላቶቻቸው እንዲሸነፉ ፈቀደ። እግዚአብሔር ሕዝቡን ለማስተማርና ለማስጠንቀቅ ችግርንና ሽንፈትን በመሣሪያነት ተጠቀመ። ይህም ሆኖ ግን ሕዝቡ ለእግዚአብሔር መታዘዝን አልተማሩም።

| |
|---|
| 1ኛ ጥያቄ፥ ሀ) የእግዚአብሔር ሕዝብ እግዚአብሔርን ለማክበርና ለእርሱም ለመታዘዝ የገቡትን ቃል ለመጠበቅ የሚከብዳቸው ለምንድን ነው? ለ) ብዙ ጊዜ ክርስቲያኖች ለኢየሱስ ያላቸውን የመጀመሪያ ፍቅራቸውን የሚተዉትና በመንፈሳዊ ሕይወታቸው እየቀዘቀዙ የሚሄዱት ለምንድን ነው? ሐ) ክርስቲያኖች ለእግዚአብሔር ያላቸውን ፍቅርና መታዘዝ ሕያውና ጠንካራ አድርገው እንዲጠብቁ ቤተ ክርስቲያን ምን ማድረግ ትችላለች? |
| 2ኛ ጥያቄ፥ ስለ መጽሐፈ መሳፍንት በመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት ውስጥ አንብብ። ሀ) ጸሐፊው ማን ነው? ለ) የመጽሐፉ ዓላማ ምንድን ነው? ሐ) የመጽሐፉ አስተዋጽኦ ምንድን ነው? |

### የመጽሐፈ መሳፍንት ርእስ:-

የዚህ መጽሐፍ ርእስ የተገኘው ከኢያሱ ሞት ጀምሮ እስከ መጀመሪያው የእስራኤል ንጉሥ እስከ ሳኦል ድረስ የነበሩ ጊዜያዊ የአገሪቱ መሪዎች በነበሩ ሰዎች የሥልጣን ስም ነው። እነዚህ መሪዎች መሳፍንት (ፈራጆች) ተብለው የሚጠሩ ሲሆን፥ ከአስተዳዳሪነት

ወይም ከፈራጅነት ይልቅ ሥራቸው ወደ ጦር መሪነት ያደላ ነበር። ለእስራኤላውያን ነፃነትን ለማምጣት እግዚአብሔር በግል የሚመርጣቸውና ኃይልን የሚያስታጥቃቸው ሰዎች ነበሩ። መሳፍንት የእስራኤልን ሕዝብ ከሚያስጨንቁአቸው ጠላቶቻቸው ነፃ ካወጡዋቸው በኋላ በነገዶቻቸው ላይ መጠነኛ የሆነ ሥልጣን ይኖራቸዋል። አንዳንዶቹ መሳፍንት ወይም ነፃ አውጪዎች በበርካታ ነገዶች ላይ ሥልጣን የነበራቸው ቢሆንም፥ ብዙ ጊዜ ግን በተወሰኑ ነገዶች ላይ ብቻ ሥልጣን የነበራቸው የአካባቢ መሪዎች ነበሩ።

እግዚአብሔር በሕዝቡ ሁሉ ላይ ገዥ የሚሆን መሪን ያላስነሣው ሆን ብሎ ነበር፤ ይኸውም እግዚአብሔር ራሱ ንጉሣቸው ነበርና ነው (መሳ. 8፡23)። የተለያዩት ነገዶች በእግዚአብሔር የሚገዙና በቃል ኪዳኑ ውስጥ የሚገኙ ሕግጋትን በመታዘዝ ሊኖሩ ይገባ ነበር። እግዚአብሔር ንጉሣቸው ስለነበር ንጉሥ አያስፈልጋቸውም ነበር። በኋላ በመጽሐፈ ሳሙኤል ውስጥ እንደምንመለከተው፥ እስራኤላውያን እንደ አሕዛብ ንጉሥ እንዲኖራቸው በጠየቁ ጊዜ ድርጊታቸው በእግዚአብሔር ላይ እንደሚፈጸም ዓመፅ ተቆጥሮባቸው ነበር (1ኛ ሳሙ. 8፡5-8)።

| |
|---|
| 3ኛ ጥያቄ፥ ሀ) ይህ ከእግዚአብሔርና ከመንግሥት ባለ ሥልጣናት ጋር ከሚኖረን ግንኙነት ጋር የሚመሳሰለው እንዴት ነው? ለ) የሚለየውስ እንዴት ነው? |

## የመጽሐፈ መሳፍንት ጸሐፊ

የመጽሐፈ መሳፍንት ጸሐፊ ማን እንደሆነና እነዚህ የተለያዩ ተግባራትን አሰባስቦ በአንድ ላይ ያቀናበራቸው ማን እንደሆነ የሚያመለክት ነገር በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አናገኝም። ዓለማውያን ምሁራን መጽሐፉ የተጻፈበትን ጊዜ በማዘግየት በዚህ መልክ የጻፈው አሪት ዘዳግምን የጻፈውና ከኢያሱ እስከ 2ኛ ነገሥት ያለውን የታሪክ ዘገባ ያቀናበረው ሰው ነው ይላሉ። ሆኖም ለዚህ ሁሉ አንዳችም ማረጋገጫ የለም።

አይሁድ ጸሐፊው ሳሙኤል ነው ብለው ያምናሉ። ይሁን እንጂ ይህን በሚመለከት ማረጋገጫ የለንም። በዘመነ መሳፍንት የተለያዩ

መሳፍንትን በሚመለከት አጫጭር ታሪኮች ሳይጻፉ አልቀሩም። በኋላ አንድ ጸሐፊ፥ ምናልባትም ሳሙኤል እነዚህን ታሪኮች ሰብስቦ በአንድ መጽሐፍ አቀነባብሮአቸው ይሆናል። 1ኛ ዜና 29፡29 እንደሚናገረው ሳሙኤል፥ ናታንና ጋድ የተባሉት ነቢያት የተለያዩ ታሪኮችን ዘግበዋል። ከብሉይ ኪዳን ጥናት እንደምንረዳው በዚሁ ጊዜ የተጻፉ ሌሎች መጻሕፍትም ነበሩ። ለምሳሌ፥ የያሻር መጽሐፍ (ኢያሱ 10፡13)፥ የእስራኤል ነገሥታት ታሪክ መጽሐፍ (2ኛ ነገ. 15፡31) እና የይሁዳ ነገሥታት ታሪክ መጽሐፍ (2ኛ ነገ. 16፡19) ይገኛሉ። እንደዚሁም በመሳፍንት መጻሕፍት ውስጥ ንጉሥ አልነበረም የሚለው ቃል ተደጋግሞ መጠቀስ የሚያመለክተን መጽሐፈ መሳፍንት ተቀናብሮ በተጻፈበት ጊዜ በእርግጥም በእስራኤል ላይ የነገሡ ነገሥታት መኖራቸው ነው።

መጽሐፈ መሳፍንትን ማን እንደጻፈው ለመናገር አስቸጋሪ ቢሆንም የተጻፈው ግን በ1000 ዓ.ዓ. ገደማ በዳዊት ዘመን እንደነበር መገመት ይቻላል።

## የመጽሐፈ መሳፍንት ታሪካዊ ሥረ - መሠረት

ባለፈው ሳምንት የጸለስጢና ምድር የተለያዩ ትላልቅ መንግሥታት የጦርነት ሜዳ እንደነበረች ተመልክተናል። የከነዓን ምድር ከእነዚህ ትላልቅ መንግሥታት ጋር ከሚተባበሩ ከተለያዩ የከተማ መንግሥታት የተዋቀረች ነበረች። በደቡብ በኩል የሚገኘው ትልቁ መንግሥት ግብፅ ነበር። በሰሜን በኩል በኢያሱና በመሳፍንት ዘመን የነበረው ትልቅ መንግሥት የኬጢያውያን መንግሥት ነበር። እነዚህ ትላልቅ መንግሥታት በጸለስጢና ውስጥ ብዙ ጊዜ ጦርነት ይገጥሙ የነበሩ ቢሆንም፥ ይህ ጦርነት እስራኤላውያንን በከፍተኛ ሁኔታ መንካቱ አጠራጣሪ ነው። እስራኤላውያን የሚኖሩት በተራራማዎቹ ስፍራዎች ነበር እንጂ ከዋናዎቹ የንግድ መተላለፊያዎች አጠገብ አልነበረም። በአብዛኛው መሳፍንት ግብፃውያንም ሆኑ ኬጢያውያን አንዱ ሌላውን ለማሸነፍ አልቻሉም ነበር፤ ስለዚህ ከነዓን በየትኛውም መንግሥት ቀጥተኛ በበላይ ተቆጣጣሪነት ሥር አልነበረችም። በዚህም ምክንያት ብዙ ትናንሽ መንግሥታት ከነዓንን ለመቆጣጠር ወይም ለመውረርና አደጋ ለመጣል ይሞክሩ ነበር። ይህ በከነዓን ምድር ላይ የተደረገ ጦርነት በውጤቱ የተለያዩ ሕዝቦች እስራኤላውያንን ለመቆጣጠርና

ለመግዛት እንደቻሉ በሚያንፀባርቅ መንገድ በመጽሐፈ መሳፍንት ተገልጧል። ከኢያሱ ሞት ጀምሮ ሳኦል እስከ ነገሠበት ጊዜ ድረስ የነበረው ሁኔታ የተለያዩ መንግሥታት እስራኤልን ያጠቁበትና የጨቆኑበት ዘመን ነበር። በእነዚህ ዓመታት ነበር የባሕር ሕዝቦች ወይም በመጽሐፍ ቅዱስ ፍልስጥኤማውያን በመባል የሚታወቁ አዲስ ነገዶች ወደ ከነዓን የባሕር ዳርቻ ተሰደው የመጡት። ወዲያውኑ አብዛኛውን የከነዓንን ምድር ተቆጣጠሩና ለብዙ ዓመታት የአይሁድ ሕዝብ ዋና ጠላት ሆኑ።

የእስራኤል ሕዝብ የተለያዩ ነገዶች በየራሳቸው ክልል መኖር ከጀመሩ ወዲህ የሕዝቡ አንድነት እየቀነሰ መጣ። በአንድነት እንዲቆዩ የሚያደርግ እንደ ሙሴ ወይም እንደ ኢያሱ ያለ ጠንካራ መሪ አልተገኘም፤ ስለዚህ ጎሰኝነት ወይም የዘር ልዩነት እየጠነከረ መጣና ነገዶቹ በየራሳቸው ሽማግሌዎች ወይም የነገድ አለቆች መተዳደር ጀመሩ። 12ቱን ነገዶች እጅግ በላላ መንገድ (ፌዴራላዊ አስተዳደር) እንዲቆዩ ያደረጉ ሁለት ነገሮች ነበሩ። የመጀመሪያው፥ለእግዚአብሔር የሚያቀርቡት የጋራ የሆነ አምልኮአቸው ነበር። የከነዓናውያንን አማልክት ሳይሆን እግዚአብሔርን እስካመለኩ ድረስ የተባበሩ ነበሩ። የእውነተኛውን አምላክ አምልኮ በሚተዉበት ጊዜ የጋራ የሆነ ሃይማኖት አይኖራቸውም ነበር። ሁለተኛው፥ ሁሉም የያዕቆብ ልጆች መሆናቸውና ይኸውም የጋራ ውርስ መያዛቸው ነበር፤ ስለሆነም አንድ ነገድ በውጫዊ ጠላት በሚጠቃበት ጊዜ ሌሎቹ ነገዶች ለእርዳታ መድረሳቸው የተለመደ ነበር፤ ነገር ግን ብዙ ጊዜ ይህንን አንድነት በሚረሱበት ጊዜ በ12ቱ ነገዶች መካከል የሚደረግ ጦርነትም የተለመደ ነበር።

የመጽሐፈ መሳፍንት ጸሐፊ ስለ ዘመኑ መሳፍንት ዝርዝር የሆነ መግለጫ የመስጠት አሳብ አልነበረውም። ለምሳሌ:- በግብፃውያንና በኬጢያውያን መካከል ስለተደረገ ጦርነት የሚጠቅሰው አንዳችም ነገር የለም። የጸሐፊው ዋና አሳብ በዚህ ዘመን ይኖሩ በነበሩ አይሁዳውያን ላይ ለደረሰው ከፍተኛ ችግር የሥነ - መለኮታዊ ትምህርት ትንተና መስጠት ነበር። የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ትኩረት በቀድሞ ዘመናት

ሁኔታ ላይ ሰፊ ገለጻ መስጠት ሳይሆን የአይሁድ መጨቆን ለምን እንደሆነ መናገር ነበር።

## የዘመነ መሳፍንት የጊዜ ቅደም ተከተል

የመጽሐፈ መሳፍትን የጊዜ ቅደም ተከተልን በተመለከተ ብዙ ክርክርና ጥርጣሬ አለ። ይህም በሁለት ዋና ዋና ምክንያቶች ነው። የመጀመሪያው፥ የእስራኤል ሕዝብ ነፃ የወጡበትና ከነዓንን የወረሱበት ጊዜ ጉዳይ በሊቃውንቱ ዘንድ አከራካሪ መሆኑ ነው። ይህ ነገር የሆነው በ15ኛው ክፍለ ዘመን (1400 ዓ.ዓ.)? ነው ወይስ በ13ኛው ክፍል ዘመን (በ1280 ዓ.ዓ.)? ወግ አጥባቂ የሆኑ ምሁራን፥ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኘው መረጃ የሚስማማው ለ15ኛው ክፍለ ዘመን ቀረብ ላለው ጊዜ ነው ወደ ማለት ያዘነብላሉ።

ሁለተኛው ጥያቄ፥ መሳፍንት የገዙት በአንድ ጊዜ ነው ወይስ በተከታታይ? የሚለው ነው። እያንዳንዱ መስፍን የገዛበትን ጊዜ በተናጠል ወስደን ከደመርነው አጠቃላዩ 410 ዓመታት ይመጣል። ሁሉም ምሁራን እንደሚስማሙበት ከሆነ ይህ ጊዜ ለዘመነ መሳፍንት እጅግ ብዙ ነው፤ ስለዚህ እነዚህ የመሳፍንትን ዘመን የምናይባቸው ሁለት አማራጮች አሉን። የመጀመሪያው፥ የእስራኤል ሕዝብ ነፃ የወጡበትና ሰዎች ማስታወስ ይችሉ ዘንድ ቀላል ለማድረግ የተሰጠ አጠቃላይ ጊዜ ተደርጎ የተሰጠ ነው የሚል ሲሆን፥ ሁለተኛው ግን፥ አንዳንዶቹ መሳፍንት ሌሎቹ መሳፍንት በሌላ ስፍራ በገዙበት ጊዜ የነበሩ የአንድ የተወሰነ ክልል ገዥዎች ነበሩ የሚል ነው። ለምሳሌ፡- ሰሜጋር፥ ቶላ፥ ያጢር፥ ኢብሃን፥ ኤሎንና አብዶን ሌሎች መሳፍንት በሚገዙበት ጊዜ የተነሡ የአንድ ክልል መሪዎች ነበሩ፤ ስለዚህ የመሳፍንት የጊዜ ቅደም ተከተል በቀረው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ካለው የጊዜ ቅደም ተከተል ጋር የሚስማማ ነው።

ዘመነ መሳፍንት ከ (1380-1050) ዓ.ዓ. ድረስ 300 ዓመታት ያህል የፈጀ ሳይሆን አይቀርም።

ቀጥሎ ለዘመነ መሳፍንት የተሰጠ የጊዜ ቅደም ተከተል እናገኛለን፡-

| | |
|---|---|
| 1. ኢያሱ | 1406-1376 ዓ.ዓ. ዓ.ዓ |
| 2. የሽማግሌዎች አገዛዝ | 1376-1366 ዓ.ዓ |

3. የመስጴጦምያ የጭቆና ዘመን 1366-1358 ዓ.ዓ.

4. የጎቶንያል አገዛዝ የ40 ዓመት ሰላም 1358-1318 ዓ.ዓ.

5. በሞዓብ የመጨቆን ዘመን 1318-1301 ዓ.ዓ.

6. የናዖድ አገዛዝና የ80 ዓመት ሰላም 1301-1221 ዓ.ዓ.

7. በከነዓናውያን የመጨቆን ዘመን 1221-1201 ዓ.ዓ.

8. የዲቦራና የባርቅ አገዛዝ የ40 ዓመት ሰላም 1201-1161 ዓ.ዓ.

9. በምድያን የመጨቆን ዘመን 1161-1154 ዓ.ዓ.

10. የጌዴዎን አገዛዝና የ40 ዓመት ሰላም 1154-1114 ዓ.ዓ.

11. የአቤሜሌክ- የ3 ዓመታት ንጉሥ 1114-1111 ዓ.ዓ.

12. የዮፍታሔ አገዛዝ -6 ዓመት 1111-1105 ዓ.ዓ.

. የሶምሶን አገዛዝ - 20 ዓመት

13. የዔሊ አገዛዝ 1066-1046 ዓ.ዓ.

14. የሳሙኤል አገዛዝ 1046-1026 ዓ.ዓ.

15. የሳኦል አገዛዝ 1026-1011 ዓ.ዓ.

** እነዚህ ጊዜያት በጣም ያልተረጋገጡ እንደሆኑና የተለያዩ ምሁራን መሳፍንት የገዙበት ዘመን ብለው የሚሰጡት ጊዜ የተለያየ መሆኑን ማስታወስ አስፈላጊ ነው።

## የመጽሐፈ መሳፍንት አወቃቀርና አስተዋጽኦ

መጽሐፈ መሳፍንት ሦስት ዋና ዋና ክፍሎች አሉት፡-

1. የዘመነ መሳፍንት መግቢያ (1፡1-3፡6)

2. የገዙ የተለያዩ መሳፍንት (3፡7-16፡31)

3. የዘመነ መሳፍንት አጠቃላይ የሥነ - ምግባር ባሕርያት (17-21)

የሚከተለው ጠለቅ ተደርጎ የተዘረዘረ የመጽሐፈ መሳፍንት አስተዋጽኦ ነው፡-

1. የመጽሐፈ መሳፍንት መግቢያ (1፡1-3፡6)

ሀ. የእስራኤላውያን ከነዓናውያንን የማስወጣት ተግባራቸውን በሚገባ አለማከናወን (1፡1-2፡5)

ለ. የእስራኤል የክሕደት ዑደት መግቢያ (2፡6-3፡6)

2. ስድስቱ የእስራኤላውያን የክሕደት ዑደቶች «የእስራኤል ልጆች በእግዚአብሔር ፊት እንደገና ክፉ ሥራ ሠሩ» (3፡7-16፡31)።

ሀ. ጎቶንያል (3፡7-11)

ለ. ናዖድ (3፡12-31)

ሐ. ዲቦራና ባርቅ (4-5)

መ. ጌዴዎን (6-8)

1)አቤሜሌክ (9)

2) ቶላዕና ኢያዕር (10፡1-5)

ሠ. ዮፍታሔ (10፡6-12፡7)

1) ኢብጻን (12፡8-10)

2) ኤሎም (12፡11-12)

3) ዓብዶን (12፡13-15)

ረ. ሶምሶን (13-16)

3. እስራኤላውያን በዘመነ መሳፍንት ያሳዩት የሥነ - ምግባር ብልሹነት፡- «ሰውም ሁሉ በፊቱ መልካም መስሎ የታየውን ያደርግ ነበር» (17-21)።

ሀ. የዳን ነገድ ታሪክ (17-18)

ለ. የብንያም ነገድ ታሪክ (19-21)

## የመጽሐፈ መሳፍንት ዓላማ

እስራኤል በጠላቶችዋ ለምን ተሸነፈች? ያለማቋረጥ በባርነት ውስጥ የሆነችውስ ለምንድን ነው? እስራኤላውያን እግዚአብሔር የሰጣቸውን የተስፋ ቃል ኪዳን በረከት ያልተለማመዱት ለምንድን ነው? እግዚአብሔር ሊያድናቸው ስላልቻለ ነውን? የከነዓናውያንና የአሕዛብ አማልክት ብርቱ ስለሆኑ ነውን?

የመጽሐፈ መሳፍንት ጸሐፊ ለመመለስ የሚሞክራቸው ጥያቄዎች እነዚህ ናቸው። የመጽሐፈ መሳፍንት ጸሐፊ እስራኤላውያን ያ ሁሉ ሥቃይ የደረሰባቸው ለምን እንደሆነ ሊገልጣቸው ይፈልግ ነበር። በመጽሐፈ መሳፍንት ውስጥ እስራኤላውያን ለምን እንደተሸነፉና በመከራ ውስጥ እንደተዘፈቁ የሚያሳዩ ሁለት ምክንያቶች ተሰውረው እናገኛለን:-

1. እስራኤላውያን ብዙ መከራና ችግር የደረሰባቸው ለእግዚአብሔር ቃል ኪዳን በታዛዥነት ስላልኖሩ ነው። እግዚአብሔር እንዳልተጠነቀቀላቸው በማሰብ እርሱን ከመውቀስ ይልቅ፥ እስራኤላውያን ለወደቁበት አስጊ ሁኔታ ራሳቸውን ብቻ መውቀስ ነበረባቸው። እውነተኛ ንጉሣቸውን እግዚአብሔርን ትተው፥ የከነዓናውያንን አማልክት፥ ሥነ - ምግባራት፥ ሃይማኖታዊ ጉዳዮችና የአኗኗር ዘይቤዎች ስለተከተሉ እግዚአብሔር እየቀጣቸው ነበር። በኦሪት ዘዳግም እንደተጠቀሰው፥ ለእግዚአብሔር አለመታዘዝ ከእግዚአብሔር ዘንድ ፍርድን አስከተለባቸው። በመጽሐፈ መሳፍንት ውስጥ በተደጋጋሚ እንደምናነበው «የእስራኤል ልጆች በእግዚአብሔር ፊት ክፉ ነገርን አደረጉ» (መሳ. 2፡11፤ 3፡7፥ 12፤ 4፡1 ወዘተ.)። በመጽሐፈ መሳፍንት የሚገኙት የመጨረሻዎቹ ሁለት ታሪኮች የሚያሳዩት የእግዚአብሔር ሰዎች ምን ያህል ከፍተው እንደነበር ነው።

የሚያሳዝነው የእግዚአብሔር ሕዝብ በታሪክ ሁሉ በፊቱ የተቀደሰ ኑሮ ከመኖር ወደኋላ ማለታቸው ነው። በዚህ ፈንታ ዓለምን መሰሉ። ውጤቱም በራሳቸው ላይ የእግዚአብሔርን ፍርድ ማስከተል ሆነ። እግዚአብሔር በረከቱን ከእነርሱ ወሰደ። ወደ እግዚአብሔር መመለስን እምቢ ሲሉ፥ እግዚአብሔር ለምርኮ አሳልፎ ይሰጣቸውና በዓለም

እንዲሸነፉ ያደርግ ነበር። ይህም ሆኖ ሳይመለሱ ሲቀሩ፥ እግዚአብሔር ይተዋቸው ነበር። በትንቢተ ሕዝቅኤል የእግዚአብሔር ክብር ኢየሩሳሌምንና ቤተ መቅደሱን እንዴት እንደተወ እናነባለን (ሕዝ. 10፡ 11፡23)። በአዲስ ኪዳን በጳውሎስ ከተጀመሩት አብዛኛዎቹ አብያተ ክርስቲያናት ቅድስናቸውን ስላጡ በመጨረሻ ተደመሰሱ ወይም ወደ መስጊድነት ተለወጡ፤ ስለዚህ አሁንም ቢሆን ያለማቋረጥ እርሱን ከተውንና እንደ ዓለም መኖር ከጀመርን እግዚአብሔር እኛንም ይተወናል።

4ኛ ጥያቄ፥ ሀ) ዛሬም ቢሆን ዓለምን የመምሰል አዝማሚያ በአብያተ ክርስቲያኖቻችን ውስጥ የሚታየው እንዴት ነው? ለ) በዘመነ መሳፍንት ከነበረው የእስራኤላውያን ታሪክ እንደ ማስጠንቀቂያ ልንወስደው የሚገባን ነገር ምንድን ነው? ሐ) እኛ ክርስቲያኖች ዓለምን መምሰል እንደሌለብን ለማስተማር መጽሐፈ መሳፍንትን እንዴት ልንጠቀምበት እንችላለን?

2. እስራኤላውያን ከፍተኛ መከራና ችግር የደረሰባቸው ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸውን ቃል ኪዳን ይጠብቁ ዘንድ የሚያስችላቸው ብቁ መሪ ስላላገኙ ነው። በመጽሐፈ መሳፍንት ኋለኛ ክፍል እንዲህ የሚል ቃል እናገኛለን፡- «በዚያም ዘመን ከእስራኤል ዘንድ ንጉሥ አልነበረም፤ ሰው ሁሉ በፊቱ መልካም መስሎ የታየውን ያደርግ ነበር» (መሳ. 21፡25)። እንደ ጸሐፊው አመለካከት፥ የእግዚአብሔር ሕዝብ የተሸነፉበትና በኃጢአት የወደቁበት አንዱ ምክንያት ጠንካራ መሪ ወይም የሚመራቸው ንጉሥ ስላልነበራቸው ነው። ከእግዚአብሔር ጋር የነበራቸውን የቃል ኪዳን ግንኙነት ለመጠበቅ የነገድ አመራር በቂ አልነበረም። መጽሐፈ መሳፍንት የተጻፈው ምናልባት በዳዊት ጊዜ ስለሆነ፥ ጸሐፊው እግዚአብሔርን የሚፈራ ጠንካራ መሪ፥ ሕዝቡ ለእግዚአብሔር ታማኝ ሆኖ ይኖር ዘንድ የሚጫወተውን ከፍተኛ ሚናና የሚሰጠውን ጥቅም ታላቅነት ተመልክቶ ይሆናል። ከኋለኛው ታሪክ እንደምንገነዘበው፥ ንጉሥ እግዚአብሔርን የሚፈራ ካልሆነ ሕዝቡ ወዲያውኑ እግዚአብሔርን ይተዋሉ። መጽሐፈ ነገሥት የሚያሳየን እስራኤል ነገሥታትን ማግኘቷ ብቻ

ቃል ኪዳንን ለመጠበቅና ከእግዚአብሔር ፍርድ ለማምለጥ በቂ እንዳልሆነ ነው።

የእስራኤል ዋና ችግር ለሰማያዊ ንጉሥዋ አለመታዘዝዋ ነው። ምድራዊው ንጉሥ እግዚአብሔርን የሚፈራ ከሆነ፥ ሕዝቡ ለቃል ኪዳኑ ታዛዥ ሆኖ እንዲኖር ይረዳል። ንጉሡ ታዛዥ ባይሆንም እንኳ፥ እስራኤላውያን ለሰማያዊ ንጉሣቸው መታዘዛቸውን መቀጠል ነበረባቸው፤ ነገር ግን ልክ በመሳፍንት ዘመን እንደ ነበረው ፈጥነው በኃጢአት ይወድቁ ነበር።

| |
|---|
| 5ኛ ጥያቄ፥ ሀ) ሕዝቡ ለእግዚአብሔር እየታዘዙ እንዲኖሩ እግዚአብሔርን ስለሚፈራ መሪ አስፈላጊነት ይህ ምን ያስተምረናል? ለ) መሪው ወደየትኛውም አቅጣጫ ቢመራ፥ እያንዳንዱ ክርስቲያን ግን የግል ግንኙነቱን ከእግዚአብሔር ጋር መጠበቅ እንዳለበት ይህ ምን ያስተምረናል? |

መጽሐፈ መሳፍንት የሚያስተምረን የእግዚአብሔር ሰዎች በትእዛዙ በማይመላለሱበት ጊዜ፥ ፍርድን ብቻ ሳይሆን፥ ጥፋትንም ጭምር በራሳቸው ላይ እንደሚያመጡ ነው። ከመሳፍንት 17-21 ያለው ክፍል ዋና ትምህርት ለቃል ኪዳኑ አለመታዘዝ በሚኖርበት ጊዜ ሕዝቡ እግዚአብሔርን በመተው ሐሰተኛ አማልክትን እንደሚያመልኩ ነው። እግዚአብሔርን በሚተዉበት ጊዜ የቅን ፍርድ ጉድለትና የእርስ በርስ መጠፋፋት ይከሰታል። ፈሪሀ እግዚአብሔር በማይኖርበት ስፍራ፥ ፍትሐዊ ሕግጋት አይኖሩም፤ ውጤቱም የሕዝቡ ሁሉ መሠቃየት ነው። የመጽሐፍ ቅዱስ መመሪያዎች በሕጎቻቸው ውስጥ እንዲሠሩ ያልፈቀዱ ሕዝቦች ያጋጠሟቸው መቅሠፍት፥ የፍርድ መዛባት፥ ጉቦኝነት፥ ጦርነትና የመሳሰሉት ነገሮች ናቸው።

6ኛ ጥያቄ፥ ይህ በኢትዮጵያ እውነት መሆኑን እንዴት አየህ?

በመጽሐፈ መሳፍንት ውስጥ ሁለት ዋና ዋና የእግዚአብሔር ሥዕላዊ ሁኔታ እናያለን። የመጀመሪያው፥ የእግዚአብሔር የሥነ - ሥርዓት እርምጃ ነው። ሕዝቡ በኃጢአት በሚወድቁበት ጊዜ እግዚአብሔር አስቸጋሪ ነገሮችን ወደ ሕይወታቸው በማምጣት ሥነ

ሥርዓትን (ዲሲፕሊንን) ያስተምራቸው ነበር። የእግዚአብሔር ፍላጎት ሊያጠፋቸው አልነበረም፤ ነገር ግን ሕዝቡ ከኃጢአት እንዲርቁና እግዚአብሔርን በሚያስከብር መንገድ ለሕዝቡ ሁሉ የሚጠቅም ኑሮ እንዲኖሩ ነበር፤ (ዕብ. 12፡4-11 ተመልከት)።

በሁለተኛ ደረጃ በምሕረት የተሞላውን የታጋሹን የእግዚአብሔር ሥዕላዊ ሁኔታ እናያለን። እግዚአብሔር ሕዝቡ በሚተዉት ጊዜ በጽድቅ በመፍረድ ወዲያውኑ ሊቀጣቸው ይችል ነበር። ይህንንም ቢያደርግ ፍጹም ትክክል ነበር። ነገር ግን እግዚአብሔር ለብዙ መቶ ዓመታት በትዕግሥት በመሥራት ይቅርታውንና በሕይወታቸው ላይ የሚደርሰውን ችግር ልባቸውን ወደ እርሱ ለመመለስ ይጠቀሙበት ዘንድ ሞከሮ ነበር። እግዚአብሔር ሕዝቡ ታማኝ ባልሆኑበት ጊዜ እንኳ ለእነርሱ ታማኝ ነበር። ወደ እርሱ በጮኹ ጊዜ ጸሎታቸውን በመመለስ፥ እነርሱን ከባርነት ነፃ ለማድረግ የሚያስፈልገውን ያደርግ ነበር። እግዚአብሔር በምሕረቱ ነቢያትን እየላከ ያስጠንቅቃቸውና ነፃ ለማውጣት መሳፍንትን ያስነሣላቸው ነበር።

| |
|---|
| 7ኛ ጥያቄ፥ ሀ) እግዚአብሔር በአሁኑ ዘመንም ምሕረቱንና ትዕግሥቱን እያሳየን ያለው እንዴት ነው? ለ) የእግዚአብሔር ምሕረት በሕይወትህ የታየው እንዴት ነው? ሐ) ለአንተ ስላለው ትዕግሥት፥ ምሕረትና ጸጋ እግዚአብሔርን አመስግነው። |

## 2ኛ ቀን:- መሳፍንት 1-16

ብዙ ጊዜ የቤተ ክርስቲያን ችግር በእግዚአብሔር ላይ የሚደረግ ግልጥ ዓመፅ ሳይሆን ለእግዚአብሔር ሙሉ ለሙሉ አለመታዘዝ ነው። እግዚአብሔርን ሙሉ ለሙሉ አላመልክም ማለት ሳይሆን፤ ነገር ግን ለእግዚአብሔር ፈቃድ በከፊል ብቻ መታዘዝ የእግዚአብሔር ሕዝብ ችግር ነው።

| |
|---|
| 8ኛ ጥያቄ፥ በቤተ ክርስቲያን ወይም በራስህ ሕይወት ውስጥ ይህ ነገር እውነት መሆኑን ያየኸው እንዴት ነው? ምሳሌዎችን ስጥ። |

ለእግዚአብሔር በከፊል መታዘዝ፥ ቆይቶ ወዳለመታዘዝ ያመራል። እግዚአብሔር ልንከተለው የሚገባንን ትእዛዝ ወይም ልናደርገው

የሚያስፈልግ ነገር ሲሰጠንና ያንንም በከፊል ብቻ ስንከተል መንፈሳዊ ውድቀት በሕይወታችን ይጀምራል። በቤተ ክርስቲያንም ተመሳሳይ ነገር ይከሰታል። በከፊል መታዘዝ ከዓለም ጋር ጓደኝነት ወደ መፍጠር ነው የሚመራው። ቤተ ክርስቲያንም ሆነች ክርስቲያን በግሉ ዓለምን መምሰል ይጀምራል! ክርስቲያን ወይም ቤተ ክርስቲያን የሥነ ምግባር ንጽሕናቸውንና ልዩ መሆናቸውን እያጡ ይሄዳሉ። ይህም ነገር ወዲያውኑ ዓለምንና ቤተ ክርስቲያንን ወደ ቅልቅል አምልኮ ይመራል። በመጨረሻም እግዚአብሔርን ሙሉ ለሙሉ ወደ መካድና ወንጌልን ወደ መቃወም ያደርሳል።

መጽሐፈ መሳፍንት እስራኤላውያን ለእግዚአብሔር እንዴት ሙሉ በሙሉ እንዳልታዘዙና እርሱ እንዳዘዘውም ከነዓናውያንን እንዳላባረሩ ያሳየናል። ስለሆነም እግዚአብሔርን የመቃወም ሂደታቸው ተጀመረ። በመጀመሪያ፥ እንደ ከነዓናውያን ማምለክ ጀመሩ። ይህም የእግዚአብሔርን ሕዝብ ወደ ከፍተኛ የሥነ - ምግባር ድቀት መራቸው። ወዲያውኑ ከነዓናውያን ይጨቁኗቸው ጀመር። እግዚአብሔር የእርሱ ወደሆነው ንጹሕ አምልኮ ሊመራቸው ጠላቶቻቸውን ድል ይነሡ ዘንድ ፈቀደ። ይህ ነገር ለጊዜው የሠራ ቢሆንም እንኳ እያንዳንዱ ተከታታይ ትውልድ እግዚአብሔርን በመተው እግዚአብሔር የሥነ -ሥርዓት እርምጃ ይወስድበት ጀመር።

| |
|---|
| 9ኛ ጥያቄ፥ መሳ. 1-16 አንብብ። ሀ) እስራኤላውያን ለእግዚአብሔር ያልታዘዙት እንዴት ነው? ለ) ሕዝቡ ባለመታዘዛቸው ምክንያት የጌታ መልአክ ያዘዘባቸው ፍርድ ምን ነበር? ሐ) በመሳ. 2፡10-19 የምታየውን የክሕደትን ዑደት፥ ፍርድና ነፃ መውጣት ግለጥ። መ) ከመሳፍንት 1-16 የእስራኤልን ሕዝብ ያሸነፉ ጠላቶችና በእነዚህ ጠላቶች ላይ ድልን ይሰጣቸው ዘንድ እግዚአብሔር ያስነሣቸውን መሳፍንት ዘርዝር። ሠ) መንፈስ ወረደባቸው ተብሎ የተጻፈላቸውን ሰዎች ዘርዝር። |

1. የዘመነ መሳፍንት መግቢያ (መሳ. 1-3፡6)።

### ሀ. እግዚአብሔር እስራኤላውያንን በጠላቶቻቸው ሁሉ ላይ ድልን እንዴት እንደሰጣቸው ለማሳየት የቀረቡ ምሳሌዎች (መሳ. 1፡1-18)

አይሁዳውያን ጠላቶቻቸውን ለማሸነፍና ከምድሪቱ ለማባረር ያልቻሉበት ምክንያት ምንድን ነው? ኃይል ስላነሳቸው ነውን? ወይስ በጌታ ርዳታ ሊያባርሩአቸው ስላልሞከሩ ነው? ወይስ የጌታን ትእዛዝ በከፊል ብቻ በመታዘዝ ስለበደሉ? ወይስ እግዚአብሔር በከነዓናውያን ላይ ድልን እንደሚሰጣቸው የገባውን ተስፋ ስላጠፈ ነው?

በዚህ ክፍል የመጽሐፈ መሳፍንት ጸሐፊ ሊያሳየን የፈለገው፥ እግዚአብሔር ከእነርሱ ጋር ስለ ነበር አይሁድን ለመቋቋም የቻለ ማንም ሰው እንዳልነበረ ነው። በይሁዳና በከነዓናውያን መካከል የተደረገውን ጦርነት በምሳሌነት በማቅረብ፥ አይሁድ በቀላሉ እንዴት ሊያጠፏቸው እንደቻሉ ያሳየናል። እንዲሁም አንድ ሰው በእግዚአብሔር እርዳታ አንድን ከተማ እንዴት እንዳሸነፈ አሳይቷል። የካሌብ ልጅ የሆነው የናትናኤል ታሪክ እግዚአብሔር ጠላቶቻቸውን ሁሉ ያሸንፉ ዘንድ ለማድረግ ፈቃደኛ እንደ ነበር የሚያሳይ ማረጋገጫ ነው።

### ለ. አይሁድ ከነዓናውያንን ለማሸነፍና ለማጥፋት አልቻሉም ነበር (መሳ. 1፡18-36)

አይሁድ ከነዓናውያንን ሊያሸንፉ ያልቻሉበትን ምክንያት በእግዚአብሔር ላይ ከማሳበብ ይልቅ እራሳቸው እግዚአብሔርን ሙሉ በሙሉ ለመታዘዝ አለመቻላቸው እንደሆነ መገንዘብ ነበረባቸው። ከእስራኤል ነገዶች ማናቸውም ቢሆኑ ለእግዚአብሔር ሙሉ በሙሉ ለመታዘዝ አልቻሉም ነበር፤ ስለዚህ በእያንዳንዱ ነገድ አካባቢ ያልተሸነፉና ያልጠፉ የከነዓናውያን ከተሞች ነበሩ።

### ሐ. ሕዝቡ ሙሉ በሙሉ ባለመታዘዛቸው ምክንያት እግዚአብሔር ያመጣው ፍርድ (መሳ. 1፡1-5)

አንድ ቀን እግዚአብሔር በእስራኤላውያን ላይ ለመፍረድ ተነሣ። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑ የሚታመነው የእግዚአብሔር መልአክ

መጥቶ ባለመታዘዛቸው ምክንያት ከነዓናውያንን ከእንግዲህ ማሸነፍ እንደማይችሉ ነገራቸው። ከነዓናውያንንና የአምልኮ ስፍራቸውን በሙሉ ስላላጠፉ፥ ከእንግዲህ እግዚአብሔር በከነዓናውያን ላይ ሙሉ ድልን እንደማይሰጣቸው ነገራቸው።

**10ኛ ጥያቄ፥ ለእግዚአብሔር ሙሉ በሙሉ መታዘዝ እንዳለብን ይህ ነገር ብርቱ ማስጠንቀቂያ እንዴት ይሆነናል?**

ለእግዚአብሔር በከፊል መታዘዝ ሙሉ በሙሉ አለመታዘዝ ነው። ያልታዘዝናቸው አንዳንድ ነገሮች መኖራቸውን እያወቅን፥ ለእግዚአብሔር በታዘዝንባቸው ነገሮች መመካት አንዳችም ረብ የለውም። በከፊል መታዘዝ አለመታዘዝ ስለሆነ፥ በእኛ ላይ የእግዚአብሔርን ፍርድ ያመጣል።


### መ. የክሕደት፥ የፍርድና ነፃ የመውጣት ዑደት (መሳ. 2፡6-3፡6)

በመሳፍንት 3፡1-6 ከነዓናውያን ሙሉ በሙሉ እንዲጠፉ እግዚአብሔር ያልፈቀደበትን ሌላ ምክንያት እናገኛለን። እግዚአብሔር የሚቀጥለው የእስራኤል ትውልድ ለቃል ኪዳኑ ይታዘዝና ይከተለው ወይም አይከተለው እንደሆነ ለመፈተን ይህንን ሕዝብ ሊጠቀምበት ፈለገ። የሚያሳዝነው፥ እያንዳንዱ ትውልድ ዓለምን (ከነዓናውያንን) ወደ መምሰል አዘነበለ፤ በአምልኮውና በሥነ ምግባሩም የተበላሸ ሆነ።

**11ኛ ጥያቄ፥ ሀ) ዛሬም እግዚአብሔር ለእርሱ ያለንን ፍቅር የሚመዝንባቸው መንገዶች የትኞቹ ናቸው? ለ) ብዙ ክርስቲያኖች በዚህ ፈተና የሚወድቁት ለምንድን ነው?**

በዚህ ክፍል፥ የመጽሐፈ መሳፍንት ጸሐፊ በዚህ ዘመን ውስጥ የእስራኤል ሕዝብ ያለፈበትን የታሪክ ዑደት ያሳየናል። በመጀመሪያ፥ አይሁድ ሌሎች አማልክትን በማምለክ በእግዚአብሔር ላይ ዓመፁ። በሁለተኛ ደረጃ፥ እግዚአብሔር ሊቀጣቸውና ለእርሱ ወደሆነ አምልኮ ሊመልሳቸው ለጠላቶቻቸው አሳልፎ ሰጣቸው። ሦስተኛ፥ እስራኤላውያን ከጠላቶቻቸው ነፃ ያወጣቸው ዘንድ ወደ እግዚአብሔር

ጸለዩ። አራተኛ ከጠላቶቻቸው የጭቆና አገዛዝ ነፃ የሚያወጡአቸውን መሳፍንት አስነሣላቸው። አምስተኛ፥ እስራኤላውያን በሰላም ጊዜ ደስ እያላቸው ኖሩ። በዚህ የሰላም ጊዜ ነበር እስራኤላውያን እንደገና በእግዚአብሔር ላይ ያመፁትና እርሱም ለጠላቶቻቸው ቀንበር አሳልፎ በመስጠት የቀጣቸው። ይህንን ዑደት ለመገንዘብ የሚከተለውን መግለጫ ተመልከት:-




በመጽሐፈ መሳፍንት ውስጥ ይህ ዑደት ስድስት ጊዜ ተደጋግሟል።

2. ዘመነ መሳፍንት (መሳ. 3:7-16)

በዚህ ክፍል የተጠቀሱትን የተለያዩ መሳፍንት በሚቀጥለው ሠንጠረዥ ተመልከት። ሕዝቡ የት እንደነበሩ ለማወቅ ከዚህ መጽሐፍ በስተጀርባ የሚገኘውን ካርታ ተመልከት።

| የመስፍኑ ስም | የእስራኤል ሕዝብ ጠላት | የጭቆና ዘመን | የግዛት የሰላም ዘመን | የመጽሐፉ ክፍል |
|---|---|---|---|---|
| 1. ጎቶንያል | መስጴጦምያ | 8 ዓመት | 40 ዓመት | 3:7-11 |
| 2. ናዖድ<br>3. ሰሜጋር | አሞን፥ ሞዓብና አማሌቅ ፍልስጥኤም | 18 ዓመት | 80 ዓመት | 3:12-30<br>3:31 |
| 4. ዲቦራና ባርቅ | ከነዓናውያን | 20 ዓመት | 40 ዓመት | 4-5 |
| 5. ጌዴዎንና ልጆቹ | ምድያማውያን | 7 ዓመት | 40 ዓመት | 6-9 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 6. ቶላ | | | 23 ዓመት | 10፡1-2 |
| 7. ኢያዕር | | | 23 ዓመት | 10፡3-5 |
| 8. ዮፍታሔ | ፍልስጥኤምና አሞን | 18 ዓመት | 6 ዓመት | 10፡6-12፡7 |
| 9. ኢብጻን | | | 7 ዓመት | 12፡8-10 |
| 10. ኤሎም | | | 10 ዓመት | 12፡11-12 |
| 11. ዓብዶን | | | 8 ዓመት | 12፡13-15 |
| 12. ሶምሶን | ፍልስጥኤም | 40 ዓመት | 20 ዓመት | 13-16 |

ስማቸው ተጠቅሶ የምናገኘው 12 መሳፍንት ቢሆኑም፥ የተለየ ትኩረት የተሰጣቸው ስድስቱ ብቻ ናቸው።

1. ጎቶንያል፡- የካሌብ ልጅ ሲሆን በቅድሚያ የተጠቀሰ ነው። የሌሎች መሳፍንት ተግባር የተመሠረተው በዚህ ሰው ምሳሌነት ላይ ነው። በጎቶንያል ታሪክ የመጽሐፈ መሳፍንት ጸሐፊ የሚተርከው የኃጢአት፥ የፍርድ፥ የንስሐና ነፃ የመውጣት ዑደትን ነው። ይህ ዑደት በመጽሐፈ መሳፍንት ሌላ ክፍል አምስት ጊዜ ተጠቅሶ ይገኛል።

2. ናዖድ፡- የዚህ ሰው ታሪክ በዝርዝር ተዘግቧል። እስራኤልን ነፃ ማውጣቱን ልዩ የሚያደርገው ሞዓባውያንን ለማሸነፍ ራሱ የሠራው ሥራ በመኖሩ ነው። ሌላው መለያው እጀ ግራኝ መሆኑ ነው።

3. የዲቦራና የባርቅን ታሪክ ልዩ የሚያደርገው ሴቶች በድሉ ውስጥ በተጫወቱት ልዩ ሚና ነው። ዲቦራ የእስራኤል መንፈሳዊ መሪ የነበረች ነቢይት ናት። ኢያዔል ደግሞ የከነዓን ንጉሥ ኢያቢስን በመግደል የዚህ ድል ተሳታፊ ነበረች።

4. በመጽሐፈ መሳፍንት ማዕከላዊ ታሪክ ላይ የጌዴዎንና የልጁን የአቤሜሌክን ታሪክ እናገኛለን። በዚህም ቦታ የጌታ መልአክ የተባለው (ክርስቶስ) ጌዴዎንን በመጥራትና በኃይል በማስታጠቅ ተግባር የተጫወተውን ሚና እንመለከታለን። በጌዴዎን ታሪክ ውስጥ ትኩረት የተሰጠው የእስራኤላውያንን ጦርነት እግዚአብሔር እንዴት እንዳሸነፈላቸው መናገር ነበር። ባደረጉት ነገር እንዳይመኩ፥ እግዚአብሔር ታላቅ ጦርን ለማሸነፍ 400 ሰዎችን ብቻ ተጠቀመ።

አይሁድ ለመጀመሪያ ጊዜ አንድን ሰው ንጉሥ ለማድረግ እንደሞከሩ እናያለን። ጌዴዎንን ንጉሣቸው እንዲሆን ጠየቁት፤ እርሱ ግን እምቢ አለ። ይህንን ያደረገው የሕዝቡ ንጉሥ መሆን ያለበት እግዚአብሔር ብቻ እንደሆነና እርሱም ሆነ ሕዝቡ፥ ሰብዓዊ ንጉሥ ከመፈለግ ይልቅ ለእግዚአብሔር ሥልጣን መገዛት እንዳለባቸው ያውቅ ስለነበረ ነው (መሳ. 8፡22-23)።

በጌዴዎን ታሪክ ውስጥ ሦስት የሚያሳዝኑ ነገሮች ተፈጽመዋል፡-

ሀ. መጀመሪያ፥ ጌዴዎን ከጠላቶቹ በተዋጋሁ ጊዜ አልረዳችሁኝም ብሎ የሱኮትን ከተማ ሲቀጣ እናያለን።

ለ. ሁለተኛው ጌዴዎን የወርቅ ኤፉድ መሥራቱ ነበር። ኤፉድ ካህናት የሚለብሱት በተለያየ ሕብር ያሸበረቀ ልብስ ነበር። ኤፉድ ብዙ ጊዜ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማወቅ የሚያገለግል መሣሪያ ነበር፤ (1ኛ ሳሙ. 23፡6-12)። ጌዴዎን ኤፉድ ለምን እንደሠራ ግልጽ አይደለም። ምናልባት የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማወቅ ተጠቅሞበት ይሆናል። በምንም መንገድ ይሁን ብቻ ወዲያውኑ ወደ አምልኮ ዕቃነት ተለወጠ። የእግዚአብሔር አምሳል ተደርጎ ተመልኳል፤ ወይም አንዳንድ ምሁራን እንደሚያስቡት፥ ኤፉድ በአንድ ጣዖት ላይ ይደረግና ሰዎች ወደዚያ በመምጣት ኤፉዱ የአማልክቶቻቸውን ፈቃድ እንደሚወስንላቸው ያምኑ ነበር።

እግዚአብሔር ጌዴዎንን በከፍተኛ ሁኔታ የተጠቀመበት ቢሆንም ይህ ነገር ለእርሱና ለቤተሰቡ የማሰናከያ ዓለት ሆነባቸው።

ሐ. የጌዴዎን ልጅ የሆነው አቤሜሌክ ራሱን አነገሠ። ይህም በእስራኤል ውስጥ የእርስ በርስ ጦርነት አስነሣ። አቤሜሌክንም አንዲት ሴት የወፍጮ ድንጋይ በራሱ ላይ ለቃ ገደለችው።

5. ዮፍታሔ፡- በኅብረተሰቡ ተንቆና ተጠልቶ የነበረ ሰው ሲሆን የሚቀጥለው ዋና መስፍን ሆነ። በእርሱም ጊዜ ሁለት የሚያሳዝኑ ነገሮች ሆኑ። በመጀመሪያ፥ ከጦርነት አሸንፎ በሚመጣበት ጊዜ

የሚያገኘውን የመጀመሪያውን ነገር ለእግዚአብሔር ለመሠዋት አደገኛ ስእለት ተሳለ። ጦርነቱን አሸንፎ በመጣ ጊዜ ያገኘው የመጀመሪያ ነገር ሴት ልጁ ስለነበረች፥ ስእለቱን መፈጸም ነበረበት። በዮፍታሔ ሴት ልጅ ላይ ስለተፈጸመው ትክክለኛ ነገር ምሁራን ይከራከራሉ። አንዳንዶች ዮፍታሔ ልጁን ለእግዚአብሔር ስለሰጠ፥ ድንግል ሆና በመገናኛው ድንኳን ውስጥ የምታገለግል ሆነች ይላሉ። ሌሎች ደግሞ ዮፍታሔ ልጁን ለእግዚአብሔር ሠውቶ መሥዋዕት አቅርቧል ይላሉ። ሰውን በመሥዋዕትነት ማቅረብ በብሉይ ኪዳን የተከለከለ ቢሆንም (ዘሌ. 18፡21፤ ዘዳ. 18፡10-12)፥ ዮፍታሔ በልጁ ላይ ያደረገው ይህን ሳይሆን አይቀርም።

ሁለተኛ፥በዮፍታሔና በኤፍሬም ነገዶች መካከል ጦርነት ተቀሰቀሰ። በዚህም ከኤፍሬም ነገድ 42000 ሰዎች ሞቱ።

6. በመጽሐፈ መሳፍንት ውስጥ የምናገኘው የመጨረሻው ትልቅ መስፍን ሶምሶን ነው። ሶምሶን ናዝራዊ ሆኖ እንደሚወለድ እግዚአብሔር ለወላጆቹ ስለነገራቸው ልደቱ ልዩ ነበር። ናዝራዊ ለተወሰነ ጊዜ ራሱን ለእግዚአብሔር አገልግሎት የለየ ሰው መሆኑን ታስታውሳለህ። የሶምሶን ናዝራዊነት ልዩ የሆነው የዕድሜ ልክ በመሆኑ ነው። ናዝራዊ በመሆኑም የወይን ፍሬ ውጤት የሆነ ማንኛውንም ነገር የማይበላ፥ ምንም ዓይነት ሬሳ የማይነካና ጠጉሩን የማይቆረጥ ነበር፤ (ዘኁ. 6፡1-21 ተመልከት)። የሚያሳዝነው ግን ሶምሶን እነዚህን ትእዛዛት ሁሉ አፍርሷል። ከፍልስጥኤማውያን ጋር ወይንን ሳይጠጣ አልቀረም፤ የሞተ አንበሳ ሬሳ ነክቷል።ጠጉሩን በተቆረጠ ጊዜ ግን እግዚአብሔር የሰጠው ኃይል ከእርሱ ተወሰደ። ሶምሶን መንፈስ ቅዱስና ታላቅ ኃይል የነበረው ቢሆንም፥ የሥነ ምግባር ሕይወቱ ግን በጣም የተበላሸ ነበር፤ ስለዚህ እግዚአብሔር እስራኤልን ለማዳን በሶምሶን ለመጠቀም ያሰበውን ያህል አልተጠቀመበትም። ለዚህ ነው ሶምሶን በእስራኤል ሕዝብ ላይ የነበረው መሪነት ፍልስጥኤማውያንን ማሸነፍና እንደገና በእነርሱ እጅ መውደቅና

መገዛት የተደጋገመበት። ፍልስጥኤማውያን በእስራኤል ላይ የነበራቸው የበላይነት እስከ ዳዊት ዘመን ድረስ ቀጥሎአል።

12ኛ ጥያቄ፦ የእግዚአብሔርን ዓላማዎች ከግብ ለማድረስ መሪዎች ራሳቸውን በእግዚአብሔር ፊት በንጽሕና መጠበቃቸው አስፈላጊ እንደሆነ የሶምሶን ታሪክ እንዴት ያስጠነቅቀናል?
13ኛ ጥያቄ፦ ሀ) ከተለያዩ መሳፍንት የምናገኛቸው አንዳንድ መንፈሳዊ ትምህርቶች ምንድን ናቸው? ለ) በእነዚህ ምዕራፎች ስለ እግዚአብሔር ባሕርይ የምንማረው ነገር ምንድን ነው?

## 3ኛ ቀን መሳፍንት 17-21

14ኛ ጥያቄ፦ የሰው ልጅ ልብ በመሠረቱ መልካም ነው ወይስ ክፉ? ለምሳሌ፦ ሕግ እንዲሁም ሕግን የሚያስፈጽም የፖሊስ ኃይል ባይኖር ኖሮ የሰዎች ዝንባሌ መልካም ይሆን ነበር ወይስ ክፉ? መልስህን አብራራ።

የመጽሐፈ መሳፍንት የመጀመሪያ ዋና ክፍል (ከምዕ. 1-16 ያለው) በእነዚያ ዓመታት የነበሩ የአይሁዳውያን ዋና የፖለቲካ ችግሮችን ግልጽ በሆነ መንገድ ያሳየናል። ትኩረታቸውም ሕዝቡን ከውጭ ኃይል ወይም ከጠላት ቀንበር ነፃ ለማውጣት እግዚአብሔር ባስነሣቸው መሳፍንትነት አመራር ላይ ነው።

የመጽሐፈ መሳፍንት የመጨረሻው ክፍል (መሳፍንት 17-21) በመሳፍንት ዘመን የነበረውን ሃይማኖታዊና የሥነ - ምግባር ጉድለት የሚያንጸባርቅ ነው። የሰው ልብ በእግዚአብሔር ቁጥጥር ሥር እስካልሆነ ድረስ ሊኖር የሚችለውን ግልጽ ሥዕል ያሳያል። ሰው «በፊቱ መልካም መስሎ የታየውን» (መሳ. 21፡25) ማድረግ ሲጀምር፥ ክፉ መሆኑ ወዲያውኑ ይረጋገጣል። ሕግ ወይም ሕግ አስፈጻሚ አካል በሌለበት ለሕገወጥነት መከሰት ጊዜ አይወስድበትም። ሕግና ሕግን የሚያስፈጽሙ የሕዝብ መሪዎች የሰው ኃጢአት በተወሰነ ቁጥጥር ሥር እንዲሆን ያደርጋሉ። እነዚህ ተከላካዮች ሲነሡ፥ የሰው ኃጢአተኝነት ወዲያውኑ ገሐድ ይወጣል።

15ኛ ጥያቄ፥ ሀ) አንተስ ይህ ነገር ሲፈጸም ያየኸው እንዴት ነው?
ለ) ይህ ስለ ሰው ክፉ ባሕርይ የሚያስተምርህ ምንድን ነው?
16ኛ ጥያቄ፥ መሳ. 17-21 አንብብ። በእነዚህ ምዕራፎች የሰው ልጅ ክፋት የታየው እንዴት ነው?

በመጽሐፈ መሳፍንት ምዕ. 17-21 የሚገኙት ታሪኮች የተፈጸሙበትን ጊዜ ማወቅ የማይቻል ነው። የዳን ነገዶች ገና ርስት በመፈለግ ላይ ስለሚገኙና የአሮን ልጅ ፊንሐስ ሊቀ ካህን በመሆኑ፥ ታሪኮቹ የተፈጸሙት በመጀመሪያዎቹ የመጽሐፈ መሳፍንት ዘመን ሳይሆን አይቀርም (መሳ. 18፡1፤ 20፡27-28)። የእነዚህ ታሪኮች ዓላማ በዘመነ መሳፍንት የነበረውን አጠቃላይ የሥነ-ምግባር መመሪያ መጥፋት ለማሳየት ነው። የእግዚአብሔርን ቃል ሊያውቁና ሌሎችን ማስተማር ይገባቸው ለነበሩ ሌዋውያን ልዩ ትኩረት ተሰጥቶአል። ከቀሩት እስራኤላውያን ሁሉ በላይ፥ ለእግዚአብሔር ሕግ በመታዘዝ እንዲኖሩ የሚጠበቅባቸው ሌዋውያን ነበሩ። እነርሱም እንደቀረው ሕዝብ ሁሉ በእግዚአብሔር ላይ ኃጢአት አደረጉ። በኃጢአታቸውም ምክንያት የቀሩት ሕዝብ ወደ ክሕደትና ጣዖት አምልኮ ሄዱ። የእነርሱም ተግባር ሕዝቡን ወደ እርስ በርስ ጦርነት መራው።

1. የሌዋውያን ክህናትና የዳን ነገድ ታሪክ (መሳ. 17-18)

የእግዚአብሔር ሕዝብን ኃጢአተኝነት የሚያመለክተው የመጀመሪያው ታሪክ፥ ስለ አይሁድ ሃይማኖት መበላሸት ይናገራል። ይህ ብልሽት የተጀመረው ከኤፍሬም ነገድ የሆነች አንዲት ሴትና ልጇ ከብር የተሠራ ምስል ሠርተው በቤታቸው ባስቀመጡ ጊዜ ነው።

ወደ ደቡብ ብዙ ኪሎ ሜትር ራቅ ብሎ አንድ ሌዋዊ ነበር። እንደምታስታውሰው፥ ሌዋውያን የእስራኤላውያን ሃይማኖታዊ መሪዎች እንዲሆኑ በእግዚአብሔር የተመረጡ ነበሩ። ደግሞም ይኖሩባቸውም ዘንድ እግዚአብሔር 48 ከተሞችን ሰጥቷቸው እንደነበረ ታስታውሳለህ። ቤተልሔም ከእነዚህ አንዷ አልነበረችም። ይህም የሚያሳየው በሙሴና በኢያሱ ዘመን ተጀምሮ የነበረው የአኗኗር ዘይቤ እየተጣሰ መሆኑን ነው። ሌዋዊ ቤተልሔምን ትቶ ስለ መሄዱ የተነገረው እውነት፥ ጨርሶ ሊገኝባት የማይገባው ከተማ ስለነበረች፥

ሥራ አግኝቶ ወደሌላ ስፍራ መሄዱ ሊሆን ይችላል። ይህም እግዚአብሔር ያዋቀረው የአኗኗር ስልት እየተጣሰ መሆኑን ያሳያል። ሌዋውያን እስራኤላውያን ለጌታ ከሚሰጡት አሥራት በሚገኘው ገቢ ኑሮአቸውን መምራት ነበረባቸው።

| |
|---|
| 17ኛ ጥያቄ፥ ሀ) የእግዚአብሔር ሕዝቦች አሥራታቸውን በማይሰጡበት ጊዜ ይህ የእግዚአብሔርን ሥራ እንዴት ይጎዳል? ለ) ይህ የአንተ ቤተ ክርስቲያንም ችግር ነውን? ከሆነስ ለምን? |

ሌዋዊው ሥራ ፍለጋ ወደ ሰሜን ተጓዘና ወደ ሚካ ቤት መጣ። ሚካም ላሠራው ጣዖት ካህን ሆኖ እንዲያገለግል ቀጠረው። ሚካ ቤቱን የአምልኮ ስፍራ ለማድረግ ፈልጎ ነበር። ይህንን ያደረገው ለእውነተኛው የእግዚአብሔር አምልኮ በኃላፊነት ማገልገል የነበረበትን አንዱን ሌዋዊ በመቅጠር ነበር። ሌዋዊው ስለ ግል ሕይወቱ እንጂ ለእግዚአብሔር ስለሚደረግ አምልኮ ግድ ስላልነበረው የተሳሳተውን አምልኮ ለመምራት ፈቃደኛ ሆነ። እውነተኛ አምልኮን ሳይሆን ገንዘብን ብቻ ፈለገ።

ከዚያ በኋላ ወዲያውኑ የዳን ነገድ አባሎች የሚኖሩበትን ስፍራ እየፈለጉ ወደዚህ ስፍራ ደረሱ። የዳን ነገዶች በሜዲትራኒያን ባሕረሠላጤ አጠገብ መሬት ተሰጥቶአቸው ነበር። መሬቱ በዚያ ስፍራ እጅግ ለም ቢሆንም፥ በከነዓናውያን ተይዞ ነበር፤ ስለዚህ የዳን ነገዶች ሌላ ስፍራ ይፈልጉ ዘንድ አምስት ወታደሮችን ላኩ። ወደ ሚካ ቤት በደረሱ ጊዜ ሌዋዊው ከደቡብ የእስራኤል ክፍል እንደመጣ ተገነዘቡ። በዚያ ስፍራ የሚካሄድ የጣዖት አምልኮ አለቃ መሆኑንም አወቁ። ከዚያ በኋላ አምስቱ ሰዎች ወደ ሰሜን 240 ኪሎ ሜትር ተጉዘው ሌሳ ወደምትባል ስፍራ ደረሱ። የወደፊት ቤታቸውም በዚያ እንዲሆን ወሰኑ። የቀሩት የዳን ነገዶች ወደ ሌሳ መጥተው ምድሪቱን ሲወሩ፥ አምስቱ ሰዎች ወደ ሚካ ቤት በመሄድ ሌዋዊውንና የሚካን ጣዖት ወደ ሌሳ ይዘው ሄዱ። ለብዙ ዓመታት ይህ ሌዋዊና ቤተሰቡ የዚህ ጣዖት ካህናት ሆነው ቀሩ። ሌሳ በኋላ «ዳን» ተብላ የተጠራች የእስራኤል የሩቅ ሰሜን ድንበር ናት።

18ኛ ጥያቄ፥ ሀ) በዚያን ጊዜ እስራኤላውያን ስለ እግዚአብሔር የነበራቸውን ደካማ አስተሳሰብ በሚመለከት ምን እንማራለን? ለ) የአይሁዳውያን ሃይማኖት በከነዓናውያን ሃይማኖት በፍጥነት የተበከለው ለምንድን ነው? ሐ) ሃይማኖታችን በዓለማዊ ልምምድ ስለመበከሉ አደገኛነት ምን እንማራለን?

ከዚህ ትምህርት የምናገኛቸው በርካታ እውነቶች አሉ። በመጀመሪያ፥ የእግዚአብሔር ሕዝብ የከነዓናውያንን ባሕልና ሃይማኖት እንዴት በፍጥነት እንደለመዱ ማየት እንችላለን። ሁለተኛ፥ ሕዝቡ የእግዚአብሔር አምልኮ ከጣዖት አምልኮ ጋር ሊቀላቀል እንደሚችል እንዴት እንዳሰበ ማየት እንችላለን። እግዚአብሔር ወደ ጣዖት ሊለወጥና ለራሳቸው ዓላማ ማስፈጸሚያና መጠቀሚያ ሊያደርጉት እንደሚችሉ አሰቡ። ሦስተኛ፥ የጣዖት አምልኮን ዋጋ ቢስነት እናያለን። ጣዖት ራሱን ከመሰረቅ ለማዳን አለመቻሉና፥ ኃይል እንደሌለው ያሳየናል።

## 2. ሌዋዊውና ቁባቱ (መሳ. 19-21)

ከዘመነ መሳፍንት የምናገኘው ሁለተኛው ታሪክ የሕዝቡን የሥነ ምግባር ብልሹነት ያሳየናል። እንዲሁም የሃይማኖት መሪዎቹ ድካምና ኃጢአት እንዳየለባቸው ለሁለተኛ ጊዜ እንመለከታለን። የመጀመሪያው ሌዋዊ ከቤተልሔም ተነሥቶ ወደ ኤፍሬም እንደሄደ፥ ሁለተኛው ሌዋዊ ደግሞ ወደ ቤተሰቦችዋ የተመለሰችውን ቁባቱን ፍለጋ ከኤፍሬም ወደ ቤተልሔም መጣ። ከቤተልሔም ቁባቱን ይዞ ወደ ኤፍሬም በሚመለስበት ጊዜ እግረ መንገዱን ጊብዓ በምትባል በብንያማውያን ከተማ መሸበትና አደረ። ልክ እንደ ሰዶምና ገሞራ ሰዎች፥ እስራኤላውያን እጅግ አስጸያፊ ተግባር ፈጸሙ። ለራሳቸው ሰዎች መስተንግዶ ማድረግ አልቻሉም። ግብረ ሰዶም ለመፈጸም ፈልገው ሰውዬውን ካደረበት ቤት ለማስወጣት ሞከሩ። ሌዋዊውን ያሳደረው ሰው ግን የገዛ ሴት ልጁንና የሌዋዊውን ቁባት አውጥቶ ሰጣቸው። ቁባቱም እስከትሞት ድረስ በመፈራረቅ ሌሊቱን ሙሉ አመነዘሩባት።

19ኛ ጥያቄ፥ ይህ ታሪክ የሌዋዊንና የእስራኤልን ሕዝብ ሃይማኖታዊና ሥነ- ምግባራዊ ክፋት እንዴት ያሳየናል?

ሌዋዊው የቁባቱን ሬሳ 12 ቦታ ቆራረጠና ለእያንዳንዱ የእስራኤል ነገድ አንዳንዱን ቁራጭ ላከ። ይህም ነገር የ12ቱን ነገዶች ቁጣ ቀሰቀሰና ምን እንደተፈጸመ ለማየት መጡ። ታሪኩን በሰሙ ጊዜ፥ ይህንን ኃጢአት የፈጸሙትን ሰዎች አሳልፈው እንዲሰጧቸው የብንያም ነገዶችን ጠየቁ። ብንያማውያን ግን ስለተቃወሙ፥ የእርስ በእርስ ጦርነት ተነሣ። በጦርነቱም 40000 እስራኤላውያንና 25100 ብንያማውያን ሞቱ። የብንያማውያን ሴቶችና ልጆች በሙሉ ተገደሉ። ከብንያም ነገድ በሙሉ የተረፉት 600 ሰዎች ብቻ ነበሩ።

ሌሎች እስራኤላውያን፥ ከእስራኤል ነገዶች አንዱ የሆነው የብንያም ነገድ ሊጠፋ እንደሆነ ተገነዘቡ፤ ስለዚህ ለእነዚህ 600 ብንያማውያን 600 ሚስቶች የሚገኙበትን ዘዴ ፈጠሩ። በዚህም የብንያምን ነገድ ጨርሶ ከመጥፋት አዳኑት።

ሰዎች ራሳቸው የሚፈልጉትን ነገር ብቻ ሲያደርጉ፥ ኃጢአታቸው አድጎ በርካታ ሰዎችን እንደሚነካና እንደሚያጠፋ አይገነዘቡም። የጊብዓ ሰዎች ኃጢአት በሺህ የሚቆጠሩ የበርካታ እስራኤላውያንን ሞትና የብንያም ነገድን ወደ ውድመት የሚያደርስ ጥፋት አስከትሎ ነበር።

20ኛ ጥያቄ፥ ሀ) እነዚህ ቁጥሮች ኃጢአት ስለሚስፋፋበት መንገድና በምድሪቱ ስለ ሕግና ሥርዓት አስፈላጊነት ምን ያስተምሩናል? ለ) ከዚህ ታሪክ ለቤተ ክርስቲያኖቻችን የሚጠቅሙና ልናዛምዳቸው የምንችል አንዳንድ ትምህርቶች የትኞቹ ናቸው?

## የመጽሐፈ መሳፍንት ዋና ዋና ትምህርቶች

21ኛ ጥያቄ፥ ከመጽሐፈ መሳፍንት እንዳነበብከው በውስጡ የሚገኙ፥ ከሕይወትህና ከቤተ ክርስቲያንህ ጋር ልታዛምዳቸው የምትችለውን ዋና ዋና እውነቶች ናቸው ብለህ የምታስባቸውን ዘርዝር።

1. መጽሐፈ መሳፍንት ለእግዚአብሔር በከፊል የመታዘዝ ውጤት ምን እንደሆነ ያሳየናል። እግዚአብሔር ከነዓናውያንን በሙሉ እንዲያጠፉ የሰጠውን ትእዛዝ አይሁድ በከፊል ብቻ ስለታዘዙት፥ ወደ ባሰ ኃጢአት የመውደቅን ሂደት ጀመሩ። ለእግዚአብሔር በከፊል መታዘዝ ብዙም ሳይቆይ፥ ለእርሱ በግልጽ ወዳለመታዘዝ ተለውጧል።

የዚህ ዓይነት ተመሳሳይ ነገር በክርስቲያን ሕይወትም ይፈጸማል። ማንም ሰው በድንገት ከኃጢአት ፈጥኖ አይወድቅም። ይልቁንም ይህ በሂደት የሚፈጸም ነው። በመጀመሪያ መጠነኛ ጅማሬ ይኖረዋል። ይህ ጅማሬ በከፊል መታዘዝ ነው። በአብዛኛው የሕይወት ክፍላችን ለእግዚአብሔር እንታዘዛለን፤ ነገር ግን ያልተናዘዝናቸው ኃጢአቶች በሕይወታችን እንዲቆዩ እንፈቅዳለን። እነዚህ ኃጢአቶች፥ ኩራት፥ ትዕቢት፥ ቁጣ፥ ወይም ቅንዓት ሊሆኑ ይችላሉ፤ ነገር ግን ብዙ ሳይቆዩ እነዚህ ኃጢአቶች አድገው ሕይወታችንን በመቆጣጠር ለእግዚአብሔር በግልጽ ወዳለመታዘዝ ያደርሱናል።

---

22ኛ ጥያቄ፥ ይህንን እውነት በራስህ ወይም በሌላው ክርስቲያን ሕይወት እንዴት አየኸው?

---

2. መጽሐፈ መሳፍንት ዓለም በክርስቲያን ላይ ተጽዕኖ ለማድረግ ያላትን ኃይልና እንዴት ወደ ኃጢአት እንደምትመራ ያሳየናል። በኢያሱ መሪነት እስራኤላውያን እግዚአብሔርን ለመከተልና እርሱን ብቻ ለማምለክ ቃል ኪዳን አደረጉ፤ ነገር ግን የእግዚአብሔር ጠላቶች የሆኑት ከነዓናውያን በመካከላቸው እንዲኖሩ ስለፈቀዱ፥ የከነዓናውያን ልምምድ ብዙም ሳይቆይ ችግር ያመጣባቸው ጀመር። ወዲያውኑ እንደከነዓናውያን ማሰብና ማምለክ ጀመሩ፤ በመጨረሻም እንደ ከነዓናውያን መኖር ጀመሩ። መጽሐፍ ቅዱስ ራሳችንን ከዓለምና ከልምምዷ እንድንለይ፥ እርሷንም ከመምሰል እንድንጠነቀቅ ያስተምረናል።

23ኛ ጥያቄ፥ 2ኛ ቆሮ. 6፡14-18 ና 1ኛ ዮሐ. 2፡15-17 አንብብ። ከዓለም ጋር ስለሚኖረን ግንኙነት በዚሀ ክፍል የተሰጠን ትእዛዝ ምንድን ነው?

ክርስቲያኖች ሁሉ ከዓለም ጋር ያለንን ግንኙነት ሙሉ በሙሉ እንድናቋርጥ መጽሐፍ ቅዱስ አያስተምረንም። ኢየሱስም የጸለየው፥ በዓለም እንድንኖር እንጂ፥ ከዓለም እንድንወጣ አይደለም (ዮሐ. 17፡14-19)። እግዚአብሔርን የማያምኑ ሰዎችን ጓደኛ እንድናደርግ፥ ወንጌልን እንድናካፍላቸው፥ በሚያስፈልጋቸው ነገር እንድንረዳቸው፥ ከጎናቸው ሆነን እንድንሠራ፥ ወዘተ. ይፈልጋል። ኢየሱስ ራሱ «የኃጢአተኞች ወዳጅ» ተብሎአል (ማቴ. 11፡19)። ከማያምኑ ጋር ያለንን ማንኛውንም ኅብረት ማቆም አለብን የሚሉ ሰዎች ተሳስተዋል። ከእነርሱ ጋር ካልኖርን፥ ካላወቅናቸውና ፍቅርን ካላሰየናቸው በቀር፥ የዓለም ብርሃንና ጨው እንዴት መሆን እንችላለን? እንድንጠነቀቅ የተነገረን ነገር ቢኖር፥ በመንፈሳዊ ሕይወታችን ላይ ዓለማዊ ተጽዕኖ እንዳይኖር ነው። እንደ እግዚአብሔር ልጆች የዓለም ፍልስፍና በሕይወታችን ላይ የማያስፈልግ ተጽዕኖ እንዳያደርግ መጠንቀቅ አለብን። ለምሳሌ፡- የትምህርት ፍላጎት፥ የገንዘብና የሥልጣን ፍቅር፥ ለራሳችን፥ ለቤተሰባችን ወይም ለጎሣችን በራስ ወዳድነት የተለየ ጥንቃቄ ለማድረግ መመኘት የለብንም።

24ኛ ጥያቄ፥ ሀ) ክርስቲያን በዓለም ፍልስፍና ተጽዕኖ ሊደረግበት የሚችለው እንዴት ነው? ለ) ክርስቲያን ከማያምኑ ሰዎች ጋር እየኖረ በዓለም ፍልስፍና ተጽዕኖ የማይደረግበት እንዴት ነው?

3. እግዚአብሔር አማኞች ዓለምን እየመሰሉ ሲሄዱ፥ ያንጻቸው ዘንድ አስቸጋሪ ሁኔታዎችን ይጠቀማል። ይህ ማለት አስቸጋሪ ሁኔታዎች ሁሉ ስለ ኃጢአት ፍርድ ናቸው ማለት አይደለም፤ አንዳንድ ጊዜ ግን ናቸው። አንዳንዶች በችግር ውስጥ በሚሆኑበት ጊዜ ኃጢአተኞች ስለሆኑ ከእግዚአብሔር ፍርድ በታች ናቸው በማለት እንዳንፈርድ መጠንቀቅ አለብን። የእግዚአብሔር ሕዝብ በኃጢአት ውስጥ በሚሆኑበት ጊዜ እግዚአብሔር ብዙውን ጊዜ

በአስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ እንዲያልፉ የሚያደርግበት መንፈሳዊ መመሪያ አለ። ይህም በሽታ፥ የወዳጅ ሞት፥ ወይም በአገር ላይ የሚመጣ ችግር ሊሆን ይችላል። በዚህ ዓይነት ጊዜ የሚመጣው ችግር ዓላማ ሕዝቡ ንስሐ ገብተው ከክፉ መንገዳቸው ወደ እግዚአብሔር እንዲመለሱ ለማድረግ ነው። እውነተኛ ንስሐ ሰውን ጠባዩን እንዲለውጥ ያደርገዋል። እስራኤላውያን ግን በእውነት ንስሐ ገብተው እንደሆነ የሚያሳይ ምንም መረጃ የለም። ከጠላቶቻቸው ነፃ እንደወጡ ብዙም ሳይቆዩ፥ ወደ ቀድሞ ክፉ ተግባራቸው ይመለሱ ነበር። የእግዚአብሔር ፍላጎት ግን ንስሐ እንድንገባና መንገዳችንን እንድንለውጥ ነው። ወደ በረከት ስፍራ የሚመልሰን በዚያን ጊዜ ብቻ ነው።

| |
|---|
| 25ኛ ጥያቄ፥ በግል ሕይወትህና በቤተ ክርስቲያንህ እግዚአብሔር ከኃጢአት ያነጻችሁ ዘንድ አስቸጋሪ ሁኔታዎችን እንዴት እንደተጠቀመ ተጨባጭ ምሳሌዎችን ስጥ። |

4. የእግዚአብሔር ሕዝብ በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ሲሆኑ ብዙውን ጊዜ እግዚአብሔር ታላቅ መሪን በማስነሣት በእርሱ አማካይነት ነጻነትን ይሰጣቸዋል። እስራኤላውያን በጠላቶቻቸው በሚጨቆኑበት ጊዜ፥ የሕዝቡን ጸሎት በመስማት መሳፍንትን አስነሣላቸው። በመጽሐፈ መሳፍንት ውስጥ የምናያቸው መሳፍንት ተቀዳሚ ተግባራቸው ወታደራዊ መሪነት ሆኖ ሕዝቡን ከባርነት ነፃ አውጥተዋል። እግዚአብሔር እነዚህን ሰዎች የመረጠው በመንፈሳዊነታቸው ለመሆኑ ምንም መረጃ የለንም። እንዲያውም አብዛኞዎቹ መሳፍንት በጣም መንፈሳዊ አልነበሩም። ሶምሶን ዘማዊ ነበር። ዮፍታሔ ልጁን ሠውቷል። ጌዴዎን ሕዝቡን ወደ ኤፉድ አምልኮ መርቷል። አብዛኞዎቹ መሳፍንት ልንከተለው የሚገባ መንፈሳዊ ምሳሌነት አልተዉልንም። ቢሆንም እግዚአብሔር ሕዝቡን ነፃ ለማውጣት ሰውን ከመንፈሳዊነቱ ውጭ እንዴት ሊጠቀምበት እንደሚችል የእነርሱ ታሪክ ያሳየናል።

ዛሬም ቢሆን እግዚአብሔር የሚሠራው በተመሳሳይ መንገድ ነው። እግዚአሔር ሕዝቡን ከባርነት ነፃ ለማውጣት መሠረታዊ ፈሪሀ

እግዚአብሔር ያለውን ሰው የመንፈሳዊ ሕይወት ደረጃውን ሳይመለከት ሊጠቀምበት ይችላል። ለምሳሌ:- እግዚአብሔር፥ አማኝ ያልሆነን የፖለቲካ መሪን በማስነሣት፥ ለአማኞች እንዲራራና ከችግሮቻቸው ነፃ እንዲያወጣቸው ሊያደርግ ይችላል።

ነገር ግን እግዚአብሔር የራሱ ሕዝብ መሪዎች የተቀደሰ ሕይወት እንዲኖራቸው ይፈልጋል። የእስራኤል ልጆች በተደጋጋሚ በኃጢአት የወደቁበት ምክንያት፥ ምናልባት እነዚህ መሳፍንት ለሕዝቡ መልካም መንፈሳዊ ምሳሌ ስላልሆኑ ይሆናል። የሰዎች ሥነ - ምግባርና መንፈሳዊ ሕይወት ብዙ ጊዜ የሚወሰነው በመሪዎቻቸው መንፈሳዊ ሕይወት ላይ መሆኑ ከቅዱሳት መጻሕፍት መመሪያዎች አንዱ ነው። መሪዎች እግዚአብሔርን ሲወዱና በቅድስና ሲያገለግሉት፥ ሕዝቡም እንዲሁ ያደርጋሉ።

| |
|---|
| 26ኛ ጥያቄ፥ ሀ) ይህ በቤተ ክርስቲያንህ እውነት ሲሆን ያየኸው እንዴት ነው? ለ) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ምርጫ መመሥረት ያለበት፥ በትምህርት፥ በዘር፥ ወይም በቤተሰብ ውርስ፥ ወዘተ. ሳይሆን በመንፈሳዊ መመዘኛ መሆን እንዳለበት ይህ ምን ያስተምረናል? |

5. መጽሐፈ መሳፍንት የሚያተኩረው በመንፈስ ቅዱስ ሥራ ላይ ነው።

| |
|---|
| 27ኛ ጥያቄ፥ ከመጽሐፈ መሳፍንት የሚከተሉትን ጥቅሶች አንብብ:- መሳ. 3:10፤ 6:34፤ 11:29፤ 14:6፥ 19፤ 15:14፤ 16:20። ይህ በዚያን ዘመን ስለነበረው የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ምን ያስተምረናል? |

ከመጽሐፈ መሳፍንት ልዩ ገጽታዎች መካከል አንዱ በመንፈስ ቅዱስ ላይ የተደረገ ትኩረት ነው። ከዚህ መጽሐፍ በፊት ስለ መንፈስ ቅዱስ አገልግሎት የተነገረው በጣም ጥቂት ነገር ነው። በመጽሐፈ መሳፍንት ግን የጌታ መንፈስ ወይም መንፈስ ቅዱስ በተደጋጋሚ ተጠቅሷል። ከላይ የተሰጡትን ጥቅሶች በሚገባ ካጠናን የሚከተሉትን ነገሮች እንመለከታለን:-

ሀ. አንድ የተለየ ተግባር ለመፈጸም በተጠሩ ውሱን መሪዎች ላይ መንፈስ ቅዱስ ይወርድ ነበር። የመንፈስ ቅዱስ በሰዎች ላይ መውረድ የተለመደ ነገር አልነበረም፤ ሆኖም እግዚአብሔር ሕዝቡን ለመምራት ወይም ነፃ ለማውጣት ይችሉ ዘንድ ለመረጣቸው ሰዎች መንፈስ ቅዱስን ይሰጣቸው ነበር። በዚህ ዓይነት እነዚህ መሳፍንት የእግዚአብሔርን ሕዝብ ከባርነት ነፃ ያወጡት በራሳቸው ኃይል ሳይሆን፥ እግዚአብሔር መንፈሱን ስለ ሰጣቸው እንደሆነ ግልጥ መሆን ነበረበት። እውነተኛው የእስራኤል ነፃ አውጭ እግዚአብሔር እንጂ መስፍኑ አልነበረም።

ለ. መንፈስ ቅዱስ ሰዎች የእርሱን ልዩ ኃይል በሚፈልጉበት ጊዜ በተደጋጋሚ ይመጣ ነበር። በመጀመሪያ አካባቢ ሶምሶን ከጠላቶቹ ጋር በሚገናኝበት ጊዜ ሁሉ የእግዚአብሔር መንፈስ በላዩ ላይ ይወርድ ነበር።

ሐ. መንፈስ ቅዱስ በሰው ደስ በማይሰኝበት ጊዜ ከዚያ ሰው ተለይቶ ይሄድ ነበር። ይህን እውነት እግዚአብሔር ከሶምሶን ተለየ ከሚለው ቃል መመልከት እንችላለን። በንጉሥ ሳኦል ታሪክ መንፈስ ቅዱስ ተወው የሚል ቃል ስናነብ (1ኛ ሳሙ. 16፡14)፥ ይህ ነገር ግልጽ ይሆንልናል። ለጸሎቱ መልስን በመስጠት መንፈስ ቅዱስ ወደ ሶምሶን እንደተመለሰ ደግሞ የዳጎንን ቤተመቅደስ በመደርመሱ እንረዳለን፤ (መሳ. 16፡28-30)።

ልናስታውሰው የሚገባን አንድ በጣም አስፈላጊ እውነት አለ። እግዚአብሔር እውነቱን ሁሉ በአንድ ጊዜ አልገለጠም። ነገር ግን ስለ እርሱ የሚናገር ተጨማሪ እውነትን በየጊዜው በዘመናት ሁሉ በዝግታ ይገልጥ ነበር። ይህ «እየጨመረ የሚሄድ መገለጥ» በመባል ይታወቃል። አይሁድ እግዚአብሔር አምላክ አብ፥ ወልድ፥ መንፈስ ቅዱስ ማለት ሥላሴ መሆኑን አያውቁም ነበር፤ ስለዚህ የእግዚአብሔርን መንፈስ የእግዚአብሔር ተቀጥያ፥ ወይም የእግዚአብሔር ኃይልና ሥልጣን፥ የመኖሩ ማረጋገጫ አድርገው ያስቡት ነበር። መንፈስ ቅዱስን ከሥላሴ አንዱ አድርገን

የምንመለከተው በአዲስ ኪዳን ብቻ ነው፤ ከእግዚአብሔር ጋር አንድ ነው፥ ሆኖም ከእግዚአብሔር የተለየ ነው።

ይህም ማለት ስለ መንፈስ ቅዱስ ያለንን መረዳት በብሉይ ኪዳን ላይ ብቻ ከመመሥረት መጠንቀቅ አለብን ማለት ነው። በኢዩኤል 2፡28 እግዚአብሔር በመጨረሻው ቀን መንፈሱን በሰዎች ሁሉ ላይ እንደሚያፈስ አስቀድሞ ተናግሮ ነበር። የዚህ ትንቢት ፍጻሜ የጀመረው በጰንጠቆስጤ ቀን ነው፤ በዚያን ጊዜ ሕዝቡ በላይኛው ክፍል ሳሉ መንፈስ ቅዱስ በሁሉም ላይ ወርዶባቸው ነበር (የሐዋ. 2)። በአዲስ ኪዳን በሚገኙ የመንፈስ ቅዱስ ሥራዎች የሚከተሉት እውነቶች ግልጽ ናቸው።

ሀ. መንፈስ ቅዱስ እግዚአብሔር በጸጋው በሚያምኑበት ጊዜ ለልጆቹ በሙሉ የሚሰጠው እንጂ ለተወሰኑ የተመረጡ ሰዎች የሚሰጥ ብቻ አይደለም። በሮሜ 8፡9 ጳውሎስ ማንም መንፈስ ቅዱስ የሌለው የክርስቶስ አይደለም ይላል። በሌላ አነጋገር፥ ይህ ማለት አማኝ አይደለም ማለት ነው። መንፈስ ቅዱስ ወደ እኛ የመጣው ባመንበትና የእግዚአብሔር ቤተሰቦች በሆንበት ጊዜ ስለሆነ፥ አሁን ወደ እኛ እንዲመጣ መጸለይ ስሕተት ነው፤ የእግዚአብሔርን መንፈስ ያለማቋረጥ እንድንሞላ መጸለይ ግን ተገቢ ነው፤ (ኤፌ. 5፡18)። መንፈስ ቅዱስን እንዳናጠፋው ኃጢአታችንን መናዘዝ አለብን (1ኛ ተሰ. 5፡19)።

ለ. እግዚአብሔር የመንፈስ ቅዱስን ሕልውና ከልጆቹ ላይ አይወስድም። ክርስቲያኖች ኃጢአት በሚያደርጉበት ጊዜ መንፈስ ቅዱስ ሊወሰድባቸውና ደግሞ ተመልሶ ሊመጣ አይችልም። ኃጢአት የሚያደርግ ክርስቲያን እንኳ መንፈስ ቅዱስ አለው። እርስ በርሳቸው ይጋጩ የነበሩ የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያኖች እንኳ መንፈስ ቅዱስ እንደነበራቸው ከ1ኛ ቆሮ. 1፡7 በግልጽ እንመለከታለን፤ ነገር ግን ኃጢአት በምናደርግበት ጊዜ በእኛ ውስጥ የሚሠራውን የመንፈስ ቅዱስ ኃይል እናጣለን።

ሐ. የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ቤተ ክርስቲያንን ያገለግሉበት ዘንድ እግዚአብሔር እንደፈለገ ለክርስቲያኖች ሁሉ ተሰጥተዋል (1ኛ ቆሮ. 12፡11)። የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ዓላማቸው ለግል ጥቅም፥ መንፈሳዊነታችንን ለመግለጥ አይደለም፤ ነገር ግን ቤተ ክርስቲያን በአጠቃላይ በመንፈሳዊ ብስለትና እግዚአብሔርን በማገልገል እንድታድግ እርስ በርሳችን ማገልገል እንድንችል ለማድረግ ነው (1ኛ ቆሮ. 14፡26)።

መ. የአንድ ሰው መንፈሳዊነት የሚመዘነው፥ በመንፈስ ቅዱስ ፍሬዎች እንጂ (ገላ. 3፡22-23)፥ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችን በመቀበል አይደለም።

ይህ ትምህርት ዛሬ ብዙ ክርስቲያኖች ከሚያስተምሩት የተለየ ቢሆንም፥ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶችን ሁሉ በጥንቃቄ በመመርመር ስለ መንፈስ ቅዱስ የሚናገሩትን ነገር ማወቅ አስፈላጊ ነው። በመጽሐፈ መሳፍንት ወይም በሐዋርያት ሥራ ውስጥ በሚገኝ አንድ ክስተት ላይ የሥነ - መለኮት ትምህርት መሥርተን፥ መንፈስ ቅዱስ የሚሠራበት መንገድ ምን ጊዜም ይኸው ነው ልንል አንችልም። በመንፈስ ቅዱስ ላይ ያለንን እምነት ከሁሉም የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል በተገኘ እውነት እንጂ በእነዚህ በጥቂት ጥቅሶች በተገኘ እውነት ላይ መመሥረት የለብንም።

** የዚህ ጥናት ክፍል የሆነ ስለ መንፈስ ቅዱስ ሥራ የሚናገር የትመማ መጽሐፍ ወደፊት ለማዘጋጀት ተስፋ እናደርጋለን።

| |
|---|
| 28ኛ ጥያቄ፥ ሀ) ከላይ የተመለከትናቸው ጥቅሶች አንዳንድ ክርስቲያኖች ስለ መንፈስ ቅዱስ ከሚያስተምሩት ትምህርት ጋር እንዴት ይጋጫሉ? ለ) ሕይወትህን መርምር። የመንፈስ ቅዱስ ኃይል በሕይወትህ እንዳይሠራ የከለከሉህ ኃጢአቶች አሉን? ሐ) የመንፈስ ቅዱስ ፍሬዎች በሕይወትህ እንዳሉ ማረጋገጫ የሚሆኑ ነገሮችን በምሳሌነት ጥቀስ። |

## 4ኛ ቀን:- መጽሐፈ ሩት

በየትኛውም ዘመን፥ ምንም ያህል ጊዜው ጨለማ ቢሆን፥ እግዚአብሔር የራሱ የሆኑ የተመረጡ ሕዝቦች አሉት። አብዛኛው ሕዝብ የሚኖረውን ኑሮ እየተቃወሙ፥ እግዚአብሔርን የሚያስከብርና ከፍ ከፍ የሚያደርግ ሕይወት የሚኖሩ ጥቂት ታማኞች አሉ፤ በመጽሐፈ ሩት ውስጥ የምናየው ነገር ይህ ነው። ዘመነ መሳፍንት በአጠቃላይ ሲታይ እጅግ የከፋ ቢሆንም፥ በእስራኤል ውስጥ እግዚአብሔርን ያከበሩ ጥቂት ሰዎች ነበሩ። መጽሐፈ ሩት የእነዚህን ጥቂት ሰዎች እምነትና እግዚአብሔር እንዴት ለእነርሱ መልካም እንዳደረገላቸው የሚያሳይ ነው።

29ኛ ጥያቄ፥ በማንኛውም አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ለእግዚአብሔር የሆኑ ቅሬታዎች ወይም ጥቂት ታማኞች የመኖራቸውን እውነትነት በሕይወትህ እንዴት አየኸው?
30ኛ ጥያቄ፥ በመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት ውስጥ መጽሐፈ ሩትን ተመልከት፤ ስለዚህ መጽሐፍ የሚናገራቸውን ዋና ዋና ነገሮች ዘርዝር።

### የመጽሐፈ ሩት ስያሜ

መጽሐፈ ሩት የተሰየመው በመጽሐፉ ታሪክ ዋና ገጸ ባሕርይ በሆነችው በሩት ነው። አስቴርን ጨምሮ በሴት ስም ከተሰየሙ ሁለት መጻሕፍት መካከል መጽሐፈ ሩት አንዱ ነው።

### የመጽሐፈ ሩት ጸሐፊ

የመጽሐፈ ሩት ጸሐፊ ማን እንደሆነ ከመጽሐፍ ቅዱስ የምናገኘው ምንም መረጃ የለም። የአይሁድ ትውፊት መጽሐፉን የጻፈው ሳሙኤል ነው ይላል። የመጽሐፉ የመጨረሻ ትኩረት በዳዊት ላይ ስለሆነ፥ ጸሐፊው ሳሙኤል አይመስልም። ስለዚህ በዳዊት ዘመነ መንግሥት፥ ወይም ከዚያ ጥቂት ራቅ ብሎ፥ እግዚአብሔር የዳዊትን የዘር ግንድ ለመጠበቅ እንዴት እንደሠራ ለመግለጽ የሚፈልግ አንድ ሰው እንደጻፈው ይገመታል። ሩት 1:1 የዘመነ መሳፍንት ፍጻሜን የሚያሳይ ይመስላል። የዳዊት ስም በመጽሐፉ መጨረሻ መጠቀሱ ሕዝቡ ዳዊትን ያውቁት እንደነበር ያሳያል።

## የመጽሐፈ ሩት ታሪክ የተፈጸመበት ጊዜ

የመጽሐፈ ሩት ታሪክ የተፈጸመው በዘመነ መሳፍንት ነው። በዘመነ መሳፍንት በየትኛው ጊዜ እንደተፈጸመ የምናውቀው ነገር የለም። አንዳንድ ምሁራን ዮፍታሔ በነበረበት ዘመን አካባቢ የተፈጸመ ነው ብለው ይገምታሉ።

## የመጽሐፈ ሩት አስተዋጽኦ

1. በአቤሜሌክ ቤተሰብ ላይ የደረሰው መከራና ኃዘን (1፡ 1-5)
2. ኑኃሚንና ሩት ወደ ቤተልሔም ተመለሱ (1፡6-22)
3. ሩት ቦዔዝን በመከር መሰብሰቢያ ስፍራ አገኘችው (2)
4. ሩት ወደ ቦዔዝ የአውድማ ስፍራ በመሄድ እንዲያገባት ጠየቀችው (3)
5. ቦዔዝ ሩትን አገባ፤ ወንድ ልጅም ወለዱ (4፡ 1-17)
6. የዳዊት የዘር ሐረግ (4፡ 18-22)።

## የመጽሐፈ ሩት ዓላማ

**31ኛ ጥያቄ፥ እግዚአብሔር መጽሐፈ ሩት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንዲካተት ያደረገው ለምን ይመስልሃል?**

መጽሐፈ ሩት ለምን እንደተጻፈና በመጽሐፍ ቅዱሳችን ውስጥ እንደተካተተ የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁራን ይከራከራሉ። ስለዚህ ጉዳይ ሦስት ዋና ዋና አመለካከቶች አሉ፡-

1. መጽሐፈ ሩት የተጻፈው የዳዊትን አያቶችና ቅድመ አያቶች በመናገር፥ እግዚአብሔር በታሪክ ውስጥ የዳዊትን የዘር ግንድ እንዴት እንደጠበቀ ለማሳየት ነው። አንዳንዶች የሩትና የቦዔዝ ታሪክ ዳዊት ከእስራኤል ሕዝብ ጋር ያለውን ግንኙነት ለማሳየት የተጻፈ ነው ይላሉ። ኑኃሚን ከባዶነት ወደ ሙላት (1፡2)፥ ከከፍተኛ ራብና ችግር (1፡ 1-5)፥ ወደ ደኅንነትና ተስፋ (4፡ 13-17) እንደተመለሰች ሁሉ፥ ራስ ወዳድ ባልሆነው በዳዊት

አመራር የእስራኤል ሕዝብ ከብሔራዊ አደጋ ወደ ሰላምና ብልጥግና ተመልሰዋል። በዚህ ዓይነት ዳዊት እውነተኛው የሩትና የቦዔዝ ልጅ መሆኑ ታየ። ይህ የመጽሐፉ ዓላማ ሊሆን የሚችል ነው ቢባልም ዋናው የመጽሐፉ ዓላማ ግን አይደለም።

2. መጽሐፈ ሩት የተጻፈው አይሁድ አሕዛብን ወደ ይሁዲነት እምነት ለመለወጥ መሞከር እንዳለባቸው ለማስተማርና አሕዛብም እግዚአብሔርን በእውነተኛ እምነት ሊያመልኩ እንደሚችሉ ለማስተማር ነበር። ይህም ቢሆን የመጽሐፉ ዋና ዓላማ መሆኑ የሚያጠራጥር ነው።

3. መጽሐፈ ሩት የሚያስተምረው፥ አጠቃላይ የሆነ ክሕደት ባለበት ዘንድ በእግዚአብሔር ላይ እውነተኛ እምነት ያላቸው ጥቂት ሰዎች ሊኖሩ እንደሚችሉ ለማሳየት ነው። ብዙ ክፋት ባለበት ስፍራ እምነት ሊኖር ይችላል። እግዚአብሔር የእነዚህን ጥቂት ሰዎች እምነት ስለሚያከብር፥ እጅግ አስቸጋሪ በሆነ ሁኔታም ውስጥ ጠበቃቸው። ከሦስቱ አመለካከቶች መካከል የመጽሐፈ ሩት ዋና ዓላማ ይህ ሳይሆን አይቀርም።

መጽሐፈ ሩትን ለመረዳት፥ ከመጽሐፈ መሳፍንት ቀጥሎ መምጣቱንና ዘመነ መሳፍንት ደግሞ ከፍተኛ ክፋትና የሥነ - ምግባር ብልሽት የታየበት ዘመን መሆኑን ማስታወስ እጅግ አስፈላጊ ነው። ይህ መጽሐፍ ንጉሥ ያልነበረበትን የዚህ ዘመን አጠቃላይ ገጽታ የሚያሳይ ነው።

መጽሐፈ ሩት፥ አብዛኛው የእግዚአብሔር ሕዝብ ከነበረበት አሳዛኝ ክሕደት ጋር በተነጻጻሪነት የቀረበ ታሪክ ነው። የመጽሐፈ ሩት ጸሐፊ፥ በታላቅ ክፋት መካከል ጨርሶ ባልተጠበቀ ስፍራ፥ ባልታሰቡ ሰዎች ልብ ውስጥ እምነት ሊኖር እንደሚችል በብዙ ንጽጽር ያሳየናል። ጸሐፊው በርካታ የተለያዩ ምሳሌዎችን በመጠቀም እውነተኛ እምነት በጥቂት ታማኝ ሰዎች ሕይወት ውስጥ የሚያመጣውን ለውጥ ያሳያል። የሚከተሉትን ተመልከት፡-

| ዘመነ መሳፍንት | መጽሐፈ ሩት |
| --- | --- |
| 1. የእግዚአብሔር ሕዝብ የሆኑት አይሁድ የእግዚአብሔርን ንጉሥነት እምቢ ብለው ጣዖታትን አመለኩ። | 1. የተናቀችው የአሕዛብ ወገን እውነተኛውን እግዚአብሔርን ለመከተል የጣዖት አምልኮን ተወች። |
| 2. ትኩረቱ በሕዝቡ ሕይወት በሚታየው ታላቅ ክፋት ላይ ነው። | 2. ትኩረቱ እንደ ሩትና በዔዝ ባሉት ጥቂት ግለሰቦች እምነት ላይ ነው። |
| 3. ትኩረቱ በወንዶችና በኃጢአተኛነታቸው ላይ ነው። | 3. ትኩረቱ በሴቶችና በእግዚአብሔር ባላቸው እምነት ላይ ነው። |
| 4. እግዚአብሔር ሕዝቡን እንደሚቀጣ ያሳያል | 4. እግዚአብሔር፥ እምነታቸውን በእርሱ ላይ ለሚያደርጉ ሰዎች ታማኝ መሆኑን ያሳያል። |

መጽሐፈ ሩት የሚመደበው «አጭር ታሪክ» ተብሎ ከሚጠራ የሥነ-ጽሑፍ ዓይነት ነው። የታሪኩ ዓላማ ትልቅ የሃይማኖት መሠረታዊ ትምህርት ለማስተማር አይደለም፤ ነገር ግን በክፋት መካከል ሰዎች ሊኖራቸው የሚችለውን እምነትና በመታዘዝ ለሚከተሉት እግዚአብሔር ያለውን ታማኝነት ለማሳየት ነው። ታሪኩ፥ እውነተኛ እምነት ተራ በሆኑ በታማኝ የእግዚአብሔር ሰዎች ሕይወት ውስጥ ምን እንደሚመስል ይገልጣል።

32ኛ ጥያቄ፥ 1ኛ ቆሮ. 1፡18-31 አንብብ። ሀ) እነዚህ ጥቅሶች ተራ ሰዎችን በመጠቀም ውስጥ የእግዚአብሔር ዓላማ ምንድን ነው ይላሉ? ለ) እግዚአብሔር ይህንን የሚያደርገው ለምን ይመስልሃል? ሐ) ይህ በቤተ ክርስቲያንህ ውስጥ ሲፈጸም የምታየው እንዴት ነው? መ) በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በሀብታሞች ወይም በተማሩ ሰዎች ላይ ከፍተኛ ትኩረት ስለማድረግ ይህ ምን ያስተምረናል? ሠ) ብዙ ጊዜ ተራ ሰዎች እውነተኛ እምነትና ታላቅ መንፈሳዊነት ለጥቂት የተማሩ ሰዎች ብቻ ነው ብለው የሚያስቡት በምን መንገድ ነው? ረ) እግዚአብሔር የተራ ሰዎችን እምነት እንደሚያከብር መጽሐፈ ሩት ምን ያስተምረናል?

33ኛ ጥያቄ፥ ሩት 1-4 አንብብ። ሀ) የአቤሜሌክ ቤተሰብ ወደ ሞዓብ የሄደው ለምን ነበር? ለ) የሩትን እምነት ከዖርፋ እምነት ጋር አወዳድር። የሩት እምነት ታላቅ የሆነው እንዴት ነው? ሐ) ሩት ለኑኃሚን ታማኝ መሆኗን ያሳየችው እንዴት ነበር? መ) እግዚአብሔር ሩት ለኑኃሚን ያሳየችውን ታማኝነት ያከበረውና ዋጋ የሰጠው እንዴት ነበር? ሠ) ከዚህ ታሪክ በእግዚአብሔር ላይ ሊኖረን ስለሚገባ ታማኝነትና እግዚአብሔር ለልጆቹ ስላለው ታማኝነት ልንማር የምንችለው ነገር ምንድን ነው?

1. የሩት ታሪክ የተፈጸመበት ጊዜና ቦታ (ሩት 1)

መጽሐፈ ሩት የሚጀምረው ታሪኩ በዘመነ መሳፍንት ወቅት የተፈጸመ መሆኑን በመናገር ነው። በይሁዳ ግዛት ራብ እንደተነሣ ይናገራል። የዚህ መጽሐፍ ጸሐፊ ራብን የተጠቀመበት በአቤሜሌክ ቤተሰብ ላይ ስለመጣው ችግር ለመናገር ብቻ ሳይሆን፥ ሕዝቡ ከእግዚአብሔር ፍርድ በታች ስለመሆናቸውም ለማጋለጥ ነበር። ሕዝቡ ለእግዚአብሔር ባለመታዘዛቸው የራብን መርገም ጭምር እንደሚያመጣባቸው እግዚአብሔር አስቀድሞ ተናግሮአል (ዘዳ. 28፡23-24)።

የአቤሜሌክ ቤተሰብ ራቡን በመሸሽ ወደ ሞዓብ ሄደ። በዚያም ለብዙ ዓመታት ስለኖሩ፥ ሁለቱ ወንዶች ልጆቻቸው ሞዓባውያን የሆኑ ሴቶችን አገቡ፤ ነገር ግን ብዙም ሳይቆይ አቤሜሌክና ሁለቱ ልጆቹ ሞቱ።

የታሪኩ ዋና ትኩረት ኑኃሚን እንዴት ባዶና ድሀ እንደሆነች ለማሳየት ነው። ባልም ሆኑ ልጆችዋን አጣች። በእርጅናዋ ወራት እንክብካቤ የሚያደርግላት አንዳችም ወራሽ፥ ወይም ራሷን የምትደግፍበት መሬት አልነበራትም፤ ስለሆነም እጅግ ተማርራ ወደ ይሁዳ ለመመለስ ወሰነች። አንደኛዋ ምራቷ በሞዓብ ስትቀር፥ ሌላኛዋ ግን ማለትም ሩት አማትዋን ለመከተል አማልክትዋን፥ ቤተሰብዋንና አገሯን ሁሉ ተወች። ሩት በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ የሚገለጥ የታማኝ ፍቅር ምሳሌ ናት። ወደ እስራኤል ምድር እንደ እንግዳ ከመሄድ ይልቅ በአገሯ መቅረት፥ ከገዛ ሕዝቧ ጋር መኖር በቀለላትም ነበር።

2. ለኑኃሚንና ለሩት እንክብካቤ ለማድረግ እግዚአብሔር የሠራው ሥራ (ሩት 2-3)

በዚህ ታሪክ ውስጥ እግዚአብሔር የተጠቀሰበት ቦታ ብዙ ባይሆንም፥ በታሪኩ ሁሉ የእግዚአብሔርን እጅ እንድናይ ለማድረግ ጸሐፊው እንደሞከረ ግልጥ ነው። ሩት እንዴት ወደ አማቷ ዘመድ የእርሻ ቦታ እንደሄደች ተመልከት። የኑኃሚን ዘመድ የሆነው ቦዔዝ ለሩት ልዩ የሆነ ትኩረትና ጥንቃቄ እንዴት እንዳደረገ እንመለከታለን። እግዚአብሔር ቦዔዝ የቤተሰብ ግዴታውን ለመፈጸም ብሎ አሕዛብ የሆነች ሴት እንዲያገባ እንዴት እንደገፋፋው ተመልከት።

ታሪኩ የሚያተኩረው በሁለት ዋና ዋና ገጸ-ባሕርያት ታማኝነት በተሞላ ፍቅር ላይ ነው። በመጀመሪያ፥ ሩት ለኑኃሚን የነበራት በታማኝነት የተሞላ ፍቅር ነው። በሁለተኛው ደግሞ፥ ቦዔዝ ለሩትና ለኑኃሚን ያሳየው በታማኝነት የተሞላ ፍቅር ነው።

ነገር ግን ከሰው የታማኝነት ፍቅር ምሳሌነት ሁሉ በላይ እግዚአብሔር ለሁለት ድሀና ምስኪን ሴቶች የነበረውን ፍቅርና እንክብካቤ እናያለን።

3. እግዚአብሔር የሩትንና የቦዔዝን ታማኝነት በማክበርና ለእርሱ ዋጋ በመስጠት ለኑኃሚን በረከቱን መለሰላት (ሩት 4)

ከሩት ታሪክ በስተጀርባ የአይሁድ ባሕል የሆነ «የመዋጀት» ተግባር እናያለን። መመሪያው በዘዳግ. 25፡5-10 ይገኛል። በዚህ ስፍራ የእግዚአብሔር ሕግ የሚለው አንድ ሰው ልጅ ሳይኖረው ቢሞት፥ ወንድሙ የሞተውን ሰው ሚስት በመውሰድ ከሴቲቱ ልጅ መውለድ እንደነበረበት ነው። በዚህ መንገድ የሚገኘው ልጅ የሟች ወንድሙ ወራሽ ይሆን ነበር፤ ደግሞም በዘሌ. 25፡25-31፥ 41-55 ሕጉ በተጨማሪ ድሀ የሆነ ሰው በድህነት ምክንያት መሬቱን ቢሸጠው፥ የዚህ ድሀ ሰው ዘመድ ገንዘቡን በመክፈል መሬቱን ሊያስመልስና በባዕድ እጅ እንዳይገባ ሊከላከል ይገባ ነበር። የእነዚህ ሁለት ሕግጋት ዓላማ የአንድን ሰው የቤተሰብና የመሬት ወራሽነት ለመጠበቅ ነበር።

በመጽሐፈ ሩት፥ ይህ ሕግ በቅርብ ዘመድ ብቻ ሳይወሰን፥ በሩቅ ዘመድም ላይ የሚሠራ ሆነ። የመዋጀት ግዴታ የወደቀው በቅርብ ዘመድ ላይ ነበር። ይህ የቅርብ ዘመድ ግዴታውን ለመወጣት ፈቃደኛ ያልሆነ ወይም የማይችል ከሆነ ብቻ ኃላፊነቱ ወደ ሌላ ዘመድ ይተላለፍ ነበር። በዚሁ መሠረት ቦዔዝ ሩትን አገባና የአቤሜሌክና የልጆቹ ወራሽ የሚሆን ልጅ አስገኘ። ልጁ የአቤሜሌክ ምድር ወራሽ ሆነ፥ ቦዔዝ ደግሞ የአቤሜሌክ ምድር የተያዘበትን ዕዳ ሁሉ የመክፈል ግዴታ ነበረበት።

ይህ ከሩት ምዕራፍ 4 ታሪክ በስተኋላ የሚገኝ ባሕላዊ ልማድ ክፍል ነው። ቦዔዝ የኑኃሚን የቅርብ ዘመድ የሆነውን ሰው ይፋ ፍርድ ወደሚሰጥበት ስፍራ አመጣው። በጥንት ዘመን የጎሣ ሽማግሌዎች በከተማይቱ በር ላይ ይገናኙና በጉዳዮች ላይ ውሳኔ በመስጠት ይፈርዱ ነበር። ወደዚህ የፍርድ ስፍራ የመጣው የቅርብ ዘመድ ለሩት ያለበትን ግዴታ ለመወጣት ፈቃደኛ አለመሆኑን ገለጠ። ይህንን ለማድረግ ያልፈለገው፥ የራሱ ልጆች ቢሞቱ ቀሪው ወራሽ ከሩት የሚወለደው ልጁ ስለሚሆን፥ የራሱንም ንብረት ለመቆጠብ ሳይሆን አይቀርም። ይህ ዘመድ ከቦዔዝ የሚለይበት ነገር ቢኖር ስለራሱ ብቻ የሚያስብ ስስታም ስለ ነበር ነው።

ቦዔዝ ሩትን የማግባት ግዴታውን ተወጣ። በዚህም ኢዮቤድ የተባለ ልጅ አገኙ። በኃዘኗ ምክንያት በብቸኝነት ተቆራምዳ የነበረችው ኑኃሚን፥ የተባረከች ኑኃሚን ሆነች። የልጅ ልጅ ማግኘቷ ብቻ ሳይሆን ምድሪቱ ለእርሷ ተመለሰችላት! በእርጅናዋ ወራት የሚጦራትንም አገኘች።

በእግዚአብሔር ሉዓላዊ ጥበብ፥ የሩትና የቦዔዝ ልጅ የእስራኤል ታላቅ ንጉሥ የሆነው የዳዊት አያት ሆነ።

| |
|---|
| 34ኛ ጥያቄ፥ ስለ እግዚአብሔርና ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ስላለው ግንኙነት ከዚህ ታሪክ የተማርካቸው ዋና ዋና ነገሮች የትኞቹ ናቸው? |

## የመጽሐፈ ሩት ዋና ዋና ትምህርቶች

በመጽሐፈ ሩት ውስጥ በተደጋጋሚ የተጠቀሱ ሁለት ቁልፍ ቃላት ይገኛሉ። እነርሱም የመጽሐፉን ዋና ዋና ትምህርቶች የያዙ ናቸው።

1. መዋጀት፡- በዚህ ታሪክ መዋጀት የሚለውን ትርጉም የሚሰጠውን የዕብራይስጥ ቃል በተለያየ መልኩ 23 ጊዜ እናገኘዋለን። በመጽሐፈ ሩት «መዋጀት» የሚለው ቃል በተለይ ያገለገለው የአይሁድን የመቤዠት ባሕል ለመግለጥ ነው። ተቤዢው ለሟች ዘመዱ ወራሽ የሆነ ልጅ ለማሳደግ፥ ወይም ለችግረኛ ዘመዱ በችግር ምክንያት የሸጠውን መሬቱን ከፍሎ ለማስመለስ፥ ወይም በባርነት ሊወድቅ ላለ ዘመዱ ዋጋ ከፍሎ ከባርነቱ ለማስቀረት ወዘተ ፈቃደኛ የሆነ ነው ። ቦዔዝ ለሩትና ለኑኃሚን ተቤዢ ሆነ።

ቦዔዝ የእግዚአብሔርና የሕዝቡ የእስራኤል ግንኙነት ተምሳሌት ነበር። ቦዔዝ ኑኃሚንና ሩትን በድህነት ምክንያት ከነበረባቸው ባርነት ዋጃቸው (ተቤዣቸው)። ፍላጎታቸውን አሟላ። ልክ እግዚአብሔር እስራኤልን ከግብፅ ባርነት ነፃ እንዳደረገ ዓይነት ማለት ነው። እርሱ የእስራኤላውያንን ፍላጎት ሁሉ ያሟላ አምላክ ነው።

ቦዔዝ የክርስቶስ ኢየሱስ ተምሳሌት ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው ሆነ፥ በመሆኑም የእኛ ዘመድ ሆነ። እንደ ዘመድነቱ በመስቀል ላይ በመሞቱ፥ እያንዳንዳችንን ከኃጢአት ባርነት ዋጀን፤ (የሐዋ. 20፡28)፤ በዚህም የተቤዢነቱን ዓላማ አሟላ። ተቤዢያችን ክርስቶስን እኛን ከባርነት፥ ከመንፈሳዊ ጉስቁልና ለመዋጀት የሚከፈለውን ዋጋ ከፈለ። በዚህም የእግዚአብሔር ቤተሰብ አባላት አደረገን።

---

35ኛ ጥያቄ፥ የተቤዠህን ክርስቶስን ለማመስገን ጊዜ ይኑርህ።

---

2. በፍቅር የተሞላ ቸርነት፡- አይሁድ «ሂሴድ» የሚል ልዩ ቃል ነበራቸው። ይህ ቃል በብዙ ልዩ ልዩ መንገዶች ሊተረጎም ይችላል። አንዳንድ ጊዜ ለቃል ኪዳኑ ታማኝነት፥ አንዳንድ ጊዜ ርኅራኄ፥ ሌላ ጊዜ ፍቅር መሆን ይችላል።

የሩት ታሪክ እንዲህ ዓይነቱን በፍቅር የተሞላ ርኅራኄ ይገልጣል። ሩት እውነተኛ ተስፋ ባይኖርም እንኳ በፍቅር የተሞላ ርኅራኄና ቸርነት ለኑኃሚን ገለጠች። የኑኃሚንን ጉስቁልና በመካፈል በታማኝነት ለኑኃሚን የሚያስፈልገውን ነገር ሁሉ ለማድረግ ከእርሷ ላለመለየት መቁረጧን ገለጠች (2፡11-12)። ቦዔዝ ሩትን በእርሻ ስፍራው በመርዳት፥ ወራሾቹን አደጋ ላይ የሚጥል ቢሆንም እንኳ፥ እርሷን ለማግባት በመፍቀድ እንዲህ ዓይነቱን በፍቅር የተሞላ ቸርነትና ርኅራኄ ለሩትና ለኑኃሚን ገለጠ።

ከሁሉም በላይ ግን በታሪኩ ውስጥ የእግዚአብሔርን በፍቅር የተሞላ ቸርነትና ርኅራኄ እንመለከታለን (2፡20)። ከዚህ ታሪክ የምንመለከተው፥ እግዚአብሔር በእርሱ የሚታመኑትን ፍቅርን በተሞላ ቸርነትና ርኅራኄ እንደሚመለከታቸው ነው። በመጽሐፈ ሩት ውስጥ እግዚአብሔር በተለያዩ ስውር መንገዶች ለሕዝቡ ጥቅም ሲሠራ እንመለከታለን። ሩትን ወደ ቦዔዝ እርሻ መራት፤ ቦዔዝም እንዲራራላት አደረገ፤ ቦዔዝና ሩት እንዲጋቡም አደረገ። ቦዔዝ፥ ሩትንና ኑኃሚንን የታላቁ የእስራኤል ንጉሥ የዳዊት አያት በሆነ ልጅ ባረካቸው።

ምንም እንኳ የእግዚአብሔርን እጅ ሁልጊዜ በሥራ ላይ ባናየውም፥ እግዚአብሔር በማይታይ መንገድ ለእርሱ ታማኝ የሆኑ ሕዝቦችን ሁልጊዜ እንደሚረዳ እንመለከታለን። የሩት ታሪክ ሮሜ 8፡28ን ይገልጣል። «እግዚአብሔርንም ለሚወዱት እንደ አሳቡም ለተጠሩት ነገር ሁሉ ለበጎ እንዲደረግ እናውቃለን።»

| |
|---|
| 36ኛ ጥያቄ፥ ሀ) በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ሆነህ መከራን በምትቀበልበት ጊዜ፥ ይህ እውነት እንዴት ያጽናናሃል? ለ) ለእግዚአብሔርና ለሌሎች ባለህ ግንኙነት ታማኝ ስለመሆን አስፈላጊነት ይህ ታሪክ ምን ያስተምርሃል? |

5ኛ ቀን፡-

የዚህን ሳምንት ትምህርት ከልስና ለሳምንታዊ ስብሰባ ዝግጅት ይረዳህ ዘንድ የውይይት ጥያቄዎችን ተመልከት

## ሳምንታዊ ስብሰባ

1. ሳምንታዊ የአምልኮ ጊዜ

2. ጸሎት

3. የትምህርቱ ክለሳ

4. ውይይት

1. ሀ) በመጽሐፈ መሳፍንት፥ እስራኤላውያን እግዚአብሔር ከእነርሱ ጋር በሲና ተራራ ላደረገው ቃል ኪዳን ያልታዘዙት እንዴት ነበር? ለ) እግዚአብሔርን ለማክበርና ለመታዘዝ የገቡትን የተስፋ ቃል ለመጠበቅ ዛሬም ክርስቲያኖች የሚቸገሩት እንዴት ነው? ሐ) ብዙ ክርስቲያኖች ለኢየሱስ የነበራቸውን የመጀመሪያ ፍቅር ጥለው በመንፈሳዊ ሕይወት እየቀዘቀዙ የሚሄዱት ለምንድን ነው? መ) ክርስቲያኖች ፍቅራቸውንና ለክርስቶስ ያላቸውን መታዘዝ ሕያው አድርገው ሊጠብቁ እንዲችሉ ቤተ ክርስቲያንህ ምን ማድረግ ትችላለች?

2. ሀ) እግዚአብሔር እስራኤላውያን እንዲጨቁኑ የፈቀደው ለምንድን ነው? እስራኤላውያን አብረዋቸው በሚኖሩ ከነዓናውያን የተጎዱት እንዴት ነበር? ለ) ብዙ ክርስቲያኖች ዓለምን የሚመስሉት ለምንድን ነው? ሐ) ክርስቲያኖች ዓለምን የሚመስሉባቸውን መንገዶች በምሳሌነት ጥቀስ። መ) ይህ ብዙ ጊዜ በክርስቲያኖች ላይ ምን ዓይነት ችግር ያመጣል? ሠ) ክርስቲያኖች ከማያምኑ ሰዎች ጋር ሲኖሩ በእነርሱ ሳይበከሉ ብርሃንና ጨው ሆነው ሊኖሩ የሚችሉት እንዴት ነው? ረ) ክርስቲያኖች ይህንን ዓለም እንዳይመስሉ ለማስተማር በመጽሐፈ መሳፍንት እንዴት ልንጠቀምበት እንችላለን?

3. ሀ) በመጽሐፈ መሳፍንት ያለው እስራኤላውያን ደጋግመው ያለፉበት ዑደት ምን ነበር? ለ) ይህ ዑደት በቤተ ክርስቲያን ይታያልን? ከታየስ እንዴት?

4. ሀ) በመሳፍንት ያየነው የእግዚአብሔር ባሕርይ ምንድን ነው? ለ) ይህ እግዚአብሔርን የሚመለከት መግለጫ እግዚአብሔርን እንድንወድና እንድንፈራ እንዴት ያደርገናል?

5. ሀ) በዘመነ መሳፍንት የነበረውንና በዚህ ዘመን ያለውን የመንፈስ ቅዱስ ሥራ አወዳድር። የሚመሳሰለውና የሚለየው እንዴት ነው? ለ) ይህ መጽሐፍ ስለ መንፈስ ቅዱስ የሚሰጠው ትምህርት ዛሬ ብዙ ክርስቲያኖች ከሚያስተምሩት ትምህርት የሚለየው እንዴት ነው? ሐ) አንተም ሆንክ ቤተ ክርስቲያንህ ስለ መንፈስ ቅዱስ ያላችሁ አቋም ምንድን ነው? (መንፈስ ቅዱስ በሁሉም ክርስቲያኖች ውስጥ ይኖራልን? ራሱንስ በተለያዩ ስጦታዎች ይገልጣልን? ወዘተ.) ይህን አመለካከትህን ለማረጋገጥ ከመጽሐፍ ቅዱስ የምታቀርበው መረጃ ምንድን ነው?

6. ሀ) በችግር ጊዜ ስለሚኖር እውነተኛ እምነት ከሩት ምን እንማራለን? ለ) ቦዔዝ የተቤዠው ለክርስቶስ መቤዠት ተምሳሌት የሆነው እንዴት ነው?

5. ጸሎት

# ትምህርት 13

## 1ኛ ቀን፦የ1ኛ ሳሙኤል መግቢያ

የአንድ ሕዝብ፥ ወይም የአንድ ቤተ ክርስቲያን መሪ በተራ ሰዎች ሥነ - ምግባርም ሆነ መንፈሳዊ ዝንባሌ ላይ የሚጫወተው ሚና በጣም ከፍተኛ ነው። መሪው ብልሹ ከሆነ፥ ከሥሩ የሚተዳደሩ ሰዎችም የተበላሹ ይሆናሉ። መሪው አምላክ የለሽ ከሆነ፥ ሕዝቡም አምላክ የለሽ ይሆናሉ። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚሆነውም ልክ እንደዚሁ ነው። የቤተ ክርስቲያኒቱን መንፈሳዊ ሕይወት ደረጃ የሚወስነው የቤተ ክርስቲያኒቱ መሪ ነው። መሪው ስግብግብ ከሆነ፥ ወይም ጠንካራ መንፈሳዊ ሰው ካልሆነ፥ የቤተ ክርስቲያኒቱ አባሎችም ስግብግብና በመንፈሳዊ ሕይወታቸው የደከሙ ይሆናሉ። የቤተ ክርስቲያኒቱ መሪ እግዚአብሔርን የሚፈራ የጸሎት ሰው፥ ደግሞም የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማወቅ የእግዚአብሔርን ቃል የሚያጠና ሰው ከሆነ፥ የቤተ ክርስቲያኒቱ አባሎችም የጸሎት ሰዎች፥ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማወቅና ለማድረግ የሚፈልጉ ይሆናሉ። በማንኛውም ጊዜ የቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ ሕይወት ዝቅ ሲል፥ ብዙ ጊዜ ችግሩ ያለው ከቤተ ክርስቲያኒቱ መሪዎች መንፈሳዊ ሕይወት ላይ ነው። የእግዚአብሔርን ፈቃድ በሙሉ ለማወቅና ለማድረግ ወሳኝ የሆኑ መልካም መንፈሳዊ መሪዎች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እስከሌሉ ድረስ ቤተ ክርስቲያኖቻችን ደካማና ውጤት የማያስገኙ ይሆናሉ።

1ኛ ጥያቄ፥ ሀ) የአንድ አገር መሪ የሥነ - ምግባር ሕይወት፥ በሚመራው አገር የሥነ -ምግባር ሕይወት ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድረው እንዴት ነው? ለ) የአንዲት ቤተ ክርስቲያን መሪ ሥነ - ምግባርና መንፈሳዊ ሕይወት በአባላቱ ሥነ - ምግባርና መንፈሳዊ ሕይወት ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድረው እንዴት ነው? ሐ) ይህ ነገር በቤተ ክርስቲያን መሪ የሚሆኑ ሰዎችን በከፍተኛ ጥንቃቄ ስለመምረጥ የሚያስተምረን ምንድን ነው?

2ኛ ጥያቄ፥ 1ኛ ጢሞ. 3፡17 አንብብ። ሀ) እግዚአብሔር በቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሕይወት ውስጥ ሊያይ የሚፈልጋቸውን የተለያዩ ባሕርያት ዘርዝር። እነዚህን ባሕርያት ለሦስት ከፈላቸው፡- ከመጽሐፍ ቅዱስ እውቀት ጋር የሚያያዙትን፥ ከመሥራት ችሎታ ጋር የሚያያዙትንና ከሥነ - ምግባርና ከመንፈሳዊ ሕይወት ጋር የሚያያዙትን። ለ) ከእነዚህ ከሦስት ክፍሎች፥ በርካታ ባሕርያት ያሉት በየትኛው ሥር ነው? ሐ) እግዚአብሔር ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ካለን እውቀትና ከመሥራት ችሎታችን በላይ ሥነ - ምግባርና በመንፈሳዊ ሕይወታችን ላይ የሚያተኩረው ለምን ይመስልሃል? መ) የቤተ ክርስቲያን አባላት መሪዎቻቸውን በሚመርጡበት ጊዜ በአብዛኛው መመዘኛቸው ምንድን ነው? ሠ) እግዚአብሔርን ለሚፈራ አንድ መሪ እነዚህ መልካም ባሕርያት ናቸው ወይስ አይደሉም? ማብራሪያ ስጥ።

መጽሐፈ ሳሙኤል ስለ እግዚአብሔር ሕዝብ መሪዎች የሚናገር መጽሐፍ ነው። በተለይ የሚያተኩረው የእግዚአብሔርን ሕዝብ በመልካም አመራር ስላልመሩ ሰዎች ነው። ልጆቹን በሚገባ ለመቆጣጠር ባለመቻሉ ምክንያት የእግዚአብሔርን አምልኮ ያበላሸው ካህኑ ዔሊ ነበር። መልካምና እግዚአብሔርን የሚፈራ ሰው ቢሆንም፥ ዳሩ ግን እንደ ዔሊ ልጆቹን መቆጣጠር ያልቻለ ሳሙኤል ነበር። በመጨረሻም ለእግዚአብሔር በሙላት ባለመታዘዙ ሕዝቡን ይመራ ዘንድ እግዚአብሔር የናቀውን የመጀመሪያውን ንጉሥ ሳኦልን እናያለን። ይህ መጽሐፍ በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ መሪ ለሆንን ሰዎች የእግዚአብሔርን ሕዝብ እንዴት መምራት እንዳለብንና እንዴትስ መምራት እንደሌለብን የሚያሳዩ በርካታ ምሳሌዎችን ይሰጠናል።

## የመጽሐፉ ርእስ

ቀደም ሲል በነበረው የዕብራይስጡ መጽሐፍ ቅዱስ፥ መጽሐፈ ሳሙኤል ዛሬ በእጃችን እንዳለው 1ኛና 2ኛ ተብሎ የተከፈለ ሳይሆን፥ አንድ መጽሐፍ ነበር። ይህንን ታሪክ በተለያዩ ምክንያቶች የተነሣ ለመጻፍ የፈለገ አንድ ጸሐፊ ያለ ይመስላል። በኋላ የዕብራይስጡ ብሉይ ኪዳን ወደ ግሪክ ቋንቋ ሲተረጎም (ሴፕቱዋጀንት የሚለው ትርጉም ማለት ነው) አንድ የነበረው ሳሙኤል፥ 1ኛና 2ኛ ሳሙኤል

በመባል ለሁለት ተከፈለ። በዘመናችን ያሉ አብዛኛዎቹ መጽሐፍ ቅዱሶች አንድ ወጥ መጽሐፍ ከመሆን ይልቅ 1ኛና 2ኛ ሳሙኤል ተብለው የተከፈሉ ሁለት መጻሕፍት አሏቸው።

የ1ኛና 2ኛ ሳሙኤል ርዕስ የተሰጠው ታሪኩን በ1ኛ ሳሙኤል ከምናገኘው እግዚአብሔርን ከሚፈራ ከአንድ ሰው ነው። መጽሐፉ የተሰየመው ከመሳፍንት ወደ ነገሥታት ዘመን በነበረው የሽግግር ዘመን ይኖር በነበረ ሳሙኤል በተባለ ሰው ስም ነው። ሳሙኤል ካህን፥ ነቢይና ከዔሊ ጀምሮ እስከ መጀመሪያው የእስራኤል ንጉሥ፥ እስከ ሳኦል ድረስ በእስራኤል ላይ በመፍረድ ያገለገለ መስፍን ነበር። መጽሐፉ በሳሙኤል ስም የተሰየመው፥ ይህ ሰው በእስራኤል ታሪክ ውስጥ የሚቀጥለው ተከታይ የታሪክ ዘመን በሆነው፥ በሳኦል፥ በዳዊትና በሰሎሞን መሪነት ሥር የነበረውን አንድ የተባበረ የእስራኤል መንግሥት ታሪክ ጀማሪ መሆኑን ዕብራውያን ስላመኑበት ስለተገነዘቡ ነበር። ሳሙኤል የነገሥታትን ዘመን ለማስተዋወቅ በእግዚአብሔር የተመረጠ መሪ ነው።

---

3ኛ ጥያቄ፥ «ሳሙኤል» የሚለውን ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት ውስጥ ተመልከት። የሳሙኤልን የሕይወት ታሪክ ባጭሩ ጻፍ።

---

## የ1ኛና የ2ኛ ሳሙኤል ጸሐፊ:-

የ1ኛና የ2ኛ ሳሙኤል መጻፍ በሁለት ደረጃዎች የተከናወነ ሳይሆን አይቀርም። አንደኛ፥ አንዳንድ ጸሐፊዎች የታሪክ መጻሕፍትን ወይም የነገሥታትን ዘገባ ድርጊቱ በተፈጸመበት ዘመን አካባቢ ጽፈዋል። ሁለተኛ፥ አንድ ያልታወቀ ጸሐፊ የተለያዩ የታሪክ መጻሕፍትን ከሰበሰበ በኋላ አንዳንድ ታሪኮችን መርጦ የአሁኖቹን የ1ኛና 2ኛ ሳሙኤል መጻሕፍት ጽፎአል።

አንዳንድ ሰዎች የነቢዩ ናታን ልጅ የነበረውና የንጉሥ ሰሎሞን የግል አማካሪ ሆኖ የሠራው ዛቡድ መጽሐፈ ሳሙኤልን ጽፏል ብለው ይገምታሉ (1ኛ ነገሥ. 4:5)፤ ነገር ግን ከሁሉም የሚሻለው የ1ኛና 2ኛ ሳሙኤል ጸሐፊ ማን እንደሆነ አይታወቅም ማለቱ ነው። ሳሙኤል ነው የጻፈው ለማለት አይቻልም፤ ምክንያቱም የ1ኛ ሳሙኤል

መጨረሻ አካባቢና የ2ኛ ሳሙኤል ታሪክ በሙሉ የተፈጸመው እርሱ ከሞተ በኋላ በመሆኑ ነው።

ጸሐፊው ማንም ይሁን ማን፥ የዳዊትንና በጥንት ዘመን የተፈጸሙ ታሪካዊ ድርጊቶችን ሁሉ ለማወቅ የሚያስችሉ የቤተ መንግሥት መዛግብትን ለማግኘት የቻለ ሰው ነበር። ማለትም ስለ እነዚህ ጊዜያት የተጻፉ ነገሮችን ሁሉ ለማግኘት ዕድል የነበረው ሰው ነው። ቢያንስ ቢያንስ ያሻር የተባለውን መጽሐፍ እንደምንጭ ለመጠቀሙ እርግጠኞች ነን (2ኛ ሳሙ. 1፡18)። በዚያን ጊዜ ቢያንስ አራት መጻሕፍት እንደነበሩ መጽሐፍ ቅዱስ ይመሰክራል። እነርሱም የሳሙኤል፥ የናታን፥ የጋድና የንጉሥ ዳዊት መጻሕፍት በመባል የሚታወቁ ናቸው (1ኛ ዜና 27፡24)። «ስለ ይሁዳ መንግሥት» (1ኛ ሳሙ. 27፡6) ስለሚናገር፥ የመጽሐፈ ሳሙኤል ጸሐፊ ከሰሎሞን ሞት በኋላ የኖረ መሆን አለበት። ይህ ሐረግ «የይሁዳ መንግሥት የሚለው» ሰሎሞን ከሞተና መንግሥቱ ለሁለት ከተከፈለ በኋላ ብቻ አገልግሎት ላይ የዋለ አጠቃቀም ነው።

## መጽሐፈ ሳሙኤል የተጻፈበት ጊዜ

የ1ኛና የ2ኛ ሳሙኤል ጸሐፊ ማን እንደሆነ ስለማናውቅ፥ እነዚህ መጻሕፍት የተጻፉት መቼ እንደሆነም አናውቅም። ጸሐፊው አሪት ዘዳግምን የጻፈው ሰው ነው ብለው የሚያምኑ ሰዎች (ስለ አሪት ዘዳግም ታሪክ ከዚህ ቀደም የተሰጠውን አሳብ ተመልከት) መጽሐፉ የተጻፈው የይሁዳ ሕዝብ ከተማረኩ በኋላ ነው ይላሉ።

ነገር ግን አብዛኞዎቹ ምሁራን መጽሐፉ የተጻፈው ከዚህ በጣም ቀደም ብሎ ነው ብለው ያምናሉ።

ስለዚህ 1ኛና 2ኛ ሳሙኤል የተጻፈው፥ ሰሎሞን በ930 ዓ.ዓ. ከሞተና የእስራኤል መንግሥት ይሁዳና እስራኤል ተብሎ ለሁለት ከተከፈለ በኋላ ሳይሆን አይቀርም።

## የመጽሐፈ ሳሙኤል ታሪክ የተፈጸመበት ጊዜ ሥረ - መሠረት

የ1ኛና 2ኛ ሳሙኤል ታሪክ በተፈጸመበት ጊዜ በደቡብ የሚገኘው የግብፅ መንግሥትም ሆነ፥ በሰሜን የሚገኘው የአሦር መንግሥት

በጣም ጠንካራ አልነበሩም። ከነዓንን ከ1113-1074 ዓ.ዓ. የተቆጣጠሩት አሦራውያን፥ በአሦር በተነሣው ዓመፅ ምክንያት በከነዓን ላይ የነበራቸውን የመቆጣጠር ኃይል አጥተው ነበር። ውጤቱም የከነዓን ምድር በውጭ ኃይሎች አለ መገዛት ሆነ። በእነዚህ ዓመታት ውስጥ በከነዓን ምድር በተለያዩ መንግሥታትና በእግዚአብሔር ሕዝብ መካከል የሚካሄድ የማያቋርጥ ጦርነት ስለነበረ፥ እስራኤላውያን ቀስ በቀስ በከፍተኛ ደረጃ ምድሪቱን ተቆጣጠሩ።

የ1ኛ ሳሙኤል ታሪክ በተፈጸመበት ጊዜ የነበሩት ጠንካራ ሕዝቦች ፍልስጥኤማውያን ነበሩ። እንደምታስታውሰው፥ ፍልስጥኤማውያን «የባሕር ሰዎች» በመባል የሚታወቁ ከሜዲትራኒያን ባሕር ደሴቶች የመጡ ሰዎች ነበሩ። የፍልስጥኤም ምድር አምስት ከተሞች በነበራቸው አምስት የተለያዩ ክፍሎች የተከፈለ ነበር። እያንዳንዱም የራሱ ዋና ከተማ ነበረው። እነርሱም አዛጦን፥ ጋዛ፥ አስቀሎና፥ ጌትና አቃሮን በመባል የሚታወቁ ነበሩ (1ኛ ሳሙ. 6፡17)። እያንዳንዱ ከተማ ከሌሎች የፍልስጥኤም ከተሞች ተለይቶ ራሱን ችሎ በአንድ ጌታ ወይም ንጉሥ ይተዳደር ነበር። እነዚህ ከተሞች በመተባበር በአንድነት ይዋጉ የነበሩት የጋራ የሆነ ጠላታቸውን በጦርነት በሚገጥሙበት ጊዜ ብቻ ነበር። ፍልስጥኤማውያን ኃያል የሆኑበት ምሥጢር የእስራኤል ሕዝብ የማያውቀውን የብረት ሥራ ስለሚያውቁ ነበር (1ኛ ሳሙ. 13፡19-22)፤ ስለሆነም እስራኤላውያን ለብረት መሣሪያዎች (ለምሳሌ ማረሻ) በፍልስጥኤማውያን ላይ ይደገፉ ነበር፤ በዚህ ምክንያት ለውጊያ የሚሆን እንደሰይፍና የመሳሰሉት አልነበራቸውም በዔሊ፥ በሳሙኤልና በሳኦል ዘመን የእስራኤላውያን ዋነኛ ጠላቶች ፍልስጥኤማውያን ነበሩ። እነርሱም አብዛኛውን የከነዓንን ምድር ተቆጣጥረው ነበር። ዳዊት እስኪነሣና እስራኤላዊያን የራሳቸውን የጦር መሣሪያ ማበጀት እስከሚማሩበት ጊዜ ድረስ የፍልስጥኤማውያንን ኃይል ለመበተን አልተቻለም ነበር።

ፍልስጥኤማውያን እስራኤላውያንን መጨቆናቸውን እየቀጠሉ ስለሄዱ በዔሊና በሳሙኤል ዘመን ሁለት ነገሮች ተፈጸሙ። የመጀመሪያው የተለያዩ የእስራኤል ነገዶች የበለጠ መተባበር በመጀመራቸው፥ በመጨረሻ በአንድ ንጉሥ ወደ መመራት

መራቸው። ይህ አንድነት የሆነው በሳኦል፥ በዳዊትና በሰሎሞን ዘመን መንግሥት ነበር። ከሰሎሞን ሞት በኋላ መንግሥቱ ለሁለት ተከፈለችና የሰሜኑ መንግሥት እስራኤል የደቡቡ መንግሥት ይሁዳ ተባለ። ሁለተኛው፥ ነገዶቹ ሁሉ በአንድነት የሚተባበሩበትና ከጠላቶቻቸው ጥበቃን የሚያገኙበት ሁኔታ የሚፈጥር አንድ የተለየ ሰው ማለትም ንጉሥ አስፈለጋቸው (1ኛ ሳሙ. 8፡20)።

ሊቋቋሙአቸው የሚችል አንዳችም ታላቅ መንግሥት በሌለበት በዳዊትና በሰሎሞን አመራር፥ የእስራኤል ሕዝብ ከግብፅ ድንበር ጀምሮ እስከ ኤፍራጥስ ወንዝ ድረስ ያለውን ክልል በሙሉ በመቆጣጠር፥ እጅግ በጣም ሰፉ። ይህም እግዚአብሔር ለአብርሃም የሰጠው ተስፋ ክፍል ነበር (ዘፍ. 15፡18-21)።

| |
|---|
| 4ኛ ጥያቄ፥ ሀ) እግዚአብሔር ለአብርሃም የሰጠውን ተስፋ ለመፈጸም የዓለምን ክስተቶች የተቆጣጠረው እንዴት ነው? ለ) ከዚህ ነገር ስለ እግዚአብሔር ምን እንማራለን? ሐ) ይህ ዛሬ የሚያጽናናን እንዴት ነው? |

## የ1ኛ ሳሙኤል አራት ዓላማዎች

1. የእስራኤል መንግሥት በአንድ ንጉሥ የሚተዳደርበት ሁኔታ እንዴት እንደተፈጠረ ለማሳየት ነው። 1ኛ ሳሙኤል ከተጻፈባቸው ምክንያቶች አንዱ የእስራኤል ሕዝብ ጊዜያዊ በሆኑ መሳፍንት መገዛቱ ቀርቶ በአንድ ንጉሥ የሚተዳደርበት ሁኔታ እንዴት እንደተፈጠረ ለመመዝገብ ነው።

እንደምታስታውሰው፥ መጽሐፈ መሳፍንት የሚያተኩረው የእስራኤል ሕዝብ ያለማቋረጥ የተገዙበትና ለእግዚአብሔር ሕዝብ የሥነ - ምግባር ብልሹነት አንዱ ምክንያት ንጉሥ ባለመኖሩ እንደ ነበር ለማሳየት ነው (መሳ. 21፡25)።

1ኛ ሳሙኤል ሕዝቡ በላያቸው የሚሠለጥን ንጉሥ ማግኘት እንዴት እንደጀመሩ ያሳየናል። በተጨማሪ አንድ ንጉሥ እንደ እግዚአብሔር ልብ ካልሆነ፥ ጠላቶቹን ሊያሸንፍና የእግዚአብሔርን ሕዝብ የሥነ - ምግባርና መንፈሳዊ ሕይወት ሊያሳድግ እንደማይችል ያሳየናል።

5ኛ ጥያቄ፥ ይህ ዛሬም በቤተ ክርስቲያን እውነት የሆነው እንዴት ነው?

2. የዳዊት ንጉሥነት ሕጋዊ እንደ ነበረና በሳኦል ላይ በተደረገ ዓመፅ፥ ወይም ዳዊት ከሳኦል ላይ የቀማው መንግሥት እንዳልሆነ ለማሳየት ነው።

የመጽሐፈ ሳሙኤል ጸሐፊ ዳዊትን በዙፋን ላይ በማስቀመጥ በእስራኤል ሁሉ እንዲነግሥ ያደረገ እግዚአብሔር እንደሆነ ለማሳየት ከፍተኛ ጥንቃቄ አድርጓል። የዳዊት ወደ ሥልጣን መውጣት ሳኦልን ለማስወገድ ባደረገው የትኛውም ዓይነት ጥረት አልነበረም። በ1ኛ ሳሙኤል ታሪክ እግዚአብሔር ዳዊትን እንደመረጠው በተደጋጋሚ እናነባለን። በተጨማሪም ሳኦል ሊገድለው የሚችልበት ብዙ ሁኔታ በተፈጠረ ጊዜ እንኳ፥ ዳዊት የመንግሥቱን ሥልጣን ከሳኦል በኃይል ለመውሰድ በፍጹም እንዳልፈቀደ በተደጋጋሚ እናነባለን።

3. እግዚአብሔር ከዳዊት ጋር እንዴት ቃል ኪዳን እንደመሠረተ ለማሳየት ነው። ይህ የ2ኛ ሳሙኤል ትኩረት ቢሆንም፥ የቃል ኪዳኑን አመሠራረት መነሻ የምናገኘው በ1ኛ ሳሙኤል ነው። እነዚህ ሁለት መጻሕፍት ቀድሞውኑ በአንድነት ያሉ፥ አንድ መጽሐፍ መሆናቸውን አስታውስ። የጋራ ትኩረታቸው እግዚአብሔር ከዳዊት ጋር ባደረገው ቃል ኪዳን ላይ ሲሆን፥ ቃል ኪዳኑም ዳዊትና ዘሩን የእስራኤል ሕዝብ ሕጋዊ ነገሥታት ለመሆን የሚያበቁ እንደነበሩ የሚገልጥ ነው።

4. እግዚአብሔርን ያሳዘነውንና ለእግዚአብሔር ክብር ያመጣውን ሁለት ዓይነት ንግሥና ለማወዳደር ነው። መጽሐፈ ሳሙኤል የሕዝቡ እውነተኛ ንጉሥ የመሆን ሥልጣን ያለው እግዚአብሔር እንደሆነ ይናገራል (1ኛ ሳሙ. 8፡7፤ 12፡12)። እግዚአብሔር የሕዝቡ እውነተኛ መሪ ስለነበር፥ እስራኤላውያን እርሱን በመታዘዝ ሊኖሩ ይገባ ነበር። ከእውነተኛ ንጉሥ (ከእግዚአብሔር) ይልቅ፥ የሰዎችን ነገሥታት ለእርዳታ መፈለግ በእግዚአብሔር ላይ የሚደረግ ዓመፅ ነበር። ምድራዊ ንጉሥ በሰማያዊው ንጉሥ

በእግዚአብሔር ሥልጣን ሥር ሊገዛ እንጂ የእግዚአብሔርን የአመራር ስፍራ ሊተካ አልተፈቀደም፤ ደግሞም አይችልም።

እግዚአብሔር ምድራዊ ንጉሥ እንዳይኖር አልከለከለም። ከብዙ ዓመታት በፊት ነገሥታት ከአብርሃም የዘር ግንድ እንደሚመጡ ተስፋ ሰጥቷል (ዘፍ. 17፡6)። ሙሴም ስለ እስራኤል ነገሥታት ግልጽ የሆኑ ትእዛዛትን ሰጥቷል (ዘዳ. 17፡14-20)። እስራኤላውያን ንጉሥ በመፈለጋቸው ሂደት ውስጥ፥ እግዚአብሔር ያልወደደላቸው የፈለጉበት ምክንያት ስሕተት ስለሆነ ነበር። ሰማያዊ የሆነውን ንጉሥ ሳይታዘዙ ምድራዊው ንጉሥ ነፃ የሚያወጣቸው መስሎአቸው ነበር። እንደዚሁም ንጉሥ የፈለጉት፥ ዓለምን ለመምሰል ነበር።

| |
|---|
| 6ኛ ጥያቄ፥ ሀ) ዛሬም በዚህ ዘመን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መሪዎች ያስፈልጋሉ የሚያስበሉት የተሳሳቱ ምክንያቶች የትኞቹ ናቸው? ለ) በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ስላለ አመራር በዓለም በተሳሳተ መንገድ ተጽዕኖ ሊደረግብን የሚችልባቸውን መንገዶች ዘርዝር (ለምሳሌ፡- ትምህርት፥ የዘር ውርስ፥ የቤተሰብ ውርስ)። |

የመጀመሪያው የእስራኤል ንጉሥ፥ ሳኦል በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ የተሾመ የተሳሳተ ዓይነት መሪ ወይም ንጉሥ ምሳሌ ነው። ሳኦል ጅማሬው መልካም ነበር። በእግዚአብሔር ተመርጦ በመንፈስ ቅዱስ ተቀብቶ ነበር። በእግዚአብሔር ሕዝብ ጠላቶች ላይ ድልን አግኝቶ ነበር፤ ነገር ግን በሰማያዊው ንጉሥ ትእዛዝ ስላልሄደ፥ በሌላ ንጉሥ ተተካ። አለመታዘዙም ለቤተሰቡ መፍረስ፥ ለራሱም ሞት አመጣበት።

ሁለተኛው የእስራኤል ንጉሥ ዳዊት፥ በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ የተሾመ የመልካም መሪ ምሳሌ ነበር። ስለሆነም በ1ኛና 2ኛ ነገሥት በተደጋጋሚ፥ ፈለጉን መከተል የሚያስፈልግ የእስራኤል ንጉሥ እንደነበረ ተጠቅሷል (2ኛ ነገ. 14፡ 3፤ 22፡2፤ 2ኛ ዜና 13፡3፤ 28፡1 ተመልከት)። ዳዊትም የተመረጠው በእግዚአብሔር ነበር። በእግዚአብሔር ላይ የነበረው የማያቋርጥ እምነት በእግዚአብሔር ጠላቶች ላይ ታላቅ ድልን እንዲቀዳጅ አደረገው። በ2ኛ ሳሙኤል ወደፊት እንደምንመለከተው ግን፥ በኋላ በሕይወቱ በተከሰተው አለመታዘዝ ለእስራኤልና ለቤተሰቡ ታላቅ ቅጣትን አስከትሏል።

በሳኦልና በዳዊት መካከል የነበረው ዋና ልዩነት ዳዊት መታዘዙና ሳኦል አለመታዘዙ አልነበረም፤ ነገር ግን ዳዊት አለመታዘዙን በተገነዘበ ጊዜ ፈጥኖ ንስሐ መግባቱ ሲሆን፥ ሳኦል ግን ለፈጸመው ተግባር ሁልጊዜ ማመካኛ ለመስጠት መሞከሩ ነበር።

| |
|---|
| 7ኛ ጥያቄ፥ መሪዎች ኃጢአት ወይም አንድ የተሳሳተ ነገር በሚፈጽሙበት ጊዜ ለስሕተታቸው ማመካኛ ከመስጠት ይልቅ ይቅርታ ስለመጠየቃቸው አስፈላጊነት ይህ ምን ያስተምረናል? |

የ1ኛ ሳሙኤል ዋና ትኩረት በሳኦል ላይ ሳይሆን በዳዊት ላይ ነበር። አብዛኛው ታሪክ በሳኦልና በዳዊት መካከል የነበረውን ተቃርኖ የሚያሳይ ነው። 2ኛ ሳሙኤል በሙሉ ስለ ዳዊት የሚናገር ነው። ከእስራኤል ነገሥታት ሁሉ መጽሐፍ ቅዱስ የበለጠ የሚናገረው ስለ ዳዊት ነው፤ ምክንያቱም ዳዊት ሌሎቹ ነገሥታት ሁሉ ምሳሌነቱን ሊከተሉት የሚገባ እግዚአብሔርን የሚፈራ መሪ ነበር። በተጨማሪ ዳዊት የእርሱ ልጅ የሆነው በፍጹም ጽድቅና ቅድስና የሚገዛው፥ ሊመጣ ያለው መሲሕ፥ የንጉሡ የኢየሱስ ክርስቶስ አምሳያ ነበር።

የ1ኛና የ2ኛ ሳሙኤል መዋቅር

የ1ኛና የ2ኛ ሳሙኤል ጸሐፊ አንድ እንደሆነ ተመልክተናል፤ ስለዚህ በመጽሐፉ ውስጥ ተመሳሳይ የሆኑ ዓላማዎችና የአጻጻፍ ስልቶችን መጠበቃችን ትክክል ነው። የሳኦልና የዳዊትን ታሪክ ማወዳደር ትኩረትን የሚስብ ነው፤ በ1ኛ ነገሥት ውስጥ የሚገኘው የሰሎሞን ታሪክም እንደዚሁ ነው። መጻሕፍቱን በቅርበት በምንመረምርበት ጊዜ፥ ጸሐፊዎቹ ሕይወታቸውንና የእርሱንም ውጤት በማወዳደር ለማመልከት እንዴት ተመሳሳይ መዋቅር እንደተጠቀሙ እንረዳለን። ሕይወታቸውን የሚያነጻጽረውን የሚቀጥለውን ሠንጠረዥ ተመልከት፡-

| | ሳኦል | ዳዊት | ሰለሞን |
|---|---|---|---|
| እንዴት እንደተቀቡ(እንደተሾሙ) | 1. በሳሙኤል አቀባበል<br>2. ሕዝቡ ፈጣን አቀባበል አደረገለት<br>3. በመንፈስ ቅዱስ | 1. በሳሙኤል<br>2. ሕዝቡ እስኪቀበለው ረጅም ጊዜ ወሰደበት<br>3. በመንፈስ ቅዱስ | 1. በዳዊት<br>2. በካህኑ ሰዶቅና በነቢዩ ናታን<br>3. ሕዝቡ ወዲያውኑ ተቀበለው |
| ስኬታማነት | በአሞናውያን ላይ ድልን አገኘ | 1. ኢየሩሳሌምን ወሰደ<br>2. ፍልስጥኤማውያንን አሸነፈ<br>3. ታቦቱን ወደ ኢየሩሳሌም ወሰደ<br>4. ከእግዚአብሔር ጋር ቃል ኪዳን አደረገ<br>5. መንግሥቱን አስፋፋ | 1. ጥበብን ለመነ<br>2. ብልህ አስተዳደርን አደረገ<br>3. ቤተ መቅደስና ቤተ መንግሥቱን ሠራ |
| ውድቀት | 1. ያልተፈቀደለትን መሥዋዕት አቀረበ<br>2. ሕዝቡን በተሳሳተ መሐላ ውስጥ እንዲገባ አደረገ<br>3. ስለ አማሌቃውያን እግዚአብሔር የሰጠውን ትእዛዝ ሳይፈጽም ቀረ | 1. ዝሙት ፈጸመና ነፍስ ገደለ<br>2. በተሳሳተ ምክንያት የሕዝብ ቆጠራ አስደረገ<br>3. ልጆቹን አልተቆጣጠረም | 1. ብዙ ባዕዳን ሚስቶችን አገባ<br>2. ጣዖትን አመለከ<br>3. ሕዝቡን በከባድ ሥራና በከፍተኛ ቀረጥ (ግብር) አስጨነቀ |
| የውድቀቶቹ ውጤት | 1. ንጉሥነቱን ተቀማ<br>2. በፍልስጥኤማውያን ተሸነፈ<br>3. የቤተሰብ ሞት አጋጠመው<br>4. ራሱን ገደለ | 1. በልጆቹ መካከል ደም መፍሰስ ሆነ (አምኖን፥ አቤሴሎምና አዶንያስ በሙሉ ሞቱ)<br>2. ልጆቹ አመፁበት<br>3. በሕዝብ ቆጠራው ምክንያት ብዙ እስራኤላውያን ሞቱ | 1. በዳዊት ተሸንፈው የተገዙትን ሕዝቦች መቆጣጠር አቃተው<br>2. ከሞተ በኋላ የእሥራኤል መንግሥት ለሁለት ተከፈለ |

ከሠንጠረዡ እንደምትመለከተው፥ የሦስቱም ነገሥታት ታሪክ የሚጀምረው ሦስቱም ወደ ሥልጣን የመጡበትን ወይም የተመረጡበትን ሁኔታ በመግለጥ ነው። ቀጥሎም የሠሯቸው አንዳንድ መልካም ነገሮች ተጠቅሰዋል። ታሪኮቹ ሁሉ ደግሞ የሚያጠቃልሉት ኃጢአት በሕይወታቸው ስላመጣው ነገር በመናገር ነው።

---

8ኛ ጥያቄ፥ ከዚህ ሠንጠረዥ ስለ አመራር የምንማረው ነገር ምንድን ነው?

---

## የ1ኛ ሳሙኤል አስተዋጽኦ

1. የዔሊና የሳሙኤል ታሪክ (1-7)

   ሀ. የሳሙኤል መወለድ (1-2፡11)

   ለ. በዔሊና በቤተሰቡ ላይ የተፈጸመ ፍርድ (2፡12-4፡22)

   ሐ. ነቢይና ፈራጅ የሆነው ሳሙኤል (5-7)

2. የንጉሥ ሳኦል ታሪክ (8-15)

   ሀ. ሕዝቡ ንጉሥ እንዲያነግሥላቸው እግዚአብሔርን ጠየቁ (8)

   ለ. ሳኦል ለንጉሥነት ተመረጠ (9-10)

   ሐ. በአሞናውያን ላይ የተገኘ ድል (11፡1-13)

   መ. እስራኤላውያን ከእግዚአብሔር ጋር የነበራቸውን ቃል ኪዳን አደሱ (11፡14-12፡25)

   ሠ. የሳኦል አለመታዘዝና እግዚአብሔር እንደናቀው (13-15)

3. የዳዊት መነሣትና የሳኦል ዘመነ መንግሥት ፍጻሜ (16-31)

   ሀ. ዳዊት በሳሙኤል ተቀባ (16)

   ለ. ዳዊት በሳኦል መንግሥት ውስጥ አገለገለ (17-20)

   ሐ. ሳኦል ዳዊትን ለመግደል ሞከረ (21-26)

   መ. የሳኦል ሽንፈትና ሞት (27-31)

## የ1ኛና የ2ኛ ሳሙኤል የጊዜ ቀደም ተከተል

የዔሊ፥ የሶምሶን፥ የሳኦልና የዳዊትን የጊዜ ቅደም ተከተል በእርግጠኝነት ማወቅ አስቸጋሪ ነው፤ ምክንያቱም ስለ ጊዜያት የሚናገሩ ጥቅሶች በጣም ጥቂት ናቸው። አንዳንዶቹ በእነዚህ መጻሕፍት የተጻፉ ታሪኮች ለጸሐፊው ዓላማ ሲባል በአንድነት የቀረቡ እንጂ የጊዜ ቅደም ተከተላቸው የተጠበቀ አይደለም ይላሉ። አንዳንዱም ምሁራን ዔሊ የሞተው ሶምሶን መሥራት በጀመረበት ጊዜ አካባቢ በ1075 ዓ.ዓ. ነው ይላሉ። ሶምሶን የሠራው ከ1075-1055 ዓ.ዓ. ነው ይላሉ። ሳሙኤል የተወለደው በ1105 ዓ.ዓ. ሲሆን እስከ 1022 ዓ.ዓ. ድረስ ኖሯል። ይህ ማለት ሶምሶንና ሳሙኤል የኖሩትና ያገለገሉት በተመሳሳይ ጊዜ ነው ማለት ነው። የሳሙኤል፥ የሳኦልና የዳዊት ሕይወትን በሚመለከት ስለኖሩበት ዘመን ቀጥሎ አንድ አሳብ ቀርቦአል። እነዚህ በምሁራን የተሰጡ ግምታዊ የሆኑ ጊዜያት ናቸው፤ ምክንያቱም ትክክለኛውን ጊዜ ለመናገር በቂ የሆነ መረጃ ባለመኖሩ።

1105 ዓ.ዓ. ሳሙኤል ተወለደ።

1080 ዓ.ዓ. ሳኦል ተወለደ።

1050 ዓ.ዓ. ሳኦል ለንጉሥነት ተቀባ።

1040 ዓ.ዓ. ዳዊት ተወለደ።

1025 ዓ.ዓ. ዳዊት በሳሙኤል ተቀባ።

1010 ዓ.ዓ. ሳኦል ሞተ፤ ዳዊት በይሁዳ ላይ መንገሥ ጀመረ።

1003 ዓ.ዓ. ዳዊት በእስራኤል ሁሉ ላይ ነገሠ።

970 ዓ.ዓ. ዳዊት ሞተ።

9ኛ ጥያቄ፥ ስለ 1ኛ ሳሙኤል ከመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት ውስጥ አንብብ። በዚያ ስፍራ የተጠቀሱትን ዋና ዋና እውነቶች ዘርዝር።

## 2ኛ ቀን 1ኛ ሳሙኤል 1-12

1ኛ ሳሙኤል ስለ መሪነት የሚናገር መጽሐፍ ነው። እግዚአብሔር በአንዳንድ መሪዎች ለምን እንደሚጠቀምና ሌሎቹን ደግሞ ለምን እንደሚተው ይናገራል። መልካም ወይም ክፉ መሪ የሚያደርጉ ነገሮች ምን እንደሆኑ ይናገራል። ይህም የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሁሉ ይህን መጽሐፍ ማጥናታቸው አስፈላጊ እንደሆነ ያሳየናል። መጽሐፉን የምንመለከተው ታሪኮችን ለመረዳት ብቻ ሳይሆን፥ እግዚአብሔርን የሚፈራ መሪ ምን እንደሚመስልም ለመረዳት ነው።

የ1ኛ ሳሙኤል የመጀመሪያ ክፍል ዔሊና ሳሙኤል የተባሉ የሁለት ግለሰቦችን ታሪክ የምናገኝበት ነው። በአንዳንድ መንገዶች በጣም ተመሳሳይ ነበሩ። ለምሳሌ፡- ሁለቱም ሕዝቡን በአምልኮ የሚመሩ ካህናት ነበሩ። ደግሞም ሕዝቡን በምክር የሚረዱ መሳፍንት ነበሩ። ሁለቱም ተመሳሳይ የሆነ ደካማ ጎን ነበራቸው። ዔሊም ሆነ ሳሙኤል ልጆቻቸውን መቆጣጠር አልቻሉም ነበር።

ነገር ግን በዔሊና በሳሙኤል ሕይወት አንዳንድ ልዩነቶችን እንመለከታለን። ለምሳሌ፡- ዔሊ ለመንፈሳዊ ነገር ንቁ አልነበረም። የሐናን ጸሎት መገንዘብ ስላልቻለ፥ እንደሰከረች ቆጥሯት ነበር። ዔሊ የእግዚአብሔርን ድምፅ መለየት አልቻለም ነበር። በታቦቱ የተመሰለው የእግዚአብሔር ሕልውና ለሕዝቡ ነፃነትን ለማምጣት እግዚአብሔርን ለማስገደድ እንደማይጠቅም አልተገነዘበም ነበር።

ሳሙኤል መንፈሳዊ ንቃት ነበረው። የሚኖረው ከዔሊ ልጆች ጋር ቢሆንም እንኳ የእግዚአብሔርን አምልኮ ባበላሸው ክፉ ተግባራቸው ለመሳተፍ ፈቃደኛ ሳይሆን ቀረ። ለእግዚአብሔር ድምፅ ንቁ የነበረና የሚያዳምጥ ነበር። ሳኦልን ለንጉሥነት መቀባት ማለት የእስራኤልን ሕዝብ ለመምራት ሥራ አሳልፎ መስጠት ቢሆንም፥ ለእግዚአብሔር በመታዘዝ ሳኦልን ቀባው። እንደ መሪ ያልተቀበሉት ቢሆንም ለእስራኤል ለመጸለይ ቃል ገባ። ሌሎች ሰዎች እርሱን በመተው ከእግዚአብሔር ጋር ያለው ኅብረት እንዲበላሽና ሕዝቡን ያገለግል ዘንድ ከእግዚአብሕር ለተቀበለው ጥሪ ታማኝ እንዳይሆን ተጽዕኖ ለማሳደር ያደረጉትን ሙከራ አከሸፈ።

10ኛ ጥያቄ፥ ሀ) ለመንፈሳዊ መሪ መንፈሳዊ ንቃት የሚያስፈልገው ለምንድን ነው? ለ) ዛሬ አንድ እግዚአብሔርን የሚፈራ መሪ በመንፈሳዊ ነገር ንቁ መሆን እንዴት እንደሚችል ምሳሌዎችን ዘርዝር ሐ) ዛሬም ቢሆን አንድ እግዚአብሔርን የሚፈራ መሪ መንፈሳዊ ንቃት እንዴት ሊጎድለው እንደሚችል የሚያሳዩ ምሳሌዎችን ጥቀስ።

በእነዚህ ታሪኮች ውስጥ እግዚአብሔርን ስለሚፈራ መሪ የሚከተሉትን ነገሮች መመልከት እንችላለን፡-

1. የእግዚአብሔርን ድምፅ ለመስማት ንቁና ፈጣን ነው።
2. ለራሱም ሆነ ለቤተሰቡ ፍላጎት ምቹ በማይሆንበት ጊዜ እንኳ ለእግዚአብሔር ይታዘዛል።
3. የእግዚአብሔር ሕዝብ ባልተቀበሉት ጊዜ እንኳ ለእነርሱ የሚጸልይ የጸሎት ሰው ነው።
4. በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ ቂም አይዝም።
5. ቤተሰቡን በመቆጣጠር፥ ከእግዚአብሔር ጋር ወዳለው ትክክለኛ ግንኙነት ይመራቸዋል።

11ኛ ጥያቄ፥ ሀ) እነዚህ አምስት ነገሮች በዚህ ዘመን ለሚገኙ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የሚያስፈልጓቸው ለምንድን ነው? ለ) እነዚህ አምስት ነገሮች በቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሕይወት ውስጥ ሊታዩ የሚችሉት እንዴት እንደሆነ የሚያሳዩ ተጨባጭ ማስረጃዎችን ስጥ። ሐ) እነዚህ አምስት ነገሮች በቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሕይወት ውስጥ ብዙ ጊዜ እንዴት እንደሚጎድሉ ተጨባጭ መግለጫዎችን ስጥ። ለምንስ ይጎድላሉ?

12ኛ ጥያቄ፥ 1ኛ ሳሙኤል 1-12 አንብብ። ሀ) የሳሙኤል እናት ማን ነበረች? ለ) ሳሙኤል ጡት በጣለ ጊዜ ለመኖር የሄደው ወደየት ነበር? ሐ) አንዳንዶቹን የዔሊ ልጆች ኃጢአት ዘርዝር። መ) እግዚአብሔር በዔሊ ላይ የፈረደው እንዴት ነበር? ሠ) ከጦርነቱ በኋላ ታቦቱ የተወሰደው ወዴት ነበር?

ረ) እግዚአብሔር ኃይሉን ለፍልስጥኤማውያን ያሳየው እንዴት ነው? ሰ) እስራኤል ምድራዊ ንጉሥን የጠየቀችው ለምንድን ነው? ሸ) እስራኤላውያን ንጉሥ እንዲያነግሥላቸው በጠየቁ ጊዜ እግዚአብሔር ምን እያደረጉ ናቸው አለ? ቀ) ሳኦል መጀመሪያ በተቀባ ጊዜ የነበረውን ባሕርይ አስረዳ። በ) በሕይወቱ የእግዚአብሔር ሕልውና እንዴት ተገለጠ?

## 1. የሳሙኤል መወለድና ጥሪ (1ኛ ሳሙ. 1-3)

የ1ኛ ሳሙኤል ጸሐፊ በሳሙኤል ሕይወት ላይ ከፍተኛ ትኩረት አድርጓል። ይህ የሆነበት ምክንያት፥ ሳሙኤል በእግዚአብሔር ዕቅድ ውስጥ ቁልፍ ሰው ስለነበር ነው። በእግዚአብሔር ትእዛዝ በእስራኤል ሕዝብ መካከል ንጉሣዊ አስተዳደር እንዲጀምር አደረገ። ደግሞም ከሙሴ ዘመን በኋላ በእስራኤል ሕዝብ መካከል የኖረ ታላቅ ነቢይ ነው።

በሌላ አንጻር መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ዳዊትና ስለ ሳኦል መወለድ አንዳችም ነገር ሳይናገር፥ አስደናቂው የሳሙኤል አወላለድን ገልጧል። ይህ ታሪክ የቀረበው ሳሙኤል በእስራኤል ታሪክ ውስጥ በሚጫወተው እጅግ ጠቃሚ ሚና ላይ ትኩረት ለመስጠት ነው። የሳሙኤል አገልግሎት በነገሥታት ዘመን የነበረው የነቢይነት አገልግሎት ምሳሌ ስለሆነ፥ በዚህም አንጻር እጅግ ጠቃሚ ነው። «የነቢያት ትምህርት ቤት ወይም ጉባኤ» በመባል (1ኛ ሳሙ. 10፡5፤ 19፡18-24) የሚታወቀውን ተቋም ለመቆርቆሩ አንዳችም ጥርጣሬ የለንም። ይህ የነቢያት ቡድን በአንድ ስፍራ አብሮ ለመኖር የተሰባሰበ የእግዚአብሔር ሰዎች ስብስብ ነበር። እነዚህ ሰዎች ልዩ በሆነ በእግዚአብሔር ኃይል የተሞሉ ነበሩ። በኋላ የምናያቸው እንደ ናታንና ጋድ ወዘተ. ያሉ ነቢያት ከዚህ የነቢያት ጉባኤ የወጡ ሳይሆኑ አይቀሩም፤ ስለዚህ የነቢያት ጉባኤ ከብዙ መቶ ዓመታት በኋላ በኤልያስና በኤልሳዕ ጊዜም እንደነበረ እንመለከታለን (ምሳሌ፡- 2ኛ ነገሥት 2፡3-15)፤ ስለዚህ የነቢያት ጉባኤ የሚባለው በሳሙኤል መሪነት ነቢያት በአንድነት የሚሰባሰቡበት ኅብረት፥ ከሳሙኤል በኋላም ለብዙ መቶ ዓመታት ሳይቀጥል አልቀረም። ይህ ኅብረት

እንዴት እንደተደራጀና ግለሰቦችም ወደዚህ ኅብረት የሚገቡት እንዴት እንደነበረ የምናውቀው ነገር የለም።

ሳሙኤልን ልዩ የሚያደርገው ሌላው ተጨማሪ ነገር ፥ሦስት ዋና ዋና የመሪነት ተግባራትን አጣምሮ መያዙ ነው። እርሱ ካህን፥ ነቢይና የፖለቲካ ገዥ ወይም መስፍን ነበር። በኋላ እነዚህ ሦስት ዋና ዋና የመሪነት ተግባሮች ለሦስት የተለያዩ ሰዎች የሚሰጡ ሆነዋል። ካህናት ከአሮን ዝርያ የሚመጡ ሆኑ፤ ነቢያት የእግዚአብሔርን መልእክት ወደ ሕዝቡ ይዘው የሚመጡ ከየትኛውም ነገድ ልዩ በሆነ መንገድ በእግዚአብሔር የተመረጡ ሰዎች ሲሆኑ፥ በኋላ በነገሥታት የተቀየሩት መሳፍንት ደግሞ የፖለቲካ መሪዎች ነበሩ። እነዚህን ሦስት የመሪነት አገልግሎቶች እንደገና አጠቃሎ የያዘው ክርስቶስ ኢየሱስ ብቻ ነው። እርሱ ካህን (ዕብ. 9፡11) ነቢይ (ሉቃ. 1፡76) እና ንጉሥ (ራእይ 17፡14፤ 19፡16) ነው።

ሳሙኤል የተወለደው ለብዙ ዓመታት መካን ሆና ከኖረች ከአንዲት ሐና ከምትባል ሴት ነበር። ይህች ሴት ከብዙ ጸሎት በኋላ እግዚአብሔር የሰጣትን ልጅ መልሳ ለእርሱ ሰጠችው። ልጁ ባደገም ጊዜ፥ በዚያን ጊዜ የእስራኤል ሕዝብ የአምልኮ ማእከል ወደ ሆነው በሴሎ ወደሚገኘው የመገናኛ ድንኳን ለአገልግሎት ተላከ። በዚያም በዔሊ እጅ አደገ።

ሳሙኤል በመገናኛ ድንኳን ውስጥ በሚያገለግልበት ጊዜ፥ የዔሊ ልጆች ግን በእግዚአብሔር ላይ ዓመፁ። የካህንነት መብታቸውን እጅግ ተገቢ ባልሆነ መንገድ በመጠቀም፥ ለስስታምነት ዓላማቸው ተጠቀሙበት። መሥዋዕት በሚያቀርቡበትም ጊዜ እግዚአብሔርን አላከበሩትም። እስራኤላውያን ለእግዚአብሔር ሊያቀርቡ ከሚገባቸው መሥዋዕቶች አንዱ የደኅንነት መሥዋዕት ነበር። በዚህ መሥዋዕት የእንስሳው የተወሰነ ክፍል በእግዚአብሔር መሠዊያ ላይ ይቃጠል ነበር። የቀረው የመሥዋዕት ክፍል ግን ይቀቀልና ከፊሉ ለካህናት፥ ከፊሉ ደግሞ አምልኮውን ለሚፈጽመው ሰው ቀርቦ በኅብረት ይበሉ ዘንድ የተፈቀደ ነበር። በእግዚአብሔር ፊት በኅብረት ይበሉት ነበር፤ የዔሊ ልጆች ግን በጣም ስስታም ስለነበሩ ለራሳቸው የሆነውን የመሥዋዕት ክፍል ብቻ አይወስዱም። አምልኮውን የሚፈጽመው ሰው

የተወሰነውን ክፍል ለእግዚአብሔር እስኪሰዋ ድረስ እንኳ አይጠብቁም። የፈለጉትን የእንስሳውን ክፍል ይወስዳሉ። በሥነ - ምግባር እጅግ የተበላሹ ስለነበሩም ወደ አምልኮው ስፍራ የሚመጡትን ሴቶች አስገድደው የግብረ ሥጋ ግንኙነት ይፈጽሙ ነበር። ዔሊ ሊገሥጻቸው ቢሞክርም እንኳ አልሰሙትም። ልጆች በነበሩ ጊዜ በሚገባ በሥርዓት አላሳደጋቸውም። ስለዚህ በዕድሜ በገፉ ጊዜ እግዚአብሔርን ረሱ፤ ይከተሉትም ዘንድ እምቢ አሉ።

| |
|---|
| 13ኛ ጥያቄ፥ ሀ) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ልጆቻቸውን በልጅነት ወራት በሚገባ ባለማሠልጠናቸው፥ ዕድሚያቸው በገፉ ጊዜ ከእግዚአብሔር ፊታቸውን የመመለስ ችግር በጣም የተለመደው እንዴት ነው? ለ) ልጆች ካሉህ አሁን፥ ከሌሉህ ወደፊትም ቢሆን፥ እግዚአብሔርን እንዲከተሉና እንዲታዘዙ እነርሱን ልታስተምርባቸው ያሰብካቸውን ዘዴዎች ግለጽ፤ (ምሳ. 22:6)። |

ልጆቹ የእግዚአብሔርን እውነተኛ አምልኮ በማበላሸታቸውና ለእርሱ ክብር ባለመስጠታቸው ምክንያት እንደሚያጠፋቸው እግዚአብሔር ዔሊን ባልታወቀ ነቢይ አስጠነቀቀው። የሊቀ ካህንነትን መብት ለሌላ፥ ማለት በእግዚአብሔር ፊት በታማኝነት ላለው ለሳሙኤል እንደሚሰጠው ቃል ገባ።

ገና በልጅነቱ ወራት እግዚአብሔር ሳሙኤልን ይናገረው ጀመር። ሳሙኤል እየተናገረው ያለው እግዚአብሔር መሆኑን ለመረዳት ጥቂት ጊዜ ወስዶበታል። በቀረው ዘመኑ ግን እግዚአብሔር ሳሙኤልን ይናገረው ነበር። ወጣት ቢሆንም እንኳ ሰዎች እግዚአብሔር ሳሙኤልን እንደመረጠውና ለሕዝቡ የእግዚአብሔርን መልእክት የሚናገር ነቢይ እንደሆነ ለማወቅ ጊዜ አልወሰደባቸውም።

2. የዔሊ ቤት መጥፋትና የቃል ኪዳኑ ታቦት ታሪክ (1ኛ ሳሙ. 4:6)

14ኛ ጥያቄ፥ የቃል ኪዳኑ ታቦት ምን እንደሆነ ከመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት ውስጥ ተመልከት።

የእስራኤል ሕዝብ ለረጅም ጊዜ ከከነዓናውያን ጋር ስለኖሩ፥ ከነዓናውያን በእግዚአብሔር ላይ ባላቸው አመለካከት ተጽዕኖ ሥር ወደቁ። ስለሆነም የእግዚአብሔርን ታቦት ወደ ጦር ሜዳ በመውሰድ፥ በጦርነቱ ድልን እንዲሰጣቸው እግዚአብሔርን ማስገደድ እንደሚችሉ ገመቱ። እንደምታስታውሰው፥ የቃል ኪዳኑ ታቦት በመገናኛው ድንኳን ውስጥ የሚገኝ ከሁሉም የሚበልጥ የተቀደሰ ዕቃ ነው። በቅድስተ ቅዱሳን ውስጥ በመቀመጥ፥ እግዚአብሔር ከእስራኤላውያን ጋር የመኖሩ ምልክት ሆኖ ያገለግል ነበር። በምድር ላይ ያለው የእግዚአብሔር ሰማያዊ ዙፋን ምልክት ተደርጎ ይቆጠር ነበር።

አንዳንድ ክርስቲያኖች እግዚአብሔር የቤተ ክርስቲያን ሕንጻ በመንግሥት ሲፈርስ ዝም ብሎ አያይም የሚል ግምት እንዳላቸው ሁሉ፥ እስራኤላውያንም እግዚአብሔር የቃል ኪዳኑ ታቦት በጠላት እንዲጠፋ አይፈቅድም የሚል የተሳሳተ ግምት ነበራቸው። የቃል ኪዳኑን ታቦት ወደ ጦር ሜዳ ይዘውት ቢሄዱ፥ እግዚአብሔር ድልን እንደሚሰጣቸው እርግጠኞች ነበሩ። እግዚአብሔር ለእነርሱ ይሠራ ዘንድ በተሳሳተ መንገድ ሊጠቀሙበት ሞከሩ። ይገዟቸው ዘንድ፥ እግዚአብሔር ፍልስጥኤማውያንን የላከባቸው፥ በኃጢአታቸው ምክንያት እንደሆነ ዘነጉ። በእውነት በንስሐ ቢመለሱ እግዚአብሔር ይቅር እንደሚላቸውና ከጠላቶቻቸው ነፃ እንደሚያወጣቸው ሊገነዘቡ ይገባቸው ነበር። እግዚአብሔር ግን ለእነርሱ በመሰላቸው መንገድ አልሠራም፤ ስለዚህ የቃል ኪዳኑ ታቦት ይማረክ ዘንድ ፈቀደ።

| |
|---|
| 15ኛ ጥያቄ፥ ዛሬ ክርስቲያኖች አንዳንድ ነገሮችን እንዲያደርግላቸው እግዚአብሔርን በዘዴ ሊጠቀሙበት የሚፈልጉባቸው መንገዶች ምንድን ናቸው? |

ከፍልስጥኤማውያን ጋር ያደረጉት ጦርነት በእስራኤላውያን ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ አሳደረባቸው። የመጀመሪያው:- እግዚአብሔር ለዔሊ የላከውን የትንቢትን ቃል አከበረ። የዔሊ ልጆች በጦርነቱ ተገደሉ። ዔሊ ራሱ የጦርነቱን ውጤት በሰማ ጊዜ ሞተ። የዔሊ ልጅ ሚስት ሳትቀር በወሊድ ሞተች። የእግዚአብሔር ክብር ከእነርሱ መወሰዱን

በመገንዘብ ልጁን «ኢካቦድ» ብላ ጠራችው። ትርጉሙም «ክብር ለቀቀ» ማለት ነው።

ሁለተኛው:- የእግዚአብሔር መንቀፍ ነበር። በጥንት ዘመን አንድ ሕዝብ ሌላውን በሚያሸንፍበት ጊዜ፥ ሕዝቡ የእነርሱ አምላክ ከተሸነፈው ሕዝብ አምላክ ስለበለጠ እንደሆነ ያስቡ ነበር፤ ስለዚህ የእስራኤላውያን አለመታዘዝ፥ በአሕዛብ መካከል የእግዚአብሔር ስም እንዲሰደብ አደረገ። ፍልስጥኤማውያንም የቃል ኪዳኑ ታቦት ዳጎን ወደሚባለው አምላካቸው ወሰዱት።

ሦስተኛ:- እግዚአብሔር ለፍልስጥኤማውያን ኃይሉን አሳያቸው። ፍልስጥኤማውያን አምላካቸው የእስራኤልን አምላክ እንዳሸነፈ ቆጥረው ነበር፤ እግዚአብሔር ግን ይህ እንዳልሆነ አሳያቸው። በመጀመሪያ ልክ እግዚአብሔርን የሚያመልክ ሰው እንደሚያደርገው፥ ዳጎን በቃል ኪዳኑ ታቦት ፊት በፊቱ እንዲደፋ አደረገ። ሁለተኛ፥ በፍልስጥኤም ምድር ሁሉ መቅሠፍት እንዲሆን አደረገ። ሦስተኛ፥ እግዚአብሔር ፍልስጥኤማውያንን የቃል ኪዳኑ ታቦት ወደ እስራኤል እንዲመልሱ አደረገ። ከተለመደው ነገር በተቃራኒ፥ ላሞች የሚያጠቧቸውን ጥጆቻቸውን ትተው ታቦቱን የተሸከመውን ሰረገላ ወደ እስራኤል ምድር እየጎተቱ ሄዱ።

አራተኛ:- እግዚአብሔር ስላላከበሩት አንዳንድ እስራኤላውያንን ቀጣ። ይኸውም እነኝህ እስራኤላውያን ስለ ታቦቱ ያልተፈቀደላቸውን ለማወቅ ስለፈለጉ ተገደሉ።

አምስተኛ:- የሴሎ ከተማና የመገናኛው ድንኳን ተደመሰሱ። አስቀድሞ ከነበረው የመገናኛ ድንኳን ውስጥ የዳነው ብቸኛው ነገር የቃል ኪዳኑ ታቦት ነው። የእስራኤላውያን የአምልኮ ማዕከል ሴሎ መሆኑ ቀረና ኖብ ሆነ (1ኛ ሳሙ. 21፡1)። ታቦቱም ወደ ተለያዩ ቦታዎች ይንቀሳቀስ ጀመር። ታቦት በነበረበት ስፍራ ሁሉ እስራኤላውያን እግዚአብሔርን ያመልኩ ነበር። ከብዙ ዓመታት በኋላ ዳዊት የቃል ኪዳኑን ታቦት ወደ ኢየሩሳሌም በመውሰድ በድንኳን ውስጥ አኖረው። በኋላ ደግሞ ሰሎሞን የቃል ኪዳኑ ታቦት ይኖርበት ዘንድ እጅግ ታላቅ ቤተ መቅደስ አሠራ።

ከዘመናት በኋላ እግዚአብሔር ኢየሩሳሌምና ቤተመቅደሱ እንዲደመሰሱ አይፈቅድም፤ ምክንያቱም ቤተ መቅደሱ የእርሱ ነውና ብለው እስራኤላውያን አሰቡ (ኤር. 7፡1-15 ተመልከት)። ሰዎች የራሳቸውን የስግብግብነት ዓላማዎች ለማሳካት እግዚአብሔርን በዘዴ ሊጠቀሙበት እንደማይችሉ አሳያቸው። ሕዝቡ ወደ ምርኮ እንዲሄዱ ፈቀደ። እግዚአብሔር መንፈስ ስለሆነ፥ በአንድ ሕንጻ ውስጥ ሊገደብና ሰዎች ሊጠቀሙበት ወይም አንድ ነገርን እንዲያደርግ በዘዴ ሊያስገድዱት አይችሉም። ለእግዚአብሔር አንድ ታላቅ ነገር በማድረግ፥ አንድን ነገር እንዲያደርግልን ለማስገደድ አንችልም። አንድ ሰው በኢየሱስ ስም ተፈውሷል ብለን በማወጃችን፥ ወይም በመጸለያችን ብቻ እግዚአብሔር ያንን ሰው እንዲፈውሰው ልናስገድደው አንችልም። ደግሞም የቤተ ክርስቲያን ሕንጻ ባለቤት መሆናችን ስደት እንደማይደርስብን ማረጋገጫ ሊሆንልን አይችልም ወይም ቤተ ክርስቲያን እንደማይዘጋ ዋስትና ሊሆን አይችልም። እግዚአብሔር ሉዓላዊና የሚፈልገውን ነገር በሚፈልገው ጊዜ የሚያደርግ አምላክ ነው። በምንም ነገር ልናስገድደው ወይም ልንቆጣጠረው አንችልም።

> 16ኛ ጥያቄ፥ ሀ) አንዳንድ ሰዎች ለእግዚአብሔር በዘዴ ለመጠቀም ሲሞክሩ ያየኸው እንዴት ነው? ለ) ምን አደረጉ? ሐ) ይህ ስሕተት የሆነው ለምንድን ነው? መ) አንዳንድ ክርስቲያኖች፥ እግዚአብሔር የማደሪያውን ሕንጻ እንዲደመሰስ ከቶ አይፈቅድም ብለው ለምን ያስባሉ?

3. ሳሙኤል ለእስራኤል ሕዝብ እንደ መስፍን ነበር (1ኛ ሳሙ. 7)። ከብዙ ዓመታት በኋላ፥ ሳሙኤል ሕዝቡን በምጽጳ ሰበሰበ። በዚያ እግዚአብሔር የሰዎችን ልብ መለወጥ ጀመረ። በፍልስጥኤማውያን የባርነት ቀንበር ሥር መኖራቸው አሰልችቶአቸው እንደ ነበር አንዳችም ጥርጥር የለም። ሳሙኤል ሕዝቡ ወደ እግዚአብሔር እንዲመለሱና ለእግዚአብሔር ቃል ኪዳን እንዲታዘዙ ለመምከርና ለማሳመን ሞከረ።

ሕዝቡ ወደ እግዚአብሔር ሲመለሱና ንስሐ በመግባት እግዚአብሔርን ሲያመልኩ፥ ፍልስጥኤማውያን ሊያጠቋቸው ወሰኑ። ዳሩ ግን ሳሙኤል ወደ እግዚአብሔር ጸለየና ፍልስጥኤማውያን ተሸነፉ። በሳሙኤል ዘመን መንግሥትን እስራኤላውያን ከፊሉን የፍልስጥኤም መንግሥት ለማሸነፍ ችለው ነበር።

4. ሳኦል የእስራኤል ንጉሥ ይሆን ዘንድ ተመረጠ (1ኛ ሳሙ. 8-11)።

ይህኛው የ1ኛ ሳሙኤል ክፍል ከዘመነ- መሳፍንት ወደ ነገሥታት ዘመን የተደረገውን የሽግግር ጊዜ ያሳየናል። ሳሙኤል የመጨረሻው መስፍን ነበር።

ሳሙኤል፥ ዕድሜው በገፋ ጊዜ የእስራኤልን ሕዝብ የመምራት ኃላፊነት ለልጆቹ ለማስተላለፍ አሰበ።

ሆኖም እንደ ዔሊ ልጆቹን በሚገባ ስላላሳደገ፥ ሊያከብሩትና ሊታዘዙት አልቻሉም፤ ስለዚህ እግዚአብሔር የሳሙኤል ልጆች የፖለቲካም ሆነ የመንፈሳዊ መሪ መሆናቸውን ሳይደግፍ ቀረ። ይልቁንም እግዚአብሔር የመጀመሪያውን የእስራኤል ንጉሥ ለመምረጥ ሳሙኤልን ተጠቀመበት።

የእስራኤል ሕዝብ የእግዚአብሔር ተወካይ ወደሆነው ወደ ሳሙኤል በመምጣት ንጉሥ ያነግሥላቸው ዘንድ ይጠይቁታል። ሕዝቡ ንጉሥ የፈለጉባቸው ሁለት ምክንያቶች ነበሩ። የመጀመሪያው፥ ልክ በአካባቢያቸው የሚኖሩ አሕዛብ ነገሥታት እንደነበሯቸው ሁሉ፥ እነርሱም ንጉሥ ይኖራቸው ዘንድ ፈለጉ። ምኞታቸው ልክ እንደቀረው ዓለም ለመሆን ነበርና እግዚአብሔር ንጉሣቸው እንደሆነ ዘነጉ። ለቃል ኪዳኑ በመታዘዝ ቢኖሩ ኖሮ ሰብአዊ ንጉሥ አያስፈልጋቸውም ነበር (1ኛ ሳሙ. 8፡5-7)። በሁለተኛ ደረጃ፥ ንጉሥን የጠየቁበት ምክንያት ከጠላቶቻቸው ነፃ ያወጣቸው ዘንድ ነው (1ኛ ሳሙ. 8፡20)።

ጥያቄአቸው ሳሙኤልን አስቆጣው። ያስቆጣውም ሕዝቡ እርሱንና ልጆቹን እንደ መሪ አለመቀበላቸው ሊሆን ይችላል፤ ነገር ግን

እግዚአብሔር፥ ሕዝቡ ንጉሥ እንዳይሆን የናቁት እርሱን ሳይሆን እግዚአብሔርን እንደሆነ ለሳሙኤል አሳየው።

ሕዝቡ የጠየቁት ጥያቄ እግዚአብሔርን ደስ እንዳላሰኘውና በእርሱ ላይ እንደተደረገ ዓመፅ መቆጠሩ ግልጥ ቢሆንም፥ እግዚአብሔር ጥያቄአቸውን በመመለስ ንጉሥ ለመስጠት ለምን እንደተስማማ (1ኛ ሳሙ. 8፡7፥ 22፤ 10፡9፤ 12፡12፥ 17) የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁራን ተደንቀዋል። እስራኤል ንጉሥ ይኖራት ዘንድ በእግዚአብሔር ዕቅድ ውስጥ እንደነበረ ከመጽሐፍ ቅዱስ በግልጥ እንመለከታለን። ከ800 ዓመታት በፊት ነገሥታት ከአብርሃም እንደሚወጡ ተናግሮ ነበር። እስራኤላውያን ወደ ከነዓን ከመግባታቸው ከ400 ዓመታት በፊት እግዚአብሔር ለሕዝቡ ስለ ንጉሥ ትምህርት ሰጣቸው (ዘዳ. 17)።

የእግዚአብሔር ዕቅድ በሕዝቡ ላይ ራሱ እንደ ዋና ንጉሥ ሊነግሥና ምድራዊ ተወካይ የሚሆን ንጉሥ እንዲኖራቸው ለማድረግ ነበር። እስራኤላውያን፥ ንጉሥ እንዲሰጣቸው እግዚአብሔርን የጠየቁት ከተሳሳተ ዓላማ ነበር። ይህ ውስጣዊ ዓላማቸው የእግዚአብሔርን ንጉሥነት አለመቀበላቸውን የሚያሳይ ነበር። እግዚአብሔር በጥያቄአቸው ያልተደሰተበት ሦስት ምክንያቶች ነበሩት። አንደኛ፥ ሕዝቡ በጠላት እጅ የወደቁበት ብቸኛው ምክንያት ንጉሥ ስለሌላቸው እንደሆነ አድርገው ያቀረቡት የተሳሳተ አሉባልታ ነበር። በጠላቶቻቸው የተሸነፉበት እውነተኛ ምክንያት ኃጢአታቸው መሆኑን አውቀው በእግዚአብሔር ፊት ንስሐ የመግባት ኃላፊነታቸውን ለመወጣት ፈቃደኞች አልነበሩም። ሁለተኛ፥ ንጉሥ የፈለጉበት ውስጣዊ አነሣሽ ምክንያታቸው የተሳሳተ ነበር። እንደሌላው የዓለም ሕዝብ ለመሆን መፈለጋቸው ነበር፤ በመሠረቱ ግን ከሌላው የዓለም ሕዝብ ሊለዩ እንጂ ሊመሳሰሉ አይገባም ነበር። ሦስተኛ፥ በጠላቶቻቸው ላይ ስለሚያገኙት ውጤታማነት በተሳሳተ መንገድ ዋስትናቸውን በእነርሱ ብጤ ሰው ላይ አደረጉ። ንጉሥ ቢኖራቸው በጠላቶቻቸው ላይ ድል እንደሚያገኙ አሰቡ። በጠላቶቻቸው ላይ ድልን የሚሰጥ እግዚአብሔር ብቻ መሆኑን ዘነጉ። ለእግዚአብሔር በመታዘዝ ቢኖሩ እንደሚጠብቃቸው የገባላቸውን የተስፋ ቃል ረሱ።

በመታዘዝ ለመኖር ስላልፈለጉ እግዚአብሔር እንደሚጠብቃቸው ማሰብ አልሆነላቸውም። ስለዚህ ንጉሥ ጠየቁ።

ሕዝቡ ንጉሥ ያገኙ ዘንድ እግዚአብሔር ፈቀደ። ሆኖም ይህ ንጉሥ በአካባቢያቸው እንደሚኖሩ ሕዝቦች ያለ ንጉሥ እንዳልሆነ አሳያቸው። ይልቁንም የሕዝቡ መሪ ለእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ራሱን አስገዝቶ የሚኖር ሰው መሆን ነበረበት። በምድሪቱ እውነተኛ ሰላምና ደኅንነት የሚኖረው ምድራዊው ንጉሥ ለሰማያዊው ንጉሥ ራሱን ሲያስገዛ ብቻ ነበር። በኋላ ሳኦል ለንጉሡ ለእግዚአብሔር ራሱን አላስገዛም በማለቱ ሰላም ጠፍቶ በጠላቶቻቸው እንደተሸነፉ እናያለን፤ ዳዊት ግን ራሱን ለእግዚአብሔር በማስገዛቱ የተከናወነለት መሪ ሆነ።

| |
|---|
| 17ኛ ጥያቄ፥ በተሳሳተ ውስጣዊ አሳብ ተነሣስተን የቤተ ክርስቲያን መሪዎችን በመምረጥ፥ እግዚአብሔርን የማያስከብር ድርጊት እንዴት መፈጸም እንችላለን? |

እግዚአብሔር ሳኦልን ለንጉሥነት እንዲመርጥ ሳሙኤልን ሲያዝ፥ ሳኦልን ደግሞ በሉዓላዊነቱ ወደ ሳሙኤል መራው። በመጀመሪያ፥ እግዚአብሔር ሳኦልን በግሉ ቀብቶት ነበር፤ ከዚያ በኋላ ደግሞ፥ በታላቅ ደስታ በተቀበሉት በሕዝቡ ሁሉ ፊት ንጉሥ መሆኑ ታወጀ። የሚገርመው ግን ሳኦል ከሳሙኤል ርቆ የሚኖረው 8 ኪሎ ሜትር ብቻ ሆኖ እያለ ሳሙኤልን አያውቀውም ነበር። ከመጀመሪያው ጀምሮ ሳኦል መንፈሳዊ ረሀብ አልታየበትም። ሳሙኤል በሠራው መሠዊያ አጠገብ እንኳ አምልኮ አልፈጸመም። ሳኦል በእስራኤል ላይ ንጉሥ ይሆን ዘንድ በእግዚአብሔር እንደተመረጠ በሁለት መንገድ አሳይቶ ነበር። የመጀመሪያው፥ በመንፈስ ቅዱስ ቁጥጥር ሥር ሆኖ ከነቢያት ጋር ትንቢት መናገርን መጀመሩ ነበር። ሁለተኛው ደግሞ፥ አሞናውያንን ለማሸነፍ መቻሉ ነበር። የሚያሳዝነው ግን የሳኦል ታሪክ በድል ሊቀጥል አለመቻሉ ነው። ሳኦል ለንጉሡ ለእግዚአብሔር ከመታዘዝ እንዴት እምቢ እንዳለና እግዚአብሔር እንደናቀው እንመለከታለን።

ሳኦል፥ ንጉሥ ሆኖ በሚገባ ከተደላደለ በኋላ፥ ሳሙኤል በእስራኤል ሕዝብ ላይ የነበረውን የካህንነትና የነቢይነት አገልግሎት

ቀጠለ፤ ነገር ግን የፖለቲካ መሪያቸው ሳኦል ሆነ። ስለዚህ ሳሙኤል የእስራኤልን ሕዝብ በአንድነት ሰበሰበ። በእግዚአብሔር ላይ የነበራቸውን ዓመፅና አጠቃላይ ታሪካቸውን አስታወሳቸው። እግዚአብሔር በኃጢአታቸው ምክንያት ለጠላቶቻቸው አሳልፎ በመስጠት እንደፈረደባቸው አስታወሳቸው። አሁን ንጉሥ በመፈለጋቸው ባሳዩት የተሳሳተ ዓላማ እግዚአብሔር ደስ አለመሰኘቱን ድንገተኛ ዝናብና የመብረቅ ነጎድጓድ በማውረድ አሳያቸው። እግዚአብሔር ሕዝቡ በእርሱ ላይ የነበራቸውን እምነት ለማደስ ሳሙኤልን ተጠቀመበት። ሳሙኤል እንደገና ከእግዚአብሔር እንዳይርቁና የውሸት አማልክትን እንዳያመልኩ አስታወሳቸው። በእግዚአብሔር ፊት በጸሎት ሊያቀርባቸውና የእግዚአብሔርን ቃል ያለማቋረጥ ሊያስተምራቸው ቃል ገባላቸው።

| |
|---|
| 18ኛ ጥያቄ፥ ሀ) ከሳኦል ሹመት በኋላ፥ ሳሙኤል የቀጠለው የእግዚአብሔርን ቃል የማስተማርና የጸሎት አገልግሎት፥ አንድ መሪ ለሕዝቡ ሊያደርገው የሚገባ ከሁሉ የተሻለ አገልግሎት የሆነው እንዴት ነው? ለ) እነዚህ ሁለት አገልግሎቶች በሕይወትህ የሚታዩት እንዴት ነው? በእነዚህ ሁለት አገልግሎቶች መሻሻል ልታሳይ የምትችልባቸው መንገዶች የትኞቹ ናቸው? |

## 3ኛ ቀን 1ኛ ሳሙኤል 13-20

በመጽሐፍ ቅዱሳችን ውስጥ እጅግ አሳዛኝ ከሆኑ ታሪኮች አንዱ የሳኦል ታሪክ ነው። እግዚአብሔርን ለማክበር ታላቅ ኃይል ነበረው። በግሩም ሁኔታ ሥራውን ለእግዚአብሔር መሥራት ጀመረ፤ ነገር ግን ብዙም ሳይቆይ ችግሮች መፈጠር ጀመሩ። በመሆኑም አንድ ቀን እግዚአብሔር ሳኦልን እውነተኛ የእስራኤል ንጉሥ እንዳይሆን ናቀው። ሳኦል ዛሬም ብዙ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በሚወድቁበት ኃጢአት ወደቀ።

በመጀመሪያ፥ ሳኦል በከፊል ለእግዚአብሔር በመታዘዝ ኃጢአት ውስጥ ወደቀ። ማቅረብ ያልተፈቀደለትን መሥዋዕት አቀረበ። ደግሞም የአማሌቃውያን ነገሥታትና መንጎቻቸውን ሙሉ በሙሉ እንዲያጠፋ ታዞ ሳለ ሕዝቡ የሚሉትን ሰማና አንዳንዶቹን በሕይወት ይኖሩ ዘንድ ተዋቸው።

ዛሬም በተመሳሳይ ኃጢአት የሚወድቁ በርካታ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች አሉ። በሕዝቡ ፊት ቆመው የእግዚአብሔርን ቃል ቢያስተምሩም እንኳ፥ በሚያስተምሩት መልክ አይኖሩም። የሚሉትና የሚኖሩት ፈጽሞ የተለያየ ነው። አሥራትን ስለማውጣት ያስተምራሉ፤ እነርሱ ግን አሥራታቸውን አይከፍሉም። ስለመመስከር ያስተምራሉ፤ ነገር ግን አይመሰክሩም። ሕይወታቸውን በእግዚአብሔር ፊት በንጽሕና አይጠብቁም። ኃይሉን ለመቀበል እግዚአብሔርን ከመፈለግና ለእርሱ ክብር ከማገልገል ይልቅ በራሳቸው ኃይል በመመራት ክብርን ለራሳቸው ይፈልጋሉ።

19ኛ ጥያቄ፥ ይህ በቤተ ክርስቲያንህ ሲፈጸም ያየህባቸውን መንገዶች ዘርዝር።

ሁለተኛ:- የእግዚአብሔርን ሕዝብ ጠላቶች ለማሸነፍ እግዚአብሔር ዳዊትን በአስደናቂ ሁኔታ በተጠቀመበት ጊዜ ሳኦል ቀና። ሳኦል በዳዊት ላይ በመቅናቱ ምክንያት ቀሪውን የሕይወት ዘመኑን በሙሉ ዳዊትን ለመግደል በመሞከር አሳለፈ። ቅንዓት አሁንም ቢሆን ከእግዚአብሔር ሕዝብ መሪዎች ዋነኛ ጠላቶች አንዱ ነው። የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሥልጣናቸውንና ክብራቸውን እንደያዙ መቆየት ይፈልጋሉ። ከእነርሱ በተሻለ ሁኔታ የታወቀ ወይም እግዚአብሔር ከእነርሱ በበለጠ ሁኔታ የሚጠቀምበት ሰው ሲነሣ ቀናተኞች ይሆናሉ። ዋና ሥራቸው የበለጠ ስጦታ ያላቸውን ሰዎች ወደ መሪነት ሥልጣን እንዳይወጡ መከላከል እንደሆነ በማሰብ የሌሎችን መሪዎች ሥራ የሚከላከሉ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች አሉ።

20ኛ ጥያቄ፥ ሀ) ይህ ነገር በቤተ ክርስቲያን ሲፈጸም ያየኸው እንዴት ነው? ለ) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች መቅናት እጅግ የሚቀልላቸው ለምንድን ነው? ሐ) በሚቀኑበት ጊዜ ስለ ቤተ ክርስቲያን መሪነት የሚረሱት ነገር ምንድን ነው?

በሌሎች መሪዎች ላይ መቅናት በምንጀምርበት ጊዜ፥ መሪዎች እንሆን ዘንድ የጠራን እግዚአብሔር መሆኑን ረሳን ማለት ነው። እናገለግለው ዘንድ ችሎታን የሰጠንና ሊኖረን የሚያስፈልገው ምን

ዓይነት አገልግሎት እንደሆነ የሚወስነው እግዚአብሔር ራሱ ነው። ቅንዓት በውስጣችን በሚያድርበት በማንኛውም ጊዜ፥ እግዚአብሔር ተስማሚ ነው ብሎ በሚያስበው ቦታ እንድናገለግል ሊያደርግ፥ ከእኛ በሚበልጥ ሁኔታ በሌሎች ሊጠቀም መብቱ እንደሆነ ዘነጋን ማለት ነው። በምንቀናበት ጊዜ ደግሞ የምናገለግለው እግዚአብሔርን ሳይሆን ለራሳችን ክብር ነው ማለት ነው።

| |
|---|
| 21ኛ ጥያቄ፥ 1ኛ ሳሙ. 13-20 አንብብ። ሀ) ሳኦል ከፍልስጥኤማውያን ጋር ከመዋጋቱ በፊት እግዚአብሔርን የሚያሳዝን ምን ነገር አደረገ? ለ) ሳኦል፥ ፍልስጥኤማውያንን በሚዋጋበት ጊዜ ወንድ ልጁን ሊያጠፋት በነበረ ጊዜ ምን ሞኝ ነገር አደረገ? ሐ) ሳኦል በእስራኤል ላይ ንጉሥ እንዳይሆን እግዚአብሔር እንዲንቀው ያደረገውን ምን ክፉ ነገር ሠራ? መ) መታዘዝ ከመሥዋዕት የሚበልጠው ለምንድን ነው? ሠ) ዳዊት ንጉሥ ይሆን ዘንድ በተመረጠ ጊዜ ሥራው ምን ነበር? ረ) ዳዊት ከጎልያድ ጋር በገጠመ ጊዜ እግዚአብሔርን ያከበረው እንዴት ነው? ሰ) ከቅንዓት የተነሣ ሳኦል በዳዊት ላይ ሊያደርገው የሞከረው ነገር ምን ነበር? ሸ) በዳዊትና በዮናታን መካከል የነበረውን ግንኙነት ግለጥ። |

ሳኦል፥ የእስራኤል ንጉሥ የሆነባቸው የመጀመሪያ ጊዜያት መልካም ቢሆኑም ብዙም ሳይቆይ ከጌታ ፊቱን መለሰ። ጥልቅ የሆነ መንፈሳዊ መረዳት እንደሌለው አሳየ። በአመራሩ ላይ የሚያደርጋቸው ውሳኔዎች በጥበብ የተሞሉ አልነበሩም። የ1ኛ ሳሙኤል ጸሐፊ፥ ሳኦል ጥበብና መንፈሳዊ መረዳት የጎደለው እንደነበር ለማሳየት በርካታ ምሳሌዎችን ጠቅሷል።

1. ሳኦል፥ ሳሙኤል እስኪመጣና መሥዋዕቱን እስኪያቀርብ ድረስ በትዕግሥት መጠበቅ አቃተው። በዚህ ፈንታ እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን በፍልስጥኤማውያን ላይ ድል እንዲሰጣቸው ለመጠየቅ እንስሳ ሠዋ። ሳሙኤል፥ እንደሚመጣና ለእግዚአብሔር እንደሚሠዋ ቃል ገብቶ ነበር። ሳኦል፥ የእግዚአብሔር ነቢይ የሚናገረው እግዚአብሔርን ወክሎ ስለሆነ አንዳንድ ነገሮች እርሱ እንደ ጠበቀው ባይሆኑም እንኳ ለእግዚአብሔር መታዘዝ ነበረበት።

ይህ የሳኦል ተግባር ለሳሙኤል ብቻ ሳይሆን፥ ለእግዚአብሔርም አለመታዘዝ ነበር። ውጤቱም :- የሳኦል መንግሥት ብዙ እንደማይቆይና እግዚአብሔርም ሕዝቡን የሚመራ ሌላ ሰው እንደሚመርጥ ሳሙኤል ለሳኦል ነገረው።

22ኛ ጥያቄ፥ ሀ) ለዚህ አነስተኛ ያለመታዘዝ ተግባር እግዚአብሔር ሳኦልን በከፍተኛ ሁኔታ የቀጣው ለምን ይመስልሃል? ለ) ዛሬ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በተመሳሳይ ሁኔታ ሊፈጽሟቸውና እግዚአብሔርን ሊያሳዝኑ የሚችሉ ነገሮች ምንድን ናቸው?

2. ሳኦል የልጁን የዮናታንን ሕይወት ሊያጠፉ የነበረ የሞኝነት ትእዛዝ ሰጠ። ከፍልስጥኤማውያን ጋር በተደረገ ጦርነት ማንም ሰው እስከዚያ ቀን ምሽት ድረስ ምንም ነገር እንዳይበላ አዘዘ። ዮናታን ግን ትእዛዙን ስላልሰማ ማር በላ። ዮናታን በእግዚአብሔር ላይ በነበረው እምነት ምክንያት ፍልስጥኤማውያንን ለመግጠም የመጀመሪያውን እርምጃ ወሰደ። እስራኤላውያን በዚህ ጦርነት ድል ቢያገኙም እንኳ ዮናታን ለሳኦል ስላልታዘዘ ሳኦል ሊገድለው ወሰነ፤ ሌላው ሠራዊት ግን ዮናታንን ከሞት አዳነው።

23ኛ ጥያቄ፥ 1ኛ ሳሙ. 14:6፥ 10፥ 12 አንብብ። ዮናታን በፍልስጥኤማውያን ላይ ድልን ለማግኘት የተረጋገጠ እምነቱን ያደረገው በማን ላይ ነበር?

የዮናታንን መንፈሳዊ ሕይወት ከአባቱ ከሳኦል ጋር ማወዳደር በጣም አስደናቂ ነው። ዮናታን በእግዚአብሔር ላይ ተማምኖ ሲዋጋ፥ ሳኦል ግን ጦርነቱን ያደረገው በራሱ ብርታት ተመክቶ ነበር። ዮናታን ድሉ የተገኘው ከእግዚአብሔር እንደሆነ አስተዋለ። ሳኦል ግን ድሉን ያገኘው ራሱ እንደሆነ አሰበ፤ ደግሞም ከእግዚአብሔር ፈቃድ ይልቅ ወደ በቀል አዘነበለ (14:24)።

3. ሳኦል አማሌቃውያንና ያላቸውን ከብቶች በሙሉ እንዲያጠፋ እግዚአብሔር በሳሙኤል በኩል የሰጠውን ትእዛዝ ሳይፈጽም ቀረ። ሳኦል ከዚህ ትእዛዝ ያልፈጸመው ነገር በጣም ጥቂት ብቻ ነበር። ዳሩ ግን የአማሌቃውያንን ንጉሥና ከሁሉ የተሻሉትን

እንስሳት መግደል ሲገባው አዳነ። ሳኦል እንስሳቱን ከመግደል የተዋቸው ለራሱ ፈልጎአቸው ይሁን ወይም እርሱ እንደሚለው ሕዝቡን በመስማት ብቻ እንደሆነ ግልጥ አይደለም፤ ምክንያቱም የትኛውም ይሁን ለእግዚአብሔር ሙሉ በሙሉ ሳይታዘዝ ቀርቷል። በከፊል መታዘዝ እንደ አለመታዘዝ የሚቆጠር ነው፤ ስለዚህ እግዚአብሔር ጽኑ የሆነ ፍርድ ፈረደበት።

| |
|---|
| 24ኛ ጥያቄ፦ የሚከተሉትን ጥቅሶች ተመልከት፡- ኢሳ. 1፡11-17፤ ሆሴዕ 6፡6፤ አሞጽ 5፡21-27። ሀ) እነዚህ ጥቅሶች ለእግዚአብሔር ስለ መታዘዝ አስፈላጊነት የሚናገሩት ነገር ምንድን ነው? ለ) እነዚህ ጥቅሶች ለዚህ ዘመን አምልኮአችን የሚያስተምሩን ነገር ምንድን ነው? |

1ኛ ሳሙ. 15፡22-23 በ1ኛ ሳሙኤል ውስጥ ከሚገኙ በጣም አስፈላጊ ከሆኑ ጥቅሶች ሁለቱ ናቸው። እነዚህ ጥቅሶች የቀድሞ እስራኤላውያንም ሆኑ የዚህ ዘመን ክርስቲያኖች ያላቸውን የተሳሳተ አስተሳሰብ ያስተካክላሉ። አይሁድ ብዙ ጊዜ የእግዚአብሔር ትኩረት በውጫዊ የአምልኮ ሥነ ሥርዓት ላይ እንደሆነ ያስባሉ። መሥዋዕት በሚያቀርቡበት ጊዜ እግዚአብሔር ስለ ልባቸው ዝንባሌና የራሳቸውን ዕለታዊ ሕይወት ስለሚኖሩበት የአኗኗር ስልት ምንም ግድ የለውም ብለው ያስቡ ነበር። ዛሬም ብዙ ክርስቲያኖች ዋናው አስፈላጊው ነገር መሰብሰባችን፥ መዝሙር መዘመራችን፥ ወዘተ. ነው ብለው ያስባሉ። ከቤተሰቦቻቸው፥ ከጎረቤቶቻቸው ጋር ስላላቸው ግንኙነት፥ ወይም በሥራ ገበታቸው ላይ በሚታየው ተግባራቸውና በዝንባሌያቸው ላይ እግዚአብሔር ምንም ትኩረት የማያደርግ ይመስላቸዋል።

እግዚአብሔር ግን በሳሙኤልና በሌሎች ነቢያት እንደገለጠው አምልኮ የሚጀምረው አምልኮውን በሚፈጽመው ሰው ዕለታዊ ሕይወት ነው። እውነተኛ አምልኮን ለመፈጸም ትክክለኛ ዝንባሌ ያስፈልጋል። በትክክለኛ ዝንባሌ ውስጥ ለእግዚአብሔር ትእዛዝ የመገዛትና የመታዘዝ ዝንባሌ አለ። ለእግዚአብሔር ካልታዘዝን፥ ሳምንቱን በሙሉ እግዚአብሔርን ደስ በሚያሰኝ ነገር ካልተመላለስን፥ እሑድ በምናመልከው ብቻ እግዚአብሔር ደስ አይሰኝም። አምልኮ

የሚጀምረው ሳምንቱን በሙሉ በምናደርገው ድርጊት ነው። እሑድ የምናደርገው ነገር ለእግዚአብሔር በመታዘዝና እርሱን በማክበር ሳምንቱን በሙሉ ያሳለፍነው ነገር ማጠቃለያ ነው።

ሳሙኤል መታዘዝ ከመሥዋዕት ይበልጣል ብሏል። በተጨማሪ፣ በእግዚአብሔር ላይ የሚፈጸም ዓመፅ፣ ለእግዚአብሔር አለመታዘዝና መሰል አድራጐቶች ሁሉ የስሕተት አማልክትን የማምለክ ያህል የከፋ ናቸው ብሏል። ለእግዚአብሔር አለመታዘዝ ማለት ፈቃዳችንን የሕይወታችን አምላክ አድርገናል ማለት ነው፤ ስለዚህ ለእግዚአብሔር በማንታዘዝበት ጊዜ በስህተት ማምለክ ጀመርን ማለት ነው። የሕይወታችን አምላክ ሆንን ማለት ነው። እግዚአብሔር በሕይወታችን ላይ ሙሉ በሙሉ የሚያደርገውን የተቆጣጣሪነት መብት እኛው ወሰድን ማለት ነው።

| |
|---|
| 25ኛ ጥያቄ፣ ሀ) ብዙ ጊዜ ክርስቲያኖች ለእግዚአብሔር ትእዛዛት በመጠኑ አለመታዘዝ ብዙ ጉዳት አያመጣም ብለው እንዴት እንደሚያስቡ የሚያሳዩ መግለጫዎችን ስጥ። ለ) በማይታዘዙበት ጊዜ እውነተኛ የጣዖት አምልኮ የሆነ በልባቸው ያደረጉት ነገር ምንድን ነው? ሐ) ከዚህ ታሪክ ትንሽ ኃጢአት ስለሚያመጣው ጉዳት ምን እንማራለን? |

እግዚአብሔር ለሳኦል የእስራኤል ንጉሥ እንዳይሆን የተናቀ መሆኑን ነገረው። መንግሥቱ ለልጆቹ እንደማያልፍ እግዚአብሔር ለሳኦል ከመናገሩ በፊት፣ ሳኦል ራሱ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ በሕይወት እያለ እንኳን የእስራኤል ንጉሥ መባሉ እንደቀረ ይነገረዋል። እርግጥ ከዚህ በኋላ ሳኦል ለብዙ ዓመታት የእስራኤል ንጉሥ ሆኖ ቢቆይም፤ ነገር ግን የእግዚአብሔር ሕዝብ ራስ (መሪ) ሆኖ በእግዚአብሔር ተወክሎ መሥራቱ ቀርቶ ነበር። እግዚአብሔር መንፈሱን ከሳኦል ላይ ወስዶ ነበር። ሳሙኤልም ከዚያ በኋላ ተመልሶ መጥቶ የእግዚአብሔርን ቃል ነግሮት አያውቅም።

26ኛ ጥያቄ፥ ሀ) መሪዎች እንደመሆናችን መጠን እግዚአብሔርን በሚያሳዝኑ ትናንሽ በሚመስሉ ነገሮች እንኳ ለእርሱ ለመታዘዝ ተጠንቅቀን መኖር እንዳለብን ይህ ታሪክ ምን ያስተምረናል? ለ) ያለ እግዚአብሔር ሕልውናና ኃይል በመሪነት ስለ መቀጠል ይህ ታሪክ ምን ያሳያል?

4. በዳዊትና በሳኦል መካከል የቀረበ ንጽጽር (1ኛ ሳሙ. 16-20)

ሀ. ዳዊት የእግዚአብሔርን መንፈስ ሲቀበል፥ ሳኦል ግን ክፉ መንፈስ ተቀበለ። እግዚአብሔር ሳኦልን ከናቀ በኋላ፥ የሚቀጥለው የእስራኤል ንጉሥ ይሆን ዘንድ ዳዊትን መረጠው። እግዚአብሔር ዳዊትን የመረጠው በውጫዊ መመዘኛ ሳይሆን በልቡ ስለነበረው ነገር ነው (1ኛ ሳሙ. 16፡7)። ዳዊት ትሑትና በእግዚአብሔር ላይ የሚታመን ሰው ነበር። በእጅጉ ኃጢአት ቢያደርግም እንኳ ለኃጢአት ሰበብ ከመስጠት ይልቅ ይቅርታ ለመጠየቅ ፈጣን ነበር። በእስራኤል ከነገሡት ነገሥታ ሁሉ ጨርሶ ተወዳዳሪ የሌለው ታላቅ ንጉሥ የሆነው ለእግዚአብሔር በነበረው ፍቅር፥ ለእግዚአብሔርና ለሕዝቡ በፍጹም ትሕትና በሰጠው አገልግሎትና ለእግዚአብሔር በነበረው መታዘዝ ነው።

የእግዚአብሔር መንፈስ ከሳኦል ከተለየ በኋላ በዳዊት ላይ መጣ፡- በሳኦል ሕይወት ግን በእግዚአብሔር መንፈስ ፈንታ በቀሪው የሕይወት ዘመኑ ሁሉ ያሠቃየው ክፉ መንፈስ አደረበት። ሳኦል ለእግዚአብሔር መታዘዝን እምቢ ስላለ እግዚአብሔር የጥበቃ እጁን ከሳኦል ላይ አነሣ፤ ስለዚህ ሰይጣን በሳኦል ቀሪ የሕይወት ዘመን ሁሉ ወደ እርሱ እየመጣ ያሠቃየው ዘንድ ሙሉ ችሎታ አገኘ። ለሰይጣንና ለክፉ መናፍስት ተጽዕኖ ራሳችንን የምናጋልጠው ለእግዚአብሔር ባለመታዘዝ በምንኖርበት ጊዜ ነው። ለእግዚአብሔር በመታዘዝ በምንኖርበት ጊዜ ግን ከሰይጣንና ከክፉ መናፍስት እንጠበቅና የእግዚአብሔር መንፈስ ይቆጣጠረናል። የሰይጣንን ሥራዎች የሚወስንና ከልካቸው እንዳያልፉ የሚያደርገው እግዚአብሔር ነው። እግዚአብሔር ሳይፈቅድለት ሰይጣን ሚፉችንን ሊነካ አይችልም።

ለ. ዳዊት የሳኦልን መንፈስ ለማረጋጋት ይችል ዘንድ ወደ ቤተ መንግሥት መጣ። ዳዊት ሙዚቀኛ ስለነበር ሙዚቃው ሳኦልን ደስ ያሰኘው ነበር፤ ስለዚህ ሳኦል ከሚታመንባቸው ሰዎች አንዱ ሆኖ የሳኦል የጦር መሣሪያ ተሸካሚ (ጋሻ ጃግሬ) ሆነ። (** የእነዚህን ተግባራት አፈጻጸም ትክክለኛ ቅደም ተከተል መረዳት አስቸጋሪ ነው። በ1ኛ ሳሙ. 17 ያለው ታሪክ የተፈጸመው በ1ኛ ሳሙ. 16 ላይ ከሚገኘው በፊት ሳይሆን አይቀርም።) ሳኦል ያገለግለው ዘንድ ወደ ቤተ መንግሥቱ የጋበዘው ሰው በእርሱ ምትክ ይነግሥ ዘንድ እግዚአብሔር የመረጠው ሰው መሆኑን መገንዘብ በጣም የሚገርም ነው። ዳዊት በዚህ መልክ ወደ ቤተ መንግሥቱ በመምጣት ያገኘው ልምምድ በእስራኤል ላይ መሪ በሆነ ጊዜ እንደ ጠቀመው አንዳችም ጥርጥር የለንም።

ሐ. ዳዊት በጎልያድና በፍልስጥኤም ሕዝብ ላይ ድልን ተቀዳጀ (1ኛ ሳሙ. 17)።- ሳኦል በፍልስጥኤማውያን ላይ ድልን ለመቀዳጀት በእግዚአብሔር አልታመነም። ዳዊት ግን ልጅ ቢሆንም እንኳ በእግዚአብሔር ላይ ጥልቅ የሆነ እምነት ነበረው። ፍልስጥኤማውያን የእግዚአብሔርን ስም በመሳደባቸው በውስጡ በተፈጠረው ቁጣ ድልን እንደሚሰጠው በእግዚአብሔር ላይ ተደገፈ። እግዚአብሔርም በጎልያድ ላይ ድልን ሰጠውና እስራኤላውያን ፍልስጥኤማውያንን እንዲያሸንፉ አስቻላቸው።

27ኛ ጥያቄ፡ ሀ) ይህ ታሪክ ለእግዚአብሔር ክብርን መስጠት የሚገባን መሆኑን በሚመለከት ትኩረት ስለመስጠት ምን ያስተምረናል? ለ) በእርሱ ከታመንን የእግዚአብሔር ኃይል ውጤታማ እንደሚያደርገን ምን ያስተምረናል?

መ. የሳኦል ቅንዓትና ዳዊትን ለማጥፋት ያደረገው ሙከራ (1ኛ ሳሙኤ. 18-26)። የቀሩት የ1ኛ ሳሙኤል ታሪኮች በአብዛኛው የሚያሳዩን ሳኦል በቅንዓት የተነሣ ዳዊትን ለመግደል ያደረጋቸውን የተለያዩ ሙከራዎችን ነው።

በተቃራኒው ግን ዳዊት ሳኦልን ለመግደል ልዩ ልዩ አመቺ ሁኔታዎች ቢያጋጥሙትም እንኳ እምቢ በማለት ታላቅ የእግዚአብሔር ሰው መሆኑን አስመሰከረ። ዳዊት በእስራኤል ውስጥ እጅግ ከታወቀ በኋላ ሳኦል በተለያዩ መንገዶች ዳዊትን ለመግደል ሞከረ። ዳዊት ሁለት ጊዜ ያህል የሳኦልን ልብ ለማረጋጋት የሙዚቃ መሣሪያውን በሚጫወትበት ጊዜ ሳኦል ሊገድለው ሞክሯል። በተጨማሪ በጦር ሜዳ እንዲገደል ለማድረግ ፍልስጥኤማውያንን በተለያየ መንገድ በመዋጋት ሁለት መቶ ሸለፈቶች እንደ እጅ መንሻ (ጥሎሽ) ይዞ እንዲመጣ አበረታታው። ዳዊትም ይህ ነገር ተሳካለትና በውጤቱ ሜልኮል የተባለችውን የሳኦልን ልጅ ከንጉሣዊ ቤተሰብ ለማግባት ቻለ። ዳዊት የተከናወነለት የሳኦል ጦር አዛዥ ሆነ።

ሳኦል በዳዊት ላይ ከነበረው ቅንዓትና ጥላቻ በተቃራኒ፥ የሳኦል ልጅና የእስራኤል ዙፋን ወራሽ መሆን የነበረበት ዮናታን ለዳዊት የነበረው አመለካከት የፍቅር ነበር። በዳዊትና በዮናታን መካከል የነበረው የፍቅር ግንኙነት፥ በቅርብ ጓደኛሞች መካከል ሊኖር የሚገባ የፍቅር ምሳሌ ነው። ዮናታን ዳዊትን ጓደኛ አድርጎ ተቀበለው። እንደ ሳኦል አባባል፥ ዳዊት የሳኦልን መንግሥት የመገልበጥ አሳብ አለው የሚለውን ነገር ዮናታን ለማመን አልፈለገም። በመጀመሪያ ሳኦል ዳዊትን ለመግደል እንደሚፈልግም አላመነም ነበር። ሳኦል እርሱን ለመግደል በሞከረ ጊዜ ግን፥ ሳኦል ዳዊትን ለመግደል እንደሚፈልግ ዮናታን አመነ። ከዚያም ከሳኦል ፊት በመሸሽ እንዲሰወር ዳዊትን አስጠነቀቀው። ዮናታን ከዳዊት ጋር ከገባው ቃል ኪዳን በግልጥ እንደምንመለከተው (1ኛ ሳሙ. 20፡12-17)፥ የቀጣዩ የእስራኤል ንጉሥ ዳዊት መሆኑን ዮናታን ተረድቶ ነበር። በዳዊት ላይ ከመቅናት ይልቅ በእርሱና በዳዊት መካከል ያለውን ጓደኝነት እንዲቀጥልና ዳዊትም የእርሱን ዝርያዎች በርኅራኄ እንዲመለከት ብቻ ጠየቀ። ዳዊትም ይህንን ቃሉን በመጠበቅ ከሳኦልና ከዮናታን ሞት በኋላ ለቤተሰቦቻቸው መልካም አደረገ (2ኛ ሳሙ. 9)።

28ኛ ጥያቄ፥ ሀ) ሳኦል ለዳዊት የነበረውንና ዮናታን ለዳዊት የነበረውን አመለካከት አወዳድር። ዮናታን ከሳኦል ይልቅ መንፈሳዊ ብስለት የታየበት እንዴት ነው? ለ) በዳዊትና በዮናታን መካከል የነበረው ኅብረት፥ ለእኛም የቅርብ ጓደኝነት ኅብረት ስለማስፈለጉ ምን ያስተምረናል? ሐ) እግዚአብሔር አንድን ሰው መርጦ መሪ ይሆን ዘንድ ቢባርከው መቅናት እንደሌለብን ይህ ምን ያስተምረናል?

## 4ኛ ቀን 1ኛ ሳሙኤል 21-31

29ኛ ጥያቄ፥ ለእግዚአብሔር በመታዘዝ ብንኖር ከማንፈልገው ነገር ሁሉ ይጠብቀናልን? ይህስ ማለት የሚያጋጥሙን መልካም ነገሮች ብቻ ናቸው ማለት ነውን? መልስህን አብራራ።

ብዙ ክርስቲያኖች እግዚአብሔርን ከታዘዝንና በእግዚአብሔር ከተባረክን ነገሮች ሁሉ በሕይወታችን በመልካም ሁኔታ ይከናወናሉ ብለው ያስባሉ። ለእግዚአብሔር እየታዘዝን የመኖራችን ምልክት ያለ ችግሮችና ያለምንም ሳንካ መኖራችን እንደሆነ ይመስላቸዋል። አንታመምም፤ ልጆቻችን አይሞቱም፤ ሰብላችንም አይበላሽም፤ ወዘተ. ይላሉ፤ ነገር ግን ይህ ስሕተት ነው። እንዲያውም ብዙ ጊዜ ነገሮች ሁሉ ያለምንም ችግር መከናወናቸው ለእግዚአብሔር ያለመታዘዛችን ምልክት ነው። ጌታ ኢየሱስ እንዳለው በመታዘዝ በምንኖርበት ጊዜ ስደትና ችግር ይገጥመናል (ዮሐ. 15፡18-21 ተመልከት)፤ ስለሆነም በሕይወታችን ችግር የመኖሩ ነገር፥ እግዚአብሔር እንደሚወደንና በእምነታችን እንድንጎለምስ ለማድረግ አስቸጋሪ ሁኔታዎችን እንደሚጠቀም ነው (ያዕ. 1፡2-4 ተመልከት)፤ ስለዚህ ማንኛውም ዓይነት ችግር ያለመታዘዝ ውጤት ነው በማለት ፈጥነን ከመፍረድ ልንቆጠብ ይገባናል።

የ1ኛ ሳሙኤል የመጨረሻው ክፍል በመሠረቱ በሳኦልና በዳዊት መካከል ያለውን ግጭት የሚተነትን ክፍል ነው። ዳዊት ንጉሥ እንዲሆን በእግዚአብሔር ተመርጦ ነበር። በእግዚአብሔር ዓይን የእግዚአብሔር ሕዝብ ትክክለኛ ንጉሥ ዳዊት ነበር፤ ነገር ግን ዳዊት በበርካታ ዓመታት ኮብላይ (ተሳዳጅ) ሆኖ በዋሻ ተደብቆ ኖረ። ከሳኦል

የግድያ ሙከራ ለማምለጥ ከቦታ ወደ ቦታ ይዞዋወር ነበር። ንጉሥ ለመሆን ምንም ዓይነት ኃይልን ለመጠቀም ፈቃደኛ ሳይሆን ቀረ። ጥላቻና ብቀላ ወደ ሕይወቱ እንዲገባ አልፈቀደም። ይልቁንም እግዚአብሔር ራሱ በሳኦል ላይ እስኪፈርድና መንግሥቱን እስኪሰጠው ድረስ ለመጠበቅ ወሰነ። ይህ ለእኛ ብርቱ ማስጠንቀቂያ ሊሆነን ይገባል። ነገሮችን በራሳችን እጅ በማከናወን የኀበጠውን ለማቃናት ከመፍጨርጨር ይልቅ እግዚአብሔርን በትዕግሥት ልንጠብቀው ይገባል። በተጨማሪ ከእግዚአብሔር ጋር በፍጹም ታዛዥነት በምንኖርበት ጊዜ እንኳ በብዙ አስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ ማለፍ እንደምንችል ያስተምረናል።

| |
|---|
| 30ኛ ጥያቄ፥ 1ኛ ሳሙ. 21-31 አንብብ። ሀ) በእነዚህ ምዕራፎች ውስጥ የምታገኘውን የሳኦልና የዳዊት ሕይወት አነጻጽር። ሳኦል ለመሪነት የማይገባ መሆኑ የታየው እንዴት ነው? ዳዊት በእስራኤል ላይ መንገሥ የሚገባው መሪ መሆኑ የታየው እንዴት ነው? ለ) በእነዚህ ምዕራፎች፥ የእግዚአብሔር እጅ በዳዊት ሕይወት ውስጥ የታየው እንዴት ነው? ሐ) እግዚአብሔርን የሚያስደስቱ ዳዊት ያደረጋቸው ወይም ሊያደርጋቸው የሞከራቸው ነገሮች ምንድን ናቸው? መ) ዳዊት የሠራዊት አዛዥ እንደመሆኑ መጠን ኃይሉ የታየው እንዴት ነው? ሠ) ሳኦል ያለማቋረጥ ለእግዚአብሔር ሳይታዘዝ መኖሩ በእግዚአብሔር፥ በራሱና በልጆቹ ሕይወት ያመጣው ውጤት ምንድን ነው? |

መጽሐፍ ቅዱስ የሰዎችን ስሕተት ከመደበቅ ይልቅ ያደረጉትን መልካምም ሆነ ክፉ ወይም የሞኝነት ነገር ሁሉ በግልጥ ይናገራል። በእነዚህ ምዕራፎች በሳኦልና በዳዊት መካከል ያሉ በንጽጽር የቀረቡት ጉዳዮችን እናያለን። በአንድ ወቅት በእስራኤል ላይ ታላቅ መሪ የነበረው ሳኦል በቅንዓት ዳዊትን ለመግደል በመሞከር ጊዜውን ሁሉ ሲያጠፋ እንመለከተዋለን። ፍልስጥኤማውያንን ከመውጋት ይልቅ ሳኦል ከዳዊት ጋር ተዋጋ፤ ደግሞ የዳዊትን ድካምና ጥንካሬ የሚገልጡ ነገሮችን እንመለከታለን።

የሳኦል ሕይወት ፍጻሜ በጣም አሳዛኝ ነው። ከእግዚአብሔር ጋር እንዳችም ግንኙነት ሳያደርግና ከእርሱም እርዳታ ሳያገኝ ከሞተው ከሳሙኤል ጋር ለመገናኘት ሞከረ። ሙታንን የማናገር ችሎታ እንዳላት ወደሚነገርላት አንዲት ጠንቋይ ዘንድ ሄደ። ጥንቆላና ጠንቋዮች በእግዚአብሔር ዘንድ ፈጽሞ የተከለከሉ መሆናቸውን ታስታውሳለህ። ሳኦል ግን የሳሙኤልን ምክር ፈለገ፤ ስለዚህ ይህች ሴት ከሳሙኤል ጋር እንድታገናኘው ፈለገ። ከዚህ በኋላ የተፈጸመው ነገር ምን እንደሆነ በትክክል ማወቅ አስቸጋሪ ነው። አንዳንድ ሰዎች የሳሙኤል መንፈስ መጥቶ ከሳኦል ጋር እንዲነጋገር እግዚአብሔር ፈቅዶ ይሆናል ይላሉ። ሌሎች ሰዎች ደግሞ በሳሙኤል መንፈስ ቅርጽ የተገለጠ ርኩስ መንፈስ ነው ይላሉ። ለዚህ ጉዳይ የምንሰጠው ምላሽ ምንም ይሁን ምን፥ እግዚአብሔር ይህንን ክፉ ሁኔታ ሳኦል የሚሞትበት ጊዜ የቀረበ መሆኑን ለመናገር ተጠቀመበት። ለጠንቋይዋ ሳይቀር አንድ ያልተለመደ ነገር እንደተፈጸመ የሚያሳየው ሳሙኤልን ባየች ጊዜ በታላቅ ፍርሃት መሸበሯ ነው። በመጀመሪያ ያልተለመደውን የሳሙኤልን መንፈስ ፈራች። በሁለተኛ ደረጃ ጠንቋዮችን ለመግደል የሞከረውን ሳኦልን ፈራች። በዚህ ታሪክ ውስጥ ዋናው ነገር ይህ እንዴት ተፈጸመ የሚለው አይደለም፤ ነገር ግን አለመታዘዝ የሚያስከትለውን ውጤት ነው። እግዚአብሔር በብዙ መንገድ ያልታዘዘውን የሳኦልን ሞት ተንብዮአል።

ሳኦል ለእግዚአብሔር መታዘዝ እምቢ ስላለ፥ ብዙ አሳዛኝ ነገሮች ተፈጸሙ። በመጀመሪያ፥ የእስራኤል ሕዝብ ስለተሸነፈ፥ ብዙ እስራኤላውያን በጦርነት ሞቱ። ሁለተኛ፥ አብዛኛዎቹ የሳኦል ልጆች ሞቱ። ሦስተኛ፥ ሳኦል በፍልስጥኤማውያን እጅ ከመሞት ይልቅ ራሱን ገደለ።

አንድ መሪ ለእግዚአብሔር አለመታዘዝ ሲጀምር፥ ነገሩ ቀላል መስሎ ሊታይ ይችላል፤ ዳሩ ግን የእርሱ አለመታዘዝ ወዲያውኑ ሌሎች በርካታ ሰዎችን መንካት ይጀምራል። ሕዝቡን የሚመራው በመንፈስ ቅዱስ ኃይል መሆኑ ቀርቶ በራሱ የግለኝነትና የስስት ኃይል ስለሚሆን፥ የቤተ ክርስቲያኒቱ አባላት በችግር ላይ ይወድቃሉ፥ ብዙዎች ቤተ ክርስቲያንን ይተዋሉ። እንዲያውም የሐሰት ትምህርት

ይቀበላሉ፥ በቤተሰቡም ላይ ችግር ይደርሳል። ልጆቹም የእርሱን ግብዝነት በማየት፥ የክርስቶስን ስም እያሰደቡ፥ ቤተ ክርስቲያንን ትተው ይሄዳሉ። በመጨረሻም አገልግሎቱ በሙሉ ይጠፋል።

| |
|---|
| 31ኛ ጥያቄ፥ ሀ) ይህ ነገር በቤተ ክርስቲያን ሲፈጸም እንዴት አይተሃል? ለ) ቤተ ክርስቲያንን ለመምራት ከሳኦል ሕይወት የምንማራቸው አንዳንድ ማስጠንቀቂያዎች ምንድን ናቸው? ሐ) ለእግዚአብሔር ክብርን ለማምጣትና ለብዙ ሰዎች በረከትን ለማስገኘት በሚያስችል ሁኔታ ለመምራት ውሳኔ የምናደርግባቸው መንገዶች የትኞቹ ናቸው? |

እነዚህ ምዕራፎች ዳዊትን ኃጢአት ያልነካካው ፍጹም ሰው አድርገው አያቀርቡትም። ስላለፉት የእግዚአብሔር ሰዎች በምናስብበት ጊዜ፥ ፍጹም እንደነበሩና ከኃጢአት ጋር እንዳልታገሉ አድርገን እንገምታለን፤ ይህ ግን እውነት አይደለም። በእነዚህ ምዕራፎች፥ ዳዊትም ራሱ ኃጢአተኛና እንደ እኛው ፍጹምነት የሌለው ሰው እንደነበር እናያለን። ይህም ቢሆን እንኳ ዝንባሌው እግዚአብሔርን ደስ ስላሰኘው፥ እግዚአብሔር በመሪነት አከበረው። ከእነዚህ ምዕራፎች ስለ ዳዊት የሚከተሉትን ነገሮች አስተውል:-

1. ዳዊት ሳይፈልግ ለበርካታ ሰዎች ሕይወት መጥፋት ምክንያት ሆነ (1ኛ ሳሙ. 21)። ዳዊት ከሴሎ በኋላ የአምልኮ ማዕከል ወደሆነችው ወደ ኖብ በሚሄድበት ጊዜ ንጉሥ ሳኦል እንደሚከታተለው ያውቅ ነበር። እርሱን የረዱትን ሰዎች ሳኦል እንዳይገድላቸው ወደ ሌላ ስፍራ መሄድ ነበረበት። ዳዊት ግን ወደ ካህኑ ስለ ሄደ፥ 85 ካህናት በሳኦል ተገደሉ።

2. ዳዊት ከፍልስጥኤማውያን ጋር በሚኖርበት ጊዜ እግዚአብሔር እንደሚጠብቀው ባለማመኑ ራሱን እንደ ዕብድ አስመሰለ (1ኛ ሳሙ. 21፡13)።

3. ዳዊት የሳኦልን ሕይወት ሁለት ጊዜ አዳነ። ዳዊት የእስራኤልን ዙፋን ለማግኘት ሲል ነፍስ ለማጥፋት አልፈለገም፤ ነገር ግን

እግዚአብሔር የተስፋ ቃሉን በጊዜው እንዲፈጽም ታግሦ ጠበቀ (1ኛ ሳሙ. 24 እና 26)።

4. ዳዊት በበቀል አንድን ቤተሰብ ሊያጠፋ ምንም ያህል አልቀረውም ነበር (1ኛ ሳሙ. 25)። የአቢግያ ባል ዳዊት ስላደረገለት ነገር ሁሉ ስላላመሰገነ፥ ዳዊት ቤተሰቡን ሊያጠፋ ነበር። ይህ ቢደረግ ኖሮ ለራስ ጥቅም በስግብግብነት ሥልጣንን አላግባብ መጠቀም እንደ መሆኑ፥ ከፍተኛ የፍርድ መዛባት ይሆን ነበር። እግዚአብሔር ግን በአቢግያ የብልህነት ተግባር በመጠቀም የዳዊት እጅ አንዳችም ጥፋት በሌለባቸው ሰዎች ደም እንዳይበከል ጠበቀው። ኋላም እግዚአብሔር ራሱ የአቢግያን ባል ቀጣው። የእስራኤል ዙፋን አንድ ቀን በዳዊት እጅ እንደሚገባ አቢግያ ቀድማ ተርድታ እንደ ነበር ማየት የሚገርም ነው።

## የ1ኛ ሳሙኤል ዋና ዋና ትምህርቶች

ቀደም ሲል እንደ ጠቀስነው፥ 1ኛ ሳሙኤል በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ ስለሚሆን መንፈሳዊ መሪነት የሚናገር መጽሐፍ ነው። የመጽሐፉ መግቢያ ዔሊና ሳሙኤል የተባሉትን ሁለት ካህናት ያነጻጽራል። የእግዚአብሔርን አምልኮ በንጽሕና ባለመጠበቁ እግዚአብሔር ዔሊን ናቀው። ሳሙኤል ደግሞ ሕዝቡን ከእግዚአብሔር ጋር አስቀድመው ወደገቡት ቃል ኪዳን ለመመለስ በመወሰኑ አከበረው። ሳሙኤልን ልዩ የሚያደርገው በእስራኤል ላይ ሊቀ ካህን፥ ሕዝቡን የሚያስተዳድር መስፍንና የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለሕዝቡ የሚያሳውቅ ነቢይ መሆኑ ነው። እንዲያውም ሳሙኤል የእስራኤልን ሕዝብ ከግብፅ ባርነት እንዲያወጣ ካደረገው ነቢይ ከሙሴ በኋላ የመጣ ተወዳዳሪ የሌለው ነቢይ ነበር።

ቀጥሎም 1ኛ ሳሙኤል ሳኦልና ዳዊት የተባሉት ሌሎች ሁለት መሪዎችን ያወዳድራል። ሁለቱም በእግዚአብሔር የተመረጡ ነበሩ። ሁለቱም ሰዎች የእግዚአብሔርን ቅዱስ መንፈስ ተቀብለዋል። እግዚአብሔር ሁለቱንም ጠላቶቹን ለማሸነፍ ተጠቅሞባቸዋል። እግዚአብሔር ግን የተከበረው በአንዱ ብቻ ሳይሆን በሌላውም ነበር። ሳኦል የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ስላልተከተለና በመንፈሳዊ ነገርና በልቡ ንቁ ስላልነበረ፥ በእስራኤል ላይ ንጉሥ እንዳይሆን እግዚአብሔር

ናቀው። በእግዚአብሐር ፊት ኃጢአቱን አምኖ ከመቀበልና ከመናዘዝ ይልቅ፥ ሁልጊዜ ለድርጊቱ ምክንያት ያቀርብ ነበር። በራሱ ኃይል ለመዋጋት ሞክሮ ነበር። ትኩረቱ በራሱ ዝነኛነት ላይ ብቻ ነበር። በመጨረሻም ሳኦል በእስራኤል ሕዝብ ላይ ጥፋትን በራሱና በልጆቹም ላይ ሞትን አመጣ። በቅንዓቱ ምክንያት የመሪነት ችሎታው በሙሉ ተወሰደበት።

ዳዊት ግን ተራ የከብቶች ጠባቂ (እረኛ) ቢሆንም እንኳ የእግዚአብሔርን ሕዝብ ለመምራት እግዚአብሔር የሚፈልገው ዓይነት ልብ ነበረው። ዳዊት ድል የሚገኘው በእግዚአብሔር መሆኑን ስለ ተገነዘበ በጦርነት ድልን እንደሚሰጠው በእግዚአብሔር በመታመን ይዋጋ ነበር። ዳዊት እግዚአብሔር በእስራኤል ላይ ንጉሥ ይሆን ዘንድ በቀባው በማንኛውም መሪ ላይ የበቀል እጁን ላለማንሣት ወሰነ። ሳኦልን በመገደል የእርሱን ሞት ለግል ጥቅሙ ሊጠቀምበት ሳይፈቅድ ቀረ። በኋላም እንደምንመለከተው፥ ኃጢአትን በሚያደርግበት ጊዜ ልቡን ወደ እግዚአብሔር የሚያቀናና ከእግዚአብሔር ዘንድ ይቅርታን የሚጠይቅ እንደ ነበር እናያለን። የዳዊት ታላቅነት በታላቅ ተግባሩ ወይም ያለ ኃጢአት በመሆኑ አይደለም፤ ነገር ግን እግዚአብሔርን ለመከተል፥ ለእግዚአብሔር ለመታዘዝና በእግዚአብሔር ላይ ኃጢአት በሚሠራበት ጊዜ ንስሐ ለመግባት በነበረው ጽኑ ፍላጎት ነው።

32ኛ ጥያቄ፥ ሀ) ብዙ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ልክ እንደ ሳኦል የሚሆኑት እንዴት ነው? ለ) ልክ እንደ ዳዊት ያሉ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ጥቂት የሆኑት ለምንድን ነው? ሐ) ከሳኦልና ከዳዊት ሕይወት ስለ መንፈሳዊ አመራር የምንማራቸውን አንዳንድ መመሪያዎች ዘርዝር። መ) እነዚህን ነገሮች ከሕይወትህ ጋር የምታዛምደውና በቤተ ክርስቲያንህ ላሉ ሌሎች መሪዎች የምታስተምረው እንዴት ነው?
33ኛ ጥያቄ፥ 1ኛ ሳሙ. 2፡30 አንብብ። ሀ) ይህ ጥቅስ በሳኦልና በዳዊት ሕይወት የተፈጸመው እንዴት ነው? ለ) በቤተ ክርስቲያን ባለህ አመራር ውስጥ እግዚአብሔርን ልታከብር የምትችልባቸውን አንዳንድ መንገዶች ጥቀስ። ሐ) በቤተ ክርስቲያን ባለህ አመራር ውስጥ የእግዚአብሔርን ስም ልታስነቅፍ የምትችልባቸውን መንገዶች ዘርዝር።

5ኛ ቀን።

የዚህን ሳምንት ትምህርት ከልስና ለሳምንታዊው ስብሰባ ዝግጅት ይረዳህ ዘንድ የውይይት ጥያቄዎቹን ተመልከት።

ሳምንታዊው ስብሰባ

1. የሳምንቱ የአምልኮ ጊዜ

2. ጸሎት

3. የትምህርቱ ክለሳ

4. ውይይት

1. ሀ) ከዔሊ ይልቅ ሳሙኤል መንፈሳዊ ንቃት ያሳየባቸው መንገዶች ምንድን ናቸው? ለ) ከዔሊና ከሳሙኤል ሕይወት ስለ መንፈሳዊ መሪነት የምንማራቸውን ነገሮች ጥቀስ። የምንመለከታቸውን ማስጠንቀቂያዎችና ልንከተላቸው የሚገባን ምሳሌዎችን ጥቅስ። ሐ) እነዚህ ትምህርቶች በዚህ ዘመን ባሉ መሪዎች ሕይወት መታየት ያለባቸው እንዴት እንደሆነ ምሳሌዎችን ጥቀስ።

2. ሀ) እግዚአብሔር የዔሊን ካህንነት የናቀው ለምን ነበር? ለ) ይህ ነገር ዛሬም በቤተ ክርስቲያን መሪዎች መካከል ችግር የሆነው እንዴት ነው? ሐ) አንድ የቤተ ክርስቲያን መሪ ልጆቹ ለእግዚአብሔር እንዲታዘዙ በሚያደርግ መንገድ ልጆቹን ሊያሳድግ የሚችልባቸውን መንገዶች ዘርዝር።

3. ሀ) እስራኤላውያን ስለ እግዚአብሔርና ስለ ታቦቱ የነበራቸው የተሳሳተ አስተሳሰብ ምን ነበር? ለ) ዛሬም ክርስቲያኖች ስለ እግዚአብሔር ሊኖራቸው የሚችለውን የተሳሳተ አስተሳሰብ የሚያመለከቱ ምሳሌዎችን ጥቀስ። ሐ) ስለ እግዚአብሔር እውነተኛ ባሕርይ ይበልጥ በተሻለ መንገድ ማስተማር የምትችለው እንዴት ነው?

4. ሀ) እስራኤላውያን እግዚአብሔር ንጉሥ እንዲሰጣቸው የፈለጉበት ውስጣዊ ዓላማ ምን ነበር? ለ) እግዚአብሔር በዚህ ደስ ያልተሰኘው ለምን ነበር? ሐ) አንዳንድ ሰዎች የቤተ

ክርስቲያን መሪ ለመሆን የሚፈልጉባቸው የተሳሳቱ ዓላማዎች የትኞቹ ናቸው? መ) ሰዎች የቤተ ክርስቲያን መሪዎችን የሚመርጡባቸውን የተሳሳቱ ዓላማዎች ጥቀስ። ሠ) እውነተኛ መንፈሳዊ መሪነት ምን እንደሆነ እንዲያውቁ የቤተ ክርስቲያን መሪዎችንና ሕዝቡን እንዴት ልንረዳቸው እንችላለን?

5. ሀ) ለእግዚአብሔር አለመታዘዝ እጅግ አስከፊ ጥፋት መሆኑን ሳሙኤል ያሳየው እንዴት ነው? ለ) ማንኛውም ዓይነት ለእግዚአብሔር ያለመታዘዝ ተግባር ከሐሰተኛ አምልኮ ጋር አንድ የሆነው እንዴት ነው?

6. ሀ) የአንድ አገር መሪ የሥነ - ምግባር ሕይወት፥ የአገሪቱን ሕዝብ ሥነ - ምግባር በሙሉ የሚነካው እንዴት ነው? ለ) የአንድ ቤተ ክርስቲያን መሪ የሥነ ምግባር ሕይወት፥ የቤተ ክርስቲያኒቱን አባላት ሥነ ምግባር በሙሉ የሚነካው እንዴት ነው? ሐ) ይህ በሳኦልና በዳዊት ሕይወት ውስጥ የተገለጠው እንዴት ነው? መ) እግዚአብሔርን የሚፈሩ መልካም መሪዎች ይመረጡ ዘንድ ቤተ ክርስቲያንህ መሪዎችን የምትመርጥበትን መንገድ እንዴት ማሻሻል ትችላለህ?

7. የዳዊትንና የሳኦልን መንፈሳዊ ሕይወት አወዳድር። ሀ) ጅማሬያቸው የሚመሳሰለው እንዴት ነው? ለ) መንፈሳዊ ሕይወታቸው የተለያየው እንዴት ነው? ሐ) የሕይወታቸው የመጨረሻው ውጤት የተለያየው እንዴት ነው? መ) ከእነዚህ ሰዎች ሕይወት፥ ስለ ቤተ ክርስቲያን አመራር የተለያዩ መመሪያዎችን ዘርዝር።

5. ጸሎት

# ትምህርት 14

## 1ኛ ቀን የ2ኛ ሳሙኤል መግቢያ፥ 2ኛ ሳሙ. 1-5፡5

እስካሁን ድረስ የዳዊትን ሕይወት እያጠናን ነበር፤ ዳዊትም በእስራኤል ነገሥታት ታሪክ ውስጥ እጅግ የከበረ ከብሉይ ኪዳን ታላላቅ ሰዎች አንዱ ነው። በብሉይ ኪዳን ከሚገኙ ሰዎች ሁሉ በላቀ ሁኔታ (ከሙሴ፥ ከኢያሱ፥ ከአብርሃምም ሳይቀር) ስለ ዳዊት ሕይወት ብዙ ነገር እናውቃለን። 1ኛ ሳሙኤል በአብዛኛው ዳዊት የእስራኤል የመጀመሪያ ንጉሥ ከነበረው ከሳኦል ጋር ስለ ነበረው ግንኙነት ይናገራል። የዳዊት ታሪክ በ2ኛ ሳሙኤልም ይቀጥላል። በ1ኛ ዜናም ተደግሟል።

| |
|---|
| 1ኛ ጥያቄ፥ 1ኛ ሳሙ. 13፡14 አንብብ። ሀ) እግዚአብሔር ዳዊትን እንደ ልቤ የሚሆንልኝ ሲለው ምን ማለቱ ነበር? ለ) አንድ ሰው እንደ እግዚአብሔር ልብ ሊሆን የሚችለው እንዴት ነው? |

እግዚአብሔር ዳዊትን «እንደ ልቤ የሆነ» ብሎ ጠራው (1ኛ ሳሙ. 13፡14)። ደግሞም «ባሪያዬ» ብሎ ጠርቶታል (2ኛ ሳሙ. 3፡18፤ 1ኛ ነገሥ. 11፡32)። እግዚአብሔር ዳዊትን በጣም የወደደው ለምንድን ነው? ከእኛ የተሻለ ስለ ነበረ ነውን? ወይስ ዳዊት ለእግዚአብሔር ጥልቅ ፍቅርና ልዩ የሆነ የጠበቀ ግንኙነት ስለ ነበረው ነው?

ዳዊት ከማናችንም የተለየ ሰው አልነበረም። ታላቅነቱ በአስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ እንኳ እግዚአብሔርን ለመውደድና ለእርሱም ለመታዘዝ ስለ ወሰነ ነው። ለእግዚአብሔር የነበረው ፍቅር ታላቅ ነበር። በመዝሙረ ዳዊት ውስጥ በተደጋጋሚ የዳዊት ልብ እግዚአብሔርን ለማወቅ ሲጓጓ እናያለን (መዝ. 27)። መንፈሱ ለእግዚአብሔር ሥራና በሕይወቱ ለሚፈጸም ኃጢአት ንቁ ነበር (መዝ. (51))።

ዳዊት ልዩ የሆነ መሪም ነበር። ታላቅና ብርቱ ተዋጊ ነበር። በጦርነት ሜዳ በነበረው ችሎታ ፍልስጥኤማውያንና ሌሎች በርካታ ሕዝቦችን አሸንፏል። ታላላቅ ተዋጊ የሆኑ ብርቱ ሰዎችን በዙሪያው ለማሰለፍም የሚችል ሰው ነበር። የሙዚቃ መሣሪያ በመጫወትና

መዝሙሮችን በመጻፍ እጅግ የታወቀ ሰውም ነበር። ዳዊት ከጻፋቸው መዝሙራት አብዛኛዎቹ በመዝሙረ ዳዊት የተመዘገቡና ዛሬም ቢሆን ለክርስቲያኖች እጅግ ተወዳጅ የሆኑ የቅዱሳት መጻሕፍት ክፍል ሆነዋል። ጻድቅ፥ ይቅር ባይ፥ ለጓደኞቹ ታማኝና በነገሮች ሁሉ በእግዚአብሔር ላይ የሚታመን መሪ ስለ ነበር፥ ብርቅና ፍጹም መሪ ነበር። ከዳዊት በኋላ የነገሡ ነገሥታት በሙሉ ከእርሱ ጋር በንጽጽር ቀርበዋል (ለምሳሌ፡- 2ኛ ነገሥት 18፡3)። በተጨማሪም ዳዊት ሰዎችን ሁሉ የሚገዛው መሢሕ፥ የታላቁ ንጉሥ የጌታ ኢየሱስ አባት ነበር። ዳዊት በጦርነት እያሸነፈ ብዙ ምድርን ያዘ። ነገሥታትን ለራሱ አስገዛ፤ የእስራኤልን ድንበር ከግብፅ ጀምሮ እስከ ኤፍራጥስ ወንዝ ድረስ አሰፋ። ለቤተ መቅደሱ ሥራ የሚያስፈልጉ ነገሮችን ሁሉ አዘጋጀ። መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ዳዊት ረዘም ላለ ጊዜ የሚነግረን አለምክንያት አይደለም።

ዳዊት እግዚአብሔርን እንዳስከበረ እኛም እርሱን የምናስከብር የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ለመሆን ብንፈልግ፥ የእግዚአብሔር ወዳጆችና የእግዚአብሔር ሕዝብ ታላላቅ መሪዎች ለመሆን እንዴት እንደምንችል ለማወቅ የዳዊትን ሕይወት ማጥናት አለብን። ለሕይወታችን ዳዊት የሄደበትን አቅጣጫ ልናስይዘው ይገባናል።

ይህ ማለት ግን ዳዊት ፍጹም ነበረ ማለት አይደለም። ዳዊት ለእግዚአብሔር ከፍተኛ ፍቅር የነበረው ብቻ ሳይሆን ትልቅ ኃጢአትም ሠርቶአል። አመንዝራ፥ ነፍሰ ገዳይ፥ በሠራዊቱ ብዛት የሚመካ፥ ኩሩና ቤተሰቡን መቆጣጠር ያልቻለ ሰው ነበር።

የእግዚአብሔር ወዳጆችና እንደ ልቡ የምንሆን መሆን፥ ወይም በእግዚአብሔር የተወደድን ሰዎችና እርሱ የሚጠቀምብን መሆን ማለት፥ አንዳችም ኃጢአት የማናደርግ ፍጹማን ወይም ትልቅ ኃጢአት የማንፈጽም ሰዎች ነን ማለት አይደለም። እግዚአብሔር ይጠቀምብን ዘንድ ግን መንፈሳዊ ንቃትን በሕይወታችን ልናሳድግ፥ ለእግዚአብሔር ጥልቅ የሆነ ፍቅር ሊኖረን፥ ከእርሱ ጋር ኅብረት የማድረግ ፍላጎት ልናዳብር፥ ኃጢአትን ልንጠላና የንስሐን አስፈላጊነት ልንገነዘብ ወዘተ. ያስፈልጋል። ዳዊት የከፋ ኃጢአት ቢሠራም እንኳ ልቡ ለመንፈሳዊው ነገርና ለእግዚአብሔር ንቁ ስለነበረ

እንዲሁም ንስሐ ስለሚገባ እግዚአብሔር በከፍተኛ ደረጃ ተጠቀመበት።

2ኛ ጥያቄ፣ ሀ) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በመንፈሳዊ ነገር ንቁ የሆነ ልብ የሚያስፈልጋቸው ለምንድን ነው? ለ) መንፈሳዊ ንቃት ያለውን ልብ ልናገኝ የምንችለው እንዴት ነው? ሐ) ልብህን ለመንፈሳዊ ነገርና ለራሱ ንቁ ለማድረግ እግዚአብሔር በሕይወትህ እየሠራ ያለው እንዴት ነው? መ)አንተ ራስህ ለእግዚአብሔር «እንደ ልቤ» የሚባል ሰው እንድትሆን ከሕይወትህ ልታስወግዳቸው የሚገቡ ነገሮች ምንድን ናቸው? አሁኑኑ ትናዘዝና ትተዋቸው ዘንድ ከቁርጥ ውሳኔ ድረስ።

3ኛ ጥያቄ፣ «ዳዊት» የሚለውን ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት ተመልከትና ስለ ሕይወቱ አስፈላጊ የሆኑ ጥቂት ነገሮችን ዘርዝር።

4ኛ ጥያቄ፣ ባለፈው ሳምንት በ1ኛ ቀን ጥናታችን የ1ኛ ሳሙኤል ጸሐፊ ማን እንደሆነና መቼ እንደተጻፈ ለማወቅ ያደረግነውን ጥናት እንደገና ተመልከተው።

1ኛና 2ኛ ሳሙኤል በመጀመሪያ አንድ መጽሐፍ ስለነበረ፣ አብዛኛው የ1ኛ ሳሙኤል ታሪካዊ መሠረት ለ2ኛ ሳሙኤልም የሚሆን ነው። ስለ 2ኛ ሳሙኤል በጣም አስፈላጊ የሆኑ የሚከተሉትን ነገሮች አስታውስ።

1. 1ኛና 2ኛ ሳሙኤል በመጀመሪያ አንድ መጽሐፍ ነበሩ። ጸሐፊያቸውም አንድ ሰው ነው። መጽሐፉ የተሰየመው በእስራኤል የነገሥታትን ዘመን በጀመረውና የእስራኤላውያንን የመጀመሪያ ሁለት ነገሥታት በቀባው በሳሙኤል ነው።

2. የመጽሐፈ ሳሙኤል ጸሐፊ ማን እንደሆነ አይታወቅም። የተጻፈው ግን ከሰሎሞን ሞት በኋላ ሳይሆን አይቀርም።

3. የእነዚህ ሁለት መጻሕፍት ማዕከላዊ ገጸ-ባሕርይ ከእስራኤል ነገሥታት ሁሉ ታላቅ የነበረው ዳዊት ነው።

## የ2ኛ ሳሙኤል አስተዋጽኦ

1. ዳዊት በይሁዳ ላይ ነገሠ (1-4)
2. ዳዊት በእስራኤል ሁሉ ላይ ነገሠ (5፡ 1-5)
3. የንጉሥ ዳዊት ተግባራት ስኬታማነት (5፡6-9፡ 12)
   - ሀ. ዳዊት ኢየሩሳሌምንና ፍልስጥኤማውያንን አሸነፈ (5፡6-25)
   - ለ. ዳዊት ታቦቱን ወደ ኢየሩሳሌም አስመጣ (6)
   - ሐ. እግዚአብሔር ለዳዊት የዘለዓለም መንግሥት ተስፋ ሰጠው (7)
   - መ. የዳዊት መንግሥት ስፋት (8)
   - ሠ. ዳዊት ለዮናታን የገባውን ቃል ኪዳን ጠበቀ (9)
   - ረ. ዳዊት አሞራውያንን አሸነፈ (10)
4. የንጉሥ ዳዊት ውድቀት (11-20)
   - ሀ. የዳዊት ምንዝርናና ነፍስ ገዳይነት (11-12)
   - ለ. የዳዊት ልጆች ዓመፅና ሞት (13-20)
5. ስለ ዳዊት አገዛዝ የመጨረሻ ትምህርቶች (21-24)

## የ2ኛ ሳሙኤልና የ1ኛ ዜና መዋዕል ንጽጽር

ብሉይ ኪዳን ታላቁ ንጉሥ የነበረውን የዳዊትን ታሪክ በሁለት የተለያዩ ነገር ግን ተደጋጋፊ በሆኑ መጻሕፍት አስፍሮአል፤ እነርሱም 1ኛና 2ኛ ሳሙኤልና 1ኛ ዜና መዋዕል ናቸው። 1ኛ ዜናን ቆይተን እናጠናለን። 1ኛና 2ኛ ሳሙኤል የሚናገሩት፥ ዳዊት እንዴት ንጉሥ እንደሆነ ሲሆን የ1ኛ ዜና ትኩረት ግን ዳዊት በሕይወት ዘመኑ ለእስራኤል ስላበረከተው ፖለቲካዊ በተለይ ደግሞ ሃይማኖታዊ ተግባር ነው። ለምሳሌ የ1ኛ ዜና 8 ምዕራፎች አብዛኛው ክፍል የሚናገረው ዳዊት ለቤተ መቅደስ ሥራው የሚሆኑ ነገሮችን እንዴት እንዳደራጀ

ነው። የሚከተለው ሠንጠረዥ ሁለቱ መጻሕፍት ስለ ዳዊት የሚናገሩትን አንዳንድ ነገሮች ያወዳድራል።

| ታሪካዊ ድርጊት | 2ኛ ሳሙኤል | 1ኛ ዜና |
|---|---|---|
| የዳዊት የዘር ሐረግ | | -1ኛ ዜና 1-9 |
| የሳኦል ሞት | - 2ኛ ሳሙ. 1፡1-27 | -1ኛ ዜና 10፡1-14 |
| የሳኦል መንግሥት ፍጻሜ | - 2ኛ ሳሙ. 1፡4-12 | |
| የኢየሩሳሌም ድል መሆን | - 2ኛ ሳሙ. 5፡1-9 | -1ኛ ዜና 11፡1-9 |
| የዳዊት የጦር ብርታት | - 2ኛ ሳሙ. 23፡ 8-39 | -1ኛ ዜና 11፡10- 12፡40 |
| የታቦቱ ወደ ኢየሩሳሌም መወሰድ | - 2ኛ ሳሙኤል 6 | -1ኛ ዜና13፡1-14፤ 14፡1-16፡43 |
| የዳዊት ቃል ኪዳን | - 2ኛ ሳሙ. 7 | -1ኛ ዜና 17 |
| ድል የሆኑ ነገሥታት ዝርዝር | - 2ኛ ሳሙ. 8፡1-13 | -1ኛ ዜና 18፡1-13 |
| በምድሪቱ የመጣ ድርቅ (ራብ) | - 2ኛ ሳሙ. 21፡1-14 | |
| የዳዊት ኃጢአት | - 2ኛ ሳሙ. 11፡1- 12፡ 31 | |
| የአምኖን ኃጢአት | - 2ኛ ሳሙ. 13፡1-36 | |
| የአቤሴሎም ዓመፅ | - 2ኛ ሳሙ. 13፡37- 18፡33 | |
| ዳዊት ያደረገው የሕዝብ ቆጠራ | - 2ኛ ሳሙ. 24፡ 1-25 | -1ኛ ዜና 21፡1-27 |
| የመጨረሻዎቹ የዳዊት ቃላት | - 2ኛ ሳሙ. 23፡1-7 | |
| የዳዊት ሞት | | - 1ኛ ዜና 29፡ 22-30 |

# የ2ኛ ሳሙኤል ዓላማዎች

1. ከዳዊት በኋላ ለሚነሡ ነገሥታትና ለቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሁሉ እግዚአብሔርን በሚያስከብር መንገድ የእርሱን ሕዝብ እንዴት መምራት እንደሚቻል ምሳሌ ለመስጠት ነው። ዳዊት ከእርሱ በኋላ የሚነሡ መሪዎች፥ ልጆቹም ጭምር ሕዝቡን እንዴት መምራት እንዳለባቸው ሊከተሉት የሚገባ ምሳሌ ነበር። በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ የተሾመ ምድራዊ መሪ፥ ከሰማያዊው ንጉሥ ሥልጣን በታች እግዚአብሔር በሚፈልገው መንገድ እንዴት እንደሚመራ የሚያሳይ ሕያው ምሳሌ ነው። የሚያሳዝነው ግን ከዳዊት ቀጥሎ ከነገሡት ዝርያዎቹ ጥቂቶቹ ብቻ የዳዊትን መንገድ ስለተከተሉ፥ ሕዝቡ ፈጥነው በኃጢአት ወደቁና በእግዚአብሔር ተፈረደባቸው።

| |
|---|
| 5ኛ ጥያቄ፥ ሀ) በቤተ ክርስቲያንህ እንዴት ማገልገል እንዳለብህ መልካም ምሳሌዎች የሆኑህ የቤተ ክርስቲያን ወይም የሌሎች አብያተ ክርስቲያናት መሪዎችን ዘርዝር። ለ) እነዚህን ሰዎች በሕይወታቸውና በሥራቸው መልካም መሪዎች ያደረጋቸው ምንድን ነው? |

2. ዳዊት በእስራኤል ሕዝብ ላይ ሕጋዊ የሆነ መሪ እንደ ነበር ለማሳየት ነው። 1ኛ ሳሙኤል እና 2ኛ ሳሙኤል ዳዊት በእግዚአብሔርም ሆነ በሕዝቡ የተመረጠ ትክክለኛ መሪ እንደነበረ የሚያሳዩ በርካታ ሥዕላዊ መግለጫዎችን ለአይሁድ ይሰጣሉ። ንጉሥነቱን ያገኘው በማታለል፥ በሸፍጥ ወይም በኃይል አልነበረም። የመንግሥቱን ሥልጣን ለማግኘት የሳኦልን ቤተሰብ አላጠፋም።

3. እግዚአብሔር ከዳዊት ቤተሰብ ጋር ልዩ የሆነ ቃል ኪዳን በማድረግ፥ በእስራኤል ላይ ንጉሥ ይሆኑ ዘንድ ግልጥ የሆነ መብት እንደሰጣቸው ለማሳየት ነው።

| |
|---|
| 6ኛ ጥያቄ፥ 2ኛ ሳሙ. 7፡8-16 አንብብ። ሀ) እግዚአብሔር ለዳዊት የሰጠውን ልዩ ልዩ ቃል ኪዳኖች ዘርዝር። |

ለ) ዘፍ. 12፡1-3 አንብብ። እነዚህ ሁለት ቃል ኪዳኖች የሚመሳሰሉት እንዴት ነው? የሚለያዩትስ?

እስካሁን ድረስ ባለው የብሉይ ኪዳን ጥናታችን፥ እግዚአብሔር ከተለያዩ ሰዎች ጋር ስላደረጋቸው አራት ዋና ዋና ቃል ኪዳኖች ተመልክተናል፡- 1) ከኖኅና ከሰው ልጆች ሁሉ ጋር የተደረገ ቃል ኪዳን (ዘፍ. 9፡8-17)፥ 2) ከአብርሃም ጋር የተደረገ ቃል ኪዳን (ዘፍ. 15፡9-21)፥ 3) ከእስራኤላውያን ጋር በሲና ተራራ የተደረገ ቃል ኪዳን (ዘጸ. 19-24) እና 4) ከሊቀ ካህኑ ከፊንሐስ ጋር የተደረገ ቃል ኪዳን (ዘኍ. 25፡10-13) ናቸው።

በዚህ ሳምንት በመጽሐፍ ቅዱሳችን ውስጥ ዐቢይ ስለሆነ አምስተኛ ቃል ኪዳን እንነጋገራለን፤ ይህም ከዳዊት ጋር የተደረገ ቃል ኪዳን ነው። ይህ ቃል ኪዳን በእስራኤል ሕዝብ ላይ ንጉሥ ወይም መሪ የመሆንን መብት የሚመለከት ቃል ኪዳን ነው። ለዚህ መጽሐፍ ጸሐፊ፥ እግዚአብሔር ከዳዊት ጋር ያደረገው ቃል ኪዳን የ2ኛ ሳሙኤል ዋና ትምህርት እንዲሁም 1ኛና 2ኛ ነገሥትን ለመረዳት የሚያስችል መሠረት ነው። በ2ኛ ሳሙ. 7፡5-16 እግዚአብሔር ለዳዊት የሰጣቸውን የሚከተሉትን የተስፋ ቃላት አስተውል፡-

1. «ታላቅ ስም አደርግልሃለሁ» (ቁ. 9)። ይህም እግዚአብሔር በዘፍ. 12፡2 ለአብርሃም ከሰጠው ቃል ኪዳን ጋር በጣም የሚመሳሰል ነው። ዳዊት በዚሁ መሠረት በዘመናት ሁሉ በእስራኤል ላይ ከነገሡ መሪዎች ጨርሶ ተወዳዳሪ የሌለው በመሆኑ እንደ አብርሃምና ሙሴ ስመ ገናና ሆነ። እንዲያውም የመጨረሻውና ዘላለማዊ የሆነው የእግዚአብሔር ሕዝቦች መሪ ኢየሱስ ክርስቶስ «የዳዊት ልጅ» ተብሎ ተጠራ (ማቴ. 1፡1፤ ማር. 10፡48)።

2. «ለሕዝቤም ለእስራኤል ስፍራ አደርግለታለሁ፥ እተክለውማለሁ» (ቁ. 10)። እግዚአብሔር በዳዊት የአመራር ሥርዓት ውስጥ የእስራኤል ሕዝብ አዲስ ዘመን እንደሚመጣለት ተስፋ ሰጠ። ይህም ዘመን የተስፋ ምድር ከሆነችው ከአገራቸው ከነዓን

ተገፍተን እንወጣለን ከሚል ፍርሃት ነፃ ሆነው የሚኖሩበት ጊዜ ይሆናል።

3. «ከጠላቶችህም አሳርፍሃለሁ» (ቁ. 11)። እግዚአብሔር በዳዊት የአመራር ዘመን፥ ከጠላቶቻቸው ዕረፍትንና ደኅንነትን፥ ሰላምንም እንደሚሰጣቸው ለእስራኤላውያን ቃል ኪዳን ገባ። እግዚአብሔር ይህንን ቃል ኪዳን ፈጸመ። እግዚአብሔር፥ በከነዓን ምድር የሚኖሩትን ጠላቶቹን ሁሉ እንዲያሸንፍ ዳዊትን ረዳው። የከነዓን ምድር ድንበርም ከግብፅ ጀምሮ እስከ ኤፍራጥስ ወንዝ ድረስ ተስፋፋ። ከዳዊት በፊትም ሆነ በኋላ በእስራኤል ምድር ውስጥ እንዲህ ዓይነት ሰላምና ብልጽግና ታይቶ አይታወቅም።

** ከላይ የተመለከትናቸው የእነዚህ ሦስት ቃል ኪዳኖች ዓላማ:- እግዚአብሔር ከዳዊት ጋር ያደረገው ቃል ኪዳን፥ ከአብርሃም ጋር በገባው በታላቁ ቃል ኪዳን ሥር አለመሆኑን ለማሳየት ነው። የዳዊት ቃል ኪዳን የአብርሃም ቃል ኪዳን አፈጻጸም ሁኔታ ተጨማሪ መግለጫ ነው። እነዚህ ሦስት ቃል ኪዳኖች መሠረታቸው የአብርሃም ቃል ኪዳን ነው፤ ነገር ግን በ2ኛ ሳሙ. 7፡12-16 የሚገኙ የተስፋ ቃሎች፥ በተለይ ለዳዊትና ለቤተሰቡ የተሰጡ አዲስ የተስፋ ቃሎች ናቸው።

4. «እግዚአብሔርም ደግሞ:- ቤት እሠራልሃለሁ ብሎ ይነግርሃል» (ቁ. 11)። ዳዊት ለእግዚአብሔር የሚሆን ቤት ወይም ቤተ መቅደስ ማሠራት ፈልጎ ነበር። ይህንን እንዲያደርግ እግዚአብሔር አልፈቀደለትም። ይልቁንም እግዚአብሔር ለዳዊት ቤት ሊሠራለት ቃል ገባለት። ይህም ቤት የንጉሣዊ ስርወ - መንግሥት በእስራኤል ላይ ሁልጊዜ የመንገሥ መብት ነው (ቁ. 16 ተመልከት)።

5. «ከወገብህ የሚወጣውን ዘርህን ከአንተ በኋላ አስነሣለሁ» (ቁ. 12)። የንጉሥነት ሥልጣኑ ለልጆቹ እንዳልተላለፈው እንደ ሳኦል ሳይሆን፥ እግዚአብሔር የዳዊት ልጆች ከእርሱ በኋላ በንጉሥነት እንደሚቀጥሉ ቃል ገባ። ከዳዊት በኋላ ሰሎሞን መንገሡ የዚህ ቃል ኪዳን ፍጻሜ ነበር። በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር

ለመጀመሪያ ጊዜ ለፖለቲካ አመራር ተከታታይ የሆነ የሥልጣን ውርስ ያደረገው በዚህ ስፍራ ነው።

6. «እርሱ ለስሜ ቤት ይሠራል» (ቁ. 13)። እግዚአብሔር ለዳዊት ቤተ መቅደስን ይሠራ ዘንድ አልፈቀደለትም፤ ነገር ግን ልጁ ቤተ መቅደሱን እንደሚሠራ ቃል ኪዳን ገባለት። በዚያም ክብሩን ያደርግ ዘንድ ተስፋ ሰጠ። ሰሎሞን ይህን በመፈጸም በጥንት ጊዜ እጅግ ታላላቅ ከሚባሉት ቤተ መቅደሶች አንዱ የነበረውን ቤተ መቅደስ ሠራ። የከርሰ ምድር ተመራማሪዎች በጥንት ዘመን ከነበሩ ሰባት አስደናቂ ነገሮች አንዱ ይህ ነው ይላሉ።

7. «እኔም አባት እሆነዋለሁ፥ እርሱም ልጅ ይሆነኛል» (ቁ. 14-15)። እግዚአብሔር ከዳዊት ልጅ ጋር ልዩ የሆነ ግንኙነት እንደሚኖረው ተስፋ ሰጠ። ይህ ግንኙነት በአባትና በልጅ መካከል እንዳለ ግንኙነት የቅርብና በፍቅር ላይ የተመሠረተ ነበር። ይህ ግንኙነት ጥፋት በሚፈጸምበት ጊዜ ቅጣትን የሚያስከትል ነበር፤ ነገር ግን እግዚአብሔር ፍቅሩን እንደማይወስድ ቃል ገብቶ ነበር። ይህ ቃል ኪዳን በከፊል በሰሎሞን የተፈጸመ ሲሆን፥ ፍጹም በተሟላ መንገድ የተፈጸመው በኢየሱስ ክርስቶስ ነው (ማር. 1፡11፤ ዕብ. 1፡5 ተመልከት)።

8. «ቤትህና መንግሥትህም በፊቴ ለዘላለም ይጠነክራል፥ ዙፋንህም ለዘላለም ይጸናል» (16)። እጅግ በጣም የሚያስደንቀውና እግዚአብሔር ለዳዊት የሰጠው ይህ የመጨረሻ ቃል ኪዳን ነው፤ ነገር ግን በሊቃውንት መካከል ከፍተኛ ውይይት ያስነሣ ነው።

እግዚአብሔር ለዳዊት የገባለት ቃል ኪዳን ትክክለኛ መግለጫው ምንድን ነው? እግዚአብሔር ለዳዊት የገባለት ቃል ኪዳን ከዘሩ ሁልጊዜ በእስራኤል ላይ የሚነግሥ ሰው እንደሚኖር ነውን? ይህ ከሆነ ቃል ኪዳኑ አልተፈጸመም ማለት ነው፤ ምክንያቱም በ586 ዓ.ዓ. የደቡብ እስራኤል መንግሥት የሆነው የይሁዳ መንግሥት ከተደመሰሰ ወዲህ፥ እስራኤልን የሚገዛ ከዳዊት ወገን የተነሣ ምንም ዓይነት ንጉሥ አልነበረም። ታዲያ ይህንን ቃል ኪዳን የምንረዳው እንዴት ነው?

1. «ለዘላለም» የሚለው ቃል በዕብራይስጥ የተለያየ ትርጉም ሊኖረው ይችላል። ይህ ቃል ፍጻሜ የሌለው ማለትም ልክ እንደ እግዚአብሔር መጀመሪያና መጨረሻ የሌለው ማለት ሊሆን ይችላል፤ ነገር ግን ያልተወሰነ ወይም ያልተለየና ያልታወቀ ጊዜ ማለትም ሊሆን ይችላል፤ (ለምሳሌ:- 1ኛ ሳሙ. 1:22፤ 2:30-31፤ ኤር. 17:4 ተመልከት)። የብሉይ ኪዳን ተጨማሪ ጥናት የሚያሳየን፥ እግዚአብሔር ለዳዊት የገባለት ቃል ኪዳን የእርሱ ዘር በእስራኤል ላይ ንጉሥ የመሆንና የመቀጠል ጊዜው ያልተወሰነ ዕድል እንደ ነበረው ነው። ይህ የመገዛት ሥልጣን ግን የተመሠረተው የዳዊት ዝርያዎች የመለኮታዊውን ንጉሥ ትእዛዛት ለመፈጸም በሚያሳዩት ፈቃደኝነት ላይ ነበር። ዳዊት በ2ኛ ሳሙ. 7:29 ከጸለየው ጸሎት ግልጽ ሆኖ እንደምናየው የዳዊት ዝርያዎች ሁልጊዜ ለእግዚአብሔር በቅንነት ባይታዘዙ መግዛታቸውን እንደሚቀጥሉ ይህ ቃል ኪዳን አይናገርም፤ ስለዚህ ዳዊት የእርሱ ዘር በኃላፊነት እንዲቀጥል ያለማቋረጥ በረከቱን እንዲሰጠው እግዚአብሔርን ይጠይቃል።

2. ይህ ቃል ኪዳን በቅድመ ሁኔታ ላይ የተመሠረተ ነበር ወይስ አልነበረም? ይህ ቃል ኪዳን በቅድመ - ሁኔታ ላይ የተመሠረተም ያልተመሠረተም ነው ለማለት እንችላለን። ለዳዊት ቃል ኪዳኑ በምንም ቅድመ - ሁኔታ ላይ ያልተመሠረተ ነበር። እግዚአብሔር ይህንን ቃል ኪዳን ለዳዊት ለመፈጸም ከዳዊት የጠየቀው ቅድመ - ሁኔታ አልነበረም፤ ነገር ግን የዘላለም ገዢነቱን የሚናገረውን የቃል ኪዳን ክፍል ለመፈጸም የተሰጡ ቅድመ - ሁኔታዎች ነበሩ። በ1ኛ ነገሥት 2:2-4 ዳዊት ይህንን ቃል ኪዳን ለሰሎሞን ሲያስተላልፍ ግልጽ እንዳደረገው «የምታደርገውንና የምትሄድበትን ሁሉ ታከናውን ዘንድ፥ በሙሴ ሕግ እንደ ተጻፈ ሥርዓቱንና ትእዛዛቱን ፍርዱንና ምስክሩንም ትጠብቅ ዘንድ፥ በመንገዱም ትሄድ ዘንድ፥ የአምላክህን የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ጠብቅ። ይኸውም ደግሞ እግዚአብሔር ስለ እኔ:- ልጆችህ መንገዳቸውን ቢጠብቁ፥ በፊቴም በፍጹም ልባቸውና በፍጹም ነፍሳቸው በእውነት ቢሄዱ ከእስራኤል ዙፋን ሰው አይቆረጥብህም ብሎ የተናገረውን ቃል ያጸና ዘንድ ነው» (በተጨማሪ 1ኛ ነገሥት

6፤ 12፤ 9፡4-7 ተመልከት)። እግዚአብሔር ለዳዊት በእስራኤል ዙፋን ላይ እንደሚቀመጥና ሊያሸንፈው ወይም ከዙፋን ሊያወርደው የሚችል ማንም እንደሌለ ቃል ኪዳን ገብቶለት ነበር፤ ከዚህ ባሻገር ልጁ በሥልጣን ላይ የመቆየቱ ነገር በልጁ ወይም በዝርያዎቹ ሁሉ መታዘዝ ላይ የተመሠረተ ነበር።

ነገር ግን ይህ ነገር ዘላለማዊና በምንም ቅድመ ሁኔታ ላይ ያልተመሠረተ መሆኑን የምናይበት ሌላ መንገድም አለ። አለመታዘዝ ለጊዜው የዳዊትን ዝርያዎች የመንገሥ መብት ቢያሰናክልም፥ የዳዊት ዋና ልጅ የሆነው መሲሑ ይህንን ቃል ኪዳን ይፈጽማል። ነቢያት አንድ ቀን ታላቁ «የዳዊት ልጅ» እንደሚመጣ ከእግዚአብሔር ዘንድ ተረድተው ነበር (ኢሳ. 9፡6-7፤ 11)፤ (ኤር. 23፡5-6፤ ሕዝ. 34፡23-24 ተመልከት)። እግዚአብሔር ሕዝቦችና ዓለምን ሁሉ ከዳዊት እጅግ በላቀ አኳኋን ይገዛል። የዳዊት ልጅ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ፥ በእግዚአብሔርና በዳዊት መካከል የተገባውን ቃል ኪዳን ይፈጽማል፤ ምክንያቱም እርሱ በሕዝቡ ላይ የሚገዛ የዘላለም ንጉሥ ነው (ለምሳሌ፡- በራእይ 21፡1-6፤ ሉቃስ 1፡32-33 ይህ ቃል ኪዳን በኢየሱስ ክርስቶስ እንደተፈጸመ ተመልከተው)። ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም አምሳያ የሌለው ንጉሥ ነው። እርሱ በጽድቅና በቅንነት ከእግዚአብሔር የንጉሥነት ዙፋን ሥር ሆኖ የሚያስተዳድር ነው። ዳዊት የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ሕይወት ምሳሌ ነው፤ ምክንያቱም ኢየሱስ ክርስቶስ በዳዊት ሕይወት ውስጥ በከፊል የታየውና እግዚአብሔር ከአንድ ንጉሥ የሚፈልገውን ነገር ስለሚፈጽም ነው።

7ኛ ጥያቄ፥ ከዳዊት ጋር ከተደረገው ቃል ኪዳን፥ ስለ እግዚአብሔር ባሕርይ፥ ስለ እግዚአብሔር ተስፋ ቃልና ስለ መታዘዝ አስፈላጊነት የምንማረው ምንድን ነው?

## 2ኛ ሳሙኤል 1-5፡5

8ኛ ጥያቄ፡- 2ኛ ሳሙኤል 1-5፥5 አንብብ። ሀ) በዮናታንና በሳኦል ሞት ምክንያት ዳዊት ስሜቱን የገለጸው እንዴት ነበር? ለ) ዳዊት በመጀመሪያ የነገሠው በየትኛው የእስራኤል ነገድ ላይ ነው? ሐ) በዳዊትና በሳኦል ቤት መካከል የተፈጸመው ነገር ምን ነበር?

መ) የሳኦል ቤት የተሸነፈው እንዴት ነበር? ሠ) ዳዊት በእስራኤል ሁሉ ላይ የነገሠው እንዴት ነበር?

ከሳኦል ሞት በኋላ፥ ዳዊት የእስራኤል ንጉሥ የሆነው ወዲያውኑ አልነበረም። ዳዊት በእስራኤል ሁሉ ላይ ለመንገሥ ከሳኦል ሞት በኋላ ሰባት ዓመት ፈጅቶበታል። ለእነዚህ ሰባት ዓመታት ዳዊት በይሁዳ ላይ ነግሦ ነበር። በእነዚህ ዓመታት ውስጥ ዳዊትን ለማንገሥ በሚፈልጉና የሳኦል ቤተሰብ በዙፋኑ ላይ መቆየት አለበት በማለት ከሳኦል ልጆች አንዱን ለማንገሥ በሚፈልጉ መካከል የእርስ በርስ ጦርነት ተካሂዷል።

የዚህ የ2ኛ ሳሙኤል ክፍል ዋና ዓላማ በሳኦል ቤተሰብ ላይ እንዳችም የበቀል ስሜት እንዳልነበረውና እንዳልተበቀለ እንዲሁም ለረጅም ጊዜ ሊገድለው ይፈልግ የነበረው ሳኦል በመሞቱ እንኳ እንዳልተደሰተ ለማሳየት ነው።

ሳኦል ከሞተ በኋላ፥ ከሳኦል ጋር ይዋጉ ከነበሩ ወታደሮች አንዱ የሳኦልና የዮናታንን ሞት ለማርዳት እየሮጠ ወደ ዳዊት መጣ። ይህ አማሌቃዊ ወታደር ይዞ ስላመጣሁት ወሬ ብቻ ሳይሆን፥ ስለ ሳኦልና ስለ ዮናታን ሞት ጭምር ዳዊት ይሸልመኛል ብሎ በማሰብ፥ በእግዚአብሔር የተቀባውን መሪ ሳኦልን እንደገደለ ተናገረ። ሳኦልን ገደልኩ ስላለ ዳዊት አስገደለው። ውሸቱ ሕይወቱን እንዲያጣ አደረገው። ዳዊት በሳኦል ሞት ምክንያት አልተደሰተም፤ ነገር ግን ሳኦልና ዮናታን በመሞታቸው አዘነ፤ ከምግብ ተለይቶ በመጾም አለቀሰ። ስለ ሳኦልና ስለ ልጁ ስለ ዮናታን ሞት የኃዘን ቅኔ ተቀኘ።

ከሳኦል ሞት በኋላ በእስራኤል ምድር ብዙ መደናገር ተነሥቶ ነበር። እስራኤላውያን ከፍልስጥኤማውያን ጋር ባደረጉት ጦርነት በመሸነፋቸውና ሳኦል በመሞቱም ፍልስጥኤማውያን አብዛኛውን ማዕከላዊ የእስራኤል ግዛት ሳይቆጣጠሩ አልቀሩም። ይሁንና የይሁዳ ነገድ ወደ ዳዊት በመምጣት ዳዊትን ለንጉሥነት ቀባው። የቀሩት የእስራኤል ነገዶችና የእስራኤል ጦር አምስት ዓመታት በፍልስጥኤማውያን ተጽዕኖ ሥር ከወደቁ በኋላ፥ ኢያቡስቴ የተባለውን የሳኦልን ልጅ የእስራኤል ንጉሥ ይሆን ዘንድ ቀቡት፤

በዚህም ምክንያት ዳዊትን በተከተሉት በይሁዳ ነገድና ኢያቡስቴን በተከተሉት በቀሩት የእስራኤል ነገዶች መካከል ለሁለት ዓመታት የማያቋርጥ ጦርነት ተካሄደ። ከኢያቡስቴ ጎን የነበረው ዋና ኃይል የእስራኤል ጦር አዛዥ አበኔር ነበር። ቀስ በቀስ ዳዊትና ከጎኑ ያለው ጦር ከኢያቡስቴና ከጎኑ ካለው ጦር ይልቅ እየበረታ መጣ። ቀጥሎም የጦር አዛዥ የነበረው አበኔር ከዳዊት ጎን ለመቆም ተስማማ። ይህም የእርስ በርስ ጦርነቱን ወደ ፍጻሜ እንዲመጣ አደረገው። የዳዊት ጦር አዛዥ የነበረው ኢዮአብ ግን የወንድሙን የአሣሄልን ደም ለመበቀል አበኔርን ገደለው። በዚህ ድርጊቱ ዳዊት ኢዮአብን ለመቅጣት ቢፈልግም እንኳ በቂ ኃይል ስላልነበረው አልቻለም። ሰሎሞን በዙፋኑ ላይ እስከተቀመጠ ድረስ ኢዮአብ በድርጊቱ ሳይቀጣ ቆየ (1ኛ ነገሥት 2፡5-6፥ 29-35)።

ኢያቡስቴም የራሱ ወገን በሆኑ ሁለት ሰዎች ተገደለ። ገዳዮቹ ዳዊት ይሸልመናል ብለው ወሬውን ይዘው መጡ። ዳዊት ግን ስለዚህ ድርጊታቸው በሞት ቀጣቸው። ከዚያም የእስራኤልም መሪዎች ተሰብስበው ዳዊትን አነገሡት። በዚህ ዓይነት አገሪቱ በአንድ መሪ የምትመራ አንድ አገር ስለሆነች የእርስ በርሱ ጦርነት ያበቃል።

> 9ኛ ጥያቄ፥ ሀ) ዳዊት ለሳኦል ቤተሰብ ከነበረው ዝንባሌ በቀልን ስላለመፈጸምና ወደ ሕይወታችን መራርነት እንዳይገባ ስለ መከላከል ምን እንማራለን? ለ) እግዚአብሔር በመሪዎች ላይ ስላለው ቁጥጥርና በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ምን ያህል ጊዜ መምራት እንዳለባቸው ምን እንማራለን?

## 2ኛ ቀን፡- 2ኛ ሳሙኤል 5፡6-12፡31

አንድ ጊዜ አንድ ታላቅ ሚሲዮናዊ እንዲህ ብሎ ተናገረ፡- «ዓለም ራሱን ሙሉ ለሙሉ ለእግዚአብሔር በሰጠ ሰው ሕይወት ውስጥ እግዚአብሔር ምን እንደሚሠራ ገና ታያለች»። ራሱን ሙሉ ለሙሉ ለእግዚአብሔር የሰጠ ሰው ሙሉ የእግዚአብሔር ኃይል አለው። ራሱን የሰጠ መሪ የእግዚአብሔር ኃይል በሙሉ በእርሱ ዘንድ አለና እግዚአብሔር ታላላቅ ነገሮችን በእርሱ ውስጥ ማድረግ ይችላል። የእግዚአብሔር ኃይል በውስጣችን እንዳይሠራ የምንከላከለው፥

ሕይወታችንን ሙሉ ለሙሉ ለእግዚአብሔር ካልሰጠንና ኃጢአትና ራስ ወዳድነት ወደ ሕይወታችን እንዲገባ ከፈቀድን ነው።

ዳዊት ራሱን ለእግዚአብሔር የሰጠ ሰው ነው፤ ስለዚህ እግዚአብሔር እጅግ አስደናቂ በሆነ መንገድ በሕይወቱ የሚጠቀምበት ሰው ሊሆን ችሏል። ዳዊት ለእግዚአብሔር በመታዘዝ ስለኖረ፥ እግዚአብሔር በንጉሥነቱ ባረከው። የእግዚአብሔርን ጠላቶች ሁሉ ድል በማድረግ ለእግዚአብሔር ሕዝብ ሰላምን አስገኘ።

10ኛ ጥያቄ፥ ሀ) ለእግዚአብሔር ራሳቸውን አሳልፈው በመስጠታቸው እግዚአብሔር በከፍተኛ ሁኔታ ስለተጠቀመባቸው የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች ምሳሌ ስጥ። ለ) ለእግዚአብሔር ያላስረከብካቸው የሕይወትህ ክፍሎች የትኞቹ ናቸው? ሐ) ራስህን ሙሉ ለሙሉ ለእግዚአብሔር በመስጠት ለራሱ ክብር በከፍተኛ ሁኔታ ሊጠቀምብህ እንዲችል ለመጸለይ ጊዜ ይኑርህ።

11ኛ ጥያቄ፥ 2ኛ ሳሙኤል 5፡6-12፡31 አንብብ። ሀ) በእነዚህ ቁጥሮች የተጠቀሱትን ዳዊት ያከናወናቸውን ልዩ ልዩ ነገሮች ዘርዝር። ለ) ዳዊት የቃል ኪዳኑን ታቦት ወደ ኢየሩሳሌም በመውሰዱ ከዳዊት ባሕርይ የምንማረው ነገር ምንድን ነው? ሐ) እግዚአብሔር ለዳዊት የገባለትን የተስፋ ቃሎች ዘርዝር። መ) ዳዊት ለዮናታን የገባውን ቃል ኪዳን የጠበቀው እንዴት ነበር? ሠ) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ብንሆንም እንኳ በትልቅ ኃጢአት ልንወድቅ እንደምንችል፥ ዳዊት ከሠራው ኃጢአት ምን እንማራለን?

በትምህርት 13 ከተመለከትነው ሠንጠረዥ እንደምታስታውሰው፥ የ1ኛና የ2ኛ ሳሙኤል እንዲሁም የ1ኛ ነገሥት ጸሐፊዎች የሳኦልን፥ የዳዊትንና የሰሎሞንን ታሪክ ለማቅረብ የተከተሉት መንገድ ተመሳሳይ ነው። በመጀመሪያ ጸሐፊዎቹና፥ እነዚህ መሪዎች ንጉሥ እንዲሆኑ እንዴት እንደተቀበሉ ይናገራሉ። ቀጥሎ እነዚህ መሪዎች የፈጸሙአቸውን ተግባራት ይተነትናሉ። በመጨረሻ በእነዚህ ጸሐፊዎችና መሪዎች ሕይወት ውስጥ በኃጢአት ምክንያት ስለሆኑ ክፉ ነገሮች ይዘግባሉ። ዳዊት ንጉሥ ይሆን ዘንድ የተቀባው ከብዙ ዓመታት

በፊት ቢሆንም እንኳ በመጨረሻ በይሁዳና በእስራኤል ላይ እንዴት ንጉሥ ለመሆን እንደበቃ ትናንትና ተመልክተናል። ዛሬ ደግሞ ዳዊት ስለ ፈጸማቸው የተለያዩ ነገሮችና ታላቅ ስላደረጉት ተግባሮቹ እንመለከታለን።

1. ዳዊት በጠላቶቹ ሁሉ ላይ ድልን ተቀዳጀ። እርሱ ድል ያደረጋቸውን የሚከተሉትን ሕዝቦች ተመልከት፡-

 ሀ. ኢያቡሳውያን፡- በመካከለኛው እስራኤል ጠንካራ ከተማ በነበረችው በኢየሩሳሌም ይኖሩ የነበሩ ሕዝቦች ናቸው። ለብዙ መቶ ዓመታት አይሁዳውያን የኢየሩሳሌምን ከተማ ለመያዝ አልቻሉም ነበር። ዳዊት ግን ከተማይቱን አሸነፈና የእስራኤል መንግሥት አዲሲቱ ዋና ከተማ አደረጋት። ኢየሩሳሌም «የዳዊት ከተማ»፥ «ጽዮን» በመባልም ትታወቃለች (2ኛ ሳሙ. 5፡7)።

 ለ. ፍልስጥኤማውያን (2ኛ ሳሙ. 5፡17-25፤ 8፡1)። ዳዊት እንደገና ሊያስቸግሩት በማይችሉበት መንገድ ፍልስጥኤማውያንንም አሸነፋቸው።

 ሐ. ሞአባውያን (2ኛ ሳሙ. 8፡2)።

 መ. በሶርያ ውስጥ የሚገኘው የሱባ ንጉሥ (2ኛ ሳሙ. 8፡3-10)፡- ዳዊት በእስራኤል በስተሰሜን የሚገኙትን ነገሥታት በሙሉ እስከ ኤፍራጥስ ወንዝ ድረስ አሸንፎአቸዋል።

 ሠ. ኤዶማውያንና አሞናውያን (2ኛ ሳሙ. 8፡11-14፤ ምዕራፍ 10)።

---

12ኛ ጥያቄ፥ በመጽሐፉ በስተጀርባ የሚገኘውን ካርታ በመመልከት እነዚህ አገሮች ያሉት የት እንደሆነ አመልክት።

---

ሳኦል በምርኮ ያገኘውን ነገር ለራሱ የወሰደ ሲሆን፥ ዳዊት ግን በምርኮ የበዘበዘውን ሁሉ ወደ እግዚአብሔር ያመጣ ነበር፤ ዳዊት ድል የሰጠው እግዚአብሔር እንደሆነ የተገነዘበ ሰው ነበር፤ ስለዚህ ምርኮውን

ሁሉ ለእግዚአብሔር ሰጠ (2ኛ ሳሙ. 8፡7-12)። ይህን ከምርኮ የተገኘ ነገር በኋላ ለቤተ መቅደሱ ግንባታ አውሉአል።

| |
|---|
| 13ኛ ጥያቄ፥ ከዚህ ነገር ስለ ዳዊት ባሕርይ የምንማረው ምንድን ነው? |

2. ዳዊት የቃል ኪዳኑን ታቦት ወደ ኢየሩሳሌም አስመጣ (2ኛ ሳሙኤል 6)። ዳዊት መንግሥቱን ካጸናና ዋና ከተማውን ከመሠረተ በኋላ፥ የነገሥታት ንጉሥ የሆነው እግዚአብሔር በኢየሩሳሌም እንዲገዛ ፈለገ። የቃል ኪዳኑ ታቦት የእግዚአብሔር ዙፋን እንደሆነ ይታሰብ ነበር፤ ስለዚህ ዳዊት የእግዚአብሔር ዙፋን በኢየሩሳሌም እንዲሆንና በእስራኤል መንግሥት ላይ እንዲገዛ ይፈልግ ነበር። ይህ ማለት ሰብአዊ የሆነው ንጉሥና መለኮታዊ የሆነው ንጉሥ በአንድነት በኢየሩሳሌም ሊገዙ ነበር።

ዳዊት የቃል ኪዳኑን ታቦት ከአሚናዳብ ቤት በታላቅ በዓል ወደ ኢየሩሳሌም አስመጣው። እግዚአብሔርን በዚህ መንገድ ያከበረው ቢሆንም፥ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ በጥንቃቄ መከተልን ግን ዘነጋ። እግዚአብሔር የቃል ኪዳኑን ታቦት ካህናት ረዘም ባሉ መሎጊያዎች ማንም ሊነካው በማይችል ሁኔታ እንዲሸከሙ አዝዞ ነበር (ዘጸ. 25፡12-15፤ ዘኁ. 4፡15)። ካህናቱ ግን ታቦቱን በሠረገላ ጭነው፥ ወደ ኢየሩሳሌም መጡ። ሠረገላው በሚንቀሳቀስበት ጊዜ መንገዱ አመቺ ባለመሆኑ እንዳይወድቅ ዖዛ የእግዚአብሔርን ታቦት ያዘ፤ እግዚአብሔርም ወዲያውኑ በሞት ቀሠፈው።

| |
|---|
| 14ኛ ጥያቄ፥ ሀ) እግዚአብሔር በዖዛ ላይ በብርቱ የተቆጣው ለምን ይመስልሃል? ለ) ይህ ታሪክ ስለ እግዚአብሔር የሚያስተምረን ነገር ምንድን ነው? |

ይህንን ታሪክ በምናነብበት ጊዜ፥ በእግዚአብሔር ሥራ እንደነቅ ይሆናል። ዳዊት ሳይቀር ተደንቆና አዝኖ ነበር። ታቦቱ እንዳይወድቅ ለማድረግ መሞከሩ መልካም ሆኖ ሳለ፥ እግዚአብሔር ዖዛን የገደለው ለምንድን ነው? እግዚአብሔር ይህንን ያደረገበት ሁለት ምክንያቶች አሉ፡-

1. ዖዛ አሳቡ መልካም ቢሆንም፥ ተግባሩ ግን የእግዚአብሔርን ትእዛዝ በቀጥታ የሚጻረር ነበር። እግዚአብሔር ታቦቱን ማንም ሰው እንዳይነካ አስጠንቅቋል። እግዚአብሔር ራሱን ለመጠበቅ ስለሚችል፥ ዖዛ ታቦቱን ለማዳን ያደረገው ሙከራ የተሳሳተ አሳብ ነበር። እግዚአብሔር ራሱን መጠበቅ ስለሚችል የማንንም እንክብካቤ አይፈልግም።

2. እስራኤላውያን እግዚአብሔርን ማገልገል ያለባቸው በፍጹም ቅድስና መሆኑን ለማሳየት ነበር። ይህ ለእስራኤላውያን አዲስ ዘመን ነበር። አሁን ለእነርሱ ጻድቅ ንጉሥ አላቸው። ሕዝቡ እግዚአብሔርን መውደድና ማገልገል ጀምረዋል። ሰማያዊ ንጉሣቸውንም በኢየሩሳሌም እንዲኖር እያመጡት ነበር፤ ነገር ግን ንጉሣቸው እንዲመጣና በመካከላቸው ተገኝቶ እንዲባርካቸው አጥብቀው ከፈለጉ፥ ራሳቸውን ሙሉ ለሙሉ ለእግዚአብሔር ሊሰጡና በፍጹምነት ለእርሱ ሊታዘዙ ይገባ ነበር።

15ኛ ጥያቄ፥ ይህ ትምህርት ዛሬም ለእኛ የሚያስፈልገን ለምንድን ነው?

ዳዊት ከስሕተቱ ተማረ። ከሦስት ወራት በኋላ ካህናቱ ልክ እግዚአብሔር ባዘዘው መሠረት የእግዚአብሔርን ታቦት ተሸክመው ወደ ኢየሩሳሌም አመጡት (ዘጸ. 25፡15፤ ዘኁ. 1፡50-53)።

ታቦቱ ወደ ኢየሩሳሌም በገባ ቀን ዳዊት ያደረገውን ነገር መመልከት በጣም የሚያስደስት ነው። ቀኑ የታላቅ በዓል ቀን ሆነ። የነገሥታት ንጉሥ ወደ ኢየሩሳሌም የመጣበት ቀን ነበር፤ ስለዚህ ዳዊት በሙሉ ኃይሉ ይጨፍር ነበር። የሳኦል ልጅ የሆነችው ሚስቱ ሜልኮል፥ ያሳየው የነበረው ሁኔታ ልክ እንዳልነበር ብትነግረውም እንኳ ዳዊት ልቡ በእግዚአብሔር ፊት ትክክል እንደ ነበር ያውቅ ነበር። ሌሎች ከሚያስቡት ነገር ይልቅ እግዚአብሔርን በማክበር ደስታውን በሙሉ ኃይሉ በመግለጥ ላይ ትኩረት አድርጎ ነበር። ሜልኮል ለእግዚአብሔር ከሚቀርብ አምልኮ ይልቅ ለባሏ ክብር ከፍተኛ ስፍራ በመስጠቷ እግዚአብሔር መሃን በማድረግ ቀጣት።

አንዳንድ ሰዎች ይህንን ጥቅስ በመጠቀም ለእግዚአብሔር በምንሰጠው አምልኮ ዛሬም ቢሆን ልንጨፍር፥ ልንዘምርና እልል ልንል ይገባል ይላሉ። በአንድ በኩል ትክክል ናቸው። እግዚአብሔር በመካከላችን ባልተለመደ መንገድ በሚሠራበት ጊዜ፥ ፍቅራችንና ደስታችንን እጅግ ግልጥ በሆነ በሚታይ መንገድ መግለጥ አለብን። ይህ ማለት ግን ዳዊት በእግዚአብሔር ፊት በየቀኑ ወይም በአምልኮ ጊዜ ይጨፍር ነበር ማለት አይደለም። ከታሪኩ እንደምንመለከተው ይህ ያልተለመደ ተግባር ነበር። ደስ የምንሰኝበት፥ የምናጨበጭብበትና የምንዘምርበት ወዘተ. ጊዜ አለን። እነዚህ ግን ልዩ ለሆኑ የአምልኮ በዓላት ሊጠበቁ ይገባል። ሁልጊዜ ወይም በየስብሰባው ሁሉ መደረግ ያለበት ነገር አይደለም። አለበለዚያ እግዚአብሔር በታላቅ ሁኔታ በሚባርከን ጊዜ ደስታችን ከመጠን ያለፈ መሆኑን በግልጥ ለማሳየት እንዴት እንችላለን? በጭብጨባና በእልልታ በጣም ተይዘን፥ የልባችንን ደስታ ሊገልጥ በማይችል አኳኋን ሃይማኖታዊ ሥርዓት ብቻ ሆኖ እንዳይቀር መጠንቀቅ አለብን። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ጸጥታ፥ ጥሞናና የጌታን ነገር የማሰላሰያ ጊዜ የበለጠ የሚፈለግባቸው ሁኔታዎች አሉ። እግዚአብሔር ኤልያስን በዝምታ ድምፅ (በሹክሹክታ) ተናገረው (1ኛ ነገሥት 19፡11-14)። በእግዚአብሔር ፊት «ዝም» እንድንልም ታዝዘናል (ዕንባ. 2፡20)። እነዚህን ነገሮች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሚዛናዊ ለማድረግ መጣር አለብን።

ዳዊት ሌሎች እንዲጨፍሩ አላደረገም። ሌሎች ስላልጨፈሩም አልወቀሳቸውም። የእርሱ ጭፈራ በልቡ ይፈስስ የነበረው የታላቅ ደስታ መግለጫ ነበር። ሌሎች በአምልኮአቸው እንደማይጨፍሩና እንደማያጨበጭቡ ተመልክተን በምንተችበት ጊዜ፥ እኛም የምንጨፍረውና የምናጨበጭበው ለተሳሳተ ዓላማ እንደሆነና መንፈሳዊ ትዕቢት በሕይወታችን ውስጥ እንዳለ ምልክት ነው። እያንዳንዱ ሰው በሚፈልገው መንገድ እግዚአብሔርን የማምለክ ነፃነት አለው። አንዱ በሌላው ላይ ሊፈርድ አይገባም። አምልኮ የግል ጉዳይ ነው። በልቡ ያለውን የአምልኮ መንፈስ ትክክል መሆንና አለመሆን የሚያውቅ እግዚአብሔር ብቻ ነው። በሌላው ሰው አገልጋይ ላይ እንዴት እንደምንፈርድ እንጠነቀቅ (ሮሜ 14፡4 ያዕ. 4፡12)።

16ኛ ጥያቄ፥ ሀ) በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ስለ አምልኮ ያለን ሚዛናዊ አመለካከት፥ አምልኮአችን ተገቢ እንዲሆንና መከፋፈል (ልዩነት) ከቤተ ክርስቲያናችን እንዲጠፋ እንዴት ይረዳናል? ለ) ሰዎች በሚያጨበጭቡበት፥ በሚጨፍሩበትና እልል በሚሉበት ጊዜ ዓላማቸው ምንድን ነው? ሐ) እነዚህ ነገሮች በመልካም ዓላማ የሚፈጸሙት መቼ ነው? መ) እነዚህ ነገሮች በመጥፎ ዓላማ የሚፈጸሙትስ መቼ ነው?

3. እግዚአብሔር የዳዊትን ፍላጎት እንደሚያከብር ከእርሱ ጋር የዘላለም ቃል ኪዳን በማድረግ ገለጠ (2ኛ ሳሙኤል 7)።

የቃል ኪዳኑ ታቦት ወደ ኢየሩሳሌም ከተወሰደ በኋላ ዳዊት ታቦቱ ይኖርበት ዘንድ ለእግዚአብሔር ቤተ መቅደስን ለመሥራት ፈለገ። እግዚአብሔር ግን ዳዊት ይህንን እንዲያደርግ አልፈቀደም። ዳዊት ቤተ መቅደሱን እንዳይሠራ የተከለከለበት ዋና ምክንያት እርሱ የጦር እንጂ የሰላም ሰው ስላልነበረ ነው (1ኛ ዜና 28፡3፤ 22፡8)። እግዚአብሔር ቤቱን እንዲሠራለት የፈለገው የሰላም ሰው ነበር። ሆኖም እግዚአብሔር በዳዊት ጥያቄና መሻት ደስ ተሰኝቷል፤ ስለዚህ ቤተ መቅደሱን የሚሠራው የእርሱ ልጅ እንደሚሆን እግዚአብሔር ነገረው። ቤተ መቅደሱን የሠራው የዳዊት ልጅ ሰሎሞን ቢሆንም እንኳ፥ ለቤተ መቅደሱ ሥራ የሚያስፈልገውን ነገር ሁሉ እንዲዘጋጅ ያደረገው ዳዊት ነበር (1ኛ ዜና 22)።

እግዚአብሔር ዳዊት ቤተ መቅደሱን እንዲሠራ ከመፍቀድ ይልቅ፥ ለእርሱ ቤቱን እንደሚሠራለት፥ ዘላለማዊ መንግሥትን፥ ዘላለማዊ ዙፋንንና ዘላለማዊ ቤትን እንደሚሰጠው ቃል ገባለት (2ኛ ሳሙ. 7፡16)። [በ1ኛው ቀን ትምህርታችን ከዳዊት ጋር እግዚአብሔር ስለገባው ቃል ኪዳን የተመለከትነውን ነገር እንደገና ተመልከት።]

4. ዳዊት ከዮናታን ልጅ ጋር የነበረው ግንኙነት (2ኛ ሳሙ. 9)

ከብዙ ዓመታት በፊት፥ ዳዊት ለእርሱና ለቤተሰቡ በጎ በማድረግ ለዮናታን ቃል ኪዳን ገብቶለት ነበር። ዳዊት ኢየሩሳሌምን ከያዘና ጠላቶቹን ካሸነፈ በኋላ የገባውን ቃል ኪዳን አስታወሰ፤ ስለዚህ ከሳኦል

ዘር የቀረ ሰው እንዳለ ማፈላለግ ጀመረ። የሳኦል ቤተሰብ በተደመሰሰ ጊዜ ሜምፌቦስቴ የሚባል ሽባ የሆነ የዮናታን ልጅ ተገኘ። ዳዊትም ሜምፌቦስቴን ወደ ኢየሩሳሌም ካስመጣ በኋላ የሳኦልን ቤትና ንብረት ሁሉ መለሰለት። በቤተ መንግሥትም ሁልጊዜ ከዳዊት ጋር በገበታ እንዲቀርብና እንዲበላ አደረገ፤ እንደተከበረ እንግዳውም ቆጠረው።

## 5. ዳዊት ከቤርሳቤህ ጋር የፈጸመው ኃጢአት (2ኛ ሳሙ. 11-12)

2ኛ ሳሙኤል 11 በመጽሐፉ ውስጥ ያለ የሽግግር ምዕራፍ ነው። ዳዊት ያደረጋቸውን ታላላቅ ነገሮች ከሚገልጠው ክፍል በመንግሥቱ ውስጥ ወደ አጋጠመው ችግር የሚያሸጋግር ምዕራፍ ነው። የዚህ ችግር ዋና ምክንያት ዳዊት የፈጸመው ኃጢአት ነበር። ዛሬ የዳዊትና የቤርሳቤህን ኃጢአት እንመለከታለን። ነገ ደግሞ ይህ ኃጢአት በመንግሥቱ ላይ ስላስከተለው ችግር እናያለን።

ዳዊት ኢየሩሳሌምን በጦርነት አሸንፎ ከያዘ አሥር ወይም ከዚያ በላይ ዓመታት ተቆጥረዋል። ዳዊት የአገሪቱ ንጉሥ እንደመሆኑ የአገሪቱ የጦር አዛዥም ነበር፤ ስለዚህ ጠላቶቹን ለመዋጋት ከሠራዊቱ ጋር አብሮ ይሄድ ነበር። በጥንት ዘመን እስራኤላውያን ጦርነቱን የሚያካሄዱት፥ የዝናብ ወቅት ካለፈና ሰብል ከተሰበሰበ በኋላ በሚያዝያ ወር ነበር፤ ነገር ግን ዳዊት በዚህ ዓመት እንደ ልማዱ ወደ ጦርነት አልሄደም ነበር።

አንድ ምሽት (ተሰላችቶ መሆን አለበት) ዳዊት ወደ ቤቱ ሰገነት ላይ ወጣ። በመካከለኛው ምሥራቅ ብዙ ቤቶች የሚሠሩት ባለሰገነት እየተደረጉ ነበር። በጣም ሞቃት በሚሆንበት ጊዜ ሰገነት የሚተኙበት አለበለዚያም የሚዝናኑበት ስፍራ ነበር። በሰገነቱ ላይ በነበረ ጊዜ ዳዊት በጎረቤቱ ቤት በመታጠቢያ ቤቷ ሆና ሰውነቷን ስትታጠብ ቤርሳቤህን ተመለከታት። ዳዊትም የንጉሥነት ሥልጣኑን ያለ አግባብ በመጠቀም እንድትመጣና ከእርሱ ጋር እንድትተኛ አደረገ። የእግዚአብሔር ሰውና የእስራኤል ንጉሥ የነበረው ዳዊት አመነዘረ። ቤርሳቤህም አረገዘች፤ ስለዚህም ከዚህ አሳፋሪ ነገር ለማምለጥ ዳዊት የሚችለውን ሁሉ አደረገ። ሁለት ነገሮችን ሞከረ፡-

1. በበዓል ቀን የቤርሳቤህን ባል ኦርዮን ከጦርነት ስፍራ ወደ ቤቱ እንዲመጣ አደረገ። ይህንን በማድረጉ ኦርዮ ወደ ቤቱ እንደሚገባና ከሚስቱ ጋር እንደሚተኛ ተስፋ አድርጎ ነበር። ኦርዮ ግን ስለ እስራኤል ጦር ገዶት፥ ይህንን ግብዣ እምቢ ብሎ ወደ ቤቱ ሳይገባና ሚስቱን ሳይጎበኝ ወደ ጦር ሜዳ ተመለሰ።

2. ዳዊት ለጦሩ መሪ ለኢዮአብ ኦርዮንን ከጦሩ ፊት ለፊት እንዲያሰልፈውና ተመትቶም እንዲሞት ጥለውት እንዲሸሹ እንዲያደርግ አዘዘው፤ ስለዚህ ዳዊት ኦርዮንን ለመግደል ጦርነቱን ተጠቀመበት። ዳዊት አመንዝራ ብቻ ሳይሆን ነፍሰ ገዳይም ሆነ።

| |
|---|
| 17ኛ ጥያቄ፥ ሀ) ብዙ ጊዜ አንድ ኃጢአት ሠርተን እርሱን ለመሸፈን ስንሞክር፥ ወደ ሌላ ኃጢአት የሚመራን እንዴት ነው? ለ) ይህ ነገር እንዴት እንደሚሆን፥ ከራስህ ሕይወት ሥዕላዊ መግለጫዎችን ስጥ። ይህን የምናደርገው ለምንድን ነው? |

ስለዚህ ጉዳይ በጣም የሚያሳዝነው ነገር ኦርዮ ከዳዊት ምርጥ ወታደሮች አንዱ የነበረ መሆኑ ነው። ኦርዮ ምርጥ ተብለው ከሚጠቀሱት ከ30 የዳዊት ወታደሮች አንዱ ነበር (2ኛ ሳሙኤል 23፡39 ተመልከት)።

እግዚአብሔር የዳዊትን ኃጢአት ሳይቀጣ አልተወውም። ምናልባት ዳዊት ወደ አመንዝራነትና ነፍሰ ገዳይነት እንደተመለሰ ማንም ሰው አያውቅም ይሆናል። ዳዊት ግን ያውቅ ነበር። ከመዝሙራቱ በአንዱ ኃጢአቱን ለእግዚአብሔር ባለመናዘዙ ምክንያት፥ የተሰማውን የውስጥ መቃተትና ሥጋዊ ሕመም ይናገራል [መዝ. (51)]። እግዚአብሔር ደግሞ ይህን ያውቅ ነበር፤ ስለዚህ የፈጸመውን ተግባር ክፉነት አስረግጦ ሊነግረው ነቢዩ ናታንን ላከበት። የዳዊትን ኃጢአት ታላቅነት በሚገልጥ መንገድ አንድ ምሳሌ ነግሮት ስለ ኃጢአቱ ወቀሰው። ዳዊት በፍርድ መሞት እንኳ እንደሚገባው ያውቅ ነበር። ዳዊት ከኃጢአቱ ንስሐ ቢገባም እንኳ በቀረው የሕይወት ዘመኑ በቤቱ መከፋፈልና ችግር እንደማይጠፋ እግዚአብሔር ነገረው። የቀረው የ2ኛ ሳሙኤል ታሪክ የሚናገረው ይህ ፍርድ በዳዊት ላይ እንዴት እንደተፈጸመ ነው።

የእግዚአብሔር ፍርድ የዳዊትና የቤርሳቤህን የመጀመሪያን ልጅ ሞት የሚያካትት ነበር።

18ኛ ጥያቄ፥ ሀ) የጎለመሱ ክርስቲያኖች እንኳ በኃጢአት ሊወድቁ እንደሚችሉ ይህ ታሪክ ምን ያስተምረናል? ለ) የዚህ ዓይነት ኃጢአት እንዳንሠራ ራሳችንን እንዴት መጠበቅ እንችላለን? ሐ) ስለ እግዚአብሔር ይቅር ባይነት ከዚህ ታሪክ የምንማረው ነገር ምንድን ነው? መ) ኃጢአት ይቅር ከተባለ በኋላ እንኳ ስለሚያስከትላቸው ነገሮች ከዚህ ምን እንማራለን?

## 3ኛ ቀን 2ኛ ሳሙኤል 13-19

19ኛ ጥያቄ፥ ሀ) ከአንድ ተራ የቤተ ክርስቲያን አባል ኃጢአት ይልቅ፥ የአንድ መሪ ኃጢአት ከፍተኛ ችግር የሚያመጣው ለምንድን ነው? ለ) ይህ ከተራ ክርስቲያን ይልቅ በመሪ ላይ ኃጢአቱን የሚያከብደው ለምንድን ነው?

ታላላቅ የእግዚአብሔር ሰዎች አንዳንድ ጊዜ በከባድ ኃጢአት ይወድቃሉ። ይህም ሲሆን በንስሐ ከተመለሱ እግዚአብሔር ይቅር ይላቸዋል። ብዙ ጊዜ ግን የኃጢአታቸው ውጤት ወይም የሚያስከትለው ክፉ ነገር አይቀርም። እግዚአብሔር ለዳዊት በኃጢአቱ ምክንያት «ለዘላለም ከቤትህ ሰይፍ አይርቅም» አለው (2ኛ ሳሙ. 12፡10)።

አንድ መሪ በኃጢአት በሚወድቅበት ጊዜ በተለይም እንደ ዳዊት ዓይነት ከባድ ኃጢአት ከሆነ፥ ብዙውን ጊዜ ውጤቱ ከተራ የቤተ ክርስቲያን አባል ኃጢአት የከፋ ነው። መሪውን የሚመለከተው በርካታ ሰው ስላለ፥ ኃጢአቱ የሚያመጣው ችግር ከሌሎች ሁሉ የላቀ ነው። በሚሰርቅበት ጊዜ ሰዎች ሁሉ በቤተ ክርስቲያን አመራር ላይ የነበራቸውን እምነት ያጠፋል። ወዲያውኑ ሰዎች አሥራታቸውን መስጠት ያቆማሉ። መሪ ቢያመነዝር የእግዚአብሔርን ስም ያስነቅፋል። በተጨማሪም የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ካመነዘሩ እኔም ባመነዝር ምንም አይደለም የሚል አስተሳሰብ በሰዎች ዘንድ እንዲፈጠር ያደርጋል። ሰዎች መሪዎቻቸውን ኃጢአትን ሲያደርጉ ካዩ፥ እነርሱም ኃጢአት ያደርጋሉ።

እግዚአብሔር በዳዊት ላይ ያመጣው ቅጣት ቤተሰቡንም የሚጨምር ነበር። ዳዊት በቤርሳቤህ ላይ የሠራውን ኃጢአት የዳዊት ልጅ መድገሙን ማየት የሚገርም ነው። አምኖን የተባለው ልጁ በከፊል እኅቱ የሆነችውን ልጃገረድ አስገድዶ ደፈራት። እንዲሁም ዳዊት ኦርዮን እንደገደለ አቤሴሎም የተባለው ሌላው ልጁም፥ ነፍስ አጠፋ።

የመሪ ኃጢአት የሚያስከትላቸውን ነገሮች ማንም ሰው ሊወስን አይችልም። ኃጢአት ለመሪ እጅግ አስከፊ ወይም ታላቅ መስሎ ላይታየው ይችላል። መሪው፥ የሠራውን ኃጢአት የመጨረሻ ውጤት ለማወቅና ለመቆጣጠር አይችልም። ኃጢአት ልጆችን እርስ በርስ በማናከስና በእግዚአብሔር ላይ እንዲያምፁ በማድረግ ቤተሰብን ያፈርሳል። ኃጢአት መከፋፈልን እንዲነሣ በማድረግም ቤተ ክርስቲያንን ሊያጠፋ ይችላል። በአጠቃላይ የአንድ አካባቢ አብያተ ክርስቲያናትን በሙሉ ሳይቀር ሊነካ ይችላል።

| |
|---|
| 20ኛ ጥያቄ፥ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በእግዚአብሔር ፊት ንጹሕ ሕይወት መኖር እንዳለባቸው ይህ ነገር ምን ያስተምረናል?<br>21ኛ ጥያቄ፥ 2ኛ ሳሙኤል 13-19 አንብብ። ሀ) አምኖን የፈጸመው ኃጢአት ምንድን ነው? ለ) አቤሴሎም የፈጸመው የመጀመሪያው ኃጢአትስ ምን ነበር? ሐ) አቤሴሎም እግዚአብሔር አስቀድሞ የተናገረውን ትንቢት ከፍጻሜ የሚያደርስ ሌላ ምን አደረገ? (2ኛ ሳሙ. 12፡10)። |

ዳዊት ኃጢአት ከሠራ ጥቂት ጊዜ በኋላ፥ በኃጢአቱ ምክንያት በእርሱና በቤተሰቡ ላይ የተሰጠው ፍርድ ተግባራዊ ይሆን ጀመር። የሚከተሉት ችግሮች እግዚአብሔር በ2ኛ ሳሙ. 12፡10 የተናገረውን ትንቢት እንዴት እንደፈጸሙ ተመልከት፡-

1. የዳዊት ታላቅ ልጅ፥ አምኖን፥ የዳዊት ልጅ የሆነችው ከፊል እኅቱን ትዕማርን አስገድዶ ደፈራት (2ኛ ሳሙ. 13፡1-22)። ትዕማር በጣም ቆንጆ ሴት ስለነበረች፥ ያመመው በማስመሰል ተኝቶ እንድታስታምመው በማድረግ አምኖንን አታለላት። በመጨረሻም አስገድዶ ደፈራት። ከደፈራት በኋላ ግን ሊያገባት

ፈቃደኛ ሳይሆን ቀረ። ትዕግር ድንግልናዋን ወንድሟ ስለወሰደ፥ ከእንግዲህ ሊያገባት የሚችል አንዳችም ሰው አልነበረም፤ ስለዚህ ሕይወቷ ተበላሸ። ወደ ወንድሟ ወደ አቤሴሎም ቤትም ሄደች። አቤሴሎም ይህንን ነገር ለመበቀል ሤራ ማውጠንጠን ጀመረ።

2. አቤሴሎም የእኅቱን ነውር ለመበቀል አምኖንን ገደለ (2ኛ ሳሙ. 13፡23-39)። አቤሴሎም አምኖንን ከቤተ መንግሥቱ ራቅ ብሎ በሚገኝ ስፍራ ሊገናኘው ዐቀደ። በዕቅዱም መሠረት አምኖንን ገደለና ወደ አያቱ ቤት ወደ ጌሹር ሸሸ። አምኖንን በመግደሉ በሕይወት ከነበሩት የዳዊት ልጆች መካከል ከአምኖን ቀጥሎ ያለ እርሱ ስለነበር፥ ዙፋን የመውረስ መብቱንም አመቻቸ።

ነቢዩ ናታን በዳዊት ላይ የተናገረው መልእክት መፈጸም ጀመረ። ትልቁ የዳዊት ልጅ አምኖን በሰይፍ ተገደለ። ይህ ክፉ ነገር የተፈጸመውና የዳዊትን ቤት ለማጥፋት ሲቀጥል የምናየው ለምንድን ነው? እግዚአብሔር አስቀድሞ ስለ ተናገረ ነው? ወይስ የዳዊትም ስሕተት አለበት?

የቤተሰቡ ችግር መነሻ ማለትም ችግሩ የጀመረውና እንዲቀጥልም የሆነው፥ ዳዊት ቤተሰቡን ስላልተቆጣጠረና ልጆቹንም ባጠፉ ጊዜ ስላልቀጣቸው ይመስላል። ዳዊት አምኖን ያደረገውን ነገር ከተረዳ በኋላ ከመቅጣት ታቅቧል (2ኛ ሳሙ. 13፡21)። ደግሞም አቤሴሎም አምኖንን ከገደለ በኋላ ዳዊት አቤሴሎምን አልቀጣውም።

በቤተሰብ ውስጥ ሥነ -ሥርዓት ከሌለ፥ ልጆች ብዙ ጊዜ እግዚአብሔርን በመተው ወደ ሥርዓተ - አልበኝነት ያዘነብላሉ። አብዛኛዎቹ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የሆኑ ሰዎች ልጆች ጌታን የማይከተሉበትና ሰነፎች፥ ትዕቢተኞችና ኃጢአተኞች በመሆን ምስክርነታቸውን የሚያበላሹበት አንዱ ምክንያት ይህ ሊሆን ይችላል። ብዙ የመሪዎች ልጆች የሚወድቁባቸው ሁለት ምክንያቶች አሉ፡- የመጀመሪያው፥ ወላጆቻቸው የጌታን ሥራ በመሥራት በጣም የተወጠሩ በመሆናቸው ተገቢ ትኩረትና ፍቅር ከወላጆቻቸው ሊያገኙ ባለመታደላቸው ነው። እግዚአብሔር ለእያንዳንዱ ወላጅ ልጆቹን በሚገባ እንዲይዝና በጌታ መንገድ እንዲመራቸው ኃላፊነት

ሰጥቶታል። ልጆቻቸውን በእግዚአብሔር ፍርሃትና በፍቅር ሊያሳድጓቸው ካልቻሉ በአገልግሎት ላይ መቆየት እንኳ የለባቸውም (1ኛ ጢሞ. 3፡4-5 ተመልከት)። ሁለተኛው፥ ለልጆቻቸው በጣም የሚሳሱ ይሆኑና ያበላሿቸዋል። ልጆቻችንን በጌታ መንገድ ማሳደግ ፍቅርና የሥነ -ሥርዓት እርምጃ የሚጠይቅ ነው። ክፉና በጎውን መለየት ከጀመሩበት ከዝቅተኛ ዕድሜያቸው አንሥቶ ትክክል የሆነውንና ያልሆነውን ነገር ለማሳየት ሥነ -ሥርዓትን ማስለመድ አለብን።

<table><tr><td>22ኛ ጥያቄ፥ ሀ) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ልጆች ብዙ ጊዜ ደካማ ባሕርይ የሚያሳዩት እንዴት ነው? ለ) ይህ የሚሆነው ለምን ይመስልሃል? ሐ) እግዚአብሔርን በሚያስከብርና ጌታን እንዲከተሉ በሚያበረታታ መንገድ ልጆችን ለማሳደግ አንተና ሌሎች የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እርስ በርስ ለመረዳዳት ምን ማድረግ ትችላላችሁ?</td></tr></table>

3. አቤሴሎም በዳዊት ላይ ዓመፅና ዙፋኑን ለመንጠቅ ሞከረ (2ኛ ሳሙ. 14-19)። ከቤትህ አይጠፋም የተባለለት ሰይፍ፥ የዳዊትን የራሱን ሕይወት እንኳ ለማጥፋት ተፈታተነው። ይህ ነገር በእስራኤል የእርስ በርስ ጦርነት ከማስነሳቱ ሌላም ዳዊት ሕይወቱን ለማዳን ሸሽቶ እንዲደበቅና ለጊዜውም ቢሆን ዙፋኑን ለአቤሴሎም እንዲለቅ አደረገ።

ዳዊት ልጁ አቤሴሎም በቤተ መንግሥት ከእርሱ ጋር ባለመሆኑ አዝኖና አልቅሶ ነበር፤ ነገር ግን አቤሴሎምን ወደቤት ሊያስመጣውና እንደ ቀድሞ ሊያየው ፈቃደኛ አልነበረም። ከኢዮአብ ልመናና ጥረት በኋላ ይህ ነገር ተፈጸመ። አቤሴሎም ወደ ቤት ከመጣም ወዲህ ዳዊት ይቅር ሊለውና ሊያየው ፈቃደኛ ሳይሆን ቀረ። ዳዊት ሊያየው ሊያነጋግረው ፈቃደኛ ስላልሆነ አቤሴሎምም በንጉሡ ላይ አማረረ። ቀስ በቀስም የሕዝቡን ልብ ወደ ራሱ በመስረቅ፥ ዙፋን ላይ ለመውጣት ይጥር ጀመር። ይህን ለማድረግ ተሳካለትና አንድ ቀን ዳዊትን ገድሎ ዙፋን ላይ ለመውጣት ተዘጋጅቶ መጣ። ዳዊት ከመዋጋት ይልቅ፥ ከብዙ ዓመታት በፊት ከሳኦል እንደ ሸሸ፥

ከአቤሴሎሃም ሸሽቶ ወደ ምድረ በዳ ሄደ። ይህም ነገር የዳዊት ጠላቶች የነበሩ እንደ ሳሚ ያሉ ሰዎች ሁሉ በግልጥ እንዲነሡ አደረጋቸው። እንደ ሲባ ያሉ የዮናታን ልጅ ባሪያ የነበሩ ሰዎችም ሜምፊቦስቴን በሐሰት ወንጅለው የሳኦልን ምድር ተቆጣጠሩ። ዳዊት እንዳይያዝና እንዳይገደል ያደረገው፥ የቅርብ ወዳጁና አማካሪው የነበረው አርካዊው ኩሲ ለአቤሴሎም የሰጠው የተሳሳተ ምክር ብቻ ነበር።

በእስራኤልም ውስጥ ታላቅ የእርስ በርስ ጦርነት ተጀመረ። በመጨረሻም የዳዊት ጦር የአቤሴሎምን ጦር አሸነፈ። ረጅም ጠጉር የነበረው አቤሴሎምም በዛፍ መሐል ተንጠልጥሎ ሞተ። የንጉሡን ትእዛዝ በመጣስ ኢዮአብ አቤሴሎምን ገደለው። ዳዊት በልጁ በአቤሴሎም ሞት ምክንያት የመረረ ኃዘን አዘነ። በኢዮአብ ምክር ግን ወደ ኢየሩሳሌም ተመልሶ ዙፋን ላይ ዳግመኛ ተቀመጠ። ዳዊት በዚህ አጋጣሚ ጠላቶቹን ለመበቀል አልፈለገም፤ በኋላ ግን እንዲበቀልለት ልጁን ሰሎሞንን አዘዞት ነበር (1ኛ ነገሥት 2፡8-9፥ 36-46)።

ይህ የእርስ በርስ ጦርነት በመጨረሻ በይሁዳና በቀሪው የእስራኤል ክፍል መካከል የተፈጠረውን መከፋፈል መነሻ ጠቁሟል። አሥሩ ነገዶች ዳዊትን በእስራኤል ላይ እንደ ነገሠ ንጉሥ ሳይሆን፥ እንደ ግል ንብረታችሁ ነው የምትጠብቁት ብለው የይሁዳን ነገድ ወቀሱ። የይሁዳ ሰዎች ከእስራኤል መሪዎች ጋር በዚህ በመከራከራቸው በእስራኤል መካከል መለያየትን አመጣ። ሰሎሞን ከነገሠ በኋላ ይህ ክፍፍል እውን ሆነና አሥሩ ነገዶች የራሳቸውን ንጉሥ ሲሾሙ፥ የይሁዳ ነገድም የራሱን ንጉሥ ሾመ።

> 23ኛ ጥያቄ፥ ሀ) ከእነዚህ ታሪኮች ውስጥ በዳዊት ሕይወት ከተፈጸሙት ችግሮችና ኃዘን የምንማራቸውን አንዳንድ መንፈሳዊ ትምህርቶች ዘርዝር። ለ) የምንማራቸው አንዳንድ መልካም ነገሮችስ የትኞቹ ናቸው? ሐ) ልንጠነቀቅባቸው የሚገቡ ነገሮችስ የትኞቹ ናቸው? መ) ሌሎች የቤተ ክርስቲያን መሪዎችን ለማስተማርና ለማስጠንቀቅ እነዚህን ምዕራፎች እንዴት መጠቀም ይቻላል?

## 4ኛ ቀን፡- 2ኛ ሳሙኤል 20-24

ክርስቲያን መሪዎችን ለመጣል ሰይጣን ብዙ ጊዜ የሚጠቀምባቸው ሦስት ዋና ዋና ነገሮች አሉ። የመጀመሪያው፥ ፍትወተ ሥጋ ነው። ዳዊት ከቤርሳቤህ ጋር ባመነዘረ ጊዜ በዚህ ኃጢአት እንዴት እንደወደቀ ተመልክተናል። የመሪን ልብ ከእግዚአብሔር ለማሸሽ ሰይጣን የሚጠቀምበት ሁለተኛው ነገር፥ ሀብት ነው። ሦስተኛው ደግሞ፥ ትዕቢት ነው። ሰይጣን የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በሥልጣናቸው፥ በኃይላቸው፥ በትምህርታቸው፥ ወዘተ. እንዲታበዩ ይፈታተናቸዋል። እግዚአብሔር ትዕቢተኛውን ሰው እንደሚያዋርድ ስለሚያውቅ፥ ሰይጣን አንድን መሪ ትዕቢት ሲጀምረው ሊያጠፋው እንደሚችል ያውቃል።

24ኛ ጥያቄ፥ ሀ) እነዚህ ሦስት ኃጢአቶች የቤተ ክርስቲያን መሪዎችን ሲያስቸግሩ ያየኸው እንዴት ነው? ለ) ሰይጣን መሪዎችን በእነዚህ ሦስት ነገሮች እንዲወድቁ የሚያደርገው ለምን ይመስልሃል? ሐ) ሕይወትህን መርምር። ሰይጣን በዚህ መንገድ በኃጢአት እንድትወድቅ አድርጎሃልን? ከሆነ ኃጢአትህን ተናዘዝና የተቀደሰ ሕይወት ኑር።

በዳዊትና በጠላቶቹ መካከል ሰላም በወረደና መንግሥቱ እያደገ በሄደ ጊዜ ስለ ኃያል መንግሥቱ ታበየ። ምን ያህል ታላቅ ሠራዊት እንዳለው በማወቅ ይመካና ይኮራ ዘንድ፥ በእስራኤል ውስጥ ያሉ ተዋጊ ሰዎች ሁሉ እንዲቆጠሩ በማድረግ የትዕቢተኝነት ምልክትን አሳየ። ነፍሰ ገዳይ የሆነው ኢዮአብ እንኳ ይህ ነገር ስሕተት መሆኑን አውቆ ነበር። ዳዊት ግን የግድ ቆጠራው እንዲካሄድ ስላለ በሕዝቡ ላይ ፍርድን አስከተለ (2ኛ ሳሙ. 24)።

በእግዚአብሔር ላይ ኃጢአት በማድረግ አመንዝራነትን ከፈጸመበት ጊዜ አንሥቶ፥ የዳዊት መንግሥት ችግሮች ይፈጠሩበት ጀመር። ዛሬ በሥልጣን ዘመኑ መጨረሻ አካባቢ ዳዊትን ስለገጠሙት የተለያዩ ችግሮች እንመለከታለን።

25ኛ ጥያቄ፥ 2ኛ ሳሙ. 20-24 አንብብ። ሀ) የዳዊት መንግሥት መፈራረስ የጀመረው እንዴት ነው? ለ) እግዚአብሔር በእስራኤል ላይ የላከው ፍርድ ምን ነበር? ለምን? ሐ) የዳዊት ኃያላን የጦር ሰዎች ካደረጓቸው ታላላቅ ነገሮች አንዳንዶቹን ጥቀስ። መ) እግዚአብሔር በእስራኤል ላይ ፍርድን እንዲያመጣ ያደረገው ዳዊት የሠራው ኃጢአት ምንድን ነው? ሠ) ዳዊት መሠዊያን የሠራው የት ነው? ለምን?

1. ከሳቤዔ ጋር የተደረገ የእርስ በርስ ጦርነት (2ኛ ሳሙ. 20):-

ከአቤሴሎም ሞት በኋላ የዳዊት ችግሮች ቀጠሉ። በመጀመሪያ በዳዊት ልጅ በአቤሴሎም የተቀሰቀሰ ሕዝባዊ ጦርነት ነበር። ይህ ጦርነት እንዳበቃ የቢክሪ ልጅ ከሆነው ከሳቤዔ ጋር ሌላ ጦርነት ተጀመረ። ይህ ጦርነት በይሁዳና በቀረው የእስራኤል ነገድ መካከል የተካሄደ ነበር። ዳዊት ኢዮአብ ልጁን አቤሴሎምን መግደሉ አስቆጥቶት እንደነበር የምናየው የጦር አዛዥነቱን ከእርሱ ወስዶ ለአሜሳይ በመስጠት ሳቤዔን እንዲወጉ ለአሜሳይና ለአቢሳ ትእዛዝ ሲሰጣቸው ነው፤ ነገር ግን ኢዮአብ በወታደሮቹ ዘንድ እንደ ጦር አዛዥ የሚታይ ስለ ነበር ይህን በሰማ ጊዜ አሜሳይን ገደለው። በአቤል ቤትመዓካ በተባለች ከተማ ያለች አንዲት ሴት፥ ኢዮአብና ጦሩ ከተማይቱን እንዳያጠፉ ሳቤዔን መግደል እንዳለባቸው ሕዝቡን አሳመነች።

2. በእስራኤል ምድር ላይ የመጣ ራብ (2ኛ ሳሙ. 21) በ2ኛ ሳሙኤል የመጨረሻ ክፍሎች ያሉት ታሪኮች ምናልባት በጊዜ ቅደም ተከተል የቀረቡ ላይሆኑ ይችላሉ፤ ነገር ግን ዳዊትን ስለገጠሙት ችግሮች የሚናገሩት ክፍሎች በሙሉ በአንድነት በመጽሐፉ መጨረሻ ሳይሰፍሩ አልቀሩም።

በዳዊት ዘመነ መንግሥት፥ በአንድ በተወሰነ ጊዜ ታላቅ ራብ ለሦስት ዓመታት ሆነ። የዚህ ራብ ምክንያት ምን እንደሆነ ዳዊት እግዚአብሔርን በሚጠይቅበት ጊዜ፥ ሳኦል የገባዖንን ሰዎች በመግደሉ ምክንያት ነው አለው።

**26ኛ ጥያቄ፥ ኢያሱ 9፡15፥ 18-26 አንብብ። ሀ) የገባዖን ሰዎች እነማን ናቸው? ለ) ከእስራኤል ጋር የገቡት ቃል ኪዳን ምን ነበር?**

የገባዖን ሰዎች የከነዓናውያን አንድ ነገድ ሆነው፥ በእስራኤል መካከለኛ ክፍል የሚኖሩ ነበሩ። ከ400 ዓመታት በፊት እስራኤላውያንን በማታለል አይሁድ እንዳይጎዷቸው ቃል አስገብተዋቸው ነበር። ሳኦል የገባዖንን ሰዎች የወጋው መቼ እንደሆነ አይታወቅም። ምናልባት በሳኦል በመጀመሪያዎቹ የንግሥና ዘመን ሳይሆን አይቀርም። በገባዖን ሰዎችና በእስራኤል መካከል የተደረገውን ስምምነት በመጣስ፥ ከብሔራዊ ቅንዓት ተነሥቶ የገባዖንን ሰዎች ለማጥፋት የሞከረ ይመስላል። ብዙ ዓመታት ካለፉ በኋላ ይህንን ስምምነት በማፍረሳቸው እግዚአብሔር በምድሪቱ ላይ ራብ በማምጣት በሕዝቡ ላይ ፈረደ።

ዳዊትም ይህን ነገር ለመበቀል ምን እንደሚፈልጉ የገባዖንን ሰዎች በጠየቃቸው ጊዜ፥ የሳኦልን ሰባት ወንዶች ልጆች እንዲሰጣቸውና እንዲገድሉአቸው ጠየቁ። 7 ቁጥር የፍጹምነት ቁጥር ነው። የተገደሉት የገባዖን ሰዎች በርካታ ቢሆኑም የ7ቱ የሳኦል ወንድ ልጆች መገደል በሳኦል ቤት ላይ ሊደርስ የሚገባውን ፍርድ ያሟላል ማለት ነበር። እንደተባለውም 7ቱ የሳኦል ዝርያዎች ተገደሉ።

ይህ እጅግ አሳዛኝ የሆነ ታሪክ አንድ ዋና ዓላማ አለው። እግዚአብሔር ልጆቹ የገቡትን ቃል ኪዳን ይጠብቁ ዘንድ ምን ያህል እንደሚፈልግ ያሳየናል። ከ400 ዓመታት በፊት እስራኤላውያን የገባዖንን ሰዎች ላለመግደል ቃል ገብተዋል፤ ስለዚህም እግዚአብሔር ቃላቸውን ይጠብቃሉ ብሎ ተስፋ አደረገ። ሰዎች ለእግዚአብሔር ቃል ሲገቡ ለመፈጸም ምንም ያህል አስቸጋሪ ቢሆን፥ የገቡትን ቃል መጠበቅ አለባቸው። ቃላቸውን በማይጠብቁበት በማንኛውም ጊዜ ከእግዚአብሔር ፍርድ ሥር ይወድቃሉ።

**27ኛ ጥያቄ፥ ሀ) እግዚአብሔር የምንገባውን ቃል መጠበቃችንን በከፍተኛ ሁኔታ እንደሚከታተል ይህ ምን ያስተምረናል?**

ለ) ለእግዚአብሔርም ሆነ ለሌሎች የገባነውን ቃል ኪዳን መጠበቅ ምን ያህል ከእኛ እንደሚፈለግ፥ ከዚህ ምን እንማራለን? ሐ) ሰዎች ዛሬ ደጋግመው የሚገቧቸውን ቃል ኪዳኖች በምሳሌነት ጥቀስ። መ) ለእግዚአሔር የገባሃቸውን አንዳንድ ቃል ኪዳኖች ጥቀስ። ሠ) እነዚህን ቃል ኪዳኖች ጠብቀሃል ወይስ አልጠበቅክም? ለእግዚአብሔር የገባሃቸው አንዳንድ ቃሎች ካሉ የእግዚአብሔር በረከት ወደ ሕይወትህ እንዲመጣ በዚህ ሳምንት ፈጽማቸው።

3. የዳዊት ትዕቢትና የሠራው መሠዊያ (2ኛ ሳሙ. 24):-

በ2ኛ ሳሙኤል የሚገኘው የመጨረሻ ምዕራፍ ዳዊት የፈጸመውን አንድ ተጨማሪ ኃጢአት ይነግረናል። ይህ ኃጢአት በእስራኤል ላይ ከፍተኛ ጥፋትን አስከትሏል። እግዚአብሔር በእስራኤል ላይ የተቆጣው ለምን እንደሆነ አናውቅም (2ኛ ሳሙ. 24:1 ተመልከት)። አንዳንድ ምሁራን እስራኤላውያን በዓመፃቸው ዳዊትን ትተው ከአቤሴሎም ጋር በመተባበራቸው ነው ይላሉ። 1ኛ ዜና 21:1-17 ስንመለከት:- ቆጠራው እንዲካሄድ ዳዊትን የፈተነው ሰይጣን እንጂ እግዚአብሔር አይደለም ይላል። እነዚህን ሁለት ታሪኮች ስናገናኛቸው፥ እግዚአብሔር በእስራኤል ላይ በአንድ ባልታወቀ ኃጢአት ላይ ለመፍረድ ወኪላቸው የሆነውን ዳዊትን እንዲያጠቃ ለሰይጣን የፈቀደለት ይመስላል። ሰይጣንም ዳዊትን ፈተነና በትዕቢት እንዲወድቅ አደረገው። የእስራኤልን ሕዝብ በሙሉ የሚወክል ስለነበር፥ እግዚአብሔር ፍርድን በዳዊት ላይ ብቻ ሳይሆን በእስራኤል ሁሉ ላይ አመጣ።

የሠራዊቱ ቆጠራ ዓላማ ዳዊት ምን ያህል ተዋጊ ሰዎች እንዳሉት ለማወቅ ይረዳው ዘንድ ነበር። የተዋጊውን ብዛት ማወቅ የፈለገው ከመታበይ ነበር። ዳዊት በሕይወቱ ዘመን በሙሉ ሲከተለው የነበረውን ዋና ትምህርት ዘነጋ። ድልን የሚሰጥ እግዚአብሔር እንጂ ሰው እንዳልሆነ አስረግጦ ያውቅ ነበር። ሠራዊቱን በማስቆጠር ግን እስከዛሬ ድረስ ላገኘው ድል ምክንያቱ የነበረው ታላቅ ጦር እንጂ የእግዚአብሔር እርዳታ እንዳልሆነ ገለጠ። ይህ በእግዚአብሔር ላይ አለመታመንን የሚያሳይ ትልቅ ምልክት ነበር።

28ኛ ጥያቄ፥ ዛሬም ቢሆን እግዚአብሔር በእኛ ውስጥ በከፍተኛ ሁኔታ ሲሠራ እንዲህ ዓይነት ተመሳሳይ ነገር ልናደርግና በእግዚአብሔር ዘንድ ያለንን ታማኝነት ልናጎድል የምንችለው እንዴት ነው?

ስኬታማነት (ለምሳሌ፡- በትምህርታችን፥ በንብረታችን፥ በቤተ ክርስቲያናችን ታላቅነትና ለጌታ በማረክናቸው ነፍሳት ቁጥር ወዘተ. ስንመካ) በራሳችን እንደተገኘ አድርገን ስንቆጥር ዳዊት በወደቀበት ኃጢአት ወደቅን ማለት ነው። መከናወንን የሚሰጥ እግዚአብሔር ነው። ያለ እርሱ አንዳችም መልካም ነገር ማድረግ አንችልም።

ለዚህ ኃጢአት ቅጣት ይሆን ዘንድ እግዚአብሔር ለዳዊት ከሦስት ነገሮች አንዱን ምረጥ አለው። ዳዊትም የሦስት ቀን ቸነፈርን መረጠ። በቸነፈሩም ምክንያት 70000 ሰዎች ሞቱ።

ዳዊትም ፍርዱን የፈጸመው መልአክ ሰዎችን መግደል ወደ አቆመበት ስፍራ ሄደ። ይህ ስፍራ የኢያቡሳዊው የኦርና አውድማ ነበር። ዳዊትም ይህንን አውድማ ገዛና በዚያ ስፍራ መሠዊያን ሠራ። ይህ ታሪክ በጣም አስፈላጊ የሆነው፥ ዳዊት መሠዊያን የሠራበት ይህ ስፍራ በኋላ የሰሎሞን ቤተ መቅደስ የተሠራበት ስፍራ ስለሆነ ነው። ይህ ማለት ቤተ መቅደሱ የተሠራው የዳዊት ቤት የንጉሣዊ ቤተሰብ ንብረት በሆነ ስፍራ ላይ ነው ማለት ነው።

## የ2ኛ ሳሙኤል ዋና ዋና ትምህርቶች

ከ2ኛ ሳሙኤል የምንመለከታቸው ሦስት ዋና ዋና ትምህርቶች አሉ።

1. ንጉሡ ዳዊት የእስራኤል የመጨረሻ ንጉሥ የሆነው የኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ ነበር። ዳዊት በንጉሣዊ አስተዳደር የመጀመሪያው የእስራኤል ንጉሥ እንደሆነ፥ ኢየሱስ ክርስቶስ መሢሑ የዳዊት ልጅም በእስራኤል ቤት ሁሉና በዓለምም ላይ የመጨረሻው ንጉሥ ነው።

2. እግዚአብሔር ሰዎች ሁሉ ወዳጆቹ እንዲሆኑ ይፈልጋል። አብርሃም የእግዚአብሔር ወዳጅ ነበር። ሙሴም እንደዚሁ፤ ዳዊትም ደግሞ እንዲሁ ነበር። የእግዚአብሔር ወዳጅ መሆን ማለት ያለ ኃጢአት መሆንና ፍጹም ቅዱስ መሆን ማለት አይደለም፤ ነገር ግን እግዚአብሔርን በፍጹም ልባችን በመውደድ፥ ወደ ልባችን ለእግዚአብሔር ንቃት ኖሮት ኃጢአት ባደረግን ጊዜ ወዲያውኑ ንስሐ በመግባትና በማስተዋል ለእግዚአብሔር በመታዘዝ መኖር አለብን ማለት ነው። የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የሆንን ሰዎች በተለይ ከእግዚአብሔር ጋር የቅርብ ግንኙነት ሊኖረን ይገባል። የእግዚአብሔር ወዳጆች መሆን ይጠበቅብናል።

| |
|---|
| 29ኛ ጥያቄ፥ ሀ) የእግዚአብሔር ወዳጅ ነህን? መልስህን አብራራ። ለ) የእግዚአብሔር ወዳጅ ለመሆን ማድረግ ያለብህ ነገር ምንድን ነው? |

3. የእግዚአብሔር ሕዝብ መሪዎች ኃጢአት እንዳይሠሩ ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ አለባቸው፤ ምክንያቱም በበርካታ ሰዎች ላይ ተጽዕኖ ሊያደርጉና የበርካታ ሰዎችን ሕይወት ሊያጠፉ ይችላሉና ነው። መሪዎች ለውድቀት ብዙ ጊዜ ቅርብ የሚሆኑት እጅግ ውጤታማና ስኬታማ ሲሆኑ ነው። በሚገባ እየታወቁና እግዚአብሔር በሥራቸው ከፍተኛ በረከት እየሰጣቸው ሲሄዱ ለመውደቅ የሚቃረቡት ያኔ ነው፤ ምክንያቱም ትዕቢት የሚሰማቸውና በራሳቸው ችሎታ መተማመን የሚጀምሩት ያኔ ነው። ዳዊት ውጤታማነቱ ከፍተኛ ደረጃ ላይ በደረሰ ጊዜ፥ በአመንዝራነትና በመግደል ኃጢአት ወደቀ። ውጤቱም እግዚአብሔር በእርሱ፥ በቤተሰቡና በአጠቃላይ በእስራኤል ሕዝብ ላይ ጥፋት አመጣ።

መጽሐፍ ቅዱስ «ስለዚህ እንደ ቆመ የሚመስለው እንዳይወድቅ ይጠንቀቅ» ይላል (1ኛ ቆሮ. 10፡12)፤ ደግሞም «በሃይማኖት ብትኖሩ ራሳችሁን መርምሩ ራሳችሁን ፈትኑ» ተብለን ታዘናል (2ኛ ቆሮ. 13፡5)። በኃጢአት አንወድቅም ብለን የምናስብበት ጊዜ፥

ከየትኛውም ጊዜ በታላቅ ሁኔታ ለመውደቅ የምንችልበት ጊዜ ስለሆነ እንጠንቀቅ።

| |
|---|
| 30ኛ ጥያቄ፥ ከ2ኛ ሳሙኤል ያገኘሃቸውንና ለቤተ ክርስቲያንህ መንፈሳዊ እድገት ለማስተማር የምትችላቸውን መንፈሳዊ እውነቶች ዘርዝር። |

## አምስተኛ ቀን

የሳምንቱን ትምህርት ከልስና ለሳምንታዊ ስብሰባ ዝግጅት ይረዳህ ዘንድ የውይይት ጥያቄዎቹን ተመልከት።

### ሳምንታዊ ስብሰባ

1. የሳምንቱ የአምልኮ ጊዜ
2. ጸሎት
3. የትምህርቱ ክለሳ
4. ውይይት

1. ሀ) መጽሐፍ ቅዱስ ዳዊት እንደ እግዚአብሔር ልብ የነበረ ሰው ነው ሲል ምን ማለቱ ነው?

   ለ) ዳዊት የእግዚአብሔር ወዳጅ የተባለበትን ምክንያት የሚገልጡ ምሳሌዎችን ከዳዊት ሕይወት ዘርዝር።

   ሐ) ለእግዚአብሔር ነገር ንቁ እንሆን ዘንድ መንፈሳዊው ንቃታችንን እንዴት መጨመር እንችላለን?

   መ) እግዚአብሔር ዛሬም ቢሆን ወዳጁ ሊላቸው የሚችላቸው፥ ከቤተ ክርስቲያንህ የምታውቃቸውን ሰዎች ጥቀስ። ሠ) ይህንን ለማለት ያስቻለህ ከሕይወታቸው የምታየውን ልዩ ነገር ወይም ተግባራቸውን ጥቀስ።

2. ሀ) እርሱን ከሚፈሩት የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እግዚአብሔር ምን እንደሚፈልግ የዳዊት ሕይወት መልካም ምሳሌ የሚሆነው እንዴት ነው? ለ) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እንዴት መምራት እንዳለባቸው ሥዕላዊ መግለጫ የሚሆኑ፥

ከዳዊት ሕይወት ያገኘሃቸው ምሳሌዎችን ጥቀስ። ሐ) ከቤተ ክርስቲያንህ ውስጥ ለሚገኙ መሪዎች በሙሉ ይህንን መመሪያ እንዴት ልታስተምሩአቸው እንደምትችሉ ተወያዩ።

3. ሀ) ከዳዊት ጋር በተገባው ቃል ኪዳን፥ ለዳዊት የተሰጡትን በረከቶች ዘርዝር። ለ) የተፈጸሙትስ እንዴት ነበር? ሐ) ገና የሚፈጸሙትስ እንዴት ነው?

4. ሀ) ስለ እግዚአብሐር ቅድስናና ሙሉ በሙሉ ለእግዚአብሐር የመታዘዝ አስፈላጊነት፥ ከዳዊትና ከታቦቱ ታሪክ የምንማረው ምንድን ነው? ለ) ከዳዊት ጥፈራ እግዚአብሐርን በሙሉ ልብ ስለ ማክበር (ስለ ማምለክ) የምንማረው ነገር ምንድን ነው? ሐ) ሚዛናዊ የሆነና የሚታይ አምልኮ በቤተ ክርስቲያንህ ውስጥ እንዴት ሊካሄድ እንደሚችል ግለጽ።

5. ሀ) ዳዊት በሕይወቱ መጨረሻ አካባቢ በኃጢአቱ ምክንያት የተጋፈጣቸውን የተለያዩ ችግሮች ዘርዝር ለ) ከዳዊትና ከቤርሳቤህ ታሪክ ስለ ኃጢአት የምንማረው ነገር ምንድን ነው? ሐ) የቤተ ክርስቲያን መሪዎችም ትልቅ ኃጢአት ሊሠሩ እንደሚችሉና የኃጢአታቸውም ውጤት ምን እንደሚሆን እነዚህ ምዕራፎች ምን ያስተምሩናል? መ) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ልጆቻቸውን እንዴት ማሳደግ እንዳለባቸው ከዳዊት ሕይወት ምን መማር እንችላለን?

5. ጸሎት

# ትምህርት 15

## 1ኛ ቀን፡- የ1ኛ ነገሥት መግቢያ

የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ሁለተኛ ዋና ክፍል የሆኑትን 12ቱን የታሪክ መጻሕፍት እያጠናን ነበር። እነዚህ መጻሕፍት ከኢያሱ እስከ አስቴር ያሉት ናቸው። እስካሁን ድረስ፥ የእስራኤል ሕዝብ በኃጢአት ምክንያት ለብዙ ዓመታት ከታገሉ በኋላ ወደ ታላቅና ኃያል መንግሥት እንዴት እንዳደጉ ተመልክተናል፤ ነገር ግን በዳዊት ወታደራዊ አመራር የእስራኤል ሕዝብና መንግሥት ወደ ከፍተኛ ስኬታማነት ደረሰ። እንዲሁም ዳዊት ከእስራኤል ታላላቅ የሃይማኖት መሪዎችም አንዱ ነበር። አብዛኛዎቹ የታሪክ መጻሕፍት የዳዊትን ታሪክ ይነግሩናል።

በዚህ ሳምንት 1ኛ ነገሥትን እናጠናለን። 1ኛና 2ኛ ነገሥት ስለ ሰሎሞን ዘመነ መንግሥት አጭር መግለጫ ከሰጡ በኋላ፥ የሰሜኑ የእስራኤል መንግሥትና የደቡቡ የይሁዳ መንግሥት ወደ ምርኮ እስከሄዱበት ጊዜ ድረስ ያለውን የእስራኤል መንግሥት አወዳደቅ ይነግረናል። ከሰሎሞን ሞት ጋር ታላቁ የእስራኤል መንግሥት እንደገና ወደዚያ ኃያልነት ሊመለስ በማይችልበት ሁኔታ እየወደቀ ሄደ። እስራኤል ልክ እንዳለፈው ጊዜ ገናና ልትሆን የምትችለው፥ በመሢሑ የወደፊት መሪነት ብቻ ነው።

1ኛና 2ኛ ነገሥት፥ የእግዚአብሔር ሕዝብ በተከታታይ በሚያምፁበት ጊዜ ስለሚያገኛቸው ቅጣት ይነግሩናል። በራእይ 3፡15፥ 19 ኢየሱስ የሎዶቅያን ቤተ ክርስቲያን እንዲህ ሲል አስጠንቅቆአል፡- «በራድ ወይም ትኩስ እንዳይደለህ ሥራህን አውቃለሁ። በራድ ወይም ትኩስ ብትሆን መልካም በሆነ ነበር»። እንዲሁ ለብ ስላልህ በራድም ወይም ትኩስ ስላልሆንህ ከአፌ ልተፋህ ነው። ... እኔ የምወዳቸውን ሁሉ እገሥጻቸዋለሁ»። የእስራኤል ሕዝብ ለእግዚአብሔር በነበራቸው አምልኮ ሲበላሹ እግዚአብሔር ይቀጣቸው ዘንድ ለጠላቶቻቸው አሳልፎ ሰጣቸው። ከ70 ዓመታት በኋላ ከምርኮ የተመለሱት ጥቂት አይሁድ ብቻ ነበሩ። እነዚህ መጻሕፍት ዛሬ ለእኛ ብርቱ ማስጠንቀቂያ ይሆኑናል። ክርስቲያኖች ዓለምን ከመሰልንና ለእግዚአብሔር የማንጠቅም ከሆንን፥ እግዚአብሔር ለዚህ ዓለም ፍርድ ይተወናል። ይህ የሥነ -ሥርዓት እርምጃ ስደት ሊሆን ይችላል። ወይም ለእግዚአብሔር ታማኝ የሆኑ ጥቂት

ቅሬታዎችን ብቻ አስቀርቶ፥ ቤተ ክርስቲያንን ሙሉ በሙሉ ማጥፋት ሊሆን ይችላል። የሎዶቅያ ቤተ ክርስቲያን ንስሐ በመግባት ወደ ኢየሱስ አልተመለሰችም ነበር። ስለዚህ ዛሬ የሎዶቅያ ቤተ ክርስቲያን ሕልውናዋ የለም። ወደ ሎዶቅያ ብንሄድ፥ ቤተ ክርስቲያኒቱ ተደምስሳ በቦታው መስጊድ ተሠርቶበት እናገኛለን።

| |
|---|
| 1ኛ ጥያቄ፥ ሀ) ዛሬ በዚህ ዘመን ያለን ክርስቲያኖች ኢየሱስ ክርስቶስን ለመውደድና ለእርሱም ለመታዘዝ በገባነው ቃል መጽናት እንዳለብን ይህ እንዴት ብርቱ ማስጠንቀቂያ ይሆንናል? ለ) ቤተ ክርስቲያን ወይም አንድ ክርስቲያን ለብ በሚልበት ጊዜ፥ እግዚአብሔር የሥነ- ሥርዓት እርምጃ የሚወስደው እንዴት እንደሆነ የተመለከትከውን ግለጥ። |

## የመጽሐፈ ነገሥት ርዕስ

እንደ 1ኛና 2ኛ ሳሙኤል፥ 1ኛና 2ኛ ነገሥትም በዕብራይስጡ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አንድ መጽሐፍ ነበሩ። ይህ አንድ መጽሐፍ ከዳዊት ሞት ጀምሮ የተከፋፈለው መንግሥት ወደ ምርኮ እስከተወሰደበት ጊዜ ድረስ ያለውን የእስራኤል ሕዝብ ታሪክ ይሸፍናል። ይህ ማለት በ1ኛና በ2ኛ ነገሥት ውስጥ ያለው የእስራኤል ሕዝብ ታሪክ ከ970-586 ዓ.ዓ. ድረስ ያለው ታሪክ ነው።

የዕብራይስጡ የብሉይ ኪዳን ክፍል ወደ ግሪክ ሴፕቱዋጀንት ትርጉም ሲተረጎም፥ መጽሐፈ ነገሥት በጣም ረጅም ስለሆነ፥ በሁለት መጻሕፍት ተከፈለና 1ኛና 2ኛ ነገሥት ተባለ። የአማርኛው መጽሐፍ ቅዱስ የሴፕቱዋጀንትን ትርጉም የተከተለ ነው።

መጽሐፉ «ነገሥት» የተባለው፥ በእነዚህ ሁለት መጻሕፍት አማካይነት ከዳዊት ሞት ጀምሮ በእስራኤል ላይ በመጨረሻ እስከነገሠው ንጉሥ እስከ ሴዴቅያስ ድረስ ያሉትን የተለያዩ ነገሥታት አጫጭር ታሪኮችን ስለያዘ ነው።

ምሁራን መጽሐፈ ሳሙኤል ከመጽሐፈ ነገሥት ጋር ያለውን ቅርበትና ግንኙነት ለብዙ ጊዜያት ተገንዝበውት ነበር። በእርግጥ የላቲን መጽሐፍ ቅዱስ፥ ለመጽሐፈ ሳሙኤልና ነገሥት 1፥ 2፥ 3 ና 4 ነገሥት የሚሉ ስሞች ሰጥቶአቸዋል። እነዚህ መጻሕፍት በአንድነት ከሳኦል ጀምሮ እስከ ሴዴቅያስ ድረስ የእስራኤል ነገሥታት ስለነበሩበት ዘመን ያለውን ታሪክ ይነግሩናል።

## የመጽሐፈ ነገሥት ጸሐፊ

የመጽሐፈ ነገሥት ጸሐፊ ማን እንደሆነ የምናውቅበት አንዳችም መንገድ የለም። ይህ መጽሐፍ እንዴት እንደተጻፈ የሚናገሩ ሁለት ዋና ዋና ፅንሰ ሐሳቦች አሉ፡-

1. የተለመደው ባሕላዊ አመለካከት፥ የኢየሩሳሌምን ውድቀት በዓይኖቹ ያየ ሰው መጽሐፈ ነገሥትን ጽፎታል የሚል ነው። ይህ ነገር እውነት ይሁን ውሸት በምንም መንገድ ልናረጋግጠው አንችልም። የአይሁድ አፈታሪክ 1ኛ እና 2ኛ ነገሥትን ኤርምያስ ጽፎታል ይላል፥ምክንያቱም 2ኛ ነገሥት 24-25 የትንቢተ ኤርምያስ 52 ተመሳሳይ በመሆናቸው ነው።

2. አሪት ዘዳግማዊ አመለካከት ያላቸው ምሁራን ደግሞ፥ መጽሐፈ ነገሥት ሕዝቡ ከምርኮ ከተመለሱ በኋላ ቆይቶ በአይሁድ ታሪክ ውስጥ ሰዎች በቡድን የጻፉት ነው ይላሉ። መጽሐፉን የጻፉት ከዳዊት ዘር የሆነውን ንግሥና ለመደገፍ፥ በአምልኮ ወቅት የንጽሕናን አስፈላጊነት ለመናገር፥ የነቢያትን ትንቢቶች ፍጻሜ ለማሳየትና በተለይም ደግሞ በአሪት ዘዳግም ውስጥ ያሉትን በረከቶችና እርግማኖች በእስራኤል ሕዝብ ታሪክ እንዴት እንደተፈጸሙ ለማሳየት ነው።

መጽሐፈ ነገሥትን ከተለያዩ መጻሕፍት ያጠናቀረው አንድ ሰው እንደ ነበር ማመን ከሁሉ የተሻለው መንገድ ነው። ይህ ያልታወቀ ጸሐፊ መጽሐፈ ነገሥትን ከ586-539 ዓ.ዓ. ባለው ጊዜ አጠናቅቆታል። የመጨረሻውን መጽሐፈ ነገሥት ለመጻፍ ጸሐፊው ሌሎች ጽሑፎችንና መጻሕፍትን በመረጃ ምንጭነት መጠቀሙ ግልፕ ነው። በእርግጠኝነት የምንጠቅሳቸው ቢያንስ ሦስት መጻሕፍት አሉ፡- የሰሎሞን የታሪክ መጽሐፍ (1ኛ ነገ. 11፡ 41)፥ 17 ጊዜ የተጠቀሰው የእስራኤል የነገሥታት ታሪክ መጽሐፍ (ለምሳሌ 1ኛ ነገ. 14፡19) ፥እንዲሁም 15 ጊዜ የተጠቀሰው የይሁዳ ነገሥታት ታሪክ መጽሐፍ (ለምሳሌ 1ኛ ነገ. 15፡23) ናቸው። እነዚህ መጻሕፍት የመጽሐፈ ነገሥት ጸሐፊ በመረጃነት የተጠቀመባቸው የቤተ መንግሥት ታሪኮች ሳይሆኑ አይቀሩም።

አንዳንድ ምሁራን መጽሐፈ ነገሥትን የጻፈው ከእስራኤል ነቢያት አንዱ ነው፤ ስለዚህም ነው በነቢያት ሥራዎች ላይ ትኩረት የሚያደርጉ

ባሕላዊ መጻሕፍትን የሚጠቀመው ይላሉ። ከመጽሐፍ ቅዱስ እንደምናውቀው፥ ነቢያት የጻፉት የትንቢትን መጻሕፍት ብቻ ሳይሆን፥ የታሪክንም መጻሕፍት ነው (ለምሳሌ:- 1ኛ ዜና 29፡29፤ 2ኛ ዜና 9፡29፤ 20፡34፤ 26፡22)።

** 2ኛ ነገሥት 25፡ 22-30 የመጽሐፈ ነገሥት ዋና ክፍል በሚጻፍበት ጊዜ ሳይሆን ኋላ የተጨመረ ይመስላል።

## የ1ኛና የ2ኛ ነገሥት የጊዜ ቅደም ተከተል

የነገሥታት ዘመን በሁለት ዋና ዋና ክፍሎች መከፈሉን ቀደም ሲል አይተናል። የመጀመሪያው ደረጃ ሳኦል፥ ዳዊትና ሰሎሞን በየተራ የነገሡበት የተባበረው የእስራኤል መንግሥት ሲሆን፥ ይህ ጊዜ ከ1050 እስከ 931 ዓ.ዓ. ድረስ የቆየ ነው። በሁለተኛ ደረጃ፥ የተከፋፈለው መንግሥት የቆየበት ጊዜ ሲሆን በሦስቱ ነገሥታት ዘመን በአንድነት የቆየችው አገር ለሁለት ተከፍላ:- በሰሜን እስራኤል፥ በደቡብ ይሁዳ የሚል መንግሥት ተቋቁሞ ነበር። ይህ ዘመን ከ931-586 ዓ.ዓ. ድረስ ቆይቷል።

1ኛ ነገሥት በተባበረው መንግሥትና ለሁለት በተከፈለው መንግሥት መካከል ስለ ነበረው የሽግግር ጊዜ የሚገልጥ ነው። በአንድነት በቆየው መንግሥት የነገሠው የመጨረሻው ሰው የዳዊት ልጅ ሰሎሞን ነበር። የ1ኛ ነገሥት ታሪክ የተቀረጸበት ጊዜ ዳዊት ከሞተበት ከ970 ዓ.ዓ. እስከ 853 ዓ.ዓ. ድረስ ነበር።

አንድ በነበረው በእስራኤል መንግሥት ላይ የነገሡት ነገሥታት እያንዳንዳቸው 40 ዓመታት ገዝተዋል። አንዳንድ ምሁራን ሳኦል፥ ዳዊትና ሰሎሞን የነገሡበትን ጊዜ በሚከተለው ሁኔታ ይገልጻሉ:-

ሳኦል - 1050-1010 ዓ.ዓ.

ዳዊት - 1010-970 ዓ.ዓ.

ሰሎሞን - 970-931 ዓ.ዓ.

ለሁለት በተከፈለው የእስራኤል መንግሥት ልናስታውሳቸው የሚገቡን ጊዜያት የሚከተሉት ናቸው:-

1. የሰሎሞን ሞትና የመንግሥቱ ለሁለት መከፈል 931 ዓ.ዓ.

2. የሰሜኑ መንግሥት ምርኮ 722 ዓ.ዓ.

3. የደቡብ መንግሥት ምርኮ 586 ዓ.ዓ.

የሚከተለው ሠንጠረዥ መንግሥቱ ለሁለት ከተከፈለ በኋላ የነገሡ ነገሥታትን የሚያሳይ ነው። እነዚህን ነገሮች ሁሉ ማስታወስ አስፈላጊ አይደለም። ሠንጠረዡ ግን የዘመኑን ታሪክ የበለጠ እንድትረዳ ያደርግሃል።

| የደቡብ ንጉሥ (ባሕርያት) | ዘመኑ | የሚገኝበት ክፍል | የሰሜኑ ንጉሥ (ባሕርያት) | ዘመኑ | የሚገኝበት ክፍል |
|---|---|---|---|---|---|
| ሮብዓም (ከፉ) | 931–913 ዓ.ዓ. | 1ኛ ነገ. 12:1–24<br>14:21–31<br>2ኛ ዜና 10–12 | ኢዮርብዐም ቀዳማዊ (ከፉ) | 930–909 ዓ.ዓ. | 1ኛ ነገ. 12:25–14:20 |
| አብያ (ከፉ) | 913–911 ዓ.ዓ. | 1ኛ ነገ. 15:1–8<br>2ኛ ዜና 13–14:1 | | | |
| አሳ (መልካም) | 911–869 ዓ.ዓ. | 1ኛ ነገ. 15:9–24<br>2ኛ ዜና 14:2–3<br>15:16–16:6 | ናዳብ (ከፉ) | 909–908 ዓ.ዓ. | 1ኛ ነገ. 15:25–31 |
| | | | ባኦስ (ከፉ) | 908–886 ዓ.ዓ. | 1ኛ ነገ. 15:27–16:7 |
| | | | ኤላ (ከፉ) | 886–885 ዓ.ዓ. | 1ኛ ነገ. 16:6–14 |
| | | | ዘምሪ (ከፉ) | 885 ዓ.ዓ. | 1ኛ ነገ. 16:9–20 |
| | | | ታምኒ (ከፉ) | 885–880 ዓ.ዓ. | 1ኛ ነገ. 16:21–22 |
| | | | ዖምሪ (ዘምበሪ) (ከፉ) | 885–874 ዓ.ዓ. | 1ኛ ነገ. 16:15–28 |
| ኢዮሳፍጥ (መልካም) | 872–848 ዓ.ዓ. | 1ኛ ነገ. 22:41–50<br>2ኛ ዜና 20:31–21:1 | አክዓብ (ከፉ) | 874–853 ዓ.ዓ. | 1ኛ ነገ.16:28–22:40 |
| ኢዮራም (ከፉ) | 848–841 ዓ.ዓ. | 2ኛ ነገ.8:16–24<br>2ኛዜና 21:1–20 | አካዝያስ (ከፉ) | 853–852 ዓ.ዓ. | 1ኛ ነገ. 22:40–<br>2ኛነገ. 1:18 |
| | | | ኢዮራም | 852–841 ዓ.ዓ. | 2ኛ ነገ. 3:1–9:25 |
| አካዝያስ (ከፉ) | 841–ዓ.ዓ. | 2ኛ ነገ. 8:24–9:29<br>2ኛ ዜና 22:1–9 | ኢዩ | 841–814 ዓ.ዓ | 2ኛ ነገ.9:1–10:36 |
| ዐታልያ (ጎቶልያ) (ከፉ) | 841–835 ዓ.ዓ. | 2ኛ ነገ.11:1–20<br>2ኛ ዜና 22–23 | | | |

| | | |
|---|---|---|
| ኢዮአስ (መልካም) | 835–796 ዓ.ዓ. | 2ኛ ነገ. 11፡1–12፤ 21 2ኛ ዜና 22፡10–24፡27 |
| አሜስያስ (መልካም) | 796–767 ዓ.ዓ. | 2ኛ ነገ. 14፡1–20 2ኛ ዜና 25፡1–28 |
| ዓዛርያ (መልካም) | 792–740ዓ.ዓ. | 2ኛነገ.15፡1–7፤ 2ኛዜና 26፡1–23 |
| ኢዮአታም (መልካም) | 750–735ዓ.ዓ. | 2ኛነገ. 15፡32–38፤ 2ኛዜና 27፡1–9 |
| አካዝ (ክፉ) | 735–715 ዓ.ዓ. | 2ኛነገ. 16፡1–20 2ኛዜና 28፡1–27 |
| ሕዝቅያስ(መልካም) | 715–686ዓ.ዓ. | 2ኛነገ. 18፡1–20፡21፤ 2ኛዜና 29፡1–32፡33 |
| ምናሴ (ክፉ) | 697–642ዓ.ዓ. | 2ኛነገ. 21፡1–18፤ 2ኛዜና 33፡1–20 |
| አሞጽ (አሞን) (ክፉ) | 642–640 ዓ.ዓ. | 2ኛነገ. 21፡19–26፤ 2ኛዜና 33፡21–25 |
| ኢዮስያስ (መልካም) | 640–609ዓ.ዓ. | 2ኛነገ. 22–23፤ 2ኛዜና 34–35 |
| ኢዮአክስ (ኢዮአሐዝ) (ክፉ) | 609ዓ.ዓ. | 2ኛ ነገ. 23፡31–33፤ 2ኛ ዜና 36፡1–4 |
| ኢዮአቄም (ክፉ) | 609–598ዓ.ዓ. | 2ኛ ነገ. 23፡34–24፡6፤ 2ኛ ዜና 36፡5–7 |
| ዮአኪን (ክፉ) | 598–597ዓ.ዓ. | 2ኛ ነገ. 24፡6–16፡3፤ 2ኛ ዜና 36፡8–10 |
| ሴዴቅያስ (ክፉ) | 597–586ዓ.ዓ. | 2ኛ ነገ. 24፡17–25፡30፤ 2ኛ ዜና 36፡11–21 |

በምርኮ

| | | |
|---|---|---|
| ኢዮአካዝ(ክፉ) | 814–798 ዓ.ዓ. | 2ኛ ነገ.13፡1–9 |
| ዮአስ (ክፉ) | 798–782 ዓ.ዓ. | 2ኛ ነገ. 13፡9–14፡16 |
| | 793–753 ዓ.ዓ. | 2ኛነገ. 14፡23–29 |
| ዘካርያ(ክፉ) | 753–ዓ.ዓ. | 2ኛነገ. 14፡29–15፡12 |
| ሳሎም (ክፉ) | 752 ዓ.ዓ. | 2ኛነገ. 15፡10–15 |
| ምናሔም (ክፉ) | 752–742ዓ.ዓ. | 2ኛነገ. 15፡14–22 |
| ፋቂያስ (ክፉ) | 742–740ዓ.ዓ. | 2ኛነገ. 15፡22–26 |
| ፋቁሔ (ክፉ) | 752–732 ዓ.ዓ. | 2ኛነገ. 15፡27–31 |
| ሆሴዕ (ክፉ) | 732–722ዓ.ዓ. | 2ኛነገ. 15፡30–17፡6 |

በምርኮ

ከዚህ ሠንጠረዥ የሚከተሉትን ነገሮች ልብ በል፡-

1. በደቡብና በሰሜኑ መንግሥታት ውስጥ የነገሥታት ቁጥር እኩል ነበር። እያንዳንዳቸው 20 ነገሥታት ነበራቸው። የሰሜኑ መንግሥት አንድ ንጉሥ በሥልጣን ላይ የቆየበት ማዕከላዊ ጊዜ 10 ዓመት ሲሆን፥ የደቡብ ግን 17 ዓመት ነበር።

2. የሰሜኑ መንግሥታት ከ930-722 ዓ.ዓ. ድረስ (208 ዓመታት) የቆየ ሲሆን፥ የደቡብ መንግሥት 931-586 (345 ዓመታት) ቆይቷል።

3. የሰሜኑ ነገሥታት በቀዳማዊ ኢዮርብዓም 1ኛ የተጀመረውን የጣዖት አምልኮ ማምለክ የቀጠሉ ሁሉም ክፉ የነበሩ ናቸው፤ ነገር ግን ከደቡብ ነገሥታት መካከል ስምንቱ መልካም ሲሆኑ፥ የቀሩት እንደ ዳዊት ስላልነበሩና ለእግዚአብሔር ስላልታዘዙ ክፉ ተብለው ተጠርተዋል። ይልቁንም እነርሱ ጣዖት አምላኪዎች ስለሆኑ ሕዝቡን ወደ ኃጢአት መሩት።

4. 2ኛ ዜና በሰሜኑ ሳይሆን በደቡብ መንግሥት ላይ ያተኮረ ነው።

5. የአንዳንዶቹ ነገሥታት ዘመናት ተደራራቢ ናቸው። (ለምሳሌ፡- ሕዝቅያስና ምናሴ የኖሩባቸውን ዘመናት ተመልከት)። ይህ የሚሆነው አባቱ በነገሠበት ጊዜ ልጁም የአባቱን የተወሰነ ክልል ይገዛ ስለነበር ነው። እነዚህን የነገሥታት ዘመናት ከሌሎች መጻሕፍት ጋር ብታወዳድር ትንሽ ልዩነት ታያለህ። ይህም የሆነው ምሁራን ስለእነዚህ ዘመናት ፍጹም በእርግጠኝነት መወሰን ስላልቻሉ ነው።

የደቡብ መንግሥት በሙሉ የተገዛት በዳዊት ዝርያ ነው። የሰሜኑ መንግሥት ግን ዘጠኝ የተለያዩ የንጉሣውያን ቤተሰብ ነበራቸው። ቀጥሎ አራቱ ንጉሣውያን ቤተሰብ ተዘርዝረዋል፡-

1. የኢዮርብዓም ሥርወ-መንግሥት 930-908 ዓ.ዓ.
2. የበአሳ ሥርወ - መንግሥት 908-885 ዓ.ዓ.
3. የዘንበሪ ሥርወ-መንግሥት 885-841 ዓ.ዓ.
4. የኢዩ ሥርወ-መንግሥት 841-752 ዓ.ዓ.
5. የመጨረሻዎቹ ነገሥታት 752-722 ዓ.ዓ.

ከሰሜኑ መንግሥት ሰባት ነገሥታት በሰው እጅ ሲገደሉ፥ አንድ ንጉሥ ራሱን ገሏል፤ አንድ ሌላ ንጉሥ በእግዚአብሔር የተገደለ ሲሆን፥ አንድ ንጉሥ በምርኮ ወደ አሦር መንግሥት ተወስዷል።

በደቡብ መንግሥት አምስት ነገሥታት በሰው እጅ ሲገደሉ፥ ሁለት በእግዚአብሔር መቅሠፍት ተመትተዋል ሦስት ደግሞ ወደ ባዕድ ምድር በምርኮ ተወስደዋል።

በ1ኛ ነገሥት ታሪክ ውስጥ የነበሩ ኃያላን መንግሥታት

1. ከ1000-931 ዓ.ዓ. በመካከለኛው ምሥራቅ የነበረ ኃያል መንግሥት የእስራኤል መንግሥት ነበር። ግብፅ በጣም ደካማ ስለነበረች በሰሜን በኩል ከነዓንን የሚፈታተን ጠንካራ መንግሥት አልነበረም። በዳዊት አመራር፥ የእስራኤል መንግሥት በደቡብ እስከ ግብፅ ድረስ፥ በሰሜን ደግሞ እስከ ኤፍራጥስ ወንዝ ድረስ ተስፋፋ። በተጨማሪም ዳዊት የሞዓብን፥ የኤዶምና የአሞንን ወዘተ. መንግሥታት ተቆጣጠረ። እነዚህ መንግሥታት በዮርዳኖስ ወንዝ በስተምሥራቅ በኩል የሚገኙ ነበሩ። ሰሎሞን ይህንን ታላቅ መንግሥት ከአባቱ ከዳዊት የተረከበ ሲሆን፥ አብዛኛውን ክፍል እስከ ሞተበት እስከ 931 ዓ.ዓ. ሊያቆየው ችሏል። ከሰሎሞን ሞት በኋላ መንግሥቱ ለሁለት ስለተከፈለች፥ የእስራኤል ኃይል በመዳከሙ፥ ሌሎች መንግሥታት አይለው ተነሡ። በሰሜንና በደቡብ መንግሥታት መካከል የተደረገው የእርስ በርስ ጦርነትም፥ ሁለቱ መንግሥታት በጣም ደካሞች እንዲሆኑ አደረገ።

2. ግብፅ:- በሰሎሞን ዘመነ መንግሥት ግብፅና እስራኤል ይተባበሩ ነበር። ሰሎሞን የግብፁን የፈርዖንን ልጅ ያገባው በዚህ ምክንያት ነው፤ ነገር ግን በሰሎሞን ዘመነ መንግሥት መጨረሻ አካባቢ ግብፅ የሰሎሞንን መንግሥት የሚቃወሙ ዓመፀኞችን መደገፍ ጀመረች (ለምሳሌ:- ቀዳማዊ ኢዮርብዓም)። መንግሥቱም ለሁለት እንደተከፈለ፥ የግብፅ ንጉሥ የከነዓንን ደቡባዊ ክፍል አጥቅቶ ከይሁዳ መንግሥት ላይ ወሰደ። የኢየሩሳሌምን ከተማ አጥቅቶ ምርኮ ወሰደ። በ1ኛ ነገሥት ታሪክ ውስጥ በሙሉ ግን የግብፅ መንግሥት እስራኤልን ወይም ይሁዳን የሚፈታተን ጠንካራ ኃይል አልነበረም።

3. ሶርያ፡- በእነዚህ ዓመታት በእስራኤል መንግሥት ላይ ችግር ሲፈጥር የነበረ የአሕዛብ ዋና መንግሥት፥ የሶርያ መንግሥት በዚያን ዘመን አረማውያን በመባል ይታወቅ ነበር። ዋና ከተማቸው ደማስቆ ነበር። ከሮብዓም ዘመን (732 ዓ.ዓ.) ጀምሮ ደማስቆ በአሶር መንግሥት እስከተደመሰሰችበት ጊዜ ድረስ፥ የሶርያ መንግሥት ለእስራኤል የማያቋርጥ፥ ለይሁዳ ደግሞ የአንዳንድ ጊዜ ፈተና ነበር (ለምሳሌ፡- ኢሳ. 7)።

4. አሶር፡- በ1ኛ ነገሥት ታሪክ መጨረሻ ገደማ፥ የአሶር መንግሥት በኃይል ማደግ ጀመረ። ከ892-648 ዓ.ዓ. ባለው ዘመን በመካከለኛው ምሥራቅ ጠንካራ መንግሥት ሆኖ ቆየ። መጽሐፍ ቅዱስ ባይገልጸውም እንኳ የእስራኤል ንጉሥ አክዓብ የአሦርን መስፋፋት ለመግታት በ853 ዓ.ዓ.፥ ከሌላ መንግሥት ጋር በመተባበር ተዋግቶ ነበር። ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጭ የሆኑ ዓለማዊ ታሪኮች አክዓብ ከሶርያ ጋር በትብብር ለመዋጋት 2000 ሰረገሎችንና 10000 ወታደሮችን ሰጥቶ እንደነበር ይናገራሉ።

## የ1ኛ ነገሥት አስተዋጽኦ

1. ሰሎሞን (1-11)
2. ሮብዓም (12)
3. የተከፋፈለው የእስራኤልና የይሁዳ መንግሥት [13-22] (931-853 ዓ.ዓ.)

   ሀ. ቀዳማዊ ኢዮርብዓም (12፡22-14፡20)

   ለ. ሮብዓም (14፡21-33)

   ሐ. አብያ (15፡1-8)

   መ. አሳ (15፡9-24)

   ሠ. ናዳብ (15፡25-32)

   ረ. በአሳ (15፡33-16፡7)

   ሰ. ኤላ (16፡8-14)

   ሸ. ዘምሪ (16፡15-20)

ቀ. ዘንበሪ (16፡21-28)

በ. አክዓብ (16፡29-34)

4. ኤልያስና ነገሥታት

ሀ. ኤልያስና አክዓብ (17፡1-22፡40)

ለ. ኢዮሣፍጥ (22፡41-50)

ሐ. አካዝያስ (22፡51-53)

## የ1ኛ ነገሥት ዓላማዎች

1. በሰሎሞን ጊዜና ከተከፋፈለ በኋላ ማለት ከ931-853 ዓ.ዓ. የነበረውን የእስራኤልን መንግሥት ታሪክ ባጭሩ ለመናገር ጸሐፊው በነገሥታት ጊዜ የነበረውን አጠቃላይና የተሟላ ታሪክ ለመናገር አይፈልግም። በእያንዳንዱ ንጉሥ ዘመን የተፈጸመውን ነገር የሚናገሩ ዝርዝር መዛግብት በቤተ መንግሥቱ ጽሑፎች ውስጥ ይገኙ ነበር፤ ስለዚህ የዚህ መጽሐፍ ጸሐፊ፥ እያንዳንዱ ንጉሥ በነገሠበት ዘመን ስለተፈጸመው ነገር እጅግ አጠር ያለ ማጠቃለያ በመስጠት፥ በተለይም ንጉሡ እንደ ዳዊት እንደነበረ ወይም እንዳልነበረ በሚያሳይ መልኩ ብቻ ባሕርዩን ለመዳሰስ ሞክሯል።

የነገሥታቱን ታሪክ በሚናገርበት ጊዜ፥ ጸሐፊው የሚከተለውን መሠረታዊ አወቃቀር ተከትሏል፡-

ሀ. የንጉሡ ማንነት ይነገርና የአባቱ ስም ይጠቀስ ነበር።

ለ. ንጉሡ ወደዚህ ሥልጣን የመጣበት ዕድሜ ተጠቅሷል። ከይሁዳ ክፍለ መንግሥት ከሆነ ብዙ ጊዜ የንጉሡ እናት ስም ተጠቅሷል።

ሐ. በንጉሡ ዘመን የተፈጸሙ ዐበይት ክስተቶች ተጠቅሰዋል።

መ. ጸሐፊው የንጉሡን የሥነ - ምግባር ባሕርይና በሕዝቡ ላይ የነበረውን መንፈሳዊ አመራርም ባጭሩ ይገመግማል። ንጉሡ ከይሁዳ ከሆነ ሕይወቱን ከዳዊት ጋር ማወዳደር፥ ከእስራኤል ከሆነ ደግሞ ከቀዳማዊ ኢዮርብዓም ጋር ማወዳደር የተለመደ ነው።

2. እግዚአብሔር በእስራኤል ላይ ለምን እንደፈረደ ለማሳየት። ጸሐፊው የ1ኛ ነገሥትን መጽሐፍ በሚጽፍበት ጊዜ፥ ሙሴ በዘዳ. 27-28 የሰጣቸው ተስፋዎች በአእምሮው ነበሩ። ጸሐፊው እስራኤል ለእግዚአብሔር በመታዘዝ በኖረችበት ጊዜ፥ እርሱ የሰጠውን የተስፋ ቃል በሙሉ እንዴት እንደፈጸመ ይናገራል፤ ነገር ግን እስራኤላውያን በእግዚአብሔር ላይ በሚያምፁበት ጊዜና ግዴታቸውን ሳይወጡ ሲቀሩ፥ በተስፋ ቃሉ የሰጠውን ፍርድ ያመጣባቸው ነበር።

| |
|---|
| 2ኛ ጥያቄ፥ ዘዳ. 27-28 አንብብ። ሀ) ለቃል ኪዳኑ ባለመታዘዝ ስለሚመጡ ፍርዶች (መርገሞች) የተነገረውን ነገር ዘርዝር። ለ) ለቃል ኪዳኑ በመታዘዝ ስለሚገኙ በረከቶች የተሰጠውንም ነገር ዘርዝር። |

3. እግዚአብሔር ነቢያትን የእርሱ አፈቀላጤ አድርጎ ወደ ነገሥታቱ እንዴት ይልካቸው እንደ ነበር ለማሳየት። እግዚአብሔር ሕዝቡን ተግባራቸው ምን ውጤት እንዳለው ሳይገነዘቡ፥ ኮብልለው እንዲሄዱ አይፈልግም ነበር። በመሆኑም እግዚአብሔር ነቢያትን እያስነሣ ድርጊታቸውን እንዴት እንደሚመለከትና እንደሚፈርድባቸው ሕዝቡን ሁሉ በተለይም ነገሥታትን እንዲያስጠንቅቁአቸው ያደርግ ነበር። እነዚህ ነቢያት እግዚአብሔር በመለኮታዊ መንገዱ የመረጣቸውና ሕዝቡን የሥነ - ምግባር እውቀት እንዲኖራቸው የሚያደርጉ ነበሩ።

| |
|---|
| 3ኛ ጥያቄ፥ ሀ) ዛሬም ክርስቲያኖች ለኅብረተሰባቸው የሥነ - ምግባር እውቀት (ብርሃን)መሆን የሚችሉት እንዴት ነው? ለ) ለኅብረተሰባቸው የእግዚአብሔር አፈቀላጤ የሚሆኑትስ እንዴት ነው? ሐ) ቤተ ክርስቲያንህ ይህንን ሚና እየተጫወተች ያለችው እንዴት ነው? ግልጥ የሆኑ መግለጫዎችን ስጥ። |

4. ዓመፀኞች፥ የማይታዘዙና ጣዖት አምላኪዎች የሆኑ የእግዚአብሔር ሕዝብ መሪዎችና ነገሥታት እንዴት በሕዝቡ ሁሉ ላይ እንዴት የእግዚአብሔርን ፍርድ እንዳመጡ ለማሳየት ነው። ብዙ ጊዜ በኃጢአት የሚወድቁት ሕዝቡ አይደሉም። የአንድ ሕዝብ መሪ የሆነው ንጉሥ በኃጢአት በሚወድቅበት ጊዜ፥ በራሱ ተጽዕኖ ሕዝቡንም ወደ ኃጢአት ይመራቸዋል። በሌላ በኩል ደግሞ ንጉሡ ጻድቅ ከሆነና ለእግዚአብሔር በመታዘዝ ከኖረ፥ ሕዝቡ

እግዚአብሔርን በሚገባ እንዲያመልኩና ለእግዚአብሔር በመታዘዝ እንዲኖሩ ሊያደርግ ይችላል።

4ኛ ጥያቄ፥ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በቤተ ክርስቲያናቸው አባላት መንፈሳዊና ሥነ - ምግባራዊ ሕይወት ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድሩ ስለመቻላቸው ከዚህ ምን ለመማር እንችላለን?

## 2ኛ ቀን፡- 1ኛ ነገሥት 1-11

በእስራኤል ሕዝብ ታሪክ ሰሎሞን በሥልጣን ላይ የነበረበት ዘመን፥ አንዳንድ ጊዜ «ወርቃማው ዘመን» ወይም ለእስራኤል ሕዝብ ከሁሉም የተሻለው ጊዜ በመባል ይታወቃል። በሰሎሞን አመራር፥ የእስራኤል ሕዝብ በዘመኑ እጅግ የታወቁና ገናና ሕዝብ ሆኑ። በብልጽግናና በሰላም የተሞላ፥ እጅግ የሠለጠነ ሕዝብ ሆኖ ነበር፤ ነገር ግን ይህ ለእስራኤል ሕዝብ አደገኛ ነበር።

5ኛ ጥያቄ፥ ዘዳ. 6፡10-13፤ 8፡7-14 አንብብ። ሀ) በእነዚህ ጥቅሶች ለእስራኤላውያን የተሰጠው ማስጠንቀቂያ ምን ነበር? ለ) እነዚህ ማስጠንቀቂያዎች በቤተ ክርስቲያንህ የተፈጸሙት እንዴት ነው? ሐ) ስደት ሲቀርና መልካም ጊዜ ሲመጣ፥ ብዙ ክርስቲያኖች በኃጢአት የሚወድቁት ለምንድን ነው?

ሰሎሞን ከአባቱ ከዳዊት ታላቅ መንግሥትን ወረሰ። ድንበሩ ከግብፅ ጀምሮ እስከ ኤፍሬጥስ ወንዝ ድረስ የሚዘልቅ ነበር። ከጠላቶች ጋር ሰላም ነበር። በምድሪቱ የተትረፈረፈ ነገር ነበር። ሰላምንና ብልጽግናን ለማግኘት ሰሎሞን መዋጋት አልነበረበትም። እንዲሁ ተሰጥተውት ነበር። ሰሎሞን አመራሩን የጀመረው በጥሩ ሁኔታ ነበር። በእግዚአብሔር ላይ ያለውን መደገፍ በማሳየት፥ የእግዚአብሔርን ሕዝብ ለመምራት ይችል ዘንድ ጥበብን ለመነ። እግዚአብሔርም ሰሎሞንን በምድር ላይ ከኖሩ ሕዝቦች ሁሉ የላቀ ጠቢብ ሰው አደረገው። ይህ ጥበቡ በመጽሐፈ ምሳሌ ውስጥ ተንጸባርቋል። የሰሎሞን ጥበብ ግን በመንፈሳዊ ሕይወቱ የበሰለ ሰው አላደረገውም። እንደ ዳዊት፥ እግዚአብሔርን በሙሉ ልቡ ማገልገል አልቻለም። ሴቶችን በመመኘት ወጥመድ ውስጥ ወደቀ። በርካታ ባዕዳን ሴቶችን አገባ። እነዚህም ሴቶች ወደ ክሕደትና ወደ ጣዖት አምልኮ መሩት። መጽሐፈ መክብብ ሰሎሞን እግዚአብሔርን በረሳ ጊዜ ስላሳለፈው የከንቱነት ኑሮ ይናገራል።

ሰላምና ብልጽግና ለሰሎሞን አደገኛ ሆነበት። እግዚአብሔርን ረሳ። በራሱ ጥበብና ብርታት ታመነ። ለራሱ ክብር የሚገደው ሰው ሆነ፤ ስለዚህ ለመንግሥቱ ከሁለት መከፈልና መውደቅ በተዘዋዋሪ መንገድ እርሱም ተጠያቂ ሆነ። የእስራኤል መንግሥት የተከፋፈለውና እስከ ዛሬ ድረስ ተመልሶ አንድ ሊሆን እስከማይችል ድረስ የተበተነው ከሰሎሞን ሞት በኋላ ወዲያውኑ ነው። የሰሎሞን ኃጢአት በዝርያዎቹ ሁሉ ላይ ከፍተኛ ችግሮችን አምጥቷል። እርሱ የጀመረው የጣዖት አምልኮ ወዲያውኑ አገሪቱን ሁሉ ችግር ውስጥ ዘፈቃት። በመጨረሻም፥ የሰሎሞን ኃጢአት የእስራኤል ሕዝብ በሙሉ ወደ ምርኮ እንዲሄዱ አደረገ።

> 6ኛ ጥያቄ፥ ሀ) ከሰሎሞን ሕይወት፥ የመሪዎች ኃጢአት በቤተ ክርስቲያን አባሎች ሁሉ ላይ ስለሚያመጣው ነገር ምን ለመማር እንችላለን? ለ) በበረከት ጊዜ ከእግዚአብሔር ስለ መራቅ ስለሚታይ አዝማሚያ ከሰሎሞን ሕይወት ታሪክ፥ የምንማረው ምንድን ነው?

ለብዙ ክርስቲያኖች፥ መንፈሳዊ ሕይወት አስቸጋሪ የሚሆነው በስደት ጊዜ ሳይሆን፥ በበረከት ጊዜ ነው። በስደት ጊዜ ክርስቲያኖች እግዚአብሔርን ሊመለከቱና በእርሱ ሊደገፉ ይገደዳሉ። በበረከትና በሰላም ጊዜ ግን እግዚአብሔርን በመርሳት፥ ፊትን ከእርሱ መልሶ ባለመታዘዝ መኖር በጣም የተለመደ ነገር ነው። ለእግዚአብሔር ከመታዘዝ ይልቅ፥ የአኗኗር ስልታችንን የማሻሻሉ ነገር የበለጠ ትኩረት የምንሰጠው ይሆናል። የቤተ ክርስቲያን መሪም ሆነ፥ ቤተ ክርስቲያን ብዙ ጊዜ በኃጢአት የሚወድቁት በበረከት ጊዜ ነው።

> 7ኛ ጥያቄ፥ 1ኛ ነገሥት 1፡11 አንብብ ሀ) ሰሎሞን በእስራኤል ላይ ንጉሥ ለመሆን የነበረበት ትግል ምንድን ነው? ለ) ሰሎሞን ያደረጋቸውን ዋና ዋና መልካም ነገሮች ዘርዝር። ሐ) ሰሎሞን ያደረጋቸውን ክፉ ተግባራት ዘርዝር። መ) በሰሎሞን አገልግሎት ውስጥ ነቢያት የነበራቸው ድርሻ ምንድን ነው?

## 1. ሰሎሞን ንጉሥ ሆነ (1ኛ ነገሥት 1-2)

ንጉሡ ዳዊት በሸመገለ ጊዜ፥ ዙፋኑን ለልጁ ለሰሎሞን የሚያስተላልፍበት ወቅት ደረሰ። ልጁ ሰሎሞን የዙፋኑ ወራሽ እንደሚሆን ዳዊት ለቤርሳቤህ ቃል ገብቶላት ነበር (1ኛ ነገ. 1፡17)። ይህ የታወቀ ነገር ይመስላል። ሰሎሞን ግን በሕይወት ያለ ትልቁ ልጅ ስላልነበረ ዙፋኑ

በተለመደው መንገድ የሚገባው ለእርሱ አልነበረም። የዳዊት ትልቁ ልጅ አምኖን ሞቶ ነበር። የሚቀጥለው ትልቁ ልጅ ዶሉሕያ (2ኛ ሳሙ. 3፡3) የሞተ ይመስላል። እንዲሁም ሦስተኛው ታላቅ ልጅ አቤሴሎምም ሞቶአል። በዚህ ጊዜ በሕይወት ያለ ትልቁ ልጅ አዶንያስ ነበር፤ ስለሆነም ከውርስ መብት አኳያ በሕይወት ያለው ታላቁ ልጅ እንደመሆኑ፥ አዶንያስ መንገሥ ነበረበት። ዳዊት ንጉሥ አድርጎ እስኪመርጠውና ይህንንም ይፋ እስኪያደርግ ከመጠበቅ ይልቅ ትልቅ ወንድሙ አቤሴሎም እንዳደረገው፥ እርሱም በኃይል ለመንገሥ ሙከራ አደረገ። ታዋቂ ለመሆንና ሕዝቡ ንጉሥ ብለው እንዲጠሩት ለማድረግ ሞከረ።

ይህንን ነገር ነቢዩ ናታን፥ ጋድና የሰሎሞን እናት ቤርሳቤህ ሲሰሙ፥ ለዳዊት ነገሩትና ሰሎሞንን በግልጥ እንዲያነግሠው ገፋፉት። ዳዊትም እንዲሁ አደረገ። በመጀመሪያ በግል፥ ቀጥሎም በሕዝቡ ሁሉ ፊት ዳዊት ሰሎሞንን አነገሠው።

ዳዊት ሰሎሞንን እግዚአብሔር በሙሴ በኩል የሰጠውን ትእዛዝ በሙሉ በጥንቃቄ እንዲጠብቅ በሚገባ አስጠነቀቀው። በተጨማሪ በሕይወት ዘመኑ በደል ያደረሱበትን ኢዮአብን፥ ሳሚን ሌሎችንም እንዲቀጣለት አዘዘው። ዳዊትም ለ40 ዓመታት ከነገሠ በኋላ ሞተ።

ሰሎሞንም ወዲያውኑ መንግሥቱን ማጠናከር ጀመረ። በመጀመሪያ፥ ወንድሙን አዶኒያስን የሚገባውን ነገር አደረገ። በመካከለኛው ምሥራቅ ባሕል፥ አንድ ልጅ ንጉሥ በሚሆንበት ጊዜ፥ ዙፋኑ ይገባናል ብለው የሚገምቱ ሰዎችን በሙሉ በመንግሥቱ ላይ ችግር እንዳይፈጥሩ ይገድላቸው ነበር። ሰሎሞን ግን ይህን አላደረገም፤ ወንድሙን አዶኒያስን ግን ምንም ዓይነት የዓመፅ ሙከራ ቢያደርግ ሕይወቱን ሊያጣ እንደሚችል አስጠነቀቀው። አዶኒያስ የሰሎሞንን ቁባቶች መጠየቁ የዓመፅ ምልክት ነበር። በጥንት ባሕል ሥልጣኑን ሁሉ ከአባቱ ለመውረሱ ምልክት ይሆን ዘንድ፥ አዲሱ ንጉሥ የቀድሞውን ንጉስ (የአባቱን) ቁባቶች ሁሉ ይወስድ ነበር፤ ስለዚህ አዶኒያስ የአባቱን ቁባቶች ሲጠይቅ ጥያቄው በዙፋኑ ላይ የመቀመጥ ጥያቄ መሆኑን ተገንዝቦ ሰሎሞን አዶኒያስን ገደለው።

በሁለተኛ ደረጃ፥ ሰሎሞን በዳዊት ላይ ዓምፆ የነበረውን ሊቀ ካህኑን አቢያታርን አስወገደ። ይህ ከብዙ ዓመታት በፊት ሊቀ ካህን የመሆኑ

መብት ከቤተሰቡ እንደሚወሰድ ለዔሊ የተነገረው ትንቢት ፍጻሜ መሆኑ ነው (1ኛ ሳሙ. 2፡27-37፤ 1ኛ ነገ. 2፡26-27)።

ሦስተኛ፥ ሰሎሞን ኢዮዓብን ለሠራው ወንጀል አስገደለው።

አራተኛ፥ ሳሚ ተገደለ።

2. የሰሎሞን ታላቅነት ማስረጃዎች (1ኛ ነገሥት 2-10)

ከዳዊት ጋር ካወዳደርነው፥ የ1ኛ ነገሥት ጸሐፊ ስለ ሰሎሞን በመናገር ያጠፋው ጊዜ በጣም አነስተኛ ነው። በእርግጥ አብዛኛው የሰሎሞን ታሪክ ከቤተ መቅደስ ሥራው ጋር የተያያዘ ነው። በጸሐፊው ዓይን ሰሎሞንን ታላቅ ያደረገው ጥበቡና ሌላው ተግባሩ ሳይሆን፥ የቤተ መቅደስ ሥራው ነው።

ሰሎሞን በነገሠ ጊዜ ዕድሜው 20 ዓመት አካባቢ ሳይሆን አይቀርም፤ ስለዚህ ይህንን ታላቅ ሕዝብ ለመምራት ችሎታ እንደሌለው ተገንዘበና ዋስትና የማጣት ስሜት ተሰማው። ምን እንደሚፈልግ እግዚአብሔር በጠየቀው ጊዜ፥ የእግዚአብሔርን ሕዝብ የሚመራበትን ጥበብ ጠየቀ (1ኛ ነገ. 3)። እግዚአብሔርም ጥበብን፥ በተጨማሪም ሀብትንና ኃይልን ሰጠው። ሰሎሞንም በምድር ላይ ከነገሡ ነገሥታት ሁሉ የሚበልጥ ታላቅ መሪ ሆነ። ከማንም የላቀ ጠቢብ ነበር። ከዳዊት ጋር ስናወዳድረው ግን በመንፈሳዊ ሕይወቱ ያነሰ ነበር። ሰሎሞን ከእግዚአብሔር ጥበብ ተሰጠው። ይህንንም ጥበብ በተለያየ መንገድ ተጠቀመበት፡-

ሀ. ከፋና ደጉን ለመለየት የሚችል ስለነበረ በጽድቅ ገዛ (1ኛ ነገ. 3፡16-28)።

ለ. መንግሥቱን በሚገባ አደራጀ። ከዚህ ጊዜ በፊት ከነበረው የነገድ አገዛዝ (አከፋፈል) ዘዴ በተለየ ሁኔታ አገሪቱን በ12 የአስተዳደር ክልሎች ከፋፈላት (1ኛ ነገሥት 4)።

ሐ. ቤተ መቅደሱን በማሠራት ረገድ 7 ዓመታት አሳለፈ (1ኛ ነገሥት 5-6)።

ከ1ኛ ነገሥት ጸሐፊ አመለካከት፥ ሰሎሞን የሠራው ከፍተኛው ነገር የቤተ መቅደሱ ሥራ ነው። የሰሎሞን ቤተ መቅደስ፥ ለብዙ መቶ ዓመታት የቆየና በመጨረሻም በ586 ዓ.ዓ. በባቢሎናውያን የተደመሰሰ ነው።

በ520 ዓ.ዓ. ሌላ ቤተ መቅደስ የተሠራ ሲሆን፥ በ70 ዓ.ዓ. ተደምስሶአል። ከዚያ በኋላ እስካሁን ድረስ እንደገና አልተሠራም። ቤተ መቅደሱ በነበረበት ስፍራ ዛሬ እጅግ የተቀደሰው ከሚባሉት መስጊዶች 2ኛ የሆነው የዓለቱ ክብ ጣራ በመባል የሚታወቀው መስጊድ ይገኛል። ለአይሁድ ይህ ስፍራ በምድር ላይ ከሚገኙ ስፍራዎች ሁሉ እጅግ የተቀደሰ ሲሆን፥ ሙስሊሞችም ደግሞ ያከብሩታል። አይሁድ ቤተ መቅደሳቸውን በዚያ ስፍራ ለመሥራት ከፍተኛ ፍላጎት ያላቸው ሲሆን፥ በርካታ የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁራን ይህ ቤተ መቅደስ ጌታ ኢየሱስ በምድር ላይ ለመግዛት ከመምጣቱ በፊት ይሠራል ብለው ያምናሉ።

የቤተ መቅደሱ መጠን ከ500 ዓመታት በፊት ከተሠራው ከመገናኛው ድንኳን በሁለት ዕጥፍ የሚበልጥ ነበር። የከርሰ-ምድር አጥኚዎች በጥንት ጊዜ ከነበሩ ሰባት አስደናቂ ነገሮች፥ አንዱ ቤተ መቅደሱ እንደነበር ስለሚናገሩ በጣም ትልቅና ያማረ ነበር። የቤተ መቅደሱ ሕንጻ ራሱ 27 ሜትር ርዝመት፥ 9 ሜትር ስፋት፥ 13.5 ሜትር ከፍታ ነበረው። በሚከተሉት ክፍሎች የተከፋፈለም ነበር:-

1. ቅድስት:- 9 ሜትር ስፋት፥ 18 ሜትር ርዝመትና 13.5 ሜትር ከፍታ ነበረው። በውስጡ አምስት የኅብስት ማቅረቢያ የወርቅ ገበታዎች ነበሩት (የመገናኛው ድንኳን አንድ ገበታ ብቻ ነበረው)፤ አምስት የወርቅ መቅረዞች- (የመገናኛው ድንኳን አንድ መቅረዝ ብቻ ነበረው)፤ እና 1 የዕጣን መሠዊያ ነበር።

2. ቅድስተ ቅዱሳን:- 9 ሜትር ስፋት፥ 9 ሜትር ከፍታና 9 ሜትር የጎን ርዝመት ነበረው። በቅድስተ ቅዱሳን ውስጥ በምድረ በዳ የተሠራውና ዳዊት ወደ ኢየሩሳሌም ያስመጣው የመጀመሪያው የቃል ኪዳን ታቦት ነበር። ክንፎቻቸውን ከግድግዳ ጫፍ እስከ ጫፍ የዘረጉ የሁለት ኪሩቦች ምስል የሚታይ ሲሆን፥ ታቦቱ ከክንፎቻቸው በታች በመሀል ነበር።

3. የካህናት አደባባይ:- ከቤተ መቅደሱ ሕንጻ ወጣ ብሎ የሚገኝ ነበር። 45 ሜትር ስፋትና 90 ሜትር ርዝመት ነበረው። በዚህ ክልል ውስጥ ስፋቱ 9 ካሬ ሜትር ሆኖ 4.5 ሜትር ከፍታ ያለው የሚቃጠል መሥዋዕት ማቅረቢያ ነበር። በተጨማሪ 2.5 ሜትር ከፍታና ዙሪያው 5 ሜትር የሆነ አንድ ትልቅ የነሐስ መታጠቢያ እንዲሁም ሁለት ሜትር ከፍታ ያላቸው 10 ትናንሽ ተንቀሳቃሽ የነሐስ

መታጠቢያዎች ነበሩ፤ ደግሞም ንጉሡ ለሕዝቡ ንግግር የሚያደርግበት አንድ ትልቅ የነሐስ መድረክ ነበር።

4. የውጪው አደባባይ፦ ይህ አደባባይ ማንኛውም ተራ ሕዝብ ለአምልኮ የሚሰባሰብበት ቦታ ነበር። 90 ሜትር ስፋትና 180 ሜትር ርዝመት ነበረው። ይህ ክፍል አራት በሮች ባሉት የግንብ አጥር የታጠረ ነበር።

** ወደ ትምህርት 8 ተመልሰህ የመገናኛውን ድንኳንና የቤተ መቅደሱን መሠረታዊ ቅርፁን ለመረዳት የቀረበውን ሥዕል ተመልከት።

ቤተ መቅደሱን የሠሩት ዋናዎቹ የሕንጻ መሐንዲሶች በፎኒሺያ ከምትገኘው በዓለም አቀፍ የባሕር ንግድና ጥበብዋ ከታወቀችው ከጢሮስ ስለነበሩ፥ የኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ በፎኒሺያ ከሚገኙ ቤተ መቅደሶች ጋር ተመሳሳይ እንደሆነ በርካታ ምሁራን ይስማማሉ።

የቤተ መቅደሱ ሥራ እንዳለቀ፥ እግዚአብሔር ሥራውን መቀበሉንና መቅደሱን ማደሪያው ለማድረግ መስማማቱን ለማረጋገጥ፥ ቤተ መቅደሱን በክብሩ ደመና ሞላው።

የሰሎሞን ጸሎት የእግዚአብሔርን ባሕርይ በጥልቀት መረዳቱን ያሳያል። በሰሎሞን ዘመን ሰዎች አማልክት በአንድ በተወሰነ ስፍራ (ቤተ መቅደስ) የሚገኙ ናቸው ብለው ያምኑ ነበር፤ ሰሎሞን ግን እግዚአብሔር ከቤተ መቅደስ የላቀ መሆኑን ያውቅ ነበር። በእርግጥ ከሰማያትም ሁሉ የላቀ ነበር (1ኛ ነገ. 8፡27)። እግዚአብሔር እንደ እኛ በቦታ የተወሰነ አይደለም። እርሱ በአንድ ጊዜ በሁሉም ስፍራ መገኘት ይችላል፤ ነገር ግን በአንድ በተወሰነ መንገድ እግዚአብሔር በልዩ ሁኔታ በቤተ መቅደስ እንደሚሆንም ያምን ነበር። የሰሎሞን ጸሎት የእግዚአብሔርን ይቅርታና ጸጋ ለኃጢአተኛው ሕዝብ የጠየቀበት አስደናቂ ጸሎት ነበር።

8ኛ ጥያቄ፥ ሀ) ብዙ ክርስቲያኖች ዛሬም እግዚአብሔር በቤተ ክርስቲያን ሕንጻ ውስጥ ይኖራል ብለው የሚያስቡት እንዴት ነው? ለ) ዛሬ በተለየ መንገድ እግዚአብሔር ማደሪያ ያደረገው ምንን ነው? (1ኛ ቆሮ. 6፡19 ተመልከት) ሐ) ይህ እውነት ለቤተ ክርስቲያን ሕንጻ ትኩረት ስለ መስጠት አስፈላጊነት ምን ያስተምረናል?

አንዳንድ ክርስቲያኖች ዛሬ እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያንን የሚያየው እንደ ሰሎሞን ቤተ መቅደስ ነው በማለት የተሳሳተ አሳብ ያቀርባሉ። እግዚአብሔር በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ስለሚኖር፥ ስፍራው ከሌሎች ስፍራዎች ይልቅ የተቀደሰ ነው ብለው ያስባሉ። ይህ የቤተ ክርስቲያንን ምንነት በተሳሳተ መንገድ መረዳት ነው። ዛሬ እግዚአብሔር የሚያድረው በሕንጻዎች ውስጥ ሳይሆን በሰዎች ውስጥ ነው (1ኛ ቆሮ. 6፡19)። እውነተኞዎቹ ቤተ ክርስቲያኖች ሰዎች ናቸው እንጂ ሕንጻው አይደለም። በአዲስ ኪዳን፥ ቤተ ክርስቲያን የሚለው ቃል በኢየሱስ ለሚያምኑ ሰዎች ኅብረት እንጂ አንድም ጊዜ እንኳ ለሕንጻ አልተሰጠም። እግዚአብሔር ቤተ መቅደሴ ሕንጻ ሳይሆን በሰዎች ልብ ነው ብሏል።

በቤተ መቅደሱ ሥራ ታሪክ መካከል፥ ሰሎሞን ለራሱ ስለሠራው የቤተ መንግሥት ሕንጻ ሥራ ጥቂት ነገር ተጠቅሷል። የዚህ መጽሐፍ ጸሐፊ ሰሎሞን ለራሱ ስለሠራው ቤተ መንግሥት በቀጥታ ባያወግዘውም እንኳ፥ ብዙ እንዳልተደሰተበት ግልጽ ነው። ሰሎሞን ቤተ መቅደሱን ለመሥራት የወሰደበት ጊዜ 7 ዓመት ሲሆን፥ የራሱን ቤተ መንግሥት ለመሥራት ግን 13 ዓመት አጥፍቷል። ይህም ሰሎሞን ቅድሚያ የሰጠው ነገር የተሳሳተ እንደነበር ያሳየናል። ከእግዚአብሔር መኖሪያ ይልቅ ለራሱ መኖሪያ ገዶት ነበር።

---

9ኛ ጥያቄ፥ በአሁኑ ጊዜ አንዳንድ ክርስቲያኖችም ይህንኑ በሚመለከት የተሳሳተ ቅድሚያ የሚሰጡት እንዴት ነው?

---

ከጸሎቱ በኋላ እግዚአብሔር ለሰሎሞን ተገለጠና ባረከው፤ ነገር ግን ከትእዛዛቱ ፈቀቅ እንዳይልም አስጠነቀቀው። አለበለዚያ እግዚአብሔር ቤተ መቅደሱንም እንደማይቀበልና እንደሚያጠፋው ነገረው። በኋላ የተፈጸመው ነገር ልክ እንደዚሁ ነበር። በሕዝቅኤል ዘመን የእግዚአብሔር ክብር ቤተ መቅደሱን ለቅቆ ሄደ (ሕዝ. 10)። እስራኤላውያን ለእግዚአብሔር ስላልታዘዙ፥ ባቢሎናውያን ቤተ መቅደሱን ደመሰሱት።

መ. የንግሥተ ሳባ ጉብኝት የሰሎሞን ታላቅነት ምልክት (1ኛ ነገ. 10) ኢትዮጵያውያን ስለ ንግሥት ሳባና ስለ ምኒልክ አስደናቂ የሆነ ታሪክ ቢኖራቸውም፥ ሳባውያን በአሁኒቱ ኢትዮጵያ የነበሩ ሰዎች ለመሆናቸው ታሪካዊም ሆነ የከርሰ ምድር መረጃው በጣም ጥቂት ነው። በተጨማሪም የንግሥተ ሳባና የሰሎሞን ልጅ የኢትዮጵያ ንጉሥ ስለመሆኑና የቃል ኪዳኑን ታቦት ሰርቆ

ስለማምጣቱ የሚቀርብ መረጃ የለም። ይልቁንም በርካታ የክርስ ምድር አጥኚዎች ሳባ በደቡብ ምዕራብ ዓረቢያ በየመን አካባቢ የምትገኝ አገር ናት ብለው ያምናሉ።

የንግሥት ሳባ ታሪክ ዓላማ፥ የሰሎሞን ዝና በዓለም ሁሉ እንዴት ተሰራጭቶ እንደ ነበር ለማሳየት ነው። ሰሎሞን በጥበቡ፥ ለእስራኤል ባስገኘው ብልጽግናና ከፍተኛ ሕንጻዎችን በመገንባቱ ዝናን አትርፎ ነበር።

3. የሰሎሞን ውድቀት (1ኛ ነገሥት 11)

ሰሎሞን በዓለም ዘንድ ምንም ያህል ጥበበኛ ይሁን፥ በእግዚአብሔር ዓይን ግን ጥበበኛ አልነበረም። ሰሎሞን በወጣትነቱ ዘመን «የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት ነው» (ምሳ. 1፡7) ሲል ጽፎ ነበር። ይህንን ሲል እውነተኛ ጥበብ የሚመጣው ከእግዚአብሔር ዘንድ እንደሆነና የሚገለጠውም ለእግዚአብሔር ወደመታዘዝ በሚያመራው በፈሪሃ እግዚአብሔርነት ነው ማለት ነበር። የሚያሳዝነው ግን ሰሎሞን በሽመገለ ጊዜ ይህንን አልተከተለም። ይልቁንም እግዚአብሔርን ረሳ፤ የእስራኤልን አምልኮ አበላሸ፤ ለእስራኤል መንግሥት መከፈል ዋና ምክንያት ሆነ። 1ኛ ነገሥት 11 የሚያተኩረው በእግዚአብሔር ፊት ክፉ ስለነበረው፥ ሰሎሞን ስላደረገውና በኋላም ዘሩ አድጎ የእስራኤልን ሕዝብ ስላጠፋው ኃጢአት ነው። የእስራኤል ሕዝብ ከሕደት እስኪጠፉና ወደ ምርኮ እስኪሄዱ ድረስ የቀጠለው ሥሩን ከሰሎሞን በማቆጥቆጥ ነው።

ሰሎሞንን ወደ ጥፋት የመሩትን የሚከተሉትን ነገሮች ተመልከት፡-

ሀ. ሰሎሞን ብዙ ሴቶችን አገባ። የአብዛኛው ጋብቻ ዓላማ ከሌሎች ሕዝቦች ጋር የፖለቲካ ስምምነት ለማድረግ ነበር። መጽሐፍ ቅዱስ ለሰሎሞን 700 ሚስቶችና 300 ቁባቶች እንደነበሩት ይናገራል። ሰሎሞን ይህንን ያደረገው ምናልባት ታላቅነቱን ለዓለም ለማሳየት ሊሆን ይችላል፤ ዳሩ ግን በምንም መንገድ ቢሆን የእግዚአብሔርን ሕግ በቀጥታ የጣሰ ነበር። (ዘዳ. 17፡17 ተመልከት)። በጥንት ዘመን ነገሥታት በመካከላቸው የሚያደርጉትን ስምምነት ወንዶችና ሴቶች ልጆቻቸውን ለጋብቻ በመለዋወጥ ያጸኑ ነበር። ሰሎሞን በርካታ ሚስቶች ያገባበት ምክንያት ይህ ለመሆኑ አንዳችም ጥርጥር የለም።

ለ. አብዛኛዎቹ ሚስቶቹ የተሳሰተ አማልክትንና ጣዖቶችን የሚያመልኩ አሕዛብ ስለነበሩ፥ ሰሎሞን ለሚስቶቹ በኢየሩሳሌም ውስጥ የሐሰት አምልኮ የሚያካሂዱበትን ስፍራ እንዲኖራቸው ፈቀደላቸው (1ኛ ነገ. 11፡7-8)። ቀጥሎም ከእነርሱ ጋር እነዚህን የሐሰት አማልክት ማምለክ ጀመረ። ሰሎሞን ዛሬም ብዙ ክርስቲያኖች በሚጠመዱበት ወጥመድ ተያዘ። ሚስቶቻቸውን ወይም ቤተሰቦቻቸውን ለማስደሰት፥ ሰዎች እውነተኛውን አምላክና ሐሰተኛ አማልክትን ወይም የቀድሞ ሃይማኖታቸውን በአንድነት ያመልካሉ። ሰሎሞን ከኢየሩሳሌም ውጭ የገነባቸው የሐሰተኛ አማልክት ማምለኪያ ስፍራዎችን ኢዮስያስ እስኪያስወግዳቸው ድረስ ለ350 ዓመታት ቆዩ (2ኛ ነገ. 23፡13 ተመልከት)።

---

10ኛ ጥያቄ፥ ሀ) ይህ ነገር በአንዳንድ ክርስቲያኖች ሲፈጸም ያየኸው ነው? ለ) ስሕተት የሆነውስ ለምንድን ነው? ሐ) ሰሎሞን ሚስቶቹን ለማስደሰት ብሉ ጣዖትን ከማምለኩ ምን ልንማር እንችላለን?

---

ሐ. ሰሎሞን የአስተዳደር አሠራሩን በከፍተኛ ደረጃ ወደ ውስብስብ ሁኔታ አደረሰው። የመንግሥት ሠራተኞች እጅግ ብዙ ከመሆናቸው የተነሣ፥ በሰሎሞን መንግሥት ውስጥ ያሉ የአስተዳደር ሰዎችንና የተለያዩ ሥራዎችን ሕዝቡ ሊደግፍ ከማይችልበት ደረጃ ደረሰ።

መ. ሰሎሞን በአንድ ጊዜ ከመጠን በላይ የሆነ ነገሮችን ለመሥራት ሞከረ። አገሪቱ ቀስ በቀስ እንድታድግ ከማድረግ ይልቅ በርካታ ትላልቅ ከተሞችን በአንድ ጊዜ ሠራ። ይህም ነገር ሕዝቡ የመንግሥት ባሪያ እንዲሆን አደረገው። በምድሪቱ በሚኖሩ ሰዎች ሁሉ ላይ የኑሮ ጫና ፈጠረባቸው። ሕዝቡ እጅግ የጠሉት ነገር ይህ ነበር። ለዚህ ነው ከሰሎሞን ሞት በኋላ ስለ ግብርና ለመንግሥት በመሥራት ረጅም ጊዜ ስለማጥፋት ያጉረመረሙት።

ሠ. ሰሎሞን ዓለም አቀፍ ንግድንና ግንኙነትን ከፍ ለማድረግ ስለሞከረ፥ ከእርሱ ጋር ግንኙነት ያደርጉ በነበሩ አሕዛብ መንግሥታት ፍልስፍናና የሃይማኖት ተጽዕኖ ሥር ወደቀ። ይህም እስራኤል ዓለም አቀፍ ስምምነት እንዲያደርጉ እግዚአብሔር

ከሰጣቸው ማስጠንቀቂያ ጋር በቀጥታ የሚፃረር ነበር (ዘጸ. 34፡12-15፤ ዘዳ. 7፡2)።

በሰሎሞን ዘመነ መንግሥት መጨረሻ አካባቢ መንግሥቱ መውደቅ ጀመረ። እግዚአብሔር ግን ለአባቱ ለዳዊት በነበረው ፍቅር ምክንያት፥ በእርሱ የሕይወት ዘመን መንግሥቱ እንደማትከፈል ቃል ገብቶለት ነበር። እግዚአብሔር ግን በሰሎሞን ላይ ፍርድን አመጣ።

1. እግዚአብሔር መንግሥቱ ለሁለት እንደምትከፈል ተናገረ። ነቢዩ አኪያ የመንግሥቱን መከፈል የሚመለከት መልእክት ተናገረ። አሥሩ ነገዶች እስራኤል ሲባሉ፥ ሁለቱ የደቡብ ነገዶች የይሁዳ መንግሥት እየተባሉ ይጠራሉ። እግዚአብሔር አሥሩን የእስራኤል ነገዶች ከዳዊት ዘር ላልሆነው ለኢዮርብዓም ሰጣቸው፤ ነገር ግን እግዚአብሔር ለዳዊት ከነበረው ፍቅር የተነሣ የይሁዳን ሁለት ነገዶች (ይሁዳና ብንያምን) በዳዊት ልጆች አመራር ሥር እንዲቆዩ አደረገ።

2. የሰሎሞን መንግሥት በተለያዩ ዓመፆች መፈረካከስ ጀመረ።

   ሀ. ከሰሎሞን አስተዳዳሪዎች አንዱ የነበረው ኢዮርብዓም፡- በሰሎሞን ላይ ዓምፆ ወደ ግብፅ ኮበለለ።

   ለ. የኤዶም መንግሥት በሰሎሞን ላይ ዓመፀ።

ግብፅ ለኢዮርብዓምና በሃዳድ መጠለያ በመስጠት ይህንን ዓመፅ እንዴት እንዳበረታታችና እንደደገፈች መመልከት የሚገርም ነው።

> 11ኛ ጥያቄ፥ ሀ) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እንደመሆናችን መጠን እንዴት መምራት እንዳለብን፥ ከሰሎሞን ሕይወት የምንማራቸውን ትምህርቶች ዘርዝር። ለ) ልንከተላቸው የሚገቡን መልካም ነገሮች የትኞቹ ናቸው? ሐ) ወደ ሕይወታችን እንዳይገቡ ልንከላከላቸው የሚገባን ነገሮች የትኞቹ ናቸው?

አብዛኛዎቹን የብሉይ ኪዳን የጥበብ መጻሕፍት እንዲጽፍ እግዚአብሔር ሰሎሞንን ተጠቅሞበታል። እነዚህን በሚቀጥለው የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ጥናት እንመለከታቸዋለን። ብዙ ምሁራን ሰሎሞን መጽሐፈ ምሳሌን የጻፈው ወጣት በነበረና ከጌታ ጋር በመልካም አካሄድ በነበረው ጊዜ ነው ይላሉ። መጽሐፈ መክብብን ደግሞ የጻፈው በሕይወቱ መጨረሻ አካባቢ ከእግዚአብሔር ርቆ የመኖርን መራራነት ከተለማመደ

በኋላ ነው። መኃልየ መኃልይ ዘሰሎሞን ደግሞ ምናልባት ሰሎሞን ከሚስቶቹ መካከል አንዷን እንዴት እንዳገባ የሚገልጥ የግጥምና የፍቅር መጽሐፍ ይሆናል ብለው ያስባሉ።

12ኛ ጥያቄ፥ 1ኛ ቆሮ. 9፡24-27 አንብብ። ጳውሎስ በሕይወቱ ለራሱ ይፈራው የነበረው ነገር በሰሎሞን ሕይወት ውስጥ የተፈጸመው እንዴት ነው? (ቁ. 27)። ጳውሎስ ከነበረው ታላላቅ ፍርሃቶች አንዱ፥ በዕድሜ በገፋ ጊዜ ለብዙዎች ከሰበከና ብዙዎችን ለክርስቶስ ከማረከ በኋላ እርሱ እንዳይወድቅና ለክርስቶስ የማይጠቅም የተጣለ እንዳይሆን ነበር፤ ስለዚህ ሕይወቱን አጥብቆ ሊቆጣጠር ወሰነ። በክርስትና ሕይወትም ሆነ በቤተ ክርስቲያን አመራር ዋናው ነገር መልካም ጅማሬ ሳይሆን ያማረ ፍጻሜ ነው። ሰሎሞን በመልካም ጀመረ፤ ነገር ግን በከፋ ሁኔታ ጨረሰ። ብዙ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እንደ ሰሎሞን ናቸው። አጀማመራቸው መልካም ነው። ዕድሜያቸው በገፋ ጊዜ ግን ከመንገዳቸው ፈቀቅ ይሉና ለቤተ ክርስቲያን የማይጠቅሙ ብቻ ሳይሆን የሚጎዱዋትም ይሆናሉ።

## 3ኛ ቀን:- 1ኛ ነገሥት 12-16

የአንድ መሪ መንፈሳዊ ሕይወት በአጠቃላይ በሰዎች መንፈሳዊ ሕይወት ላይ ታላቅ ተጽዕኖ እንደሚያሳድር ተመልክተናል። ብዙ ጊዜ መሪው ለእግዚአብሔር ታዛዥ በሚሆንበትና ራሱን ለእግዚአብሔር ሙሉ በሙሉ አሳልፎ በሚሰጥበት ጊዜ፥ ሕዝቡም ለእግዚአብሔር ራሱን አሳልፎ በመስጠት ታዛዥ ይሆናል። መሪው ለእግዚአብሔር በሙላት በማይታዘዝበት ጊዜ፥ ሕዝቡን ከእውነት በቀላሉ ያርቀዋል። 1ኛና 2ኛ ነገሥትን በምናነብበት ጊዜ፥ የእስራኤልና የይሁዳ ነገሥታት የሕዝቡን መንፈሳዊ ሕይወት በከፍተኛ ደረጃ እንዴት እንደነኩት እንመለከታለን።

የምንኖርበት ዘመን በርካታ ስጦታ ያላቸው የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ወይም ሰባኪዎች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚሠሩበት ዘመን ነው። ራሳቸውን ለእግዚአብሔር በሰጡት ጥቂቶች፥ እግዚአብሔር በከፍተኛ ሁኔታ ይጠቀምባቸዋል። ለራሳቸው ጥቅም በስግብግብነት የሚሠሩና ብዙዎችን የሚያስኮበልሉም አሉ። ጳውሎስ ለእግዚአብሔር መንጋ የማይራሩ «ጨካኝ ተኩላዎች» እንደሚነሡ አስጠንቅቋል። እንዲያውም እነዚህ ሐሰተኛ አስተማሪዎች የሚነሡት ከቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንደሆነ ተናግሯል (የሐዋ. 20፡29-30 ተመልከት)። በዚህ ዘመን በርካታ ሐሰተኛ አስተማሪዎችና መሪዎች ስላሉ፥ የእውነትን መንገድ ለመከተል

ራሳችንን የሰጠን ሰዎች፥ የራሳችንና የመንጋችንን ሕይወት ከጥፋትና ከኩብለላ መጠበቅ አለብን። በዚህ ዘመን የቤተ ክርስቲያን መሪዎች መሥራት ከሚገባቸው ዋና ዋና ሥራዎች አንዱ ምዕመናን በስሕተት ትምህርት እንዳይወድቁ መጠበቅ ነው። ይህንን ለማድረግ ግን መንፈሳዊ ሕይወታችን መንጋው ክርስቶስን ለመከተል የሚችልበትን መልካም ምሳሌነት የሚያሳይ እንዲሆን እርግጠኞች መሆን አለብን። የሐሰት አስተማሪዎች በቤተ ክርስቲያኖቻችን ያሉትን ምዕመናን እምነት ለማጥፋት እንዳይችሉ፥የመሪዎች ሕይወት የሚጫወተው ሚና ከፍተኛ ነው።

| |
|---|
| 13ኛ ጥያቄ፥ ሀ) አንድ መሪ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሕይወቱ መልካም ተጽዕኖ የሚያሳድረው እንዴት ነው? ለ) ይህ በቤተ ክርስቲያንህ እንዴት እንደተፈጸመ መግለጫ ስጥ። ሐ) አንድ የቤተ ክርስቲያን መሪ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሕይወቱ ከፍተኛ የከፋት ተጽዕኖ ሊያደርግ የሚችለው እንዴት ነው? መ) ይህ ነገር በቤተ ክርስቲያንህ እንዴት እንደተፈጸመ መግለጫ ስጥ። |
| 14ኛ ጥያቄ፥ 1ኛ ነገሥት 12-16 አንብብ። ሀ) በእነዚህ ዓመታት ውስጥ ያገለገሉ ነገሥታትን ዘርዝር። ለ) ከየትኛው መንግሥት እንደነበሩ ጥቀስ። ሐ) ምን ዓይነት መንፈሳዊ ባሕርይ እንደነበራቸውም ጥቀስ። መ) በነገሡበት ዘመን የተፈጸሙትን ጠቃሚ ነገሮች ዘርዝር። |

1. ሮብዓም፡- የይሁዳ ንጉሥ (931-913 ዓ.ዓ.)

አባቱ ሰሎሞን ከሞተ በኋላ ሮብዓም በእስራኤል ሁሉ ላይ ነገሠ። የእስራኤል ሕዝብ ሊያነግሡት በመጡ ጊዜ አንድ ቅድመ ሁኔታ ጠየቁት። ያለባቸውን የሥራ ጫናና ግብር ቢቀንስላቸው እንደሚያነግሡት ቃል ገቡለት። ይህንን ባያደርግ ግን እንደሚያምፁበት አስታወቁት።

ሮብዓምም በዕድሜ የገፉትን ሰዎች ምክር ሳይሆን፥ የወጣቶቹን ምክር ስለሰማ ቀንበራቸውን የባሰ እንደሚያከብድባቸው ነገራቸው። በዚህ

ጊዜ አሥሩ ነገዶች ዓመፁበትና ቀዳማዊ ኢዮርብዓምን ንጉሣቸው ይሆን ዘንድ መረጡት። የይሁዳና የብንያም ነገዶች ግን ከሮብዓምና ከዳዊት ሥርወ መንግሥት ከመጡ ነገሥታት ጋር ቆዩ።

በሮብዓም ዘመነ መንግሥት፥ የእስራኤል ሕዝብ በሁለት ታላላቅ መንግሥታት ተከፈለ። የመጀመሪያው፥ አሥሩን ነገዶች የያዘው የሰሜኑ መንግሥት ሲሆን፥ እስራኤል ተብሎ ተጠራ። አንዳንድ ጊዜ ኤፍሬም ተብሎም ይጠራል። ከሰሜኑ ክፍል የሚበዛው የኤፍሬም ነገድ ነበርና። በነቢያት መጻሕፍት በኋላ ዋና ከተማቸው ባደረጉት በሰማርያ ስምም ይጠራል። የነቢያትን መጽሐፍ በምናነብበት ጊዜ፥ የእስራኤልን ስም ስናገኝ ያ ቃል የሚናገረው በአጠቃላይ ለእስራኤል ይሁን ወይም ለሰሜኑ የእስራኤል መንግሥት መወሰን በጣም አስፈላጊ ነው።

ሁለተኛ፥ የደቡብ መንግሥት ደግሞ ይሁዳ ተብሎ ተጠራ፥ አንዳንድ ጊዜ የዚህ መንግሥት ዋና ከተማ በሆነችው በኢየሩሳሌም ስምም ይጠራል። የብንያም ነገዶችም ከይሁዳ ጋር ነበሩ።

እስራኤልና ይሁዳ በተከፋፈሉ ጊዜ ብዙዎች ካህናትና ሌዋውያን እንደዚሁም እግዚአብሔርን የሚፈሩ ሌሎችም ሰዎች ከእስራኤል ወደ ይሁዳ ተሰደዱ።

በሮብዓም ዘመን በእስራኤልና በይሁዳ መካከል ብዙ ጊዜ ጦርነት ይካሄድ ነበር። በመጀመሪያ ሮብዓም የጌታን መንገድ ተከተለ። መንግሥቱ የበለጠ በጸናች ጊዜ ግን በእግዚአብሔር ላይ ዓመፀና በመንግሥቱ ውስጥ የጣዖት አምልኮ እንዲንሰራፋ አደረገ። ውጤቱም እግዚአብሔር ግብፃውያን እንዲመጡና እንዲወጉት፥ ከከተሞቻቸውም አብዛኛውን ከይሁዳ መንግሥት እንዲወስዱ ማድረጉ ነበር። በሮብዓም ዘመነ መንግሥት የደቡብ መንግሥት ኃይል ቀስ በቀስ እየቀነሰ ሄደ።

## 2. ቀዳማዊ ኢዮርብዓም የእስራኤል ንጉሥ (931-910 ዓ.ዓ.)

የሰሎሞን አስተዳዳሪዎች ከነበሩ ሰዎች መካከል አንዱ የሆነው ኢዮርብዓም የሰሜኑ መንግሥት ንጉሥ ይሆን ዘንድ በአሥሩ ነገዶች ተመረጠ። ለእግዚአብሔር፥ የሚታዘዝ ከሆነ ከእርሱ ጋር ቃል ኪዳን እንደሚያደርግ እግዚአብሔር ለኢዮርብዓም ነገረው (1ኛ ነገ. 11፡38)። ኢዮርብዓም ግን ይህንን ሥልጣን እንደጨበጠ ወዲያውኑ በእግዚአብሔር ላይ ዓመፀ። በሰሜኑ የእስራኤል መንግሥት ውስጥ የሚገኙ ሰዎች ወደ

ኢየሩሳሌም በመሄድ እግዚአብሔርን እንዳያመልኩ፥ ኢዮርብዓም ሁለት የማምለኪያ ማዕከሎችን አሠራ፤ ከእነዚህም አንዱ በስተሰሜን የሚገኘው ዳን የሚባለው ስፍራ ሲሆን፥ ሌላኛው ደግሞ በስተደቡብ ቤቴል ተብሎ የሚጠራው ስፍራ ነው። በሁለቱም ማዕከሎች ሕዝቡ የሚያመልኩትን የጥጃ ምስል ሠራላቸው። በዚህም ኢዮርብዓም ሕዝቡን ወደ ጣዖት አምልኮ መራቸው።

እስራኤላውያን በምድረ በዳ የጥጃ ምስል እንዳመለኩ ታስታውሳለህ። ይህ የጥጃ ምስል አምልኮ ከግብፅ የመጣ ነው። ይህ አፒስ የሚባለው ለእንስሳት፥ ለሰዎችና ለእርሻ ጭምር ሕይወትን፥ ጤንነትን፥ ብርታትንና ፍሬያማነትን ይሰጣል ተብሎ የሚታሰበው አምላክ (ጣዖት) ምስል ነበር። አንዳንድ ምሁራን ኢዮርብዓም የግብፃውያንን አምልኮ ከከነዓናዊያን ጥጃን ከማምለክ ጋር ቀላቅሎአል ይላሉ። የኢዮርብዓም ፍላጎት ሕዝቡ ለአምልኮ ወደ ኢየሩሳሌም ከሚሄዱ ይልቅ፥ በዚህ ስፍራ ጣዖትን በመሥራት የእግዚአብሔር ምልክት ብቻ እንዲሆንና ሕዝቡ እግዚአብሔርን እንዲያመልኩ ቢሆንም፥ እነዚህ የጥጃ ምስሎች ወዲያውኑ ጣዖት ሆነው መመለክ ጀመሩ። በኋላም ከባዓል አምልኮ ጋር ተቀይጦ፥ ሰዎች በመሥዋዕትነት የሚቀርቡበት ቦታ ሆነ (2ኛ ነገ. 17፡ 15-17)።

ኢዮርብዓም ይህንን ባደረገ ጊዜ እግዚአብሔር ነቢይ ላከና እንዲገሥጸውና መንግሥቱም ለረጅም ጊዜ እንደማትቆይ እንዲነግረው አደረገ። መሠዊያው እንደሚረከስ የተነገረው ትንቢትም ከ300 ዓመታት በኋላ በኢዮስያስ ተፈጸመ (2ኛ ነገ. 23፡ 15-20 ተመልከት)።

| |
|---|
| 15ኛ ጥያቄ፥ ይህ ትንቢትና ፍጻሜው ስለ እግዚአብሔር ቃል ኃይል ምን ያስተምረናል? |

ከይሁዳ የሆነው የዚህ ያልታወቀ ነቢይ ታሪክ በጣም አሳዛኝ ነው። እግዚአብሔርን ከመስማት ይልቅ ሌላውን ነቢይ ሰማና ስላለመታዘዙ ሞተ፤ ስለዚህ በአልታወቀ ነቢይ ላይ የደረሰው ነገር ኢዮርብዓምንና የእግዚአብሔርን ሕዝብ በሙሉ፥ ለእግዚአብሔር ቃል በጥንቃቄ ስለ መታዘዝ አስፈላጊነት አስተምሯል።

3. የይሁዳ ንጉሥ አቢያ (913-910 ዓ.ዓ.)

አቢያ የነገሠው ለሦስት ዓመታት ብቻ ነበር። ልክ እንደ አባቱ እንደ ሮብዓም በእግዚአብሔር ፊት ክፉ ነገርን አደረገ። የጣዖት አምልኮ እንዲስፋፋ ፈቀደ።

በእነዚህ ሦስት ዓመታት በእስራኤል ከነገሠው ከቀዳማዊ ኢዮርብዓም ጋር ከፍተኛ ጦርነት አካሂዷል። አቢያ አንዳንዶቹን የእስራኤል ግዛቶች በጦርነት ለመያዝ ችሎ ነበር።

4. የይሁዳ ንጉሥ አሳ (910-869 ዓ.ዓ.)

በይሁዳ ከነገሡ ነገሥታት መካከል መልካም ከነበሩት አንዱ ነው። አባቱና አያቱ የሠሩትን ክፉ ነገር ሁሉ ከአገሪቱ ለማስወገድ ሞከረ። እግዚአብሔርን የሚፈራ ሰው እንደ መሆኑ መጠን የባዕድ አምልኮ መሠዊያዎችን አፈራረሰ። ጣዖታትን ሁሉ ነቃቅሎ ጣለ። የጣዖት አምልኮ የሚፈጸምባቸውን ከፍተኛ ስፍራዎች ሁሉ አጠፋ። ሕዝቡንም ለሙሴ ሕግ እንዲታዘዙ ነገራቸው። በይሁዳ ምድር መንፈሳዊ መነቃቃት ስለነበረ፥ በእስራኤል ያሉ እግዚአብሔርን በታማኝነት ያመልኩ የነበሩ ሰዎች ወደ ይሁዳ ምድር መጡ።

አሳ ያስተዳድር በነበረባቸው በመጀመሪያዎቹ አሥር ዓመታት ፍጹም ሰላም ነበር። በዚህ ጊዜ የይሁዳ ከተሞችንና ጦሩን አደራጀ፤ ነገር ግን ከእስራኤል ጋር በተደረገው ጦርነት የእስራኤል ንጉሥ አሳን ድል ለማድረግና አንዳንድ ከተሞችን ከይሁዳ መንግሥት ለመውሰድ ቻለ። ከኢየሩሳሌም 8 ኪሎ ሜትር በስተ ሰሜን ርቃ የምትገኘውን የራማ ከተማን ለመውሰድም በቃ። ይህንን ያደረገበት አንዱ ምክንያት የእስራኤል ሰዎች እግዚአብሔርን ለማምለክ ወደ ይሁዳ እንዳይሄዱ ነበር። አሳ በእስራኤል በተጠቃበት ጊዜ የሶርያን እርዳታ ጠየቀና በአንድነት እስራኤልን አጥቅተው ከይሁዳ እንዲወጡ አደረጉ።

የሚያሳዝነው በዘመነ መንግሥቱ መጨረሻ አሳ ፊቱን ከእግዚአብሔር መለሰ። እንዲያውም በሶርያ ላይ መደገፉን በመቃወም ስለተናገረው የእግዚአብሔር ነቢይ የነበረውን አናኒን አሰረው (1ኛ ዜና 16፡7-10 )።

5.የእስራኤል ንጉሥ ናዳብ (910-909 ዓ.ዓ.)

የቀዳማዊው ኢዮርብዓም ልጅ የነበረው ናዳብ በሰሜኑ መንግሥት ላይ ለመንገሥ የቻለው ሁለት ዓመት ብቻ ነበር። ልክ እንደ አባቱ ክፉ

መሪ ነበር። ባኦስ ገደለውና ልክ ነብዩ እንደተነበየው መንግሥቱ ከቀዳማዊ ኢዮርብዓም ቤት ተወሰደ (1ኛ ነገ. 14)።

6. የእስራኤል ንጉሥ ባኦስ (909-886 ዓ.ዓ.)

ናዳብን ገድሎ በእስራኤል ላይ የነገሠ ሰው ነበር። በመጀመሪያ የወሰደው እርምጃ በእግዚአብሔር ላይ ባገኘው የንጉሥነት ሥልጣን ላይ ችግር ይፈጥሩብኛል ብሎ ያሰባቸውን የኢዮርብዓምን ዝርያዎች ሁሉ መፍጀት ነበር።

ባኦስ ከይሁዳ ጋር የተዋጋ መሪ ሲሆን፥ ሶርያ ከሰሜን መጥታ እስከትዋጋው ድረስ ተሳክቶለት ነበር። ባኦስ ክፉ ነበርና በቀዳማዊ ኢዮርብዓም የተጀመረው የጣዖት አምልኮ እንዲቀጥል ስላደረገ፥ እግዚአብሔር መንግሥቱን እንደሚወስድበት ተናገረው።

7. የእስራኤል ንጉሥ ኤላ (886-885 ዓ.ዓ.)

የባኦስ ልጅ ኤላ በእስራኤል ላይ የነገሠው ለሁለት ዓመታት ብቻ ሲሆን፥ የእኩሌቶቹ ሰረገሎች አለቃ በሆነው በዘምሪ ተገደለ። በኤላ ሞት የባኦስ ቤተሰብ ነቢዩ ኢዩ በተናገረው መሠረት ተደመሰሰ (1ኛ ነገ. 16፡ 1-4)።

8. የእስራኤል ንጉሥ ዘምሪ (885 ዓ.ዓ.)

ዘምሪ የተባለው ሰው በኃላፊነት ለሰባት ቀናት ብቻ ነገሠና የጦሩ አዛዥ በነበረው በዘንበሪ ተገደለ።

9. የእስራኤል ንጉሥ ዘንበሪ (885-874 ዓ.ዓ.)

ስለ ዘንበሪ አገዛዝ በመጽሐፍ ቅዱስ ብዙ የተነገረን ነገር ባይኖርም፥ ከእስራኤል ታላላቅ ነገሥታት አንዱ እንደነበር በዓለም ታሪክ ተጽፎ እንመለከታለን። ሥርወ መንግሥቱም የሰሜኑን መንግሥት ጥንካሬ ሊጨምርና ዝነኛ ሊያደርገው ችሎ ነበር። ዘንበሪ የጦሩ አዛዥ ሆኖ በሚንግሥበት ጊዜ የመጀመሪያው ዐቢይ ትኩረቱ የሰሜኑን መንግሥት ማጠናከር ነበር። ያደረገው የመጀመሪያ ነገር ዋና ከተማውን ወደ ሰማርያ ማዞርና ከጥቃት ለመከላከል በዙሪያዋ ምሽግ መሥራቱ ነበር። የሰማርያ ከተማ እስከ 722 ዓ.ዓ. ድረስ የሰሜኑ መንግሥት ዋና ከተማ ሆና ነበር።

በበርካታ የነቢያት መጻሕፍት ውስጥ የሰሜኑ መንግሥት በዋና ከተማው ስም ሰማርያ በመባል ይታወቅ ነበር።

ዘንበሪ ሞአባውያንን ለማሸነፍና በጣም ሀብታም ለመሆን የቻለ ሰው ነበር። በዚህ ጊዜ ከይሁዳ ጋር የተደረገ አንዳችም ጦርነት ያለ አይመስልም።

ዘንበሪ አገዛዙን ለማስፋፋት ይችል ዘንድ ከፊኒሺያ ጋር ስምምነት አድርጎ ነበር። ፊኒሺያ በሰሜን ምዕራብ የሚገኝ የጢሮስና የሲዶና ግዛት ነበር። ጢሮስና ሲዶና እጅግ ጠንካራ አገር የነበሩና በሜዲትራኒያን ባሕር አካባቢ ከሚገኙ አገሮች ሁሉ በዓለም አቀፍ ንግዳቸው የታወቁ ነበሩ፤ ደግሞም የበአል አምልኮ ማዕከልም ነበሩ።

ስምምነቱን ሕጋዊ ለማድረግ ዘንበሪ ልጁን አክዓብን ከፊኒሺያ (ሲዶና) ንጉሥ ሴት ልጅ ከኤልዛቤል ጋር አጋባው። ይህ ስምምነት ለሕዝቡ መልካም ሊሆን ቢችልም፥ በመንፈሳዊ አንጻር ግን ለሰሜኑ መንግሥት እጅግ የከፋ ነገር አስከትሏል። የአክዓብ ሚስት የነበረችው ኤልዛቤል የበአልን አምልኮ ወደ እስራኤል ስላመጣች፥ አብዛኛዎቹን የእግዚአብሔር ነቢያት አስገደለች። በዚህ ምክንያት ዘንበሪ «ከእርሱ አስቀድሞ ከነበሩት ይልቅ እጅግ ከፋ» ተብሎ ተጽፏል (1ኛ ነገ. 16:25)።

10. የእስራኤል ንጉሥ አክዓብ (874-853 ዓ.ዓ.)

አክዓብ ጥሩ የፖለቲካ መሪ ነበር። የሰሜኑን መንግሥታት የግዛት ክልል ለማስፋፋት፥ ለመከላከል ምቹ የሆኑ ከተሞችን ለመገንባት፥ ወዘተ. ችሎ ነበር።

አክዓብ ከደቡብ የይሁዳ መንግሥት ጋርም ጥሩ ኅብረት ለመፍጠር ችሎ ነበር። ሴት ልጁን አታሊያህን በእርሱ ዘመን የይሁዳ ንጉሥ ለነበረው ለኢዮሳፍጥ ልጅ ለኢዮራም ድሮለት ነበር። ይህም የግንኙነታቸው ማስሪያ ነበር። ይህ በይሁዳ ሕዝብ ሁሉ ላይ ታላቅ ጥፋት የሚያስከትል ክፉ ተግባር እንደነበረ ኢዮሳፍጥ አላስተዋለም ነበር። ከሞላ ጎደል የዳዊትን ቤት በሙሉ ሊያጠፋ ተቃርቦ ነበር።

አክዓብ የበኣል አምልኮን ስላስፋፋና ይህም እጅግ ክፉ ተግባር ስለነበር «ከእርሱ በፊት ከነበሩት ሁሉ ይልቅ በእግዚአብሔር ፊት ክፉ አደረገ» ተብሎ ስለ እርሱ ተጽፏል (1ኛ ነገ. 16፡30)።

በአክዓብ ዘመነ መንግሥት መጨረሻ አካባቢ ከሶርያ ጋር ጦርነት የተደረገ ቢሆንም፥ በኤልያስ እርዳታ አክዓብ ጦርነቱን በድል ለመወጣት ችሏል። በኋላም ከይሁዳ ጋር በአንድነት በመተባበር በብሉይ ኪዳን ብዙ ጊዜ አራም ተብሎ ከሚጠራውና በአሁኑ ጊዜ በመስጴጦምያ ዋናው ኃይል ከሆነው ከሶርያ ጋር ተዋግቷል። በዚህም ጦርነት አክዓብ ተገደለ።

የእስራኤል ንጉሥ የነበረው አክዓብ እጅግ ታዋቂ የሆነው ታሪኩ ነገ ከምናጠናው ከእግዚአብሔር ነቢይ ከኤልያስ ጋር በነበረው የጠበቀ ግንኙነት ነው።

| |
|---|
| 16ኛ ጥያቄ፥ ከእነዚህ የእስራኤልና የይሁዳ ነገሥታት ልትማር የምትችላቸውን አንዳንድ መንፈሳዊ ትምህርቶች ዘርዝር። |

4ኛ ቀን 1ኛ ነገሥት 17-22

እጅግ የከፋ ነገር ባለበት ዘመን ሁሉ፥ እግዚአብሔር የራሱ የሆኑ ታማኝ ሰዎች አሉት። እነዚህ ሰዎች ብዙ ጊዜ «ቅሬታዎች» የምንላቸው፥ ለሐሰት ትምህርት አንንበረከክም የሚሉ፥ ወይም ከፍተኛ ስደት ባለበት ጊዜ እምነታቸውን በጽናት ይዘው የሚቆዩ ሰዎች ናቸው።

ብዙውን ጊዜ በእነዚህ የጨለማ ወቅቶች፥ ለእግዚአብሔር ታማኝ የሆኑ ሰዎች ተስፋ ሊቆርጡና በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ያለውን እምነታቸውን ለመተው ሊፈተኑ ይችላሉ። ለብቻ ከመቆም ይልቅ፥ የዓለምን የአኗኗር ስልት በመከተል ከብዙኃኑ ጋር መተባበር እጅግ ቀላል ነው።

ኤልያስ ብቸኛው የእግዚአብሔር ነቢይ ነበር። እጅግ ክፉ በነበረው በአክዓብ ዘመን ብዙዎቹ የእግዚአብሔር ነቢያት በአክዓብ ሲገደሉ፥ ኤልያስ በእምነቱ ጸንቶ ቆመ። አንድ ጊዜ ኤልያስ እጅግ ተስፋ ቆርጦ ሞቱን ሲለምን እግዚአብሔር እንዲህ በማለት አጽናናው:- «እኔም ከእስራኤል ጉልበታቸውን ለበኣል ያላንበረከኩትን ሁሉ፥ በአፋቸውም ያልሳሙትን ሁሉ፥ ሰባት ሺህ ሰዎች ለእኔ አስቀራለሁ።» (1ኛ ነገሥት 19፡18)።

17ኛ ጥያቄ፥ ሀ) ሁሉም የተዉት በሚመስልበት ጊዜ ለእግዚአብሔር መቆም አስቸጋሪ የሚሆነው ለምንድን ነው? ለ) በእነዚህ አስቸጋሪ ጊዜያት ተስፋ መቁረጥ ቀላል የሚሆነውስ ለምንድን ነው? ሐ) ጨለማው እጅግ ድቅድቅ በሚሆንበት ጊዜ እንኳ ለእግዚአብሔር ታምነው የሚቆሙ ቅሬታዎች አሁንም ስላሉት በእግዚአብሔር ላይ የምንጽናናው እንዴት ነው?
18ኛ ጥያቄ፥ 1ኛ ነገሥት 17-22 አንብብ። ሀ) ኤልያስ ያደረጋቸውን የተለያዩ ተአምራት ዘርዝር። ለ) ኤልያስ የጣዖታትን ከንቱነት ያሳየው እንዴት ነው? ሐ) በእዚህ ክፍል የተጠቀሱት ሦስት ነገሥታት እነማን ናቸው? መ) ስለ መንፈሳዊ ሕይወታቸው ሥዕላዊ መግለጫ ስጥ።

ከ1ኛ ነገ. 17-2ኛ ነገ. 8 ያሉት እነዚህ ምዕራፎች፥ ከነገሥታቱ ይልቅ በኤልያስና በኤልሳዕ ላይ ያተኩራሉ።

19ኛ ጥያቄ፥ ከመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት ኤልያስና ኤልሳዕ የሚለውን ክፍል ተመልከት። ስለ ሕይወታቸው ጠቃሚ የሆኑ እውነቶችን ዘርዝር።

የ1ኛ ነገሥት የመጨረሻ ክፍል (ምዕ. 17-22) የሚያተኩረው ኤልያስ ከእስራኤል ጋር ስለ ነበረው ግንኙነት ነው። ኤልያስና ኤልሳዕ ያገለገሉት በሰሜኑ የእስራኤል መንግሥት ነው። የበአል አምልኮ በእስራኤል እንዳይስፋፉ ለመከላከልና ሕዝቡን ወደ እውነተኛው የእግዚአብሔር አምልኮ ለመመለስ የተጠሩ የእግዚአብሔር ነቢያት ነበሩ።

በኤልያስና በኤልሳዕ ታሪክ ውስጥ ልናስታውሳቸው የሚገባን በርካታ እውነቶች አሉ፡-

1. በብሉይ ኪዳን የሚገኙ ነቢያት ተግባር የግድ የወደፊቱን ነገር መተንበይ አልነበረም፤ ነገር ግን ነቢዩ እግዚአብሔር በቀጥታ የሚናገረውና በእርሱም በኩል ከሕዝቡ ጋር ግንኙነት የሚያደርግበት ሰው ነበር። አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔር ለነቢያቱ ወደፊት ስለሚሆነው ነገር ይነግራቸው ነበር። ብዙ ጊዜ ግን ነቢዩ የእግዚአብሔርን ቃል የሚያመጣው ለዚያን ጊዜ ነበር።

2. በዘመኑ የነበሩት የፖለቲካ መሪዎች (ነገሥታት) እግዚአብሔርን በሚተዉበት ጊዜ፥ የእርሱን መልእክት ለሕዝቡ ያደርሱ ዘንድ

የተለዩ ሰዎችን ይመርጥ ነበር። ነቢያቱም ሕዝቡ በጣዖት አምልኮ እንዳይያዙ ያስጠነቅቁ ዘንድ እግዚአብሔር ይጠቀምባቸው ነበር።

3. የነቢያት ዘመን ተብሎ በሚጠራው ጊዜ የተነሣ የመጀመሪያው ነቢይ ኤልያስ ነበር። ከኤልያስ ዘመን ጀምሮ፥ በሕዝቡ ላይ ስለሚመጣው የእግዚአብሔር ፍርድ የሚያስጠነቅቅ የነቢያትን ተከታታይ አገልግሎት እናያለን። ኤልያስና ኤልሳዕ «የነቢያት ጉባኤ» በመባል የሚታወቀውን የነቢያትን የቡድን አገልግሎት መርተዋል። ይህ የነቢያት ቡድን ለብዙ ዓመታት በእስራኤል ውስጥ አገልግሏል።

ለአይሁድ ኤልያስ የእውነተኛ ነቢያት ምሳሌ ለመሆን በቅቷል። አለባበሱና አኗኗሩን በኋላ የተነሡ ነቢያት ሁሉ የተከተሉት ነበር። በተለይ ደግሞ መጥምቁ ዮሐንስ ይህንን አድርጎአል። ብሉይ ኪዳን የሚጠናቀቀው ወደ እስራኤል በሚመጣ እንደ ኤልያስ ባለ ነቢይ እንደሚሆን ተነግሮ ነበር (ሚል. 4:5)። ኢየሱስ የዚህ ትንቢት ፍጻሜ መጥምቁ ዮሐንስ እንደሆነ ተናግሯል (ማቴ. 11:14)። ኢየሱስ በተራራው ላይ በተለወጠ ጊዜ የሕግ መሪ ከነበረው ከሙሴና የነቢያት መሪ ከነበረው ከኤልያስ ጋር እንደተገናኘ መመልከት የሚያስደንቅ ነው።

4. ኤልያስና ኤልሳዕ መልእክታቸውን በጽሑፍ ያላስተላለፉ ነቢያት ናቸው። ይህንን ስንል በእስራኤል የተነበዩ ቢሆንም እንኳ፥ መልእክታቸውን ለሕዝቡ በጽሑፍ አላስቀሩም ማለታችን ነው። ከእነርሱ በኋላ የተነሡት ሆሴዕ፥ ኢሳይያስ፥ ኤርምያስ ወዘተ. መልእክታቸውን በጽሑፍ ያስተላለፉ ነቢያት ናቸው።

5. የኤልያስና የኤልሳዕ አገልግሎት በበአል አምልኮ ላይ የቀረበ ቀጥተኛ ተቃውሞ እንደሆነ መመልከት አስፈላጊ ነው። የሚከተለውን የበአል አምልኮና የኤልያስና የኤልሳዕ አገልግሎት ንጽጽር ልብ በል:-

| በአልና የእግዚአብሔር ነቢያት የሆኑት- | ኤልያስና ኤልሳዕ |
|---|---|
| - በአል ዝናምን የሚቆጣጠር የማዕበል አምላክ ነበር | - ኤልያስ በምድሪቱ ላይ ድርቅ እንዲመጣ አዘዘ |
| - በአል የተትረፈረፈ ምርትን እንደሚሰጥ ያረጋግጥ ነበር | - እስራኤል ከፍተኛ ራብና ድርቅ ገጠማት ይሁን እንጂ በእግዚአብሔር |

| | |
|---|---|
| | እርዳታ ኤልያስና ኤልሳዕ ግን እህልና ዘይት ሰጡ |
| - በአል መብረቅንና እሳትን ይቆጣጠር ነበር | - ኤልያስ በእግዚአብሔር ስም በማዘዝ እሳትን ከሰማይ አወረደ |
| - በአል ሕይወትና ሞትን ይቆጣጠር ነበር | - ኤልያስና ኤልሳዕ በእግዚአብሔር ስም በሽተኛን ፈወሱ ሙታንን አስነሡ |

ኤልያስና ኤልሳዕ የሠሩአቸው ተአምራት እውነተኛ አምላክ እግዚአብሔር ብቻ እንደሆነና በአልም ኃይል የሌለው ውሸተኛ አምላክ (ጣዖት) እንደነበረ በግልጥ የሚያሳይ ነበር።

---

20ኛ ጥያቄ፥ ክርስቲያኖች የዚህ ዓይነት ኃይል ያለው እግዚአብሔር ብቻ እንደሆነ የማወቃቸው አስፈላጊነት ምንድን ነው?

---

በ1ኛ ነገሥት 17-22 ዋናው ነቢይ ኤልያስ ነበር። ስለ ኤልያስ የሚከተሉትን ነገሮች ተመልከት፡-

1. እግዚአብሔር ድርቅና ራብ እንደሚመጣ፥ የድርቁና የራቡ ዘመን እንደሚያበቃም ለመናገር የተጠቀመበት ሰው ነበር።

2. እግዚአብሔር በቁራዎች የመገበው ሰው ነበር።

3. መበለቲቱን ለመመገብና ልጇን ከሞት በማስነሣት ወደ ሕይወት ለመመለስ እግዚአብሔር የተጠቀመበት ሰው ነበር።

4. ለእስራኤል በሙሉ እውነተኛው አምላክ እግዚአብሔር ብቻ እንደሆነና የጣዖት አምልኮ አንዳችም ዋጋ የሌለው ከንቱ ነገር እንደሆነ አሳየ። በቀርሜሎስ ተራራ የእግዚአብሔር እሳት ከሰማይ ወርዳ መሥዋዕቱን እንድትበላ አደረገ። ከዚያ በኋላ 400 የበአል ነቢያትንም አስገደለ።

5. ኤልዛቤል የተባለችውን ሴት ፈርቶ ወደ ምድረ በዳ ሸሸና ሞትን ለመነ። እግዚአብሔርም ተገናኘውና ገሠጸው። ለበአል ያልሰገዱ ሌሎች ሰዎች እንዳሉትም ነገረው።

6. እግዚአብሔር ኤልሳዕን የሚቀጥለው ታላቁ የእስራኤል ነቢይ አድርጎ ለመጥራት ኤልያስን ተጠቀመበት።

7. ኤልያስ የአክዓብን ቤት ፍጻሜና የኤልዛቤልን መሞት ተነበየ።

በኤልያስ ዘመን የነበሩ ሌሎች ሁለት ነገሥታትም ተጠቅሰዋል:-

1. ኢዮሣፍጥ የይሁዳ ንጉሥ (872-848 ዓ.ዓ.)

ከይሁዳ ታላላቅ ነገሥታት አንዱ ኢዮሣፍጥ ነበር። በአሳ የተጀመረውን መንፈሳዊ መነቃቃት ቀጠለ። የጣዖት አምልኮን አጠፋ። በተለይ ደግሞ አሺራ የተባለችውን የከነዓናውያንን የልምላሜ ሴት አምላክ አጠፋ። በይሁዳ ሁሉ እንዲሰማሩና ለሕዝቡ የእግዚአብሔርን ሕግ እንዲያስተምሩ ሌዋውያንና መኳንንትን አደራጀ። በእርሱ የአመራር ዘመን በይሁዳ ምድር ታላቅ መንፈሳዊ መነቃቃት አስነሣ። ለእግዚአብሔር ታማኝ ስለሆነ እርሱ አከበረው። ፍልስጥኤማውያንና ዓረቦችን በበላይነት ሊቆጣጠርና ምድሪቱንም ጠንካራ ሊያደርጋት ቻለ።

የኢዮሣፍጥ ትልቁ ችግር ከእስራኤል ጋር መስማማቱና ልጁን ለአክዓብ ቤት መዳሩ ነበር። ይህ ድርጊቱ እርሱንና ቤተሰቡን በመንፈሳዊ ነገር ሊጎዳ እንደሚችል አላሰበም ነበር። ከሞተ አሥር ዓመት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ይህ ባለማስተዋል የተፈጸመ ድርጊት ቤተሰቡን ሊያጠፋ ደረሰ። ይህ ያለማስተዋል ተግባር በመላው ይሁዳ የጀመረውን ሃይማኖታዊ ተሐድሶ አደናቀፈው።

ኢዮሣፍጥ ከአክዓብ ጋር የነበረው የጓደኝነት ግንኙነት ሊያስገድለው ምንም ያህል አልቀረውም ነበር። ኢዮሳፍጥ የእስራኤልን ሽንፈት የተናገረውን የእግዚአብሔርን ነቢይ ሚክያስን ስላልሰማ ከአክዓብ ጎን ቆሞ በመዋጋት ላይ ሳለ ሊገደል ነበር። ነቢዩ ሚክያስ እንደተናገረው፥ አክዓብ በጦርነቱ ተገደለ።

> 21ኛ ጥያቄ፥ ሀ) እግዚአብሔርን የሚፈራ መሪ ከዓለም ጋር ስለሚኖረው ግንኙነት የኢዮሣፍጥ ሕይወት እንዴት ጥሩ ማስጠንቀቂያ ይሆናል? ለ) ከማያምኑ ጋር ስለሚደረግ ጋብቻ አደገኛነትና ይህም በአማኝ ልጆች ላይ ስላለው ተጽዕኖ ምን ያስተምረናል?

እግዚአብሔርን የሚፈሩ መሪዎች ሲሰምርላቸውና እግዚአብሔር በኃይል ሲጠቀምባቸው፥ ሰይጣን ከዓለም ጋር የጠበቀ ግንኙነት እንዲኖራቸው በማድረግ ሊያጠፋቸው ይሞክራል። የተከበረ ክርስቲያናዊ መሪ አንዳንድ ጊዜ ከሌሎች የሃይማኖት መሪዎች ጋር ግንባር እንዲፈጥር

ወይም የፖለቲካ መሪ እንዲሆን ይመረጣል። ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸውን የጠበቀ ግንኙነትና በቤተ ክርስቲያን ያላቸውን ንጹሕ አቋም ከዓለም ጋር በዚህ ዓይነት ኅብረት ውስጥ ሆነው መጠበቅ የሚችሉ ጥቂት ክርስቲያን መሪዎች ብቻ ናቸው። ይህ ነገር ብዙ ጊዜ የመሪውን ሕይወት ወደ ማጥፋትና በቤተ ክርስቲያን ላይ ጉዳት ወደማምጣት የሚያዘነብል ነው። ክርስቲያኖች በሚመሠርቱት ኅብረትና ከዓለም ጋር በሚኖራቸው ግንኙነት በከፍተኛ ጥንቃቄ ሊኖሩ ይገባል። እግዚአብሔር ብዙ ጊዜ እርሱን የሚፈሩ መሪዎችን በዚህ ዓይነት ሁኔታ ውስጥ እንዲያገለግሉ የሚያስችላቸው ቢሆንም፥ እርምጃቸውንና እምነታቸውን በከፍተኛ ጥንቃቄ ሊይዙ ይገባል።

2. የእስራኤል ንጉሥ አካዝያስ (853-852 ዓ.ዓ.)

እንደ አባቱ እንደ አክዓብ፥ አካዝያስም ክፉና የበአልን አምልኮ የተከተለ ሰው ነበር። ሁለት ዓመታት ብቻ ከነገሠ በኋላ ወደቀና ሞተ። የቀረው የአካዝያስ ታሪክ በ2ኛ ነገሥት ውስጥ ይገኛል።

---

22ኛ ጥያቄ፥ በዚህ ክፍል ከተጠቀሱት ነገሥታትና ከኤልያስ ሕይወት ስለ መንፈሳዊ መሪነት የተጠቀሱትን አንዳንድ ትምህርቶች ዘርዝር።

---

5ኛ ቀን፡-የዚህን ሳምንት ትምህርት ከልስና ለሳምንታዊ ስብሰባ ዝግጅት ይረዳህ ዘንድ የውይይት ጥያቄዎችን ተመልከት።

## ሳምንታዊ ስብሰባ

1. ሳምንታዊ የአምልኮ ጊዜ
2. ጸሎት
3. የትምህርቱ ክለሳ
4. ውይይት
    1. ሀ) 1ኛ ነገሥት የተጻፈባቸው ዓላማዎች ምንና ምን ነበሩ? ለ) የ1ኛ ነገሥት ታሪክ ለቤተ ክርስቲያን መሪዎች የሚያስፈልገው ለምንድን ነው? ሐ) 1ኛ ነገሥትን ለቤተ ክርስቲያንህ የምታስተምርባቸውን መንገዶች ግለጥ።
    2. ሀ) በ1ኛ ነገሥት ውስጥ ያሉ ነቢያት ሚና ምን ነበር? ለ) ዛሬም የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ተመሳሳይ ሚና ሊጫወቱ የሚችሉት

እንዴት ነው? ሐ) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እንደ ቀድሞዎቹ ነቢያት ሊሆኑ የሚችሉባቸው መንገዶች የትኞቹ ናቸው?

3. ዘዳ. 6፡10-13፤ 8፡7-14 አንብብ። ሀ) እነዚህ ማስጠንቀቂያዎች በሰሎሞን ሕይወት የተፈጸሙት እንዴት ነው? ለ) በቤተ ክርስቲያንህ ውስጥስ የተፈጸሙት እንዴት ነው? ሐ) በአብያተ ክርስቲያኖቻችን ውስጥ እነዚህ ነገሮች እንዳይፈጸሙ መሪዎች ማድረግ የሚችሉት ነገር ምንድን ነው?

4. ከሰሎሞን ሕይወት በቤተ ክርስቲያን ስላለ መንፈሳዊ መሪነት የምንማረው ነገር ምንድን ነው? አዎንታዊ ሆኑ አሉታዊ ነገሮችን ዘርዝር።

5. ሀ) የእስራኤልና የይሁዳ ነገሥታት መንፈሳዊ ሕይወት በሕዝቡ መንፈሳዊ ሕይወት ላይ እንዴት ተጽዕኖ ያሳድር እንደነበረ ጥቀስ። ለ) ይህ ነገር ዛሬም እውነት የሆነው እንዴት ነው? ሥዕላዊ መግለጫ ስጥ። ሐ) ይህ ነገር በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አግባብነት ስላለው መሪነት አስፈላጊነት እንዴት ያስጠነቅቀናል?

6. ሀ) ኢዮሳፍጥ ከአክዓብ ጋር ስለነበረው ግንኙነት፥ ከዓለም ጋር አጥብቆ ወዳጅ ስለመሆን ምን መማር እንችላለን? ለ) በዚህ ዘመን ያሉ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ከሌሎች ሃይማኖቶች መሪዎች ጋር በማይገባ መንገድ እንዴት ግንኙነት ሊኖራቸው እንደሚችል ምሳሌዎችን ስጥ። ሐ) በዚህ ዘመን ያሉ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ከመንግሥት ባለሥልጣኖች ጋር ሊኖር ስለሚገባ መልካም ግንኙነት ከሚገባ በላይ ትኩረት ሊሰጡ እንዴት እንደሚችሉ ምሳሌዎችን ስጥ። መ) በዚህ የተሳሳተ ኅብረት እነርሱም ሆኑ ሌሎች ክርስቲያኖች ሊጎዱ የሚችሉት እንዴት ነው? ሠ) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ከሌሎች ሃይማኖት መሪዎችና የፖለቲካ መሪዎች ጋር የሚኖራቸው ተገቢ ግንኙነት ምንድን ነው?

5. ጸሎት

# ትምህርት 16

1ኛ ቀን:- የ2ኛ ነገሥት መግቢያ፥ 2ኛ ነገሥት 1-8:15

1ኛ ጥያቄ፥ ጸሐፊው ማን እንደሆነና መጽሐፉ መቼ እንደተጻፈ ወዘተ. የተሰጠውን የመግቢያ አሳብ ከትምህርት 15 1ኛ ቀን ጥናት ተመልከት።

በመጀመሪያ 1ኛና 2ኛ ነገሥት አንድ መጽሐፍ እንደነበሩ ታስታውሳለህ። በኋላ ወደ ሁለት መጻሕፍት የተከፈሉት መጽሐፉ እጅግ በመርዘሙ ምክንያት ነበር። የነገሥት መጽሐፍ ርዕስ የተገኘው በ1ኛና 2ኛ ነገሥት ከሰሎሞን ጀምሮ እስከ ሴዴቅያስ ድረስ በእስራኤልና በይሁዳ የነገሡ ነገሥታት አጫጭር ታሪኮች የሚገኙበት መጽሐፍ ከመሆኑ አንጻር ነው።

2ኛ ጥያቄ፥ 2ኛ ነገሥት 17:7-23 አንብብ። ሀ) እግዚአብሔር እስራኤልንና ይሁዳን ያጠፋው ለምንድን ነው? ለ) በዚህ ክፍል የተሰጡትን የተለያዩ ምክንያቶችን ዘርዝር።

እስራኤላውያን በእግዚአብሔር የተመረጡት ለእርሱ የተለዩ ሕዝብ እንዲሆኑ ነበር። በአብርሃም በኩል ከእግዚአብሔር ጋር የዘላለም ቃል ኪዳን ነበራቸው። በሲና ተራራ እግዚአብሔር በታላቅ መንገድ ተገናኛቸውና ትእዛዛቱን ሰጣቸው። እስራኤላውያን ለምን ጠፉ? ወደ ምርኮ የሄዱት ለምንድን ነው? ራብ፥ በሽታ፥ ሞት፥ ጦርነትና ምርኮ በእነርሱ ላይ የመጣው ለምንድን ነው?

የ1ኛና 2ኛ ነገሥት መጻሕፍት ሊመልሱት የሚሞክሩት ጥያቄ ይህ ነው። አዎን፥ የእስራኤል ሕዝብ የተለዩ ነበሩ። አዎን፥ እግዚአብሔር ቃል ኪዳኑን ከአብርሃም፥ ከእስራኤላውያንና ከዳዊት ጋር አድርጎ ነበር። የእግዚአብሔር ሕዝብ የጠፉበት ምክንያት ግን በእግዚአብሔር ሳይሆን በራሳቸው ጥፋትና ስሕተት ነበር። የእግዚአብሔር ቃል ነበራቸው፤ ስለዚህ ቃሉን ማወቅ ይጠበቅባቸው ነበር። ነገር ግን እያወቁ በግትርነት በእግዚአብሔር ላይ ዓመፁ። ቅዱሱ እግዚአብሔር ኃጢአታቸውን ሳይቀጣ ሊያልፋቸው ስላልቻለ አስቀድሞ በተደጋጋሚ ባስጠነቀቃቸው መሠረት አስማረካቸው።

ዛሬም እግዚአብሔር ተመሳሳይ ነገር በቤተ ክርስቲያኑ ሊያደርግ ይችላልን? በቤተ ክርስቲያኑ ላይ ራብ፥ በሽታና ጥፋት እንዲመጣ መፍቀድ ይችላልን? እግዚአብሔር እኛን ለምርኮ ማለትም ለሌላው ሃይማኖት ቁጥጥር አልፈን እንድንሰጥ ሊያደርግ ይችላልን? ለእነዚህ ሁሉ ጥያቄዎች መልሱ አዎን የሚል ነው። እኛም ልክ እንደ እስራኤላውያን ከሆንን፥ የእግዚአብሔርን ቃል ካላወቅንና ካልታዘዝን እንጠፋለን። የ2ኛ ነገሥት መልእክት ለእግዚአብሔር ካልታዘዝን፥ እግዚአብሔር በእስራኤላውያን ላይ እንደፈረደ፥ በእኛም ላይ እንደሚፈርድ የሚያመለክት ማስጠንቀቂያ ነው። ጉዳዩ እግዚአብሔር ባለፈው ዘመን እንዴት ተጠቀመብን የሚለው አይደለም። ቁም ነገሩ እግዚአብሔርን አሁንና ወደፊት እንዴት እንደምናገለግለውና ከእርሱም ጋር እንዴት እንደምንራመድ ነው።

3ኛ ጥያቄ፥ 2ኛ ዜና 7:14 አንብብ። ሀ) በዚህ ቁጥር እግዚአብሔር የገባቸው የተስፋ ቃሎች ምንድን ናቸው? ለ) ለዚህ የተስፋ ቃል የተሰጠው ቅድመ ሁኔታ ምንድን ነው? ሐ) አንተና ቤተ ክርስቲያንህ እነዚህን ቅድመ ሁኔታዎች እያሟላችሁ ያላችሁት እንዴት ነው? ይህንን ጥቅስ በቃልህ አጥና።

## የ2ኛ ነገሥት ታሪክ የተፈጸመበት የዘመን ርዝመት

በ1ኛ ነገሥት የተጻፈው ታሪክ ከዳዊት ሞት ከ971 ዓ.ዓ. ጀምሮ እስከ 853 ዓ.ዓ. ድረስ በነበረው ጊዜ መፈጸሙን ተመልክተናል። በ1ኛ ነገሥት ታሪክ ጊዜ የሰሎሞንን መንግሥትና ቀጥሎም እስራኤል በሰሜን፥ ይሁዳ ደግሞ በደቡብ ሆኖ ለሁለት የተከፈለውን መንግሥት ተመልክተናል።

2ኛ ነገሥት የተከፈለውን የእስራኤል መንግሥት ታሪክ ይቀጥላል። የሚናገረውም ከ853-586 ዓ.ዓ. ስላለው ጊዜ ነው። በዚህ ጊዜ ውስጥ ከተፈጸሙ ድርጊቶች በጣም አስፈላጊዎቹ በ722ዓ.ዓ. የተፈጸመው የሰሜኑ መንግሥት ጥፋትና ከብዙ ዓመታት በኋላ በ586ዓ.ዓ የተከናወነው የደቡብ መንግሥት ጥፋት ነው።

## በ2ኛ ነገሥት የታሪክ ዘመን የነበሩ ዋና ዋና ኃይላት

የ2ኛ ነገሥት የታሪክ ዘመናት በዋና ዋና የዓለም መንግሥታት ዘንድ ከፍተኛ ትግል የተካሄደባቸው ጊዜያት እንደነበሩ 2ኛ ነገሥት ይነግረናል።

የጳለስጢና ምድር በዚህ ትግል መሀል ተይዛ ጦርነትን አሳልፋለች። እስራኤላውያን የትኛውን ወገን መደገፍ እንዳለባቸው ለመወሰን የተቸገሩበት ጊዜ ነበር፤ ስለዚህ ነገሥታቱ ከአንድ ኃያል መንግሥት ጋር የነበራቸውን ስምምነት እርሱን በሚጥለው ሌላ ኃያል መንግሥት ሲቀይሩና ሲዋዥቁ እንመለከታለን። በእነዚህ ዓመታት በእስራኤልና በይሁዳ መንግሥታት ታሪክ ውስጥ ታላቅ ሚና የተጫወቱ ሦስት ዋና ዋና መንግሥታት ነበሩ።

1. ግብፅ፡- በእነዚህ ዓመታት ግብፅ እስከዚህም ብርቱ የሆነችበት ጊዜ ጨርሶ አልነበረም። ነገር ግን ወደ ቀድሞ ስፍራዋ ለመመለስና የመካከለኛው ምሥራቅ ዋና መንግሥት የመሆን ሕልም ሁልጊዜ ነበራት፤ ስለዚህ ግብፅ ብዙ ጊዜ እንደ አሦርና ባቢሎን ካሉት ሌሎች ኃያላን መንግሥታት ጋር ግጭት በመፍጠር ጦርነትን ታካሂድ ነበር። ይህም ጦርነት ብዙ ጊዜ የሚደረገው በከነዓን ምድር ነበር። በተጨማሪ ብዙ ጊዜ ግብፅ በመሰጴጦሚያ የሚገኙ ሌሎች ግዛቶችንና መንግሥታትን ለመውጋት የእስራኤልንና የይሁዳ መንግሥታትን ድጋፍ ለማግኘት ትሞክር ነበር። ግብፅ በአሦርና በባቢሎን የተሸነፈች ብትሆንም፥ የምትገኘው እጅግ ርቃ ስለ ነበር፥ እነርሱ ሊቆጣጠሯት አልቻሉም ነበር።

በ2ኛ ነገሥት ያለው ታሪክ በተፈጸመበት ዘመን፥ ግብፅ በሁለት ዋና ዋና መንገዶች በጳለስጢና ላይ ተጽዕኖ አድርጋበት ነበር። በመጀመሪያ፥ በ609 ዓ.ዓ. ኢዮስያስ ብልህነት በጎደለው መንገድ ከግብፅ ጋር ተዋግቶ በጦርነቱ ተገደለ። ልጁም ኢዮአካዝ ወደ ግብፅ በምርኮ ተወሰደ። የግብፅ ንጉሥ በእርሱ ምትክ ኢዮአቄም የተባለውን ወንድሙን አነገሠው።

ሁለተኛ፥ በ586 ዓ.ዓ. ኢየሩሳሌም ከተደመሰሰች በኋላ፥ ብዙ አይሁድ ተሰድደው ወደ ግብፅ ሄዱ። ነቢዩ ኤርምያስንም አስገድደው ከእነርሱ ጋር ወሰዱት። በዚያም በርካታ የሆነ የአይሁድ ኅብረተሰብ ሰፈረና ለብዙ መቶ ዓመታት በዚያ ኖረ። ሴፕቱዋጀንት የሚባለው የግሪክ ቋንቋ መጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈው በ70 ዓ.ዓ. አካባቢ በግብፅ ነበር።

2. አሦር፡- ባለፈው ሳምንት የአሦር መንግሥት በእስራኤል ሕዝብ ታሪክ ውስጥ የተጫወተውን ከፍተኛ ሚና ተመልክተናል፤ ሆኖም እስከ 853 ዓ.ዓ. ለእስራኤል መንግሥት ዋና ፈተና የነበረች ሶርያ ናት። በ745 ዓ.ዓ. በአሦር ቴልጌልቴልፌልሶር የተባለ ታላቅ ንጉሥ

በሥልጣን ወንበር ላይ ተቀመጠ። የአሦርንም ግዛት ማስፋፋት ጀመረ። ለመጀመሪያ ጊዜ አንድ አገር ወርረው የሚይዙ ሕዝቦች በተወረረችው ከተማ ላይ ያደርጉት ስለ ነበረው ነገር ያስተዳደር መመሪያ ለውጥ አመጣ። ይህም ያስተዳደር መመሪያ በተወረረው አገር የሚኖሩ የሚጠቅሙ ዜጎችን (የተማሩ፥ ንጉሣዊ ቤተሰብ የሆኑ፥ የሥነ - ጥበብ ሰዎች ወዘተ.) መውሰድና በግዛቷ ሁሉ ውስጥ መበትን ነበር። ሌሎች የተወረሩ ሕዝቦችን ደግሞ ወደ ሌላ የተወረረ ከተማ አምጥተው ማስፈር ነበር። ይህም ያ ሕዝብ እንደገና እንዳያንሰራራና እንዳይዋጋ የማድረጊያ ዘዴ ነበር። አሦር እስራኤልን ባሸነፈች ጊዜ ሕዝቡን ወደ ምርኮ የወሰደችውና በግዛቱ ሁሉ ውስጥ የበተነችው ለዚህ ነበር። ሕዝቡ ወደ እስራኤል እንደገና ለመመለስ ጨርሶ አልቻለም። ይህንን ልምድ አሦራውያን ብቻ ሳይሆኑ፥ ባቢሎናውያንም አደረጉት። ይሁዳን ባሸነፉ ጊዜ፥ ሕዝቡን ወደ ምርኮ ወሰዱና በባቢሎን ግዛት ሁሉ ውስጥ በተኑአቸው። የባቢሎን መንግሥት በፋርስ መንግሥት በተሸነፈና በወደቀ ጊዜ፥ ወደ እስራኤል ለመመለስ የቻሉ አይሁድ በጣም ጥቂትና የተወሰኑ ብቻ ነበሩ።

የቴልጌልቴልፌልሶር ልጅ ስልምናሶር 5ኛ ከ727-722 ዓ.ዓ. የገዛ ንጉሥ ሲሆን፥ የእስራኤልን መንግሥትና የሰማርያን ከተማ የከበባትና አሸንፎ የያዛት እርሱ ነበር። አጠቃልሎ ይህን ከማድረጉ በፊት ግን ዳግማዊ ሳርጎን በተባለው የጦር ጀኔራሉ ተገደለ። ዳግማዊ ሳርጎን የሰሜኑን መንግሥት የማረከና ወደ ግዛቱም የደባለቀ ሰው ነው።

የሳርጎን ልጅ የሆነው ሰናክሬም (704-681 ዓ.ዓ.) በኋላ በሕዝቅያስ ዘመነ መንግሥት ይሁዳን ወግቶ ወደ 200000 የሚደርሱ ሰዎች ወደ ምርኮ ቢወስድም፥ ኢየሩሳሌምን ግን ለመውጋትና አሸንፎ ለመያዝ አልቻለም። ኢየሩሳሌም ከመውደቋ በፊት በራሱ ሁለት ልጆቹ ተገደለ።

የሚቀጥለው የአሦር ንጉሥ፥ አስራዶን ይባል ነበር። የይሁዳ ንጉሥ የነበረውን ምናሴን በምርኮ ወደ ባቢሎን የወሰደ እርሱ ነበር (2ኛ ዜና 33፡10-13)። የመጨረሻው ታላቁ የአሦር ንጉሥ አሱርባኒፓል (668-630 ዓ.ዓ.) የሚባለው ሲሆን፥ እርሱም መንግሥቱን እስከ ግብፅ ድረስ አስፋፍቷል። እርሱ ከሞተ ከጥቂት ጊዜ በኋላ፥ የአሦር መንግሥት መዳከም ጀመረና በመጨረሻ በ605 ዓ.ዓ. በባቢሎናውያን ተደመሰሰ።

3. ባቢሎን፡- የ2ኛ ነገሥት ታሪክ በተፈጸመበት ዘመን በእስራኤል መንግሥት ላይ ተጽዕኖ ያደረገ ሦስተኛው ታላቅ መንግሥት የባቢሎን መንግሥት ነበር። የባቢሎን መንግሥት ከ626-539 ዓ.ዓ. ድረስ ጠንካራ ነበር። በአሦር እጅ በነበረችም ጊዜ የባቢሎን ምድር በጣም ታዋቂ ክፍለ አገር ነበረች። ከአሱርባኒፓል ሞት በኋላ በ633 ዓ.ዓ. የባቢሎን ከተማ በአሦር ላይ ማመፅ ጀመረ። ከ626-605 ዓ.ዓ. የባቢሎን ንጉሥ በነበረው በናቦፖላሳር አመራር የባቢሎን መንግሥት ብቅ አለና የአሦርን መንግሥት ለመጣል ቻለ። በ612 ዓ.ዓ. የአሦር ዋና ከተማ የነበረችው ነነዌ ተደመሰሰች። በ609 ዓ.ዓ. የአሦር ጦር ተደመሰሰ። ናቦፖላሳር የይሁዳን መንግሥት ጦር ማጥቃት ቢጀምርም ሊያሸንፍ ግን አልቻለም ነበር።

ከናቦፖላሳር በኋላ፥ በባቢሎን መንግሥት ውስጥ በታላቅነቱ አቻ የማይገኝለት ናቡከደነፆር ነገሠ። እርሱም ከ605-562 ዓ.ዓ. በሥልጣን ላይ ቆየ። የይሁዳ መንግሥት ሦስት ጊዜ የተጠቃውና በመጨረሻም በምርኮ የተወሰደ በእርሱ ዘመነ መንግሥት ነበር።

1. አብዛኛው ንጉሣዊ ቤተሰብና ጠቃሚ የሆኑ ዜጎች የተወሰዱት በ605 ዓ.ዓ. ነበር። ከኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ አብዛኛው ሀብት ወደ ባቢሎን የተወሰደውና ዳንኤልና ሦስቱ ጓደኞቹ ወደ ምርኮ የተወሰዱት በዚህ ጊዜ ነበር (ዳን. 1፡1)። የይሁዳ መንግሥት የባቢሎን መንግሥት አገልጋይ የሆነውም ያኔ ነበር።

2. በ597 ዓ.ዓ. የሆነው ምርኮ፡- ኢዮአቄም ከግብፅ ጋር አብሮ በባቢሎን ላይ ባመፀ ጊዜ፥ ባቢሎን ኢየሩሳሌምን አጥቅታ ወረረቻት። በዚህ ጊዜ የንጉሣዊው ቤተሰብ ሌላ አባሎች የሆኑት ንጉሥ ዮአኪንና እጅግ ታዋቂ ከሆኑት 10000 ያህል የኢየሩሳሌም ዜጎች እንደነ ሕዝቅኤል ያሉት ጭምር ወደ ባቢሎን ተወሰዱ።

3. በ586 ዓ.ዓ. የሆነው ምርኮ፡- የመጨረሻው የይሁዳ ንጉሥ ሴዴቅያስ በባቢሎን ላይ ባመፀ ጊዜ ናቡከደነፆር ትዕግሥቱን አጣ። በ588 ዓ.ዓ. ከኢየሩሳሌም ጋር መዋጋት ጀመረ። ከግብፅ ጋር ለመዋጋት ሲል ከኢየሩሳሌም ጋር የጀመረውን ውጊያ አቆመ። ከጥቂት ቆይታ በኋላ ግን በ586 ዓ.ዓ. ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሰና ከረጅም ውጊያ በኋላ በወረራ ኢየሩሳሌምን ያዘ። የሴዴቅያስ ልጆች ተገደሉ። እርሱንም ዓይኑን አሳውረው ወደ ምርኮ ወሰዱት።

የኢየሩሳሌም ቅጥር፥ እንዲሁም ከብዙ ዓመታት በፊት የተሠራው የሰሎሞን ቤተ መቅደስ ተደመሰሱ። በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ አይሁድ በምርኮ ተወሰዱ። ድሀ የሆኑ ሰዎች ብቻ በምድሪቱ ላይ ቀሩ። ናቡከደነፆር ጎዶልያስን በይሁዳ ላይ ሾመው፤ ነገር ግን በእስማኤል ተገደለ። የቀሩትም አብዛኛዎቹ ሰዎች ወደ ግብፅ ሸሹ።

ከናቡከደነፆር ሞት በኋላ፥ የባቢሎን መንግሥት ኃይል ፈጥኖ በመቀነሱ በ539 ዓ.ዓ. በሜዶንና በፋርስ የተባበረ ኃይል ከሥልጣን ተወገደ። አይሁድን ወደ ትውልድ አገራቸው እንዲመለሱ የፈቀደ፥ በብሉይ ኪዳን የተጠቀሰ የመጨረሻ ኃያል መንግሥት የሜዶንና የፋርስ መንግሥት ነው።

በሚከተለው ሠንጠረዥ ትላልቅ ነቢያትን፥ በነቢያት ጊዜ የነበሩትን የእስራኤልና የይሁዳ ነገሥታት በአሕዛብ መንግሥታት ላይ የነበሩትንም ዋና ዋና ነገሥታት ትመለከታለህ። ይህ ሠንጠረዥ የሚያጠቃልለው ከ2ኛ ነገሥት ጀምሮ እስከ ብሉይ ኪዳን መጨረሻ ድረስ ያለውን ነው።

| ዘመኑ | የነቢዩ ስም | የእስራኤል ዋና ዋና ነገሥታት | የይሁዳ ዋና ዋና ነገሥታት | ዋና የአሕዛብ ንጉሥ |
|---|---|---|---|---|
| 875–850 ዓ.ዓ. | ኤልያስ (875–850 ዓ.ዓ.) | አክዓብ (874–853 ዓ.ዓ.) | ኢዮሳፍጥ (872–848 ዓ.ዓ.) | የሶርያ መንግሥት ቤንሃዳድ |
| 825 ዓ.ዓ. | ኤልሳዕ (852–795 ዓ.ዓ.) | ኢዮራም፥ ኢዩ፥ ኢዮአካዝ፥ | ኢዮራም፥ ኢዮአስ | ሐዛኤል |
| 800 ዓ.ዓ. | ኢዩኤል (835) | | | |
| 775 | ዮናስ (782–753 ዓ.ዓ.) | ዳግማዊ ኢዮርብአም (793–753) | ኤሜስያስ(792–767 ዓ.ዓ.) | ዳግማዊ ቤንሃዳድ |
| 750 ዓ.ዓ. | አሞጽ(760–753 ዓ.ዓ.) | | ዖዝያን (792–740 ዓ.ዓ.) | |
| 725 ዓ.ዓ. | ሆሴዕ (755–715 ዓ.ዓ.) | ፋቁሔ፥ ሆሴዕ | ኢዮአታም (750–735 ዓ.ዓ.) | ረአሶን |
| | ኢሳይያስ (740–680 ዓ.ዓ.) | | አካዝ (735–715 ዓ.ዓ.) | አካዝ (የአሦር መንግሥት) ሣልሳዊ ትግላትፐለሰር |
| 700 ዓ.ዓ. | ሚክያስ (735–700ዓ.ዓ.) | ምርኮ (722 ዓ.ዓ). | ሕዝቅያስ (715–686 ዓ.ዓ.) | ዳግማዊ ሰርጎን ሰናክሬም |
| 675 ዓ.ዓ. | | | ምናሴ (697–686ዓ.ዓ.) | አስራዶን |
| 650 ዓ.ዓ. | ናሆም (664–654ዓ.ዓ.). | | | 5ኛ ሻልምናኤሴር |
| 625 ዓ.ዓ. | ሶፎንያስ (632 ዓ.ዓ.) ኤርምያስ (627–580 ዓ.ዓ.) | | | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | ዕንባቆም (609–605 ዓ.ዓ.) | ምርኮ (722 ዓ.ዓ.) | ኢዮስያስ (640–609 ዓ.ዓ.) | አሱርባኒፓል<br>የባቢሎን መንግሥት |
| 600 ዓ.ዓ. | አብድዩ (605–586 ዓ.ዓ.) | | ዮአኪም<br>ሴዴቅያስ (597–586 ዓ.ዓ.) | ናቦጶላሳር<br>ናቡከደነፆር (605–562 ዓ.ዓ.) |
| 575 ዓ.ዓ. | ሕዝቅኤል (593–571 ዓ.ዓ.)<br>ዳንኤል (605–535 ዓ.ዓ.) | | ምርኮ (586–539 ዓ.ዓ.) | ናቦኒደስ/ቤልሻዛር |
| 550 ዓ.ዓ. | | | | |
| 525 ዓ.ዓ. | | | | የሜዶንና የፋርስ መንግሥት |
| 500 ዓ.ዓ. | ሐጌ ዓ.ዓ.(500ዓ.ዓ)<br>ዘካርያስ (520–480ዓ.ዓ) | | የቅሬታዎች መመለስ<br>ዘሩባቤል (539ዓ.ዓ) | ቂሮስ(550–530ዓ.ዓ.)<br>ዳርዮስ ቀዳማዊ (521–486 ዓ.ዓ.) |
| 475 ዓ.ዓ. | | | | ዘሬክስ (486–464)ዓ.ዓ. |
| 450 ዓ.ዓ. | | | | አርጤክስስ (464–423 ዓ.ዓ.) |
| 425 ዓ.ዓ. | ሚልክያስ (432–424 ዓ.ዓ.) | | ዕዝራ (458–435 ዓ.ዓ.) | |
| 400 ዓ.ዓ. | | | ነህምያ (444–420 ዓ.ዓ.) | ዳግማዊ ዳርዮስ (423–404 ዓ.ዓ.) |

## የ2ኛ ነገሥት አስተዋጽኦ

1. የመጨረሻው የኤልያስ አገልግሎትና ወደ ሰማይ መወሰዱ (2ኛ ነገ. 1-2፡18)

2. የጌታ ነቢይ የሆነው የኤልሳዕ አገልግሎት (2ኛ ነገ. 2፡19-8፡15)

3. የእስራኤልና የይሁዳ ነገሥታት እስከ እስራኤል ምርኮ ድረስ (2ኛ ነገ. 8፡16-17፡41)

   ሀ. የይሁዳ ንጉሥ ኢዮራም (8፡16-24)

   ለ. የይሁዳ ንጉሥ አካዝያስ (8፡25-29)

   ሐ. የእስራኤል ንጉሥ ኢዩ (9-10)

   መ. የይሁዳ ንግሥት ጎቶልያ (11)

   ሠ. የይሁዳ ንጉሥ ኢዮአስ (12)

   ረ. የእስራኤል ንጉሥ ኢዮአካዝ (13፡1-9)

   ሰ. የእስራኤል ንጉሥ ዮአስ (13፡10-25)

   ሸ. የይሁዳ ንጉሥ አሜስያስ (14፡1-22)

   ቀ. የእስራኤል ንጉሥ ዳግማዊ ኢዮርብዓም (14፡23-29)

   በ. የይሁዳ ንጉሥ ዖዝያን (15፡1-7)

   ተ. የእስራኤል ንጉሥ ዘካርያስ (15፡8-12)

   ቸ. የእስራኤል ንጉሥ ሻሎም (15፡13-16)

   ኀ. የእስራኤል ንጉሥ ምናሔም (15፡17-22)

   ነ. የእስራኤል ንጉሥ ፋቂስያስ (15፡23-26)

   ኘ. የእስራኤል ንጉሥ ፋቁሔ (15፡27-31)

   አ. የእስራኤል ንጉሥ ኢዮአታም (15፡32-38)

   ከ. የይሁዳ ንጉሥ አካዝ (16)

   ኸ. የእስራኤል ንጉሥ ሆሴዕ (17፡1-6)

ወ. የእስራኤል መማረክ (17፡7-41)

4. ከሕዝቅያስ ጀምሮ ይሁዳ እስከተማረከች ድረስ የነበሩ የይሁዳ ነገሥታት (2ኛ ነገ. 18-25)

   ሀ. ሕዝቅያስ (18-20)

   ለ. ምናሴ (21፡1-18)

   ሐ. አሞን (21፡19-26)

   መ. ኢዮስያስ (22፡23-30)

   ሠ. የይሁዳ ንጉሥ ኢዮአሐዝ (23፡31-35)

   ረ. የይሁዳ ንጉሥ ኢዮአቄም፡- የመጀመሪያው የባቢሎን ምርኮ (23፡36-24፡7)

   ሰ. የይሁዳ ንጉሥ ዮአኪን፡- ሁለተኛው የባቢሎን ምርኮ (24፡8-17)

   ሸ. የሴዴቅያስ በምርኮ ወደ ባቢሎን መወሰድ (24፡18-25፡21)

   ቀ. በምርኮ ጊዜ የተፈጸሙ ድርጊቶች (25፡22-30)

## 2ኛ ነገሥት የተጻፈባቸው ዓላማዎች

1. ከ853 ዓ.ዓ. ጀምሮ የእስራኤልና የይሁዳ መንግሥታት ወደ ምርኮ እስከ ተወሰዱበት ጊዜ ድረስ በእስራኤልና በይሁዳ የነገሡ ነገሥታትን ታሪክ በአጭሩ ለመተረክ ነው።

2. የእስራኤልና የይሁዳ መንግሥታት ወደ ምርኮ የተወሰዱበትን ምክንያት ለመግለጥ ነው። ይህ መጽሐፍ በግልጽ የሚያሳየው እስራኤልና ይሁዳ የጠፉት አሦርና ባቢሎን ታላቅ ስለ ነበሩ አለመሆኑን ነው። እንዲሁም አጋጣሚ ወይም ተፈጥሮአዊ የሆነ የታሪክ ክስተትም አይደለም። እስራኤልና ይሁዳ የጠፉት ትእዛዛቱን ስላልጠበቁ፥ እግዚአብሔር በቀጥታ ባመጣባቸው ፍርድ ነው። በእግዚአብሔር ላይ ዓመፁና በዚያ ፈንታ ሌሎች አማልክትን አመለኩ።

የ2ኛ ነገሥት ታሪክ እግዚአብሔር በታሪክ ሁሉ ውስጥ ያለውን አመለካከት ያሳየናል። ታሪክ የነገሮች ተፈጥሮአዊ አፈጻጸም ብቻ አይደለም። አንድ ሕዝብ ሌላውን የሚወጋበት፥ አንድ ንጉሥም ሌላውን የሚገዛበት ታሪክ ብቻ አይደለም። ተፈጥሮአዊ የሆነ የድርቅ፥ የበሽታና የሞት ታሪክም አይደለም። ይህኛው ክርስቲያን ያልሆኑ ሰዎች ታሪክን የሚመለከቱበት መንገድ ነው። እግዚአብሔር ግን ታሪክን የሚመራ ነው። ራብንና በሽታን የሚልክ እርሱ ነው። ጦርነቶችንና አሕዛብን ሁሉ የሚቆጣጠር እርሱ ነው። ሕዝቡ በምርኮ እንዲወሰዱ የሚፈቅድ እርሱ ነው። ክርስቲያኖች ግን በጎም ሆኑ ክፉ ነገሮችን ሁሉ ያያሉ። እንዲሁም የእግዚአብሔር እጅ በሥራ ላይ ሆኖ ማየት ይቻላል።

4ኛ ጥያቄ፥ ሀ) ክርስቲያኖች በታሪክ ላይ ይህን አመለካከት ማስታወስ የሚያስፈልጋቸው ለምንድ ነው? ለ) መንግሥት በትምህርት ቤቶች ከስተማረን ታሪክ እዚህ ያለው አመለካከት እንዴት ሊለያይ ቻለ?

3. ከምርኮ በኋላ የሚኖሩ እስራኤላውያንና ክርስቲያኖች ከእግዚአብሔር ቅጣት እንዳያገኛቸው ለእርሱ በመታዘዝ መኖር እንዳለባቸው ለማስጠንቀቅ ነው።

5ኛ ጥያቄ፥ ሀ) ክርስቲያኖች የ2ኛ ነገሥትን እውነት ማወቃቸው በጣም አስፈላጊ የሚሆነው ለምን ይመስልሃል? ለ) የእግዚአብሔር ፍርድ ሳይመጣባቸው በቅድስና ይኖሩ ዘንድ ይህንን መልእክት ለቤተ ክርስቲያንህ አባሎች ለማስተማር የምትችለው እንዴት ነው?
6ኛ ጥያቄ፥ 2ኛ ነገሥት 1-8፡15 አንብብ። ሀ) በእነዚህ ዓመታት የተጠቀሱትን የተለያዩ ነገሥታት ዘርዝር። ለ) ባሕርያቸው ምን ይመስል ነበር? ሐ) ኤልሳዕ የሠራቸውን የተለያዩ ተአምራት ዘርዝር።

እንደምታስታውሰው፥ የ1ኛ ነገሥት መጨረሻና የ2ኛ ነገሥት መጀመሪያ የሚያተኩሩት ኤልያስና ኤልሳዕ በተባሉ ሁለት ነቢያት ላይ ነው። እነዚህ ሁለት ነቢያት በእስራኤል የሠሩና ሕዝቡን ወደ እግዚአብሔር ለመመለስ የጣሩ ነበሩ። የኤልያስ ታሪክ በአብዛኛው የሚገኘው በ1ኛ ነገሥት ውስጥ ነው። የሕይወቱ የመጨረሻ ታሪክ በ2ኛ ነገሥት 1-2 ውስጥ ይገኛል። 2ኛ ነገሥት 2-8 የሚያተኩረው ደግሞ በኤልሳዕ ታሪክ ላይ ነው።

1. የነቢዩ ኤልያስ የመጨረሻ ሥራና ከዚህ ዓለም መሄዱ (2ኛ ነገ. 1-2፡18)፡- በ1ኛ ነገሥት መጨረሻ ላይ አካዝያስ ስለሚባል የእስራኤል ንጉሥ ተመልክተናል። አካዝያስ የነገሠው ለሁለት ዓመታት ብቻ ሲሆን፥ ከፍተኛ ውድቀት ስላጋጠመው ታመመ፤ ስለዚህ ስለ መሞቱና በሕይወት ስለመኖሩ ለማወቅ ወደ ኤልያስ ላከ። የእግዚአብሔር ነቢይ መከበር ያለበት መሆኑንና እንደማንኛውም አገልጋይ መልእክት ተልኮበት መታዘዝ እንደሌለበት ለማሳየት፥ ኤልያስ ከሰማይ እሳት አወረደና ወደ ንጉሡ ሊወስዱት የመጡትን ሰዎች እንድትበላ አደረገ። በመጨረሻም ኤልያስ ወደ ንጉሡ ዘንድ በሄደ ጊዜ እንደሚሞት ነገረው። ከዚያ በኋላ ብዙም ሳይቆዩ ንጉሥ አካዝያስ ሞተ።

ታማኝ የሆነውን ነቢዩ ኤልያስን እግዚአብሔር አከበረው። ሄኖክ ሞትን እንዳላየ ሁሉ ኤልያስም አልሞተም። እግዚአብሔር ሰማያዊ ሰረገሎችን ልኮ ኤልያስን ወደ መንግሥተ ሰማያት አስወሰደው።

በብሉይ ኪዳን መጨረሻ፥ እግዚአብሔር መሢሑ ከመምጣቱ በፊት ኤልያስ እንደሚመለስ የተስፋ ቃል ሰጥቶ ነበር (ሚል. 4፡5 ተመልከት)። ይህ ትንቢት በመጥምቁ ዮሐንስ ተፈጽሟል(ማቴ. 11፡14)። በአዲስ ኪዳን ኤልያስ የብሉይ ኪዳን ነቢያትን በመወከል፥ በተራራ ላይ ኢየሱስ ክርስቶስን ተገናኝቶታል (ማቴ. 17፡2-8)።

2. የነቢዩ የኤልሳዕ አገልግሎት (2ኛ ነገ. 2-፡8፡15)

ከብዙ ዓመታት በፊት እግዚአብሔር፥ ኤልሳዕን ለነቢይነት እንዲጠራው ለኤልያስ ነግሮት ነበር። ኤልሳዕ ሀብታም ቤተሰቦቹን ትቶ (አባቱ ብዙ ጥማድ በሬዎችና አገልጋዮች እንደነበሩት አስተውል) ከኤልያስ ጋር ተጓዘ። ከኤልያስ ጋር በነበረበት ጊዜ ጌታን መውደድ ተማረ። ኤልሳዕ ልምድ ካለው ነቢይ ጋር አብሮ በመሥራት ለነቢይነት ሠለጠነ።

| |
|---|
| 7ኛ ጥያቄ፥ ሀ) የቤተ ክርስቲያን መሪዎችን በማሠልጠን ሥራ ውስጥ፥ አዳዲስ መሪዎችን ልምድ ካላቸው መሪዎች ጋር ቀላቅሎ ማሠልጠን እንዴት ጥሩ መንገድ ሊሆን ይችላል? ለ) የቤተ ክርስቲያንህ መሪዎች ለመሪነት የሚሠለጥኑት እንዴት ነው? ሐ) ይህ ዓይነት የማሠልጠኛ ዘዴ ተግባራዊ ሊሆን የሚችልባቸውን መንገዶች ዘርዝር። |

ከኤልሳዕ ታሪክ የሚከተሉትን ነገሮች አስተውል:-

1. ኤልያስ ሞትን ሳያይ ወደ ሰማይ በሚወሰድበት ጊዜ በማየት፣ በመንናጸፊያው የተመሰለውን የኤልያስን ኃይልና ሥልጣን ተቀበለ። ኤልያስ ከሄኖክ ቀጥሎ ሞትን ሳያይ ወደ ሰማይ የተወሰደ ሁለተኛ ሰው ነው (ዘፍ. 5፡24)።

2. ኤልሳዕ በርካታ ተአምራትን አደረገ:-

   ሀ. መራራ ውኃን አገልግሎት ላይ ሊውል ወደሚችል ንጹሕ ውኃ ለወጠ።

   ለ. በመላጣነቱ ለመቀለድ የሞከሩ ልጆችን ድብ እንዲበላቸው አደረገ።

   ሐ. የእስራኤል ነገሥታት ለነበሩት ለኢዮሳፍጥና ለኢዮራም ከሞዓባውያን ጋር ሲዋጉ ረዳቸው።

   መ. የመበለቲቱን ዘይት በመባረክ እንዳትራብ አደረገ።

   ሠ. የሱነማይቱን ልጅ ከሞት አስነሣ።

   ረ. የተመረዘ ምግብን ሊበላ ወደሚችል ንጹሕ ምግብነት ለወጠ።

   ሰ. በ20 ዳቦ 100 ሰዎችን መገበ።

   ሸ. የሶርያ ጄኔራል የነበረውን ንዕማንን ከለምጹ አነጻው።

   ቀ. ጠፍቶ የነበረው የመጥረቢያ ጫፍ በውኃ ላይ እንዲንሳፈፍ አደረገ።

   በ. ሊይዙት የመጡትን የሶርያ የጦር ኃይላትን አሳውሮ ለእስራኤል ንጉሥ አሳልፎ ሰጣቸው።

   ተ. የሶርያ ጦር ኃይል የሰማርያን ከተማ ከመከበብ እንደሚመለሱ አመለከተ።

   ቸ. ቤንሃዳድ የሚባለው የሶርያ (አራም) መሪ እንደሚሞትና በምትኩ አዛሄል የሚባለው ሰው እንደሚነግሥ አመለከተ። ራቅ ብሎ በሚገኘው የሶርያ ግዛት ውስጥ የሚገኙ ሰዎች እንኳ፣ ኤልሳዕ የእግዚአብሔር ነቢይ እንደሆነ አውቀው ነበር። ሶርያ

(አዛሄል) በእስራኤል ላይ ስለምታገኘው ድልም አስቀድሞ ተናግሮ ነበር።

| |
|---|
| 8ኛ ጥያቄ፥ ሀ) ከኤልሳዕ ታሪክ ስለ ቤተ ክርስቲያን አመራር የምናገኛቸውን መንፈሳዊ ትምህርቶች ዘርዝር። ለ) ከኤልሳዕ አገልጋይ ከሱ ምኞት የምንማረው ነገር ምንድን ነው? ሐ) ስለ መንፈሳዊ ዓይን ከኤልሳዕ፥ ከአገልጋዩና ከሶርያ የጦር ኃይል የምንማረው ነገር ምንድን ነው? |

## 2ኛ ቀን፡- 2ኛ ነገሥት 8፡16-12፡21

አንድ የተሳሳተ ውሳኔ፥ወይም ዓለምን ለማስደሰት ሲባል የሚወሰድ እርምጃ በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ ከፍተኛ ጥፋትን ሊያመጣ ይችላል። ኢዮሳፍጥ በልጁና የእስራኤል ንጉሥ በነበረው በአክዓብ ሴት ልጅ መካከል ጋብቻ እንዲፈጸም በማድረግ፥ በሁለቱ መንግሥታት መካከል ሰላምን ብቻ የፈጠረ መስሎት ነበር። ይህ ተግባር በእስራኤል ያደረጋቸውን ሃይማኖታዊ ተሐድሶዎች በሙሉ እንደሚያጠፋ አልተረዳም ነበር። ልጆቹን ሁሉ ለሞት የሚዳርግ ነገር እንደሆነ አላስተዋለም ነበር። የዳዊትን ዘር በሙሉ ሊያጠፋ የሚችል ነገር እንደነበረም አላወቀም።

| |
|---|
| 9ኛ ጥያቄ፥ በዚህም ዘመን የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የሚያደርጉት ተመሳሳይ ውሳኔ እንዴት በከፍተኛ ሁኔታ የቤተ ክርስቲያን መፍረስን ሊያስከትል እንደሚችል ምሳሌዎችን ጥቀስ። |

ምንም እንኳ አንድ የቤተ ክርስቲያን መሪ የሚያደርጋቸው ውሳኔዎች፥ ብዙውን ጊዜ በቤተ ክርስቲያኑ ላይ ከፍተኛ ለውጥ የማያስከትሉ ቢሆንም፥ ሆኖም ግን በርካታ መልካም ነገሮችን ወይም ጉዳቶችን ሊያመጡ ይችላሉ። ለምሳሌ፡- አንዳንድ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የዓለም አቀፍ አብያተ ክርስቲያናት ምክር ቤት ተብሎ በሚጠራው ኅብረት ውስጥ፥ለክርስትና አንድነት ስንል መግባት አለብን ብለው ይወስናሉ። ቤተ ክርስቲያናቸው ምስክርነቷንና መጽሐፍ ቅዱስ በእግዚአብሔር መንፈስ መሪነት የተጻፈ የእግዚአብሔር ቃል እንደሆነ የተቀበለችውን እምነት እንድታጣ ያደርጋሉ። ይህን መሰሉ እርምጃ ብዙ ክርስቲያኖች ወደ መንግሥተ ሰማያት የሚያደርሱ መንገዶች በርካታ ናቸው፤ በኢየሱስ ላይ ያለ እምነት ብቻ አይደለም ወደሚል እምነት

እንዲያመሩ አድርጎአቸዋል። ይህም ማለት ዛሬ ራሳቸውን ክርስቲያን ብለው የሚጠሩ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ክርስቲያኖች ኢየሱስን የማያውቁና ያልዳኑ ሰዎች ናቸው። አንዳንድ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ከትርፍ ገንዘብ ለራሳቸው ጥቅምን ያገኙ ዘንድ የልማት ሥራን ለመጀመር ፈጥነው መወሰናቸው፥ ወደ ቤተ ክርስቲያን ክፍፍል፥ የቤተ ክርስቲያን ተቀዳሚ ተግባር ምን እንደሆነ ወደ አለመረዳት፥ በአንዳንድ ሁኔታዎች ለእግዚአብሔር ያላቸውን ፍቅር ሁሉ ወደ መቀነስ አድርሶአቸዋል። የልማት ሥራ ወንጌልን ለማስፋፋት መሣሪያ ሊሆን ቢችልም፥ በሚገባ ካልተያዘ ቤተ ክርስቲያንን ለማፍረስ፥ ወይም የቤተ ክርስቲያን ተቀዳሚ ኃላፊነቷ ከሆነው ከወንጌል ሥራና ከማስተማር አገልግሎት ፈቀቅ እንድትል ዋና የሰይጣን መሣሪያ ሊሆን ይችላል።

| |
|---|
| 10ኛ ጥያቄ፥ 2ኛ ነገ. 8፡16-12፡21 አንብብ። ሀ) በዚህ ክፍል የተጠቀሱ የተለያዩ ነገሥታትን ዘርዝር። ለ) የእያንዳንዱን ንጉሥ ባሕርይ ዘርዝር። ሐ) እያንዳንዱ ንጉሥ በነገሠበት ጊዜ ስለ ተፈጸሙት ዋና ዋና ጉዳዮች ግለጥ። መ) የኢዮሳፍጥ ውሳኔ የይሁዳን መንግሥት ሊያጠፋ የነበረው እንዴት ነው? |

1. ኢዮራም፡- የይሁዳ ንጉሥ (848-841 ዓ.ዓ.)

ኢዮራም ከአባቱ ከኢዮሳፍጥ ጋር ተባባሪ መሪ ሆኖ የሠራ ቢሆንም፥ ሥልጣን ሙሉ ለሙሉ ለመጨበጥ የበቃው ግን አባቱ ከሞተ በኋላ ነው። ኢዮሳፍጥ ሲሞት፥ ኢዮራም ከአባቱ የመንግሥት አስተዳደር መመሪያ ዞር በማለትና ስድስት ወንድሞቹን በመግደል መንግሥቱን ደም በማፍሰስ ጀምሯል። ሕዝቡም ወደ ጣዖት አምልኮ እንዲመለሱ አድርጓል። እንደምታስታውሰው፥ ይህ ሰው ያገባው የበአልን አምልኮ ወደ እስራኤል ያመጡትን የአክዓብንና የኤልዛቤልን ሴት ልጅ ነበር። በሚስቱ በጎቶልያና በአባቱ በአክዓብ ተጽዕኖ የበአልን አምልኮ ወደ ይሁዳ አስገባ፤ እንዲሁም በይሁዳ ከተሞች ዙሪያ የነበሩትን የጣዖት ማምለኪያ ስፍራዎች አደሰ።

በኢዮራም ዘመነ መንግሥት፥ የይሁዳ መንግሥት መዳከም ጀመረ። ኤዶማውያን በይሁዳ ላይ ዓመፁ። ፍልስጥኤማውያንና ዓረቦችም ኢየሩሳሌምን በማጥቃት ብዙ ብዝበዛ ከማድረጋቸውም በላይ በርካታ የንጉሣውያን ቤተሰብ አባሎችን ማርከው ወሰዱ።

ኢዮራም በከፉ ደዌ ተመትቶ ሞተ። ሕዝቡ ግን እጅግ ስለጠላው፥ በይሁዳ ነገሥታት መቃብር አልተቀበረም።

2. የይሁዳ ንጉሥ አካዝያስ (841 ዓ.ዓ.)

ከማንኛውም የይሁዳ ንጉሥ ያነሰ አጭር ጊዜ የገዛው አካዝያስ ነበር። በሥልጣን ላይ የቆየው ለአንድ ዓመት ብቻ ነበር። በእናቱ በጎቶልያ ተጽዕኖ አባቱ በጀመረው መንገድ የጣዖትና የበአልን አምልኮ ለማካሄድ ሳይገደድ አልቀረም። እንዲሁም የእስራኤል ንጉሥ በነበረው በአጎቱ በኢዮራም ማበረታቻና ምክር ሶርያን ለመውጋት ከእስራኤል ጋር ተባበረ። አካዝያስ ኢዮራምን ለመጎብኘትና ከእርሱ ጋር በመተባበር ለመዋጋት ሲሄድ፥ ኤልዛቤልንም ሆነ ኢዮራምን በመግደል ሥልጣን ከያዘው ከኢዩ ጋር ተገናኙ። ኢዩም አካዝያስንና በርካታ የይሁዳ ገዥዎችን ገደለ (2ኛ ዜና 22፡7-9)።

3. የእስራኤል ንጉሥ ኢዩ (841-753 ዓ.ዓ.)

በሰሜኑ የእስራኤል መንግሥት ለረጅም ጊዜ የቆየው፥ የኢዩ ሥርወ መንግሥት ነበር።

ኢዩ ሥልጣንን በያዘ ጊዜ፥ የእስራኤል መንግሥት በጣም የተዳከመ ቢሆንም በከፊል እንደገና ሊያጠናክረው ችሎ ነበር።

ኢዩ ቀጣዩ የእስራኤል ንጉሥ እንደሚሆንና የአክዓብን ቤት እንደሚያጠፋ በነቢዩ ኤልሳዕ ተነግሮት ነበር። ኢዩ የጦሩ አዛዥ ስለ ነበር፥ ኢዮራምንና ኤልዛቤልን ከሥልጣናቸው ለማስወገድ ቻለ። ይህ ሰው በጣም ደም የተጠማ ሰው ነበር። የአክዓብን 70 ልጆች ገድሏል። የእስራኤል ንጉሥ የነበረውን ኢዮራምን፥ የእስራኤልን ንግሥት ኤልዛቤልና የይሁዳን ንጉሥ አካዝያስን ገደለ። ይህን በማድረጉ የኤልሳዕ ትንቢት እንዲፈጸም አደረገ። በተጨማሪ የበአል ነቢያትንም ገደለ። ከብዙዎቹ የእስራኤል ነገሥታት የተሻለ ቢሆንም እንኳ በእስራኤል ምድር የነበረውን የጣዖት አምልኮ ስላላጠፋ፥ እርሱም ክፉ መሪ ነበር።

በኢዩ ዘመነ መንግሥት በአሦርና በሶርያ መካከል ጦርነት ነበር። ኢዩ ለአሦር ግብር ሰጠ። በኋላ ግን ሶርያ በአሦር ላይ የበላይነቱን ልታገኝና አንዳንዱን የእስራኤል ምድር ወርራ ለመያዝ ችላ ነበር።

4. የይሁድ ንግሥት የነበረችው ጎቶልያ (841-835 ዓ.ዓ.)

በእስራኤልም ሆነ በይሁዳ ለመግዛት የቻለች ብቸኛ ሴት ንግሥት ጎቶልያ ነበረች። እርሷ የአክዓብና የኤልዛቤል ልጅ ነበረች። አካዝያስ በኢዩ እጅ በተገደለ ጊዜ የይሁዳን መንግሥት ለማስተዳደር የቀሩ ንጉሣውያን ቤተሰቦች በጣም ጥቂት ነበሩ፤ ስለዚህ ጎቶልያ ዙፋኑን ወረሰችና ለ6 ዓመታት ገዛች። የእርሷ አስተዳደር ብዙ ደም የፈሰሰበት ነበር። በይሁዳ ዙፋኑ ይገባኛል የሚል ማንኛውንም ሰው በመግደል የዳዊትን ዝርያዎች ለማጥፋት ሞከረች። በኢዮሳፍጥ የተደረገውን ተሐድሶ የተመለከተው ካህኑ ዮዳሄ ግን የአካዝያስን ከሁሉም ታናሽ የሆነውን ልጅ ኢዮአስን በቤተ መቅደስ ሸሸገው። ስድስት ዓመት ከሸሸገው በኋላም የጦሩን አዛዥ ጠርቶ ገና የሰባት ዓመት ልጅ ቢሆንም እንኳ በይሁዳ ላይ ንጉሥ ሆኖአል ብለው በአንድነት አወጁ። ጎቶልያ በሕዝቡ ዘንድ የተጠላች ስለነበረች የጦሩ አዛዦች ኢዮአስ ንጉሥ እንዲሆን በመስማማት ጎቶልያን ገደሏት።

5. የይሁዳ ንጉሥ ኢዮአስ (835-796 ዓ.ዓ.)

ኢዮአስ መንገሥ በጀመረ ጊዜ ገና የሰባት ዓመት ልጅ ነበር። ኢዮአስን በቤተ መቅደስ ያሳደገው ሊቀ ካህኑ ዮዳሄ የቅርብ አማካሪው ነበር፤ ስለዚህ ኢዮአስ ከይሁዳ ምድር የበአል አምልኮንና ሌሎች የጣዖት አምልኮዎችን ሁሉ እንዲያስወግድ ዮዳሄ አበረታታው። በአብዛኛው የሥልጣን ዘመኑ ኢዮአስ እግዚአብሔርን ተከተለ።

በዮዳሄ አመራር የይሁዳ ሕዝብ ለእግዚአብሔር ለመታዘዝ ያላቸውን ፈቃደኝነት አረጋገጡ። ቃል ኪዳንቸውንም ከእግዚአብሔር ጋር አደሱ። ኢዮአስ ቤተ መቅደሱንም ማደስ ጀመረ። እግዚአብሔርን በማይፈሩ መሪዎች ዘመን ለመጠገን አስቸጋሪ እስኪሆን ድረስ ፈራርሶ የነበረው ቤተ መቅደስ እንዲሠራ ሕዝቡ ገንዘብ ማዋጣት ጀመሩ።

ሆኖም ሕዝቡ ከእግዚአብሔር ጋር ባደሱት ቃል ኪዳን ብዙ አልቆየም። የሚያሳዝነው ነገር ኢዮአስ ለመንፈሳዊ አመራር በዮዳሄ ላይ ተደገፈ እንጂ፥ እርሱ ራሱ በእምነቱ ጠንካራ አልነበረም፤ ስለዚህ ዮዳሄ እንደሞተ ወዲያውኑ ሕዝቡ በእግዚአብሔር ላይ ዓመፁና ወደ ጣኦት አምልኮ ተመለሱ። ኢዮአስ ራሱም ጣዖት ማምለክ ጀመረ። በቤተ መቅደስ ኢዮአስን ያሳደገው የካህኑ የዮዳሄ ልጅ የነበረው ዘካርያስም፥ ኢዮአስ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ መተላለፍ መልካም እንደማይሆን በማመልከት እንደገና አስጠንቀቃቸው። ኢዮአስ ግን በእግዚአብሔር ቤት

አደባባይ ውስጥ በድንጋይ ተወግሮ እንዲገደል አስደረገ (2ኛ ዜና 24፥ 17-22)።

ኢዮአስ እግዚአብሔርን ስለተወ፥ በሕይወቱ ላይ መከራን አመጣ። ለሶርያ መንግሥት ግብር ለመክፈል ተገደደ። በኋላም ግብሩን መክፈል ሲያቆም፥ የሶርያ ኃይል በጉልበት ወደ ኢየሩሳሌም በመግባት ከኢዮአስ ጋር ተዋጋ። ኢዮአስ በውጊያው ቆስሎ በተኛ ጊዜም የገዛ አገልጋዮቹ ተማምለውበት በአልጋው ላይ ሳለ ገደሉት። ይህም በዘካርያስ ላይ የፈጸመውን በደል ለመበቀል ነበር።

| |
|---|
| 11ኛ ጥያቄ፥ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ስለሚኖር መንፈሳዊ መሪነት ከእነዚህ ቁጥሮች ምን እንማራለን? |

## 3ኛ ቀን፡- 2ኛ ነገሥት 13-17

ሕይወትንና ቤተ ክርስቲያንን በሚመለከት አንዱ አስደናቂ ነገር የሰው ተፈጥሮአዊ ዝንባሌ ከሕይወት ወደ ሞት መሆኑ ነው። በሰው አነጋገር፥ እኛ የምንጓዘው ከሕይወት ወደ ሞት ነው። ቤተ ክርስቲያንም እንዲሁ ከሕይወት ወደ ሞት ለማዝገም ትሻለች። ለመከላከል አስቸጋሪ የሆነ የመፈራረስ ሂደት አለ። በመንፈሳዊ አባባል ደግሞ ይህ ሂደት ለእግዚአብሔር ካለን ፍቅር ወደ ሥርዓታዊ የሃይማኖት ልማድ፥ በመጨረሻም ቤተ ክርስቲያን ሙት ወደምትሆንበት ሁኔታ ያደርሳል። ይህ ሂደት ብዙ ዓመታት የሚወስድ ቢሆንም እንኳ ለማቆም ግን አስቸጋሪ ነው። ይህ ዝንባሌ ያለማቋረጥ ልንዋጋውና ልንታገለው እንደሚገባ ኃይለኛ የስበት ኃይል እንዳለው ማግኔት ነው። ይህ ሲሆን ብቻ ነው ለእግዚአብሔር የነበረንን የመጀመሪያ ግላዊ ፍቅር ልንጠብቅና እንደ ቤተ ክርስቲያን ያለማቋረጥ ልናድግ፥ ልንለምድና ለእግዚአብሔር ክብር ልንሠራ የምንችለው።

| |
|---|
| 12ኛ ጥያቄ፥ ሀ) በሕይወትህ ይህንን ወደ መንፈሳዊ ሞት የሚወስደውን ዝንባሌ እንዴት ተመለከትከው? ለ) በቤተ ክርስቲያንህ ውስጥ ይህን ዝንባሌ የምታየው እንዴት ነው? |

የእስራኤልና የይሁዳ ነገሥታትን በምንመለከትበት ጥናታችን፥ በመበላሸትና በመፈራረስ ወደ መንፈሳዊ ሞት የሚወስደውን ተፈጥሮአዊ ዝንባሌ መመልከት እንችላለን። ምንም እንኳ እግዚአብሔርን የሚፈሩ መሪዎች ሕዝቡን ወደተገቢውና በእግዚአብሔር ላይ ወዳለው ትክክለኛ

አምልኮ ለመምራት ቢሞክሩም፥ ሕዝቡ ወደ ጣዖት አምልኮ ለመመለስ ብዙ ጊዜ አይወስድባቸውም ነበር። በኃጢአት መውደቅና ከጌታ መራቅ ቀላል ነገር ነው። መንፈሳዊ መሠረታችንን እንደገና መገንባት ግን ብዙ ጊዜ በጣም አስቸጋሪ ነው።

| |
|---|
| 13ኛ ጥያቄ፥ 2ኛ ነገሥት 13-17 አንብብ። ሀ) በእነዚህ ቁጥሮች የተጠቀሱትን ነገሥታት ዘርዝር። ለ) ስለ መንፈሳዊ ሕይወታቸው ሥዕላዊ መግለጫ ስጥ። ሐ) በነገሡበት ዘመን ስለተፈጸሙ ዋና ዋና ነገሮች ጥቀስ። መ) እግዚአብሔር በእስራኤል ላይ በመፍረድ አይሁድን ወደ ምርኮ እንዲሄዱ ያደረገበት ምክንያት ምንድን ነው? |

1. የእስራኤል ንጉሥ ኢዮአካዝ:- (814-798 ዓ.ዓ.)

የኢዮአካዝ ዘመን ለእስራኤል በጣም አስቸጋሪ ነበር። አዛሄል የተባለው የሶርያ ንጉሥ ያለማቋረጥ እነርሱን የጨቆነበትና በሰሜኑ መንግሥት ክልል ውስጥ ከፊሉን መሬት የወረረበት ጊዜ ነበር። እንደ ኤዶም፥ አሞንና ፍልስጥኤም ያሉ ሕዝቦች እስራኤልን ያጠቁበትም ጊዜ ነበር።

በመጨረሻም ኢዮአካዝ እጅግ ተስፋ ቆርጦ ፊቱን ወደ እግዚአብሔር መለሰና ከእርሱ እርዳታን ጠየቀ። እግዚአብሔርም ጸሎቱን ሰምቶ ረዳውና የእስራኤልን ምድር በእንግዳ መንግሥት ሙሉ ለሙሉ ከመወሰድ ጠበቀው።

ኢዮአካዝ እግዚአብሔር ቢረዳውም እንኳ ሙሉ ለሙሉ እርሱን አልተከተለም። ይልቁንም ከብዙ ዓመታት በፊት በቀዳማዊ ኢዮርብዓም የተጀመረውን የጣዖት አምልኮ ቀጠለ።

2. የእስራኤል ንጉሥ ዮአስ:- (798-782 ዓ.ዓ.)

በዮአስ ዘመነ መንግሥት፥ የሶርያ ንጉሥ የነበረው አዛሄል ስለ ሞተ፥ እስራኤላውያን ከሶርያውያን ይደርስባቸው የነበረው ጭቆና ቀነሰ። ኤልሳዕ ብርቱ ደዌ ታሞ ከሞት አፋፍ ላይ ደርሶ በነበረበት ጊዜ ዮአስ ወደ እርሱ መጣ። ንጉሥ ዮአስ እግዚአብሔርን የማይከተል መሪ ቢሆንም እንኳ፥ የእግዚአብሔር ኃይላት በሙሉ ከእርሱ ጎን እንደሆኑና ኤልሳዕ የእግዚአብሔር ሰው እንደሆነ የተገነዘበ መሪ ነበር። ለዚህ ነው ኤልሳዕን «የእስራኤል ሰረገላና ፈረሰኞች» ብሎ የጠራው። እውነተኛው የእስራኤል

ጦር እግዚአብሔር ነበር እንጂ ሌላ ሥጋዊ ጦር አልነበረም። ኤልሳዕ የሶርያን ጦር ሽንፈት አስቀድሞ ተናግሮ ነበር። እስራኤልም ሶርያን ለማሸነፍና ከሰሜኑ የእስራኤል ክፍል የወሰደችውን ግዛት ሁሉ ለማስመለስ ችላ ነበር፤ በተጨማሪ ዮአስ ኤዶምንም ለማሸነፍ ችሎ ነበር።

በዮአስ ዘመነ መንግሥት በይሁዳ ንጉሥ ከነበረው ከአሜስያስ ጋር ጦርነት ተደርጎ ነበር። የእስራኤል ጦር ይሁዳን ለማሸነፍና የኢየሩሳሌምን ቅጥር የተወሰነ ክፍል ለመደምሰስ ችሎ ነበር።

ዮአስ እንደቀሩት የእስራኤል ነገሥታት ሁሉ፥ የጣዖት አምልኮውን ቀጠለ። እግዚአብሔርን ለመፍራትና ለእርሱ ለመታዘዝም አልቻለም።

3. የይሁዳ ንጉሥ አሜስያስ (796-767 ዓ.ዓ.)

አሜስያስ በይሁዳ ላይ ለብዙ ዓመታት የነገሠ ቢሆንም፥ አብዛኛውን የሥልጣን ዘመኑን ያጠፋው ከልጁ ከዖዝያን ጋር ነበር። በአሜስያስ ዘመነ መንግሥት ይሁዳ በጣም ብርቱ ነበረች። ኤዶምንም ለማሸነፍ ችለው ነበር። ኤዶምን ካሸነፉ በኋላ ግን አሜስያስ ከኤዶም ጣዖትን አስመጣና በኢየሩሳሌም በማቆም አመለከው። ስላገኘው ድል ለእግዚአብሔር ክብርን ከመስጠት ይልቅ ጣዖትን አከበረ።

ቆይቶም አሜስያስ ባለማስተዋል ከእስራኤል ጋር ጦርነት ጀመረና ተሸነፈ (791-790 ዓ.ዓ.)። በዚህ ጊዜ አሜስያስ እስረኛ የነበረና የእስራኤል ንጉሥ የነበረው ዮአስ እስኪሞት ድረስ እንደገና ወደ ሥልጣኑ ለመመለስ ያልቻለ ይመስላል። በእርሱ ምትክ ግን ልጁ ዖዝያን ነግሦ ነበር። በኋላ ግን አሜስያስ ከእስሩ ተለቀቀና ወደ ይሁዳ ተመለሰ። ሕዝቡ ግን ጠልተውት ስለ ነበር ሊገድሉት አሴሩበት። አሜስያስ በዚህ ምክንያት ሸሽቶ ወደ ላኪሽ ከተማ ቢሄድም፥ ያሴሩበት ሰዎች ተከታትለው ገደሉት።

አሜስያስ የጣዖት አምልኮን የሚከተል ክፉ ንጉሥ ነበር።

4. የእስራኤል ንጉሥ ዳግማዊ ኢዮርብዓም (793-753 ዓ.ዓ.)

ከዓለም ታሪክ አመለካከት፥ ዳግማዊ ኢዮርብዓም በሰሜኑ የእስራኤል መንግሥት ከነበሩት ታላላቅ ነገሥታት አንዱ ነበር። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ግን ስለ እርሱ የተነገረው ነገር በጣም ጥቂት ነው። ምክንያቱም የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፊዎች ፍላጎት መንፈሳዊ ታላቅነትን መግለጽ እንጂ

የፖለቲካ ዝናን ወይም ችሎታን ማሳወቅ አይደለም። ዳግማዊ ኢዮርብዓም የእግዚአብሔር ሰው ስላልነበረ፥ መጽሐፍ ቅዱስ አያመሰግነውም። በእስራኤል ላይ ለመንገሥ የመጀመሪያው በነበረው በቀዳማዊ ኢዮርብዓም የተጀመረውን የጣዖት አምልኮ ማካሄዱን ቀጠለ።

ከዳዊትና ከሰሎሞን ዘመነ መንግሥት በኋላ እጅግ ሰላምና ብልጽግና የሞላበት፥ ለእስራኤል መልካም የነበረ ጊዜ የዳግማዊ ኢዮርብዓም ዘመነ መንግሥት ነበር። በሰሜን በኩል አንዳችም ኃያል መንግሥት ስላልነበረ፥ ኢዮርብዓም ፖለቲካዊ ተጽዕኖውን እስከ ኤፍራጥስ ወንዝ ድረስ ለማስፋፋት ችሎ ነበር። እስራኤልም እጅግ ባለጠጋ መንግሥት ሆና ነበር። ከዮርዳኖስ ወንዝ በስተምሥራቅ ያለውን የሶርያን ምድርም ወሰደች።

ሆሴዕና አሞጽ የተባሉት ነቢያት ያገለገሉት በዳግማዊ ኢዮርብዓም ዘመነ መንግሥት ነበር። በምድሪቱ ውስጥ ከፍተኛ ብልጽግና የነበረ ቢሆንም፥ በሀብታምና በድሀ መካከል ከፍተኛ የሆነ የፍርድ አድልዎ ነበር። የሕዝቡ ሥነ - ምግባርም በእጅጉ ድቀት ይታይበት ነበር። ለእግዚአብሔር ባላቸው አምልኮም ግድ የለሾች ነበሩ።

---

14ኛ ጥያቄ፥ ብልጽግና፥ ወደ ፍርድ መዛባት፥ ወደ ሥነ - ምግባር ድቀት በእግዚአብሔር ላይ ወዳለ የአምልኮ ግድየለሽነት የሚያመራው እንዴት ነው?

---

ከዳግማዊ ኢዮርብዓም ዘመነ መንግሥት በኋላ፥ በ722 ዓ.ዓ. እስከተደመሰሰች ድረስ የእስራኤል ብሔር ፈጥና መፈራረስ ጀመረች።

5. የይሁዳ ንጉሥ አዛርያ (ዖዝያን) (791-740 ዓ.ዓ.)

ከዳዊትና ከሰሎሞን ዘመነ መንግሥት በኋላ፥ በይሁዳ ከነገሡ ታላላቅ ነገሥታት አንዱ ዖዝያን ወይም አዛርያ ነው። ጥሩ የፖለቲካ መሪ መሆኑ ብቻ ሳይሆን፥ እግዚአብሔርን የሚፈራና የሚያመልከም ነበር።

ዖዝያን በትረ መንግሥቱን በጨበጠ ጊዜ፥ የይሁዳ መንግሥት በጣም ደካማ ነበር። ለእስራኤልና ለሶርያ አገልጋይ ነበር። ከዮአስ ሞት በኋላ ግን ይሁዳ ከእስራኤል ጋር መልካም ግንኙነት ነበራት። ዖዝያን የይሁዳን ጦር እንደገና መመሥረት ችሎ ነበር። እንደዚሁም ፍልስጥኤማውያን፥ ዓረቦችንና አሞናውያንን ለማሸነፍም ችሎ ነበር።

ከዚህ ቀደም በሰሎሞን ጊዜ ብቻ እንደሆነው፥ ሕዝቡን ባለጸጋና በዚህም ተደስተው የሚኖሩ አደረጋቸው።

በዘመን መንግሥቱ መጀመሪያ አካባቢ ዖዝያን እግዚአብሔርን አጥብቆ ተከተለ። እጅግ ባለጸጋ የሆነውም እግዚአብሔርን ስለተከተለና የእርሱን ትእዛዛት ስለ ጠበቀ ነበር (2ኛ ዜና 26፡5-7)።

በሥልጣንና በዝና እጅግ ከፍ ባለ ጊዜ ግን ታበየ። ካህናቱ ቢከለክሉትም እንኳ እምቢ ብሎ ወደ ቤተ መቅደስ በመግባት፥ ለካህናት ብቻ የተፈቀደውን ዕጣን በመሠዊያው ላይ የማጠን ሥርዓትን ፈጸመ። ይህ በእግዚአብሔር ትእዛዝ ላይ የማመፅና ትዕቢትን የማሳየት ግልጥ ድርጊት ነበር። የእግዚአብሔር ፍርድ በዚህ ድርጊቱ ምክንያት ፈጣንና ኃይለኛ ቅጣትን መላክ ነበር። ዖዝያን ወዲያውኑ በለምጽ ተመታ። ይህም በሕይወቱ ላይ ዐበይት ውጤቶችን አስከተለ። ሞትን ባይሞትም እንኳ ከሕዝቡ ሁሉ ጋር እንዳይገናኝ ተገለለ። በቤተ መንግሥቱ ውስጥም ለመኖር አይችልም ነበር። ወደ ቤተ መቅደሱ ለአምልኮ እንደገና መሄድ ጨርሶ አይችልም ነበር። በዚህ ጊዜ ነበር ልጁ ኢዮአታም በይሁዳ ላይ ተባባሪ ገዥ የሆነው። በዖዝያን ዘመነ መንግሥት መጨረሻ አካባቢ የአሦር መንግሥት በኃይሉ እጅግ ገናና እየሆነ ሄደ። ከአሦር ጋር ለመዋጋትና ለማሸነፍ ቢሞክርም አልሆነለትም። ተሸነፈ። ከዖዝያን ሞት በኋላም የይሁዳ መንግሥት ብርታት በፍጥነት እየቀነሰ መጣ።

ዖዝያን ለ52 ዓመታት የነገሠ ቢሆንም፥ ብቻውን በንጉሥነት ሥልጣን ላይ የቆየው ግን ለ17 ዓመታት ብቻ ነበር። ከዚህ ቀጥሎ ከይሁዳ ታላላቅ ነገሥታት አንዱ የነበረው የዖዝያን ዘመነ - መንግሥት ዋና ዋና ዓመታት ተጠቅሰዋል፡-

797 ዓ.ዓ. አሜስያስ መንገሥ ጀመረ።

791 ዓ.ዓ. ዖዝያን ከአሜስያስ ጋር ይገዛ ጀመር።

768 ዓ.ዓ. ዖዝያን ለብቻው መንገሥ ጀመረ።

750 ዓ.ዓ. ዖዝያን በለምጽ ስለተመታ ኢዮአታም ከእርሱ ጋር መንገሥ ጀመረ።

740 ዓ.ዓ. ዖዝያን ሞተ።

**15ኛ ጥያቄ፥ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በሚሰምርላቸው ጊዜ በትዕቢት የመውደቅ አደጋ ከፊታቸው እንዳለ፥ ከዖዝያን ሕይወት ምን ለመማር እንችላለን?**

5. የእስራኤል ንጉሥ ዘካርያስ (753 ዓ.ዓ.)

ዘካርያስ በእስራኤል ላይ ለረጅም ጊዜ ለመንገሥ አልቻለም። ለስድስት ወራት ሥልጣኑን ከተቆጣጠረ በኋላ በሻሎም ተገደለ።

6. የእስራኤል ንጉሥ ሻሎም (752 ዓ.ዓ.)

የዳግማዊ ኢዮርብዓም ልጅ የነበረውን ዘካርያስን ገድሎ በሥልጣን ላይ ከወጣ ከአንድ ወር በኋላ በምናሔም ተገደለ።

7. የእስራኤል ንጉሥ ምናሔም (752-741 ዓ.ዓ.)

ምናሔም በእስራኤል ላይ ለ10 ዓመታት ለመንገሥ ቢችልም፥ ዘመነ መንግሥቱ በጣም አስቸጋሪ ከነበሩት ጊዜያት አንዱ ነው። በዚህ ጊዜ የአሦር ኃይል ስለ ጨመረ፥ ጥቃት እንዳይደርስበት ከፈለገ ለአሦር ንጉሥ ቀረጥ የመክፈል ግዴታ ነበረበት።

8. የእስራኤል ንጉሥ ፈቃሕያ (741-739 ዓ.ዓ.)

የምናሔም ልጅ የነበረው ፈቃሕያ የመንግሥት ሥልጣን በያዘ ጊዜ፥ የእስራኤል መንግሥት በአሦር መንግሥት ቁጥጥር ሥር ሆኖ አገልጋዩ ነበር። ስለዚህ ፈቃሕያ ብዙ ኃይል አልነበረውም። በእነዚህ ጊዜያት በመንግሥት ሥልጣን ውስጥ ከነበሩት ሰዎች አንዳንዶቹ በአሦር መንግሥት ቁጥጥር መሆናቸውን አይወዱትም ነበር። ከእንደነዚህ ዓይነት ሰዎች አንዱ ፋቁሔ እንደነበር የማያጠራጥር ነው። ፋቁሔ ፈቃሕያን ገደለና የሚቀጥለው የእስራኤል ንጉሥ ሆነ።

9. የእስራኤል ንጉሥ ፋቁሔ (739-731 ዓ.ዓ.)

በፋቁሔ ዘመነ መንግሥት ሶርያ ዋናዋ ኃያል መንግሥትና ለእስራኤል መንግሥት ፈተና ነበረች። የሶርያ ኃያል መሆን ለፋቁሔ የፀረ አሦር አቋም ትልቅ እርዳታ ሆኖት ነበር። ረአሶን የተባለው የሶርያ ንጉሥም አሦርን ለመውጋት ከእስራኤልና ከይሁዳ ሕዝቦች ጋር የጦር ቃል ኪዳን ትብብር ለማድረግ ሞክሮ ነበር። ይሁዳ ይህን ትብብር (ፌዴሬሽን) ለመቀበል ሳትፈቅድ ስትቀር፥ ሶርያና እስራኤል በመተባበር

ይሁዳን ወጉ። በዚህም ጦርነት ከኢየሩሳሌም በቀር ሌላው የይሁዳ ግዛት በሙሉ በእነርሱ እጅ ወደቀ። በመጨረሻም አካዝ የአሦርን እርዳታ በጠየቀ ጊዜ የሶርያና የእስራኤል ኃይሎች ወደ ግዛታቸው መመለስ ግድ ሆነባቸው።

ኢየሩሳሌም ሙሉ በሙሉ ያልተጠቃችበት ሁለት ምክንያቶች ነበሩ፡-

1. እግዚአብሔር በእስራኤል ላይ እንደሚፈርድ አንድ ነቢይ የእስራኤልን ንጉሥ አስጠንቀቀው።

2. የይሁዳ ንጉሥ የነበረው አካዝ የአሦርን እርዳታ ለመነ፤ ስለዚህ የአሦር ንጉሥ የነበረው ቴልጌልቴልፌልሶር ሶርያን አጠቃ። በ732 ዓ.ዓ. የሶርያ ዋና ከተማ የነበረችው ደማስቆ ተደመሰሰችና አሦር ሶርያን ተቆጣጠረች።

በዚህ ጊዜ የአሦር መንግሥት እስከ እስራኤል ድንበር ድረስ ምድሪቱን ስለ ተቆጣጠረና የእስራኤልን መንግሥት ለማጥቃት የተዘጋጀ ስለ መሰለ፥ በመንግሥቱም ውስጥ የፀረ አሦር አስተዳደር ማካሄድ ተቀባይነት ሊኖረው አይችልም ነበር። ስለዚህ ፋቁሔ በሆሴዕ መሪነት ተገደለ።

እስራኤል የምትጠፋበት ጊዜ የቀረበ ቢሆንም የእግዚአብሔር ሕዝብ ግን ወደ እርሱ አልተመለሱም ነበር፤ ይልቁንም እስከመጨረሻው ድረስ የጣዖት አምልኮአቸውን ቀጠሉ።

10. የይሁዳ ንጉሥ የነበረው ኢዮአታም (750-732 ዓ.ዓ.)

ኢዮአታም መንገሥ የጀመረው ከአባቱ ጋር በአንድነት ሲሆን፥ ጠቅላላ አመራሩን ለብቻው የወሰደው ግን በ740 ዓ.ዓ. ነበር። ኢዮአታም የአባቱን የዖዝያንን የአመራር ፈለጎች (ፖሊሲዎች) የተከተለ ቢሆንም ለብቻው ለመግዛት የቻለው ግን ለ4 ዓመታት ብቻ ነበር። በቤተ መቅደስ ይካሄድ የነበረውን አምልኮ ደገፈ። ቀደም ሲል በይሁዳ የነበሩትን ጣዖታት ለማጥፋት ግን ቁራጥ አልነበረም።

ኢዮአታም አሦርን ለመደገፍ አልፈለገም። የይሁዳ መሪዎች ግን የአሦርን ኃይል መዳበር እየፈሩ ሲመጡ፥ ከአሶር ጋር በሰላም ለመኖር ፈለጉና ልጁን አካዝን የኢዮአታም ተባባሪ መሪ አደረጉት። በዘመነ

መንግሥቱ መጨረሻ አካባቢም ከእስራኤልና ከሶርያ በኩል ችግር ገጥሞት ነበር።

## 11. የይሁዳ ንጉሥ አካዝ (735-716 ዓ.ዓ.)

አካዝ አባቱ በሥልጣን ላይ በነበረ ጊዜ እርሱም ወደ መንግሥት ሥልጣን የመጣው የአሦር ደጋፊ ስለነበረ ነው። አሦርን ለመውጋት ሶርያና እስራኤል እንዲተባበራቸው በጠየቁት ጊዜ እምቢ በማለቱ፥ እስራኤልና ሶርያ ይሁዳን አጠቁና ከይሁዳ በሺህ የሚቆጠሩ ሰዎችን ወደ ምርኮ ወሰዱ። ስለዚህ እርዳታ ለመጠየቅ ተወካዮቹን ወደ አሦር ላከ። አሦርም ሶርያን አጠቃችና ደማስቆን አጠፋች። እስራኤላውያንም ከይሁዳ እንዲወጡ አደረጉ። አካዝም ለአሦር መንግሥት ለመገበር ተገደደ።

አካዝ የአባቱን መመሪያዎች ተቃረነ። ጣዖት አምላኪና በይሁዳ ከነገሡት እጅግ ክፉ ነገሥታት አንዱ ነበር። አካዝ ልጁን እንኳ ለጣዖት አምልኮ የሠዋ ሰው እንደሆነ ተጽፏል። አካዝ የአሦርን ንጉሥ ለመገናኘት ወደ ደማስቆ ሄደ። እዚያ እያለ አንድ ትልቅ የጣዖት መሠዊያ ያያል። የዚህን የጣዖት መሠዊያ ተመሳሳይ ያሠራና በኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ ውስጥ ያኖረዋል። ከዚህ በኋላም ለእግዚአብሔር ሳይሆን ለሌሎች የውሸት አማልክት በዚህ መሠዊያ ላይ መሥዋዕትን ያቀርቡ ዘንድ ሕዝቡን ያበረታታቸዋል።

የሰሜኑ የእስራኤል መንግሥት ወደ ምርኮ የተወሰደው አካዝ በይሁዳ ላይ ሥልጣን በነበረው ጊዜ ነበር። አካዝ እግዚአብሔርን ብቻ ያመልክ ዘንድ ለእርሱም ይታዘዝ ዘንድ ከእስራኤል ውድቀት አልተማረም። ነቢዩ ኢሳይያስ ያገለገለውና በእግዚአብሔር ላይ ይታመን ዘንድ አካዝን ለማበረታታት የሞከረው በዚህ ሰው ዘመነ መንግሥት ነበር። አንዳንዶቹ ትላልቅ የኢሳይያስ ትንቢቶች የተሰጡትም በዚህ ዘመን ነበር (ለምሳሌ፡- ኢሳ. 7፡14፤ 9፡6-7)።

## 12. የእስራኤል ንጉሥ ሆሴዕ (731-722 ዓ.ዓ.)

ሆሴዕ ሥልጣን የያዘው የእስራኤል ንጉሥ የነበረውን ፋቁሔን በመግደል ነበር። ሆሴዕ ሥልጣን በያዘ ጊዜ ደማስቆ በአሦር እጅ የወደቀች ሲሆን፥ እስራኤልም የአሦር አገልጋይ ሆና ነበር። ከጥቂት የእስራኤል ግዛት በስተቀር አብዛኛው የእስራኤል ግዛት በአሦር ቁጥጥር ሥር ሆኖ ነበር።

በ727 ዓ.ዓ. የአሦር ንጉሥ ሞተ። ይህንንም ሆሴዕ፥ የአሦር መንግሥት በእስራኤል ላይ የነበረውን የበላይነት ለማስወገድ ጥሩ ዕድል አድርጎ ቆጠረው፤ ስለዚህም ከግብፅ መንግሥት ጋር ተባበረ። በ725 ዓ.ዓ. ግን የአሦር መንግሥት የእስራኤል ዋና ከተማ የነበረችውን ሰማርያን አጠቃች። ለሦስት ዓመታት ከተማዋን ለመከላከል ቢችሉም፥ በ722 ዓ.ዓ. ግን የሰማርያ ከተማ ተደመሰሰች። ከ28000 የሚበልጡ ሰዎች ተገደሉ። የቀሩት እስራኤላውያንም በምርኮ ተግዘው በአሦር ግዛት በሙሉ፥ በተለይም በፋርስ ተበተኑ። በባቢሎን የነበሩ ሌሎች ሕዝቦች ደግሞ ወደ እስራኤል እንዲመጡና እንዲኖሩ ተደረገ። የሰሜኑ የእስራኤል ሕዝብ ከሌሎች ጋር በጋብቻ የተሳሰሩትና የተቀላቀሉት በዚህ ጊዜ ነበር። ስለዚህም እውነተኛ እስራኤላውያንም ሆነ ሙሉ አሕዛብ መሆናቸው ቀረ። እምነታቸውም ሙሉ በሙሉ ጣዖትን ማምለክ ወይም እውነተኛውን እግዚአብሔርን ማምለክ አልነበረም። ይልቁንም የሰማርያ ሰዎች የእግዚአብሔርን አምልኮ ከአሕዛብ አምልኮ ጋር ቀላቀሉት። ዝርያዎቻቸውም በአዲስ ኪዳን ዘመን ሳምራውያን በመባል ይታወቁ የነበሩት ሲሆኑ፥ በአይሁዶችም የተጠሉትም የእግዚአብሔርን እውነተኛ አምልኮ ስላበላሹ ነበር።

እግዚአብሔር ሕዝቡ ወደ ምርኮ እንዲሄዱ የፈቀደው ለምን ነበር? የመጽሐፉ ጸሐፊ በ2ኛ ነገ. 17፡7-23 ለመመለስ የሚሞክረው ይህንን ጥያቄ ነው። እነዚህ ጥቅሶች እስራኤል በነገሥታት ዘመን የነበራትን ታሪክ በአጭሩ የሚያቀርቡና ከእግዚአብሔር ጋር የነበራትን ግንኙነት የሚናገሩ ናቸው። በአጭሩ የመጽሐፈ ነገሥት ጸሐፊ ለዚህ ጥያቄ የሚሰጠው መልስ፥ አይሁድ በማያቋርጥ ሁኔታ ለእግዚአብሔር ስላልታዘዙ እግዚአብሔር ቀጣቸው የሚል ነው። ትኩረት የተደገረበት ዋናው ኃጢአትም የጣዖት አምልኮና የውሸት አምልኮ ነው።

በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ያለውን የእስራኤልን የውድቀት ማሽቆልቆል መገንዘብ በጣም የሚያስገርም ነው። በመጀመሪያ፡- ጸሐፊው በሕዝቡ የተሳሳተ አምልኮ ላይ ያተኩራል። ጣዖታትን ያለማቋረጥ አመለኩ።

ሁለተኛ፡- ሕዝቡ ወደ እግዚአብሔር ለመመለስ ፈቃደኞች አልነበሩም። እግዚአብሔር ሕዝቡን ያለማቋረጥ ወደ እርሱ መመለስ እንዳለባቸው ወይም ፍርዱን እንደሚቀበሉ በነቢያት ያስጠነቅቃቸው

ነበር። ሦስተኛ:- በአምልኮ ብቻ ሳይሆን በተግባርም ጭምር፥ አይሁድ በዙሪያቸው ያሉትን አሕዛብ መሰሉ። ልጆችን እንደ መሥዋዕት ይሠዉ ጀመር። በሥነ - ምግባር የወደቁና ጣዖት አምላኪ ሆኑ። አራተኛ:- እግዚአብሔር ወደ ራሱ ሊመልሳቸው ይችል ዘንድ ጊዜያዊ ቅጣትን ቀጣቸው። ጭቆና ይደርስባቸው ዘንድ ለተለያዩ ሕዝቦች አሳልፎ ሰጣቸው። ይህም ሆኖ ግን ሕዝቡ ወደ እግዚአብሔር አልተመለሱም። አምስተኛ:- እግዚአብሔር ወደ ምርኮ ይጓዙ ዘንድ ተዋቸው።

እግዚአብሔር በነገሥታት ዘመን ያደረገውን ተመሳሳይ ሂደት ዛሬም ይጠቀማል። ሕዝቡ ከእውነት እየራቁ ሲሄዱ፥ አምላክነቱን ሲክዱና አምልኮአቸውን ሲያበላሹ፥ በመጀመሪያ እግዚአብሔር የተመረጡ ሰዎችን ወደ እነርሱ በመላክ በግልጥ እንዲያስጠነቅቋቸውና ይህ እውነተኛ አምልኮ እንዳልሆነ፥ በእግዚአብሔር ፊትም ተቀባይነት እንደሌለው እንዲነግሯቸው ያደርጋል። ሕዝቡም ካልተመለሱ እግዚአብሔር በአስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ እንዲያልፉ ያደርጋል። ይህም ራብ፥ ስደት፥ ወይም ሌሎች ነገሮች ሊሆኑ ይችላሉ። የእግዚአብሔር ሕዝቦች በዚህም ሁኔታ ሊመለሱ ካልፈቀዱ፥ እግዚአብሔር ሙሉ በሙሉ እንዲጠፉ ይተዋቸዋል።

> 16ኛ ጥያቄ፥ ሀ) ይህ ክፍል በዘመናችን ላሉ አብያተ ክርስቲያናትም ጠንካራ ማስጠንቀቂያ የሚሆነው እንዴት ነው? ለ) ይህ ነገር ባለፈው ጊዜ እንዴት እንደተፈጸመ ምሳሌዎችን ጥቀስ። ሐ) እኛ በግላችንም ሆነ አብያተ ክርስቲያኖቻችን ይህንን ወደ ጥፋትና ምርኮ የሚወስደውን ማሽቆልቆል አለመጀመራችንን ለማረጋገጥ ምን ማድረግ እንችላለን?

## 4ኛ ቀን:- 2ኛ ነገሥት 18-25

ለእግዚአብሔር ሕዝቦች በጣም ጥሩ መምህራን ከሆኑት ነገሮች አንዱ ታሪክ መሆን አለበት። ከዚህ ቀደም የተፈጸሙ ነገሮች ብዙ ጊዜ ወደፊትም ይደገማሉ። ከዚህ ቀደም በነበረው ዘመን የእግዚአብሔር ሰዎች ችግር ገጥሟቸው ከነበረ ወደፊትም ተመሳሳይ ችግር እንደሚገጥማቸው ጥርጥር የለውም። የሐሰት ትምህርቶችን በምሳሌነት ውሰድ። ዛሬ ቤተ ክርስቲያንን የሚያስቸግሩ የሐሰት ትምህርቶችን፥ በአብዛኛው ከዚህ ቀደም የእግዚአብሔርን ሕዝብ ያስቸግሩ የነበሩ ናቸው። ቤተ ክርስቲያን ከዚህ ቀደም የሐሰት ትምህርቶችን ያስተናገደችበት መንገድ፥ ዛሬ የሐሰት ትምህርቶችን በሚመለከት ትምህርት ሊሆነን ይገባል። የቤተ ክርስቲያንን

ታሪክ ማጥናት አስፈላጊ የሆነበት አንዱ ምክንያት ይህ ነው። እንደዚሁም በብሉይ ኪዳን የእግዚአብሔር ሕዝብ የሆኑትን የአይሁድ ታሪክ ልናጠና አስፈላጊ የሆነበት አንዱ ምክንያት ይህ ነው። እንደዚሁም እነርሱም ልክ እንደ እኛ ሰዎች ስለነበሩ፥ የገጠሟቸው ችግሮችና ፈተናዎች እኛንም ይገጥሙናል። እነርሱን በአስቸገሯቸው ተመሳሳይ ኃጢአቶች የመውደቅ ዝንባሌ በእኛም ላይ ይታያል ማለት ነው (1ኛ ቆሮ. 10፡11 ተመልከት)።

የይሁዳ ሕዝብ ከታሪክ ለመማር አልቻለም። ወገኖቻቸው የሆኑ እስራኤላውያን ወደ ምርኮ የተወሰዱት ለእግዚአብሔር መታዘዝና እርሱን ማምለክ እምቢ ስላሉ ነበር። ከዚህ ተምረው ወደ እግዚአብሔር ከመመለስ ይልቅ፥ ልክ በሰሜኑ መንግሥት እንደነበሩት እስራኤላውያን ተማርከው እስኪሄዱ ድረስ በኃጢአታቸው ቀጠሉ። ታሪክ ራሱን በመድገም፥ የእግዚአብሔር ሕዝብ እንደ ወገኖቻቸው እስኪማረኩ ድረስ የወገኖቻቸውን ኃጢአት አደረጉ።

> 17ኛ ጥያቄ፥ ሀ) የቀድሞ አባቶቻችን በወደቁበት ተመሳሳይ በሆነ ኃጢአትና ችግር ስለ መውደቅ ዝንባሌ ከዚህ ምን እንማራለን? ለ) የራስህን ቤተ ክርስቲያንና በዘመናት ሁሉ የነበሩ አብያተ ክርስቲያናትን ታሪክ ማጥናት እጅግ ጠቃሚ የሆነው ለምንድን ነው? ሐ) ስለ ታሪካችሁ በቤተ ክርስቲያንህ የሚገኙ ሌሎች መሪዎችን ማስተማር የምትችሉት እንዴት ነው? መ) ለቤተ ክርስቲያን መሪዎች ልታቀርብ ስለምትችላቸው ነገሮች አሳብ ስጥ።
>
> 18ኛ ጥያቄ፥ 2ኛ ነገሥት 18-25 አንብብ። ሀ) በእነዚህ ዓመታት በይሁዳ የነገሡትን ነገሥታት ዘርዝር። ለ) የእያንዳንዳቸው ባሕርይ ምን ይመስል ነበር? ሐ) የእነዚህ ነገሥታት ዘመናት ዋና ዋና ተግባራት ምን ነበር? መ) የይሁዳን ውድቀትና ሕዝቡ ለምን ወደ ምርኮ እንደተወሰዱ ግለጥ።

እስራኤል በምርኮ የተወሰደችው በ722 ዓ.ዓ. ነበር። እስራኤላውያን በሕዝብነት ወደ አገራቸው ጨርሶ አልተመለሱም። ይልቁንም በዓለም ሁሉ ባሉ ሕዝቦች መካከል ተበተኑ። ይህ ሕዝብ ምን እንደደረሰባቸው ስለማይታወቅና ወደ አገራቸው ጨርሶ ስላልተመለሱ፥ አንዳንድ ሰዎች «የጠፉት አሥሩ የእስራኤል ነገዶች» በማለት ጠርተዋቸዋል። እግዚአብሔር ወደፊት አንድ ቀን ወደ አገራቸው

እንደሚመልሳቸው ተስፋ ሰጥቶአቸዋል (ኢሳ. 11፥11-16)። ዘመናዊው የእስራኤል መንግሥት በ1948 ዓ.ም. መመሥረቱ የዚህ ቃል ኪዳን ከፊል ፍጻሜ ነው።

ይሁዳ የተባለው የእስራኤላውያን ደቡባዊ መንግሥት፥ አገራቸውን ለ136 ዓመታት ለማቆየት ችሎ ነበር። የይሁዳ መንግሥት ወደ ምርኮ የተወሰደው በ586 ዓ.ዓ. ነበር። በእግዚአብሔር ጸጋ ምክንያት ግን የዚህ ሕዝብ ቅሬታዎች ከ50 ዓመታት በኋላ በ539 ዓ.ዓ. ወደ አገራቸው ለመመለስ ችለዋል። ይህንን ጉዳይ በይበልጥ በመጽሐፈ ዕዝራና ነህምያ ውስጥ እናጠናለን።

1. የይሁዳ ንጉሥ ሕዝቅያስ፡- (716-687 ዓ.ዓ.)

ሕዝቅያስ ወጣት በነበረ ጊዜ፥ የእስራኤልን ሕዝብ ውድቀትና እንዴት ወደ ምርኮ እንደ ተወሰዱ በዓይኑ ተመልክቷል። ይህ ነገር ሕይወቱን በጣም ሳይነካው አልቀረም፤ ስለዚህ ወደ ንጉሥነት ሥልጣኑ በመጣ ጊዜ እንደ አባቱ እንደ አካዝ ሳይሆን፥ እግዚአብሔርን ፈራ። ሕዝቅያስ ታላቅ ሃማኖታዊ መሪ ነበር። የይሁዳን ሕዝብ እግዚአብሔርን ወደ ማምለክ ለመመለስ አቅሙ የፈቀደውን ሁሉ አድርጓል። ከዳዊት ቀጥሎ እግዚአብሔርን በመፍራት ከሁሉ የተሻለ በመሆኑ የሚጠቀስ ታላቅ መሪ ሕዝቅያስ ነው።

ሕዝቅያስ በአሦር መንግሥት ቁጥጥር ሥር ቢሆንም፥ የሕዝቡን ሃይማኖታዊ ሕይወት ለመለወጥ የሚሠራበት ነፃነት ነበረው። እስራኤላውያን ወደ ምርኮ የተወሰዱት እግዚአብሔር ከእነርሱ ጋር ላደረገው ቃል ኪዳን ባለመታዘዛቸው እንደሆነ ተገንዝቦ ነበር፤ ስለዚህ ሕዝቅያስ ለእግዚአብሔር ለመታዘዝ አጥብቆ ጣረ። ለረጅም ጊዜያት ተዘግቶ የነበረውን ቤተመቅደስ በመክፈት እና በመጠገን ለአምልኮ የሚመች መልካም ስፍራ አደረገው። በእስራኤል ቀርተው የነበሩ አይሁዳውያንን በፋሲካ በዓል ወደ ኢየሩሳሌም በመምጣት እግዚአብሔርን እንዲያመልኩ ጋበዛቸው። የሐሰተኛ አምልኮ መጣሪያ የሆኑ ነገሮችን ሁሉ ለማጥፋት ጣረ። ሙሴ ከብዙ ዓመታት በፊት ሠርቶት የነበረውንና በኋላ እስራኤላውያን የአምልኮ መጣሪያ አድርገውት የነበረውን የነሐስ እባብ አጠፋ (ዘኁ. 21፥4-9 ተመልከት)። የቤተ መቅደሱ አምልኮ በሥርዓት እንዲካሄድ ሕዝቅያስ የሌዋውያንን አገልግሎትና አሥራትን የመሰብሰቢያ ዘዴዎችን በሚገባ አደራጀ።

ሕዝቅያስ በዚያን ዘመን ከነበረው ከኢሳይያስ ጋር በቅርበት ሳይሠራ አልቀረም።

ሕዝቅያስ በመጨረሻ ከአሦራውያን ጋር እንደሚዋጋ ያውቅ ነበር፤ ስለዚህ የይሁዳን ብሔር ለመከላከል በከተሞች ምሽግ ሠራ። አሦራውያንንም ለማረጋጋትና ለማስደሰት ከቤተ መቅደስ ወርቅ አውጥቶ ሰጣቸው፤ ሆኖም በ701 ዓ.ዓ. አሦራውያን ወረሩትና ከኢየሩሳሌም ከተማ በቀር የይሁዳን መንግሥት በጠቅላላ ወሰዱ። በግንቦች የታጠሩ አርባ ስምንት ከተሞች ተደመሰሱና 200 000 አይሁድም በምርኮ ተወሰዱ። ሕዝቅያስ ግን በእግዚአብሔር ስለታመነ፥ እግዚአብሔር ኢየሩሳሌምን ከጥፋት አዳነ። የአሦር ንጉሥ ነገሥት ግዛት አንዱ ክፍለ ሀገር በነበረው በባቢሎን በተነሣው ዓመፅ የአሦር ጦር ወደ አገሩ ለመመለስ ግድ ሆነበት።

በኋላም ሕዝቅያስ በጠና ታመመ። በእግዚአብሔር ምሕረት ግን 15 ዓመታት በዕድሜው ላይ ተጨመረለት። በዚህ ጊዜም ልጁ ምናሴ አብሮት መግዛት ጀመረ። ከበሽታው በማገገሙ ደስታቸውን ሊገልጹለት ለመጡት ለባቢሎን ልዑካን ባለማስተዋል ሀብቱን በሙሉ አስጎበኛቸው። ባቢሎናውያን አንድ ቀን ኢየሩሳሌምን እንደሚያጠፉና ወርቁን እንደሚወስዱበት ለመገንዘብ አልቻለም ነበር።

2. የይሁዳ ንጉሥ ምናሴ፡- (692-642 ዓ.ዓ.)

በይሁዳ ላይ ከነገሡ ነገሥታት ሁሉ ረጅም ዘመን የነገሠው ምናሴ ነው። ለ55 ዓመታት በሥልጣን ላይ ቆይቷል። ይህ ዘመን ከሕዝቅያስ ጋር አብሮ የገዛበትን ጊዜንም ይጨምራል።

ምናሴ ሕዝቅያስ ከሞተና ብቻውን ንጉሥ መሆን ከጀመረበት ጊዜ አንሥቶ በእግዚአብሔር ላይ ፊቱን በማዞር ጀርባውን ሰጠው። ሕዝቅያስ በይሁዳ ያደረጋቸውን ተሐድሶዎች በሙሉ ለማበላሸት አሰበ። ሕዝቡን ወደ ጣዖት አምልኮ መራ። ትላልቅ የአምልኮ ስፍራዎችንና የጣዖታት መሠዊያዎችን ለበአልና የአሞናውያን አምላክ ለሆነው ለሞሎክ አሠራ። ከኢየሩሳሌም ከተማ ውጭ ለሞሎክ ጣዖት ልጆቹን ሳይቀር ሠዋ። በቤተ መቅደሱ ውስጥ የጣዖት አምልኮን አቆመ። እግዚአብሔርን ለማምለክ የፈለጉትን እጅግ ብዙ ሰዎችን ገደለ። እንዲያውም የአይሁድ አፈ ታሪክ ኢሳይያስ የሞተው በምናሴ ትእዛዝ በመጋዝ ለሁለት ተሰንጥቆ ነው

ይባላል። በምናሴ ዘመነ መንግሥት የእግዚአብሔር ሕዝብ የሥነ - ምግባር ሕይወት ተበላሸ። እንዲያውም አብረዋቸው ከነበሩት ከነዓናውያን የባሰ ተበላሹ።

በምናሴ ዘመነ መንግሥት ይሁዳ ለአሦር መንግሥት እንደ ባሪያ ነበር፤ ነገር ግን ባቢሎን በአሦር ላይ በምታምፅበት ጊዜ ምናሴም በአሦር ላይ ለማመፅ ሞከረ። ሆኖም ወደ አሦር በምርኮ ተወሰደና በኋላ ተለቀቀ (2ኛ ዜና 33፡10-13 ተመልከት)። ምናሴ በምርኮ ላይ በነበረበት ጊዜ ከከፉ ተግባሩ ሁሉ የተመለሰ ይመስላል። ወደ ይሁዳ በተመለሰ ጊዜም ሕዝቡ እግዚአብሔርን ወደ ማምለክ እንዲመለሱ አበረታታ፤ ነገር ግን በዚህ ተግባሩ ብዙ ውጤታማ መሆን አልቻለም።

| |
|---|
| 19ኛ ጥያቄ፥ ሀ) የአንድ ሰው መንፈሳዊ እምነት ወደ ልጆቹ ሊተላለፍ እንደማይችል፥ የምናሴ ሕይወት ጥሩ ምሳሌ የሚሆነን እንዴት ነው? ለ) ወላጆች ልጆቻቸውን የእግዚአብሔርን መንገድ ሊያስተምሯቸው የሚያስፈልገው ለምንድን ነው? |

3. የይሁዳ ንጉሥ አሞን፡- (643-641 ዓ.ዓ.)

ስለ አሞን አገዛዝ ብዙ የምናውቀው ነገር የለም፤ ነገር ግን እንደ አባቱ እንደ ምናሴ የመጨረሻ የሕይወት ዘመን ሳይሆን፥ ምናሴ ሕዝቡን ወደ ጣኦት አምልኮ እንደመራባቸው እንደ መጀመሪያው ዘመን ኖረ። አሞን በይሁዳ ሰዎች ተገደለና ልጁ ኢዮስያስ በእርሱ ፈንታ ነገሠ።

4. የይሁዳ ንጉሥ ኢዮስያስ (641-609 ዓ.ዓ.)

ኢዮስያስ በይሁዳ ላይ በነገሠ ጊዜ የ8 ዓመታት ልጅ ነበር። በይሁዳ ላይ ከነገሡና እግዚአብሔርን ይፈሩ ከነበሩ መሪዎች ኢዮስያስ የመጨረሻው ነበር። ከኢዮስያስ ሞት በኋላ፥ በባቢሎናውያን ወደ ምርኮ እስኪወሰድ ድረስ የይሁዳ ብሔር በጣም ፈጣን በሆነ ሁኔታ እየተዳከመ ሄደ።

ኢዮሳያስ መንገሥ በጀመረ ጊዜ የአሦር መንግሥት መውደቅ ጀምሮ ነበር። ይህም ኢዮሳያስ የእስራኤል ግዛት የነበረውን አንዳንድ ምድር ለመውሰድ እስኪችል ድረስ ግዛቱን ለማስፋፋት ረዳው። በዘመነ መንግሥቱ መጨረሻ አካባቢ፥ በ612 ዓ.ዓ. የአሦር ዋና ከተማ የሆነችው ነነዌ በባቢሎናውያን እጅ ወደቀች።

ኢዮስያስ ከነገሠ ከ10 ዓመታት በኋላ አንድ ነገር ልቡን ለወጠውና እግዚአብሔርን እንዲከተል አደረገው። ኢዮስያስ እግዚአብሔርን መፈለግና የሕዝቡን ልብ ወደ እግዚአብሔር ለመመለስ መሥራት ጀመረ። ሕዝቡ ቤተ መቅደሱን በመሥራት ላይ ሳሉ፥ ከስምንት ዓመታት በኋላ ፔንታቱክ ብለን የምንጠራቸው የሙሴ ሕግጋት በቤተ መቅደሱ ተገኙ። ለብዙ ዓመታት ሰዎች ሁሉ የእግዚአብሔርን ቃል ለማንበብ ያልቻሉ ይመስላሉ። ይልቁንም የእግዚአብሔር ቃል በምናሴ ዘመነ መንግሥት በቤተ መቅደሱ ውስጠኛ ክፍል ሳይሸሸግና ሳይጣል፥ ሳይረሳም አልቀረም።

የእግዚአብሔር ቃል ተገኝቶ በዘዳግም 27-28 የተጻፉት መርገምቶች ሁሉ በተነበቡ ጊዜ፥ በይሁዳ ሕዝብ ላይ ፍርዱ በደጅ እንደ ቀረበ ኢዮስያስ አወቀ። እግዚአብሔርም ነቢያትን ወደ ኢዮስያስ ላከና የኢየሩሳሌም ጥፋት የማይቀር እንደሆነና እርሱ እግዚአብሔርን ስለፈራ ግን በእርሱ ዘመነ መንግሥት ይህ እንደማይፈጸም አስታወቀው። ኢዮስያስም ሕዝቡን ወደ እግዚአብሔር ለመመለስና ከእግዚአብሔር ጋር የነበራቸውን ቃል ኪዳን ለማደስ ተግቶ ሠራ። ለጣዖት አምልኮ የሆኑ መሣሪያዎችን በሙሉ አጠፋ። እስከ ቤቴል ድረስ ሳይቀር ሄዶ ቀዳማዊ ኢዮርብዓም ከ300 ዓመታት በፊት ያቆማቸውን ጣዖታት አፈራረሰ። ይህንንም በማድረጉ አንድ ያልታወቀ ነቢይ የተነበየውን ትንቢት ከፍጻሜ አደረሰው፤ (1ኛ ነገሥት 13 ተመልከት)። ኢዮስያስ ለጣዖት አምልኮ የሚያገለግሉ ውጫዊ ነገሮችን ሊያጠፋ ቢችልም፥ በሰዎቹ ውስጣዊ ሕይወት ላይ ተጽዕኖ ማድረጉ ግን እጅግ አጠራጣሪ ነው። ምክንያቱም ኢዮስያስ እንደሞተ ሕዝቡ ወደ ጣዖት አምልኮ ተመልሰዋል።

> 20ኛ ጥያቄ፥ ሀ) የሐሰተኛ አምልኮ አካሄድን ወይም የሰዎችን ውስጣዊ ልብን መለወጥ ከውጫዊ ነገሮች ይልቅ የበለጠ አስቸጋሪና ከባድ የሚሆነው ለምንድን ነው? ለ) ለማያምኑ ሰዎች በምንመሰክርበት ጊዜ ወይም የቤተ ክርስቲያን ሰዎችን በምናስተምርበት ጊዜ በውጫዊ ለውጥ ላይ ከማተኮር ይልቅ በውስጣዊ ለውጥ ላይ የማተኮር አስፈላጊነት ይህ ምን ያስተምረናል?

በኢዮስያስ ዘመን ያገለግል የነበረው ዋና ነቢይ ኤርምያስ ነበር።

በ609 ዓ.ዓ. ኢዮስያስ ብልህነት የጎደለው ስሕተት ፈጸመ። የግብፅ ንጉሥ ከአሦር ጋር በመተባበር አዲሱን ኃያል መንግሥት ባቢሎንን

ለመውጋት ወደ ሰሜን በሚጓዝበት ጊዜ በይሁዳ በኩል ያልፍ ነበር። ኢዮስያስ ከግብፅ ንጉሥ ምንም ዓይነት ጠብ አጫሪነት ሳይኖር የግብፅን ንጉሥ ለመውጋት ሄደ፤ በጦርነቱም ቆሰለና ቆይቶ ሞተ።

5. የይሁዳ ንጉሥ ኢዮአሐዝ (ሻሉም) (609 ዓ.ዓ.)

ኢዮስያስ በሞተ ጊዜ፥ በእርሱ ምትክ ልጁ ኢዮአሐዝ ነገሠ፤ ነገር ግን በሥልጣን ላይ ለረጅም ጊዜ ሊቆይ አልቻለም። ከሦስት ወራት በኋላ ግብፃውያን ከባቢሎን ጦርነት ሲመለሱ፥ ኢዮአሐዝ ቆይቶ ወደ ሞተበት ወደ ግብፅ ማርከው ይዘውት ሄዱ።

6. የይሁዳ ንጉሥ ኢዮአቄም (609-598 ዓ.ዓ.)

ግብፃውያን ኢዮአሐዝን ማርከው ሲወስዱ፥ ኢዮአቄም የተባለውን ወንድሙን በዙፋኑ ላይ አስቀመጡት። በዚያን ጊዜ ስሙን ወደ ኢዮአቄም ለወጡት። ግብፃውያን በተጨማሪ የይሁዳ መንግሥት ከባድ ቀረጥ እንዲከፍል አደረጉት።

በ605 ዓ.ዓ. የባቢሎን ንጉሥ የሆነው ናቡከደነፆር ብዙም ሳይቆይ ኢየሩሳሌምን አጠቃ። ኢዮአቄም ለእርሱ ራሱን ማስገዛት ግድ ሆነበት። በዚህ ጊዜ ናቡከደነፆር የይሁዳ ዋና ዋና ሰዎችን ማርኮ ወደ ባቢሎን ወሰደ። ከእነዚህም መካከል ዳንኤል፥ ሐናንያ፥ ሚሳኤልና አዛርያ ይገኙበታል። ይህ በይሁዳ ላይ ከደረሰው ምርኮኝነት የመጀመሪያው ነበር።

ኤርምያስ በንጉሡ ኢዮአቄም ዘመንም አገልግሎአል። ኢዮአቄም ግን የኤርምያስን ቃል መስማት እምቢ አለና የጻፈውን የተቀደሰ ጽሑፍ አቃጠለ። ኢዮአቄም የጣዖት አምልኮን ከማበረታታቱም ሌላ አባቱ እንዳደረገው የእግዚአብሔርን መንገድ ሳይከተል ቀረ። ከዚህ የተነሣ እግዚአብሔር በኢዮአቄም ላይ ፈረደና ተገቢ የሆነው የንጉሣውያን ቤተሰብ የቀብር ወግ ሳያገኝ ቀረ። አንዳንድ ምሁራን በ598 ዓ.ዓ. ባቢሎንን ለመውጋት በተደረገ ጦርነት እንደሞተ ያስባሉ።

7. የይሁዳ ንጉሥ ዮአኪን (597 ዓ.ዓ.)

የኢዮአቄም ልጅ የሆነው ዮአኪን በሥልጣን ላይ የቆየው ለሦስት ወራት ብቻ ነበር። እርሱ የመንግሥት ሥልጣን በያዘ ጊዜ ይሁዳ ከባቢሎን ጋር በጦርነት ላይ ነበረች። ዮአኪን እጁን ለባቢሎን ሰጠ። ናቡከደነፆር በቤተ መቅደሱ ውስጥ የነበሩ የከበሩ ነገሮችን ሁሉ ዘረፈ። ዮአኪንና

ሌሎች የይሁዳ ትላላቅ ሰዎችን በምርኮ አጋዛቸው። ሕዝቅኤል ተማርኮ የሄደው በዚህ ጊዜ ነበር። ዮአኪን በባቢሎን መልካም እንክብካቤ ተደረገለት። ከናቡከደነፆር ሞት በኋላ ከታሠረበት ከመለቀቁም በቤተ መንግሥት በእንክብካቤ ተያዘ። ወደ እስራኤልም ጨርሶ ሳይመለስ ቀረ።

8. የይሁዳ ንጉሥ ሴዴቅያስ (ማታንያህ) (597-586 ዓ.ዓ.)

ሴዴቅያስ የኢዮአሐዝ የመጨረሻ ልጁ ነበር። በሥልጣን ላይ ያስቀመጠው የባቢሎን ንጉሥ ናቡከደነፆር ሲሆን፥ ማስተዳደር የሚችለውም በባቢሎን መንግሥት ሥልጣን ሥር ነበር። ለጊዜው ሴዴቅያስ ለባቢሎን መንግሥት ታማኝ ነበር፤ ነገር ግን ግብፅ በ588 ዓ.ዓ. በባቢሎን ላይ ስታምፅ ሴዴቅያስም ዓመፀ። ይህም በእርሱና በኢየሩሳሌም ከተማ ላይ የባቢሎንን ሙሉ ቁጣ አስከተለ። በ586 ዓ.ዓ. ኢየሩሳሌም ተሸነፈች። የሴዴቅያስ ልጆችም በእርሱ ፊት ተገደሉ። ሴዴቅያስንም ዓይኑን አውጥተው ወደ ባቢሎን በምርኮ ወሰዱት። ሌሎች ብዙ ሰዎችም ተማርከው ተወሰዱ። የኢየሩሳሌም ቅጥር፥ የሰሎሞን ቤተ መቅደስና አብዛኛው የከተማይቱ ክፍል ተደመሰሰ።

በእነዚህ ዓመታት ውስጥ ኤርምያስ ለንጉሡ ሴዴቅያስ ምክር ሊሰጠው ቢሞክርም ሴዴቅያስ ኤርምያስን መስማት እምቢ አለና ኤርምያስን አሳደደው።

9. የይሁዳ ገዥ ገዳልያ

ኢየሩሳሌም ከተደመሰሰች በኋላ ናቡከደነፆር ገዳልያን የይሁዳ ገዥ አደረገው፤ ይሁን እንጂ እስማኤል የተባለው የንጉሣውያን ቤተሰብ ዝርያ የነበረ ሰው ሥልጣኑን ስለፈለገ ገዳልያን ገደለው። በዚህ ምክንያት ሊመጣ ያለውን የባቢሎናውያንን ቁጣ በመፍራት፥ አብዛኛዎቹ አይሁዳውያን ወደ ግብፅ ሸሽተው ሄዱ። ኤርምያስንም ከእነርሱ ጋር እንዲሄድ አስገደዱት። እርሱም በዚያው በግብፅ ሞተ።

በ2ኛ ነገሥት የተጻፈው ታሪክ እጅግ አሳዛኝ ታሪክ ነው። የእግዚአብሔር ሕዝብ ያለማቋረጥ ልባቸውን እንዳደነደኑና እውነተኛውን አምላክ ከማምለክ ይልቅ ሐሰተኛ አማልክትን እንዴት እንዳመለኩ ይናገራል፤ በዚህ ምክንያት እግዚአብሔር የሰሜኑም ሆነ የደቡቡ መንግሥታት ወደ ምርኮ እንዲሄዱ አደረገ። ለደቡብ መንግሥት ግን ፍርዱ ጊዜያዊ ነበር። የኢየሩሳሌም ቅጥር ከፈረሰ ከ50 ዓመታት በኋላ

እግዚአብሔር በአሕዛብ መንግሥታት ልብ ውስጥ በመሥራት፥ የራሱ ሕዝብ ወደ ኢየሩሳሌም እንዲመለሱ አደረገ። የሚያሳዝነው ግን አብዛኛዎቹ አይሁድ በምርኮ በነበሩበት ስፍራ ኑሮአቸው የሚያረካ ስለሆነላቸው ለመመለስ ፈቃደኞች ሳይሆኑ ቀሩ። እግዚአብሔር በሰጣቸው ምድር በድኅነት ከመኖር ይልቅ የዓለምን ምቾት መረጡ።

> 21ኛ ጥያቄ፥ ሀ) ከ2ኛ ነገሥት የተማርካቸውን መንፈሳዊ ትምህርቶች ዘርዝር። ለ) እነዚህ ትምህርቶች በቤተ ክርስቲያንህ አባላት መንፈሳዊ ዕድገት ውስጥ እንዴት አስተዋጽኦ ሊያደርጉ ይችላሉ? ሐ) እነዚህን ትምህርቶች በቤተ ክርስቲያንህ ውስጥ ለሚገኙ ሌሎች ሰዎች የምታስተምርባቸውን መንገዶች ዘርዝር።

## መጽሐፈ ነገሥት ከአዲስ ኪዳን ጋር ያለው ግንኙነት

ከመጻሐፍ ነገሥት የተጠቀሱ በርካታ ጥቅሶች በአዲስ ኪዳን ውስጥ ባይኖሩም በ1ኛና በ2ኛ ነገሥት የተፈጸሙ ድርጊቶችን የመረዳት ጉዳይ ግን በአዲስ ኪዳን በአጠቃላይ እናገኛለን። በአዲስ ኪዳን ሰሎሞን በተደጋጋሚ ተጠቅሷል። ማቴ. 1፡1-17 ከአብርሃም ጀምሮ እስከ ኢየሱስ ያለውን የጌታን የዘር ግንድ ያሳየናል። በእነዚህ ጥቅሶች በመጽሐፈ ነገሥት የተጠቀሱት አብዛኞቹ ነገሥታት ተዘርዝረዋል። የሰሎሞን ጥበብና ሀብት አንዳንድ ጊዜ ተጠቅሷል (ለምሳሌ፡- ማቴ. 12፡42፤ ሉቃስ 12፡27)።

የ1ኛና የ2ኛ ነገሥት ታሪኮች በቀጥታ ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ ባያመለክቱም፥ ከቀረው የመጽሐፍ ቅዱስ አመለካከት ጠቃሚ እውነቶችን ማየት እንችላለን። በብሉይ ኪዳን የደኅንነት ግንድ የሆነውን የኢየሱስ ክርስቶስን የትንቢት መስመር እናገኛለን። ይህ ትንቢት የጀመረው የሰይጣንን ራስ እንደሚቀጠቅጥ የተነገረለት የሴቲቱ ዘር ጉዳይ ከተጠቀሰበት ከአሪት ዘፍጥረት ነው (ዘፍ. 3፡15)። ይህ መስመር ከዚያ እስከ አብርሃም፥ ቀጥሎም እስከ ዳዊት፥ ከዚያም በይሁዳ ነገሥታት በኩል ያለፈ ነው።

ሰይጣን የአብርሃምና የይሁዳ የዘር ግንድ ልዩ እንደ ነበረና መሢሑ ከዚያ እንደሚመጣ ያውቅ ነበር። ስለዚህ በታሪክ መጻሕፍት በተደጋጋሚ ሰይጣን ይህንን የዘር ግንድ እንዴት ሊያጠፋ እንደሞከረ የሚያሳየውን የተደበቀ እውነት እናያለን። በዘፍጥረት ሰይጣን የግብፅን ንጉሥ

በመጠቀም ሣራን እንደ ሚስቱ እንዲወስድና የአብርሃም የዘር ግንድ እንዲቋረጥ ለማድረግ ሞክሮ ነበር። ሰይጣን ድርቅና ራብን በመጠቀም የእስራኤልን ቤተሰብ ለማጥፋት ቢሞክርም፥ እግዚአብሔር በዮሴፍ ተጠቅሞ እንዴት ከራብ እንዳዳናቸው እይተናል።

በ2ኛ ሳሙኤል ለዳዊት ዘር የተሰጠውን የዘላለም ዙፋን ተስፋ ተመልክተናል። በመጽሐፈ ነገሥት በአጠቃላይ የምናየው፥ ለዘላለም ዙፋን የተሰጠው ቃል ኪዳን ከትውልድ ወደ ትውልድ እየተላለፈ እንዴት እስከ ምርኮ ታሪክ ድረስ እንደመጣ ነው። ጎቶልያ የተባለችው ክፉ ንግሥት ታሪክ የሚያሳየው፥ የዳዊትን ዝርያ እንዳለ በማጥፋት ሰይጣን የእግዚአብሔርን ዕቅድ ለማበላሸት እንዴት እንደሞከረ ነው። የዳዊት ንጉሣዊ ቤተሰብ በሙሉ የጠፋና ከእርሱ የዘር ግንድ አንድ ሰው ብቻ የቀረ ይመስላል። ሰይጣን ያንን የቀረውን ሰው ማስገደልና መስመሩ እንዲቋረጥ ማድረግ ቢችል ኖሮ መሢሑ በዳዊት ዘር በኩል መምጣቱን ሊያስቀር ይችል ነበር። እግዚአብሔር ግን አንድ ሰው እንዲቀርና የዳዊት የዘር ግንድም እንዲጠበቅ አደረገ። ኢየሱስ በቤተልሔም ትንሽ ሕፃን በነበረ ጊዜ ሄሮድስ ሊያስገድለው መሞከሩ በሰይጣንና በእግዚአብሔር መካከል የነበረው የዚያው ጦርነት ክፍል ነበር።

ሰይጣን እግዚአብሔርን ለማሸነፍ የቱንም ያህል ቢጥርም ሁልጊዜ በእግዚአብሔር ይሸነፋል። ሰይጣን ምንም ያህል ተግቶ ቢሠራም፥ እግዚአብሔር ለእኛና ለቤተ ክርስቲያን ያለውን ዕቅድ ሊደመስስ አይችልም።

| |
|---|
| 22ኛ ጥያቄ፥ በስደት፥ በሐሰት ትምህርት፥ ወዘተ በምንጠቃበትና የተሸነፍን በሚመስለን ሰዓት ይህ እውነት እንዴት ያበረታታናል? |

5ኛ ቀን፡-

የዚህን ሳምንት ትምህርት ከልስና ለሳምንታዊው ስብሰባ ዝግጅት ይረዳህ ዘንድ የውይይት ጥያቄዎችን ተመልከት።

## ሳምንታዊ ስብሰባ

1. የሳምንቱ የአምልኮ ጊዜ

2. ጸሎት

3. የትምህርቱ ክለሳ

4. ውይይት

1. ሀ) እግዚአብሔር፥ እስራኤልና ይሁዳ ወደ ምርኮ እንዲሄዱ የፈቀደው ለምን ነበር? ለ) ይህ ዛሬ ለእኛ ማስጠንቀቂያ የሚሆነው እንዴት ነው? ሐ) እንደ «ምርኮ» ባሉ አንዳንድ ልምምዶች እግዚአብሔር አንተን ወይም ቤተ ክርስቲያንህን ያስጠነቀቀባቸውን ነገሮች በምሳሌነት ዘርዝር።

2. 2ኛ ዜና 7፡14 አንብብ። ሀ) እግዚአብሔር በዚህ ቦታ የሰጠው የተስፋ ቃል ምንድን ነው? ለ) ይህንን የተስፋ ቃል ለመቀበል የተሰጡ ቅድመ ሁኔታዎች ምንድን ናቸው? ሐ) ይህ ጥቅስ ዛሬ በኢትዮጵያ ሊፈጸም የሚችለው እንዴት ነው? መ) ክርስቲያኖች ለአገራቸው ፈውስን በማምጣት የሚጫወቱት ሚና ምንድን ነው?

3. ሀ) በትምህርት ቤት የተማርከውንና በ2ኛ ነገሥት የተማርከውን የታሪክ አመለካከት አወዳድር። ልዩነታቸው ምንድን ነው? ለ) ክርስቲያኖች መጽሐፍ ቅዱሳዊ የታሪክ አመለካከት አቋም ሊኖራቸው የሚገባው ለምንድን ነው? ሐ) በመጽሐፈ ነገሥት፥ መጽሐፍ ቅዱሳዊ የታሪክ አመለካከት እንዴት እንደተገለጠ ምሳሌዎችን ስጥ።

4. ሀ) ኢዮሳፍጥ ከአክዓብ ጋር የመሠረተው ጓደኝነት እርሱንና ቤተሰቡን ሊያጠፉ የነበረው እንዴት ነው? ለ) ዛሬ ከዓለም ጋር የሚኖር ወዳጅነት (ለምሳሌ፡- ከሌሎች ሃይማኖት መሪዎች ወይም ከመንግሥት የተሾሙ ባለሥልጣናት ጋር የሚመሠረት ጓደኝነት) የቤተ ክርስቲያን መሪዎችን የሚያጠፋው እንዴት ነው?

5. ሀ) ከይሁዳና ከእስራኤል ነገሥታት አመራር አንዳንድ አሉታዊ ምሳሌዎችን ጥቀስ። ለ) ከይሁዳና ከእስራኤል ነገሥታት አመራር አዎንታዊ ምሳሌዎችን ጥቀስ። ሐ) መልካም ወይም ክፉ ያደረጋቸው ምን ነበር? መ) እግዚአብሔርን የሚፈራ ሰው ስለሚሰጠው አመራር ከመጽሐፈ ነገሥት አንዳንድ መመሪያዎችን ስጥ።

6. ሀ) አብያተ ክርስቲያናትም ሆኑ ክርስቲያኖች ወደ መንፈሳዊ ሞት ወይም መንፈሳዊ ለብታ ስለሚያዘነብሉበት ሁኔታ መጽሐፈ ነገሥት እንዴት መልካም ምሳሌ ይሆነናል? ለ) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ይህንን ተፈጥሮአዊ ዝንባሌ ለማስወገድ ምን ማድረግ ይችላሉ?

7. ሀ) የእግዚአብሔርን ሕዝብ መንፈሳዊ ሕይወት ለመወሰን ነገሥታት የሚጫወቱት ሚና ምን ነበር? ለ) የክርስቲያኖችን መንፈሳዊ ሕይወት ለመወሰን የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የሚጫወቱት ሚና ምንድን ነው? ሐ) ከውጫዊ ነገር ይልቅ ውስጣዊ ዝንባሌን መለወጥ አስቸጋሪ የሚሆነው ለምንድን ነው? መ) ክርስቲያኖችን በሚመለከት የምናየውን ውጫዊ ተግባራቸውን ብቻ ሳይሆን፥ ውስጣዊ ዝንባሌያቸውንና አሳባቸውን እንዲለውጡ ምን ማድረግ እንችላለን?

5. ጸሎት።

# ትምህርት 17

## 1ኛ ቀን፡- የ1ኛና 2ኛ ዜና መዋዕል መግቢያ

1ኛና 2ኛ ዜና፥ ከዳዊት ጊዜ ጀምሮ የይሁዳ መንግሥት በባቢሎን እጅ እስከ ወደቀበት ድረስ ያለውን የነገሥታትን ዘመን ታሪክ እንደገና ይናገራሉ። ብዙ ሰዎች እነዚህ ታሪኮች ለሁለተኛ ጊዜ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ለምን እንደገቡ በማሰብ ይገረማሉ። ሁለት ሰዎች የመኪና አደጋን የመሰለ ክስተት ቢመለከቱ፥ የሚሰጡት ገለጣ አንድ ዓይነት እንደማይሆን ሁሉ መጽሐፈ ዜና መዋዕልም የብሉይ ኪዳን ነገሥታትን ታሪክ የጻፈበት የራሱ የሆነ የተለየ ዓላማ አለው። 1ኛና 2ኛ ዜናን በመረዳት ስለ ዳዊት፥ ስለ ሰሎሞንና ስለ ሌሎች የይሁዳ ነገሥታት ከፍተኛ ግንዛቤን እናገኛለን።

---

1ኛ ጥያቄ፥ ሀ) የአንድን ታሪክ የተለያዩ አመለካከቶች ማየት ጥሩ የሚሆነው ለምንድ ነው? ለ) ስለተፈጸመው ነገር እውነተኛውን ለመረዳት ይህ የሚጠቅመን እንዴት ነው?

---

ቀደም ሲል ከተመለከትነው ጥናታችን እንደምታስታውሰው፥ የሳሙኤልን፥ የነገሥታትንና የመሳሰሉትን የታሪክ መጻሕፍት የጻፉ ጸሐፊዎች ዓላማቸው በዚያ ዘመን የተፈጸሙትን ነገሮች ሁሉ መተንተን አልነበረም። ይልቁንም የጻፉት ነገር ሕዝቡ አባቶቻቸው በወደቁበት ተመሳሳይ ኃጢአት እንዳይወድቁ ለማስተማር ግልጥ ዓላማዎች ነበሯቸው። የ1ኛና 2ኛ ዜና መጻሕፍት ጸሐፊም የመጽሐፈ ነገሥት ታሪክ የያዘውን የነገሥታት ታሪክ የደገመበት ምክንያት ነበረ። ይህም ዓላማ ከምርኮ በኋላ የነበሩ አይሁዳውያን እግዚአብሔርን እንዴት እንደሚያመልኩና ለእርሱ እንዴት ታማኝ ሆነው ሊቆዩ እንደሚችሉ፥ በዚህም ዓይነት በእግዚአብሔር መባረክን ማግኘት እንደሚችሉ ለማስተማር ነበር።

የ1ኛና 2ኛ ዜና መጻሕፍት አብዛኛውን የ2ኛ ሳሙኤል፥ የ1ኛና 2ኛ ነገሥት ታሪክ ይደግሙታል። ከሳኦል ሞት በኋላ ስለ ነበረውና በሉዓላዊነቱ ስለ ቆየው የእስራኤል መንግሥት ይተርኩልናል። 1ኛ ዜና መዋዕል የእስራኤል ታላቅ ንጉሥ በነበረው በዳዊት ላይ ያተኩራል። አንድ መልካም የሆነ የአይሁድ ሕዝብ መሪ ምን እንደሚመስል በማሳየት፥ የአይሁድ ሕዝብ መሪዎችና የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ምሳሌነቱን ይከተሉ ዘንድ የዳዊትን ታሪክ እንደገና ይነግረናል።

2ኛ ጥያቄ፥ ሀ) ክርስቲያኖች አርዓያነቱን መከተል ይችሉ ዘንድ መልካም ምሳሌነት ያለው ሰው የሚያስፈልጋቸው ለምንድን ነው? 1ኛ ቆሮ 11፡1 ተመልከት። ለ) ጳውሎስ ለክርስቲያኖች የሰጠው ትእዛዝ ምንድን ነው? ሐ) ይህ ትእዛዝ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በሙሉ ለአባሎቻቸው ሊናገሩት ከሚገባው ትእዛዝ የሚመሳሰለው እንዴት ነው?

2ኛ ዜና መዋዕል በድጋሚ የሚናገረው የመጽሐፈ ነገሥት የመጀመሪያውንና ሁለተኛውን ታሪኮች ነው። ይህም ታሪክ በድጋሚ የሚያወሳው የንጉሥ ሰሎሞንና የይሁዳን ነገሥታት ታሪክ ነው። ታሪኩ የሚያበቃውም የይሁዳ ሕዝቦች ወደ ምርኮ እስከተወሰዱ ድረስ ያለውን በመናገር ነው።

2ኛ ዜና የ2ኛ ሳሙኤል እንዲሁም የ1ኛና የ2ኛ ነገሥት ታሪክ በድጋሚ የቀረበበት ቢሆንም፥ የመጽሐፈ ዜና መዋዕል ዓላማ ከመጽሐፈ ነገሥት ዓላማ የተለየ ነበር፤ ስለዚህ ጉዳይ በኋላ እናጠናለን።

3ኛ ጥያቄ፥ 1ኛና 2ኛ ዜና መዋዕልን ከመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት ተመልከት። ስለ መጻሕፍቱ የተጠቀሱትን አስፈላጊ የሆኑ እውነቶች ዘርዝር።

## የ1ኛና 2ኛ ዜና መዋዕል ርዕስ

እንደ 1ኛና 2ኛ ሳሙኤልና እንዲሁም እንደ 1ኛና 2ኛ ነገሥት ሁሉ፥ 1ኛና 2ኛ ዜና መዋዕል በመጀመሪያ አንድ መጽሐፍ ነበር። ልክ እንደ ሌሎቹ መጻሕፍት ሁሉ መጽሐፈ ዜና መዋዕል ለሁለት የተከፈለው የዕብራይስጡ ብሉይ ኪዳን፥ ወደ ግሪክ ቋንቋ በተተረጎመበት ጊዜ ነው። በዕብራይስጥ መጽሐፍ ቅዱስ የዚህ መጽሐፍ ርዕስ ከመጽሐፉ መጀመሪያ ዐረፍተ ነገር ላይ የተገኘ ሲሆን፥ የነገሥታት «ዘመን ቃላት» ወይም «ድርጊቶች» የሚል ነው። «ዜና መዋዕል» የሚለው የእንግሊዝኛው ቃል ትርጉም «ዘገባ» ማለት ሲሆን፥ በነገሥታት ዘመን የነበረው መለኮታዊ ታሪክ ዘገባ ማለት ነው። በአማርኛ «ክስተቶች ወይም ታሪክ» ማለት ነው።

## የመጽሐፈ ዜና መዋዕል ጸሐፊ

መጽሐፍ ቅዱስ የዚህ መጽሐፍ ጸሐፊ ማን እንደሆነ ጨርሶ ስለማይናገር፥ በበኩላችንም የምንሰጠው አስተያየት ግምታዊ ነው።

የዕብራውያን ትውፊት የመጽሐፉ ጸሐፊ ታሪኩን በመጽሐፈ ዕዝራ ያነበብነው ካህን ዕዝራ ነው ይላል። መጽሐፈ ዕዝራ፥ ነህምያና ዜና መዋዕል በአንድ ጸሐፊ መጻፋቸውን የሚያመለክት በርካታ ተመሳሳይነት አለ በማለት ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁራን ይስማማሉ፤ ነገር ግን ሌሎች ምሁራን ደግሞ በርካታ ልዩነትም ስላለ ጸሐፊው ዕዝራ አይደለም ይላሉ። 1ኛና 2ኛ ዜና የተጻፉት በአንድ ሰው ነው።

ጸሐፊው ማን እንደሆነ ባናውቅም ዳሩ ግን የታሪክ ሰው፥ የሥነ መለኮት ትምህርት አዋቂና ሃይማኖታዊ መምህር መሆኑን ከጻፈው መጽሐፉ እንገነዘባለን። ይህንን የምንመለከተው የጻፋቸውን ነገሮች በመረጠበት ሁኔታ ነው። በአንድ በኩል መጽሐፈ ዜና መዋዕል «ስብከት» እንደሆነ መመልከት እንችላለን፤ ምክንያቱም ጸሐፊው ለእግዚአብሔር በታማኝነት ስለ መቆምና እርሱን በቅድስና ስለማምለክ አንዳንድ እውነቶችን ለሕዝቡ ለማስተማር እንደተጠቀመበት ስለምናይ ነው። የብሉይ ኪዳን ታሪኮችን የማስተማርያ መሣሪያዎች አድርጎ ተጠቅሞባቸዋል።

## መጽሐፈ ዜና መዋዕል የተጻፈበት ጊዜ

የመጽሐፈ ዜና መዋዕል ታሪኮች ከዳዊት ዘመን ከ1020 ዓ.ዓ. ጀምሮ የይሁዳ ሕዝብ እስከተበተኑበት እስከ 538 ዓ.ዓ. ያለውን ጊዜ ያጠቃልላል። ጸሐፊው ማን እንደሆነ ስላላወቅን፥ ይህ መጽሐፍ መቼ እንደተጻፈ በእርግጠኝነት መናገር አንችልም። ከመጽሐፉ በግልጽ የምንመለከተው ግን፥ ባቢሎን ከወደቀች ከብዙ ዓመታት በኋላ የተጻፈ ሳይሆን እንደማይቀር ነው። ይህ የተጻፈው አይሁዶች ከስደት ወደ ይሁዳ በ538 ዓመተ ዓለም ከተመለሱ በኋላ ነው። ጸሐፊው ዕዝራ ከሆነ፥ የተጻፈው በ450 ዓ.ዓ. ነው። አንዳንድ ምሁራን መጽሐፉ የተጻፈው በ300 ዓ.ዓ. ነው ብለው ቢያስቡም፥ ከዘሩባቤል በኋላ በ400 ዓ.ዓ. ሳይሆን አይቀርም (1ኛ ዜና 3፡ 17-21)።

## የመጽሐፈ ዜና መዋዕል ጸሐፊ የተጠቀመባቸው ምንጮች

የመጽሐፈ ዜና መዋዕልን ታሪክ የጻፈው አንድ ጸሐፊ ብቻ ቢሆንም መጽሐፉን ለመጻፍ ግን የተለያዩ ነገሮችን አልተጠቀመም ማለት አይደለም። በዚህ ዘመን ያሉ ምሁራን የተለያዩ መጻሕፍትን እንደሚያነቡና ሲጽፉም እንደሚጠቅሱ ሁሉ የዜና መዋዕል ጸሐፊም በተለያዩ መረጃዎች ተጠቅሞአል። የዜና መዋዕል ጸሐፊ ለዓላማው ምቹ

ሆነው ያገኛቸውን የተለያዩ ታሪኮች ከተለያዩ መጻሕፍት በመጠቀም ሌሎቹን ታሪኮች ትቶአቸዋል። ለምሳሌ በ2ኛ ሳሙኤል የዳዊትንና የቤርሳቤህን የኃጢአት ታሪክ እናነባለን። የዜና መዋዕል ጸሐፊ ይህንን ታሪክ የሚያውቀው ቢሆንም የጻፈበትን ዓላማ ስለማያንጸባርቅ አላካተተውም። ቀጥሎ ጸሐፊው መጽሐፈ ዜና መዋዕልን ለመጻፍ እንደ ከተጠቀመባቸው ከምናውቃቸው መጻሕፍት አንዳንዶቹ ተዘርዝረዋል፡-

1. የመጽሐፍ ቅዱስ የተለያዩ መጻሕፍት፥ እንደእነ ፔንታቱክ፥ ሳሙኤልና ነገሥት የመሳሰሉ
2. የተለያዩ የዘር ሐረግ የተተነተነባቸው ሌሎች መጻሕፍት (1ኛ ዜና 4፡33፤ 5፡17፤ 7፡9)
3. ደብዳቤዎችንና የታወቁ የመንግሥት መዛግብትን (1ኛ ዜና 28፡11-12፤ 2ኛ ዜና 32፡16-17)
4. በሌላ መዛግብት የተጻፉ ግጥሞችና ቅኔዎች፥ ጸሎቶች ንግግሮችና መዝሙሮች (1ኛ ዜና 16፡8-36፤ 29፡10-22፤ 2ኛ ዜና 29፡30፤ 35፡25)
5. እንደ እስራኤልና የይሁዳ ነገሥታት መጽሐፍ፥ የዳዊትንና የሰሎሞንን መመሪያዎች የያዙ ሌሎች የታሪክ መጻሕፍት (2ኛ ዜና 16፡11፤ 26፡22፤ 35፡4)
6. በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የማይገኙ የነቢያት ጽሑፎች፥ ማለትም (የሳሙኤል፥ የናታንና፥የጋድ ዜና መዋዕል፥ የአሒያና የአዶ ትንቢቶች፥ የሸማያ፥ የኢዩና የኢሳይያስ ዘገባዎች ናቸው፤ 1ኛ ዜና 29፡29፤ 2ኛ ዜና 9፡29፤ 12፡15፤ 20፡34፤ 32፡32)።

## የዜና መዋዕል ታሪካዊ ሥረ መሠረት

የዜና መዋዕልን ዓላማ ለመረዳት መቼ እንደተጻፈና ለምን እንደተጻፈ መረዳት ያስፈልጋል። መጽሐፈ ዜና መዋዕል የተጻፈው የይሁዳ ሕዝብ በባቢሎን ከተደመሰሱ በኋላ ነበር። የይሁዳን ሕዝብ ታላቅና ልዩ ያደረጓቸው ያለፉ ነገሮች ሁሉ ጠፍተዋል። ቤተ መቅደሱ ተደምስሷል። የኢየሩሳሌም ቅጥርም ፈርሷል። ማንኛውም የዳዊት ዘር አሁን በዙፋን ላይ የለም። ከ70 ዓመታት በኋላ በ538 ዓ.ዓ. አንዳንድ ሰዎች ወደ ኢየሩሳሌም ቢመለሱም፥ የይሁዳ ሕዝብ በቁጥር ጥቂትና በፖለቲካም

ደካማ ነበሩ። ይሁዳ የፋርስ መንግሥት አንዲ ክፍለ ሀገር ነበረች። ሕዝቡም ራሳቸውን የቻሉ ሕዝብ ሳይሆኑ በፋርስ መንግሥት ቁጥጥር ሥር ነበሩ። ቤተ መቅደሱ የተሠራ ቢሆንም ከቀድሞው የሰሎሞን ቤተ መቅደስ ጋር ሲወዳደር በጣም ትንሽና ከመኖር የሚቆጠር አልነበረም። የኢየሩሳሌም ቅጥሮች በነህምያ መሪነት እንደገና ቢሠሩም፥ የታላቁ የዳዊት መንግሥት ዋና ከተማ የነበረችው ኢየሩሳሌም ትንሽና ደካማ ነበረች።

ከዚህም የተነሣ የይሁዳ ሕዝብ ተስፋ ቆረጡ። «እግዚአብሔር አሁንም ከእኛ ጋር ነውን?» ብለው ጠየቁ። ከባቢሎን መፍረስ በኋላ ከእግዚአብሔር ጋር የሚኖረን ግንኙነት ምንድን ነው? እግዚአብሔር ከአብርሃምና ከዳዊት ጋር የገባቸው ቃል ኪዳኖች አሁንም ይሠራሉ ወይስ ቀርተዋል? ከባቢሎን ውድቀት በኋላ ለብዙ ዓመታት ስለኖሩ፥ እግዚአብሔር የመረጠን ሕዝብ ከሆንን የይሁዳ ሕዝብ እንዲጠፉ ለምን ፈቀደ? እግዚአብሔር ስሙንና ክብሩን ለማድረግ የመረጣት ከተማ ኢየሩሳሌም ለምን ጠፋች? እነዚህና የመሳሰሉት ጥያቄዎች ስለነበሩዋቸው፥ የሕዝባቸውን ታሪክ መማር ነበረባቸው። እግዚአብሔር በዓለም ሕዝብ ሁሉ ላይና በይሁዳም ላይ ያለውን የሉዓላዊነት ቁጥጥር መማር ነበረባቸው። እግዚአብሔር ከአብርሃም፥ ከእስራኤልና ከዳዊት ጋር ለገባው ቃል ኪዳን በመታዘዝ ታማኝ የመሆናቸውን አስፈላጊነት መማር ነበረባቸው። የኃጢአት ውጤት ምን እንደሆነና የእግዚአብሔርን ፍርድ እንዴት እንደሚያመጣ መረዳት ነበረባቸው። እግዚአብሔር አንድ ቀን የእስራኤልን መንግሥት ለመመለስ ጻድቅ የሆነውን ንጉሥ እንደሚያስነሣ ሊነገራቸው ይገባ ነበር። መጽሐፈ ዜና መዋዕል የማስጠንቀቂያና የማበረታቻ መጽሐፍ ነው።

---

4ኛ ጥያቄ፥ ሀ) የቤተ ክርስቲያናችንን ታሪክ መረዳት የሚያበረታታን እንዴት ነው? ለ) የቤተ ክርስቲያናችንን ታሪክ መረዳት ከእውነት እንዳንርቅ የሚያስጠነቅቀን እንዴት ነው?

---

መጽሐፈ ዜና መዋዕል የታሪክ ዘገባውን የጀመረው ከፍጥረት መጀመሪያ ነው። ከአዳም ይጀምራል። የተለያዩ ሰዎችን የዘር ሐረግ በመመልከት፥ የእምነት መስመር ከአዳም ጀምሮ በተለያዩ የእምነት አባቶች ወደ ዳዊት እንዴት እንደደረሰ ያሳየናል። ጸሐፊው የዘር ሐረጎችን

በመዘርዝር፥ የአመራር ሥልጣን ወደ ሌዋውያንና ካህናት፥ ደግሞም ወደ ዳዊትና ልጆቹ እንዴት እንደደረሰ ያሳየናል።

በመጽሐፈ ዜና መዋዕል ውስጥ የተተነተኑት ታሪኮች ግን ዳዊት ከነገሠበት (ከ 1020 ዓ.ዓ. የባቢሎን ምርኮ እስከ ሆነበት እስከ 538 ዓ.ዓ. ጊዜ ያለውን የሚያካትቱ ናቸው። ይህም ማለት ሁለቱ መጻሕፍት ከ2ኛ ሳሙኤል እስከ 2ኛ ነገሥት መጨረሻ ድረስ ያለውን ጊዜ የሚያካትቱ ናቸው ማለት ነው።

ጸሐፊው የሚገልጸው የእነዚህን ጊዜያት ታሪክ ቢሆንም የሚያተኩረው ግን በተለዩ እውነቶች ላይ መሆኑ ግልጽ ነው። የሚከተሉትን ነገሮች ልብ ብለህ ተመልከት፡-

1. ጸሐፊው የእግዚአብሔርን ሕልውናና ቤተ መቅደሱን በሚያመለክተው በቃል ኪዳኑ ታቦት ላይ ያተኩራል።

2. ጸሐፊው በሰሜኑ የእስራኤል መንግሥት ላይ ከማተኮር ይልቅ፥ በይሁዳ ላይ በነገሡት በዳዊት ልጆች ላይ ያተኩራል። በተለይ ደግሞ የዳዊት መንፈሳዊ ልጆች በመሆን በይሁዳ ምድር ሃይማኖታዊ መነቃቃትን ባመጡ ሰዎች ላይ ያተኩራል (ምሳሌ፡- አሳ፥ ሕዝቅያስ፥ ኢዮስያስ ወዘተ)።

እነዚህ ሁለት እውነቶች በጣም ጠቃሚ የሆኑት ለምንድን ነው? መጽሐፈ ዜና መዋዕል የተጻፈው ኢየሩሳሌም ከፈረሰችና ባቢሎንም ከወደቀች በኋላ መሆኑን ማስታወስ ያስፈልጋል። በእርግጥ የተጻፈው አንዳንድ የአይሁድ ቅሬታዎች ለመኖር ወደ ኢየሩሳሌም በተመለሱበት ጊዜ ነበር። ቤተ መቅደሱን ቢገነቡም እንኳ፥ ሰሎሞን የሠራው ዓይነት ቤተ መቅደስ አልነበረም። የኢየሩሳሌምን ቅጥሮች ሠርተዋል። በፖለቲካ አንጻር ግን አሕዛብ በሆነው በፋርስ መንግሥት ቁጥጥር ሥር ነበሩ። በይሁዳ ሕዝብ የቀድሞ የፖለቲካ አመራር ታላቅነት ላይ ከማተኮር ይልቅ፥ የመጽሐፈ ዜና መዋዕል ጸሐፊ የፖለቲካ ታላቅነት የመንፈሳዊ ታላቅነትን ያህል አስፈላጊ እንዳልሆነ ሊያስገነዝባቸው ፈለገ። ዳዊትና ሰሎሞን ሌሎችም የቀድሞ ነገሥታት ዕቅዳቸው በከፍተኛ ደረጃ ሊከናወንላቸው የቻለው፥ በነበራቸው የግል ኃይልና ሥልጣን ሳይሆን ለእግዚአብሔርና ለሕጉ በነበራቸው ታዛዥነት ምክንያት ነበር። ስለዚህ ጸሐፊው የፖለቲካ ታላቅነት ከመንፈሳዊ ታላቅነት ቀጥሎ የሚመጣ ነገር

መሆኑን ሊያሳያቸው ፈልጎ ነበር። ይሁዳ በፖለቲካ ወደ ታላቅነት ልትመጣ የምትችለው፥ በመንፈሳዊ ነገር ታላቅ ከሆነች በኋላ ብቻ ነበር።

| |
|---|
| 5ኛ ጥያቄ፥ ይህ እውነት ዛሬም በዚህ ዘመን በመንፈሳዊ ነገር ታላቅ ሳይሆኑ፥ በቁጥር ሊበዙና በልማት ተግባር የታወቁ ለመሆን ለሚፈልጉ አብያተ ክርስቲያናት ጠቃሚ የሚሆነው እንዴት ነው? |

ከ500-300 ዓ.ዓ. የይሁዳ መንግሥት፥ በተለይ በስተሰሜን በኩል በሰማርያ የሐሰት ትምህርት መስፋፋት አጋጥሞት ነበር። በቀድሞው ሰሜናዊ እስራኤል ከነበሩ አይሁድና አሕዛብ የመጡ እነዚህ ድብልቅ ሳምራውያን፥ የራሳቸውን የተበላሸ አምልኮ ከመጀመራቸው እንዲያውም የረከሰ ቤተ መቅደስ በመሥራት አሁራ ማዝዳ የሚባለውን አምላካቸውን ማምለክ ጀምረው ነበር፤ ከዚያም በኋላ የግሪክ ሃይማኖት የመስፋፋት አደጋም ነበር። ስለዚህ የዜና መዋዕል ጸሐፊ፥ ለእግዚአብሔር ያላቸውን አምልኮ በንጽሕና የመጠበቅ አስፈላጊነትን ለአይሁድ ያስታውሳቸዋል። ጊዜያዊ የሆኑ ተሐድሶዎች በዕዝራና በነህምያ አልፎ አልፎ ቢደረጉም፤ ለረጅም ጊዜ ግን አልቀዩም። ሕዝቡ ወዲያውኑ ወደ ጣዖት አምልኮ ይመለሱ ነበር።

| |
|---|
| 6ኛ ጥያቄ፥ ሀ) የእግዚአብሔር ሕዝብ ዓለምን መምሰል እንደሌለባቸውና የሐሰት ትምህርት ገብቶ እውነተኛ እምነታቸውን እንዲያጠፉ መፍቀድ እንደሌለባቸው ማስታወስ የሚያስፈልገው ለምንድን ነው? ለ) የሐሰት ትምህርትን ቤተ ክርስቲያንህን እንዴት እንደ ጎዳት ምሳሌ ስጥ። ሐ) የቤተ ክርስቲያንህ መሪዎች ሐሰተኛ ትምህርት ለመዋጋት ምን ያደርጋሉ? መ) የሐሰት ትምህርትን በተሻለ ሁኔታ ለመዋጋት የቤተ ክርስቲያንን መሪዎች ምን ማድረግ ይችላሉ? ሠ) የሐሰት ትምህርትን ለመዋጋት፥ ታሪክን በተሻለ ሁኔታ መረዳት ለምን ይጠቅማል? |

አይሁድ ሌላ ንጉሥ በእነርሱ ላይ እንደሚነግሥ ተስፋ ቢያደርጉም፥ ከዳዊት ዘር የሆነ ንጉሥ ከዚያ በኋላ አልተነሣም። ከረጅም ጊዜ ጀምሮ ተስፋ የተሰጣቸውን መሢሕ ሲጠብቁ ቢቆዩም ነፃ ሊያደርጋቸው ገና ወደ እነርሱ አልመጣም ነበር።

የመጽሐፈ ዜና መዋዕል ጸሐፊ ሌላ ታሪክ እንዲጽፍ ያስፈለገበት ምክንያት ይህ ነበር። ሕዝቡን ሊያስታውስ የፈለገው አንድ ቀን እስራኤል

ተመልሶ እንደሚቅዋቋም ነበር። እንደ ዳዊት ያለ እጅግ መልካም መሪ አንድ ቀን ሕዝቡን እንደገና ይመራል። በእርሱም መሪነት እውነተኛ ሃይማኖታዊ ተሐድሶ ይኖርና ሕዝቡ እግዚአብሔርን ይወዳሉ፤ ይታዘዙታልም። ይህ ሰው እስኪደርስ ድረስ ሕዝቡ ለእግዚአብሔር ታማኞች እንዲሆኑና በኃጢአታቸው ምክንያት የእግዚአብሔርን ፍርድ እንዳይቀምሱ ያስጠነቅቃቸዋል፤ ያበረታታቸዋልም።

መጽሐፈ ዜና መዋዕልን ከሌሎች መጻሕፍት ጋር ስናወዳድረው፥ ጸሐፊው በውስጡ ያቀረባቸውን ነገሮች በመምረጥና በማደራጀት ከሌሎቹ የተለየ ነው። በተጨማሪም በአንዳንዶቹ የዜና መዋዕል ታሪኮች ውስጥ የሚገኙ አንዳንድ ታሪኮችና ቁጥሮች በሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ከሚገኙት የተለዩ ናቸው። የእነዚህ ልዩነቶች ምክንያቶች ምን እንደሆኑ ሙሉ በሙሉ ባናውቅም የሚከተሉት ነገሮች ለልዩነቶቹ መከሰት ምክንያት ከሆኑት አንዳንዶቹ ናቸው:-

1. በመጽሐፈ ሳሙኤልና ነገሥት ውስጥ ምን እንደተጻፈ ይህ ጸሐፊ ያውቅ ስለነበር በድጋሚ ሊጽፈው አልፈለገም፤ ነገር ግን ዜና መዋዕልን ለመጻፍ የተነሣበትን የሥነ - መለኮት ዓላማ ለመደገፍ የሚያስችሉትን ነገሮች ብቻ መረጠ።

| |
|---|
| 7ኛ ጥያቄ፥ የሚከተሉትን ክፍሎች አወዳድር። በዜና መዋዕልና በሌሎቹ ክፍሎች መካከል ያለውን የቁጥር ልዩነት ዘርዝር (2ኛ ሳሙ. 23:8 እና 1ኛ ዜና 11:11፤ 2ኛ ሳሙ. 24:9 እና 1ኛ ዜና 21:5)። |

2. በመጽሐፈ ዜና መዋዕል፥ ሳሙኤልና ነገሥት መካከል ባሉ ተመሳሳይ ታሪኮች አንዳንድ የቁጥር ልዩነቶች አሉ። በተመሳሳይ ታሪክ ውስጥ ካሉ 213 ቁጥሮች፥ 19ኙ ልዩነት አላቸው። ይህንን አንዳንዶቹ ጸሐፊዎች በሚገለብጡበት ጊዜ የሠሩት ስሕተት ነው ለማለት እንችላለን። ሌሎቹ ደግሞ ቀጥተኛ ቁጥሮች ሳይሆኑ ግምታዊ ወይም የተጠጋጉ ናቸው።

ለእነዚህ ልዩነቶች ምክንያቶቹ ምን እንደሆኑ ሙሉ ለሙሉ ባናውቅም፥ መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል ስለ መሆኑና ስሕተትም እንደሌለበት ያለንን መረዳት አይለውጠውም። ቀደም ሲል እንደተማርነውና ክርስቲያኖችም እንደመሆናችን መጽሐፍ ቅዱስ

በመጀመሪያ ጽሑፎቹ ምንም ስሕተት እንደሌለበት ቢገኝበትም እንኳ በቅጂዎች ምክንያት ስሕተት እንደሚፈጥር እናምናለን። ለዚህ ልዩነት አሁን ግልጽ የሆነ ምክንያት ባይኖረንም፥ መጽሐፍ ቅዱስ ሐቀኛና አንዳች ስሕተት የሌለበት ለመሆኑ እርግጠኞች መሆን እንችላለን። አንድ ቀን ያ ልዩነት ከምን እንደመጣ እንገነዘባለን።

## የዜና መዋዕል አስተዋጽኦ

1. ከፍጥረት ጀምሮ አይሁድ ከባቢሎን ምርኮ እስከ ተመለሱበት ጊዜ ድረስ ያለውን እምነት የሚመለከት የትውልዶች ታሪክ የዘር ሐረግ (1ኛ ዜና 1-9)
2. የተባበረው የእስራኤል መንግሥት
   ሀ. የዳዊት ታሪክ (1ኛ ዜና 10-29)
   ለ. የሰሎሞን ታሪክ (2ኛ ዜና 1-9)
3. የይሁዳ መንግሥት ታሪክ (2ኛ ዜና 10-36፡16)
4. የይሁዳ መንግሥት መጣረክ (2ኛ ዜና 36፡17-23)

## የመጽሐፈ ዜና መዋዕል አወቃቀር

1ኛ እና 2ኛ ዜና መዋዕልን በአራት ዋና ዋና ክፍሎች መክፈል ይቻላል።

1. የመጀመሪያው ክፍል በተለይ የሚያተኩረው የዘር ሐረግ (ትውልድ) ላይ ነው (1ኛ ዜና 1-9)። ይህ ዝርዝር የዘር ሐረግ ለእኛ ምንም የሚጠቅመን ባይመስለንም፥ ለአይሁድና ለመጽሐፈ ዜና መዋዕል በጣም አስፈላጊ ነበር። ጸሐፊው ከአዳም ጀምሮ እስከ ይሁዳ መታደስ ድረስ የዘለቀውን የዘር ሐረግ የጠቀሰበት ሦስት ታላላቅ ምክንያቶች ነበሩት:-

የመጀመሪያው፥ ጸሐፊው ከአዳም ጀምሮ ከምርኮ በኋላ እስካሉት አይሁድ ድረስ የነበረውን የእምነት መስመር (የዘር ሐረግ) ለመናገር ፈልጎ ነው። ይህ የእምነት መስመር አይሁድ ከእስራኤልም ሆነ ከይሁዳ ቢሆኑ አንድ ሕዝብ እንደሆኑ የሚያሳይ ነበር። የዘር ግንዳቸው ከአንድ አባት ከአብርሃምና ከአንድ ሰው ከአዳም እንደሆነ የሚያሳይ ነበር።

ሁለተኛው፥ የዘር ግንዱ (ሐረጉ) የሚያተኩረው በሌዊና በይሁዳ ነገድ ላይ ነበር። እነዚህ ሁለት ነገዶች የክህናትና የነገሥታት ነገዶች ስለሆኑ በጣም አስፈላጊዎች ነበሩ። ጸሐፊው እነዚህ ሁለት ነገዶች አሁንም ቢሆን የሕዝቡ ትክክለኛ መሪዎች እንደሆኑና የዘር ሐረጋቸውም እንዴት እንደ ቀጠለ ለማሳየት ፈልጎ ነበር። የሌዊ ነገዶች የሃይማኖት መሪዎች ነበሩ። በመጽሐፈ ነህምያ እንደምንመለከተው፥ የዘር ሐረጋቸው ዞሮ ዞሮ ወደ አሮን የማይደርስ በቤተ መቅደስ ውስጥ እንደ ካህናት ማገልገል አይችሉም ነበር (ነህ. 7፡64-65)። መጽሐፈ ዜና መዋዕል በተጻፈበት ጊዜ ነገሥታት ባይኖሩም፥ የይሁዳ ነገድ መኖር ብቻ እንኳን ከዳዊት ዘር የሆነ ንጉሥ እስራኤልን እንደሚገዛ እግዚአብሔር ለዳዊት የገባው ቃል ኪዳን ማረጋገጫ ነበር።

ሦስተኛ፥ ይህ የዘር ሐረግ ዝርዝር ሕጋዊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ መፍትሔ ለመስጠት የሚረዳ ነበር። ይህ የዘር ሐረግ በኩር የሆኑ የወንዶች ስም ስለሚዘረዝር፥ የቤተሰብ ውርስ፥ የፖለቲካ ሥልጣንና የመሬት ባለመብትነት መስመርን የሚያሳይ ነበር።

በዜና መዋዕል ያለውን የዘር ሐረግ ዝርዝር በኦሪት ዘፍጥረትና በማቴዎስ ወንጌል ካለው ጋር ስናወዳድር አንዳንድ ልዩነቶችን እንመለከታለን። ይህንን ልዩነት የምናብራራበት የተለመደው መንገድ፥ የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፊዎች ብዙ ጊዜ የዘር ሐረጎችን ለማሳጠር ከመሀል አንዳንዶቹን ስሞች መተዋቸው ነው። በዕብራይስጥ «ልጅ» የሚለው ቃል «ዘር» ማለትም ስለሚሆን፥ በአንዳንድ ሁኔታዎች የዘሩን ሐረግ በማሳየት ረገድ በርካታ ትውልዶች ይዘለላሉ።

2. ዳዊትና የሰሎሞን ዘመነ መንግሥት፡- የመጽሐፈ ዜና መዋዕል ጸሐፊ አብዛኛውን የ1ኛና የ2ኛ ሳሙኤል ክፍል እንደገና ቢተርከም፥ በዜና መዋዕል ውስጥ የተሰጠው ትኩረት ለየት ያለ ነው። የመጽሐፈ ዜና መዋዕል ጸሐፊ ያተኮረው ዳዊት ከእግዚአብሔር ጋር የነበረውን ልዩ ግንኙነት ከቃል ኪዳኑ ታቦትና ከቤተ መቅደሱ ጋር በነበረው ግንኙነት እንዴት እንደገለጠው በማሳየት ነው። የመጀመሪያው የእስራኤል ንጉሥ የነበረው ሳኦል የእግዚአብሔርን ታቦት ተወና እርሱንም እግዚአብሔር ንቆ ተወው። ዳዊት ግን የእግዚአብሔርን ታቦት አከበረና ወደ ኢየሩሳሌም አመጣው፤ እንዲሁም እግዚአብሔር ዳዊትን ቤተ መቅደሱን ይሠራ ዘንድ ባይፈቅድለትም

እንኳ የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ ለመሥራት የሚያስፈልገውን ነገር ሁሉ አዘጋጀ። የቃል ኪዳኑ ታቦትም መኖር የነበረበት በዚያ ነበር።

**8ኛ ጥያቄ፥ የመጽሐፈ ዜና መዋዕል ጸሐፊ ስለ ቃል ኪዳኑ ታቦት በጣም ያሳሰበውና ትኩረቱን በእርሱ ላይ ያደረገው ለምን ይመስልሃል?**

አይሁድ እግዚአብሔር በሰማይ የሚኖርና ከሰማይ ሆኖ የሚገዛ መሆኑን የሚያውቁ ቢሆንም እንኳ የቃል ኪዳኑን ታቦት የእግዚአብሔር ሕልውና ቁሳዊ አምሳያ አድርገው ይመለከቱት ነበር። በእርግጥ እግዚአብሔርን በታቦቱ አይወስኑትም ነበር። ታቦቱ ግን የእግዚአብሔርን ሰማያዊ ዙፋን በምድር ላይ የሚወክል ምድራዊ ዙፋን ነበር፤ ስለዚህ እግዚአብሔር በመካከላቸው ለመሆኑ ቁሳዊ የሆነ ተወካይ እንጂ የሚመለክ ነገር አልነበረም። በዳዊት ዓይን ይህን የእግዚአብሔር ሕልውና ምልክት የሆነው የእግዚአብሔር ታቦት ጊዜያዊ በሆነ ሕንጻ ወይም በድንኳን መኖሩ ትክክል አልነበረም። ዳዊት ለእግዚአብሔር ወይም ለታቦቱ የሚሆን ቤት ማለትም ቤተ መቅደስ ለመሥራት መፈለጉ ለእግዚአብሔር ያለው ፍቅር መግለጫ ነበር። ይህን እንዲያደርግ እግዚአብሔር ለዳዊት ባይፈቅድለትም እንኳ የዳዊት ልጅ የአባቱን ምኞት ፈጽሞአል።

**9ኛ ጥያቄ፥ ሀ) ለእግዚአብሔር ያለንን ፍቅር ለማረጋገጥ ዛሬ ልናደርጋቸው የምንችል አንዳንድ ነገሮች ምንድን ናቸው? ለ) እግዚአብሔር ዛሬ የሚኖረው የት ነው? (1ኛ ቆሮ. 6፡19)። ሐ) ዳዊት በብሉይ ኪዳን ታቦቱንና ቤተ መቅደሱን ባከበረ ጊዜ ለእግዚአብሔር የሰጠውን ዓይነት ክብር እንዴት ለእግዚአብሔር መስጠት እንችላለን?**

መጽሐፈ ዜና መዋዕል በሰሎሞን ላይም አተኩሮአል። ሰሎሞን ታላቅ የሆነው ስለ ጥበቡና ስለ ታላቁ ቤተ መንግሥቱ ሳይሆን፥ እግዚአብሔር የሚመለከበት ትልቅ ቤተ መቅደስ በመሥራቱ ነበር።

የመጽሐፈ ዜና መዋዕል ጸሐፊ ስለ ዳዊትም ሆነ ስለ ሰሎሞን አንዳችም ክፉ ነገር አለመጨመሩን ማየት የሚያስገርም ነው። ይህን ያላደረገው የእነዚህን ሁለት ሰዎች ኃጢአትና ችግር ባለማወቁ አልነበረም፤ ነገር ግን በዳዊትና በሰሎሞን ሕይወት ታሪክ ላይ ያተኮረው ሁለት ዓላማዎች ስለነበሩት ነው። በመጀመሪያ፥ ዳዊትንና ሰሎሞንን

ሌሎች ነገሥታትና የእግዚአብሔር ሕዝብ መሪዎች ሁሉ ሊከተሏቸው የሚገቡ መልካም ምሳሌነት ያላቸው መሪዎች እንደሆኑ ለማመልከት ነበር። እግዚአብሔርን ስለሚወዱትና ስለሚያከብሩት እርሱም በተራው አከበራቸው። እንደ ጸሐፊው አመለካከት ፍጹም መሪዎች እንደመሆናቸው፥ ለመጨረሻው ታላቅ ንጉሥ ተምሳሌቶች ነበሩ፤ ያም ንጉሥ እንደ ዳዊት የሚነግሥ መሢሕ ሲሆን ከኃጢአት ግን የራቀ ነው።

በሁለተኛ ደረጃ፥ ጸሐፊው ዳዊትና ሰሎሞን እንዴት የሙሴና የኢያሱ ምሳሌዎች እንደ ነበሩ አሳይቶአል። ዳዊት እንደ ሙሴ ነበር። ሁለቱም በእግዚአብሔር የተወደዱ ነበሩ። ሁለቱም እግዚአብሔርን የሚፈሩ መሪዎች ነበሩ። ይሁን እንጂ ሁለቱም የተመኙት ነገር አልሆነላቸውም። ሙሴ ወደ ተስፋይቱ ምድር መግባት አልቻለም፤ ዳዊት ደግሞ ቤተ መቅደሱን መሥራት አልቻለም። የሁለቱም ግብ በእነርሱ ቦታ በተተኩ ሰዎች ከፍጻሜ ሊደርስ ቻለ።

ሰሎሞን እንደ ኢያሱ ነበር። የእግዚአብሔርን ሕዝብ ወደ ዕረፍትና ወደ ብልጽግና ለማድረስ በሁለቱም እግዚአብሔር ተጠቅሞባቸዋል (1ኛ ዜና 22፡8-9 ና ኢያሱ 11፡23፤ 21፡44)። ዳዊትና እግዚአብሔር ለሰሎሞን የሰጡት የማበረታቻ ቃላት በአብዛኛው ለኢያሱ ከተሰጡት ጋር ተመሳሳይ ነበሩ። (1ኛ ዜና 22፡11-13፥ 16፤ 28፡7-10፥ 20፤ 2ኛ ዜና 1፡1ን ከዘዳ. 31፡5-8፥ 23፤ ኢያሱ 1፡5-9 ጋር አወዳድር)።

3. የይሁዳ ነገሥታት፡- መጽሐፈ ዜና መዋዕል ሁሉንም የይሁዳ ነገሥታት ባይጠቅስም እንኳ «መልካም» ለሆኑና እግዚአብሔርን ለሚፈሩ መሪዎች ጸሐፊው በተለይ ትኩረት የሰጠው ነው። እንደ ዳዊትና ሰሎሞን በነበሩና ቤተ መቅደሱን በማንጻት፥ ንጹሕ የሆነ የእግዚአብሔር አምልኮ እንደገና በመጀመር፥ እንዲሁም የጣዖት አምልኮ በማጥፋት እግዚአብሔርን ባከበሩ መሪዎች ላይ አትኩሮአል።

4. መጽሐፈ ዜና መዋዕል የሚደመደመው በምርኮ ነው። ጸሐፊው ትኩረት ያደረገው፥ ነቢያት ሕዝቡ ወደ ምርኮ እንደሚወሰዱና ይሁዳ እንደምትጠፋ፥ እንደምትታደስም በተናገሩት ላይ ነው። የእግዚአብሔርን ቅጣት ያስከተለው የእግዚአብሔር ሕዝብ ዓመፅ ነበር። ይህ ቅጣት የዳዊት ሥርወ - መንግሥት መጥፋትንና የቤተ

መቅደሱን መደምሰስ አስከተለ። የዳዊት ሥርወ መንግሥት ሊታደስ ባይችልም ቤተ መቅደሱ ግን እንደገና ተሠርቶአል።

መጽሐፈ ዜና መዋዕል የተጻፈባቸው ዓላማዎች

1. መጽሐፍ ቅዱስ የሚያተኩረው በእግዚአብሔር ላይ ነው። እርሱ የፍጥረታትና የሁሉ ጌታ እንዲሁም ታሪክን የሚመራና የሚወስን ነው። የመጽሐፈ ዜና መዋዕል ትኩረትም በእግዚአብሔር ላይ ነው። ጸሐፊው ከምርኮ የተመለሱ እስራኤላውያን አሁንም እግዚአብሔር ለእነርሱ እንዴት እንደሚሠራ እንዲያዩ ይፈልግ ነበር፤ ስለዚህ እግዚአብሔር በእስራኤል ሕዝብ ታሪክ ውስጥ ያለውን ሚና በመናገር ላይ አተኮረ። እስራኤልን ከዓለም ሕዝብ ሁሉ መካከል የመረጠው እግዚአብሔር ነበር (1ኛ ዜና 16፡13)። እግዚአብሔር ከእስራኤላውያን መካከል በታቦቱ ፊት የሚያገለግሉ ሰዎችን ማለት ሌዋውያንን መረጠ (1ኛ ዜና 15፡2)። ዳዊትን ለንጉሥነት መረጠው (1ኛ ዜና 28፡4)። ሰሎሞንን ቤተ መቅደሱን ለመሥራት መረጠው (1ኛ ዜና 28፡5-6)። እንደዚሁም ኢየሩሳሌምን የልዩ ክብሩ መኖሪያ እንድትሆን የመረጣትና (2ኛ ዜና 6፡6) ስሙንና ክብሩን በቤተ መቅደሱ ውስጥ ያኖረው እግዚአብሔር ነው (2ኛ ዜና 7፡12፥16)።

ጸሐፊው የነገሥታትን ዘመን ታሪክ የከለሰው፥ እግዚአብሔር ዓላማውን ከዚህ በፊት በነበሩት ዘመናት እንደ ፈጸመ ለእስራኤላውያን ያለውንም ዓላማ እንደሚፈጽም ለማስተማር ነበር። እግዚአብሔር አሁንም ቢሆን ዓላማና ዕቅድ አለው። እግዚአብሔር ሕዝቡን አልተወም፥ አልረሳምም (1ኛ ዜና 17፡16-27)። ለአይሁድ የመጽሐፈ ዜና መዋዕል መልእክት የተስፋ መልእክት ነበር። እግዚአብሔር ለዳዊትና ለሰሎሞን እንዳደረገ አንድ ቀን ለእስራኤላውያን ሁሉ ያደርጋል (ዘካ. 14፡12-21)።

| |
|---|
| 10ኛ ጥያቄ፥ ሮሜ 8፡29-30 አንብብ። ሀ) እግዚአብሔር የእስራኤልን ሕዝብ በአንድነት እንደመረጠ፥ እኛንስ በግል የመረጠን እንዴት ነው? ለ) እግዚአብሔር በቀድሞ ዘመን የሠራቸውን ነገሮች ማወቅ ዛሬ እኛን እንዴት ያነቃቃናል? |

2. ጸሐፊው ዳዊትና ሰሎሞን በእስራኤል ሕዝብ ላይ ንጉሥ ይሆኑ ዘንድ እግዚአብሔር የገባላቸው ቃል ኪዳን ትክክለኞች ወራሾች መሆናቸውን በማሳየት ላይ ሊያተኩር ፈልጓል። «እውነተኞች እስራኤላውያን» በይሁዳ የነበሩትና በተለይ ደግሞ ከምርኮ የተመለሱት ነበሩ። የይሁዳ ነገድ አንድነቱን መጠበቅ አስፈላጊው ነበር፤ ምክንያቱም አንድ ቀን እግዚአብሔር በይሁዳ ሕዝብ መካከል በኃይል ለመሥራት ስለሚፈልግ ይመለሳል፤ ነገር ግን ደራሲው በተጨማሪ ሊያስተምር የፈለገው የእስራኤልን አንድነት በተመለከተ ነበር።በዜና መዋዕል መጽሐፍ ብዙ ጊዜ በእሥራኤል ይኖሩ የነበሩ አይሁዳውያን ወደ ይሁዳ በመምጣት እውነተኛውን እግዚአብሔርን ማምለክ እንዴት እንደቀጠሉ ተጽፏል። ከይሁዳ ነገድ የሆነው መሢሑ የዳዊት ልጅ ይመጣና ዳዊት ከዚህ ቀደም እንደነገሠው ይነግሣል። ዳዊትና ሰሎሞን በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ ለሚነግሡ ሌሎች መሪዎች ሁሉ ምሳሌ ነበሩ።

| |
|---|
| 11ኛ ጥያቄ፥ ከዳዊትና ከሰሎሞን ሕይወት ጥናትህ፥ ለቤተ ክርስቲያን አመራር መልካም ምሳሌዎች የሚሆኑ ነገሮች የትኞቹ ናቸው? |

3. ለእግዚአብሔር ንጹሕ የሆነ አምልኮ አስፈላጊ መሆኑን ለሕዝቡ ለማስታወስ ነበር። ከምርኮ የተመለሱት አይሁድ የቀድሞ አባቶቻቸው እንዳደረጉት የአሕዛብን የአኗኗር ዘይቤና አምልኮ የመልመድ ፈተና ደርሶባቸው ነበር። አሁን ያንን ወደ መሰለ ሁኔታ ውስጥ ለመግባት ተቃርበው ነበር፤ ስለዚህ ጸሐፊው ለሕዝቡ ስለ ንጹሕ አምልኮ ለማስተማር የቀድሞውን ነገር ተጠቀመበት። ትንሽና ኢምንት ቢመስላቸውም እንኳ በመካከላቸው ያለውን ቤተ መቅደስ ማክበር ነበረባቸው። አምልኮአቸውንም በቤተ መቅደስ ውስጥ ብቻ መፈጸም ነበረባቸው። ለእግዚአብሔር የሚሆነውን አምልኮ ለመምራት የተመረጡትን የካህናትና የሌዋውያንን ትምህርትም መታዘዝ ነበረባቸው።

| |
|---|
| 12ኛ ጥያቄ፥ ሀ) ዛሬስ የክርስቲያኖች አምልኮ ሊበላሽ የሚችለው እንዴት ነው? ለ) አምልኮአችን ንጹሕና እግዚአብሔርን የሚያከብር መሆኑን ለማረጋገጥ፥ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ዛሬም ማድረግ የሚችሉት ነገር ምንድን ነው? |

4. በረከት እንዲኖር መታዘዝ መኖር እንዳለበት ለሕዝቡ ለማስታወስ ነበር። ሕዝቡ እግዚአብሔር ለሰጣቸው ሕግጋት መታዘዝ ነበረባቸው። የእግዚአብሔር መልእክተኞች የሆኑት ነቢያት፥ የእግዚአብሔርን ቃል ወደ እነርሱ ይዘው ሲመጡ ሊታዘዙአቸው ይገባ ነበር። ጸሐፊው ኃጢአት በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ የእግዚአብሔርን ፍርድ እንደሚያመጣ ሊያስታውሳቸው ይፈልግ ነበር (1ኛ ዜና 28፡9)። በተጨማሪ ደግሞ ንስሐ፥ ለእግዚአብሔር መታዘዝና በእርሱ መታመን ካለ፥ እግዚአብሔር ሰላምን፥ ድልንና ብልጽግናን እንደሚሰጣቸው ለመግለጽም ፈልጎ ነበር (2ኛ ዜና 7፡14)።

---

13ኛ ጥያቄ፥ ሀ) ዛሬስ ይህ ትምህርት ለእኛ የሚያስፈልገው እንዴት ነው? ለ) አለመታዘዝ ፍርድን፥ መታዘዝ ደግሞ በረከትን ወደ ክርስቲያን ሕይወት እንዴት እንደሚያመጣ ምሳሌዎችን ዘርዝር።

---

## የመጽሐፈ ዜና መዋዕል ዋና ዋና ትምህርቶች

1. ከመዝሙረ ዳዊት በቀር በብሉይ ኪዳን ከሚገኙ መጻሕፍት ሁሉ በላይ አይሁድ እግዚአብሔርን በብሉይ ኪዳን ዘመን እንዴት እንዳመለኩ በማሳየት፥ ዛሬም እግዚአብሔርን እንዴት ማምለክ እንዳለብን የሚያስተምር መጽሐፍ ዜና መዋዕል ነው። በመጽሐፈ ዜና መዋዕል በርካታ የግልና የኅብረት አምልኮ ምሳሌዎችን እናገኛለን (ለምሳሌ፥ 2ኛ ዜና 31፡20-21)። ዛሬም ቢሆን በርካታ ክርስቲያኖች እግዚአብሔርን በእውነት ማምለክ የምንችለው ልክ የብሉይ ኪዳን ዓይነት የአምልኮ መንገድ ወይም ውጫዊ ሁኔታ ከተከተልን ነው ይላሉ። በምንጸልይበት ወይም በምንዘምርበት ጊዜ እጆቻችንን ማንሣት አለብን ይላሉ፤ መጨፈርና እልልታ ማሰማት አለብን ይላሉ። ይህ ግን በጕችንና ከርማዎች ጥጃዎችን መሠዋት አለብን ወይም በበገናና በጥንታዊ መዛሪያዎች ብቻ መጠቀም አለብን ወዘተ እንደማለት ነው። አምልኮ የምትኖርበትን ማንኛውንም ዓይነት ባሕል ቅርፅ ይይዛል። እግዚአብሔር የሚፈልገው ዋናው ነገር ውስጣዊ ልባችንን እንጂ ውጫዊ የአምልኮ ቅርፃችንን አይደለም። እግዚአብሔርን የሚያከብረው በምስጋናና በአምልኮ የተሞላ ልብ ነው። በመጽሐፈ ዜና መዋዕል ውስጥ የሚገኙትን የአምልኮ

ምሳሌዎች በሙሉ በጥንቃቄ ብናጠና ከሚከተሉት ነገሮች አንዳንዶቹን እንመለከታለን፡-

ሀ. የኅብረት አምልኮ ሥነ - ሥርዓት ያለውና አምልኮውን እንዲመሩ በተመረጡ ሰዎች የሚመራ እንዲሆን ብዙውን ጊዜ በቁጥጥር መካሄድ አለበት። በመጽሐፈ ዜና መዋዕል እንደምናየው፥ ሕዝቡ አምልኮ የሚፈጽሙት እንደፈለጉት ሳይሆን፥ ብዙ ጊዜ የእግዚአብሔርን ሕዝብ አምልኮ በሚመሩት በካህናት መሪነት ነበር (ለምሳሌ፥ 2ኛ ዜና 35፡1-19)።

ለ. አምልኮ እግዚአብሔር ለሚሠራው ታላቅ ሥራ ድንገተኛ ምላሽ የሚሆንባቸው ጊዜያትም አሉ። እነዚህ የተለመዱ ዓይነት የአምልኮ ጊዜያት አይደሉም። እግዚአብሔር ታላቅና ያልተለመዱ ነገሮች ሲያደርግልን የሚፈጸሙ ናቸው (ለምሳሌ፥ 1ኛ ዜና 16፡28-36)።

ሐ. አምልኮ ሥርዓት ሆኖ መፈጸም የለበትም፤ ወይም ልማድ ሆኖ፥ ወይም ሌሎች ስላደረጉት፥ ወይም መንፈሳዊ ለመምሰል ስለፈለግን የሚፈጸም ነገር አይደለም። ይልቁንም የአምልኮ ምንጩ ለእግዚአብሔር ያለን ፍርሃት ወይም ፍቅር ነው (ለምሳሌ፥ 2ኛ ዜና 6፡31፥ 33፤ 1ኛ ዜና 28፡9፤ 2ኛ ዜና 19፡9)።

መ. አምልኮ መዝሙር ከመዘመርና የእግዚአብሔርን ቃል ከመስማት በላይ ነው። ከምንፈጽማቸው ውጫዊ የሃይማኖት ሥርዓቶች በላይ ነው። ይልቁንም አምልኮ እግዚአብሔርን ከሚወድና እርሱንም ለማክበር ከተዘጋጀ ልብና አእምሮ የሚመነጭ ውስጣዊ ዝንባሌ ነው (ለምሳሌ፥ 1ኛ ዜና 16፡10-11፤ 28፡9፤ 2ኛ ዜና 15፡12፥ 15)።

ሠ. አምልኮ ዝም ብሎ መቀመጥ ሳይሆን፥ መላ ሰውነታችንን የሚያካትት ነው። ከሁሉም የሚሻል አንድ የተለየ ዓይነት አምልኮ የለም፤ ነገር ግን የተለያዩ ዓይነት የሰውነት አቋሞች፥ ተግባራትና እንቅስቃሴዎች ተጠቅሰዋል (ለምሳሌ፥- 2ኛ ዜና 20፡18፤ 29፡26-30፤ 31፡2፤ መዝ. 5፡7፤ 20፡5፤ (28)፡2፤ (47)፡1፤ (95)፡6፤ (123)፡1)። እነዚህ ሁሉ የሚያስተምሩት፥ እግዚአብሔርን ለማምለክ እኛነታችን ሁሉ አገልግሎት ላይ መዋል እንዳለበት ነው። በአምልኮ ውስጥ ሙሉ ለሙሉ መሳተፍ አለብን እንጂ ዝም ብለን

ልንቀመጥና ምስጋናውንና ዝማሬውን ሁሉ ሌሎች እንዲያደርጉልን መጠበቅ የለብንም። አምልኮ ዝም ብሎ ተቀምጦ የመመልከት ድርጊት አይደለም። ለምሳሌ፥ መዘምራን ሲዘምሩ ብቻ የማዳመጥ ሳይሆን መሳተፍ አለብን። (ለምሳሌ፥ በአንድነት መዘመርና እግዚአብሔርን ማመስገን ነው)። በአምልኮ ፕሮግራማችን ለሕዝቡ ሁሉ በቂ ጊዜ በመስጠት በአምልኮ እንዲሳተፉ ለማድረግ መጠንቀቅ እንጂ በመዘምራን እንዲስተናገዱ ብቻ ማድረግ የለብንም።

ረ. አምልኮ ድብቅ በሆነው በልባችን ክፍል ሊፈጸም ቢችልም፥ ብዙ ጊዜ የሚገለጠው ግን በንግግር ነው፤ ስለዚህ በመጽሐፈ ዜና መዋዕል ውስጥ ሕዝቡ በጉባኤ መሐላ ሲያደርግ፥ እግዚአብሔርን ሲያመሰግን፥ ወደ እግዚአብሔር ሲጸልይና ሲዘምር እንመለከታለን።

| |
|---|
| 14ኛ ጥያቄ፥ ሀ) እነዚህ ከላይ የተመለከትናቸው እውነቶች፥ በእግዚአብሔር ፊት እውነተኛ አምልኮ ምን እንደሆነ እንድንረዳ እንዴት ይረዱናል? ለ) በተለያዩ ክርስቲያኖች ላይ አንዳንድ ጊዜ ችግር የሚፈጥሩት የትኞቹ እውነቶች ናቸው? ለምን? ሐ) የቤተ ክርስቲያን መሪ እንደ መሆንህ መጠን በቤተ ክርስቲያንህ ውስጥ ያለውን የአምልኮ ብቃት በማሻሻል፥ አምልኮው የሚፈጸመው ከልማድ ሳይሆን፥ ከልብ እንዲሆን ምን ማድረግ ትችላለህ? |

2. በመጽሐፍ ቅዱስ በአጠቃላይ የምንመለከተው አንድ መንፈሳዊ መመሪያ አለ። መታዘዝ ከእግዚአብሔር ዘንድ የሆነ በረከትን ሲያመጣ፥ አለመታዘዝ ደግሞ የእግዚአብሔርን ፍርድ ወይም የሥነ - ሥርዓት እርምጃን ያመጣል። የእግዚአብሔር የሆኑት እስራኤላውያን ለእግዚአብሔር በሚታዘዙ ጊዜ ይባረኩና ሰላምን ያገኙ ነበር። እንደዚሁ እግዚአብሔርን ስንታዘዝ እግዚአብሔር ዛሬም እኛን ይባርከናል፤ ነገር ግን በተመሳሳይ መንገድ፥ ለእግዚአብሔር በማንታዘዝበት ጊዜ በአንድ መንገድ የእግዚአብሔርን ፍርድና ቅጣት እንቀበላለን።

| |
|---|
| 15ኛ ጥያቄ፥ ሀ) ለእግዚአብሔር በታዘዝህ ጊዜ እግዚአብሔር እንዴት እንዳከበረህና እንደባረከህ ምሳሌዎችን ስጥ። ለ) ለእግዚአብሔር ባልታዘዝክ ጊዜ እግዚአብሔር እንዴት እንደ ቀጣህ ምሳሌዎችን ስጥ። |

3. የመጽሐፈ ዜና መዋዕል ጸሐፊ በእግዚአብሔር ፊት የእውነተኛ ንስሐ ባሕርይ ምን እንደሚመስል ሊያስተምረን ፈልጎ ነበር። እግዚአብሔር የሚቀጣና ያለአድሎ የሚፈርድ አምላክ ቢሆንም፥ የምሕረትና የፍቅር አምላክም ነው። በእግዚአብሔር ፊት ባለመታዘዝ ስንኖር፥ ፍርዱንና ቁጣውን እንቀበላለን። እግዚአብሔር ግን ይቅር ሊለንና ለሕዝቡ ምሕረትን ሊያሳይ ሁልጊዜ ፈቃደኛ ነው። የእግዚአብሔር ሕዝብ በእውነት ንስሐ ሲገቡና ኃጢአት ከሞላበት ሕይወት ተመልሰው እግዚአብሔር በሰጣቸው የመታዘዝ መንገድ ሲኖሩ፥ እግዚአብሔር ይቅር ይላቸውና ከእርሱ ጋር ያላቸውን ኅብረት ያድስላቸዋል፤ ነገር ግን ንስሐ እናዝናለን ከማለትና ይቅርታን የመጠየቅ ዝንባሌ ከማሳየት የላቀ ነው። ንስሐ አቅጣጫን መለወጥ፥ የኃጢአትን መንገድ መካድ እንጂ ለኃጢአት ተግባር ይቅርታን መጠየቅ ብቻ አይደለም።

| |
|---|
| 16ኛ ጥያቄ፥ ሀ) እውነተኛና ሐሰተኛ ንስሐን አወዳድር። የሚለያዩት እንዴት ነው? ለ) እውነተኛ ንስሐን የሚመለከቱ ምሳሌዎችን ጥቀስ። ሐ) የሐሰተኛ ንስሐን ምሳሌዎች ጥቀስ። መ) በሕይወትህ ያሉ አሁን ንስሐ ልትገባባቸው የሚያስፈልጉ ነገሮች ምንድን ናቸው? የእግዚአብሔርን በረከት ለመቀበል አሁኑኑ አድርገው። |

## 2ኛ ቀን:- 1ኛ ዜና 1-21

በመጽሐፈ ዜና መዋዕል የሚገኙ አብዛኞዎቹ ታሪኮች ከመጽሐፈ ሳሙኤልና ከነገሥት ታሪክ የተደገሙ ስለሆኑ፥ ለሚቀጥሉት ሦስት ቀናት 1ኛና 2ኛ ዜና መዋዕልን በሙሉ በማንበብ ጥያቄዎችን ትመልሳለህ። እነዚህን ምዕራፎች በሚመለከት የሚሰጥ መግለጫ አይኖርም።

| |
|---|
| 17ኛ ጥያቄ፥ ሀ) ከእነዚህ ምዕራፎች ስለ እግዚአብሔር የምንማራቸውን ነገሮች ዘርዝር። ለ) በእነዚህ ምዕራፎች እንደሚታየው፥ እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኙ የተግባር ሰዎች ስለመሆን፥ ከዳዊት ሕይወት ምን መማር እንችላለን? ሐ) ከእነዚህ ጥቅሶች ስለ አምልኮ ልንማራቸው የምንችል አንዳንድ ነገሮች ምንድን ናቸው? |

## 3ኛ ቀን:- 1ኛ ዜና 22 - 2ኛ ዜና 9

18ኛ ጥያቄ፥ ሀ) ከሰሎሞን ሕይወት እግዚአብሔርን ስለማገልገል የምንማራቸውን ነገሮች ዘርዝር። ለ) ከእነዚህ ምዕራፎች ስለ አምልኮ ልንማራቸው የምንችል አንዳንድ ነገሮች ምንድን ናቸው? ሐ) በእነዚህ ምዕራፎች ውስጥ ሕይወትህን የነኩትን መንፈሳዊ ትምህርቶችን ዘርዝር።

## 4ኛ ቀን:- 2ኛ ዜና 10-36

19ኛ ጥያቄ፥ ሀ) ከእነዚህ ምዕራፎች ስለ እግዚአብሔር ልንማራቸው የምንችል ነገሮችን ዘርዝር ለ) ለመንፈሳዊ መሪነት መልካም ምሳሌ የሚሆኑ የነገሥታትን ስም ዘርዝር። ከአመራራቸው የምንማረው ነገር ምንድን ነው? ሐ) ከእነዚህ ምዕራፎች ስለ አምልኮ የምንማረው ነገር ምንድን ነው? መ) ከእነዚህ ጥቅሶች ስለ ንስሐ ልንማራቸው የምንችል አንዳንድ ነገሮችን ጥቀስ።

## 5ኛ ቀን:-

የዚህን ሳምንት ትምህርት ከልስና ለሳምንታዊው ስብሰባ ዝግጅት ይረዱህ ዘንድ የውይይት ጥያቄዎችን ተመልከት።

### ሳምንታዊ ስብሰባ

1. ሳምንታዊ የአምልኮ ጊዜ
2. ጸሎት
3. የትምህርቱ ክለሳ
4. ውይይት

   1. ሀ) የፖለቲካ ታላቅነት አስፈላጊነቱ ከመንፈሳዊ ታላቅነት ያነሰ መሆኑን መጽሐፈ ዜና መዋዕል የሚያስተምረን እንዴት ነው? ለ) ይህ እውነት የሆነው ለምንድን ነው? ሐ) ብዙ ክርስቲያኖች ከመንፈሳዊ ብስለት ይልቅ በፖለቲካ ወይም በሌላ ሥጋዊ ነገር በሌሎች ሰዎች ዘንድ ታዋቂነትን ለማግኘት የሚፈልጉት ለምንድን ነው? መ) ይህ ነገር ቤተ ክርስቲያን ከሚገባ በላይ ታላቅ ለመሆን ወይም በልማት ለመታወቅ ትኩረት መስጠት እንደሌለባት ሊያስተምረን የሚገባው እንዴት ነው?

2. ሀ) የእግዚአብሔር ልጆች ዓለምን መምሰል እንደሌለባቸው ዜና መዋዕል እንዴት እንደሚያስተምር ምሳሌዎችን ስጥ። ለ) የእግዚአብሔር ሕዝብ ዓለምን መምሰል እንደማይገባቸው የእግዚአብሔርን ሕዝብ እውነተኛ እምነት የሚያጠፉ የሐሰት ትምህርቶች እንዲገቡ መፍቀድ እንደሌለባቸው፥ ሕዝቡን ማስታወስ የሚያስፈልገው ለምንድን ነው? ሐ) የሐሰት ትምህርት ከዚህ ቀደም ቤተ ክርስቲያንህን እንዴት ጎድቷት እንደነበር ምሳሌዎችን ጥቀስ። መ) የሐሰት ትምህርቶችን ለመከላከል የቤተ ክርስቲያንህ መሪዎች ምን እያደረጉ ናቸው? ሠ) የሐሰት ትምህርቶችን በተሻለ ሁኔታ ለመከላከል ምን ማድረግ ይችላሉ? የሐሰት ትምህርቶችን ለመከላከል ታሪክን በተሻለ ሁኔታ መረዳት ምን ይጠቅማል?

3. ሀ) ዳዊት ለቃል ኪዳኑ ታቦትና ለቤተ መቅደሱ ባደረገው ነገር ለእግዚአብሔር ያለውን ፍቅር እንዴት ገለጠ? ለ) ለእግዚአብሔር ያለንን ፍቅር ዛሬም ተመሳሳይ በሆኑ መንገዶች የምንገልጠው እንዴት ነው? ሐ) በብሉይ ኪዳን ዘመን እግዚአብሔር ክብሩን የሚያኖረው በየት ነበር? መ) ዛሬ የእግዚአብሔር ምድራዊ ማደሪያ የት ነው? (1ኛ ቆሮ. 6፡19 ተመልከት) ሠ) ዳዊት በብሉይ ኪዳን ዘመን እግዚአብሔርን ባከበረበት ተመሳሳይ መንገድ ዛሬም መሪዎች እግዚአብሔርን ሊያከብሩት የሚችሉባቸውን መንገዶች ዘርዝር።

4. ሀ) በመጽሐፈ ዜና መዋዕል እንዳየነው፥ ንጹሕ አምልኮ በብሉይ ኪዳን የተበላሸው እንዴት ነበር? ለ) አምልኮ ለማደስ የሞከሩ ነገሥታትን ዘርዝር። ሐ) ዛሬ ንጹሕ አምልኮ ሊበላሽ የሚችለው እንዴት ነው? መ) ንጹሕ አምልኮን ጠብቀው ለማቆየት መሪዎች ምን ማድረግ አለባቸው?

5. ሀ) መጽሐፈ ዜና መዋዕል በመታዘዝና በበረከት፥ ባለመታዘዝና በችግሮች መካከል ያለውን ግንኙነት እንዴት ያሳየናል? ምሳሌዎችን ጥቀስ። ለ) ይህ ግንኙነት (መመሪያ) ዛሬ በቤተ ክርስቲያን የሚታየው እንዴት ነው? ምሳሌዎችን ስጥ። ሐ) የሕዝቡን ሃይማኖታዊ ሕይወት ለመወሰን በዜና መዋዕል ውስጥ

ነገሥታት ምን ድርሻ እንዳላቸው ተጠቅሷል? መ) በቤተ ክርስቲያን አባላት ሃይማኖታዊ ፍቅር ላይ የቤተ ክርቲያን መሪዎች ተጽዕኖ የሚያሳድሩት እንዴት ነው?

6. ሀ) ስለ እውነተኛ አምልኮ በዜና መዋዕል የተጠቀሱ እውነቶች በእግዚአብሔር ዓይን እውነተኛ አምልኮ ምን እንደሆነ ለመረዳት እንዴት ይጠቅሙናል? ለ) በክርስቲያኖች ላይ አንዳንድ ጊዜ ችግር የሚፈጥሩት የትኞቹ እውነቶች ናቸው? ለምን? ሐ) የቤተ ክርስቲያን መሪ እንደመሆንህ መጠን፥ በቤተ ክርስቲያንህ ውስጥ ያሉትን ሰዎች የአምልኮ ብቃት በማሻሻል አምልኮአቸው በልማድ ሳይሆን ከልብ እንዲመነጭ ለማድረግ እንዴት ልትረዳቸው ትችላለህ?

5. ጸሎት

# ትምህርት 18

## 1ኛ ቀን:- የመጽሐፈ ዕዝራ መግቢያ

ብዙ ጊዜ ከመገንባት ይልቅ የሚቀለው ማፍረሱ ነው። የሐሰት ትምህርቶች በጥቂት ሳምንታት ወይም በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ወደ ቤተ ክርስቲያን ሊገቡና የብዙ ሰዎችን ሕይወት በቀላሉ ሊያጠፉ ይችላሉ፤ ዳሩ ግን አንዲት ቤተ ክርስቲያን በሐሰት ትምህርት ወይም በመለያየት ከፈረሰች በኋላ እንደገና እርስዋን መገንባት ብዙ ዓመታትንና እጅግ አስቸጋሪ የሆኑ ሥራዎችን ይጠይቃል።

| |
|---|
| 1ኛ ጥያቄ፥ ሀ) ቤተ ክርስቲያን ወይም የክርስቲያኖች ሕይወት ሊጠፋ የሚችልባቸውን መንገዶች ዘርዝር። ለ) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የፈረሰውን ነገር የሚገነቡባቸውን መንገዶች ዘርዝር። ሐ) በዚህ መንገድ ቤተ ክርስቲያንህ የፈረሰችበትና እንደገና የተሠራችበት ሁኔታ ካለ ምሳሌዎችን ዘርዝር። |

መጽሐፈ ዕዝራና ነህምያ የፈረሰው ነገር እንዴት እንደተገነባ የሚናገሩ ናቸው። ካለፈው ሳምንት ትምህርት እንደምታስታውሰው፥ እግዚአብሔር በእስራኤል ሕዝብ ዓመፅና ኃጢአት ምክንያት፥ ባቢሎናውያን የኢየሩሳሌምን ከተማና የክብር ደመናው እንዲቀመጥበት ያዘዘውን ቤተ መቅደስ እንዲያጠፉ መፍቀዱን ተመልክተናል። አብዛኞዎቹ የይሁዳ ሰዎች በኃጢአታቸው ምክንያት በምርኮ ተወሰዱ። በመጽሐፈ ዕዝራና ነህምያ ግን የእግዚአብሔር ሕዝብ እንዴት ተመልሰው ለመቋቋምና ቤተ መቅደሱን እንደገና መሥራት እንደጀመሩ እናያለን። የአይሁድ ሕዝብ ቅሬታዎች ከምርኮ ወደ ይሁዳ ተመለሱ። ቤተ መቅደሱ፥ በመጨረሻም የኢየሩሳሌም ቅጥሮች ተሠሩ። ከሁሉ በላይ እጅግ አስፈላጊ የሆነው ግን የእግዚአብሔርን ሕዝብ መንፈሳዊ ሕይወት መሥራት ነበር። ይህም ቤተ መቅደሱንና ቅጥሮቹን ከመሥራት እጅግ የከበደና ረጅም ጊዜ የወሰደ ነበር።

እስካሁን ድረስ የተመለከትናቸው የታሪክ መጻሕፍት፥ አይሁድ ወደ ምርኮ ከመሄዳቸው በፊት በነበራቸው ታሪክ ላይ የሚያተኩሩ ነበሩ። እነዚህም ከመጽሐፈ ኢያሱ እስከ 2ኛ ዜና መዋዕል ያሉት ናቸው። አይሁድ ከምድራቸው ተግዘው ወደ ምርኮ ከሄዱ በኋላ ስላለው ታሪክ የሚናገሩ ሦስት መጻሕፍት አሉ። እነዚህ ሦስት የመጨረሻ መጻሕፍት

ዕዝራ፥ ነህምያና አስቴር ናቸው። በዚህ ሳምንት ከምርኮ በኋላ ስለነበረው ታሪክ ከሚናገሩት መጻሕፍት የመጀመሪያ የሆነውን መጽሐፈ ዕዝራን እንመለከታለን።

2ኛ ጥያቄ፥ ስለ መጽሐፈ ዕዝራ ከመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት አንብብ። ከዚያም በዚህ ስፍራ ስለ መጽሐፈ ዕዝራ የተጠቀሱ ጠቃሚ እውነቶችን ዘርዝር።

## መጽሐፈ ዕዝራና ነህምያ

ልክ እንደ መጽሐፈ ሳሙኤል፥ ነገሥትና ዜና መዋዕል መጽሐፈ ዕዝራና ነህምያም በዕብራይስጡ ብሉይ ኪዳን አንድ መጽሐፍ ነበሩ። ዕዝራና ነህምያ በጊዜያቸው የተፈጸመውን ድርጊት እየተከታተሉ ራሳቸው የመዘገቡት ቢመስልም፥ ብዙ ምሁራን የሚስማሙት ጽሑፎቹን የሰበሰባቸውና ወደ አንድ መጽሐፍ በማጠቃለል ያቃናቸው ሌላ ሰው እንደሆነ ነው።

በዕብራይስጡ መጽሐፍ ቅዱስ በኋላ ወደ ግሪክ ቋንቋ ሲተረጎም፥ ተርጓሚዎቹ አንድ የነበረውን መጽሐፍ ለሁለት ከፈሉት። በግሪኩ መጽሐፍ ቅዱስ እነዚህ ሁለት መጻሕፍት 1ኛና 2ኛ ዕዝራ በመባል ይታወቃሉ። በኋላ የእነዚህ መጻሕፍት ርዕስ የመጀመሪያው ዕዝራ፥ ሁለተኛው ደግሞ ነህምያ ተብሎ ተሰየመ። እነዚህን ስያሜዎች ያገኙት በመጻሕፍቱ ውስጥ ባሉት ዋና ገጸ ባሕርያት በዕዝራና በነህምያ ነው።

## የመጽሐፈ ዕዝራና ነህምያ ጸሐፊዎች

የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁራን መጽሐፈ ዕዝራና ነህምያ በማን እንደተጻፉና እንዴት እንደተጻፉ ያላቸው አመለካከት የተለያየ ነው። የአብዛኛዎቹ አስተሳሰብ ዕዝራና ነህምያን የጻፈው ዜና መዋዕልን የጻፈው ሰው ነው የሚል ነው። ይህንንም ያሉበት ምክንያት የመጽሐፈ ዜና መዋዕል አጨራረስና የመጽሐፈ ዕዝራ አጀማመር ተመሳሳይ በመሆኑ ነው። በተጨማሪ በአጻጻፍ ስልቱም ተመሳሳይነት እናገኛለን።

ሌሎች ምሁራን ደግሞ መጻሕፍቱ ብዙ ተመሳሳይነት ቢኖራቸውም፥ የተጻፉት ግን በተለያዩ ጸሐፊዎች ለመሆኑ የሚያሳምኑ በቂ ልዩነቶች እናገኛለን ይላሉ።

ምሁራን መጽሐፈ ዕዝራንና ነህምያን ያቀናበረው ሰው የተጠቀመባቸው ሦስት የተለያዩ ምንጮች አሉ ይላሉ። በመጀመሪያ፥

ዕዝራ በእርሱ ዘመን ስለተፈጸሙት ክስተቶች ዘግቧል። ሁለተኛ፥ ነህምያ የኢየሩሳሌምን ቅጥሮች እንዴት እንደሠራ ዘግቧል። ሦስተኛ ደግሞ፥ በሼሺባዛር (ዘሩባቤል) መሪነት አይሁዶች በመጀመሪያ እንዴት ወደ ኢየሩሳሌም እንደተመለሱ የሚናገር የተለየ ዘገባ ነበር። መጽሐፈ ዕዝራና ነህምያን በአንድ ላይ እንዲሆኑ ያደረገው ሰው ከሦስት የታሪክ ምንጮች በማሰባሰብ በአንድ መጽሐፍ እንዲጠቃለል አድርጓል።

ጸሐፊው ዕዝራ በእርሱ ስም የተሰየመውን የመጀመሪያ መጽሐፍ ጽፎ ሊሆን ይችላል። በፋርስ መንግሥት ውስጥ ሥልጣን የነበረው ሰው ስለነበር፥ አይሁድ ወደ ይሁዳ እንዲመለሱ የተፈቀደበትን ማዘዣ ቅጂና ሌሎች የቤተ መንግሥት መዛግብት ቅጂዎች ኖረውት ሊሆን ይችላል። ከዚህም የተነሣ አይሁድ እንዴት ወደ ምድራቸው እንደተመለሱና ዕዝራ ከስንት ዓመታት በኋላ በምድሪቱ መንፈሳዊ መነቃቃትን እንደመራ አጭር መግለጫ ጽፎ ሊሆን ይችላል። መጽሐፈ ነህምያ የተጻፈው በነህምያ ሊሆን ይችላል። መጻሕፍቱ ባላቸው ተመሳሳይነት ምክንያት፥ የመጨረሻው ሰው መጠነኛ ለውጦችን አድርጎ ወደ አንድ መጽሐፍ አዋሕዶአቸው ሊሆን ይችላል። መጽሐፈ ዕዝራ ከሌዊ ነገድ በሆነ፥ ከምርኮ በኋላ በእስራኤላውያን ታሪክ ውስጥ ታላቅ ሚና በተጫወተና ትልቅ ስፍራ በነበረው ዕዝራ በተባለ ጸሐፊ ስም ተሰይሟል። ዕዝራ የተወለደው በምርኮ ምድር ነበር። ያደገውም በባቢሎን ነበር። ለዕዝራ የእግዚአብሔርን ሕግ ስላስተማሩት፥ ወላጆቹ እግዚአብሔርን የሚፈሩ ሰዎች ሳይሆኑ አይቀሩም። ዕዝራ በባቢሎን ምድር እስራኤላውያንንና የብሉይ ኪዳን ሕግን የሚያውቅ ዝነኛ ሰው እየሆነ እንደመጣ ይመስላል። አንዳንድ ምሁራን ዕዝራ በፋርስ መንግሥት ውስጥ የአይሁድ ጉዳይ ሚኒስትር ሆኖ እንደተሾመ ይገምታሉ። የፋርስ ንጉሥ ከነበረው ከአርጤክስስ ጋር ግንኙነት የነበረውም ለዚህ ነበር። በ538 ዓ.ዓ. ሕዝቡ በዘሩባቤል መሪነት ወደ ኢየሩሳሌም ሲመለሱ ዕዝራ ያልተመለሰበትን ምክንያት አናውቅም። ምናልባት በጣም ወጣት ስለነበረ ይሆናል። በ458 ዓ.ዓ. ግን ዕዝራ ወደ ኢየሩሳሌም ለመመለስ ከፋርስ ንጉሥ ፈቃድ አገኘ። ንጉሡ ከቤተ መንግሥቱ ገንዘብ እንዲጠቀም ለዕዝራ ፈቃድ ሰጠው። ዕዝራ አንዳንድ ሌዋውያን ከእርሱ ጋር እንዲመለሱ በማሳመን፥ በቤተ መቅደስ ውስጥ የሚደረገውን አምልኮ በመምራት ይረዱት ዘንድ አደረገ።

ዕዝራ ወደ እስራኤል ከተመለሰ በኋላ በእስራኤል ሕዝብ ታሪክ ውስጥ ታላቅ ሚናን ተጫወተ። በመጀመሪያ፥ እግዚአብሔር ዕዝራን

ሁለት መንፈሳዊ እንቅስቃሴዎችን በእግዚአብሔር ሕዝብ መካከል ለመምራት ተጠቀመበት (ዕዝራ 9-10፤ ነህ. 8-9)። ሁለተኛ፥ ዕዝራ የእግዚአብሔርን ሕግ በጥንቃቄ በማጥናት የታወቀ ሰው ነበር። ለዚህ ነው አይሁድ በሕግ ሥራና እውቀት «የተካኑ» የሃይማኖት መሪዎች አባት አድርገው የሚቆጥሩት። በአዲስ ኪዳን የተጠቀሱት የፈሪሳውያንና የጸሐፍት አባት ነበር። በዕዝራ ዘመን ከምርኮ የተመለሱ አብዛኛዎቹ አይሁዳውያን የራሳቸው የሆነውንና መጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈበትን የዕብራይስጥን ቋንቋ ስለማያውቁ ዕዝራና ሌሎች ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስን ለእነርሱ ለመተርጎም ተገድደው ነበር። አብዛኛዎቹ አይሁድ የባቢሎንና የፋርስ የንግድ ቋንቋ የነበረውን አራማይክን ብቻ ያውቁ ነበር።

---

3ኛ ጥያቄ፥ ሀ) በመጽሐፍ ቅዱስ እውቀት የመጠቁ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የሚያስፈልጉት ለምንድን ነው? ለ) በቤተ ክርስቲያንህ ውስጥ ያሉ፥ በዚህ ሁኔታ በሚገባ የሠለጠኑ ሰዎችን ስም ዘርዝር።

---

## መጽሐፈ ዕዝራና ነህምያ የተጻፉበት ጊዜ

የመጽሐፈ ዕዝራና ነህምያ ጸሐፊ ማን እንደሆነ ስለማናውቅ የተጻፉበትንም ጊዜ በእርግጠኝነት ማወቅ አንችልም። በመጽሐፉ ውስጥ የተገለጡ ድርጊቶች የተፈጸሙት ከ538-420 ዓ.ዓ. ባለው ዘመን ነበር፤ ስለዚህ መጽሐፉ በ400 ዓ.ዓ. አካባቢ ተጠናቅቆ ሳይጻፍ እንዳልቀረ መገመት ይቻላል።

## የመጽሐፈ ዕዝራና ነህምያ ሥረ - መሠረት

---

4ኛ ጥያቄ፥ 2ኛ ዜና 36፡15-19 አንብብ። ሀ) የኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስና ቅጥሮች ምን ሆኑ? ለ) የይሁዳ ሕዝብና ንጉሡስ ምን ሆኑ?

---

እንደምታስታውሰው በ2ኛ ነገሥትና በ2ኛ ዜና መጨረሻ ላይ የይሁዳ ሕዝብ በባቢሎናውያን መማረካቸውን ተመልክተናል። ቤተ መቅደሱና የኢየሩሳሌም ከተማም ተደምስሰዋል። ንጉሡም ተገድሎ ሕዝቡ ተማረኩ። ይህ ሁሉ የሆነው በ586 ዓ.ዓ. ነበር። ዋና ዋና የሆኑ ምርኮዎች የተፈጸሙት ሦስት ጊዜ ብቻ ቢሆንም፥ የባቢሎን ንጉሥ አይሁዳውያንን በምርኮ የወሰደው አራት ጊዜ ይመስላል። በመጀመሪያ፥ ዳንኤልና ሌሎች በምርኮ የተጋዙት በ605 ዓ.ዓ. ሲሆን፥ ሁለተኛ፥ ሕዝቅኤልና ንጉሡ ኢዮአኪን የተጋዙት በ597 ዓ.ዓ. ነበር። ሦስተኛ፥ በ586 ዓ.ዓ. ቤተ መቅደሱ የፈረሰበትና አብዛኛውን ሕዝብ የሚመለከት ዋናው ምርኮ

ተፈጸመ፤ ነገር ግን ሌላ አራተኛ መማረክም በ582 የነበረ ይመስላል (ኤር. 52:30)። የቀሩት አንዳንድ እስራኤላውያን ወደ ግብፅ ሸሽተው ሄዱ።

## አይሁድ በምርኮ ምድር

አይሁድ በ586 ዓ.ዓ. ከተማርኩበት ጊዜ ጀምሮ ሕዝቡ ከምርኮ እንዲመለሱ እስከተፈቀደበት እስከ 538 ዓ.ዓ. ድረስ ስለነበረው ሁኔታ የሚናገር የታሪክ መጽሐፍ የለም። በእነዚህ አምሳ ዓመታት ሁለት ዋና ዋና ነቢያት ነበሩ። አንዱ በባቢሎን መንግሥት ውስጥ የኖረውና የሠራው ዳንኤል ሲሆን፥ ሌላው በምርኮ ከነበሩት ወገኖቹ ጋር በባቢሎን የኖረው ሕዝቅኤል ነበር። በባቢሎን ስለኖሩባቸው ስለ እነዚህ 50 ዓመታት የምናውቀው ብዙ ነገር የለም። በባቢሎንና በመካከለኛው ምሥራቅ ተበትነው የኖሩ ይመስላሉ። ነገር ግን ይሁዳ ከተደመሰሰችበት ከ586 ዓ.ዓ. በኋላ ሕዝቡ በምርኮ ምድር ማረስና የንግድ ሥራ መሥራት ጀመሩ። በባቢሎናውያንም እጅ ክፉ ነገር አይደርስባቸውም ነበር።

## የባቢሎን መንግሥት

ከአሦር መንግሥት መውደቅ በኋላ፥ የባቢሎን መንግሥት ዓለምን መምራት ጀመረ። ኃይላቸው እጅግ ታላቅ የነበረ ቢሆንም፥ መንግሥታቸው የቆየው ግን በሜዶንና በፋርስ እስኪ.ተካ ድረስ ከ70 ዓመታት ጥቂት ለሚበልጥ ጊዜ ነበር። የባቢሎን መንግሥት ዋና ዋና መሪዎች የነበሩት ከዚህ እንደሚከተለው ተዘርዝረዋል:-

1. ናቦጳላሳር (626-605 ዓ.ዓ.) በባቢሎን መንግሥት የመጀመሪያ ንጉሥ የናቡከደነፆር አባት የነበረው ናቦጳላሳር ነበር። በአሦር ላይ የተደረገውን ዓመፅ በመምራት፥ የባቢሎንን ከተማ በ626 ዓ.ዓ. ያዘና ንጉሥ ሆነ። የአሦርን መንግሥት ሙሉ በሙሉ ለማጥፋት የቻለው በ609 ዓ.ዓ. ነበር።

2. ናቡከደነፆር (605-562 ዓ.ዓ.) በባቢሎን መንግሥት ውስጥ እጅግ ታላቅ የነበረው መሪ ናቡከደነፆር ነበር። አባቱ ከመሞቱ ከጥቂት ጊዜ በፊት፥ በከነዓን ላይ የተደረገውን ጦርነት በመምራት ይሁዳ ለባቢሎን መንግሥት እጅ እድትሰጥ አድርጎ ነበር። ናቡከደነፆር ራሱ እስከነበረበት ዘመን ድረስ ከነበሩ መንግሥታት ሁሉ የላቀ እጅግ ገናና መንግሥትን ያቋቋመው ታላቅ ጦረኛ ስለነበረ ብቻ ሳይሆን፥ ታላቅ ከተማና ሕንጻ ገንቢም ስለነበረ ነው። የባቢሎንን ከተማ

በጠላት እንደማትደፈር አድርጎ ገነባት። ከጥንቱ ዓለም ሰባት አስደናቂ ነገሮች አንዱ የተባለውን የአትክልት ስፍራ ለሚስቱ ሠራላት። እርሱ ከሞተ በኋላ የባቢሎን መንግሥት ኃይል እየተዳከመ ሄደ።

3. ከናቡከደነፆር በኋላ ሌሎች አራት ነገሥታት ይኖሩ ነበር። በመጀመሪያው የነገሠው አቬል ሙርዱክ ወይም ኢቭል ሜሮዳክ በመባል የሚታወቀው ሰው (562-560 ዓ.ዓ.) ሲሆን፥ ሁለተኛ ኔርግሊሳር (560-556 ዓ.ዓ.) ቀጥሎም ናቦኒዱስ (556-539 ዓ.ዓ.) ነገሠ። ይህ ሰው ከፖለቲካ አመራር ይልቅ ትኩረቱ በሃይማኖታዊ ጉዳይ ላይ ነበር። ብሔራዊ እምነት የነበረውን የማርዱክን አምልኮ የሚያስፈጽሙትን ቀሳውስት ባስቀየመ ጊዜ ሕዝቡ ከሥልጣን አወረዱትና ልጁን ብልጣሶርን በምትኩ አነገሡበት። ናቦኒዱስም ለመኖር በዐረቢያ ወዳለ ቤተ መንግሥት ሄደ። የፋርስ ወታደሮች በ539 መጥተው የባቢሎንን መንግሥት ባሸነፉበት ጊዜ በሥልጣን ላይ የነበረው መሪ ብልጣሶር ነበር። እግዚአብሔር መንግሥትህ ተደምስሳለች ብሎ በግድግዳ ላይ በጻፈና ዳንኤልም በዚያ ምሽት መንግሥቱ እንደምትከፈል በተናገረ ጊዜ በሥልጣን ላይ ያለው መሪ ብልጣሶር ነበር (ዳን. 5)።

## ሜዶንና ፋርስ

የሜዶንና የፋርስ ንጉሠ ነገሥት ግዛት ከ539 አንስቶ የግሪክ ንጉሥ በነበረው ታላቁ እስክንድር እስከ ተሸነፈበት እስከ 331 ዓ.ዓ. ድረስ በገናንነት ቆይቷል። የመጽሐፍ ቅድስ ታሪክ ግን የፋርስ መንግሥት ከ539 - 400 ዓ.ዓ. የቆየበትን ዘመን ብቻ የሚሸፍን ነው። የፋርስ ዘመነ መንግሥት በዓለም ውስጥ ካሉት መንግሥታት ይልቅ በዚያን ጊዜ ላቅ ያለና ገናና ገዢ እንደ ነበረ የዓለም ታሪክ ይመሰክራል። ከዚህ በመቀጠል በፋርስ ዘመነ መንግሥት እስከ 400 ዓመተ ዓለም ድረስ ይገዙ የነበሩት የንጉሦች ስም ተዘርዝረዋል።

1. ታላቁ ቂሮስ:- (559-530 ዓ.ዓ.):- ፋርስን እስከዚያ ዘመን ድረስ ከነበሩ መንግሥታት ሁሉ የላቀች እጅግ ታዋቂ ያደረጋት የቂሮስ ወታደራዊ አመራር ነበር። ቂሮስ በሜዶን ቁጥጥር ሥር የሚኖር ንጉሥ ነበር፤ ነገር ግን በሜዶን መንግሥት ላይ ዓመፀ። በኋላም የሜዶንን ሕዝብ ከእርሱ ጋር እንዲተባበሩ አስገደዳቸውና የሜዶንና

የፋርስ ንጉሠ ነገሥት ግዛት የተባለውን መንግሥት አቋቋመ። በጥምሩ ውስጥ ዋናውን ቦታ የያዘው የፋርስ መንግሥት ነበር፤ ስለዚህ ብዙ ጊዜ ይህ መንግሥት የፋርስ መንግሥት ይባል ነበር። የቂሮስ የንጉሠ ነገሥት ግዛት ከሜዶን ወደ ባቢሎን፥ እስከ ሕንድ ወሰን፥ እንዲያውም እስከ ግብፅ ድረስ ሰፋ።

አሦራውያንና ባቢሎናውያን ከተጠቀሙበት መንገድ በተለየ ሁኔታ፥ ቂሮስ በጎነትንና ርኅራኄን በማሳየት ሕዝቡ እንዲከተሉት አደረገ። እንደምታስታውሰው፥ አሦራውያንና ባቢሎናውያን ዋና የሆኑ ሰዎችን ማርኮ የመውሰድና በግዛታቸው ሁሉ ውስጥ የማሰራጨት ፖሊሲ (መመሪያ) ነበራቸው፤ ስለዚህ አሦር ከእስራኤል፥ ባቢሎን ደግሞ ከይሁዳ የወሰዷቸውን ሕዝቦች መንግሥታቸው ሁሉ ውስጥ አሰራጭተዋቸው ነበር። ፋርስ ግን በምርኮ ተይዘው የመጡትን እነዚህን ሰዎች ሁሉ ወደ አገራቸው እንዲመለሱና የአምልኮ ስፍራቸውንም እንደገና እንዲገነቡ ፈቀዱላቸው። ይህ ነገር የተፈቀደው ለአይሁድ ብቻ ባይሆንም፥ በመጽሐፈ ዕዝራ አይሁድ ይህንን ዕድል እንዴት እንደተጠቀሙበትና ወደ እስራኤል ተመልሰው ቤተ መቅደሳቸውን እንደሠሩ እንመለከታለን።

| 5ኛ ጥያቄ፥ ኢሳ. 45፡1፥ 13 አንብብ። ይህ ለኢሳያስ ትንቢት ፍጻሜ የሆነው እንዴት ነው? |
|---|

2. ካምቢሴስ (530-522 ዓ.ዓ.)። ይህ ሰው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አልተጠቀሰም፤ ነገር ግን አይሁድ በቂሮስ ዘመነ መንግሥት ሊሠሩ የጀመሩትን ቤተ መቅደስ እንዳይሠሩ በዚህ ሰው ዘመን መንግሥት ተከልክለው ነበር።

3. ቀዳማዊ ዳርዮስ (522-486 ዓ.ዓ.)፡- ይህ ንጉሥ ታላቁ ዳርዮስ በመባል የሚታወቅ ሲሆን፥ አይሁድ ቤተ መቅደሳቸውን እንዲሠሩ እንደገና የፈቀደ ሰው ነው (ዕዝ. 6፡1-12፤ ሐጌ 1፡1)። የቤተ መቅደሱ ሥራ በ516 ዓ.ዓ. ተጠናቀቀ። ዳርዮስ ታላላቅ ከሚባሉት የፋርስ የጦር መሪዎች አንዱ ሲሆን፥ የፋርስን መንግሥት እስከ ግሪክ ድረስ ያስፋፋ ሰው ነበር። በሥሩ ላሉ መንግሥታት ሁሉ አንድ ዓይነት ሕግ ለመስጠት ስለሞከረ «ሕግ ሰጪ» በመባል ይታወቃል።

4. ቀዳማዊ አርጤክስስ (486-425 ዓ.ዓ.)። ይህ ሰው በዕብራይስጡ መጽሐፍ ቅዱስ አህሳዊሮስ በመባል ይታወቃል። በአማርኛው መጽሐፍ ቅዱስ ግን አህሳዊሮስን ከአርጤክስስ በኋላ ከነገሠው

ከአርጤክስስ ጋር የሚምታታ የተሳሳተ አተረጓጎም አለ። አርጤክስስ ወይም አህሳዊሮስ ብለን የምንጠራው አስቴርን ያገባው ንጉሥ ነው። በተጨማሪ በዕዝራ 4፡6 ተጠቅሷል። (ማስታወሻ፡- በዕዝራ 4፡7 ላይ የተጠቀሰው ግን የሚቀጥለው ንጉሥ አርጤክስስ ነው)። በዓለም ታሪክ የአርጤክስስ ዝና ካሸነፉት ከግሪኮች ጋር ባደረገው ጦርነት የታወቀ ነው። በተጨማሪ ትልልቅ ከተሞችን በመሥራት ችሎታው ይታወቃል።

5. ቀዳማዊ አርጤክስስ (464-425 ዓ.ዓ.)፡- አርጤክስስ በመጽሐፍ ቅዱሳችን የተጠቀሰው የመጨረሻው የፋርስ ንጉሥ ነው። በመጀመሪያ ዕዝራ፥ ቀጥሎም ነህምያ ወደ ይሁዳ እንዲመለሱ የተፈቀደላቸው በእርሱ ዘመነ መንግሥት ነበር።

## የመጽሐፈ ዕዝራ፥ ነህምያና አስቴር ቅደም ተከተል

የመጽሐፈ ዕዝራ፥ ነህምያና አስቴር ታሪክ አፈጻጸም በጊዜ ቅደም ተከተል መሠረት አልቀረበም። በመቀጠል የእነዚህ መጻሕፍት ቅደም ተከተላቸውን እናያለን።

1. የመጀመሪያዎቹ አይሁዳውያን ወደ ኢየሩሳሌም መመለስ፡- ዕዝራ 1-6 (539-515 ዓ.ዓ.)

2. የአስቴር ታሪክ፡- አስቴር 1-10 (በ480 ዓ.ዓ.ገደማ)

3. የተሐድሶው መሪ ዕዝራና ሁለተኛው የአይሁድ ቡድን ከምርኮ መመለስ፡- ዕዝራ 7-10 (457 ዓ.ዓ.)

4. የአስተዳዳሪው ነህምያና የሦስተኛው የአይሁድ ቡድን ከምርኮ መመለስ፡- ነህ. 1-13 (444-430 ዓ.ዓ.)

(ማስታወሻ፡- አንዳንድ ምሁራን ዕዝራ 7፡8ን በሚመለከት የአጻጻፍ ስሕተት አለ ይላሉ፤ ይኸውም በአርጤክስስ በሰባተኛው ዓመት የሚለው ቃል በሠላሳ ሰባተኛው ዓመት መሆን አለበት ብለው ያስባሉ። ይህም የዕዝራን መመለስ ወደ 428 ዓ.ዓ. በማራዘም ከነህምያ በኋላ ያደርገዋል። ይህንን ለማመን ግን በቂ ምክንያት የለም።)

## የመጽሐፈ ዕዝራ አስተዋጽኦ

1. የመጀመሪያው የአይሁድ ቡድን ከምርኮ መመለስና የቤተ መቅደሱ እንደገና መሠራት (ዕዝራ 1-6)፡-

ሀ. የምርኮኞቹ መመለስ (1)

ለ. ከምርኮ የተመለሱት ሰዎች ዝርዝር (2)

ሐ. የመሠዊያው መሠራትና የቤተ መቅደሱ ሥራ መጀመር (3)

መ. በቤተ መቅደሱ ሥራ ላይ የደረሰው ተቃውሞና በአይሁድ ላይ የደረሱ ሌሎች ተቃውሞዎች (4፡1-23)

ሠ. የቤተ መቅደሱ ሥራ መፈጸም (4፡24-6፡22)።

2. ሁለተኛው የአይሁድ ቡድን በዕዝራ መሪነት ከምርኮ መመለሱና መንፈሳዊው ተሐድሶ (7-10)

ሀ. ለመመለስ የሚያስችል ፈቃድ (7)

ለ. የተመለሱት ሰዎች ስም ዝርዝር (8)

ሐ. ዕዝራ በኢየሩሳሌም የቀሰቀሰው ተሐድሶ (9-10)

## የመጽሐፈ ዕዝራ ዋና ዋና ዓላማዎች

መጽሐፈ ዕዝራ የተጻፈባቸው ሁለት ዐበይት ምክንያቶች አሉ፡-

1. አይሁድ ከምርኮ ተመልሰው እንደገና በይሁዳ መኖር እንዴት እንደ ጀመሩ ለመናገር ነው። በሁለት ክፍለ ጊዜያት የተከፈለ ሲሆን አንዱ በዘሩባቤል፥ ሌላው ደግሞ በዕዝራ መሪነት ከምርኮ ስለተመለሱት አይሁድ ይናገራል። ይህ ታሪክ ከ538-456 ዓ.ዓ. የተፈጸመው ነገር ባጭሩ የቀረበበት ነው።

2. የዕዝራ መልእክት የተጻፈው በይሁዳ ይኖሩ ለነበሩት አይሁዳዊያን ጭምር ሲሆን፥ እግዚአብሔር ሊሠራ የጀመረውን ነገር እንደተወና እንደረሳቸው ተሰምቶአቸው እጅግ ተስፋ ቆርጠው ስለነበር፥ እነርሱን ለማበረታታት ነበር። ጸሐፊው እግዚአብሔር በነቢያት በኩል የተናገረውን ትንቢት ለመፈጸም ታማኝ እንደሆነ ሊያሳያቸው ፈልጎ ነበር (ለምሳሌ፡- ኢሳ. 43፡1-7)። ይህም ትንቢት አንድ ቀን እግዚአብሔር ሕዝቡን ከምርኮ እንደሚመልስ የሚናገር ነበር። እግዚአብሔር እስካሁንም ድረስ በአይሁድ ታሪክ እየሠራ ነበር። የቤተ መቅደሱ ሥራ እግዚአብሔር በመካከላቸው እንደሚሠራ የሚያሳይ አንዱ ምልክት ነበር። ጸሐፊው የዚህን ዘመን ታሪክ

በመጠቀም፥ ሕዝቡ የእግዚአብሔርን በረከት ለመለማመድና የይሁዳ መንግሥትም ቀድሞ ወደነበረው ታላቅነት እንዲመጣ ከፈለጉ፥ የቃል ኪዳኑ ሕዝብ እንደመሆናቸው መጠን ለእግዚአብሔር በመታዘዝ መኖር እንደነበረባቸው ለማስጠንቀቅ ፈልጎአል። የንጽሕና ሕይወት መኖር አለባቸው።

6ኛ ጥያቄ፥ ሀ) በግል ሕይወታችን፥ በቤተ ክርስቲያናችንና በኅብረተሰባችን ውስጥ የምናገኘው በረከት ለእግዚአብሔር ቃል ከመታዘዛችን ጋር የሚያያዘው እንዴት ነው? ለ) ለእግዚአብሔር ለመታዘዝ በሕይወትህ ውስጥ ልትለውጣቸው ከሚገቡ ነገሮች አንዳንዶቹን ጥቀስ። ሐ) በተሻለ ሁኔታ ለእግዚአብሔር ለመታዘዝ በቤተ ክርስቲያንህ ውስጥ ልታደርጋቸው የሚገቡ አንዳንድ ነገሮችን ጥቀስ።

## 2ኛ ቀን፡- ዕዝራ 1-6

7ኛ ጥያቄ፥ ኤር. 25፡7-12፤ 29፡10፤ ኢሳ. 43፡1-7 አንብብ። ወደ ምርኮ ከመሄዳቸው በፊት፥ እግዚአብሔር ለይሁዳ ሕዝብ የሰጣቸውን ቃል ኪዳኖች ጥቀስ።

የክርስቲያን ሕይወት ተስፋ የተመሠረተው በእግዚአብሔር ላይ ባለ ጠንካራ እምነት ነው። ልንሞት በተቃረብንበት ሰዓት ወይም በከፍተኛ ስደት ውስጥ እንኳ ተስፋ ያለን፥ እግዚአብሔር ቃሉን እንደሚያከብርና የተስፋ ቃሉን እንደሚጠብቅ ስለምናምን ነው።

8ኛ ጥያቄ፥ ዛሬም ቢሆን አስቸጋሪ በሆኑ ሁኔታዎች ውስጥ ልንጨብጣቸው የምንችል አንዳንድ የተስፋ ቃሎችን ጥቀስ።

የይሁዳ ሕዝብ ተማርከው ከመሄዳቸው በፊት፥ ከ70 ዓመታት ምርኮ በኋላ እንዲመለሱ እግዚአብሔር ነግሮአቸው ነበር። ከምርኮ እንዲመለሱ ያደርግ ዘንድ የሚጠቀምበትን ንጉሥ ስም እንኳ በኢሳይያስ በኩል ነግሮአቸው ነበር። የዚህ ንጉሥ ስም ቂሮስ ነበር (ኢሳ. 45፡1)። አይሁድ ለ70 ዓመታት የእግዚአብሔርን የተስፋ ቃል ጠበቁ። ወዲያውኑ የፋርስ ንጉሥ የነበረው ቂሮስ ሜዶንን መውጋት ጀመረና የባቢሎንን ከተማ ወሰደ። አይሁዶች ቂሮስ የባቢሎንን ከተማ መማረኩን በተመለከቱ ጊዜ በመካከላቸው የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን እየተፈጸመ እንደሆነ በማሰብ እንዴት ደስ እንደተሰኙ መገመት ትችላለህ።

የክርስትና መሠረት በእግዚአብሔር የተስፋ ቃል ማመን ነው። በኢየሱስ ክርስቶስ ብናምን በተሰጠን የተስፋ ቃል መሰረት የዘላለም ሕይወት ይኖረናል። የማይገቡንን ነገሮች እንኳ ለመልካም እንደሚያደርግልን (ሮሜ 8:28) በሰጠን የተስፋ ቃል ላይ እንተማመናለን። እንዲሁም እግዚአብሔር ከሙታን እንደሚያስነሣንና ከእርሱም ጋር ለዘላለም በሕይወት እንደሚያኖረን በተሰጠን የቃል ኪዳን ተስፋ እናምናለን (1ኛ ቆሮ. 15)። የእነዚህን ተስፋዎች አንዳንድ ውጤቶች በምድር እንለማመዳለን፤ ነገር ግን እግዚአብሔር ከሰጠን የተስፋ ቃሎች አብዛኛዎቹን በሙላት የምንለማመዳቸው ወደ መንግሥተ ሰማያት ከደረስን በኋላ ነው። እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳን ለነበሩ አይሁድ የገባውን የተስፋ ቃል አስደናቂ በሆነ መንገድ ማክበሩ በማይዋሸውና ቃል ኪዳኑን ሁልጊዜ በሚፈጽመው አምላክ ላይ እምነታችንን እንድንጥል ያበረታታናል።

> 9ኛ ጥያቄ፥ ይህ እውነት ዛሬም ክርስቲያኖችን የሚያበረታታው እንዴት ነው?
> 10ኛ ጥያቄ፥ ዕዝራ 1-6 አንብብ። ሀ) ቂሮስ ያሟላው ትንቢት ምንድን ነው? ለ) እግዚአብሔር ፈቃዱን ለመፈጸም ቂሮስን የተጠቀመበት እንዴት ነው? ሐ) ወደ ይሁዳ የተመለሱት ሕዝብ ቁጥር በአጠቃላይ ስንት ነው? መ) ሌላስ የተመለሰ ነገር ምንድን ነው? (ዕዝራ 1:7)። ሠ) ሕዝቡ ወደ ኢየሩሳሌም እንደደረሱ በቅድሚያ የሠሩት ነገር ምን ነበር? ረ) የቤተ መቅደሱን ሥራ የተቃወመው ማን ነበር? ሰ) ቤተ መቅደሱ በመጨረሻ የተሠራው በማን ዘመነ መንግሥት ነበር?

በዕዝራ 1-6 የተፈጸሙ ድርጊቶች የተጀመሩት በ538 ዓ.ዓ. ነበር። ቂሮስ ባቢሎንን በወጋና በባቢሎን ተማርከው በግዞት የመጡ የተለያዩ ሕዝቦች ወደ የአገራቸው እንዲመለሱ በፈቀደ ጊዜ፥ ከእነዚህ ሕዝቦች አንደኛው ከይሁዳ የመጡ የአይሁድ ሕዝብ ነበሩ። በቅድሚያ ወደ አገራቸው የተመለሱት አይሁድ ግን በአጠቃላይ 50000 ያህል ብቻ ነበሩ፤ የቀሩት ግን በባቢሎን የነበራቸው ሕይወት ተመችቶአቸው ስለነበር በዚያ ቆዩ። በዚህ በመጽሐፈ ዕዝራ የመጀመሪያ ክፍል መጨረሻ ላይ የተጠቀሰው ድርጊት ከ20 ዓመታት በኋላ በ516 ዓ.ዓ. የተፈጸመው የቤተ መቅደሱ ሥራ ነበር።

እግዚአብሔር የአሕዛብ ንጉሥ በሆነው በቂሮስ ልብ ውስጥ በመሥራት፥ ከእርሱ ቀደም የነበሩትን የአሦርንና የባቢሎንን ነገሥታት መመሪያ እንዲቀይር ማድረጉ፥ ጸሐፊውን እንዳስደነቀው እንመለከታለን። እንዲያውም ጸሐፊው አይሁድ ወደ አገራቸው እንዲመለሱ የታዘዙትን ሕጋዊ ሰነድ ሁለት ጊዜ ጠቅሶታል። በመጀመሪያ፥ በምዕ. 1፡2-4 ሕጋዊ የሆነው የፈቃድ ትእዛዝ በዕብራይስጥ ቋንቋ ተተርጉሞ እንመለከተዋለን። ይህም ለአይሁድ የተደረገ የትርጉም ቅጂ ሳይሆን አይቀርም። ጸሐፊው የመንግሥቱ የመግባቢያ ቋንቋ በነበረው በአራማይክ ቋንቋ የቀረበውን ጽሑፍ በምዕ. 6፡3-5 እንደገና አቅርቦታል። ቂሮስ አይሁድ ወደ አገራቸው እንዲመለሱ መፍቀድ ብቻ ሳይሆን ባቢሎናውያን ከቤተ መቅደሳቸው የወሰዱባቸውን የአምልኮ ዕቃዎቻቸውንም መለሰላቸው።

ሕዝቡ ወደ ኢየሩሳሌም በሚመለስበት ጊዜ የመጀመሪያውን ቡድን የመራው ሰው የይሁዳ አለቃ የነበረው ሼሽባደር ነበር፤ ስለዚህ ሰው ማንነት ምሁራን የተለያዩ አሳቦች አሏቸው። በዚህ አንጻር ሁለት ዋና ዋና አመለካከቶች ይቀርባሉ፡- በመጀመሪያ፥ አንዳንዶች ሼሽባደር ሺናአሰር በመባል የሚታወቅ ወደ ግዞት ተወስደው ከነበሩት የኢዮአኪን ልጆች አንዱ ነበር ይላሉ (1ኛ ዜና 3፡18)። ይህ ሰው ሽማግሌ ቢሆንም፥ አይሁድ በሚመለሱበት ጊዜ ሕጋዊ የሆነና የታወቀ መሪ ነበር። ምናልባትም በሰማርያ ከሰማርያ ገዢ በታች ሆኖ ይሁዳን ያስተዳድር የነበረ ሰው ሳይሆን አይቀርም ይላሉ። የቤተ መቅደሱን ግንባታ ሥራ የጀመረ ቢሆንም፥ ስለ ሞተ ወይም ሥራውን ለመምራት እስከማይችል ድረስ ስለ ሸመገለ አመራሩን ዘሩባቤል ከእርሱ ተረከበ። ይህንን አመለካከት ከተቀበልን፥ ዘሩባቤል የሼሽባደር የወንድም ልጅ ነው ማለት ነው። ሕጋዊ የሆነውን የታወቀው መሪ ሼሽባደር ሲሆን፥ ዝነኛ የሆነና ከሕዝቡ ጋር ግንኙነት የነበረው መሪ ግን ዘሩባቤል ነው ይላሉ።

ሁለተኛ፥ ሌሎች ምሁራን ደግሞ ሼሽባደር የዘሩባቤል ሌላው ስም ነው ይላሉ። እነዚህ ሁለት ሰዎች ስለ አንድ ሰው የተነገሩ እንደሆኑ ያስባሉ። ሼሽባደር የዘሩባቤል ባቢሎናዊ ስሙ ነው ይላሉ። ሁለቱም ሰዎች አለቆች ወይም ሹማምንት ነበሩ (ዕዝራ 5፡14፤ ሐጌ 1፡1)፤ ሁለቱም የቤተ መቅደሱን መሠረት ጥለዋል (ዕዝራ 3፡2-8፤ 5፡16፤ ሐጌ 1፡14-15)። ሌሎችም የታሪክ መጻሕፍት ሁለቱ ስሞች የአንድ ሰው

ናቸው ይላሉ፤ ስለዚህ ሼሽባዳርና ዘሩባቤል የአንድ ሰው ሁለት ስሞች ሳይሆኑ አይቀሩም።

| |
|---|
| 11ኛ ጥያቄ፥ ከመጽሐፉ ጀርባ የሚገኘውን ካርታ ተመልከት። ምርኮኞቹ ወደ ይሁዳ በተመለሱበት ጊዜ የመረጡትን መንገድ ተመልከት። |

አይሁድ ከ4 ወራት ጉዞ በኋላ ወደ ኢየሩሳሌም ሲደርሱ፥ ለእግዚአብሔር መሥዋዕት የሚያቀርቡበት መሠዊያ መሥራት፥ ቅድሚያ የሰጡት ተግባር ነው። አይሁድ በምርኮ በነበሩባቸው 70 ዓመታት ለእግዚአብሔር መሥዋዕት ማቅረብ አልቻሉም ነበር። የዳስ በዓል በማክበርም እግዚአብሔርን አመለኩ።

ለ50 ዓመታት ያህል ቤተ መቅደሱ የተበላሸና ለአምልኮ አገልግሎት ያልዋለ ነበር (586-538 ዓ.ዓ.)፤ ስለዚህ ወደ ኢየሩሳሌም የተመለሱት ሕዝብ እግዚአብሔርን የሚያመልኩበትን ቤተ መቅደስ መሥራት ጀመሩ። ገና መሠረቱን እንደጣሉ ተቃውሞ ገጠማቸው። በሰሜን እስራኤል ይኖሩ የነበሩ አንዳንድ ሰዎች ወደ ኢየሩሳሌም በመምጣት የቤተ መቅደሱን ሥራ ለማገዝ ፈለጉ። የአሕዛብና የአይሁድ ቅይጥ እንጂ ሙሉ ለሙሉ አይሁድ ስላልነበሩ፥ የብሉይ ኪዳን ሕግም አሕዛብ ወደ ቤተ መቅደሱ እንዲገቡ ስለማይፈቅድ፥ ቤተ መቅደሱን እንዲሠሩና ከእነርሱ ጋር እንዲያመልኩ ለማድረግ አይሁድ ሳይፈቅዱ ቀሩ። የእግዚአብሔር አምልኮ ይበላሽና እንደገና የእግዚአብሔር ፍርድ ያጋጥመናል ብለው ፈሩ።

| |
|---|
| 12ኛ ጥያቄ፥ ሀ) የማያምኑ ሰዎች ለእግዚአብሔር ያለንን ንጹሕ አምልኮና የተቀደሰ አኗኗራችንን እንዲያበላሹ የምንፈቅድባቸውን መንገዶች ዘርዝር። ለ) ይህ ነገር በቤተ ክርስቲያንህ ሲፈጸም ያየኸው እንዴት ነው? የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የእግዚአብሔር አምልኮ ንጽሕና እንዲጠበቅና ሌሎችም በአኗኗራቸው ዓለምን እንዳይመስሉ ለማበረታታት ምን ማድረግ ይችላሉ? |

ሳምራውያን የቤተ መቅደሱን ሥራ ማገዝ እንደማይችሉ ሲነገራቸው፥ አይሁድ የቤተ መቅደሱን ሥራ እንዲያቆሙ እንዲያደርግ የፋርስን መንግሥት ጠየቁ። አይሁድ የቤተ መቅደሱን ሥራ እንደገና በ538 ዓ.ዓ ጀመሩ፤ ነገር ግን ሥራውን እንዲያቆሙ ስለተገደዱ እስከ

520 ዓ.ዓ. ድረስ እንደገና ሊጀምሩ አልቻሉም። ይኸውም ከ18 ዓመታት በኋላ ማለት ነው።

ዕዝራ 4 አይሁድ በሰማርያ ሕዝብ አማካይነት የደረሰባቸውን የተለያየ የቤተ መቅደስ ሥራ ማደናቀፊያ መንገድ የተገለጠበት ክፍል ነው። የተቃውሞው ዓይነት የተዘረዘረው በጊዜ ቅደም ተከተል መሠረት እንዳልሆነ መገንዘብ ያስፈልጋል። ቀጥሎ አይሁድ የደረሱባቸውን ሦስት የተለያዩ ዓይነት ተቃውሞዎች እንመለከታለን።

አንደኛ፥ ቤተ መቅደሱን የመሥራት ተግባር እንደቆመና እስከ ዳርዮስ ዘመን ድረስ ሊቀጥል እንዳልቻለ እንመለከታለን (ዕዝራ 4፡5)።

ሁለተኛ፥ በኋላ የአስቴር ባል በነበረው በንጉሥ አርጤክስስ ዘመነ መንግሥት በአይሁድ ላይ ስለ ቀረበው ክስ እንመለከታለን። ይህም የሆነው ከ485-465 ዓ.ዓ. በነበረው ጊዜ ነው።

ሦስተኛ፥ በአርጤክስስ ዘመነ መንግሥት የኢየሩሳሌምን ቅጥር እንደገና በመሥራት ረገድ ስለ ደረሰው ተቃውሞ እንመለከታለን (ዕዝራ 4፡7-23)። አርጤክስስ የነገሠው በ464 ዓ.ዓ. ስለነበር፥ ይህ ክስ የቀረበው እርሱ በነገሠበት ዘመን አካባቢ ሳይሆን አይቀርም። በኋላ ዕዝራና ነህምያ ወደ ኢየሩሳሌም እንዲመለሱና የኢየሩሳሌም ቅጥሮችም እንዲሠሩ የፈቀደው እርሱ ነበር። ይህ ክፍል የሚናገረው ስለ ቤተ መቅደሱ ሥራ ስለ ከተማይቱ መሠራት ነው፤ ምክንያቱም በዚህ ጊዜ የቤተ መቅደሱ ሥራ ተጠናቅቆ ነበር።

የዕዝራ 5 ና 6 ታሪክ በ520 ዓ.ዓ. ወደ ተፈጸመው የዳርዮስ ዘመን ይመልሰናል። ሐጌና ዘካርያስ የተባሉት ነቢያት ሕዝቡ ቤተ መቅደሱን ይሠሩ ዘንድ እንዴት እንዳበረታቱ የሚናገር ነው። ቤተ መቅደሱን መሥራት በጀመሩበት ጊዜ የሰማርያው ገዢ አይሁድ ይህን ነገር ለማድረግ ፈቃድ አላቸው ወይ? ብሎ የሚጠይቅ ደብዳቤ ለፋርስ መንግሥት ጻፈ። ይህንንም ለማረጋገጥ በተደረገው ፍለጋ፥ አይሁድ ወደ አገራቸው እንዲመለሱና ቤተ መቅደሱን እንዲሠሩ የተፈቀደበት ሰነድ ቅጂ ተገኘ። አይሁድ ሥራቸውን ቀጠሉ። ቤተ መቅደሱን ሠርተው ለማጠናቀቅ አራት ዓመታት ፈጀባቸው። የቤተ መቅደሱም ሥራ በ516 ዓ.ዓ. ተጠናቀቀ። ኢየሱስ ከመወለዱ ጥቂት፥ ቀደም ብሎ የሄሮድስ ቤተ መቅደስ እስኪሠራ ድረስ ለአይሁድ ዋናው የአምልኮ ማዕከላቸው ይህ ቤተ መቅደስ ነበር።

13ኛ ጥያቄ፥ ሀ) የእግዚአብሔር ሰዎች ለእግዚአብሔር አንድ ነገር ለማድረግ በሚነሡበት ጊዜ ሁሉ፥ በአብዛኛው ተቃውሞ የሚኖረው ለምን ይመስልሃል? ለ) ይህንን ነገር በቤተ ክርስቲያንህ ያየኸው እንዴት ነው? ሐ) ዮሐ. 15፡18-21፤ 17፡11-16 አንብብ። ዓለምን እየመሰሉ ለማይኖሩ ክርስቲያኖች የተሰጠው ተስፋ ምንድን ነው? መ) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሕዝባቸው ለእግዚአብሔር የተቀደሰ ሕይወት ለመኖር የሚፈልግ ከሆነ ለተቃውሞ እንዴት ሊያዘጋጁት ይገባል?

## 3ኛ ቀን፡- ዕዝራ 7-10

ውጫዊ የሆነው የአምልኮ ስፍራ የሚደመሰስበት ጊዜ ቢኖርም እንኳ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የሚያጋጥማቸው ከዚህ የባሰ ከፍተኛ ችግር አለ። ይህም የእግዚአብሔር ሕዝብ መንፈሳዊ ሕይወት እንደገና መሠራት የሚያሻው ሆኖ ሲገኝ ነው። ተፈጥሮአዊ የሆነው ዝንባሌ የእግዚአብሔር ሕዝብ የመጀመሪያ ፍቅራቸውን በመተው ከእምነታቸው ፈቀቅ ማለታቸው ነው። የቤተ ክርስቲያን መሪዎችና አባላቱ በእግዚአብሔር ፊት በቅድስና የመመላለስ ፍላጎታቸው ቀስ በቀስ እየጠፋ ይሄዳል፥እንዲሁም ለማያምኑ ሰዎች ጠንካራ ምስክሮች መሆናቸው ይቀራል። አምልኮ ልማዳዊ ብቻ ሊሆን ይችላል፥ በኋላም በእግዚአብሔር ላይ ያላቸውን እምነት ይተዋሉ።

14ኛ ጥያቄ፥ ሀ) ይህን ዝንባሌ በቤተ ክርስቲያንህ ውስጥ እንዴት ነው ያየኸው? ለ) መሪ እንደመሆንህ መጠን በቤተ ክርስቲያንህ ውስጥ ያሉ ሰዎች ፍቅራቸውን እንዳይተዉ፥ ንጽሕናቸውን እንዳያጓድሉና እግዚአብሔርን የማምለክ ፍላጎታቸው እንዳይቀንስ ልታደርጋቸው የምትችልባቸውን ነገሮች ዘርዝር።

የመጽሐፈ ዕዝራ የመጨረሻው ክፍል አጋማሽ የሚነግረን፥ የሕዝባችንን መንፈሳዊ ሕይወት ንጹሕና ለእግዚአብሔር ታዛዥ እንዲሆን አድርገን እንዴት እንደምናድሰው ነው። የካህኑ ዕዝራ ታሪክ ኃጢአትን የሚጠላና ሕዝቡ በእግዚአብሔር ፊት በቅድስና እንዲኖሩ የሚፈልግ መሪ ጥሩ ምሳሌ ነው።

15ኛ ጥያቄ፥ ዕዝራ 7-10 አንብብ። ሀ) ወደ ይሁዳ እንዲመለስ ለዕዝራ የፈቀደለት ንጉሥ የትኛው ነው? ለ) ዕዝራ በምዕ. 7፡6፥10 የተገለጸው እንዴት ነው? ዛሬም የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ይከተሉት

ዘንድ ይህ መልካም ምሳሌ የሚሆነው እንዴት ነው? ሐ) ከዕዝራ ጋር የተመለሱት ሰዎች ብዛት ምን ያህል ነበር? መ) ዕዝራ ሕዝቡ ከአሕዛብ ጋር በጋብቻ የመጣመርን ኃጢአት እንደሠሩ ሲሰማ ምን አደረገ? ሠ) በእግዚአብሔር ፊት ሕዝቡን ወደ ተቀደሰ አካሄድ ለመመለስ ዕዝራ ምን አደረገ? ረ) በእነዚህ ምዕራፎች «የእግዚአብሔር ሕግ» የሚለው ቃል የተጠቀሰው ስንት ጊዜ ነው?

በመጽሐፈ ዕዝራ ምዕራፍ 6 እና 7 በምናገኛቸው ክስተቶች መካከል የብዙ ዓመታት ልዩነት አለ። የመጽሐፈ አስቴር ጠቅላላ ታሪክ የተፈጸመው በዚህ ጊዜ ነው። የምዕ. 6 ታሪክ የተፈጸመው በ516 ዓ.ዓ. ሲሆን፥ ከዕዝራ 7-10 ያለው ታሪክ የተፈጸመው ደግሞ በ458 ዓ.ዓ. በአንድ ዓመት ውስጥ ነበር። ይህም ማለት በምዕ. 6 ና 7 መካከል 57 ዓመታት አሉ ማለት ነው።

ዕዝራ የዘር ግንዱ ከአሮን ወገን የሆነ ካህን ነበር። ወላጆቹ ከዘሩባቤል ጋር ከምርኮ ስላልተመለሱ፥ የተወለደው በምርኮ ምድር ነበር፤ ነገር ግን ዕዝራ ለእግዚአብሔርና ለቃሉ ከፍተኛ ፍቅርን አጎለበተ። ዕዝራ በአይሁድ ዘንድ የታወቀና በፋርስ መንግሥት በምርኮ ላይ ሳሉ እንኳ ሳይወክላቸው አልቀረም። ዕዝራ የእግዚአብሔርን ቃል ያውቅ ነበር። ያለማቋረጥ ያጠናው፥ ትምህርቱን ሁሉ ይከተልና በውስጡ ያለውን እውነት በሙሉ ለሕዝቡ ለማስተማር በሚገባ ይተጋ ነበር (ዕዝራ 7፡6፥ 10)። የመጽሐፍ ቅዱስ አስተማሪ ሥራ ምን እንደሆነ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በሚገባ ከሚገልጹት ክፍሎች አንዱ ይህ ነው። የመጽሐፍ ቅዱስ አስተማሪ እግዚአብሔርን ማወቅ አለበት። እግዚአብሔርን ማወቅ ማለት ቃሉን ማወቅ ማለት ነው። የእግዚአብሔርን ቃል ለማወቅ የብዙ ዓመታት ጥናት ይጠይቃል። አስተማሪ የተጻፈውን የእግዚአብሔርን ቃል ማወቅ ብቻ ሳይሆን፥ በውስጡ ያሉትን እውነቶች ለሌሎች ማስተማርና በመታዘዝም መመላለስ ይገባዋል።

16ኛ ጥያቄ፥ ሀ) ብዙ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የእግዚአብሔርን ቃል ለማጥናት በጣም ጥቂት ጊዜ ብቻ የሚሰጡት ለምንድን ነው? ለ) ስለ እግዚአብሔር ቃል እውቀታቸውና ለቃሉ ባላቸው መታዘዝ የታወቁ የቤተ ክርስቲያንህ ሰዎችን ስም ዘርዝር። ሐ) እነዚህ ሰዎች ሌሎችን ለማስተማር እግዚአብሔር የተጠቀመባቸው እንዴት ነው?

ዕዝራ ወደ ይሁዳ ለመመለስ ስለፈለገ ንጉሥ አርጤክስስን ፈቃድ ጠየቀው። እግዚአብሔርም የአርጤክስስን ልብ ከፈተና ለዕዝራ ፈቃድ ብቻ ሳይሆን ገንዘብም እንዲሰጠው አደረገ።

ዕዝራም ወደ ይሁዳ ለመመለስ የሚፈልጉ አይሁዳውያንን ሰበሰበ። ከእነዚህ መካከል ግን የእግዚአብሔርን ቃል ለማወቅና ሌሎችን ለማስተማር፥ ለእግዚአብሔር የሚደረገውን አምልኮ መምራት የሚጠበቅባቸው ሌዋውያን ጥቂት መሆናቸውን አየ። ስለዚህ አብረውት እንዲሄዱ በተለይ ሌዋውያንን ጠየቃቸው። በመጨረሻም 1800 ወንዶችና ቤተሰቦቻቸውም ከዕዝራ ጋር ከምርኮ ተመለሱ። ይህም ከምርኮ፤ የተመለሰው ሁለተኛው ቡድን ነበር። ጉዞው ከ1400 ኪሎ ሜትር በላይ ስለነበር፥ ዕዝራና ሕዝቡ 3 ወር ተኩል ፈጀባቸው።

ዕዝራ ወደ ይሁዳ በደረሰ ጊዜ በቀጥታ ከሕዝቡ ኃጢአት ጋር ተፋጠጠ። ሕዝቡ በይሁዳ ለ80 ዓመታት የቆዩ ሲሆን፥ ለእግዚአብሔር የነበራቸው ፍቅር እየቀዘቀዘ ሄዶ ነበር። ኃጢአትም ወደ አምልኮአቸው ገብቷል። በትንቢተ ሚልክያስ ውስጥ የሕዝቡ መንፈሳዊ ችግር ምን እንደሆነ እንመለከታለን፤ ነገር ግን ዕዝራ የተዋጋው ኃጢአት በአይሁዳና በአሕዛብ መካከል የተደረገ ቅይጥ ጋብቻ ነበር።

| |
|---|
| 17ኛ ጥያቄ፥ ሀ) ይህ ነገር ዕዝራን በጣም ያሳሰበው ይመስልሃል? ለ) አንድ ክርስቲያን የማታምን ሴት ቢያገባ መንፈሳዊ ሕይወቱ እየቀዘቀዘ ሲሄድ ያየኸው እንዴት ነው? |

ሰሎሞን ወደ ኃጢአት ካመራባቸው መንገዶች አንዱ ከአሕዛብ ሴቶች ጋር ጋብቻ መመሥረቱ እንደሆነ ዕዝራ ከመጽሐፍ ቅዱስ፥ በተለይ ደግሞ ከሰሎሞን ታሪክ ያውቅ ነበር። ባዕዳን የሆኑት የሰሎሞን ሚስቶች ሰሎሞን እውነተኛውን አምላክ ትቶ የተሳሳቱ አማልክትን እንዲያመልክ አደረጉት። ይህ ነገር በአይሁድም ላይ እንዳይፈጸም ዕዝራ ሰግቶ ነበር። ዛሬ በርካታ ክርስቲያኖች የማያምን ሰው በማግባት ይህንን ሰው በኋላ አማኝ አደርገዋለሁ ይላሉ፤ ይህ ግን ብዙ ጊዜ አይሆንም። ይልቁንም ቀስ በቀስ ወደ ዓለም በመግባት ለእግዚአብሔር ያላቸውን ፍቅርና ለሌሎች የነበራቸውን ምስክርነት ያጣሉ።

ስለዚህ ዕዝራ ይህን ኃጢአት በሚመለከት ፈጣን ምላሽ ሰጠ። በሕዝቡ መካከል ልብሱን ቀደደ፤ አመድ በራሱ ላይ ነሰነሰ፤ ጠጉሩን

ነጨ፤ በመሬት ላይ ተቀምጦ በእግዚአብሔር ፊት ያለቅስ ጀመር። ስለ ሕዝቡ ኃጢአት ከእግዚአብሔር ዘንድ በግልጽ ይቅርታን ጠየቀ።

| |
|---|
| 18ኛ ጥያቄ፥ ሀ) ዕዝራ ስለ አይሁድ ሕዝብ ኃጢአት ከሰጠው ምላሽ በኃጢአት ላይ የነበረውን ጥላቻ እንዴት እናያለን? ለ) በቤተ ክርስቲያን መሪነታችን በእግዚአብሔር ሕዝብ ዘንድ ኃጢአት ስናይ ማድረግ ስላለብን ነገር ከዕዝራ ምላሽ ምን እንማራለን? |

ሕዝቡ ዕዝራ ያደረጋቸውን ነገሮች በተመለከቱ ጊዜ፥ አንድ ስሕተት እንዳለ ወዲያውኑ አወቁ። በእግዚአብሔር ፊት ኃጢአተኝነታቸውን በማወቅ ንስሐ መግባት ጀመሩ። ከዚያም ዕዝራ ለእግዚአብሔር ሕግ ለመታዘዝና አይሁድ ካልሆኑ ሰዎች ጋር ጋብቻን ላለመፈጸም ከእግዚአብሔር ጋር ቃል ኪዳን እንዲገቡ አደረገ። ሕዝቡም ይህንን ነገር በመታዘዝ ባዕዳን ሚስቶቻቸውን አሰናበቱ። ለእግዚአብሔር ለመታዘዝ ቃል ኪዳን ገቡ። የሚያሳዝነው ግን ይህ ቃል ኪዳን ለረጅም ጊዜ አለመቆየቱ ነው፤ ምክንያቱም በነህምያ ዘመን ሕዝቡ በተመሳሳይ ኃጢአት ወድቀው እናገኛቸዋለን።

ኃጢአት ወደ እግዚአብሔር ሕዝብ መካከል ሲገባ መሪዎች ወዲያውኑ እርምጃ መውሰድ አለባቸው። በእግዚአብሔር ፊት ራሳቸውን ትሑታን ሊያደርጉና ስለ ሕዝቡም ሆነ ስለ ራሳቸው ኃጢአት ንስሐ ሊገቡ ያስፈልጋል። ሕዝቡንም ስለ ኃጢአታቸው በመውቀስ ንስሐ እንዲገቡ ንጹሕ ሕይወትን በእግዚአብሔር ፊት እንዲኖሩ ለማድረግ መቻል አለባቸው።

| |
|---|
| 19ኛ ጥያቄ፥ አሁን የራስህንና የቤተ ክርስቲያንህን ሕይወት መርምር። ሀ) አንተና ሌሎች ሰዎች በእግዚአብሔር ፊት የምትመላለሱት በንጽሕና ነውን? ለ) በአንተና በቤተ ክርስቲያንህ ውስጥ ችግር የፈጠሩ አንዳንድ ኃጢአቶችን ጥቀስ። ሐ) አሁን እግዚአብሔር አንተንና ቤተ ክርስቲያንህን ንጹሕ እንዲያደርግ ለመለመን የጸሎት ጊዜ ይኑርህ። መ) ስለ ኃጢአታቸው በፍቅር ልትወቅሳቸውና ወደ ንስሐ እንዲመጡ ልታደርጋቸው የምትችላቸው ሰዎች ካሉ፥ በዚህ ሳምንት አነጋግራቸው። |

4ኛ ቀን፡-

## የመጽሐፈ ዕዝራ ዋና ዋና ትምህርቶች

1. መጽሐፈ ዕዝራ እግዚአብሔር የተስፋ ቃሉን በመጠበቅ ረገድ ታማኝ እንደሆነ ያስተምረናል።

እግዚአብሔር የአይሁድን ሕዝብ ከማስማረኩ በፊት፥ እንደሚመልሳቸው ተስፋ ሰጥቶአቸው ነበር (ኢሳ. 43፡1-7፤ ኤር. 29፡10 ተመልከት)። ኢየሩሳሌም ከተደመሰሰች ከ50 ዓመታት በኋላ እግዚአብሔር ቃል ኪዳኑን ለመፈጸም በአንድ አረማዊ ንጉሥ ተጠቀመ። እግዚአብሔር ሕዝቡ ታማኝ ባልነበሩበት ሰዓት እንኳ ታማኝ ነበረና፥ ዛሬም በእግዚአብሔር ላይ ኃጢአት ብንሠራም እንኳ፥ ሙሉ ለሙሉ እንደማይጥለን ዋስትና ሊኖረን ይችላል። እግዚአብሔር የተስፋ ቃሉን ለእኛ በመፈጸም እጅግ የዘገየ ቢመስልም፥ በራሱ ጊዜና ፍቅር በተሞላ መንገድ እንደሚፈጽምልን እርግጠኞች መሆን እንችላለን።

ነገር ግን እግዚአብሔር ሊባርካቸው የሚፈቅደው፥ ወደ እርሱ በንስሐ ለመመለስ የሚፈቅዱትን ብቻ ነው። የእግዚአብሔር ሕዝብ ከኃጢአታቸው ተመልሰው ንስሐ በሚገቡበት ጊዜ እግዚአብሔር ለእነርሱ ሊሰጣቸው የሚፈልገውን በረከት ይመልስላቸዋል።

| |
|---|
| 20ኛ ጥያቄ፥ ሀ) የእግዚአብሔርን ታማኝነት በሕይወትህ የተለማመድከው እንዴት ነው? ምሳሌዎችን ጥቀስ። ለ) ስለዚህ ጉዳይ እርሱን ለማመስገን ጊዜ ወስን። |

2. እግዚአብሔር በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የፈረሱትን ነገሮች እንደገና ለማነጽና ለማደስ እንዴት እንደሚሠራ መጽሐፈ ዕዝራ ያስተምረናል። መጽሐፈ ዕዝራ ስለ ቤተ መቅደሱና ስለ እግዚአብሔር ሕዝብ መንፈሳዊ ሕይወት እንደገና መታነጽ ያስተምረናል። የእግዚአብሔር ሕዝብ በመታዘዝ ለመኖር በሚጥሩበትና እግዚአብሔር በኃይል እንዲጠቀምባቸው በሚፈልግበት ጊዜ ሰይጣን ይህንን ነገር የማስቆም ሙከራ ለማድረግ ሁለት ነገሮችን ይጠቀማል። የመጀመሪያው፥ ተቃውሞ ወይም ስደት ነው። ሰይጣን የቤተ መቅደሱን ሥራ ለ20 ዓመታት ለማስተጓጎል የሰማርያ ሰዎችን ተቃውሞ ተጠቀመ፤ ነገር ግን የእግዚአብሔር ሕዝብ ሁልጊዜ ታማኝ ከሆኑ፥ በሚቃወሟቸው ሁሉ ላይ ድልን

ይቀዳጃሉ። ሁለተኛ፥ ሰይጣን የእግዚአብሔርን ሥራ ለማስቆም የእግዚአብሔር ሰዎች ለእርሱ ያላቸውን ፍቅር እንዲያጡና ባለመታዘዝ እንዲኖሩ ለማድረግ ይጥራል። ሰይጣን የእግዚአብሔር ሕዝብ ከእርሱ ተለይተው በኃጢአት እንዲወድቁ የሚያደርገው፥ ጥረት ከፍተኛ ነው። እግዚአብሔር ለሥራው ያልነጹ ዕቃዎችን አይጠቀምም። ይልቁንም ኃጢአት የእግዚአብሔርን ፍርድ ያመጣል። የመጽሐፈ ዕዝራ ጸሐፊ በሁለት ነገሮች ላይ አትኩሯል። የመጀመሪያው የእግዚአብሔር ሕዝብ አለመታዘዝ ሌላ ምርኮ እንዳያመጣባቸው ከመሥጋቱ ላይ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ፥ የእግዚአብሔር ሕዝብ የማያምኑ ሰዎችን በማግባትና እንደ ዓለም በመኖር የራሳቸውን ማንነት የማጣታቸው ነገር ያሳስበዋል። ዛሬም ቢሆን እነዚህን ሁለት አደጋዎች ፊት ለፊት እንጋፈጣለን።

---

21ኛ ጥያቄ፥ ሀ) እነዚህ ትምህርቶች ዛሬ ለክርስቲያኖች የሚያስፈልጉት ለምንድን ነው? ለ) መጽሐፈ ዕዝራን ለቤተ ክርስቲያንህ የምታስተምርባቸውን መንገዶች ዘርዝር።

---

መጽሐፈ ዕዝራ ከአዲስ ኪዳን ጋር ያለው ግንኙነት በአዲስ ኪዳን ፈሪሳውያንና ጸሐፍት የሚባሉ የሕግ መምህራንና የሃይማኖት መሪዎች ቡድን እናያለን። እነዚህ የጌታ ኢየሱስ ዋና ጠላቶች የነበሩና በመስቀል ላይ እንዲሞትም ያደረጉ ናቸው። ለወጋቸው ከሚገባ በላይ ትኩረት በመስጠት የእግዚአብሔርን ሕግ ስለጣሱ፥ ኢየሱስ ግብዞች ናችሁ በማለት ብዙ ጊዜ ሲወቅሳቸው እንመለከታለን (ማቴ. 15፡1-9 እና 23፡13-35 ተመልከት)። እነዚህ የሃይማኖት መሪዎች ከየት መጡ? ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁራን የአዲስ ኪዳን ፈሪሳውያን ወይም የሕግ መምህራን ይህን በሚመለከት የመጀመሪያው ጸሐፊ የነበረውን የዕዝራን ባሕል የተከተሉ ናቸው ብለው ያስባሉ፤ ነገር ግን ዕዝራ ከእነርሱ በተለየ ሁኔታ ለእግዚአብሔር ሕግ ባለው ታዛዥነት፥ ራሱን ዝቅ በማድረግ፥ በትሕትናው፥ ደግሞም ለውስጥ ንጽሕና በሚሰጠው ትኩረት የታወቀ ነበር። ሆኖም በመጽሐፈ ዕዝራ ውስጥ እነዚህ ፈሪሳውያንና የአይሁድ ሃይማኖት መሪዎች የሆኑ ሰዎች ኢየሱስ በምድር ከኖረበት ከብዙ መቶ ዓመታት በፊት የነበረውን ሥረ መሠረታቸውን እንመለከታለን። በመጽሐፈ ዕዝራ የሚከተሉትን ነገሮች መመልከት እንጀምራለን፡-

1. የሕዝቡ ዋና መሪዎች፥ የፖለቲካ አመራሩን የያዙት ነገሥታት ወይም ገዥዎችና አስተዳዳሪዎች ሳይሆኑ፥ መንፈሳዊ መሪዎች ነበሩ። እነርሱም ካህናትና ሌዋውያን ነበሩ። ካህናቱ ከጊዜ ወደ ጊዜ ኃይላቸውና ተሰሚነታቸው እየጨመረ ስለመጣ፥ በኋላ የፖለቲካ አመራሩንም ጠቅልለው ያዙ፤ ስለዚህም ካህናቱ ከመንፈሳዊ ነገር ይልቅ፥ በፖለቲካ ጉዳዮች ማተኰር ጀመሩ። በኢየሱስ ዘመን የነበሩ የአይሁዳ መሪዎች የሃይማኖት መሪዎች ሲሆኑ፥ የአይሁድ ሕዝብ ከፍተኛ የሥልጣን አካል የሆነው የካህናት አለቆች ሸንጎ አባላት ነበሩ።

| |
|---|
| 22ኛ ጥያቄ፥ ዛሬም የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በፖለቲካ ጉዳይ ውስጥ እጅግ ጠለቅ ብለው በሚገቡበት ጊዜ ችግር የሚመጣው ለምንድን ነው? |

2. የእግዚአብሔርን ሕግ ማጥናትና መተርጎም ብቸኛ ኃላፊነታቸው የሆነ ጸሐፍት የሚባሉ ባለሙያዎች አገልግሎት መጀመር (ዕዝራ 7፡10)፥ እንደነዚህ ዓይነት መሪዎች ተፈላጊ ነበሩ፤ ነገር ግን አደገኛም ሊሆኑ ይችላሉ። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚገኙ አባላት በታወቁ መሪዎች ትምህርት ላይ ብቻ ከተደገፉና የእግዚአብሔርን ቃል ለራሳቸው ማጥናት ካቆሙ እነርሱም ሆኑ ቤተ ክርስቲያን በፍጥነት እየደከሙ ይሄዳሉ። ከመጽሐፍ ቅዱስ እጅግ አስፈላጊ ትምህርቶች አንዱ ክርስቲያኖች ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት ካህናት ስለሆኑ (1ኛ ጴጥ. 2፡9)፥ እኛ ሁላችን የእግዚአብሔርን ቃል የማጥናትና የመተርጎም ኃላፊነት አለብን የሚል ነው።

3. ለእግዚአብሔር ቃል ሙሉ በሙሉ በመታዘዝ ጉዳይ ላይ በማተኮር፡- እነዚህ በሙያው የተካኑ ጸሐፍት ወዲያውኑ ወደ ከፋት የተለወጠ አንድ ነገር ማድረግ ጀመሩ። ግን ሕዝቡ መታዘዝ እንዳለባቸው አድርገው ተጨማሪ ሕግጋትን መስጠት ጀመሩ። ግን ይህንን ያደረጉት ለመልካም ነበር? የታወቁ የእግዚአብሔር ሕግጋትን እንዳይጥሱ ተጨማሪ ጥበቃ ማድረጋቸውስ አስፈላጊ ነበር? ለመሆኑ እግዚአብሔር ሕዝቡን ያስማረከው የእግዚአብሔርን ሕግ ስለ ጣሱ አይደለምን? እነርሱ ግን ተጨማሪ ሕግጋት ቢያወጡ ሕዝቡ በጽሑፍ ያለውን የእግዚአብሔርን ሕግ ለመጣስ ብዙ ዕድል አይኖረውም ብለው አሰቡ። ብዙም ሳይቆዩ ከእግዚአብሔር ሕግ ይልቅ በዚህ

መልክ በተሰጡ ሕጎች (ወግና ልማዶች) ላይ ማተኮር ጀመሩ፥ (ማለትም:- ምሕረት፥ ቅን ፍርድና፥ እምነትን ለመሳሰለው) ከሁሉ ይልቅ አስፈላጊ ለሆነው ለእግዚአብሔር ሕግ መታዘዛቸውን ከማረጋገጥ ይልቅ፥ ሕዝቡ እነርሱ ላወጡት ሕግ መታዘዝ አለመታዘዛቸውን በማጣራት ላይ ትኩረት አደረጉ።

23ኛ ጥያቄ፥ ሀ) ይህ ተመሳሳይ ነገር በአብያተ ክርስቲያኖቻችን እንዴት ሊፈጸም ይችላል? ለ) በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የተጨመሩ ቤተ ክርስቲያንህ የምታስተምራቸው ሕጎች የትኞቹ ናቸው? ሐ) እነዚህ ሕግጋት ለክርስቲያን የማሰናከያ ዓለት የሆኑት እንዴት ነው?

አንዲት ቤተ ክርስቲያን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በሚገኙ ሕግጋት ላይ ሌሎች ተጨማሪ ሕግጋትን ስትጨምር፥ አንድ አደገኛ ነገር መከሰት ይጀምራል። ሰዎች ከመጽሐፍ ቅዱስ ሕግ ይልቅ የሰዎችን ሕግ መከተል ይጀምራሉ። (ማቴ. 23፡23፤ ማር. 7፡1-9)። ወዲያውኑ የሰዎችን ሕግ ከጠበቁ መንፈሳዊ እንደሆኑ ያስባሉ። በመቀጠልም አምልኮአቸው እግዚአብሔርን ከልብ ከማምለክ ይልቅ ሕግን መጠበቅ ወደ መሞከር ይለወጣል። የግል እምነት አስፈላጊነት ለመዳን ሕግን መጠበቅ ያሻል በሚለው ተተክቶአል። መጽሐፍ ቅዱስ ይህንን ሕጋዊነት ብሎ ሲጠራው፥ ሐዋርያው ጳውሎስ የሮሜንና የገላትያን መልእክቶች የጻፈው ይህንን አቋም በሚፃረር መንገድ ነው። (ስለ ሕጋዊነት ተጨማሪ ትምህርት ለማግኘት ገላትያ-ያዕቆብ የተባለውን የትመማ መጽሐፍ አጥና)።

4. ከዓለም የመለየት አስፈላጊነት ወዲያውኑ አይሁድ የዓለምን ሕዝብ እንዲጠሉና ከአሕዛብ ጋር ምንም ግንኙነት ሊያደርጉ እንደማይገባ እንዲወስኑ አደረጋቸው። ዕዝራና ነህምያ በግልጥ እንዳስተማሩት የእግዚአብሔር ሕዝብ ከአሕዛብ ጋር የጋብቻ ኅብረት ማድረግ የለባቸውም። ነገር ግን ከአሕዛብ ጋር ከሚደረግ ግንኙነት ሙሉ በሙሉ እንዲርቁ አላስተማሩም። በኋላ የተነሡት የአይሁድ መሪዎች ግን ከአሕዛብ ጋር ከሚደረግ ማንኛውም ዓይነት ግንኙነት መራቅ እንዳለባቸው ሕዝቡን አስተማሩ። መሪዎቹ በንጽሕና በመቆየት ላይ ትኩረት ስላደረጉ ከአሕዛብ ጋር መብላት ወይም ኅብረት ማድረግ እንደሚያረክሳቸው ገመቱ። እግዚአብሔር እነርሱን የመረጠበት አንዱ ምክንያት ለአሕዛብ ብርሃን እንዲሆኑ መሆኑን ረሱ (ኢሳ. 42፡6 ተመልከት)።

24ኛ ጥያቄ፥ የዚህ ዓይነት ተመሳሳይ ነገር ዛሬም በቤተ ክርስቲያን ሊፈጸም የሚችለው እንዴት ነው?

ብዙ ጊዜ በአብያተ ክርስቲያኖቻችን ከሚፈጸሙት አሳዛኝ ነገሮች አንዱ፥ ክርስቲያን ካልሆኑ ሰዎች ጋር ያለንን ማንኛውንም ግንኙነት ቀስ በቀስ ማቋረጣችን ነው። በዓለም ተጽዕኖ እንዳይደረግብን ከሚገባ በላይ በመሥጋት ክርስቲያን ያልሆኑ ጓደኞች እንዲኖሩን እንኳ አንፈቅድም። ከክርስቲያኖች ጋር ብቻ እንኖራለን፤ ቢመችን ጊዜያችንን ሁሉ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለማሳለፍ እንሞክራለን ወዘተ። እግዚአብሔር ግን ለዓለም ብርሃንና ጨው እንድንሆን ጠርቶናል (ማቴ. 5፡13-16)። ይህንን ነገር መፈጸም የምንችለው ከማያምኑ ሰዎች ጋር ኅብረት ሲኖረን ብቻ ነው። ኢየሱስ የጸለየው ከዓለም ክፉ ነገሮች እንድንጠበቅ እንጂ፥ ከዓለም እንድንወጣ አይደለም (ዮሐ. 17፡9-16፥18 ተመልከት)።

25ኛ ጥያቄ፥ ሀ) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች አባሎቻቸው ክርስቲያን ካልሆኑ ሰዎች ጋር ግንኙነት በማድረግ ወንጌልን እንዲያካፍሏቸው ለማበረታታት ምን ማድረግ ይችላሉ? ለ) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች አባሎቻቸው ከሌሎች ክርስቲያኖች ጋር ከሚገባ በላይ አዘውትረው ጊዜያቸውን በማሳለፍ ለማያምኑ ሰዎች ሊመሰክሩ እስከማይችሉ ድረስ እንዳይሆኑ ምን ማድረግ ይችላሉ? ሐ) የምትገናኛቸው ክርስቲያን ያልሆኑ ሰዎች እነማን እንደሆኑ ዘርዝር። መ) ስለ ኢየሱስ የመሰከርክላቸው መቼ ነበር? ሠ) በዚህ ሳምንት ለምታውቀው ለአንድ ለማያምን ሰው ፍቅር በተሞላው መንገድ ስለ ክርስቶስ ልትነግረው ቀጠሮ ያዝ። (ለምሳሌ፡- ሻይ ወይም ምሳ ጋብዘው)። ይህን ለማድረግ የምታውቀው ክርስቲያን ያልሆነ ሰው ከሌለ፥ እግዚአብሔር አንድ ሰው እንዲሰጥህና በዚህ ሳምንት ልትመሰክርለት እንድትችል ጸልይ።

## 5ኛ ቀን፡-

የዚህን ሳምንት ትምህርት ከልስና ለሳምንታዊ ስብሰባ ዝግጅት ይረዳህ ዘንድ የውይይት ጥያቄዎችን ተመልከት።

### ሳምንታዊ ስብሰባ

1. የሳምንቱ የአምልኮ ክፍለ ጊዜ
2. ጸሎት
3. የትምህርቱ ክለሳ

4. ውይይት

1. ሀ) የዕዝራ ታሪክ ስለ እግዚአብሔር ሕዝብ እንደገና አመሠራረት የሚተርክ ታሪክ የሚሆነው እንዴት ነው? ለ) በዕዝራ ዘመን ከተፈጸመው ነገር ቤተ ክርስቲያን የምትለየውና የምትመሳሰለው እንዴት ነው? ሐ) ዛሬም ቤተ ክርስቲያን ልትጠፋ የምትችልባቸውን መንገዶች ዘርዝር። መ) የቤተ ክርስቲያንን ወይም የቤተ ክርስቲያን አባላትን ሕይወት እንደገና ለመሥራት እግዚአብሔር አንተን እንዴት እንደተጠቀመብህ የሚያሳዩ ምሳሌዎችን ስጥ። ሠ) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ቤተ ክርስቲያንን እንደገና ለመገንባት ምን ማድረግ ይችላሉ?

2. ሀ) በዚህ ዘመን ካሉ የቤተ ክርስቲያን መሪዎችና አስተማሪዎች እግዚአብሔር ምን እንደሚፈልግ ዕዝራ መልካም ምሳሌ ሊሆን የሚችለው እንዴት ነው? ለ) በቤተ ክርስቲያንህ ውስጥ የእግዚአብሔርን ቃል በማወቅና በማስተማር ሥልጡን የሆኑ ሰዎችን ጥቀስ። ሐ) ዛሬ በቤተ ክርስቲያናችን የእግዚአብሔርን ቃል በሚገባ አውቀው ለማስተማር የሚችሉ የሠለጠኑ ሰዎች በጣም ጥቂት የሆኑት ለምንድን ነው? መ) አንድ ሰው እንደ ዕዝራ መሆን የሚችለው እንዴት ነው? ሠ) የቤተ ክርስቲያንህ መሪዎች ልክ እንደ ዕዝራ መሆን እንዲችሉ ለመርዳት ምን ማድረግ ትችላለህ?

3. ሀ) አይሁድ በከፊል አይሁዳውያን የሆኑትን ሳምራውያን በቤተ መቅደሱ ሥራ እንዳይረዷቸው ለምን ከለከሉ? ለ) በዚህ ዘመን ክርስቲያን ያልሆኑ ሰዎች በአምልኮአችንና በሕይወታችን ላይ ተጽዕኖ ያደርጉ ዘንድ እንዴት ልንፈቅድላቸው እንችላለን? ሐ) ዓለም በቤተ ክርስቲያን ላይ ያላት ተጽዕኖ በተቻለ መጠን እንዲቀንስ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ምን ማድረግ ይችላሉ?

4. ሀ) አይሁድ ቤተ መቅደሱን ለመሥራት በሚሞክሩበት ጊዜ ተቃውሞውን የተጋፈጡት እንዴት ነበር? ለ) የእግዚአብሔር ሰዎች ለእግዚአብሔር አንድ ነገር ለማድረግ በሚዘጋጁበት ወቅት ብዙውን ጊዜ ተቃውሞ የሚገጥማቸው ለምን ይመስልሃል? ሐ) ይህንን በቤተ ክርስቲያንህ ውስጥ ያየኸው እንዴት ነው? መ) ዮሐ. 15፡18-21፤ 17፡11-16 አንብብ። ዓለምን አንመስልም በማለት ለሚኖሩ ክርስቲያኖች ምን የተስፋ ቃል ተገብቶላቸዋል?

ሠ) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ለእግዚአብሔር የተቀደሰ ሕይወት እንዲኖሩ ከፈለጉ አባሎቻቸውን ለተቃውሞ ማዘጋጀት ያለባቸው እንዴት ነው?

5. ሀ) በዕዝራ ዘመን አይሁድ ፈተነው በኃጢአት የወደቁት እንዴት ነበር? ለ) ቤተ ክርስቲያንም በኃጢአት የምትወድቀው ወይም ለእግዚአብሔር ያላትን ፍቅርና ለወንጌል ያላትን ቅንዓት የምታጣው እንዴት ነው? ሐ) ዕዝራ በኃጢአት ላይ ከነበረው ዝንባሌ የምንማረው ነገር ምንድን ነው? መ) በአሁኑ ዘመን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለሚፈጸም ኃጢአት የምንሰጠው ምላሽ ምንድን ነው?

6. ሀ) ከዕዝራ ዘመን በኋላ የነበሩ አይሁድ ራሳቸውን ከአሕዛብ በጣም የለዩት እንዴት ነበር? ለ) ይህ ድርጊታቸው እግዚአብሔር እነርሱን የጠራበትን ዓላማ ያጠፋው እንዴት ነው? ሐ) ዛሬስ በዘመናችን ይህ ነገር በክርስቲያኖች ላይ የሚፈጸመው እንዴት ነው? መ) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች አባሎቻቸውን ክርስቲያን ካልሆኑ ሰዎች ጋር ግንኙነት በማድረግ ወንጌል እንዲያካፍሉአቸው ለማበረታታት ምን ማድረግ ይችላሉ? ሠ) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች አባሎቻቸውን ከክርስቲያኖች ጋር ከሚገባ በላይ ኅብረት በማድረግና በመቆየት ለማያምኑ ሰዎች ሊመሰክሩላቸው እስከማይችሉ ድረስ እንዳይደርሱ ምን ማድረግ ይችላሉ? ረ) ግንኙነት ያለህን ክርስቲያን ያልሆኑ ሰዎች ስም ዝርዝር ጻፍ። ሰ) ስለ ኢየሱስ የመሰከርክላቸው መቼ ነበር? ሸ) በዚህ ሳምንት ለምታውቁት ለማያምን ሰው ስለ ወንጌል በፍቅር ለመመስከር ሙከራ ያደረጋችሁበትን ውጤት በሚመለከት አንዳችሁ ለሌላችሁ ንገሩ።

5. ጸሎት

# ትምህርት 19

## 1ኛ ቀን:- የመጽሐፈ ነህምያ መግቢያ

እንደ ዕዝራ ሁሉ ነህምያም የእግዚአብሔርን ሕዝብ እንደገና ስለ ማነጽ የሚናገር ታሪክ ነው። ምናልባት ስለ መልካም የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከሚገኙ እጅግ ግልጽ ከሆኑ ምሳሌዎች አንዱ ይህ ነው። የእግዚአብሔር ሕዝብ እርሱ የሰጣቸውን ሥራ ውጤታማ በሆነ መንገድ እንዲያከናውኑ እንዴት ማደራጀት እንደሚቻል ያሳያል።

1ኛ ጥያቄ፥ ሀ) እግዚአብሔር ሕዝቡ እንዲሠሯቸው የሚፈልጋቸውን ነገሮች ውጤታማ በሆነ መንገድ ለመሥራት ይቻል ዘንድ ጥሩ አደረጃጀት የሚጠይቁ ሥራዎችን ዘርዝር። ለ) በቤተ ክርስቲያን መሪዎች ዘንድ ጥሩ የሆነ አደረጃጀት ወይም አስተዳደር ባለመኖሩ በቤተ ክርስቲያንህ ውስጥ በሚገባ ያልተሠሩ ሥራዎች የትኞቹ ናቸው?
2ኛ ጥያቄ፥ ነህምያን ከመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት ተመልከት። ስለ መጽሐፈ ነህምያ የተጠቀሱ አንዳንድ ጠቃሚ ነገሮችን ጥቀስ።
3ኛ ጥያቄ፥ ባለፈው ሳምንት የመጀመሪያ ቀን ትምህርት ስለ መጽሐፈ ዕዝራና ነህምያ የተመለከትናቸውን ነገሮች ከልስ። ጸሐፊው ማን እንደሆነ፥ በይሁዳ ላይ የነበረው ኃያል መንግሥት ማን እንደነበረና የመጽሐፈ ዕዝራና ነህምያ ዋና ዋና ዓላማዎችን ዘርዝር።

ባለፈው ሳምንት የመጽሐፈ ዕዝራና ነህምያ የመጀመሪያ ዘገባዎች የተጻፉት በዕዝራና በነህምያ እንደሆነ ተመልክተናል። እነዚህ ዘገባዎች ተጠናቅረውና ወደ ይሁዳ ስለተመለሱት ምርኮኞች የሚናገረው ታሪክ ታክሎባቸው ዕዝራ-ነህምያ ወደሚል አንድ መጽሐፍ ተጠቃለሉ። የዕብራይስጡ መጽሐፍ ቅዱስ ወደ ግሪክ ቋንቋ በተተረጎመበት ጊዜ ግን ይህ መጽሐፍ በሁለት ክፍል ተከፈለ።

መጽሐፈ ነህምያ ስያሜውን ያገኘው የመጽሐፉ ዋና ገጸ ባሕርይ ከሆነው ከነህምያ ነው። እርሱም የይሁዳ ገዥ በመሆን የኢየሩሳሌምን ቅጥሮች እንደገና በበላይነት ይቆጣጠር ነበር።

## የነህምያ ዘመን

ነህምያ በምርኮ ዘመን በምርኮ አገር የተወለደ አይሁዳዊ ነው። እግዚአብሔር በፋርስ መንግሥት ውስጥ ከፍተኛ ሥልጣን እንዲያገኝ አደረገው። ነህምያ የንጉሡ ጠጅ አሳላፊ ነበር። ይህ ከፍተኛ የሥልጣን ስፍራ ባይመስልም፥ ጠጅ አሳላፊነት በጥንት ዘመን የንጉሡ ወዳጅ ለሆነና በከፍተኛ ደረጃ ታማኝነት ላለው ሰው የሚሰጥ ሥራ ነበር። ጠጅ አሳላፊ ታማኝ መሆን የነበረበት ሰዎች ንጉሡን የመግደል ሙከራ የሚያደርጉበት አንዱ መንገድ በሚበላው ወይም በሚጠጣው ነገር ላይ መርዝ በመጨመር ስለ ነበር ነው፤ ስለዚህ ይህ ማለት ነህምያ የፋርስ ንጉሥ የቅርብ አማካሪ ከሆኑት ሰዎች አንዱ ነበር ማለት ነው። ነህምያ በመንግሥት ዘንድ በጣም ጥሩ ሥራ ያለውና ጥሩ ኑሮን የሚኖር ቢሆንም፥ ወገኖቹንና ጨርሶ አይቷት የማያውቃትን ኢየሩሳሌምን አልረሳም። ነህምያ እግዚአብሔርን የሚወድ፥ ስለ እግዚአብሔር ክብርና ስለ ሕዝቡ በጣም የሚገደው ሰው ነበር። የኢየሩሳሌም ቅጥር ባለመሠራቱ የእግዚአብሔር ስም ተነቅፎ ስለ ነበረና ሕዝቡም ለጠላት ጥቃት ተጋልጠው ስለ ነበር ነህምያ ስለ ደኅንነታቸው ገደደውና የኢየሩሳሌምን ቅጥር በመሥራት እርሱን ይጠቀምበት ዘንድ እግዚአብሔርን ለመነ።

ነህምያ አብሮት ይሠራ የነበረው የፋርስ ንጉሥ አርጤክስስ በመባል ይታወቃል። በሥልጣን ላይ የቆየው ከ464-425 ዓ.ዓ. ነበር። አርጤክስስ በዘመነ መንግሥቱ መጀመሪያ ላይ አይሁድን ስደት እንዲደርስባቸው ያደረገ ቢሆንም፥ ለዕዝራ ግን የተለየ ርኅራኄ በማሳየት በ458 ዓ.ዓ. ዕዝራንና አንዳንድ አይሁድን ወደ አገራቸው እንዲመለሱ አድርጓል። ከ13 ዓመታት በኋላ ደግሞ ነህምያ ሌላ ቡድን እየመራ ወደ አገሩ እንዲሄድ አርጤክስስ ፈቅዶለታል። ነህምያ ወደ ኢየሩሳሌም አገሩ ከተመለሰ በኋላ ለ12 ዓመታት (444-432 ዓ.ዓ.) የይሁዳ ገዥ በመሆን አገልግሏል። ከ12 ዓመታት በኋላ ግን ወደ ፋርስ በመመለስ በአርጤክስስ መንግሥት ውስጥ እንደገና አገልግሏል። ከዚያ በኋላ በፋርስ ምን ያህል እንደቆየ ባናውቅም፥ በመጨረሻ ወደ ኢየሩሳሌም በመመለስ የይሁዳ ገዥ እንደሆነ እንመለከታለን። ለሁለተኛ ጊዜ ገዥ የሆነበት ዘመን ምን ያህል እንደሆነ አናውቅም።

ነህምያ ገዥ ሆኖ ስለሠራበት ጊዜ ብዙ የምናውቀው ነገር የለም። ከነህምያ 1-12 የሚገኘው ታሪክ በአብዛኛው የተፈጸመው ነህምያ በኢየሩሳሌም በአገለገለባቸው በመጀመሪያዎቹ ዓመታት ነው።

የነህምያ የመጀመሪያ አገልግሎት የኢየሩሳሌምን ቅጥር እንደገና መሥራት ነበር። ይህ ነገር በጣም አስፈላጊ የሆነው ለምንድን ነው? ሁለት ዋና ዋና ምክንያቶች ነበሩ:- የመጀመሪያው፥ በጥንት ዘመን ሕዝቦች ድንገት ከሚመጣ የጠላት ጦርና ከሚዘርፍ ወራሪ የሚከላከሉበት ዋናው መንገድ የከተማ መከለያ ቅጥር ነበር፤ ስለዚህ በኢየሩሳሌም ከተማ ዙሪያ ቅጥር እስከሌለ ድረስ የእግዚአብሔር ሕዝብ ሰላም ሊኖራቸውና የደኅንነት ዋስትና ሊያገኙ አይችሉም ነበር። ይልቁንም በማያቋርጥ ፍርሃት መኖር ዕጣ ፈንታቸው ነበር። ልክ ቅጥሩ እንደተሠራ ሕዝቡ በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ላይ በማተኮር የእግዚአብሔርን ቃል ለመስማትና ለመታዘዝ የነበራቸውን ፈቃደኝነት ማየት የሚያስገርም ነው።

ሁለተኛ:- የኢየሩሳሌም ቅጥሮች የእግዚአብሔር ሕዝብ ያሉበት መንፈሳዊ ሁኔታ ምልክት ነበሩ። ቅጥሮቹ እስካልተሠሩ ድረስ እግዚአብሔር ስሙን ሊያኖርባትና ሊመለከባት ተስፋ ለሰጣት ለዚህች ከተማ በቂ ትኩረት እንደሌለ የሚያሳይ ነበር። እግዚአብሔር ሊመለከበት ባለው ስፍራ ስሙን ለማኖር ቃል ገብቶ ነበር። የእግዚአብሔር ከተማ የነበረችው የኢየሩሳሌም ውጫዊ ሁኔታ የእግዚአብሔርን ሕዝብ የልብ መንፈሳዊ አቋም የሚያንጸባርቅ ነበር።

---

4ኛ ጥያቄ፥ የአብያተ ክርስቲያናቶቻችን ውጫዊ ሁኔታ ብዙ ጊዜ መንፈሳዊ ሁኔታቸውን የሚያመለክተው እንዴት ነው?

---

## የነህምያ አስተዋጽኦ

1. የነህምያ የመጀመሪያ አስተዳደር (1-12)
   ሀ. ነህምያ ስለ ኢየሩሳሌም ሰማ (1)
   ለ. ነህምያ ወደ ኢየሩሳሌም ተጓዘ (2)
   ሐ. በኢየሩሳሌም ቅጥር ይሠሩ የነበሩ ሰዎች ዝርዝር (3)
   መ. የኢየሩሳሌም ቅጥር ሥራ የገጠመው ተቃውሞ (4)
   ሠ. የኢየሩሳሌም ቅጥር ሥራን ያስቆሙ ውስጣዊ ችግሮች (5)
   ረ. የቅጥሩ ሥራ ተፈጸመ (6)
   ሰ. ወደ ይሁዳ የተመለሱ ምርኮኞች ዝርዝር (7)

ሸ. በዕዝራ አመራር ሥራ የተነሣ መንፈሣዊ መነቃቃት (ተሐድሶ) (8-10)

ቀ. በኢየሩሳሌም የሚኖሩ ሰዎች ተመረጡ (11)

በ. የካህናት ዝርዝርና የቅጥሩ መመረቅ (12)

2. የነህምያ ሁለተኛ አስተዳደር፥ መንፈሳዊ ተሐድሶ (13)

## 2ኛ ቀን:- ነህምያ 1-4

> 5ኛ ጥያቄ፥ ሀ) ለአንድ የተዋጣለት የቤተ ክርስቲያን መሪ በጣም አስፈላጊ ባሕርይ ምን ይመስልሃል? መሪው ምን መሆን አለበት? ምንስ ማድረግ አለበት? ወዘተ. ለ) በኢትዮጵያ ውስጥ የተዋጣላቸው የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ናቸው ብለህ የምታስባቸውን አንዳንድ ሰዎች በምሳሌነት ጥቀስ። ሐ) ውጤታማ ያደረጋቸው ነገር ምንድን ነው?

በመሪነት እግዚአብሔር የሚጠቀምበት ሰው ምን ዓይነት ነው? የፈረሱ መንፈሳዊ ቅጥሮችን እንደገና በመሥራት ጠንካራ ቤተ ክርስቲያንን መመሥረት በሚያስችል መንገድ የእግዚአብሔርን ሕዝብ መምራት የሚችል ምን ዓይነት ሰው ነው? መጽሐፈ ነህምያ ስለ እንደዚህ ዓይነት ሰው ይነግረናል። ይህ ሰው ነህምያ ነበር። ነህምያ ውጫዊና የሚታይ የነበረውን የኢየሩሳሌምን ቅጥር ለማሠራት ኃላፊነት የነበረበት ፖለቲካዊ መሪ ቢሆንም፥ የእግዚአብሔር ሕዝብ የፈረሱ የቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ ቅጥሮችን እንደገና ሊሠሩ በሚችሉበት መንገድ እንዴት መምራት እንደሚቻል በርካታ ነገሮችን ከእርሱ እንማራለን። በነህምያ ጥናታችን እግዚአብሔር ነህምያን ሊጠቀምበት የቻለው በእግዚአብሔር ፊት በነበረው መንፈሳዊ ሕይወትና የእግዚአብሔርን ሕዝብ ለመምራት በነበረው የአስተዳደር ችሎታ እንደነበረ እንመለከታለን።

> 6ኛ ጥያቄ፥ ነህምያ 1-4 አንብብ። ሀ) ስለ ነህምያ ግለጥ። ስለ ነህምያ መንፈሳዊ ሕይወት ከእነዚህ ቁጥሮች የምንማረው ነገር ምንድን ነው? ለ) ከእነዚህ ቁጥሮች ስለ ነህምያ የማቀድና የመምራት ችሎታ ምን እንማራለን? ሐ) የኢየሩሳሌምን ቅጥሮች እንደገና ለመሥራት በሞከረ ጊዜ፥ ነህምያን ያጋጠሙትን የተለያዩ ችግሮችና ትግሎች ጥቀስ።

የንጉሡ አርጤክስስ ጠጅ አሳላፊና አማካሪ የነበረው ነህምያ የሚኖረው በፋርስ መንግሥት ዋና ከተማ በሱሳ ባለው ቤተ መንግሥት

ውስጥ ነበር። አንዳንድ ዘመዶቹና ሌሎች አይሁዶች ከኢየሩሳሌም ወደ ፋርስ ነህምያን ለመጎብኘት መጡና የኢየሩሳሌም ከተማ የነበረችበትን ሁኔታና የእግዚአብሔር ሕዝብም በዚያ እንዴት እንደሚኖሩ ነገሩት።

ነህምያ እግዚአብሔርን የሚፈራ ታላቅ መሪ ያደረጉትን የሚከተሉትን ነገሮች ተመልከት:-

1. ነህምያ የእግዚአብሔር ሕዝብ ስለ ነበሩበት ሁኔታ የሚገደው ሰው ነበር። የሚኖረው በኢየሩሳሌም አካባቢ ባይሆንም፥ ጉዳዩ ያሳስበው ስለ ነበር ሕዝቡን በሚመለከት ወደ እርሱ የመጡትን አይሁድ ጠየቀ። ነህምያ ሕዝቡ ስለ ነበሩበት አሳዛኝ ሁኔታ ሲሰማ አለቀሰ። እንዲሁም በእግዚአብሔር ፊት ጾመና ጸለየ።

2. ነህምያ የጸሎት ሰው ነበር። በመጽሐፈ ነህምያ በአጠቃላይ ሁኔታዎች አስቸጋሪ በሚሆኑበት ጊዜ ነህምያ ፊቱን ወደ እግዚአብሔር ሲመልስ እንመለከተዋለን።

| |
|---|
| 7ኛ ጥያቄ፥ የሚከተሉትን ጥቅሶች ተመልከት:- ነህ. 1:4፤ 2:4፤4:9፤6:9 ሀ) በእነዚህ ጥቅሶች ነህምያ የጸለየባቸውን ጊዜያትና ስለምን እንደጸለየ ዘርዝር። ለ) ከእነዚህ ጥቅሶች ስለ ጸሎት የምንማረው ነገር ምንድን ነው? |

3. ነህምያ የእግዚአብሔርን ቃል ያውቅ ነበር። በምዕራፍ 1 የተጻፈውን የነህምያን ጸሎት ስንመለከት፥ ነህምያ የይሁዳን ታሪክ እንደሚያውቅ ማለትም የሙሴን ሕግ፥ እግዚአብሔር ከእስራኤል ጋር የገባውን ቃል ኪዳንና እግዚአብሔር ሕዝቡን እንደገና ለማደስና ለማነጽ የሰጠውን ተስፋ በሚገባ ማወቁን እንመለከታለን።

4. ነህምያ ኃጢአቱንና የአባቶቹን ኃጢአት የሚናዘዝ መሪም ነበር። ነህምያ ከእግዚአብሔር ጋር ያለውን ኅብረት የሚያበላሽና የሚያጠፋ፥ እግዚአብሔር ለጸሎቱ ሊሰጠው ያለውን መልስ የሚያግድ አንዳችም ነገር እንዳይኖር የሚፈልግ ሰው ነበር። ኃጢአት ይህንን ሊያደርግ እንደሚችል ያውቅ ስለ ነበረ ኃጢአቱን ተናዘዘ።

5. ነህምያ ሥራው ውስጥ ለመግባት ራሱን በማዘጋጀት፥ ሕዝቡን እንደገና ለመሥራት እንዲጠቀምበት እግዚአብሔርን ለመነ። እግዚአብሔርን ሌላ ሰው እንዲያስነሣ አልጠየቀውም፤ ግን

ለእግዚአብሔር ምን መሥራት እንደሚችልና ያንን ለማድረግ ምን እንደሚጠበቅበት ጠየቀ።

| |
|---|
| 8ኛ ጥያቄ፥ ሀ) እነዚህ አምስት መንፈሳዊ መመዘኛዎች ለቤተ ክርስቲያን መሪዎች የሚያስፈልጉት ለምንድን ነው? ለ) በሕይወትህ ውስጥ የሚኖሩትስ እንዴት ነው? ሐ) በእነዚህ አምስት የሕይወትህ አቅጣጫዎች ለማደግ የምትችለው እንዴት ነው? |

ነህምያ 2-3 የነህምያን የአስተዳደር ብቃቶች ይነግሩናል። በመጨረሻም ወደ ኢየሩሳሌም እንደሚመልሰውና የፈረሰውን ቅጥር እንደገና የመሥራት ሥራውን ሊያከናውን የሚችለው እግዚአብሔር እንደሆነ ቢያውቅም፥ እግዚአብሔር በሰዎች መገልገል ደስ እንደሚለውም ያውቅ ነበር፤ ስለዚህ ነህምያ ጸለየና ዕቅድ አወጣ። ነህምያ መጸለይ በጀመረበት በኪስሊቭ፥ በኅዳር ወርና ወደ ኢየሩሳሌም ለመሄድ ፈቃድ በጠየቀበት በኒሳን፥ በመጋቢት ወር መካከል የአራት ወራት ልዩነት አለ። እግዚአብሔር የንጉሡን ልብ ሲከፍት፥ ነህምያ ለመንቀሳቀስ ዝግጁ ነበር። ነህምያ እግዚአብሔር ጸሎቱን እንደሚመልስ ስላመነ፥ በኢየሩሳሌም ለምን ያህል ጊዜ እንደሚቆይና ሥራውን ለመሥራት ምን እንደሚያስፈልገው፥ ሄዶም ምን እንደሚሠራ ለንጉሡ ለመናገር ተዘጋጅቶ ነበር። ነህምያ የዕቅዱን ምንነት በሚመለከት ንጉሡ እስኪጠይቀው ድረስ አልጠበቀም፤ ነገር ግን በእምነት አስቀድሞ ዐቀደ። እግዚአብሔር በሮችን እስከሚከፍትለት ድረስም ጠበቀ። ጥሩ የቤተ ክርስቲያን መሪ ሁልጊዜ የእግዚአብሔርን ሥራ እንዴት እንደሚሠራ የሚያቅድ፥ ሥራውን ለማሻሻል ምን መደረግ እንዳለበትና እንዴት ማደረግ እንዳለበት የሚወስን የተግባር ሰው ነው።

ቅጥሮቹን እንደገና ለመሥራት ምን እንደሚያስፈልግ ለማወቅ የፈረሱትን የኢየሩሳሌምን ቅጥሮች እየዞረ በመጎብኘቱ የነህምያን የአስተዳደር ብቃት እንመለከታለን። ከዚያም ሕዝቡን በሥራው ውስጥ እንዲሳተፉ ጠየቃቸው። አንድ ጥሩ መሪ ሁልጊዜ እንደሚያደርገው፥ ነህምያ ሥራውን ብቻውን ለመሥራት ጥረት አላደረገም፤ ነገር ግን በርካታ ሰዎች በሥራው እንዲሳተፉ የተቻለውን አደረገ። ነህምያ እያንዳንዱ ሰው አንድ የተወሰነ ኃላፊነት እንዲወስድ ሥራውን ከፋፈለ። በነህምያ ምዕራፍ 3 በቅጥሩ ሥራ ላይ የተሰማሩትን ሰዎች ስም ዝርዝር እናገኛለን። ሥራውን የሠሩት ሰዎች ምን ዓይነት እንደነበሩ መመልከት

መልካም ነው። የከተማ ሹማምንት፥ ነጋዴዎች፥ ድሆች፥ የሃይማኖት መሪዎች፥ ወንዶች፥ ሴቶች ወዘተ ነበሩ። ሥራውን አንሠራም ያሉ የቴቁሔ መኳንንት ብቻ ነበሩ (ነህ. 3፡5)። እነርሱ ትዕቢተኞች ነበሩ።

> 9ኛ ጥያቄ፥ ሀ) በቤተ ክርስቲያንህ ውስጥ መሠራት ካለባቸው ሥራዎች አንዱን ጥቀስ። ለ) ይህ ሥራ ከፍጻሜ እንዲደርስ መወሰድ ያለበት እርምጃ ምንድን ነው? ሐ) ይህ ሥራ በሚገባ ወደ ፍጻሜ እንዲደርስ ለተለያዩ ሰዎች ሥራዎችን ለማከፋፈል የሚቻለው እንዴት ነው? መ) በዚህ ሥራ ውስጥ ለመሳተፍ ትችል ዘንድ እግዚአብሔር በሩን እንዲከፍትልህ በጸሎት ጠይቀው።
> 10ኛ ጥያቄ፥ ኤፌ. 4፡11-13 አንብብ። ሀ) እነዚህ ቁጥሮች የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ለአባላት ማድረግ ስላለባቸው ነገሮች የሚናገሩት ምንድን ነው? ለ) ይህ በቤተ ክርስቲያንህ የተፈጸመው እንዴት ነው?

በነህምያ ምዕራፍ 4 ቅጥሩ መሠራት ከተጀመረ ወዲህ ስለ ተፈጠረው የመጀመሪያ ተቃውሞ እንመለከታለን። ማንኛውም ሰው ለእግዚአብሔር ለመሥራት ሲጀምርና የእግዚአብሔር ሕዝብም ለመሥራት ሲደራጁ፥ ሥራውን ለማቆም ተቃውሞ መፈጠር ይጀምራል። ይህ ተቃውሞ በቤተ ክርስቲያን ክልል ውስጥ በሚገኙ፥ ወይም ከቤተ ክርስቲያን ውጭ ከሚገኙ ሰዎች ሊመጣ ይችላል። መሪዎች ማረጋገጥ ያለባቸው ነገር የእግዚአብሔር ሥራ በተቃውሞ ውስጥ ሁሉ የሚቀጥል መሆኑን ነው። በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ስለተቃውሞ የሚከተሉትን ነገሮች ተመልከት፡-

1. በመጀመሪያ፥ ተቃውሞ የመጣው ፌዝ በተቀላቀለበት ንግግር መልክ ነበር። የአይሁድ ሕዝብ ጠላቶች የነበሩት ጦቢያና ሰንባላጥ ሌሎችም፥ ሕዝቡ በሚሠሩት ሥራ ላይ በመቀለድ ተስፋ ቆርጠው ሥራውን እንዲያቆሙ ለማድረግ ሞከሩ።

> 11ኛ ጥያቄ፥ ሀ) ሰዎች ሌሎች ስለ እነርሱ የሚሉትን ነገር በሚመለከት የሚገዳቸውና በሚቀልዱባቸውም ጊዜ ተስፋ ቆርጠው የጀመሩትን ሥራ የሚያቆሙት ለምንድን ነው? ለ) የዚህ ዓይነት ተቃውሞ በክርስቲያኖች ላይ ሲሠራ ያየኸውን ምሳሌ ስጥ።

2. ሁለተኛ፥ ተቃውሞው በሕዝቡ ላይ ችግር የማድረስ ወይም ጥቃት የማምጣት መልክ ያዘ። በእርግጥ ጠላቶቻቸው በዚህ ስፍራ

የማጥቃት ዛቻ ብቻ ነው ያሰሙት። ብዙ ጊዜ ለቤተ ክርስቲያን የሚከብደው በቀጥታ የሚመጣው ስደት ሳይሆን የጥቃትና የስደት ዛቻ ነው። ከኢየሩሳሌም በስተ ሰሜን ይገኝ የነበረው የሰማርያ ገዥ ሰንባላጥና ሌሎችም ግብረ አበሮቹ ሠራተኞቹን ባልጠበቁት ሰዓት ሊያጠቋቸው አስፈራሯቸው። የነህምያ መልስ ግን የሚያስገርም ነበር። በመጀመሪያ፥ ሊጠብቃቸው የሚችል እግዚአብሔር ብቻ እንደሆነ የተገነዘበበትን ጸሎት ነህምያ ጸለየ። ሁለተኛ፥ነህምያ ሕዝቡ ሊደርስ ከሚችል ጥቃት ለመከላከል በተጠንቀቅ እንዲቆሙ አደረገ። ሦስተኛ፥ ነህምያ የሕዝቡን ትኩረት ይጠብቀናል ወዳለው ወደ እግዚአብሔር መለሰ። አራተኛ፥ ሕዝቡ ሥራውን መቀጠላቸውን አረጋገጠ። ሕዝቡ ራሳቸውን ለመጠበቅ ብለው፥ ሥራቸውን ከማቆም ይልቅ ሥራውን እንዲቀጥሉ አደፋፈረ። ነህምያ ሰይጣን ሥራውን ለማስቆም እንደሚጥር ያውቅ ስለ ነበር፥ ሕዝቡ ሥራውን እንዲቀጥሉ አበረታታቸው።

እነዚህ ሁለት ዘዴዎች ሰይጣን የእግዚአብሔርን ሥራ ለማስቆም ብዙ ጊዜ የሚጠቀምባቸው መንገዶች ናቸው። ሁለቱም ዘዴዎች ያነጣጠሩት በእግዚአብሔር ሕዝብ እንጂ በመሪው ላይ አልነበረም። ነገ ደግሞ ሰይጣን ሥራውን ለማስቆም መሪውን ነህምያን እንዴት እንዳጠቃ እንመለከታለን።

| |
|---|
| 12ኛ ጥያቄ፥ ሀ) ቤተ ክርስቲያንህን ስለ መምራት ከእነዚህ ምዕራፎች የተማርካቸውን ትምህርቶች ዘርዝር። ለ) እነዚህ እውነቶች በሕይወትህ በተግባር ላይ የሚውሉባቸውን መንገዶች ዘርዝር። |

## 3ኛ ቀን:- ነህምያ 5-10

ማንኛውም የቤተ ክርስቲያን መሪ በተጋለጠ ስፍራ ላይ ያለ ነው። ሰይጣን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚገኘውን ማንኛውንም አባል የሚያጠቃ ቢሆንም፥ በተለይ በቀጥታ የሚያነጣጥረው በቤተ ክርስቲያን መሪዎች ላይ ነው። ጥቃቱን የሚያደርገው በሦስት ዋና ዋና ፈተናዎች ነው። አንደኛ፥ በትዕቢት ይፈትናቸዋል። ሰይጣን መሪዎችን በኃይላቸው፥ በችሎታቸውና በውጤታማነታቸው እንዲታበዩ ይፈትናቸዋል፤ በዚህ ዓይነት በእግዚአብሔር ላይ መታመናቸውን ስለሚያቆሙ ያለ ውጤት ይቀራሉ። በሁለተኛ ደረጃ የገንዘብ ፍቅር ያጠቃቸዋል። በዚህም ሕዝቡ በአደራ የሰጡአቸውን ገንዘብ ያለ አግባብ ይጠቀሙበታል። በሦስተኛ ደረጃ፥ መሪዎች በፍትወተ ሥጋ እንዲወድቁ ያደርጋል።

13ኛ ጥያቄ፥ መሪዎች በእነዚህ ሦስት ፈተናዎች ሲወድቁ ያየኸው እንዴት ነው?

ሰይጣን ሕዝቡን ተስፋ በማስቆረጥ፥ በስደትና በማስፈራራት ሊያሸንፋቸው ስላልቻለ፥ እስራኤላውያንን በሌላ መንገድ ማጥቃት ጀመረ። ጥቃቱንም በተለይ የሕዝቡ መሪ በነበረው በነህምያ ላይ አነጣጠረ።

14ኛ ጥያቄ፥ ነህምያ 5-10 አንብብ። ሀ) ሰይጣን በእስራኤላውያን መካከል የአሳብ መከፋፈል እንዲመጣ ያደረገው እንዴት ነበር? ለ) ሰይጣን ነህምያን ለማጥፋት የሞከረው እንዴት ነበር? ሐ) የኢየሩሳሌምን ቅጥር ለመሥራት የፈጀው ጊዜ ምን ያህል ነበር? መ) የእግዚአብሔርን ቃል የማንበብ ውጤትስ ምን ነበር?

የእግዚአብሔር ሕዝብ በዓላማቸው አንድ ሲሆኑ፥ ለእግዚአብሔር በመታዘዝ ሲኖሩና ለእርሱ ለመሥራትም ሲስማሙ ሰይጣን ይፈራል። አንድ ሰው ለብቻው ተነጥሎ መሥራቱ አያስፈራውም። ነገር ግን በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የታጠቁ ክርስቲያኖች በአንድነት ሆነው በቡድን የእግዚአሔርን ሥራ ከፍጻሜ ለማድረስ መሥራት ሲጀምሩ ይፈራል።

15ኛ ጥያቄ፥ ሀ) እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን እንድትሠራ የጠየቃትንና በግል ከሚሠሩ ይልቅ በቡድን ቢከናወኑ የበለጠ በጥሩ ሁኔታ ሊሠሩ የሚችሉ ነገሮችን ዘርዝር። ለ) በእግዚአብሔር ሥራ ውስጥ የሚሳተፉት የቤተ ክርስቲያናችን አባሎች ጥቂቶች የሆኑት ለምንድን ነው? ሐ) ብዙ አባላትን ማሳተፍ የምንችልባቸውን መንገዶች ዘርዝር (ኤፌ. 4፡11-13 ተመልከት)።

ነህምያ የኢየሩሳሌምን ቅጥር የሚሠሩ ሰዎችን ሲያደራጅ ተቃውሞ ተነሣበት። በቅድሚያ ተቃውሞው የመጣው የእግዚአብሔርን ሕዝብ ተስፋ ለማስቆረጥና ስደትን እንዲፈሩ በማድረግ ነበር። ይህ ዘዴ ውጤት ሳያስገኝ ሲቀር፥ ሰይጣን ሌሎች መንገዶችን ሞከረ።

በመጀመሪያ፥ ሰይጣን በአይሁድ መካከል መከፋፈልን ሊያመጣ ሞከረ (ነህ. 5)። በነህምያ ዘመን በእስራኤል ምድር ራብ ነበር። በተጨማሪ የፋርስ መንግሥት የሚጠይቀው ግብር ለሕዝቡ ሸክም ሆነ፤ ስለዚህ አንዳንድ ሰዎች ግብር ለመክፈልና የሚበሉትን ለማግኘት ሲሉ

መሬታቸውን ለሀብታሞች መሸጥ ነበረባቸው። ሌሎች ደግሞ ልጆቻቸውን ለባርነት አሳልፈው መስጠት ነበረባቸው። የሚያሳዝነው ነገር ሀብታም የሆኑ አይሁድ ይህን አጋጣሚ ለመጠቀም መሞከራቸው ነው። ገንዘባቸውን ከድሆች አይሁዳውያን ላይ በርካሽ ዋጋ መሬት ለመግዛት ተጠቀሙበት፤ እንዲሁም የገዛ ሕዝባቸውንም በባርነት ያዙ።

| |
|---|
| 16ኛ ጥያቄ፥ ሀ) ዛሬም በኢትዮጵያ ይህ እንዴት ሊፈጸም ይችላል? ለ) በእንደዚህ ዓይነት አስቸጋሪ ጊዜያት ሀብታም ክርስቲያኖች ማድረግ ያለባቸው ነገር ምንድን ነው? ሐ) መዝ. (35)፡ 10፤ (140)፡ 12 አንብብ። እግዚአብሔር ወደ ድሆች የሚመለከተው እንዴት ነው? |

ነህምያ የአይሁድን መሪዎች በተለይም ገንዘባቸውን ያለ አግባብ በመጠቀማቸውና ለወንድሞቻቸው ምሕረት ባለማሳየታቸው ሀብታሞቹን ገሠጻቸው። ይህ ጉዳይ መከፋፈልን ሊያመጣና የተጀመረው ሥራ እንዲቆም ሊያደርግ ይችል ነበር፤ ነገር ግን ነህምያ በፍጥነት ስብሰባ በመጥራቱና ለችግሩ መፍትሔ በመፈለጉ፥ የመከፋፈል ነገር ቀረና የቅጥሩ ሥራ ቀጠለ።

ሁለተኛ፥ ጦቢያና ሰንባላጥ ነህምያን ማጥቃት በመጀመር ሥራውን እንዲተው ለማድረግ ሞከሩ። እነዚህ ሰዎች መሪው ከሥራው ከተለየ ሥራው እንደሚቆም ያውቁ ነበር። መሪው በቅርቡ የማይከታተለው ከሆነ ወይም ብዙ ጊዜ በሥራው ላይ ከሌለ ሥራው ሊሠራ አይችልም። ጦቢያና ሰንባላጥ ለነህምያ መልካም የሚመስለውን አሳባቸውን አቀረቡለት። ስለ አሳባቸው ለመመካከርና ሰላምን በአንድነት ለማምጣት ስለሚቻልበት መንገድ በመሰባሰብ እንዲወያዩበት አሳብ አቀረቡለት። ኦኖ ከኢየሩሳሌም 30 ኪሎ ሜትር ርቆ በይሁዳ ጫፍ የሚገኝ ስፍራ ነበር። ነህምያ ግን ሥራውን ትቶ ወደዚያ መሄድ እምቢ አለ። እግዚአብሔር ቅጥሩን ይሠራ ዘንድ እንደጠራው ያውቅ ነበር፤ ስለዚህ ሥራው እስኪጠናቀቅ ድረስ በዚያ ሥራ ላይ መቆየትን መረጠ።

| |
|---|
| 17ኛ ጥያቄ፥ አንድ መሪ እግዚአብሔር ከሰጠው ሥራዎች እጅግ ሊርቅ የሚችልበትንና በዚህ ምክንያት ሥራው እየተዳከመ ሊሄድ የሚችልባቸውን መንገዶች ዘርዝር። |

ሦስተኛ፥ ጠላቶቻቸው በሕዝቡ ፊት የነህምያን መልካም ምስክርነት ለማበላሸት ሞከሩ። ለነህምያ ግልጽ ደብዳቤ ላኩለት። የደብዳቤው አሳብ

በንጉሡ ላይ ለማመፅ መምከርህ ተሰምቶአልና ይህንን ማረጋገጫ ወደ ንጉሡ ከመላካችን በፊት ናና እንማከር የሚል ነበር።

ለአንድ መሪ ምስክርነቱን መጠበቅ በጣም አስፈላጊ ነገር ነው። ሕዝቡ መሪውን የማያምነው ከሆነ፥ ወይም መጥፎ ምስክርነት ካለው ወዲያውኑ የቤተ ክርስቲያኒቱ አባላት እርሱን መከተል ያቆማሉ። የነህምያ ምላሽ ግን የሚያስፋፉት ወሬ ውሸት መሆኑን በሕዝቡ ሁሉ ፊት ማሳወቅ ነበር። ነህምያ በእነዚህ ሁሉ ተቃውሞዎች ውስጥ ሥራውን እንዲቀጥል ከእግዚአብሔር ዘንድ ብርታትን ጠየቀ። አንድን መሪ እጅግ ተስፋ ሊያስቆርጡት ከሚችሉት ነገሮች አንዱ፥ የሚፈጽመውን ተግባር ሌሎች ሰዎች በተሳሳተ መንገድ ሲረዱትና በሐሰት ሲወነጅሉት ነው። ሕዝቡ ሁሉ እውነትን ያውቁና ይረዱ ዘንድ የተፈጸሙትን ተግባራት ለመግለጥ መምከር አስፈላጊ ቢሆንም፥ መሪዎች በእንደዚህ ዓይነት የሐሰት ውንጀላ ሊረቱ አይገባም።

አራተኛ፥ ጠላቶች ነህምያ ስለ ሕይወቱ እንዲሠጋና ሕይወቱን ለማዳን ወደ ቤተ መቅደስ ሸሽቶ ካልተሸሸገ እንደሚገደል በመናገር አስፈራሩት። ይህም የነህምያን ምስክርነት ለማበላሸት የተደረገ ሙከራ ነበር። ነህምያ በጣም ቢፈራና ሕይወቱን ለማዳን ብሎ ቢደበቅ ኖሮ፥ ሕዝቡም ራሳቸውን መጠበቅ እንደሚያስፈልጋቸው አውቀው ሥራውን ሊያቆሙ ይችሉ ነበር። መሪዎች ከሌሎች የቤተ ክርስቲያን አባላት ሁሉ በተሻለና በበለጠ ሁኔታ በስደት ጊዜ ራሳቸውን ለመሸሸግና ለመከላከል መምከር ጨርሶ የለባቸውም። ስደትን ለመጋፈጥ፥ አስፈላጊ ከሆነ ለወንጌል ለመሞት እንኳ፥ የመጀመሪያዎቹ መሆን አለባቸው። መሪዎች ደፋሮች ሲሆኑና ተቃውሞን ሲጋፈጡ፥ ሕዝቡ ድፍረትን ያገኛሉ። መሪዎች ግን ሕይወታቸውን ለመጠበቅና ለመሸሸግ ከሞከሩ፥ ሕዝቡም ለወንጌል ከመኖር ይልቅ ሕይወታቸውን በመጠበቅ ላይ ያተኩራሉ።

ነህምያና ሕዝቡ በጠላቶቻቸው ሙከራ ለመሸነፍ ፈቃደኞች ባለመሆናቸውና በአንድ አሳብ አብረው ስለሠሩ የቅጥሩ ሥራ በ52 ቀናት ውስጥ ተጠናቀቀ።

---

18ኛ ጥያቄ፥ ስለ ቤተ ክርስቲያን አመራር ከነህምያ ሕይወትና ከቅጥሩ መሠራት ምን ለመማር እንችላለን?

---

**19ኛ ጥያቄ፥ በነህምያ 8-10 እንደተጻፈው በሕዝቡ መንፈሳዊ እንቅስቃሴ ውስጥ የእግዚአብሔር ቃል እውቀት ምን ድርሻ ነበረው?**

በምዕ. 7 ከምርኮ ወደ ኢየሩሳሌም የተመለሱ ሰዎች ስም ከተዘረዘረ በኋላ፥ በዕዝራና በነህምያ መሪነት በእስራኤል ስለ ተካሄደው መንፈሳዊ መነቃቃት (ተሐድሶ) እናነባለን። አንዳንድ ጊዜ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ቁሳቁሳዊ የሆኑ ሌሎች ነገሮችን መገንባት በጣም ቀላል ነው፤ ነገር ግን የሰዎችን መንፈሳዊ ሕይወት መገንባት በጣም አስቸጋሪ ነው። ነህ. 8-10 በእስራኤል የቅጥሩ ሥራ ከተፈጸመ በኋላ ስለተካሄደው መንፈሳዊ መነቃቃት ይገልጣል። ስለ መንፈሳዊ መነቃቃት የሚከተሉትን ነገሮች ተመልከት:-

1. መንፈሳዊ መነቃቃት የተጀመረው ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል ማንበብና ማጥናት በጀመሩበት ጊዜ ነው፤ (ነህ. 8:4-9)። ዕዝራ ለሕዝቡ የእግዚአብሔርን ቃል በሚያነብበት ጊዜ ሕዝቡ ለእግዚአብሔር ቃል እየታዘዙ እንዳልኖሩ ተገነዘበ። ብዙ ሰዎች የዕብራይስጥን ቋንቋ ማለትም መጽሐፍ ቅዱስ መጀመሪያ የተጻፈበትን ቋንቋ የማይረዱ ስለነበሩ፥ ነህምያ ሕዝቡ መልእክቱን እንዲረዱ ቅዱሳት መጻሕፍትን ወደ አራማይክ ቋንቋ በቃል ይተረጉምላቸው ነበር።

2. የእግዚአብሔር ቃል በእንባ የተረጋገጠ የግል ንስሐን ወደ ሰዎቹ ሕይወት አመጣ፤ (ነህ. 8:9)። ሕዝቡ የእግዚአብሔርን ቃል በሰሙ ጊዜ እያንዳንዱ ሰው በኃጢአት እንደሚኖር ተገነዘበ። ይህም ጥልቅ ኀዘን፥ ልቅሶና በእግዚአብሔር ፊት የግል ንስሐን አስከተለ።

3. የእግዚአብሔርን ቃል ማንበብና መረዳት ሕዝቡን ለእግዚአብሔር ወደ መታዘዝ መራቸው። ሕዝቡ ከ800 ዓመታት በፊት ከኢያሱ ዘመን ወዲህ ከተከበሩት በዓላት ሁሉ በላቀ ሁኔታ የዳስ በዓል አከበሩ።

4. የእግዚአብሔርን ቃል ማንበብ በሕዝብ ፊት በግልጽ መናዘዝንና ንስሐን አመጣ። ሕዝቡ በግል ስለ ኃጢአታቸው ማወቅ ብቻ ሳይሆን፥ የእግዚአብሔር ጉባኤ እንደ መሆናቸው መጠን ስለ ኃጢአታቸው በአንድነት በግልጽ ከተናዘዙ በኋላ ንስሐ ገቡ።

5. ሕዝቡ ለእግዚአብሔር ለመታዘዝ መወሰናቸውን ለማሳየት በመሪዎቻቸው በኩል ከእግዚአብሔር ጋር የነበራቸውን ቃል ኪዳን አደሱ። እንዲሁም ለሙሴ ሕግጋት እንደሚታዘዙ በጽሑፍ ለእግዚአብሔር ቃል ሰጡ። በተለይ ከአሕዛብ ጋር ላለመጋባት መወሰናቸውን፥ በሰንበት መግዛትና መሸጥ እንደሚያቆሙ፥ አሥራትና ምጽዋት በመስጠት የቤተ መቅደሱን አገልግሎትና የአምልኮ መሪዎች የሆኑትን ሌዋውያኑን እንደሚደግፉ ቃል መግባታቸው ተገልጿል።

20ኛ ጥያቄ፥ ሀ) መንፈሳዊ መነቃቃት (ተሐድሶ) በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ ስለሚያስከትለው ውጤት፥ በእስራኤል ሁሉ ላይ በኃይልና በፍጥነት ከተስፋፋው ከዚህ መንፈሳዊ መነቃቃት ምን እንማራለን? ለ) የዚህ ዓይነቱ መንፈሳዊ መነቃቃት ለቤተ ክርስቲያናችን ያስፈልጋል ብለህ ታስባለህን? ምክንያትህን ግለጥ። ሐ) የዚህ ዓይነቱ መንፈሳዊ መነቃቃት እንዲኖር የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሊያደርጉት የሚገባ ነው ብለህ የምታስበውን ነገር ተናገር። መ) የዚህ ዓይነት መንፈሳዊ መነቃቃት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ፈጥኖ እንዲመጣ ጸልይ።

## 4ኛ ቀን፡- ነህምያ 11-13

ሕዝቡ ስለ ኃጢአታቸው ሕዝባዊ ኑዛዜ በማድረጋቸውና ለእግዚአብሔር ሕግጋት ለመታዘዝ በግልጽ ቃል ኪዳን በመግባታቸው ብቻ ይህ ውሳኔ ለረጅም ጊዜ ይቆያል ማለት አይደለም። ቤተ ክርስቲያንን በሚመለከት የሚያሳዝነው ነገር እግዚአብሔርን ለመከተልና ለእርሱም ለመታዘዝ ብዙ ጊዜ በርካታ ቃል ኪዳን ብንገባም፥ ወዲያውኑ ባለመታዘዝ መመላለሳችን ወይም ቤተ ክርስቲያን ብዙውን ጊዜ መልሳ በኃጢአት ስለምትወድቅ፥ ሕዝቡ ለእግዚአብሔር የተስፋ ቃል ከመግባታቸው በፊት በነበሩበት ሁኔታ መኖር መጀመራቸው ነው።

21ኛ ጥያቄ፥ ሀ) በቤተ ክርስቲያንህ ውስጥ ሰዎች ለእግዚአብሔር የሚያደርጓቸውን አንዳንድ የተስፋ ቃሎች ዘርዝር። ለ) ከእነዚህ ተስፋዎች አብዛኞዎቹ ሳይፈጸሙ የሚቀሩት እንዴት ነው? ሐ) ለእግዚአብሔር የገባሃቸው አንዳንድ የተስፋ ቃሎችን ጥቀስ። መ) ከገባሃቸው የተስፋ ቃሎች መካከል የፈጸምሃቸው የትኞቹ ናቸው? ሠ) ያልፈጸምሃቸውስ የትኞቹ ናቸው? ረ) ልትፈጽማቸው ያልቻልክበት ምክንያት ምንድን ነው?

22ኛ ጥያቄ፥ ነህምያ 11-13 አንብብ። ሀ) ነህምያ ኢየሩሳሌምን እንደገና በሕዝብ ለመሙላት ምን አደረገ? ለ) የኢየሩሳሌም ቅጥር ለእግዚአብሔር አልፎ የተሰጠበትን ሥርዓት ግለጥ። ሐ) ነህምያ ከፋርስ ከተመለሰ በኋላ ወደ ኢየሩሳሌም ያመጣቸውን የተለያዩ መንፈሳዊ መነቃቃቶች ዘርዝር።

አሁን የኢየሩሳሌም ቅጥር ተሠርቶ ስላለቀ ነህምያ ሌሎች ሁለት ዓላማዎች ነበሩት። በመጀመሪያ፥ በኢየሩሳሌም የሚኖሩ በርካታ ሰዎችን መፈለግ ሲሆን፥ ይህም ከተማይቱ ባዶ እንዳትሆን ለማድረግ ነበር፤ ስለዚህ ነህምያ ሕዝቡ ዕጣ እንዲጥሉና ከየአሥሩ ሰው አንድ ሰው በኢየሩሳሌም እንዲኖር ወሰነ።

ሁለተኛ፥ ነህምያ የቅጥሩን መሠራት ምክንያት በማድረግ በሚኖረው መንፈሳዊ በዓል ላይ የሚያገለግሉ መዘምራንና የሃይማኖት መሪዎችን አደራጀ። ቅጥሩን ለመጨረስ የቻሉት በእግዚአብሔር እርዳታ መሆኑን ተገንዝበው ስለ ነበር ምርጫውን ለእግዚአብሔር አሳልፈው ሰጡት። ነህምያ ሕዝቡንና መዘምራኑን በሁለት ቡድን በማደራጀቱ ከቅጥሩ ጫፍ አንሥቶ በኢየሩሳሌም ቅጥር ዙሪያ እየዘመሩ እግዚአብሔርን ያመሰግኑ ነበር። ለሕዝቡ ሁሉ ይህ ታላቅ በዓል ነበር።

ነህምያ የይሁዳ ገዢ ሆኖ ለ12 ዓመታት ከሠራ በኋላ ወደ ፋርስ በመመለስ ከንጉሥ ጋር መሥራት ጀመረ። በዚያ የቆየው ስንት ጊዜ እንደነበር ባናውቅም፥ በመጨረሻ ወደ ኢየሩሳሌም ተመልሶ እንዲኖር ተፈቀደለት። የሕዝቡ መንፈሳዊ ሕይወት በከፍተኛ ሁኔታ ስለቀነሰና በኃጢአት ስለ ወደቁ፥ ነህምያ ለተወሰነ ጊዜ ከእነርሱ ርቆ እንደ ነበር በግልጥ ያሳየናል።

ነህምያ ወደ ኢየሩሳሌም በተመለሰ ጊዜ ሕዝቡ በኃጢአት ወድቀው አገኛቸው። ነህምያ በፈሪሀ እግዚአብሔር ላይ የተመሠረተ የኃጢአት ጥላቻ ነበረው። ሕዝቡ በቅድስና መኖር እንዳለባቸው የወሰነ ሰው ነበር፤ ስለዚህ ወዲያውኑ እርምጃ ወሰደ። በመጀመሪያ፥ እንግዶች (ባዕዳን) የሆኑ ሰዎች በሙሉ ወደ ቤተ መቅደስ እንዳይመጡ አገለላቸው (ነህ. 13፡1-3)።

ሁለተኛ፥ የእግዚአብሔር ሕዝብ ጠላት የነበረውንና ካህኑ ኤልያሴብ በቤተ መቅደሱ አጠገብ አንደኛው ክፍል ውስጥ እንዲኖር የፈቀደለትን

ጦቢያን አባረረ። ነህምያ የጦቢያ ክፋት ሕዝቡን እንዲበክል አልፈለገም፤ ስለዚህ የጦቢያ የሆኑትን ንብረቶች ሁሉ አውጥቶ በመንገድ ላይ በተናቸው።

ሦስተኛ፥ ነህምያ ሕዝቡ አሥራት ለሌዋውያን መስጠት ማቆማቸውና በዚህም ምክንያት ሌዋውያን የአምልኮ ፕሮግራም የመምራት አገልግሎታቸውን አቋርጠው፥ ሥራ ፍለጋ በይሁዳ ሁሉ ለመበተን እንደተገደዱ ተገነዘበ። ነህምያ ሕዝቡ አሥራት እንዲሰጡና ሌዋውያንም አምልኮ ወደ መምራት አገልግሎታቸው እንዲመለሱ አደረገ።

አራተኛ፥ ነህምያ ሕዝቡ አናደርግም ብለው ቃል ከገቡት ነገሮች መካከል፥ በሰንበት የመሸጥና የመግዛት ነገር ሲለማመዱ ተመለከተ፤ ስለዚህ የከተማይቱ በሮች ዓርብ ማምሻውን ተዘግተው ሰንበት (ቅዳሜ) ካለቀ በኋላ ብቻ እንዲከፈቱ አዘዘ። ነጋዴዎቹንም ከእንግዲህ በሰንበት ቀን ቢመጡ እንደሚቀጡ በመንገር አስጠነቀቃቸው። (ማስታወሻ፡- ለአይሁድ ሰንበት የሚጀምረው ዓርብ ማምሻውን ከ12 ሰዓት በኋላ ሲሆን፥ የሚያበቃው ቅዳሜ ከ12 ሰዓት በኋላ ወደ ማታ ነው።)

አምስተኛ፥ ሕዝቡ ከአሕዛብ ጋር መጋባት ጀምረው ነበር። እንደምታስታውሰው፥ ይህንን አናደርግም ብለው ቃል ከገቡ ብዙ ዓመታት አላለፉም ነበር (ዕዝራ 10፡2፥ 10-14)። ነህምያ በታላቅ ቁጣ ሕዝቡን ተራገመ፤ ጠጉራቸውን ነጨ፤ ባዕዳን ሚስቶቻቸውንም እንዲያባርሩ አደረገ።

| |
|---|
| 23ኛ ጥያቄ፥ ሀ) ዛሬ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የምናደርጋቸውንና ከእነርሱ መንጻት የሚገባንን ተመሳሳይ ነገሮች ዘርዝር። ለ) የነህምያን ምሳሌነት በመከተል ቤተ ክርስቲያንህን እንዴት ልታነጻ ትችላለህ? ሐ) ከነህምያ ሕይወትና ለኃጢአት ከነበረው ጥላቻ የምንማረው ምንድን ነው? |

## የመጽሐፈ ነህምያ ዋና ዋና ትምህርቶች

ከመጽሐፈ ነህምያ ልንማራቸው የምንችለው በርካታ ነገሮች ቢኖሩም፥ ሦስቱ ግን በጣም አስፈላጊና ከሌሎቹ የላቁ ናቸው።

1. አንዲት ቤተ ክርስቲያን ልትገነባና ጤነኛ ልትሆን ከተፈለገ ተገቢ የሆኑ መሪዎች ያስፈልጓታል። እነዚህ መሪዎች ከሁሉ በፊት ተገቢ

መንፈሳዊ መመዘኛዎችን ማሟላት አለባቸው። እግዚአብሔርን መውደድ አለባቸው፤ ለእግዚአብሔር ሕግ ሊገዳቸው ያስፈልጋል፤ ኃጢአትን ሊጠሉና የጸሎት ሰዎች ሊሆኑም ይገባል።

2. መሪዎች እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያን የሰጣትን ሥራ እንዲሠሩና ውጤታማ በሆነ መንገድ እንዲፈጽሙ ለማድረግ በሚያስችል ሁኔታ፥ የእግዚአብሔርን ሕዝብ ሊያደራጁትና ሊያቅዱ ይገባል። ቤተ ክርስቲያን በሚገባ መደራጀት አለባት። እንዲሁም እያንዳንዱ የቤተ ክርስቲያን አባል የተሰጠውን መንፈሳዊ ስጦታ አካሉን ለማነጽ እንዲያውለው በተናጠል የተለየ ኃላፊነት ሊሰጠው ይገባል።

3. ቤተ ክርስቲያን ለእግዚአብሔር ልታደርግ የገባችውን ግዴታ ዘወትር ልታድስ ያስፈልጋታል። አይሁድ ኃጢአታቸውን በግልጥ እንደተናዘዙ እኛም ኃጢአታችንን በመናዘዝ ራሳችንን በግልና በቡድን ማንጻት አለብን። ለእግዚአብሔርም በመታዘዝ ግልጽ ቃል ኪዳን ማድረግ አለብን። ወደ ኃጢአት ላለመመለስም ጥንቃቄ ማድረግ አለብን። ለእግዚአብሔር የገባነውንም ግዴታ ያለማቋረጥ ልናድሰው ያስፈልጋል። የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በተለይ የሕዝባቸውን የሕይወት ንጽሕና ለመጠበቅ ጠንቃቆች መሆን አለባቸው።

| |
|---|
| 24ኛ ጥያቄ፥ ሀ) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እነዚህን ሦስት እውነቶች ማወቅና ከሕይወታቸው ጋር ማዛመድ የሚያስፈልጋቸው ለምንድን ነው? ለ) በቤተ ክርስቲያንህ የእነዚህን ሦስት እውነቶች መኖር ወይም አለመኖር የምታየው እንዴት ነው? ሐ) በአሁኑ ጊዜ በቤተ ክርስቲያንህ ከእነዚህ ሦስት እውነቶች በጣም አስፈላጊ የሆነውና የሚፈለገው የትኛው ነው? መ) ይህን ያልክበት ምክንያት ምንድን ነው? |

## 5ኛ ቀን፡-

የዚህን ሳምንት ትምህርት ከልስና ለሳምንታዊ ስብሰባ ዝግጅት ይረዳህ ዘንድ የውይይት ጥያቄዎቹን ተመልከት።

## ሳምንታዊ ስብሰባ

1. የሳምንቱ የአምልኮ ጊዜ

2. ጸሎት

3. የትምህርቱ ክለሳ

4. ውይይት

1. ሀ) ነህምያን እግዚአብሔርን የሚፈራ መሪ ያደረጉትን መንፈሳዊ ብቃቶች ግለጥ። ለ) እነዚህ ብቃቶች አስፈላጊ የሆኑት ለምንድን ነው? ሐ) አብዛኛዎቹ የቤተ ክርስቲያንህ መሪዎች ይህ ብቃት አላቸውን? መልስህን አብራራ። መ) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እነዚህን ብቃቶች በሕይወታቸው የሚያጎለብቱት እንዴት ነው?
2. ሀ) ከነህምያ የምንማረው የመልካም አስተዳደር መመሪያ ምንድን ነው? ለ) ለመልካም የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ይህ የሚያስፈልገው ለምንድን ነው? ሐ) እነዚህን መመሪያዎች ለቤተ ክርስቲያናችን መሪዎች እንዴት እናስተምራቸዋለን?
3. ሀ) ሰይጣን የኢየሩሳሌምን ቅጥር ሥራ ለማስቆም የሞከረባቸውን የተለያዩ መንገዶች ዘርዝር። ለ) በሠራተኞቹ ላይ ለማድረግ የሞከረው ነገር ምን ነበር? ሐ) በነህምያ ላይ ለማድረግ የሞከረው ነገር ምን ነበር? መ) ዛሬም ቢሆን ሰይጣን በቤተ ክርስቲያን ይህንኑ ተመሳሳይ ዘዴ የሚጠቀመው እንዴት ነው? መልስህን አብራራ።
4. ሀ) በዕዝራ መሪነት የተደረገውን መንፈሳዊ መነቃቃት አብራራ። እንዴት ተጀመረ? የመኖሩስ ማረጋገጫ ምን ነበር? ለ) የእግዚአብሔር ቃል እውቀት በመንፈሳዊ መነቃቃት ውስጥ የነበረው ሚና ምንድን ነው? ሐ) መንፈሳዊ መነቃቃት ዛሬም ያስፈልጋልን? መልስህን አብራራ። መ) በቤተ ክርስቲያንህ ውስጥ መንፈሳዊ መነቃቃት እንዲጀመር ልታደርግ የምትችላቸውን ነገሮች ዘርዝር። ሠ) በቤተ ክርስቲያንህ ውስጥ መንፈሳዊ መነቃቃት እንዲጀመር የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሊያደርጉት የሚችሉት ነገር ምንድን ነው?
5. ሀ) ነህምያ ወደ ፋርስ በሄደ ጊዜ የሕዝቡ መንፈሳዊ ሕይወት ምን ሆነ? ለ) ይህ የሆነው ለምን ይመስልሃል? ሐ) ዛሬም በቤተ ክርስቲያናችን ውስጥ ተመሳሳይ ነገር የሚፈጸመው እንዴት ነው? መ) ነህምያ በሕዝቡ ሕይወት ኃጢአትን ሲያይ ምን ያደርግ ነበር? ሠ) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ስለ ኃጢአት ያላቸው ምላሽ እንደ ነህምያ የመሆኑ አስፈላጊነት ምንድን ነው? ረ) ቤተ ክርስቲያንህ ለእግዚአብሔር ያላትን መንፈሳዊ ፍቅር ታድስ ዘንድ ልታደርጋቸው የሚገቡ ነገሮች ምንድን ናቸው?

5. ጸሎት

# ትምህርት 20

## 1ኛ ቀን:- የመጽሐፈ አስቴር መግቢያ

> 1ኛ ጥያቄ፥ ባለፉት 20 ዓመታት ስለ ተፈጸመው የኢትዮጵያ ታሪክ አስብ። መንግሥትን፥ ቤተ ክርስቲያንንና የግል ሕይወትህን በመቆጣጠር ረገድ የእግዚአብሔርን ሉዓላዊነት እንዴት አየህ? ምሳሌዎችን ስጥ።

መጽሐፈ አስቴር እግዚአብሔር በማይታይ መንገድ በሉዓላዊነቱ ሕዝቡን እንደሚጠብቅ የሚያሳይ መጽሐፍ ነው። የእግዚአብሔር ሰዎች የእግዚአብሔር እጅ በሥራ ላይ ሆኖ ባያዩም እንኳ፥ እግዚአብሔር በብዙ በማይታዩ መንገዶች ለራሳቸው ጥቅምና ለመንግሥቱ መስፋፋት በመሥራት ላይ ነው። ክርስቲያን ያልሆነ ሰው እንደ ዕድል የሚያየውን ነገር እኛ ክርስቲያኖች ዕድል እንዳይደለ እናውቃለን። ይልቁንም እግዚአብሔርን የማያምኑ ሰዎችንም ሆነ እጅግ ጥቃቅን የምንላቸውን ድርጊቶች ሁሉ ፈቃዱን ለማድረግ ይጠቀምባቸዋል።

መጽሐፈ አስቴር በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ልዩ መጻሕፍት ከምንላቸው አንዱ ነው። ምሁራን በብሉይ ኪዳን ውስጥ ከሚገኙ እጅግ በጣም ጥሩ ከሚባሉ ሥነ ጽሑፎች አንዱ ነው ይላሉ። ሆኖም ግን በቀረው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ውስጥ ወይም በማንኛውም ጥንታዊ ጽሑፍ ተመሳሳይ የሆነ ሥነ - ጽሑፍ አለመገኘቱ በጣም ያልተለመደ ነገር ነው። መጽሐፈ አስቴር እጅግ አስደናቂ የሆነ ታሪክ ቢሆንም፥ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ለምን እንደተካተተ ምሁራን ብዙ ጊዜ በመደነቅ ይጠይቃሉ። በመጽሐፈ አስቴር ውስጥ የእግዚአብሔር ስምም ሆነ ለእግዚአብሔር የሚቀርብ አምልኮ ወዘተ ጨርሶ አልተጠቀሰም፤ ስለዚህ መጽሐፉን ለማይረዱት ሰዎች ምንም ዓይነት ሃይማኖታዊ ጠቀሜታ አይታያቸውም። ሌሎች ምሁራን ደግሞ መጽሐፉ ስለ ሌሎች ዓለማዊ ታሪኮች የሚጠቅሰው አንዳችም ነገር ስለሌለ የታሪኩን እውነተኛነት ይጠራጠራሉ። ስለሆነም ይህ ነገር አጭር ልብ ወለድ ወይም ሰዎችን ለማስተማር የተሰጠ ምሳሌ ነው ይላሉ፤ ነገር ግን መጽሐፈ አስቴርን ከማንበብ የምንረዳው ነገር ጸሐፊው ታሪኩን በእውነተኛነቱ እንደተመለከተው ነው (ለምሳሌ:- አስቴር 10:2)።

## የመጽሐፈ አስቴር ርእስ

መጽሐፈ አስቴር ከዋና ዋናዎቹ ባሕርያት አንዷ በሆነችው በአስቴር ስም የተሰየመ ነው። አስቴር አባትና እናቷ የሞቱባት በኋላም የፋርስ ንግሥት የሆነችና የአይሁድን ሕዝብ ሁሉ ያዳነች ሴት ናት። ሁለት የመጽሐፍ ቅዱስ መጻሕፍት በሴቶች ስም ተሰይመዋል፤ አንደኛው መጽሐፈ ሩት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ መጽሐፈ አስቴር ነው። መጽሐፈ አስቴር ወደ ግሪክ ቋንቋ በተተረጎመበት ጊዜ ሰዎች የተለያዩ ነገሮችን ያክሉበት ጀመር። እነዚህ ታሪኮች መርዶክዮስ ስላየው ሕልም፥ መርዶክዮስ ለአርጤክስስ ስለጻፋቸው የተለያዩ ደብዳቤዎችና አስቴርና መርዶክዮስ ስላደረጉዋቸው የተለያዩ ጸሎቶች የሚናገሩ ናቸው። እነዚህ ታሪኮች በካቶሊክና በኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት መጽሐፍ ቅዱሶች ውስጥ የታከሉ ቢሆኑም፥ በመጀመሪያው መጽሐፈ አስቴር ውስጥ ያልነበሩ ታሪኮች ወይም ጥቅሶች ናቸው።

## የመጽሐፈ አስቴር ጸሐፊ

መጽሐፈ አስቴርን ማን እንደጻፈው መጽሐፉ ራሱ የሚናገረው ነገር የለም። በአይሁድ አፈ ታሪክ መሠረት መጽሐፈ አስቴር የተጻፈው በመርዶክዮስ ነው ቢባልም ይህን በሚመለከት አንዳችም መረጃ የለንም። ሆኖም መጽሐፉን በምናጠናበት ጊዜ በግልጥ የምንረዳው ነገር ጸሐፊው አንድ አይሁዳዊ፥ የተማረና የሥነ -ጽሑፍ ችሎታ ያለው፥ የፋርስ ቤተ መንግሥትን መዛግብትና የቤተ መንግሥት ባህልንም ሊያገኝ የሚችል ሰው እንደ ነበረ ነው (አስቴር 10፡2)። እንዲሁም ጸሐፊው በአስቴርና በመርዶክዮስ መካከል የተደረጉትን ውይይቶች ያውቅ ነበር። መርዶክዮስ እነዚህን ሁሉ መመዘኛዎች ስለሚያሟላ መጽሐፉን እርሱ ጽፎት ሊሆን ይችላል።

## መጽሐፈ አስቴር የተጻፈበት ጊዜ

ጸሐፊው ማን እንደሆን ስለማይታወቅ፥ መቼ እንደተጻፈም አናውቅም። የምናውቀው ነገር ቢኖር ከ200 ዓ.ዓ. በፊት መጻፉን ነው። መጽሐፉ ከ400-350 ዓ.ዓ. ባለው ጊዜ ሳይጻፍ አልቀረም። ከዚያ በኋላ የፉሪም በዓል የአይሁድ ብሔራዊ በዓል ሆነ።

## የመጽሐፉ ታሪካዊ ሥረ መሠረት

ቀደም ሲል እንደተመለከትነው፥ የአስቴር ታሪክ የተፈጸመው በመጽሐፈ ዕዝራ አጋማሽ ላይ ነው። የተፈጸመውም በዕዝራ 6 ና በዕዝራ 7 መካከል ነው። እንደ መጽሐፈ ዕዝራና ነህምያ የመጽሐፈ አስቴር ታሪክ የተፈጸመው በይሁዳ ሳይሆን በፋርስ ምድር ነው። እግዚአብሔር በሥራ ላይ የነበረው በይሁዳ ብቻ ሳይሆን፥ በምርኮ በነበሩ አይሁድ መካከልም ነበር።

የመጽሐፈ አስቴር ታሪክ በተፈጸመበት ጊዜ ንጉሥ የነበረው ሰው በመጽሐፍ ቅዱስ አሕሻዊሮስ በመባል የሚታወቀው ቀዳማዊ አርጤክስስ ነበር። የዚህ ሰው አባት ታላቅ ጦረኛ የነበረውና የፋርስን መንግሥት ክልል በጣም በከፍተኛ ሁኔታ ያስፋፋው ታላቁ ዳርዮስ ነበር።

አርጤክስስ አዳዲስ ምድርን በወረራ ከመያዝ ይልቅ፥ ትኩረቱ ዋና ከተማ የነበረችውን ሱሳንና ሌሎች ዋና ዋና ከተሞችን በመሥራት ላይ ነበር። አማካሪዎቹ ግን ግዛቱን እስከ አውሮጳ ድረስ ለማስፋፋት ይችል ዘንድ ግሪክን እንዲወጋ መከሩት፤ ነገር ግን በዚህ ጦርነት አልተሳካለትም። ግሪኮች በጦርነቱ አሸንፉትና አብዛኛውን ጦሩንና የባሕር ኃይሉን ደመሰሱበት።

የዓለም ታሪክ ስለ አርጤክስስ የሚናገረው በርካታ ነገር ቢኖርም አስቴርን ግን የሚጠቅስ ታሪክ የለም። አስጢን የምትባል አንዲት ሚስት እንደ ነበረችውና በኋላም እርሷን በማስወገድ አስቴርን በንግሥትነት እንዳገባ የሚናገር ታሪክም የለም። የዓለም ታሪክ የሚናገረው አሚስቴሪስ ስለተባለች አንዲት ንግሥት ብቻ ነው። ይህ ስም የአስጢን ወይም የአስቴር ሌላ ስም እንደሆነም የምናውቀው ነገር የለም።

የአስቴር ታሪክ የተፈጸመው ንጉሡ አርጤክስስ ከግሪኮች ጋር ለመዋጋት ወደ ጦር ሜዳ ከመሄዱ በፊት ሳይሆን አይቀርም። ብዙ ምሁራን የግብዣው ዓላማ በግሪክ ላይ ስለሚደረገው ወረራ ለመነጋገር ነበር ብለው ያስባሉ። አስጢን እንደተወገደች አስቴር ወዲያውኑ ንግሥት ያልሆነችበት ምክንያትም ይህ ሊሆን ይችላል። አስጢን የተወገደችው አርጤክስስ በነገሠ በሦስተኛው ዓመት ሲሆን፥ አስቴር ንግሥት የሆነችው ደግሞ በ7ኛው ዓመት ነው። በመካከሉ የ4 ዓመታት ልዩነት አለ ማለት

ነው። ይህም ማለት የመጽሐፈ አስቴር ታሪክ የተፈጸመው ከ483-471 ዓ.ዓ. ነበር ማለት ነው።

## የመጽሐፈ አስቴር ዓላማዎች

1. መጽሐፈ አስቴር የእግዚአብሔርን ታላቅነትና በዓለም ሕዝብ ሁሉ ላይ ያለውን የበላይ ተቆጣጣሪነት ለአይሁድ ለማስተማር የተጻፈ ታሪክ ነው። ጸሐፊው አይሁድን ለማስተማር የፈለገው ነገር፥ ሕዝቡ የሚኖሩት በተስፋይቱ ምድር ሳይሆን በምርኮ ምድር ቢሆንም እንኳ፥ እግዚአብሔር ለቃል ኪዳኑ አሁንም ቢሆን ታማኝ መሆኑን ነው፤ ነገር ግን ይህንን እውነት ለማስተማር ጸሐፊው የተጠቀመው የመጽሐፍ ቅዱስን የተለመደ መንገድ አይደለም። በብሉይ ኪዳን ውስጥ በአጠቃላይ ግልጽ ተአምራትን በማድረግ እግዚአብሔር ለሕዝቡ ያስተማራቸውን እውነቶች እናያለን። እስራኤላውያን ቀይ ባሕርን የተሻገሩበትንና ፈረዖን ከነሠራዊቱ የሰጠመበትን፥ ሕዝቅያስ ባደረገው ጦርነት እግዚአብሔር 180000 የአሦር ወታደሮችን የደመሰሰበትን ታሪክ እናነባለን። በመጽሐፈ አስቴር ውስጥ ግን የእግዚአብሔርን የበላይ ተቆጣጣሪነት ለማመልከት ጸሐፊው ልዩ የሆነ የአጻጻፍ ስልት ሲጠቀም እናያለን። ጸሐፊው ሆን ብሎ የእግዚአብሔርን ስም አልጠቀሰም። ይልቁንም እግዚአብሔር የአይሁድን ሕዝብ ከጥፋት ለማዳን በጣም ጥቃቅንና ኢምንት ናቸው የሚባሉ ድርጊቶችን እንዴት እንደ ተጠቀመባቸው በተደጋጋሚ ትኩረት ሰጥቶት እናያለን።

ለምሳሌ:- አስቴር ንግሥት ሆና ለመመረጥና ሕዝቧን ከጥፋት ለማዳን ቻለች። መርዶክዮስ እንደአጋጣሚ በንጉሡ ላይ የተደረገውን ሴራ ለመስማትና ንጉሡን ለማስጠንቀቅ ከሚችልበት ሁኔታ ላይ ደረሰ። ንጉሡ አንድ ለሊት እንቅልፍ ርቆት ስለ መርዶክዮስ እንዲያነብብና የሚያሸልመው ድርጊት እንዲጋለጥ ሆኖ መርዶክዮስ ተሸለመ። አንድ የማያምን ሰው ይህንን ተመልክቶ አይሁድ ከጥፋት ለመዳን ዕድለኞች ሆኑ ቢልም፥ እንደ ጸሐፊው አስተሳሰብ ዕድል የሚባል ነገር የለም። ይልቁንም እግዚአብሔር ጥቃቅን ድርጊቶችን እንኳ በመቆጣጠር ለሕዝቡ ያለውን ዕቅድ ለመፈጸም ይጠቀምበታል።

2ኛ ጥያቄ፥ ሀ) ሰዎች የሆኑት በዕድል ነው ብለው የሚያስቧቸውን አንዳንድ ነገሮች ዘርዝር። ለ) እነዚህ ነገሮች የተፈጸሙት በዕድል

እንደሆን የሚያስቡ ክርስቲያኖች አሉን? አብራራ። ሐ) ለዓለም ዕድል ናቸው ተብለው የሚታሰቡ ነገሮችን የጎለመሱ ክርስቲያኖች የሚመለከቱአቸው እንዴት ነው?

ብዙ ጊዜ የእግዚአብሔር አሠራር በማያምኑ ሰዎች ወይም በሥጋዊ ክርስቲያኖች ዘንድ የማይታዩና ለመረዳት የሚያስቸግሩ ቢሆኑም እንኳ በክርስቲያኖች ዘንድ ግን ግንዛቤ ውስጥ የሚገቡ ናቸው። ለእኛ በሚያደርገው ነገር ሁሉ የእግዚአብሔርን እጅ በመሥራት ላይ መሆኑን ለማየት መቻል አለብን። የብሉይ ኪዳን ተአምራት በማይፈጸሙበት ጊዜና አይሁድ በዓለም ሁሉ ተሠራጭተው በፋርስ መንግሥት ቁጥጥር ሥር በነበሩበት ጊዜ ሁሉ፥ እግዚአብሔር የጥንቱን ዓይነት ተአምራት ባይሠራም አይሁዳውያንን ግን አሁንም እንደደገፋቸው ነበር። እግዚአብሔር ነገሮችን ሁሉ በቁጥጥር ሥር በማድረግ ሕዝቡን ይጠብቅ ነበር (ለምሳሌ፡- ዘካ. 1፡21)። እግዚአብሔር የክፉዎችን ዕቅድ ፍሬ ቢስ ለማድረግ ይሠራ ነበር (መዝ. (140)፤ መጽሐፈ ምሳሌ 10፡24-25 አንብብ)።

3ኛ ጥያቄ፥ የአሁኑ ዘመን ክርስቲያኖችስ ይህንን እውነት መረዳት ያለባቸው ለምንድን ነው?

2. አይሁድ ፉሪም የሚባል ዓመታዊ በዓል ነበራቸው። ይህ ቀን ለአይሁድ እጅግ ከተወደዱ በዓላት አንዱ ሆነ። መጽሐፈ አስቴርን በማንበብ፥ በመብላትና በመጠጣት፥ ደግሞም ስጦታን በመለዋወጥ ያከብሩታል። የመጽሐፈ አስቴር ጸሐፊ ለአይሁድ የፉሪምን በዓል አጀማመር ለመግለጥ ፈልጓል።

3. እኛ በቀላሉ የምንገነዘበው ባይሆንም፥ ጸሐፊው በአማሌቃውያንና በአይሁድ መካከል ስለሚደረገው የማያቋርጥ ጦርነት መናገሩ እንደሆን አይሁድ ይገነዘቡት ነበር። ከብሉይ ኪዳን ታሪክ እንደምንመለከተው፥ እስራኤላውያን ከግብፅ ከወጡ በኋላ የመጀመሪያዎቹ ጠላቶቻቸው አማሌቃውያን ነበሩ (ዘጸ. 17፡8-16 ተመልከት)፤ ስለዚህ እግዚአብሔር አማሌቃውያንን ሙሉ በሙሉ እንዲያጠፏቸው አይሁድን አዘዘ፤ (ዘዳ. 25፡17-19)። አይሁድ ግን ይህንን በማድረግ ለእግዚአብሔር ስላልታዘዙ፥ በብሉይ ኪዳን ታሪክ በአጠቃላይ በአማሌቃውያንና በአይሁድ መካከል የተደረገውን

የማያቋርጥ ጦርነት እንመለከታለን (ለምሳሌ. 1ኛ ሳሙ. 15፤ 1ኛ ዜና 4፡43)። በእስራኤላውያን አእምሮ አማሌቃውያን እነርሱንና እግዚአብሔርን ለሚቃወሙ የእግዚአብሔር ሕዝብ ጠላቶች ሁሉ ተምሳሌት ናቸው። ሐማ ከአማሌቃውያን ወገን እንደመጣ ተገልጦአል (መጽሐፈ አስቴር 3፡1-6፤ 9፡5-10)። የሐማ ዕቅድ እንደ ከሸፈና እርሱም እንደተደመሰሰ በማሳየት፥ የእግዚአብሔር ሕዝብ ጠላቶች የሆኑ ሁሉ አንድ ቀን በተመሳሳይ ሁኔታ እንደሚጠፉ ጸሐፊው አስተምሮአል።

4ኛ ጥያቄ፥ ይህ ትምህርት ዛሬ እኛን የሚያበረታታን እንዴት ነው?

## የመጽሐፈ አስቴር አስተዋጽኦ

1. አስጢን ከንግሥትነትዋ ተሻረች (1)
2. አስቴር ንግሥት ሆነች (2፡1-18)
3. መርዶክዮስ በንጉሡ ላይ የተደረገውን ሴራ አጋለጠ (2፡19-23)
4. ሐማ አይሁድን ለማጥፋት ያወጣው ዕቅድ (3)
5. መርዶክዮስ የአይሁድን ሕዝብ እንድትረዳ አስቴርን አሳመናት (4)
6. የአስቴር የመጀመሪያ ግብዣ (5፡1-8)
7. መርዶክዮስ ተሸለመ (5፡9-6፡14)
8. የአስቴር ሁለተኛ ግብዣና የሐማ መሰቀል (7)
9. የአይሁድ ሕዝብ ሕይወት መትረፍና የመርዶክዮስ መሾም (8-10)

5ኛ ጥያቄ፥ ስለ አስቴር ከመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት አንብብ፤ አስፈላጊ የሆኑ ትምህርቶችንም ዘርዝር።

## 2ኛ ቀን፡- አስቴር 1-6

ብዙ ጊዜ እግዚአብሔር በዓለም ላይ ለሕዝቡ ያለውን ዕቅድ ለመፈጸም የሚሠራው እንዴት ነው? ብዙ ጊዜ ቀይ ባሕርን እንደመክፈል ያሉ ታላላቅ ተአምራትን ይሠራልን? ብዙ ጊዜ እኛ ክርስቲያኖች

እግዚአብሔር ይህንን የመሳሰሉ ታላላቅ ተአምራትን እንዲሠራ እንፈልጋለን። በመሆኑም በልሳን መናገርና ፈውስን ወደ መሳሰሉ አስደናቂ ተግባራት እንሳባለን። አዎን እግዚአብሔር ዛሬም ቢሆን በመካከላችን በታላላቅ መንገዶች ይሠራል፤ ነገር ግን ለአስደናቂ ነገሮች ብቻ ትኩረት በመስጠታችን፥ እግዚአብሔር በተለመዱ ጥቃቅን ነገሮችም ውስጥ እንደሚሠራ እንዘነጋለን። እግዚአብሔር የመንግሥት ከፍተኛ ባለሥልጣናትን ውሳኔ በመቆጣጠር ይሠራል። እግዚአብሔር ለወንጌል ሥራ ከፍተኛ ጥቅም ሊሰጡ በሚችሉበት ትክክለኛ ስፍራ ልጆቹን በማስቀመጥ ይሠራል። እግዚአብሔር ልናስባቸው በማንችል በሕይወታችን በሚፈጸሙ ጥቃቅን ነገሮች ውስጥ እንኳ ሲሠራ እናገኘዋለን። ለምሳሌ፥ በየቀኑ ሊጎበኙን የሚመጡ ሰዎችን የሚቆጣጠር እግዚአብሔር ነው። በመንገድም ሆነ በቢሮ የሚመጡትንና የሚገናኙንን ሰዎች የሚቆጣጠር እግዚአብሔር ነው። ክርስቲያኖች እንደመሆናችን በአስደናቂ ነገሮች ላይ ብቻ የምናተኩር መሆን የለብንም፤ ነገር ግን እግዚአብሔር በሚያደርጋቸው ዕለታዊ የተለመዱ ነገሮችም ላይ ማተኮር ያስፈልገናል። በሕይወታችን የሚፈጸሙ ነገሮች በሙሉ በእግዚአብሔር መሪነት የሚከናወኑ ናቸው። እነዚህ ለእኛ በጣም ጥቃቅን የሚመስሉ ነገሮች ልናስተውላቸው እስከማንችል ድረስ በጣም አስፈላጊ ነገሮች ሊሆኑ ይችላሉ።

> 6ኛ ጥያቄ፥ ሀ) ሰዎች ብዙ ጊዜ የሚያተኩሩባቸውን የእግዚአብሔርን ኃይል የሚያሳዩ አስደናቂ ሁኔታዎች የሚገልጹ ነገሮችን ዘርዝር ለ) እግዚአብሔር በሥራ ላይ እንደሆነ የሚያሳዩ ብዙ ሰዎች የማይገነዘቡአቸውን ተራና የተለምዱ የሚመስሉ ነገሮችን ዘርዝር። ሐ) ተአምራታዊ ከሆኑ መንገዶች ይልቅ በእነዚህ የተለመዱ ነገሮች ላይ የእግዚአብሔር እጅ እንዳለ ሌሎች የበለጠ እንዲገነዘቡ ለማድረግ ልብ ልትላቸው የምትችልባቸውን መንገዶች ዘርዝር።
> 7ኛ ጥያቄ፥ አስቴር 1-6 አንብብ። ሀ) በእነዚህ ምዕራፎች ውስጥ የተገለጹትን ዋና ዋና ድርጊቶች ዘርዝር። ለ) ለአይሁድ ሕዝብ ጥቅም ሲል እግዚአብሔር እንዴት በሥራ ላይ እንደሆነ የሚያሳዩ የተለያዩ ጥቃቅን ነገሮችን ዘርዝር።

አስቴር 1-6 የአስቴርን ታሪክ የተለያዩ ደረጃዎች ያሳያል። በፋርስ ቤተ መንግሥት ውስጥ የተፈጸሙ ጨርሶ የማይገናኙ የሚመስሉ ነገሮችን ይዟል። እነዚህ ታሪኮች ቢነገሩንም ለዋናው ታሪክ ያላቸው አስፈላጊነት

አልተጠቀሰም። ለታሪኩ መሠረት የሆነው ዋናው ነገር በሐማ በተመሰለው በእግዚአብሔር ሕዝብ በእስራኤላዊያን ጠላትና በአስቴርና በመርዶክዮስ በተመሰለው በእግዚአብሔር ሕዝብ መካከል ያለውን ትግል ነው። ቀጥሎ ይህንን ትግልና በባዕድ ምድር ሕዝቡን ለመታደግ በመሥራት ላይ የነበረውን የእግዚአብሔርን እጅ የሚያሳዩትን ነገሮች እስተውል።

1. ንግሥት አስጢን ከንግሥትነት ሥልጣንዋ ተወግዳ አንዲት የማትታወቅ አስቴር የተባለች ሴት የምትቀጥለዋ የፋርስ ንግሥት ሆና ተመረጠች። ይህ በጣም አስፈላጊ የነበረው በፋርስ ንጉሥ በአርጤክስስ ውሳኔ ላይ ተጽዕኖ ለማድረግና የአይሁድን ሕዝብ ከጠቅላላ ጥፋት ለማዳን የቻለች ንግሥት አስቴር ስለነበረች ነው። እግዚአብሔር በአንድ የአሕዛብ ግብዣ ተጠቅሞ አንዲት ንግሥት እንድትወገድና ሕዝቧን ለማዳን እንድትችል አስቴር ንግሥት እንድትሆን አደረገ።

2. የአስቴር አጎት የነበረው መርዶክዮስ ንጉሡን ለመግደል የተደረገውን ሴራ ሰማና ይህንን ለንጉሡ ነገረ። መርዶክዮስ ይህን ሴራ በማክሸፉ ረገድ ያበረከተው በቤተ መንግሥቱ መዛግብት ውስጥ ተጻፈ። ይህ መረጃ የአይሁድ ሕዝብ ጠላት የነበረው ሐማ የሚጠላውን መርዶክዮስን ለማክበር በተገደደበት ጊዜ አስፈላጊ ሆነ። የንጉሡ የግል አማካሪ የነበረውን የሐማ ስፍራ የወሰደም መርዶክዮስ ነበር። በዚህም ውስጥ የእግዚአብሔርን እጅ እናያለን። እግዚአብሔር ንጉሡ እንዳይገደል አደረገ፤ ቢገደልም ኖሮ አስቴር በአዲሱ ንጉሥ ላይ ተጽዕኖ ማድረግ አትችልም ነበር። እግዚአብሔር ሴራውን ሊያከሽፍ በሚችልበት ትክክለኛ ስፍራ ላይ መርዶክዮስን አስቀመጠው። በኋላም የመርዶክዮስን ሥራ እግዚአብሔር ለንጉሥ አስታወሰና በፋርስ መንግሥት ውስጥ እጅግ አስፈላጊ በሆነ ስፍራ በማስቀመጥ እንዲያከብረው አደረገ።

3. አጋጋዊው ሐማ ያለ ምንም ምክንያት የጠላቸውን የአይሁድን ሕዝብ ለማጥፋት ሴራ አሴረ። እንደምታስታውሰው፥ አጋግ ከአማሌቃውያን ነገሥታት አንዱ ነበር (1ኛ ሳሙ. 15፡20)፤ ስለዚህ ሐማም አማሌቃዊ መሆኑን መገመት ትክክል ነው። ሐማ በምድሪቱ ያሉትን አይሁድ በሙሉ ለማጥፋት ከአርጤክስስ ፈቃድ አገኘ።

4. መርዶክዮስ አይሁድን ለማዳን የምትችለውን ሁሉ ማድረግ እንዳለባት አስቴርን አሳመናት። አስቴር 4፥14 በመጽሐፉ ውስጥ ያለ ቁልፍ ጥቅስ ነው። ስለ ሕይወቷ ለፈራችው ለአስቴር መርዶክዮስ እንዲህ አላት:- «አንቺ:- በንጉሥ ቤት ስለሆንሁ ከአይሁድ ሁሉ ይልቅ እድናለሁ ብለሽ በልብሽ አታስቢ። በዚህ ጊዜ ቸል ብትይ ዕረፍትና መዳን ለአይሁድ ከሌላ ስፍራ ይሆንላቸዋል፥ አንቺና የአባትሽ ቤት ግን ትጠፋላችሁ፤ ደግሞስ ወደ መንግሥት የመጣሽው እንደዚህ ላለው ጊዜ እንደሆነ ማን ያውቃል?» በዚህ ንግግር ውስጥ ሁለት እውነቶችን እናያለን። የመጀመሪያው፥ ከአይሁድ ሕዝብ ጋር ዘላለማዊ ቃል ኪዳን ያደረገው እግዚአብሔር የአይሁድ ሕዝብ እንዳሉ እንዲጠፉ እንደማይፈቅድ መርዶክዮስ ያውቅ እንደ ነበር ነው። ብዙ ሰዎች ቢሞቱም እንኳ፥ እግዚአብሔር አይሁድን ሙሉ ለሙሉ ከመጥፋት ሁልጊዜ ይጠብቃቸዋል።

ሁለተኛው ነገር እግዚአብሔር የራሱን ዓላማ ለመፈጸም ግለሰቦችን በልዩ የኃላፊነት ስፍራ በማስቀመጥ እንደሚጠቀምባቸው መርዶክዮስ ተገንዝቦ ነበር። መርዶክዮስ አስቴር ንግሥት የሆነችው በዕድል እንዳልሆነ ያውቅ ነበር። አስቴርን የፋርስ ንግሥት በማድረግ አይሁድን ለማዳን ሊጠቀምባት የወደደው እግዚአብሔር እንደሆነ መረዳት አለብን።

| |
|---|
| 8ኛ ጥያቄ፥ እግዚአብሔር ጠቃሚ የሆኑ ክርስቲያኖችን ትክክለኛ በሆነ የአመራር ስፍራ በማስቀመጥ ለቤተ ክርስቲያን ዕድገት እንዴት እንደተጠቀመባቸው የሚያሳይ በኢትዮጵያ ውስጥ የተፈጸመ ተመሳሳይ ሁኔታ ግለጥ። |

5. አስቴር ወደ ንጉሡ በመሄድ ወደ አዘጋጀችው ግብዣ እንዲመጣ ጠየቀችው። በፋርስ ባሕል ማንም ሰው ንግሥቲቱም ብትሆን እንኳ ያለ ንጉሡ ጥሪ እርሱ ወዳለበት መግባት አይችልም ነበር። አስቴር ወደ ንጉሡ በመግባቷ በትረ መንግሥቱን የምታመለክተውን በትር ወደ እርሷ ካልዘረጋላት ሕይወቷን እንኳ ልታጣ እንደምትችል ታውቅ ነበር፤ ነገር ግን የእርሷ ሕይወት ከወገኖች ሁሉ ሕይወት እንደማይበልጥ ተገነዘበች። ስለዚህ በፈቃዷ ወደ ንጉሡ ገባች። ይህንን ከማድረጓ በፊት ግን እግዚአብሔር በሥራዋ የተዋጣለት ያደርጋት ዘንድ አይሁድ ሁሉ እንዲጸልዩና እንዲጸልዩ ጠይቃ ነበር። አስቴር፥ በንጉሡ ፊት ሞገስ እንድታገኝ ሊያደርግ የሚችል እግዚአብሔር እንደሆነ ታውቅ ነበር፤ ስለዚህ አይሁድ ሁሉ

እንዲጸልዩላት ጠየቀች። እግዚአብሔር ጸሎቷን አከበረ። እንዲሁም በእግዚአብሔር ጥበቃ ላይ የነበራትን እምነት ሕይወቷን እንኳ ለመሠዋት ፈቃደኛ መሆኗን በንጉሡ ፊት ምገስ በመስጠት አከበረላት።

6. ለእርሱ ክብር ለመስጠት መርዶክዮስ ባለመስገዱ ሐማ ተቆጣ። ስለዚህ ለመርዶክዮስ የመስቀያ ግንድ አዘጋጀ፤ ነገር ግን መርዶክዮስን ለመስቀል ከንጉሥ ፈቃድ ከመጠየቁ በፊት፥ እግዚአብሔር ለንጉሡ እንቅልፍ በመከልከል መርዶክዮስ ሕይወቱን ማዳኑን እንዲያስታውስ አደረገው። በዚያን ጊዜ ሐማ፥ የሚጠላውን መርዶክዮስን ለማክበር ተገደደ፤ ስለዚህ ጸሐፊው የማያምኑ ሰዎች የእግዚአብሔርን ሕዝብ ቢጠሉም እንኳ አንድ ቀን ሊያከብሯቸው እንደሚገደዱ ያስተምረናል።

| |
|---|
| 9ኛ ጥያቄ፥ ፊልጵ. 2፡9-11 አንብብ። የኢየሱስ ጠላቶች አንድ ቀን እርሱን እንዲያከብሩት የሚገደዱት እንዴት ነው?<br>10ኛ ጥያቄ፥ ሀ) ከዚህ የመጽሐፈ አስቴር ክፍል የምንማራቸውን አንዳንድ ጠቃሚ ትምህርቶች ዘርዝር። ለ) እነዚህ እውነቶች ለቤተ ክርስቲያንህ የምታስተምርባቸውን መንገዶች በሚመለከት ዕቅድ አውጣ። |

## 3ኛ ቀን፡- አስቴር 7-12

| |
|---|
| 11ኛ ጥያቄ፥ ምሳሌ 21፡1 አንብብ። ሀ) እግዚአብሔር በምድር መሪዎች ላይ ስላለው ቁጥጥር ይህ ጥቅስ ምን ያስተምረናል? ለ) ክርስቲያኖች ከመንግሥት ጋር በሚሠሩበት ጊዜ ይህ ነገር እንዴት ማበረታቻ ይሆናቸዋል? ሐ) ይህ ነገር ሲፈጸም እንዳየህ ምሳሌዎችን ስጥ። |

እግዚአብሔር ስለ ሕዝቡ ብሎ ሁልጊዜ የሚሠራ መሆኑን አይተናል። ተአምራትን ባናይም እንኳ እግዚአብሔር በሥራ ላይ አይደለም ማለት አይደለም። እግዚአብሔር ብዙ ጊዜ የሚሠራው ሕዝቡ እንኳ በማያውቁት መንገድ ነው። ክርስቲያኖች ግን ዕድል ወይም አጋጣሚ የሚባል ነገር እንደሌለ መገንዘብ አለባቸው። ይልቁንም ጸጋን የተሞላው ሰማያዊ አባታችን ለክብሩ፥ ለመንግሥቱና ለሕዝቡ ሲል ነገሮችን ሁሉ እየተቆጣጠረ ይሠራል።

መጽሐፈ አስቴር፥ እግዚአብሔር በአስቴር ዘመን ይህንን ለአይሁድ እንዴት እንዳደረገላቸው የሚገልጥ ሥዕላዊ ታሪክ ነው። የእግዚአብሔር ጠላቶች፥ የእርሱን ሕዝብ አይሁድን ለማጥፋት ቢወስኑም እንኳ እግዚአብሔር እነርሱን ለማዳን በአንዲት ሴት በመጠቀም በጸጥታ ሠራ።

| |
|---|
| 12ኛ ጥያቄ፥ አስቴር 7-12 አንብብ። ሀ) አስቴር ሕዝቧን ከጥፋት ያዳነችው እንዴት ነው? ለ) በዚህኛው የአስቴር ታሪክ ክፍል የእግዚአብሔር እጅ የታየው እንዴት ነው? ሐ) ከዚህ ታሪክ የምንማረው መንፈሳዊ ትምህርት ምንድን ነው? |

አስቴር 1-6 እስራኤላውያን ራሳቸውን ያገኙበትን አደገኛ ሁኔታ የሚገልጥ ሲሆን፥ አስቴር 7-12 ግን እግዚአብሔር የሐማና የጠላቶቹን ዕቅድ ለማፈራረስ እንዴት እንደሠራና ሕዝቡን እንደጠበቀ ይገልጣል።

## የሚከተሉትን ትምህርቶች ተመልከት:-

1. አስቴር፥ እርስዋንና ሕዝቧን ያለ ምንም ምክንያት ሊገድል ማሰቡን በመናገር ሐማን ከሰሰችው። በውጤቱም ሐማ መርዶክዮስን ለመስቀል ባዘጋጀው ግንድ ላይ ተሰቀለ (መዝ. (28)፡1-5 ተመልከት)።

2. ንጉሥ አርጤክስስ በመንግሥቱ ሁሉ አይሁድን ለመዋጋት በሚያስቡ ወይም በሚሞክሩ ጠላቶቻቸው ሁሉ ላይ የመበቀል ሥልጣን ለአይሁድ እንደተሰጣቸው የሚገልጥ ትእዛዝ አስተላለፈ። ንጉሡም መርዶክዮስን የቅርብ አማካሪው አደረገው። በአንድ ወቅት በቤተ መንግሥት የሐማ የነበረውን የክብር ስፍራ መርዶክዮስ ወሰደ።

3. አይሁድ በጠላታቸው በሐማ ላይ ስላገኙት ድል የፉሪምን በዓል አከበሩ። ፉሪም የሚለው ቃል «ፉር» ከሚለው የዕብራይስጥ ቃል የተገኘ ሲሆን፥ ትርጉሙም ዕጣ ማለት ነው። ይህም የሚያመለክተው ሐማና ንጉሡ አይሁድን ስለሚያጠፉበት ቀን ለመወሰን ያወጡትን ዕጣ ነው (አስቴር 3፡7)። እስራኤላውያንን ለማጥፋት ሐማ ዕጣ ቢጠቀምም እግዚአብሔር ግን ሁኔታዎችን በመቆጣጠር ዕጣው በእግዚአብሔር ሕዝብ ጠላቶች ላይ ወደቀና ብዙ ሺህ አሕዛብ ተገደሉ። አይሁድ ዛሬም ይህንን በዓል በታላቅ ደስታ ያከብሩታል። በዚህ በዓል ዕለት መጽሐፈ አስቴር ለቤተሰቡ አባላት በሙሉ ይነበባል።

## የመጽሐፈ አስቴር ዋና ትምህርት

የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ የግለሰቦች ታሪክ ብቻ ሳይሆን በእግዚአብሔርና በሰይጣን መካከል የሚካሄድ ጦርነት ታሪክ ነው። ከኦሪት ዘፍጥረት ጀምሮ እስከ ዮሐንስ ራእይ ድረስ የዚህን ጦርነት ፍንጮች እናያለን። ሰይጣን በጦርነቱ ለመዋጋት የተለያዩ መንገዶችን ቢጠቀምም ዓላማው ሁልጊዜ አንድ ነው። የእግዚአብሔርን ዕቅድና የእግዚአብሔርን ሕዝብ ለማጥፋት ይፈልጋል።

በእግዚአብሔር ሕዝብ ታሪክ ውስጥ ሁሉ ሰይጣን የደኅንነት መስመር እንዲቋረጥ ለማድረግ በመሞከር የእግዚአብሔርን ዕቅድ ለማበላሸት ታግሏል። ከዘፍ. 3፡15 እንደምታስታውሰው፥ ከሴቲቱ ዘር ሰይጣንን የሚያጠፋ ሰው እንደሚመጣ እግዚአሔር ተስፋ ሰጥቷል። ሰይጣን የሴቲቱ ዘር ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑን ስለሚያውቅ የሚመጣበትን የዘር ግንድ ለማጥፋት የተቻለውን ሁሉ ያደርግ ነበር። እንደምታስታውሰው፥ የግብፅ ንጉሥ ሣራን በሚስትነት እንዲወስድ በማድረግ የአብርሃምን የዘር ግንድ ለማቋረጥ ሞክሮ ነበር። ርብቃንም መኻን በማድረግ የዘር ሐረጉ እንዲያበቃ ለማድረግ ሞክሮ ነበር። በኋላም ሰይጣን የእስራኤልን ሕዝብ ሁሉ በራብ ለመጨረስ የሞከረ ቢሆንም፥ እግዚአብሔር ግን በዮሴፍ በኩል እነርሱን ታድጎአቸዋል። በኋላም መሢሑ የሚመጣው በእርሱ በኩል መሆኑን እግዚአብሔር ለዳዊት ነግሮታል (2ኛ ሳሙ. 7፡14)። ሰይጣን ግን የዳዊትንም ዘር ለማጥፋት በመሞከር የእግዚአብሔርን ዕቅድ ሊያበላሽ ጥሮ ነበር። እንደምታስታውሰው፥ እግዚአብሔር ካዳነው ከአንድ ትውልድ በቀር ጎቶልያ የዳዊትን ዘር በሙሉ አጥፍታ ነበር፤ (2ኛ ነገ. 11፡1-3)። አሁን ደግሞ በአስቴር ታሪክ ሰይጣን ሐማ የተባለውን የአንድ ሰው ጥላቻ በመጠቀም አይሁድን ሁሉ ለማጥፋት ሞክሮ ነበር። አይሁድ ተደምስሰው ቢሆን ኖሮ መሢሑ ባልተወለደና ዓለምም አዳኝን ባላገኘ ነበር። እግዚአብሔር ግን የሰይጣንን ዕቅድ አከሸፈ።

ይህ እውነት ከኢየሱስ ዘመን ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ ያለውን አንዳንድ የአይሁድ ታሪክ ለመረዳት ይጠቅመናል። በየትኛውም ስፍራ ይሁኑ አይሁድ ሁልጊዜ የሚሰደዱ ሰዎች ነበሩ። ይህም በተለይ የታየው በ2ኛው የዓለም ጦርነት ሂትለርና ጀርመኖች ከ6 ሚሊዮን የሚበልጡ አይሁዳውያንን ቢገድሉም፥ እግዚአብሔር ግን አሁንም ቢሆን ለአይሁድ ሕዝብ ዕቅድ ስላለው ሙሉ በሙሉ ሊያጠፏቸው ባለመቻሉ ነው፤ ስለዚህ

በአጠቃላይ በታሪክ ሁሉ ቅሬታዎቹን በመጠበቅ አንድ ቀን ሊገበኛቸውና በመካከላቸው ታላቅ ሥራን ሊያደርግ ዕቅድ አለው (ሮሜ 11 ተመልከት)።

| |
|---|
| 13ኛ ጥያቄ፥ ሀ) የማያምኑ ሰዎች ከክርስቲያኖች ጋር የሚታገሉትና ሊያጠፏቸው የሚሹት ለምን እንደሆነ ለመረዳት ይህ እውነት እንዴት ይረዳናል? ለ) ይህ እውነት በተጨማሪ ሕዝቡ ሙሉ በሙሉ እንዲጠፋ እግዚአብሔር እንደማይፈቅድ ምን ያስተምረናል? |

## 4ኛ ቀን፡- የታሪክ መጻሕፍት ክለሳ

እስካሁን ድረስ ባካሄድነው ጥናታችን ሁለት ዋና ዋና የብሉይ ኪዳን ክፍሎችን ተመልክተናል። በመጀመሪያ ፔንታቱክ በሚል ስም የታወቁትን በሙሴ የተጻፉትን አምስቱን የብሉይ ኪዳን መጻሕፍትን ተመልክተናል። በሁለተኛ ደረጃ፥አሥራ ሁለቱን የታሪክ መጻሕፍትን ተመልክተናል። እነዚህ የታሪክ መጻሕፍት የተጻፉት በተለያዩ ያልታወቁ ጸሐፊዎች ነበር። የሚናገሩትም በብሉይ ኪዳን ያሉትን የቀሩትን የእግዚአብሔር ሕዝብ ታሪክ ነው። ታሪኩም ከ1400 እስከ 400 ዓ.ዓ. ድረስ ያለውን ዘመን የሚሸፍን ነው። እነዚህ 12 መጻሕፍት የ1000 ዓመታት ታሪክ ይሸፍናሉ። ታዲያ ሁሉም የታሪክ መጻሕፍት ቢሆኑም በትምህርት ቤት እንደምንማራቸው የታሪክ መጻሕፍት የተጻፉ አይደሉም። ይልቁንም እያንዳንዱ መጽሐፍ የተጻፈው መንፈሳዊ እውነትን ለእግዚአብሔር ሕዝብ ለማስተማር ነው። ከእነዚህ መጻሕፍት በምናነብበት፥ በምናጠናበትና በምንሰብክበት ጊዜ በውስጣቸው ያለው መንፈሳዊ እውነት ምን እንደሆነ ልንረዳና ለቤተ ክርስቲያን አባሎቻችን ልናስተምር ይገባናል።

| |
|---|
| 14ኛ ጥያቄ፥ ሀ) 12ቱን የታሪክ መጻሕፍት ዘርዝር። ለ) እያንዳንዱን መጽሐፍ በሚመለከት መጽሐፉ የሚናገራቸውን ዋና ዋና የታሪክ ወቅቶች ዘርዝር። ሐ) በመጽሐፉ ውስጥ የሚገኙ ዋና ዋና ገጸ ባሕርያትን ግለጥ። መ) በእያንዳንዱ መጽሐፍ ውስጥ የሚገኙትን ዋና ዋና ትምህርቶች ዘርዝር። |

የሚከተሉትን መጻሕፍት ዝርዝር ተመልከት

1. ኢያሱ፡- እንደምታስታውሰው ኢያሱ ሙሴ ከሞተ በኋላ የእስራኤል ሕዝብ መሪ ነበር። ሕዝቡን ወደ ከነዓን ለመምራትና በዚያ የሚኖሩ ጠላቶቻቸውን ሁሉ ለማሸነፍ እግዚአብሔር የተጠቀመበት ሰው

ነበር። ኢያሱ በእግዚአብሔር ጠላቶች ላይ ስለሚገኝ ድል የሚናገር መጽሐፍ ነው። በኢያሱ ዘመን የተገኘው ድል አብዛኛው በምድራዊ ጠላቶች ላይ ነበር፤ ለእኛ ግን በመንፈሳዊ ጠላቶቻችን ላይ ስለሚገኝ ድል የሚያስተምረን ነው።

2. መሳፍንትና ሩት፡- ዘመነ መሳፍንት ኢያሱ ከሞተ አንሥቶ እስከ መጀመሪያው የእስራኤል ሕዝብ ንጉሥ እስከ ሳኦል ዘመን ድረስ የሚዘልቅ ሲሆን ወደ 400 ዓመታት ይጠጋል። የመጽሐፈ መሳፍንት ዋና አሳብ «ሰውም ሁሉ በፊቱ መልካም መስሎ የታየውን ያደርግ ነበር» (መሳ. 17፡6፤ 21፡25) በሚለው ጥቅስ ውስጥ ይገኛል። አይሁድ እግዚአብሔርን በመካድ የሐሰት አማልክትን (ጣዖታትን) የተከተሉበት የክሕደት ጊዜ ነበር። መጽሐፈ መሳፍንት አይሁድ ያለፉበትን የውድቀት ሂደት ይናገራል። በመጀመሪያ፥ በእግዚአብሔር ላይ ኃጢአት ሠሩ። ሁለተኛ፥ እግዚአብሔር በጠላቶቻቸው በከነዓናውያን እጅ አሳልፎ በመስጠት ቀጣቸው። ሦስተኛ፥ ለተወሰነ ጊዜ በባርነት ቀንበር ሥር ቆዩ። አራተኛ፥ እግዚአብሔር ከጠላቶቻቸው እጅ ነፃ እንዲያወጣቸው ወደ እርሱ ጮኹ። አምስተኛ፥ እግዚአብሔር ፈራጅ የሆነ መስፍንን ወይም የጦር መሪን በማስነሣት ጠላቶቻቸውን እንዲያሸንፉና እንደገና ኃጢአት ሠርተው እስኪፈረድባቸው ድረስ የነፃነት ዘመን ሰጣቸው። በዚህ ዘመን የተነሡ ዋና ዋና መሳፍንት ናትናኤል፥ ናዖድ፥ ዲቦራና ባርቅ፥ ጌዴዎን፥ ዮፍታሔና ሶምሶን ነበሩ። የመጽሐፈ ሩት ታሪክ የተፈጸመው በዘመነ መሳፍንት ሲሆን፥ አብዛኛው ሕዝብ እንዴት እግዚአብሔርን እንዳላከበረና በዚህ ዓይነት ጨለማ ውስጥ እግዚአብሔርን የሚያከብሩ ጥቂት ሰዎች እንደነበሩ የሚያሳይ ነው።

3. 1ኛ ሳሙኤል፡- 1ኛ ሳሙኤል እስራኤል ከዘመነ መሳፍንት በአንድ ንጉሥ ሥር አንድ መንግሥት ሆና ትተዳደር ወደነበረችበት ወደ ነገሥታት ዘመን ስላደረገችው የሽግግር ጊዜ የሚናገር መጽሐፍ ነው። መጽሐፉ የእስራኤል የመጨረሻ መሳፍንት ስለሆኑት ስለ ዔሊና ስለ ሳሙኤል ይገልጣል። በተጨማሪ የመጀመሪያው የእስራኤል ንጉሥ ስለሆነው ስለ ሳኦልም ይናገራል። ስለ ሳኦል ውድቀትና ተከታዩ የእስራኤል ንጉሥ እንዲሆን እግዚአብሔር ዳዊትን እንዴት እንደመረጠው ይናገራል። የ1ኛ ሳሙኤል አብዛኛው ታሪክ

የሚናገረው ስለ ዳዊት ዝና አጀማመርና ሳኦልም ዳዊትን ለመግደል ስላደረጋቸው የተለያዩ ሙከራዎች ነው።

4. 2ኛ ሳሙኤልና 1ኛ ዜና መዋዕል፡- እነዚህ ሁለት መጻሕፍት የሚሸፍኑት ተመሳሳይ ጊዜያትን ነው። የሚናገሩትም በእስራኤል ተወዳዳሪ ስላልተገኘለት ስለ ታላቁ ንጉሥ ነው። እግዚአብሔር ለዳዊት የዘላለም ቃል ኪዳንን በመግባት በእስራኤል ሁሉ ላይ ገዥ የመሆን መብትን ለዘሩ እንደ ሰጠ እንመለከታለን። ይህንን ቃል ኪዳን ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ እንዴት እንደሚፈጽመው አይተናል። እነዚህ መጻሕፍት በዳዊት ሕይወት ስለታየው መንፈሳዊ ታላቅነትና ወታደራዊ ኃይል ይናገራሉ። 2ኛ ሳሙኤል በዳዊት ወታደራዊ ታላቅነትና ኃጢአት ላይ ሲያተኩር፥ 1ኛ ዜና የሚያተኩረው ደግሞ በዳዊት መንፈሳዊ ሕይወትና ታቦቱን ወደ ኢየሩሳሌም በመውሰድና ለቤተ መቅደሱ ሥራ ዝግጅት በማድረግ እግዚአብሔርን እንዴት እንዳከበረ በመናገር ላይ ነው።

5. 1ኛ ነገሥትና 2ኛ ዜና መዋዕል 1-18፡- እነዚህ መጻሕፍት ከተባበረው የእስራኤል መንግሥት ወደ ተከፋፈለው መንግሥት የተደረገውን የሽግግር ዘመን የሚናገሩ ናቸው። የሁለቱም መጻሕፍት የመጀመሪያ ክፍሎች የሚናገሩት ጠቢብ ስለነበረው ስለ ዳዊት ልጅ ስለ ሰሎሞን ነው። 1ኛ ነገሥት እስራኤልን ወደ ክሕደት በመምራት የእስራኤልን መንግሥት በሁለት ስለከፈለው ስለ ሰሎሞን ኃጢአት ይናገራል። 2ኛ ዜና መዋዕል ሰሎሞን የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ እንዴት እንደሠራ ይናገራል። ቀጥሎ እነዚህ መጻሕፍት የሚናገሩት አንድ የነበረው የእስራኤል መንግሥት እንዴት ለሁለት እንደተከፈለ ነው። በስተ ሰሜን የሚገኙት አሥሩ ነገዶች እስራኤል ተብለው የተጠሩ ሲሆን፥ ዋና ከተማቸውም ሰማርያ ነበረች። የብንያምና የይሁዳን ነገዶች የያዙት ሁለቱ ነገዶች ዋና ከተማቸውን ኢየሩሳሌም በማድረግ የይሁዳን መንግሥት መሠረቱ። 1ኛ ነገሥት የሰሜኑንና የደቡቡን መንግሥታት የተለያዩ ነገሥታት በአጭር በአጭሩ ሲያቀርብ፥ 2ኛ ዜና ደግሞ ያተኮረው በደቡብ መንግሥት ነገሥታት ላይ ነው። እንደዚሁም 1ኛ ነገሥት በነቢያት ሥራ ላይ ያተኮረ ሲሆን፥ 2ኛ ዜና የሚያተኩረው ግን በሌዋውያን ሥራ ላይ ነው።

6. 2ኛ ነገሥትና 2ኛ ዜና መዋዕል 19-36፡- እነዚህ መጻሕፍት የሰሜኑ መንግሥት እስራኤል በ722 ዓ.ዓ. በአሦር መንግሥት መደምሰሱንና የይሁዳ መንግሥት የሚባለው የደቡብ መንግሥት ደግሞ በ586 በባቢሎናውያን መማረኩን ይናገራሉ። 2ኛ ነገሥት የሚናገረው ስለ ሰሜኑና ስለ ደቡቡ መንግሥት ሲሆን፥ 2ኛ ዜና የሚያተኩረው ግን በደቡቡ መንግሥት ላይ ሆኖ በተለይ ደግሞ በይሁዳ እውነተኛ አምልኮን ለመመለስ የተሐድሶ ሥራ በሠሩ እግዚአብሔርን በሚፈሩ መሪዎች ታሪክ ላይ ነው። 2ኛ ነገሥት በነቢያት ሥራ ላይ ማተኮሩን ሲቀጥል፥ 2ኛ ዜና ግን ስለ ሌዋውያን ሥራ ይናገራል።

7. መጽሐፈ ዕዝራ፥ ነህምያና አስቴር፡- እነዚህ ሦስት መጻሕፍት የሚናገሩት ከኢየሩሳሌም መደምሰስ በኋላና አይሁድ ወደ ተስፋይቱ ምድር ከተመለሱ በኋላ ስላለው ጊዜ ነው። ዕዝራና ነህምያ የሚያተኩሩት ከምርኮ ወደ ይሁዳ በተመለሱት አይሁድ ላይ ነው። መጽሐፈ ዕዝራ በዕዝራና በዘሩባቤል መሪነት የተመለሱትን የመጀመሪያዎቹን ሁለት የእስራኤል ቡድኖች የሚገልጽ ሲሆን፥ በተጨማሪ ስለ ሁለተኛው ቤተ መቅደስ መሠራትና ዕዝራ በይሁዳ ስለመራው መንፈሳዊ መነቃቃት ይናገራል። መጽሐፈ ነህምያ ደግሞ ስለ ኢየሩሳሌም ቅጥር መሠራትና ሕዝቡ የእግዚአብሔርን ቃል በሰሙ ጊዜ በመካከላቸው ስለተፈጸመው መንፈሳዊ መነቃቃት ይናገራል። መጽሐፈ አስቴር የሚያተኩረው በምርኮ ምድር በነበሩ አይሁድ ላይ ነው። መጽሐፉ እግዚአብሔር ሕዝቡን በቸርነቱ የፋርስ ንግሥት አድርጎ ባስቀመጣት በአስቴር አማካይነት ከመደምሰስ እንዴት እንደጠበቃቸውና የሐማን ዕቅድ እንዳከሸፈ ይናገራል።

የብሉይ ኪዳን ጥናት የመጀመሪያ ክፍል የሆነውን የዚህን መጽሐፍ ጥናት የመጨረሻውን ፈተና ለመውሰድ ተዘጋጅ።

የቀሩትን የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት በሚቀጥለው ጥናት እንመለከታለን።

አምስተኛ ቀን:-

የዚህን ሳምንት ትምህርት በመከለስ ለመጨረሻው ፈተናህ ተዘጋጅ (ማስታወሻ:- ለመጨረሻ ፈተናህ በእያንዳንዱ መጻሕፍት ዋና ዋና ትምህርቶች ላይ አተኩር። ጸሐፊው ማን ነበር? መቼ ተጻፈ? የመጽሐፉ ዓላማ ምን ነበር? የመጽሐፉ ዋና ዋና ትምህርቶችስ ምንድን ናቸው? በእያንዳንዱ መጽሐፍ ውስጥ ያለውን አጠቃላይ ነገር በመረዳት ከሌላው መጽሐፍ በምን እንደሚለይ ለመገንዘብ ሞክር። ለመጨረሻ ፈተናህ ዝርዝር ነገሮችን ማወቅ አያስፈልግህም።)


ሳምንታዊ ስብሰባ


ሀ. የሳምንቱ የአምልኮ ጊዜ

ለ. ጸሎት


ሐ. የትምህርቱ ክለሳ

መ. የመጨረሻ ፈተናን መውሰድ



በብሉይ ኪዳን ጊዜ
የታወቀው ዓለም
N
ትንሹ እስያ
የአርመን አገር
የአራራት ተራራዎች
የካስፒያን ባሕር
የካስፒያን ተራራዎች
ሚዶን
የዛግሮስ ተራራዎች
ካራን
ነነዌ
አሶር
በሁለት ወንዝ መካከል
የሒዶቄል ወንዝ
(ጤግሮስ)
ኤላም
የኤፍራጥስ ወንዝ
ባቢሎን
የከለዳውያን አገር
ኡር
የፋርስ ባሕር
ቆጵሮስ
ፊንቄ
አርኖ
ደማስቆ
የአርሞንዔም ተራራ
ታላቁ ባሕር
ፍልስጥኤም
ሞአብ
ምድረ በዳ
ኤዶምያስ
የዓረብ ምድረ በዳ
ግብፅ
የአባይ ወንዝ
የሲና ተራራ
የስዊዝ ባሕር
የአካባ ባሕር
የኤርትራ ባሕር




ታላቁ ባሕር
ከነዓን
ግብፅ
ራዕምሴስ
ጎሼን
የኔቦ ተራራ
የጨው ባሕር
ቃዴስ በርኔዓ
የሆር ተራራ
ኤላት
ማራ
ኤሊም
ሐሴሮት
ራፊዲም
የሲና ተራራ
የሲን ምድረ በዳ
N
0 20 40 60 80 100
ኪሎሜትር
የእስራኤል ሕዝብ
በምድረ በዳ ዙረት
የኤርትራ ባሕር





የፍልስጥኤም አገር
በእስራኤል ነገዶች
እንደተከፋፈለ


ጥቁር ባሕር
የካስፒያን ባሕር
ሊዲያ
አራራት
ጠርሴስ
ጎዛን
ሐማ
ሐራን
ታላቁ ባሕር
ቆጵሮስ
ሲዶና
ጢሮስ
ኢየሩሳሌም
አሦር
ነነዌ
የጤግሮስ ወንዝ
የኤፍራጥስ ወንዝ
ደማስቆ
ሞአብ
ባቢሎን
ዑር
ሱሳ
ኤላም
ሜዶን
ፋርስ
የፋርስ ባሕረ ሰላጤ
አረቢያ
የኤርትራ ባሕር
ሜምፊስ
ግብጽ

... የአሦር መንግሥት


ጥቁር ባሕር
ካስፒያን ባሕር
የአሲሪያ ግዛት
አርማንያ
ሜዶን
ኤላም
ቆጵሮስ
ሶርያ
ኢየሩሳሌም
ባቢሎን
ግብጽ
ናይል ወንዝ
የኤርትራ ባሕር
የፋርስ ባሕረ ሰላጤ
ዓረብ
የባቢሎናውያንን ግዛት ያሳያል



ጥቁር ባሕር
የካስፒያን ባሕር
ባክትሪያና
ሜዶን
ግዛት
አረቢያ
የቀይ ባሕር
ግብፅ
ፋርስ
ኢትዮጵያ
የፋርስን ግዛት ያሳያል

# የብሉይ ኪዳን ጥናት ት.መ.ማ

## አንደኛ መጽሐፍ

### የጽሕፈት ሥራ ተግባር

ለዚህ ትምህርት ዲፕሎማ ለመቀበል እያንዳንዱ ተማሪ ለሚከተሉት ጥያቄዎች በሙሉ መልስ በመስጠት፥ በሉክ ወረቀት 10 ገጽ ወይንም በደብተር 20 ገጽ ጽሑፍ ማቅረብ አለበት።

ከዘፍጥረት ጀምሮ በምርኮ እስከተወሰዱበት ጊዜ ድረስ ያለውን የእስራኤልን ሕዝብ ታሪክ በጊዜ ቅደም ተከተል መሠረት በአጭሩ አጠቃለህ ጻፍ። ከማጠቃለያህ በመቀጠልም ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስህን ስጥ:-

ሀ. አንድ ክርስቲያን በብሉይ ኪዳን ዘመን የነበረውን የእግዚአብሔርን ሥራ በግልጽ መረዳት የሚያስፈልገው ለምንድን ነው?

ለ. ስለ ብሉይ ኪዳን የሚኖረን ጥሩ ግንዛቤ አዲስ ኪዳንን በተሻለ መልኩ ለመረዳት የሚያግዘን እንዴት ነው?

ሐ. ከእስራኤል ታሪክ ስለ እግዚአብሔር ምን ልንማር እንችላለን?

መ. እንደ እግዚአብሔር ሕዝብ እግዚአብሔር በግል ሕይወታችን ስለሚፈልግብን ነገር ከእስራኤል ታሪክ ምን ልንማር እንችላለን?

ሠ. እግዚአብሔር በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እና በቤተ ክርስቲያን በኩል ሊሠራው ስለሚፈልገው ነገር ከእስራኤላውያን ታሪክ ምን ልንማር እንችላለን?

# የጥናት መምሪያና ማብራሪያ (በት.መ.ማ መልክ የተዘጋጁ) መጻሕፍት፣

1. የብሉይ ኪዳን አሰሳ፣ 1ኛ መጽሐፍ
2. የብሉይ ኪዳን አሰሳ፣ 2ኛ መጽሐፍ
3. ኦሪት ዘፍጥረት
4. ኦሪት ዘሌዋውያን እና ዕብራውያን
5. ትንቢተ ኢሳይያስ
6. ትንቢተ ዳንኤል
7. የአዲስ ኪዳን አሰሳ፣ 1ኛ መጽሐፍ
8. የአዲስ ኪዳን አሰሳ፣ 2ኛ መጽሐፍ
9. የዮሐንስ ወንጌል
10. የሐዋርያት ሥራ
11. የሮሜ መልእክት
12. 1ኛና 2ኛ ቆሮንቶስ
13. የገላትያና ያዕቆብ መልእክቶች
14. የዮሐንስ ራእይ
15. መንፈስ ቅዱስ
16. የመጽሐፍ ቅዱሳዊ ክርስትና የጥናት መምሪያ
17. ክርስቲያናዊ ትምህርት በኢትዮጵያ

BIBLE BASED BOOKS
SIM PUBLISHING